
| |
|---|
| «የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር! » |
| የጨለማዉ ገዥ በእሳት ሰንሰለት ታስሮ የገለጸዉ ምስጢር፡፡ |
| ጸሐፊዉ ከጨለማዉ ገዥ ተቃዋሚ አንዱ፡፡ |
| የጨለማዉ ገዥ ከነገሠባት አገር ከኢትዮጵያ የተገኘ፡፡ |

መጀመሪያና መጨረሻ በሌለዉ  በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ባለችዉ ሚጢጢዋ ዓለም ዉስጥ የጨለማዉ ገዥ የነገሠባቸዉ አገራትን የሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ!




ታህሳስ፲፮፥፳፻ወ፬(2004) ዓ.ም.


ኢሜል፡ godservant40@yahoo.com

**ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ የተላለፈ የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር!**

**<u>የጀርባ ሽፋን ላይ የሚወጣ</u>**

ይህ መጽሐፍ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ገጥሞኝ በማያዉቅ መልኩ የተጻፈ ነዉ:: ይኸዉም በጽሑፍ መልክ ሆነ በስብከት እንዲሁም በንግግር ተመልክቼ ሆነ ሰምቼ በማለዉቀዉ መልኩ ስለተጻፈ ነዉ:: አዎን! ሰይጣናት ደካማነታችንንና ስንፍናችንን እንዲሁም ዐመፃና ክህደታችንን ተመልክተዉ «እነዚህ የአዳም ዘሮች ማንነታችንንና ስራችንን በግልጽ ብንነግራቸዉ ምን ያመጣሉ! ስለ ምድራዊዉ ሆነ ሰማያዊዉ ምስጢር ብንገልጽላቸዉ ከቁም ነገር ስላማይቆጥሩትና ሁል ጊዜ ምርጫቸዉ እኛን ስለሚያደርጉ ያለዉን እዉነታ በደንብ ነግረናቸዉ ፍርዱን እናስብስባቸዉ:: እነሱ እንደሆነ እንኳን እኛን የጨለማ ገዥንና አበጋዝ ቀርቶ ፈጣሪያቸዉን እንኳ የማይሰሙና ለራሳቸዉ ጥቅም የሚናገራቸዉን  የማይቀበሉ ናቸዉ:: በእርግጥ ጆሯቸዉ ለእኛ ክፍት ነዉ:: እጃቸዉና እግራቸዉ ለእኛ ለጨለማ ስራ የተፋጠነ ነዉ::» በማለት እያሾፉብንና እየተሳለቁብን፣ እንዲሁም እያላገጡብን ስለሆነ ማንነታቸዉንና ምንነታቸዉን በደንብ አዉቀን እንዲሁም ከእግዚአብሔር የሆነዉን እዉነት አስተዉለን ምርጫችንን በማስተካከል ህብረታችንንና አንድነታችንን ከሁሉ ፈጣሪ አምላክ ጋር ማድረግ ይጠበቅብናል:: በእግዚአብሔር ገላጭነትና ትዕዛዝ የተጻፈ መጽሐፍ ስለሆነ  የቅዱስ ኪዳን ሕዝቦች ኢትዮጵያዉያን  ሆን የዓለም ሕዝብ ሁሉ ሊያነበዉ የሚገባ መጽሐፍ መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ::

ኀዘንተኛዉና መከረኛዉ ሰዉ ከእግዚአብሔር ባሪያ አንዱ!

**ማዉጫ** **ገጽ**


1. **የፊት ለፊት ሽፋን ...........................................................................1**
2. **የኋላ ሽፋን ..................................................................................2**
3. **ማዉጫ... ....................................................................................3**
4. **ማስታወሻ ...................................................................................4-5**
5. **ማሳሰቢያ ... ...............................................................................5-13**
6. **መቅድም ......................................................................................14-16**
7. **መግቢያ ......................................................................................17-18**
8. **ክፍል አንድ ...............................................................................19-123**
9. **ክፍል ሁለት ................................................................................124-250**
10. **ክፈል ሦስት ...............................................................................251-363**
11. **ከፍል አራት ...............................................................................364-463**

## ማስታወሻ

-ይህ መጽሐፍ የተጻፈዉ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ስለሆነ ማንም ሰዉ ለንግድ ወይንም ለትርፍ እንዳያዉለዉ::

-ማንም ሰዉ ከመጽሐፉ አንዳች ቃል ሆነ ዐረፍተ ነገር እንዲሁም አንቀጽና ምእራፍ ሳይቀንስና ሳይጨምር ለወገኖቹ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ በኢንተርኔት፣ በሲዲ፣ በወረቀት እያባዛ፣ በመጽሐፍ መልክ፣ ባጠቃላይ በማንኛዉም መልክ ማስተላለፍ ይችላል::

- በመጽሐፍ መልክ የሚያሰራጭ ሰዉ የድካሙን ዋጋ ብቻ በማተሚያዉ ዋጋ ላይ በመጨመር ማሰራጨት ይኖርበታል እንጂ ለገቢ ማግኛና ለትርፍ ብቻ መሰብሰቢያ የሚያዉለዉ ከሆነ ዋጋ እንደሚከፍልበት ሊያዉቅ ይገባል::

እንዲሁም ማንም ይሁን ማን ከመጽሐፉ በራሱ ስልጣን አንዳች ቢቀንስ ሆነ ቢጨምር በምድርም በመለኮት ስልጣን ታስሮ ፍዳዉን እንደሚቀበልና ነፍስ ከሥጋዉ ከተለየች በኃላ ደግሞ ነፍሱ በረቂቅ አካል ተገልጻና ነጻነቷ ተገድቦ በአንድ ቦታ ላይ በመቶ እጥፍ ፍዳዋን እንደምትቀበል ሊያዉቅ ይገባል::

ስለዚህ አንዳች ከመቀነስና ከመጨመር ይልቅ «አልቀበለዉም» የሚል ሰዉ ከመለኮት ፍርድ ባያመልጥም ፍርዱ ግን እንደሚቀልለት በዚሁ ለማሳወቅ እወዳለሁ::

ጸሐፊዉ ማንም ሰዉ እንዲያሳትመዉና ለወገኖቹ ለአዳም ዘር እንዲያደርስ ፈቃዱ የሆነና አምስት ሳንቲም ከማንም ሰዉ እንደማይፈልግ በዚሁ ለመግለጽ ይወዳል:: ዋናዉ ፍላጎቱ የአዳም ዘር በእግዚአብሔር መልእክት ተጠቅሞ ራሱንና ወገኑን ከጥፋትና ከመደምሰስ እንዲያድን ብቻ ነዉ:: ለማሳታምና ለማሰራጨት የሚፈልግ ሰዉ በግልጽ ማንነቱንና አድራሻዉን በእ-ጦማር (በኢሜል) አድራሻዬ አሳዉቆኝ ከኔ ፈቃድ ሲያገኝ ብቻ ማሳተምና ማሰራጨት

ይችላል፡፡ ምክንያቱን የተለያዩ ሰዎች በተለያየ መልክ እናዳያሳትሙትና ለንግድ ስራ እንዳያዉሉት፣ እንዲሁም እግዚአብሔር የፈቀደለት አካል ወይንም ግለሰብ ብቻ እንዲያሳትመዉ ለማድረግ በማሰብ ነዉ፡፡

-የእግዚአብሔርን መልእክት መቀበልና አለመቀበል የእያንዳንዱ ሰዉ ነጻ ምርጫ ነዉ፡፡ በእግዚአብሔር መልእክት ላይ መቃወም ግን በራስ ላይ መከራና ችግር እንዲሁም ጥፋት ማምጣት እንደሆነ ሁሉም ሰዉ ሊረዳዉ ይገባል፡፡ ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ ላይ በድፍረት የሚቃወም ሰዉ በምድርም በሰማይም በመለኮት እሳት ሰንሰለት የታሰረና ለእያንዳንዱ የዐመጻዉና ክህደት ተግባሩ በምድርም በሰማይም ዋጋ የሚከፍልበት መሆኑን ሊያዉቅ ይገባል፡፡

-ጸሐፊዉ ከዓለም አንዳች ነገር ፈልጎ እንዳልጻፈዉና ከአምላኩ ስለታዘዘ ብቻ መልእክቱን ለወገኖቹ ለአዳም ዘር ለማድረስ  እንደፈለገ ሁሉም ሰዉ እንዲያዉቅለት ይፈልጋል፡፡

- በዚህ መጽሐፍ ሆነ መልእክት ለሚመጣ ማንኛዉ ነገር ተጠያቂዉ እኔ መልእክቱን አምጪዉ ሰዉ ብቻ መሆኔን ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡ ለምታሳራጨላቸዉ ሰዎች የኢሜል አድራሻዬን መግለጽ ትችላላችሁ፡፡

መልካም ንባብና መረዳት፣ማስተዋል፣ ለወገኖቼ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ በሙሉ!

# ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የተጻፈዉ በሥጋና ደም ስሜት መነሻነት ሳይሆን፤ ያልኖረበት ጊዜ የሌለ፣ የማይኖርበት ጊዜ የማይኖር፣ ረቂቁንና ግዙፉን ፍጥረት በመለኮታዊ ኃይሉ የፈጠረ፣ ሁሉ በእርሱ የእርሱ የሆነ፣ ከእርሱ እይታና ቁጥጥር ዉጭ የሆነ አንዳች ነገር የሌለ፣ ካለእርሱ ፈቃድ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊኮን የማይቻል፣ ፊተኛዉና መጨረሻዉ፣ አልፋና ዖሜጋ የሆነዉ ፈጣሪ አምላክ ከመስከረም አጋማሽ  እስከ ታህሳስ መጀመሪያ ድረስ በተለያዩ ቀናትና ሰዓት ወደ ኅሊናዬ በሚያሳስበኝና በሚናገረኝ ድምጽ ብቻ ተመርቼ ነዉ የጻፍኩት፡፡

ምናልባት «አንተ ማነህና ነዉ እግዚአብሔር የሚናገርህ?» የሚል ሰዉ ካለ፤ እኔ ታላቁ አባት አብርሃም ራሱን በጠራበት ስም «ከአፈርና ከአመድ»፣ ታላቁ ነብይና ንጉሥ ዳዊት ራሱን በጠራበት ስም «ከትልና ከሞተ ዉሻ እንዲሁም ከድዉይ»፣ ታላቁ ነብይና ሐዋርያ ዮሐንስ ራሱን በጠራበት ስም «ከጫማ ተሸካሚና በምድረበዳ ከሚጮኽ ድምጽ»፣ ታለቁ ሐዋርያ ጳዉሎስ ራሱን በጠራበት ስም «ከጥራጊ ጉድፍና ከጭንጋፍ»፣ ታላቁ ጻድቅ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ራሱን ከጠራበት ስም «ኃጢአቴ ከዓለም ኃጢአት ይበልጣል»፣ ታላቁ ትሑቱ የእግዚአብሔር መልአክ ራሱን ከጠራበት «ከአንተ ጋር ከወንድሞችህ ነብያት ጋር የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ» ካለዉ እኩል፤ ባጠቃላይ ጻድቃንና ቅዱሳን ራሳቸዉን በጠሩበት «ኃጢአቴ ከሰማይ ከዋክብት ከምድር አሸዋ የበዛ ነዉ» ካሉት እኩል ልቆጠር የማይገባኝ ተራ፣ ወራዳ፣ ኃጢአተኛና መሃይም ሰዉ ነኝ፡፡

ጽሑፉ የተጻፈዉ በጸሐፊዉ ሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ እዉቀት ደረጃና በቀጥታ ከእግዚአብሔር በተገለጸለትና በተነገረዉ እዉቀት ደረጃ ሲሆን፤ አሁን የተሰማራበት ሙያ ከሥነ ጽሑፍ ሙያ ዉጭ የሆነ አንድ ገጽ ደብዳቤ ለማርቀቅ የሚከብደዉ የነበረ ሰዉ ነዉ፡፡ ይሁንና የእግዚአብሔር ጥሪ ሆነና ይኸዉ ለመጽሐፍ የሚበቃ ጽሑፍ <u>463 ገጽ</u> በሶስት ወራት ዉስጥ ከእግዚአብሔር ማሳሰቢያ የተሰጠዉንና የተነገረዉን በእጅም፣ በኮምፒተርም ሊጽፍና ለወገኖቹ ለኢትዮጵያዉያንና ለአዳምና ሔዋን ዘሮች ለዓለም ሕዝብ ሊያስተላልፍ ችሏል፡፡

ጸሐፊዉ እንደማንኛዉም የአዳም ዘር በኃጢአት ወድቆ የነበረ በአጭር ዓመታት ዉስጥ መዉደቅን መነሳትን የተመለከተ፤ ማንኛዉም ሰዉ የሚሰማዉ ስሜት የሚሰማዉ፤ እንደማንኛዉም ሰዉ በተለያየ ሕይወት ዉስጥ ያለፈ፤  ራሱን በንስሐ እያጠራ ያለ ሰዉ ነዉ፡፡ ራሱን « ንጹህና ቅዱስ ነኝ» ብሎ የማያመጻድቅ ይልቁኑ «የዐመፀኞች ዋና ዐመፀኛ፣

የከሃዲያንም ዋና ከሃዲ፣ የርኩሳንም ዋና ርኩስ ነኝ፤» በማለት ነዉ ጸሎቱንና ምስጋናዉን ለፈጣሪ የሚያቀርበዉና ለራሱም ሆነ ለወገኖቹ ለአዳም ዘር  የሚጸልየዉ፡፡

ሁል ጊዜ የወገኖቹ የአዳምና ሔዋን ዘሮች ድኅነታቸዉንና መልካም ሕይወት እንዲኖራቸዉ የሚፈልግ፤ በሚያየዉና በሚሰማዉ ተቃራኒ ተግባርና ሕይወት ኀዘንተኛ የሆነ፤ ኀዘኑም ሲያይልበት «በዚህች ምድር መፈጠር አልነበረብኝም፤» በማለት መፈጠሩን የሚያማርር፤ ከዉጭ ሲታይ ሁሉ የተሟላለት የሚመስልና ኀዘንተኛ የማይመስል ሰዉ ነዉ፡፡ጸሎቱና ምኞቱ ሁሉም የሰዉ ዘሮች ከእዉነተኛዉ አምላክ አንድነትና ህብረት ፈጥረዉ አምላካቸዉን በእዉነትና በመንፈስ እንዲያመልኩትና እንደ ቃሉ ሆነዉ በመገኘት በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ በበረከት፣ በፍቅር፣ በሰላም፣ በመተሳሰብ፣ በመረዳዳት፣ በቅንነት፣ በእዉነተኛነት፣ በርኅራኄ፣ በቸርነት፣ በይቅርባይነት፣ በደስታ፣ በጤና እንዲኖሩና ከሁሉም በላይ ደግሞ ሕያዉ ሆነዉ እንደ ቅዱሳን መላእክት በሚኖሩበት ለእግዚአብሔር ሰማያዊ መንግስት እንዲበቁ ነዉ፡፡

ጸሐፊዉ ዉጫዊ ጠባዩ ለሰዎች ስሜት እጅግ የሚጠነቀቅ፤ የራሱም ስሜት በቀላሉ የሚጎዳ፤ በዚህም ምክንያት ስሜቱ ሊጎዳበት ከሚችል ከማንኛዉም ነገር መራቅን የሚመርጥ ነበር፡፡ ከሁሉ ሰዉ ጋር በሰላምና በፍቅር፣ በመተሳሰብ መኖርን የሚፈልግ፤ ሌሎች ከሚጎዱበት ራሱ መጎዳትን የሚመርጥ ሰዉ ነዉ፡፡ በእግዚአብሔር አገልገሎት ወስጥ ደግሞ ማንም ሰዉ ስለ እዉነት ራሱን መካድና ስለ እዉነት መመስከር አለበት እንጂ ከእግዚአብሔርና ከሙሉ እዉነታ አስበልጦ ለራስና ለሰዉ ስሜት ቅድሚያ መስጠት ስለማይቻል ያለዉን ሙሉ እዉነታ በመጽሐፉ ዉስጥ ለራሱ ሆነ ለሌላዉ ስሜት ቅድሚያ ሳይሰጥ እግዚአብሔር ያጻፈዉን በሙሉ ጽፏል፡፡

ምንም እንኳን አንዳንድ ሰዎች ስለተገሰጹና ገበናቸዉ ስለተጋለጠባቸዉ እንዲሁም የዐመፃ ስራቸዉ ስለተመሰከረባቸዉ እዉነትን ስለማይፈልጉና ራሳቸዉን ለንስሐ ለማብቃት ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ ምክንያት ኅሊናቸዉን በማደንደን ለጥል፣ ለበቀል፣ ለጥላቻ ሊነሳሱ እንደሚችሉ ቢታወቅም፤ እግዚአብሔር ያሳሰበዉንና የተናገረዉን አንዳች ሳይቀንስና ሳያስመስል በግልጽ በመጽሐፉ ላይ አስፍሯል፡፡ ስለዚህ እንደ ታናሽ ወንድምነቴ የምመክረዉ ማንም ሰዉ በተገሰጸዉ ሆነ ገበናዉ በተጋለጠበት የዐመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ስራዉ ፈጥኖ ንስሐ እንዲገባና ከአምላኩ እንዲታረቅ፤ እንዲሁም አንድነቱንና ህብረቱን ከእዉነት ጋር ብቻ እንዲያደርግ ነዉ እንጂ ለዚህ ቅርፊት ሥጋዉ ሳስቶና ለጊዜያዊዉ ስልጣን፣ ክብር፣ ጥቅም፣

ብልጽግና፣ ዝና ሲል ከፈጣሪዉ ጋር እንዳይጣላና በሕያዉ ነፍሱ ላይ የሞት ሞት ፍርድ እንዳያመጣ ነዉ።

በዐይን የሚታየዉም የማይታየዉም በእግዚአብሔር እይታና ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነ ማንም ፍጡር በራሱ ስልጣንና ኃይል ማንንም ምንም ሊያደርግ አይችልም። ይልቁኑ በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ የሚቃወምና ለጥቃት የሚነሳ ከሆነ እጅግ የከፋዉን ቅጣት ይቀበላል። ለሥጋዉም ለነፍሱም ሳይሆን የንስሐ እድሜዉን ያሳጥራል። እግዚአብሔር ከፈለገ በዐይን ቅጽበት ጊዜ ዉስጥ የሚታየዉንንም የማይታየዉንም ከመኖር ወደ አለመኖር ሊያሳልፍ ይችላል። ምክንያቱም እያንዳንዱ ፍጥረት ከእርሱ በወጣ ኃይል የተዋቀረና በእርሱ እይታና ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነ ነዉ። በተቃራኒዉ ደግሞ አሁን ከሚታዩትና ከማይታዩት ፍጥረታት በእልፍ አእላፋት እጥፍ በዐይን ቅጽበት ዉስጥ ካለመኖር ወደ መኖር ሊያመጣ የሚችል አምላክ ነዉ።

ስለዚህ የአዳም ዘር የሆን ሁላችንም ተራ፣ ወራዳ፣ ኃጢአተኛ ሰዎች መሆናችንን አምነን እጃችንን ለእግዚአብሔር መስጠትና ለፈቃዱ መሰለፍ ይጠበቅብናል እንጂ ለወንበሬ፣ ለክብሬ፣ ለጥቅሜ፣ ለዝናዬ.. ወዘተ በማለት ለቅርፊት ሥጋችን በመቆም « እንዴት እንዲህ እንባላለን? እንዴት ማንነታችን ይገለጻል? እንዴት የዐመፃ ስራችን ለዓለም ይተዋወቃል? እንዴት ገበናችን ይወጣል? እንዴት እንደዚህ እንደፈራለን?.. ወዘተ» በማለት ለክፋት፣ ለተንኮል፣ ለምቀኝነት ፣ ለጥላቻ፣ ለበቀል፣ ለዐመፃ፣ ለክህደት፣ ለርኩሰት፣ ለግድያ፣ ለጥፋት፣ ብንሰለፍ በመቶ እጥፍ የምንጎዳዉ ራሳችን ነን እንጂ የእግዚአብሔር አገልጋዮችንንና መልእክተኞችን አንዳች ልናደርጋቸዉ አንችልም። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የሆነ ሰዉ በሚሊዮኖች አይደለም በቢሊዮን የሚቆጠሩትን በእግዚአብሔር ኃይል ድል ሊያደርጋቸዉ ይችላል። ምክንያቱም ሁሉን የሚያደርገዉ እግዚአብሔር ነዉና ለእግዚአብሔር ደግሞ ሁሉ ቀላልና ተራ ነገር ነዉ።

በመሆኑም በራሳችን ስልጣን እንኳን መስራትና መናገር ቀርቶ ማሰብ የማንችል የመጨረሻ ተራ ሰዎች መሆናችንን ልናምን ይገባል። እግዚአብሔር በነጻነት ስለሚገዛ ነዉ እንጂ የዐመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባራችንን ታግሶ ታግሶ ጽዋዉ ሞልቶ ሲፈስ የማያዳግም እርምጃ በእያንዳንዱ ዐመጸኛ ላይ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ይወስዳል። የእግዚአብሔር ፈቃዱ ማንኛዉም ሰዉ በሥጋ ሞት እስከሚጠራ ድረስ በነጻነት በእዉነትና በመንፈስ እንዲያመልኩት ነዉ። ነገር ግን እያንዳንዱ ሰዉ በተሰጠዉ ነጻ ኅሊና ተመርቶ ነገሮችን በማመዛዘንና በማገናዘብ በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት፣ በመልካም ተግባር

ካልተሰለፈ በምድራዊ ሕይወቱ ዘመን ሆነ ነፍሱ ከዚህ ሥጋዉ ስትለይ እንደ ዐመፃዉ ደረጃ ዋጋ ይከፍልበታል፡፡

በእግዚአብሔር አሰራር ዉስጥ በግማሽ እዉነታ ሆነ ሙሉ እዉነታ ባልሆነ ተግባር እግዚአብሔርን ማስደሰትና ሙሉ ፍሬ ማፍራት አይቻልም፡፡ በዓለም ላይ የሚታየዉ ሰዎች ቁንጽል እዉነታ ይዘዉ በወርቃማ ቃላቶችና አባባሎች ተሸፍነዉ የዲያብሎስን ፈቃድ በአራቱም ማዕዘን ሲፈጽሙና ሲያስፈጽሙ ነዉ፡፡ በሃይማኖትና በፖለቲካ ሕይወት ስንመለከት ደረጃዉ ቢለያይም በዉስጡ ያሉት ሰዎች የተወሰነ እዉነት ይዘዉ ነዉ «በእዉነት እናገለግላለን፤ የሕዝብ አገልጋይ ነን፤» በማለት ሕዝቡ ለእግዚአብሔርም ለዲያብሎስም እንዲገዛ በማድረግ በዐመፃ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ እንዲመላለስ የሚያደርጉትና ምናልባት የያዙት እዉነት ከ1 እስከ 90 ፐርሰንት ሊደርስ ይችል ይሆናል፡፡ 90 ፐርሰንት ከ80 ፐርሰንት እንዲሁም 50 ፐርሰንት ከ40 ፐርሰንት የተሻለ ቢሆንም፤ በጎደሎ እዉነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሙሉ በሙሉ ለመፈጸም ሆነ ለማስፈጸም አይቻልም፡፡ የዓለም ሕዝብ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጆቹ ስለሆኑ በሙሉ እዉነት ብቻ ሊገለገሉና ሊጠበቁ ይገባል እንጂ በተወሰነ ፐርሰንት የዲያብሎስ ፈቃድ፣ በተወሰነ ፐርሰንት የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም በማድረግ የእግዚአብሔር ሕዝብነታቸዉንና ልጅነታቸዉን ማስጠበቅ አይቻልም፡፡

ሰዎች ለስልጣን፣ ለክብር፣ ለጥቅም፣ ለግል ብልጽግና፣ ለዝና ባላቸዉ መስገብገብና ራስ ወዳድነት ለራሳቸዉ የሚመች የራሳቸዉን እዉነት ፈጥረዉ ሕዝቡን ለራሳቸዉ ፍላጎትና ዓላማ ያሰልፉታል፤ በስሙ ይነግዱበታል፤ ከእግዚብሔር ጋር ያጣሉታል፤ የዲያብሎስን ፈቃድ ይፈጽሙበታል፤ ያስፈጽሙበታል፤ እግዚአብሔርን ያስቆጡበታል፤ በዚህ ምክንያት ሕዝቡን ለመከራ፣ ለችግር፣ ለስቃይ፣ ለልመና፣ ለስደት፣ ለእስርና ለሞት ይዳርጉታል፡፡ ራሳቸዉን ግን ለተንደላቀቀና ለድሎት ሕይወት እንዲሁም ለተለየ ክብረትና ግነት ያዘጋጃሉ፡፡ በዓለም የሚታየዉ እዉነታ ይህ ነዉ፡፡ የእግዚአብሔር እዉነታ ግን በመሪነት ሆነ በባለስልጣንነት እንዲሁም በተለያየ ኃላፊነት ያሉት ሁሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ አገልጋይ(ባሪያ)ና እረኛ ናቸዉ እንጂ በሕዝብ ላይ የሚሰለጥኑና የሚነግሡ አይደለም፡፡ እንደ አገልጋይነታቸዉ፣ ሕዝቡ ሊደረግላቸዉ የሚገባዉን ያደርግላቸዋል እንጂ በሕዝብ ገንዘብና ንብረት ላይ አይሰለጥኑም፤ ለራሳቸዉ መጠቀሚያና እንዲሁም አድሎና በደል መፈጸሚያ አያደርጉም፡፡ ምክንያቱም ተጠሪነታቸዉ ለአምላክ ሲሆን አገልጋይነታቸዉ (ባሪያነታቸዉ) ደግሞ ለሕዝብ ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት ሁል ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና

ለማስፈጸም ይተጋሉ እንጂ ከዲያብሎስ ጋር አንዳች አንድነት ሆነ ህብረት ፈጥረዉ ሕዝቡን በዐመፃ ሕይወት እንዲመላለስና ከአምላካቸዉ ፈቃድ እንዲወጡ አይደርጉም።

አሁን በዓለም የሚታዩት የዓለም መንግስታት ከኢትዮጵያ መንግስት ጭምር በበላይ ዲያብሎስ የሚመራቸዉና ፈቃዱን የሚያስፈጽማቸዉ ሲሆን፤ የዐመፃና የክህደታቸዉ ጽዋ ሞልቶ እያፈሰሰ ስለሆነ እያንዳንዱ መንግስት፣ ቡድን፣ ግለሰብ የዘራዉን የዐመፃ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፍሬ በማጨድና መራራዉን ጽዋ በመጠጣት ላይ ይገኛል። ከእንግዲህም እያንዳንዱ መንግስት እጁን ለእግዚአብሔር እስከሚሰጥ ድረስ የባሰዉን የቅጣት ጽዋ እየጠጣ ያልፋል እንጂ፤ እግዚአብሔር እጅግ በቅርብ ጊዜ ዉስጥ በኢትዮጵያ ምድር የሚዘረጋዉን መንግስቱን ሊያስቀር ሆነ ሊያዘገይ የሚችል አንዳች ኃይል ሆነ አቅም ማንም ሰዉ የለዉም። ስለዚህ እያንዳንዱ የዓለም መንግስታት ሆኑ አሁን በወንበር ላይ ያሉት «የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪዎች ነን» ከሚሉት ጭምር ካለምንም ቅድመ ሁኔታና ድርድር ወንበሩን ለእግዚአብሔር እዉነተኛ እንደራሴዎች እንዲለቁና በእዉነተኛ ንስሐ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር በመስጠትና እርሱ በሚያዘጋጀዉ ስርዐት ሊመላለሱ ይገባል። ምክንያቱም ጥቅሙ ለራሳቸዉ ነዉና።

« እግዚአብሔርንም አናዉቅም፤ ትዕዛዙንም አንጠብቅም፤ መልእክቱንም አንቀበልም» ቢሉ ደግሞ፤ የዐመፃ ልጆች ከምድሪቱ እንደሚጸዱና ኢትዮጵያም ሆነች ዓለም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ለተመረጡትና ለተቀቡት ለኢትዮጵያዉያኑ በሥጋዊና በመንፈሳዊ ወንበር ላይ ለሚቀመጡት ለአንድ ንጉሠ ነገሥትና ለአንድ እጨጌ ተላልፋ እንደምትሰጥ እግዚአብሔር ተናግሯል። « ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል?» የሚል ሰዉ ካለ ደግሞ ፈጣሪዉን የንስሐ እድሜ ይለምን እንጂ አሁን ባለነዉ ትዉልድ በቅርቡ በዓለም ላይ የሚታይ ነዉ። የዓለም ሕዝብ ግን አሁን በሚያሳየዉ ደንዳና ኅሊና በእግዚአብሔር ቁጣ ለመጠረግ ራሱን እያዘጋጀነዉ እንጂ እዉነትን ለመቀበል ፈቃደኛ አይደለም። ትዉልዱ ግን፣ ማንም አይነካቸዉም የተባሉት በእግዚአብሔር ቁጣ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ከወንበራቸዉ እያተቆረጡ በዐይኑ እያየና ከተለያዩ ታሪኮች እያነበበ የስልጣን እድሜዉን ለማስረዘም ከንቱ ሥጋዊ መጠበብን ያደርጋል።

ጸሐፊዉ በማንም ድርጅት ሆነ ግለሰብ አንዳች በደል ያልተፈጸመበትና በማንም ላይ አንዳች ጥላቻ ሆነ በቀል የሌለዉ ሲሆን፤ የዲያብሎስን ስራ ግን ዋና ተቃዋሚና የዲያብሎስን ፈቃድ ከሚፈጽሙት ጋርም አንዳች አንድነት ሆነ ህብረት የሌለዉ ነዉ። ከዲያብሎስ አገልጋይነታቸዉ በእዉነተኛ ንስሐ ቢመለሱ ደግሞ በእዉነት አንድነትና ህብረት ሊፈጥር የሚችል ነዉ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የተዘጋጀ ነዉ። እያንዳንዱን ሰዉ የሚመለከተዉ በዉጫዉ ገጽታዉ ወይንም ባለዉ ቁሳቁስና ስልጣን

ሳይሆንበእያንዳንዱ ሰዉ ግንባሩ ፊት ለፊት በአንጎል ዉስጥ ያለችዉን በተለምዶ እእምሮ ወይንም ኅሊና በጥንቱ አጠራር ደግሞ ልቦና በመባል የምትታወቀዉና ሰዎች የተገለጹበት ሥጋ(ሰዉነት) በድን እንዳይሆን ሕይወትን ሰታ የምታንቀሳቅሰዉን አካላዊና ረቂቅ ነፍሱን ብቻ ነዉ:: ቅንነት የጎደላት፣ እዉነተኛነት የሌላት፣ መልካም የሆነዉን የምትጠላ፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ ትዕቢት፣ ዐመፃ፣ እብሪት፣ ርኩሰት፣.. ወዘተ የሞላባት ነፍስ በየትኛዉም መልክና ቁሳቁስ፣ እዉቀትና ጥበብ፣ እንዲሁም ኃይልና ስልጣን ትገለጽ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ የሌላትና እንደ ሰይጣናት በዐመፀኛነት ስለምትታይ፤ በእዉነተኛ ንስሐ ከአምላኳ ጋር ታርቃ ከእዉነት ጋር አንድነትና ህብረት እስካልፈጠረች ድረስ ጸሐፊዉ የሚመለከታት በእግዚአብሔር እይታ እንደ ዐመፀኛነቷ ነዉ::

ዓለምንም በነጥብ ደረጃ ነዉ የሚመለከታት:: ምክንያቱም ይህ የምናየዉ ዓለም ከእሱ ዉጭ ያለዉ ዓለም እግዚአብሔር እንደ አማናዊ ባሕርይዉ የሚኖርበት ቦታ «አማናዊ ሕዋ» በመባል የሚታወቀዉ መጀመሪያና መጨረሻ ለሌለዉ ቦታ ሲካፈል ማለትም አንድ ሚሊዮን ቁጥር ለትየለሌ ወይንም ለኢንፊኒቲ(∞) ቢካፈል የሚሰጠን ቁጥር አልቦ(ዜሮ) ስለሆነ፤ የዚህች ዓለም መጠንም ከቀሪዉ ዓለም ጋር ሲነጻጸር የአፈር ብናኝ አይደለም የአተም መጠን ያህል እንኳ አትሆንም:: ምድራዊ ዘመኑንም የዐይን ቅጽበት እድሜ እንኳ የማትሞላ መሆኑን ነዉ ያስተዋለዉ:: ምክንያቱም ከቅርፊት ሥጋዉ ሲለይ ለሕያዉነት ዘመን እንደሚኖርና ምድራዊ ዘመን ቆይታዉን ለትየለሌ ወይንም ለኢንፊኒቲ(∞) ዘመን ቢካፈል አልቦ(ዜሮ) ዉጤት ስለሚሰጥ የእያንዳንዱ ሰዉ ምድራዊ ዘመን ቆይታዉ ከሥጋ ሞት በኋላ ከሚኖራዉ እድሜ አንጻር ሲታይ ከዐይን ቅጽበት ( ከማይክሮ ሰከንድ) እድሜ የማይበለጥ ነዉና::

ሌላዉ ለመግለጽ የምፈልገዉ እያንዳንዱ ቃላት፣ ዐረፍተ ነገር፣ አንቀጽ፣ ምእራፍ የተጻፈበት ምክንያት ስላለዉ፤ እያንዳንዱ አንባቢ « እግዚአብሔር ምን ሊያስተምረኝና ሊያሳዉቀኝ ፈልጎ ነዉ በዚህ መልኩ እንዲገለጽ ያደረገዉ?» በማለት አጻፊዉን መንፈስ ቅዱስን መጠየቅ ነዉ ያለበት እንጂ ነጥብ በማትሞላዉ እዉቀቱ፣ ከልምሾነት በማያልፈዉ ኃይሉ ተመክቶ፣ በሥጋና ደም ስሜቱ ተመርቶ የሚያነበዉ ከሆነ ይሰናከልበታል፤ ይወድቅበታል፤ ይደመሰስበታል:: ስለዚህ ማንም ይሁን ማን ራሱን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ አድርጎ ተራነቱን ተረድቶ ታላቅ ተስፋዉን አስተዉሎ እዉነተኛ ማንነቱን አዉቆ እንዲያነበዉና እንዲረዳዉ በትህትን አሳስባለሁ:: እንዲሁም እግዚአብሔር ሊያደርግ የወሰነዉን ማስቀረት ሆነ ማዘግየት ማንም ሰዉ አይችልምና ራሱን ክዶ ከሙሉ እዉነት ጋር ይሰለፍ እንጂ «ቤተሰቤ፣ዘመዴ፣ዘሬ፣ ጎጤ ፣ ወገኔ.. ወዘተ» እያለ ከሐሰት ጋር ከቆመ ከመዉደቅና

ከመጠረግ ሊተርፍ አይችልም:: በመሆኑም ማንም ሰዉ የሚያመዛዝንና የሚያገናዝብ ኅሊና አለዉና አቋሙን አስተካክሎ የሚያዋጣዉን እዉነተኛዉን አምላክ እንዲመርጥ በማክበር እጠይቃለሁ:: ጸሐፊዉ ቀደም ሲል አቋሙ በዚህ መልክ ያልነበረ ሲሆን፤ አሁን ግን እግዚአብሔር፤ እሱም(ጸሐፊዉ) ሆነ ሌላዉም የሰዉ ዘር ወደ ሙሉ እዉነታ እንዲመጣ ፈልጎ ነዉና ያለዉን ምድራዊ ሆነ ሰማያዊ እዉነታን ያጻፈዉ፤ እያንዳንዱ ሰዉ እንደ ጸሐፊዉ አፋጣኝ አቋም ማስተካከያ ርምጃ ወስዶ ወደ ሙሉ እዉነት ትዉልዱ እንዲመጣ እንደ ታናሽ ወንድምነቱ ይመክራል::

ባጠቃላይ እግዚአብሔር የፈቀደዉ በዚህ መጽሐፍ ተጽፏል:: ሊቀበለዉ የሚገባ ይቀበለዉ፤ ሊቀበለዉ የማይፈልግ ደግሞ ዋጋ እንደሚከፍልበት አዉቆ አይቀበለዉ:: ለእያንዳንዱ ምርጫዉ ክፍት ነዉ:: እግዚአብሔርን የሚል ግን የወገኖቹ ጥፋት አሳስቦት ይህን ሁለተኛዉን የእግዚአብሔር መልእክትን ሆነ በመስከረም ፳፻ወ፫(2003) ዓ.ም. የተጻፈዉን የመጀመሪያዉን የእግዚአብሔር መልእክት አንዳች ሳይጨምርና ሳይቀንስ ለወገኖቹ ለኢትዮጵያዉያንና ለአዳም ዘሮች በሙሉ ያስተላልፍ::

ጸሐፊዉ ባለፈዉ ዓመት በመስከረም ወር ፳፻ወ፫(2003) ዓ.ም በእግዚአብሔር ትዕዛዝ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ!» በሚል አርስት የተጻፈዉን የእግዚአብሔር መልእክት፣ እግዚአብሔር ለራሱ ዓለማ ላስነሳቸዉ አካላት እንዲሰጥ በታዘዘዉ መሰረት ለሚወክሉት ግለሰቦች ቢሰጥም ተቀባይነት ባለማግኘቱና መልእክቱም እንዲዳፈን በመደረጉ፤ ከእግዚአብሔር ሳይታዘዝ የወገኖቹ መጥፋት አላስቻለዉምና በራሱ ቅንነት አሳብ ተነሳስቶ በመጽሐፍ መልክ አሳትሞ ለጥቂት ሰዎች የሰጠና በኋላም በእግዚአብሔር እንዲያሰራጭ እስከሚታዘዝ ድረስ ያቆመ ሲሆን፤ እንዲሁም በየካቲት ወር ፳፻ወ፫(2003)ዓ.ም. ለተወሰኑ ግለሰቦችና ለተለያዩ መገናኛ ብዙኃን  በኢሜል አድራሻቸዉ መልእክቱን ያስተላለፈ ቢሆንም መልእክቱን አንብቦ በግልጽ «የእግዚአብሔር መልእክት ነዉ::» ብሎ የተቀበለዉና ለወገኖቹ ያደረሰ አንድ ሰዉን ብቻ  ነዉ ከዉጭ አገር ያገኘዉ:: በዚህም ምክንያት ከኀዘን ዉጭ አንዳች ተስፋ ሳይቆርጥ ለ፳፻ወ፬(2004) ዓ.ም ደርሶ እግዚአብሔር ሁለተኛዉን መልእክት ከመስከረም፳፻ወ፬(2004)ዓ.ም አጋማሽ እስከ ታህሳስ መጀመሪያ ድረስ እንዲጽፍ አድርጎታል::

ከዚህ በተጨማሪ በኀዘን ዉስጥ እያለ ጥቅምት ፳፯፥፳፻ወ፬( 27/2004) ዓ.ም ከእግዚአብሔር፤ በተለመደዉ ነፍሱ ብቻ በምትሰማዉ ድምጽ የመጀመሪያዉንም ይህንንም ሁለተኛ መልእክት ለወገኖቹ ለአዳም ዘር እንዲያሰራጭ ተነግሮታል:: ለአንድ ዓመት ያህል

እንቆቅልሽ የነበረዉ የእግዚአብሔር መልእክት ስርጭት ተፈቶለት አሁን በሙሉ ነጻነትና ፈቃድ ያገኘ ስለሆነ የእግዚአብሔርን መልእክት እግዚአብሔር ባሰሰበዉና በመራዉ መንገድ ሁሉ ለወገኖቹ ለአዳም ዘር በተጠናከረ መልኩ ያደርሳል፡፡

ጸሐፊዉ በሰዉ ለመወደድ ወይንም ድጋፍ ለማግኘት ወይንም ተቀባይነት ለማግኘት ሲል በእግዚአብሔር መልእክት ላይ አንዳች የሚቀንሰዉና የሚያሻሽለዉ ነገር እንደሌለ በዚሁ አጋጣሚ ያሳዉቃል፡፡ እንዲሁም ማንም ሰዉ ከሚሰድበዉና ከሚያዋርደዉ በላይ ራሱን ያዋረደ ስለሆነ ማንኛዉንም ስድብ ሆነ ትችት በጸጋና በአኮቴት እንደሚቀበለዉ ይገልጻል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የእግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ አምላኩን ለማክብር ሲል አሟሟቱ በከፋ መልኩ እንዲሆን ስለሚፈልግ ቅርፊት ሥጋ ለባሽን ፈርቶ እዉነትን ለዓለም ከማሳወቅ ወደ ኋላ የማይል በራሱና በሚያፈቅራቸዉ፣ በሚወዳቸዉ፣ በሚንሰፈሰፍላቸዉ በቤተሰቡ ላይ ጭምር የፈረደ፤ ሰማያዊዉን የእግዚአብሔር መንግስት በናፍቆት የሚጠባበቅ መሆኑን እንዲታወቅለት ይፈልጋል፡፡

# መቅድም

በመጀመሪያ ሳይገባኝ ለእግዚአብሔር መልእክት ጸሐፊነት በመመረጤ የሁሉ ፈጣሪ የሆነዉን እዉነተኛዉን አምላክ አመሰግናለሁ::

የተከበራችሁ አባቶቼ እናቶቼ ወንድሞቼ እህቶቼ፤ እግዚአብሔር ከብሉይ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ሕዝቡን በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ይናገራል፤ ያስተምራል፤ ይገስጻል፤ ያስጠነቅቃል:: የእግዚአብሔርን ቃል ሰምቶ ከበደሉ፣ ከዐመፃዉ፣ ከክህደቱ ባጠቃላይ ከኃጢአት ተግባር የሚመለስና እዉነተኛ ንስሐ የሚገባ ሰዉ ተጠቃሚ ይሆናል:: በተቃራኒዉ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል የማይሰማ፣ ኅሊናዉን የሚያደነድን ሰዉ ስለ ዐመፃዉ ሆነ ስለ ክህደቱ በመቶ እጥፍ ዋጋ ከፍሎበት ተዋርዶ፣ ተቀቶ ያልፋል:: ወደ ሁለተኛዉ ዓለም ዳግም የንስሐ እድል ወደማያገኝበት ቦታ ይጓዛል:: ለዚህም ማስረጃ በተለያዩ ታሪኮችና መዋዕለ ዜናዎች ላይ ተገልጿል:: እንዲሁም በዚህች በአጭር ዘመናችን እንኳ በዐይናችን ብዙ አይተናል፤ በጆሮዋችንም ሰምተናል::

እግዚአብሔር በተለያየ ዘመን መልእክቱን በአገልጋዮቹ ነብያት፣ መምህራን፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን፣.. ወዘተ አማካይነት ለሕዝቡ ቢያስተላልፍም መሪዎች ሆኑ ሕዝቡ አልተቀበሉትም:: ይልቁኑ በመልእክተኞቹ ላይ የተለያየ መከራና ስቃይ ነዉ ያደረሱባቸዉ:: በዚህም ዋንኞቹ ዐመፀኞች፣ ተቃዋሚዎች፣ አሳዳጆች፣ ገዳዮች፣ በመሪነት ላይ ያሉ ሥጋዉያን መሪዎችና ባለስልጣናት እንዲሁም መንፈሳዊያን የሃይማኖት መሪዎችና አስመሳይ አገልጋዮች ናቸዉ:: ይሁንና እነሱ አለፉ እንጂ እዉነት እስከአሁን ድረስ ሙሉ በሙሉ ማንም ሊያጠፋት አልቻለም::

እግዚአብሔር እንደ ሰዉ ለዉሳኔ ሆነ ለፍርድ አይቸኩልምና እያንዳንዱ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ፈጻሚንና አስፈጻሚን ታግሶ ታግሶ በተለያየ ዘመን በተለያየ መልኩ ዋጋ እንዲከፍሉበት እያደረገ ወደ ሁለተኛዉ መቀጫ ቦታ ጠርቷቸዋል:: እዉነተኞችን ደግሞ በክብርና በድል አክሊል አሳርፏቸዉ ወደ መንግስቱ አስገብቷቸዋል:: በኛ ዘመንም እግዚአብሔር በምርጥ ባለሟሎቹና እንደራሴዎቹ እንዲሁም በአገልጋዮቹ አማካይነት መልእክቱን ቢያስተላልፍም የሚሰማዉ ሰዉ አላገኘም:: ይልቁኑ እንደ ቀድሞዎቹ ዐመፀኛ ሰዎች፤ መልእክት አምጪዎችን የሚያሳድድና የሚያሰቃይ፣ የሚያስር፣ የሚገል ትዉልድ ነዉ የተፈጠረዉ:: አሁን ደግሞ እግዚአብሔር፤ «እስቲ ትዉልዱ የሚቀበለዉና ሌት ተቀን

ፈቃዱን ለመፈጸም የሚተጋለት ዲያብሎስንና ጭፍሮቹን ሰይጣናትን ስለሆነ « የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር!» በሚል አርስት ያለዉን ሙሉ እዉነታ አስተላልፎልናል።

ጸሐፊዉ እንደማንኛዉም የአዳም ዘር የእግዚአብሔር ግሳጼ የሚመለከተዉና «ለምን እንዲህ አባላለዉ?» የማይል፤ በቅንነትና በእዉነት የሚቀርብለትን ግሳጼና ምክር ሁሉ በፍጥነት ለመጠቀም የሚሽቀዳደም አንዳች የተለየ ክብርን፣ ምስጋናን፣ ሽልማትን፣ ዝናን፣ ጥቅምን የማይፈለግ ነዉ። ለእነዚህም ሲል ኅሊናዉን የማይሸጥ እዉነትን ብቻ የሚፈልግ ነዉ። በዚህ መጽሐፍ እግዚአብሔር፤ ጸሐፊዉ ከዚህ በፊት ሆነ አሁን ባለነበበዉ፣ ባልሰማዉ፣ ባልተመለከተዉ ለየት ያላ አጻጻፍ እንዲጽፍ አድርጎታል። ጸሐፊዉ ከዚህ በፊት የሚያዉቀዉ ማንኛዉም የእግዚአብሔር መልእክት « እግዚአብሔር ይላል» እያለ ነዉ። በዚህ መጽሐፍ ደግሞ እያንዳንዱ ምእራፍ መጨረሻ ላይ «የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ይላል» ነዉ የሚለዉ።

ይህም የሚያሳየዉ ለዘመናት ትዉልዱ ከእግዚአብሔር መልእክት ይልቅ የዲያብሎስን መልእክት ስለሚሰማና ዲያብሎስ የሚያሳስበዉንና የሚናገረዉን ስለሚፈጽም እግዚአብሔር፤ « እስቲ ትዉልዱ በሚቀበለዉና በሚሰማዉ መልክ ላቅርብለት» በሚል አሳብ በዚህ መልኩ እንዲጻፍ እንዳደረገ ጸሐፊዉ ያምናል። ተናጋሪዉ ዲያብሎስ ቢመስልም እግዚአብሔር እዉነታዉን እንድናዉቅና ከዲያብሎስ ፈቃድና ከእግዚአብሔር ፈቃድ በግልጽ ምርጫ እንድናደርግ ፈልጎ ነዉ በዚህ መልኩ እንዲጻፍ ያደረገዉ። ስለዚህ እያንዳንዱ ሰዉ የሥጋና የደም ስሜቱ ሳያይልበትና በእያንዳንዱ ሰዉ ኅሊና ለመፈታተንና ለማዳከም እንዲሁም ለማጎሳቆል ለዐይን ቅጽበት እንኳ ለማይለዩት ለርኩሳን መናፍስት ኅሊናዉን አሳልፎ ሳይሰጥ፤ በቅንነት፣ በእዉነት፣ በትዕግስት «እኔ አዋቂ ነኝ፤ ንጹህና ቅዱስ ነኝ፤ ትክክለኛ ነኝ፤» ብሎ ራሱን ሳያመጻድቅና በራሱ ሳይመካ « እግዚአብሔር ምን ይለኛል? ምንስ ሊያሳዉቀኝ ፈልጎ ነዉ በዚህ መልኩ መልእክቱን ያስተላለፈዉ? እኔም ምን አቋም መዉሰድ አለብኝ?» በማለት በትሕትና ከመጀመሪዉ እስከ መጨረሻዉ ድረስ በተረጋጋ መንፈስ ዉስጥ ሆነን እናንበዉ፤ አንብቡት።

ግልጽ ካልሆነላችሁ ደግሞ በጸሎት አምላካችሁን በመጠየቅ ደጋግማችሁ አንብቡት። ከዚያም ዲያብሎስ «አድርጉ» የሚላችሁንና ደስ የሚሰኝበትን አታድርጉ። እርሱ የማይፈልገዉንና የሚጠላዉን ደግሞ አድርጉ። ጸሐፊዉ የራሱ ስራና ፈጠራ ስላልሆነ እንደ ማንኛዉ ሰዉ ጽሑፉን ያነባል፤ በሚያስለቅሰዉ ቦታ ላይም ያለቅሳል፤ በሚያሳዝነዉ ቦታ ላይም ያዝናል። በሚያስቆጨዉ ቦታ ላይም ይቆጫል። በታላቅ ተስፋዉ ደግሞ እጅግ

ይጽናናል። ማንነቱንም በደንብ አዉቆ እንደማንነቱና እንደተራነቱ ራሱን በአምላኩና በፈጣሪዉ ፊት ዝቅ አድርጎ ይኖራል፤ በእዉነትና በመንፈስ አምላኩን ያመልካል፤ የተለያዩ እዉቀቶችንም ከመጽሐፉ አግኝቷል።

ሌላዉ ጸሐፊዉ የራሱን ሆነ የእያንዳንዱን ሰዉ ያደፈና የጎደፈ ባሕርይ እንዲሁም ጎሰቋላ ኑሮና ሕይወት በደንብ ስላስተዋለ፤ እያንዳንዱን ሰዉ የሚመለከተዉ እግዚአብሔር፤ እንዲያይበት በሰጠዉ ዐይን ነዉ እንጂ ማንም እንዲታይበት በሚፈልገዉ መልኩ አይደለም። ለሰዉ ዐይን ሲታዩ ለዐይን የማይገቡ ምስኪኖች የሆኑ እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮችን ግን የመመልከቱ አቅምና ብቃት የሌለዉ ስለሆነ እነሱ እንዲመለከቱት የሚመኝ ሰዉ ነዉ። ከዚህ በተጨማሪ ማንንም ሰዉ በቀለሙ፣ በነገዱ፣ በዘሩ፣ በቋንቋዉ፣ በሃይማኖቱ ምክንያት የማይጠላና ልዩነት የማያደርግ «ሁሉም ሰዉ የአዳም ዘር ነዉ፤ አባቴ፣ እናቴ፣ ወንድሜ፣ እህቴ፣ ልጄ፣ ናቸዉ።» ብሎ የሚያምን ነዉ። እያንዳንዱ ሰዉ ለእግዚብሔር መንግስት የታጨ ነዉ። እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆኖ ከተገኘ እንደ ምርጫዉ ሕያዉ ሆነ እንደ ቅዱሳን መላእክት በገነትና በሰማያት ዉስጥ ይኖራል፤ በተቃራኒዉ ደግሞ የዲያብሎስን ፈቃድ ነዉ የምፈጽመዉ ካለ፤ እንደ ምረጫዉ በሲኦልና በገሃነመ እሳት ዉስጥ ይኖራል ብሎ በእምነት ብቻ ሳይሆን በእርግጠኝነት ያምናል። ስለዚህ እያንዳንዱ ሰዉ ተስፋዉን ሰማያዊ አድርጎ፤ እዉነትን ሳይሸራርፍ ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ፤ አንድነቱንና ህብረቱን ከአምላኩ ጋር ብቻ አድርጎ እንዲኖር፣ ጸሐፊዉ የሚቀበለዉና የሚሰማዉ ሰዉ ካለ ራሱን ዝቅ አድርጎና ተንበርክኮ ትዉልዱን ይለምናል።

## መግቢያ

እግዚአብሔር ላለፉት ዘመናት መልእክቶቹን በተለያየ መንገድ ያደረሰ ሲሆን፤ በዚኛዉ መልእክት ደግሞ ከዚህ በፊት ባልተሞከረበት መልክ ነዉ ያቀረበዉ:: ይኸዉም ትዉልዱ ከእግዚአብሔር የሆነዉን ከመስማትና ከመፈጸም ይልቅ በጨለማዉ ገዥና መንፈስ የሚመሩትን ሰዎች የሚሰማና የሚሉትንም ስለሚፈጽም « እስቲ ትዉልዱ በሚሰማዉና በሚፈጽመዉ መልክ የጨለማዉ ገዥና በእርሱ መንፈስ የሚመሩ ሰዎች የሚሰሩትን፣ የሚናገሩትን፣ የሚያስቡትን በሚገባቸዉ ቋንቋ ይቅረብላቸዉና «በግልጽ ዲያብሎስ ይሻለናል፣ የሚናገረዉንና የሚመክረዉን ተግባራዊ እናደርጋለን እንጂ እግዚአብሔር የሚደሰትበትንና የሚፈቅደዉን አንፈጽምም» ካሉ ደግሞ የባሰዉን ዋጋ ይከፍሉበታል:: በተቃራኒዉ ደግሞ እኔን እግዚአብሔርን የሚሉ ከሆነ ደግሞ ዲያብሎስ የሚመክረዉንና የሚደግፈዉን አይፈጽሙ:: ይልቁኑ እርሱ ከሚለዉ በተቃራኒ በመሰለፍ እኔን ደስ በሚያሰኝ ሕይወት ይመላለሱ» በማለት ነዉ በዚህ መልኩ መልእክቱ ለትዉልዱ እንዲደርስ ያደረገዉ::

በክፍል አንድ የጨለማዉ ገዥ አንዳች እንዳይቀባጥር በእሳት ሰንሰለት ተጠፍሮ« እናንተ የአዳምና ሔዋን ዘሮች» እያለ ተግባሩን፣ ንግግሩን፣ አስተሳሰቡንና ምክሩን ያቀርባል:: « እናንተ አስመሳዮች ለእኔ ደግሞ ምርጦች» እያለ ይናገራል:: እንዲሁም « እናንተ ምርጦቼ እንደራሴዎቼ መሪዎች፣ ባለሟሎቼ ባለስልጣናት፣ ዉዶቼ ካድሬዎች» እያለ ያለዉን እዉነታ ዘክዝኮ ይናገራል:: ከነዚህ በተጨማሪ በእርሱ መንፈስ በበላይ መሪነትና በሽዋጅ መንፈስነቱ ስንቶቹን እዉነተኛ የሚመስሉ ነገር ግን የእርሱ አገልጋዮች መሆናቸዉን ይመሰክርባቸዋል:: በዘጠኝ ምእራፍ የተከፋፈለ ነዉ::

በክፍል ሁለት ደግሞ ያልታሰቡትና ያልተገመቱት ሰዎች ከእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ ወስጥ ካሉት ሰዎች ይልቅ ተመርጠዉ ከእዉነተኛዉ ከእግዚአብሔር አገልጋዩ ጋር ቃለ ምልልስ ያደረጉት ታሪካዊ ዉይይትና በተለየ ስፍራ እዉነትን የጠየቁ ሰዎች ስለእዉነት ምን እንደተባሉ እንዲሁም ከተለያየ ጉዳዮች ጋር የተያያዙና የተከደነዉ የተገለጸላቸዉ የተሰወረዉ እንዲያዉቁት የተደረገበትን ያሳየናል:: በሰባት ምእራፍ የተከፋፈለ ነዉ::

ክፍል ሦስት የተለያዩ መሪዎችና ባለስልጣናት እንዲሁም የእግዚአብሔር ልዩ ባለሟሎችና መልእክተኞች ያደረጉት ታሪካዊ ንግግርና ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ ብዙ ጉዳዮች ቀርበዉበታል:: እንዲሁም የተለያዩ ማኅበራዊ ጉዳዮችንና የጨለማዉ ገዥ ለ7503 ዘመን ያጠናቸዉ ጥናቶች ተገዶ እንዲገልጽ የተደረገዉ ቀርቦበታል:: በዘጠኝ ምእራፍ የተከፋፈለ ነዉ::

ክፍል አራት ደግሞ የጨለማዉ ገዥ በክፍል አንድ አድበስብሷቸዉና በዝርዝር ያልገለጻቸዉ ጉዳዮችንና እዉነታዎችን ለመግለጽ ባይፈልግም በእሳት ሰንሰለት ተጠፍሮ እየተቀጣ ሁሉንም ጉዳዮች በግልጽ ለአዳም ዘሮች ገልጿል። በአስራ አንድ ምእራፍ የተከፋፈለ ነዉ።

ስለዚህ የተከበራችሁ የአዳምና ሔዋን ዘሮች እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ምድራዊዉም ሰማያዊዉም ምስጢር ግልጽ ባለ መልኩ እንዲቀርብ ያደረገ ስለሆነ ከመጀመሪያዉ እስከ መጨረሻዉ በትዕግስት፣ በቅንነት አንብበን እግዚአብሔር በሚፈቅደዉ ሕይወት እንመላለስ። ገበናችን የተጋለጠብን ሰዎች ደግሞ ፈጥነን እዉነተኛ ንስሐ እንግባ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሊያደርግ ያሰበዉን ከማድረግ ወደ ኋላ የማይመለስና ማንም ፍጡር እቅዱንና አሳቡን ሊያስቀር ሆነ ሊያዘገይ ስለማይችል ባለችዉ አጭር ቀናቶች እጃችንን ለእግዚአብሔርና ለእዉነተኛ እንደራሴዎቹ ሰተን ፈቃዱን ብቻ ለመፈጸምና ለማስፈጸም መሰለፍ ይኖርብናል እንጂ ከሚጠረጉትና ከምድር ከሚጸዱት የዐመጻ ልጆች ጋር አንዳች አንድነትና ህብረት ፈጥረን በእግዚአብሔር እዉነታ ላይ ልንቃወምና እግዚአብሔርን ልንገዳደር አይገባም። እግዚአብሔር በተለያየ መንገድ በዚህ መጽሐፍ ዉስጥ የተናገረዉ ቃል አንዷ እንኳ አትቀርም። አሁንም እየተፈጸመ ነዉ፤ ለወደፊትም በባሰ ሁኔታ ይፈጸማል። ስለዚህ እንክርዳድ ያልተደባለቀበትን ፣ ከንቱ ሥጋዉ መጠበብ የማይታይበተን፣ የሥጋና የደም ስሜት የልተጨመረበትን፣ ባጠቃላይ ለሥጋችንም ለነፍሳችንም በሚጠቅመን እዉነት ስር ሆነን እንመላለስ፤ እንኑር። እግዚአብሔር ከመጭዉ የጥፋትና የጠረጋ ቁጣዉ ጠብቆን እዉነት ለምትነግሥበት ለመልካሙ ዘመን ለኢትጵዮጵያ ትንሳኤ ያድርሰን ይላል የእግዚአብሔርን መልእክት አምጪዉ ታናሹ ልጃችሁና ወንድማችሁ ።

## ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ የተገለጸ የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር!

# ክፍል አንድ

## ምእራፍ አንድ

« እናንተ አምላካችሁን በራሳችሁ እዉቀት ደረጃ ለመገደብና በራሳችሁ ሥጋዊ እዉቀትና ጥበብ ለማገልገልና ለመገልገል የምትፈልጉ ሊቀ ሊቃዉንትና ሊቀ ምሁራን፤ ስለ ድፍረታችሁና በራሳችሁ ስለመተማመናችሁ ያለኝን አድናቆት እየገለጽኩላችሁ፤ ለወደፊትም ከእናንተ እዉቀትና አስተሳሰብ በላይ የሆነዉን አንዳች እንዳትቀበሉ:: እንኳን ፍጡር ሰዉ አይደለም እርሱ እግዚአብሔር ተገልጾ ቢናገራችሁ፣ ቢያዛችሁ፣ ቢገልጽላችሁ፣ እንዳትሰሙ፤ እንዳትቀበሉ::

ነገር ግን እዉቀታችሁ እንዲጎለብትና እንዲበለጽግ ከኔ ከጨለማዉ ገዥ የሆኑትን ለየት ያሉ ትምህርቶችንና እዉቀቶችን ተቀበሉ:: ለምሳሌ «ሰዎች የተገኙት ከተፈጥሮ ነዉ:: ከጦጣ መሰል እንስሳ በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ ( በኢቮልሽን) አማካይነት ነዉ:: አሁን ላሉበት ብቃት የደረሱት የኒያንደርታንና የክሮማግነን እድገት ደረጃ አልፈዉ ነዉ:: እግዚአብሔር የሚባል ነገር የፈጠሩት የገዥ መደቦች ሕዝቡን ሊጨቁኑበት ለመጠቀሚነት ነዉ::.. ወዘተ» የሚሉትን እናንተም ተቀብላችሁ ሌሎቹንም ብታስተምሩ ዋጋችሁ ከኔ ዘንድ ታላቅና የተለያየ የክብር ማዕረግ የሚያስጣችሁ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ አሳዉቃችኋለሁ::

እንዲሁም እናንተ እዉቀታችሁን የምታመልኩና የምታስመልኩ የአዋቂዎች አዋቂ፤ ከእናንተ እዉቀት በላይ የሆነዉንና የተለየዉን የማትቀበሉ ሊቆች፤ ለእናንተም የተለየ አድናቆቴን እየገለጽኩላችሁ፤ እናንተ አምላካችሁ ተገልጾ « ያለዉ እዉነታ ይህ ነዉ:: ይህ ትክክል ነዉ:: ይህ ትክክል አይደለም::» ብሎ እዉነታዉን ቢገልጽላችሁ እንኳ እዉቀታችሁ ጣዖት ስለሆነባችሁ « ከእኛ እዉቅትና አስተሳሰብ የተለየ ምንም ይሁን ምን አንቀበልም::» ለማለት ወደ ኋላ የማትሉ ትዕቢታችሁ ከኔ ከጨለማዉ ገዥ ላቅ እያለ ቢያስቀናኝም ተባባሪ ስላገኘሁ በአቋማችሁ አንዳች ቅሬታ አይሰማኝም:: ይልቁና በርቱ፣ ቀጥሉበት፣ ከራሳችሁ እዉቀትና አስተሳሰብ ዉጭ ከኔ ከጨለማዉ ገዥ ካልሆነ በስተቀር አንዳች እንዳትቀበሉ::

ታዲያ አንዳንድ የእዉነት ምስጢር ያልተገለጸላቸዉ ሰዎች « እግዚአብሔር ምስጢራትንና እዉቀትን የሚገልጸዉ ጸሐፊዉ በነበረበት ዘመን ያለዉን እዉነታን ተከትሎ በጻሐፊዉ እዉቀት ደረጃና ትዉልዱም በሚቀበለዉ አይነት ሲሆን፤ በትንቢት ደረጃ የሚገልጸዉም ጸሐፊዉ በተገለጸለት በሚያዉቀዉና በሰማዉ እዉቀት ነዉ እንጂ ጸሐፊዉ ሊገባዉና ሊረዳዉ እንዲሁም ትዉልዱ ሊያዉቀዉና ሊረደዉ በማይችል መልኩ አይደለም:: በእግዚአብሔር መንፈስ ብቻ የሚመራ ሰዉ፤ ጸሐፊዉ የጻፈዉን ሊያዉቅ፣ ሊረዳና ሊገለጽለት ይችላል:: ስለዚህ ከእግዚአብሔር የሆኑ ሰዎች መሪያቸዉ አንዱ መንፈስ ቅዱስ ስለሆነ ከእግዚአብሔር የሆነዉን ማወቅና መለየት አይቸገሩም:: ትልቁ ራስን ባዶ አርጎ በእግዚአብሔር ፊት መቅረብ ነዉ እንጂ የተከደነ የማይገለጽ የተሰወረ የማይታወቅ አንዳች ነገር የለም » የሚሉትን አባባል አንዳች እንዳትቀበሉ::

ይልቁኑ ለእናንተ ሳይነገራችሁና ሳይገለጽላችሁ ከእናንተ ባነሱ ሰዎች የሚገለጽና የሚታወቅ እዉቀት ሆነ ምስጢር የቅድስናችሁና የክብራችሁን ማዕረግ ዝቅ የሚያደርግ ስለሆነ፤ አለመቀበል ብቻ አይደለም የተለያየም ስያሜ በመስጠት እንድታወግዟቸዉ፤ እንድታሳድዷቸዉ፤ ከምዕመናን ጋር እንድታጣሏቸዉ፤ ሕዝቡ እንዳይቀበላቸዉ እንድታደርጉ ታላቁን የጨለማ ምክሬን እመክራችኋለሁ::

ምክንያቱም ሙሉ እዉነትን ይዞ ከመጡ ገበናችሁ ይጋለጥባችኋል:: የእናንተን እዉቀት የሚያመልክ ሰዉ አታገኙም:: የተለየ የከበሬታና ከፍታ ቦታ አይቀርብላችሁም:: የሚያገናችሁና የሚያደንቃችሁ ሰዉ ያንሳል:: «ከእናንተ በላይ አዋቂና ከእግዚአብሔር ጋር የተለየ ግንኙነት ያለዉ ሰዉ አለ::» ተብሎ ሰዎች ሁሉ እናንተን መከተል ይተዉና በመስቀል ላይ የተሰቀለዉን አምላካቸዉን ይከተላሉ:: ፈቃዱን ለመፈጸም ለማስፈጸም ይተጋሉ:: የሰዉ አምላኪና ተከታይ አይሆኑም:: ባጠቃላይ እኔ የጨለማዉ ገዥ የምፈልገዉ ተግባር እንዳይፈጸም ማሰናከያና እንቅፋት ይሆኑብኛል:: ስለዚህ አንድ ሲደመር አንድ ሁለት መሆኑ ቢታወቅም፤ እናንተ ካላመናችሁበትና ካልተቀበላችሁት በእናንተ ፍላጎት ላይ ካልተመሰረተ በቀር በተለመደዉ አካሄዳችሁ በስብሰባ «ይታያል፤ ይገመገማል፤ ይወሰናል::» በማለት ከእግዚአብሔር የሆነዉን ሙሉ እዉነት እስከ እለተ ምጽአት ድረስ በቢሮክራሲ

አፍናችሁ ያዙ እንጂ ለሕዝብ ሆነ ለምዕመን እንዳታሳዉቁ፤ እንዳትገልጡ ከአደራ ጭምር ነዉ እኔ የጨለማዉ ገዥ ከሠራዊቶቼ ጭምር የማሳስባችሁ::

እናንተ የአዳም ዘሮች፤ በራሳችሁ ስልጣን እንኳን መስራትና መናገር ቀርቶ ማሰብ የማትችለሁ ተራ ደካማ ሆናችሁ ሳለ፣ እንዲሁም በራሳችሁ ስልጣን አንዲት ቀን በእድሜያችሁ ላይ መጨመር የማትችሉ፤ ዛሬ ትሙቱ ነገ ትሙት አንዳች የማታዉቁ፤ በራሳችሁ አንዳች ዋስትና የሌላቸዉ ሆናችሁ ሳለ፣ እኛ ሰይጣናት የማናደርገዉን እርስ በእርስ በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት ፣ ሰዉን ከሰዉ በማጣላት፣ በትዕቢት፣ በትምክህት፣ በአብሪት፣ በግፍ፣ በበደል፣ በአድሎ፣ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በመናፍቅነት፣ በጥል፣ በጥላቻ፣ በተለያዩ ባዕድና ጣዖት አምልኮ፣ በተለያዩ ርኩሰት ሕይወት የምትመላለሱትና እለት እለት እግዚአብሔርን የምታስቆጡትና እኔን የጨለማዉ ገዥን የምታስደስቱት ስለምን ይሆን!? በዚህ ምድር እንደ እኛ በረቂቅ አካል ተገልጻችሁ ቢሆን ኖሮ በእኛ ዘንድ ያለዉን ህብረትና አንድነት ፍቅር እናሳያችሁ ነበር:: እናንተ ግን ስንትና ስንት ዋጋ ተከፍሎላችሁ፣ በእግዚአብሔር መንግስት ሕያዉ ሆናችሁ የመኖር እድል ተሰቷችሁ፣ የንስሐ እድል እያላችሁ፣ በከፋና በከረፋ ሕይወት መመላለሳችሁ ስለምን ይሆን? ወይስ የኔና የባሪያዎቼን የሰይጣናትን ወዳጅነት ፈልጋችሁ ይሆን? እንደዛ ከሆነ በርቱ ቀጥሉበት በማለት ታላቁን የጨለማ ምክራችንን እንለግሳችኋለን ::

እናንተ የእግዚአብሔር መልእክቶችን በባለሚሎቹና በአገልጋዮቹ አማካይነት ደርሷችሁ እንደ ምናባዊ አሳብና በሥጋና ደም ስሜት የተጻፉ አድርጋችሁ ያጥላላችሁ፣ የናቃችሁ፣ ከቁም ነገር ያልቆጠራችሁ፣ ያላነበባችሁ፣ ያዳፈናችሁ፣ ባጠቃላይ በሥጋና ደም ስሜታችሁ ተመርታችሁ በራሳችሁ እዉቀትና አሳብ የገደባችሁ፣ አንቀበለዉም ያላችሁ፣ በመልእክቱና በጽሑፉ የተባለዉንም አንጠቀምበትም ተግባራዊ አናደርግም ያላችሁ ቆራጥና ጀግኖች የሆናችሁ የዓለም መንግስታት መሪዎች ፣ ባለስልጣኖች፣ ኃላፊዎች፣ መንፈሳዊ መሪዎችና አለቆች፣ የተለያዩ ቡድኖችና ማኅበሮች፣ እንዲሁም ግለሰቦች፤ በመጀመሪያ ደረጃ ስለደንዳናነታችሁ በጨለማ ስሜ እያመሰገንኳችሁ ድንዳኔያችሁ ከኔ ደንዳናነት ላቅ እያለ

ቢያስቀናኝም፤ የእግዚአብሔርን መልእክት ከቁም ነገር የማይቆጥር ትዉልድ በማግኘቴ እጅጉን ደስተኛ መሆኔን በዚሁ አጋጣሚ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

ታዲያ አንዳንድ የደንዳናነት ታላቅነት ያልገባቸዉ ስዎች « ስለደንዳናነታችሁና የዐመጻ፣ የክህደት፣ እንዲሁም የርኩሰት ተግባራችሁ ዋጋ ትከፍሉበታላችሁ።» እያሉ የሚናገሯችሁና የሚያስፈራሯችሁን አንዳች አትስሙ፤ ከቁም ነገርም አትቁጠሩ። የእናንተ የአዳም ዘር ጀግንነትና ታላቅ ተጋድሎ የታየዉ በፍጡር በኩል የሚተላለፈዉን መልእክት አይደለም እርሱ መልእክተኞችን እያስነሳ የሚልከዉና የሁሉ ፈጣሪ የሆነዉ እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም ተገልጾ ሲያስተምራችሁ፣ ሲናገራችሁ ባለመቀበላችሁና ከዚያም ብቃት አልፋችሁ በመቃወማችሁ፣ በመስደባችሁ፣ በማዋረዳችሁ፣ በሐሰት በመወንጀላችሁ፣ በመትፋታችሁ፣ በመግረፋችሁ፣ በማሰቃየታችሁ፣ በማዳፋታችሁ፣ በመስቀላችሁ፣ በመግደላችሁ ጭምር ነዉ። ታዲያ እናንተ በኔ ዘንድ ብትደነቁ፣ ብትሞገሱ ያንስባችኋል እንጂ አይበዛባችሁም። ስለዚህ የአሁኖቹን መልእክተኞች ደግሞ «አንቀበልም» ማለት ብቻ አይደለም ከበፊቶቹ በመቶ እጥፍ ብታደርጉባቸዉ የበለጠ በኔ ዘንድ ሞገስ ታገኛላችሁ፤ ለታለቁ የጨለማ መንግስቴና ሽልማት ትበቃላችሁ።

እነሱ «እንዲህ ሆኗል፤ እንዲህ ይሆናል።» ይላሉ እንጂ «እስቲ ካሉት ነገር አንድ ነገር እንኳ መረጃ ያቅርቡልን?» ብትሉ አንዳች መልስ የሚሰጣችሁ አንድም ሰዉ የለም። «ይኸዉ በዓለም እየታየ ያለዉ ከዚህ በፊት ያልታየ የተለያዩ ክስተቶች፣ የየአገራቱ ሕዝቦች በመንግስታቸዉ ላይ መነሳታቸዉ፣ በኢኮኖሚዉ በለጸጉ የሚባሉት አገሮች በችግር ላይ መዉደቃቸዉ፣ የእግዚአብሔር ቁጣ የሆኑት የተላያዩ የተፈጥሮ አደጋ የሆኑት ድርቅ፣መሬት መንቀጥቀጥ፣ ጎርፍ፣ እሳተ ገሞራ፣ አዉሎ ንፋስ፣ ሰደድ እሳት፣ የበረዶ ክምር፣ የበረዶ መቅለጥ፣ ዉሽፍር የቀላቀለ ከባድ ዝናብ፣ የኒዉክለር ጨረር፣ ጦርነት... ወዘተ በተለያዩ ቦታዎች ባልተለመደ በከፍተኛ ደረጃ መከሰታቸዉ፤ ማንም አይነካቸዉም አይነቀንቃቸዉም የሚባሉት መሪዎች በዜጎቻቸዉ እየተዋረዱ ከወንበራቸዉ መቀረጣቸዉ፤ ሰዎች ለድህነት፣ ለችግር፣ ለመከራ በከፍተኛ ደረጃ ላይ መጋለጣቸዉ፣ የኑሮ ወድነቱ መክፋቱ፣ እርስ በእርስ ሕዝቦችና መንግስታት መጣላታቸዉ ... ወዘተ» በማለት ቢናገሯችሁ፤ « ይህ ሁሉ የሆነዉ

የጨለማዉን ገዥ ስላስቆጡትና አልታዘዝም ስላሉት ነዉ እንጂ ይህች ምድር የጨለማዉ ገዥ በመሆኗ እግዚአብሔር በዚህች ምድር ጉዳይ ጣልቃ አይገባም» በሏቸዉ:: « ከዚህ የባሰ ሁኔታ በከፋ መልኩ ገና ይመጣል፣ ይቀጥላል » ቢሏችሁ:: « የጨለማዉ ገዥ ደስ በሚሰኝበት ሕይወት ከተመላለስን መአቱን ከእኛ ያርቅልናል እንጂ ለእግዚአብሔር እጃችንን አንሰጥም» በሏቸዉ::

አንዳንዶች ኢትዮጵያን በተመለከተ «የዐመጻዉ፣ የክህደቱ፣ የርኩሰቱ ጽዋ ሞልቶ በመፍሰስ ላይ ነዉ:: እንዲሁም እዉነተኞቹ ኢትዮጵያዉን ስለ እዉነት የሚያነቡት እንባ ጽዋዉን ሞልቶ በመፍሰስ ላይ ነዉ:: የሚቀረዉ የዓለም የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ጽዋ ሞልቶ መፍሰስ ከጀመረ የቆየ ቢሆንም እስከአሁን ድረስ ስለእዉነት የሚያነባ ሰዉ ጠፍቶ ጽዋዉ የግማስ ግማሹ እንኳ መሙላት ስላልቻለ የኢትዮጵያኑ እንባ ከአገራቸዉ አልፎ ለዓለም ሕዝብም በማንባት የዓለሙን ጽዋ በመሙላት ላይ በመሆናቸዉ ያኔ የዐመጻ፣ የክህደቱ፣ የርኩሰቱ ተግባር በኢትዮጵያ ብቻ አይደለም ከዓለም ይቆማል:: ምድርቱም ከዐመጻ ልጆች በእግዚአብሔር ቁጣ ትጸዳለች:: የሕዝብ ደም መጣጮችም ይጠረጋል:: የኢትዮጵያም ትንሳኤ ለዓለም ይበሰራል:: መልካም ዘመን ይመጣል::» በማለት የሚናገሩትንና የሚያስተላልፉትን መልእክት አትስሙ:: እነሱ በእናንተ ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ተግባር ቀንተዉ ስለሆነና እኔም እድሉን ስላልሰጠዋቸዉ ነዉ ዝም ብለዉ የሚቀባጥሩት እንጂ ከሚሏችሁ አንዱም እንደማይሆነ በጨለማዉ ስሜ በዲያብሎስ በመማል ላረጋግጥላችሁ እችላለሁ::

እናንተ በታላቅ ዉለታችሁ ከሥጋዉያን መሪዎችና ባለስልጣኖች በላይ የተለየ ቦታ የሰጠዋችሁ የሃይማኖት መሪዎችና ኃላፊዎች በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችኋለሁ:: ይኸዉም ለምርጥ ባለሟሎቼና አገልጋዮቼ ከዚህ ከማይቀርበት ሥጋ መለየት እናንተ «ሞት» የምትሉት ነፍስ ከሥጋ ስትለይ ይህች ሕያዉ ነፍሳችሁን ሲያሳምጽ፣ ሲያስረክስ የነበረዉን ሥጋ እናንተ «ሬሳ » የምትሉትን በተቀደሰዉ ስፍራ የተለየ ቦታ የምትሰጡና እንደ ቅዱሳን ጻድቃን እንዲሁም ለአገራቸዉና ለሕዝባቸዉ ታላቅ ስራ እንደሰሩ ሰዎች እንዲታሰቡ በቤተክርስቲያን አጸድ ፊት ለፊት ቦታ ላይ በክብር ሐዉልታቸዉን በማቆማችሁ ነዉ:: እንዲሁም

የእግዚአብሔር ባለሚሎችና ለአገራቸዉና ለሕዝባቸዉ ታሪክ የሰሩ ሰዎች ይህች ነፍሳቸዉ ከሚጠሩበትና ከሚነጥሩበት ከሥጋቸዉ ተላይታ ወደተዘጋጀላቸዉ ስፍራ ሲሄዱ የከበረ ሥጋቸዉ በቤትክርስቲያን አጸድ አይደለም በጓሮ እንኳ እንዲቀበሩ እድል ባለመስጠታችሁና መታሰቢያቸዉን በማጥፋታችሁ ጭምር ነዉ::

ከዚህ በተጨማሪም የእነዚህ የኔ የጨለማ ተግባር ፈጻሚና አስፈጻሚ ባለሚሎችና አገልጋዮች ሬሳ በመሳምና በመሳለም የበረከታቸዉና የጸጋቸዉ ተካፋይ መሆናችሁን እግዚአብሔርንም ሰዉንም ሳታፍሩ በግልጽ በቴሌቭዥንና በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ለዓለም ስላሳያችሁና ስላስመሰከራችሁ ያላኝን አድናቆት በዚሁ አጋጣሚ እገልጽላችኋለሁ:: የእናንተ ነፍስ መግቢያ ቦታ ባዉቅም  የሬሳችሁ መዉደቂያ ቦታ ግን አሁን አልነግራችሁም:: ምክንያቱም እስከመጨረሻ ለኔ በምታሳዩኝ ታማኝነት ነዉና መዉደቂያ (መቀበሪያ ቦታ) የማዘጋጅላችሁ:: ይህንኑ አዉቃችሁ በታማኝነትና በጽናት እስከመጨረሻዉ እናንተም ባለሚሎቼና አገልጋዮቼ እንድትሆኑ ስለፈለኩና ከኔ በረከትና ጸጋ እንዳትለዩ በማሰብ ነዉ መቀበሪያ ቦታችሁን ምስጢር ያደረኩት::

እናንተ «እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን፤ ፓትርያሪክ፣  ጳጳስ፣  ቆሞስ፣ መነኩሴ ፣ ቄስ፣ ዲያቆን፣ መምህር፣ ሰባኪ፣ ዘማሪ ፣መስካሪ ... ወዘተ ነን፤ » በማለት ራሳችሁን የምታመጻድቁና በእዉነትና በመንፈስ እግዚአብሔርን የማታመልኩ በእዉነትም የማታገለግሉ፤ ሌላዉ ቢቀር ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ይታዘበናል የማትሉ፤ የጨለማ ስራ ተባባሪዎችና አስፈጻሚዎች፤ ለኔም ለጨለማዉ ገዥ አገልጋዮቼና ምርጦቼ ሰዎች፤ በእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ ዉስጥና  በእዉነተኛዉ ወንበር ላይ ሆናችሁ እንደጻፎች፣ ፈሪሳዉያን፣ አይሁድ ካህናትና አለቆች ዳግም አምላካችሁን የመስቀል እድል ባላማግኘታችሁ ባዝንላችሁም፤ በተዘዋዋሪ ግን እሱን አምላካችሁን በሚያሳዝንና በሚያስቆጣ ተግባር ላይ ተሰልፋችሁ ስመለከት ነፍሴ እጅጉን ሐሴት ታደርጋለች::

ታዲያ አንዳንድ ተመሳስሎ መኖርና ከራስ በላይ ንፋስ መመሪያን የማያቁቁ ግትሮች የሚሉትን አትስሙ:: ይኸዉም በማቴዎስ ወንጌል በምእራፍ ፲፥፴፮-፴፱(10:36-39) በመጥቀስ «

ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባዉም፤ ከኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይን ሴት ልጁን የሚወድ ለኔ ሊሆን አይገባዉም፤መስቀሉን የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለኔ ሊሆን አይገባዉም:: ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፣ ስለእኔ የሚያጠፋ ያገኛታል» በማለት፤ «እንኳን ለስልጣን፣ ለክብር፣ ለግል ብልጽግና፣ ለገንዘብ፣ ለሽልማት፣ ለዝና ጎሊናን መሸጥና ከነፈሰዉ ጋር መንፈስ፤ እንደ ቦይ ዉኃ መነዳትና የዲያብሎስ እንደራሴዎችን ፈቃድ ፈጻሚና አስፈጻሚ መሆን ቀርቶ፤ በቤተሰቤ ላይ ችግር ሊመጣ ይችላል፣ ቤተሰቦቼ ቅር ይሰኙብኛል፣ ከወንበሬ ልነሳ እችላለሁ፣ ከተመቻቸዉ ኑሬዬ ልፈናቀል እችላለዉ፣ መከበር ሊቀርብኝና ልዋረድ እችላለሁ፣ የመግነንና የመሸለም እድል ላያጋጥመኝ ይችላል.. ወዘተ » በሚል ስጋትና ፍርሀት የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ ተባባሪና አስፈጻሚ መሆን አይደለም፤ ስለ እዉነት በመመስከርና በእዉነት በመኖር ምክንያት ስደት፣ እስራት፣ ችግርና ስቃይ፣ ግድያ፣ መሰቀል ሁሉ ቢመጣ፤ እንኳን «የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ» የሚል አይደለም፤ «የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ነኝ፤ በእርሱ አምናለሁ» የሚል ሁሉ መፈጸም ያለበት የዉዴታ ግዴታዉ ነዉ:: ያለበለዚያ ለእግዚአብሔር መንግስት ሊበቃና የክርስቶስ ወገን ነዉ ለማለት አይቻልም » በማለት የሚናገሩትን ሰዎች አትስሙ::

ይልቁኑ «እኛ ከእናንተ በላይ ቃሉን እናዉቃለን፤ እንደ አቡነ ዘበሰማያት እናነበንበዋለን:: ክርስቶስ ይህን የተናገረዉ ለኛ ለአገልጋዮቹ በተለይ ደግሞ ትዳርና ልጅ ለሌለን ሳይሆን ለምዕመኑ ነዉ :: እኛ የክህነት ስልጣን ስለያዝንና «መምህርና ሰባኪ» የሚል ስያሜ ስለተሰጠን በዚችዉ ሰማያዊ ሹመት በምድር ብቻ አይደለም በሰማይም እንከብርበታለን፤ እንገንበታለን፤ እንሸለምበታለን:: አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ እንመለክበታን ::» በማለት አፋቸዉን ልታሲዙና ከዚያም በተጨማሪ ለሥጋዉያን ጌቶቻችሁ ተናግራችሁ ማሳሰር ወይን ማስገደል ይጠበቅባችኋል:: እነዚህ በምድር እንዲህ ከደፈሯችሁ በሰማይማ እንዴት ይታዘዙላችኋል? ያከብሯችኋል? «ቅዱስ አባታችን፣ ብጹዕ አባታችን፣ የሰማይ መልአክ፣ ሊቀ ምሁራን፣ መጋቤ ሐዲስ» ይሏችኋል?

እናንተ ለመሰበክም፣ ለምስጋናም፣ ለትምህርትም፣ ለጸሎትም ወረተኞች ሆናችሁ እንደ ሥጋና ደም ስሜታችሁ የምትንቀሳቀሱ ለኔ ምቹ ለስላሳ መሬት የሆናችሁልኝ ሰዎች፤ በዚህ ወረተኛነታችሁ እስከ መጨረሻዉ እንድትጸኑ በጨለማዉ ስሜ እመክራችኋለሁ:: ታዲያ አንዳንድ ለኔ የማይመቹኝ፣ ራሳቸዉን የሚገዙና በስሜት የማይመላለሱ ሰዎች የሚሉትን አትስሙ:: ይኸዉም « የእግዚአብሔር ቃል ሁሌም አዲስ ነዉ:: ሌት ተቀን ሰይጣን እንደሚፈታተናችሁና እንደሚያዳክማችሁ ሁሉ እናንተም ሁል ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል ልትታደሱና ልትጠነክሩ ይገባል:: ኃይልን የምትጎናጸፉት በእግዚአብሔር ቃልና ጸሎት ነዉ:: እንደ ዓለማዊ ሕይወት ለጊዜ ማሳለፊያና መደበሪያ የምትተቀሙበት አይደለም:: ካለ እግዚአብሔር ቃልና ካለ ጸሎት በመብላትና በመጠጣት ብቻ የምትመላለሱ ከሆነ እንኳን ለነፍሳችሁ አይደለም ለሥጋችሁም ኃይል አታገኙም::» በማለት የሚያስተምሩትንና የሚናገሩትን አንዳች እንዳትሰሙ:: የሚሏችሁን እንዳትፈጽሙ::

እነሱ የጨለማ ግዛቴን አሰራር ያልገባቸዉና በጎሊናችሁ ሰልጥኜ እናንተ « ድብርት፣ ዱካክ፣ ጭንቀት» እያላችሁ ብትሰይሙኝም የማዳከምና የማስጨነቅ ስሜቶችን በመፍጠር እንደማልከሰክሳችሁ፣ እንደማስረክሳችሁ፣ እንደማስከፋችሁ፣ እንደማማርራችሁ፣ ባጠቃላይ ፍዳና መከራ እነደማደርስባችሁ ያልተረዱ ስለሆነ ነዉ::

እነሱ የጎሊና ሰላማቸዉና እርካታቸዉ ቢጠበቅ ኖሮ እንደእናንተ በተረጋጋ፣ ባልተቅበዘበዘና ወረተኛ ባልሆነ ሕይወት ይመላለሱ ነበር:: ነገር ግን እንደእናንተ የረካ፣ ሰላም የሞላዉ፣ ጽናት ያለዉ ጎሊና በማጣታቸዉ ምክንያት ይኸዉ ለእግዚአብሔር ቃል ትኩረት በመስጠጥ ሌት ተቀን በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በምስጋና፣ በቅን አሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት ፍዳዬን እያሳዩኝ ያሰቃዩኛል፣ ያቃጥሉኛል፣ ያበሳጩኛል፣ ያነዱኛል::

ስለዚህ ከንደነዚህ ካሉት የኔን አንድነትና ህብረት ከማይፈልጉት «ጎሊናቸዉን በቀላሉ አልሸጥም፣ አልቦዝንም፣ ወረተኛ አልሆንም፣ አረክስም፣ አልልከሰከስም፣ አልከፋም፣ አልጨክንም» ከሚሉት ሰዎች እኔን ካስቸገሩ ለእናንተም ወደ ኋላ ከማይሉ፤ ራሳችሁን

አግላችሁ በሥጋና በደም ስሜታችሁ ብቻ እንደፈለጋችሁ ብትኖሩ የሚሻላችሁ መሆኑን ደግሜ ደጋግሜ በጨለማዉ ስሜ እመክራችኋለሁ::

እናንተ በዚህ ምድር ቆይታችሁ ዉስጥ «ራሳችንን ማወቅ ከጀመርንበት ጊዜ ጀምሮ የሰራነዉን፣ የተናገርነዉንና ያሰብነዉን  የኃጢአት ተግባር፣ ንግግርና አሳብ እኛ ከረሳናቸዉ እግዚአብሔር አያስታዉሳቸዉም» ብላችሁ የምታምኑና «ነፍሳችን ከሥጋ ከተለየች በኋላ ምንም የምታዉቀዉ፣ የምትረዳዉ፣ የምታስተዉለዉ ነገር የለም::» የምትሉ ሊቀምሁራን፤ ለዚህ ታላቅ አስተሳሰባችሁና እዉቀታችሁ በጨለማዉ ስሜ አደንቃችኋለሁ:: ታዲያ አንዳንድ እዉቀት የሌላቸዉ አላዋቂ ሰዎች፤ « ነፍስ ካወቅን ጀምሮ የሰራነዉ፣ የተናገርነዉ፣ ያሰብነዉ ሳይቀር እግዚአብሔር በባሕርይዉ መዝገብ ላይ ልክ በኮምፒተር የምንመዘግባቸዉ የተለያዩ መረጃዎች ተመዝግበዉ እንደሚቀመጡ ሁሉ ተመዝግቦ ይቀመጣል::

ልክ በኮምፒተር  የተመዘገ እንዲጠፋ እስካልተደረገ ድረስ ማንኛዉንም መረጃ(ዳታ) መዝግቦ እስከመጨረሻዉ እንደሚቆይና እንዲጠፋ (ዲሌት) ካልተደረገ በስተቀር እንደማይጠፋ ሁሉ፤ በእግዚአብሔር የባሕርይ መዝገብ ላይ የተመዘገበዉ ኃጢአት በእዉነተኛ ንስሐ እንዲደመሰስ ወይን እንዲጠፋ ካልተደረገ በስተቀር ነፍስ ከሥጋ ስትለይ የተረሱት ሆነ ያልተረሱት የኃጢአት ተግባር፣ ንግግር፣ አሳብ ጭምር ነፍሳችን በምትገለጽበት ረቂቅ አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) ሆና እያስታወሰች እስከ መጨረሻዉ ፍርድ ቀን ሁሉ ትዝ እያላት በሲዖል ዉስጥ ትጨነቃለች:: ትሰቃያለች:: «ምን አይነት የመጨረሻ ፍርድ ነዉ የሚጠብቀኝ እያለች ታወጣለች፣ ታወርዳለች፤ በዚህም ምክንያት ካለእረፍት (እንቅልፍ በዚያ የለምና) እጅግ ትጨነቃለች::

በተቃራኒዉ ደግሞ እዉነተኛ ንስሐ ገብተዉ ስለ ኃጢአት ተግባራቸዉና ንግግራቸዉ፣ አሳባቸዉ ጭምር ተጸጽተዉ የክርስቶስን መለኮት የተዋሀደዉን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙን የተቀበሉ የሚያስታዉሱትም የማያስታዉሱትም ኃጢአት ሁሉ ከእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ ስለሚደመሰስ ነፍስ ከሥጋቸዉ ስትለይ፤ ልክ በህጻንነት እድሜያችን የምንፈጽመዉ ተግባርና ንግግር ትዝ እንደማይለን ሁሉ  አንዳች ትዝ የሚላቸዉ ኃጢአት

የለም፡፡ ንጹህ ኅሊና ብቻ ይዘዉ በገነት ዉስጥ በመግባት በሰማያዊ መላእክት አኗኗን ይኖራሉ እንጂ በምድራዊ ሕይወታቸዉ በሥጋ በመገለጻቸዉ ምክንያት የሚያጋጥማቸዉ ያደፈና የጎደፈ ባሕርይ የሆኑት ዐይነ ምድር፣ ሽንት፣ ላበት፣ ንፍጥ፣ አክታ የመሳሰሉትና የጎሰቆለ ባሕርይ የሆኑት ድካም፣ ማንቀላፋት፣ ማዘን፣ ማልቀስ፣ መተከዝ፣ በናደድ፣ መበሳጨት፣ መታመም፣ መቸገር፣ መዉጣት፣ መዉረድ፣ ምድራዊ መብልና መጠጣት መብላት፣ መጠጣት፤ በጨለማና በብርሃን፣ በሙቀትና በቅዝቃዜ በተፈራረቀ ሕይወት መኖር ከሌለበት፤ ከሙቀት፣ ከቅዝቃዜ፣ ከዝናም ለመከላከል ቤት፣ መጠለያ መስራት በማያስፈልግበት፤ ሰዎች በራሳቸዉ ጊዜ የፈጠሩት ጉስቁልና ሕይወትና ጠባይ የሆኑት ጥል፣ ጦርነት ፣ ግድያ፣ ስርቆት፣ ዝሙት፣ አመንዝራነት ፣ ዘፈን ፣ ዳንኪራ፣ ዘረኝነት ፣ ጎጠኝነት ፣ ባዕድና ጣዖት አምልኮ፣ ጥንቆላ፣ መተት፣ አስማት፣ ሟርት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ቅናት፣ ምቀኝነት፣ ጥል፣ ቂም በቀል፣ አድማ፣ መከፋፈል፣ መለያየት፣ ስስት፣ ራስ ወዳድነት፣ ስግብግብነት.. ወዘተ የመሳሰሉት ከማይታዩበትና ከማይታሰቡበት፤

ባጠቃላይ አዳምና ሔዋን በገነት ኑሮ ዉስጥ እያሉ «እግዚአብሔር አትብሉ» ብሎ ያዘዛቸዉን ትዕዛዝ ተላልፈዉ የዲያብሎስን የክፋትና ተንኮል ምክር ሰምተዉ በራሳቸዉ ምኞትና ፍላጎት ተገፋፍተዉ በድፍረት ከምሳሌያዊ ባሕርይ የተፈጠረችዉን ፍሬ በመብላታቸዉ ምክንያት የተገለጹበት ረቂቅ አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) ወደ አለመኖር አልፎ ይህ ግዙፉ ሥጋ መብላትና መጠጣት የግድ የሚያስፈልገዉ አካል፤ በምድር ዉስጥ የሚያስፈልጉት የሚታዩና የማይታዩ ፍጥረቶች የሆኑት ፀሐይ፣ አየር፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ እንስሳት፣ እፀዋት፣ አእዋፋት፣ መሬት፣ ዉኃ.. ወዘተ የመሳሰሉት ተዘጋጅቶለት፤ በመጨረሻዉ ቀን በእለተ አርብ ከአፈር (ከመሬት) ተበጅቶ አማናዊዋ ፍጥረት በገነት የነበረችዉ ነፍስ እንድትዋሀደዉ ተደርጎ በመፈጠሩና በዚህ ምድር ዉስጥ ነፍሳት የሚጠሩበት፣ የሚነጥሩበት፣ የሚቀጡበት ሆኖ በመዘጋጀቱ ምክንያት ላደፈና ለተጎሳቆለ ባሕርይ እንዲሁም ለጎስቋላ ኑሮና ሕይወት በመዳረጉ ምክንያት የተከሰቱት ባሕርያትና ሕይወት፣ ጠባይ የማይከሰትበትን ሕይወትና ኑሮ ይኖራሉ፡፡

ፈተናና መከራ ካለባት ከጎስቋላ ምድር መመጣታቸዉን እንጂ አንዳች የምድራዊ የኃጢአት ተግባራቸዉ፣ ንግግራቸዉ፣ አሳባቸዉ ትዝ የማይላቸዉ፤ የጉስቁልናና የፈተና ኑሮዋቸዉ የነበረዉ አንዳች ስሜት የማይሰጣቸዉ ይሆናል፡፡ በቅድስናና በደስታ ሕይወት ብቻ ይኖራሉ፡፡ ለአዳም ዘር ወገኖቻቸዉ ደግሞ ያስባሉ፤ ይጸልያሉ፡፡ ስለዚህ እደነዚህ ጻድቃን እድል እንዲያጋጥመን ሕይወታችንን በንስሐና በቅዱስ ቁርባን በመምራት ልንመላለስ ይገባል» በማለት የሚያስተምሩትንና የሚናገሩትን ተረት ተረት አንዳች እንዳትሰሙ፤ እንዳትቀበሉ፡፡

እንኳን ፍጡሮቹን ሰዎች አይደለም እግዚአብሔር ተገልጦ ቢያስተምራችሁ፣ ቢናገራችሁ ወይንም እኔ የጨለማዉ ገዥ ሳት ብሎኝ በጸሎቱና በጸበሉ ተቃጥዬና ታስሬ ብለፈልፍ እንኳ « እኛ እግዚአብሔርንም፣ ሰይጣናትንንም አናዉቅም፡፡ እኛ የተገኘነዉ ከተፈጥሮ ከጦጣ መሰል እንስሳ በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ (በኢቮልሽን) አማካይነት ነዉ፡፡ ከቁስ አካል የተገኘን ስለሆነ በቅርቡ ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ዉስጥ አዉለን እንደፈለግነዉ እንሆናለን፡፡ የሐሳብያዉያን ከንቱ እምነት ምን እንደሆነ እድሜ ለማርክስ፣ ለኤንግልስ፣ ለሌኒን፣ ለቻርልስ ዳርዊንናና ለተለያዩ ፈላስፋዎች አዉቀናል፡፡» በማለት ለማንኛዉም ሰዉ ምላሽ ሰታችሁ አፋቸዉን አዘጉ፡፡ ይህ ምላሻችሁ ነዉ በኔ ዘንድ ሞገስ የምታገኙበትና ለታላቅ አገልግሎት የምትታጩበት፡፡

እናንተ የአዳም ዘሮች፤ ለወደፊት ከምትኖሩበት ጊዜ አንጻር የአሁኑ ምድራዊ ዘመናችሁ የዐይን ቅጽበት እድሜ እንኳ የማይሞላ መሆኑን ያላስተዋላችሁ፤ ይኸዉም ለወደፊት ነፍስ ከሥጋችሁ በሥጋ ሞት ስትለይ የማትኖሩበት ጊዜ የለምና አሁን በምድር የምትኖሩት ዘመን ከሥጋ ሞት በኋላ ለምትኖሩት ዘመን ሲካፈል ለምሳሌ መቶ አመት ብትኖሩና ለትየለሌ (ለኢንፊኒት) ቢካፈል አልቦ (ዜሮ) ዘመን ይሆናልና ነዉ፡፡ ታዲያ ለዚህች ለዐይን ቅጽበት እድሜያችሁ ታላቅ መስዋዕትነት በመክፈላችሁ፣ ይኸዉም ይህን ታላቁ ሥጋችሁን አፍቅራችሁና ዋጋ የሌላትን ነፍሳችሁን ንቃችሁ ለሥጋችሁ በሚመች ኑሮና ሕይወት በመመላለሳችሁና የታላቅነታችሁ መገለጫ የሆነዉን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ፈጻሚና አስፈጻሚ በመሆናችሁ ነዉ፡፡ ለዚህ ብቃታችሁ ደግሞ በኔ በጨለማዉ ገዥ

አማካይነት የሰማዕትነት፣ የታጋይነት፣ የንጉሥነት፣ የንግሥትነት፣ የጀግንነት ሲያሜ አሰጣችኋለሁ:: ይህ ብቻ አይደለም በምርጦቼ እንደራሴዎቼና በባለሟሎቼ እንዲሁም በዉዶቼ አማካይነት አስገንናችኋለሁ፤ አከብራችኋለሁ፤ ከፍ ከፍ አደርጋችኋለሁ::

የዚህ ምድር ቆይታችሁ ከዐይን ቅጽበት ጊዜ እጅግ እጅግ ያነሰ መሆኑን ባታስተዉሉትም እኔ ከእናንተ ተሸዬ ምግባር ባይኖረኝም ወደዚህች መቀጫ ምድር ከተወረወርኩ በኋላ የፈጠረኝ አምላክ እንዳለ አምኛለሁ:: እናንተም ከዚህች ምድር በኋላ ሁለተኛዋ መጣያ ቦታ ሲያል ስትገቡ እንደኔ ሳትወዱ በግዳጃችሁ የእግዚአብሔርን ህልዉና ታምናላችሁ:: እንደእናንተ ወገኑ ላይ እንደሚጨክንና ግፍ እንደሚፈጽም ፍጡር አለሞሆናችንን ሁላችሁም እንድታዉቁልን እንፈልጋለን:: በእኛ በሰይጣናት ዘንድ ተጣልተንና እርስ በእርስ ለመለያየት ተቧድነን አናዉቅም::

ታዲያ እንዲህ ስላችሁ ተፋቀሩ፣ ተዛዘኑ፣ ተረዳዱ፣ ለማለት ፈልጌ ሳይሆን እናንተ ራሳችሁን አዋቂና ጥበበኛ አድርጋችሁ ትቆጥራላችሁ እንጂ አንዳች እዉነተኛ እዉቀትና ጥበብ የሌላቸዉ፣ የዐይን ቅጽበት እድሜ የማይሞላ ዘመናችሁን እንኳ በአግባቡ የማትኖሩ፣ የመጨረሻ መሃይሞች መሆናችሁን ልመሰክርባችሁ ፈልጌ ነዉ እንጂ፤ አሁን የምታሳዩትን የዐመጻና የክህደት፣ እንዲሁም የርከሰት ተግባራችሁን አጠናክራችሁ ብትቀጥሉ ነዉ የኔ የጨለማ ጌታችሁ ፍላጎትና ምክር ::

እናንተ የአዳም ዘር! የምርጥ እንደራሴዎቼ የዓለም መንግስታት መሪዎችና የባለሟሎቼ ባለስልጣነት እንዲሁም የዉዶቼ ካድሬዎች ታላቅነታቸዉንና ብቃት ደረጃ ላይ መድረሳቸዉን በዋናነት የምትለዩት በቴሌቭዥኑ፣ በሬዲዮኑ፣ በሕትመት ዉጤቶች ፣ በስብሰባ.. ወዘተ የሚቀርቡትን የተለያዩ ወሬዎች፣ ዘፈኖች፣ ዳንኪራዎች፣ ፊልሞች፣ ጨዋታዎች፣ መዝናኛ መርሐ ግብሮች .. ወዘተ የሆኑትን በደንብ አድርጋችሁ ስትከታተሉና ስታዳምጡ እንዲሁም ስታነቡ ነዉ::

ታዲያ አንዳንዶች ተስፋቸዉን በማይታየዉና በማይጨበጠዉ የሚያደርጉ ቁስ አካላዊነትን የሚቃወሙና በምናባዊ አስተሳሰብ የሚመላለሱ ሰዎች የሚሉትን «ኅሊናን ማስደንዘዣ፤ ነፍስን ማሳበጃና መግደያ፤ ሥጋን ደግሞ የጨለማዉ ገዥ ማደሪያና መጫወቻ

ማድረጊያ ነዉ፡፡» እያሉ የሐሰት ፕሮፖጋንዳ የሚነዙትን ሐሳብያዉያንን አንዳች እንዳትሰሙ፡፡ እነሱ ይህች የምትጣፍጥና ያማረች ዓለምን የናቁና ሥጋቸዉ ላይ በደልና ኢሰብአዊ ተግባር የሚፈጽሙ፣ ለማያዉቋት ነፍሳቸዉ የሚተጉ፣ የኔ ዋና ተቃዋሚና ያመጹብኝ ናቸዉ፡፡

በመሆኑም እናንተ በምንም ሁኔታ ከነዚህ አይነት ሰዎች ጋር አንድነትና ህብረት እንዳትፈጥሩ፡፡ የዐመጻዉንና የርኩሰቱን ተግባርና ትዕይንት በደንብ አድርጋችሁ አጧጡፉ፡፡ ቀኒቷ እየመሸችባችሁ ጨለማዉ እየመጣባችሁ ስለሆነ ባለቻችሁ የቀን ዘመን የጨለማዉን ስራ በደንብ አድርጋችሁ ለአዳም ዘር አሳዩ፤ አሳምጹ፤ አስረክሱ፤ ባጠቃላይ እኔ የጨለማዉ ጌታችሁ የማሳስባችሁን ሁሉ ወደ ተግበር እየለወጣችሁና እያጣፈጣችሁ ለአዳም ዘር አቅርቡ ፡፡

እናንተ ይህች ሕያዉ ነፍሳችሁ የማትሞት፣ የማትበሰብስ፣ ከመኖር ወደ አለመኖር የማታላፍ፣ ከዚህ ከምትቀጣበትና ከምትጠራበት በኔ የጨለማዉ ገዥ ከምትቀጠቀጥበት ግዙፍና ቅርፊት ከሆነዉ ሥጋ ስትለይ የሚጠብቃትን ሕይወት ያላወቃችሁ ሰዎች፤ በዚህ ምድር ዉስጥ በተለያየ ምክንያት የእስር ቤት ኑሮና ሕይወት የቀመሱ ሰዎችን « በእስር እያላችሁ የነፍሳችሁ ነጻነት እንዴት ነበር? ጭንቀታችሁና መሰልቸታችሁ እንዴት ነበር?» ብላችሁ ጠይቋቸዉ፡፡ እነሱ፣ ለዚያዉም ወንጀል ሰርተዉ እንደሆነ የንስሐ እድል አላቸዉ፤ በሐሰት ተወንጅለዉ ከሆነ መፈታትን የሚያገኙ ናቸዉ፡፡ የእናንተ ነፍስ ግን በዚህች ምድር ነጻነቷን ተጠቅማ በመልካም ተግባር፣ በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ አምልኮ ካልተመላለሰች በቀር ከተገለጸችበት ሥጋ ከተለየች ዳግም የንስሐ እድል የሌላት፤ ዳግም ብትጸጸት ዋጋ የማታገኝበት፤ ዳግም እዉነተኛ አምልኮ መፈጸም የማትችል፤ ዳግም መልካም የመስራት እድል የማያጋጥማት፤ ቅን የማሰብ እድል የሌላት በመሆኑ ነጻነቷ ተገድቦ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በሲዖል እንደ ዐመጻ፣ ክህደቷ፣ ርኩሰቷ ደረጃ እንደምትቀጣ፤ ከመጨረሻ ፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ ለሕያዉነት ዘመን በገሃነመ እሳት ዉስጥ እንደ ዐመጻ ደረጃዋ በባሰ ሁኔታ ፍዳዋን እንደምትቀበልና እንደምትቀጣ እያወቃችሁ፤ ስለምን ይሆን እኔን የጨለማዉ ገዥን ምርጫችሁ አድርጋችሁ ሌት ተቀን ፈቃዴን ለመፈጸምና ለማስፈጸም የምትተጉት? ስለምን

ይሆን እንደ ቅዱሳን መላእክት ሆናችሁ በእግዚአብሔር መንግስት ሕያዉ ሆናችሁ የምትኖሩበትን ሕይወት ንቃችሁና አቃላችሁ መከራና ስቃይ ያለበትን ሲያልና ገሃነመ እሳትን ምርጫችሁ አድርጋችሁ የምትመላለሱት?

ወይስ «ነፍሳችን ከሥጋዋ ስትለይ አንዳች የምታዉቀዉ ነገር የለም፡፡» ያሉትን የፈላስፎች እምነት ተከትላችሁ «በዚህች ምድር እንደ አህዛብ( እግዚአብሔርን እንደማያምኑት) ሰዎች እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንጨፍር፣ እንዝፈን ፣ እንርከስ፣ እንልከስከስ፣ ባጠቃላይ በሥጋና ደም ስሜታችን በመመራት እንደ እንስሳ የፈለግነዉን እንፈጽም፡፡» በማለት በነፍሳችሁ ላይ የመጨረሻ የሞት ፍርድ ወስናችሁ ቅርፊት ሥጋችሁን ደግሞ አግናችሁት ተስፋችሁን ምድራዊ ስላደረጋችሁ ይሆን? ወይስ « የግብር አባታችን ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ብቻዉን በገሃነም እሳት ዉስጥ ለምን ይቀጣል? እኛም ባሮቹና አገልጋዮቹ የመከራዉና የስቃዩ ተካፋይ እንሁን» በማለት አዝናችሁልኝ ለማጽናናት ፈልጋችሁ ይሆን? ይህ ከሆነ በእርግጥ ስለ አዘኔታችሁና ስለማጽናናታችሁ በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችኋለሁ፡፡ እኔ በዚህች ምድር ማዘንና ማጽናናት የማልችል ቢሆንም በመጨረሻዉ መንግስቴ ግን እንደማጽናናችሁና እንደማዝንላችሁ በዚሁ አጋጣሚ ቃል እገባላችኋለሁ፡፡

እናንተ የአዳም ዘሮች፤ እንደሚድሁ ህጻናት ስትሆኑብኝ እጅግ ኀዘን ይሰማኛል፡፡ ይኸዉም ያገኛችሁትን ሳትጸየፉና ሳትመረምሩ ወደ አፋችሁ ለማስገባት ስትጣደፉ እንዲሁም ቅዘኑን፣ ትፋቱን ሳትጸየፉ በእጃችሁና በእግራችሁ ስትጫወቱበት በማየቴ ነዉ፡፡ ምክንያቱም በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት፣ ባጠቃላይ በኃጢአት ሕይወት ዉስጥ በመጨማለቃችሁ ምናልባት እንደ ህጻናት ተቆጥራችሁ ምህረት ይደረግላችኋል በሚል ስጋት ሲሆን፤ ነገር ግን የሚያመዛዝንና የሚያገናዝብ ኅሊና እንዳላችሁ እንኳን ፈጣሪ እኔም በደንብ ስለማዉቅ አድሎ የሌለዉ ፍርድ ከኔ ጋር በአንድነት እንደምታገኙ ሳስብ እጅጉን እጽናናለሁ፡፡

እናንተ አምላካችሁን « አማላጅ» ብሎ ለመስደብና ለማዋረድ እንዲሁም የሕይወት ምስጢር ቁልፋችሁን ድንግል ማርያምን «እንደ እኛዉ ተራ ሰዉ ናት፣ አታማልድም» በማለት የምታቃልሉና የምታዋርዱ ቅዱሳን መላእክት «ተራ ተላላኪ ናቸዉ» ብላችሁ ዝቅ

የምታደርጉ፤ ነብያትን ፣ ሐዋርያትን ፣ ሰማዕታትን ፣ ጻድቃንን ክብራቸዉን ዝቅ ለማድረግና ከራሳችሁ ጋር ለማስተካከልና ለማቅለል ወደ ኋላ የማትሉ ደፋሮችና ቀራጦች ሰዎች፤ ድፍረታችሁና ቀራጥነታችሁ ከኔ አይሎ ቢያስቀናኝም ቀጥሉበት፣ በርቱ፣ እግዚአብሔርን ሆነ ቅዱሳንን ለመሳደብና ለማዋረድ ወደ ኋላ እንዳትሉ ታላቁን የጨለማ ምክሬን እለግሳችኋለሁ::

ታዲያ የኔን ምስጢር ያልተረዱና እንደ እናንተ ደፋር ያልሆኑ አላዋቂ ሰዎች፤ «እግዚአብሔር የሚታወቀዉና ከእርሱ የተለያየ ጸጋ የሚገኘዉ በትህትና እንደ አብርሃም፣ ከእግዚአብሔር የሚገኝ ታላቅነትንና ብቃትን ከቁም ነገር ሳይቆጥሩ የራስን ማንነት እንኳ በመካድ «አፈርና አመድ ነኝ::» እንደ ንጉሥ ዳዊት« የሞተ ዉሻ፣ ትል፣ ድዉይ ነኝ::» እንደ መጥምቀ መለኮት ዮሐንስ « እኔ ለጫማ ጠራጊነትና ተሸካሚነት እንኳ የማልገባ ነኝ::» እንደ ሐዋርያዉ ጳዉሎስ «እኔ የዓለም ጥራጊ ጉድፍ፣ ጭንጋፍ ነኝ::» እንደ አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ « እኔ ኃጢአቴ ከዓለም ኃጢአት ይበልጣል::» እንደ ትሁቱ መልአክ « ለእኔ እንዳትሰግድል እንደ እናንተዉ የእግዚአብሔር አግልጋይና መስካሪ ነኝ::» ባጠቃላይ ቅዱሳንና ጻድቃን «ኃጢአታችን ከሰማይ ከዋክብት ከምድር አሸዋ ይበዛል.. ወዘተ» በማለትና ራስን በእግዚአብሔር ፊት በማዋረድ ነዉ እንጂ በትዕቢትና በዐመጻ እንዲሁም በመሳደብና በማዋረድ አይደለም::» በማለት የሚያስተምሩትንና ድፍረታችሁን፣ ቀራጥነታችሁን የሚቃወሙትንና የሚነቅፉትን አትስሙ፤ አትቀበሉ:: እንደዚህ አይነት ትህትና ሆነ ራስን ዝቅ ማድረግ የሚያዋርዳችሁና ከቅድስና ሆነ ከክብር የሚለያችሁ፤ እንደ እኔ «የሚያገሳ አንበሳ፣ ዘንዶ» ከመባል የሚከለክላችሁ፤ ምድራዉያንን ብቻ ሳይሆን ሰማያዉያንን ጭምር ከመሳደብና ከማዋረድ ወደ ኋላ የሚጎትታችሁ የደካሞችና የሰነፎች አባባል ነዉ::

አንዳንድ ከጸጋዬ የተለዩ የኔን ጣዕም ያልቀመሱ ሰዎች ደግሞ « ያለ ወላዲተ አምላክ ዓለም አይድንም:: እንኳን እሷን ያቃለለ፣ የሰደበ፣ ያዋረደ ቀርቶ ያላመሰገነ፣ ያልተማጸነ፣ ያላገነነ የእግዚአብሔርን መንግስት መዉረስ አይደለም መመልከት አይችልም:: የአዳም ዘሮች የሕይወት ምስጢር ቁልፍ የሆነችዉ እርሷ፣ በዲያብሎስ የተዘጋብንን ማስተዋል ካልከፈተችልን በስተቀር ነገረ መስቀሉን ሆነ እዉነትን ማስተዋል አንችልም፤ በደመ ነፍስ የምንመላለስ፣ የምንኖር እንሆናለን እንጂ ተስፋችን ሰማያዊ አድርገን በእዉነተኛ መንፈሳዊ

ሕይወት መመላለስና መኖር አንችልም፡፡» እያሉ የሚያስተምሩትን በምንም ሁኔታ እንዳትሰሙ፤ እንዳትቀበሉ፡፡

እነሱ የኔን የጨለማ ሕይወት ምስጢር ያላስተዋሉ፣ የማይፈሩኝ ደፋሮች፣ ፈቃዴን የማይፈጽሙና የማያስፈጽሙ ዐመጸኞች፣ የኔ ዋና ተቃዋሚ ጠላቶቼ የሆኑ ሰዎች ስለሆኑ ነዉ፡፡ ከነዚህ ከካዱኝ ሰዎች ጋር በምንም መልኩ አንድነትና ህብረት እንዳትፈጥሩ፡፡ አንድነትና ህብረት ከፈጠራችሁ ግን አሁንም ሆነ ወደፊት በኔ መንግስት አንዳች ቦታ የማታገኙና ዐይነ ኅሊናችሁ ስለሚከፈትና ከንቱነታቸሁን ስለምታዉቁ ከዐመጻ፣ ከክህደት፣ ከርኩሰት፣ ባጠቃላይ ከኃጢአት ተግባርና ንግግር የመሳተፍ እድል አታገኙም፡፡ አምለካችሁን ሆነ ቅዱሳንን የመሳደብና የማዋረድ ስልጣን አታገኙም፡፡ በመሆኑም የኔ የጨለማዉ ገዥ ኃይልና ድፍረት እንዳይለያችሁ ሁል ጊዜ እኔን ደስ በሚያሰኝ ሕይወት እንድትመላለሱና በትጋት እንድታመልኩኝ በጥብቅ አሳስባችኋለሁ፡፡» **ይላል የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ዋና አዛዥና አስፈጻሚ ተሳዳቢዉ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከጭፍሮቹ ሰይጣናት ጭምር፡፡**

## ምእራፍ ሁለት

« እናንተ የአዳምና ሔዋን ዘሮች! እኔ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከሠራዊቶቼ ሰይጣናት ጋር በመሆን ምን ያህል ከህጻንነታችሁ ጀምሮ እንደምንከባከባችሁ ልንገልጽላችሁ እንወዳለን። በዚያዉም ጭካኔያችንና ማንነታችን ምን እንደሚመስል እናስተዋዉቃችኋለን። እኔ የጨለማዉ ገዥ፤ አባታቸዉ እንድሆን የሚፈልጉ ሁሉ ካለምንም አድሎ የግብር አባታቸዉ የምሆን ነኝ። እኛ ሰይጣናት እናንተን መፈታተንና ማስጨነቅ የምንጀምረዉ ገና በእናታችሁ ማህፀን ዉስጥ ነፍሳችሁ ከሥጋችሁ ጋር በወንድና በሴት ግንኙነት (በተራክቦ) አማካይነት ከሚፈጠረዉ ጽንስ ጋር ተዋህዳ ሰዉ ስትሆን ነዉ። የእናንተ ሰዉ መሆን ስለሚያስጨንቀንና ስለማያስደስተን በጽንሱ ላይ በምንችለዉ መንገድ ጥቃት ከመፈጸምና ከመፈታተን ወደ ኋላ አንልም። ከጽንስ ማስወረድ ጀምሮ ማንኛዉንም ጉዳት በጽንሱ ላይ ከማምጣትና ከመፈታተን አንዳች አንቦዝንም።

የእግዚአብሔርን ፍጥረቶችንና ልጆችን በመጀመሪያ ደረጃ በኃላፊነትና በወላጅነት የተቀበለችዉ እናቲቱ ስለሆነች፤ በዚህ ስለምንቀናና ስለምንመቀኝ በጽንሱ ላይ በምንፈጥረዉ የተለያየ ፈተናና ጥቃት የመጀመሪያዋ ተጠቂዋና ተፈታኟ እናቷን በማድረግ የተለያዩ ያልተለመዱ ስሜቶች እንዲሰማት እናደርጋለን። የኛ ጥረት በዚህ ተማራ ሌላ ጊዜ ላለማርገዝ እንድትወስን ሲሆን፤ ብዙ ጊዜ አይሳካልንም። እንኳን የእርግዝናዉን ስሜት ቀርቶ ምጡንም ወዲያዉ ትረሳለች። በዚህም ኃይሌ የተገደበና የፈለኩትን ጥቃት ሆነ ጉዳት ማድረስ ባለመቻሌ፣ እንዲሁም በክፋትና በተንኮል ተግባሬ ዉጤት ማምጣት ባለመቻሌ ሁሌ እንደተናደድኩና እንደተበሳጨሁ እስከአሁን አለሁ።

ምንም ማድረግ ያልቻልኩት ጽንስና ምንም ጉዳት ላደርስባት ያቃተኝን ህጻን፣ እናቱ ጊዜዉን ጠብቃ በማማጥ ተጨንቃ ትወልዳለች፤ በጭንቀቷም እኔ ደስተኛ ነኝ። ምክንያቱም ተባባሪና አስጨናቂ ስለሆንኩ ነዉ። በማህጸን ዉስጥ ፈተናዬንና ጥቃቴን ከቁም ነገር የማይቆጥረዉ ህጻን ወደ ምድር ተወልዶ ሲገለጽ የማያስተዉለዉንና ሊከላከለዉ

የማይችለዉን መንፈሳችንን ወደ ኀሊናዉ በማስግባት ሰላሙንና እርካታዉን በመንሳት ከመጀመሪያዉ ዓለም በለቅሶ አቀባባል እንድትቀበለዉ እናደርጋለን።

ባይገባዉም የዓለም ክፋትንና ጭከናን እናስተዋዉቀዋለን። ወደ ደስታ ዓለም ሳይሆን በቀደሙት ወላጆቹ አዳምና ሔዋን ዐመጻና በደል ምክንያት ወደ ሚቀጣበትና ወደ ሚጠራበት፣ ነጥሮም ወደ እዉነተኛዉ የእርሱ ግዛት ገነት የሚመለስበት ፈታኝ ዓለም መምጣቱን እንሳዉቀዋለን። ባይገባዉ የሕይወትና የሞት መንገድ በጋራ እንዳሉና በነጻ ምርጫዉ ምንም ሳይገደድ በሚመርጠዉ መንገድ ዉስጥ መመላለስና የምርጫዉን ዉጤት በመጨረሻ ላይ እንደሚያገኝ፤ የኛን መንገድ ከተከተለ በምድራዊዉም ሆነ ከዓለም እልፈት በኋላ የመንግስታችን ወራሽነቱን እናረጋግጥለታለን። ባጠቃላይ በሚጠራበት፣ በሚነጥርበት ዓለም ዉስጥ በነጻ ፈቃዱ መኖር እንደሚችል እንነገረዋለን።

ከዉልደቱ ጀምሮ በምንችለዉ አቅም ሁሉ ነፍስ ከሥጋዉ እስክትለይ ድረስ እንፈታተነዋለን፣ የምንችለዉን መሰናክል ሁሉ በማምጣት በአምላኩ ላይ እንደኛ እንዲያምጽ እንጥራለን። በለቅሶ አቀባበል ያደረግንለት ህጻን እንደማንኛዉም አዋቂ ሰዉ ወደ ነፍሱ (ኀሊናዉ) ግንባራችሁ ፊት ለፊት በአንጎላችሁ ዉስጥ ወደ ምትገኘዉ እናንተ አእምሮ(ኀሊና) ወደምትሏት ነፍሳችሁ እንገባለን፣ እንወጣለን፣ ወደ ተለያዩ የሥጋ አካሎቻችሁ ዉስጥ እንገባለን፣ እንወጣለን። ይህ አካላችሁ ለእኛ ልክ እንድ ትልቅ ሰፋፊ ወንፊት ክፍት ነዉ። ከእኛ ከተገለጽንበት አካል ረቂቅነት ሲታይ የእናንተ አካላችሁ ክፍተት ከአፋችሁ ስፋት ይበልጣል። በዚህች ምድር ዉስጥ እኛን የሚያግደን ረቂቅ ነገር የለም። እናንተ በሳይንሱ ረቂቅ ነገር «አተመ» ከምትሉት እጅግ እንረቃለን። ማንም በራሱ ጥበብና በኃይሉ ሊያየን ሆነ ሊይዘን አይችልም።

በዚህ ምክንያት ነፍሳችሁን ለመፈታተን፣ ለማስጨነቅ፣ ለማዳከም፣ ለማጎሳቆል፣ ክፋትና ተንኮል ለማሳሰብ፣ ለዐመጻና ለክህደት ሕይወት ለማነሳሳት፣ ሰለምና እርካታ ለመንሳት ወደ ኀሊናችዉ የምንገባዉ ሰይጣናት፤ ከኅሊናችሁ በአፋችሁ በኩል ስንወጣ ታዛጋላችሁ፤ ታፋሽካላችሁ፤ ባፍንጫችሁ በኩል ስንወጣ ታስነጥሳላችሁ፤ ከመተንፈሻ አካላችሁ በአፋችሁ በኩል ስንወጣ ትስላላችሁ፤ ከሆዳችሁ በአፋችሁ በኩል ስንወጣ

ታገሳላችሁ፤ ከሆዳችሁ እዳሪ ስንወጣ በፊንጢጣችሁ በኩል ትፈሳላችሁ፤ በቆዳችሁ በኩል ስንወጣ ታካላችሁ፤ በመገጣጠሚያ አካላችሁ በኩል ስንወጣ ትንጠራራላችሁ:: ከዚያ ዉጭ ደግሞ ዝም ብለን ከንፍጥ፣ ከአክት፣ ከሰገራ፣ ከሽንት፣ ከላበት ጋር ሆነን ከአካላችሁ እንወጣለን:: ሳናስበዉ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ሲመጣብን ከኅሊናችሁ ሆነ ከአካላችሁ ብን ብለን ተቃጥለን እንወጣለን:: «ኅሊናዬ ተጨነቀ፣ ሰላም አጣዉ፣ እርካታ አጣዉ፣ ተቅበዘበዝኩ፣ ደበተኝ፣ ተጫጫነኝ» የምትሉት እኛ ወደ ኅሊናችሁ ስንመጣ፣ ስንፈታተናችሁና ስናስጨንቃችሁ ነዉ::

የእኛ ስራ እናንተን መፈታተን፣ ማጎሳቆል፣ ማድከም፣ ሰላምና እርካታ መንሳት፣ ማሳመጽ፣ ክህደትና ርኩሰት እንድትፈጽሙ መታገል ነዉ:: በዚህም እኛ እረፍት እናገኛ ለን:: የክፋት፣ የተንኮል፣ የምቀኝነት ተግባሩን እናንተም ጥቅም እንደማታገኙበት እያወቃችሁና ይልቁኑም ሰላምና ደስታችሁን እንደምታጡበት እየተረዳችሁ እንደምትፈጽሙ ሁሉ፤ እኛም ሰይጣናት እንደማንጠቀምበት ብናዉቅም ከምቀኝነት ፣ ከክፋት፣ ከተንኮል ጠባያችን የተነሳ እንፈጽመዋለን::

ያደፉ፣ የጎደፉ ባሕርያታችዉ ዉስጥ ማደራችንና ዙፋን ማድረጋችን እንደማያስገርማችሁ እንገምታለን:: ምክንያቱም እናንተም ከእግዚአብሔር ጸጋ ስትለዩ የምትፈጽሙትንና የምትዉሉበትን፣ የምታድሩበትን በደንብ እናዉቃለንና:: ሌላዉን ባንገልጽ እንኳ ከሱስ ባሕርያችዉ ብንነሳ የሚጎዳችሁ መሆኑን እያወቃችሁና ከክብራችሁ እንደሚያዋርዳችሁ እየተረዳችሁ፣ ለኑሮዋችሁ የምታወጡትን ወጭ እንደሚጋራችሁ እያስተዋላችሁ፣ ይኸዉ የሚሸተዉን የሚገማዉን ትንባሆ ታሸቱ ትምጉት የለም ወይ? ጫቱን፣ አደንዛዥ ዕፁን ትቅሙ ትጠቀሙ የለም ወይ? ጽዳታችሁን መጠበቅ ተስኗችሁ በቁማችሁ ትሸቱ፣ ሌላዉንም ታሸቱ የለም ወይ? ታዲያ የኛ በዐይነምድርና በሽንት ዉስጥ ዙፋናችንን ዘርግተን መኖራችንና ቦታዉን መምረጣችን ምን ያስገርማል! ምን ያስደንቃል? ይልቁኑ እኛ ሙሉ በሙሉ ከእግዚአብሔር ጸጋ የተለየን ስለሆነ በዚህ ጉስቁልና ሕይወት ዉስጥ መኖራችን ብዙ አያስደንቅም:: እናንተ ግን እግዚአብሔርን የመምሰል እድል

ተሰቷችሁ፣ እንደ ቅዱስን መላእክት የመሆን ተስፋ እያላችሁ የኛን ፈለግ መከተላችሁና የማይገባ ተግባርና ድርጊት መፈጸማችሁ ነዉ ሊያስገርምና ሊያስደንቅ የሚገባዉ፡፡

ታዲያ እንደዚህ ስላችሁ - አታጭሱ፣ አትቃሙ፣ አደንዛዥ ዕፆችን አትጠቀሙ፣ በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት ሕይወት ዉስጥ አትመላለሱ፤ ጽዳታችሁን ጠብቁ ለማለት ፈልገን ሳይሆን ራሳችሁን ሳታስተካክሉና እንደሰዉነታችሁ ባሕርይ ሳትመላለሱ እኛን ማንቋሸሽና ማጥላላት አቁም ለማለት ፈልገን ነዉ፡፡ እንዲሁም ገና ራሳችሁን ሳትገዙ፣ የሱስ ስሜታችሁን ሳታሸንፉ፣ ኅሊናችሁን ስናስጨንቅና ስንፈታተን ምሳችን የሆኑት የተለያዩ ሱሶች እያቀረባችሁ ለእኛ መስዋዕት የመታቀርቡ ከሆነ፤ እንዴት የራሳችሁን ስሜት አሸንፋችሁ ለአዳም ዘር የሚጠቅም መልካም ነገር እንሰራለን፣ ለሕዝቡ መስዋዕት እንሆናለን ብላችሁ ትለፍፋላችሁ? ራሳችሁንና ስሜታችሁን የገዛችሁ ብትሆኑ ኖሮ እኛም ለፖለቲካ አገልግሎት አንፈልጋችሁም ነበር፡፡ እኛ የፈለግናችሁ እንደ ሱሱ ኅሊናችሁን ስናስጨንቅ የተለያየ የግፍ፣ የጭከና፣ የበደል፣ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር እየፈጸማችሁ ስለምታስፈጽሙልንና እንደ ልባችን ስለሆናችሁ ነዉ ምርጫችን ያደረግናችሁ፡፡

ሌላዉ ልንገልጽላችሁ የምንፈልገዉ ለማፋሸኩ፣ ለማዛጋቱ፣ ለማስነጠሱ፣ ለማግሳቱ፣ ለመፍሳቱ፣ ለማከኩ፣ ለመንጠራራቱ እንደ ሌሎች ስያሜ እንዳታወጡልንና እንዳትሰይሙኝ አደራ እንላለን፡፡ ይኸዉም ቫይረስ፣ ባክቴሪያ፣ ጀርም፣ ካንሰር፣ ኤድስ፣ ብርድ፣ አላርጂክ፣ ዱካክ፣ ድብርት፣ ጭንቀት፣ ..ወዘተ እይላችሁ እንዳትሰዩሙንና በተሰጣችሁ የመከላከያ ጸጋ ጸሎት፣ ጾም፣ ስግደት፣ ቅን ሐሳብ፣ መልካም ተግባር፣ እዉነተኛ አምልኮ፣ የክርስቶስን ሥጋና ደም ተጠቅማችሁ ፍዳችንን እንዳታሳዩን ነዉ፡፡ ከዚያ ዉጭ በግልጽ ሰይጣናት፣ ዛር፣ ዉቃቢ፣ ጠንቋይ፣ ቦረንትቻ፣ መተት፣ አስማት ..ወዘተ እያላችሁ ስያሜ ብትሰጡን ስማችን ስለሆነ ቅር አይለንም፡፡ የምንመካበት ስም ስለሆነ አናፍርበትም፡፡

በዚሁ አጋጣም የምንገልጽላችሁ የአምላካችሁ የቸርነት ስራ ነዉ፡፡ ይኸዉም አመናችሁት አላመናችሁት እኛን የማጥቂያና ኃይል ማዳከሚያ የተለያዩ መድኃኒቶችን የመፍጠር እዉቀት ሰቷችሁ አንዳንዴ እኛን ልምሾና አቅመቢስ ስታደርጉን እያየን መበሳጨታችን ነዉ፡፡ የእናንተን አቅመቢስነት የተረዳነዉ ደግሞ ኤድስ ሆነ ካንሰር እያላችሁ

ስያሜ ብትሰጡንም እኛን የሚያጠቃና ልምሾ የሚያደርግ መድኃኒት እስካሁን አለማግኘ ታችሁ ነዉ። የምናዝንባችሁ ደግሞ እስከአሁን ማንም ሐኪም እዉቅና ያልሰጠን በመሆኑ ነዉ። ይሁንና እኛም በእናንተ እንድንታወቅ ስለማንፈልግ አንዳች ቅሬታ የለንም።

ሌላዉ ትዝብታችን ደግሞ አቅማችሁን አለማወቃችሁ ነዉ። ይኸዉም በገነት አኗኗራችሁ እንደ መላእክት እንቅልፍ አልነበረባችሁም ነበር። ቀንና ሌሊት የሚባል ነገር አልነበረም።ሁሌ ትጉሃን ንጹሀን ሆናችሁ በእርካታና በደስታ ሕይወት ብቻ አምላካችሁን ማመስገን ነበር ዋና ስራችሁ። ታዲያ ክብር አልወደዳችሁምና የኔን ፍጡሩን ንግግር ከአምላክ ንግግር አስበልጣችሁ በመቀበላችሁ በዉርደት ጸጋችሁ ተገፎ ራቁታችሁን ወደዚህች ምድር ወደ እኔ ግዛት ገባችሁ።

ይህ በዐይናችሁ የምታዩትም የማታዩትም ሁሉ በዚህች ቀድሞ ድቅድቅ ጨለማ ብቻ ሞልቶበት በነበረዉ ምድር ዉስጥ የተፈጠረዉ ለእናንተ ዐመጸኞች ሲባል ነዉ እንጂ ለኔ አስፈልጎኝ አይደልም። ታዲያ ያ በገነት የተገለጻችሁበት ረቂቅ አካል (ምሳሊያዊ ባሕርይ) ወደ አለመኖር ካለፈ በኋላ ይህ የምትቀጡበትን ሥጋ ለብሳችሁ (ተዋህዳችሁ) እንድትገለጹበት ተደረገ። ነፍሳችሁም ኃይሏና አቅሟ በዚህ ሥጋችሁ ተገደበ። በእርግጥ የምትናገረዉ፣ የምትሰራዉ፣ ሁሉን የምትፈጽመዉ፣ በግንባራችሁ ፍትለፊት በአንጎላችሁ ዉስጥ ያለችዉ እናንተ ኅሊና(አእምሮ) የምትሏት ነፍሳችሁ ናት። አፈጣጠሯ ከእግዚአብሔር ባሕርይ የተገኘ ች የማትሞት፣ የማታልፍ ሕያዉ ፍጥረት ናት።

ይሁንና ኃይሏና አቅማ የተገደበ በመሆኑ እኛ ከመቅበዝበዝ እረፍት የምናገኘዉ ወደ ኅሊናችሁ ቀርበን አዳክመናችሁ ስታንቀላፉልን ብቻ ነዉ። ልክ ከእሳት ዉስጥ ወቶ ወደ ዉኃ ዉስጥ የሚጣል እንጨት «ትሽ» ብሎ እንደሚቀዘቅዝ ሁሉ፤ እኛም እናንተ ስታንቀላፉልን ከስቃያችን ቀዝቀዝ ስለምንል ነዉ በእንቅልፍ የምንዘርራችሁ እንጂ ለእናንተ አዝነን አይደለም። በተለይ በቅን አሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ አምልኮ የሚመላለሱ ሰዎች በቀኑ ጊዜ ስለሚያበሳጩንና ስለሚያቃጥሉን እንቅልፋቸዉ ለእኛ ገነት ወስጥ ገብተን እንደማረፍ ነዉ የምንቆጥረዉ።

ቀኑንና ሌሊቱን ሁሉ ብታንቀላፉልን ምርጫችን ቢሆንም እናንተ የማታስተዉሉት እኛም የማናዉቀዉ ኃይል ጠዋት ላይ ሳናስበዉ ይመጣና ከጎሊናችሁ ብን አድርጎ እንደ እሳት ወላፈን አቃጥሎን ያባረናል:: እናንተም ትነቃላችሁ በእኛ ላይ ትበረታላችሁ:: ነገር ግን እንዲህ ኃይልን የሚያጎናጽፋችሁንና ብርታት የሚሰጣችሁን አምላክ በአሳባችሁ፣ በተግባራችሁ፣ በአምልኮታችሁ ማስደሰትና ማመስገን ሲገባችሁ፤ በተቃራኒዉ ለክፋት፣ ለበቀል፣ ለጥል፣ ለተንኮል፣ ለዐመጻ፣ ለክህደት፣ ለርኩሰት፣ ባጠቃላይ ለኃጢአት ተግባር ትሰለፋላችሁ:: እኛም ስንፈልግ ሌላዉ እረፍት በምናገኝበትና በምንዝናናዉ ቦታ በየመሸታዉ ቤት፣ በዳንኪራዉ ቤት፣ በየጠንቋዩ ቤት፣ በመተተኛዉ ቤት፣ በየምናምንቴዉ ቦታ እናልከሰክሳችኋለን::

እኛን በተለየ ሁኔታ እያበሳጩን ፣ እያማረሩን ያሉት ኢትዮጵያዉያን ካህናት አገልጋዮችና ምእመን ናቸዉ:: ይኸዉም እረፍት በምናገኝበት በሰዎች ኅሊና ዉስጥ በምንነግሥበት ሰዐት ሌሊት ተነስተዉ ምስጋናዉንና ጸሎቱን እያቀረቡ እረፍት ስለሚነሱን ነዉ:: ምናለ ሌሊት እንኳ ቢያሳርፉን! እነሱ እንደጨከኑብን እኛም አንተኛላቸዉም:: ለዚህም ነዉ የተለያየ ፈተና የምናመጣባቸዉና ሌት ተቀን እነሱን ለማጥፋት የምንሰለፈዉ:: ሌላዉ ዓለም እንደልባችን ስለሆነ ቀንም ሌሊትም ስለምንሰለጥንባቸዉ እንኳን በሌሊት በቀንም አያበሳጩንም፣ አይረብሹንም፣ አያቃጥሉንም::

እዚህ ኢትዮጵያ ግን በከተማም፣ በገጠርም፣ በዋሻም፣ በገዳምም በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በምስጋና፣ በምህላ፣ በእንባ ፍዳችንን እያየን ነዉ:: ትተናቸዉ እንዳንሄድ ከእናንተ አዳም ዘሮች በላይ እልኸኛ ነን:: እንዳናጠፋችዉ ኃይላችንን ልምሾ ያደርጉብናል:: እንደ አማራጭ መንገድ የያዝነዉ የተለዩ ለኛ እንደልባችን የሆኑትን ሰዎች የኛን የሱስን (የጨለማዉ ገዥ) እንዲቀበሉና እንዲያመልኩት በማድረግ፤ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ አገልጋዮችን ሆነ ምዕመኑን ከጾም፣ ከስግደት፣ ከሌሊት ጸሎትና ምስጋና መለየት፣ ከእዉነተኛ አምልኮ ስርዐት ማዉጣትና በኛ ስታይ (ለሥጋ በሚመች ስርዐት) መምራት ነዉ:: በዚህም እድሜ ለእንደራሴ መንግሰቴ ዉጤታማ እየሆን ነዉ::

በዚህ አጋጣሚ በክርስትና ስም የኛን የሱስን ተቀብላችሁና አምናችሁ በተለያየ ስም የተደራጃችሁ የእምነት ደርጅቶቼ አባላትና ዉዶቼ አገልጋዮች ስለፈጸማችሁትና

ስለምትፈጽሙት ታላቅ አገልግሎትና ተጋድሎ በጨለማዉ ስሜ እያመሰገንኳችሁ ለወደፊት ደግሞ ጠንክራችሁ እንድትሰሩ አሳስባችኋለሁ:: ለዚህም ማበረታቻ እንዲሆናችሁ የፈለጋችሁትን በፈለጋችሁት ጊዜ እንድትበሉ፣ እንድትጠጡ፣ የፈለጋችሁትን አይነት አለባበስ እንድትለብሱ፣ በፈለጋችሁት ጊዜ ወደ አዳራሼ በመምጣት አምልኮታችሁን እንድትፈጽሙ፣ በፈለጋችሁት ሰርዐት እንድታገለግሉ፣ በፈለጋችሁት መሳሪያና ዜማ እንዲሁም የጭፈራ አይነት ምስጋናዉን እንድታቀርቡልኝ ሙሉ ነጻነት ሰጥቻችኋለሁ::

የኔን መንግስትም ለመዉረስ በእኔ የሱስ ማማን ብቻ በቂያችሁ ነዉ:: ስለ ምግባር፣ ስለ ጾም አንዳች አሳብ አይግባችሁ:: የሚያሰክር መጥጡንም ቢሆን ብትጠጡት ችግር ስለሌለዉ አሁን ተደብቃችሁ እንደምትጠጡት ብትጠጡም እኔ ቅር አይለኝም:: ነገር ግን እነዚያ የእዉነተኛዉ ኢየሱስ ክርስቶስ አማኞች የእናንተ የሱስ ለየት ያለና ትክክለኛ ሃይማኖት እንዲመስላቸዉ « በኛ በየሱስ እምነት አስካሪ መጠጥ አይጠጣም» ብትሉ ብዙ ፍሬ ልታፈሩልኝ ትችላላችሁ:: ከዚያ ዉጭ ስለ ምታደርጉት ዝሙት ሆነ መዳራት፣ ስርቆት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ጥላቻ በኔ ዘንድ ይቅር እንደምትባሉ ከወዲሁ ዋስትና እሰጣችኋለሁ:: ብቻ እኔን ሁሌ በቀጥታ ይቅር በለኝ በሉ:: ባጠቃላይ ትዉልዱ ከሚጨናነቅበት ጠባብ መንገድ አስወጥታችሁ በሰፊዉ መንገድ ካስገባችሁልኝ ለዚህ ዉለታችሁ በመጨረሻ ታላቁን የጨለማዉ መንግስቴን ከተባባሪዎቻችሁና ከተከታዮቻችሁ ጭምር አወርሳችኋለሁ::

ከዚህ በተጨማሪ ወደ መጨረሻዉ ዘመን ለማድረስ መንገድ ጠራጊነቱን በደንብ እየተወጣችሁና ታለቅ ምስክርነት የሆነዉ፣ እዉነተኛ አምላክ የሆነዉን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን «አማላጅ» እያላችሁ የምትሰድቡልኝና የምታዋርዱልኝ፤ እኔን ደግሞ ደስ የምታሰኙ ኝ ስለሆነ፤ እንዲሁም ደመኛዬ ጠላቴ የሆነችዉን ለዘመናት ያስቸገረችኝን እናቱን ድንግል ማርያምን እየናቃችሁ፣ እያቃለላችሁ፣ እያጥላላችሁ፣ እየሰደባችሁ፣ እያዋረዳችሁ ስለሆን፤ በተጨማሪም ተቃዋሚ ጠላቶቼን ቅዱሳን መላእክትን እያስናቃችሁና እያጥላላችሁ፣ እየሰዳባችሁ ስለሆነ፤ እንዲሁም በምድራዊ ዘመናቸዉ ያደረሱብን መከራና ስቃይ አንሶ አሁን ደግሞ በእግዚአብሔር መንግስት ዉስጥ ሆነዉ ለሰዉ ዘሮች ምህረትና ይቅርታ የሚለምኑትን ነብያትን ፣ ሐዋርያትን ፣ ሰማዕታትን ፣ ጻድቃንን የምታጥላሉ፤ የምታዋርዱ፣ የምትሰድቡ፣

የምትንቁ ዉድ ሰባኪያኖቼና አማኞቼ  ስለሆናችሁ በጨለማዉ ስሜ ዳግም ምስጋናዬን አቀርብላችኋለሁ:: ሌት ተቀን በምታምኑበት በየሱስ ስሜ እባርካችኋለሁ:: የጨለማዉ ጌታ የሱስ ይባርካችሁ እላለሁ::

ታዲያ በኔ የማያምኑ አንዳንዶች « ስንቶቹ ነብያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን የተለያየ ጸዋትዎ መከራና ተጋድሎ ፈጽመዉ የገቡበትን ገነት በኋላም የሚገቡበት መንግስተ ሰማያት እንዴት ዘና ብለን ሳንጸልይ፣ ሳንጾም፣ ሳንሰግድ፣ ራሳችንን ሳንገዛ፣ በእዉነተኛ አምልኮ ሳናመሰግን፣ ቅን ሳናስብ፣ መልካም ሳንሰራ፣ ኃጢአታችንን በእዉነተኛ ንስሐ ሳናጠራ፣ መለኮት የተዋሀደዉን ሥጋና ደሙን ሳንቀበል፣ ባጠቃላይ ነፍሳችን ከአምላኳ ጋር ታርቃ አንድነትና ህብረት ሳትፈጥር የእግዚአብሔርን መንግስት እንወርሳለን?» በማለት የሕይወትን መንገድ ያሚያወሳስቡትንና መንገዱን ጠባብ የሚያደርጉትን መንገዱ የጠፋባቸዉን ሰዎች አትስሙ:: መንገዳቸዉንም አትከተሉ::

እነሱ በማቲዎስ ወንጌል ም.፯፥፲፫(7:13) ላይ ያለዉን « በጠበበዉ ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወሰወደዉ ደጅ ሰፊ፣ መንገዱም ትልቅ ነዉና፣ ወደ እርሱ የሚገቡ ብዙዎች ናቸዉ፤ ወደ ሕይወት የሚወስደዉ ደጅ የጠበበ፣ መንገዱም የቀጠነ ነዉና፣  የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው::» የሚለዉን ቃል መመሪያ የሚያደርጉ፤ እኔ ያዘጋጀዉትን፣ የተሻሻለና የታደሰ ሰፊዉን መንገድ ያላወቁ ናቸዉ:: ይልቁኑ « የሱስን ተቀበሉ፤ የሱስ ያድናል፤ ከዚያ ዉጭ ምግባር፣ ጾም፣ አያድንም::» እያላችሁ በየመንገዱ፣ በየአዳረሹ፣ በየትምህርቱ ቤቱ፣ በየለቅሶ ቤት፣ ብቻ ባገኛችሁት ቦታ ስበኩ:: ሕዝቡ ከታሰሩበትና ከተተበተቡበት የጾም ስርዐት፣ የምስጋና ስርዐት፣ ከሥጋዉና ከደሙ ለዩ:: በመጨረሻም በኔ ሰፊዉ መንገድ አስገቧቸዉ:: ያኔ የጨለማዉ መንግስቴን ይወርሳሉ:: ሁላችሁም በኔ ሰፊዉ መንግስቴ ከኔጋር ሕያዉ ሆናችሁ ትኖራላችሁ:: ትነግሣላችሁ::

እንዲሁም እነሱ የእግዚአብሔር ፍርድና ዉሳኔ እጅግ ጥብቅ ሞሆኑን ለማሳወቅ በማርቆስ ወንጌል ም.፱፥፵፪-፵፰(9:42-48) ላይ ያለዉን «በእኔም ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ ትልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር

ቢጣል ይሻለዉ ነበር፡፡ እጅህ ብታሰናክልህ ቁረጣት፤ሁለት እጅ ኖሮህ ትላቸዉ ወደ ማይሞትበት እሳቱም ወደ ማይጠፋበት ወደ ገሃነመ ወደማይጠፋ እሳት ከመሄድ ጉንድሽ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻላል፡፡ እግርህ ብታሰናክልህ ቁረጣት፤ ሁለት እግር ኖሮህ ትላቸዉ ወደማይሞትበት እሳቱም ወደማይጠፋበት ወደ ገሃነመ ወደማይጠፋዉ እሳት ከመጣል አንካሳ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል፡፡ <u>ዓይንህ ብታሰናክልህ አዉጣት፤ ሁለት ዓይን ኖሮህ ትላቸዉ ወደ ማይሞትበት እሳቱም ወደ ማይጠፋበት ወደ ገሃነመ እሳት ከመጣል አንዲት ዓይን ኖራህ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት ይሻልሃል</u>፡፡» በማለት የአምላካቸዉን ቃል በቀጥታ በመጥቀስ ሊያስፈራሯችሁ ሲፈልጉ፤ እናንተ ግን «ጌታ ርኅሩኅ ነዉና መቸስ ጨክኖ ትሉ ወደማይሞትበት እሳቱም ወደማይጠፋበት ገሃነመ እሳት ዉስጥ አይከተንም፡፡ ይህን ትምህርት የሰጠዉ ርኅሩኅ መሆኑን ዘንግቶት ይሆናል እንጂ « የጌታን ስም የጠራ ሁሉ ይድናል» በማለት ተነግሯል ፡፡ ስለዚህ እኛ የየሱሴን ስም ጌታን ስለምንጠራ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ሳይሆን የእግዚአብሔር መንግስት ዉስጥ ነዉ የምንገባዉ፡፡» በማለት ልታሳፍራቸዉና አፋቸዉን ልታሲዙ ይገባል፡፡

ምናልባት እነሱ፤ «በፍርድ ቀን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ብዙዎች በስምህ አላስተማርንምን? ብዙ ተአምራትን አላድረግንምን? ትንቢት አልተናገርንም? ፈዉስ አላደረግንምን? » ይሉኛል እኔ ግን የዐመጻና የክህደት ሕይወታቸዉን አዉቃለሁና ስለ ዐመጸኛነታቸዉ እመሰክርባቸዋለሁ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ አይድንም፡፡ ፈቃዴን የሚፈጽምና የሚያስፈጽም ብቻ ነዉ የሚድነዉ» ብሏል፤ በማለት እንኳን እናንተን በኔ በጨለማዉ ገዥ ባዘጋጀዉት የሕይወት መንገድ የምትመላለሱትን ቀርቶ እርሱ ባለቤቱ በመሰረተዉ የሕይወት መንገድ ዉስጥ ሆነዉ በስሙ የሚነግዱበትን አስመሳይ አገልጋዮችን እንኳ «እናንተ ዐመጸኞች ለዲያብሎስና ለሠራዊቱ ወደ ተዘጋጀላቸዉ የዘላለም መቀጫ ቦታ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ግቡ» ብሎ ካለምንም አድሎ እንደሚፈርድባቸዉ ከመጽሐፍ ቅዱስ በመጥቀስ የሚናገሩትን ሆነ የሚያስተምሩትን አንዳች እንዳትሰሙ፤ እንዳትቀበሉ፡፡

ምክንያቱም ከሰማችሁ ፍርዱ ይብስባችኋልና ዝም ብላችሁ «የሱስ ጌታ ነዉ፤ የግል አዳኜ ነዉ» ብላችሁ በአቋራጭ መንገድ ወደ እግዚአብሔር መንግስት መግባት ይሻላችኋል።

እነሱ የጳዎሎስን መልእክት ወደ ገላቲያን ሰዎች ም.፭፥፲፮-፳፬(5፡16-24) «ነገር ግን እላለሁ፣ በመንፈስ ተመላለሱ፣ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ። ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፣ እነዚህም እርስ በእርሳቸዉ ይቀዋወማሉና፤ ስለዚህ የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም። በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም። የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነዉ እርሱም ዝሙት፣ ርኩስት፣ መዳራት፣ ጣዖትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት ይህንም የሚመስል ነዉ። <u>አስቀድሜ እንዳልኩ፣ እንደዚህ ያሉትን የሚያርጉ የእግዚአብሔር መንግስትን አይወርሱም።</u> የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የዉሃት፣ ራስን መግዛት ነዉ። እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም። የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑት ሥጋና ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።» የሚለዉን ሕያዉ ቃል ወዲያ ወዲህ እንዳትሉ የሚያደርገዉን ጥቅስ እየጠቀሱ ተስፋ ሊያስቆርጧችሁና ከኔ ከጨለማዉ ገዥ ሊለያችሁ ቆርጠዉ ከተነሱት ሰዎች ጋር አንዳች አንድነትና ህብረት እንዳትፈጥሩ።

እነሱ ዓለማቸዉ ዘና ብላችሁ እየዘሞታችሁ፣ እየተዳራችሁ፣ ምንፍቅና እየፈጸማችሁ፣ እየተለያያችሁ ከምትኖሩት የደስታ ሕይወት ሊለያችሁና፤ በምቀኝነት ሕይወት እንዳትኖሩና በእግዚአብሔር ቃል እንዳትዘፍኑ፣ እንዳትጨፍሩ ሊያደርጓችሁ የሚፈልጉ «ካለ ምግባርና እዉነተኛ እምነት የእግዚአብሔርን መንግስት አትወርሱም» በማላት ከኔ ከሰፊዉ የሕይወት መንገድ ሊያወጧችሁ የሚፈልጉ በኔ ተቃራኒ መንፈስ የሚመሩ ናቸዉ። ይልቁኑ እናንተ በሰፊዉ መንገድ ሊያስኬዳችሁ የሚያስችለዉን ቃል ከመጽሐፍ ቅዱስ እየመረጣችሁ ለእናንተ እንደሚመች አድርጋችሁ በመተርጎም አፋቸዉን ልታዘጉ ይገባል እንጂ በምንም ሁኔታ

ከምትዝናኑበትና ከምትጨፍሩበት እንዲሁም እንደፈለጋችሁት ከምትሆኑበት ዓለም ሊለያችሁ የሚችል እምነት ሆነ ሃይማኖት እንዳትቀበሉ::

እነሱ ሲያስፈልጋቸዉ ደግሞ እንኳን እናንተ ሌላዉም ሰዉ በእዉነተኛ ንስሐ ወደ እግዚአብሔር ካልተመለሱ እንደሚጠፉ ለመግለጽ በሉቃስ ወንጌል ምእራፍ፲፫፥፩-፭(13:1-5) ያለዉን ከመጥቀስ ወደ ኋላ አይመለሱም:: ይኸዉም «በዚያን ጊዜም ሰዎች መጥተዉ ጲላጦስ ደማቸዉን ከመሥዋዕታቸዉ ጋር ስለደባለቀዉ ስለ ገሊላ ሰዎች አወሩለት:: ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸዉ - እነዚህ የገሊላ ሰዎች ይህ ስለ ደረሰባቸዉ ከገሊላ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ኃጢአተኞች የሆኑ ይመስላችኋልን? እላችኋለሁ፣ አይደለም፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ:: ወይስ በሰሊሆም ግንብ የወደቀባቸዉና የገደላቸዉ እነዚያ አስራ ስምንት ሰዎች በኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሁሉ ይልቅ በደለኞች ይመስላችኋልን? አይደለም፣ እላችኋለሁ፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ::» ብሏል እግዚአብሔር ቢሏችሁ፤ « እኛ እኮ ኃጢአተኞች አይደለንም፤ ጻድቃን ነን:: እንኳን መጥፋት አይደለም አንዲቱ ጸጉራችን አትነካም፤ ይልቅ - እናንተ ኃጢአተኞች በየሱስ ስም እንጸልይላችሁና ጻድቅ የሚለዉን ማእረግ እናጎናጽፋችኋለን» በማለት ኃይለኛ የመልስ ምት ስጧቸዉ እንጂ በምንም መልኩ « እኛ ኃጢአተኛ፣ በደለኛ፣ ከሃዲ፣ መናፍቅ ነን» ብላችሁ ንስሐ እንዳትገቡ፤ እዉነትንም እንዳትቀበሉ ከአደራና ከማስጠንቀቂያ ጭምር ነዉ የምመክራችሁ::

እናንተ የአዳም ዘሮች ትዝብቴን ልንገራችሁ:: ይኸዉም የኛን ያህል ኃይልና ብቃት ሳይኖራችሁ ሁሉን እንደምታደርጉ እንደፈለጋችሁት መሆን እንደምትችሉ ትደነፋላችሁ፣ ተፈጥሮን እንቆጣጠራለን እያላችሁ ትታበያላችሁ፣ እንዲህ ይሆናል እያላችሁ መፈክር ታሰማላችሁ :: አንዳንዴ እኛ ሰይጣናት እርስ በእርስ ስንጫወት «እነዚህ የአዳም ዘሮች በዚህ ግዙፉ ያደፈና የጎሰቆለ ባሕርይ በተላበሰዉ ሥጋ ተገደቡ እንጂ እንደኛ በረቂቅ አካል ተገልጸዉ ቢሆን ኖሮ በቅጽበት ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስ ይችላሉና ፈጣሪን ከሰማያት

ዉስጥ እናዉርድ» በማለት ሰማያዊ ጦርነት ያዉጁ ነበር እንላለን፡፡ አንዳንዴ ደግሞ በበሽታ ስትያዙ፣ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ላይ ሆናችሁ ዐይናችሁ ክርትት ክርትት ሲል፤ በተቃራኒ ኃይል ተሸንፋችሁ ስትማረኩና ባለጊዜነታችሁ ተሽሮ የዘራችሁትን ስታጭዱ ኩምሽሽ ብላችሁ ስንመለከታችሁ «አይ የሰዉ ጥጋብና እብሪት! ያ የሚደነፋና የሚታበይ አንደበትና ሕይወት ወዴት ሄደ?» እንላለን፡፡

በንግግራችሁና በድርጊታችሁ ሁል ጊዜ እንታዘባችኋለን፡፡ ይኸዉም ከራሳችሁ ሆነ ካለፉት ሰዎች እጣ ፈንታ መማር ተስኗችሁ ቀደም ያሉት የፈጸሙትን ግፍ፣ ጭከና፣ በደል፣ አድሎ ተንኮል፣ ደባ፣ ብቻ ምኑ ተነግሮ ያልቃል እናንተም ትደግማላችሁ፡፡ እነሱ የዘሩትን ፍሬ መራራም ቢሆን ሳይፈልጉት ጠጥተዉት ማለፋቸዉን እያወቃችሁ «ነግ በኔ »ሳትሉና፤ «እኛም የዘራነዉን እናጭዳለን፡፡ መራራም ከሆነ መራራዉን ነዉ የምንጠጣዉ፡፡» ብላችሁ መልካም ፍሬ ከማፍራት ይልቅ ለክህደት፣ ለዐመጻ፣ ለርኩሰት፣ ለጭካኔ ተግባር ታጥቃችሁ ትሰለፋላችሁ፡፡ አምላካችሁንም እለት እለት ታስቆጣላችሁ፡፡

ታዲያ እንዲህ ስላችሁ እግዚአብሔርን በመፍራት ኑሩ፤ በቅንነትና በእዉነት ሕዝቡን ምሩ፤ አገልግሉ፤ ተስፋችሁን ሰማያዊ አድርጋችሁ በሰማያዊ ስርዐት ተመላለሱ፤ በሥጋችሁም በነፍሳችሁም የምትጠቀሙበትን ተግባር ፈጽሙ፤ «የዘራነዉን እናጭዳለን» ብላችሁ ፍሩ፤ «ለሰራነዉ ግፍና በደል ዋጋ እንከፍልበታለን» ብላችሁ ስጉ፤ «መልካም ከሰራን በሥጋችንም በነፍሳችንም ዋጋ እናገኝበታለን» ብላችሁ አስቡ፤ ስላለፈዉ ኃጢአታችሁ ንስሐ ግቡ፤ ከዚህ በኋላ ወደ ልባችሁ ተመልሳችሁ እግዚአብሔር በሚደሰትበት ሕይወት ተመላለሱ፤ ለማለት ፈልጌ እንዳልሆነ በተለይ እንደራሴዎቼ መሪዎችና ባለሟሎቼ ባለስልጣናት እንዲሁም ዉዶቼ ካድሬዎች በደንብ ታዉቃላችሁ፡፡

በመሆኑም ከላይ የዘረዘርኩትን መልካም ተግባራት ከፈጸማችሁ እነዚያ የቀደሙት እንደወደቁት አይወድቁ አወዳደቅ ነዉ የምትወድቁትና የታላላቅ መሪዎችና ባለስልጣናት እጣ ፈንታ ነዉ የሚደርስባችሁ፡፡ ስለዚህ ሕዝቡን በኃይልና በጭከና እንድታስተዳድሩ፤ ራሳችሁን ብቻ እያበለጸጋችሁ ሕዝቡን እንድታደኸዩ፤ በክፋት፣ በተንኮል፣ በዐመጻና በክህደት፣ በርኩሰት፣ በጭከና፣ በበደል፣ በግፍ፣ በጭቆና፣ በዘረኝነትና በጎጠኝነት ሕይወታችሁ

እሰከመጨረሻዉ እንድትጸኑ ነዉ የጨለማዉ ምክሬ:: ባጠቃላይ እኔን በሚያስደስት እግዚአብሔርን በሚያስቆጣ ተግባርና ንግግር ላይ እንድትተጉ በመጨረሻም የኔን ጨለማ ግዛት መንግስቴን እንድትወርሱ ነዉ ፍላጎቴና ምኞቴ::

የዚህ ምእራፍ ማጠቃለያዬ ከህጻንነታሁ ጀምሮ ነፍስ ከሥጋችሁ እስከምትለይ እናንተ ከዓለም ዉጣ ዉረድ ከኔ ፈተና የምትገላገሉበትን ያ የምትፈሩት ሞት እስኪመጣባችሁ ድረስ የምፈታተናችሁ፣ የማጎሳቁላችሁ መሆኑን በዚህ ምድር ቆይታችሁ ሌት ተቀን የኔን የጨለማዉ ገዥ ፈቃድ ለመፈጸም ለማስፈጸም የምትተጉ፣ በዚህም ድርጊታችሁ ሲያልና ገሃነመ እሳትን እንደምትወርሱ፣ በምድርም የስራችሁን እንደምታገኙና ዋጋም እንደምትከፍሉበት፣ ባጠቃላይ ጎስቋላ ኑሮና ሕይወታችሁን እንድታዉቁ፣ እንድታስተዉሉ በግልጽ ያስቀመጥኩላችሁ፤ ከንቱነታችሁን አስተዉላችሁ፣ ራሳችሁን በእግዚአብሔር ፊት አዋርዳችሁና ዝቅ አድርጋችሁ እንድትኖሩ፣ ለሰዉ ልጆችም ቅን እንድታስቡ፣ መልካም እንድትሰሩ፣ በበደል ዉስጥ ያላችሁትም ንስሐ ገብታችሁ የክርስቶስን ሥጋና ደም ተቀብላችሁ ለሰማያዊ መንግስት እንድትበቁ ፈልጌ ሳይሆን፤ የልባችሁን ደንዳናነት አዉቃለሁና እንኳን የኔን የፍጡሩን ለዚያዉም የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስን ቃልና ንግግር ሰምታችሁ መቀበልና መለወጥ ቀርቶ ፈጣሪ አምላካችሁ በሥጋ ተገልጾ፣ የተለያየ ፈዉስና ተአምራት በማድረግ በትህትና ያስተማራችሁን፣ የተናገራችሁን ሕያዉ ቃል ተቀብላችሁ ተግባራዊ አላደረጋችሁም::

ይልቁኑ ሰደባችሁት፣ አዋረዳችሁት፣ ወነጀላችሁት፣ ተፋችሁበት፣ ገረፋችሁት፣ አንገላታችሁት፣ ተሳለቃችሁበት፣ ዘበታችሁበት፣ አዳፋችሁት፣ ሰቀላችሁት፣ በመስቀል ላይ ሆኖ «ተጠማሁ» ቢላችሁ እንኳ ሳትራሩለትና ሳታዝኑለት መራራ ሀሞትን አቀረባችሁለት፤ ባጠቃላይ እንኳን ለመጋቢያችሁና ለአጠጪችሁ እግዚአብሔር ቀርቶ ለኔ ለጠላታችሁ ዲያብሎስ መደረግ የሌለበትን ድርጊት ፈጸማችሁ:: ሁለት ሺህ ዘመን አልፎ እንኳ እስካሁን ድረስ አላመናችሁበትም፤ እንደ ቃሉ ሆናችሁ አልተገኛችሁም፤ ከሃዲዎችና አስመሳዮች ናችሁ::

ታዲያ እንዲህ ስላችሁ እመኑበት፣ ትዕዛዙንና ሕጉን በመጠበቅ እንደ ቃሉ ሆናችሁ ተገኙ፣ በእዉነትና በመንፈስ አምልኩት ማለቴ ሳይሆን ማንነታችሁንና ድርጊታችሁን እወቁ፤

እኔ ከእናንተ በመቶ እጥፍ ስለምሻል ለኔ ፍርዱ ይቀልልኛል፤ በእናንተ ላይ ፍርዱ እጅግ ይብሳል፤ ስለዚህ ፍርዱን እንዳቀልልላችሁ ሌት ተቀን እኔን የጨለማዉን ገዥ ዲያብሎስን በደንብ አምልኩኝ፤ ፈቃዴን ለመፈጸምና ለማስፈጸም ትጉ፤ የስራችሁን ዋጋ እሰጣችኋለሁ፤ መንግስቴንም አወርሳችኋለሁ ለማለት ፈልጌ መሆኑን እናንተ የአዳም ዘሮች በደንብ ታዉቃላችሁ ብዬ ነዉ::

ባጠቃላይ የኔን ጨካኝነት ፣ የአምላካችሁን ፍቅርና ትዕግስት በደንብ የዘረዘርኩላችሁ እኔን ጨካኙና ክፋዉን የግብር አባታችሁን እንድትጠሉ፣ እዉነተኛ አባታችሁን እግዚአብሔርን እንድትወዱና ፈቃዱን እናንተም ፈጽማችሁ ሌላዉንም በማስፈጸም መንግስቱን እንድትወርሱ ፈልጌ ሳይሆን፤ እኛ ሰይጣናት እንደ እናንተ፤ አምላክ ተገልጦልን « ይህን አታድርጉ፣ ይህን ካደረጋችሁ ይቅር እላችኋለሁ፣ ወደ መጀመሪያዉ መኖሪያችሁ መንግስተ ሰማያት አስገባችኋለሁ» ብሎ አስተምሮንና ተስፋ ሰቶን ቢሆን ኖሮ እንኳን በዐመጻና በክህደት መመላለስ ቀርቶ ምድራዊ ዘመናችንን በመቸገርና በኀዘን፣ በእንባ ብናሳልፍ ምርጫችን ነዉ :: ነገር ግን ለእናንተ የተሰጠ እድል ለእኛ አልተሰጠም:: ለዚህም ነዉ በዐመጻችንና በክህደታችን የጸናነዉና እናንተንም ከአምላካችሁ ጋር በማጣላትና በማስቀጣት ተግባርና አሳብ ላይ እንድትሰለፉ ሌት ተቀን የምንፈታተናችሁና ለዐይን ቅጽበት እንኳ የማንለያችሁ:: እናንተንም በተግባራችሁና በንግገራችሁ ብቻ አይደለም አሳባችሁን የምንከታተልና እንደ ዉሎዋችሁና አዳራችሁ በተለያየ ፈተና ለመጣል የምንተጋዉ::

እናንተ ግን እንኳን ስለእዉነት ራሳችሁን ክዳችሁ በእዉነት በመኖር የተለያዩ ፈተናዎችን መታገስና ስለነገረ መስቀሉ ማንባት ቀርቶ፤ የምትበሉትን ፣ የምትጠጡትን ሳያጎልባችሁና የመዳኛን መንገድ አቅልሎላችሁ «ሥጋዬን ከበላችሁ ደሜን ከጠጣችሁ ሕያዉ ሆናችሁ በመንግስቴ ትኖራላችሁ:: ምንም ከማይጠቅማችሁ ከክፋት፣ ከተንኮል፣ ከምቀኝነት ፣ ከቅናት፣ ከትዕቢት፣ ከዐመጻ፣ ከክህደት፣ ከጥንቆላ፣ ከመተት፣ ከአስማት፣ ከድግምት፣ ከተለያዩ ባዕድና ከጣዖት አምልኮ፣ ከግድያ፣ ከስርቆት፣ ከበደል፣ ከግፍ፣ ከዝሙት፣ ከአመንዝረኛነት፣ ከዘረኝነት፣ ከጎጠኝነት ፣ ከዘፋኝነት ፣ ከዳንኪራ፣ ከሚርት፣ ከቂም በቀል፣

ከጥላቻና ከጥል፣ ባጠቃላይ ከሚያረክሱና ከሚጎዳችሁ ተግባር ተለዩ:: ቅን አስቡ፣ መልካም ስሩ፣ ከዘልማድ ሕይወት ወታችሁ በእዉነትና በመንፈስ አምልኩኝ:: » ያለዉን የሚጠቅማችሁን ትዕዛዝ «አንፈጽምም» ብላችሁ፤ እለት እለት እግዚአብሔርን በሚያስቆጣ እኔን ዲያብሎስን በሚያስደስት ተግባርና ድርጊት ላይ ተሰማርታችሁ ትዉላላችሁ፤ ታድራላችሁ::

ታዲያ እንዲህ ስላችሁ እኔን አታስደስቱ፤ እግዚአሔርንም አታስቆጡ ለማለት ፈልጌ ሳይሆን ፤ «ምርጫ እናዉቃለን፣ በትክክለኛዉ መንገዳችንም እንጓዛለን፣ አዋቂዎች ምሁር ነን » ብላችሁ ራሳችሁን ስለምታመጻድቁ፤ ምርጫችሁና መንገዳችሁ ምን እንደሚመስል እንድታዉቁትና የኔ መንገድ ተመራጭ ያደረጋችሁ የአዋቂዎች አዋቂ መሆናችሁን ልመሰክርባችሁ ነዉ:: በመጨረሻ የኔ የጨለማ ገዥ ወዳጅና ባሪያ የሆነ ሰዉ የምጠይቀዉ፤ ሌት ተቀን ለመፈታተንና ለማጥቃት ስቀርባቸዉ እንደ ካስ እያነጠሩኝ የሚመልሱኝ ያስቸገሩኝን፣ በዐለት ላይ የታነጹ ፣ በቅን አሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ አምልኮ ዉስጥ ሆነዉ በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት የሚያቃጥሉኝና ጉዳት ላደርስባቸዉ ያልቻልኩትን እንደ ግድግዳ የሆኑብኝን ሰዎች ከኔ ግዛት ትለዩልኝ ዘንድ ነዉ:: በዚህ ድርጊታችሁም የምትመኙትንና ሌት ተቀን የምትጋደሉለትን ጨለማዉ ግዛቴን ሲያልን በኋላም የጋራ መንግስታችንን ታላቁን መንግስተ ገሃነመ እሳትን አወርሰዋለሁ:: » **ይላል ሐሳቹና ጨካኙ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ሰይጣናት ጭምር::**

# ምእራፍ ሦስት

« እናንተ የአዳም ዘር፤ የመጀመሪያ የገነት አኗኗራችሁን ባለማየታችሁ እድለኞች ናችሁ:: ይኸዉም እንደ ቅዱሳን መላእክት በረቂቁ አካል( ምሳሌያዊ ባሕርይ) የተገለጻችሁበትን፤ እንደዚህ ምድራዊ ኑሮ መብላት፣ መጠጣት የሌለበትን ፤ በመብላታችሁ፣ በመጠጣታችሁ ምክንያት የተከሰተባችሁ ያደፈና የጎደፈ ባሕርይ የሆኑት ዐይነምድር፣ ሽንት፣ ላበት፣ መሽተት የሌለባችሁን፤ ለመኖር ስትሉ መዉጣትና መዉረድ የሌለባችሁን፤ ዝናብ፣ ፀሐይ፣ ሙቀት፣ ቅዝቀዜ ለመከላከል መጠለያ የማያስፈልጋችሁና የማይፈራረቁባችሁን፤ ስራችሁ የነበረዉ እንደ ቅዱሳን መላእክት ለፈጣሪያችሁ ምስጋና ማቅረብ ብቻ መሆኑን፤ በዚያም እዉነተኛ ደስታንና እርካታን የምታገኙ እንደነበረ፤ የዚህ ምድራዊ ኑሮ አኗኗር ስርዐት አለመኖሩን፤ ብርሃንና ጨለማ እንደማይፈራረቅባሁችሁ፤ ሁሌ በማይጠፋ በእዉነተኛ ምሳሌያዊ ብርሃን ዉስጥ ትኖሩ የነበረዉን፤ ቀን ከሌሊት በኔ የማትፈተኑበትን ሕይወት፤ ሁል ጊዜ በሰላም፣ በደስታ፣ በእርካታና በቅድስና ሕይወት ብቻ መኖሩን፤

እንዲሁም ጎስቋላ ባሕርይ የሆኑት ማልቀስ፣ ማማጥ፣ መዳህ፣ ማዘን፣ መቸገር፣ መተከዝ፣ መራብ፣ መጠማት፣ መታመም፣ መሞት የመሳሰሉት እንደማይከሰትባችሁ፤ በራስ ተነሳሽነትና ፈቃደኝነት የተፈጠሩ የማይገቡ ባሕርያትና ጠባይ የሆኑት መለያየት፣ በጠላላት፣ መበቃቀል፣ መከፋፈል፣ አድሎ፣ በደል፣ ግፍ፣ ጭከና፣ ጭቆና፣ ግድያ፣ ጦርነት ፣ ልዩነት ፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት ፣ ቅናት፣ ጣዖትና ባዕድ አምላኮት፣ ክህደት፣ ዐመጻ፣ ዝሙት፣ አመንዝረኛነት ፣ ዘረኝነት ፣ ጎጠኝነት ፣ ዘፋኝነት ፣ ዳንኪርተኛነት ፣ የተለያዩ ርኩሰት ተግባር የመሳሰሉት የማይታዩበትን፤

ባጠቃላይ ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርያት እንደሌሉባችሁ አዉቃችሁና አስተዉላችሁ ቢሆን ኖሮ፤ እንኳን እርስ በእርስ መገዳደል፣ መጨካከን ፣ መከፋፋት፣ ራስ ወዳድነት፣ ስግብግብነት፣ አድሎ፣ በደል ፣ዐመጻና ክህደት፣ የተለያዩ የርኩሰት ተግባርን መፈጸም ቀርቶ በኅሊናችሁ አታስቡትም ነበር:: አንዲት ቀን በዚህች ምድር ዉስጥ መኖርን አትመርጡም ነበር:: ለክፋትና ለተንኮል ተግባር አትሰለፉም ነበር:: በዐመጻ፣ በክህደት፣

በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ አትኖሩም ነበር ። ባጠቃላይ ተስፋችሁን ሰማያዊ በማድረግ እግዚአብሔርን በመፍራት ትኖሩ ነበር።

አንዳንድ ቀን ወደ ልቤ ስመለስ የእግዚአብሔርን ፍርድ አደንቃለዉ። ይኸዉም « እነዚህ የአዳም ዘሮች ይህ ሁሉ ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርያትን ተላብሰዉ እደዚህ በከፋና በከረፋ የዐመጽ፣ የክህደትና ርኩሰት ተግባርና ሕይወት ይመላለሳሉ። እርስ በእርስ ይገዳደላለሁ፤ይመቀኛኛሉ፤ ይጣላሉ፤ይከፋፈላሉ፤ ይለያያሉ። ሌት ተቀን አምላካቸዉን በሚያስቆጣ ተግባርና ንግግር ላይ ይሰማራሉ። ስለዚህ በዚህች ምድር ዉስጥ በዚህ ጎስቋላ ኑሮና ሕይወት መኖራቸዉ ሲያንሳቸዉ ነዉ። እኛ ሰይጣናት እንኳ እርስ በእርስ አንጣላ፣ አንገዳደል፣ አንከፋፈል፣ በአንድነትና በህብረት ሆነን የአዳም ዘርን መፈታተንና ማጎሳቆል ነዉ ተግባራችን። በእኛ ሰንድ ተስፋ መቁረጥና ስንፍና የለም፤ እስከመጨረሻዉ ነፍስ ከሥጋችሁ እስከመትለይ ድረስ በትጋትና በቆራጥነት የአዳም ዘርን ከመፈታተንና ከማጎሳቆል ወደ ኋላ አንልም። በእኛ ዘንድ እርስ በእርስ ምቀኝነት ፣ ተንኮል፣ ቅናት፣ መጠላለፍ የለም። በአንድ ዓላማ በአዳም ዘር ላይ ዘመቻ ማድረግ ነዉ ሌት ተቀን እቅዳችንና ተግባራችን።

እግዚአብሔር ግን በአዳምና ሔዋን በዐመጻቸዉ መጸጸትና እንዲሁም እናንተ ልጆቻቸዉ ባላወቃችሁትና ባልፈጸማችሁት ዐመጻ ምክንያት፤ በቅን አሳብና በመልካም ተግባር እንዲሁም በእዉነትና በመንፈስ በምትፈጽሙት እዉነተኛ አምልኮ አማካይነት ዳግም ወደ ገነትና ከፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ ወደ መንግስተ ሰማያት የመግባት እድል ሰጣችሁ። እናንተ ደግሞ ከአዳምና ሔዋን ብሳችሁ አንድ ትዕዛዝ መሻርና መጣስ አይደለም አንዱን ቀላል ትዕዛዝ መፈጸም ያልቻላችሁ የዐመጸኞች ዋና ዐመጸኛ ናችሁ። የከሃድያንም ዋና ከሃዲ ናችሁ። ምክንያቱም እኔ ዐመጸኛና ከሃዲ የተባልኩት ዲያብሎስ እንኳ የእናንተ የአዳም ዘር ያህል በእግዚአብሔር ላይ የሚያስቆጣ ተግባር አልፈጸምኩም፤ አልፈጽምም።

እኛ ሰይጣናት እንደ እናንተ ዳግም ወደ መንግስተ ሰማያት ወደ መጀመሪያ መኖሪያችን የመመለስ እድል ቢሰጠን ኖሮ ሌት ተቀን እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት ተግባርና አሳብ ዉስጥ በተመላለስን ነበር! ነገር ግን እኔ ዋናዉ አለቃቸዉ ዲያቢሎስ የተባልኩት ሆነ

ሠራዊቱ ሰይጣናት የተባሉት ሁሉ በነጻ ኅሊናችን ተመርተን በእግዚአብሔር ላይ ዐመጻና ክህደት በመፈጸማችን እንዲሁም አንዳንዶቹ «እኔ ነኝ የፈጠርኳችሁ ለኔ ተገዙ፤ እኔን አምልኩ» ስል፤ እንደነ ሚካኤልና ገብርኤል መቃወምና ከእነሱ ጋር መሰለፍ ትተዉ « ምናልባት ጌታችን ሊሆን ስለሚችል ከእርሱ ጎን መሰለፍ አለብን» ያሉት ሁሉ ጸጋቸዉን ተገፎ ይኸዉ ከኛ ጋር በጎስቋላ ባሕርይ በምሳሌያዊ ባሕርይ (በረቂቅ አካል) ተገልጸዉ ፍዳቸዉን በዚህች ምድር ያያሉ።

የተገረምኩትና የታዘብኩት የእግዚአብሔር ፍርድ ደግሞ እኛ በአንድ ጊዜ ዐመጻችንና ክህደታችን ለዚያዉም በግልጥ ማንነቱን ሳናዉቅ፤ ነገር ግን ኅሊናችን እየመሰከረብን በፈጸምነዉ ዐመጻ እንደ ቅዱሳን መላእክት የነበረዉ ጸጋ ተገፎ ቅድስናችንን አተን በተጎሳቆለ ባሕርይ ዉስጥ እንድንኖር ወደዚህች ምድር ቀድሞ ( አዳምና ሔዋን ከገነት ተባረዉ እስከሚመጡ ድረስ) ድቅድቅ ጨለማ ዉስጥ መጣላችን ነዉ። እንዲሁም የእናንተ አባትና እናት የሆኑት አዳምና ሔዋን በግልጽ እግዚአብሔርን እያወቁና አንዲት ምሳሌያዊ ባሕርይ የሆነች ፍሬ «አትብሉ» ተብለዉ «ከበላችሁ ደግሞ የሞት ሞትን ትምታላችሁ» ተብለዉ የኔን ፈተና ማለፍ አቅቷቸዉ በድፍረት በመብላታቸዉ ምክንያት ከኛ በከፋ መልኩ ባደፈ፣ በጎደፈ፣ በጎሰቆለ ባሕርይ እንዲገለጹና በገነት ተገልጸዉበት የነበረዉን ረቂቅ አካል ( ምሳሌያዊ ባሕርይ) ወደ አለመኖር አሳልፎ ይህን ግዙፍ ሥጋ ከመሬት አበጅቶት ነፍሳቸዉ እንድትገለጽበት በማድረጉ ነዉ።

የኔን ቃል አምነዉ በመቀበላቸዉና ዐመጻ በመፈጸማቸዉ ምክንያት ይኸዉ ሌት ተቀን ወደተለያዩ አካላችሁና ነፍሳችሁ እየቀረብኩ እንደገነቱ ፈተና በኅሊናችሁ ኃጢአት እንድትፈጽሙ ሹክ እላችኋለሁ። ኃይላችሁንም አዳክማለሁ፤ አጎሳቁላችኋለሁ። «አትሞቱም፤ እንደእግዚአብሔር ትሆናላችሁ» ያልኩትን አምናችሁ ስለተቀበላችሁና ስላመጻችሁ ከዚህ ከተገለጻችሁበት ሥጋ በሞት ትለያላችሁ። እንዲሁም «የሞት ሞትን ትሞታላችሁ» የተበለዉን፤ «አትሞቱም» ስላችሁ አምናችሁ ስለተቀበላችሁና ስላመጻችሁ የሞት ሞት የሆነዉ ዳግም የንስሐ እድል የማታገኙበትን፣ በኃጢአታችሁ ምክንያት ነፍስ ከሥጋችሁ

ስትለይ በቀጥታ ወደ ሲያል ገብታ ነጻነቷ ተገድቦ እስከ ፍርድ ቀን ድረስ በስጋት፣ በጭነቀት፣ በስቃይ ትኖራለች::

ከፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ የበለጠ ነጻነቷ ተገድቦ ከኛ ጋር እሳቱ ወደ ማይጠፋ ምሳሌያዊ ባሕርይ እሳት፣ ትሉ ወደ ማይሞት ምሳሌያዊ ባሕርይ ትል ወደ ሞላበት ገሃነመ እሳት ዉስጥ ትገባላችሁ:: እስከ ሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ ከእናንተ ሆነ ከእኛ አእምሮ ቁጥር በላይ የሆነ ዘመን ካትሪሊዮን ጊዜ ካትሪሊዮን ዘመን እጅግ እጅግ በላይ በፍጡር ኀሊና የማይደረስበት $(1000000000000000000000000000000000000000000000000000000000000)^{100000000000000000000000000000000000000000000000000000000000000000000}$ ከዚህም ዘመን በላይ እጅግ በላይ ዘመን በጭንቀት፣ በስቃይ፣ በመሰቀቅ ፍዳችንን ካየንና ስለ ዐመጻና ክህደት ተግባራችን እንደ ዐመጻና ክህደት ተግባራችና ንግግራችን ደረጃ ዋጋ ከከፈልን በኋላ፤ በመንግስተ ሰማያት ዉስጥ የሚኖሩት ቅዱሳን መላእክትና ቅዱሳን ሰዎች (ነፍስ) ለዚሁ ዘመን ያህል በረቂቅ አካል (በምሳሌያዊ ባሕርይ) በቅድስና፣ በንጽህና፣ በደስታ፣ በእርካታ አምላካቸዉን በእዉነትና በመንፈስ ካመለኩ በኋላ፤ ጸጋቸዉ እጅግ ሲበዛ እንደ አማናዊ ባሕርያቸዉ ( ካለ ምሳሌያዊ ባሕርይ) በመንፈስ ደረጃ ብቻ መጀመሪያና መጨረሻ በሌለዉ አማናዊ ሕዋ ዉስጥ ከመጀመሪያዉና ከመጨረሻዉ፣ ያልኖረበት ጊዜ የሌላ የማይኖርበት ጊዜ የማይኖር፣ የሁሉ ፈጣሪና አስገኝ ከሆነዉ ከአምላካቸዉ ጋር ሕያዉ ሆነዉ በመጨረሻ ቅድስናና ደስታ ሕይወት ሲኖሩ፤

እኛና እናንተ ኃጢአትን ፈጽማችሁ ከነዐመጻና ክህደት ተግባራችሁ ንስሐ ሳትገቡ በሥጋ ሞት የምትጠሩ ሁሉ እዛዉ እምንቀጣበት ገሃነመ እሳት ዉስጥ፤ ሕያዉ ፍጥረት ስለሆን (ከሕያዉ አምላክ ባሕርይ የተገኘን ስለሆነ) እንደ ምሳሌያዊ ባሕርይና ምሳሌያዊ ፍጥረት ከመኖር ወደ አለመኖር ማለፍ ስለማንችል፤ በገሃነመ እሳት ዉስጥ ፍዳችንን ከጨረስን በኋላ፤ ልክ እናንተ ሰዎች በዚህች ምድር ስታንቀላፉ ነፍሳችሁ ሕያዉ ብትሆንም አንዳች እንደማታስተዉሉና ስሜት እንደማይሰማችሁ ሁሉ ያኔ እኛም ሆን እናንተ አንዳች ማስተዋል ሳይኖረን የራሳችንን ህልዉና አተን በበድን ሕይወት በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ በአንዲት ነጥብ ቦታ ላይ ተወስነን እንኖራለን::

እኛ ሰይጣናት ታዲያ የገረመንና የታዘብነዉ በራሱ ስልጣን ሁሉን ማድረግ የሚቻለዉ የሁሉ ፈጣሪና አምላክ አፍቅሯችሁና አክብሯችሁ ባሕርይዉን ዝቅ አድርጎ በዚህ በጎስቋላ ሥጋችሁ በምድር ተገልጸ መንግስቱን እንድትወርሱና ሕያዉ ሆናችሁ እንድትኖሩ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ፤ ከምን መከልከል እንዳለባችሁ ከማስተማርና ፈዉስ፣ ተአምራት ከማድረግ አልፎ የተለያየ ጸዋትዎ መከራዎችን ከእናንተ ተቀብሎ ታስሮ፣ ተደብድቦ፣ ተሰድቦ፣ ተተፍቶበት፣ ተገርፎ፣ እጅግ አሰቃቂ ድርጊት ተፈጽሞበት፤ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሕይወት የሚሆናችሁን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙን ሰዉቶ መስጠቱና፤ እናንተ ደግሞ ሥጋዉና ደሙን መቀበል አይደለም ከነአካቴዉ ክዳቻሁት « ፍጡር ነዉ፣ ነብይ ነዉ፣ አማላጅ ነዉ፣ እንደማንኛዉ ሰዉ ነዉ፣ ሐሳች ነዉ.. ወዘተ» በማለት ክዳችሁታል:: ኣላመናችሁበትም:: እለት እለት ትሰድቡታላችሁ:: ታዋርዱታላችሁ:: ትዕዛዙንና ሕጉን ባለማክበር ታምጹበታላቸሁ:: ታዲያ ከኛ በባሰ ሁኔታ እንዴት የከፋዉ ቅጣት አይጠብቃችሁ!

ታዲያ እንዲህ ስላችሁ «ንስሐ ያልገባችሁ ንስሐ ገብታችሁ መለኮት የተዋሃደዉን ሥጋዉና ደሙን ብሉ፤ ጠጡ፤ እንዲሁም ያላመናችሁ ደግሞ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ተጠምቃችሁ ከእግዚአብሔር ልጅነት አግኙ፤ በሥጋና ደሙ ታተሙ፤ ከኃጢአት ተግባር ተለዩ ፤ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝና ሕግ ጠብቁ፤ አምልኮታችሁንም በዘልማድ ሳይሆን በእዉነትና በመንፈስ ፈጽሙ» ለማለት ፈልጌ ሳይሆን፤ ትዝብቴን ልገልጽላችሁ ነዉ እንጂ በኛ በሰይጣናት በኩል ለአንድ ሰዉ እንኳ አዝነንና ራርተን ወደ ገነትና መንግስተ ሰማያት እንዲገባ የምንፈቅድለት ሰዉ የለም:: ሁላችሁም እግዚአብሔር የሆነዉን እዉነተኛ አምላክ ፈጣሪ ኢየሱስ ክርስቶስን ክዳችሁ፤ በኃጢአት ሕይወት፣ በዐመጻና በክህደት እንድትኖሩና አብረን በገሃነመ እሳት ዉስጥ እንዲፈረድብን ነዉ ሌት ተቀን ጥረታችን:: የእኛ ቅጣት የሚነጻጸረዉ ከእናንተ ግፍ፣ ጭከና፣ ዐመጻ፣ ክህደትና ርኩሰት ሕይወት አንጻር ስለሆነ፤ እኛ ፍርዱ እንዲቀልልን እናንተን በመፈታተን የከፋ በደልና ዐመጻ እንድትፈጽሙ ነዉ ትግላችንና ፍላጎታችን::

እኛ በአንድ ጊዜ ጥፋታችን ለዚህ ጉስቁልና ሕይወት ከተዳረግንና በኋላ (በፍርድ ቀን) የባሰዉ ቅጣት የሚጠብቀን ከሆነ፤ እንዲሁም አዳምና ሔዋን የሚባሉት ሁለቱ ነፍሳት

በአንዲቱ ትዕዛዝ መተላለፋቸዉ ምክንያት ለዚህች ምድር ጉስቁልና ሕይወትና ለሲዖል ሕይወት ከተዳረጉ፤ እናንተ የአዳም ዘርማ ታላቅ ዋጋ በመስቀል ላይ ተከፍሎላችሁ ከንቱ በማድረጋችሁና ስንትና ስንት ትዕዛዝ እየጣሳችሁ እንዴት የከፋ ቅጣት አይጠብቃችሁ!? ታድያ እንዲህ ስላችሁ የእግዚአብሔርን ፍርድ እንድትፈሩና እዉነትን እንድትቀበሉ፣ ከእዉነት ጋር እንድትሰለፉ ለማሳሰብ ሳይሆን፤ የእግዚአብሔር ፍርድ ጥብቅ መሆኑን እንድታዉቁና ተስፋ ቆርጣችሁ እንደኔና ሠራዊቶቼ ሰይጣናት በዐመጻና በክህደት ተግባራችሁና ንግግራችሁ እንድትጸኑ፤ በመንግስቴም እንደምራራላችሁ ለመግለጽ ያህል ነዉ።

ሌላዉ ቢሰማችሁም ባይሰማችሁም አንድ እዉነት እነግራችኋለሁ። ይኸዉም እኔ ዲያብሎስ የሰይጣናት አለቃና ሠራዊቴ ሰይጣናት በእምነት ደረጃ ከእናንተ የሰዉ ሰሮች ከዘጠና እጅ (ፐርሰንት) በላይ ከሆናችሁት በመቶ እጥፍ እንበልጣችኋለን። በዚህም ፍርዱ ለእኛ ይቀላል። ምክንያቱም እኛ በእግዚአብሔር ላይ ብናምጽም ህልዉናዉን (መኖሩን) አልካዳንም። ከዚያም በላይ ሰዉ ሆኖ ከእመቤታችሁ፣ ከንግሥታችሁ ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ሆኖ ፍጹም ሰዉ ፍጹም አምላክ ሆኖ በዚህ ምድር ለሰላሳ ሶስት ዘመን ኖሮ የተለያየ መከራ ተቀብሎ፣ ተሰቅሎ፣ ሞቶ መነሳቱን እናዉቃለን እናምናለን።

ለእኛ ግን ምናችንም ስላልሆነ ብናዉቅም፤ ብናምንም አንዳች የንስሐ ሆነ መልካም ተግባር ምልክት አላሳየንም፣ አናሳይምም። እናንተ ግን እጅግ ብዙዎቻችሁ የእግዚአብሔርን ህልዉና የማትቀበሉ፣ በቁስ አካል የምታምኑ ፣«በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ ( በኢቮልሽን) አማካይነት ከጦጣ መሰል እንስሳ ወደ ሰዉ ተለወጥን» የምትሉ አሳፋሪና ከእብደት ያልተለየ ኅሊና የያዛችሁ ናችሁ። እንዲሁም «እምነት አለን» የምትሉት ደግሞ በተለያዩ አማልክት የምታምኑና የማታዉቁትን አምላክ የምታመልኩ፤ የኢየሱስ ክርስቶስን እግዚአብሔርነት ፈጣሪነት የካዳችሁና ያልተቀበላችሁ ናችዉ። ከዚህ በተጨማሪም በእግዚአብሔርነቱ ያመናችሁትም በስሙ ትነግዱበታላችሁ እንጂ እንደ ቃሉ የማትኖሩ፣ ትዕዛዙንና ሕጉን የማትጠብቁ አስመሳዮች፣ ምግባር የሌላችሁ ናችሁ። በዚህ ብቻ የምንቀጣበት ቦታ ገሃነመ እሳት ቢሆንም የቅጣቱ ደረጃ ለእኛ እንደሚቀልልን እንተማመናለን። ይኸዉም እኛ

በዐመጻችንና በክህደታችን ብንጸናም  እንደእናንተ የመዳን እድል ስለሌለን ነዉ:: እንዲሁም ምግባር ባይኖረንም የእግዚአብሔርን ህልዉናና ፈጣሪነት አልካድንም:: «ኢየሱስ ክርስቶስም እግዚአብሔር አምላክ ፈጣሪ አይደለም» ብለን አልካድንም:: ነገር ግን እንዳትድኑ ምቀኞች ነንና በኀሊናችሁ «እግዚአብሔር አይደለም፤ ፍጡር ነዉ፤ አማላጅ ነዉ፤ ነብይ ነዉ፤ ሐሳች ነዉ፤» ለማለት ግን አልተከለከልንም:: የምንላችሁን  መቀበል አለመቀበል ደግሞ ሙሉ ነጻነት ያላት የኀሊናችሁ(ነፍሳችሁ) ድርሻ ነዉ::

ታዲያ ይህን እዉነት መመስከሬ እዉነቱን እንድታዉቁና ከእዉነት ጋር እንድትሰለፉ ለመምከር ሳይሆን፤ እናንተ ብቻ ሳትሆኑ እዉነት መስካሪ፤ ልመስክር ካልኩ እኔም እዉነትን መናገር እንደምችል እንድታዉቁና እንደእናንተ የምታስብ ሕያዉ የሆነች ነፍስ እንዳለኝ እንድታዉቁና ራሳችሁን የተለያ አድርጋችሁ እንዳትቆጥሩ እንዲሁም ማንነታችሁን እንድታዉቁ ለማሳሰብ ያህል ብቻ ነዉ::

እናንተ የአዳም ዘሮች በኃጢአት መልከስከሳቻሁና በዐመጻ ሕይወት መጽናታችሁ ከኔ ታላቅ ዋጋ የሚያሰጣቸችሁ ቢሆን ኖሮና እናንተም አሁን እንደሚታየዉ እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ ተግባር፣ ንግግር፣ ስድብ፣ ምሴን ብታቀርቡልኝ ብዙ አያስደንቀኝም:: እኔን የሚያስደንቀኝ ነገር እኔ የጨለማዉ ገዥ በሥጋችሁም እንድትጎሳቆሉ በነፍሳችሁም የዘላለም ሞት እንድታገኙ ቀን ከሌሊት የምፈታተናችሁ ዋንኛ ጠላታችሁን ለማስደሰት እጅጉን መትጋታችሁ ነዉ:: ይህ ነዉ በእኔ ዘንድ ሳይቀር ትዝብት ዉስጥ የጣላችሁ:: በሥጋችሁ ቢመቻችላችሁ ብዙ እንዳማያስጨንቀኝ ሳልገልጽላችሁ ማለፍ አልፈልግም:: ምክንያቱም በዚህች ምድር የተገለጻችሁበት የዚህ ቅርፊት ሥጋ ምድራዊ ክብሩንና መጨራሻዉን እኔም እናተም ጠንቅቀን እናዉቀዋለን::

ዋናዉ ፍላጎቴና ትግሌ ነፍሳችሁን አሳምጾ ለገሃነመ እሳት ፍርድ ማቅረብ ነዉ:: ለዚህ አይደል እናንተ ኢትዮጵያዉያን እንደመንግስተ ሰማያትና እንደ ገነት የምትቆጥሯቸዉና ሌት ተቀን ወደእነሱ ለመሄድ በምኞት የምትቃጠሉባቸዉ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሬ ዉስጥ ያስገባዋቸዉን ልዩ አገሮቼን አሜሪካን፣ አዉሮፓን ፣ኤሽያን አብለጭልጬ የማጓጓችሁ:: « እኛ በሚታይና በሚዳሰስ ነገር እንጂ በምናባዊ አሳብ አናምንም ማቴሪያሊስት ነን::» በማለት

ለነፍሳችሁ አንዳች ቦታ አለምስጠታችሁ የእዉቀታችሁን ምጥቀት የሚያሳይ በመሆኑ መቼም እኔም የማልታይ የማልዳሰስ በመሆኔ ከኔ የሆነዉን ለመቀበልና ለመስማት ወደ ኋለ የማትሉ መሆኑን የኅሊናችሁን አሳብና ምጥቀት ስለማዉቅ ስለታላቅነታችሁ ምስክርነት ሳልሰጥ ባልፍ ኅሊናዬ ይወቅሰኛል።

ሌላዉ ቢቀር « እኛ የሰዉ ዘሮች ከጦጣ (ከእንስሳነት) በቀስ በቀስ ለዉጥና እድገት(በሲቭሊሽን) አማካይነት ነዉ የተለያዩ እድገቶችን አልፈን ለአሁኑ ስብእና የበቃነዉ» በማለት ማንነታችሁን መግለጻችሁና በትምህርት ተቋማችሁ ይህንኑ ከህጻን እስከ አዋቂዉ ድረስ እንዲማርና በዚህ አስተሳሰብ ተስፋዉን ምድራዊ ብቻ አድርጎ እንዲኖር፤ ተረት ተረት የሆነዉን «መንግስተሰማያት፣ ገነት፣ ሲዖል፣ ፈጣሪ፣ እግዚአብሔር፣ ሰይጣናት..... ወዘተ» የሚባለዉን አስተምሮ መሰረዛችሁና ማስቀረታችሁ ዋናዉ የታላቅነታሁና ምሁርነታችሁ መገለጫ በመሆኑ በራሴዉ በጨለማዉ ስም ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ።

እናንተ ኢትዮጵያዉን በችግርና በመከራ ዉስጥ እያላችሁ እንኳ «እግዚአብሔርን» ብላችሁ ሙጭጭ ብላችኋል። ታዲያ እንደ አሜሪካን፣ጃፓን፣ ቻይና፣ ህንድ፣አዉሮፓ፣ ኤሽያ፣ መካከለኛዉ ምስራቅ ..ወዘተ አገራት በሥጋችሁ ብትበለጽጉማ ለእኔ አንዳች ቀዳዳ እንዳማትከፍቱልኝና ርኅራኄ እንደማታሳዩኝ አዉቃለሁና፤ ለዚህም ነዉ በችግር እየገባዉና በምርጥ እንደራሴዎቼ አማካይነት ከሕይወት መንገድ እያወጣሁ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ያሰለፍኳችሁ። በቅርብ ጊዜ ዉስጥ ደግሞ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሬ ዉስጥ እንደማዉላችሁ ተገንዝባችሁ ከወዲሁ እጃችሁን ብትሰጡኝና የተሟላ አምልኮቴን ብታቀርቡልኝ የተሻለ መሆኑን በጨለማዉ ስሜ እመክራችኋለሁ ።

የኔ ተስፋና ምኞት የእናንተን ዉድቀትና ጥፋት ማየት ነዉ። ምክንያቱም እስከአሁን ለእኔ ያስቸገራችሁና እጅ አንሰጥም ብላችሁ የምትጋደሉት እናንተና አገራችሁ ኢትዮጵያ ናት። ለኔ አስቸግረዉኝ ለእናንተ ጥብቅና የሚቆሙ ከእናንተዉ ወተዉ በቅድስና ሕይወት የሚመላለሱት ብቻ ሳይሆን ሰማያዉያን ቅዱሳን መላእክት፣ ጻድቃን ፣ ሰማዕታት፣ ነብያትና ሐዋርያት ጭምር በመሆኑ ነዉ አቅመቢስነቴና ልምሾነቴ እየባሰ ኃይሌ እየተዳከመ ያለዉ። ከሁሉ በላይ ያማረረችኝና ፍዳዬን የምታሳየኝ፤ ስሟ እንኳ እንዲነሳ የማልፈልገዉ ያች

የምትመኩባት የአደራ እናታችሁ «ቅድስት ድንግል ማርያም» የምትባለዉ ናት:: ከግዛቴ ወዴት እንድሄድላት ነዉ የምትፈልገዉ? የአዳም ዘሮች ራሳቸዉ መተዉ «ንጉሣችን ሁን፤ ፈቃድህን እንፈጽምልሃለን» አሉኝ እንጂ፤ አንድ ሰዉ እንኳን አስገድጄ «ይህን አድርግ፤ ይህን አታድርግ» አላልኩም:: ሁሉም በሥጋዊ ስሜቱ እነደእንስሳ እየሆነ ነዉ እንጂ ይኸዉ በ7503 ዘመን ቆይታዬ እስኪ «ሰይጣን መሳሪያ ደግኖብኝና አስገድዶኝ ነዉ ኃጢአት የሰራዉት» የሚል አንደሰዉ ከተገኘ ይመስክርብኝ?

እንዲያዉም እኔ የማላዉቀዉን የርኩሰት ድርጊት እየፈጸሙና እየተሳደቡ ተቸግሬያለሁ:: ምክንያቱም በሚሰሩትና በሚናገሩት ሁሉ «ሰይጣን ነዉ እንዲህ ያስደረገኝ » እያሉ፤ በእኔ ስለሚያላክኩና ፍዳዬን ለማባስ እለት እለት ስለሚወነጅሉኝ ነዉ:: ዞሮ ዞሮ እዉነታዉ በመጨረሻዉ ፍርድ ቀን ይታወቃል:: አሁን ግን እናንተ ለሰዉ ልጆች በኀዘንና በምልጃ ጥብቃን የምትቆሙ ሁሉ፤ እነዚህ የአዳም ዘርን ከኔ አምልኮትና ስርዐት ለዩልኝ:: እኔ በራሴ ግዛት በነጻነት መኖርና ራሴን በራሴ ማስተዳደር ነዉ የምፈልገዉ:: የአዳም ዘርን ሁሉ ለማስተዳደር ይኸዉ ለዘመናት ስወጣ ስወርድ ኖሬያለሁ:: እናንተ የአዳም ዘሮች፤ እባካችሁ አሁን እንኳ ትንሽ ልረፍበት፤ ራሳችሁን በራሳችሁ አስተዳድሩ፤ ከፈለጋችሁ ንጉሣችሁን እግዚአብሔርን፤ ንግሥስታችሁን እናቱን ድንግል ማርያምን፤ ባለስልጣኖቻችሁን ቅዱሳን መላእክትን ጻድቃንን አድርጉ:: ካለፍላጎቴና ካለስራዬ ለኔ የሰጣችሁኝን ሹመትና ስልጣን ከኔ አንሱልኝ::

«አይ ምርጫችን አንተን ነዉ፤ ካላንተ አይሆንልንም» የምትሉ ከሆነ ደግሞ፤ እኔ በምርጫ አምናለሁና፤ ድካም ቢሰማኝም ሌላ ብዙ የምሰራዉ ስራ ቢኖርም፤ ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ እንደምትሉ እኔም ለእናንተ ያልሆነ ጉልበትና ጊዜ አይኑር እያልኩ፤ በተጠናከረ መልኩ መከራና ችግር፣ ስቃይ፣ ረሀብ፣ በሽታ፣ ስደት፣ ጦርነት ረብሻ፣ ጭንቀት፣ ብጥብጥ፣ ፍንዳታ፣ ጎርፍ፣ አዉሎ ንፈስ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ባጠቃላይ ልክ የሚያስገባችሁና ስርዐት የሚያሲዛችሁን እንዲሁም ምርጫችሁን እንድታስተካክሉ የሚያደርገዉን መልካሙን ስጦታና አገልግሎቴን ለማቅረብና ለማስቀረብ በታላቅ ትዕቢት በፊታችሁ እቆማለሁ::

ታድያ እናንተ ቅዱሳንን፣ ድንግል ማርያምን ለማቅለልና ለመሳደብ  እዉነተኛዉን እግዚአብሔር ለማስካድ በተለያየ የእምነት ድርጅቴ ስልጠና የወሰዳችሁ ሁሉ፤ የሰለጠናችሁበትን ዓለማ በሚገባ ተረድታችሁ ለታላቁ የዐመጻና ክህደት ተግባር እንድትሰለፉ ከወዲሁ በጥብቅ አሳስባችኋለሁ፡፡ እኔጋ መገለባበጥና መመሳሰል የሚባል ነገር ስለማይሰራ ላዘጋጀዋችሁ ክብር እንድትበቁ ኀሊናችሁን ከመካድና ከመሸጥ ጀምሮ ደማችሁን እስከመገበር ድረስ ወደ ኋላ እንዳትሉ ከአደራ ጭምር ነዉ የማሳስባችሁ፡፡ ድል ለሰፊዉ የዲያብሎስ ባሪያና እንደራሴ መንግስታት፣ ባለስልጣናት፣ ካድሬ ሁሉ፡፡ »  **ይላል ዐመጸኛዉና ትዕቢተኛዉ  ጨካኙ አረመኔዉ የጨለማ ገዥ ዲያብሎስ ከባሪያዎቹ ሰይጣናት ጭምር፡፡**

## ምእራፍ አራት

« እናንተ ወገኖቻችሁ የአዳምና ሔዋን ዘሮች ሲራቡ፣ ሲጠሙ፣ ሲቸገሩ፣ ሲያዝኑ፣ በሐሰት ሲወነጀሉ፣ ባጠቃላይ ሲጎሳቆሉና በችግርና በመከራ ዉስጥ ሲኖሩ አንዳች የርኅራኄና ኀዘኔታ ስሜት የማይሰማችሁ ሰዎች፤ ጭከናችሁ ከኔ ላቅ እያለ ብታስቀኑኝም በድርጊታችሁ አድናቆት እንጂ አንዳች ቅሬታ የለኝም:: ዋናዉ እናንተ ከበላችሁ፣ ከጠጣችሁ፣ ከዘፈናችሁ፣ ከጨፈራችሁ፣ ከተዝናናችሁ፣ ነጻ ከሆናችሁ፤ ሌላዉ ተራብ አልተራብ፣ ተጠማ አልተጠማ፣ ተቸገር አልተቸገረ፣ ታረዘ አልታረዘ፣ ታመመ አልታመመ፣ ተወነጀለ አልተወነጀለ ፣ ባጠቃላይ ተጎሳቆለ አልተጎሳቀለ ምንም ሊያሳስባችሁና ሊያስጨንቃችሁ አይገባም:: በኔ የሚያስጠይቃችሁ «ተራብ» ብላችሁ ብታበሉ፤ «ተጠማ» ብላችሁ ብታጠጡ፤ «ታረዘ» ብላችሁ ብታለብሱ፤ «ተቸገረ» ብላችሁ ብትረዱ፤ «በሐሰት ተወነጀለ» ብላችሁ ነጻ ብታሶጡ፤ «ተገፋ» ብላችሁ ብትደግፉ፤ «ክፋት፣ ተንኮል፣ ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ነገሠ» ብላች ብታጉረመርሙና ብትቃወሙ ነዉ እንጂ፤ የዚህ ተቃራኒ ተግባር ከፈጸማችሁ እኔ አንዳች አልፈርድባችሁም፤ የሚፈርድባችሁ ካለ ይፍረድባችሁ እንጂ::

እናንተ በአዳም ዘር በአባቶቻችሁ፣ በእናቶቻችሁ፣ በወንድሞቻችሁ፣ በእህቶቻችሁ፣ ባጠቃላይ በወገናችሁ ላይ በቅናትና በምቀኝነት እንዲሁም በክፋት ተነሳስታችሁ መተት የምታስመትቱና የምታስጠነቁሉ፤ ልዩ ሠራዊቴን ሰይጣናትን ካለ እቅዳቸዉና ፕሮግራማቸዉ ወደ ሰዎች በመብል፣ በመጠጥ፣ በልብስ፣ በቤት ዉስጥና በዉጭ በምታስቀብሩት አማካይነት ወገኖቻችሁን በማሰቃየትና በማጎሳቆል ላይ ያላችሁ ወዳጆቼና ባሮቼ፤ ስለክፋትና ተንኮል ተግባራችሁ በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችኋለሁ:: ነገር ግን እንደምኞታችሁና ፍላጎታችሁ የወገናችሁን ሀብት ንብረት፣ እዉቀት፣ ወንበር፣ ብልጽግና፣ ደስታ፣ ሰላም መዉሰድ ባለመቻላችሁ ቅር ተሰኝቻለሁ::

በዚህ ምድር ያሰባችሁት ሳይሳካላችሁ በባሰ ጉስቁልና ብትኖሩም ስለክፋትና ምቀኝነት ተግባራችሁ በዚህ ምድር ያልተሳካላችሁን ሁሉ በፍርድ ቀን በመንግስቴ የማሳካላችሁና የማሟላላችሁ መሆኔን በዚሁ ቃል እገባላችኋለሁ:: በዚህች ምድር ዉስጥ መተተኞች፣

ጠንቋዮች፣ አስማተኞች፣ ሟርተኞች ሌት ተቀን እንዴት እንደማደርጋቸዉ አስተዉላችሁ ቢሆን ኖሮ  ወደ እነሱ ድርሽ አትሉም ነበር፡፡ በቀጥታ እኔ የግብር አባታቸዉን እንድፈጽምላችሁ በቀጥታ ካላችሁበት ሆናች ትጠይቁኝ ነበር፡፡ ዞሮ ዞሮ እነሱ የደረሱበት ብቃት ላይ ለመድረስ እንደልቤ ልጋልባቸሁና ልጫወትባችሁ ያስፈልጋልና ማንኛዉንም መስዋዕት ለማቅረብ ዝግጅት እንድታደርጉ በዚሁ አሳስባችኋለሁ፡፡ «እምቢ» ብትሉ ደግሞ እንደልማዴ አሳብዳችኋለሁ፡፡ የቁም ስቃያችሁን አሳያችኋለሁ፡፡ እናንተ ወገናችሁን ለመጉዳትና ለማሰቃየት ወደ ኋላ የማትሉ ቆራጥ ጀግኖች ስለሆናችሁ ለምርጥ ቧለሟልነት እፈልጋችኋለዉና መተተኞቼን፣ ጠንቋዮቼን ፣ አስማተኞቼን ፣ ባጠቃላይ ምርጥ አገልጋዮቼን ደጅ ከመጥናት ወደ ኋላ  እንዳትሉ ታላቅ ምክሬን አቀርብላችኋለሁ፡፡

እናንተ የአዳምና ሔዋን ዘሮችን እያጠፋችሁ ራሳችሁንም በማጥፋት የሰማዕትነት ማዕረግ ከኔ የምትጠብቁ ምርጥ የሰዎች አጥፊዎቼ፤ በመጀመሪያ ስለምርጥ አስተሳሰባችሁና እምነታችሁ ያለኝን አድናቆት ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡ ይኸዉም « ሰዉን እየገደሉ፣ እያሰቃዩ ፣ እያቆሰሉ፣ እያሸበሩ፣ ገነት መንግስተ ሰማያት እንገባለን፡፡ » ብላችሁ በማሰባችሁና ይህንንም እለት እለት በተግባር ስለምትፈጽሙ ነዉ፡፡ እኔም ገነት ለመግባት  ተስፋ  አለኝ በማለት በእናንተ ተግባር እጽናናለሁ፡፡ መቸስ እናንተ ምህረት አግኝታችሁ እኔ የእንነተን ያህል እንኳ ጭከና ያላሳየዉትን እንዴት ፈጣሪ ይፈርድብኛል?

ታድያ አንዳንድ ሰዎች በሰዎች ላይ ማስፈረድ የሚፈልጉ «እንኳን ነፍሰ ገዳይ ንጹህ ደም አፍሳሽ ቀርቶ ወንድሙን «ደንቆሮ»  ብሎ የሚሰድብ ገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል፡፡» ብሏል አምላካችን እያሉ የሚያወሩትን አስፈራሪዎችን አታዳምጡ፡፡ እነሱ የኔ መንገድ የጠፋባቸዉ፣ ቢፈልጉኝ ሊያገኙኝ ያልቻሉ፣ በዚህም ምክንያት  ለበቀል የሚፈልጉኝ ናቸዉ፡፡ መንገዴ ከመንገዳቸዉ የሰማይና የምድር ያህል ልዩነትና ርቀት ስላለዉ የኔን ሙሉ ፈቃድ ሳይፈጽሙ በምንም መልኩ በኔ መንገድ ዉስጥ ሊገቡ አይችሉም፡፡ እናንተ ግን ጨለማዉ አክሊሌን ለማግኘት ብዙ የአዳምና ሔዋን ዘሮችን በፈንጅ ሆነ በቦንብ እንዲሁም በማንኛዉ ማጥፊያ መሳሪያ ልታጠፉልኝ እንደምትችሉ አምናለሁ፡፡ እንደምታጠፉልኝ ቁጥር ብዛት ደግሞ ከፍ ያለ ሽልማት እንደምሰጣችሁ በዚሁ ቃል እገባላችኋለሁ፡፡

እናንተ ስልጣነ ክህነት ይዛችሁ በተለያየ ኃጢአት ተግባር ላይ የተሰማራችሁ ክቡራን አባቶቼና ወንድሞቼ ፤መቼስ በኔ ዘንድ ሞገስ አግኝታችሁ በዚህ ስም ስለጠራዋችሁ እንደምትደሰቱ ስለማዉቅ ነዉ በለመዳችሁት አጠራር የጠራዋችሁ:: በኔ ዘንድ በመልካም ባለሟልነታችሁ እዉቅና ስላገኛችሁ ሌላ «ምን እናድርግልህ?» ብላችሁ ጭንቀት እንዳይገባችሁ:: ከሚገባዉ በላይ በተግባራችሁና ንግግራችሁ ስላስደሰታችሁኝና አምላካችሁንም ስላሰቆጣችሁልኝ ለኔ በቂዬ ነዉ:: ምክንያቱም የስራችሁን ዋጋ ታገኙበታላችሁና::

በተለይ እንደደረጃችሁ አድናቆቴን ብገልጽላችሁ ድስታዉን አልችልም:: የመጀመሪያ ተደናቂዎቼ በተለያዩ የዐመጻና የርኩሰት መድረክ ላይ ተገኝታችሁ ጉባዔዬንና ባዕድ አምልኮቴን የምትባርኩ፤ ታቦቱንና ጣዖቱ፣ ቤተ መቅደሱና ቤተ ርኩሱን፣ እምነቱንና ክህደቱን አንድ የምታደርጉ፤ በቀሚሳችሁና በካባችሁ ተሸፍናችሁ ፓለቲካዊ ተግባሬን የምታከነዉኑና በትርፍ ሰዐታችሁም መተትና ተመሳሳይ ተግባር የምትፈጽሙ፤ ከከበዳችሁ ደግሞ ከእናንተ በላይ ለሆነዉ ምርጥ ባለሟሌ ሪፈር የምታደርጉ፤ በስዉር ዝሙት የምትፈጽሙ ናችሁ:: በሁለተኛ ደረጃ ለስልጣን፣ ለክብረ፣ ለጥቅም፣ ለግል ብልጽግና፣ ለዝና ኅሊናችሁን እየሸጣችሁ ከነፈሰዉ ጋራ የምትነፍሱ የዐመጻ፣ የክህደት፣የርኩሰት ተግባር ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች ናችሁ ::

እንዳንዶች የሕይወት ምስጢር ያልገባቸዉ « እነዚህ አገልጋዮች እግዚአብሔር ምን ያላደረገላቸዉና ያጎደለባቸዉ ነገር አለ? ምዕመኑ እንደ አምላክ እንደራሴ ተመልክቶ ለቅዱሳን ከሚያቀርበዉ አክብሮት ባልተናነሰ መልኩ ክብር እየሰጣቸዉ፣ «አምጣ» ያሉትን እያቀረበላቸዉ፣ «አድርግ» የተባለዉን እያደረገላቸዉ፣ ንግግራቸዉን እንደ አምላክ ንግግር ቆጥሮ ወደ ተግባር ለመለወጥ ሌት ተቀን የሚተጋ፣ ለአገልግሎት የሚጠቀሙበትን ከመኪና እስከ አይሮፕላን ድረስ እያዘጋጁላቸዉ፣ መልካም ያማረ ማረፊያ ቤትና መስሪያ ቤት እየሰሩላቸዉ፣ ለመሆኑ ምን ጉደለብን ብለዉ ነዉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ከመትጋት ይልቅ ለዲያብሎስ እንደራሴዎች ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የሚተጉትና የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፈጻሚና አስፈጻሚ የሚሆኑት?

እንዲሁም ከዚህ በፊት በእዉነትና በመንፈስ አምላካቸዉን አምልከዉ ምዕመኑንም በእዉነትና በመንፈስ አስመልከዉ ወደ አምላካቸዉ እቅፍ የሄዱትን የእግዚአብሔር አገልጋዮች መዋዕለ ዜና አያዉቁም እንዳይባል በቅዱሳት መጽሐፍት፣ በገድላት፣ በስንክሳር፣ በተለያዩ ድርሳናት ላይ የነብያት ፣ የሐዋርያት፣ የሰማዕታት፣ የጻድቃን፣ የመምህራን፣ የሊቃዉንት፣ የካህናት፣ የፖትሪያሪክ ፣ የጳጳሳት፣ የዲያቆናት ያሳለፉት ተጋድሎ በደንብ ቀርቧል:: ተጋድሏቸዉን ከማንበብ አልፈዉ ለምዕመናን እንደሚያስተምሩት ይታወቃል:: የቀድሞዎቹ እዉነተኛ አገልጋዮች እንዳሁኑ በተመቻቸና ነጻነት ባለዉ ሕይወት ዉስጥ አልነበረም አገልግሎት ሲሰጡ የነበረዉ፤ እንደልባቸዉ የሚበሉት፣ የሚጠጡት፣ መጠለያ፣ መጠጊያ፣ ለመንገድ መንቀሳቀሻ ሳይኖራቸዉ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በእዉነት አገልግለዋል:: ያጋጠማቸዉን ፈተናና መከራ፣ ስቃይ፣ ስደት፣ ግርፋት፣ ስቅላት፣ ግድያ የመሳሰሉትን ሳይፈሩና ሳያስመስሉ፣ ሳይሰቀቁ ስለ እዉነት መስክረዋል:: ስለ እዉነት ራሳቸዉን ክደዋል፤ በእዉነትም ኖረዋል:: እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆነዉ በመገኘት ለምእመኑ አርአያና ምሳሌ ሆነዋል:: በየዋሻዉና በየገዳማቱ ራሳቸዉን ዝቅ አድረገዉ በመኖር በሰይጣናት እየተፈተኑ ለአገራቸዉና ለሕዝባቸዉ ጸልየዋል፤ አንብተዋል:: እንኳን አይሮፕላንና መኪና ቀርቶ በቅሎ አተዉ በእግራቸዉ በረሀ ለበረሃ እየተጓዙ ወገናቸዉን በከተማም በገጠርም አስተምረዋል:: ነገሥታትን ፣ ጠንቋዮችን፣ አስማተኞችን ሳይፈሩና ሳያስመስሉ እዉነትን ለሕዝብና ለምእመን ገልጸዋል:: ባጠቃላይ ያጋጠማቸዉን ፈተናና መከራ በጽናትና በትዕግስት በማሳለፍ ደማቸዉን ሳይቀር ገብረዉ በሰማዕትነት በታላቅ ተጋድሎ መልካም ፍሬ በማፍራት ወደ አምላካቸዉ እቅፍ ሄደዋል::

ታዲያ የአሁኖቹ አገልጋዮች፤ ሁሉ ተሟልቶላቸዉ ሌላዉ ቢቀር የእግዚአብሔርን ትዕዛዝና ሕግ እየጠበቁ ለምእመን አርአያ ምሳሌ ለምን አይሆኑም? በሚያስተምሩት ቃል ሆነዉ ስለምን አይገኙም? በዐመጻና በርኩሰት ተግባር ላይ እየተሰማሩ በምን አንደበትና ሞራል ነዉ የእግዚአብሔር አገልጋይና የሃይማኖት አባት ነን የሚሉት? የላመኑትንና ያልታመኑለትን አምላክ እንዲሁም ፈለጋቸዉን ያልተከተሉትን ቅዱሳንን የሚያስተምሩት

ስለምን ይሆን? በእርግጥ በእግዚአብሔር ሆነ በቅዱሳን ስም በመነገድ ጥቅም ያገኙበታል፤ ይከብሩበታል፤ ይበለጽጉበታል፤ ይሸነግሉበታል፤ ያስመስሉበታል፤ ሲብስም ይመለኩበታል፡፡

እግዚአብሔር እጅግ ታጋሽ ቢሆንም ፍርዱም እጅግ ጥብቅ ነዉ፡፡ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፍሬያቸዉን በመቶ እጥፍ ያጭዳሉ፡፡ ከወንበራቸዉ ይቆርጣቸዋል፡፡ እዉነተኛ አገልጋዮቹን በእዉነተኛ ወንበር ላይ አስቀምጦ ምእመኑን ያስጠብቃል፤ በእዉነትና በመንፈስ እንዲያመልኩት ያስደርጋል፡፡ አሁንም ምዕመኑን እየጠበቀ ያለዉ ራሱ ባለቤቱ ነዉ እንጂ እንደ አስመሳይ አገልጋዮች ቢሆን ኖሮ ምዕመኑ ግልብጥ ብሎ ወደ ክህደትና መናፍቃን ጎራ ይገባ ነበር፡፡ አንዳንዶች ተሰናክለዉ ወደ መናፍቃን ጎራ የገቡትም በነዚህ አሰናካይና አስመሳይ አገልጋዮች ምክንያት ነዉ፡፡ ለእነዚህ ሁሉ ነፍሳት ተጠያቂዎች ናቸዉ» በማለት የሚለፍፉትን ዲስኩር አትስሙ፡፡ እነሱ የሚናገሩትን ስለማያዉቁ ነዉ እንደዚህ የእብድና የወፈፌ ንግግር የሚናገሩት፡፡

ይህ ሁሉ በእናንተ መከበር፣ ምቾት፣ ስልጣን ቀንተዉ ነዉ እንጂ፤ ይህ እድል ቢሰጣቸዉ እኔን በግልጽ ከማምለክ የማይመለሱ ሐሰተኞች አስመሳይ አገልጋዮች ራሳቸዉ ናቸዉ፡፡ እናንተ ቅዱሳን፣ ብጹዐን፣ ክቡራን፣ መላእክት፣ ጻድቃን ናችሁ፡፡ ይህንን እኔ የጨለማዉ ገዥ እመሰክርላችኋለሁ፡፡ እነሱ ከኔ ጋር አንድነትና ህብረት እንዳይፈጥሩ መንገዱን ስለዘጋዉባቸዉ ነዉ በቅናትና በምቀኝነት ተነሳስተዉ እደዚህ ስማችሁን የሚያጠፉትና ስሜታችሁን የሚነካ ንግግር የተናገሩት፡፡

እስቲ በደንብ አስተዉሉ በሚታየዉ ዓለም ዉስጥ መዝናናት፣ መጨፈር፣ በምቾትና በድሎት ሕይወት መኖር ካልቻሉ እንዴት ከሥጋ ሞት በኋላ ይመቸናል፣ እንደሰታለን፣ እንዝናናለን ብለዉ ያስባሉ? ይህ ሁሉ ማስተዋል የሌላቸዉ መሃይሞች ስለሆኑ ነዉ በዐይናቸዉ ያላዩትን የምቾትና የደስታ ሕይወት በተስፋ የሚጠባበቁት፡፡ እናንተ ግን የገባችሁ ብልጦች ናችሁና የምድሩ ምስጢር ስለተገለጸላችሁ በዐይናችሁ ያላያችሁትን ዓለም ንቃችሁ ለምትበሉበት፣ ለምትጠጡበት፣ ለምትዝናኑበት፣ ለምትጨፍሩበት፣ ለምትበለጽጉበት፣ ለምትከብሩበት፣ ታላቅ ቅዱስ ለምትባሉበት፣ አባታችን አምላካችን ለምትባሉበት፣ ለምትገኑበት፣ ለምትመለኩበት ኑሮና ሕይወት ታላቅ ተጋድሎ በመፈጸም ላይ በመሆናችሁ

እጅግ እደለኞች ናችሁ:: ያላያችሁትን ዓለም ደግሞ በኔ ዘንድ ሞገስ በማግኘታችሁ አሁን አንድነትና ህብረት እንደፈጠርን ሁሉ በጋራ የምንወርሰዉና ሁለተኛ መንደላቀቂያ ቦታችን እንደምናደርገዉ በድጋሜ በጨለማዉ ስሜ አረጋግጥላችኋለሁ:: አንዳች ስለ ኩነኔ ስጋት አይግባችሁ:: ብታጡ ብታጡ የኔን የክብር ወንበርና መንግስት አታጡም:: እኔ የግብር አባታችሁ እስካለሁ ድረስ በመኖሪያዬ ቦታ እንደማታጡ እርግጠኛ ሆኜ ቃል እገባላችኋለሁ::

እናንተ በአገልግሎታችሁና በስብከቶቻችሁ «ኢየሱስ አድኖኛል፤ ወደ አብ የሚወስደዉ መንገድ ኢየሱስ ብቻ ነዉ፤ ኢየሱስ ጾሞልኛልና መጾም አያስፈልገንም .. ወዘተ» በማለት ሰዎች የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጠበቁ አልጠበቁ፣ ጾሙ አልጾሙ ፣መልካም ተግባር ሰሩ አልሰሩ ማሰብና መጨነቅ እንደሌለባቸዉ የምታስተምሩና « በኢየሱስ ብቻ ካመንክ ድነንል፤ ገነት መንግስተሰማያትን ትወርሳለህ» በማለት ምስክርነትን የምትሰጡ ምርጥ አገልጋዮቼ!

ለዚህ ታላቅ ምስክርነታሁ የእግዚአብሔርን ሕግ ጠበቃችሁ አልጠበቃችሁ፣ ጾማችሁ አልጾማችሁ፣ ምጽዋዕት አደረጋችሁ አላደረጋችሁ፣ መልካም ምግባር ኖራችሁ አልኖራችሁ፣ በኔ የሱስ ስላመናችሁና ሕዝቡን ከምግበራና ከእግዚአብሔር ሕግ እንዲርቅ በማድረጋችሁና ታላቅ ምስክርነት ስለሰጣችሁ የመንግስቴ ወራሽ እንደምትሆኑ ምንም ጥርጥር አይግባችሁ:: ምናልባት አንዳንድ መናፍቃንና ከሃድያን « ኢየሱስ ክርስቶስ የአዳምንና ሔዋን ዘሮች አድኗል እንጂ፤ የተወሰነ ነገድ ወይንም ዘር ወይንም ቋንቋ ተናጋሪ አላዳነም:: ለሁሉም ዘር በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ዋጋ ከፍሎላቸዋል:: ይህ ዋጋ በሰዉ ዘር ላይ የተፈረደዉን የሲዖል ፍርድ የሚሽርና ድኅነታቸዉን አምነዉ የእግዚአብሔርን ሕግና ትዕዛዝ ጠብቀዉ ክርስቶስ ለአርአያና ለምሳሌ የፈጸመዉን ከቀላሉ መጸለይና መጾም ጀምሮ ግዳጅ ከመጣባቸዉም የተለያዩ ፈተናዎችንና መከራዎችን እስከ መሰቀል ድረስ ተቀብለዉ ገነት መንግስተ ሰማያት እንዲገቡ ነዉ እንጂ፤ እንደ መፈክር «ኢየሱስ የግል አዳኜ ነዉ፤ ኢየሱስ አድንሆል » በማለት መልካም ምግባር ሳይዙና ሕጉና ትዕዛዙን ሳይጠብቁ ገነት መንግስተ ሰማያትን መዉረስ አይቻልም::

ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ፣ ከአደራ እናታችን፣ ከመዳኛችን ምክንያት ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ፣ ከሁለት አካል አንድ አካል ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኖ የተለያየ ጸዋዕትዎ መከራ

በመቀበሉና በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ቅዱስ ሥጋዉን በመቁረሱና ክቡር ደሙን በማፍሰሱ እንዲሁም ለሚበሉትና ለሚጠጡት  የዘለዓለም ሕይወት የሚሆናቸዉንና  ኃጢአታቸዉም የሚደመሰስበት  መሆኑን በማስተማሩ፣ እኛን ከሞት ወደ ሕይወት ለማሸጋገር ባሕርይዉን ብቻ ዝቅ አድርጎ ራሱን በማዋረዱ ምክንያት «አማላጅ ነዉ» እያሉ የካዱትና እለት እለት የሚሰድቡት የተለያዩ ፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች መንገዳቸዉ የተሳሳተና ክህደት የሞላዉ ነዉ:: እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ አማላጅ ወደ አብ የሚላላክ ሳይሆን በህልዉና፣ በአገዛዝ፣ በስልጣን፣ በመለኮት፣ ባጠቃላይ በባሕርይ፣ ከባሕርይ አባቱ ከአብ፣ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር  አንድ የሆነ፤  የማይበልጥ የማያንስ ነዉ እንጂ መናፍቃንና ከሃድያን እንደሚሉት አማለጅ፣ ፍጡር፣ ነብይ አይደለም::

እርሱ የጌቶች ጌታ፣ የአማልክት አምላክ ፣ የነገሥታት ንጉሥ፣ አልፋና ዖሜጋ፣ ያልኖረበት ጊዜ የሌለ የማይኖርበት ጊዜ የማይኖር፣ ለእያንዳንዱ እንደ እምነቱና ስራዉ የሚፈርድበት፤ የሚፈርድለት፤ ካለ እርሱ ፈቃድ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊኮን የማይቻል፤ አብን ሆነ መንፈስ ቅዱስን ለማወቅ በመጀመሪያ እርሱን እንደ እግዚአብሔርነቱ ማወቅና ማምለክ ግድ የሆነ፤ ስለ አብ ሆነ ስለመንፈስ ቅዱስ ብቸኛ ገላጭ እርሱ የሆነ፤ ማንም ሊያዘዉ ሆነ ሊያስገድደዉ የማይችል የኃያላን ኃያል የሆነ አምላክ ነዉ::» በማለት ምስክርነትን የሚሰጡትን አትስሙ:: እነሱ የኔን የሱስና የድንግል ማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ልዩነቱ ስላልገባቸዉና  የኔ ዋና ተቃዋሚዎቼ  ስለሆኑ ነዉ:: እኔ እስከመጨረሻዉ ድረስ ላጠፋቸዉና የኔን የሱስን ለማንገሥ የሞት ሽረት እያደረኩ ስለሆነ እናንተም አንዳች ተስፋ ሳትቆርጡ እስከመጨረሻዉ ድረስ ከጎኔ ተስልፋችሁ እንድትቆሙ በጥብቅ አሳስባችኋለሁ::

በተለይ በተለይ ያቺ የሕይወታችሁ ጥፋት ምክንያት የሆነችዉ የእነሱ ኢየሱስ እናት ማርያም የሚሏትን ከምዕመኖች ልበና ሙሉ በሙሉ መንግላችሁ ካላወጣችሁ በስተቀር ትግላችን ከባድ ይሆናል:: ስለዚህ የአማልጅነት ተግባር ለኔ የሱስ ሰታችሁ እሷን ከአማልጅነት ማሻር፤ እሷን ብቻ አይደለም ደመኛ ጠላቶቼን መላእክትን፣ ነብያትን፣ ሐዋርያትን፣ ሰማዕታትን፣ ጻድቃንን መታሰቢያቸዉን ማጥፋት አለባችሁ:: በመጨረሻም ካለ

ትጥቅ ባዷቸዉን ስለምታገኙ ወደኔ የሱስ ማምጣትና ማስመለክ ትችላላችሁ:: ከዚያም ለእናንተ ያወጅኩትን ሙሉ ነጻነት ለነሱም አዉጃለሁ::

ይኸዉም ለዘመናት የተጫነባቸዉን ጾም አስቀርላቸዋለሁ:: የተተበተቡበትን የአምልኮ ስርዐት እሸርላቸዋለሁ:: እንደፈለጉ በአዳራሽ ዉስጥ እንዲየመልኩኝ፣ የፈለጉትን የአለባበስ ስታይል እፈቅድላቸዋለሁ:: በመንፈሳዊ ስም ሽፋን ዘፈኑንና ዳንኪራዉ እንደፈለጉ እንዲዝናኑበት አደርጋለሁ:: ከፈለጉም በመድረክ ላይ የተለያዩ ትዕይንቶች እያፈጠርኩ፣ እያንዘፈዘፍኩ፣ እያስጓራሁ፣ እያስጮኩ፣ እየዘረርኩ፣ ዘመናዊ ዛር አሳያቸዋለሁ:: ብቃት ደረጃ ላይ ለደረሱት ደግሞ ልሳኔ ልሳናቸዉ እንዲሆን አደርጋለሁ:: ባጠቃላይ ለሥጋቸዉ በሚመች መልኩ ስርዐት ዘርግቼ አምልኮታቸዉን እንዲፈጽሙልኝና እንዲዝናኑ አደርጋለሁ:: ስለ ጾም ሆነ ስለ ስርዐት እንዲሁም ስለ መልካም ምግባር አንዳች አታስቡ፤ ብቻ ወደ እኔ ጨለማዉ ንጉሥ ዐይናችሁን ጨፍናችሁና አቀርቅራችሁ ጸሎታችሁን አቅርቡ፣ ነፍሳትን ማርኩልኝ፣ አብዙልኝ፣ እኔ ብቻ ስለሁንኩ የጨለማዉ መንገድ፤ ማንም እናንተን ያልተቀበለ በመንገዴ ገብቶ ሊመላለስና መንግስቴን ሊወርስ አይችልም:: እናንተን የተቀበላችሁን ግን ለታላቁ መንግስቴ አበቃቸዋለሁ:: ይህንንም በታለቁ ስሜ የጨለማዉ ገዥ በመማል የመስቀሉ ተቃዋሚና ተቀናቃኝ በሆነዉ በኮከቡ ዓርማዬ በማተም አረጋግጥላችኋለሁ:: » **ይላል አታላዩና ሸዋጁ የርኩስ መንፈስ ባለቤት የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከሠራዊቶቹ ሰይጣናት ጭምር::**

# ምእራፍ አምስት

« እናንተ ልበደንዳኖች የንስሐ ጥቅም ያላወቃችሁ፤ እስከመጨረሻዉ በኃጢአታችሁ የምትጸኑ ጽኑአን፤ እኔን አርአያና ምሳሌነት አድርጋች በዐመጻችሁ የጸናችሁ ወድ ጓደኞቼ የሆናችሁ ሰዎች፤ ንስሐ ብትገቡ ወዮላችሁ! ቀደም ብሎ የሰራችሁት ኃጢአታችሁ ስለማይደመሰስ ዞሮ ዞሮ መምጫችሁ ወደ እኔ መንግስት ስለሆነ በመንግስቴ በገሃነመ እሳት ዉስጥ አይቀጡ አቀጣጥ ነዉ የምቀጣችሁ፡፡ ስለዚህ አርፋችሁ በኃጢአት ተግባራችሁ እስከመጨረሻዉ ድረስ ጸንታችሁ በበደልና በዐመጻ ሕይወታችሁ እንድትኖሩ ታላቅ ምክሬን እመክራችኋለሁ፡፡

ምናልባት አንዳንድ ሐሰተኛ መምህራን «ዳዊት እግዚአብሔርን የሚፈራ ቅን፣ ቆራጥ፣ ጀግና ስለነበረ እግዚአብሔር ከፍ ከፍ አድርጎት ንጉሥ አደረገዉ፡፡ ለተወሰነ ጊዜ አምላኩን በተግባር፣ በንግግር፣ በአሳብ ሳይቀር በመፍራትና ደስ በሚያሰኝ ሕይወት ዉስጥ ከኖረ በኋላ ምቾትና ድሎት ሲበዛበት ኅሊናዉ ደነደነና ያ ከበግ እረኝነት አንስቶ ለንጉሥነት የቀባዉንና ያበቃዉን አምላክ መርሳት ጀመረ፡፡ እንኳን በአሳብና በንግግሩ ሊፈራዉ ቀርቶ በተግባር የባለሟሉን ሚስት ደፈረ፣ ታማኝ አገልጋዩንም አስገደለ፡፡ ታዲያ ፍርዱ ጥብቅ የሆነዉ አምላክ ነብዩን ናታንን ላከበት፣ አስገሰጸዉ፣ ለመማማሪያም ይሆን ዘንድ በተለያየ መንገድ ቀጣዉ፣ አዋረደዉ፣ ስለኃጢአቱ ዋጋን አስከፈለዉ፡፡ ይሁንና ገር የንስሐ ልቦና ያላዉ ንጉሥ ዳዊት በበደሉና በኃጢአቱ እጅጉን አዘነ፣ አለቀሰ ፣አልጋዉን በእንባ አራሰ፣ በእዉነት ተጸጸቶ አምላኩን ይቅርታ ጠየቀ፡፡ ርኅራኄዉም እጅግ የሆነ ይቅርባይ አምላክም፤ ይቅር አለዉ፡፡ በቀሪ ዘመኑ ባሳየዉ የንጽህናና የቅድስና ተግባሪ፣«እንደ ልቤ» አለዉ፡፡ የቅድስና የጻድቅነት ማዕረግ ሰጠዉ፡፡

በመሆኑም በኃጢአት የወደቃችሁ በእዉነተኛ ንስሐ ኃጢአታችሁ ከሰማያዊ መዝገብ ላይ ይደመሰስላችኋል። ንስሐ በገባችሁበትና በተጸጸታችሁበት ኃጢአት ዳግም አንዳች አትጠየቁም። ስለዚህ አንዳች ተስፋ ሳትቆርጡ ስላለፈዉ ዐመጻችሁና ክህደታችሁ፣ ርኩሰት ተግባራችሁ ንስሐ ግቡ። በቀሪ ሕይወታችሁም እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት ኑሮ ኑሩ እንጂ «እግዚአብሔር የኔን በደል ይቅር አይልም» የምትሉና ተስፋ የምትቆርጡ ከሆነ ዲያብሎስ ደስ ይለዋል፤ ይህን አቋም ይፈልገዋል። የእርሱ ባሪያ ሆናችሁ እርሱ በሚቀጣበት በገሃነመ እሳት ቦታ እናንተም ትቀጣላችሁ።» በማለት የሚያስተምሩትን ትምህርት አንዳች እንዳትቀበሉ። እኔ ከእናንተ በላይ ቂመኛና ተበቃይ ስለሆንኩ ንስሐ ከገባችሁና በበደላችሁ፣ በዐመጻችሁ ከተጸጸታችሁ ከኔ ጋር የመጨረሻ ጥል ነዉ የምታደርጉት። እኔ ይቅር አልላችሁም። እንደካዳችሁኝ እክዳችኋለሁ። ለመንግስቴም አትበቁም። ይህንንም በታላቁ ጨለማዉ ስሜ አረጋግጥላችኋለሁ።

እናንተ ጸሎታችሁን በዘልማድ የምታነበንቡ፣ በአሳባችሁ የተለያየ ጉዳዮችና ቦታዎች ላይ የምትነጉዱ አዛኝ ሰዎች፤ ስለርኅሩኅነታችሁ እያመሰገንኩ፣ ለወደፊት ደግሞ ጸሎቱን ሙሉ በሙሉ እንድትተዉት አሳስባችኋለሁ። ሙሉ በሙሉ ከተዋችሁት ለመበቀል የወሰንኩባቸዉ ሰዎች እድል አያጋጥማችሁም። ይኸዉም እነዚህ ሌት ተቀን እንደብረምጣድ በእሳት መሃል ጥደዉኝ ኀሊናቸዉን በመሰብሰብና በተመስጦ ጸሎት እሳቱን ከመሃል እያፋፋሙ ያነደዱኝን፣ ያቃጠሉኝን በተለመደዉ በባዶ ጉራ እንደበቴ አይቀጡ አቀጣጥ እቀጣቸዋለሁ። ታዲያ እናንተም መሃል ለማሃል ባይሆንም ዳር ዳሩን እያቀጣጠላችሁ በወላፈኑ በመጠኑም ቢሆን ስለምትለበልቡኝ ሙሉ በሙሉ ጸሎታችሁን ማቆም አለባችሁ። ያለበለዚያ እኔም በገሃነመ እሳት ዉስጥ አልራራላችሁም። እነሱ ግን የኔን እድል እንዳያገኙ መንገዱን ሁሉ እዘጋባቸዋለሁ። ለእናንተ ግን ሰፊ መንገድን አሳያችኋለሁ።

የትምህርት መመሪያዉ (ፖሊሲ) በኔ ቁጥጥር ዉስጥና በክህደት እምነት ዙሪያ ዉስጥ ስለሚከናወን የሥጋዊ ጥበብና እዉቀት በመገኘቱ ምንም እንኳን ሰዎች ከጉስቁልና ሕይወት መለየታቸዉ ባያስደስተኝም አንዳች ቅናት ግን የለብኝም:: ዋናዉ ዓላማዬ ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ድረስ በየተቋማቱ «ሰዉ የተገኘዉ ከተፈጥሮ በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ(በኢቮልሽን) አማካይነት ከጦጣ መሰል እንስሳ ነዉ:: » በሚለዉ የትምህርት አቅጣጫ ስለሚመራ ለኔ ለጨለማዉ ገዥ «የተፈጥሮ ባለቤት ፈጣሪ እግዚአብሔር የለም::» የሚለዉ የክህደት ትምህርት በቂዬ ነዉ::

የገረመኝና የታዘብኩት ግን ሌላዉ የዓለም ሕዝብ በዚህ የክህደት ትምህርትና አስተሳሰብ ቢሄዱ ብዙም አያስገርመኝም፤ አያስደንቀኝም:: ምክንያቱም ክህደቱ ከእነሱ ስለፈለቀ:: እኔን የገረመኝ ገና ከህጻንነት እድሜያቸዉ በአርባና በሰማኒያ ቀን በጥምቀት ከእግዚአብሔር ልጅነትን አግኝተዉ «ማርያም ማርያም» እየተባለ ተወልደዉ ከህጻን እስከ ምሁሩ ድረስ በዚህ በክህደት ትምህርቴ መመራታቸዉና የቅሬተ አጽም አጥኝዎችም ከዉጭ ከሃዲያን የጌቶቻቸዉን ትምህርት ተከትለዉ ለሰዉ ልጆች እድሜና ለተፈጥሮ ተረት ተረቴን ትምህርት በሚሊዮንና በቢሊዮን እድሜ እየሰጡ ነጭ ዉሸቱን ለአገራቸዉና ለዓለም ሕዝብ ማቅረባቸዉ ነዉ:: ምንም እንኳን የሰዉ ዘር የተገኘባት፤ ከገነት የተሰደዱት አዳምና ሔዋን በመባል የሚታወቁት ሁለቱ ነፍሳት በዚህች ምድር የተገለጹበት ሥጋ የተበጀዉ ከዚህችዉ ኢትዮጵያ ዔደን ገነት ከተባለችዉ ምድር(መሬት) ግዮን ( የአባይ) መነሻ አገር መሆኑን እኔ ፈጡሩ የጨለማዉ ገዥ ብቻ አይደለም መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ የሆኑ ሁሉ ያዉቃሉ::

ታዲያ የዚህ ታሪክ ባለቤቶች የሆኑት ኢትዮጵያዉያን አስር ሺህ እድሜ እንኳ የማይሞላትን ሚጢጢዋን ምድር (ዓለም) እንደሌሎቹ አገሮች ዐመጻና ክህደትን በመፈጸም ከእግዚአብሔር ለማስካድ በሚሊዮንና በቢሊዮን እድሜ ይሰጣሉ:: በየትምህርት ተቋማቱ ለትዉልዱ ያስተምራሉ:: በዚህም ተደፋፍረዉ «ተፈጥሮን እንቆጣጠራለን» በማለት ሌት ተቀን ይታበያሉ::

እዚህ ላይ የኔ ተግባር በዐመጻና በክህደቱ እንዲሰለፉ በኅሊናቸዉ ሹክ ማለት እንጂ ማንንም አስገድጄ ወይንም በግልጽ አዝዥ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ተግባር ዉስጥ

እንዲሰለፉ አላደረኩም:: እያንዳንዱ ሰዉ በነጻ ኅሊናዉ ተመርቶ ነዉ በተግባርም፣ በንግግርም፣ በአሳብም ኃጢአት የሚፈጽመዉ እንጂ፤ የእግዚአብሔርን ድምጽ ለይቶ መልካም መስራትና ቀና ማሰብ የራሱ ምርጫ ነዉ:: እንዲሁም በተፈጥሮ ባሕርይዉ መልካም መስራትና ቀና ማሰብ የራሱ ፈቃድ ነዉ:: በተቃራኒዉ ደግሞ ኅሊናዉ(ነፍሱ) የኔን የጨለማዉ ገዥ ድምጽ ሰምታ የተባለዉን ወደ ተግባርና ንግግር በመለወጥ ኃጢአት ለመስራት የራሷ ፍላጎትና ዉሳኔ ነዉ:: ማንም አስገድዷት ኃጢአት የሚያስፈጽም አካል ስለሌለ በኔ ላይ አንድ ሰዉ እንዳያላክክ:: ስለ ድርጊቱ ዋጋ የሚቀበለዉም ወይንም በተቃራኒዉ ዋጋ የሚከፍለዉም በነጻ ኅሊናዉ ተመርቶ የሚሰራዉ ራሱ የአዳም ዘር ብቻ ነዉ::

እኔ የጨለማዉ ገዥ ተስፋ በመቁረጥና የመዳን ተስፋ ስለሌለኝ ነዉ ሌት ተቀን የአዳም ዘርን ለመፈታተንና ለማጎሳቆል እንዲሁም መከራና ስቃይ ለማድረስ የምተጋዉና ርካታም የማገኘዉ ይህ እቅዴና ምኞቴ ሲሳካልኝ ብቻ ነዉ:: የእናንተ የአዳም ዘር ለኃጢአት ተግባር መነሳሳት ግን ግራ ገብቶኛል:: ምናልባት ለኔ አዝናችሁልኝ «ዲያብሎስ ከሰራዊቱ ሰይጣናት ጋር ብቻቸዉን ለምን ገሃነመ እሳት ዉስጥ ይኖራሉ? በዚያ ማን ያጽናናቸዋል?» በማለት አዝናችሁልን፣ ወዳችሁን ይሁን እናንተና ፈጣሪ ነዉ የሚያዉቀዉ::

ወይስ በኔ አሳሳቢነት ባለሟሎቼና አገልጋዮቼ ያስተማሯችሁ የማታለያና ሽወዳ ትምህርት ይኸዉም « የሰዉ ልጆች ሚች፣ ፈራሽ፣ በስባሽ ናቸዉ:: ከሞት በኋላ አንዳች የሚያዉቁትና የሚያስተዉሉት ነገር የለም:: ትንሳኤ የሚባለዉ ዉሸት ነዉ፤.. ወዘተ» በማለት ያስተማሯችሁንና የነገሯችሁን እዉነት አድርጋችሁ ተቀብላችሁ ይሆን? በዚህ ምክንያትም « በዚህች ምድር እያለን እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንዝፈን ፣ እንጨፍር፣ እንደለቅ፣ ባጠቃላይ እንደፈለግነዉ እንሁን፤ ምንድነዉ የእግዚአብሔር ትዕዛዝና ሕግ የሚባለዉ? ተረት ተረት አይደለም ወይ? ምንድነዉ ክርስትና? የገዥ መደቦች የፈጠሩት አይደለም ወይ? .. ወዘተ» በማለት የአህዛብ አኗኗርን ስለመረጣችሁ ይሆን?

የእናንተ ሆነ የኔ የጨለማዉ ገዥ ፈጣሪ የሆነዉ እግዚአብሔር እስከሚሰቀል ድረስ አታሎኝ (ግልጽ ሳይሆንልኝ) ፍጡር፣ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ብቻ መስሎኝ የነበረዉ፤

በክፋት ጻፎችንና ፈሪሳዉያንን እንዲሁም የአይሁድ አለቆችንና ካህናትን ያነሳሳሁበትና የእናንተ ወገኖች የሆኑት የአዳም ዘር በደልና ግፍ የፈጸሙበት፤ ራቁቱን በመስቀል ላይ በመስቀል ለእናንተ ፍቅሩን የገለጸዉንና ሥጋዉን ቆርሶ ደሙን አፍሶ ሕይወት እንዲሆናችሁ « ብሉ፣ ጠጡ» ያላችሁን፤ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ፣ ምን ማድረግ እንደሌለባችሁ ሰዉ ሆኖ በግልጽ ያስተማራችሁን፤ የተለያዩ ተአምራትንና ፈዉስ ያደረገላችሁን፤ ስደትን፣ ስድብን፣ ግርፋትን፣ ዉንጀላን፣ ዉርደትን፣ ባጠቃላይ የተለያዩ ስቃይንና መከራን ለአርአያነትና ለምሳሌነት የተቀበለዉን አምላካችሁን ኢየሱስ ክርስቶስን መርሳታችሁና መካዳችሁ በኔ በኩል ግምት ዉስጥ የገባችሁና የቀለላችሁ መሆኑን እየገለጽኩ ነገር ግን በአቋማችሁ ደስተኛ መሆኔን በዚሁ አጋጣሚ አሳዉቃችኋለሁ::

በሌላ በኩል ደግሞ ገና ከመወለዳችሁ ጀምሮ ነፍስ ከሥጋችሁ እስክትለይ ድረስ ሌት ተቀን የምፈታተናችሁን፣ የማጠቃችሁን፣ የማሰቃያችሁን፣ የማስጨንቃችሁን፣ መከራና ችግር የማፈራርቅባችሁን፣ ባጠቃላይ በዚህ ምድር ቆይታችሁ ፍዳችሁን የማሳያችሁን የጨለማዉ ገዥንና ሠራዊቴ ሰይጣናትን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም በመትጋታችሁና የኃጢአት ተግባር በመፈጸም የኔ ባሪያ መሆንን በመምረጣችሁ ማፈሪያዎች መሆናችሁን እመሰክርባችኋለሁ:: ነገር ግን በዚሁ አቋማችሁ እስከመጨረሻዉ እንድትጸኑ አስጠነቅቃችኋለሁ::

ከእግዚአብሔር የታዘዛችሁትና የተማራችሁት ግን ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግስት እንኳን እኔን በዐይናችሁ የማታዩኝን የጨለማ ገዥን ቀርቶ በዐይናችሁ የምታያቸዉን ምድራዊ ሰዎች ነገሥታቱን፣ ፕሬዘዳንቶቹን፣ ጠቅላይ ሚኒስትሮችን፣ ባለስልጣናቱን፣ የጦር አዛዦቹን፣ የተለያዩ ኃላፊዉችን .. ወዘተ ሳትፈሩና ኅሊናችሁን ሳትሸጡ ስለ እዉነት እንድትመሰክሩና በእዉነትም እንድትኖሩ ነበር::

እንኳን «ለዘሬ፣ ለጎጤ ፣ለዘመዴ፣ለቤተሰቤ ፣ለወላጆቼ፣ ለልጆቼ .. ወዘተ» በማለት ኅሊናችሁን መሸጥና በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት መመላለስ ቀርቶ የራሳችሁን ማንነት እንኳ ንቃችሁና ክዳችሁ እዉነተኛ አገልጋይና አማኝ መሆን ይጠበቅባችሁ ነበር:: እናንተ ግን እንኳን በእዉነትና በመንፈስ እግዚአብሔርን ማመንና ማገልገል እንዲሁም

በመልካም ተግባርና በቅን አሳብ ተመላልሳችሁ ተስፋችሁን ገነትና መንግስተ ሰማያትን አድርጋችሁ መኖር አይደልም፤ የሚጎዳችሁን የኃጢአት ተግባር ለመፈጸምና እኔን ጠላታችሁን ዲያብሎስን ደስ በሚለኝ ሕይወት ለመኖር የምትተጉ ናችሁ።

የሚያሳዝነዉ ግን እናንተ እንደምትወዱኝ እኔ አልወዳችሁም። ለዚህም ነዉ በምትሰሩት ኃጢአት ምላሼ ደስታን፣ እርካታን፣ ሰላምን ከመስጠት ይልቅ ኀሊናችሁ ደስታንና እርካታን እንዲሁም ሰላም እንዳያገኝ አድርጌ ተስፋቢስ ሕይወት እንድትኖሩ፤ የተቅበዘበዛችሁ እንድትሆኑና ባዶነት እንዲሰማችሁ የማደርገዉ። ከዚህ በተጨማሪም በተለያየ በሽታ እንድትያዙ በማድረግ የተለያየ ችግርና መከራ በማምጣት ተቃራኒ መልስ ነዉ የምሰጣችሁ። በመጨረሻም ንስሐ ሳትገቡ በክፉ አሟሟት እንዲትሞቱ በማድረግ ለሲያልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ አሳልፌን የምንሰጣችሁ።

ታዲያ እናንተ እንዲህ እንደምንጨክንባችሁ እያወቃችሁ፤ በፍቅር፣ በቸርነት ፣በርኅራኄ፣ በበረከት፣ በጸጋ የሚያስተዳድራችሁንና በኋላም በመንግስቱ ሕያዉ ሆናችሁ እንድትኖሩ ፈቃዱ የሆነዉን እግዚአብሔርን «እኛ አንተን አንፈልግም። ፈቃድህንም አንፈጽምም። በሕያዉ መንግስትህም መኖር አንመርጥም።» ማለታችሁ ክብር የማይወድላችሁ መሆኑን እያስመሰከራችሁ እንደሆነ እንኳን በፈጣሪያችሁና በቅዱሳኑ ዘንድ አይደለም፤ በኔ ርኩሱ ዲያብሎስ ዘንድ የታወቀ ነዉ። ይሁንና ስለደንዳናነታችሁ የጨለማዉ መንግስቴ ወራሽ ስለምትሆኑና መጨረሻችሁ እንደኔ ያማረ ስለሚሆን በዚህ እንደምትጽናኑ ተስፋ አደርጋለሁ።

የእግዚአብሔር ፍርድ ከዓለም እልፈት በኋላ ብቻ አይደለም። በዚህች ምድር ዉስጥ እናንተ የአዳም ዘሮች ሆናችሁ እኛ ሰይጣናት (ርኩሳን መናፍስት) እንደ ዐመጻ ደረጃችን እንቀጣለን። ፍዳችንን እናገኛለን። ቀድሞ ይህች ዓለም ሳትፈጠር በፊት በመጀመሪያዉ ፍጥረት ምሳሌያዊ ባሕርይ ቦታ በሰማያት ዉስጥ « ይህን አታድርጉ» ሳንባል እኔ ሳጥናኤል የተገለጥኩበት አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) ከሌሎቹ መናፍስት (መላእክት) የበለጠ ስለነበረ ከሁሉ በፊት የነበርኩ አይነት ስሜት ተሰምቶኝ « እኔ ነኝ የፈጠርኳችሁ፤ እኔን አምልኩ።» በምልበት ጊዜ እጅግ የብዙ ብዙ መናፍስት (መላእክት) ያልተቀበሉኝና በሰዉ ዘንድ ብዙ የሆኑ

ነገር ግን ካልተቀበሉኝ መናፍስት ቁጥር አንጻር አንድ መቶኛ የማይሞሉ እልፍ አእላፋት መናፍስት አምነዉብኝና የተወሰኑት ደግሞ በጥርጣሬ ተቀብለዉኛል።

ይሁንና «አልቀበልም» ካሉኝ መናፍስት ጋር ጥል ስንፈጥር በተለይ ከሚካኤል፣ ከገብርኤል ጋር ኃይለኛ ትንቅንቅ በምናደርግበት ወቅት ቀድሞ የማናዉቀዉና ያላየነዉ ነገር ግን ከኛ በላይ የሆነ እንዳለ ኅሊናችን የሚመሰክርብን የሁላችን ፈጣሪ በብርሃናዊ ባሕርይ ተገልጾ ታየን። የኔንና ከኔ ጋር ህብረት የፈጠሩ እንዲሁም በዉስጣቸዉ «ፈጣሪያችን ሊሆን ይችላል።» በማለት በጥርጣሬ የተቀበሉኝን ጭምር እንደ ዐመጻችን ደረጃ ጸጋችንን ገፎ አዋርዶን ጎስቋላ ባሕርይ እንደንለብስ አድርጎ «ርኩሳን መናፍስት» የሚል ስያሜ ሰቶን እኔንም «የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ» ብሎኝ ከሰማያት ቀጥላ የተፈጠረችሁ ሁለተኛዋ ምሳሌያዊ ቦታ ትልቋ ዓለም ዉስጥ አነስ ያለች ምድር በዉስጧ ፈጥሮና በድቅድቅ ጨለማ እንድትሞላ በማድረግ ወደዚህች ምድር ተጣልን።

በተቃራኒዉ ደግሞ እኛን የተቃወሙ እንደ ጽናታቸዉ ደረጃ የተለያየ ሹመትና የክብር ጸጋ ተሰቷቸዉ በሰማያት ዉስጥ አምላካቸዉ በብርሃናዊ ባሕርይ ተገልጾ መመለክ ጀመረ። እንዲሁም በኛ ዐመጸኞች መናፍስት ምትክ ሌላ ሕያዉ ፍጥረት ካለመኖር ወደ መኖር ለማምጣት ፈልጎ በሁለተኛዋ ምሳሌያዊ ቦታ ዓለም ዉስጥ ከምድር በስተቀኝ የምትገኝ ገነት የተባለች ምድር (ቦታ) አዘጋጅቶ ሁለት ሕያዋን ፍጥረቶች ከባሕርይዉ እንዲሰርጹ (እንዲወጡና) በምስሌያዊ ባሕርይ (ረቂቅ አካል) እንዲገለጹ በማድረግ በገነት አኖራቸዉ።

እኛ እንደተሳሳትነዉና እንዳመጽነዉ እንዳያምጹና በግልጽ ተገዥነታቸዉን እንዲያረጋግጡ አንዲት ከምሳሌያዊ ባሕርይ ፍሬ አዘጋጅቶ እንዳይበሏት አዘዛቸዉ። ከበሉ ግን የሞት ሞትን እንደሚሞቱ ጭምር አስጠነቀቃቸዉ። ስራቸዉ እሱን ማመስገንና በቅድስና፣ በደስታ ኑሮ ብቻ እንዲኖሩ እንዲሁም ሌሎች እንደነሱ የሆኑ ሕያዋን ፍጥረቶች በእነሱ ምሳሊያዊ ባሕርይ ግንኙነት ብቻ ካለመኖር ወደ መኖር እንደሚመጡና የሁሉም ወላጆች እንደሚሆኑ ተነግሯቸዉ ነበር። በመጨረሻም ቁጥራቸዉ ከኛ ርኩሳን መናፍስት እኩል በሚሆንበት ሰዐትና ባቀደዉ ዘመን ወደ ሰማያት ዉስጥ በማስገባት በቅዱሳን መላእክት ስርዐት ሊያኖራቸዉ ነበር እቅዱ። እኛም ዐመጸኞቹ ርኩሳን መናፍስት እነሱ ወደ ሰማያት

ዉስጥ እስከሚገቡ ድረስ በዚህች ቀድሞ ድቅድቅ ጨለማ ብቻ በነበረችዉ ምድር ወስጥ እየተቀጣንና እየተሰቃየን እንድንኖር ለማድረግና በኋላም እነሱ ወደ ሰማያት ዉስጥ ሲገቡ ህልዉናችንን አጥፍቶ በአንድ ቦታ ሳናስተዉልና ሳናዉቅ እንድንኖር ለማድረግና በመጨረሻም ዓለምን ከመኖር ወደ አለመኖር ለማሳለፍ ነበር እቅዱ::

ይሁንና ገና አንድ ሕያዉ ፍጥረት(ነፍስ) በምሳሌያዊ ባሕርይ ግኝኙነት ካለመኖር ወደ መኖር ሳይመጣ እኔ የጨለማዉ ገዥና ሠራዊቶቼ ሰይጣናት በእኛ ምትክ ሌላ ሕያዉ ፍጥረት መፈጠሩ ገባንና ቅናትና ምቀኝነት አደረብን:: ከዚያም እኔ ክፋትና ተንኮል የሞላብኝ የጨለማዉ ገዥና ጌታ ወደ ገነት እንድገባ ተፈቅዶልኝ ሔዋን በመባል የምትታወቀዉን ሕያዉ ፍጥረት (ነፍስ) የገነት አኗኗራቸዉን ጠየኳት:: እሷም እንደሷ በምሳሌያዊ ባህርይ (በረቂቅ አካል) የተገለጽኩ ነበርኩና አንዳች ጥርጣሬ ሳያድርባት የተባሉትን ሁሉ ዘክዝካ ነገረችኝ::

እኔም ዉድቀታቸዉንና ጥፋታቸዉን እፈልገዉ ነበርና ምክንያቱም በእኛ ምትክ ስለተፈጠሩ ቅናት አድሮብናልና፤ እንዲሁም እነሱ አምላካቸዉ ላይ ካመጹ ለእኛ ምህረት ይደረግልናል በሚል ግምት « አትብሉ የተባላችሁትን ፍሬ ከበላችሁ እንደእርሱ ሁሉን አዋቂ፣ ፈጣሪ ስለምትሆኑ ነዉ አትብሉ ያላችሁ» በማለት፤ የዐመጻ ምክሬን መከርኳት:: ለካስ የእምነት ጽናታቸዉ ይታይ ዘንድና በነጻ ኅሊናቸዉ በእዉነትና በመንፈስ እንደሚያመልኩትና የታዘዙትንም ትዕዛዝ «እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ያየናልና ትዕዛዙን መጠበቅ አለብን::» ብለዉ ትዕዛዙን እንደሚጠብቁና እንደማይጠብቁ ለማየት ነዉና እኔም ወደ ገነት እንድግባ የተፈቀደልኝ፤ ልክ ክፉ ምክሬን እንደመከርኩ ከገነት እንድወጣ ተገድጄ ወዲያዉ ወደዚህች ምድር ተመለስኩ:: ምክሬን ተግባራዊ ያድርጉ አያድርጉ በወቅቱ ያላወኩ ሲሆን ለካስ ምክሬን በመቀበል በምኞት ተቃጥላ ኖሯልና ያቺ ያልተፈቀደችላቸዉን ፍሬ በመጀመሪያ ሔዋን በመቀጠልም አዳም በመባል የሚታወቀዉ በላ::

ወዲያዉ ከእግዚአብሔር ጸጋ ተለዩ:: ባዶነት ተሰማቸዉ:: ያ ለታላቅ ዓላማ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣቸዉ አምላክ እንደበፊቱ በብርሃናዊ ባሕርይ ተገልጾ ያልተፈቀደላቸዉን ፍሬ ለምን እንደበሉ ጠየቃቸዉ:: አዳምም በሔዋን አሳበበ:: ሔዋንም በእኔ አሳበበች:: ይሁንና

ሁሉቱም ማንም ሳያስገድዳቸዉ በነጻ ኅሊናቸዉ ተመርተዉ ነጻ ፈቃዳቸዉን ተጠቅመዉ በምኞት ተሸንፈዉ የበሉ በመሆናቸዉ ምንም አስተያየት ሳይደረግላቸዉ ይህች የእኛ መኖሪያ ብቻ የነበረችዉ በድቅድቅ ጨለማ ተሞልታ የነበረች ምድር አሁን የምታያቸዉና በሥጋዊ አይናችሁ የማታያቸዉ ፍጥረቶች ሁሉ ተፈጥሮላቸዉ በመጨረሻ ይቀጡበት፣ ይጠሩበትና ይነጥሩበት ዘንድ ይህ የለበሳችሁትን ሥጋ ከመሬት አዘጋጅቶ ቀድሞ በገነት ዉስጥ ተገልጠዉበት የነበረዉን ረቂቅ አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) ወደ አለመኖር አሳልፎት ይህን ግዙፉን ምሳሌያዊ ፍጥረት የሆነዉን ሥጋ ነፍሳቸዉ ተዋህዳ እንድትገለጽበት አደረገ።

አዳምን በወንድ ጾታ ሔዋንን በሴት ጾታ እንዲገለጹና ቀድሞ በእነሱ አማካይነት በምሳሌያዊ ባሕርይ ግንኙነት ብቻ ሌሎች ነፍሳት ካለመኖር ወደመኖር እንዲመጡ ያዘዘዉን ሽሮ እነሱና የልጅ ልጆቻቸዉ ሁሉ በምሳሌያዊ ፍጥረት ግንኙነት (በወንድና በሴት ጾታ ግንኙ ነት) አማካይነት እንደሚወልዱ ገልጾላቸዉ፤ እነሱም በዚህ ምድር ቆይታቸዉ እኔን የጨለማዉን ገዥ ክፉ ምክር ሰምተዉ ነዉና ያዐመጹት እኔ ገዥቻዉ እንደምሆን፣ ሌት ተቀን እንደምፈታተናቸዉና እንደምቀጠቅጣቸዉ፣ ከዚህ ከሚቀጡበት ለመኖር ግድ መብላትና መጠጣት ካለበት ሥጋቸዉ ሲለዩ ደግም ድቅድቅ ጨለማ ቦታ ሲያል እንደሚጠብቃቸዉ፤ ምንም ሳይለፉ፣ ሳይወጡ፣ ሳይወርዱ የሚኖሩበትን ገነትን ስለናቁና ስላመጹ በዚህች ምድር ወተዉ፣ ወርደዉ፣ በድካማቸዉ እንደሚኖሩ፤ ሔዋንም የመጀመሪያ ክፉ ምክር ተቀባይና የዐመጻ ፈጻሚ በመሆኗ በገነት በምሳሌያዊ ባሕርይ ግንኙነት አማካይነት እንኳን ምጥና ጭንቀት አይደለም መዉለዷን እንኳ አንዳች የተለየ ስሜት በማይሰማት መልክ ከእግዚአብሔር ባሕርይ የሚሰርጹትን ሕያዋን ነፍሳት የሆኑት አማናዊ ፍጥረቶች (ሁሉንም የሰዉ ዘሮች) በእናትነት ካለመኖር ወደ መኖር የሚመጡባትን ባለመፈለጓ በምጥና በጭንቅ እንድትወልድና ዘሮዎቿም እንደእሷ እንደሚወልዱ ነግሯቸዉ ተለያቸዉ።

እነሱም ባደፈ፣ በጎደፈ፣ በጎሰቆለ ባሕርይ መኖር፤ በኔም ሌት ተቀን መፈተንና መቀጥቀጥ ደረሰባቸዉ። ይሁንና ለዚህ ሕይወት በመዳረጋቸዉና አምላካቸዉ ላይ በማመጻቸዉ ምክንያት እጅግ ያዝኑ፣ ይተክዙ ጀመር። አምላካቸዉንም በእንባና በለቅሶ፣ በጸጸት ይቅርታ ሁሉ ጊዜ ይጠይቁት ነበር። አምላካቸዉም ርኅሩኅ ነዉና ኀዘናቸዉንና

እንባቸዉን ተመልክቶ ስለሁለት ነገር ንስሐቸዉን ተቀበለ። አንደኛዉ እዉነተኛ ንስሐ ስለገቡ። ሁለተኛ እናንተ የእነሱ ዘሮች ባላወቃችሁትና ባለመጻችሁት ዐመጻ በእነሱ ላይ የተፈረደዉ ፍርድ ሁሉ በእናንተም ላይ ስለጸና እናንተም ስላሳዘናችሁት የእናንተ የሰዎች ነፍስ ከእኛ ሰይጣናት ቁጥር እስኪሞላ ድረስ ያሉትን ነፍሳት ከባሕርይዉ አስርጾ ለቅጽበት ያህል በነጻ ኅሊናችሁ ያሳያችሁትን የእምነት ጽናትና አምላካችሁን የመፈለግ ብቃታችሁን ተመለከተ።

በእይታዉ ዉስጥም እጅግ ብዙዎቻችሁ እሱ ከሚጠብቀዉ ደረጃ ዝቅ ብላችሁ ቀላችሁ ነዉ የተገኛችሁት። ጥቂቶች ደግሞ ከመቅለል አልፈዉ እንደኔና እንደ ሌሎች ሰይጣናት የማይገባ አሳብ በዚያች ቅጽበት በማሰባቸዉ እንደኛ ሆነዉ ነዉ ያገኛቸዉ። የተወሰኑት ደግሞ የሚፈልገዉን ደረጃ  አሟልተዉ በምርጥ ነፍሳትነት ደረጃ ያገኘዉ። ጥቂቶች ደግሞ ከሚጠብቀዉ ደረጃ ልቀዉ በብቃት ነፍስነት ነዉ ያገኘዉ። አንዲት ነፍስ ደግሞ ከሁላችሁ እጅግ ልቃና በቅታ ነዉ ያገኘዉ። በነጥብ ደረጃ ሲታይ እጅግ በቅታ የታየችዉ ከመቶ መቶ ነጥብ ያገኘች ስትሆን፤  ሌሎች የበቁ ነፍሳት ደግሞ ከ90 እስከ 99 ነጥብ፤ ምርጥ ነፍሳት ደግሞ ከ60 እስከ 89 ነጥብ፤ የቀለሉ ነፍሳት ደግሞ ከ40 እስከ 59 ነጥብ፤ ከመቅለል አልፈዉ በእኛ ደረጃ የታዩት ደግሞ ከ20 እስከ 39 ነጥብ ያገኙ ናቸዉ። ለአዳምም እጅግ ልቃና በቅታ የተገኘችሁ ነፍስ ስትወለድ «ከእርሷ ተወልጄ አድንሃለዉ። ወደ ቀደመ ግዛትህ ገነትና ወደ መጀመሪያ ወደተፈጠርክበት ዓላማ ሰማያት ዉስጥም አስገባሃለዉ» በማለት ቃል ገብቶለት አጽናናቸዉ።

እኔ የጨለማዉ ገዥና ጭፍሮቼ ሰይጣናት ግን እጅጉን ተናደድን፤ ተባሳጨን፤ የሚቻለን ቢሆን ኖሮ በዚያች ቅጽበት ዉስጥ ታንቀን ራሳችንን ብናጠፋ ምርጫችን ነበር። ነገር ግን እንድ እናንተ በግዙፍ ሥጋ ስላልተገለጽን አልተቻለንም። ከዚያች ጊዜ ጀምሮ በተጠናከረ መልኩ አዳምንና ዘሮቹን ሁሉ በመፈታተንና ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት እንዲፈጽሙ በማድረግ ወደ ገነት ሆነ መንግስተ ሰማያት እንዳይገቡ መፈታተንን ጀመርን።

የመጀመሪያዉ ጥረቴ ተሳክቶልኝ ምስኪኑ አቤል በወንድሙ ቃኤል እንዲገደል በማድረግ ከገነት ውድቀታቸዉ በኋላ ከትልቋ ዓለም ዉጭና አጠገብ የተፈጠረችዉ ሲዖል

ዉስጥ እንዲጋዝ አደረኩ:: ምንም እንኳ በሲዖል ዉስጥ የመጀመሪያዉ ነፍስ በምሳሌያዊ ባሕርይ (በረቂቅ አካል) ተገልጻ ብትገባም፤ ጻድቅ ነፍስ ነበረችና በእግዚአብሔር ረድኤት ስለምትጠበቅ አንዳች የጭንቅ ሆነ የመከራ ሕይወት አላጋጠማትም:: ይልቁኑ ካደፈና ከጎሰቆለ ባሕርይ ተለይታ በተረጋጋና በረካ ሕይወት ዉስጥ ነበር የምትኖረዉ:: ታዲያ ለ5500 ዘመን ነፍሳት ወደ ሲዖል ሲጋዙ እግዚአብሔርን በመፍራት ይመላለሱ የነበሩ ሰዎች ነፍሳቸዉ በሲዖል ዉስጥ ብትኖርም የሲዖል ሕይወት አይከብዳቸዉም ነበር:: በተቃራኒዉ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ውስጥ ተመላልሰዉ ከነኃጢአታቸዉ የሞቱ ሰዎች ደግሞ ልክ እናንተ «ወንጀል ስትሰሩ ታወቀብኝ አልታወቀብኝ፤ ተደረሰብኝ አልተደረሰብኝ::» በማለት እንደምትጨነቁ እነሱ ደግሞ በባሰ ሁኔታ« ምን ፍርድ ይጠብቀን ይሆን?» እያሉ እንደ ኃጢአታቸዉ ደረጃ በሲዖል ዉስጥ በስጋትና በጭንቀት ይሰቃዩ ነበር::

5500 ዘመን ሲያልቅ ያቺ የሰዉ ዘሮች መዳኛ ምክንያት የሆነችዉ ትጠበቅ የነበረችዉ ነፍስ ኢያቄምና ሀና ከሚባሉ እግዚአብሔርን በመፍራት ከሚኖሩ ቤተሰቦች ተወልዳ ለአቅመ ሔዋን ስትደርስ ያ ለአዳም « ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለዉ::» ብሎ ቃል የገባለት አልፋና ዖሜጋ ፍጥረታት ከመፈጠራቸዉ በፊት በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ እንደ አማናዊ ባሕርይዉ የነበረ፤ በሕያዉነት ዘመን ዉስጥ ከዛሬ 7503 ዓመት በፊት ሰማያትንና እልፍ አእላፋት ወትእልፊት መናፍስትን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ፤ በኋላም ዓለምንና በዉስጧ የሚታዩትንና የማይታዩትን ፍጥረቶች ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ፤ ከፈለገም በዐይን ቅጽበት ዉስጥ አሁን ካላዉ ፍጥረት በእልፍ አእላፋት እጥፍ ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣት የሚችል፤ ከፈለገም የሚታየዉንም የማይታየዉን ዓለም በዐይን ቅጽበት ጊዜ ዉስጥ ከመኖር ወደ አለመኖር ማሳለፍ የሚችል፤ ካለእርሱ ፈቃድ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊኮን የማይቻል፤ ሁሉን የሚመለከትና የሚቆጣጠር፤ ያልኖረበትና የማይኖርበት ጊዜ የሌለ፤ ለእያንዳንዱ እንደ ስራዉና እምነቱ የሚፈርድለትና የሚፈርድበት እዉነተኛ ፈጣሪ አምላክ እግዚአብሔር፤ ከአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ሳይጎል፣ ከሰማያት ሳይጎል፣ ከዓለም መግቦቱ ሳይጎል፣ ባጠቃላይ በሁሉ ቦታ ምሉእ እንደሆነ ባሕርይዉን ብቻ ዝቅ አድርጎ ከእመቤታችሁ ከመዳኛችሁ ምክንያት ከአደራ እናታችሁ ከኔ ደግሞ ከዘመናት ደመኛዬና ጠላቴ ከሆነችዉ ከድንግል

ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ፣ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ከሁለት አካል አንድ አካል፤ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በመሆን በተዋህዶ ፍጹም ሰዉ ፍጹም አምላክ ሆና ተወለደ::

እኔም የጨለማዉ ገዥ ታወኩ፣ ተሸበርኩ፣ ተጨነኩ፣ በሄሮድስ አማካይነት ለማስገደል ብሞክርም አልቻልኩም:: በሥጋ ከተገለጸ ሰላሳ አመት ሲሞላዉ በሚያስተምርበት፣ በሚፈዉስበት፣ ተአምራትን በሚያደርግበት ጊዜ ሰዎችን በተለይ «የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን::» የሚሉትን የልባቸዉን ክፋት፣ ትዕቢት፣ ቅናት፣ ዐመጻ አዉቃለሁና በተለያየ ጊዜ ጥቃት እንዲፈጽሙበት ባነሳሳም ሳይሳካልኝ ቀርቶ ራሱ በፈቀደዉ ጊዜ የተለያዩ መከራዎችን ተቀብሎ በመስቀል ላይ በመሰቀል ነፍሱን ከሥጋዉ ሲለይ፤ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ሄዶ እስከዚያች ሰዐት ድረስ በሲኦል በረቂቅ አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) ተገልጸዉ ይኖሩ የነበሩትን ነፍሳት ሁሉንም ነጻነትን አዉጆላቸዉ በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ ለገነት የሚያበቃ የጽድቅ ስራ የነበራቸዉን ይኸዉም በምድራዊ ዘመናቸዉ በኪዳነ ልቡና ተመርተዉ መልካም የሰሩትና በኃጢአት ሲወድቁም በኅሊናቸዉ ጸጸት ያደረጉ፣ እንዲሁም በኪዳነ ኦሪት ተመርተዉ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ የጠበቁና በኃጢአት ሲወድቁም የኃጢአት ስረየት የተደረገላቸዉ ነፍሳት በቀጥታ ወደ ገነት የገቡ ሲሆን:: ሌሎቹ ነፍሳት ግን በሲኦልና በዓለም አጠገብ በተፈጠረችሁ አራተኛዋ ምሳሌያዊ ባሕርይ ቦታ ወደ ማረፊያ ቦታ ነዉ የገቡት:: እነዚህ ነፍሳት የእግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስን የመጨረሻዉን ፍርድ ለማግኘት የዓለም እልፈትን ቀን እየተጠባበቁ ይገኛል:: በማረፊያ ቦታም ከሲኦል ድቅድቅ ጨለማ ኑሮ ተገላገሉ እንጂ በምድር ዉስጥ እንደፈጸሙት ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ደረጃ ነፍሳቸዉ እየተቀጣች ነዉ የሚገኘዉ::

ከክርስቶስ ስቅለት በኋላ የሚሞቱት ሰዎች (ነፍስ ከሥጋቸዉ ተለይታ) በረቂቅ አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) ስትገለጽ የሚገቡት ወደ ገነት፣ ማረፊያ ቦታና ሲኦል ዉስጥ ነዉ:: ወደ ገነት የሚገቡት በእርሱ በኢየሱስ ክርስቶስ በእግዚአብሔርነቱ አምነዉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሥም የተጠመቁ፣ መለኮት በተዋሀደዉ በክርስቶስ ሥጋና ደም የታተሙ፣ መልካም ምግባር ያላቸዉ፣ በኃጢአት ሲወድቁ ደግሞ እዉነተኛ ንስሐ ገብተዉ መለኮት የተዋሀደዉን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የተቀበሉ ክርስቲያኖች ብቻ ናቸዉ::

ወደ ሲዖል የሚገቡት ደግሞ በኪዳነ ልቦና ወይም በኪዳነ ኦሪት ወይንም በኪዳነ ወንጌል ተመርተዉ መልካም ያልሰሩ፤ በኃጢአት የኖሩ፤ ስለ ኃጢአታቸዉ ያልተጸጸቱና ንስሐ ያልገቡ፣ ባጠቃላይ ዳግም ፍርድ የማያስፈልጋቸዉ በፍርድ ቀን በቀጥታ ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ከኔ ከጨለማዉ ገዥና ከሠራዊቴ ሰይጣናት ጋር አብረዉ የሚጣሉ ዐመጸኛና ከሃዲ ሰዎች (ነፍሳት) ናቸዉ።

ወደ ማረፊያ ቦታ የሚገቡና የመጨረሻ የክርስቶስን ፍርድ የሚጠባበቁት ሰዎች ደግሞ በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ በመሰላቸዉ ሕይወት ዉስጥ በመልካም ተግባርና በቅን አሳብ የተመላለሱና ኃጢአት ሲፈጽሙ የኀሊና ጸጸት ያደረጉ ነገር ግን በእዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ ዉስጥ ያልተመላለሱ፤ እንዲሁም በምድራዊ ሕይወት ቆይታቸዉ ነፍሳቸዉ የእምነትና የምግባር ደረጃዋ ያልታየ ህጻናትና ተመሳሳይ ሕይወት የሚታይባቸዉ ነፍሳት ናቸዉ። እነዚህ በማረፍያ ቦታ ቆይታ በሚያሳዩትና በሚያቀርቡት የእዉነትና የመንፈስ አምልኮ ለመንግስተ ሰማያት የሚያበቃ ብቃት ላይ ከደረሱ በፍርድ ቀን ወደ መንግስተ ሰማያት የመግባት እድል አላቸዉ።

አሁን የኛ ሰይጣናት የዐመጻ ተግባር ነጻነት የሚገደበዉ የእናንተ የሰዉ ዘሮች በገነት፣ በሲዖል፣ በማረፊያ ቦታ፣ በዚህች ምድር፣ እንዲሁም ነፍሳቸዉን እጅግ ብቃት ደረጃ ላይ በማድረሳቸዉ ምክንያት እግዚአብሔር በመለኮታዊ ስልጣኑ ወደ ሰማያት ያስገባቸዉና የሚያስገባቸዉ ቅዱሳን ነፍሳት ቁጥር ጠቅላላ ድምር ከእኛ ሰይጣናት ቁጥር እኩል በሚሆንበት ወቅት ነዉ።

በዚያን ጊዜ በዚህች ዓለም ዉስጥ ያሉት በዐይን የሚታዩትም የማይታዩትም ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ። እኛና በዚህች ምድር ዉስጥ የሚኖሩት ሰዎች ኃጢአተኛ ሰዎች በመቅሰፍት ሞት፤ ጻድቃን ደግሞ በምህረት ሞት ነፍስ ከሥጋቸዉ ትለይና ምሳሌያዊ ባሕርይ (ረቂቅ አካል) ትለብስና በቀጥታ ከዓለም ዉጭ ወዳለችዉ ማረፊያ ቦታ ለመጨረሻ ፍርድ ይቀርባሉ። በዚህች ዓለም ዉስጥ በገነት ያሉት ጻድቃን ነፍሳት የማረፊያ ቦታ የመጨረሻዉን ፍርድ ተመልክተዉ በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማያት ይገባሉ። በሲዖል ያሉት ነፍሳት ደግሞ የመጨረሻ ፍርዳቸዉን ተቀብለዉ ወደ ገሃነመ እሳት ከኛ ሰይጣናት ጋር

አብረዉ ይጣላሉ:: በማረፊያ ቦታ ቆይታቸዉ ለመንግስተ ሰማያት የሚያበቃ ብቃት ላይ የሚደርሱት ነፍሳት ደግሞ ከገነት ከነበሩት ነፍሳት ጋር በቀጥታ የመጨረሻ ፍረድ ተፈርዶላቸዉ እንደቅዱሳን መላእክት በሰማያዊ ስርዐት ለመኖር ወደ ሰማያት ዉስጥ ይገባሉ:: እንዲሁም በመጨረሻዉ የዓለም እልፈት ወቅት በኃጢአታቸዉ በመቅሰፍት ሞት ወደ ማረፊያ ቦታ የተጠሩት ነፍሳት ደግሞ ከኔ ፈቃዴን ከፈጸሙልኝ ከጨለማዉ ገዥ ጋር ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ይጣላሉ::

በተቃራኒዉ ደግሞ በምህረት ሞት ወደ ማረፊያ ቦታ የተጠሩት ነፍሳት ደግሞ ከወዳጆቻቸዉ ጻድቃን ጋር ወደ ሰማያት ይገባሉ:: በመጨረሻም ሲዖልም፣ ማረፊያ ቦታም፣ ዓለምም ምሳሌያዊ ባሕርይ ናቸዉና ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ:: መጀመሪያና መጨረሻ በሌለዉ አማናዊ ሕዋ ዉስጥ ሁለቱ ምሳሌያዊ ቦታ ሰማያትና ገሃነመ እሳት ብቻ ይቀራሉ:: በገሃነመ እሳት ዉስጥ እኛ ሰይጣናትና እናንተ ርኩሳን ነፍሳት (ዐመጸኛ ሰዎች) ነፍሳችን በረቂቅ አካል (በምሳሌያዊ ባሕርይ) ሆና እሳቱ በማይጠፋ ምሳሌያዊ ባሕርይ ትሉ በማይሞት ምሳሌያዊ ባሕርይ እንደ ዐመጻችን ደረጃ እየተቀጣን ለሕያዉነት ዘመን እንኖራለን::

በዚህ አጋጣሚ በኖኅ ዘመን የነበሩት ዐመጸኛና ርኩሳን ሰዎችን በጨለማዉ ስሜ ላመስገናቸዉ እፈልጋለሁ:: ምክንያቱም በዚያን ወቅት እጅግ የከፋና የከረፋ የዐመጻ ተግባር ባይፈጽሙና ከምድር ባይደመሰሱ ኖሮ፤ የሰዎች ነፍስ ቁጥር ገና ዱሮ ከእኛ ሰይጣናት ቁጥር እኩል ስለሚሆን ፤ ነጻነታችን ተገድቦ ገና ዱሮ ነበር ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ የምንጣል የነበረዉ:: አሁንም ምኞታችን እናንተ የአዳም ዘሮች ኃጢአታችሁ እጅግ ከፍቶ ከምድር ትደመሰሱና እንደኖኅና ቤተሰቡ አይነቶች ብቻ ቀርተዉ የምድራዊ ዘመናችን እድሜ እንዲራዘም፤ የእናንተም ምድራዊ ቅጣት ዘመን እንዲራዘም ስለምንፈልግ ነዉ::

ሌላዉ ቅሬታዬን በእናንተም ሆነ በኔ ፈጣሪ ላይ አቀርባለሁ:: ይኸዉም እኔ የመዳን እድል ሳይሰጠኝ፣ ዋጋ ሳይከፈልልኝ ስላመጽኩ ነዉ ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ እንድጣል የሚፈረድብኝ:: እናንተ የአዳም ዘሮች የመዳን እድል ተሰቷችሁ፣ በመስቀል ላይ ታላቅ ዋጋ ተከፍሎላችሁ «እኛ በእግዚአብሔር መንግስት መኖር አንፈልግም፤ በመስቀል ላይ የተሰቀለዉና ዋጋ የከፈለልንን አምላክ አንፈልገዉም፤ አናምንበትም » ብላችሁ ነዉ፤

በኃጢአት ተግባር የጸናችሁና ከኔ ከጨለማዉ ገዥ ዐመጻና ክህደት በላቀ ደረጃ ላይ ተገኝታችሁ «እንዴት እኩል በገሃነመ እሳት ቦታ ላይ ይፈረድብናል?» በማለት ነዉ፡፡

የእናንተ ገሃነመ እሳት እጥፍ ወይንም እስኬር መሆን ይገባዉ ነበር፡፡ ዞሮ ዞሮ እኛ ሰይጣናት ሆን  እናንተ የሰዉ ዘሮች እንደ ዐመጻና ክህደታችን ደረጃ ስለሆነ የስቃዩና የጭንቀቱ ስሜት የሚሰማን፤ በዚያዉ በገሃነመ እሳት ዉስጥ ቅጣቱ ይለያይልናል፡፡ እዛም ጌታችሁና አዛዣችሁ እንደምሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ ታዲያ እዚህ «ፈቃድህን እንፈጽምልህ፤ ያንተ ባለሟልና ባሪያ እንሁንልህ፡፡» እያላችሁ እንደምታስቸግሩኝ፤ እዚያ ደግሞ ይህን ተጋድሏችሁን እንዳታሳዩኝ አስቀድሜ አስጠነቅቃችኋለሁ፡፡ በዚህ ምድራዊ ዘመናችሁ ለኔ የምታሳዩት ታማኝነትና ስራ አስፈጻሚነት ለኔ በቂዬ ነዉ፡፡ »    **ይላል የዐመጸኞች፣ የከሃዲያንና የርኩሳን ጌታ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ፡፡**

## ምእራፍ ስድስት

« እናንተ እግዚአብሔርን ባወቃችሁና ምስጢራቱን በተረዳችሁ ቁጥር እየደፈራችሁት የምትሄዱና እለት እለት በድፍረት ተግባራችሁ የምታስቆጡት አስመሳይ አገልጋዮች፤ እግዚአብሔር ባወቃችሁትና በተረዳችሁት፣ እንዲሁም ምስጢራትን ባወቃችሁና በተረዳችሁ መጠን አምላካችሁን በተግባር፣ በንግግር፣ በአሳብ በፍጹም ልትፈሩትና ልታከብሩት እንዲሁም ደስ በሚሰኝበት ሕይወት ብቻ ከማንም በላይ መመላለስ ሲገባችሁ፤ እግዚአብሔርን ከማያዉቁ ሰዎች በላይ በድፍረት ኃጢአት የምትመላለሱ በመሆናችሁ እናንተ ለፈጣሪያችሁ ያልበጃችሁ ለኔ ለጨለማዉ ገዥም የማትበጁ ስለሆነ እናንተን በተለየ ሁኔታ ሌት ተቀን የምፈታተናችሁ፣ የማጠቃችሁ፣ የማጎሳቁላችሁ፣ ጌታችሁ ሆኜ የምነግሥባችሁ መሆኑን በግልጽ አሳዉቃችኋለሁ።

እናንተ ለሰዉ ዘሮችና ለፍጥረቶች በሚሊዮንና በቢሊዮን እድሜ የምትሰጡና የተፈጥሮ ባለቤትና ፈጣሪ የሆነዉን እግዚአብሔርን ለማስካድ «ሰዎች የተገኙት በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ (በኢቮልሽን) አማካይነት ከጦጣ መሰል እንስሳ ነዉ።» በማለት የምታምኑና የምታሳምኑ ዐመጸኛና ከሃዲዎች፤ የተማራችሁት ምድራዊ እዉቀት ለወገኖቻችሁ ለአዳም ዘር በሚጠቅም ተግባርና እዉቀት ላይ ማዋል ሲገባችሁ እናንተ ግን ዐመጻን፣ ክህደትን፣ ርኩሰትን፣ ሐሰትን ለማንገስና ሰዎች ሌላዉ ቢቀር በኅሊናቸዉ ሕግ እንኳ እንዳይመሩ፣ ኅሊናቸዉን እንዳይሸጡ ላለማድረግ በነፍሳቸዉ አንዳች የሚጠየቁበት ነገር የሌለ አድርገዉ እንዲያስቡ አስደርጋችሁ ለግፍ፣ ለጭካኔ፣ ባጠቃላይ ለኃጢአት ተግባር እንዲሰለፉ አደፋፍራችኋቸዋል።

እስቲ የዛሬ አምሳ አመት የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ስንት ነበር? ሰላሳ ሚሊዮን ይሞላ ነበርን? አሁንስ ከሰማኒያ ሚሊዮን በላይ አይደለምን? ከሁለት መቶ ዓመት በፊት አምስትና አስር ሚሊዮን ይሆኑ ነበርን? በዚሁ መልክ ወደ ኋላ አምስት መቶ፣ አንድ ሺህ፣ ሁለት ሺህ፣ ሶስት ሺህ፣ አራት ሺህ.. ወዘተ እያላችሁ ስትሄዱ ምን ያህል ሕዝብ ነበር? የአሜሪካ፣ የቻይና፣ የህንድ ሕዝብ አሁን በመቶ ሚሊዮንና በቢሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ነዉ ያላቸዉ፤

ከሁለት መቶ ዓመት በፊት ምን ያህል ነበር የሕዝብ ብዛታቸዉ? በአስራና በመቶ ሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ ነበራችሁን? አልነበራቸዉም:: ከዛሬ አምስት መቶ፣ አንድ ሺህ፣ ሁለት ሺህ ዓመት በፊት ምን ያህል ሕዝብ ነበራቸዉ? ምንምና በሺህዎች የሚቆጠሩ ብቻ ነበር::

ይህም የሚያሳየዉ ደግሞ እንደአሁን ዘመናዊነት ሳያጠቃቸዉና የስግብግብነት ሕይወት ሳይነግስባቸዉ፣ «የቤተሰብ ምጣኔ» የሚባለዉ የአህዛብ ስርዐት ሳይመሰረት በፊት በነበረዉ የአወላለድ ስርዐት በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም የሕዝቡ ቁጥር እጅግ አነስተኛ እንደነበረና ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን የሕዝቡ ብዛት እጅግ እየጨመረ መምጣቱንና አሁን ከሰባት ቢሊዮን ሕዝብ በላይ መድረሱ ነዉ የሚታወቀዉ::

ታዲያ የሰዉ ዘሮች በሚሊዮን ቀርቶ በመቶ ሺህዎች የሚቆጠር እድሜ ቢኖራቸዉ ኖሮ አሁን በቢሊዮንና በትሪሊዮን የሚቆጠር አይደለም እልፍ አእላፋት ወትእልፊት እጅግ እጅግ ብዙ የሆኑ ሕዝቦች በዓለም ላይ በኖሩ ነበር:: ነገር ግን አሁን ያለዉ የሕዝብ ቁጥር እጅግ አነስተኛ አስራ ቢሊዮን ዉስጥ እንኳ ያልገባ በመሆኑ የሰዉ ዘሮች ታሪክ በሚሊዮን እድሜ ሊቆጠር ቀርቶ እጅግ አጭር ዘመን መሆኑንና አስራ ሺህ እድሜ የማያስቆጥር መሆኑን ይገልጻል::

እናንተ ግን የኔ የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስ አገልጋይ በመሆናችሁ ኅሊናችሁን አደንድናችሁ ክህደትን ትፈጽማለችሁ፤ ታስፈጽማላችሁ:: ተፈጥሮ የምትሉት የእግዚአብሔር ፍጥረታት ሌት ተቀን የሚከናወነዉ፣ የሚታየዉ ሁሉ የእግዚአብሔር ህልዉናን የሚመሰክር፤ ሁሉም ፍጥረት በስርዐትና በአግባቡ በመንቀሳቀሱ በበላይ እያንዳንዱን ፍጥረት የሚቆጣጠር ሕይወት ያለዉ ኃይል መኖሩን፣ ተፈጥሮ የምትሉት ሆነ ኅሊናችሁ ይመሰክርባችኋል:: እኔ የጨለማዉ ገዥ ባዶነታችሁን እንድታዉቁ የፈለኩት ዋንኛዉ ምክንያት በእግዚአብሔር እንድታምኑና ለእሱ እጅ እንድትሰጡ ፈልጌ ሳይሆን የኔን ህልዉና ጭምር ስለካዳችሁ በዚህ ክህደታችሁ ተቆጥቼ መሆኑን አሳዉቃችኋለሁ::

እናንተ በዘመናዊ ትምህርታችሁ የተለየ ሁኔታን (ኤክሰፕሽናል ኬስ) እያላችሁ ስታስተምሩ የእግዚአብሔርን ልዩ ተግባራቱንና ተአምሩን ግን « እንዴት ይሆናል?» በማለት የምትጠራጠሩና እንደ ፈጠራ ታሪክ፣ እንደ ተረት ተረት የምታዩ ደፋሮችና እምነት

የሌላችሁ ሰዎች፣ እንዲሁም በእምነት ዉስጥ የምትመላለሱ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች፤ «ሰዉ ካለመብልና ካለመጠጥ አርባ ቀን ቆየ» ሲባል ይደንቃችኋል፤ ሐሰት ነዉ ትላላችሁ:: «ሰዉ ነፍሱ ከሥጋዉ ሳትለይ ወደ ሰማይ ዐረገ፤ ወደ ፈጣሪዉ ተወሰደ» ሲባል፤ እዉነት አይመስላችሁም:: « ባሕር እንደ ግድግዳ ቆመ» ሲባል አይዋጥላችሁም:: በተፈጥሮ ሕግ ሊሆን የማይችለዉን የእግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳንና ጻድቃን « እንዲህ አደረጉ» ሲባል ጆሯችሁን ያሳክካችኋል፤ ተረት ተረት ይመስላችኋል::

ሰዉ በእናቱ ሆድ አምላኩን ሲያመሰግንና ምልክት ሲያደርግ፤ ተወልዶ በሶስተኛዉ ቀን አምላኩን ሲያመሰግንና ምልክት ሲያደርግ፤ «ግዙፉ ሰዉ እንደ መናፍስት በአየር ላይ ተነጥቆ ከቦታ ቦታ ለአገልግሎት ተንቀሳቀሰ »ሲባል፤ «በጭራሽ አይሆንም እንዴት ሊሆን ይችላል?» የምትሉ ከቁሳዉያን አስተሳሰብ ያልተለየ አስተሳሰብ ያላችሁና ታላቁን አእምሯችሁን አጥባችሁ እኔን የጨለማዉ ገዥን በኅሊናችሁ ያነገሣችሁ አማኝ መሳዮች፤ ጥያራ(አይሮፕላን) ወይንም ሊሊኮፍተር እንዲፈጠር እዉቀትና ጥበብ የሰጠ አምላክ እንዴት ይህን ሊያደርግ አይችልም?

ይህስ በዐይናችሁ የምትያቸዉ ፍጥረቶች ሁሉ ምሳሌያዊ ፍጥረት ቀድሞ ያልነበሩ በእግዚአብሔር ኃይል የተዋቀሩ መሆናቸዉን ሳታስተዉሉ ቀርታችሁ ይሆን? ወይስ እኔ የጨለማዉ ገዥ የአምላካችሁን ኃይል እንድትጠራጠሩ በጆሮዋችሁ ሹክ እያልኳችሁ አደንዝዣችሁ ይሆን? ወይስ ነጥብ በማትሞላዉ እዉቀታችሁና ጥበባችሁ ተመክታችሁ የእግዚአብሔርን እዉቀትን፣ ጥበብን በጠባቧ ኅሊናችሁ ለመገደብ ፈልጋችሁ ይሆን ተአምራቱንና ድንቃድንቅ ስራዉን የምትጠራጠሩትና ለመቃወም የምትደፋፈሩት? ወይስ እንደኔ እንደ ጨለማዉ ገዥ «ደፋር፣ ከሃዲና ዐመጻኛ» በመባል ልትፎካከሩኝ በማሰብ ይሆን? መልሱን ለእናንተ ትቸዋለሁ::

«ሙሴ የኤርትራን ባሕር ከፍሎ ሕዝቡን አሻገረ፣ አርባ ቀንና ሌሊት ካለመብልና መጠጥ ቆየ፤ ሄኖክና አልያስ ሥጋዊ ሞትን ሳያዩ ወደ ሰማይ ዐረጉ፤ ወደ ፈጣሪያቸዉ ተወሰዱ፤ ነብያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን የተለያየ ፈዉስንና ተአምራትን አደረጉ፤ ድንግል ማርያም እንደ ልጇ በሥጋ ሞታ ተነሳች፤ በኋላም እንደ ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ

ዐረገች፤.. ወዘተ » የሚለዉን ትምህርት ለመቀበልና ለመስማት ፈቃደኛ ባትሆኑም እነዚህ ሊሆኑ የሚችሉ ቀላል ክስተቶች ቀርቶ፤ በዐይን የሚታዩትም የማይታዩትም ምሳሌያዊ ፍጥረቶችና ምሳሌያዊ ባሕርይ ስለሆኑ እግዚአብሔር ከፈለገ በዐይን ቅጽበት (በማይክሮ ሰከንድ) ወስጥ ከመኖር ወደ አለመኖር ሊያሳልፋቸዉ ይችላል፡፡ የእግዚአብሔር መላእክት ሆኑ እግዚአብሔር የፈቀደላቸዉ ነፍሳት በዐይን ቅጽበት ዉስጥ የብዙ ብርሃን ዓመት ርቀትን በዐይን ቅጽበት ጊዜ ዉስጥ ተጉዘዉ ማንኛዉም ቦታ ሊገኙና ወዳጆቻቸዉን ሊታደጉና ሊጠብቁ ይችላሉ፡፡

እግዚአብሔር፤ ድንግል ማርያም እንደሌሎቹ ነብያትና ጻድቃን ሥጋዊ ሞትን ሳታይ በቀጥታ እንድታርግና ወደ ሰማያት ዉስጥ እንድተገባ ማድረግ ሲችል፤ በሥጋዋ ሞታ፣ እንደገና ነፍስ ከሥጋዋ ተዋህዳ እንደ ልጅዋ በትንሳኤ የተነሳችዉና ወደ ሰማያት ያረገችዉ፤ ክብሯና ቅድስናዋ ከሌሎች ቅዱሳን በላይ መሆኑን ፍጥረታት እንዲያዉቁና የአዳም ዘሮችም የመዳኛቸዉ ምክንያት መሆኗን ተረድተዉ እንዲሁም ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች የሆነች የነብያትና የጻድቃን እመቤትና ንግሥት መሆኗን አምነዉ  በተለየ ሁኔታ እንድያከብሯት ፈልጎ ነዉ፡፡ ታዲያ እኔ የጨለማዉ ገዥ ይህን መናገሬ ክብሯን እንድታዉቁና እንድትመኩባት ለማሳሰብ ፈልጌ ሳይሆን በእሳት ሰንሰለተ ተጠፍሬ እዉነቱን እንድገልጽ ሳልፈልግ እንድመሰክር ተገድጄ መሆኑን አዉቃችሁ ተቃራኒዉን እንድታስቡ በዚሁ ምክሬን እለግሳችኋለሁ፡፡

የእግዚአብሔርና የድንግል ማርያም ባለሟሎች ድንግል ማርያምን አመስግነዉ አመስግነዉ፣ መስለዉ መስለዉ መርካት ስላልቻሉ አንደበት ስላጠራቸዉ «ምሳሌ ተመስሎላት ተመስሎላት፤ ተመስግና ተመስግና የማትጠገብ፤ የሕይወታችን ምስጢር ቁልፈ፤» እያሉ ሲገልጿትና በቅዱስ ኪዳኑ ጸሎታቸዉ «እናታችን ማርያም ሆይ! በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ: «ሰላም» እንልሻለን፡፡ በአሳብሽ ድንግል ነሽ፡፡ በዚህ የንጽህና ባሕርይሽ የአሸናፊዉ የእግዚአብሔር እናት ኾነሻልና :ሰላምታ ለአንቺ ይገባል፡፡

ማሕፀንሽ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነዉን ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ አንቺ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ የተባረክሽ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ፡፡ ቀድሞ በነብያት «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ

እግዚአብሔር » የተባልሽ፣ እኛም «እምነ ጽዮን» ስንልሽ የኖርን በሰማይና በምድር ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ።

እግዚአብሔር አንቺን የደኅነታችን ምክንያት አድርጎ ኪዳነ ምህረቱን ለዘለዓለም ፈጽሟልና «ጸጋን የተሞላሽ ብፅዕት ነሽ» እያልን ዘወትር እናወድስሻለን። በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አንቺ ለእኛ የአደራ እናታችን፣ እኛም ለአንቺ የአደራ ልጆችሽ ነንና ከተወደደዉ ልጅሽ ያልተለየዉ እናትነትሽ ከእኛም ምንጊዜም እንደማይለየን እናምናለን። ይህን ያደረገ ቸሩ አባታችን ልዑል እግዚአብሔር እናመሰግነዋለን።» እያሉ ጸሎታቸዉንና ምስጋናቸዉን ሲያቀርቡ፤

ያልታደለዉ ትዉልድ ደግሞ የመዳኛዉ ምክንያት መሆኗን ሳይገባዉና እናቱ እንድትሆነዉ የተሰጠችዉ ተስፋዉን፣ መጽናኛዉን፣ እመቤቱን ፣ ንግሥቱን ከመጥላቱና ከመካዱ በተጨማሪ እለት እለት ይሰድባታል፤ ያጥላላታል፤ ያዋርዳታል፤ ያቃልላታል። እኔ የጨለማዉ ገዥ እንኳ ድፍሬ የማልናገረዉን ስትናገሩና ስትሳደቡ፤ ስልጣን ቢኖረኝ ኖሮ ከምድረ ገጽ ባጠፋዋችሁ እመርጥ ነበር። ምክንያቱም እኔ ጌታችሁ የጨለማዉ ገዥ መሆኔን ብታዉቁና በኅሊናችሁ ነግሼ መጫወቻ እንዳደረኳችሁ ብታስተዉሉ በዚህ ልቅ አፋችሁ እጅግ አድርጋችሁ እንደምተሰድቡኝና እንደምታዋርዱኝ በደንብ አዉቃችኋለሁና ነዉ።

እናንተ የአዳም ዘሮች! ለእናንተ የተሰጠዉ የንስሐ እድልና በመስቀል ላይ ዋጋ የተከፈለላችሁ እድል ለኔ ለጨለማዉ ገዥ ተሰቶኝ ቢሆን ኖሮ ሌት ተቀን እናንተን ለማጥቃት፣ ለመፈታተን፣ ለማድከም፣ ለማሰቃየት የምተጋዉን ያህል በተቃራኒዉ በእዉነተኛ እምነትና አምልኮ ሆኜ የጽድቅ ስራ በሆኑት በመልካም ተግባር፣ በቅን አሳብ፣ በንስሐ፣ በሥጋና ደሙ፣ በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በምስጋና ሌት ተቀን እተጋ ነበር። ምን የደርጋል ታዲያ ፈላጊና ተፈላጊ አልተገናኘም። ለእናንተ ነዉ የድኅነት እድሉ የተሰጠዉ። ለእናንተ ነዉ በጥምቀት ዳግም ከእግዚአብሔር የመወለድ እድልና ለሕያዉነት ሕይወት የሚያበቃዉ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የተዘጋጀዉ። ለእናንተ ነዉ ወደ ገነትና ወደ እግዚአብሔር መንግስት የመግባት እድል የተመቻቸዉ። ነገር ግን እናንተ የአዳም ዘሮች እድላችሁን መጠቀም አልቻላችሁም።

ምን አይነት ኅሊና ቢኖራችሁ ነዉ ይህን ባደፈና በጎሰቆለ ባሕርይና በጉስቁልና ኑሮና ሕይወት መኖርን መርጣችሁ በዐመጻ ሕይወት የምትጸኑትና የኔ ባሪያ መሆንን የምትመርጡት!? እኔን ዲያብሎስን ከጭፍሮቼ ሰይጣናት ጭምር ለማወቅ ከፈለጋችሁ፤ እኛ በዚህች ምድር በጎስቋላ ባሕርይ ተገልጸን እየተቀጣን ቢሆንም የኔን የክፋትና ተንኮል ምክር ሰምታችሁና እኔን መርጣችሁ ከገነት ወደዚህች ወደ እኔና ጭፍሮቼ መቀጫ ቦታ በመግባታችሁ እኛ በረቂቅ አካል እናንተ ደግሞ በግዙፍ አካል እየተቀጣጣን እንገኛለን።

እናንተ በጸሎቱ፣ በጾሙ፣ በስግደቱ፣ በምስጋናዉ፣ በስብከቱ፣ በቅን አሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ አምልኮ ሌት ተቀን ስትቀጠቅጡን እኛ ደግሞ በዚህ ሕይወት ዉስጥ እንዳትመላለሱ ሌት ተቀን በተለያየ መልኩ እንፈታተናችኋለን። በኃጢአት ስትወድቁልን ደግሞ በደንብ አድርገን እንቀጠቅጣችኋለን፤ እናሰቃያችኋለን፤ የተለያየ በሽታና ችግር እናመጣባችኋለን፤ ባጠቃላይ እናጎሳቁላችኋለን። ከዚህ በተጨማሪ ወደ ማንኛዉም የአዳም ዘር ወደ ኅሊናዉ፣ ለእኛ ሰፊ ወንፊት ወደሆነዉ የተለያዩ የሥጋ ብልት፣ ወደ መገጣጠሚያ አካል ክፍል እንገባለን፤ እንወጣለን ።

ስንፈልግ ከመብልና ከመጠጥ ጋር፣ ስንፈልግ ከምትተነፍሱት አየር ጋር፣ ስንፈልግ በቀጥታ እንገባባችኋለን። እናንተን ልንጎዳና ልንሰለጥንባችሁ የምንችለዉ ግን ፈቃዳችንን የምትፈጽሙና የምታስፈጽሙ ከሆነ ነዉ። ከዚያ ዉጭ በራሳችን ስልጣንና ኃይል እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚመላለሱትን ሰዎች መጉዳትና ማጎሳቆል አንችልም።

በግልጽ በተጨባጭ እኛን ማወቅ ከፈለጋችሁ ከኅሊናችሁ ስንወጣ በአፋችሁ በኩል «ኣኣ » ብላችሁ በማዛጋትና በማስፋሽክ እንወጣለን። በአፍንጫችሁ በኩል ደግሚ «እንጥስ» እንድትሉ እያስደረግን በማስነጠስ እንወጣለን። ስንፈልግ ከንፍጣችሁ ጋር እንወጣለን። ከመተንፈሻ አካላችሁ በጉሮሯችሁ በኩል «ሑሁ » ብላችሁ እንድትስሉ በማድረግ እንወጣለን። ስንፈልግ ከአክታ ጋር እንወጣለን። ከሆዳችሁ ዉስጥ የገባነዉ ደግሞ በፊንጢጣችሁ በኩል በፈስ መልክ እንወጣለን። ከመገጣጠሚ አካላችሁ «እህ» ብላችሁ እንድትንጠራሩ አስደርገን እንወጣለን። በቆዳችሁ በኩል ደግሞ በማሳከክ እንወጣለን። ሌሎቻችን ደግሞ ከዐይነምድርና ከሽንታችሁ ጋር እንወጣለን። አንዳንዴ ደግሞ ሳናስበዉ በእግዚአብሔር መንፈስ ተቃጥለን

ምንም ምልክት ሳናሳይ ከጎሊናችሁና ከአካላችሁ ብን ብለን እንወጣለን። ስንፈልግ ደግሞ በራሳችሁ አፍንጫና አፍ ተጠቅመን እናኮራፋለን፤ እንጮሃለን። ታዲያ ይህ ሕይወት ሆነናነዉ ሌት ተቀን የኛ ባሪያና ፈቃድ ፈጻሚ፣ አስፈጻሚ የምትሆኑት? እንደልማዳችሁ ደግሞ እንዲህ በግልጽ ማንነታችንን ስለገለጽንላችሁ የተለያየ ስም አዉጡልና አሏችሁ። ከዘመናዊዉ ስም የምንመርጠዉ «ድብርት፣ ዱካክ፣ ጭንቀት.. ወዘተ » የምትሉትን እንጂ የተለያየ የቫይረስ፣ የባክቴሪያ፣ የጀርም.. ወዘተ የሚል ስያሜ ብትሰጡን ቋንቋችሁ ስለማይገባን እኛ ማንነታችንን አንለዉጥም።

ታዲያ ማንነታችንን በግልጽ ያሳወቅናችሁ ህልዉናችንን እንድታዉቁና የኛ መኖርና በመስቀል ላይ ታላቅ ዋጋ የከፈለላችሁን እዉነተኛ አምላክ መኖሩን እንድታዉቁና እንድታምኑበት እንዲሁም እኛን ረቂቆቹን ይዛችሁ እንድትበቀሉንና እንድታስሩን ሳይሆን፤ በፍርድ ቀን « ይኸዉ የኛን ማንነት እየገለጽንላቸዉ፤ የአንተንም ማንነት እያሳወቅናቸዉ፤ የአዳም ዘሮች ግን «እኛ የምንመርጠዉና ፈቃድህን ለመፈጸም ዝግጁ የሆነዉ አንተን ጨካኙን ጠላታችንን ነዉ። የምንጠላዉና ፈቃዱን ለመፈጸም ፈቃደኞች ያልሆነዉ ደግሞ በመስቀል ላይ የተሰቀለዉን አምላካችንን ነዉ።» በማለት ሳልፈልጋቸዉ እኔን መርጠዉ እለት እለት እኔን በሚያስደስት ሕይወት የሚመላለሱት። ስለዚህ በኔ ላይ የምትፈርደዉን ፍርድ አቅልልኝ። በእነሱ ላይ ግን አብስ።» ብዬ ፍርዳችሁን ላስብስባችሁና የኔንም ፍርድ ለማቅለል በማሰብ ነዉ እንጂ እስከ መጨረሻዉ ማንነቴን ሰዉሬ መጫወቻዬ ባደርጋችሁ ነዉ ምርጫዬ የነበረዉ።

እናንተ ግን እንኳን በፈጣሪያችሁ ዘንድ በኔ የጨለማዉ ገዥ ዘንድ ቀላችሁ አግኝቻችኋለሁ። ምክንያቱም ሌት ተቀን እናንተን ለመፈታተንና ለማጥቃት እንደምተጋና ለዐይን ቅጽበት እንኳ የማልለያችሁ ጠላታችሁ መሆኔን እያወቃችሁ፤ ለዐይን ቅጽበት እንኳ ከጥበቃዉና ከመግቦቱ ከእናንተ ከማይለያዉ አምላካችሁ አስበልጣችሁኝ እኔን ደስ በሚያሰኝ በኃጢአት ሕይወት ዉስጥ በመኖራችሁ ነዉ። በተለይ በግልጥ እኔን የምታመልኩና የኔ ባሪያ ሆናችሁ በወገናችሁ አዳም ዘር ላይ የምትመትቱና የምታስመትቱ፣ የምትጠነቁሉና

የምታስጠነቁሉ፣ ለእናንተ በፍርድ ቀን በገሃነመ እሳት በመንግስቴ ተጨማሪ ቦነስ እንደማሰጣችሁ በዚሁ ቃል እገባላችኋለሁ:: እናንተ የአዳም ዘሮች! እኔ ከህጻን እስከ አዋቂ፣ ከኃጢአተኛ እስከ ቅድስና ማእረግ ከደረሰ ጭምር የምፈታተንና ያማጠቃ፣ ከተሳካልኝም ደግሞ የተመረጡትን ሰዎች ሳይቀር በኃጢአት የምጥል ጨካኝ አረመኔ መሆኔን እያወቃችሁ ምርጫችሁ እኔን ማድረጋችሁ እግጅ አስገራሚ ፍጡሮች መሆናችሁን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ::

እናንተ የአዳም ዘሮች በምድራዊ ሕይወት ቆይታችሁ የምትሰጡት የስም ሹመት ብቻ አይደለም፣ ከሥጋ ሞት በኋላ የሚሰጣችሁ ስያሜ ጭምር ነዉ እኔን የጨለማዉ ገዥን የሚያስገርመኝና የሚያስደንቀኝ::: ይኸዉም ዘመናችሁን ሁሉ የኔን ፈቃድ እየፈጸማችሁና እያስፈጸማችሁ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት፣ በጭከና፣ በግፍ፣ በዘረኝነት፣ በጎጠኝነት፣ በዘፋኝነት፣ በዳንኪርተኛነት፣ በዝሙት፣ በባዕድና ጣዖት አምልኮ .. ወዘተ እየተመላለሳችሁ በማይቀረዉ ሥጋ ሞት ነፍስ ከሥጋዋ ተለይቶ ወደተዘጋጀላት ቦታ (ይግባኝ፣ ይቅርታ፣ ንስሐ የማያባልበትና ዋጋዋን እንደ ዐመጻዋ ደረጃ የምትቀበልበት ቦታ) ተጠርታ ስትሄድ « ሰማዕት፣ ጀግና፣ ንጉሥ፣ ንግስት ..ወዘተ» የመሳሰለት ስያሜ ሲሰጣት ስሰማና በተቃራኒዉ ደግሞ ስለ እዉነት መስክረዉ በእዉነት ኖረዉ እግዚአብሔርን ደስ በሚሰኝበት ሕይወት ተመላልሰዉ ስለ እዉነት ራሳቸዉን ክደዉ በመመስከራቸዉ ምክንያት በዐመጻ ልጆች በግፍና በጭከና ተገለዉ ወደ አምላካቸዉ እቅፍ የሄዱትን እንደ ቅዱሳን መላእክት በቅድስናና በፍጹም ደስታ ሕይወት የኖሩትንና የሚኖሩትን ለታላቅ ክብርና ሽልማት የበቁትንና የሚበቁትን ደግሞ «ዐመጸኞች፣ ከሃዲያን» በማለት ስም ስታወጡላቸዉ በመስማቴና በመመልከቴ ነዉ::» **ይላል ለማንም ፍጡር አንዳች ርኅራኄ የሌለዉ ዋናዉ ዐመጸኛዉና ከሃዲዉ ዲያብሎስ ከጭፍሮቹ ሰይጣናት ጭምር::**

## ምእራፍ ሰባት

« እናንተ በምርጥ እንደራሴዎቼ መሪዎቻችሁና በባለሟል አገልጋዮቼ ባለስልጣናት እንዲሁም በዉዶቼ ካድሬዎች ኀሊናችሁ ተመርዞ ጥላቻና በቀል ተሞልቶ በዘረኝነትና በጎጠኝነት ሕይወት ያላችሁ መልካም ፍሬዎቼ:: በመጀመሪያ አገልጋዮቼን፤ በቶሎ አሳብባችሁ ለፍሬ በማድረሳችሁ በጨለማዉ ስሜ እያመሰገንኳቸዉ እናንተም በዘረኝነትና በጎጠኝነት የተበከለ ኀሊና የያዛችሁ ሰዎች የምጸየፈዉን ስያሜ « ኢትዮጵያዊ ነኝ::» የሚለዉን ንቃችሁና ተጸይፋችሁ የምፈልገዉንና የምወደዉን « እኔ ትግሬ ነኝ:: እኔ ኦሮሞ ነኝ:: እኔ አማራ ነኝ:: እኔ አፋር ነኝ:: እኔ ሱማሌ ነኝ:: እኔ ጋምቤላ ነኝ:: እኔ አኙዋክ ነኝ:: እኔ ቤንሻንጉል ኔኝ:: እኔ ጉሙዝ ነኘ:: እኔ ሐረሪ ነኝ:: እኔ ሃድያ ነኝ:: እኔ ወላይታ ነኝ:: እኔ ሲዳማ ነኝ:: እኔ ከፊቾ ነኝ:: እኔ ስልጤ ነኝ .. ወዘተ» በማለት በጎጣችሁ መጠራትን የመረጣችሁ፤ እንኳን ለዚህ ማዕረግ በቃችሁ እያልኩ፤ በቅርቡ ደግሞ በናፍቆት እየተጠባበቃችሁት ያለዉን የዜግነት ስማችሁን « ትግራዉያን፣ ኦሮሚያዉያን፣ አማራዉያን፣ አፋርያዉያን፣ ሱማሌያዉያን ቁጥር ሁለት፣ ጋምቤላዉያን ፣ አኙዋክያዉያን፣ ቤንሻንጉሊያዉያን፣ ጉሙዝያዉያን፣ ሐረሪያዉያን፣ ሃዲያዉያን፣ ወላይታዉያን፣ ሲዳማዉያን፣ ከፊቾኛዉያን፣ ስልጤያዉያን .. ወዘተ» በማለት በሰማኒያዉ በብሔር ብሔረሰቡ ስም የተለያዩ ነጻ መንግስታትን መስርታችሁ በዜግነት ስማችሁ ስትጠሩ እኛ ሰይጣናት ለማየት ያብቃን፤ የኢትዮጵያዊነት የዜግነት መለያ በዓለም ላይ ተሰርዞ ለማየት ያድላችሁ፤ ታላቁን የኔን የጨለማዉ ገዥና የመሪዎቻችሁን ምኞት ያሳካላችሁ፤ ያሳካልን በአንድ ላይ እንላለን::

ታዲያ አንዳንድ ከእንስሳ መሰል ከጦጣ በቀስ በቀስ ለዉጥና እድገት (በኢቮልሽን) አማካይነት አሁን ላሉበት ስብእና መብቃታቸዉን የማያምኑ ሰዎች፤ « የእግዚአብሔር ፍጥረት የሆን ሕያዋን ፍጥረት በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠርን የእግዚአብሔር ልጆች ነን:: የአዳምና ሔዋን ዘሮች ነን:: የኖኅ ልጆች የካም፣ የሴም፣ የያፌት ዘሮች ነን:: ከሁሉም በላይ ደግሞ የሶስቱ ነገድ ዉህድ የሆነዉ ዘር ኢትዮጵያዊ ነን:: » በማለት

የእግዚአብሔር ሕያዋን ፍጥረቶች መሆናቸዉንና የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ኢትዮጵያዊ መሆናቸዉን የሚመሰክሩትንና የሚናገሩትን አትስሙ:: እነሱ ሐሳብያዉያን ናቸዉ:: እናንተ ግን ቁሳዉያን ተፈጥሮን ልትቆጣጠሩ የደረሳችሁ አዋቂዎችና ምሁራን ናችሁ:: በዚህ የክህደትና የዐመጻ ሕይወታችሁ ከጸናችሁ ጨለማዉ መንግስቴን እንደማወርሳችሁ አንዳች ጥርጣሬ እንዳይገባችሁ::

እናንተ ምርጦቼ እንደራሴዎቼ መሪዎችና ባለሟሎቼ ባለስልጣናት እንዲሁም ዉዶቼ ካድሬዎች «ላለዉ ይጨመርለታል፤ የሌለዉ ያዉ ያለዉ ይወሰድበታል:: » የሚለዉን ቃል ለመፈጸም ሌት ተቀን የምትተጉ አገልጋዮቼ፤ የእለት ኑሮዋቸዉን ለማሸነፍና ለመደጎም በትንንሽ ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተዉ የነበሩትን ምስኪኖች ያተረፉትን ብቻ አይደለም ዋናቸዉን ጭመር እንዲገብሩ አድርጋችሁ ስራቸዉን ያዘጋችሁና ያስመረራችሁ በተቃራኒዉ ደግሞ ሚሊዮነሮችን ባላቸዉ ላይ ገንዘቡንም፣ መሬቱንም፣ ንብረቱን በላይ በላይ እንዲጨመርላቸዉ በማድረግ የፖለቲካ ደጋፊዎቻችሁንና አባሎችሁን ያናጠጣችሁ በመሆኑ ቃሉን በራሳችሁ አተረጓጎም ተግባራዊ አድርጋችኋልና ያለኝን አድናቆት ልገልጽላችሁ እወዳለሁ:: ሌሎቹንም አባባሎች በራሳችሁ እየተረጎማችሁ ለስልጣን ቁጥጥራችሁ ያመቻችሁ ዘንድ «ለባለስልጣናት ታዘዙ፤ ተገዙ::» ተብሏልና ሕዝቡን ኅሊናዉን እንዲሸጥ በማስደረግ «እናንተ ኢትዮጵያዉያን ለሕገ መንግስታችን ብቻ አይደለም ለምንናገረዉ ንግግሮችና አባባሎች ሁሉ ተገዙ፤ ስንሰድባችሁና ስናዋርዳችሁም «አዎን ስድባችሁ ለእኛ ምርቃት ነዉ:: ጭከናችሁም ለእኛ የርኅራኄ መገለጫ ነዉ:: ግፋችሁም ለእኛ የቸረነት ስራ ነዉ::» እንዲሉ አድርጉ::

እናንተ ሕዝቡን በባዶ ተስፋ የምትሞሉ ኅሊናችሁ እዉነቱን እያወቀ የማይሆነዉን ይሆናል፤ የሆነዉን እዉነት እንዳልሆነ፤ ያልተደረገዉን እንደተደረገ አድርጋችሁ የጌቶቻችሁን ገበና በሐሰት ሸፋፍናችሁ በተለያየ መገናኛ ብዙሃን (ማስ ሚድያ) በተለያዩ ሕትመቶች የምታቀርቡ ዘጋቢዎች፤ የእንደራሴዎቼ መሪዎች የባለሟሎቼን ባለስልጣናት ፈቃድ ፈጻሚና አስፈጻሚ በሞሆናችሁ በጨለማዉ ስሜ እያመሰገንኳችሁ ለወደፊት ሕዝቡን « ላም አለኝ በሰማይ ወተቷንም አለይ::» እስከሚል ድረስ በባዶ ተስፋ ኅሊናቸዉን ሞልታችሁ ጌቶቻችሁን

ተስፋ እንዲያደርጉና እንዲያመልኩ አድርጉ:: የጌቶቻችሁን ግፍ፣ ዐመጻ፣ ክህደት፣ በደል፣ አድሎ፣ ርኩሰት፣ ክፋትና ክርፋት ተግባራቸዉን ደግሞ በደንብ አድርጋችሁ ሸፋፍኑ:: በተለይ እዉነተኞችና ንጹሃን «ኅሊናችንን አንሸጥም ከነፈሰዉ ጋር አንነፍስም» ብለዉ ለኅሊናቸዉ የቆሙትንና ስለ እዉነት በሚመሰክሩት ሰዎች ላይ የሐሰት ምስክር አቀነባብራችሁና ማስተባበያ የሚሰጡ ኃላፊዎችን አዘጋጅታችሁ በተለያየ ወንጀል እንዲከሰሱ አድርጉ:: ታዲያ አንዳንድ ተስፈኞች «አንድ ቀን እዉነት ትነግሥና ሐሰትን ታጋልጣለች፤ ታዋርዳለች» በማለት የሚናገሩትን አትስሙ፤ አንዳችም ሥጋት አይግባችሁ:: ከኔ ከጨለማዉ ገዥ እዉቀት ዉጭ በዚህ ዓለም ሌላ እዉቀት የለም:: የሚሆነዉን ሁሉ ስለማዉቅ «እንዲህ ሊፈጠር ይችላል፤ የአሁኖቹ መሪዎች ሆኑ ባለስልጣናት ከወንበራቸዉ ሊቆረጡ ይችላሉ፤ የዘሩትን የዐመጻና የክህደት ፍሬ ሊያጭዱ ይችላሉ» የሚል ስጋት አንዳች አይግባችሁ:: እስከ ሺህ ዘመን ድረስ ትዉልዳቸዉን ብቻ አነግሥላችኋለሁ::

እናንተ ስም አወጣጥና ስያሜ የምታዉቁ አዋቂዎች፤ በዚህ ስም አወጣጣችሁ አድናቆቴንና ሙገሳዬን እገልጽላችኋለሁ:: ይኸዉም አገር በመገንጠል በማስገንጠል እንዲሁም ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን በማስፋፋት የሞቱትን አገልጋዮቼን ጀግኖች «ሰማዕታት፣ ታላቅ ታሪክ ሰሪዎች» እያላችሁ በመሰየማችሁና መታሰቢያም በማድረጋችሁ ነዉ:: በተቃራኒዉ ደግሞ ለአገራቸዉና ለሕዝባቸዉ ታሪክ ሰርተዉ ያለፉትን ኢትዮጵያዉያንን በጥላቻ፣ በቂም በቀልነት ተነሳስታችሁ ስማቸዉን በማጥፋታችሁና መታሰቢያቸዉን በመደምሰሳችሁ ጭምር ነዉ:: ለወደፊቱ ደግሞ ይህን ታላቅ ተግባራችሁን በማጠናከር ለእናት አገራቸዉ ኢትዮጵያ ታሪክ የሰሩትን ብቻ ሳይሆን «ጻድቃን ቅዱሳን » የሚባሉትን ሁሉ መታሰቢያቸዉን ከምድረ ገጽ እንድታጠፉልኝ በጨለማዉ ስሜ አዛችኋለሁ:: በዚህ ድርጊታችሁ ደግሞ የመረጣችሁትን መንግሥቴን አወርሳችኋለሁ::

እናንተ ኢትዮጵያዉያን ተራማጅ ኃይሎች የሶሻሊስት፣ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ፣ የካፒታሊስት የመሳሰሉት እግዚአብሔር የለሽ ስርዐቶች ለመቀበልና አሜሪካዊ፣ አዉሮፓዊ፣ አረባዊ ስርዐት ለመዘርጋት ወደ ኋላ የማትሉና የራሳችሁን ኢትዮጵያዊ ስርዐት ለመዘርጋት

ፈቃደኛ ያልሆናችሁ፤ ስለ ታለቅ አስተሳሰባችሁና ቆራጥነታችሁ እንዲሁም እንደማንነታችሁ ለመኖር አለመፈለጋሁ ያለኝን አድናቆቴን በጨለማዉ ስሜ እያቀረብኩ፤ ለወደፊትም በምንም መልኩ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራዉን ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተ ክህነቱ፣ ቤተ መንግስቱ በአንድ የሚመራበትን የእግዚአብሔር መንግስት ስርዐት እንዳትዘረጉ:: የምትዘረጉ ከሆነ ግን ከኔ ምድራዊ መንግስት የምትለዩና ያጎናጸፍኳችሁን ርኩሰት፣ ዐመጻ፣ ክህደት የምትፈጽሙበትን ዴሞክራሲ መብታችሁን አሳጣችኋለዉ:: ከክፋት፣ ከተንኮል፣ ከምቀኝነት ፣ ከትዕቢት፣ ከዝሙት፣ ከባዕድ አምልኮ፣ ከዘፋኝነት ፣ ከዳንኪርተኛነት ፣ ከአመንዝራነት ፣ ከጥላቻና ከጥል፣ ከቂምና ከበቀል፣ ከበደልና ከአድሎ፣ ከስግብግብነትና ከስስት፣ ከራስ ወዳድነት፣ ባጠቃላይ በዚህች አገር ካነገሣችሁት ከኔ ታላቅ ስራ እለያችኋለሁ:: ስለዚህ ከነዚህ መልካም ፍሬ እንዳትለዩ የጨለማ ስርዐቴን ለመጠበቅ ታጥቃችሁ እንድትነሱ በዚህ አጋጣሚ አሳስባችኋለሁ::

እናንተ በተለየዩ መገናኛ ብዙሃን በሆኑት በንፋስ ስዕል(ቴሌቭዥን)፣ በንፋስ ድምጽ(በሬድዮን)፣ በጦማረ ሕዝብ(በጋዜጣ)፣ በመጽሔት፣ በመጽሐፍ፣ በድኅረ ገጽ (በኢንተርኔት) በመሳሰሉት የጊዜ ማባከኛና ማጥፊያ ወሬና የተለያዩ ማደንዘዣ ትዕይንቶች እንዲሁም ርኩሰት የተሞሉ ፊልሞች የምታስተላልፉና ትዉልዱም ሌት ተቀን ስለ ዘፈን፣ ስለዳንኪራ፣ ስለአገዳደል፣ ስለ አደባደብ፣ ስለዝሙት፣ ስለስርቆት ስለመሳሰሉት ተግባር እንዲያስብ በማድረጋችሁ በጨለማዉ ስሜ ምስጋና እቸራችኋለሁ:: ከዚህ በተጨማሪ ሕዝቡን ለጦርነት፣ ለጥላቻ፣ ለበቀል፣ ለግድያ፣ ለዐመጽ፣ ለክህደት፣ ለርኩሰት በማነሳሳታችሁ እንዲሁም የክህደትና የመናፍቅነት እምነት እንዲስፋፋ፤ የክህደት ፍልስፍና እንዲነግሥ በማድረጋችሁ ስለ መልካም አገልግሎታችሁ በድጋሜ በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችኋለሁ::

በተለይ በዚህ መልኩ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባርና ንግግር እንዲተላለፍ ላደረጋችሁ ታላላቅና ለአናሳ መንግስታቶቼ መሪዎችና ባለስልጣናት እንዲሁም እንደማዕረጋችሁ ለካድሬዎቼ በጨላማዉ ስሜ ደግሜ ደጋግሜ አመሰግናችኋለሁ:: በዚሁ

አጋጣሚ እነዚህ መገናኛ ብዙኃን ዋናዉ መሳሪያዬና በቀላሉ ተግባሬና ንግግሬን የማስተላልፍበት፣ ቅስቀሳ የማደርግበት፣ ጥሩ ዉጤት ያስገኘልኝ በመሆኑ ይህን ታላቅ መሳሪያ በምንም መልኩ ለማይታወቀዉ «መንግስተ ሰማያት» ለሚባለዉ ዓለም አገልግሎት እንዳይሰጥበት እያስጠነቀኩ እዉነታ የሚባል ነገር ቢተላለፍበት ከወንበራችሁ የምቆርጣችሁና ከአገልግሎቴም የምሽራችሁ መሆኔን እግልጽላችኋለሁ።

ስለዚህ ለሥጋችሁ ሆነ ለነፍሳችሁ የሚጠቅም ነገር ብታስተላልፉበትና ሕዝቡ ተስፋዉን ሰማያዊ አድርጎ መኖር ቢጀምር፣ ጦርነት ቢቆም፣ ርኩሰት ባይታይበት፣ ሕይወት የሆነዉና የእርካታ የደስታ ምንጭ የሆነዉ ኮንደም ሰንሴሽን ባይተዋወቅበት፣ ሰዎች ለበቅልና ለጥላቻ እንዲነሳሱበት ባይደግበት፤ ክፋት፣ ተንኮል፣ ዐመጻ፣ ክህደት ባይስፋፋበት፤ ዘፈንና ዳንኪራ ባይታይበት፣ ጊዜ ማባከኛና ማጥፊያ እንዲሁም የጎሊና ማደንዘዣ ወሬና ትዕይንቶች ባይተላለፍበት፣ ባጠቃላይ ሐሰት ባይነግሥበትና ለእዉነት ቦታ ከተሰጠዉ፤ በሕገ መንግስቴ አዋጅ መሰረት በዐመጻና በክህደት፣ በወንጀል የምጠይቃችሁና ከመንግስቴም የምሽራችሁና በመንግስቴም የማላኖራችሁ መሆኑን ከወዲሁ እንድታዉቁ አቋሜን እነግራችኋለሁ። በተቃራኒዉ ደግሞ ለመንግስታቶቼ ታማኝ አገልጋይ ሆናችሁ የሐሰት ዘገባና እዉነተኞቹን በሐሰት መረጃ በመወንጀል ለዓለም የምታሳጡ ጋዜጠኞች በወደፊቱ መንግስቴ መገናኛ ብዙኃን ዘርፍ በሚንስትርነትና በከፍተኛ ባልስጣንነት ማዕረግ እንደምሾማችሁ ቃል እገባላችኋለሁ።

በተለይ እናንተ ኢትዮጵያዉያን አድናቆቴን ልቸራችሁ እወዳለዉ። ምክንያቱም የራሱን ታሪክና ማንነት በራሱ አንደበት የሚያጥላላና የሚደመስስ፤ የአገሪቱና የሕዝቡ ጥፋትን የሚፈልጉ ግለሰቦችና ቡድኖች የጻፉትን የክህደትና የሐሰት የፈጠራ ታሪክ ወደ እዉነትነት ለዉጦ አገሩንና ሕዝቡን ለማጥፋት የተሰለፈ የራስ መንግስትና የራስ አገልጋይ

በዓለም ላይ እስከአሁን ድረስ ባለማየቴ ነዉ፡፡ ይልቁኑ ሌላዉ ዓለም የሌለዉን ታሪክ እንኳ እየፈጠረ ማንነቱን ከፍ ከፍ የሚያደርግና የሚያገን ሆኖ ስመለከት እናንተ ደግሞ ማንነታችሁን እያጠፋችሁ እንቁ ታሪካቸሁን፣ እምነታችሁን፣ ባህላችሁን ደብቃችሁና አጥፍታችሁ፤ የሌሎች አገራትን የሐሰት ታሪክ፣ የክህደት እምነት፣ የርኩሰት ባህል እያሳያችሁና እያስፋፋችሁ በመሆኑ የአድናቆት አድናቆቴን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ለዓለም ሕዝብን «እናንተ የዓለም ሕዝቦች ሆይ! እናንተ ብቻ አይደላችሁም ያበዳችሁትና የእብደታችሁ መገለጫ የሆነዉን ቀድሞ በየጣዖቱና ባዕድ አምልኮ ቦታ እንዲሁም በየዛሩ፣ በየጥንቆላዉ ቦታ በግልጽና በድብቅ የሚቀርበዉን የዛርና የእብደት ትዕይንት የሆነዉን ማጓራቱን፣ መንዘፍዘፉን፣ መንቀጥቀጡን፣ መዝለፍለፉን፣ መንፈራገጡን፣ መሸከርከሩን፣ መዝለሉን፣ ጎንበስ ቀና ማለቱን፣ መዘረሩን ባጠቃላይ ከሰዉነት ባሕርይ ለይቶ ወደ ጨለማዉ ገዥ ባሕርይ የሚያስለዉጣችሁን፤ በዘመናዊ መልክ በመሳሪያ አጅበን ይኸዉ ከሰማንያ በላይ የብሔር ብሔረሰባችን ማንነት መገለጫ የሆነዉን ዘፈናችንና ዳንኪራችንን፣ ጭፈራችንን ተመልከቱ፤ ማንነታችንንም እወቁ፤ በዚህ ተግባራችን ከእናንተ በምንም መልኩ አንተናነስም፤ ማንነታችን ይህን ይመስላል፡፡ » በማለት ራሳችሁን ማስተዋወቃችሁና ከኔ መንፈስ ተቃራኒ የሆነዉ መንፈስ ያዘጋጀዉን ለእግዚአብሔር የሚቀርበዉን ምስጋና ዝማሬ፣ ሽብሸባ «የገዢ መደቦች የፈጠሩት ነዉ፤ ኋላ ቀር ነዉ፡፡» ብላችሁ ከማንነታችሁ መገለጫነት በመሰረዛችሁ አድናቆቴን ከፍ ያደርገዋል፡፡

ባጠቃላይ የእንደራሴዎቼ መሪዎቻችሁንና የባለሟሎቼ ባልስልጣትን ፈለግ ተከትላችሁና አገልጋይ ሆናችሁ እዉነተኛ ታሪካችሁን፣ ማንነታችሁን ደምስሳችሁ ዓለም ለእናንተ ያወጣለችሁን ታላቅ ስም ረሀብተኛነት፣ ድህነት፣ ለማኝነት፣ ተመጽዋችነት፣ ጦረኝነት፣ ስደተኝነት፣ ችግርተኝነት፣ የሚበላዉና የሚጠጣዉ የሌለዉ፣ አዉሬ፣ በጣዖትና

ባዕድ አምልኮ የሚመላለስ ሕዝብ፣ የመሳሰሉትን ስያሜ ለብሳችሁ፤ ታቅፋችሁ፤ አጥልቃችሁ፤ ተንተርሳችሁ፤ ማንነታችሁን በመቅበር ሌት ተቀን የኔ የጨለማዉን ገዢ ፈቃድ ፈጻሚና አስፈጻሚ በመሆናችሁ የኔን ኒሻን ሽልማት ባበረክትላችሁ ደስ ባለኝ።

አደራ የምላችሁ በነፍሳችሁ ስሜት ተመርታችሁ የማንነታችሁ መገለጫ የሆኑትን ታሪክ፣ እምነት፣ ስርዐት፣ ባህል ለዓለም ብታስተዋዉቁ እንቆራረጣለን። ምክንያቱም የነፍሳችሁን ስሜት ለመቆጣጠርና እንደፈለኩት ለማሽከርከር ይከብደኛልና በዚህም ምክንያት ፍላጎታችሁን ማሟላት ስለማይቻለኝ ነዉ። ነገር ግን በደመ ነፍሳችሁ የምትመሩ ከሆነ ለኔ እንደልቤ ስለምትሆኑልኝና እንምርጫችሁና ፍላጎታችሁ እስከ እብድነትና እራቁትነት ማዕረግ አደርሳችኋለሁ። የተለያዩ ጸጋዬን አድዬ ለታላቁ ጨለማዉ መንግስቴ አበቃችኋለሁ።

እዚህ ላይ ብዙ መስራት ሲጠበቅባችሁ ያላከናወናችሁትን በዚሁ አጋጣሚ ላስዉቃችሁ እወዳለሁ።ይኸዉም የግንቦት ሃያ ፍሬ የሆነዉ ሕገ መንግስታችሁ የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከመገንጠል ድረስ በዳንኪራና በጭፈራ የታወጀዉን ተግባራዊ አለማስደረጋችሁና ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታቶቼን እስከ አሁን ድረስ በፌደራል መንግስቴ ለሃያ ዓመት በሞግዚትነት እንዲተዳደሩ በማድረጋችሁ ነዉ። በዚህም ምክንያት የክልላት መንግስታቶቼ በፌደራል መንግስት በደልና ግፍ ተፈጽሞባቸዋል። ነጻ መንግስትነታቸዉን አዉጃዉ አምልኮታቸዉን በነጻነት እንዳያመልኩ ተደርገዋል። የማንነታቸዉ መገለጫ የሆነዉ ቋንቋቸዉና ባህላቸዉ በመጤዎች ተበርዟል። አንዱ ብሔረሰብ ከአንዱ ብሔረስብ ተጋብቷል፤ ተዋህዷል፤ ወዳጅነትና ጉርብትና ፈጥራል፤ በአንድነትና በህብረት እየኖሩ ይገኛል። ይህ ደግሞ ለሕገ መንግስቴና ለህልዉናዬ አደጋ ስለሆነ አስፈላጊዉን መስዋዕት ልትከፍሉ ይገባችኋል።

ስለዚህ በአምስቱ ዓመት  የእድገትና ትራኒስፎርሜሽን ዓመት ዉስጥ ተገነጣጥለዉ የራሳቸዉን ነጻ መንግስት ሊመሰርቱና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የሚለዉን ስም ከምድረ ገጽ ልታጠፉ ይገባችኋል፡፡ የኔን ትዕዛዝ በቀላሉ እንድትፈጽሙ፣ እንድታስፈጽሙ እንዲሁም በነጻነት እንድታመልኩኝ የኔ መንፈስ የማይወደዉና የማይቀበለዉን «የቅዱሱ ኪዳን» ሕዝብ እንድታጠፉልኝና በአጭር ጊዜ ዉስጥ ኦሮሚያ አገርና ኦሮሚያዉያን ዜጎችን፣ ትግሪያ አገርና ትግራዉያን ዜጎችን፣ አማሪያ አገርና አማራዉያን ዜጎችን፣ ሱማሊያ2 አገርና ሱማሊያዉያን ዜጎችን፣ አፋሪያ አገርና አፋራዉያን ዜጎችን፣   ሐረሪያ አገርንና ሐረሪያዉያን ዜጎችን፣ ጋምቤሊያ አገርና ጋምቤላዉያን ዜጎችን፣ ቤንሻንሊያ አገርና ቤንሻንጉሊያዉያን ዜጎችን፣ ጉሙዚያ አገራና ጉሙዚያዉያን ዜጎችን፣ ሲዳሚያ አገርና ሲዳማዉያን ዜጎችን፣ ስልጢያ አገራና ስልጤዉያንን  ዜጎችን፣ ሃዲዩያ አገርና ሃዲዩያዉያን ዜጎችን፣ ወላይቲዩያ አገርና ወላይታዉያን ዜጎችን፣ አገዊያ አገርና አገዉያዉያን ዜጎችን፣ ኩነሚያ አገርና ኩነማዉያን ዜጎችን.. ወዘተ ሰማንያ የብሔር ብሔረሰቦች ነጻ መንግስታትና አገራት መስርታችሁ እንድታሳዩኝ አስጠነቅቃችኋለሁ፡፡ እዚህ ላይ ላስታዉሳችሁ የምፈልገዉ ብሔር ብሔረሰቦች፣ ነፍጠኞች የመሳሰሉትን ስያሜዎች የምደጋግማቸዉ፤ ተጠብቤ ያወጣዋቸዉ ቋንቋዬ ስለሆኑና ታላላቅ ተግባራትን ያስፈጸምኩበት ባለዉለተኛዬ መጠሪያ ስለሆኑ ነዉ እንጂ፤ እናንተም ደስ ስለሚሏችሁ በናፍቆት  ከኔ በላይ በየቀኑ እንደ አቡነ ዘበሰማያት እንደምትደግሟቸዉ ጠፍቶኝ አይደለም፡፡

እናንተ በትዉልዳችሁና በዜግነታችሁ ኢትዮጵያዉያን ሆናችሁ ሳላ አገራችሁ በመጥፎ ስትነሳ፣ ስሟ ሳይቀር ከመጽሐፍ ቅዱስ ሲደመሰስና ሲለወጥ ደስ የሚላችሁ በመናፍቅነትና በክህደት እምነት ኅሊናችሁ የተመረዘና የኢትዮጵያዊነት ጥላቻ በዉስጣችሁ የነገሠ እንደፍላጎቴና ምኞቴ የሆናችሁ ምርጦቼ፤ እናንተንም በተለየ ሁኔታ ላደንቃችሁና በአቋማችሁ እስከመጨረሻዉ ጸንታችሁ ኢትዮጵያዊነትና ተዋህዶ ሃይማኖትን ለማጥፋት እንድትተጉ

አሳስባችኋለሁ:: ይህን የምታደርጉት ለሃይማኖታችሁ ለሃይማኖቴ ቀንታችሁ በመሆኑ የምላችሁን ሁሉ ተግባራዊ ካደረጋችሁ እንደ ሰማዕት ቆጥሬያችሁ ለታላቁ ጨለማዉ መንግስቴ አበቃችኋለሁ::

እናንተ የአገራችሁና የስራችሁ መመሪያ አድርጋችሁ አነስተኛ ገቢ ያላቸዉን አይደለም መካከለኛ ገቢ ያላቸዉን ሳይቀር የቦታና የቤት ባለቤት እንዳይሆኑ የሚያደርግ፤ ሀብታሞች ብቻ በቤት ላይ ቤት፣ በቦታ ላይ ቦታ እንዲኖራቸዉ፤ ደሀዉ እንዲፈናቀል፣ እንዲከራተት፣ በየመንገዱ እንዲወድቅ፣ በልመናና በጉስቁልና ኑሮ እንዲኖር የምታደርጉ፤ የታላላቅና የአናሳ መንግስታቴ እንደራሴዎች የሆናችሁ መሪዎችና ባለስልጣናት፤ በመጀመሪያ ደረጃ የመመሪያችሁ መንፈስ «ከራስ በላይ ንፋስ» በሚለዉ መርህ የምትመሩና የምትመሩ በመሆኑ ከፍተኛ አድናቆቴን እገልጽላችኋለሁ:: መቼስ ይህን ሁሉ የምታደርጉት ለራሳችሁ የምትበሉት፣ የምትጠጡት፣ የምትጠለሉበት፣ የምትጠጉበት በማጣታችሁ ስለሆነ ፈጣሪያችሁም በስራችሁ ቅር እንደማይሰኝ እገምታላሁ::

በኔ ዘንድ ግን ሊያስጠይቃችሁ የሚችለዉ እናንተ እንዲህ እየተቸገራችሁ፣ እየተራባችሁ፣ እየተጠማችሁ፣ እየታረዛችሁ፣ መጠለያና መጠጊያ እያጣችሁ፣ እየተጎሳቆላችሁ፣ ብርድና ሙቀቱ፣ ዝናብና ፀሐዩ እየተፈራረቀባችሁ በየመንገዱና በየጥጋጥጉ የወደቁትን፣ ዘመድ ወገን ጠያቂ አተዉ በየቤታቸዉ የተዘጋባቸዉን፣ እንኳን ቦታና መኖሪያ ቤት ሊኖራቸዉ ቀርቶ የእለት ጉርሳቸዉን ለማግኘት ሌትና ቀን የሚንከራተቱትን ፣ ገቢያቸዉ አልበቃ ብሏቸዉ ቁርስና እራታቸዉን እየዘለሉ በምሳ ብቻ የሚዉሉ የሚያድሩትን ፣ ህጻናት ልጆቻቸዉን ማስተማር አቅቷቸዉ በቤታቸዉ አስረዉ ያሉትን፣ እምቢ ብለዉ ትምህርት ቤት የሚሄዱትንና በጠኔ ተቸግረዉ በመቀመጫቸዉ የሚወድቁትንና መማር ተስኗቸዉ በመምህራንና በበጎ አድራጊዎች እርዳታ ትምህርታቸዉን የሚማሩትን፣ ባጠቃላይ በጉስቁልና ሕይወት የሚኖሩትን ሰዎች ብትረዱ፤ ብታበሉ፤ ብታጠጡ፤ ብታላብሱ፤ መጠለያ ብትሰጡ፤ የቤትና የቦታ ባለቤት ብታደርጉ፤ ባጠቃላይ እንደእናንተ ብታደርጉ ነዉ እንጂ፤ አሁን ባላችሁ ራስወዳድነት፣ ስግብግብነት፣ አድሎና በደል በተሞላዉ ሕይወት በቅንጦት፣ በድሎት ሕይወት ብትኖሩ አንዳች በኔ በኩል አልጠይቃችሁም:: የሚጠይካችሁ አካል ካለ ግን

በኔ በኩል ዋስትና ልገባላችሁ የሚያስቸግረኝ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ እየገለጽላችኋለሁ:: ነገር ግን የጦር መሳሪያና የሰላ ምላሳችሁ ዋስትናችሁ እንዲሆን ጨለማዉ ምክሬን እመክራችኋለዉ::

እናንተ ኑሮዋችሁን በብልጠጥ የምትመሩ፤ ሌላዉ ወገናችሁ አድሎና በደል ሲፈጸምበት፤ ሲገፋ፣ ሲገፈተር፣ ግፍና ጭከና ሲፈጸምበት፣ ሲቸገር፣ ሲጎሳቆል፤« በእኔ ላይ እስካልደረሱ፤ እኔም እንደልቤ እንድሆን ፣ እንዲመቸኝ፣ እንድዝናና፣ እንድጨፍር፣ እንድሰክር ፣ እንድዘሙት፣ እንድሳደብ፣ እንድመጻደቅ፣ እንድታበይ፣ እንድመካ፣ እንድጠቀም ካደረጉ፤ ከራስ በላይ ንፋስ ነዉና እንደፈለጉት ቢሆኑ «አንዳች ትንፍሽ አልልም፤» በማለት የጌቶቻችሁን ፈለግ የተከተላችሁ ምርጦቼ ሰዎች፤ መንግስተ ሰማያትንም እንደዚሁ በብልጠት ሕይወት ትገቡበታላችሁና እንደፈለጋችሁት ሕይወታችሁንና ኑሮዋችሁን እንድትመሩ አሳስባችኋለሁ::

ታዲያ በኔ መንግስት ዉስጥ የመግባት እድል ቢያጋጥማችሁ በዚሁ ሕይወታችሁ ብቃት ደረጃ እንደምሾማችሁና እንደምሸልማችሁ አዉቃችሁ ለወገናችሁ ለአዳም ዘር አንዳች ርኅራኄ እንዳታሳዩ፤ አንዳች ጥብቅና እንዳትቆሙላቸዉ:: የኔ የጨለማዉ ገዢ መመሪያ እንደዚህ አይነት ስለሆነ ለተግባራዊነቱ ተባባሪ እንድትሆኑ በዚሁ አጋጣሚ ላሳስባችሁ እወዳለሁ::

እናንተ የርኩሰቱን ተግባር በግልጽ በተለያዩ ፊልሞች ለአዳም ዘር እንዲታይ የምታስደርጉና እናንተም በግልጽና በድብቅ የምትመለከቱና የምትፈጽሙ ምድራዊያን እንደራሴዎቼ መሪዎችና ባለሟሎቼ ባለስልጣናት፣ እንዲሁም በርኩሰቱ ተግባር የተሰማራችሁ የፊልሙ ተዋናዮች አገልጋዮቼ ሰዎች፤ በመጀመሪያ ደረጃ ትዉልዱ ኅሊናዉ የሚመረዝበትን ፣ የሚረክስበትን ፣ የሚደነዝዝበትን ትዕይንት በማሳየታችሁና በማበረታታችሁ በአርካሹ፣ በአዘሚቹ፣ በአሴሳኙ ጨለማ ስሜ አመሰግናችኋለሁ:: ወደ ልባችሁ ተመልሳችሁ ርኩሰት ተግባራችሁንና የርኩሰት ስራ አስፈጻሚ መሆናችሁን እንዳታስተዉሉ ታላቅ ምኞቴን በዚሁ አጋጣሚ እገልጽላችኋለሁ::

እናንተ በተለያየ ሱስ በሲጃራዉ፣ በጫቱ፣ በአደንዛዥ ዕፁ፣ በመሳሰሉት ተጠምዳችሁ ራሳችሁን መግዛት አቅቷችሁ « ሕዝብን እንመራለን፤ እናስተዳድራለን ፤ ራስን በመግዛት መልካም ተግባር እንዲፈጸም እናደርጋለን፡፡» የምትሉ የአገራት መሪዎችና ባለስልጣኖች፤ ስለ ታላቅ አስተሳሰባችሁ ሙገሳዬን እየገለጽኩላችሁ፤ ራሳችሁን መግዛት ተስኗችሁ ከተለያየ ሱስ ሊያላቅቃችሁ የሚችል መካሪ  መሪ የሚያስፈልጋችሁ ሆኖ ሳለ፤ እናንተ ግን ከቀላሉ ሱስ ለዚያዉም ራሳችሁን ከሚጎዳና ከሚያዋርድ መላቀቅና ሰሜታችሁን መቆጣጠር ሳትችሉ የኔን ታላቅ ፈተና ተቋቁማችሁ እንዴት ላለመግደል፣ ላለመስረቅ፣ ላለመበደል፣ ላለመዘሞት፣ ግፍንና በደልን ላለመፈጸም፣ ባዕድና ጣዖትን ላለማምለክ፣ እዉነተኞችን ላለማሳሰርና ላለማሳደድ፣ ክፋትና ተንኮል ቂምና በቀልን ላለመፈጸም፣ ባጠቃላይ የኔ ፈቃድን ላለመፈጸም ምን ዋስትና አላችሁ!?

ዋስትና የሚሆናችሁን አምላክ ክዳችሁ እኔ በኅሊናችሁ የማመጣዉን ቀላሉን የማስጨነቅና የማድከም ፈተና ለመቋቋም የተለያዩ ምሶቼን ሱሱን በየጊዜዉና በየቀኑ የምትገብሩልኝ ከሆነ፤ የሰዉ ደም እንድታቀርቡ ፈተና ባመጣባችሁ የምታቀርቡልኝ መሆኑን ኅሊናችሁ እያወቀ በወንበር ላይ ተቀምጣችሁ «እዉነተኛ አገልግሎትና ፍርድ እንሰጣለን» ማለታችሁ ለራሴም ስላስገረመኝ ነዉ ገበናችሁን ለዓለም የገለጽኩት እንጂ፤ ከክፉ ተግባራችሁ ተከልከሉ፣ አታጭሱ፣ አትቃሙ፣ አደንዛዥ ዕፆችን በተለያየ መልኩ አትዉስዱ፣ ደም አትገብሩልኝ፣ ከባዕድና ከጣዖት አምልኮ ተለዩ ፣ እግዚአብሔር የለም የሚለዉን ፈልስፍናችሁን ተዉ፣ እንደ ልቤ ከመሆን ተከልከሉ ለማለት ፈልጌ እንደልሆነ የሚገባችሁ ይመስለኛል፡፡  ይልቁኑ በሚበላዉ፣ በሚጠጣዉ፣ በሚቃመዉ፣ በሚጨሰዉ፣ በሚወጋዉ፣ በሚሸተተዉ፣ በሚቀባዉ ሁሉ ኅሊናችሁን አደንዝዛችሁ፡፡ «አድርጉ፣ ፈጽሙ» የምላችሁን ሁሉ እንድታስፈጽሙልኝ ነዉ የእኔ የጨለማዉ ገዥ የመሪያችሁ ጥረትና ፍላጎት፡፡» **ይላል አምታታዉና አታላዩ መንፈስ ዲያብሎስ፡፡**

# ምእራፍ ስምንት

« እናንተ ኢትዮጵያን፤ ወደ አሜሪካንና አዉሮፓ እንዲሁም ኤሽያና  አረብ አገራት መሄድ ገነትና መንግስተ ሰማያት መግባት አድርጋችሁ የምትቆጥሩና ከዚያም የመጣ ከገነት እንደመጣ አድርጋችሁ የምትቆጥሩና የምታዩ ለስደት ልባችሁ የቋመጠ ሰዎች፤ በመጀመሪያ መለስተኛዉ ሲያል የሆኑ አገራቴን እንደ ገነትና መንግስተ ሰማያት በመቁጠራችሁ በጨለማዉ ስሜ እያመሰገንኩኝ፤ በተቻላችሁ መንገድ በእግርም፣ በፈረስም፣ በግመልም፣ በመኪናም፣ በባቡርም፣ በመርከብም፣ በአይሮፕላንም፣..ወዘተ በመሳሰሉት ወደ መንግስታቶቼ ለመግባታ ታላቅ ተጋድሎ አድርጉ:: የዋናዉ ሲያል ኑሮ እንዲቀልላችሁ በመለስተኛዉ ሲያል ልምምድ ብታደርጉ ይሻላችኋልና ደንቡንና ሰርዐቱን በመከተል ርኩሰቱ በነገሠባቸዉ አገራት የሚፈጸመዉን ርኩሰት ተግባር ሆነ ድርጊት በአግባቡ እንድትፈጽሙ በዚሁ አሳስባችኋለሁ::

ታዲያ እዛ ቆይተዉ የመጡትን እዉነተኛ ኢትዮጵያዉያንን ስለ ኑሮና ሕይወታቸዉ እንዳትጠይቁ:: ምክንያቱም እዛ ሄዳችሁ የገነትና የመንግስተ ሰማያትን ኑሮ እንዳትኖሩ እያማረሩና እያጥላሉ ይናገሯችኋልና:: ይልቁኑ እዚህ ሲያል አገራችሁ ዉስጥ ያገኛችሁትን እየሰራችሁ እንድትኖሩ ይመክሯችኋል:: እኔ ግን እዉነቱን እነግራችኋለሁ:: በኔ ግዛቶች የፈለጋችሁትን ርኩሰት ተግባር እንድትፈጽሙ ሙሉ ዴሞክራሲ አጎናጽፋችኋለሁ፤ ልቅ ወሲብ ሆነ ገብረሰዶም ጭምር በነጻነት እንድትፈጽሙ ሙሉ መብታችሁን አስከብርላችኋለሁ:: ጥቃት ሆነ ጉዳት እንዳይደርስባችሁ ሙሉ ዋስትና እሰጣችኋለሁ:: እንደ ኢትዮጵያዊነታችሁ እንድትከበሩ አደርጋለሁ:: እንደ አዋቂና ጀግና እንድትታዩ ሞገስን እሰጣችኋለሁ:: በሄዳችሁበት ሁሉ ጌታና አዛዥ አደርጋችኋለሁ::

እናንተ ኢትዮጵያዉያን የስራ ባህላችሁ አስደሳች የሆነ ዳተኝነት፣ ስንፍና፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ ስርቆት የተሞላዉና በዚህ የስራ ጠባያችሁ ከቀጠላችሁ ከበለጸጉት አገሮች ተርታ እንደምትሰለፉና ለዓለምም እንደምትተርፉ ያለኝን ታላቅ ተስፋ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ:: ታዲያ ከሌላ አገር የመጡ ዜጎች የሕንጻዉ፣ የመንገዱ፣ የፋብሪካዉ፣ የተለያዩ አገልግሎት አዉታሮች ግንባታ ላይ በንቃት፣ በትጋት፣ በታማኝነት፣ በቆራጥነት፣ በቅንነትና በእዉነት ፣

ስንፍናን አርቀዉ የሚሰሩ ሰዎችን እንዳትመለከቱ:: እነሱ የስንፍና፣ የምቀኝነት ፣ የስርቆት፣ የዳተኝነት፣ የጠማማነት፣ የክፋት ምስጢር ስላልገባቸዉና ምርጫቸዉ ድህነት፣ ለማኝነት ፣ ችግረኛነት፣ ተረጂነት ስለሆነ ነዉ::

እናንተ አፋችሁ ላይ እንደመጣላችሁ ለመናገርና ለመሳደብ ወደ ኋላ የማትሉ ደፋሮችና አንደበታችሁ አንደበቴ የሆነ፤ በኔ ዘንድ ሞገስ ማግኘታችሁን እየገለጽኩላችሁ የድንፋታና የስድብ ንግግራችሁን እለት እለት እያሻሻላችሁ የሰዉ ጆሮ ጭዉ የሚያደርግ፣ ጋጠወጥ የሆነ፣ ቅኖችንና እዉነተኞችን የሚያዋርድ በማድረግ የተያዘላችሁን ደረጃ እንድታሻሽሉ እመክራችኋለሁ::

እናንተ ስልጣናችሁን፣ ክብራችሁን፣ ጥቅማችሁን፣ ዝናችሁን በብልጠት ለቀጣይ ትዉልዳችሁ ለማስተላለፍ ሌት ተቀን የምትተጉ፤ ሰዎችን ለማጥመድና ወደ ገደል ለመወርወር ነገር የምትሸርቡ፣ በሐሰት የምትወነጅሉ፣ ይህ ብልጣብልጥነታችሁ ተሐድሶ ያስፈልገዋልና ጠንከር ያለ የጭካኔና የግፍ ተግባር ብትጨምሩ ፍላጎታችሁንና ምኞታችሁን በቀላሉ ማሳካት እንደምትችሉ እኔ የጨለማዉ ገዥ አረጋግጥላችኋለሁ::

ታድያ አንዳንድ መሃይሞችና ኋላ ቀር ሰዎች « እግዚአብሔር ሁሉን ይመለከታል፣ ለሁሉ እንደስራዉ ይፈርድለታል፣ ይፈርድበታል::» በማለት የሚናገሩትን አትስሙ:: እነሱ ገና ከክሮማግነንና ከኒያንደርታ እድገት ወደ ዘመናዊዉ ሰዉ እድገት ያልደረሱ ናቸዉ:: በዚህች ምድር ዉስጥ ስራችሁን፣ ንግግራችሁን፣ አሳባችሁን ሁሉ እንድከታተልና እንድቆጣጠር የተሾምኩ እኔ የግብር አባታችሁ ዲያብሎስ ስለሆንኩ በተግባራችሁ ሆነ በንግግራችሁ እንዲሁም በአሳባችሁ አንዳች ፍርሐት እንይግባችሁ:: ከኔ ዉጭ ማንም አይከሳችሁም:: አያስፈርድባችሁም:: ይልቁኑ የምላችሁን በሚገባ ተግባራዊ ካላደረጋችሁና ታማኝነታችሁን ሁል ጊዜ በክፋት፣ በተንኮልና በምቀኝነት ተግባር ካለረጋገጣችሁልኝ፤ ያላደረጋችሁትን ሁሉ እንዳደረጋችሁ አድርጌ በማሳበቅ አስፈርድባችኋለሁ :: በሐሰት ወንጅዬ አስኮንናችኋለሁ:: ስለዚህ በተግባራችሁ፣ በንግግራችሁ፣ በአሳባችሁ እኔን ብቻ እንድትፈሩ እንጂ ሌላ ፍጡር ሆነ ፈጣሪ ይመለከታል፣ ይሰማል ብላችሁ አንዳች እንዳትፈሩ::

እናንተ ቂመኞች የሆናችሁና ይቅርታ የጠየቃችሁን ሰዉ ይቅር የማትሉ፤ ብትሉም ለማስመሰል እንጂ ከልባችሁ «ይቅር ለእግዚአብሔር» ብላችሁ እዉነተኛ ሰላምንና ፍቅርን ለመመስረት የማትፈልጉ፣ በኔ አርአያና ምሳሌ የምትመላለሱ፣ ዉስጣችሁ ትዕቢትና ዐመጻ የሞላባችሁ፣ ወርቃማ ጠባያችሁንና ባሕርያችሁን እያደነኩ ሌሎች ወገኖቻችሁንም እናንተን አርአያና ምስሌ አድርገዉ እንዲከተሉና ለጨለማዉ መንግስቴ ብቁ እንድተደርጓቸዉ አሳስባችኋለሁ::

ታድያ አንዳንዴ ያልሆነዉንና ያልተባለዉን ነገር በኅሊናችሁ ስነግራችሁ እንደዉሸት ቆጥራችሁ የሰይጣን ንግግርና አሳብ ነዉ ብላች ወርቃማ ንግግሮቼን እንዳታቃልሉ:: እናንተዉ ናችሁ የምትጎዱት :: ይኸዉም የጠብ፣ የተንኮል፣ የክፋት፣ የጥላቻ፣ የበቀል ምክሬን ሰምታችሁ ወደ ተግባር ካለወጣችሁ ሰላም፣ ርካታ፣ ደስታ፣ ቅድስና አታገኙምና:: እዚህ ላይ የማሳስባችሁ ግልጽ ንግግርና ዉይይት ለበቀልና ለጥላቻ ሕይወታችሁ እንቅፋት ስለሚሆን፤ ከማንም ጠበኛችሁ ሆነ ቅር ከተሰኛችሁበት ሰዉ ጋር ስለምንም ነገር በግልጽ እንዳትነጋገሩ::

እናንተ ሰዎች የደስታ ምንጭ ናቸዉ ብላችሁ የሰዉ ተከታይና አድናቂ እንዲሁም አምላኪ የሆናሁ ሰዎች፤ ምንም እንኳን ድርጊታችሁን ባልቃወምም የኔን ተከታይነትና አድናቂነት እንዲሁም አምላኪነት ችላ እንዳትሉና የደስታ ምንጮች ምንጭ መሆኔንም እንድታስተዉሉ አሳስባችኋለሁ:: አንዳንድ አላዋቂዎችና የዚህች ምድር ምስጢር ያልገባቸዉ «እዉነተኛ ደስታ በዚህች ምድር የለም፣ ያለዉ የኅሊና እርካታና ሰላም ነዉ::እሱም የሚገኘዉ በቅን አሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛነት ሕይወት ነዉ» በማለት የሚናገሩትን አትስሙ:: ዉሸተኞች መሆናቸዉን በታላቁ የጨለማ ስሜ ምዬ አረጋግጥላችኋለሁ::

እስት አስቡት ስትዘፍኑ፣ ስትጨፍሩ፣ በተለያዩ ትዕይንቶች ስትዝናኑ ምን ያህል እዉነተኛ ደስታ እንደምታገኙ እናንተዉ ራሳችሁ ምስክሮች ናችሁ:: ደስታችሁ ለቀናት፣ ለወራት አብራችሁ የሚኖር መሆኑን እኔም በደንብ እመሰክርላችኋለሁ:: ታድያ « ለዚያች ጊዜ ብቻ ፈተናህን ከኅሊናችን ስለምታርቅና ፈተናህን ልብ ስለማንለዉ አንዳንዴም ደግሞ ሱሰኞች ሆነን ባሪያዎችህ እንድንሆን ለተወሰነ ደቂቃ ከኅሊናችን ስለምትርቅልን ነዉ የተዝናናንና የተደሰትን የሚመስለን » በማለት አስተያየት እንደማትሰጡ እገምታለሁ::

ከፈለጋችሁ የደስታ ምንጭ አድርገችሁ የምትገምቷቸዉን ዘፋኞች፣ ዳንኪርተኞች፣ የተለያዩ አርቲስቶች፣ እንዲሁም የተለያዩ ሱሰኞችን ምን ያህል በሕይወታቸዉ ደስተኞች እንደሆኑና ሌት ተቀን በሰላም፣ በእርካታ፣ ደስታ በተሞላበት ሕይወት እንደሚኖሩ ጠይቋቸዉ:: ስለ ባዶነት ሕይወት፣ ሰላምና እርካታ ያጣች ነፍስ ምን እንደምትመስል ይነግሯችኋል:: በተቃራኒዉ ደግሞ ቅን የሚያስቡ፣ መልካም የሚሰሩ፣ እዉነተኛ ሰዎችን ስለረካች ነፍስ ፣ ሰላምና ብሩህ ተስፋ የተሞላች ነፍስ ምን እንደምትመስል ይነግሯችኋል::

ነገር ግን ጊዜ እንዳይባክንባችሁ እኔ እንዳልኳችሁ እግዚአብሔር መፍራት ያለባቸዉና በተቀደሰ ሕይወት የሚኖሩ ሰዎች እርካታ የሌላቸዉ፣ ሰላምና ብሩህ ተስፋ የማይታይባቸዉ፣ በተቅበዘበዘና ተስፋ ቢስ በሆነ ሕይወት የሚኖሩ፣ ከስጋትና ከጭንቀታቸዉ የተነሳ ሞታቸዉን የሚናፍቁ፣ የቅዱሳንን ህብረት የሚፈልጉ ሰዎች ናቸዉ:: በተቃራኒዉ ደግሞ በዘፋኝነት፣ በዳንኪርተኛነት ፣ በተለያዩ ርኩሰት ትዕይንት፣ በሱስ ሕይወት የተጠመዱ ሁሉ፤ እርካታ፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ብሩህ ተስፋ፣ በተረጋጋ ሕይወት የሚኖሩና ስጋትና ጭንቀት ስለሌለባቸዉ ለዘለዓለም በዚህች ምድር መቆየት የሚመኙና የኔን የጨለማዉ ገዥ ወዳጅነት የሚመርጡ ናቸዉ::

እናንተ በእዉቀታችሁና በጥበባችሁ የምትመኩና ራሳችሁን የተለየ አድርጋችሁ የምትቆጥሩ ታላላቆቼ፤ መቼስ በኔ ዘንድ ታላላቅ ያስባላችሁ « የእዉቀትና የጥበብ ባለቤት እግዚአብሔር ነዉ:: እሱ ነዉ ሁሉን የሚገልጸዉ:: ሊመሰገንና ሊገን የሚገባዉ እርሱ ነዉ::» ስለማትሉና ራሳችሁን ከፍ ከፍ የምታደርጉና የምታገኑ፣ በተዝዋዋሪ እኔን የምታስመሰግኑ «ተፈጥሮ ምስጋና ይግባዉ እኔም ልመስገን ::» ስለምትሉ ነዉ::

የናንተን ያህል የማመዛዘንና የማገናዘብ፣ የማስተዋል ኅሊና የሌላት ንብ በብዙ ኪሎሜትር ርቀት ተጉዛ ከአበባዎች ላይ የምትፈልገዉን ቀስማ ካለምንም አቅጣጫ አሳይ ( ኮምፓስ) ሳትጠቀም ወደ ተነሳችበት ቦታ ወደ ቀፎዋ ትመለሳለች፤ ይህንኑ ድግግሞሽ ሕይወት እስከመጨረሻዉ ሳትቸገር ትፈጽማለች:: መቸስ በእናንተ የላቀ አስተሳሰብ ከበላይ የሚቆጣጠርና የሚመራ ኃይል እንደሌለ ስለሚታመን ከሰዉ የላቀ ኃይል እንዳላት

በጥናታችሁ ዉስጥ አለማስገባታችሁ እንድታዘባችሁ አድርጎኛል። ምክንያቱም እናንተ ለመርከባችሁ፣ ለአይሮፕላናችሁ አቅጣጫ መሪ መሳሪያ በመጠቀም ስትጓጓዙ እርሷ በተፈጥሮ ኃይሏ ካለምንም እርዳታ ስትጓዝ ታላቅነቷን በማስመስከሯ ነዉ። ይኸዉም አንድ ቀን አምላኳን ስትክድ፣ ራሷን ከፍ ከፍ ስታደርግ፣ ስታገን ስምቻት አለዉቅም።

ይልቁኑ እናንተ የሰዉ ዘሮችን የሚጠቅም ነገር ስታዘጋጅ ነዉ የምመለከታት። እናንተ ደግሞ በተቃራኒዉ በገባችሁት መንገድ መዉጣት እየተሳናችሁ « የትኛዉ መንገድ ነዉ ወደዚያ ቦታ የሚወስደዉ» እያላችሁ ስትቸገሩ እንዲሁም ለአዳም ዘር መጥፊያና ማጥፊያ መሳሪያ ለመስራት ስትተጉ በማየቴ ነዉ። ታዲያ እንዲህ ስላችሁ በጥናታችሁ ቦታ አልሰጣችሁም ለማለት ፈልጌ ነዉ እንጂ ለሰዉ ዘሮች የሚጠቅም መልካም መሳሪያና የእዉቀትና የጥበብ ዉጤቶች ስሩ ለማለት ፈልጌ አይደለም። እንዲሁም ራሳችሁን አታግንኑ፣ ከፍ ከፍ አታድርጉ፣ እግዚአብሔርን አክብሩ ለማለት ፈልጌ አለመሆኑን በደንብ እንደምትረዱ እገምታለዉ። በመሆኑም ለወደፊት የአዋቂነትና የታላቅነት መገለጫችሁን ሕዝብና አሕዛብን የሚያጫርስና የሚጨርስ መሳሪያ አሁን ካለዉ በረቀቀ መንገድ እንድትፈጠሩ አሳስባችኋለሁ።

አደራ የምላችሁ የአዳም ዘር ከጉስቁልና ኑሮና ሕይወት የሚላቀቅበትን ቴክኖሎጂ ሆነ ጥበብ እንዳትፈጥሩ፤ ሰዎች እናንተን እንዳይበልጧችሁ ከድንቁርና የሚለዩበትን እዉቀት አታካፍሉ። እነዚያን አእምሯቸዉ ያልተከፈተዉንና ያልተራቀቀዉን ኢትዮጵያዉያን ሊቃዉንትንና መምህራንን እንዳትመለከቱ። ምክንያቱም በተለይ ቅኔን ሲራቀቁበትና ሲፈላሰፉበት እንደእናንተ በተገኘ ጥናትና ግኝት ተመርተዉ ሳይሆን፤ በቅጽበት የሚፈጥሩት፤ ቤት መምታት ብቻ ሳይሆን ሰምና ወርቅ አላብሰዉ ከወቅቱ ጋር የሚሄደዉን ታሪክ አዋህደዉ የሚያቀርቡ፤ ያ ብቻ አይደለም ለእናንተ የሚረቅባችሁን ዜማ ልክ ጠብቀዉ የሚያቀርበ ስለሆነ በደቂቃ ዉስጥ ወዲያዉ የሚፈጥሩትን የነሱን እዉቀት ካስተዋላችሁ ባዶነት ስለሚሰማችሁና እግዚአብሔር ከፈቀደላቸዉ ደግሞ በዚህ ኢትዮጵያዊ አእምሮ ለሰዉ ዘር የሚጠቅም ከእናንተ በመቶ እጥፍ ጥበብና ቴክኖሎጂ ሊፈጥሩ የሚችሉ ስለሆነና የእናንተ ጥበብና እዉቀታችሁ ከንቱ ስለሚሆንባችሁ ነዉ።

እናንተ ሀብት ንብረት ለልጆቻችሁ፣ ለልጅ ልጆቻችሁ፣ ለዘመድ አዝማዳችሁ፣ ለዘር ነገዳችሁ፣ ለጎጥ ወገናችሁ ብቻ የምትሰበስቡና የምታከማቹ፤ ሌላዉ የአዳም ዘር ወገናችሁን የማታዩ፤ «ለእኔ ብቻ፣ እኔ ብቻ ላግኝ» የምትሉ፤ መርካት ያልቻላችሁ ስግብግብና ስስት በተሞላ ሕይወት የምትኖሩ ዉዶቼ፤ ኅሊናችሁ እንዳይሰማዉና ባዶነት እንዳያጋጥመዉ የአንዳንድ ሞኝ ሰዎች ድርጊት አትመልከቱ:: ይኸዉም እነዚህ የምድራዊ ብልጽግና ምስጢር ያልገባቸዉ ሰዎች « እኔ ከሞትኩ ሀብት ንብረቴን ለችግረኛ ልጆችና ለችግረኛ ሰዎች ይሁንልኝ» ብለዉ የሚናዘዙትን ፤ እንኳን ለሩቁ ለዘር፣ ለጎጥ፣ ለዘመድ አዝማድ ቀርቶ ለልጆቻቸዉ የማይሳሱትን ሰዎች አትመልከቱ:: እነሱ የማያዉቁትን ዓለም ተስፋ አድርገዉ የሚኖሩ፣ ከኔ ጋር አንድነትና ህብረት የሌላቸዉ፣ ከኔ ከጨለማዉ ጸጋ የራቁ፣ ባላቸዉ ነገር ኅሊናቸዉ የሚረካ፣ የኅሊና ሰላማቸዉ የተጠበቀ፣ ያማይቅበዘበዙ፣ ስስትና ስግብግብነት የሌለባቸዉ ናቸዉ:: እነዚህ በጨለማዉ መንግስቴ አንዳች ስፍራ ስለሌላቸዉ እናንተም የእነሱ እጣ ፈንታ እንዳይደርስባችሁ በምንም መልኩ እነሱን አትምሰሉ::

እናንተ ሌት ተቀን ስለምትበሉት፣ ስለምትጠጡት፣ ስለምትለብሱት የምታስቡና የምትጨነቁ እንዲሁም የምትጠበቡ፤ ለዚህ ሆዳችሁና ለሰዉነታችሁ ከማንኛዉም ነገር ቅድሚያ ሰጣችሁ ሆዳቸዉ አምላካቸዉ ከሆነ ሰዎች ጋር አንድነትና ህብረት ፈጥራችሁ የምትመላለሱ ሰዎች፤ ስለመብሉ አይነት፣ ስለመጠጡ አይነት፣ ስለልብሱ አይነት በመጨነቃችሁ ያለኝን አድናቆት ልገልጥላችሁና ከሁሉ በፊት ቅድሚያ ለሆዳችሁና ለሰዉነታችሁ በመስጠታችሁ የተመረጣችሁ መሆኑን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ::

ታዲያ አንዳንድ የሆዳቸዉን ክብርና ታላቅነት ያልተረዱ አላዋቂዎች « ቢያንስ ቢያንስ ለዚህ ሆዳችሁ ወደ እዳሪና ወደ ሽንት ለሚለወጠዉ መብልና መጠጥ እንደምታስቡ ለሕያዉ ነፍሳችሁ ብታስቡ ምናለበት?» የሚሉትንና የሚያስተምሩትን ሰዎች አትስሙ:: እነሱ የዚህን ሥጋችሁን ክብር ስላላወቁ የወፈረ፣ የደለበ፣ ያማረበት ሥጋ ለመሬት ተስማሚ መሆኑን ስላልተገነዘቡ እንኳን ስለሚበሉት፣ ስለሚጠጡት፣ ስለሚለብሱት መጨነቅ አይደለም ከምግብ ተከልክለዉ ሥጋቸዉን በጾም ለመቅጣት የማይመለሱና ጥሬና ዳቤ ለመመገብ የማይሰቀቁ በሥጋቸዉ ላይ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት የሚፈጽሙ ጨካኞች ናቸዉ::

እናንተ ግን ይህን ሥጋችሁን አክብራችሁና አፍቅራችሁ የተለያየ የምግብና የመጠጥ አይነት እያቀረባችሁለት በቀን ሶስቴ ጊዜ አይደለም አስሬ ከመመገብ የማትመለሱ፤ ሌት ተቀን የምትተጉለት የምታዩትንና የምትዳስሱትን ዓለም ተስፋ አድርጋችሁ « እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንጨፍር፣ በዚህች ምድር እያለን ነዉ ደስታዉ ከዚያ በኋላ ሕይወት የለም፤ በቀረችን አጭር ዘመን ሥጋችን ይድላዉ፣ እኛም እንዝፈን ፣ እንደለቅ » የምትሉ ለሥጋችሁ ታላቅ መስዋዕትነትን የምትከፍሉ ቆራጥ፣ ጀግናና ታታሪ መሆናችሁን ያስመሰክራል:: አንዳንዶች ሳይገባቸዉ ይህን ታላቅ ሥጋ «ቅርፊት» እያሉ ቢያቀሉትም፤ እናንተ ግን በነፍሳችሁ ኃይል ሳይሆን በሥጋችሁ ኃይል ስለምትንቀሳቀሱ ለዚህ ታላቅ ሥጋችሁ ሌት ተቀን ከመስራት ወደ ኋላ እንዳትሉ:: በምግብ እጥረትና ረሀብ የሚከሰቱት ደም ብዛት፣ ስኳር፣ መስባት እንዳያስቸግራችሁ በድሎት ኑሮ እንድትኖሩ ጾም የሚባል፣ ስግደት የሚባል ነገር እንዳትፈጽሙ:: «የፈለጋችሁትን በፈለጋችሁት ጊዜ ብሉ፣ ጠጡ፣ ጨፍሩ፣ ዝፈኑ፣ዘሙቱ፣ ተዝናኑ፣ ለዚህች አጭር ዘመናችሁ እንደፈለጋሁት ሁኑ» በማለት ነዉ እኔ የጨለማዉ ገዥ ታላቅ ምክር የምመክራችሁ::

ታዲያ አንዳንድ ሰዎች « እነዚህ ከእግዚአብሔር የተለያየ ጸጋ የሚገኝበትንና ዲያብሎስን ድል ለማድረግ ኃይልን የሚጎናጸፉበትን ጸሎት፣ ጾም፣ ስግደት በትጋት ፈጽሙ፤ ለነፍሳችሁ ይጠቅማታል» ሲባሉ፤ «እምቢ አሻፈረኝ» የሚሉ ሰዎች፤ በደዌ ዳኛ በአልጋ ቁራኛ ሲያዙና በሽተኞች ሲሆኑ « ይህን አትብሉ፣ ይህን አትጠጡ፣ የሰዉነት እንቅስቃሴ አድርጉ፣ ሥጋችሁ ይፈወሳል፤ ይድናል::» ሲሏቸዉ እንደ እግዚአብሔር ትዕዛዝ አድርገዉ ሲፈጽሙ፤ ነፍሳቸዉ የምትፈወስበትን ፣ የምትድንበትን፣ ኃይልን የምታገኝበትን ግን ሊፈጽሙ ቀርቶ ከቁም ነገር ቆጥረዉ አይሰሙም::» የሚሉትን ሰዎች አባባል አትስሙ:: ብትሰሙም ከቁም ነገር አትቁጠሩ:: እነሱ «ከሞት በኋላ ሕይወትና ፍርድ አለ» ብለዉ የሚያስቡ ሐሳባዉያን ናቸዉ:: እናንተ ደግሞ እንደ አዋቂ ምሁር የሚያስቆጥራችሁ እንደቁሳዉያኑ « እንወለዳለን ፣ እንኖራለን ፣ እንሞታለን ፣ የእኛ ሕይወት በዚህ ይደመደማል:: ትንሳኤና ፍርድ የለም::» እንደሚሉት እዉነተኞች ሁኑ::

እናንተ ለልጆች ርኅራኄና ፍቅር የሌላችሁ የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጆችን ኃላፊነት ተሰምቷችሁ በአግባቡና በስርዐቱ የማታሳድጉ ወንዶችና ሴቶች፤ በምድርም ዋጋ እንደምትከፍሉበት በሰማይም እንደምትጠየቁበት ብታዉቁም፤ የኔ የጨለማዉ ገዥ ባሕርይና ጠባይ ስለመረጣችሁና እንዲሁም ከኔ ዋጋ ስለምትጠብቁ ከኔ ዘንድ የበለጠ ዋጋ እንድታገኙ ልጆቻችሁን አስርቡ፣ አስጠሙ፣ አስጨንቁ፣ መከራና ስቃይ አድርሱ፣ መሃይም ደንቆሮ እንዲሆኑ አድርጉ፣ ስርዐት አልበኛ እንዲሆኑ በጋጠወጥነት አሳድጓቸዉ፣ ከልጅነት ጀምሮ እግዚአብሔር መፍራት እንዳይኖራቸዉ ክፋትና ተንኮል፣ ምቀኝነትና ቅናትን ፣ ጥላቻንና በቀልን ፣ ርኩሰትን ሁሉ በደንብ አስተምሯቸዉ::

ታዲያ አንዳንድ የሕይወት ምስጢር ያልገባቸዉ አላዋቂዎች « ልጆቻችንን በእንክብካቤና በስርዐት ካሳደግን የመጀመሪያ ተጠቃሚዎች እኛ ወላጆች ነን:: ምክንያቱም ዋጋ ስለከፈልንበት መልካም ዋጋ እንቀበልበታለን:: ከዚያም ጥቅሙ ለጎረቤት፣ ለሰፈር፣ ለአገር፣ ለዓለም ይተርፋል:: በመልካም ሕይወት በስርዐት ካላሳደግን ደግሞ በመጀመሪያ ዋጋ የምንከፍለዉ እኛ ወላጆች ነን:: ከዚያም ችግሩ ለጎረቤት፣ ለሰፈር፣ ለአገር፣ ለዓለም ይተርፋል:: ልጁን በእንክብካቤና በመልካም ስርዐት የሚያሳድግ ወላጅ ነዉ በአዳም ንስሐ ጊዜ የታዩትን ምርጥ ነፍሳት ወላጅ የመሆን እድል የሚያጋጥመዉና እንዲሁም እግዚአብሔርን በመፍራት የሚመላለሱ፣ በቅዱስ ሥጋዉና በክቡር ደሙ የተወሰኑ ወላጆች ናቸዉ የበቁ ነፍሳት ወላጅ የመሆነዉ እድል የሚያጋጥማቸዉ እንጂ ከጋብቻ ዉጭ የሚወለዱ፣ ለልጆቻቸዉ ርኅራኄና ፍቅር የሌላቸዉ፣ እግዚአብሔር መፍራት የማይታይባቸዉ፣ ልጆቻቸዉን በስርዐት የማያሳድጉ ወላጆች ግን እንደ ደረጃቸዉ የትዕቢት «የፈረኦን ወንድምና እህቶችን)፣ የክፋት (የይሁዳ ወንድምና እህቶችን)፣ የዐመጻ ( የአርዮስ ወንድምና እህቶችን)፣ እንዲሁም አእምሮ ቀላልና አእምሮ ህጻናት የሆኑ ነፍሳት ወላጆች ነዉ የሚሆኑት::» እያሉ የሚናገሩት ሰዎች አትስሙ::

እነሱ ለኔ የሚመቹ ልጆች ወላጅ የመሆን እድል ስላላጋጠማዉ ነዉ እንጂ፤ ሌባ፣ ቀማኛ፣ ነፍስ ገዳይ፣ ወንበዴ፣ ሽፍታ፣ ዐመጸኛ፣ ከሃዲ፣ መናፍቅ፣ ክፋትና ተንኮል የሞላዉ፣ ጥላቻና በቀል ያረገዘ ቀራጥ ጀግና ሰዉ ወላጅ ቢሆኑ ደስታዉን አይችሉም ነበር:: ስለዚህ

እናንተ በዝሙትና በአመንዝራ ሕይወት ለኔ የሚመቹ ልጆች ወላጆች እንድትሆኑና ለታለቅ አገልግሎት እንድታበቋቸዉ፣ እናንተም እንድትበቁ በመጨረሻም በታለቁ ጨለማዉ መንግስቴ ለመኖር እንድትችሉ ታላቅ ምክሬን እለግሳችኋለሁ፡፡

እናንተ በልጆቻችሁ ጥፋትና ስህተት ፈጣሪያችሁን የምታማርሩና እኔንም የምትረግሙ ሰዎች፤ በመጀመሪያ ደረጃ ልጆቻችሁ ወደ ማይገባ ቦታ እንዳይሄዱና እንዳይዉሉ አታደርጉም ነበር? እኔ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ፤ ወደ መቃሚያዉ፣ ሺሻዉ፣ ስካሩ፣ አደንዛዥ ዕጹ፣ ዝሙቱ፣ ጥንቆላዉ፣ አስማቱ፣ ባዕድና ጣዖት አምልኮ፣ መተቱ፣ አስማቱ፣ ሟርቱ ቦታና ዘፈኑና ዳንኪራ ርኩሰቱ ትዕይንት በሚቀርብበትና በሚታይበት እንዲሁም ለሥጋችሁም ለነፍሳችሁም አንዳች ጥቅም በማታገኙበት ጊዜ ማባከኛና ማጥፊያ ቦታዎች ሂዱ ብዬ አዝዣለሁኝን? ራሳችሁ ናችሁ በራሳችሁ ፈቃድ ወደ እኔ ልዩ ስፍራ የምትመጡና በራሳችሁ ወገኖችና እኔም በራሴ ኃይል ወደ ጎሊናችሁና አካላችሁ የምገባዉና ከሰዉነት ማዕረግ የምናዋርዳችሁና የምናጎሳቁላችሁ፡፡

እስቲ ራሳችን ተገፋፍተን ያስመተትንበት ሰዉ አለ? የራሳችሁ የአዳም ዘሮች ወገኖቻችሁ ናቸዉ በመተትና በድግምት ወደ ሰዎች የሚሊኩንና ጉዳትና ጥቃት እንድንፈጽም የሚያደርጉን፡፡ እናንተ ግን « ሰይጣን ነዉ እንዲህ ያደረገብኝ» ብላችሁ ያለ ስሜ ስም ትሰጡኛላችሁ፡፡ « ሰይጣን አስገድዶኝ ይህን አድርግ፤ ይህን አታድርግ፡፡» ብሎኛል የሚል እስቲ አንድ ሰዉ ካለ ይመስክር?! እናንተ ግን ፍላጎቴ ባይሆንም የቅንጩዉ፣ የንፍሮዉ፣ የእንስሳቱ ደም አንሶ የሰዉ ደም ትገብሩልኛላችሁ፤ ትበትኑልኛላችሁ፡፡ አንድ ፊቱኑ ከሰዉነት ባሕርይ ተለይታችሁ ሰይጣናዊ ባሕርይ ብትላበሱና በኔ አገዛዝ ስርዐት ዉስጥ ብትመላለሱልኝ ለአስተዳደር ይመቸኝ ነበር፡፡ ምክንያቱም አንዳንዶቻችሁ ባለሰብኩትና ባልጠበኩት መንገድ ከኔ ባሪያነት አፈትልካችሁ በመዉጣት ከአምላካችሁ ጋር ታርቃችሁና አንድነትን ፈጥራችሁ እያበሳጫቹኝና እያነደዳችሁኝ ትገኛላችሁና ነዉ፡፡ የኔ ምርጫ ንስሐ ከምትገቡ ብትሞቱልኝ ነበር የምፈልገዉ፡፡

እናንተ«ምን ባደርግላቸዉ ምን ያደርጉልኛል? » በሚለዉ በታላቁ መሪያችሁ መርህ የምትመሩ ዉለታንና ጥቅምን ካላገኛችሁ በቀር ለወገናችሁ ድጋፍ፣ ርኅራኄ፣ ቸርነት

የማታደርጉ ሰዎች፤ ከኔ ዘንድ ታላቅ ዋጋ አላችሁና በጭካኔ፣ በስስት፣ በስግብግብነትና በራስ ወዳድነት ሕይወት መኖራችሁን አጠናክሩ፡፡

ታዲያ አንዳንድ የብልጠት ኑሮ ምስጢር ያልገባቸዉ « በፍርድ ቀን ዋጋ ለማግኘት ዉለታንና ጥቅምን ሳትጠብቁ ነዉ ወገናችሁን የአዳም ዘርን መርዳትና ማገልገል ያለባችሁ እንጂ፤ ሰቶ መቀበል የአህዛብ እግዚአብሔርን የማያምኑ ሰዎች መመሪያ ነዉ፡፡ » በማለት የታለቁ መሪያችሁን ንግግር የሚያቃልሉና ከኔ ዋጋ የሚቀበሉበትን መንገድ ያላወቁ ሰዎች ስለሆኑ እነሱን አትምሰሉ፡፡ «ትንሳኤ፣ ፍርድ፣ ኩነኔ፣ ገነት» የሚባል ነገር እንደሌለ በጨለማዉ ስሜ በመማል አረጋግጥላችኋለሁ፡፡

ስለዚህ እናንተ ከጠገባችሁና ሌሎች እንዲጠግቡ የምትፈልጉት ሰዎች ከጠገቡላችሁ፣ ሌላዉ ወገናችሁ «ተራበ፣ ተጠማ፣ ተቸገረ» ብላችሁ አንዳች አታስቡ፡፡ ከእነሱ ጥቅም የምታገኙ ከሆነ ብቻ ሰቶ በመቀበል መርህ መሰረት እርዱ እንጂ፤ አንዳች ጥቅም በማታገኙ ብት በሰብአዊ ርኅራኄ ሀብታችሁን፣ ንብረታችሁን፣ ዋስትናችሁን አሳልፋችሁ እንዳትሰጡ፡፡ አንዳንዶች « ከሀብትና ከንብረታችሁ ጋር አብራችሁ አትቀበሩም፤ ድሆችንና ችግረኞችን ብትረዱ ምናለበት ?» የሚሉትን አትስሙ፡፡ እነሱ በእናንተ ቀንተዉ « ቱጃር፣ ሀብታም፣ የደላዉ፣ የተንደላቀቀ፣ ሁሉን የሚያስገብር፣ የሚያሽከረክር፣ የፈለገዉን ማድረግ የሚችል ታላቅ » እንዳትባሉ ለማድረግ ነዉ ፍላጎታቸዉ፡፡ » **ይላል አንዳች ለሰዉ ዘሮች ርኅራኄ የሌለዉ ጨካኙ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ፡፡**

## ምእራፍ ዘጠኝ

« እናንተ « የሚያሰናክል ሰዉ ወዮለት!» የሚለዉን የእግዚአብሔርን ቃል አቃላችሁ በቆራጥነትና በጀግንነት የራቁትነት አለባበስ ለብሳችሁ ወንዱን ለዝሙት የምታነሳሱና ገላችሁን የምታስመልኩ ዘመናዊ መለስተኛ ጣዖቶቼ፤ በመጀመሪያ ስለ ድፍረት አለባበሳችሁ አድናቆቴንና ሙገሳዬን አቀርብላችኋለሁ:: በማስከተል ደግሞ አሁን ከምታሳዩት በላይ ደረታችሁን፣ ጡታችሁን፣ እምብርታችሁን፣ ቂጣችሁን፣ ታፋና ዳሌያችሁ ገላልጣችሁ በየመንገዱና በየቦታዉ ለአዳም ዘር እንድታሳዩና ይህ የማይፈርስና የማይበሰብስ አካላችሁንም በተወጣጠረ ሱሬና በአጭርና በተቀዳደደ ቀሚስ ወጣጥራችሁ ወንዱን ለዝሙት እንዲነሳሳና በማየትም ኀሊናዉ በፍትወት እንዲረክስ እንድታደርጉልኝ ታለቁን የጨለማ ምክሬን እለግሳችኋለሁ:: እንደብቃታችሁም ደረጃ ዋጋዬን እከፍላችኋለሁ:: የመጨረሻ ብቃት ደረጃ ላይ ስትደርሱ ደግሞ ራቁታችሁን አስኬዳችኋለሁ:: አደራ የምላችዉ ደግሞ አርአያና ምሰሌ የሆኗችሁ የአሜሪካንና የአዉሮፓ ሴቶች በሰፊ ልዩነት እየበለጧችሁ ስለሆነ በተቻለ ፍጥነት አለባበሳችሁ እነሱን መተካከልና መብለጥ እዳለበት አሳስባችኋለሁ::

እናንተ ሰላምታችሁ « ሃይ ሃይ፣ እንዴት ነዉ እንዴት ነዉ፣ እሺ እሺ፣ ሰላም ነዉ ሰላም ነዉ ፣አማን ነዉ አማን ነዉ፣ ኬፍ ኬፍ፣ ታዲያስ ታዲያስ፣ ጫሪዉ ጫሪዉ » የሆነ:: ያ የምትጠሉትን የእግዚአብሔር ስም የማትጠሩና የማታመሰግኑ ሰዎች፤ በሰላምታ አሰጣጣችሁ ብደሰትም ከኔ ዘንድ ዋጋ እንድታገኙ ቢያንስ ቢያንስ «የጨለማዉ ገዥ፣ የጨለማዉ ጌታ ይመስገን» ብላችሁ ልታመሰግኑኝ ይገባል:: ከዚያ ዉጭ «እግዚአብሔር ይመስገኝ» እንዳይባል በዚህ መልኩ ሰላምታ መሰጣጣታችሁ የሚያስመሰግናችሁ ነዉ:: አንዳንዴ ተሳስታችሁ «እንዴት ዋላችሁ? እንዴት አደራችሁ?» ካላችሁ ደግሞ አንዳንዶች «እግዚአብሔር ይመስገኝ» ከሚለዉ በተጨማሪ፤ መንፈሴ የማይወደዉን ስም « እመ አምላክ፣ ወላዲተ አምላክ ትመስገን » የሚሉ አሉና፤ ለነዚህ መልስ አሰጣጥ የሚረዳ ሰላምታ አትሰጣጡ:: ሌላዉ የሰላምታ አሰጣጣችሁ ያስደሰተኝ ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ምድር አይቼዉ የማለዉቀዉን ከመዳራት ያልተለየዉን የወንድና የሴት ደረት ለደረት ተቃቅፎ መተሻሸቱንና

ከንፈር ለከንፈረ በአደባባይ መሳሳሙን ነዉ። ለወደፊት ደግሞ በዚህ ስልጣኔ አካሄዳችሁ በአደባባዩ እንደዉጭዎቹ ዝሙቱንና ርኩሰቱን እንደምታሳዩኝ እገምታለሁ። ያኔ የኔ የጨለማዉ ጌታ ዋጋችሁ ከፍ ይላል።

እናንተ ሌት ተቀን ይህን የማይበሰብስና የማይፈርስ ሥጋችሁን (ገላችሁን) «ሞትኩልሽ ሞትኩልህ፣ ታመምኩልሽ ታመምኩልህ፣ ወደድኩሽ ወደድኩህ፣ ከነፍኩልሽ ከነፍኩልህ፣ አበድኩልሽ አበድኩልህ፣ አፈቀርኩሽ አፈቀርኩህ፣ ጣዖቴ ነሽ ጣዖቴ ነህ ፣ መድኃኒቴ ነሽ መድኃኒቴ ነህ ፣ ንግስቴ ነሽ ንጉሤ ነህ ፣ ጨርቄን ጣልኩልሽ ጨርቄን ጣልኩልህ.. ወዘተ» በማለት የምታስመልኩና እናንተም አብዳችሁ ትዉልዱን እያሳበዳችሁ ያላችሁት ዘፋኞቼና እኔኳ በሥጋ ብገለጥ የማልችለዉን የዳንኪራና የጭፈራ አይነት የምታሳዩ ዘመናዊ ከዳሚዎቼ፤ ጥንታዊዉንና ኋላ ቀሩን በየጣዖታትና በየጠንቋዩ፣ በየዛሩ፣ በየሚርቱ ቤት የሚቀርበዉን ማጓራት፣ መዘረር፣ መንቀጥቀጥ፣ መንፈራገጥ፣ መሽከርከር፣ መወራጨት፣ መንፈራገጥ፣ ጎንበስ ቀና ማለት፣ መዝለፍለፍ፣ መንከባለል፣ መዝለልን..ወዘተ በዘመናዊ መልክ በመሳሪያ አጅባችሁ የሰዉ ኅሊና በሚቀበለዉና በሚመቸዉ መልክ አቀናብራችሁ በማዘጋጀታችሁና ለትዉልዱ በማቅረባችሁ ታላቅ ሙገሳዬን በጨለማዉ ስሜ አቀርብላችኋለሁ።

ታዲያ አንዳንድ የደስታ ምንጭ ያልገባቸዉና የኔን ኃያልነት ያልተቀበሉ « ትዉልዱ በመስቀል ላይ የተከፈለለትን ታላቅ ዋጋ እንዳያስተዉልና ወደ ልቡ እንዳይመለስ አምላክን ያህል ራቁቱን በመስቀል ላይ ሰቅሎ ዘፈኑና ዳንኪራዉን ማቅረቡ ማንን ለማስደሰት ነዉ? ዋጋ ለከፈለዉ አምላክ ምስጋናና ዉዳሴ ማቅረብ ሲገባ ነፍስን ከማሳበድ ባልተናነሰ መልኩ «ሰይጣናት ደስ ይበላቸዉ፤ እኛም ህብረታችን ከእናንተ ጋር ነዉ» በማለት ተስፋቸዉ ምድራዊ የሆነ አህዛብ የሚሉትን «እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንዝፈን ፣ እንደለቅ፣ ሞተን በስብሰን የምንቀር ስለሆነ በዚህች በአጭር ሕይወታችን ዘመን እንደፈለግነዉ እንሁን።» በማለት የአህዛብን ተግባር ዘፈኑንና ዳንኪራዉን የምንፈጽመዉ ለምንድ ነዉ?!።» ለሚሉት አንዳች ጆሮ ሰታችሁ እንዳታዳምጡና እንኳን «የእብደት ተግባር ነዉ።» ማለት አደለም «ሰይጣን መሆን ነዉ።» ቢሏችሁ አንዳች ከሙያችሁ አርቲስት ከሚያስብላችሁ ከዘፋኝነትና ከዳንኪርተኛ

ነት ሕይወት አትለዩ:: ይልቁኑ እግዚአብሔርን ለማስቆጣት በዘፈናችሁ ዉስጥ እንደ የሱስ ተከታዮች ፕሮቴስታንቴ ድርጅቶቼ አባልና እንደ ተሐድሶች በቃሉ ዝፈኑበት:: ጨፍሩበት:: ምን ያመጣሉ? ልትደሰቱና ልትዝናኑ ነዉ ወደዚህች ምድር የመጣችሁት:: እኔም ከጎናችሁ ስለምቆም በአንዳች ነገር እንጠየቃለን ብላችሁ ስጋት አይደርበችሁ:: ያ በመስቀል ላይ የተሰቀለዉን «አምላካችን» የሚሉሁትን እርሱት፤ እኔ የግብር አባታችሁ አምላክ እሆናችኋለሁ::

እናንተ « አባትህንና እናትህን አክብር» የሚለዉን የማይታየዉን እግዚአብሔር ማክበራችሁ የሚገለጽበትን ትዕዛዝ አሽቀንጥራችሁ በመተዉ አባትና እናቶቻችሁን እንዲሁም ታላላቆቻችሁን ሁሉ የምታዋርዱ፣ የምታንጓጥጡ፣ የምትሰድቡ፣ የኔን አርአያ የተከተላችሁ ዘመናይ ታላላቅ ትዉልዶች፤ ለእናንተም ሙገሳዬን በጨለማዉ ስሜ አቀርብላችኋለሁ:: በእኔ ዘንድ መከባበር የሚባል ነገር እንደማይሰራ አዉቃችሁ ድርጊታችሁን በማጠናከር ከቀላል ምልክቶች ደረትን ከምንፋት፣ እግርን ከማንፈራገጥ፣ ዐይን ከማፍጠጥ፣ ከፍ ዝቅ ከማድረግ ጀምሮ ማንኛዉንም የከፋ ድርጊት ከመፈጸም እንዲሁም አዛዉንቶችንም «የእንጨት ሽበት» ብሎ ከመሳደብ ወደ ኋላ እንዳትሉ:: የኔን የጨለማዉ ገዥ መንግስት መዉረስ የምትችሉት እንዲህ በትዕቢት በተሞላ ሕይወት ስትመላለሱ ብቻ ነዉ::

እናንተ « የሰዉ ገንዘብ ካልነካንና ከግለሰብ ካልሰረቁ በተመደብኩበት ወንበርና የስራ ቦታ ላይ ሆኜ የመንግስት ገንዘብ ባጭበረብር፣ ብሰርቅ፣ ሰዉን ብጠቅምበትና እኔም ብጠቀምበት ኃጢአት አይሆንብኝም፤ ታላቁ መሪያችንም የብልጠት ስርቆትን ይደግፋል፤ ያበረታታል ::» ብላችሁ ኅሊናችሁን በማሳመን በብልጠት የሕዝብን ገንዘብ የምትሰርቁ ሰራተኞች፤ ይህን ታላቅ ተግባራችሁን የማበረታታ ሲሆን፤ ከዚህ በተጨማሪ የግለሰቦችን ገንዘብና ንብረት ብትሰርቁ በኔ ዘንድ በአስተያየት የምትታለፉና የማትጠየቁበት ስለሆነ የስርቆቱን አቅጣጫ እንድታሰፉት በጨለማዉ ስሜ አሳስባችኋለሁ::

ታዲያ አንዳንድ ወግ አጥባቂና የብልጽግና ምስጢር ያልገባቸዉ ሰዎች « የግለሰብን ገንዘብና ንብረት አትስረቅ የመንግስትን ገንዘብና ንብረት ስረቅ የሚል የእግዚአብሔር ትዕዛዝ

የለም፡፡ የግለሰብም ሆነ የመንግስት ገንዘብና ንብረት መስረቅ የአሰራረቁ አይነት ይለያያል እንጂ ያዉ ስርቆት ነዉ፡፡ ደግሞ መንግስት ራሱን ፈላጭ ቆራጭ አድርጎ ሕዝቡን በአድሎና በበደል ስለሚያስተዳድር ነዉ እንጂ መንግስት ማለት ሕዝብ ማለት ነበር፡፡ የመንግስት ገንዘብና ንብረት መስረቅና ማባከን ማለት በተዘዋዋሪ የሕዝብን ገንዘብና ንብረት መስረቅና ማባከን ነዉ፡፡

ይሁንና ራሱ መንግስት የተባለዉ ከላይ እስከታች ባሉት ባለስልጣናት የሕዝቡን ገንዘብ ስለሚበዘብዙ ትክክለኛ ትርጉሙ ተዛብቶ ሁሉም በየፊናዉ የመንግስት ገንዘብና ንብረት ማለት የዘራፊዎች ገንዘብና ንብረት አድርጎ በመቁጠር የሕዝብን ገንዘብና ንብረት በተለያየ መልኩ ይዘርፋል፡፡ ይሰርቃል፡፡ ያባክናል፡፡ ነገር ግን ወደ ትክክለኛዉ ነገር ስንመጣ መንግስት እንኳን የራሱ ገንዘብና ንብረት ሊኖረዉ ቀርቶ ከመሪዉ እሰከ ቀበሌ ያለዉ ሰራተኛ ከሕዝብ ከሚሰበሰበዉ ገንዘብ ነዉ የሚከፈለዉና ንበረቱም የሚገዛዉ፡፡ በዚህም ምክንያተ መንግስት የሕዝብ አገልጋይ ነዉ እንጂ በሕዝብ ላይ ግፍ፣ ጭቆና፣ አድሎ፣ በደል፣ ማጉላላት፣ መግድል፣ ማሰቃየት፣ ማሰር፣ ማሳደድ፣ ማጣላት፣ መከፋፈል፣ መለያየት፣ ማሳደም፣ ጥላቻና በቀል ማስፈጸም አልነበረበትም፡፡

ሕዝቡም በመሳሪያና በሰላይ ደኅንነቶች ተረግጦ በመገዛቱና ካለ ፍላጎቱ በተጽህኖ በካርድ በግድ እንዲመርጥ በመደረጉ ነዉ እንጂ፤ ዐመጸኛንና ክህደት እንዲሁም ርኩሰት አስፈጻሚ፣ ዘረኝነትና ጎጠኝነትን እያስፋፋ ሕዝብን የሚከፋፍልና አገርን የሚያስገነጥልና የሚያጠፋን መንግስት « አንተ እግዚአብሔር መፍራት የሌለብህ፣ እግዚአብሔርን የማታዉቅ የዲያብሎስ ስራ አስፈጻሚ ነህ ብሎ፡፡» እስከታች ድረስ ያሉትን በሕዝብ ስም የሚነግዱትን የሕዝብ ደም መጣጮችን ባለስልጣናትንና ካድሬዎችን ከወንበር አስወርዶ በቅንነትና በእዉነት የሚያገለግለዉን እግዚአብሔርን መፍራት ያለበትን አገልጋይ ነበር በየወንበሩ ላይ ማስቀመጥ የነበረበት፡፡

ይሁንና ይህ ለጊዜዉ አልተቻለም፡፡ ባልስልጣናቱና ካድሬዎቹ በተመደቡበት የስራ ቦታ ሁሉ ባይታመኑ እንኳ እናንተ ሰራተኞች ግን ለሕዝቡ ታማኝ ሆናችሁ የሕዝብን ገንዘብና ንብረት መጠበቅ አለባችሁ፡፡ አስተሳሰባችሁን  ማስተካከል ይኖርባችኋል፡፡ በስርቆቱ በምድራዊ

ሕግም፣ በሰማያዊ ሕግም ትጠየቁበታላችሁ:: ስላለፈዉ አልመታመናቸዉ ንስሐ ልትገቡና ያልታመናችሁለትን ሕዝብ በምትችሉት አቅም ሁሉ ልትክሱት ይገባል::» በማለት የእንደራሴዎቼን የመሪዎችና የባለሚሎቼን ባለስልጣናት እንዲሁም የዉድ ካድሬዎቼን ስም ለማጥፋት የሚፈልጉትንና ከብልጠት ስርቆርት ሊከለክሏችሁ የሚፈልጉትን ሰዎች አንዳች እንዳትሰሙ::

እነሱ በድህነት ለመማቀቅ የሚፈልጉ፣ ነፍሳቸዉን የሚወዱ፣ ለአገራቸዉ የሚቆረቆሩ፣ ሕዝብን የሚወዱ ናቸዉ:: እናንተ ግን  እነሱን አትምሰሉ:: ባገኛችሁት አጋጣሚ ሁሉ የሕዝብ ገንዘብና ንብረት ነዉ የሚባለዉን ለመስረቅና ለማባከን እንዲሁም ለማጥፋት ወደ ኋላ እንዳትሉ:: በኔ ዘንድ ደሀ፣ ያልበለጸገ ቦታ የለዉምና በተቻላችሁ ፍጥነት በስርቆትም ይሁን በማታለል፣ በአቋራጩ መንገድም ይሁን ዐይን ባወጣ መንገድ የሕዝብን ገንዘብንና ንብረት ለግላችሁ በማድረግ እንደ ቱጃሮቹ ሁኑ:: የትኛዉ ቱጃር ነዉ በንጹህ ላቡ ወቶ ወርዶ ሀብትና ንብረት ያፈራዉ? ሁሉም በኔ መንገድና ምክር ተጉዘዉ ነዉ ለዚህ ደረጃ የበቁት:: ስለዚህ እናንተም እንደነሱ ለመሆን ከፈለጋችሁ ታላቁን የጨለማ ምክሬን ልትሰሙ ይገባችኋል::

እናንተ ተስፋችሁን ምድራዊ አድርጋችሁ የታላቅነታችሁ መገላጫ በሆነዉ በእብሪትና በትዕቢት መናገራችሁና መደንፋታችሁ፣  በኃይላችሁና በጦራችሁ መመካታችሁ፣ በካድሬዎቻችሁና በደኅንነታችሁ መተማመናችሁ፣ እንዲሁም በእዉቀታችሁና በጥበባችሁ መታበያችሁ፣ በሀብታችሁና በብልጽግናችሁ መመካታችሁ፣ ከዚህ በተጨማሪ ባማረዉ ገላችሁ ተመክታችሁ ሰዉነታችሁን በመገላለጥና በተወጣጠረ ልብስ አካላችሁን የምታስመልኩ፤ ባጠቃላይ ተፈጥሮ በለገሰቻችሁ የሰላ አንደበት፣  ልኬት በሌላዉ እዉቀትና ጥበብ፣ አብሯችሁ በሚኖር ሀብት ንብርት፣ ብልሽት በማይታይበት ገላችሁ ተመክታችሁ የዐመጻ ስራ የምትፈጽሙና የምታስፈጽሙ ሰዎች፤ በመጀመሪያ ደረጃ እኔ የጨለማዉ ገዥ ስለታላቅነታችሁ እመሰክርላችኋለሁ:: በማስከተል ደግሞ አንዳንድ አላዊቂዎችና ተስፋቸዉን የማይታየዉን ሰማያዊ መንግስት አድርገዉ የሚመላለሱት ሰዎች የሚሉትን እንዳትሰሙ እመክራችኋለሁ::

ይኸዉም «እነዚህ ራሳቸዉን በማስታበይና በእብሪት ሌት ተቀን የሚደነፉ፣ የሚያስፈራሩ፣ በደልን፣ አድሎ፣ ግፍ፣ የሚፈጽሙ፤ በትዕቢትና በዐመጻ ሕይወት የሚመላለሱ፤ በኃይላቸዉ፣ በጦራቸዉ፣ በካድሬዎቻቸዉ፣ በደኅንነታቸዉ፣ በሀብትና ንብረታቸዉ፣ በብልጽግናቸዉ፣ በእዉቀታቸዉ፣ በጥበባቸዉ፣ በገላቸዉ .. ወዘተ የሚመኩና የሚታበዩ፤ በእግዚአብሔር ቦታ ላይ ሆነዉ መመለክንና መግነንን የሚፈልጉ፤ ነጥብ በማትሞላ እዉቀታቸዉና ጥበባቸዉ የሚመኩና የሚመጻደቁ፤ ለደቂቃ እንኳ በራሳቸዉ ስልጣን በምድር መቆየት የማይችሉ፤ በዐይን ቅጽበት ዉስጥ ከመኖር ወደ አለመኖር በሚያልፍ እንዳልነበረ በሚሆን ኮልኮሌ የሚመኩ፤ በሰከንድ ዉስጥ በሚበላሽና በሚፈረካከስ ገላቸዉ የሚመኩና ራሳቸዉን የተለየ አድርገዉ በመቁጠር ቅርፊት ሥጋቸዉን የሚያስመልኩ፤ ባጠቃላይ ይህ በሥጋዊ ዐይን በሚታየዉ ምሳሌያዊ ፍጥረት በሆነዉ ጥንት ባልነበረዉ ቁሳቁስ ነገር የሚታበዩና የሚመኩ ሰዎች፤ ምድራዊ ክብራቸዉን ቢያዉቁና ቢያስተዉሉ እንኳን ራሳቸዉን የተለየ አድርገዉ ሊቆጥሩና ሊታበዩ ፣ በራሳቸዉና ባላቸዉ ሊመኩ፣ በእግዚአብሔር ቦታ ላይ ተቀምጠዉ ራሳቸዉን ሊያስመልኩና ሊያገኑ፣ እንዲሁም ቅርፊት ሥጋቸዉን ሊያስመልኩ ቀርቶ አንዲት ቀንን በዚህ ምድር ዉስጥ መቆየትን አይፈልጉም ነበር።

ምክንያቱም እንደዚህ የሚታበዩትም ሆኑ በራሳቸዉና ባላቸዉ የሚመኩት እንዲሁም ራሳቸዉን የሚያመጻድቁትም ሆኑ የሚያስመልኩት ሰዎች ቀድሞ በገነት አኗኗር ዉስጥ ያልነበረዉና የማይከሰተዉ በአዳምና ሔዋን ዐመጻ ምክንያትና በስደት ወደዚህች ምድር ዉስጥ በመግባታቸዉ ምክንያት በሰዉ ዘሮች ላይ ከተከሰተዉ ያደፈና የጎደፈ ባሕርይ ከሆነዉ ከዐይነ ምድር፣ ከሽንት፣ ከሽታ፣ ከላበት፣ ከንፍጥ፣ ከአክት ሕይወት ያልተለዩ፤ የጎሰቆሉ ባሕርያት ከሆኑት ከመድከም፣ ከማልቀስ፣ ከማዘን፣ ከማንቀላፋት፣ ከመቁሰል፣ ከመድማት፣ ከመዳህ፣ ከማማጥ፣ ከመቅበዝበዝ፣ ከስጋት፣ ከአሳብ፣ ኑሮን ለማሸነፍ ከመዉጣት ከመዉረድ፣ ከመታመም፣ ከማርጀት በሥጋ ከመሞት፣ በነፍስ ደግሞ እዉነተኛ ፍርድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከመቀበል.. ወዘተ መለየት ያልቻሉ፤ እንዲሁም ጉስቁልና ኑሮና ሕይወት ከሆኑት በፀሐይ፣ በሙቀት፣ በቅዝቀዜ፣ በተፈራረቀ አየር ፀባይ ዉስጥ ከመመላለስ፤ ዝናብ፣ ብርድ፣ ሙቀት ለመከላከል መጠለያና ማረፍያ ከመስራት፤ ሌት ተቀን በሰይጣናት ከመፈተንና ሰይጣናት ከኅሊናና ከአካል ዉስጥ ሲወጡ ከሚገለጹበት ከማፋሸክ ፣ ከማስነጠስ፣ ከመሳል፣ ከማግሳት፣ ከማሳከክ ፣ ከመንጠራራት፣ ከፈስ ያልተላቀቁ፣ ከዚህ በተጨማሪ ሰዎች ወደዚህች ምድር ከገቡ በኋላ በራሳቸዉ ጊዜ በፈጠሩት የስግብግብነት፣ የራስ ወዳድነት፣

የጥላቻ፣ የወገንተኝነት ፣ የዘረኝነት ፣ የጎጠኝነት ፣ የክፋት፣ የተንኮል፣ የምቀኝነት ፣ የጦርነት ፣ የግድያ፣ የስርቆት፣ የጥንቆላ፣ የአስማት፣ የመተት፣ የዝሙት፣ የዘፋኝነት፣ የዳንኪርተኛነት፣ የመከፋፈል፣ የቂም በቀል፣ የእብሪት፣ የትዕቢት፣ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ ..ወዘተ ሕይወት ዉስጥ የሚመላለሱ በመሆኑ ነዉ።

በዚህም ምክንያት የዚህች ምድራዊ ሕይወት ሕይወት ሳይሆን ነፍሳት በሥጋቸዉ የሚቀጡበትና እንደ ነጻ ምርጫቸዉ እግዚአብሔርን ከመረጡ ፈቃዱን ፈጽመዉ እጅግ እጅግ እጅግ አጭር የሆነችዉን ዘመናቸዉን (ከዚህች ምድራዊ ዘመን በኋላ የማይኖሩበት ጊዜ ስለማይኖር ሕያዉ ሆነዉ ስለሚኖሩ የምድራዊ ቆይታቸዉ ጊዜ የዐይን ቅጽበት እድሜ ያህል እንኳ ርዝመት ስለሌለዉ ነዉ) ወደ እዉነተኛ መኖሪያቸዉ ገነት ከፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ ቅዱሳን መላእከት ባሉበት ሰማያት ዉስጥ የሚገቡበት ነዉ። በተቃራኒ ደግሞ በሥጋ ከተገለጹ በኋላ በዐመጻና በክህደት እንዲሁም በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ የሚጸኑት ሰዎች ደግሞ ነፍሳቸዉ በምሳሌያዊ ባሕርይ እንደ ሰይጣናት ተገልጻ ነጻነቷም ተገድቦ በባሰ ሁኔታ የምትቀጣበት ቦታ ዉስጥ ሲያል፣ ከፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ እሳቱ ከማይጠፋበት ትሉ ከማያንቀላፋበት ገሃነመ እሳት ዉስጥ በመግባት ለሕያዉነት ዘመን እንደ ዐመጻዋ ደረጃ ከሰይጣናት ጋር ይቀጣሉ።» በማለት ከእኔ ከጨለማዉ ገዥ ፈቃድ አስፈጻሚነትና ፈጻሚነት ሊለያችሁ የሚፈልጉትን ፣ በእኔ ላይ እለት እለት ዐመጻና ክህደት እየፈጸሙ የሚያስቸግሩኝን፣ እንዲሁም አንዳች ርኅራኄ ሳያደርጉልኝ ሌት ተቀን ፍዳዬን የሚያሳዩኝን ፣ የሚያሰቃዩን ሰዎች አንዳች አትስሙ።

ይልቁኑ በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት፣ በመልካም ተግባር፣ በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ እያሰቃዩንና መከራ እያደረሱብ ስለሆነ ተበቀሉልኝ። እናንተ ግን ታላቅ ሰዎችና ባለችሁ አጭር ዘመን ዉስጥ እኔ ደስ ለማሰኘት የምትተጉ ለእኔ ምርጦችና ወዳጆች መሆናችሁን ደግሜ እመሰክርላችኋለሁ። እናንተ «ሞተን፣ በስብሰን እንቀራለን።» ብትሉም እኔ ግን ሞታችሁና በስብሳችሁ እንደማትቀሩ ሕያዋን እንደምትሁኑ ሙሉ ዋስትናና ለወደፊት ደግሞ እኔን እንደማስደሰታችሁ ደረጃ የሚያምረዉንና እጅግ መዝናናትን በማደርግበት መንግስቴ የመኖር እድል እንደምሰጣችሁ በጨለማዉ ስሜ ቃል እገባላችኋለሁ።

እናንተ «ፖለቲካ፣ ዴሞክራሲ» የሚለዉ ልዩ ቋንቋዬ ስያሜ ያልገባችሁና በተደጋጋሚ ማብራሪያ እንድሰጥበት እየጠየቃችሁ የምታስቸግሩኝ ሰዎች፤ አሁን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ምላሼንና ማብራራዬን እኔ የጨለማዉ ገዥ እሰጣችኋለሁ። ፖለቲካ የሚለዉ ስያሜ የተፈለሰፈዉ በቀጥታ እዉነታ የሚለዉ የእግዚአብሔር እዉነትን ለመቃወምና ስያሜዉንም

ጭምር ለመተካት ታስቦ በእግዚአብሔር ተቃራኒ መንፈስ አሳሳቢነትና መሪነት የተፈጠረ ታላቅ ቃል ነዉ:: በዚህም ምክንያት ሰዎች የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት አስተሳሰብን ኅሊናቸዉ በቀላሉ እንዲቀበለዉና ወደ ተግባርም ለመፈጸም እንዲቻል እንደ ዶግማና ቀኖና በርዕዮተ ዓለም መልክ እንዲቀበሉት የተደረገ ነዉ:: ልዩ ጥበብና ፍልስፍ እንዲጨመርበትና ወርቃማ ቃላቶች እንዲካተቱበት የተደረገዉ፤ ሰዎች ተታለዉ ለኔ ለጨለማዉ ገዥ ፈቃድ ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች እንዲሆኑ፤ በነጻ ፈቃዳቸዉ እንዲቀበሉት፣ እንዲመሩበት፣ እንዲተዳደሩበት፣ እንዲታገሉበት፣ እንዲጋደሉበት፣ እንዲፋጩበት፣ እንዲገዳደሉበት፣ እንዲጨካከኑበት፣ እንዲከፋፈሉበትና እንዲለያዩበት፣ አንድ እንዳይሆኑበት፣ ባጠቃላይ ተስፋቸዉን ምድር አድርገዉ እንዲመላለሱበት ለማስቻልና በመጨረሻም ለታላቁ ለጨለማዉ መንግስቴ ለማብቃት ታስቦ ነዉ::

በመሆኑም የምርጦቼ እንደራሴዎቼ መሪዎች ሆነ የባለሚሎቼ ባለስልጣናት፣ የዉዶቼ ካድሬዎች፣ እንዲሁም ተጠባባቂ እጭዎቼ አስተሳሰብና ዓላማ እግዚአብሔር መፍራት ያለበትንንና ፈቃዱን የሚፈጽሙበትንንና የሚያስፈጽሙበትን ስርዐት መዘርጋትና ሕዝቡ ምድራዊ በረከት እንዲያገኝ አድርገዉ ለሰማያዊ ሕያዉ ሕይወት ለማብቃት ሳይሆን፤ የእግዚአብሔርን ህልዉና በመካድ «ሰዉ የተገኘዉ ከተፈጥሮ ነዉ:: በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ (በኢቮልሽን) አማካይነት ከጦጣ መሰል እንስሳ ወደ ሰዉ ተለዉጦ ነዉ:: ጽድቅና ኮነኔ የሚባል ነገር የለም:: ሰዉ በዚህች ምድር ሞቶ፣ በስብሶ ይቀራል እንጂ ትንሳኤ፣ ገነት፣ መንግስተ ሰማያት የሚባል ነገር የለም ..ወዘተ::» በማለት በኔ በጨለማዉ ገዥ ፍልስፍና የሚመሩ ፍጹም ለኔ ታማኝ ሆነዉ ባሪያዎቼ የሆኑና ሕዝቡም ባሪያዎቼ እንዲሆኑ ሌት ተቀን የሚተጉልኝ የምርጦቼ ምርጥ መሆናቸዉን በዚሁ አጋጣሚ እመሰክርላቸዋለሁ::

ታዲያ በዚህ ፍልስፍናዬ የተለያዩ ሃይማኖቶችና እምነቶችን፣ እንዲሁም የተለያዩ ርዕዮተ ዓለሞች በየጊዜዉ እንደ ፋብሪካ ምርት እንዲመረቱና ሕዝቡም እንዲከፋፈል፣ እንዲለያይ፣ በጥላቻ እንዲተያይ፣ እንዲጣላ፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንዳይሆን አድርጌ ሙሉ በሙሉ በጨለማ ስርዐቴ እንዲመላለሱ አድርጌያለሁ:: ስለዚህ ፖለቲካ የምለዉ ቋንቋዬ እጅግ ፍሬ ያፈረሁበት ለሕዝቡም ፍትህ፣ እኩልነት፣ ነጻነት ፣ አንድነት፣ ክብር፣ ታላቅነት፣ ብልጽግና፣ ሰላም፣ ዲሞክራሲ... ወዘተ ባጠቃላይ ወርቃማ የሆኑ ነገር ግን ወደ ተግባር የማይለወጡ አባባሎችንና ቃላቶችን አጎናጽፌዋለሁ:: ስለዚህ እያንዳንዱ አባሌና ተከታዬ እንዲሁም ደጋፊዬ ዉለታዬን አሰቦ በየቦታዉ ሐዉልት አቁሞልኝ

ሊያመልከኝ እንደሚገባ በዚሁ ትዕዛዝና መመሪያዬን ለእንደራሴዎቼና ለባለሚሎቼ፣ ለዉዶቼ አስተላልፋለሁ::

ታዲያ አደራ የምላችሁ እዉነታ የምትባለዉን ስርዐት ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተ ክህነቱ፣ ቤተ መንግስቱ በአንድ መንፈስ ቅዱስ የሚመሩበትና ወደ ተግባር ተለዉጦ ሕዝቡ በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት፣ በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት፣ በመልካም ተግባር፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ በሚሆኑበት፣ ባጠቃላይ እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበትና ምድራዊ በረከት በሚያገኙበት፤ ለሰማይዊ መንግስት በሚበቁበት ሕይወት እንዲመላለሱ እንዳታደርጉ:: ይልቁኑ ዴሞክራሲ መብታቸዉን ተጠቅመዉ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት የሚመላለሱበትን፤ እንዲሁም አድሎ፣ በደል፣ ግፍ፣ ጭከና.. ወዘተ የሚፈጸምበትን የበለጠዉን ስርዐት አዘጋጁላቸዉ::

ሌላዉ ጥያቄያችሁ ስለ ዴሞክራሲ ምንነትና መገለጫዉ ሲሆን፤ ዴሞክራሲ ልክ እንደፖለቲካዉ እዉነታን ለመቃረንና ሰማያዊ ስርዐትን ለመተካት ያዘጋጀሁት ልዩ ፍልስፍና ቋንቋዬ ነዉ:: ይህም መሪዎች ሆኑ ባለስልጣኖች እንዲሁም ካድሬዎች እንደ ዶግማና ቀኖና ተመልክተዉት ኅሊናቸዉን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ለመፈጸምና ለማስፈጸም እንዲቀበለዉ በርዕዮተ ዓለም መልኩ ያዘጋጀዉላቸዉ ሲሆን ዉጤቱም ሕዝቡ በሙሉ ነጻነቱ ተጠቅሞ ከፈለገ «እግዚብሔር የለም» ከፈለገ «እግዚአብሔር አለ» ብሎ በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት ፣ በትዕቢት፣ በዐመጻ፣ በዝሙት፣ በግብረ ሰዶም፣ በዘፈን ፣ በዳንኪራ፣ በጣዖትና ባዕድ አምልኮ፣ በዘረኝነት ፣ በጎጠኝነት ፣ በአስማት፣ በጥንቆላ፣ በመተት ..ወዘተ ሕይወት ዉስጥ ምንም ሳይፈራና ሳይሸማቀቅ እንዲመላለስ በማድረግ ለታላቅ ክብር ለማብቃት በማሰብ ነዉ በበላይ ሆኜ ዴሞክራሲ ስርዐት የዘረጋዉላችሁ::

ታዲያ ይህን የተጎናጸፋችሁትን ዴሞክራሲ መብታችሁን ለመገደብና ብሎም ለማስቀረት ሰማያዊ ስርዐት ናፋቂዎችን አንዳች እንዳትቀበሉ፤ እንዳትሰሙ:: እነሱ ከዚህ ከሚጣፍጠዉ ሕይወት ሊለያችሁና እግዚአብሔርን በመፍራትና በማስደሰት እንድትኖሩ አድርገዉ ከስስት፣ ከስግብግብነት፣ ከራስ ወዳድነት ሕይወት ለይተዉ በመተሳሰብ፣ በመረዳዳት፣ በመተዛዘን እንድትኖሩና ሕይወታችሁም በቅድስና እንድትመላለስ ሊያደርጉ ስለሆነ አንዳች እንዳትሰሟቸዉ፤ የሚሉትንም እንዳትፈጽሙ:: ይልቁኑ ሌት ተቀን ኮንደሙን በቴሌቭዥንና በሬድዮን ፣ በስብሰባ እያስተዋወቃችሁ ዝሙትን አስፋፉ:: ከህጻን እስከ አዋቂዉ ድረስ ነፍሱን በማሳበድ ሌት ተቀን በዘፈኑና በዳንኪራዉ አስጨፍሩት:: በተለያዩ ትዕይንቶችና ወሬዎች

ኅሊናዉን አደንዝዙ:: ብቻ ምን እኔ እነግራችኋለሁ እናንተ ከኔ በላይ ሕዝቡ ማድረግ ያለበትን ታዉቃላችሁና እንደማሳስባችሁና እንደምመራችሁ ሁሉን አስፈጽሙልኝ:: ለጠቅላላ እዉቀት ስለ ፖለቲካና ዴሞክራሲ የዚህን ያህል ካልኳችሁ ለወደፊቱ በዋናዉ መንግስታችን የበለጠ ማብራሪያ እንደምሰጣችሁ በጨለማዉ ስሜ ቃል እገባላችኋለሁ:: ዋናዉ ለዚያ መንግስት ያብቃችሁ እላለሁ::

እናንተ ኢትዮጵያዉያን ተራማጅ ኃይሎች፤ የሶሻሊስት፣ የአብዮታዊ ዲሞክራሲ፣ የካፒታሊስት፣ የኢምፔሪያሊስት .. ወዘተ እግዚአብሔር የለሽ ስርዐቶችን ለመቀበልና አዉሮፓዊ፣ አሜሪካዊ፣ ኤሽያዊ፣ አረባዊ ስርዐት ለመዘርጋት ወደ ኋላ የማትሉ፤ የራሳችሁን ኢትዮጵያዊ ስርዐት ለመዘርጋት ፈቃደኛ ያልሆናችሁ፤ ስለተራማጅ አስተሳሰባችሁና እንደማንነታችሁ ለመሆን አለመፈለጋችሁ ያለኝን አድናቆት እኔ የጨለማዉ ገዥ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ:: ለወደፊትም በምንም መልኩ ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተ ክህነቱ፣ ቤተ ምልክናዉ አንድ ሆነዉ በሚመሩበት የእግዚአብሔር መንግስት ስርዐት እንዳትዘረጉ:: ከዘረጋችሁ ግን ከኔ መንግስት የምትለዩና የፈለጋችሁትን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር መፈጸም እንደማትችሉ አሁኑን እንድታዉቁ እፈልጋለሁ:: በዚህም ምክንያት ኃጢአትን ማንገስ ስለማትችሉ የእግዚብሔር ባሪያ ሆናችሁ የምትቀሩና የኔን የጨለማ መንግስት ማግኘት ተስኗችሁ ሰማያዊ መንግስት ልትገቡ እንደምትችሉ አዉቃችሁ ከኔ እንዳትለዩ እስከመጨረሻዉ አንድነታችሁንና ህብረታችሁን ለኔ ብቻ መግለጽ ይጠበቅባችኋል:: ያኔ ከአንዱ ወደ አንዱ ወንበር አሸጋግራችኋለሁ:: ኅሊናችሁን በምታገለባብጡት ብቃት ደረጃ እኔም በዚያኑ ልክ እያገለባበጥኩ ወደፈለጋችሁት ወንበር አደርሳችኋለሁ::

ታዲያ በኔ ታቃራኒ መንፈስ የሚመሩ፤ ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግስት ናት እያሉ ስለ ሰባቱ ቅዱስ ኪዳናት የሚናገሩትን አትስሙ:: የእናንተ የኢትዮጵያ ታሪክ እንኳን 7500 አይደለም 3000 እንኳ አይሆንም:: ምርጥ እንደራሴዎቼ መሪዎቻችሁና ባለሟሎቼ ባለስልጣናት እንዲሁም ዉዶቼን ካድሬዎች መጠየቅ ትችላላችሁ:: በአስተያየት የአንድ መቶ ዓመት ታሪክ አላችሁ ቢባልም ዋናዉ ታሪካችሁ የጀመረዉ በአዲሲቷ ኢትዮጵያ ዘመን ስለሆነ ታሪካችሁ ገና ሃያ ዓመትን አስቆጥሯል::

እናንተ የአዳም ዘሮች፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ እንደ እናንተዉ ሕያዉ የሆንኩ ፍጥረት ነኝ:: እንደእናንተዉ የማልሞት ከመኖር ወደ አለመኖር የማላልፍ፣ እንደ እናንተዉ የሚያስብ ኅሊና ያለኝ ዘመዳችሁ ነኝ:: ታዲያ እኔ የሚያስገርሙኝና የሚያስደንቁኝ ጥያቄዎች ሁሉ ጊዜ በኅሊናዬ ይመላለሳሉ::

ለምሳሌ ያህል፣ እኔ ምን አድርጌላችሁ ነዉ ሌት ተቀን እኔ የጨለማዉ ገዥ ደስ በምሰኝበት ሕይወት  የምትመላለሱት? ምንስ ዉለታ አድርጌላችሁ ነዉ በቴሌቭዥኑ፣ በሬድዮኑ፣ በሕትመቱ፣ በስብሰባዉ፣ በትምህርቱ፣ በድረ ገጽ ለኔ ፈቃድ የምትተጉትና ሌት ተቀን ፈቃዴን የምትፈጽሙትና የምታስፈጽሙት? ምን እንድከፍላችሁ ነዉ የአምላካችሁ ህልዉና የምትክዱትና «የተገኘነዉ  ከጦጣ መሰል እንስሳ ነዉ:: እንደ እንስሳ ሟች፣ ፈራሽ፣ በስባሽ ነን:: ከሞት በኋላ ሕይወት የለም፤ አንዳች አናዉቅም፤ አንጠየቅም::» በማለት ክህደት የምትፈጽሙት? ባጠቃላይ  ምን ተስፋ  አድርጋችሁ ነዉ የተለያየ ኃጢአት በመፈጸም ሌት ተቀን የምትመላለሱት?

ሌላዉ ግራ የገባኝ ስለምን ይሆን የኔን የጨለማዉ ገዥ ስርዐት ለመዘርጋትና የበላይነቴን ለማረጋገጥ በነፍሳችሁ ፈርዳችሁ፤ በሥጋችሁ ጫካና በረሀ ገብታችሁ፤ ገንዘባችሁን፣ እዉቀታችሁን፣ ጉልበታችሁን፣ ባጠቃላይ ሰዉነታችሁን መስዋዕት አድርጋችሁ የምትታገሉልኝ? ስለምን ይሆን ለነፍሳችሁ ድኅነትና ሕያዉነት በሥጋችሁ ፈርዳችሁ ራሳችሁን በመካድና ስለ እዉነት በመመስከር በቆራጥነት ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሕይወታችሁን የማታሰልፉት?

በዚህች ምድር  አንድ ቀን ቀርቶ አንድ ሰዐት እንኳ በራሳችሁ የመቆየት ስልጣንና ዋስትና የሌላችሁ መሆኑ እየታወቀ ስለምን ይሆን በትዕቢትና በእብሪት የምትናገሩት? ስለ ምን ይሆን የምትደነፉት? እግዚአብሔርስ ምን ያላደረገላችሁ ነገር አለና ነዉ  «እኛ ምርጫችን የዲያብሎስ እንደራሴዎችንና ስራ አስፈጻሚዎችን ነዉ:: ዲያብሎስ ይንገሥብን እንጂ እጃችንን ለእግዚአብሔር አንሰጥም:: እንዲነግሥብንም አንፈልግም::» በማለት እኔን የጨለማዉን ገዥ አብልጣችሁ የመረጣችሁኝ?

ምንስ በደላችሁና ነዉ ሌት ተቀን እሱን በሚያስቆጣና በሚያሳዝን ተግባርና ሕይወት የምትመላለሱትና እኔን የጨለማዉን ገዥ ለማስደሰት የምትሯሯጡት? ምን ያልከፈለላችሁ ዋጋ ኖሮ ነዉ ሁል ጊዜ በመስቀል ላይ ራቁቱን ሰቅላችሁ የኔን ምስ ዳንኪራዉን፣ ዘፈኑን፣

የተለያዩ አጸያፊ ትዕይንቶችን እያቀረባችሁ የምታላግጡበትና እኔን ደግሞ ዙፋን ላይ አስቀምጣችሁኝ ነፍሴን የምታስደስቷት?

እኔ የተለያየ ፈተና፣ መከራ፣ ችግር፣ ስቃይ፣ በዚህች ምድር እያመጣሁባችሁ፣ ሌት ተቀን ፍዳችሁን እያሳየዋችሁ፣ በኋላም ለሲያልና ለገሃነመ እሳት ፍርድ እያዘጋጀዋችሁ፣ እረ ለመሆኑ ምን አድርጌላችሁ ነዉ እንዲህ ሙጭጭ ብላችሁ ከእኔ ከጨለማዉ ገዥ አልላቀቅ ብላችሁ የምታስቸግሩኝ?» **ይላል የፖሊቲካና የዴሞክራሲ ጽንስ አሳብ አፍላቂና ሊቀ ምሁር እንዲሁም አስመሳዩና አታላዩ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ**።

# ክፍል ሁለት

## ምዕራፍ አንድ

« ከኢትዮጵያ በአራቱም ማዕዘን ከተለያዩ ህብረተሰብ የተሰባሰቡ ሴቶች የተሰማቸዉን ቅሬታና ጥያቄ በሃይማኖት ለማይመስሏቸዉ አባት አቀረቡ::ይኸዉም «እርሶ በሃይማኖት ባይመስሉንም ኑሮዎና ሕይወትዎን ስንሰማና ስንመለከት እግዚአብሔር ለሁሉ አባትና አገልጋይ አድርጎት ያዘጋጀት ስለመሰለን ነዉ ወደእርሶ የመጣነዉ:: ከመገለጫዎቾ ጥቂቶቹን ብንገልጽ የሰዉ ዘርን ሁሉ የሚወዱ፤ «አንተ የዚህ ዘር፣ የዚህ ወገን ነህ» ሳይሉ ካለ አድሎ አገልግሎት የሚሰጡ፤ ካለ ይሉኝታና ፍርሐት የሚያስተምሩና የሚናገሩ፤ መለያየትንና ክፍፍልን የማይፈጥሩ፤ ትልቁንም ትንሹንም የሚያከብሩ፤ የተለየ ከበሬታና ምስጋና የማይፈልጉ፤ በእግዚአብሔርና በኢትዮጵያዊነቶ የሚመኩና እግዚአብሔርንም ኢትዮጵያንም የሚያፈቅሩና የሚወዱ፤ መልካም ስነምግባር ያሎት፤ በተናገሩትና ባስተማሩት ቃል ሆነዉ የሚገኙ፤ ማንንም የማይሸነግሉ፤ ስለ እዉነት በመመስከሮ የሚመጣቦትን ፈተናና መከራ በትዕግስት፣ በጽናት፣ በቆራጥነት የሚወጡ፤ ባጠቃላይ ለእዉነተኛ አገልግሎት የተሰለፉ በመሆኖ ነዉ እኛ በአራቱም ማዕዘን የምንገኝ በሃይማኖት ባንመሳሰልም ኢትዮጵያዉያን ነንና እናቶቻችንንና እህቶቻችንን እንዲሁም ልጆቻችንን ወክለን የመጣነዉ:: ለሥጋችንም ለነፍሳችንም የሚጠቅመንን ምላሽ ይሰጡናል በሚል እምነት ነዉ ከብዙ ዓመታት በኋላ ተሳክቶልን ዛሬ እዚህ ያሉበት አጥቢያ ልንመጣ የቻልነዉ::

የመጀመሪ ጥያቄያችን ፈጣሪ በፍጥረቱ እንደማያዳላና ለወንዱ የሚፈቀድ ኃጢአት ለሴቷ የሚከለከል ኃጢአት፣ እንዲሁም ለሴቷ የሚፈቀድ ኃጢአት ለወንዱ የሚከለከል ኃጢአት የሚያዘጋጅ አይመስለንም:: ታዲያ የኛ ሃይማኖትና መምህራን « ወንዶች አቅም ካላቸዉ ብዙ ሚስቶችን ማግባት ይችላሉ:: ሴት ግን ከአንድ በላይ ባል ሊኖራት አይገባም» ይላሉ:: ለምን እኛ ሴቶች ብዙ ባሎችን እንድናገባ አይፈቀድልንም? ሎሎቹን ጥያቄዎች መልሱን እንደሰጡን በማከታተል ብናቀርብ ይሻላል» በማለት የጠየቁ ሲሆን፤ እኛም አባት እንደሚከተለዉ ምላሻቸዉን ሰተዋል::

« እናቶቼ፣ እህቶቼና ልጆቼ! የአንዱ አምላክ የፈጣሪ ፍጥረቶችና ልጆች መሆናችሁን ተገንዝባችሁ  የአዳምና ሔዋን ዘሮች መሆናችሁን አዉቃችሁ፤ ኢትዮጵያዊ መሆናችሁን ተረድታችሁ፤ የሃይማኖት፣ የዘር፣የነገድ፣ የቋንቋ መለያየት ተጽህኖ ሳያመጣባችሁ እዉነትን ፍለጋ በብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጣችሁ፣ ደክማችሁ፣ እንደ አባትና ወንድም፣ ልጅ

አይታችሁኝ የተለያዩ ጥያቄዎቻችሁን ለማቅረብ በመምጣታችሁ እግዚአብሔር ይስጥልኝ፡፡ እግዚአብሔር የጥያቄዎቻችሁን መልስ ይስጣችሁ፡፡ የኔ የሥጋና የደም ስሜት አንዳች አይቀላቀልበት» በማለት የመግቢያ ንግግር ካደረጉ በኋላ፤

«ለመጀመሪያ ጥያቄያችሁ እናንተ እንዳላችሁት ለወንድ የሚፈቀድ ኃጢአት ለሴት የሚከለከል ኃጢአት የለም፡፡ እንዲሁም ለሴት የሚፈቀድ ኃጢአት ለወንድ የሚከለከል ኃጢአት የለም፡፡ እግዚአብሔር ወንዱም ሴቱም ከኃጢአት እንዲከለከል፣ ትዕዛዙንና ሕጉን እንዲጠብቅ፣ እሱን በተግባሩም፣ በንግግሩም፣ በአሳቡም ጭምር በመፍራት እንዲመላለስ ነዉ ፈቃዱ፡፡ ነገር ግን ሰዎች ለራሳቸዉ የሚመችና የሚያደላ ትዕዛዝ፣ ሕግ፣ ስርዐትና ወግ አዘጋጅተዉ በእግዚአብሔር ስም መነገድና ለራስ ጥቅም ማዋል ከጥንት ጀምሮ የተለመደና የታወቀ ነዉ፡፡ በእግዚአብሔር ሕግና ትዕዛዝ ዉስጥ «ወንዶች ብዙ ሴቶችን ማግባት ይችላሉ፡፡ ሴቶችም ብዙ ወንዶችን ማግባት ይችላሉ» የሚል የለም፡፡ ይልቁኑ በሐዲስ ዘመን በአዳምና ሔዋን የተጀመረዉ አንድ ለአንድ ጋብቻ ስርዐት ነዉ የጸናዉ፡፡ በዚህምመሰረት አንድ ወንድ አንድ ሴት ብቻ ነዉ ሊያገባ የሚችለዉ እንጂ የተለያዩ ሴቶችን እያማረጠ ማግባት አይችልም ማለት ነዉ፡፡ በኛ ሃይማኖት ከአንድ ሕጋዊ ሚስቱ ዉጭ ወደ ሌላ ሴት የሚሄድ ባል አመንዝራ ነዉ፡፡ እንዲሁም ከጋብቻ ዉጭ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት ዝሙት ነዉ፡፡ ስለዚህ «ለምን እኛ ሴቶች ብዙ ወንዶችን እንድናገባ አይፈቀድልንም?» ያላችሁት ጥያቄ አግባብ አለመሆኑን አዉቃችሁ ለወደፊት ወንድሞቻችሁና ልጆቻችሁ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት የሚለዉን የእግዚአብሔር ቃል በመጠበቅ በአዳምና ሔዋን ጋብቻ ስርዐት ተከትለዉ እንዲኖሩ አስተምሯቸዉ፤ ምከሯቸዉ፡፡

ሁለተኛ ጥያቄያችሁ « በሃይማኖት የማይመስለንን ሰዉ ከገደልን ገነት ትገባላችሁ» የሚል ትምህርት የሚሰጡ መምህራን አሉ፡፡ ፈጣሪ ደግሞ መግደል ኃጢአት ነዉ ብሏል፡፡ «ይህ ትምህርት ለኅሊናችን ስለከበደን ምላሽ ቢሰጡን?» በማለት ለጠየቃችሁት ደግሞ፤ በእኛ ሃይማኖት እንኳን «ፈጣሪን አምናለሁ፤ አመልካለሁ፡፡» የሚለዉን ቀርቶ ሃይማኖት የሌለዉን መግደል ኃጢአት ነዉ፡፡ ሰዎች በሃይማኖት ሽፋን የራሳቸዉን ዓላማ ለማስካት የሚፈጽሙትን የግፍ ተግባር ኅሊናቸዉ እንዲቀበል በራሳቸዉ የሥጋና የደም አሳብ ተመርተዉ የጻፉት ነዉ እንጂ እንኳን ወንድምና እህት የሆነዉን የአዳም ዘርን፣ የእግዚአብሔርን ፍጥረትና ልጆችን መግደል አይደለም መስደብ ራሱ ለምድራዊና ለሰማያዊ ፍርድ የሚዳርግ ነዉ፡፡ በመሆኑም እንኳን ክርስቲያኖችን ቀርቶ እግዚአብሔርን የማያምኑ አህዛብን የገደለ የሲያልና የገሃነመ እሳት ፍርድ ነዉ የሚጠብቀዉ እንጂ ገነት መንግስተ ሰማያትን አይወርስም፡፡

ሦስተኛዉ ጥያቄያችሁ « እኛ በአንድ ፈጣሪ አምላክ እናምናለን፤ እናንተም ክርስቲያኖች በአንድ ፈጣሪ አምላክ ነዉ የምናምነዉ ትላላችሁ። ታዲያ ለምን አምልኮታችን ይለያያል?» በማለት ለጠየቃችሁት፤ እናንተ እንዳላችሁት ፈጣሪ አንድ ነዉ።እሱም ያልኖረበት ጊዜ የሌለ፣ የማይኖርበትም ጊዜ የማይኖር፣ ፍጥረታትን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ፣ ከፈለገም በዐይን ቅጽበት ዉስጥ ከመኖር ወደ አለመኖር ማሳለፍ የሚችል፣ እንዲሁም አሁን ከሚታየዉ ፍጥረታት በእልፍ አእላፋት እጥፍ ካለመኖር ወደ መኖር ማምጣት የሚችል ምንም የማይሳነዉ፣ ሁሉ በኃይሉ ስለተፈጠረ ኃይሉ ደግሞ በእርሱ ቁጥጥር ዉስጥ በመሆኑ ሳያዉቀዉና ሳይፈቅደዉ አንዳች ነገር ሊሆን የማይችልና አንዳችም ማድረግ የማይቻል፣ መጀመሪያና መጨረሻ በሌለዉ አማናዊ ሕዋ ዉስጥ እንደ አማናዊ ባሕርይዉ ያለ፣ በሰማያት ዉስጥ በእልፍ አእላፋት ወትእልፊት ቅዱሳን መላእክት በብርሃናዊ ባሕርይዉ የሚመለክ። ባጠቃላይ እሱን ለመግለጽ የምንችልበት አንደበትና ቃላት የሌለን ኃያል ገናና ርኅሩኅ ደግ አፍቃሪ አምላክ ነዉ።

ታዲያ ይህ እዉነተኛ አምላክና አባታችን ሊታወቅ ሆነ ልንረዳዉ የምንችለዉ በእዉነትና በመንፈስ ስናመልከዉ፤ በስራችን፣ በንግግራችንና በአሳባችን ጭምር እሱን በመፍራት ስንመላለስ፤ በትህትናና በፍቅር ሆነን ፈቃዱን ስንፈጽምና ስናስፈጽም ብቻ ነዉ። ያለዉ እዉነታ ደግሞ ተቃራኒ ነዉ። ይኸዉም እጅግ ብዙዎቻችን አምልኮታችን በዘልማድ ነዉ እንጂ በሚያመዛዝነዉና በሚያገናዝበዉ ኅሊናችን ተመርተን በእዉነትና በእምነት አናመልከዉም። በዚህም ምክንያት የተለያዩ ሃይማኖቶችና አምልኮዎች ሊፈጠሩ ችሏል። እልፍ አእላፋት ወትእልፊት መላእክት ሲፈጠሩ የነበረ፣ አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ የነበረ፣ በብሉይ ዘመን በኪዳነ ልቦናን በኪዳነ ኦሪት ይመለክ የነበረ፣ አሁን በሐዲስ ዘመን ደግሞ በኪዳነ ወንጌል የሚመለከዉ ያዉ የነበረዉ ያለዉ የሚኖረዉ ሕያዉ እግዚአብሔር አንዱ አምላክ ነዉ። የእናንተ ሙስሊሞች ሆነ የእኛ ክርስቲያኖች ፈጣሪ አንድ ብቻ ነዉ። እሱም «አዶናይ ኤልሻዳይ ያህዌህ ጸባዖት» በመባል የሚታወቀዉ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ነዉ።

ይሁንና ሰዎች በራሳቸዉ ሥጋን ደም አሳብ ተመርተዉ በፈጠሩት ሃይማኖት ስያሜ ይኸዉ ለዘመናት ተለያይተን እንገኛለን። እናንተ ግን በቅንነት፣ በየዋህነት፣ በግልጽነት ተነሳስታችሁ ልዩነቱን ለማወቅ በመነሳታችሁ እግዚአብሔር የዋህና ቅን ልቦናችሁን ተመልክቶ እዉነቱን ሊያሳዉቃችሁ እንደወደደ አምናለሁ። እኔም እዉነቱን ፍርጥርጥ አድርጌ እነግራችኋለሁ። እንኳን እናንተ የምታመልኩት አምላክና እኛ የምናመልከዉ አምላክ አንድ አይነት ሊሆን ቀርቶ ክርስቲያኖች የምንባባለዉ እንኳ የምናመልከዉ አምላክ ይለያያል።

ይኸዉም ለምሳሌ «ፕሮቴስታንት» የሚባሉት በክርስትና ስም የሚጠሩት እጅግ ብዙ የተከፋፈሉ የእምነት ድርጅቶች ሳታዉቁና ሳትሰሙ አይቀርም፡፡ ባገራችን እንኳ በአብዛኛዉ ሕብረተሰብ «ጴንጤ» ነዉ የሚባሉት፡፡ በዓለም ዉስጥ በአስራ ሺህ ስም ይታወቃሉ፡፡ ታዲያ ብዙዎቹ ክርስቲያን የሚለዉን ስያሜ ነዉ የሚጠቀሙት፡፡ ነገር ግን እነሱ የሚያመልኩት አምላክና እኛ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከተያ ክርስቲያኖች አምላክ የሰማይና የመሬት ያህል ልዩነት አለዉ፡፡ ብዙዎች ግን በክርስትና ስም ስለሚጠሩ አንድ አይነት ይመስላቸዋል፡፡

እኛ የምናመልከዉ አምላክ ቀደም ብዬ የጠቀስኩላችሁ ፈጣሪ ያልኳችሁ የመልከጼዴቅ፣ የአብርሃም፣ የሙሴ ፣ የነብያት ፣ የሐዋርያት፣ የሰማዕታት፣ የጻድቃን አምላክ ነዉ፡፡ ይህ አምላክ በብሉይ ዘመን በተለያየ መልኩ ሲመለክ፣ ሲገለጽ የነበረ፤ ነብያትንና መምህራንን እያስነሳ ሕዝቡን ያስተምር፣ ሲያጠፉም ይገስጽ ነበር፡፡ አዳምና ሔዋን በዐመጻቸዉ ምክንያት ይኸዉም አትብሉት የጠባሉትን ፍሬ የሰይጣንን ክፉና ሐሰት ምክር ሰምተዉ በመብላታቸዉ ምክንያት ከገነት ተባረዉ ወደዚህች ሰይጣናት መኖሪያና መቀጫ ምድር ሲገቡ፣ እዉንተኛ ንስሐ ስለገቡና በዐመጻቸዉም እጅግ ስለተጸጸቱ፣ እንዲሁም እኛ ልጆቻቸዉ ባላወቅነዉና ባልፈጸምነዉ ዐመጻ በእነሱ ምክንያት የዚህች ምድርና የሲዖል ቅጣት ስለተፈረደብን፤ እያንዳንዱ የአዳምና ሔዋን ዘር በነጻ ኅሊናዉ በሚፈጽመዉ እዉነተኛ አምልኮና መልካም ምግባር ያጣዉን መንግስት ገነትን እንዲሁም ከፍርድ ቀን በኋላ መንግስተ ሰማያትን እንዲወርስ ለማስቻል አዳምን « ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለዉ፡፡» ባለዉ ቃል ኪዳን መሰረት፤

ያ ሁሉን በራሱ ስልጣን ማድረግ የሚችለዉ፤ ምንም የማያሳነዉ የሁሉ ፈጣሪ አምላክ የሆነዉ እግዚአብሔር፤ መጀመሪያና መጨረሻ በሌለዉ አማናዊ ሕዋ ዉስጥ ሳይጎል፣ ከሰማያት ዉስጥ ሳይጎል፣ ከዓለም መግቦቱ ሳይጎል፣ እንዲሁም ፍጥረታቱን ከመቆጣጠርና ከመጠበቅ ሳይለይ መለኮታዊ ባሕርይዉን ብቻ ዝቅ አድርጎ፤ አዳምና ሔዋን ንስሐ በገቡበት ወቅት የሰዎች ነፍስ በዚህች ምድር ዉስጥ ካሉት ሰይጣናት ቁጥር እኩል እስከሚሆን ድረስ አስቀድመዉ በአዳምና ሔዋን ምሳሌያዊ ባሕርይ ግንኙነት አማካይነት እንዲወለዱ በእግዚአብሔር እቅድ ዉስጥ የነበሩ ነፍሳት በቅጽበት ከባሕርይዉ አስርጾ ካለመኖር ወደ መኖር በማምጣት በራሳቸዉ ህልዉና በነጻ ኅሊናቸዉ በዚያች ቅጽበት ዉስጥ ያሳዩትን የእምነት ብቃት በባሕርይዉ ተመልክቶና አዉቆ፤ እጅግ የብቃት ቅድስናና እምነት የታየባት አንዲት ነፍስ ተመልክቶ አዳምን «እሷ ስትወለድ ሰዉ ሆኜ አድንሃለዉ፡፡» ብሎ ቃል በገባለት መሰረት ያቺ የበቃች ነፍስ ሰዉ ሆና ተወልዳ ለአቅመ ሔዋን ስትደርስ መላኩን ቅዱስ

ገብርኤልን ልኮ የእግዚአብሔር ልጅ የተባለዉን ኢየሱስ ክርስቶስን በድንግልና ጸንሳ እንደምትወልድ ተነግሯት ባመነች ጊዜ፤ ያ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለዉ መለኮት ባሕርይዉን ወስኖ ከእመቤታችን ፣ ከአደራ እናታችን፣ ከቅድስተ ቅዱሳን ፣ ከንጽህይተ ንጹሃን ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ከሁለት አካል አንድ አካል፣ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በመሆን በተዋህዶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኖ ተወልዶ፤ የተለያዩ ተአምራትንና ፈዉስን አድርጎ፤ በመጨረሻም የተለያየ ጸዋትዎ መከራ ተቀብሎ በመስቀል ላይ የተሰቀለዉን አምላክ ነዉ የምናመልከዉ።

ይህ እዉነተኛ ፈጣሪ አምላክ ነዉ እኛ ሥላሴ ወይንም አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ በመባል የሚታወቁትን በመለኮት፣ በህልዉና፣ በአገዛዝ፣ በመፍጠር፣ ባጠቃላይ በባሕርይ አንድ የሆነዉን በስም፣ በአካል፣ በግብር ሦስት የሆነዉን የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት በግልጽ ያሳወቀን። ታዲያ የእናንተ ሃይማኖት መስራች የሆነዉ «ነብያችን» የምትሉት መሀመድ ይህ ምስጢር ስለረቀቀበት ነዉ «እግዚአብሔር አይወርድም፤ አይወለድም» ብሎ ያስተማረዉና በዓለም ላይ ይህ አይነቱ አስተሳሰብ በትዉልዱ ጎሊና እንዲሰርጽ ያደረገዉ።

እናንተ ከቅርቦቹ አባቶቻችሁና እናቶቻችሁ በወረሳችሁት ሃይማኖት አስተሳሰብ እምነት ያላችሁ ሲሆን፤ እኔ የሚገርመኝና የሚያሳዝነኝ በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ በግልጽ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር፣ አምላክ ፣ አልፋና ዖሜጋ፣ ፈጣሪ፣ መጀመሪያዉና መጨረሻዉ፣ ሁሉ በእርሱ ለእርሱ መሆኑን እያነበቡ፤ «መጽሐፍ ቅዱስ ነዉ መመሪያችን» እያሉ፤ ይህን እዉነተኛ አምላክ « አማላጅ ነዉ። ፍጡር ነዉ።» የሚሉት የተለያዩ የፕሮቴስታን እምነት ድርጅቶች አባላት ናቸዉ። አብዛኛዎቹም ከእዉነተኛዉ ሃይማኖታቸዉ «ኢየሱስ ክርስቶስን ተማላጅ፣ ዳኛ፣ ፈራጅ፣ ፈጣሪ ነዉ።» ብላ ከምታስተምረዉ ከኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት ኮብልለዉ የወጡ ናቸዉ።

ለዚህም ነዉ ድርጊታቸዉ አስገራሚና አሳዛኝ ነዉ ያልኩት። ከእርሱ በላይ እሱን የሚያዝ አምላክ የለም። ከእርሱ ጋር የሚስተካከሉትና በመለኮታዊ ባሕርይ አንድ የሆኑትን አብና መንፈስ ቅዱስ በመባል የሚታወቁትን ሁለት አካላት እርሱ ወልድ በመባል የሚታወቀዉ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነዉ በሥጋ ተገልጦ ያስተዋወቀን። ከነዚህ ሦስት አካላት ዉጭ ያሉት ሁሉ የእነሱ ፍጥረቶች ናቸዉ። የፕሮቴስታንቱ እምነት ልክ እናንተ «ኢሳ( ኢየሱስ)፣ እግዚአብሔር ሳይሆን ነብይ ፍጡር ነዉ።» እንደምትሉ እነሱም

«የእግዚአብሔር መልእክተኛ ፍጡር ነዉ። አማላጅ ነዉ። ወደ እግዚአብሔር የሚማልድ ጌታ ነዉ።.. ወዘተ» የሚል ስያሜ ነዉ የሚሰጡት።

ስለዚህ « መልእክተኛም፣ አማላጅ ጌታ ነዉ። ፍጡር ነዉ። » ቢባል ያዉ የፍጡር ስራ ስለተሰጠዉ እምነቱ ከእናንተ እምነት ብዙ አይለይም። ነገር ግን በእነርሱ ላይ ፍርዱ ይብስባቸዋል። ምክንያቱም እናንተ ባለማወቅ ከቤተሰባችሁ በመዉረስ ስለሆነ የካዳችሁት፤ እነሱ ግን ከእዉነተኛዉ አምልኮ ወተዉ በመካዳቸዉ ነዉ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክረዉን ትተዉ፤ ሰዉ ሆኖ በተገለጸበት በመዋዕለ ሥጋዌዉ ዘመን «የምትለምኑትን ሁሉ በስሜ እኔ አደርገዋለሁ፤በስሜ ለምኑ። እኔና አብ አንድ ነን ፡» እያለ፤ እነሱ ግን በራሳቸዉ ሥጋና ደም ስሜት በመመራት « አንተ አማላጅ ጌታ! ከአንተ በላይ የሆነዉን አምላካችንን ይቅር እንዲለን፣ የምንፈልገዉን እንዲሰጠን አማልደን።» እያሉ እለት እለት ያላግጡበታል፤ ይሰድቡታል። እኛ ግን «ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ አማላጅ ሳይሆን ምልጃን የሚቀበል ተማላጅ፣ የጌቶች ጌታ፣ ፈጣሪ፣ ፈራጅ፣ እግዚአብሔር ፣ አምላክ ።» ብለን ነዉ የምናምነዉ።

የእኛ እምነት እንኳን ከፕሮቴስታንቶች ቀርቶ ከካቶሊክ እምነት ጋርም አንድነትና ህብረት የለንም። ይኸዉም እግዚአብሔር ባሕርይዉን ዝቅ አድርጎ ሰዉ በመሆኑ ከሁለት አካል በአንድ አካል ከሁለት ባሕርይ በአንድ ባሕርይ ተገልጦ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ መሆኑን ስለማያምኑና የተለያየ ጸዋዕትዎ መከራ የተቀበለዉ፣ በመስቀል ላይ የተሰቀለዉ፣ ነፍሱ ከሥጋዉ የተለየችሁ፣ ከሙታን ተለይቶ የተነሳዉ እግዚአብሔር ነዉ ብለዉ ስለማያምኑ ነዉ። እኛ ግን «ሰዉ የሆነዉ እግዚአብሔር ነዉ፤ የተለያዩ ተአምራትና ፈዉስ ያደረገዉ እግዚአብሔር ነዉ፤ የተለያዩ መከራዎችን የተቀበለዉ እግዚአብሔር ነዉ፤ በመስቀል ላይ የተሰቀለዉ እግዚአብሔር ነዉ፤ ነፍሱን ከሥጋዉ የለየዉ «ሞተ» የተባለዉ እግዚብሔር ነዉ፤ በሶስተኛዉ ቀን ከሙታን ተለይቶ የተነሳዉ እግዚአብሔር ነዉ፤ በአርባኛ ዉ ቀን ወደ ሰማያ«ዐረገ» የተባለዉ እግዚአብሔር ነዉ፤ በሃምሳኛዉ ቀን የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ያደለዉ እግዚአብሔር ነዉ፤ በመጨረሻዉ ፍርድ ቀን በማረፊያ ቦታ ላይ ለሁሉ ፍጥረት በግልጽ ተገልጾ የመጨረሻ ፍርድ የሚሰጠዉ እግዚአብሔር ነዉ።» ብለን ነዉ የምናምነዉ ።

ታዲያ እንደዚህ ስላችሁ እኛ የተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ ስለሆን ብቻ ምግባር ሳይኖረን የእግዚአብሔርን መንግስት እንወርሳለን፤ እናንተ ደግሞ ትኮነናላችሁ ለማለት ፈልጌ ሳይሆን፤ እዉነታዉን እንድታዉቁና ምርጫችሁን እንድታስተካክሉ፤ ሰዎች የእግዚአብሔርን

መንግስት ሊወርሱ የሚችሉት በእዉነተኛ እምነት ዉስጥ ሆነዉ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ሲጠብቁና መልካም ምግባር ሲኖራቸዉ ብቻ መሆኑን እንድታዉቁ ነዉ:: «የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ ነን፤ ክርስቲያን ነን ::» በማለት ራሳቸዉን የሚያመጻድቁና ምግባር የሌላቸዉን ሰዎች ሕይወት ከኔ በላይ እናንተ እንደምታዉቁ እገምታለሁ::

ማነዉ በዝሙት ሕይወት ዉስጥ የሚመላለስ? ማነዉ በአመንዝራ ሕይወት ዉስጥ የሚኖር? ማነዉ በግድያ፣ በስርቆት ዉስጥ ያለዉ? ማነዉ በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት ሕይወት ዉስጥ የሚታየዉ? ማነዉ በዘፋኝነትና በዳንኪራ ሕይወት ዉስጥ የሚሰለፈዉ? ማንዉ ሰክሮ የማይገባ ስራ የሚሰራዉ? ማነዉ በተለያዩ ባዕድ አምልኮት ዉስጥ የሚመላለሰዉ? ማነዉ በዘረኝነት ፣ በጎጠኝነት ሕይወት ዉስጥ የሚኖረዉ? ማነዉ በጥላቻ፣ በቂም በቀል ሕይወት የሚኖረዉ? ማነዉ በስግብግብነት፣ በስስት፣ በአድሎ፣ በበደል ሕይወት ዉስጥ የሚገኘዉ? ማነዉ በመዋሸት፣ በማጭበርበር፣ በማታለል ሕይወት ዉስጥ የሚታየዉ?

የትኛዉ ሃይማኖት መሪ ነዉ ሐዉልቱን አስቁሞና ስዕሉን አስሎ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግና የሚያስመልክ? ማነዉ በሐሰት የሚወነጅልና እዉነተኞችን የሚያሳድድ፣ የሚያሳስር፣ የሚያስገድል፣የሚያስደበድብ፣የሚያሰድብ? ማነዉ ከነርኩሰት ሕይወቱ ቤተ መቅደስ ዉስጥ የሚገባው? ማነዉ በሚናገረዉና በሚያስተምረዉ ሕያዉ ቃል ሆኖ የማይገኝ? ማነዉ ምእመኑን እየሸነገለ የማስመሰል ሕይወት የሚኖርዉ? ማነዉ የሕይወት መንገድን አዉቆ እየተመላላሰ እያለ «ንስሐ አልገባም፣ መለኮት የተዋሀደዉን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙን አልቀበልም፣ ሕያዉ ሆኜ በእግዚአብሔር መንግስት መኖርን አልመርጥም፤ አልኖርም» የሚለዉ? ማነዉ በወገኑ ላይ መተት የሚያስመትትና የሚመትት? ማነዉ አካልን በሚያሳይ በተገላለጠና በተወጣጠረ ልብስ እየወጣ እየገባ አካሉን የሚያመልክና የሚያስመልክ? ባጠቃላይ ማነዉ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት የሚመላለሰዉ?

አራተኛ ጥያቄያችሁ ከአምልኮ ስርዐት ጋር ስለተያያዘዉ « የእኛ ጾም ስርዐትና ስግደት ከእናንተ ለምን ሊለይ ቻለ?» በማለት ለጠየቃችሁት፤ እግዚአብሔር እንዲመለክ የሚፈልገዉ በእዉነትና በመንፈስ ነዉ:: ይህም ሰዎች ለታይታና ለዉዳሴ ከንቱ የሚፈጽሙት አምልኮ ሆነ ስርዐት በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ አይገኝበትም:: ስግደቱ ሆነ ጾሙ ሰዉ ራሱን ዝቅ አድርጎ ለእግዚአብሔር ተገዢነቱን የሚገልጽበትና የተለያየ ጸጋ የሚያገኝበት ታላቅ መሳሪያ ነዉ:: ታዲያ ስግደቱም ቢሆን እየተነሱ እየወደቁ ነዉ እንጂ ቁጭ ብሎ ጎንበስ ቀና ማለት ብቻ አይደለም:: እግዚአብሔር ጸጋን የሚያድለዉ የተለየ አለባበስ፣ አመጋገብ፣ አጠጣጥ በማየት አይደለም፤ ወይንም የተለየ አኗኗር በማየት አይደለም፤ በግንባር ላይ ምልክት በማየተ

ወይንም ያደገ ጠጉርንና ጢምን በማየት አይደለም፡፡ እርሱ የሚመለከተዉና ጸጋን የሚያድለዉ በንጹህ ልቦናና በንስሐ ሕይወት የሚቀርብ ጸሎት፣ ጾም፣ ስግደት፣ ምስጋና፣ ምጽዋት ነዉ፡፡ በዉስጡ ዐመጽ፣ ክህደት፣ ርኩሰት፣ ጥላቻ፣ ቂም በቀል፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት ፣ ምንዝርና ፣ ሴሰኝነት በመሳሰሉት ሕይወት ዉስጥ እያሉ የሚቀርብ መስዋዕት ሆነ ልመና ዋጋ አይገኝበትም፡፡ እግዚአብሔር እንደሰዉ በዉጫዊ መገለጫ የሚታለል ስላልሆነ ሕይወታችንን በንስሐ እያደስን በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት፣ በመልካም ተግባር ካልቀረብን ሰማያዊ ጸጋንና መንግስትን ማግኘት አንችልም፡፡

ጾም ዋናዉ ዓላማዉ ይህ ኃጢአት የሚስማማዉ ሥጋን ላማደከምና ነፍስን ለማጠንከር የምንጠቀምበት ትልቅና ዋና መሳሪያ ነዉ፡፡ ይህም የሚሆነዉ በመጀመሪያ ከጥሉላት ምግብ መከልከል፡፡ ይኸዉም ከቅቤዉ፣ ከሥጋዉ፣ ከእንቁላሉ፣ ከወተቱ ..ወዘተ ባጠቃላይ ይህን ሥጋ ከሚያወፍሩና ከሚያደልቡ ምግቦችና መጠጦች መከልከል ነዉ፡፡ በማስከተል ደግሞ ለተወሰነ ሰዐት ከማንኛዉም ምግብና መጠጥ መከልከል ያስፈልጋል፡፡ እናንተ ከመብልና ከመጠጥ ተከልክላችሁ ብትዉሉም በማታዉ መርሐ ግብር የፈለጋችሁትን ትበላላችሁ፤ ትጠጣላችሁ፡፡ ይህ ደግሞ የቀኑን መርሐ ግብር ወደ ምሽት መለወጥ ነዉ እንጂ ምሉእ የሆነ ጾም አይደለም፡፡ ነገር ግን ቀን ጥዉልግ ብላችሁ ስትታዩ፤ እንኳን ርኅሩኅ ፈጣሪ ቀርቶ እኛም እናዝንላችኋለን፡፡ ምክንያቱም እምነታችሁ ስለሚያዝ ነዉ እንጂ ከጥሉላት መብል «ተከልከሉ » ብትባሉ መከልከል የምትችሉ፤ «በዚህ መልኩ ስገዱ» ብትባሉ መስገድ የምትችሉ ቆራጦች መሆናችሁን አስመስክራችኋል፡፡ ይህን ድካማችሁን ተመልክቶ እግዚአብሔር አንድ ቀን ወደ እዉነተኛ አምልኮ ስርዐትና እምነት ያመጣችኋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

እንኳን እናንተን ቀርቶ ክርስቲያን የሚለዉን ስያሜ ይዘዉ የፈለጉትን መብላት፣ የፈለጉትን መጠጣት፣ እንደ ፈለጉት መተኛት አንሷቸዉ፤ የሚጾሙትን ፣ የሚሰግዱትን ፣ የሚጸልዩትን የሚቃወሙ፣ የሚያጥላሉ፣ የሚተቹ፣ በተዝዋዋሪ «ለምን ሰይጣናት በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት ሌት ተቀን ይቀጠቀጣሉ፣ ይቃጠላሉ፣ ኃይላቸዉ ይድክማል?» በማለት ጥብቅና የሚቆሙላቸዉ የተለያዩ ፕሮቴስታንት ክፍልፋይ ድርጅቶች አባላት፤ አንድ ቀን ወደ ልባቸዉ ሲመለሱና ሸዋጁን መንፈስ ሲረዱ ወደ እዉነተኛዉ አምልኮና ስርዐት ይመለሳሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን፡፡

አምስተኛ ጥያቄያችሁ « በኛ ቅዱስ ቁራን እንደተገለጸዉ ኢሳ(እናንተ ኢየሱስ ክርስቶስ የምትሉት) ከነብያት አንዱ እንደሆነ በድንግልና ከመሪያም( እናንተ ማርያም ከምትሏት)

መወሉድን የተለያዩ ፈዉስና ተአምራት እንዳደረገ በፍርድ ቀንም እሱ እንደሚፈርድ ይገልጻል፡፡ ነገር ግን እኛ በድንግልና ያልተወለደዉን እንደ እሱ ተአምራትና ፈዉስ ያላደረገዉን ነብያችን መሀመድን የምናከብረዉን ያህል አናከብረዉም፤ ቦታ አንሰጠዉም፤ ያዘዘዉን ትዕዛዝ አንፈጽምም፡፡ ታዲያ ሁለቱም ነብይ ከሆኑ መሪያቸዉ አንድ መንፈስ መሆን እንዳለበትና የሁለቱ ትምህርት መቃረንና መለያየት እንደሌለበት እናምናለን፡፡ እኛ እንደምናየዉና እንደምንሰማዉ ትምህርታቸዉም ተቃራኒ አንደ አይነት እንዳልሆነ ነዉ የምንረዳዉ፡፡ ነብዩ ኢሳ ነብያችን መሀመድ ከመነሳቱ አምስት መቶ አመት በፊት ነዉ ሲያስተምርና ሲመሰክር የነበረዉ፡፡ ከሱ የተለየ ትምህርትና እምነት እንዴት ተፈጠረ? የሚል በዉስጣችን ጥያቄ አለ፡፡ እንዲሁም ሁለቱ የሚመሩበት መንፈስ ተቃራኒ ነዉ የሚል ስጋት ነዉ ያለንና ለዚህ ምላሽ ቢሰጡን፡፡» በማለት ለጠያቃችሁት ጥያቄ ያለኝ መልስ እንደሚከተለዉ ነዉ፡፡

የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዉ ቢለያይም ዓላማዉና ተግባሩ አንድ ነዉ፡፡ ይኸዉም ሰዎች በእዉነትና በእምነት ፈጣሪን አምልከዉ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝና ሕግ ጠብቀዉ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንዲኖሩ፣ በምድርም በረከት፣ ከሥጋቸዉ በማይቀረዉ ሥጋ ሞት ሲለዩ ደግሞ ገነት መንግስተ ሰማያት እንዲወርሱ የሚያደርግ ነዉ፡፡ ኃጢአትን በተመለከተ እንኳን በተግባር እንዲፈጸም ቀርቶ በንግግርና በአሳብ እንዲፈጸም የማይፈቅድ ነዉ፡፡ እናንተ እንደገመታችሁት በሁለቱ በኩል አንድነትና ህብረት የለም፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ሁለቱም የሚመሩበት መንፈስ የተለያየ ነዉ ማለት ነዉ፡፡ ሰዎች ግን ለራሳቸዉ ዓላማ መጠቀሚያ ለማድረግ ከዚያም ከዚህ እያደረጉ የተለያዩ እምነቶች ዶክትሪን በማሰባሰብ የራሳቸዉን እምነት በሥጋና በደም ስሜት ይፈጥራሉ፡፡ በዚህም ምክንያት ሰዎች ክህደቱ እምነት እየመሰላቸዉ በመታለል በሞት መንገድ ይጓዛሉ፡፡ በዓለም ላይ ያለዉ እዉነታ ይህን ይመስላል፡፡

ታዲያ የኛን ኢየሱስን (ኢሳን) በአምላክነቱ ባታምኑትም ከእግዚአብሔር ነዉ ብላችሁ ትቀበላላችሁ፡፡ እኛ ግን እናንተ «ነብያችን » የምትሉትን ከእግዚአብሔር ነዉ ብለን አንቀበለም፡፡ አንድነትና ህብረት የላቸዉም ብለን ነዉ የምናምነዉ፡፡ ምናልባት አንዳንድ «የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ሰባኪ ነን፡፡» እያሉ በሥጋና በደም ስሜት በድንፋታና በትዕቢት የሚያስተምሩ ሰዎች «ነብዩ መሀመድ» ብለዉ ቢጠሩትም፣ ቤተክርስቲያናችን እዉቅና አልሰጠችዉም፡፡ ከብሉይ ሆነ ከሐዲስ ዘመን ነብያት ጋር አልደመረችዉም፡፡

እነዚህ «ሰባኪ ነን፡፡» ባዮችም ራሳቸዉንና ቢጠዎቻቸዉን እንጂ ሃይማኖታችንን አይወክሉም፡፡ በእናንተ ቁራን(መጽሐፍ) ላይ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ነብይ መቅረቡ ምናልባት አንዳንድ እዉቀቱ የሌላቸዉ ክርስቲያኖች « እዛም ኢየሱስ ይታመናል» በሚል እምነት ወደ

እናንተ ሃይማኖት እንዲመጡ ለመሳብና እናንተም «የክርስቲያን አምላክ ሆነ የሙስሊሞች አምላክ አንድ ነዉ።» ብላችሁ እንድትገምቱና የሰማይና የመሬት ያህል ልዩነት መኖሩን እንዳታስተዉሉ ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር፤ እናንተዉ እንዳላችሁት «ነብያችን ነዉ» ለምትሉት ለመሀመድ እንኳ የምትሰጡትን ክብርና መታሰቢያ ለኢየሱስ ክርስቶስ አልሰጣችሁም:: ስለዚህ እናንተም እንደተጠራጠራችሁት የክርስቶስ መንፈስና መሀመድ የሚመራበት መንፈስ አንድ አይነት ያልሆነና የሚቃረን መሆኑን አዉቃችሁ በአንዱ መንፈስ ቅዱስ ብቻ ልትመሩ ይገባል:: ከዚያ የትኛዉ ሐሰት መሆኑን በደንብ ልታስተዉሉና ልትረዱ ትችላላችሁ::

ስድስተኛዉ ጥያቄያችሁ « እኛ ሙስሊሞችና እናንተ ክርስቲያኖች ወይንም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች በአብዛኛዉ በአለባበስ እንለያያል:: እኛ እንኳን ደረታችንን፣ ጡታችንን፣ እንብርታችንን፣ ዳሌና ታፋችንን ቀርቶ ጸጉራችንን ባታችንን እንዳይታይ እስከ ቁርጭምጭሚታችን ደረስ እንሸፍናለን:: አንዳንዶች እህቶቻችን ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፊታቸዉን ጭምር ይሸፍናሉ::እናንተጋ ግን ቤተክርስቲያን ከሚያዝወትሩት ዉጭ ያሉት አብዛኛዎቹ እንኳን ባታቸዉንና እግራቸዉን መሸፈን አይደለም ደረትና ጡታቸዉን፣እንብርታቸዉን፣ ዳሌና ታፋቸዉን ጭምር ገላልጠዉ ነዉ የሚሄዱት:: አንዳንዶቹም በተወጣጠረ ሱሬና ከቁምጣ በማይለይ ቀሚስ መላ የአካላቸዉን ቅርጽ ለኃላፊዉ ለአግዳሚዉ እያሳዩ ነዉ የሚሄዱት:: ታዲያ የእናንተ ሃይማኖት እንደዚህ አይነቶች አለባበስን ይፈቅዳል ወይ?» በማለት ላቀረባችሁት ጥያቄ የምሰጣችሁ ምላሽ የሚከተለዉ ነዉ:

በመጀመሪያ ጥሩ የታዘባችሁ መሆኑን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ:: የእናንተ አለባበስ ሰዉነትን የማይገላልጥ እንደ ቀድሞዎቹ እናቶቻችን ስርዐት ያለዉ የጨዋ አለባበስ ቢሆንም ኢትዮጵያዊ መልኩን አሳጥታችሁት ሙሉ በሙሉ አረባዊ አድርጋችሁታል:: ኢትዮጵያዊ አለባበስ ብታደርጉት የበለጠ የማንነታችሁ መገለጫ ይሆናል እንጂ የሚያዋርዳችሁና የሚያሳፍራችሁ አይደለም:: ደረታችሁን፣ ጡታችሁን፣ መላ አካላችሁን እስከ ቁርጭምጭሚታችሁ ድረስ የሚሸፍን የአገር ባህል ከነነጠላዉ አለላችሁ:: ሌሎች ዘመናዊ ልብሶችም በዚያዉ መልኩ የተሰጋጁ ልብሶች አሉላችሁ:: አንዳንዶች ፈጣሪ ያዘዘዉ መስሏቸዉ ፊታቸዉን የሚሸፋፍኑትም ካለማወቅ የመጣና ኢትዮጵያዉያን ባልሆኑ ሰዎች አማካይነት ልክ እንደዘመናዊዉ ፋሽን ከዉጪ የፈለሰ ነዉ እንጂ ይህ በኢትዮጵያ ያልነበረ አለባበስ ነዉ:: ይህች ነፍሳችሁ በዚህ ሥጋ ስትገለጽ የማንነቷ መለያ ፊቷ ነዉ:: ስለዚህ ይህ መለያ ገጿ «ይሸፈን» የሚል ትዕዛዝ እንኳን በእኛ መጽሐፍቶች በእናንተም ያለ አይመስለኝም:: ይህ ሰዎች ለራሳቸዉ ዓላማ እንደፈጠሩት ይገመታል::

ወደ እኛ አለባበስ ስንመጣ ቅጥ ያጣ አለባበስ የሚታየዉ ይህ ስልጣኔና ሉላዊነት (ግሎባላይዜሽን) የፈጠረዉ ትዉልዱ ኢትዮጵያዊ አለባበሱን እንዲተዉና አዉሮፓዊነትንና አሜሪካዊነትን እንደታላቅነት ቆጥሮ ማንነቱን እንዲለዉጥ በመደረጉ ነዉ፡፡ በሃይማኖታችን ግን እንኳን ደረትና ጡት፣ እምብርት፣ ዳሌ፣ ባት የመሳሰሉትን ገላልጦ ወንዶችን ለዝሙት ማነሳሳትና ይህን ሥጋን ማምለክና ማስመለክ ቀርቶ ኦሪት ዘዳግም ፳፪፥፭ (22:5) በግልጽ «ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ ወንድም የሴት ልብስ አይልበስ፤ ይህን የሚያደርግ በአምላክህ እግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ ነዉ፡፡» በማለት እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ተናግሮናል፡፡ ታዲያ ይህ ቃል በግልጽ እየተቀመጠና በሐዲስ ዘመንም ሽክምና ትብታብ ስላልሆነ ያልተሻሻለና ያልተሻረ ነዉ፡፡ ምክንያቱም በምእመን ላይ አንዳች ሽክም ያልሆነ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ይኸዉም በተወጣጠረ አለባበስ በሰዎች ኅሊና የነገሠዉ የዝሙት መንፈስ ተጠቃሚ ስለሚሆን ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት ወንዱ ሆነ ሴቱ በተግባር እንኳ ባይፈጽሙት በኅሊናቸዉ ዝሙትን ካሰቡ ስለሚጠየቁበት ነዉ፡፡

እናንተ ግን ማየት ያለባችሁና እንደአርአያ መከተል ያለባችሁ «ዘመናዊ ነን» ብለዉ እንደ ዉጭዎቹ ራቁታቸዉን በመሆን የከበረ ገላቸዉን ያሚያራክሱትንና የሚያረክሱትን እንዲሁም ሰዉነታቸዉን በተጣበበና ወተወጣጥረ አለባበስ ለብሰዉ የተለየ እንደሆነ በመቁጠር ለዓለም እያስተዋወቁ የሚሄዱትን ሳይሆን፤ የከበረ ገላቸዉን አክብረዉ በክብር ሸፍነዉ የሚሄዱትን እናትና እህቶቻችሁን ነዉ፡፡ ሌላዉ እህቶቻችንን ለዚህ አለባበስ ተጽህኖ የዳረጋቸዉ በወንዱ ኅሊና ዉስጥ የነገሠዉ የዝሙት መንፈስ ነዉ፡፡ ይኸዉም ይህ መንፈስ የሚፈልገዉና ለዐይኑ እይታ የሚወደዉ የተገላለጠ አለባበስና የተወጣጠረ አካልን ነዉ ፡፡ በዚህም ምክንያት ሴቱም ወንዱም ይህን ቅርፊትና በስባሽ ሥጋን እያስመለከዉና እያመለከዉ ይገኛል፡፡

እነዚህ እህቶቻችን እዉነተኛ የነፍስ እረኛ ቢያገኙ ኖሮ የአህዛብን (እግዚአብሔርን የማያመልኩ ሰዎችን) አለባበስን አይለብሱም ነበር፡፡ እንደቀደሙት ወላጆቻቸዉ እግዚአብሔር መፍራት ያለበት ኢትዮጵያዊ አለባበስ እንደሚለብሱ እገምታለሁ፡፡ አሁን ግን እንኳን በዓለም ያሉት አይደለም በቤተክህነትና በሃይማኖት አገልግሎት ቦታ ያሉ ጸሐፊዎችና ሰራተኞች ጭምር ለመቀጠር መስፈርቱ የራቁትነትና ጥብቅብቅ ያለ ልብስ መልበስ እስኪመስል ድረስ በዚህ አለባበስ አባቶች ፊት እየገቡ ይወጣሉ፡፡ ስለዚህ በዉጭ ያሉት ላይ ብዙ ለመፍረድ

ይከብዳል:: ነገር ግን አላስተዋሉም እንጂ ስለአህዛባዊ አለባበስና ወንዶችን በኀሊናቸዉ ዝሙትን በመመኘት እንዲረክሱ በማድረጋቸዉ ንስሐ ገብተዉ አለባበሳቸዉን እስካላስተካከሉ ድረስ ይጠየቁበታል፤ ዋጋም ይከፈሉበታል:: እንዲሁም የዝሙት መንፈስ በኀሊናዉ እንዲነግሥበት የፈቀደ ወንድ በተግባር እንኳ ባይፈጽም በኀሊናዉ ስለመርከሱ ንስሐ እስካልገባና ወደ ኀሊናዉ የሚመጣበትን የዝሙት መንፈስ እስካልተቃወመዉ ድረስ ይጠየቅበታል፤ ዋጋም ይከፈልበታል:: ስለዚህ እናንተም ሆናችሁ እኛ ትዉልዱ እግዚአብሔር መፍራት ያለበትን አለባበስ እንዲለብስ ማስተማርና መጸለይ ይጠበቅብናል::

እዚህ ላይ ታዲያ ወላጆቻችሁ ለዚህ ጨዋ አለባበሳችሁ አስተዋጽኦ እንዳደረጉላችሁ በሚገባ ልታስተዉሉ ይገባል:: ምክንያቱ በህጻንነታችሁ ሆነ ከፍ ስትሉ ሌሎች በዚህ አህዛብ አለባበስ ሰዉነታቸዉን ገላልጠዉና ወጣጥረዉ ሲሄዱ የስልጣኔ መለያ አድርጋችሁ እናንተም በእነሱ አለባበስ ትገለጹ ነበር:: ነገር ግን ወላጆቻችሁ ቁጥጥር ስላደረጉባችሁና የከበረዉ ገላ(ሰዉነት) የሚቀልበትና የሚራከስበት አለባበስ መሆኑን ስላስተማሯችሁ ነዉ ከዚህ ቅጥ ያጣ አለባበስ ልትጠበቁ የቻላችሁትና እናንተም ለወላጆቻችሁ ታዛዥ ሆናችሁ በመገኘታችሁ ለዚህ ጨዋ ስርዐት ያለዉ አለባበስ የበቃችሁት:: እናንተም ልጆቻችሁንና እህቶቻችሁን እግዚአብሔር መፍራት ባለዉ አለባበስ እንዲገለጹ ማስተማርና አሁን አዉሮፓዉያንንና አሜሪካዉያንን ለመምሰል የሚደረገዉ የራቁትነትና ገላን የማስመልከ እንዲሁም ራስን ወደ ጣዖትነት የመለወጥ አለባበስ የዉርደትና የዉድቀት አለባበስ መሆኑን ልታስተምሯቸዉ ይገባል:: ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያዉያን እስከሆናችሁ ድረስ የኢትዮጵያዊነት አለባበስ ቢለብሱ የበለጠ የማንነታቸዉ መገለጫና መከበሪያ እንደሚሆንም ልታስረዷቸዉ ይገባል::

እናንተ ገበናችንን ለመሸፈን ብትሞክሩም ያለዉን፣ የሚታየዉን፣ ሊስተካከልና ሊታረም የሚገባዉን በግልጽ እነግራችኋለሁ:: ይኸዉም ይህ ቅጥ ያጣ አለባበስ በአንዳንዶች ወደ ቤት ክርስቲያን በሚመጡ እናቶችና እህቶች ላይ ይታያል:: ምክንያቱም በዘልማድ ስለሚመላለሱ፣ ወደ ቤተክርስቲያን የመጡበትን ዓላማ ባለማስተዋልና እንዳንዶች ደግሞ ደንታ ቢስ በመሆንና በመዳፈር በታይት፣ በሱሬ፣ በአጭር ቀሚስ፣ የዉስጥ ገላን በሚያሳይ አለባበስ የሚገቡ የሚወጡ አሉ:: እነሱ ገላቸዉን እያመለኩና እያስመለኩ ይመስላቸዋል እንጂ የከበረ ገላቸዉን እያቃለሉት መሆኑን አላስተዋሉትም:: እንዲሁም በእያንዳንዱ ሰዉ ኅሊና ሴት ተቀን የሚፈታተኑት ርኩሳን መናፍስት ስላሉ እያንዳንዱ ወንድ በአለባበሳቸዉ በመፈተን በተግባር እንኳ ባይረክስ በኅሊናዉ እንዲረክስ ያደርጉታል:: ታዲያ ይህ ለዝሙት የሚያነሳሳ አለባበስ በዋናነት የሚጠቀመዉ ለሰዎች ጥፋትና ዉድቀት ለሚተጉት ለሰይጣናት ነዉ::ምክንያቱም ወደ ሴት ተመልክቶ ለዝሙት የሚመኝ ሰዉ በተግባር ባይፈጽመዉ እንኳ በአሳቡ ረክሷልና ፍርዱ እንደተግባሩ ባይከብድም በኅሊናዉ እስካልተጸጸተበት ድረስ በፍርድ ቀን ይጠየቅበታል::

ያሰናከለዉም ሰዉ የሰይጣናት መሳሪ በመሆኑ በተግባር ባያስፈጽም እንኳ ይጠየቅበታል። የዚህን ያህል የእግዚአብሔር ፍርድ ጥበቅ መሆኑን ሁሉም ሰዉ ሊያዉቅ ያገባል።

ታዲያ ትዉልዱ የእግዚአብሔርን ቃል አስተዉሎ ቢሆን ኖሮ እንኳን በተቀሰደሰዉ ስፍራ ቀርቶ በዓለም ላይ በዚህ አለባበስ አይሄድም ነበር። አሁን ግን በዓለም ቀርቶ በእግዚአብሔር ቤት ሳይቀር የዲያብሎስ ስርዐትና የአህዛብ ስርዐት ስለነገሠ የከበረዉ ገላ ተገላልጦና ተወጣጥሮ፤ ተራክሶና ተዋርዶ በየቦታዉ ይታያል። እናንተ አሁን እኔጋ ስትመጡ ሁላችሁም ከአናታችሁ እስከ እግራችሁ ድረስ ገላችሁን በሚያስከብር አለባበስና ወንዶችን ለዝሙት በማያነሳሳ እግዚአብሔር መፍራት ያለበት አለባበስ ነዉ የቀረባችሁት። ይህ ደግሞ ፈጣሪን ማክበርና መዉዳድ እንዲሁም ለሰዉ ማሰናከያ አለመሆንን መምረጣችሁን ያሳያል። አሁንም እንደገና የምላችሁ እናንተ የሚቀራችሁ አረባዊ አልባበሳችሁን ወደ ኢትዮጵያዊ አለባበስ መቀየር ብቻ ነዉ እንጂ አሁን የሚታየዉ አለባበሳችሁ የጨዋ አለባበስ ነዉ።

ሌላዉ ደግሞ ለወደፊት ወደ ሕይወት መንገድ ዉስጥ እንደምትገቡ ተስፋ ስለማደርግ አንዳንድ ወንዶችና ሴቶች በቤተ ክርስቲያን በተለያየ መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ የተሰማሩ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች እንደ አፍኒንና ፊንሐንስ በእግዚአብሔር ቤት ሳይቀር ርኩሰትን በመፈጸምና በማስፈጸም፣ በመዳራት፣ በዝሙት፣ በስርቆት፣ በማጣላት፣..ወዘተ ሕይወት ከመመላለስ ወደ ኋላ የማይሉ ኀሊናቸዉን ያደነደኑ ሰዎችን ብትመለከቱ ስሜታችሁ እንዳይጎዳ። እኛ ለእዉነተኛ ንስሐ እንዲበቁ ነዉ ጸሎታችን፤ እግዚአብሔር ግን ታግሶ ታግሶ ከቤቱ እንደሚያጸዳቸዉና በምድርም ሆነ በሰማይ ስለ ድፍረት ኃጢአታቸዉ ዋጋ እንደሚያስከፍላቸዉ ይታወቃል።

ሰባተኛ ጥያቄያችሁ «አንዳንድ ሴቶች ወንዱን መጨበጥ እንደመርከስ ይቆጥራሉ። ይህ በእናንተ ዘንድ በምን መልኩ ነዉ የሚታየዉ?» በማለት ለጠየቃችሁት ያለኝ መልስ: ጥያቄያችሁ ያስታወሰኝ ነገር ቢኖር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዉ ሆኖ በምድር በተገለጸበት ዘመን በሚያስተምርበት ወቅት የነበሩ የጻፎችና የፈሪሳዉያን እንዲሁም የአይሁድ ካህናትና አለቆችን ሕይወት ነዉ። እነዚህ ሰዎች እግዚአብሔርን እናመልካለን የሚሉ ነገር ግን ትዕዛዙን የማይጠብቁና ሕጉን የሚሽሩ ናቸዉ። ታዲያ የሚቆረቆሩት ለወግ ልማዳቸዉ ነዉ እንጂ ለእግዚአብሔር ሕግ አልነበረም። በዚህም ምክንያት ራሳቸዉ በፈጠሩት ወግና ስርዐት ሕዝቡን ያስጨንቁ ነበር። ታዲያ በዝሙት፣ በስርቆት፣ በጥል፣ በክፋት፣ በሴሰኝነት ፣ በስድብ፣ በተንኮል፣ በቅናት ባጠቃላይ በሚረክሱበት ሕይወት እየተመላለሱ እነሱ ግን በእጅ ሳይታጠቡ መብላት እንደመርከስ ነበር የሚቆጥሩት።

ከሁሉ በላይ አሳዛኝና አስገራሚ ተግባራቸዉ ደግሞ፤ የሙሴ አምላክ የሰንበት ጌታ እዛዉ አጠገባቸዉ ሆኖ ለዘመናት (ለዓመታት) በአልጋ ቁራኛ በደዌ ዳኛ ተይዘዉ የነበሩትን በእለተ ሰንበት ስለፈወሰ፤ ያ ለሰላሳ ስምንት ዓመት በአልጋ ተኝቶ ከአልጋዉ ጋር ተጣብቆ ሲማቅቅ የነበረዉን እንዲሁም እድሜ ልካቸዉን ሰዉነታቸዉ ታሞ የነበሩት በሽተኞች ስለተፈወሱና ከታሰሩበት አጋንንት ስለተፈቱ፣ ነጻነትን ስላጋኙ የነሱ መፈወስና መዳን አንዳች ስሜት ሳይሰጣቸዉ አስመሳይ አገልጋዮች ነበሩና « ሰንበትን ሻረ፡፡ የሙሴን ሕግ ጣሰ፡፡ ከእግዚአብሔር አይደለም፡፡» በማለት ሊገሉትና በሐሰት ሊወነጅሉት ሁል ጊዜ ሲሹ እሱ በፈቀዳት ቀን ሁሉ ተሳክቶላቸዉ አሰቀሉት፡፡ እነሱ ግን ከእንስሳታቸዉ አንዱ በጉድጓድ ዉስጥ ቢወድቅ የሚያነሱ ከስብራት ሆነ ከሞት የሚያድኑ ናቸዉ፡፡ ነገር ግን ለትልቁ ሕያዉ ፍጡር ለሰዉ ደንታ የሌላቸዉ ጨካኞች ነበሩ፡፡ የድፍረታቸዉ ድፍረት ደግሞ ለስም አጠራሩ ክብር ምስጋን ይግባዉና « ይህ በብዔል ዜቡል በአጋንንት አለቃ ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም» በማለት ይሰድቡትና ስሙን ያጠፉ ነበር፡፡ አሁንም ለሰዎች መፈወስና መዳን ፣ ከአጋንንት እስራት መፈታት አንዳች ደንታ የሌላቸዉ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ እንከን እየፈለጉና ቃላት እየሰነጠቁ የእግዚአብሔርን አገልጋዮች የሚያሳድዱ፤ የእዉነት እንቅፋቶች፣ እዉቀታቸዉን የሚያመልኩ፣ ገበናቸዉ እንዳይጋለጥ ሌት ተቀን ከእግዚአብሔር የሆኑትን ለማሳደድ የሚተጉ ዳግማዊ ጸሐፎች፣ ፈሪሳዉያን ፣ የካህናት አለቆችና ካህናት ሞልተዋል፡፡

እነዚህ እዉቀታቸዉን የሚያመልኩና የሚያስመልኩ እንዲሁም ራሳቸዉን ንጹህና ቅዱስ አድረገዉ በመቁጠር ከእግዚአብሔር የሆነዉን ሙሉ እዉነታ መቀበል አይደለም መስማት የማይፈልጉ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች፤ አሁን ለእናንተ በእዉነትና በቅንነት የምናጋረዉን ንግግር « እግዚአብሔር በዚህ ሰዉ ላይ አድሮ ምን ይናገረኛል፣ ምን ያስተምረኛል፣ ምንይመክረኛል፣ እንዴት አድርጎ እየገሰጸኝ ነዉ?» በማለት ኅሊናቸዉን ከክፋትና ከተንኮል አጽድተዉ በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ፥ በቅንነት እየመረመሩ ከመስማትና ከመጠቀም ይልቅ « ይህን ሰዉ በምን እናጥምደዉ፣ እንዴት አድርገን ከሥጋዊና ከመንፈሳዊ መሪዎች እናጣላዉ፣ ከምእመኑና ከሕዝቡ እንዴት አድርገን እንለየዉ፣ እናጣላዉ፣ እንዴት አድርገን እናስወነጅለዉ?» በማለት ለጥፋትና ለዉድቀት ነዉ ራሳቸዉን የሚያዘጋጁትና ራሳቸዉም ተሰናክለዉ ሌላዉንም የሚያሰናክሉት፡፡ ታዲያ ፍርዱ ከማንም በላይ እንደ ጸሐፍት ፈሪሳዉያን ይብስባቸዋል፡፡

ወደ እጅ መታጠቡ ልመለስና እነዚያ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች ከክርስቶስ ጋር ከነበሩ ሰዎች ዉስጥ እጃቸዉን ሳይታጠቡ ሲበሉ አይተዉ « ዘራፍ አካኪ እንዴት ሕጋችን ይሻራል? በደለኞች ኃጢአተኞች ናቸዉ፡፡» በማለተ ሲያሳጧቸዉና ኢየሱስ ክርስቶስም የሙሴ

ተቃዋሚ አድርገዉ ነበር ይናገሩ የነበረዉ። ነገር ግን ክርስቶስ ሰዉን የሚያረክሱት «ክፉ አሳብ፣ መግደል፣ ምንዝርነት፣ ዝሙት፣ መስረቅ፣ በዉሸት መመስከር፣ ስድብ.. የመሳሰሉት ናቸዉ።» በማለት አስተማራቸዉ እንጂ ታጥቦ አለመብላት እንዳማያረክስና ኃጢአተኛ እንደማያስብል በማስረዳት ወጋቸዉ የእግዚአብሔር ሕግ እንዳልሆነ መስክሮባቸዋል። አሁንም እጅ ታጥቦ መብላት ለንጽህናና ለጤና ጠቃሚ መሆኑ ቢታመንበትም ለጽድቅና ኩነኔ የሚያበቃ አይደለም። ብዙዎቻችን ዋንኛ የኃጢአት ተግባር ቦታ ሳንሰጠዉ እንደዚህ ለመሳሰሉ ለሰዎች ወግና ስርዐት ነዉ ትኩረት የምንሰጠዉ። ለኩነኔ የሚያበቃዉን፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ስንሽር ምንም አያመስለንም፤ የራሳችን ወግ ግን ከእግዚአብሔር ሕግ በላይ አድርገን ነዉ የምንቆጥረዉ።

ብዙዎቻችን መንፈሳዊ ሕይወታችንን በዘልማድ ነዉ የምንመራዉና የምንኖረዉ። አንዳንድ ሁኔታዎችን ብንመለከት: ወላጆቻችንንና ቤተሰባችንን እየበደልንና እያሳዘንን ወደ ቤተ ክርስቲያን ብንመላለስ፣ ጸሎትና ምስጋና ብናቀርብ ምን ዋጋ እናገኛለን? እግዚአብሔር፤ ወላጆቻችንንና ቤተሰባችንን እያሳዘንና እየበደልን የምናቀርበዉን መስዋዕት ይቀበላልን? እንኳን የቅርቦቹን ቤተሰብ አይደለም ማንኛዉንም የአዳም ዘር እያሳዘንና እየበደልን ለእግዚአብሔር ተገዥ ነን፤ ፈቃዱን እንፈጽማለን እናስፈጽማለት ማለት እንችላለን? አንችልም። በሚታየዉ ነገር ታምነን በእዉነትና በቅንነት ካልተመላለስን እንዴት የማናየዉን እግዚአብሔርን ልናስደስትና ፈቃዱን ልንፈጽም እንችላለን? አንችልም። እጅግ ብዙዎቻችን የማስመሰል ሕይወትና እንደ ጊዜ ማሳለፊያና ለኑሮ መደጎሚያ ካልሆነ በስተቀር መንፈሳዊነቱ ሳይገባን በሥጋና በደም ስሜታችን ነዉ የምንወጣዉ፣ የምንገባዉ፣ የምናገለግለዉ። አንድነትና ሕብረት የሌለን በኃጢአት ተግባር ነዉ እንጂ ከዚያ ዉጭ ግን ከቤተሰባችን ሆነ ከወላጆቻችን እንዲሁም ከማንኛዉ ሰዉ ጋር በፍቅር፣ በሰላም፣ በመተሳሰብ፣ በመረዳዳት፣ በመተዛዘን፣ በቅንነት ፣ በእዉነተኛ ሕይወት ነዉ መኖር ያለብን።

በኃጢአት ተግባርም ቢሆን በሥጋና ደም ስሜት በግብታዊነትና በትዕቢት ሕይወት በመኮነንና በመወንጀል ሳይሆን በእዉነተኛና በቅንነት አእምሮ በተረጋጋ ሁኔታ በማስተማር፣ በማስረዳት ከዚያ ሕይወት እንዲለዩ ማድረግ ነዉ የሚጠበቅብን እንጂ ባለማወቅ ኃጢአቱ፣ ክህደቱ፣ ምንፍቅናዉ፣ ዐመጻዉ እንደ ትክክልና እዉነት እንዲሁም እንደታላቅ ተግባር ቆጥረዉ የሚመላለሱ ብዙ ወገኖች አሉና ከኛ የሚጠበቀዉ እንክርዳድ ያልተደባለቀበት፣ የሥጋና ደም ስሜት ያልተቀየጠበትን የእግዚአብሔርን ሙሉ እዉነታ ብቻ ማሳወቅ ነዉ የሚጠበቅብን። የእግዚአብሔር ሙሉ እዉነት ተገልጾለት «አልቀበላችሁም» የሚል ሰዉ ካለ፤

እርሱ እግዚአብሔር ተገልጾ ቢናገረዉም አይቀበልምና ከትዕቢት( ከፈርኦን ወንድምና እህት) ፣ ወይንም ከክፋት (ከይሁዳ ወንድምና እህት) ፣ ወይንም ከዐመጻ (ከአርዮስ ወንድምና እህት) አንዱ መሆኑን ልታዉቁና ልታስተዉሉ ይገባችኋል::

እናንተ አሁን ያላችሁትም ወገ ሰዎች በሥጋና ደም ስሜት ሆነዉ የፈጠሩት እንጂ ሰዉ ሰዉን በመጨበጡ አያረክስዉም:: ኃጢአትም ሆነ ርኩሰት በመጨባበጥ አይተላለፍም:: ይልቁኑ ሰዉን መጸየፍ ነዉ በደልና ኃጢአት የሚሆነዉ:: ምክንያቱም አንድ ሰዉ ግብረስጋ ግንኙነት አድርጓል ወይንም ኃጢአት ፈጽሟል በሚል ስሜት ሰዉን ማግለል የራስን ማንነት አለማወቅ ነዉ:: እንኳን እግዚአብሔር የፈቀደዉ በጋብቻ የሚፈጸም ግብረ ሥጋ ግንኙነት ሰዉን ማርከስ አይደለም፤ ኃጢአትን የፈጸመ ሰዉ ቢጨብጠን አንዳች አያረክሰንም:: በመሆኑም እናንተም ሆናችሁ ሌሎች በሰዎች ወግ ሳይሆን መመራት ያለባችሁ የምታመዛዝንና የምታገናዝብ ኅሊናችሁ በእዉነትና በመንፈስ መርምራ በምትቀበለዉ ልማድና ስርዐት ነዉ መጓዝ ያለባችሁ::

ከልማድና ከስርዐት ጋር የገጠመኝን ልንገራችሁ:: አንዲት እህት ንስሐ ትገባላች፤ ስለ ኃጢአቷም ትጸጸታለች፤ በመጨረሻም የታዘዘችሁን ቀኖና ከጨረሰች በኋላ « በአዲስ አገር ባህል ልብስ ቁረቢ::» ተብላ ነበርና ምንም እንኳን ቀደም ብሎ ነጭ የአገር ልብስ ቢኖራትም « በአዲስ» ስለተባለች በወቅቱ መግዣ ገንዘብ ስላልነበራት ስለ ጨርቅ ሲባል ዋናዉ ሕይወትን ከሚሰጠዉ መብልና መጠጥ ተከልክላለች:: ምንም እንኳን ከቅዱስ ቁርባን ስርዐት በላይ የከበረ ስርዐት በዚህ ምድር ዉስጥ ባይኖርም ሰዉ እንደአቅሙና ኑሮዉ መኖር አለበት :: መቸስ በአገራችን ባህል ጋብቻ ትልቅ ቦታ አለዉና በሰርግ ጥሪ ቦታ ላይ ያለንን ጥሩ ልብስ ለብሰን እንደምንገኝ ሁሉ ከሱ እጅግ የከበረዉ ቅዱስ ቁርባን ላይ ስንገኝ ደግሞ የበለጠ ንጽህናችንን ጠብቀን ያማረዉን ነጭ የአገር ልብስ ለብሰን መገኘት ይኖርብናል:: ነገር ግን አቅሙ የማይፈቅድለት ሰዉ ያላቸዉን የተጣፈች ልብስ ብትሆን እሷን አጥቦና ንጽህናዉን ጠብቆ ሊቀርብ ይገባዋል እንጂ «አዲስ ልብስ ካለበስኩ ንስሐዬ ዋጋ አይኖረዉም፣ ቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙን አልቀበለም» የሚልና የሚያዝ ሰዉ ልብሱን ከቅዱስ ቁርባን በላይ ክብር ሰቶቷል ማለት ነዉ:: ይህም የተሳሳተ አስተሳሰብ ነዉ:: አንዳንድ አገልጋዮችና ምእመን ዋናዉን ኃጢአት ቦታ ሳይሰጡና እንደኃጢአት ሳይቆጥሩ ወግና ልማዳቸዉን ግን ከእግዚአብሔር ሕግ በላይ የሚያደርጉ አሉ::

ከዚህ ጋር የሚዛመድ ገጠመኜ ደግሞ አንዳንድ አገልጋዮችና ምእመን ከቆረቡ በኋላ አፍ በጨርቅ ግጥም ተደርጎ ካልተያዘ እንደ ሕግና ስርዐት መጣስ ይቆጥራሉ:: ያ አፍ በጨርቅ እንዲያዝ የተፈለገዉ ዋናዉ ምክንያት ምግብ ከመቀመሱ በፊት ወደ አፍ ዉስጥ

ምንም ነገር እንዳይገባ ለመከላከል እንጂ የቀረቡት አገልጋዮች ካህናትና ዲያቆናት ከቀረቡ በኋላ ይናገሩ፣ ይቀድሱ፣ ይዘምሩ፣ ያስተምሩ የለም ወይ? ሕግ መጣስ ስርዐት ማፍረስ ቢሆን ኖሮ እነሱም አፋቸዉ እንደታፈነ ምግብ እስኪቀምሱ ድረስ ይቆዩ ነበር፡፡ ታዲያ አንድ ቀን አንድ ምእመን ቅዱስ ቁርባን ከተቀበለ በኋላ አፉን በጨርቅ ሳያፍን ዝም ብሎ ተቀምጦ ኖሮ አንድ ካህን ያዩትና በቁጣና በግሳጼ አፉን በነጠላዉ እንዲሸፍን ያደርጉታል፡፡ ነገር ግን ይህ ንስሐ ገብቶ ለታላቅ ክብር የበቃዉ ሰዉ ሊበረታታ፣ ሊመረቅ ሲገባዉ ተቃራኒ ግሳጼና ቁጣ ሊደርስበት አይገባም ነበር፡፡ ታዲህ ተናጋሪዉና ገሳጩ ካህን ራሳቸዉ ቆራቢ ነበሩ፡፡ በእሳቸዉ አስተሳሰብ እሳቸዉ  ሕግና ስርዐት መጣስ ይችላሉ፣ ምእመናን ደግሞ አይችሉም ማለት ነዉ፡፡

ሌላዉ ገጠመኝ አንድ ቀን ቤተክርስቲያን ቅዳሴ እየተቀደሰ አንድ በወጣትነትና በጎልማሳነት እድሜ  ያለ፣ አግልግሎቱ ምን እንደሆነ የማይታወቅ ብዙዉን ጊዜዉን በአንድ ገዳም ወይንም በአንድ ቦታ ተወስኖ መኖር ያልቻለ፣ ከአንዱ ገዳም ወደ አንዱ ገዳም፣ ከአንዱ ቦታ ወደ አንዱ ቦታ ዝም ብሎ የሚንቀሳቀስ አንዳች ምስክርነትን ሆነ አገልግሎት የማይሰጥ ሰዉ፤ ምስባክ እንዳለቀ የእለቱን ወንጌል ካህኑ በኢትዮጵያዉኛ(በአማርኛ) ቋንቋ ሲያነቡ «ዘራፍ አካኪ ምን ጋዜጣ ያነብብናል» በማለት ሲናገር አጠገቡ ያሉት አንድ አገልጋይ ሲቆጡት ወዲዉ « ድብድብ ይዞ የተቀደሰዉን ቦታ ደም በደም አደረጉት፡፡ ያ «ምን ጋዜጣ ያነበንብብናል » ያለዉ ሰዉ በእርሱ ቤት ለሃይማኖቱ ተቆርቋሪ መስሎ «ለምን በግእዝ አይነበብም?» ለማለት ፈልጎ ሲሆን፤ የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ ደግሞ አንዳች ግእዝን የማያዉቅ መሃይሙ መሆኑ ነዉ፡፡ ይህ ሰዉ ስለነፍሳት መዳን አንዳች ስሜት የሌለዉ ራሱንም ምእመኑን ለመግደል ቆርጦ የተነሳ ነዉ እንጂ ምእመኑ በሚሰማዉ ቋንቋ እንዲማር መደረጉ ምእመኑ የሚያምነዉን እምነት እንዲያዉቅና ለመልካም ስራና ለእዉነተኛ ሕይወት እንዲነሳሳ እንዲሁም ለንስሐ ለቅዱስ ቁርባን እንዲበቃ የሚያደርገዉ ነዉ እንጂ ሃይማኖትን የሚያጠፋና የሚጎዳ አይደለም፡፡ ይልቁኑ ምእመኑ ማንነቱን ሲያዉቅ የሕይወትን መንገድ ሲያስተዉል  ለቋንቋዉ በመቅናት ግእዝን ለመማርና ለማወቅ ይሰለፋል እንጂ ማንነቱንና የሕይወትን መንገድ ሳያስተዉል እንዴት ለቋንቋዉ ትኩረት ሰቶት ለማወቅና ለመማር ይነሳሳል!?

እኛ ኢትዮጵያዉያን ነን ግእዝ ቋንቋችንን እያጥላላነዉና እየናቅነዉ ያለነዉ እንጂ ኢትዮጵያዉያን ያልሆኑት የዉጭ አገር ሰዎች ለቋንቋዉ ትኩረት በመስጠት በመካነ አእምሮ(በዩኒቨርስቲ) ደረጃ እንደ ቋንቋ ራሱን ችሎ ትምህርት ይሰጥበታል፡፡ የሚያሳዝነዉና የሚያስገርመዉ ደግሞ በባለቤቶቹ ኢትዮጵያዉያን ዘንድ እንኳን በኮሌጅና በዩኒቨርስቲ ደረጃ

ሊሰጥ ቀርቶ በመለስተኛና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርቤት እንኳ አይሰጥም። ይልቁኑ ኀሊናችን በዲያብሎስ ፍልስፍና በፖለቲካዉ እንዲበከልና እንዲመረዝ ስለተደረገ ለማጥፋትና ለማጥላላት እንዲሁም ለማናናቅ ነዉ የተሰለፍነዉ። ይህ ደግሞ በተለየ በሥጋዊዉ ሆነ በመንፈሳዊ የእዉቀት ደረጃ ከፍ ያለ ማእረግ ላይ የደረሰን ሰዎችን ግምት ዉስጥ የሚጥለንና ተጠያቂም የሚያደርገን ነዉ። ምክንያቱም የዉጭ ምሁራን ትኩረት ሰተዉት ቋንቋን ለማወቅና ለማሳወቅ ጥረት ሲያደርጉ እኛ የጨለማዉ ገዥ የዲያብሎስን ስራ ለመስራትና ለማስፈጸም የምንተጋዉን ያህል ግማሹን ጥረት ለቀደምት ቋንቋችን አንዳች ትኩረት ሰተን ትዉልዱ እንዲያዉቀዉ ባለማድረጋችን ነዉ።

ባጠቃላይ ሲታይ ከላይ በገጠመኝ መልክ እንደገለጽኩላችሁ ብዙዎቻችን እደዚህ በመሳሰሉ አስተሰሰቦች ኀሊናችን ተተብትቧል። «የቱነዉ ለጽድቅና ለኩነኔ የሚያበቃዉ? የቱነዉ ስርዐት? የቱ ነዉ ወግና ልማድ?» የሚሉትን በሚገባ መለየት አልቻልንም። ስለዚህ እናንተም ለወደፊት እንደዚህ ነገሮች ቢያጋጥሟችሁ ባለማወቅ ስለሆነ እንዳይሰማችሁ፣ ተስፋም እንዳትቁርጡ ሁሉን በትዕግስት ማሳለፍ ይኖርባችኋል። ከዚህም በላይ በእዉነተኛዉ በእግዚአብሔር ቤት ፈተና ሊያጋጥማችሁ ይችላል። እንደዚህ አይነት የወግና የልማድ ሕይወት አገልጋዩ ሆነ ምዕመኑ የእግዚአብሔርን ቃል ሲያስተዉልና በእዉነትና በመንፈስ አምላኩን ማምለክ ሲጀምር ይተዋል የሚል እምነት አለኝ።

አንዳንዶቹ ደፋር እግዚአብሔር መፍራት አንዳች የሌለባቸዉ «አገልጋይ ነን» ባዮች ከነጫማቸዉ ወደ ቤተክርስትያን ዉስጥ እየገቡ ራሳቸዉ ስርዐት አፍራሽ እየሆኑ ሌሎቹን ስርዐት አታፍርሱ የሚሉ አስመሳይ ሰዎች ሊገጥሟችሁ ይችላልና እናንተ እነሱን አትምሰሉ። መጠበቅ ያለበትን ስርዐት እነሱ ባይጠብቁትም እናንተ መጠበቅ ይኖርባችኋል። በእነርሱ ላይ ፍርዱ እጅግ ይብሳል። በዚሁ የታዘብኩትን ልንገራችሁ፤ አንዳንድ አገልጋዮች ምዕመኑን በቤተክርስቲያን ዉስጥ ተንቀሳቃሽ ስልካችሁን (ሞባይላችሁን) አጥፉ እያሉ እነሱ ግን አለማጥፋት ብቻ አይደለም ያወሩበታል። ይደዉሉበታል። ምእመኑም ይህን እያየ በመደፋፈር የአምልኮቱን ቦታ የሁከት ቦታ አስመስለዉት ቅዳሴዉን፣ ዝማሬዉን፣ ጸሎቱን፣ ስብከቱን፣ በዘፈንና በመዝሙር ያዉካሉ።

አገልጋይ ሆን ምእመን፤ እግዚአብሔርን ምን ያህል እንደናቅነዉና በዘልማድ ሕይወት መኖራችንን የሚያሳየዉ በአንድ ባለስልጣን ሆነ ኃላፊ ቢሮ ስብሰባ ስናደርግ ስልካችንን እናጠፋለን ወይንም ድምጽ አልባ እናደርገዋለን። በእግዚአብሔር ቤትና በመንፈሳዊ መድረኮች ላይ ግን እንደተራ ቦታና ተግባር ቆጥረን እንኳን ማጥፋትና ድምጽ አልባ ማድረግ አይደለም በጩኸት አገልግሎቱን ሲረብሽ ደንገጥ የማንል የምናወራና የምናሶራ ሰዎች ነን። ይህ

የሚያሳየዉ በሚታይና በሚጨበት ብቻ የምናምን ቁሳዉያን መሆናችንንና በቤተክርስቲያን ሆነ በመንፈሳዊ መርሐግብር ላይ የምንገኘዉ በዘልማድና ለጊዜ ማሳለፊያ መሆኑን ነዉ፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ለመነጋገር፣ ለማመስገን ፣ ቃሉን ለመማር ቢሆን ኖሮ ቢያን ቢያንስ የምድረዊ ባለስልጣን ስብሰባ አክብረን በስርዐት እንደምንገኝ ሁሉ በእግዚአብሔት ቤትና ቃሉ በሚሰበክበት ቦታ ሁለንተናችንን ሰብስበን እንገኝ ነበር፡፡ እንኳን በእግዚአብሔር ቤት ቀርቶ የተለየ መርሐግብር በሚከናወንበት ቦታ ቢያንስ ቢያንስ ድምጹን ልናጠፋ ይገባል እንጂ ጎሊናችንን ደንዳናና ለሰዉ ስሜት ደንታቢስ መሆን የለብንም፡፡ በደንዳናነታችንና በደንታቢስነታችን በእግዚአብሔር ዘንድ ሆነ በሰዉ ሰንድ የምንቀለዉና ግምት ዉስጥ የምንገባዉ እኛዉ ነን፡፡

ስምንተኛዉ ጥያቄያችሁ «በአሁን ሰዐት አንዳንድ የሃይማኖት አባቶችና መምህራን ሲያስተምሩና ሲሰብኩ - ክርስቲያኖች እንዲህ በደልና ግፍ ፈጽመዉባችኋል፡፡ የእነዚህ አገር ዜጎች እንዲህ ፈጽመዉባችኋል፡፡ እነዚህ ዜጎች ከምድረ ገጽ መጥፋት አለባቸዉ» እያሉ ለጥላቻና ለበቀል እያነሳሱን ነዉ፡፡ በዚህ ትምህርታቸዉ እኛም ሆን ቤተሰቦቻችን ዉስጣችን ቂም ይዞ ለበቀል ወቅትና ጊዜ ነዉ የምንጠብቀዉ፡፡ ይህ አስተሳሰባችን ትክክል ነዉ አይደለም? ለሚለዉ ያሎትን አስተያየት እንዲሰጡን?» ላላችሁት የሚኖረኝ መልስ፡

በዚህ ግልጽነታችሁና የዋህነታችሁ እግዚአብሔር እዉነታዉን ሊያሳዉቃችሁ እንደወደደ አምናለሁ፡፡ በዚህች ፈተና በሞላባት ዓለም አይደለም ምንም ተጽህኖ በሌለበት ገነት ዉስጥ በቅዱሳን መላእክት አኗኗን ይኖሩ የነበሩት የመጀመሪያ የገነት ፍጡሮችና የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት አዳምና ሔዋን እንኳ እግዚአብሔርን ለመሆን ስለፈለጉ በምኞት ተሸንፈዉ «አትብሉ» የተባሉትን ፍሬ በመብላታቸዉና ከገነት ተባረዉ በዚህች ጎስቋላ ምድር ዉስጥ ቃሉን ከሰሙትና ከተማመኑበት ዲያብሎስ ጋር በዚህ በግዙፉ ሥጋ ተገልጸዉ መኖራቸዉና ይህችም ምድር ለዚህ ሥጋዊ ኑሮ የሚያስፈልጉ ፍጥረቶች ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ መሬት፣ ዉኃ፣ አየር፣ እፀዋት፣ እንስሳት፣ አእዋፋት.. ወዘተ ባጠቃለይ በዐይን የሚታዩትንና የማይታዩትን ፍጥረታት ፈጥሮላቸዉ ከመሬት (ከአፈር) በተዘጋጀዉ ሥጋ ተገልጸዉ ሲቀጡና እኛም ልጆቻቸዉ በእነሱ ዐመጻ ምክንያት በሥጋ ተገልጸን እየተቀጣን መሆኑ ግልጽ ነዉ፡፡

ታዲያ በገነት እንኳ የመጀመሪያ ንጹህ ፍጥረቶች አዳምና ሔዋን ተሳስተዋል፡፡ በእግዚአብሔር ላይ ዐመጻና ክህደት ፈጽመዋል፡፡ በዚህች ምድር ዉስጥ ደግሞ የሰይጣናት ፈተና የረቀቀና የጠነከረ በመሆኑና ነፍሳችንም የተገለጸችሁ ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርይ በተላበሰዉ ሥጋ ስለሆነ ራሳችንን ካልገዛንና በሥጋና ደማችን ስሜትና ፍላጎት የምንመራ

ሕያዉ ነፍሳችንን እንደ እንስሳ ደማዊ ነፍስ አድረገን ከቆጠርን በኃጢአት ሕይወት እንመላለሳለን:: ዐመጽን፣ ግፍን ፣ በደልን፣ ርኩሰትን እንፈጽማለን:: ነገር ግን ስለ ድርጊታችን በሥጋችን በዚህ ምድር እያለን ዋጋ እንከፍልበታለን:: ከሁሉ በላይ ደግሞ ነፍሳችን ከሥጋችን ከተለየች በኋላ ነጻነታችን ተገድቦ እንደ ኃጢአታችን ደረጃ እንቀጣለን:: በተቃራኒዉ ደግሞ በቅን አሳብ፣ በመልካም ተግባር ከተመላለስን በዚህ ምድር እያለን ዋጋ እንቀበልበታል:: ከሁሉ በላይ ግን ነፍስ ከሥጋ ስትለይ እዉነተኛ ዋጋ ይከፈላታል:: ስለዚህ በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረች ነፍስ መሆን ያለበትንና የሌለበትን በማመዛዘን ነገሮችን ሁሉ መለየት ይጠበቅባታል::

ስለዚህ አሁን እናንተ «ወቅትና ጊዜ ነዉ የምንጠብቀዉ::» ብላችሁ ለበቀል መነሳሳታችሁን ትክክል መሆኑን አለመሆኑን የኅሊናችሁ ሕግ ይመሰክርላችኋል ወይንም ይመሰክርባችኋል:: ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ባሕርይ የተገኘች ሕያዉ ፍጥረት በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረች ስለሆነ፡

ሀ. በራሷ ጊዜ የምታስበዉ የራሷ መልካም ይሁን መጥፎ አሳብ አላት:: መልካም ከፈጸመች ተጠቃሚዋ ራሷ ናት:: በተቃራኒዉ መጥፎ ከፈጸመች ተጎጂዋና ተጠያቂዋ ራሷ ናት::

ለ. ሁል ጊዜ በሚመለከታትና በሚቆጣጠራት አምላክ በቀጥታ የሚነገራት መልካምና እዉነተኛ የሆነ አሳብ አለ:: ይህን የሚነገራትን ተግባራዊ ካደረገች የምትጠቀመዉ ራሷ ናት:: በተቃራኒዉ «እንቢ» ብላ ካልፈጸመች የምትጎዳዉና የምትቀለዉ ራሷ ናት::

ሐ.ገና ከህጻንነቷ ጀምሮ የሚፈታተናትና የሚከታተላት የእግዚአብሔር ተቃራኒ መንፈስ ሰይጣናት አሉ:: እነዚህ ሰይጣናት በቀጥታ እዛዉ ነፍሳችን (ኅሊናችን) ጋር ሆነዉ የሚናገሩን ክፉ አሳብ አለ:: ይህን ክፉ አሳብ ነፍሳችን ተቀብላዉ ወደ ተግባር ከለወጠችሁ ተጠያቂዋ ራሷ ናት:: በተቃራኒዉ በነጻ ኅሊናዋ ተመርታ ከተቃወመችሁና ወደ ተግባር ካለወጠችሁ አጥጠየቅበትም:: ይልቁኑ ከእግዚአብሔር ስለ ተቃዉሟ ጸጋ ታገኝበታለች::

ባጠቃላይ ከራሷ፣ ከአምላኳ፣ ከሰይጣናት የሚመጣላትን አሳብ በተፈጥሮዋ የመለየትና የማገናዘብ ሙሉ ነጻነት ስለተሰጣት የመቀበልም ያለመቀበልም የራሷ ምርጫ ነዉ:: መልካሙን ከመረጠች በምድርም በሰማይም ዋጋ ታገኝበታለች:: በተቃራኒዉ ደግሞ መጥፎዉን ከተቀበለችና ወደ ተግባር ከለወጠች በምድርም በሰማይም ዋጋ ትከፍልበታለች:: በመሆኑም ከእኛ የአዳም ዘሮች የሚጠበቀዉ ሁል ጊዜ በቅን አሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት ብቻ መመላለስ ነዉ::

ነገር ግን ከዚህ በተለየ ሕይወት « ክርስቲያኖች፣ እነዚህ አገር ዜጎች፣ እነዚህ አገሮች በደልና ግፍ ፈጽመዉብናል።» በማለት እናንተም ለግፍና ለበደል ከተሰለፉችሁ በተዝዋዋሪ « እግዚአብሔር ሆይ! እኛ ከአንተ በላይ ፈረጅ ነንና ጠላቶቻችንን እንበቀላለን፤ እናጠፋለን፤ እንዳልነበሩ እናደርጋቸዋለን።» ማለታችሁ መሆኑን ማወቅ ይኖርባችኋል። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር እናንተንም በመቶ እጥፍ ሊበቀላችሁ እንደሚችል ማወቅ አለባችሁ። ስለዚህ እያንዳንዱ አገር(መንግስት)፣ ቡድን ፣ ግለሰብ የዘራዉን ማጨዱ ስለማይቀር እግዚአብሔር ስለሁሉም እንደሚበቀል አዉቃችሁ እዉነተኛ ፍርድ እንዲፈርድ ለእርሱ ሁሉን አሳልፉችሁ ስጡ እንጂ ማንንም ሰዉ ለማጥፋት ወቅትና ጊዜ መጠበቁ ከእግዚአብሔር አይደለም። ስለዱሮዉ የሚያወሩላችሁን ደግሞ እናንተ በወቅቱ ስላልነበራችሁ በእርግጠኝነት ስለተደረገዉ መናገር አትችሉም። እንኳን ስለጥንቱ አይደለም አሁን ባለንበት ዘመን እንኳ እዉነተኛ በሐሰት ሲወነጀል ፣ ወንጀለኛዉ ደግሞ እንደታላቅ ጀግና ሲታይ እያየነዉ። በመሆኑም ሰዎች ለራሳቸዉ ዓላማ መጠቀሚያ ሰዎችን በጥላቻ አነሳስተዉ ግፍ ለማስፈጸም ሲፈልጉ ያልተደረገዉንና ያልተፈጸመዉን እንደተደረገና እንደተፈጸመ አድርገዉ ሊያቀርቡ እንዲሁም ነገሮችን እያጣመሙ በማቅረብ ለጥፋትና ለዉድቀት ሊዳርጓችሁ ይችላሉ።

እዚህ ላይ እንደምሳሌ ባቀርብላችሁ አሁን ያለዉ አህአዴግ መንግስት የዛሬ ሃያ አመት ገዳማ በሰማንያ ሶስት ዓ.ም. ወንበር ላይ ከወጡ በኋላ ሕዝቡን ለመከፋፈልና ለመለያየት ፈልገዉ በባለስልጣኖቻቸዉና በካድሬዎቻቸዉ አማካይነት በቴሌቭዥን፣ በሬድዮ፣ በሕትመቶች፣ በስብሰባ አዳራሽ፣ እንዲሁም በግለሰቦች ዉይይት ላይ «ክርስቲያኖች ወይንም ነፍጠኞች ወይንም አማሮች ሴቶቻችሁን ጡታቸዉን በመቁረጥ፣ ወንዶቹን ደግሞ በመስለብ፣ ግፍና በደል ፈጽመዉባችኋል። ቋንቋችሁን፣ ባህላችሁን፣ ሃይማኖታችሁን ለዉጠዋል።» በማለት በሕዝቡ ላይ ጥላቻ በመፍጠር ለበቀልና ለጥፋት አነሳስተዉት እናንተም እኛም የምናዉቀዉ፤ በዓለም ዘንድም የታየዉ፤ በእግዚአብሔር መዝገብ ላይም በፈሰሰዉ ንጹህ ደም የተጻፈዉና የተመዘገበዉ የአብያተክርስቲያናት መቃጠል፣ የክርስቲያኖች መጨፍጨፍ፣ መሰደድ፣ መፈናቀል፣ መበደል ተከስቷል። አሁንም የእናንተ አንዳንድ «የሃይማኖት አባቶችና መምህራን » የተባሉ በዚሁ መልክ ለጥፋትና ለበቀል እያነሳሷችሁ መሆኑን ይታወቃል።

በተለያየ ዘመን በተለያዩ ወገኖች በደልና ግፍ፣ አድሎና መድሎ ተፈጽሞ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን አሁን ያለነዉ ትዉልዶች ከተፈጸመዉ ስህተት ትምህርት በመቅሰም ዳግም እንደዚያ አይነት ጥፋት እንዳይመጣ ማድረግና፤ በተቃራኒዉ ደግሞ ከመልካም ተግባሮች ትምህርት ወስደን ለበለጠ ተግባር መነሳት ይኖርብናል እንጂ የስልጣን

እድሜያችንን ያስረዘምን እየመሰለን በክፋት፣ በተንኮል፣ በጥላቻና በበቀል ሕይወትና ተግባር ዉስጥ ከተመላለስን የከፋዉን ጥፋት በራሳችን ላይ እንደምናመጣ ካለፉት መዋዕለ ዜናና ታሪኮች መረዳት ይኖርብናል:: ምክንያቱም እያንዳንዱ የዘራዉን ፍሬ መራራ ይሁን ጣፋጭ መጠጣቱ አይቀርምና:: ስለዚህ ዋጋ እንድንቀበልበት ፍሬያችን መልካም ጣፋጭ መሆን ይጠበቅበታል::

በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ከተገለጹት መዋዕለ ዜና ወይንም ታሪክ ብንመለከት፡ እግዚአብሔር በፍጥረቱ አድሎና መለያየት አያደርግም :: ነገር ግን ከጎናቸዉ ሊሰለፍ የሚችለዉ እሱን በመፍራትና በእዉነተኛ አምልኮ ከሚመላለሱ ሰዎች ጋር ብቻ ነዉ:: ፍርዱ ደግሞ እሱን አዉቀዉ በእዉነት የማያመልኩት ላይ እጅግ ይብሳል:: የግብጽ ፈርዖንና ሰራዊቱ «እግዚአብሔርን አናዉቅም፤ እስራኤልንም አንለቅም:» በማለት ስለታበዩ በተለያየ መቅሰፍትና በመጨረሻም በባሕር ዉስጥ ሰጥመዉ እነሱም መታሰቢያቸዉም መጥፋቱ ይታወቃል:: እስራኤላዉያን ደግሞ የአባቶቻቸዉ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ከግብጽ ባርነት ነጻ እንዳወጣቸዉ እያወቁና ቃል ወደተገባላቸዉ ከነዓን ምድር እንደሚያስገባቸዉ በባለሟሉና በአገልጋዩ በነብዩ በሙሴ እየተነገራቸዉ በተደጋጋሚ በእግዚአብሔር ላይ ዐመጻና ክህደት ስለፈጸሙ ከግብጽ ከወጡት ከግማሽ ሚሊዮን ታላላቅ ሰዎች መሀል ሁለት ሰዉ ብቻ ነዉ እግዚአብሔርን አስደስቶ ከንዓን መግባት የቻሉት:: ሌሎቹ በመንገድ፣ በበረሀዉ ረግፈዉ ቀርተዋል:: ይህም የሚያሳየዉ እግዚአብሔር በፍጥረቱ ሳያዳላ ለእያንዳንዱ እንደ ስረዉ እንደሚፈርድበትና እንደሚፈርድለት ነዉ::

ወደ እስራኤል ታሪክ ስንመለስ እስራኤላዉያን በእዉነተኛ አምልኮ ዉስጥ ሲመላለሱ የአህዛብ ነገሥታት ሊያጠቋቸዉ ሆነ ሊጎዷቸዉ አይችሉም ነበር:: በተቃራኒዉ ደግሞ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ሲተላለፉና በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ተግባር ሲመላለሱ በዙሪያቸዉ ያሉት ሆነ የሩቅ የአህዛብ ነገሥታታ መከራ ያደርሱባቸዉ ነበር:: የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባራቸዉ ከመክፋቱ የተነሳ እግዚአብሔር ተቆጥቶ ለባቢሎን ንጉሥ ለናቡከደነጾር አሳልፎ ሰቷቸዉ ነበር:: ለሰባ ዓመትም በባርነት ሲማቅቁ ነበር:: በኋላም በእዉነተኛ ነብያትና መምህራን እንዲሁም አማኞች አማካይነት በመንግስትነት ሊቀጥሉ ችለዉ ነበር::

ይሁንና ጌታችን መድኃኒታችን እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዉ ሆና በምድር በተገለጸበት ዘመን እዉነተኛ ትምህርት ስለሰጣቸዉ፣ ስለእዉነት ስለመሰከረ፣ የሕይወትን መንገድ ስላሳየ፣ በሽተኞችን ስለፈወሰ፣ የተለያዩ ተአምራትን ስላደረገ፣ መገሰጽ የሚገባቸዉን ስለገሰጸና የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ ተግባራቸዉን ስለገለጸ፤ ጻፎች፣ ፈሪሳዉያን ፣

የአይሁድ ካህናትና አለቆች በሐሰት ወንጅለዉት ስለሰቀሉትና «በእሱም አናምንም » በማለት ክህደት ስለፈጸሙ ወደ1900 ዓመት ገዳማ ካላመንግስት በዓለም ላይ ተበትነዉ ይኖሩ እንደነበረ ይታወቃል።አሁንም አምላክነቱን ያልተቀበሉትና ያላመኑበት ቢሆንም የመጨረሻዉን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ የክፉ ትንቢት ለመፈጸም በመንግስትነት ተቋቁመዋል። ይህም የሚያሳየን እግዚአብሔርን እያወቁ ዐመጻና ክህደት የሚፈጽሙ ሰዎች ሆኑ አገራት እጅግ የከፋ ቅጣት እንደሚጠብቃቸዉ ነዉ።

በተቃራኒዉ ደግሞ ምንም እንኳን በተለያየ ጊዜ የተለያዩ ቡድኖችና አገሮች ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዉያንን ሊያጠፉ ቢነሱም እስከ አሁን ድረስ አምላኳን አጥብቃ ስለያዘች ይኸዉ ለብዙ ሺህ ዓመታት በነጻነት ተጠብቃ አለች። ምክንያቱም ሕዝቦቿ ኪዳነ ኦሪት ሳይመጣ በፊት በኪዳነ ልቦና አምላካቸዉን በእዉነትና በመንፈስ ያመልኩት ነበር። በኋላም ኪዳነ ኦሪትን የተቀበሉና ታቦተ ጽዮንን ደግም በባለአደራነት ተረክበዉ ይኸዉ እስከአሁን ድረስ ታማኝነታቸዉን እያረጋገጡ ይገኛል። ክርስትናዉንም የተቀበሉት አምላካቸዉ ፈዉስና ተአምራትን አድርጎ፣ ምልክትን አይተዉ ወይንም የእሱን ቀጥተኛ ትምህርት ሰምተዉ ሳይሆን፤ የሚመሩበት መንፈስ ቅዱስ የጌታችን የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዝሙር የሆነዉን ሐዋሪያ ፊሊጶስን አገናኝቷቸዉ አንዳች ጥርጣሬ ሳያድርባቸዉና ምልክት ሳይፈልጉ በጥምቀት ልጅነትን አግኝተዋል። በኋላም በተሟላ ስርዐት አምላካቸዉን በማምለክ እስከ አሁን ድረስ ሰባቱን ቅዱስ ኪዳናትን ጠብቀዉ ይገኛሉ።

በንጉሥ ዳዊት ሕይወት ዜና መዋዕል ብንመለከት፣ ንጉሥ ዳዊት ገና ከህጻንነቱ ጀምሮ እግዚአብሔርን የሚፈራ በእግዚአብሔር የሚተማመን እግዚአብሔርም « እንደ ልቤ» ያለዉ ታላቅ አባት ነዉ። ገና በልጅነቱ እግዚአብሔር ኃይልና ሞገስ ሆኖቱ በጉልበቱና በኃይሉ ይመካ የነበረዉን ጎልያድን በወንጭፍ በአንዲት ድንጋይ አዋርዶታል። ከዚያም ለንጉሥነት በቅቶ እስራኤልን ማስተዳደር ችሏል። ይሁንና ወንበር ላይ ከወጣ በኋላ በምቾትና በድሎት ጎሊናዉ ደንድኖ ያ ከበግ እረኝነት አንስቶ ለንጉሥነት ያበቃዉን አምላክ በመዘንጋት የታማኝ አገልጋዩን ሚስት ደፈረ። ከዚያም ታማኝ አገልጋዩን አስገደለ። እግዚአብሔር በፍርዱ አድሎ አያደረግምና ድርጊቱን ለነብዩ ናታን ገልጾለት በነብዩ አማካይነት ገሰጸዉ። ከንግሥናዉ ወንበር በልጁ እንዲሰደድ አደረገ። በሚስቶቹም መደፈርና በስደቱ ተዋረደ። ነገር ግን ቅን ልቦና ነበረዉና ለቀጣይ ትዉልድ ሁሉ መማሪያና መመሪያ ይሆን ዘንድ እዉነተኛ ንስሐን አስተማረን። አልጋዉ እስከሚርስ ድረስ ስለ ኃጢአቱ አንብቷል። አምላኩን በመበደሉ እጅግ ተጸጽቷል። እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ አምላኩን አስደስቷል። በዚህም ምክንያት « እንደ ልቤ» ተባለ። የጽድቅና የቅድስና ማዕረግ አገኘ።

በአሁን ትዉልድ ቢሆን ኖሮ አስተሳሰባችን ሰይጣናዊ ስለሆነና እንደ እግዚአብሔር ስላልሆነ፤ በነብዩ በንጉሥ ዳዊት ሕይወት ላይ የስም ማጥፋትና ዉንጀላ ነበር የምናደርገዉ እንጂ ከዉድቀቱ በእዉነተኛ ንስሐ መነሳቱንና እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ አምላኩን ደስ አሰኝቶ ጻድቅና ቅዱስ መባሉን አንመሰክርም:: ምክንያቱ እንኳን እንዲህ የገዘፈ ኃጢአት በሰዉ ላይ ተገኝቶ አይደለም የሰዎችን እንከን እየፈለግንና ቃላት እየሰነጠቅን ቅኖችንና እዉነተኛ ሰዎችን የምንወነጅል ስለሆነ ነዉ:: በሌላ በኩል ደግሞ እንኳን የንጉሥን ገበና እንዲህ ለመማማሪያ በጽሑፍ ማዉጣት ቀርቶ በአንደበት እንኳ ሰዎች አይናገሩም:: ኃጢአቱ እንኳ ተፈጽሞ በዓለም ቢታወቅ እንኳ ምንም በማያዉቀዉ ሰዉ ይላከካል፣ በሐሰት ምስኪኑ ይወነጀላል እንጂ «ንጉሥ ሆይ እግዚአብሔር የማይወደዉን ተግባር ፈጽማሃል» ብሎ የሚገስጽ እዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ በአሁን ጊዜ ያለ አይመስለኝም::

ይልቁን «በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ተግባርህ በርታ፤ ከጎንህ አለን፤ አስፈጻሚዎችህ ነን» በማለት የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተባባሪ ነዉ የሚሆኑት:: ከላይ ከተገለጹት የምንረዳዉ እግዚአብሔር እዉነተኛ ፍርድ እምደሚሰጥና እዉነተኛ ንስሐ ለሚገቡትም ፍጹም ይቅርታ እንደሚያደርግና ለታላቅ ክብር እንደሚያበቃ ነዉ:: ስለዚህ እናንተ ለጥላቻና ለበቀል የሚያነሳሳዉ ያ ክፉ ጠላት ዲያብሎስ መሆኑን አዉቃችሁ እግዚአብሔር ይበቀል፣ ይፍረድ እንጂ እንኳን የቅርብ ወገኖቻችሁን ኢትዮጵያዉያንን አይደለም ሌሎች ወገኖቻችሁ የአዳምና ሔዋን ዘሮች ላይ ለበቀል መነሳሳት የለባችሁም::

ሌላዉ የምመክራችሁ ያላየነዉን ትዉልድ የዱሮዉን እያነሱ እርስ በእርስ ተፋቅረንና በአንድነት ከመኖር ይልቅ እንድንጣላ፣ እንድንገዳደል፣ እንድንበቃቀል፣ እንድንከፋፈል የሚያደርጉ ሰዎች መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ ሳይሆን ርኩስ መንፈስ መሆኑን ልናዉቅ ይገባል:: ዱሮ ሰዎች በነበራቸዉ አስተሳሰብና ንቃተ ኅሊና እርስ በእርስ ተጣልተዉ፣ ተገዳድለዉ፣ ተበቃቅለዉ ሊሆን ይችላል:: ከአምላክም እዉነተኛ ፍርድ እንደተቀበሉ ምንም ጥርጥር የለዉም:: ስለእዉነት ብቻ መከራን የተቀበሉ፣ የተገደሉ በእግዚአብሔር ዘንድ ትልቅ ቦታ እንደሚጠብቃቸዉና ግፈኞችና ዐመጻኞች እጅግ የባሰ ፍርድ ዉስጥ እንደሚገኙ በእምነት ለምንመላለስ የታወቀ ነዉ:: በምድራዊ ዘመናችን ዉስጥ በዐመጻና በክህደት ሕይወት ዉስጥ ለተመላለሱና ለሚመላለሱ ሰዎች ዘመዴ፣ ዘሬ፣ ጎጤ ፣ ባለዉለታዬ በሚል ስሜት ለግለሰቦች ክብርና ዝና ጥብቅና መቆም የለብንም:: ሁሌም ስለእዉነት ነዉ ልንመሰክር የሚገባዉ እንጂ በቅንነትና በእዉነተኝነት ተመርቶ እንኳን የሌላ ሰዉ የራሰችንን ገበና፣ ድክመት፣ ስህተት ቢጋለጥብንና ቢነገረን ትምህርት ልንወስድበትና ልንታረምበት፣ ልንስተካከልበት ይገባል::

ሌላዉ ማወቅ ያለባችሁ እግዚአብሔር በእዉነት ለሚገዛለት ትዉልድ (ሕዝብ) መልካም እረኛ ይሰጠዋል:: በተቃራኒዉ ለዐመጸኛና ለከሃዲ ትዉልድ የሚቀጣዉ ጨካኝና ከሃዲ መሪ ይሰጠዋል:: ይህም የሚሳየዉ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደምርጫዉና ፍላጎቱ ነዉ የሚሰጠዉ:: ጥቂት እዉነተኞች ተገኝተዉ በቅንነትና በእዉነት፣ እግዚአብሔርን በመፍራት የሚመላለሱ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ የሚፈጽሙ፣ የሚያስፈጽሙ፤ መልካም እረኛ እግዚአብሔር እንዲሰጣቸዉ ከጠየቁ፣ ስለ እነሱ ሲል ከመሃከላቸዉ መልካም እረኛ አስነስቶ ለእዉነተኛ አገልግሎት ይሾምላቸዋል:: ስለዚህ እናንተም ሆናችሁ እኛ ፈጣሪ አምላካችን አንድ ስለሆነ ያ እዉነተኛ አምላክ የእርሱ የሆነዉን መንግስት እንዲሰጠንና የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ እንዲፈጸም ልንጸልይና ሁሉን ለእርሱ አሳልፈን መስጠት ይጠበቅብናል እንጂ በሰይፍና በጦር መሳሪያ የሚመጣ መንግስት በዚያዉ በመጣበት ሰይፍና ጦር መሳሪያ እንዲሁም በእግዚአብሔር ቁጣ ስለሚወገድ እደዚህ አይነቱን መንግስት በምን ሁኔታ መጠበቅ የለብንም::

እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ በአንድ ጊዜ የዐመጻ ልጆችን እንዳልነበሩ አድርጎ ሰማያዊ ስርዐት ሊዘረጋ ይችላል:: በመሆኑም አሁን እንደምናየዉ በጦር መሳሪያ ተመክተዉና ሕዝቡን አስፈራርተዉ፣ በደጎንነት እያሰለሱና በካድሬዎቻቸዉ ቅስቀሳ እያደረጉ ለይስሙላ በካርድ ተመረጥን ለማለት በሥጋዊ ምርጫ የሚመሩትን ተከትለን እኛም የእነሱ አጫፋሪና አጃቢ ከሆን በተዝዋዋሪ « እግዚአብሔር ሆይ እኛ የምንፈልገዉ የዲያብሎስን ስርዐት ነዉ:: የምንመርጠዉም የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ስራ አስፈጻሚዎችን ነዉ:: እነሱ ይንገሡብን የአንተን ንግሥና አንፈልግም::» ማለታችን እንደሆነ ሊገባን ይገባል::

ወደ ሰማያዊዉና አሁን ወዳለንበት እዉነታ ስንመጣ ደግሞ እግዚአብሔር የሚወደዉ፤ እርስ በእርስ ለምንቀያየምበት፣ ለምንጣላበት ይቅር ተባብለን ከጥላቻና ከበቀል ሕይወት ስንወጣ ነዉና የበደልነዉን ክስን የተበደልን ይቅር ብለን ተሳስበን ፣ ተቻችለን ፣ ተፋቅረን ስንኖር ነዉ:: ከዚያ ዉጭ «ባለ ጊዜና ባለ ወንበር ነኝ» በሚል ስሜት በደልና ግፍ፣ አድሎና በቀል የምንፈጽም ከሆነ በዚህ ምድር ላይ ሳይቀር ዋጋ እንከፍልበታለን:: እንኳን መግደልና ግፍ መፈጸም አይደለም አንድ ወገናችንን በድህነቱና ችግሩ ምክንያት « አንተ ደሀ መናጢ ቡቱታም ጨርቃም» ብለን ብንሰድበዉ ለዚሁ ንቀትና ትምክህት ስድባችን ወደ ምድራዊ ፍርድ ቤት ቀርበን ሊፈረድብን እንደሚገባ ነዉ ቃሉ የሚያስተምረን:: እንዲሁም እንኳን በተግባር በወገናችን ላይ የምንፈጽመዉ የኃጢአት ተግባር አይደለም፤ እኛ እንደቀላል የምንቆጥረዉ ስድብ አንድ ምንም የማይሰማ ደንቆሮን አይሰማም ብለን «ደንቆሮ» ብለን ብንሰድበዉና አንድ አይነስዉር አያይም ብለን የማይገባ ነገር ብናደርግበት ወይንም ብናሾፍበት

ፈጣሪን እንደሰደብንና እንዳቃለልን ስለሚቆጠር ይኸዉም እነሱ ባይሰሙና ባይመለከቱ እግዚአብሔር ሆነ ሌላ ሰዉ ይሰማል ይመለከታልና እንዲህ ያደረጉ ደግሞ በምድራዊ ፍርድ ብቻ የሚታለፉ ሳይሆኑ እዉነተኛ ንስሐ ካልገቡ የገሃነመ እሳት ፍርድ እንደሚጠብቃቸዉ ነዉ ቃሉ የሚያስረዳን:: ይህም የሚያሳየዉ የእግዚአብሔር ፍርድ በምድርም በሰማይም ምን ያህል ጥብቅ መሆኑን ነዉ::

በዚህ ምድርም በወገኑ ላይ ኢ-ሰብአዊ ተግባር የሚፈጽም ሰዉ ሆነ አግባብ የሆኑ ሕጎችን የሚጥስ በምድራዊ ፍርድ ወንበር ቀርቦ እስርና የተለያየ ቅጣት እንደሚደርስበት ይታወቃል:: በእግዚአብሔር ዘንድ ደግሞ እንኳን በተግባር ለሚፈጸም ኃጢአት ሆነ ወንጀል አይደለም በንግግርና በአሳብ የሚፈጸም ኃጢአት ያስጠይቃል:: በምድራዊ ሕይወታችን ቆይታ በተግባራችን፣ በንግግራችን፣ በአሳባችን ጭምር እግዚአብሔርን በመፍራት የምንመላለስ ከሆነ በምድራዊ ሕግ ሆነ በሰማያዊ ፍርድ አንጠየቅም:: ምናልባት «ኅሊናችንን አንሸጥም:: የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ተባባሪና አስፈጻሚ አንሆንም» በማለታችን በሐሰት ብንወነጀል እንኳ፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ለታላቅ ክብር የምንበቃበትና ዋጋ የምናገኝበት ይሆናል እንጂ በነፍሳችን አንዳች አንጎዳበትም::

ሌላዉ ስለ እዉነት በመመስከራችሁና «ከነፈሰዉ ጋር አንነፍስም፤እንደ ቦይ ዉኃ አንነዳም፤ ከእዉነት ጋር ነዉ አንድነትና ህብረት ያለን::» በማለታችሁ ፈተና፣ ችግር፣ እስር፣ ግድያ ቢመጣባችሁ የሚታደጋችሁና የሚጠብቃችሁ የእዉነት አምላክ ስለሆነ እስከ መጨረሻዉ ስለ እዉነት መጽናት አለባችሁ እንጂ ግፈኞችንና ሐሰተኞችን ፈርታችሁ የዐመጻና የሐሰት ተባባሪ ከሆናችሁ እነዚያ የፈራችዋቸዉ መሪዎችና ባለስልጣናት፣ እንዲሁም ካድሬዎች የዐመጻ ጽዋቸዉ ሲሞላ እግዚአብሔር በቁጣዉ እንዳልነበሩ ስለሚያደርጋቸዉ እናንተም ሰለተባባሪነታችሁና አስፈጻሚነታችሁ በምድርም በሰማይም ዋጋ መክፈላችሁ አይቀርም:: ስለዚህ በምድርም በሰማይም ዋጋ እንድታገኙ እስከ እለተ ሞታችሁ (ሕያዉ ነፍሳችሁ ከዚህ ከተገለጻችሁበት ሥጋ እስከምትለይ ድረስ) አንድነታችሁና ህብረታችሁ ከእዉነት አምላክ ጋር ብቻ ማድረግና እግዚአብሔርን በመፍራት ልትመላለሱ ይገባል::

በዚሁ አጋጣም ስለተለያዩ የሰዉ ልጆች ባሕርይና ጠባይ ልንገራችሁ:: በዚህ ምድር ዉስጥ አምስት የተለያየ ጠባይ ያላቸዉ ሰዎች አሉ:: የመጀመሪያዎቹ እንደማንኛዉም ሰዉ በሥጋ የተገለጹና በነጻ ኅሊናቸዉ ተመርተዉ መልካም ሆነ መጥፎ የመስራት ሙሉ ፈቃድና ነጻነት ያላቸዉ ሲሆን፤ ነገር ግን ነጻ ኅሊናቸዉንና ፈቃዳቸዉን ለትዕቢት፣ ለክህደት፣ ለዐመጻ የሚያዉሉ አይነታቸዉ ሶስት የሆነ ነዉ::

ሀ. ትዕቢት የተባለዉ ሰዉ ፈርኦንን የሚመራዉ የነበረ ርኩስ መንፈስ ( ሰይጣናት) የሚመራቸዉ ዉስጣቸዉ ትዕቢት የተሞላ ሰዎች ናቸዉ። እነዚህ ሰዎች በኃይላቸዉ፣ በእዉቀታቸዉ፣ በሀብታቸዉ፣ በስልጣናቸዉ ስለሚመኩ እግዚአብሔር መፍራት በዉስጣቸዉ አንዳች የሌለባቸዉ ልበደንዳናና እብሪተኛ ናቸዉ።

ለ. ክፋት የተባለዉ ሰዉ ይሁዳን ይመራዉ የነበረ ርኩስ መንፈስ (ሰይጣናት) የሚመራቸዉ ዉስጣቸዉ ክፋትና ተንኮል፣ ምቀኝነት የሞላባቸዉ፤ ሌት ተቀን ለራሳቸዉ ጥቅም ብቻ የቆሙ፣ ጥቅማቸዉን ለማግኘት ሰዎችን በሐሰት፣ በተንኮል፣ በክፋት፣ በምቀኝነት ለማጥፋት ሆነ ግፍ ለመፈጸም እንዲሁም በደል ለማድረስ ወደ ኋላ የማይሉ፤ ኅሊናቸዉ እንኳ ስህተታቸዉን ቢመሰክርባቸዉ የማይሰሙትና የማይቀበሉት ኅሊናቸዉን ያደነደኑ ሰዎች ናቸዉ።

ሐ. ዐመጻ የተባለዉ ሰዉ አርዮስን ይመራዉ የነበረ ርኩስ መንፈስ (ሰይጣናት) የሚመራቸዉ ዉስጣቸዉ ለራሳቸዉ ሥጋና ደም ስሜት ተግባርና እምነት የቆመ፤ ከእግዚአብሔር የሆነዉን እዉነት ለመቀበል ፈቃደኛ የማይሆኑ፣ ቢቀበሉት እንኳ «ጥቅም እናገኝበታለን» በሚል እምነት እንጂ ከኅሊናቸዉ አምነዉበት የማይቀበሉ፤ ባገኙት አጋጣሚ ለራሳቸዉ ዐመጻ ስራ የሚነሳሱ በሥጋና ደም ስሜታቸዉ ብቻ የሚንቀሳቀሱና በደመ ነፍሳቸዉ የሚመሩ ሰዎች ናቸዉ።

ሁለተኛዎቹ ሰዎች አእምሮ ቀላል የሚባሉት ናቸዉ። እነዚህ ሰዎች በአብዛኛዉ ጊዜ ኅሊናቸዉን ለመገለባበጥ ወደ ኋላ የማይሉ፤ በሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚመሩ፤ ለጥቅማቸዉ ሲሉ የዲያብሎስ ፈቃድ የሚያስፈጽሙና የሚፈጸሙ፤ ሥጋዉያን መሪዎችንና ባለስልጣናትን ተከትለዉ «አድርጉ፣ ፈጽሙ።» የሚሏቸዉን ሁሉ ሰዉን እስከመግደልና እስከማሰቃየት የሚደርሱ፤ ሆዳቸዉና ጥቅማቸዉ አምላካቸዉ የሆነ፤ ከነፈሰዉ ጋር የሚነፍሱ፣ እንደ ቦይ ዉኃ ወደወሰዷቸዉ የሚሄዱ፤ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት የሚመላለሱ ሰዎች ናቸዉ።

ሶስተኛዉ ሰዎች አእምሮ ህጻን የሚባሉ ናቸዉ። እነዚህ በሥጋቸዉ አዋቂዎች ቢሆኑም ራሳቸዉን በሚገባ ያልገዙ፣ የሥጋና የደም ስሜታቸዉ የሚያይልባቸዉና የሚያሸንፋቸዉ ነዉ። ኅሊናቸዉ እዉነትን ቢያዉቅና ቢመርጥም ፈተናዉን፣ ችግሩን በጽናት ለማሳለፍ ራሳቸዉን የማያዘጋጁ ቆራጥነት የሚጎላቸዉ ሰዎች ናቸዉ። በዚህም ምክንያት

በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ለጥቅማቸዉ ሲሉ ለመመሳለስ ወደ ኋላ የማይሉ ናቸዉ።

አራተኛዉ ሰዎች አእምሮ አዋቂዎች የሚባሉ ናቸዉ። እነዚህ ሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ ትምህርት ቢማሩም ባይማሩም ነገሮችን በሚገባ የማስተዋልና የማመዛዘን ችሎታ ያላቸዉ፤ ሁሉ በትክክል ቢመራ የሚመርጡ ሲሆን፤ ነገር ግን ትክክል ያልሆነዉን « ትክክል አይደለም። የዐመጻ የክህደት የርኩሰት ተግባር ነዉ» ለማለት የማይደፍሩ፤ ስለ እዉነት ራሳቸዉን መካድ የማይፈልጉ፤ ቆራጥነትና ጽናት የሚጎላቸዉ፤ ኑሮ በመመሳሰል የሚለዉን ፈሊጥ የሚከተሉ ሰዎች ናቸዉ።

አምስተኛዉ ሰዉ አእምሮ ጽኑአን የሚባሉ ናቸዉ። እነዚህ ትክክለኛዉንና እዉነቱን ማወቅ ብቻ አይደለም ሰዎች ሁሉ በትክክለኛዉ መንገድ እንዲሄዱ የሚፈልጉና ለዚያም ማንኛዉን ዋጋ ለመክፈል ቆራጦች የሆኑ፤ ራሳቸዉም ለመካድ የማይከብዳቸዉ፤ ኅሊናቸዉን በቀላሉ ለመገለባበጥ የማይቻል፤ ያላመኑበትንና ያልተቀበሉትን በተጽህኖ ሆነ በግዳጅ እንዲቀበሉ ቢደረግ ለመቀበል ፈቃደኛ የማይሆኑ፤ ስለ እዉነት ማንኛዉንም ችግርና መከራ ለመቀበል ዝግጁ የሆኑ፤ እስከ ሞት ድረስ ራሳቸዉን አሳልፈዉ የሚሰጡ ለእግዚአብሔር አገልግሎት ምቹ የሆኑ ሰዎች ናቸዉ።

ስለዚህ በዚህ በተለያየ አይነት ሰዎች የተሞላች ምድር አግባብ የሆነ ሕግና ስርዐት ለሰዉ ልጆች ያስፈልጋል። ማንም ሰዉ ኃይል፣ ጉልበት፣ ስልጣን፣ ሀብት፣ ወገን ፣ ዘመድ አለኝ ብሎ ሌላዉን መጉዳትና ማጥቃት የማይችልበት፤ እንዲሁም በተቃራኒዉ ሌላዉ ሰዉ ኃይል፣ ጉልበት፣ ስልጣን፣ ሀብት፣ ወገን ፣ ዘመድ የለኝም ብሎ አድሎና በደል፣ ግፍ፣ ጥቃት እንዳይፈጸምበት ሁሉ ሰዉ በእኩልነት የሚመራበትና የሚዳኝበት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተዘጋጀ ሕግና ስርዐት ሊኖር ይገባል።

አሁን ያለዉ ሕግና ስርዐት የይስሙላና ለማስመሰል በሸዋጁ መንፈስ መሪነት የተዘጋጀ፣ በወረቀት ላይ ነዉ የሰፈረዉ እንጂ ተግባራዊ የማይሆን፣ ሰዎች ስልጣናቸዉንና ኃይላቸዉን ተመክተዉ በፈለጉት ጊዜ የሚሽሩት፣ የሚጠቅማቸዉ ከሆነ ደግም እንደፈለጉት አድርገዉ የሚጠቀሙበት፣ ለመበቀልም ከፈለጉ ለራሳቸዉ እነደሚመች አድርገዉ የሚበቀሉበት፣ ባጠቃላይ በሥጋና ደም ስሜት የተዘጋጀ ስለሆነ፤ ሰዎች በሥጋና ደም ስሜታቸዉ ተግባራዊ የሚያደርጉት ለእዉነት ያልቆመ፣ የእዉነታ ተቃራኒ በሆነዉ በፓለቲካ

ስሜት የተዘጋጀ፣ በተዝዋወረ የዲያብሎስ ፈቃድ የሚፈጸምበት፣ የእግዚአብሔር ሰማያዊ ስርዐት ተቃራኒ የሆነዉ በዴሞክራሲ ሽፋን የተቀመረ፣ የአምባገነኖች ሕግና ስርዐት ነዉ፡፡

በዚህም ምክንያት እንኳን ለነፍሳችን አይደለም ለሥጋችን የማይጠቅም የአህዛብ (እግዚአብሔርን የማያምኑና የካዱ ሰዎች) ስብስብ በዲያብሎስ መንፈስ መሪነት የተዘጋጀ፣ ሕዝቡን ለማታለልና ጎሊናዉን ለማሸጥ አልፎ አልፎ ወርቃማ ቃላቶችና አባባሎች ያሉበት ነዉ፡፡ በመሆኑን በትክክል ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ቅንነትና እዉነተኛነት የተላበሱ፣ ለምድራዊዉም ለሰማያዊዉም ሕይወት የሚጠቅሙ፣ እግዚአብሔር የሚከብርበትና የሚመሰገንበት ሕግና መመሪያ፣ እንዲሁም ስርዐት ነዉ የሚያስፈልገን እንጂ፤ በአገር ዉስጥ ሆነ በዉጭዉ ዓለም ያለዉ የአህዛብ ሕግና ስርዐት ወደ ሞትና መቀመቅ የሚወስደን እና በሥጋችንም በነፍሳችንም የማንጠቀምበት ነዉ፡፡

የአህዛብን ሕገ መንግስትና ስርዐት እንደምናየዉ ሕዝቡ ከፈለገ ዲያብሎስን እንዲያመልክ ፣ ከፈለገም የተለያዩ አማልክት እንዲያመልክ፣ ከፈለገም በባዕድና በጣዖት አምልኮ እንዲመላለስ የሚፈቅድ፤ ራሱ መሪዉና ባለስልጣናቱ ከእግዚአብሔት መቀባትንና መመረጥን የማይፈልጉ፣ በተዝዋዋሪ የጨለማዉ ገዥን ፈቃድ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ በዲያብሎስ የተቀቡ ናቸዉ፡፡

በእግዚአብሔር መንግስት ግን ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተ ክህነቱ፣ ቤተ ምልክናዉ በአንድላይ በመንፈስ ቅዱስ ስለሚመራ የእግዚአብሔር ፈቃድ ብቻ ነዉ ከታች እስከ ላይ የሚፈጸመዉ፡፡ ከላይ እስከታች ያሉ የእግዚአብሔር እንደራሴዎችና የሕዝብ ጠባቂዎች የሕዝቡ አገልጋዮችና እረኞች ናቸዉ እንጂ በሕዝብ ስም እየነገዱ፤ ሕዝቡን የሚያሰቃዩ ፣ የሚያጉላሉ፣ ችግርና መከራ የሚያመጡበት፣ ለእስራትና ለግድያ እንዲሁም ለስደት የሚዳርጉት አይደለም፡፡ ራሳቸዉን በአምላክና በሕዝብ ፊት ዝቅ አድርገዉ በሥጋዉም በነፍሱም የሚጠቀምበትን ተግባር ለመፈጸምና ለማስፈጸም የሚተጉ ናቸዉ እንጂ ሕዝቡን የሚከፋፍሉ፣ የሚለያዩ፣ የሚያጣሉ፣ ለጥላቻና ለበቀል ያሚያነሳሱ፣ ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን የሚያነግሡ፣ ባዕድና ጣዖት አምልኮ የሚያስፋፉ፣ የሕይወትን መንገድ እያጠፉ ክህደትንና መናፍቅነትን የሚዘሩ፣ ዐመጻንና ርኩሰትን የሚያስፈጽሙ አይደለም፡፡ በእዉነት የሚኖሩ፤ ስለእዉነት ራሳቸዉን ክደዉ የሚመሰክሩ፤ መልካም እረኝነታቸዉንና አገልጋይነታቸዉ ለእግዚአብሔርም ለሕዝብም የሚያሳዩ ናቸዉ፡፡ ሕዝቡን ለነጣቂ ተኩላና ለጨካኞች፣ ለግፈኞች አሳልፈዉ የማይሰጡ፤ መስዋዕት ለመሆን እንደ አምላካቸዉ ራሳቸዉን የሚያስቀድሙ ናቸዉ እንጂ ምንደኛ

ቅጥረኞች፣ ሕዝቡን ለዲያብሎስ እንደራሴዎች አሳልፈዉ ሰተዉ ራሳቸዉን የሚያድኑ አይደሉም።

እዚህ ላይ የአንዳንዶቹን *ሥጋዉያንና መንፈሳዉያን* ፍጹም ከእዉነት የራቀ አስተሳሰባቸዉን ልገልጽላችሁ እዉዳለዉ። ይኸዉም አስተሳሰባቸዉ የእዉነታ ፍጹም ተቃራኒ በሆነዉ በፖለቲካ ኅሊናቸዉ የተበከለና የተመረዘ ስለሆነ የእግዚአብሔር ፍጥረቶችና ልጆች የሆኑት የአዳም ዘሮች «ለዲያብሎስ ሰርዐት መገዛትና ፈቃዱንም መፈጸምና ማስፈጸም አለባቸዉ።» ብለዉ የሚያምኑና ሳይፍሩና ሳይሸማቀቁ በድፍረት የሚናገሩ ናቸዉ። አብዛኛ ዎቹ ደግሞ በዚሁ በዲያብሎሳዊ ስርዐት ዉስጥ ቁልፍ ቦታ ይዘዉ የክህደት፣ የዐመጻ፣ የርኩሰት ተዋናይ ሆነዉ የምታገኟቸዉ እነ ሆዱ እምላኩና እነ ጥቅማቸዉና ክብራቸዉ፣ ዝናቸዉ ከኅሊናዉ በላይ የሆነ ሰዎች ናቸዉ። እነዚህ በብልጣብልጥነት የእግዚአብሔርን መንግስት መዉረስ እንደሚችሉ አድርገዉ የሚያስቡ ከንቱ *ሥጋዊ* መጠበብ የሚያደርጉ በእግዚአብሔር ስምና በቃሉ የሚነግዱ አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች ናቸዉ እንጂ ፍጹም ኅሊናዉ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመራ ሰዉ በተቃራኒ መንፈስ ከሚመራ ሰዉ ጋር ሆነ ድርጅት ወይንም ቡድን አንድነትና ህብረት ሊኖረዉ አይችልም።

አሁን ወዳለዉ የኢትዮጵያ መንግስት እዉነታ ስንመጣ ደግሞ « ከዚህ በፊት እንዲህ አልተደረገላችሁም፤ እኛ ግን እንዲህ ሰራንላችሁ፤ እንዲህ አደረግንላችሁ፤ እንዲህ እናደርግላችኋለን.. ወዘተ» በማለት ራሳቸዉን ባያመጻድቁና በአጉል ተስፋ ሕዝቡን እየሞሉ ኅሊናዉን ባያደነዝዙ፤ እንዲሁም በአቅማቸዉ ለአገራቸዉና ለሕዝባቸዉ አገልግለዉ ያለፉትን እየኮነኑ ራሳቸዉን ታላቅ ለማድረግ ኅሊናቸዉን ባይሸጡ፤ ይልቁኑ « እኛ መስራት ከሚጠበቅብን ያነሰ ነዉ የሰራነዉ። ብንሰራም መስራት ያለብንን ነዉ የሰራነዉ። ለወደፊት ደግሞ እግዚአብሔር ባሳሰበንና በረዳን መጠን የበለጠዉን እንሰራለን። » ቢሉና፤ « በሕዝብ ስም የተበደርነዉን፣ የተረዳነዉን፣ እንዲሁም ከሕዝብ የሰበሰብነዉን ሙሉ በሙሉ በአግባቡ በልማት ላይ ማዋል ተስኖን የተወሰኑ ግለሰቦች እንዲጠቀሙበትና በአቋራጭ መንገድ እንዲከብሩበት በማድረጋችን፤ በዘመድ አዝማድ በጎጥ ተቧድነን ሕዝቡን በረሀብና በችግር ባንቀጣዉ ኖሮ፤ አሁን ከተሰራዉ ግንባታ በላይ ብዙ ግንባታዎችን እናከናዉን ነበር።» በማለት ንስሐ ቢገቡ፤ ከዚህ በተጨማሪም « ግንባታዉንና ልማቱን ያከናወነዉና የምናከናዉነዉ፤ አስተሳሰባችንና መመሪያችን አገራዊ ራእይ ይዘን በኢትዮጵያዊነት ብሔር ሳይሆን በጎጣዊ ስሜት፣ ለወደፊት ኢትዮጵያ የምትባል አገር ተከፋፍላና ተበታትና ህልዉናዋን ስታጣ ክልል መንግስታት የራሳቸዉን ነጻ መንግስትነት ሲያዉጁ ተጠቃሚ በምንሆንበት ምልኩ አድሎና

በቀል በተሞላበት አስተሳሰብ ስለሆነ፤ ይህንን በክፋትና በተንኮል የተሞላዉ አስተሳሰባችንን ትተን በአራቱም ማዕዘን ያሉት «ኢትዮጵያዉያን ወንድምና እህቶቻችን፣ እናትና አባቶቻችን ናቸዉ።» ብለን ከእንግዲህ ካለ አድሎና በቀል በእኩልነት እናገለግላለን።» በማለት የዘረኝነትንና ጎጠኝነት አስተሳሰባቸዉን ቢተዉ፤ ማንም ሰዉ ከተመቻቸለትና ገንዘብ እርዳታ ካገኘ ሊሰራቸዉ የሚችለዉን መንገዶች፣ ህንጻዎች፣ ግድቦች፣ የመብራትና የስልክ አዉታሮች፣ ፋብሪካዎች ፣ የትራንስፓርት ዘርፎች.. ወዘተ እና « ለፖለቲካ ዓላማችን ነዉ የሰራነዉ።» በማለት በራሳቸዉ ጎጣዊ አስተሳሰብ ባይመሩ ኖሮ፤ ለተሰሩት የትምህርት፣ የጤና፣ የህንጻ፣ የዉሃ.. ወዘተ ግንባታዎችና አገልግሎቶች፤ እንዲሁም ለፓለቲካዊ ድጋፍና ለካድሬነት ምልመላ ባይጠቀሙበትና የራሳቸዉን ሰዉ ብቻ ባያበለጽጉበትና «ኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን ናቸዉ፤ የስራ እድል እንፍጠርላቸዉ፤ ራሳቸዉንም ቤተሰባቸዉንም ይርዱ፤ ለእናት አገራቸዉም የራሳቸዉን አስተዋጽኦ ያድርጉ።» በሚል አስተሳሰብ ተደራጅቶ ቢሆን ኖሮ ስለ አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማት፤ ባጠቃላይ ለሥጋዊ ሕይወታችን ጥቅም ስለሚሰጡን ሁሉ የእግዚአብሔር ስም እንዲጠራ ባይፈልጉም፤ እግዚአብሔር ይስጣችሁ፤ አገራችሁንና ሕዝባችሁን በቅንነትና በእዉነት የምታገለግሉበትን ልቦና ያድላችሁ፤ ለንስሐና ለእግዚአብሔር መንግስት ያብቃችሁ ብለን እንመርቃቸዉ ነበር።

እንዲሁም በጨለማዉ ገዥ ገላጭነትና አሳሳቢነት በፈጠሩት «ብሔር ብሔረሰቦች» ቋንቋ፤ ኢትዮጵያዉያንን በዘር፣ በጎጥ፣ በቋንቋ ከፋፍለዉ እርስ በእርሱ በጥላቻና በንቀት እንዲተያዩ፣ እንዲከፋፈል፣ እንዲለያዩ፣ ራሳቸዉን የተለየ አድርገዉ እንዲቆጥሩ፣ እንዲገዳደሉ፣ እንዲበቃቀሉ፣ ቂምና በቀል እንዲያረግዙ፣ ለጥፋትና ለበቀል ጊዜ እንዲጠብቁ፣ እንዲጨካከኑ፣ አንዱ በአንዱ እንዲነሳሳ፣ ባጠቃላይ የበላይ መሪያቸዉ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ ያሳሰባቸዉን የዐመጻና የክህደት ፍሬዎችን ባያፈሩ፤ በእግዚአብሔር እዉነት ፣ በኢትዮጵያዊነት ፣ በሰንደቅ ዓለማ ላይ ዐመጻና ክህደት ባይፈጽሙና ባያስፈጽሙ፤ ከህጻን እስከ አዋቂ ድረስ « ብሔር ብሔረሰቦች» በሚል ሽፋን በዘፈንና በዳንኪራ ባያሳብዷቸዉና የጨለማን ስራ ባያሰሯቸዉ፤ «በብሔር ብሔረሰብ» ስም የራሳቸዉን መሰሪ ተግባር ባይፈጽሙና በሕዝቡም ስም ባይነግዱ ኖሮ በየበረሀዉ፣ በየገጠሩ፣ በየጫካዉ የተረሱና ትኩረት ያልተሰጣቸዉ ወገኖቻችን ኢትዮጵያዉያን እንዲታወቁ በመደረጉና ራሳቸዉን የሚያመጻድቁና በዘራቸዉ፣ በጎጣቸዉ የሚመኩ ሰዎች ደግሞ በበረሀ ሆነ በጫካ እንዲሁም በገጠር የሚኖሩ ሰዎች እንደማንኛዉ ኢትዮጵያዊ እኩል መሆናቸዉን እንዲያዉቁ በመደረጉና

ትኩረት ስለተሰጣቸዉ፤ እግዚአብሔር ለሙሉ እዉቀትና ለእዉነተኛ እረኛነት ያብቃችሁ በማለት እንመርቃቸዉ ነበር።

ከዚህ በተጨማሪም «የእግዚአብሔር እዉነታን እንኳን ኢትዮጵያዉያን አይደለም ሌላዉ የዓለም ሕዝብ ሁሉ የአንዱ እግዚአብሔር ፍጥረቶችና የአዳም ዘሮች ናቸዉ። የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ከፈለጉ ደግሞ ማንኛዉም ሰዉ በጥምቀት በመንፈስ ከእግዚአብሔር ተወልዶ ለሰማያዊ ሆነ ምድራዊ የእግዚአብሔር መንግስት ሊበቃና አገልጋይ ሊሆን ይችላል። ማንም ሰዉ በዘሩ፣ በጎጡ፣ በቋንቋ የበላይ አይደለም፤ እንዲሁም የበታች አይደለም። ሁሉ ሰዉ በእግዚአብሔር ፍጥረትነቱ ካመነ በእግዚአብሔር ዘንድ እኩል ነዉ። እግዚአብሔርን ከካደና ዐመጻና ክህደት እንዲሁም ርኩሰት ከፈጸመ እዉነተኛ ንስሐ ገብቶ ከአምላኩ እስከሚታረቅ ድረስ እርሱ እንደ ሰይጣናት በእግዚአብሔር እዉነታ ላይ ያመጸ በመሆኑ ዐመጸኛና ከሃዲ ስለሆነ እንደ ማንኛዉ ሰዉ በሰዉነቱ እኩል ቢሆንም ስለዐመጸኛ ነቱ ግን ባዶና ተራ የሆነ አሳዛኝ ፍጥረት መሆኑን ማስተዋል ይኖርበታል።

ሰዎች በቋንቋ፣ በባህል፣ በሃይማኖት የተለያዩት በኃጢአታቸዉ ምክንያት ነዉ እንጂ በጽድቅ ስራቸዉ አይደለም። ሰዎች ራሳቸዉን ለማምለክና ለማስመለክ እንዲሁም ለማግነንና የበላይ ለመሆን ነዉ ልዩነትን እየፈጠሩ ክፍፍልና መለያየት የሚያደርጉት እንጂ እግዚአብሔር አንድ እንደሆነ ሁሉ ለእግዚአብሔር መንግስትም የሚያበቃ አንድ የሕይወት መንገድ ብቻ ነዉ ያለዉና ሕያዉ ሆኖ በእግዚአብሔር መንግስት ዉስጥ መኖር የሚፈልግ ሰዉ በአንዱ እዉነተኛ ሃይማኖት ሊመላለስ ይገባዋል። « አይ የራሴን የሥጋና የደም ስሜት ፈቃዴን ነዉ የምከተለዉ፤ ራሴነዉ የማገነዉና የማስመልከዉ የሚል ሰዉ ካለ ስለ ዐመጻዉ እንደ ሰይጣናት በምድራዊ ሕይወቱም ዘመንና ከሁሉ በላይ ደግሞ ነፍሱ ከቅርፊት ሥጋዉ ስትለይ ለሕያዉነት ዘመን የባሰ ዋጋ እንደሚከፍልበት እያወቀ እንደ ማንኛዉ ሰዉ ምድራዊ ኑሮዉን መኖር ይችላል።

እግዚአብሔርን የሚል ሰዉ ደግሞ ከአህዛብ( እግዚአብሔርን ከማያምኑ) ሰዎች የተወረሰዉን የአህዛብ ባህልና ልማድ እርግፍ አድርጎ በመተዉ ለእግዚአብሔር አገልግሎትና መንግስት የሚያበቃዉን ባህልና ስርዐት ሊከተል ይገባዋል። «አይ እኔ እግዚአብሔር የሚባል ነገር አላዉቅም፤ ዘርያዎቼም ጦጣዎች ናቸዉ፤ ተፈጥሮ ናት ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣችኝ» የሚል ዐመጸኛና ከሃዲ ሰዉ ካለ በግል ሕይወቱ በዐመጻዉና በክህደቱ ሊጸና ይችላል። ነገር ግን ዋጋ እንደሚከፍልበትና ሌላዉን የእግዚአብሔርን ሕዝብ ግን ሊያሳምጽና ሊያስክድ እንደማይችል ማወቅ ይኖርበታል። ባጠቃላይ እያንዳንዱ ሰዉ በግል ሕይወቱ እግዚአብሔርን ሊክድና ላያምን ቢችልም በእግዚአብሔር እዉነታ ላይ ግን ዐመጻንና ክህደትን

መፈጸምና ማስፈጸም እንደማይችል ሊረዳ ይገባዋል:: ምክንያቱም እያንዳንዱ ሰዉ ለማንኛዉ ሰዉ የሚፈቀደዉ ሙሉ ነጻነት በግል ሕይወቱ የሚፈቀድለት ቢሆንም፤ በእግዚአብሔር ፍጹም እውነታ ላይ ማንንም ሊያሳምጽ ሆነ ሊያስክድ አይችልም:: እንኳን በእግዚአብሔር እዉነታ ላይ ቀርቶ የጨለማዉ ገዥ እንደራሴዎች በእርሱ አሳሳቢነትና መሪነት ባዘጋጁት ሕገ መንግስት ላይ ዐመጻና ክህደት ሲፈጸም ዋጋ እንደሚከፈልበት ይታወቃል:: በእግዚአብሔር ሕገ መንግስት ላይማ እንዴት በምድርም በሰማይም የበለጠዉ ዋጋ አይከፈልበት! እጅግ ይከፈልበታል::» በማለት እንነግራቸዉ ነበር::

የጨለማዉ ገዥ እንደራሴና አገልጋይ የሆኑት ሰዎች ለራሳቸዉ መሰሪ ዓላማ የፈጸሙት አንዳንድ ተግባሮች እግዚአብሔር ለበጎ ያዉለዋል:: እነሱ ግን ሕዝብን ለመሸንግል፤ የስልጣን እድሜያቸዉን ለማስረዘም፤ ትዉልዱ ኅሊናዉን እንዲሸጥና በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ዉስጥ እንዲመላለስ በማድረግ ከአምላካቸዉ አጣሉት:: ለእግዚአብሔር ቁጣም አሳልፈዉ ሰጡት:: ማስተዋሉን አጡ እንጂ ራሳቸዉን በእግዚአብሔርና በሕዝብ ፊት ዝቅ አድርገዉ ቢመላለሱና በቅንነትና በእዉነት ቢያገለግሉ ኖሮ እንኳን በምድር ብቻ አይደለም በሰማይም ይገኑ፣ ይከበሩ፣ ይሸለሙ ነበር::

በዚህች ምድር የተፈቀደላቸዉን የስልጣን ዘመንም ማንም ሊያሳጥርባቸዉ ሆነ ሊያስረዝምላቸዉ እንደማይችል ቢያዉቁና አስተዉለዉ ቢሆን ኖሮ በተፈቀደላቸዉ ዘመን እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት ሕይወት በመመላለስ ፈቃዱን ፈጽመዉና አስፈጽመዉ ወደ አምላካቸዉ እቅፍ ይሄዱ ነበር:: አሁን ግን እንኳን ፈቃዱን መፈጸምና ማስፈጸም አይደለም፤ ራሳቸዉን ከዐመጻ፣ ከክህደት፣ ከርኩሰት ተግባር መለየት አልቻሉም:: ሕዝቡንም ከማሳመጽ፣ ከማስካድ፣ ከማስረከስና የአምልኮ ምንዝርና ከማስፈጸም አልተመለሱም:: በመሆኑም በሥጋቸዉ ሆነ በነፍሳቸዉ ላይ በራሳቸዉ ነጻ ፈቃድ ታላቅ መከራና ቅጣት እያመጡ መሆኑን መገንዘብ ይገባቸዋል:: እግዚአብሔር እንደ ፍጡር የዓመታት ወይንም የወራት ዝግጅት አይስፈልገዉም:: የፈለገዉን በፈለገዉ ቀንና ሰዐት ማከናወን ይችላል:: ዛሬ ከወንበራቸዉ ማንሳት ከፈለገ ዛሬዉኑ በፈለገዉ መንገድ ከወንበራቸዉ ሊቆርጣቸዉ ይችላል:: በተቃራኒዉ ደግሞ ቀኑ ካልደረሰ የዓለም ሕዝብ ተባብሮ ከወንበራቸዉ ሊያነሳቸዉ ቢጥር ሊያነሳቸዉ አይችልም::

የተፈቀደላቸዉ ቀን ሊረዝም የሚችለዉ ቀና ካሰቡ፣ መልካም ከሰሩ፣ በእዉነት ከኖሩ ብቻ ነዉ:: በተቃራኒዉ የተፈቀደላቸዉ ቀን ሊያጥር የሚችለዉ ዐመጻቸዉ፣ ክህደታቸዉ፣ ርኩሰታቸዉ ሲከፋ፤ ግፍና ጭካኔያቸዉ ሲያይል ነዉ:: ከዚያ ዉጭ ግን በተቆረጠላቸዉ ቀን

በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ከወንበራቸዉ ተቆርጠዉ ወንበሩ ለባለተረኛዉ ተላልፎ ይሰጣል:: ታዲያ እነሱም ሆኑ እኛ ሰዉ በራሱ ኃይልና ስልጣን ወደ ወንበር የሚመጣ ይመስለናል እንጂ እግዚአብሔር ባወቀና በፈቀደዉ መንገድ አይመስለንም:: እንዲሁም ወንበሩ የሚጸናዉ በራስ ኃይልና ስልጣን ይመስለናል እንጂ በእግዚአብሔር ቸርነትና ጥበቃ መሆኑን አይገባንም:: እዉነታዉ ግን ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥርና እዉቅና የሚከናወን ነዉ:: ሕዝቡ ከእግዚአብሔር የሆነ መልካም ስርዐትን ከፈለገና ከጠየቀ እንደጥያቄዉና ምርጫዉ መልካም ስርዐትን ይሰጠዋል:: በተቃራኒዉ ደግሞ የዐመጻና የክህደት እንዲሁም የርኩሰት ስርዐት ከፈለገ የሚቀጣበትንና ዋጋ የሚከፍልበትን ስርዐት ይሰጠዋል:: እግዚአብሔር እንደ ሕዝቡ ፍላጎትና ጥያቄ ነዉ ደግ መሪ ወይንም ጨካኝ መሪ የሚሰጠዉ::

አንዳንድ ምሳሌ ብንመለከት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት የነበሩት አጼ ኃይለ ሥላሴ የስርዐት ማብቂያቸዉ በደረሰ ወቅት እሳቸዉም ሆኑ ሌላዉ ሰዉ ባላሰበዉና ባልጠበቀዉ መንገድ ከወንበራቸዉ ሊቆረጡና እሳቸዉም ባለስልጣኖቻቸዉም የተለያየ መከራና ግድያ ሊደርስባቸዉ ችሏል:: ከዚያም የኮሌኔል መንግስቱ ኃይለማርያም ስርዐት ማብቂያ ላይም ባልታሰበና ባልተጠበቀ ጊዜ ከወንበራቸዉ ተቆርጠዉ እሳቸዉም ለስደት ባለስልጣኖቻቸዉም ለችግርና ለእስር ተዳርገዋል:: አሁንም ባለተረኛዉ አቶ መለስ ዜናዊ የስርዐታቸዉ ማብቂያ መዳረሱ ቢታወቅም በምን መልኩ ከወንበራቸዉ እንደሚቆረጡና እሳቸውም ሆኑ ባለስልጣኖቻቸዉ ስለ ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት ተግባራቸዉ ምን ዋጋ እንደሚከፍሉ ቸሩ መድኃኔዓለም አንድዬ ነዉ የሚያዉቀዉ::

እኛ ግን የአዳም ዘሮች ወንድምና እህቶቻችን ናቸዉና ስለ ዐመጻ፣ ስለክህደት፣ ስለርኩሰት ተግባራቸዉ ንስሐ ገብተዉ ለእግዚአብሔር እጃቸዉን ሰተዉ በሰዉ ሳይሆን በራሱ ጊዜ እንዲጠራቸዉ ነዉ ምኞታችንና ጸሎታችን:: የማንንም ጥፋትና ዉድቀት አንመኝም:: በዉድቀታቸዉና በጥፋታቸዉም አንደሰትም:: ምክንያቱም አንድነታቸዉንና ህብረታቸዉን ከአምላካቸዉ ጋር ካደረጉ ሁላችንም በእግዚአብሔር መንግስት እዉነተኛ አምላካችንን በመስቀል ላይ ዋጋ የከፈለልንን በእዉነትና በመንፈስ እያመለክነዉ ሕያዉ ሆነን በመንግስቱ መኖር ነዉ ፍላጎታችንና ልምናችን:: በዚሁ አጋጣሚ ስለ ነፍሳቸዉ የሚያስብላቸዉ ሰዉ ካለና እነሱም ለመስማት ፈቃደኛ ከሆኑ ማንም ይሁን ማን በዚህ ምድር የዘራዉን ፍሬ ማጨዱና መራራዉን ፍሬ መጠጣቱ ስለማይቀር፤ በእዉነተኛ ንስሐ ቢመለሱና መልካም ፍሬ ማፍራት ባለመቻለቸዉ ምክንያት መልካም ፍሬ ለሚያፈሩትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ለተመረጡትና ለተቀቡት ለኢትዮጵያዉያኑ ለሥጋዊዉ ሆነ ለመንፈሳዊዉ ወንበር ለታጩት እዉነተኛ እንደራሴዎች ወንበሩ ቢለቁ የተሻለና የሚበጃቸዉ እንደሚሆን እንዲነግሯቸዉና እንዲያስረዷቸዉ እፈልጋለሁ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር

ሊያደርግ ያሰበዉንና የወሰነዉን ማንም ፍጡር ሊያስቀረዉ ሆነ ሊያዘገየዉ ስለማይችል መራራዉን ጽዋ ጠጥተዉ ከምድሩም ከሰማዩም ሳይሆኑ ቀርተዉ ዳግም የንስሐ እድል ወደ ማይገኝበት ቦታ ከሄዱ ፍርዱ እጅግ ይብስባቸዋልና ነዉ።

ከዉጭዎቹ ምሳሌ ብንመለከት ደግሞ የኢራቁ መሪ ሳዳም ሁሴንና የሊቢያዉ መሪ ሙሀመድ ጋዳፍ «ማንም አይነካቸዉም፤ ከወንበራቸዉም ማንም አይነቀንቃቸዉም» ሲባል፤ የተቆረጠባቸዉ ቀን ሲደርስ ባላሰቡትና ባልጠበቁት መንገድ ከወንበራቸዉ ሊቆረጡና የዉርደት ሞት ሊሞቱ ችለዋል። የግብጹ መሪም ብንመለከት ባለሰቡበትና ባልጠበቁበት ቀን በተከበሩበትና በገነኑበት አገርና ሕዝብ፣ በራሳቸዉ ሕዝብ ተዋርደዉ ከወንበራቸዉ መቆረጣቸዉና የቁም ስቃያቸዉን እያዩ መሆኑን እናዉቃለን።

ታዲያ በዚህ አጋጣሚ ሌሎች የዓለም መንግስታት መሪዎች የሚነግራቸዉ ካለና እነሱም ለመስማት ፈቃደኛ ከሆኑ «ነግ በእኔ» ብለዉ ከመዉደቃቸዉና ከመዋረዳቸዉ በፊት ለእግዚአብሔር እጃቸዉን እንዲሰጡና ወንበሩንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙትና ለሚያስፈጽሙት ለኢትዮጵያዉያኑ ለተመረጡትና ለተቀቡት እዉነተኛ ለእግዚአብሔርና ለእመቤታችን ድንግል ማሪያም ባለሟሎችና እንደራሴዎች አሳልፈዉ ቢሰጡ የተሻለና የሚበጃቸዉ እንደሚሆን እንዲነግሯቸዉና እንዲያስረዷቸዉ እፈልጋለሁ። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለዓለም መንግስታት መዉደቅም መነሳትም ምክንያት የምትሆነዉን ኢትዮጵያን የሚጎበኝበት ወራት ደርሷልና በዚያን ወቅት በኢትዮጵያ ለሚቋቋመዉ የእግዚአብሔር መንግስት እጁን የማይሰጥ መንግስት ሆነ ቡድን እንዲሁም ግለሰብ ዳግም የንስሐ እድሜ ሳያገኝ በእግዚአብሔር ቁጣ ከምድር ይጠረጋልና ነዉ። ጥቅሙ ለራሳቸዉ ነዉ እንጂ እግዚአብሔር «አደርገዋለዉ።» ያለዉን የዓለም ሕዝብ በአንድላይ ቢሰለፍ ሊያስቀረዉ ሆነ ሊያዘገየዉ አይችልምና።

ወደ ነፍስ ጉዳያችን ስንመጣ ደግሞ አሁን ያለዉ የኢትየጵያ መንግስት እንደ ሌሎቹ አገራት መንግስት ሕዝቡንና ምእመኑን ሙሉ በሙሉ ገሏል። ከእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃራኒ ተግባር እየፈጸመ የተመረጠዉን የእግዚአብሔርን ሕዝብ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት እንዲመላለሱ በማድረግ የኃጢአትን ተግባር አንግሷል። ክህደትንና መናፍቅነትን አሳፋፍቷል። የእዉነትን መንገድ አጥፍቷል። ዳንኪራንና ዘፈንን ከህጻን ኅሊና እስከ አዋቂ ኅሊና ዉስጥ በማስረጽ ነፍሳትን አሳብዷል።

ባጠቃላይ በእግዚአብሔር እዉነታ ሲታይ ፍጹም የዲያብሎስን ስርዐት ዘርግቶ የእርሱን ፈቃድ እየፈጸመና እያስፈጸመ ነዉ። ለዚህ ምስክሩ በቴሌቭዥን፣ በሬድዮ፣ በተለያዩ ሕትመቶች የሚታየዉና የሚደመጠዉ፣ የሚነበበዉ ይህንኑ የዲያብሎስን ስራ ያሳያል።

ሕዝቡም የአምልኮ ምንዝርና እንዲፈጽምና በርኩሰት ሕይወት እንዲመላለሱ በማድረጉ በራሱ ላይም በሕዝቡ ላይም የእግዚአብሔርን የከፋዉን ቁጣ እንደሚያመጣ በእምነት ዉስጥ ያለ ሰዉ ይረዳዋል።

ታዲያ ይህን በመናገሬ ነገ የሚደርስብኝን ፈተና፣ መከራ፣ ስደት፣ እስራት፣ ግድያ ሳልገምት ቀርቼ አይምሰላችሁ። ቢበዛ ሊጎዱት ሆነ ሊገሉት የሚችሉት ይህን የተገለጽኩበትን ቅርፊት ሥጋ እንጂ ነፍሴን እንኳን ሊጎዱ አይደለም ይልቁኑ ለታላቅ ክብርና ሽልማት ያበቋታል። ተስፋዬ ምድራዊ ቢሆን ኖሮ ለጊዜያዊ ስልጣን፣ ክብር፣ ጥቅም፣ ዝና፣ ድሎትና ምቾት ስል እንደሌሎቹ ወገኖቼ ኅሊናዬን በመሸጥና በማገለባበጥ የኢህአዴግ ወይን አጋር ድርጅት ዉስጥ አባልና የጨለማዉ ገዥ አገልጋይ መሆን እችል ነበር። እንዲሁም በወገኖቼ አናት ላይም ተረማምጄ ወንበር ላይ እወጣ ነበር። ነገር ግን ሁሉ ተራና ኃላፊ ስለሆነ ስለ እዉነት ከመመስከር ዉጭ ከነችግሬና ከሚመጣብኝ ፈተና ጋር ለመኖር ራሴን ያዘጋጀዉት።

ወደ ኢትዮጵያዊነትና ወደ ሕዝቡ ስንመጣ፣ ይህ የኢህአዴግ መንግስት በጣት የሚቆጠሩትን እጅግ ጥቂት ሰዎች በዘመድ አዝማድና በጎጥ ተቧድነዉ እንዲሁም አንዳንዶችን በአቋራጭ መንገድ ዉስጥ (በጉቦ፣ በትዉዉቅ፣ በጥቅማ ጥቅም.. ወዘተ) እንዲገቡ አድረጎ ቢያበለጽግም እጅግ እጅግ ብዙዎቹን ኢትዮጵያዉያንን ግን በድህነት አረንቋ ዉስጥ እንዲማቅቁ፤ የቀሩት ደግሞ በየመንገዱና በየእምነት ተቋማት ዙሪያ እንዲወድቁ፤ ለልመናና ለችግር፣ ለሮሮ እንዲዳረጉ ያደረገ አንዳች ለሕዝብ ርኅራኄ የሌለዉ ጨካኝ መንግስት መሆኑ ይታወቃል።

ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ልክ እንደ ነፍሳችን ሙሉ በሙሉ አጥፍተዋል። ደምስሰዋል። ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን በማስፋፋት ኢትዮጵያዊነት ሃይማኖትን ክደዋል። ሕዝቡን አስክደዋል። የከፋና የከረፋ ተግባራቸዉ ዉጤት በእናንተ ላይ እንኳ ብንመለከት፡ ከአራቱም ማዕዘን ከኢትዮጵያ ምድር የመጣችሁ ኢትዮጵያዉያን መሆናችሁ ቢታወቅም «አይደለንም ብትሉ» እንኳ፤ መልካችሁ የሚፈርድባችሁ ሲሆን፤ ይኸዉም በነብዩ አርምያስ እንደተነገረዉ ትንቢተ ኤርምያስ ም.፲፫፥፳፫(13፥23) «በዉኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን፣ ወይስ ነብር ዥንጉርጉርነቱን ሊለዉጥ ይችላልን?» ለሚለዉ «አዎን ኢትዮጵያዊ መልኩን ሊለዉጥ ነብርም ዥንጉርጉርነቱን ሊለዉጥ ይችላል በማለት በእግዚአብሔር እዉነታ ላይ ዐይን ያወጣ

ክህደትና ዐመጻ እየፈጸማችሁ መሆኑን ስለሚመሰክርባችሁ ነዉ፡፡ እንኳን እናንተ በዓለም ላይ የተበተነዉ ትዉልድ ኢትዮጵያዊ መሆናቸዉን መልካቸዉ ይመሰክርባቸዋል፡፡

እናንተ አሁን ስትተዋወቁኝ በኢትዮጵያዊነት ስሜት ሳይሆን « እኔ የመጣሁት ከትግራይ (ከትግሬ) ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ብሔሬም ትግሬ ነዉ፡፡ እኔ የመጣሁት ከኦሮሚያ (ከኦሮሞ) ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ብሔሬም ኦሮሞ ነዉ፡፡ እኔ የመጣሁት ከአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ብሔሬም አማራ ነዉ፡፡እኔ የመጣሁት ከሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ብሔሬም ሱማሌ ነዉ፡፡ እኔ የመጣሁት ከአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ብሔሬም አፋር ነዉ፡፡ እኔ የመጣሁት ከሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ብሔሬም ሐረሪ ነዉ፡፡ እኔ የመጣሁት ከጋንቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ብሔሬም ጋንቤላ ነዉ፡፡ እኔ የመጣሁት ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ብሔሬም ጉሙዝ ነዉ፡፡ እኔ የመጣሁት ከአዲስ አበባ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ብሔሬም ስልጤ ነዉ፡፡ እኔ የመጣሁት ከድሬደዋ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ብሔሬም ጉራጌ ነዉ፡፡ እኔ የመጣሁት ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፤ ብሔሬም ሲዳማ፣ ሃድያ፣ ወላይታ፣ ከፊቾ፣ ባስኬቶ .. ወዘተ» በማለት ነዉ እንጂ አንዳችሁም « እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ ከዚህ ስፍራ ነዉ የመጣሁት፡፡» በማለት ስለኢትዮጵያዊነት ብሔራችሁ አንዳች አልገለጻችሁም፡፡ የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጆች መሆናችሁን የዘነጋችሁ፤ የአዳም ዘርነታችሁን ያላወቃችሁ፤ የኖኅ ልጆች የሆኑት የካም፣ የሴም፣ የያፌት ነገዶች ዉህድ የሆነዉ የተመረጠዉ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ኢትዮጵያዊ መሆናችሁን የካዳችሁ ናችሁ፡፡

እዉነተኛዉ ማንነታችሁን አዉቃችሁ ቢሆን ኖሮ እንኳን በኅጣችሁ ተመጻድቃችሁ ልትጠሩበት ቀርቶ ልትሰሙት ኅሊናችሁ ይከብደዉና ይጸየፈዉ ነበር፡፡ ነገር ግን ሌት ተቀን በቴሌቭዥኑ፣ በሬድዮኑ፣ በሕትመት ዉጤቱ ፣ በስብሰባዉ፣ በሽልማቱ የዲያብሎስ ቋንቋ የሆነዉ «ብሔር ብሔረሰቦች» እንደ አቡነ ዘበሰማያት ሲደጋገም ኅሊናችሁ ስለተለማመደና ሆን ተብሎ ጥላቻና በቀል በኅሊናችሁ እንዲያድር ስለተደረገ ኢትዮጵያዊነታችሁን ከልቦናችሁ መንግላችሁ በማዉጣት ኅጣችሁን በልባችሁ አንግሣችኋል፡፡

ለነገሩ እናንተ ብቻ ሳትሆኑ ሕይወት የሌላቸዉ መኪኖች ሳይቀር በታርጋቸዉ «አማራ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ አፋር፣ ሱማሌ ፣ ሐረሪ፣ ጋንቤላ፣ ቤንሻንጉል፣ ደቡብ፡፡» ተብለዉ እየተጠሩ በማየታችን ይህ አሁን ያለዉ መንግስት ኢትዮጵያ የሚለዉን ስም ምን ያህል ጥላቻ እንዳደረበትና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዉያንን ለማጥፋት የተሰለፈ ቅጥረኛና ምንደኛ መንግስት

መሆኑን ያሳይል። አልገባቸዉም እንጂ እንኳን እነሱ ሌሎች አገሮች ኢትዮጵያን ሊያጠፉ የተሰለፉ ሁሉ በእግዚአብሔር ቁጣ ከምድሪቱ ይጠፋሉ፤ ይጠረጋሉ።

ታዲም ይህን ያልኩት በሥጋና ደሜ ስሜት ተነሳስቼ ሳይሆን የኔም ሆነ የእናንተ ፈጣሪ እግዚአብሔር የተናገረዉ ነዉ። በኖኅ ዘመን የዐመጻ ሰዎችንና ልጆችን እንዳልነበሩ አድርጎ ከምድር የጠረገ፣ በሎጥ ዘመን የሰዶምና የጎሞራ ሰዎችን በእሳት ዲን ያጠፋ፣ ግብጻዉያንን በተለያዩ መቅሰፍት የገሰጸ፣ ፈርኦንና ሠራዊቱን በባሕር ዉስጥ አስጥሞ መታሰቢያቸዉን ከምድረ ገጽ ያጠፋ፣ ባጠቃላይ በብሉይ ዘመን ሆነ በሐዲስ ዘመን የሰዉ ልጆችን ኃጢአት ታግሶ ታግሶ ባላሰቡትና ባልጠበቁ ጊዜ የዐመጻ ዋጋቸዉን የሚከፍል አምላክ፤ አሁንም ያለዉ ያዉ እርሱ ስለሆነ፤ ፍቅሩና ርኅራኄዉ የትየለሌ ስለሆነ ነዉ እስከአሁን ለዘመናት እኛችንን እስከምንሰጥ ድረስ በትዕግስት እየጠበቀን ያለዉ እንጂ የዐመጻና የክህደት ጽዋችን በአሁን ሰዐት ጽዋዉን ሞልቶ በመፍሰስ ላይ ይገኛል። ስለ ኢትዮጵያም ጉዳይ እያንዳንዱ አገር(መንግስት)፣ ቡድን ፣ ግለሰብ፣ እግዚአብሔር ስለ ምስጢር አገሩና ስለ ድንግል ማርያም አስራት አገርነቷ ዋጋ እንዲከፍሉበት ያደርጋል። እድሜዉንና ጤንነቱን ይስጠን እንጂ በቅርቡ ሁሉ ተፈጽሞ እናያለን። ኢትዮጵያ ግን ትንሳኤዋ ለዓለም ሁሉ ይገለጻል። ጥፋቷንና ዉድቀቷን የሚመኙ ሁሉ ዉርደትን ይላበሳሉ፤ ያፍራሉ።

እስቲ አንድ ጥያቄ እንድጠይቃችሁ ፍቀዱልኝ? እርስ በእርስ ፊታችሁን ተተያዩ፤ መልካችሁ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ ቢሆንም ኢትዮጵያዊነተታችሁን እንጂ ጎጣችሁን፣ ቋንቋችሁን፣ ሃይማኖታችሁን አይመሰክርም። ይህም የሚያሳየዉ የጎጥና የሃይማኖት ልዩነት የፈጠሩት ራሳቸዉ ግለሰቦች እንጂ እግዚአብሔር እንዳልሆነ ነዉ የምንረዳዉ። መልካችሁ «ይህ ኦሮሞ ነዉ፣ ይህ ትግሬ ነዉ፣ ይህ አማራ ነዉ፣ ይህ አፋር ነዉ፤ ይህ ሱማሌ ነዉ፣ ይህ ሃዲያ፣ ነዉ፣ ይህ ወላይታ ነዉ፣ ይህ ጉራጌ ነዉ፣ ይህ ስልጤ ነዉ... ወዘተ» ብሎ ይገልጻችኋልን? ፈጽሞ አይገልጻችሁም። «እነዚህ ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ» ብሎ ኢትዮጵያዊ ብሔራችሁን ብቻ ነዉ የሚመሰክርባችሁ። እንኳን አሁን ኢትዮጵያዉያን የምንባለዉ ቀርቶ በዙሪያችን ያሉት ጎረቤት አገራት መልኳቸዉ ኢትዮጵያዉያን መሆናቸዉን ነዉ የሚመሰክርባቸዉ።

ነገር ግን ቀኝ ገዥዎች በከፋፋይ ሴራቸዉ ምክንያት ይኸዉ በጎጥና በቋንቋ ተለያይተንና ተከፋፍለን እንገኛለን። እነሱም ቀኝ ገዥዎች ባወጡላቸዉ የዜግነት መጠሪያ ይጠራሉ እንጂ ኢትዮጵያዊ መሆናቸዉን አያዉቁም። እንኳን ቀደም ያሉት ቀርቶ ይኸዉ የዛሬ ሃያ አመት ወያኔ(ኢህአዴግ) መንግስት ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት

ከተነሳዉ ከሻዕብያ ቡድን ጎን በመሰለፍ « ኤርትራ የተባለች አገር የኢትዮጵያ ቀኝ ግዛት ዉስጥ ነበረች። አሁን እኛ የምንመራት «ኢትዮጵያ» የምትባል አገር ኤርትራን በቀኝ ግዛት ለዘመናት ስተገዛ ቆይታ በእኛ ነጻ አዉጪነት ነጻነቷን ስላገኘች ደስ ብሎናል፣ ደስ ይበላችሁ፤ በመንግስታቱ በአባልነት በአስቸኳይ መዝግቧት» በማለት ማፈሪያና አሳፋሪ ታሪክ ሰርተዋል።

በዚህም ምክንያት ከወንድም እህቶቻችን ጋር ተለያይተናል። ኢትዮጵያዊነት ዜግነታቸዉን አንቀበልም «ኤርትራዊ ነን» ብለዉ ኢትዮጵያዊነት ሃማኖታቸዉን ክደዋል። መልካቸዉን የሚነግራቸዉ ሰዉ ጠፍቶ ወይንም መስታወት አተዉ ይሆናል ወይንም እዉነተኛ የነፍስ ዐይናቸዉ አልተከፈተ ይሆናል እንጂ እለት እለት ኅሊናቸዉ(ነፍሳቸዉ) «አንተ እንዴት ኢትዮጵያዊ አይደለሁም ብለህ ክህደት ትፈጽማለህ?» እያለች እንደምትመሰክርባቸዉ ይታወቃል። ለሁሉም ጊዜዉ ሲደርስ እያንዳንዱ ቡድን ሆነ ግለሰብ ዋጋ እንደሚከፍልበት አዉቆ ንስሐ ቢገባ የሚበጀዉ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ለመናገርና ለመምከር እፈልጋለሁ። ሻዕብያና ወያኔ « ልከክልክ እከክልኝ» እንዳልተባባሉ፤ አስር አመት እንኳ ሳይሞላቸዉ በእግዚአብሔር ቁጣ «አይንህን ላፈር» እየተባባሉ ይኸዉ እለት እለት ሲጠላለፉና ሲወነጃጀሉ እንመለከታለን። የሚያሳዝነዉ ግን አንድ ወገን የሆነዉ ትዉልድ እርስ በእርስ እንዲገዳደል፣ እንዲጠላላ፣ ደሙን በከንቱ እንዲፈስ አድርገዉ ኅሊናቸዉን አደንድነዉ በወንበር ላይ እስከ አሁን ካለእፍረት መቀመጣቸዉ ነዉ። ነገር ግን ቀናቸዉ ሲደርስ ስለዐመጻና ክህደት ተግባራቸዉ በዚህ ምድርም ከቅርፊት ሥጋቸዉን ሲለዩም በመቶ እጥፍ ዋጋ ይከፍሉበታል። እናንተ ግን ከጎጣዊ አስተሳሰብ ራሳችሁን አጽድታችሁ አገራዊና አለማቀፋዊ አስተሳሰብ ልትይዙ ይገባል። የሰዉ ዘሮች ሁሉ ወገኖቻችን የአዳምና ሔዋን ዘሮች የአንዱ እግዚአብሔር ፍጥረቶችና ልጆች ናቸዉ።

እናንተም እንኳን የ7500 ዘመን ታሪካችሁን አይደለም የ3000 ዘመን ታሪካችሁን በመሪዎቻችሁና በካድሬዎቻቸዉ አማካይነት ኅሊናችሁ እንዲመረዝ በመደረጉ ወደ መቶ አመት የለወጡትን «አዲሲቷ ኢትዮጵያ» እያሉ ሲያላግጡና ሲሳለቁ ተባባሪ ሆናችሁ። እናንተም ስለተቀበላችዋቸዉ ለወደፊት ደግሞ እንደ እቅዳቸዉና ምኞታቸዉ አገሪቱ ብትንትኗ ወቶ በጎጥ ስማችሁ ነጻ መንግስት መስርታችሁ « እኔ ኦሮሚያዊ ነኝ። እኔ ትግራዊ ነኝ። እኔ አማራዊ ነኝ። እኔ ሱማሌያዊ ነኝ። እኔ አፋራዊ ነኝ። እኔ ሐረሪያዊ ነኝ። እኔ ጋምቤላዊ ነኝ። እኔ ቤንሻንጉላዊ ነኝ። እኔ ሲዳማዊ ነኝ። እኔ ሃዲያዊ ነኝ።.. ወዘተ» በማለት እንድትጠሩ ነዉ የመጨረሻ ግባቸዉና ፍላጎታቸዉ።

አሁን ግን እግዚአብሔር እናንተን መርጧችሁ እዉነቱን እንድታዉቁ ወደዚህ መርቷችኋልና ያለዉን እዉነታ እነግራችኋለሁ። ይኸዉም ኢትዮጵያ የጊዮን (አባይ) ወንዝ

የሚነሳባት በተለያዩ ወንዞች የተከበበች የመጀመሪያዉ የሰዉ ዘሮች የአዳምና ሔዋን መገኛና በሥጋ ተገልጸዉባት የኖሩባት አገር ናት:: በኋላም እንደ አሁን ዘመን የሰዉ ዘሮች ኃጢአት እየበዛና እየከፋ ሲሄድ የዐመጻዉና የክህደቱ፣ የርኩሰቱ ጽዋ ሲሞላ የሰዉ ዘሮች ከምድረ ገጽ ጠፍተዉ ኖኅና ቤተሰቡ ብቻ ተርፈዋል:: ከዚያም የእርሱ ልጆች የሆኑት ካም፣ ሴም፣ ያፌት እንደገና እየተዋለዱ በዝተዉ በአራቱም ማዕዘን በሚበተኑበት ወቅት የሶስቱ ነገዶች ዉህድ የሆነዉ ኢትዮጲስ ተወልዶ ዳግም ለኢትዮጵያዉያን ትዉልድ መነሻ ሊሆን ችሏል:: በኋላም የእርሱ ትዉልዶች በኢትዮጵያ ምድርና በሌላዉ ዓለም ተበትነዉ ሲኖሩ በሰዎች በደልና ኃጢአት፣ ዐመጻና ርኩሰት ምክንያት አንድ ቋንቋ የነበረዉ የዓለም ሕዝብ ቋንቋዉ እንዲደባለቅ በመደረጉ ይኸዉ በቋንቋ፣ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በአኗኗር ተከፋፍለንና ተለያይተን እንገኛለን::

በዚህም ምክንያት ከ195 በላይ አገሮችና መንግስታት ሊፈጠሩና በጥላቻ፣ በጥል ሲኖሩ ይታያል:: አንዱ አንዱን ሊያጠፋ፣ አንዱ በአንዱ ላይ የበላይ ለመሆን በጨለማዉ ገዥ እየተመሩ ሕዝቡን ለስቃይና ለችግር ዳርገዉታል:: አሁን ያለዉ የኢትዮጵያ መንግስት ደግሞ «በኢትዮጵያ ዉስጥ ከሰማኒያ በላይ ቋንቋ ይነገራሉ» ብሎ በብሔር ብሔረሰብ ስም አደራጅቶና ኢትዮጵያዊነትን ብሔር አጥፍቶ 80 አገራትንና መንግስታትን ፈጥሮ የዓለም አገራትን ከ195 ወደ 275 ለማድረስ ሌት ተቀን ሲተጋ እናየዋለን:: ነገር ግን ኢትዮጵዊነት እንኳን ለሶስቱ ነገዶች ዉህድ ዘር አይደለም ለሌላዉም የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚተረፍ መለያ ነዉ::

በሃይማኖት ደረጃ ደግሞ አዳምና ሔዋን ንስሐ ገብተዉ ቃል ኪዳን ከተሰጣቸዉ በኋላ የእግዚአብሔር እንደራሴ ሆነዉ በኪዳነ ልቦና ልጆቻቸዉንና የልጅ ልጆቻቸዉን ሲያስተዳድሩ፣ ሲመሩ፣ ሲያስተምሩ እንደነበረ ይታወቃል:: ከጥፋት ዉኃ በኋላ ደግሞ ኖኅ በቀስተ ደመና ቃል ኪዳን ተቀብሎ የእግዚአብሔር እንደራሴ በመሆን ቤተሰቡንና ትዉልዱን ሲመራ ሲያስተዳድር ነበር:: ከዚያም የጌታችን የመድኃኒታች የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ የሆነዉ ኢትዮጵያዊዉ መልከጻዴቅ በካህንነትና በንጉሥነት ትዉልዱን ሲያስተዳድር ሲመራ ነበር:: በዚህ አገልግሎት እያለ እግዚአብሔር ለዓላማ ያዘጋጀዉን ከአህዛብነት ወደ እግዚአብሔር ማመን የመጣዉን አብርሃምን ባርኮ አስተምሮ ለእግዚአብሔር እንደራሴነት አብቅቶታል::

አብርሃምም በግዝረት ለእግዚአብሔር ራሱንና ቤተሰቡን ለይቶ የእግዚአብሔር እንደራሴ ሆኖ ቃል ኪዳን ተቀብሎ ትዉልዱን ሲመራ ሲያስተዳድር ነበር:: በኋላም ዘሮቹ በፈጸሙት ዐመጻ ምክንያት በግብጽ በባርነት ከቆዩ በኋላ እግዚአብሔር ለአብርሃም በገባለት

ቃል ኪዳን መሰረት ኢትዮጵያዊዉ ካህኑ ዮቶር ጋር ሲያገለግልና ሲማር የነበረዉን ታላቁን ነብይ ሙሴን አስነስቶ ወገኖቹን ከግብጽ ባርነት ነጻ አዉጥቶ ታቦተ ጽዮንንና ኪደነ ኦሪትን ከአምላኩ መቀበሉና ሕዝቡን መምራቱ፣ ማስተዳደሩ ይታወቃል፡፡ በመቀጠልም እግዚአብሔር «እንደ ልቤ» የተባለዉን ነብይ፣ ንጉሥ ዳዊትን ቀብቶ በዙፋን ላይ ማስቀመጡና ሕዝቡን በእንደራሴነት እንዲያስተዳድር፣ እንዲመራ አድርጓል፡፡ ከዚህ በኋላ የአብርሃም ዘር የሆነዉ የንጉሥ ዳዊት ልጅ ንጉሥ ሰሎሞን፤ ከመልከ ጼዴቅ ዘር ከኢትዮጵያዊቷ ንግስት ማክዳ (አዜብ) ጋር ግንኙነት ፈጥሮ ኢትዮጵያዊዉ ቀዳማዊ ምኒልክ ሊወለድና ኪዳነ ኦሪቱ ከነስርዐቱ ከታቦተ ጽዮን ጭምር ወደ ኢትዮጵያ ሊመጣ ችሏል፡፡

በመጨረሻም ከኢትዮጵያዊዉ መልከ ጼዴቅ ዘርና ከአብርሃም ከዳዊት ዘር የተገኘችሁ ቅድስት ድንግል ማርያም ስትወለድ በአዳምና ሔዋን እዉነተኛ ንስሐ ጊዜ « ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ፡፡» ብሎ  ለአዳም ቃል ኪዳን የገባለት የመልከጸዴቅ፣ የአብርሃም፣ የይስሐቅ፣ የያዕቆብ፣ የካህኑ ዮቶር፣ የሙሴ ፣ የነብያት አምላክ ካለበት ሳይጎል ባሕርይዉን ብቻ ዝቅ አድርጎ በተዋህዶ ከእመቤታችን ቅድስት ማርያም ተወለደ፡፡ ከሁለት አካል አንድ አካል፤ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በመሆን ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኖ በምድር ተመላልሶ ክርስትናን መሰረተ፡፡ ኪዳነ ወንጌልን ለዓለም ሰጠ፡፡

ኢትዮጵያም፤ እርሱ ሰዉ የሆነዉ አምላክ የተለያዩ ጸዋትዎ መከራዎችን ተቀብሎ፣ በመስቀል ተሰቅሎ፣ ቅዱስ ሥጋዉን ቆርሶ ደሙን አፍሶ፣ ትንሳኤን አሳይቶ ወደ ቀደመ ክብሩ ከተመለሰ በኋላ በዚያዉ ዓመት (፴፬)በ34 ዓ.ም. በሐዋርያዉ ፊሊጶስ አማካይነት በአዲስ ኪዳኑ አበሜሌክ( ባኮስ) አማካይነት ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ሊገባና ሊስፋፋ ችሏል፡፡ ባጠቃላይ ኢትዮጵያ ሰባቱን ቅዱስ ኪዳናትን ጠብቃ የተገኘች ብቸኛ አገር በመሆኗ የእግዚአብሔር ምስጢር አገር ለመሆን በቅታለች፡፡ መንፈስ ቅዱስ አሳስቦኝ በኔ እዉቀት ደረጃ ይህን ካልኳችሁ ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፉ መጽሐፍቶች ለምሳሌ እንደ «ኢትዮጵያዊዉ በማንነቱ ፍለጋ» በ፲፱፺፩(በ1991)ዓ.ም፣ «ኢትዮጵያ የዓለሙ መፋረጃ» በ፲፱፺፫(በ1993)ዓ.ም፣ «ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት» ቁጥር1እና2 በ፲፱፺፯(በ1997) ዓ.ም.፣ ቁጥር 3 በ፲፱፺፰(በ1998)ዓ.ም «የምስራች» በ፳፻፩(በ2001).ዓ.ም የመሳሰሉትን መጽሐፍቶች ብታነቡ ሰፊ እዉቀት ታገኙበታላችሁ፡፡ የኢትዮጵያዊነት ምንነታችሁን ትረዱበታላችሁ፡፡

አሁን ያላችሁ እዉቀት በአንዳንድ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት በተሰለፉ በኢትዮጵያዉያንና በአንዳንድ ለኢትዮጵያ ጥሩ አመለካከት በሌላቸዉ የዉጭ አገር ሰዎች

የተጻፉ ታሪኮችን ነዉ የምታገኙት:: ስለዚህ ስንዴ ብቻ የምታገኙበትን ብትመርጡ በሥጋችሁም በረከት በነፈሳችሁም ድኅነት ታገኙበታላችሁ:: አሁን ኅሊናዉን የሸጠዉ «ተማርኩ ምሁር ነኝ» የሚለዉ «እገሌ ስለ ኢትዮጵያና ስለ ሕዝቡ እንዲህ ብሏል» እያሉ ሆዳቸዉን ለመሙላትና ለጊዜያዊ ስልጣንና ጥቅም ሲሉ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን እያጠፉ ያሉትን አስመሳይ ምሁራን፤ ምን ያህል የመጨረሻ መሃይሞች መሆናቸዉን በራሳቸዉ ላይ እየመሰከሩ በማየታችን « ምነዉ እንደዚህ ዐይን ያወጣ ክህደት ከሚፈጽሙ ንጹህ ኅሊናቸዉን ይዘዉ በኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታቸዉ ላይ ክህደትን ሳይፈጽሙ በመሃይምነትና በድህነት ኖረዉ ቢሆን እጅግ ይሻላቸዉ ነበር:: አሁን ግን ሊሚያልፍ ጊዜ የማያልፍ ክህደትና ዐመጻ በእናት አገራቸዉ ላይ መፈጸማቸዉ ለዘለዓለም የዉርደትን ስም ተላብሰዉ በምድርም በሁለተኛዉ ዓለምም ይኖራሉ» እንላለን::

እዚህ ላይ አንድ እዉነታ ልንገራችሁ፤ እዉነተኛ ሰዎች በቅንነትና በእዉነት የሚሰጡንን ምክርና ትምህርት እኛም በቅንነትና በእዉነት ልንቀበለዉ ይገባል:: እንኳን መጨረሻቸዉ ምን እንደሚሆን በእርግጠኝነት ስለማናዉቀዉ ግለሰቦች ዝናና ክብር አይደለም በቅርበት ስለራሳችን ስለምናዉቀዉ በሥጋና ደም ስሜት ለራሳችን ጥብቅና ልንቆም አይገባም:: ደካማ ጎናችንን አዉቀን ራሳችንን ማስተካከልና ማረም፤ ጠንካራ ጎናችንን ደግሞ የበለጠ ማጠናከር ነዉ የሚገባን እንጂ «ድክመታችን ለምን ተነገረን? ጉድለታችን ለምን ተገለጸ?» ብለን በቅንነትና በእዉነት ከሚናገረን ሰዉ ጋር ጠብ የምንገባ፣ የምናቃወም ከሆነ በተዝዋዋር ከእዉነት አምላክ ጋር እየተጣላን መሆኑን በሚገባ ልንገነዘብ ይገባል:: ያ ስለ እዉነት የሚናገረዉ ሰዉ ተቃዉሙና ቅሬታ እንዳይቀርብበት እዉነታዎችን ሊደብቅና ሊሸፋፍን ይችላል:: እንዲሁም በሁሉ ዘንድ ለመወደድ ሲል እያንዳንዱ በሚፈልገዉ ስሜት ሊናገርና ሊሸነግል ይችላል:: ነገር ግን እንደዚህ አይነት ሰዉ የእግዚአብሔር አገልጋይ ለመሆን አይችልም:: «እዉነቱን እዉነት፤ ሐሰቱን ሐሰት፤ እምነቱን እምነት፤ ክህደቱን ክህደት፤ ከእግዚአብሔር የሆነዉን ከእግዚአብሔር፤ ከዲያብሎስ የሆነዉን ከዲያብሎስ፤» ማለት ካልቻለ እሱ እዉነተኛ እረኛ አይደለም::

ምክንያቱም እንደ አለማዉያኑ «ተመሳስለህ ኑር፣ ከራስ በላይ ንፋስ» የሚለዉን የሥጋዉያን ፈሊጥ ተከትሎ ለሆዱና ለጥቅሙ ያደረ ነዉ እንጂ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚጠብቅ የእግዚአብሔር ባለሟልና አገልጋይ አይደለም:: ስለዚህ እናንተም አንድነትና ህብረት ልትፈጥሩ የሚገባችሁ ስለ እዉነት ራሱን ክዶ ከሚመሰክርና በእዉነትና በመንፈስ ከሚያገለግል ሰዉ ጋር እንጂ ስለ ግለሰቦች ክብርና ዝና ስትሉ ከእዉነተኛ ሰዉ ጋር እንዳትጣሉ:: እግዚአብሔር እንኳን በተግባርና በንግግር የፈጸምነዉን ኃጢአት አይደለም

በአሳባችን የፈጸምነዉን ኃጢአት ያዉቃል፡፡በወሬ ማጣፈጥና በማስመሰል አናታልለዉም፡፡ ስለ እዉነት ይፈርዳል፤ ይዳኛል እንጂ እንደ ሰዉ « ይህ ሰዉ ከዚህ በፊት እንዲህ መልካም ነገር አድረጎልኛል፣ ባለዉለታዬ ነዉ፣ ዘመዴ ወገኔ ነዉ ይጠቅመኛል.. ወዘተ» በማለት በሥጋዊ አስተሳሰብ ተመርተን ከእግዚአብሔር እዉነታ ጋር እንዳንጣላ፡፡

ያለፉትን ሰዎች እንዲሁም ከባለጊዜነት የተሻሩትን ሰዎች መዉቀስ፣ መኮነን ፣ መወንጀል ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በአካለ ሥጋ በዚህች ምድር የሌሉት ሊከራከሩንና እዉነታዉን ሊገልጹ አይችሉምና፤ በአካለ ሥጋ ያሉት ደግሞ ከወንበራቸዉ ስለተሻሩ አቅም ኖሯቸዉ ሊከራከሩና ሊሰሙ እንዲሁም ሊያስሩን፣ ሊቀጡን ስለማይችሉ ነዉ፡፡ ትልቁ የኅሊናችን እዉነተኛነትና ጽናት የሚለየዉ በሥጋና ደም ስሜት ባልሆነ መልኩ በቅንነትና በእዉነኛ ኅሊና፣ ባለ ጊዜ የሆኑ ሊጎዱንና ሊያጠቁን የሚችሉትን ባለወንበሮች የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባራቸዉን መቃወምና « ይህ ትክክል አይደለም፡፡ በዚህ መንገድ ሂዱ፡፡ ይህ ደግሞ ጥሩ ነዉ በዚሁ ቀጥሉ፡፡» በማለት ካለምንም ፍርሐት የሚገስጽና ስለመልካም ተግባር የሚያበረታታ አደርባይ ያልሆነ ሰዉ ነዉ፡፡

በአሁን ሰዐት እነደዚህ የሚያደርግ እንኳን ከሥጋዉያን ቀርቶ ከመንፈሳዉያን ከተገኘ እግዚአብሔር ያዉቃል፡፡ ሁላችንም ማለት ይቻላል መስሎ ማደርን የምንመርጥ፣ ስለ እዉነት ደፍረን የማንመሰክር ሰዎች ነን፡፡ ቅድሚያ የምንሰጠዉ ለጥቅማችን፣ ለክብራችን፣ ለስልጣናችን፣ ለዝናችን ነዉ ፡፡ በዚህም ምክንያት የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ስራ አስፈጻሚዎች፤ ሆዳቸዉ አምላካቸዉ የሆነ፤ ሲፈልጉ በሆዳችን ኅሊናችንን ያሸጡናል፣ ሲፈልጉ በብልጭልጩ ያታልሉናል፣ ነፍሳችንን እየገደሉ ለሥጋችን « ይህን ሰራንላችሁ፡፡» እያሉ ይሸነግሉናል፡፡ ለመሆኑ ሥጋችን የምትፈልገዉ ነገር ሁሉ ተሟልቶ ነፍሳችን ከደኸየችና ከተጎሳቀለች ምን ጥቅም አለዉ?! ይህ ቅርፊት ሥጋችን ምን ቢደላዉና ቢመቸዉ ለአፈር አስረክበን ነዉ እዉነተኛዋን ሕያዉ ነፍሳችንን ይዘን በረቂቅ አካል (በምሳሌያዊ ባሕርይ) ሆነን ወደተዘጋጀልን ቦታ የምንሄደዉ፡፡

በምድራዊ ሕይወታች ዘመን የሚታየዉ የማስመሰልና የሽንገላ ሕይወትና ኑሮ እጅግ የሚያስገርምና የሚያሳዝን ነዉ፡፡ በአሁን ዘመን ሰዉ ጥቅም እሳካላገኘበት ድረስ ሰዉን አይፈልግም፡፡ ጥቅም የሚያገኝበት ከሆነ ግን ኅሊናዉን ሸጦ ማንኛዉንም ነገር ከማድረግና ከመናገር ወደ ኋላ አይመለስም፡፡ ለዚህም ነዉ ገንዘብ ያላቸዉ፣ ባለወንበር፣ ታዋቂ ዝነኛ ሰዎች ብዙ ወዳጅና ወገን አላቸዉ፡፡ ሁሉ ያወድሳቸዋል፤ ያገናቸዋል፡፡ ነገር ግን አንድ ቀን ሁሉን ነገር ቢያጡ ዞር ብሎ የሚያያቸዉ የለም፡፡ ምክንያቱም ግንኙነቱ ስለ ኅሊና ስለ

እዉነት ሳይሆን ስለ ጥቅም ብቻ ስለነበረ ነዉ:: በተቃራኒዉ ደሀና ባለጊዜ ያልሆነ ሰዉ ማንም አይፈልገዉም:: ምክንያቱም ጥቅም አይገኝበትምና:: ነገር ግን አንድ ቀን ሀብታም ወይንም ባለወንበር ቢሆን ሁሉም ወዳጁና «ምን ልታዘዝ? ምን ላድርልህ? ምን ጎደለብህ? እንደህ ልሁንልህ፤ እንዲህ ነህ፤» ብሎ የሚቀርበዉና የሚያገነዉ ነዉ:: ይህ ጠባይ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች ሳይሆን የአህዛብ እግዚአብሔርን የማያምኑና የማያመልኩ ሰዎች ጠባይ ነዉ:: ነገር ግን ይህን ጠባይ የያዝን ሰዎች ደግሞ በአፋችን የእግዚአብሔር አማኛና አገልጋይ ነን የምንል ነን::

እዉነተኛ ሰዉ ግን ማንኛዉም ግንኙነት ከጥቅም ጋር በማያያዝ ሳይሆን ሀብታሙም ደሀዉም፣ ባለወንበሩም ተራዉም፣ ዝነኛዉም ታዋቂ ያልሆነዉም፣ ባጠቃላይ ሁሉም ሰዉ የእግዚአብሔር ፍጥረቶችና ልጆች የአዳምና ሔዋን ዘሮች ናቸዉ ብሎ እንደ ወገኑ በመቁጠር ነዉ ሊቀርብ የሚገባዉ:: ከእግዚአብሔር ዘንድ ደግሞ የተለየ ዋጋ የሚያገኘዉ አንዳች ዉለታ ሊመልስለት ለማይችለዉ አንዳች ዉለታ ሳይጠብቅ ችግረኛንና ደሀን ሰዉ እርዳታና እገዛ ሲያደርግለት ነዉ:: በዓለም የሚታየዉ ግን በተገላቢጦሹ ነዉ:: ያለዉን ሰዉ እንኳን ያላቸዉ የሌላቸዉ ሰዎች ተበድረዉ ዉለታ ቢዉሉለት ፈቃዳቸዉ ነዉ፤ ምክንያቱም አንድቀን የበለጠዉን ዉለታ ይዉልልኛል በሚል እምነት :: በተቃራኒዉ ደግሞ የሌለዉን ሰዉ ሀብት የተረፈዉ ሰዉ እንኳ ዞር ብሎ አያየዉም፤ ምክንያቱም አንዳች ጥቅም ስለማላገኝበት ስለምን መልካም ነገር አደርግለታለሁ በሚል እምነት:: ይህ ሁሉ ጸባይ የአህዛብ ነዉ እንጂ በእግዚአብሔር እናምናለን የሚሉት ሰዎች አልነበረም:: እየታየ ያለዉ ግን እግዚአብሔርን የማያምኑ ሰዎች አንዳች ዉለታን ሳይጠብቁ በሰብአዊነት ብቻ እርዳታን ያደርጋሉ:: እምነት አለኝ የሚለዉ ግን በስስትና በስግብግብነት ሕይወት እየተመላለሰ የዓለም ሀብትን ንብረት የእርሱ ሆኖ ሌት ተቀን ቢተኛበት ምርጫዉ ነዉ::

በዚህች ስደት ዓለም ዉስጥ ከታች ምንም ከሌለዉ እስከ በሀብት እሰከ በለጸገዉና ከተራዉ ሰራተኛ እስከ አገር መሪዉ ድረስ ያለዉ ልዩነት የስራ ድርሻ ነዉ እንጂ እያንዳንዱ ሰዉ የራሱ ድርሻና ኃላፊነት ያለበት ነዉ:: ይልቁኑ ስልጣኑ ከፍ እያለ የሚሄድ ሰዉ የብዙ ሰዉ ኃላፊ ስለሆነ የበለጠ የአገልግሎት ተግባር ሊፈጽምና የሁሉም አገልጋይ መሆኑን ተረድቶ ከእግዚአብሔር ብቻ ዋጋ በመጠበቅ እንደ አገልጋይነቱ ሊመላሰስና ሊያገለግል ይገባል እንጂ ራሱን የተለየ አድርጎ በመቁጠር ሰዎች እንዲያመልኩትና እንዲያገኑት ማስደረግ የለበትም:: በሀብትም የበለጸገዉ ወገኑን ሊረዳና ከችግር ሊያላቅቅ ይገባል እንጂ በድሆች አናት ላይ ልረማመድ፣ ልመለክ ማለት የለበትም::

ይህን ርዕስ ለማጠቃለል አሁን ያለዉ የኢትዮጵያ መንግስት ሕዝቡንና ምእመኑንም በነፍሱ አሳምጿል፤ አስክዷል፤ አስረክሷል:: ይህም ስርዐቱ የሚመራዊ እንደ ሶሻሊስት ስርዐት እግዚአብሔር የለሽ በሆነዉ ፍልስፍና በአብዮታዊ ዲሞክራሴ እንዲሁም በሌላኛዉ ክህደት በካፒታሊስት ስም የዲያብሎስን ፈቃድ እየፈጸመና እያስፈጸመ በመሆኑ ነዉ:: ለዐመጻና ለክህደት ተግባር ያሰለፉት ሕዝቡንና ምእመኑን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔር አገልጋዮች የተባሉትን የሃይማኖት አባቶችን ጭምር ነዉ:: በዚህም ምክንያት የእግዚአብሔርን ስም እየጠሩ ተግባራቸዉ ግን የጨለማዉ ገዥ ተግባር መፈጸምና ማስፈጸም ነዉ:: ለዚህም በየጊዜዉ በመገናኛ ብዙሃን፣ በቴሌቭዥን፣ በሬድዮን ፣ በሕትመት ዉጤቶች፣ በስብሰባ ላይ የምንመለከተዉ፣ የምናዳምጠዉ፣ የምናነበዉ ነዉ:: ምዕመኑንም የአምልኮ ምንዝርና እንዲፈጽም አድርገዋል:: ሌላዉ ደግሞ ኢትዮጵያዊነትን ሙሉ በሙሉ ደምስሰዉ ዘረኝነትንና ጎጠኝነትን አስፋፍተዋል፤ ኢትዮጵያዊ ሃይማኖትን አጥፍተዋል:: ለዚህም ምስክሩ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊ ብሔሩን እንዲክድ አስገድደዉ በየቀበሌዉ መታወቂያ ላይ በጎጡ ብሔር እንዲጠራ አድርገዉታል::

ወደ ቋንቋ ስንመጣ በመጀመሪያ እንድታዉቁ የምፈልገዉ የሰዎች ቋንቋ የተለያየዉ የጽድቅ ዋጋ ሆኖ ሳይሆን የሰዎች የክፋት፣ የተንኮል፣ የክህደት፣ የዐመጻ፣ የርኩሰት ሕይወት እግዚአብሔርን ስላስቆጣ የኃጢአት ዋጋ ሆኖ ነዉ በሰዎች ላይ የተከሰተዉ እንጂ ቀድሞ የሰዉ ዘሮች የሚነጋገሩበትና የሚግባቡበት አንድ ቋንቋ ብቻ ነበር:: ከዚህች ምድራዊ ሕይወት በሥጋ ሞት ስንለይም በእግዚአብሔር መንግስት በአንድ ቋንቋ ነዉ የምንግባባዉ፤ የምንነጋገረዉ:: ስለዚህ የቋንቋ መለያየትን የሚያስፋፋ መንግስት ሆነ ግለሰብ በተዝዋዋሪ ሰዎችን በዐመጻቸዉ፣ በክህደታቸዉ፣ በርኩሰታቸዉ እየቀጣቸዉ ከእግዚአብሔር ጸጋ እያራቃቸዉ መሆኑን ሊያዉቅ ይገባል:: የእግዚአብሔር ፈቃድና ጸጋዉ የበዛለት ግለሰብ ሆነ ቡድን እንዲሁም መንግስት የአዳምን ዘር ወደ አንድነት የሚያመጣና የቀድሞ የጽድቅ ስራ እንዲሰሩ በማድረግ ወደ አንድ የሚግባቡበትና የሚዋሃዱበት ቋንቋ ነዉ የሚያመጣዉ እንጂ እንደ ባቢሎን ሰዎች ቋንቋቸዉን የሚደበላልቅ፣ አንድ እንዳይሆኑ፣ እንዲከፋፈሉ፣ እንዲለያዩ የሚያደረግ ከሆነ ግን የክፉ ትንቢት ፈጻሚ የዐመጻ ሰዉ ነዉ ማለት ነዉ::

ታዲያ አሁን በኢትዮጵያ የሚታየዉ የክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች ዉጤት ነዉ:: ይኸዉም ኢትዮጵያዉኛ ቋንቋችሁን አማርኛ የሚባለዉን እንድትጠሉ፣ እንዳትነጋገሩበት፣ እንዳትማሩበት፣ እንዳትሰሩበት በመደረጉ ብዙዎቻችሁ በአስተርጓሚ ነዉ የቀረባችሁት:: አንዳንዳንዶቻችሁ ገና ከህጻንነታችሁ ጀምሮ በቋንቋዉ ላይ ጥላቻ እንዲያድረባችሁ በመደረጉ ምክንያት የራሳችሁን ቋንቋ ትታችሁ በባዕዳን ቋንቋ እንግሊዘኛ እንድትማሩ፣ እንድትናገሩ

ስለተደረጋችሁ ይኸዉ ጥያቄያችሁን በአማርኛ ከማቅረብ ይልቅ በእንግሊዘኛ ለማቅረብ ተገዳችኋል፡፡

ሌላዉ ቢቀር እናንተ ከአራቱም ማዕዘን ከኢትዮጵያ ምድር የመጣችሁት እርስ በእርስ መነጋገርና መግባባት፣ አንድነት መፍጠር ተስኗችሁና አቅቷችሁ በጎጥ በጎጥ ተለያይታችሁና ተቧድናችሁ ትነጋገራላችሁ፣ ትወያያላችሁ፣ በአንድ ላይ ለመነጋገር ደግሞ አስተርጓሚ ትፈልጋላችሁ፡፡ እናንተ ብቻ አይደላችሁም ፊደል ቆጠሩ፣ ተማሩ የተባሉት በኮሌጅና በዩንቨርስቲ ዉስጥ የሚማሩ በጎጥ በጎጥ ተባድነዉ፣ ተከፋፍለዉ ሲወጡ ሲገቡ እንዴት ያሳዝናሉ! በስተት እንኳ በንግግራቸዉ ዉስጥ አማርኛ ከተናገሩ ያ እንግሊዘኛዉን እየደባለቀ የሚናገረዉ ሰዉ የአማርኛዉን ቋንቋ ሲደባለቅ ከሰማ «ዛራፍ አካኪ» ብሎ የተናገረዉ ምስኪን ጓደኛ ላይ ያንባርቃል፤ ይገስጻል፤ ይተቻል፤ ይቆጣል፡፡ ይህ መንግስት እደዚህ አይነት ትዉልድ ነዉ የፈጠረዉ፡፡ ይህም የሚያሳየዉ ሕዝቡ አንድነትና ፍቅር ህብረት እንዳይኖረዉ፤ በጉርብትና በጋብቻ እንዳይዋሀድ ያደረገዉ ጥረቱ እንዳቀደዉና እንደተመኘዉ መሳካቱን ነዉ፡፡ ስንቶች መሰላችሁ በጎጣቸዉ መለያየት ምክንያት ጥላቻ ተፈጥሮባቸዉ ከጋብቻቸዉ የተፋቱት! ስንቶቹ መሰላችሁ የአዳም ዘር መሆናቸዉን ዘንግተዉ የማይፈልጉትን የጎጥ ዘር ደም በዉስጣቸዉ በመኖሩ በስሪንጅ መጠዉ ማሶገድ ቢችሉ ከራሳቸዉም ከልጆቻቸዉም መጠዉ ለማስወገድ በቁጭትና በጥላቻ የሚናገሩ! ብቻ ያዉ እናንተም የምታዉቁት ብዙ ብዙ ነገር ታይቷል፤ ተሰምቷል፡፡

የሚገረመዉና የሚያስተዛዝበዉ እነዚህ የዲያብሎስ እንደራሴ የሆኑት መሪዎችና ባለስልጣናት እንዲሁም ካድሬዎች፤ እነሱ በጠሉትና ባስጠሉት አማርኛ ቋንቋ ይናገሩበታል፡፡ አገር ይመሩበታል፤ ያስተዳድሩበታል፤ ይሰሩበታል፡፡ እንኳን እነሱ አይደለም ልጆቻቸዉ እንዲማሩበት፣ እንዲነጋገሩበት ያደርጋሉ፡፡ ማመዛዘንና ማገናዘብ የተሳነዉን የዋሁን ደግሞ ጥላቻ ፈጥረዉበት እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ደርሶ እንኳን አገር ሊመራበትና ሊያስተደድርበት ቀርቶ ራሱን መግለጽ እንዳይችል አድርገዉታል፡፡ ይህም የሚያሳየዉ በአገሪቱ በአራቱም ማዕዘን አገሪቷን እነሱና ልጆቻቸዉ ብቻ እንዲያስተዳድሩ፣ እንዲመሩ፣ እንዲሰሩ ለማድረግ የፈለጉና ያቀዱ ነዉ የሚመስለዉ፡፡ ወይንም ለወደፊት እያንዳንዱ «ብሔር ብሔረሰብ» ነጻ መንግስት መስርቶ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ጠፍታ ሁሉም በጎጡ ቋንቋ ጠቅላይ ሚንስትር፣ ፕሬዘዳንት፣ ሚኒስትር፣ ኃላፊ እንዲሆን አቅደዉና ፈልገዉ ይሆናል፡፡ ማፈሪያና አሳፋሪ አስተሳሰብ ያዙ እንጂ፤ እንኳን በአራቱም ማዕዘን ያሉ ኢትዮጵያዉያን በጋራቸዉ ቋንቋ ኢትዮጵያዉኛ ቋንቋ (አማርኛ) ቋንቋቸዉ መነጋገር፣

መማር፣ መስራት አይደለም፤ ሌሎች የአፍሪካ አገራት በባዕዳን ቋንቋ በእንግሊዘኛዉ፣ በአረብኛዉ፣ በፈረንሳይኛዉ፣ ይናገራሉ፤ ይማራሉ፤ ይሰራሉ፤ ይመሩበታል፤ ያስተዳድሩበትል፡፡

እናቶቼና እህቶቼ፤ እናንተ ግን ወደ ሙሉ እዉነት ደርሳችሁ አንድነታችሁንና ህብረታችሁን ከእግዚአብሔር ከሆነ እዉነታ ጋር ብቻ አድርጋችሁ አዲሱ ትዉልድ ወደ እዉነተኛ ማንነቱ መቶ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነቱን በሚገባ ተረድቶ፣ አስተሳሰቡን ሰማያዊ አድረጎ፣ በእዉነትን በመንፈስ አምላኩን አምልኮ፣ ወገኖቹን የአዳም ዘር በቅንነትና በእዉነት አገልግሎ በቀሪዉ ዘመን ለእግዚአብሔር መንግስት  የሚያበቃ ሕይወት ይዞ፣ ታሪክ ሰርቶ እንዲያልፍ አድርጉት እንጂ አሁን እንደሚታየዉ የከፋና የከረፋ አሳብ ፈጥረዉ አገሪቱን በቋንቋ ከፋፍለዉ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት እንደተሰለፉት የክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች እንደሆኑት የዐመጻ ልጆች እንዳይሆኑ፡፡ እነሱ ለፈጸሙት የዐመጻና የክህደት ተግባር በቅርቡ ዋጋ ከፍለዉበት በእግዚአብሔር ቁጣ ከወንበረቸዉ መቀረጣቸዉና መጠረጋቸዉ አይቀርም፡፡ ኢትዮጵያ ሆነች ዓለም ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተምልክናዉ በአንድ ላይ ሆነዉ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚመሩና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም በእግዚአብሔርና በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ለተመረጡና ለተቀቡ ለኢትዮጵያዉያኑ ለአንድ ንጉሠ ነገሥትና ለአንድ እጨጌ ተላልፋ እንደተሰጠቻቸዉ ልታዉቁ ይገባል፡፡ «መች?» ብሎ የሚጠይቅ ሰዉ ካለ ከእግዚአብሔር በተነገረኝ መሰረት አሁን በኔና በእናንተ ትዉልድ መሆኑን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡

እንኳን ብሔራዊ ቋንቋችሁንና ለዓለም የሚተረፈዉን አማርኛ አይደለም የጥንቱ ቀዳሚ ቋንቋችሁን አሁን ሊጠፋ የደረሰዉንና ትዉልዱ ቦታ ያልሰጠዉን ምድራዊ ሆነ ሰማያዊ ምስጢራትን ለማወቅ የሚረዳችሁና የተለያዩ የጥንት መጽሐፍትን ለመመርመር የምትችሉበት እንዲሁም መንፈሳዊ አገልግሎቱንም ምሉእ የሚያደርገዉን ግእዝ ቋንቋችሁን ልታዉቁና ልጆቻችሁም እንዲማሩት ልታደርጉ ይገባችኋል፡፡ አሁን ያለዉ የተማረዉ ክፍል ለራሱ ቋንቋ ትኩረት ሊሰጥ ቀርቶ፤ ለባዕዳኑ ቋንቋ ለእንግሊዘኛ ፊደል ጥንቃቄ የሚሰጠዉን ያህል እንኳ ለግእዙ በተለምዶ አማርኛ ፊደል ለምንለዉ ጥንቃቄ አይሰጥም፡፡ ለምሳሌ የእንግሊዘኛዉ ፊደል ኢ በሚጻፍበት ቦታ ኤ ብትጽፉ ስህተት እንደሆነና  በካፒታል ሌተር መጻፍ ያለበትን በስሞል ሌተር ብትጽፉ መምህሮቻችሁ ነጥብ እንደማይሰጧችሁና ስህተት እንደሆነ እንደሚያሳዉቋችሁ ይታወቃል፡፡

ወደ ራሳችንን ቋንቋ ስንመጣ ግን በአንደኛና በሁለተኛ ደረጃ ያለ ተማሪ አይደለም ባለ ሰርተፊኬት፣ ባለ ዲፕሎማ፣ ባለአንድ፣ ባለ ሁለት፣ ባለ ሶስት ድግሪ ይዘን በአማርኛዉ

አጻጻፍ፤ ስ እና ሲ፣ ር እና ሪ፣ ም እና ሚ፣ ሠ እና ሰ .. ወዘተ የመሳሰሉትን እየለዋወጥንና ፊደል እያጎደልንና እየጨመርን እንደፈለግነዉ ነዉ የምንጽፈዉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያን ቁጥር በተማሪዉም ባልተማሪዉም አይታወቅም፡፡ እስቲ ከእናተ መካከል የኢትዮጵያዉያን  አስር ቁጥርን ጽፎ የሚያሳየኝ ሰዉ አለ? የለም፡፡ ነገር ግን የዐረብ ቁጥርን ብጠይቅ ከህጻን አስከ አዋቂ ድረስ  ያዉቀዋል፡፡ ይህ ሁሉ የሆነዉ ለአገሩ ቋንቋና ፊደል የሚቆረቆር አካል ሆነ ግለሰብ ባለመኖሩና ይልቁንም የራሰን ማጥፋትና ማጥላላት ዘመቻ እየተደረገ ስለሆነ ነዉ፡፡

ይህ ገዱይ ሁላችንንም የሚመለከት ቢሆንም በዋናነት ለዘመናት እንደ ትምህርት ሚኒስቴር ሲያገለግል የነበረዉ ቤተ ክህነት፣ እንኳን ማስተማርና ማስጠበቅ ቀርቶ አብዛኛዎቹ የዐመጻና የክህደት ተባባሪ ሆነዉ በማጥፋቱና በማጥላላቱ ዘመቻ ላይ ናቸዉ፡፡ ስለዚህ እናንተ ያልተማራችሁትንና ያልተገለጸላችሁን እዉነተኛ ማንነታችሁንና የራሳችሁን እንዴት ልታዉቁ ትችላላችሁ!፡፡ ታሪካችሁንም ብጠይቃችሁ ዉጪዎችና ስለ ኢትዮጵያዊነት አንዳች ስሜት የሌላቸዉ ይልቁኑ ሊያጠፏት የተነሱ ሰዎች የጻፉትን ታሪክ ነዉ የምትነግሩኝ፡፡  ይህ ደግሞ ስህተታችንን የሚያሳዉቀንና የሚያስተምረን ሰዉ ባለመኖሩ ምን ያህል እኛ ኢትዮጵያዉያን የራሳችን የሆነዉን ነገር የምናቃልልና የምናጣጥል፤ በተቃራኒዉ ደግሞ የራሳችን ያልሆነዉን እንደምናገንና እንደምናራቅቅ ነዉ የሚያሳየን ፡፡

ይህም የሆነበት ዋንኛ ምክንያት ካለፉት ስርዐቶች ጀምሮ የትምህርት ስርዐቱ እንደማንነታችን እንዳንማርና የራሳችንን እንዳናዉቅ በዉጭዎች ተጽህኖ ስር እንድንወድቅ ስለተደረገ ነዉ፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ እግዚአብሔርን በግልጽ ክደን የሰዉ ስር የተገኘዉ «ከጦጣ መሰል እንስሳ በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ ( በኢቮልሽን) አማካይነት ነዉ፡፡» በማለት በክህደት የተሞላ ዘመናዊ ትምህርት እንድንማር ስለተደረገ ነፍሳችን በሞት ሕይወት ዉስጥ እንድትመላለስ ተደርጓል፡፡ ታዲያ አምላኩን የካደ ትዉልድ እንዴት ስለማንነቱ ያስብ? እንዴት የአዳም ዘሮች ሁሉ «አባቶቼ፣ እናቶቼ፣ ወንድሞቼ፣ እህቶቼ፣ ልጆቼ ናቸዉ» ብሎ ያስብ? እንዴት ተስፋዉን ሰማያዊ አድርጎ እግዚአብሔርን በመዉደድና በመፍራት ይመላለስ? እንዴት እግዚአብሔርም ሰዉም ደስ የሚሰኝበትን ተግባር ለመፈጸም ይትጋ? እንዴት በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት፣  በመልካም ተግባር ይመላለስ? ባጠቃላይ ማንነቱንና ምንነቱን አዉቆ ከኃጢአት ተግባርና ንግግር ራሱን ለይቶ ሌት ተቀን እግዚአብሔርን አስደስቶ ይኑር?

ዘጠነኛዉ ጥያቄችሁ የሆነዉ « የእኛ የሃይማኖት አባቶችና መምህራን አልኮል መጠጦች ይከለክላሉ፤ ጫትንና ሲጃራንም አንዳንዶቹ ይከለክላሉ፤ እንዳንዶቹ ደግሞ ይፈቅዳሉ፤ በእናንተ ሃይማኖት «በግድ መጠጣት አለበት፡፡» በሚመስል መልኩ አንዳንድ

አገልጋዮችና ምዕመናን ጠጥተዉ ሲሰክሩ ይታያሉ:: ሌላዉ ደግሞ በእናንት አንዳንድ የሃይማኖት ሰዎች ቡና ይከለከላል:: በነዚህ ላይ ያሎትን አስተያየት ቢሰጡን?» በማለት ላቀረባችሁት ጥያቄ ያለኝ ምላሽ የሚከተለዉ ነዉ::

በእርግጥ የአልኮል መጠጥ ጉዳቱ በታላቁ አባት በኖኅ ሕይወትና በሎጥ ሕይወት ታይቷል:: የአልኮል መጠጥ ራሳችንን እንዳንገዛና ለኃጢአት ተግባር እንድንደፋፈር የሚያደርግ፤ ራሳችንን ጥለን እንድንዋረድና እንድንቀል የሚያደርግ፤ ባጠቃላይ ሰይጣናት ፈተና አምጥተዉ ድል የሚያደርጉበት መሳሪያ መሆኑን በሁላችንም ዘንድ ይታመናል የሚል ግምት አለኝ:: ይሁንና በእኛ አገር በኢትዮጵያ ቀደም ያሉት አባቶቻችንና እናቶቻችን፣ ወንድምና እህቶቻችን እንደ ዉኃ ለጥም ብቻ ነበር ጠላዉን፣ ጠጁን ፣ ብርዙን የሚጠቀሙበት እንጂ ለመስከርና ለመወላገድ አልነበረም:: ይህንን የሚጠጡት ራሳቸዉን የገዙ መጠናቸዉን የሚያዉቁ ነበሩ እንጂ አሁን እንደሚታየዉ በዳንኪራዉ፣ በዘፈኑ ቤት፤ ለስካር፣ ለጭፈራ፣ ለዝሙት፣ ለጥልና ለድብድብ፣ ለድፍረት አልነበረም:: አሁን ግን በዓለሙም በተቀደሰዉ ስፍራም ሰዎች ሰክረዉ ይንገዳገዱበታል፣ ይጣሉበታል፣ ይደባደቡበታል፣ ይገዳደሉበታል:: ይህም የሚያሳየዉ የሚጠጣዉ ለዉኃ ጥም ሳያሆን ለስካር መሆኑን ነዉ:: ከዚህ አንጻር ባይጠጣ ይመረጣል:: ነገር ግን ራሳቸዉን ገዝተዉ ለዉኃ ጥምነት ብቻ የሚጠጡትንና በበዐል ላይ ለበዐሉ ድምቀትና ለመገባበዝ በስርዐቱ ራሳቸዉን ገዝተዉ የሚስተናገዱትን መንቀፍና እንደረከሱ መቁጠር ግን አግባብ አይደለም::

ሲጃራንና ጫትን በተመለከተ ብዙዎች የእናንተ የሃይማኖት አባቶችና መምህራም እንደሚያስተምሩት ለሰዉነት ጎጂ የሆኑ፤ ለሥጋችን ሆነ ለነፍሳችን አንዳች ጥቅም የሌላቸዉ፤ ኅሊናን የሚያደነዝዙ፤ ሰይጣናት፣ ሰዎች በሱስ እንዲያዙ አድርገዉ ባሪያዎቻቸዉ እንዲሆኑ የሚያደርጉበት መሳሪያ ነዉ:: ባጠቃላይ እነሱና የተለያዩ አደንዛዥ ዕፅች የሰይጣናት ምሶች ስለሆኑ በኛም ዘንድ የማይፈቀዱ፣ የተከለከሉ፣ የተወገዙ፣ የሚያረክሱ ዕፆች ናቸዉ::

ቡናን በተመለከተ አብዛኛዉ የሃይማኖት አባቶችና ምዕመኑ የሚጠጡት ቢሆንም እንዳንድ አባቶች የቡናን ጉዳትና የሱስ ጠንቀኝነት ተረድተዉ እንዲሁም ባዕድ አምልኮ የሚፈጸምበት መሆኑን ተመልክተዉ «አትጠጡ» ይላሉ:: ቡናዉ እንደመጠጡ ሱሰኛ የሚያደርጋችሁ ከሆነና እሱን ካልጠጣችሁ አይናችሁ የማይከፈት ከሆነ፤ ጠዋት፣ ቀን ፣ ማታ በእሱ ኃይል የምትንቀሳቀሱ ከሆነ በተዝዋዋሪ የሱስ ባሪያ ሆናችኋልና ባትጠጡ ይመከራል:: ነገር ግን በኢትዮጵያ ባህል ለበዐሉ፣ ለጉርብትናዉ፣ ለጨዋታ፣ ባዕድ አምልኮ ስርዐት

በሌለበት ሁኔታ የምትጠጡ ከሆነ «ለምን ትጠጣላችሁ?» ብዬ ተቃዉሞ አላቀርብም:: በራሴ ግን ከዚህ በፊት ኃይለኛ ሱስ እንዲይዘኝ ስላደረገና ከጥቅሙ ጉዳቱ ስላየለብኝ እኔ አልጠጣም::

አስረኛዉ ጥያቄያችሁ የሆነዉ የራሳችሁ ስብዕና በተመለከተ « አንዳንድ የሃይማኖት አባቶችና መምህራን እኛ ከወንዶች ያነስን፣ በአደባባይ መዉጣት እንደሌለብን፣ እንደወንዱ በነጻነት መንቀሳቀስና ኃላፊነት ቦታ ላይ መቀመጥ እንደሌለብን፣ ለመሪነትና ለአስተዳዳሪነት ብቃት የሌለን አድርገዉ ያስተምራሉ:: በዚህ በኩል ያሉትን አስተያየት ቢሰጡን?» በማለት ለጠየቃችሁት ጥያቄ ምላሼ የሚከተለዉ ነዉ::

እናቶቼና እህቶቼ እናንተ በኃላፊነት ማስተዳደር ካልቻላችሁ፤ ታዲያ የትኛዉ ሰዉ ነዉ ኃላፊነት ሊሸከምና ሊያስተዳድር የሚችለዉ!? የትኛዉ ወንድ ነዉ ከማህፀን ጀምሮ ፅንሱ የተለያየ ድካምና ጠባይ ሲያመጣ ተቋቁሞና ታግሶ ዘጠኝ ወር ሙሉ ኃላፊነቱን ወስዶ ድርሻዉን የሚወጣ? የትኛዉ ወንድ ነዉ የጭንቋን ሰዐት ተጨንቆ አምጦ የሚወልደዉ? የትኛዉ ወንድ ነዉ ጡቱን አጥብቶ ሽንቱንና ቅዘኑን ሳይጸየፍ አጥቦ፣ ተንከባክቦ፣ መግቦ የሚያሳድግ? የትኛዉ ወንድ ነዉ«ልጄ ተራበ ተጠማ ተጎዳ ተጎሳቆለ?» ብሎ በስስትና በርኅራኄ ልጁን የሚንከባከብና ለቁም ነገር የሚያበቃ? የትኛዉ ወንድ ነዉ ስለልጆቹ ራሱን ጎድቶ «ልጄ ይብላ፤ ይመቸዉ::» ብሎ ስለልጆቹ ሁሉን ችሎና ታግሶ የሚኖር? የትኛዉ ወንድ ነዉ ልጁን በፍቅርና በርኅራኄ፣ በስርዐት ተንከባክቦ፣ ወቶ፣ ወርዶ ለወግ ለማእረግ የሚያደርስ? እንግዲህ እናንተ ለኃላፊነት፣ ለአሰተዳዳሪነት፣ ለመሪነት አትበቁም ከተባለ በዓለም ዉስጥ ለኃላፊነት ሆነ ለመሪነት የሚበቃ ሰዉ የለም ማለት ነዉ::

ሴቶች ሆናችሁ ወንዶች ያለን ልዩነት በሕያዉ ነፍሳችን ባሕርይ ሳይሆን፤ በተገለጽንበት ሥጋ ነዉ:: ይኸዉም ወንድና ሴት ጾታ ብቻ ነዉ እንጂ ነፍሳችን የጾታ ሆነ የሌላ  ልዩነት አንዳች የላትም:: ስለዚህ አንዳች የማንበላለጥ መሆኑን ልታዉቁ ይገባል:: ይልቁኑ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆናችሁ ከተገኛችሁ በቅድስና ብቃት ልትበልጡን ትችላላችሁ:: ይኸዉም በቅድስና ሕይወቷ ብቃት ደረጃ ላይ በመድረሷ ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ለመሆን የበቃችሁ ነፍስ፤ የአዳም ተስፋ፣ የደናግል መመኪያ፣ የጻድቃን እመቤት፣ የሰማዕታት አክሊል፣ የደካሞች ምርኩስ፣ የህሙማን ፈዉስ፣ የድኅነታችን ምልክት፣ የቅዱሳን ሞገስ፣ ብቻ ምሳሌ ተመስሎላት ተመስሎላት፣ ተመስግና ተመስግና የማትጠገብ እመ አምላክ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም በሴት ጾታ ነዉ በሥጋዋ የተገለጸችሁ:: ስለዚህ እናንተም ሆናችሁ እኛ ወንዶች በአደባባይ መዉጣት፣ መስራት፣ መናገር፣ መማር፣ ማስተማር፣ መጸለይ፣ ማመስገን፣ ኃላፊ፣ አስተዳዳሪ ፣ መሪ መሆን

እንችላለን:: ትልቁ ሁላችንም ጠንክረን መስራት፣ መማር፣ ስለ እዉነት መጽናት፣ መትጋት፣ እግዚአብሔርን በመፍራት መመላለስ ነዉ የሚጠበቅብን:: ከዚያ ዉጭ ለእናንተ የሚፈቀድ ለእኛ የሚከለከል መልካም ሆነ መጥፎ ነገር የለም:: በሌላ በኩል ለእኛ የሚፈቀድ ለእናንተ የሚከለከል መልካም ሆነ መጥፎ ነገር የለም:: ሁላችንም እንደ እምነተታችንና ምግባራችን ነዉ የሚፈረድልንና የሚፈረድብን:: በእግዚአብሔር ዘንድ በጾታችን ምክንያት አንዳች አድሎ አይደረግም::

ልጆቻችንንም በስርዐት፣ በትጋት፣ በንቃት፣ በብቃት የማሳደጉ ደርሻ የወንዱም የሴቱም ነዉ:: እግዚአብሔርን በመፍራት እንዲያድጉ አድርገን በስርዐት ካሳደግን በምድርም የመጀመሪያዉ ጥሩ ዋጋ ተከፋዮች እኛዉ ወላጆች ነን:: ምክንያቱም የእግዚአብሔርን ልጆች በኃላፊነት ተረክበን እንደ እዉነተኛ አባትነቱ እንዲያከብሩት እንዲያመልኩት አድርገናልና ዋጋችን ከፍ ያለ ይሆናል:: በተቃራኒዉ በስርዓት ካላሳደግን፣ ጋጠ ወጥ ካደረግናቸዉ፣ እግዚአብሔርንም ሰዉንም የማያፍሩ የማያከብሩ ከሆነ የመጀመሪያዉ ዋጋ ከፋዮች እኛ ወላጆች ነን:: ከዚያም ጥፋታቸዉ ለቤተሰብ፣ ለጎረቤት፣ ለመንደር፣ ለአገር ይተርፋል::

በዚሁ ላሳዉቃችሁ የምፈልገዉ ነገር ልጆችን አርግዛ የመዉለድ ድርሻ የሴቷ ብቻ እንጂ የወንዱ እንዳልሆነ ሁሉ በኑሮዋችንም ወንዱም የራሱ ድርሻ አለዉ:: ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌዉ በአምላክነቱ ባሕርይ ባወቀዉ ለሐዋርያነት የመረጣቸዉ አስራ ሁለቱም ደቀመዛሙርት ወንዶች ብቻ ናቸዉ:: በዚህም ምክንያት በክህነት አገልግሎት ዉስጥ የሚሳተፉት ለመቀደስና ለማቁረብ የተፈቀደላቸዉ ወንዶች ብቻ ናቸዉ:: ነገር ግን ከዚያ ዉጭ በጸሎቱ በምስጋናዉ ወንዱም ሴቱም በጋራ ያገለግላል፤ ይገለገላል:: ታዲያ አንዳንድ ዘመን አመጣሽ እህቶቻችን የዓለሙ ዐመጻ አልበቃ ብሏቸዉ በፖለቲካ ኅሊናቸዉ ተመርዞ «ለምን ቄስ፣ ጳጳስ አንሆንም?» በማለት በየአደባባዩና አዳራሹ ሲናገሩ ይታያል፤ ይደመጣል:: በእዉኑ እነዚህ ሰዎች ለእግዚአብሔር አገልግሎት ቀንተዉ ነዉን? ወይስ የሃይማኖቱን እዉነተኛ መድረክ ወደ የጨለማዉ ገዥ ፖለቲካ መድረክ ለመለወጥ ፈልገዉ ይሆን? እንኳን እግዚአብሔር ያልፈቀደዉ አይደለም ተፈቅዶለትና ብቃቱም ኖሮት «ለዚህ አገልግሎት ታጭተሃል» ቢባል እንኳ፤ « እኔ ያልተገባዉ ሰዉ ነኝ::» ብሎ በትህትና ለአገልግሎት ይሰለፋል እንጂ በትዕቢትና በዐመጻ ኅሊና እንዴት እግዚአብሔርን ማገልገል ይቻላል?! ታዲያ አንዳንዶች ለዐመጻ ስራቸዉ እንደማጣቀሻ የሚጠቀሙት የሕይወት መመሪያችን የሆነዉ መጽሐፍ ቅዱስን ለራሳቸዉ በሚመች መልኩ አድርገዉ በማቅረብ ነዉ:: ለዚህ መፍትሔዉ ኅሊናችን በእዉነትና በመንፈስ ቅዱስ ብቻ እንድትመራ ማድረግ ነዉ:: ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የሆነዉን፣ የሰዉ

ወግና ልማድ የሆነዉን፣ ከሥጋና ደም ስሜት የሆነዉን፣ የክህደቱን፣ የመናፍቅነቱን ባጠቃይ ሰንዴዉንና እንክርደዱን ያሳዉቀናል።

አስራ አንደኛ ጥያቄያችሁ የሆነዉ «በዚህ አጋጣሚ አንዳንድ መምህራን በወር አበባ ጊዜ ሴት ትረክሳለች ይላሉ። ለዚህ ያሎትና አስተያየት ቢሰጡን?» በማለት ለጠየቃችሁት ያለኝ መልስ፡ ርኩስ የሚለዉን ለወር አባባ እነሱ ሆኑ እናንተ ስተሰጡ ኅሊናዬ ይዘገንነዋል። ምክንያቱም ወር አበባ እንኳን ርኩስ ሊያስብል ቀርቶ ያደፈና የጎደፈ ባሕርያት ከሆኑት ከዐይነምድር፣ ከሽንት፣ ከላበት፣ ከንፍጥ፣ ከአክታ ዉስጥ እንኳ አልተቆጠረም። ይህ የሚያሳየን ደግሞ እነዚህ ያደፉና የጎደፉ ባሕርያት ርኩስ የማያስብሉን ከሆነ እንዴት ከነዚህ ዉስጥ ያልተካተተዉ ወር አበባ ርኩስ ያስብለናል!? እንደዚህ ብለዉ የሚያስተምሩ ማንነታቸዉን ያላወቁ የወር አበባ ጥቅሙን ያልተረዱ ሰዎች ብቻ ናቸዉ።

የወር አበባ ጥቅሙ የእግዚአብሔር ፍጥረቶችንና ልጆችን ወደዚህች ምድር በኃላፊነት ካለመኖር ወደ መኖር ለማምጣት ብቃት ያላቸዉ መሆኑን ሴቶች የሚያዉቁበት ከእርግዝናጋ የተያያዘ ልክ አፋችን ዉስጥ የገባዉን ምግብ ለማዋሃድ ምርቅ  አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ሴቶችም ልጆችን ለመዉለድ የግድ ወርአበባ መታየቱ አስፈላጊ ስለሆነ ነዉ በእድሜ ገደብ ተወስኖ በሴቶች ላይ የሚከሰተዉ እንጂ የሚያረክሳቸዉ፣ ከወንድ የሚያሳንሳቸዉ ጸያፍ ነገር አይደለም። ስለዚህ እናንተም ከደዚህ አይነቱ አስተሳሰብና አመለካከት ራሳችሁን ነጻ አድርጋችሁ ሌሎች ወገኖቻችሁን ልታስተምሩ ይገባችኋል እንጂ የምትሳቀቁበት፣ የምታፍሩበትና የምትሸማቀቁበት አይደለም። ልክ ምራቅ ሲመጣባችሁ አንዳች ነገር እንደማይሰማችሁ ሁሉ ወር አበባም ሲመጣባችሁ አንዳች ነገር ሊሰማችሁ አይገባም። ምራቃችሁን በመዋጥ ሆነ በመትፋት መቆጣጠር እንደምትችሉ ሁሉ  ወር አበባችሁ እስከሚቆምላችሁ ድረስ በተለያዩ መከላከያ ልትቆጣጠሩና እንደማንኛዉም ሰዉ ጽዳታችሁን ልትጠብቁ ይገባል።

በዚህ አጋጠሚ በእኛም ቤተክርስቲያን በብዙዎቹ ይህ አመለካከት በወንዱ ብቻ ሳይሆን በሴቱም የሚነጸባረቅ ነዉ። ለወደፊት አምልኮታቸዉን በዘልማድ ሳይሆን በእዉነትና በመንፈስ ሲያደርጉ ትክክለኛዉን አስተሳሰብ ይይዛሉ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። « ወደ ቤተክርስቲያን መቅደሱ ወዳለበት አትግቡ።» ሲባል «ርኩስ ስለሆናችሁ አትግቡ።» ለማለት ተፈልጎ ሳይሆን ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ቤት ናትና ከምንም በላይ ለቦታዉ ንጽህናችንን ጠብቀንና ክብር ሰተን እንድንገኝ ለማሰወቅ ነዉ እንጂ በቤተክርስቲያን አጸድ ዉስጥ ሆናችሁ ጸሎት ሆነ ምስጋና ለማቅረብ የሚከለክላችሁ ነገር የለም። ልክ ምራቁን መቆጣጠር የማይችል ጤናዉ የታወከ ሰዉ እስከሚሻለዉ (እስከሚቆምለት) ድረስ ስለ ንጽህና ሲባል ቤተክርስቲያን

ዉስጥ እንደማይገባና ስለ መለኮት የተዋሀደዉ ቅዱስ ቁርባን ክብር ሲባል እንደማይቀበል ሁሉ፤ ወር አበባ የሚፈሳትም ሴት ወር አበባዋ እስከሚቆምላት ድረስ ስለንጽህና ሲባል ቤተክርስቲያን ዉስጥ አትገባም፤ ስለ ቅዱስ ቁርባንም ክብር ሲባል አትቀበልም። ከዚህ ጋር በተያያዘ ለምሳሌ በቤተክርስቲያን ስርዐት መሰረት ባልና ሚስት የሚቆርቡ ከሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት እስከሚቆርቡ ለሶስት ቀንና ከቆረቡ በኋላ ለሁለት ቀን ይከለከላሉ። ይህ የሆነበት ምክንያት የግብረሥጋ ግንኙነት የሚያረክስ ወይንም ከቅድስና የሚለይ ሆኖ ሳይሆን ከቅዱስ ቁርባን በላይ የሆነ ስርዐት የለምና ለቅዱስ ቁርባን ክብር ሲባል ነዉ።

ታዲያ ይህ ስርዐት ነዉ እንጂ ትምህርተ ሃይማኖት ዶግማ አይደለም። በእዉነትና በመንፈስ ብቻ የሚመሩ እዉነተኛ አገልጋዮች( በተግባራቸዉም፣ በንግግራቸዉም፣ በአሳበቸዉ ጭምር እግዚአብሔር በቀጥታ ይመለከተኛል፣ ያዳምጠኛን ብለዉ እግዚአብሔር በመፍራት የሚመላለሱ ራሳቸዉን ክደዉ ስለእዉነት የሚመሰክሩ ፣ በሚናገሩት እዉነት ቃል ሆነዉ የሚገኙ፤ የማያስመስሉ፤ የዚህ ዓለም ስልጣን ክብር ዝና ጥቅም የናቁ ሰዎች) በመንፈስ ቅዱስ ተመርተዉ አሁን ካለዉ እዉነታ ተነስተዉ ቀኑን ቢጨምሩ ወይንም ቢቀንሱ ስርዐት ነዉና ለምን እንደዱሮዉ አይሆንም ብለን መቃወም ሆነ መተቸት አንችልም። ነገር ግን ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ «እናሻሽል፣ እናድስ» ቢሉ መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ ስላልሆነ ይኸዉም እዉነተኛ አገልጋዮች ባለመሆናቸዉ አንቀበላቸዉም፤ አንከተላቸዉም።

ለምሳሌ የክርስቶስን ሥጋና ደም ትዉልዱ «እዉነተኛ መለኮት የተዋሀደዉ አድርጎ አምኖ ለመቀበል ይከብደዋል፣ ይረቅበታልና እንደ ፕሮቴስታን አማኞች ምሳሌ ለመታሰቢያ ነዉ ብለን እናቀብል።» የሚል አገልጋይ ቢነሳ እሱ በአታላዩ(ሸዋጁ) የዲያብሎስ መንፈስ የሚመራ የሥጋና የደም ስሜቱ የገዛዉና በደመ ነፍሱ የሚመራ፣ ሥጋዊዉ አስተሳሰብ ያየለበት በመሆኑ ልንቀበለዉና ልንሰማዉ አይገባም፤ ፍጹም ክህደት ነዉና። እንኳን እዉነተኛ ዉን መለኮት የተዋሀደዉን ሥጋና ደም መካድ አይደለም ከድኅነታችን (ከመዳኛችን) ጋር ፍጹም የማትለየዉ ወላዲት አምላክ ድንግል ማርያምን ከአምልኮ ስርዐታችን፣ ከምስጋናዉ፣ ከቅዳሴዉ የሚለይ ሰዉ ካላ እሱ የሕወትን መንገድ ያላወቀ ወይንም የካደ ነዉ። ምክንያቱም እሱ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዉ ሆኖ የተገለጸዉ ከእርሷ በነሳዉ ሥጋና ደም ነዉ። ይህ የዘላለም ሕይወትን የሚሰጠን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም የመጣዉ ከሰማይ አይደለም፤ ፍጹም የአዳም ዘር ከሆነችዉ ከቅድስት ድንግል ማርያም ነዉ የተገኘዉ። ይህም አዳኛችን ቸሩ መድኃኔዓለም ቢሆንም የመዳኛችን ምክንያት የአዳም ተስፋዉ የነበረች እመቤታችን ድንግል ማርያም ናት። ከእርሷ የተለየ እምነት ሆነ ሃይማኖት ከእዉነት የራቀ ነዉ።

ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን እሷን ይዘዉ ነዉ ለሰማያዊ ክብርና ሽልማት የበቁት። አሁን ያለዉ ትዉልድ ግን እጅግ ያሳዝናል። ምክንያቱም ጻድቃን፤ ምሳሌ መስለዉላት መስለዉላት መግለጽ አቅቷቸዉ «በምን እንመስልሽ?» ብለዉ ምሳሌ አልበቃ ብሏቸዉ ነበር። እንዲሁም አመስግነዉ አመስግነዉ መጥገብ ስላልቻሉ ስንትና ስንት ዉዳሴ አቅርበዉላት አረኩም። አሁን ግን እንኳን የራሳችንን ምስጋና ማቅረብ አይደለም ጻድቃን ያዘጋጁልንን ምስጋናዋን ልንጠቀምበት አልቻልንም። ይባስ ብሎ የሚያቃልሏት፣ የሚሰድባት፣ የሚያዋርዷት፣ የሚክዳት ትዉልዶች በዚህ በተቀደሰች አስራት አገሯ ተፈጥረዋል። እሷን በመካዳቸዉ ምክንያት መንገዱ ጠፍቶባቸዉ እዉነተኛዉን አምላክ ተማላጁን ፣ ፈራጁን ክደዉ «አማለጅ የሱሴ» እያሉ እዉነተኛዉን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን እለት እለት ይሰድቡታል፤ ያዋርዱታል።

ይህ አላጋጩና ሸዋጁ የዲያብሎስ መንፈስ በኅሊናቸዉ አድሮ ከሕይወት መንገድ ማዉጣት ብቻ አይደለም እግዚአብሔርን ፣ እመቤታችን ድንግል ማርያምን ፣ ቅዱሳንን ፣ ጻድቃንን እንዲቃወሙና እንዲሰድቡ አስደርጓቸዋል። እናንተ ምንም እንኳ ባለማወቅ የአምላክ እናትነቷን ባትቀበሉም «የኢየሱስ እናት ድንግል ናት።» ብላችሁ እንደምታምኑና እንደምታከብሯት ይታወቃል። ለወደፊት የሕይወት ምስጢራት ሲገለጥላችሁ ማንነቷን በደንብ ታዉቃላችሁ። ቅንነታችሁንና የዋህነታችሁን አይታ ነዉ እዉነትን እንድታዉቁ ወደእኔ የመራቻችሁ። የሕይወታችሁ ምስጢር ቁልፍ የሆናችሁ እርሷ ድንግል ማርያም ናት። ልጇን « እነዚህ ባለማወቅ ከሕይወት መንገድ የወጡ የዋሀንና ቅኖችን ነፍሳት እንዴት ከዐመጻ ልጆች ጋር አብረህ ታጠፋቸዋለህ?» በማለት ያቀረበችዉን ምልጃዋን ሰምቶ ነዉ እዉነትን ሊያሳዉቃችሁ የወደደዉ። እናንተ ብቻ ሳትሆኑ ብዙ ባለማወቅ በተሳሳተ እምነትና ሕይወት የሚመላለሱ ቅኖችና የዋሀን አሉ። እነሱም በሂደት ወደ እዉነታዉ ይመጣሉ። ለዚህም ነዉ ነፍሳትን ከእሳትና ከጥፋት እያወጣች ወደ ሕይወት ስለምታመጣ ዲያብሎስ ከነጭፍሮቹ ሰይጣናት ጋር በመሆን ቀን ከሌሊት ትዉሉድን ከድንግል ማርያም ለመለየት የሞት ሽረት ጦርነት የሚያደርገዉ። ዲያብሎስ ትዉልዱን ከእርሷ ለየ ማለት ከአምላካቸዉ መለየቱን እርግጠኛ ነዉ የሚሆነዉ። ምክንያቱም ከእርሷ የተለየዉ ትዉልድ ነዉ አምላኩን «አማላጅ፣ፍጡር።» እያለ የሚክደዉና የሚሳደበዉ፤ እንዲሁም ቅዱሳንን እያቃለለ የሚያዋርደዉ።

እዚህ ላይ አንድ ያላወቃችሁትንና ያላስተዋላችሁትን እዉነታ እነግራችኋለሁ። ይኸዉም እመ አምላክ ድንግል ማርያም በሰማያት ከብራና ገና በፍጹም ደስታ መኖር ስትችል እርሷ ግን የመረጠችዉ ስለ አደራ ልጆቿ የአዳም ዘር ስትል ከመክበርና ከመግነን ይልቅ

ኀዘንተኛ መሆንን መርጣለች:: ምክንያቱም የአዳም ዘር ጥፋት አላስቻላትምና:: ነገር ግን ስለ እርሷና ስለቅዱሳን እንዲሁም በዚህች ምድር ስለ እዉነት ስለሚያዝኑ ሲል እግዚአብሔር በአራቱም ማዕዘን ያሉ ነፍሳት(የሰዉ ዘሮች) የሚድኑበትን ሰማያዊ ስርዐት በቅርቡ ይዘረጋል:: ለዚህ ሰማያዊ ስርዐት ኅሊናቸዉን አደንድነዉ እንቅፋት የሚሆኑትን የዐመጸ ልጆችን ደግሞ እጃቸዉን ለአምላክ ለመስጠት ፈቃደኛ አይደሉምና ከምድሪቱ በእግዚአብሔር ቁጣ ይጠረጋሉ::

ሌላዉ ማወቅ ያለባችሁ የኛ የዐመጻ፣ የክህደትና የርኩሰት ተግባር የረበሸዉና ያወከዉ የቅዱሳንና የጻድቃን ደስታን ብቻ ሳይሆን እርሱን ባለቤቱን እግዚአብሔርን ኀዘንተኛ አድርገነዋል:: ምክንያም እንኳን በተግባራችንና በንግግራችን ብቻ አይደለም በአሳብ ጭምር የምንረክሰዉና የምናምጸዉን በመላዉ ዓለም እያንዳንዱ ሰዉ የሚፈጽመዉን እየተመለከተና እየሰማ እንዳያጠፋን ሕያዉ ፍጥረቶቹና ልጆቹ ስለሆን ባሕርይዉ ይገድበዋል፤ ፍቅሩና ርኅራኄዉ እጅግ ያይልበታል:: ዝም ብሎ እንዳይምረን ደግሞ እንዲሁ ባሕርይዉ ይገድበዋል፤ ይልቁኑ ፍርዱ ጥብቅ እንዲሆን ያደርገዋል:: በዚህ ምክንያት እሱም እንደቅዱሳንና ጻድቃን ስለ እዉነት ኀዘንተኛ እንዲሆን አድርገነዋል:: ነገር ግን ከፍርድ ቀን በኋላ ግን እያንዳንዱ እንደ ስራዉና እምነቱ ስለሚፈረድለትና ስለሚፈረድበት ቅዱሳን ሆኑ ጻድቃን ፍጹም በሆነ ደስታ በመንግስቱ ሕያዉ ሆነዉ ይኖራሉ፤ ማንም ፍጡር በእዉነተኞች ላይ በደል ሆነ ግፍ፣ አድሎ መፈጸም አይችልም:: በተቃራኒዉ ደግሞ በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ በእዉነተኛ አገልጋዮችና ምእመን ላይ ግፍ፣ በደል፣ አድሎ የሚፈጽም ግፈኛና ጨካኝ ሰዉ፣ ነፍስ ከሥጋዉ እንደተለየች ስለዐመጻዉና ጭከናዉ በመቶ እጥፍ ዋጋ ይከፍልበታል:: በዚህ ምድርም የዐመጻዉና የግፍ ጽዋዉ ሲሞላ ፍዳዉን ያገኛል::

የእመቤታችን እዉነተኛ ወዳጅ ቢወድቅ ይነሳል፤ ቢደክም ያበረታል:: ተስፋ ቢቆርጥ ተስፋዉ ይለመለማል:: ቢገፋ ይነሳል:: ቢያዝን ይጽናናል:: ቢደኸይ ይበለጽጋል:: ቢሞት ሕያዉ ይሆናል:: ሌላዉ ማወቅ ያለባችሁ በመጽሐፍ ቅዱስ ዉስጥ ከዘፍጥረት ጀምሮ እስከ ዮሐንስ ራእይ ድረስ በግልጽና በምሳሌ በተለያየ መልኩ ተገልጻለች:: ከአምላክ ማዳን ተግባር ጋር ፍጽም ልተለይ የማትችል የድኅነታችን ምክንያት መሆኗን በሚገባ ልታዉቁ ይገባል:: እዚህ ላይ ታዲያ በስሟ የሚነግዱ አገልጋዮችና ምእመናን እንዳሉ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ:: እነዚህ አስመሳዮች ለእግዚአብሔር ትዕዛዝና ሕግ አንዳች ደንታ የሌላቸዉ፤ ለሆዳቸዉና ለክብራቸዉ የቆሙ፤ ስለ ነፍሳት መዳን አንዳች ስሜት የሌላቸዉ፤ ሲፈልጉ ለኃጢአታቸዉ ሽፋን እሷን የሚያደርጉ፤ ትዉልዱ ከንስሐ ከሥጋና ደሙ የሚለዩ፤ እነሱ የማይሸከሙትና የማይፈጽሙትን ሸክም በምእመን ላይ ጭነዉ ምእመኑን የሚያስጨንቁ፤ የሚያስቸግሩ

ናቸዉ። እነዚህን እግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን እመ አምላክም፣ ቅዱሳንም ስለሚያዉቋቸዉ አላጋጩ ዲያብሎስ እንዳላገጠባቸዉ ለንስሐ ሳይበቁ ከነዐመጻቸዉና ርኩሰታቸዉ በሥጋ ሞት ተጠርተዉ የባሰዉን ፍርድ የሚቀበሉ ናቸዉ። እዉነተኛ ወዳጆቿ ግን በሥጋ ድካም በኃጢአት ቢወድቁ እንኳ ለንስሐ ለሥጋና ደሙ አብቅታቸዉ ለሰማያዊ መንግስት ታጫቸዋለች።

በአሁን ሰዐት ቤተክርስቲያን በዉጭም በዉስጥም እየተፈተነች ትገኛለች። ይኸዉም አንዳንድ እንደ ሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚንቀሳቀሱ አታላዩ (ሸዋጁ) የፕሮቴስታን መንፈስ ራሱን በማሻሻልና በመሰወር ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ለቤተክርስቲያን ተቆርቋሪና አገልጋይ በመምሰል ከቤተክህነቱ ጀምሮ እስከ አጥቢያ አብያተክርስቲያናት ድረስ በተደራጀና በጥቅማ ጥቅም በተሳሰረ መንገድ የቤተክርስቲያኒቱን እምነት፣ ስርዐት፣ አስተምሮ፣ ትዉፊት ለመለወጥና ለቅርፊት ሥጋ የሚመች ስርዐትና አስተምህሮ በምእመኑ ኅሊና ለማስረጽ ሌት ተቀን የሚተጉ ተኩላዎች አሉ። የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ ደግሞ ሽፋንና ድጋፍ አድርገዉ የሚመላለሱት ዋና የሃይማኖት መሪ የተባሉትንና የእሳቸዉን ጋሻ ጃግሬ መከታ አድርገዉ ነዉ። እነዚህ ስብከቱን መናፍቅ መናፍቅ አድርገዉ ያሸተቱ፤ መዝሙሩን ዘፈንና ዳንኪራ ያደረጉ ናቸዉ። ምእመኑ የእመቤታችን ፍቅር በልቡ የታተመ ስለሆነ በቀላሉ መመንገል እንደማይችሉ በመረዳታቸዉ ከልባቸዉ ሳይሆን ለማስመሰል ስለ እርሷ እንክርዳድ በተደባለቀ መልኩ ያስተምራሉ። ሲፈልጉ ደግሞ በክብር እንዳትጠረ ልክ ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በክብርና እንደ እግዚአብሔርነቱ እንዳይጠራ ልክ እንደ ፕሮቴስታንቱ « የሱሴ ወይንም ኢየሱስ» እንዲባል እሷንም «እመ አምላክ ፣ እመቤታችን ፣ ቅድስት፣ ድንግል፣ እመ ብርሃን» ብለን በክብር እንዳንጠራት «ማርያም ብቻ» እንድንላት በየመድረኩ እያለማመዱን ነዉ።

ታዲያ ከንደነዚህ አይነቶቹ ጋር ባለማወቅ በየዋህነትና በቅንነት የሚመላለሱትን እግዚአብሔር አጥርቷቸዉ ለእዉነተኛ አገልግሎት ያሰልፋቸዋል። ነገር ግን በዓለማ የሚንቀሳቀሱትን ደግሞ ኅሊቸዉን እንደ ትዕቢት(ፈርኦንን ይመራዉ የነበረዉ የትዕቢት መንፈስ)፣ ክፋት( ይሁዳን ይመራዉ የነበረዉ የክፋትና የተንኮል መንፈስ)፣ ዐመጻ( አርዮስን ይመራዉ የነበረዉ ሸዋጁ መንፈስ) የደነደነ ወደ ንስሐ የማይቀርቡና እዉነተኛ ንስሐ የማይገቡ፤ እንኳን ፍጡሮቹ የሆኑት አገልጋዮቹን ሊሰሙ ቀርቶ አምላክ በሥጋ ተገልጾ ቢናገራቸዉ ተአምራትንና ፈዉስ ቢያደርግ የማይቀበሉት እጅግ የታበየና በዐመጽ የተሞላ ሕይወት ስለያዙ እግዚአብሔር ያበጥራቸዋል፤ ከስንዴዉ ይለያቸዋል፤ እንደእንክርዳድነታቸዉ እንደ ቆሻሻ ተቆጥረዉ ከሌሎች የዐመጻ ልጆች ጋር ይጠርጋቸዋል።

እነዚህን ብቻ አይደለም እዉቀታቸዉን አምልከዉና አስመልከዉ ያሉ፤ «ከእግዚአብሔር የሆነዉን ሙሉ እዉነታ አንቀበልም፣ ከእኛ እዉቀትና አስተሳሰብ ዉጭ ያለዉን አንቀበልም፣ አንመራበትም» ብለዉ እግዚአብሔርን በራሳቸዉ እዉቀትና በጠባብ አእምሮዋቸዉ የሚወስኑትን፣ የሚቃወሙትን፣ የጸሐፎችና የፈሪሳዉያን እንዲሁም የአይሁድ ካህናት አለቆች ሕይወት የያዙትን ደንዳና አገልጋዮችንም የሚጠራ ልብ ያላቸዉን ያጠራቸዋል፤ ለእዉነተኛ ምሉእ አገልግሎት ያበቃቸዋል። እብሪተኞቹንና ዐመጸኞቹን ደግሞ ያበጥራቸዋል፤ ከስንዴዉ ይለያቸዋል፤ ይጠርጋቸዋል።

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩላችሁ ስርዐት ለማሻሻል የሚችለዉ እዉነተኛ የእግዚአብሔ እንደራሴዎችና አገልጋዮች ብቻ ናቸዉ እንጂ እንደ እኔ አይነቱ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሆና የማይገኝ፤ ኅሊናዉን የሚያገለባብጥና የሚሸጥ፤ ለሥጋ ፈቃዱ የሚያደላ፤ ቢሆንለት ሰባቱ አጿማት ተሽረዉለት ዓመቱን ሙሉ የፈለገዉን ለመብላት የሚመኝ፤ በዳንኪራዉና በዘፈኑ ሌት ተቀን ኅሊናዉ ስላበደ ደስ ብሎት እንዲሰማዉና እንዲዝናናበት ሲያስፈልገዉም እንዲጨፍርበት ልክ እንደ ፕሮቴስታንቱ የእግዚአብሔርን ቃል መጫወቻና ማላገጫ እንዳደረጉት ዘፈን መሰል መዝሙር በኦርጋን፣ በጊታር፣ በሳክስፎን፣ በጃስ ታጅቦ እንዲቀርብለት የሚፈልግ፤ እንዲሁም ስብከቱን ሆነ መዝሙሩን እንደ ንግድ ስራ ቆጥሮ የቤተክርስቲያኒቱን እምነት፣ ስርዐት፣ አስተምህሮ፣ ትዉፊት ባልጠበቀ መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል መሸቀጫ የሚያደርግ፤ በአናቱ ላይ ለጥቅሙና ለስልጣኑ ብቻ ሲል ቆብ ደፍቶ ስዉር ዐመጻዉንና ርኩሰቱን ለመፈጸም ደግሞ ሽጉጥ ታጥቆ የሚሄድ፤ በዘመድ አዝማድ፣ በጎጥ ተቧድኖ በእግዚአብሔር ቤት ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የሚፈጽም፤ ከዐመጻ ልጆች ጋር አንድነትና ህብረት ፈጥሮ ምዕመኑን የሚያሳምጽ፤ ስለ እዉነት ራሱን ክዶ መመስከር የማይችል፤ ለስልጣኑ፣ ለክብሩ፣ ለጥቅሙ፣ ለዝናዉ ያደረ፤ ሆዱ ከሞላ፣ ክብሩ ከተጠበቀ በቤተክርሰቲያን ላይ ደባ ሲፈጸም ዝም የሚል፤ ተስፋዉን ምድራዊ አድርጎ የሚመላለስ፤

ባዶ ቀፎ የሆነ፤ ከጸጋ እግዚአብሔር የራቀ፤ የእግዚአብሔር ቃል አሳምሮ ብቻ የሚናገርና ለራሱ ሥጋዊ ፈቃድ የሚያዉል፣ እንደቃሉ ሆና የማይገኝ፤ ምእመኑ በዘልማድ እንዲመላለሱ የሚያደርግ፤ እዚህ መታችሁ ስላጨበጨባችሁና እልል ስላላችሁ ብቻ መንግስተ ሰማያት ትወርሳላችሁ እያለ ምእመኑን ከንስሐና ከቅዱስ ቁርባን የሚለይ፤ በባዶ ሕይወት በትዕቢትና በእብሪት የሚያስተምር፤ እንደ ቦይ ዉሀ ወደ ወሰዱት አቅጣጫ

የሚሄድና የዲያብሎስን ስርዐት ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ምእመኑንም ለማሳመጽ ሌት ተቀን የሚተጋ፤ የካድሬነት ተግባር የሚፈጽም፤ የዐመጻን ስራ የማያወግዝ፤ ራሱ የማይሸከመዉን ሸክምና የማይፈጽመዉን ትብታብ በሰዎች ጫንቃ ላይ የሚጭንና የሚተበትብ፤ የወንጌል እንቅፋት የሆነ፣ ባጠቃላይ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸምና ለማስፈጸም አንዳች ብቃቱ የሌለዉ እንደእኔ አይነቱ  አገልጋይ ሆነ ምእመን እንኳን ስርዐት ሊያሻሽል ቀርቶ ከሚያገለግልበት ወንበር ሊነሳና ራሱን በእዉነተኛ ንስሐ አጥቦ ከእዉነት ጋር ሊሰለፍ እንዲሁም በእዉነትና በመንፈስ ብቻ አምልኮቱን ሊፈጽምና ሊመላለስ ይገባዋል፡፡

እዚህ ላይ አንዳንዴ ከጥያቄያችሁ ወጣ እያልኩ የምናገራችሁ ከሥጋና ደም አሳቤ ሳይሆን እኔም ሳለስበዉ መንፈስ ቅዱስ እንድናገር እያደረገ ነዉ እንጂ ለጥያቄያችሁ በቀጥታ ቃል በቃል እግዚአብሔር የሚያናግረኝን እመልስላችሁ ነበር፡፡ ነገር ግን ግድ ይገለጽ ዘንድ ያስፈልጋልና ከጥያቄዎችሁ መልስ ዉስጥ የሚገቡትን እዉነታዎች እንድታዉቁና ልብ እንድትሉት ለወደፊት ሸዋጁ መንፈስ በኀሊናቸዉ የሚፈነጭባቸዉ «አገልጋይ ነን፣ ሰባኪ ነን ፣ ዘማሪ ነን፤ » በሚሉ ሰዎች እንዳትበከሉና እንዳትመረዙ ፈልጎ ነዉ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያለዉን እዉነታ እንድታቁ ያደረገዉና የሚያደርገዉ፡፡

ወደ ቀደመ ነገሬ ልመለስና አንዳንድ ምዕመናን ሆኑ አገልጋዮች በሽተኛን ሰዉ እንዲሁም የተለያየ ቁስል ያለበትን ሰዉ ጠበሉን እንዲጠጣ ሲያደርጉ ወር አበባ የታያትን ሴት እንደርኩስ ቆጥረዉ ብትታመም እንኳ እንድትጠጣ አይፈቅዱላትም፡፡ ይህም የሚያሳያዉ የቀድሞዎች ጸሐፍት ፈሪሳዉያን አይሁድ ካህናት ርኩሰቱንና ርኩሰት ያልሆነዉን መለየት የተሳናቸዉ፤ ወጋቸዉንና ልማዳቸዉን እንደ እግዚአብሔር ሕግ የሚቆጥሩ ሰዎችን ሕይወት የተላበስን መሆኑን ነዉ የሚያሳያን፡፡ በዚህ አጋጣሚ ከንጽህና ጋር የታዘብኩትን ልንገራችሁ፡፡ እናንተ ወደ መስገጃ ቦታ ስትገቡ የእግራቸሁን ንጽህና ሳይቀር ጠብቃችሁ በፍርሐት ስትገቡ፤ በእኛ ቤተክርስቲያን ግን ብዙዎቻችን በዘልማድ ስለማምንመላለስ፤ እንኳን ንጽህናችንን ጠብቀን ወደ ቤተክርስቲያን ዉስጥ ልንገባ ቀርቶ በዋልንበትና በከረመምንበት ካልሲ ከነሽታዉ ስንገባ አንዳች ሐፍረት አይሰማንም፡፡ ነገር ግን አንድ ሰርግ መርሐግብር ላይ ብንጠራ ሰዉነታችንንም ታጥበን ያማረዉን ልብስ ለብሰን ነዉ የምንገኘዉ፡፡

በዚሁ አንዳንድ አገልጋዮች ራሳቸዉ የማይፈጽሙትንና የማያደርጉትን የዋሁ ምእመናን ላይ ጭነዉ ባልና ሚስትን የሚያጣሉ፣ ልዩነት የሚፈጥሩበትን ትምህርት ልንገራችሁ፡፡ ይኸዉም ምእመኑ የዋህ ቅን ስለሆነ አንድ መምህር ሆነ ካህን የሚለዉን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ስለሚነሳ፤ አንድ ቀን አንዱ መምህር በጾም ወቅት የግበረ ሥጋ

ግንኙነት አታድርጉ በማለት ያስተማረዉን ትምህርት አንድ እህት ይዛ ከባለቤቷ ጋር መጣላት ደረጃ ላይ ደርሳ ነበር። ይሁንና አንድ እዉነተኛ የነፍስ እረኛ አግኝተዉ ስለ ጾም ሆነ ስለ ግብረ ሥጋ ግንኙነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት በመስጠት ሊያስታርቋቸዉ ችለዋል።

የጾም ስርዐት በአዋጅ የተደነገገ ሲሆን ማንም ሰዉ በራሱ ስልጣን ሊያሻሽለዉ፣ ሊቀንሰዉ፣ ሊጨምርበት አይችልም። ነገር ግን እያንዳንዱ ሰዉ በሥርዓቱ መሰረት ከጾመ ከእግዚአብሔር ጸጋ የሚያገኝበትና ለእዉነተኛ ሕይወት የሚበቃበት ነዉ። ስንፍና ካድረገ ደግሞ የሚፈልገዉን ጸጋ የማያገኝበት ለሰይጣን ፈተና የሚጋለጥበት ነዉ። ሰዉ በራሱ ፈቃድ የአዋጅ ጾምን ብቻ አይደለም የግሉን ጾም ቢጾም የበለጠ ጸጋ ያገኝበታል እንጂ «ለምን ከአዋጅ ጾም ዉጭ ጾምክ» የሚለዉ ሰዉ የለም። ከዓመት ዓመት በቆሎና በሽንብራ ሊኖር ይችላል። በጾም ወቅት ባልና ሚስት ሁለቱም ፈቃደኛ ሆነዉ ከግብረ ሥጋ ተከልክለዉ እዉነተኛ ጾም ከጾሙ የበለጠዉን ጸጋ ያገኛሉ። ነገር ግን አንዳቸዉ እንኳ ስሜታቸዉን መቆጣጠር ካልቻሉና የሚፈተኑ ከሆነ ግንኙነት ቢያደርጉ ኃጢአትነት የለዉም። ታዲያ «ያ ግብረ ሥጋ ግንኙነት» አታድርጉ ብሎ የሚያስተምረዉ «መምህር ነኝ» ባዩ፤ እንኳን በሰባቱ አጿሚት ከግንኙነት ሊከለከል ቀርቶ ትልቁ የጌታችን ጾም በሆነዉ ዐብይ ጾምና ከህጻን እስከአዋቂ ድረስ ሱባኤ የሚገቡበትና መሬት ላይ ወርዶዉ በሚተኙበት በእመቤታችን ፍልሰታ ጾም እንድሁም ሁሉም አምልኮቱን ለመፈጸም ወደ ቤተተክርስቲያን በሚሄድበት በእለት ሰንበት እሁድና በዐበይት በዐላት እንኳ ግንኙነት ይፈጽማል። ይህ የሚያሳየዉ ታዲያ አስመሳይ የአፍ አገልጋይ መሆኑን እንጂ እዉነተኛ አገልጋይና እረኛ አይደለም። አንዳንድ አገልጋዮች ቢያንስ አርአያና ምሳሌ ለመሆን ግድ መፈጸም ያለባቸዉን እንኳ ሳይፈጽሙ እነሱ የማይፈጽሙትንና ሊያደርጉት ፈቃደኛ ያልሆኑትን፣ ሰዎች እንዲያደርጉትና እንዲፈጽሙት ያደርጋሉ፤ ያስገድዳሉ።» በማለት ከአራቱም ማእዘን ለተሰባሰቡት ለእስልምና እምነት ተከታይ ሴቶች ከተናገሩ በኋላ፡

በመጨረሻ እኛ አባት « የእግዚአብሔር ፍጥረቶችና ልጆች፤ በመቶና በሺዎች ኪሎሜትር አቋርጣችሁ መምጣታችሁ ነፍሳችሁ እዉነትን የተራበችና የምትፈልግ መሆኑን ይገልጻል። ስለዚህ ከሥጋና ከደም ስሜት ርቃችሁ ሙሉ እዉነትን ለማግኘት ፈቃደኛ ከሆናችሁ ያልጠየቃችሁትንም ሙሉ እዉነታ ልንገራችሁ?» በማለት የጠየቁ ሲሆን፤ የሴቶቹም ተወካዮች በአንድ ላይ «እኛ ገንዘባችንን፣ ጊዜያችንን ሰዉተን ከአራቱም ማዕዘን የመጣነዉ ሙሉ እዉነትን ይዘን ለመሄድ ነዉና ሊነግሩን የሚፈልጉትን ሁሉ ቢነግሩን እኛ ደስተኞች ነን።» በማለት መልሰዉላቸዋል።

እኛም አባት « ራሳችሁን ከሥጋና ከደም ስሜት አርቃችሁ በእዉነተኛ ነፍሳችሁ ባሕርይ ልትሰሙኝ ፈቃደኛ ከሆናችሁ ያለዉን እዉነታ እነግራችኋለሁ:: ሥጋና ደም ስሜት ማለት ለምሳሌ እናንተ እኛ «አምላክ እግዚአብሔር» ብለን የምናመልከዉን ኢየሱስ ክርስቶስን « ነብይ ነዉ ፍጡር ነዉ:: እንደ ነብያችን መሀመድ ነብይ ነዉ::»ብላችሁ ስትናገሩ ምንም እንኳን ባለማወቅ እየሰደባችሁትና እያዋረዳችሁት መሆኑ ቢታወቅም፤ «ለምን እንዲህ ትላላችሁ?» ብዬ አልተቃወምኳችሁም:: ነገር ግን የነብያት አምላክ እግዚአብሔር መሆኑን ነዉ የመሰክርኩት:: እንዲሁም እናንተ « ነብያችን መሀመድ» ስትሉ « እሱ ነብይ አይደለም ሐሰተኛ ነዉና ነብይ አትበሉት» አላልኩም:: ነገር ግን በኛ ኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት እንደ ነብይ የማይቆጠርና የእርሱን ትምህርት የማንቀበል የተሳሳተ የክህደት እምነት ነዉ ብዬ ነዉ የመሰከርኩት:: እናንተም « እንዴት ፍጡሩንና ነብይ የሆነዉን ኢሳን (ኢየሱስ ክርስቶስን) እግዚአብሔር ነዉ አምላክ ነዉ ትላላችሁ» በማለት አልተቃወማችሁም:: እኔም በትዕግስት እናንተም በትዕግስት ነዉ የተደማመጥነዉ:: በዚህም ምክንያት እዉነት አንድ ብቻ ስለሆነ ወደ አንድ ሙሉ እዉነት እንመጣለን ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ::

እናንተ «ነብይ ነዉ» የምትሉት መሀመድ አሁን ካለበት ቦታ ወደዚህች ምድር ዳግም የመምጣት እድል ቢሰጠዉ ከማንም በላይ « እኔ ነብይ ነዉ እንጂ አምላክ አይደለም» ብዬ ያስካድኩት ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ ራሱ ነዉ አላህ(እግዚአብሔር)» በማለት ይመሰክር ነበር:: ይሁንና ከሥጋ ሞት በኋላ በዐመጽና በክህደት እንዲሁም በርኩሰት ሕይወት የተመላለሰች ነፍስ በረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ስለምትገለጽ እንደምኞቷና ፍላጎታ አንዳች የሚሆንላት ነገር የለም:: ይልቁኑ ነጻነቷ ተገድቦ ባለችበት ቦታ እንደ ምድራዊ ዐመጻ ደረጃ ትቀጣለች፤ ፍዳዋን ትቀበላላች:: በነጻነት ማምለክ ሆነ እዉነትን መፈለግ፣ ምርጫን ማስተካከል፣ ንስሐ መግባት፣ መጸጸት፣ ስለእዉነት መመስከር፣ በእዉነት መኖር የሚቻለዉ በነጻ ኅሊናችን ተመርተን የፈለግነዉን መስራት አለመስራት፣ መናገር አለመናገር፣ ማሰብ አለማሰብ በምንችልባት በዚህች ምድር ዉስጥ ብቻ ነዉ::

ነፍስ ከሥጋ ስትለይ ምንም አማራጭ ስለሌላት ብትጸጸትም ዋጋ የለዉም:: ይልቁኑ ገና ከሥጋዋ በሞት ስትለይ በምድር ዉስጥ እያለች የሰራችዉን የኃጢአት ተግባር፣ ንግግር፣ አሳብ ጭምር ትዝ እያላት እስከፍርድ ቀን ድረስ በሲዖል ትጨነቃላች፤ ትሰጋለች:: ልክ አንድ ወንጀል ሰርተን ታወቀብን አልታወቀብን እያል እንደምንጨነቅ በዚያም እጅግ በባሰ ሁኔታ ነፍሳችን ትጨነቃለች:: « ምን ይሆን የመጨረሻዉ ፍርድ?» እያች ታወጣለች ታወርዳለች:: «ምንስ ሌላ አማራጭ አለኝ?» እያለች ትብገነገናለች፤ ትቆጫለች:: በዚህ ምድር ቢሆን ኖሮ የንስሐ እድል ስላላት በኃጢአቷ ተጸጽታ በእንባ ታጥባ መረጋጋትና እረፍትን ታገኝ ነበር::

በዚያ ግን ዳግም የንስሐ እድል የለም፡፡ መጽናናትና መረጋጋት የለም፡፡ በዚያ ሁል ጊዜ መጨነቅና መሰቃየት ነዉ ያለዉ፡፡

እንኳን መሀመድ አይደለም በኛ ሥጋዊ አመለካከት «ታላላቅ ሰዎች» የሚባሉት የአገራት መሪዎች ፣ ባለስልጣኖች፣ ፈላሳፎች፣ ሳይንቲስቶች፣ ዘፋኞች፣ ዳንኪርተኞች .. ወዘተ የመሳሰሉት ሰዎች ካሉበት ቦታ ወደዚህች ምድር የመመለስ እድል ቢያጋጥማቸዉ ከማንም በላይ በሕይወታቸዉ ዘመን ሁሉ በእዉነት እየኖሩ ስለ እዉነት ይመሰክሩ ነበር፡፡ ከተድላና ከድሎት ኑሮ ይልቅ ዘመናቸዉን ሁሉ በችግርን፣ በመከራ፣ በኀዘን አልፈዉ የእግዚአብሔርን መንግስት መዉረስን ይመርጡ ነበር፡፡ ራሳቸዉን በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ልጆች ፊት ዝቅ አድርገዉ በቅንነትና በእዉነት ያገለግሉ ነበር፡፡ አምልኮታቸዉንም በእዉነትና በመንፈስ ያደርጉ ነበር፡፡ ምን ያደርጋል ታዲያ! ነፍስ ከሥጋ ከተለየች በኋላ ዳግም ሌላ እድል አይሰጣትም፡፡ ስለዚህ እኔም ሆንኩ እናንተ በእዉነት መመላለስና መኖር የምንችለዉ እንዲሁም እዉነትን መምረጥና መከተል የምንችለዉ በዚህች ምድር ዉስጥ በእምነት እግዚአብሔር እንዳለ አምነን፣ ጽድቅና ኩነኔ እንደሚጠብቀን ተገንዝበን፣ በነጻ ኅሊናችን አመዛዝነንና አገናዝበን ነዉ፡፡ አሁን እናንተ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን አቋርጣችሁ የመጣችሁት በዚህ ነጻነታችሁ ተጠቅማችሁ እዉነትን ለማግኘት ስለሆነ፤ ከእንግዲህ በእዉነት ብቻ እንደምትመሩና የሚመጣባችሁንም ማንኛዉንም ፈተናና መከራ በጽናት፣ በትዕግስት፣ በአኮቴት እንደምትቀበሉ፣ በመጨረሻም ወደ እዉነተኛዉ አምላካችሁ እቅፍና አባታችሁና አምላካችሁ ወዳዘጋጀላችሁ ወደ እዉነተኛዉ የቅድስናና የደስታ ቦታ እንደምትሄዱ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ምናልባት ይህን ለማድረግ ከከበዳችሁ አንድ እዉነት ልንገራችሁ፡፡ በዚህች ምድር ዉስጥ የፈለጋችሁት ነገር ተሟልቶላችሁ በምቾት በድሎት ኑሮ ብትኖሩ እዉነተኛዉን ደስታ አይደለም እዉነተኛዉን እርካታ አታገኙም፡፡ ምክንያቱን እዉነተኛዉ እርካታ የሚገኘዉ በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት፣ በመልካም ተግባር ከተመላለስን ብቻ ነዉ፡፡ እዉነተኛ ደስታ የሚገኘዉ ደግሞ በእግዚአብሔር መንግስት የሰይጣናት ፈተና በሌለባቸዉ ቦታዎች በገነት፣ በሰማያት፣ እንዲሁም በአማናዉ ሕዋ ዉስጥ ነዉ፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ስለ አማናዊ ሕዋ ልንገራችሁ፡፡

አማናዊ ሕዋ የሚባለዉ ቦታ ፍጥረታት ከመፈጠራቸዉ በፊት ማለት ሰማያትና በዉስጧ ያሉ ፍጥረቶች በሙሉ እንዲሁም ዓለምና በዉስጧ ያሉ ፍጥረቶች በሙሉ ከመፈጠራቸዉ በፊት የነበረ አሁንም ያለ ለወደፊትም የሚኖር እግዚአብሔር በአማናዊ

ባሕርይዉ የሚኖርበት መጀመሪያና መጨረሻ የሌለዉ ቦታ ነዉ፡፡ በአሁን ሰዐት በዚህ አማናዊ ሕዋ ዉስጥ ቀድሞ ያልነበሩ ፍጥረቶች የሆኑት ሰማያት፣ ዓለም፣ በዓለም ዉስጥ ደግሞ ገነትና አሁን የምንኖርባት ምደር ትገኛለች፡፡ ከዓለም ጎን ደግሞ ሲዖል፣ ከሲዖል በላይ ደግሞ ማረፊያ ቦታ ያሉ ሲሆን፤ በፍርድ ቀን ዓለም፣ ሲዖል፣ ማረፊያ ቦታ ወደ አለመኖር አልፊዉ በአማናዊ ሕዋ የሚተኩ ሲሆን በዚያን ጊዜ ደግሞ እሳቱ የማይጠፋ ትሉ የማይሞት ተደርጎ በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ገሃነመ እሳት ይዘጋጃል፡፡

ምሳሌያዊ ሕዋ የሚባለዉ ደግሞ ይህ በዐይናችን ስንመለከት ምን እንደሆነ የማናየዉ ክፍት ቦታ ሁሉ ነዉ፡፡ ምሳሌያዉ ሕዋ በዚህች ዓለም፣ በሲዖል፣ በማረፊያ ቦታ የሚገኝ ሲሆን፤ በሰማያት ግን ብርሃናዊ ሕዋ ነዉ ያለዉ፡፡ ይህም እግዚአብሔር በብርሃናዊ ባሕርይዉ ተገልጾ የሚመለክበት ቦታ ስለሆነ ነዉ፡፡ ለበለጠ ማብራሪያ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ!» በሚል አርስት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት  በመስከረም ወር በ፳፻ወ፫(2003) ዓ.ም. የተጻፈዉን መጻሐፍ ማንበብና በፊት ለፊት ሽፋን ላይ በስዕላዊ መግላጫ ቦታዎቹ ስለተገለጹ መመልከት ትችላላችሁ፡፡

በዚህች ምድር በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት እየተመላለሱ «ደስተኛ ነኝ፤» የሚል ሰዉ ካለ እሱ ራሱን እያታለለ ያለ ሐሰተኛ ሰዉ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር ጸጋ በራቅን ቁጥር የሰይጣናት መንፈስ በኅሊናችንና በአካላችን ስለሚሰለጥን እርካታን ያጣን፤ ሰላም የሌለን፤ ተቅበዝባዥ ነዉ የምንሆነዉ፡፡ ሌላዉ በዚህች ምድር ትልቁም ትንሹም፣ የተማረዉም ያልተማረዉም፣ አማኙም ከሃዲዉም፣ እዉነተኛዉም ሐሰተኛዉም፣ ሀብታሙም ደሀዉም፣ መሪዉም ተመሪዉም፣ አለቃዉም ተከታዩም፣  ቀዩም ጥቁሩም፣ ነጩም ጠይሙም፣ ረጅሙም አጭሩም፣ መልከ ቀናዉም መልከ ጥፉም፣ ባጠቃላይ የአዳም ዘር ሁሉ በአዳምና ሔዋን ኃጢአት ምክንያት ባደፈ፣ በጎደፈ፣ በጎሰቆለ ባሕርያት ዉስጥ ነዉ የሚመላለሰዉ፡፡ እንዲሁም በጉስቁልና ኑሮና ሕይወት ዉስጥ ነዉ የሚወጣዉ፣ የሚወርደዉ፡፡ ከዚህ ዉጭ ሰዎች የሚለያዩት በሚታየዉ ኮልኮሌ ቁሳቁስ ነዉ ሀብታም ደሀ ተብሎ በልዩነት ሕይወት ዉስጥ የሚኖረዉ እንጂ ከላይ ከተገጹት ሕይወት ዉጭ የሚኖር ሰዉ የለም፡፡

ታዲያ ምን የሞላልን ሰዎች ብንሆን እንኳ የምድራዊዉ ሕይወት «ሕይወት ነዉ» ብለን አንድ ቀን በዚህ ምድር መኖርን አያስመኝም፡፡ ነገር ግን በነጻ ኅሊናችን ተመርተን በምንፈጽመዉ ተግባር እንመዘን ዘንድ በምድር ዉስጥ መቆየት ግድ ነዉና ለመጥራትና ለመንጠር እንዲሁም በአዳምና ሔዋን ዐመጻ ምክንያት ልንቀጣ እርሱ እስከፈቀደዉ ቀን ድረስ

በዚህች ምድር እንቆያለን:: ስለዚህ ከእኛ ከአዳም ዘሮች የሚጠበቀዉ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ በቅንነት ፣ በእዉነት ፣ በመልካም ተግባር መመላለስ ብቻ ነዉ:: ፈጣሪ አምላካችንን በእዉነትና በመንፈስ ስናመልከዉ ያኔ ምድራዊ ኑሮዋችንን በሰማያዊ ሕይወት ስለምንመራ ይህች ምድርን የእግዚአብሔር መንግስት ምሳሌ አድርገን ልንኖርባት እንችላለን:: በሥጋ ሞት ስንጠራ ይህንኑ የተቀደሰ ሕይወት እንደያዝን በቀጥታ ወደ እዉነተኛ መኖሪያ ቦታችን እንሄዳለን:: ከዚያ ዉጭ ነፍሳችን እዚህ ምደር ዉስጥ ከአምላኳ ጋር ሳትታረቅና አንድነትና ህብረት ሳትፈጥር በክፋት፣ በተንኮል፣ በትዕቢት፣ በክህደት፣ በርኩሰት፣ ባጠቃላይ በኃጢአት ሕይወት ብትኖር፤ እንደ ምድራዊ ዐመጻ ሕይወቷ የባሰ ስቃይና መከራ፣ ጭንቀት ወዳለበት ድቅድቅ ጨለማ ቦታ ሲያል በኋላም ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ነዉ የምተገባዉ::

ስለዚህ ያለዉ እዉነታ ይህን ይመስላልና ለወደፊት ከምንኖረዉ ዘመን አንጻር ምድራዊ ዘመናችን የዐይን ቅጽበት እድሜ እንኳ ያህል ስላልሆነ በምድር ዉስጥ ያለዉን ጉስቁልና ባሕርይና ኑሮ በትእግስትና በጽናት እያለፋችሁ ከእንግዲህ በኋላ ስለ እዉነት ራሳችሁን መካድና በእዉነት መኖር ይጠበቅባችኋል:: ወደመጣችሁበት ቦታ ስትመለሱ በተረጋጋና በጸና ስሜት ቀስ ብላችሁ ወደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ካህናት ዘንድ ቀርባችሁ ያለዉን ሁኔታ አስረድታችሁ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ( በሥላሴ) ስም ተጠምቃችሁ ከእግዚአብሔር በመንፈስ ልትወለዱና እዉነተኛ ልጆቹ ልትሆኑ፣ እንዲሁም በቅዱስ ሥጋዉና በክቡር ደሙ ልትታተሙ ይገባችኋል:: እስከዛዉ ድረስ ግን በልቦናችሁ ጌታችን መድኃኒታን ኢየሱስ ክርስቶስን « ፈጣሪያችን አግዚአብሔር ሆይ! እሰከ ዛሬ ባለማወቅ አምላክነትህን ክደን ከአንተ በላይ ሌላ የማይታወቅ ፈጣሪ «አላህ» ብለን ሰይመን ክደንህ ነበር አሁን ግን ነብይና ፍጡር አለመሆንክህንና ፍጥረታትን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣህ፣ ሁሉ በአንተ ለአንተ የሆነ መሆኑን ተረድተናል:: ስላለፈዉ ባለማወቅ ስለካድንህ ይቅር በለን:: ከዚህች ቅጽበት ጊዜ ጀምሮ ነፍሳችንን ለአንተ አስረክበናል ከእንግዲህ በኋላም እንዳንተፈቃድ ብቻ ለመመላለስ ወስነናልና የቸርነትህን ስራ ስራልን::» በማለት ልትጸልዩ ይገባል::» በማለት የመጨረሻ ምክራቸዉን ለግሰዋቸዋል::

ሴቶቹ ግን « ፈቃዶት ከሆነ አንድ የመጨረሻ ጥያቄ እንጠይቆት! ይኸዉም እግዚአብሔር ለእዉነተኛ አገልጋዮቹና ወዳጆቹ የሚደብቀዉ ምስጢር የለምና በአሁን ሰዐት በአገርና በዓለም ዉስጥ የተለያዩ እምነት ድርጅቶችና ግለሰቦች «ዓለም በዚህ ቀን ፣ በዚህ ወር፣ በዚህ ዓመት ታልፋለች::» እያሉ ለሕዝቡና ለአማኞቻቸዉ ይናገራሉ:: እና የዓለም እልፈት መቼ እንደሚሆን በዚሁ ቢነግሩን?» በማለት የመጨረሻ ጥያቄያቸዉን ያቀረቡ ሲሆን፤ እኛም አባት የሚከተለዉን ምላሽ ሰተዋቸዋል::

« እናቶቼ፣ እህቶቼና ልጆቼ በመጀመሪያ ደረጃ የእግዚአብሔር አገልጋይና ወዳጅ እኔ ብቻ ሳልሆን እናንተም ሌሎቹም እዉነትን የሚፈልጉና በእዉነት የሚኖሩ ሁሉ ናቸዉ:: ልዩነታችን የአገልግሎት የስራ ድርሻችን ብቻ ነዉ እንጂ፤ የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጆች የሆኑትን በአግባቡ በስርዐት ማሰደግና ለቁም ነገር ማብቃት ራሱ ታላቅ ስራና አገልግሎት ነዉ:: ከሁሉም በላይ የኃያሉ የገናናዉ የርኅሩኅ አምላክ እናንተም እኔም ሌላዉም ልጆቹ ነን:: ዋናዉ እንደልጅነታችን ሆነን ተገኝተናል? ወይስ ልጆች ሳለን «ልጅነትን አንፈልግም ብለን በዐመጻና በክህደት ሕይወት ተሰልፈና ወይ?» የሚለዉ ነዉ ልዩነት ሊፈጥር የሚችለዉ እንጂ፤ የአዳም ዘር ሁሉ እኩል የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጆች ናቸዉ:: እንኳን የእግዚአብሔር ልጅ መሆን አይደለም የንጉሥ፣ የፕሬዘዳንት፣ የጠቅላይ ሚኒስትር፣ የሚኒስትር፣ የአስተዳዳሪ ፣ የሀብታም፣ የታዋቂ የመድረክ ሰዉ፣ ልጆች መሆንን የተለየ ስሜት በሰዎች ላይ ይፈጥር የለም ወይ? ታዲያ እነዚህ መጨረሻቸዉ ምን እንደሚሆን የማይታወቅ የፍጡር ልጆች መባል ያዚህን ያህል የተለየ ስሜት የሚፈጥር ከሆነ ከእግዚአብሔር በጥምቀት በመንፈስ ተወልደን እዉነተኛ ልጆቹ መሆን ምን አይነት ስሜት ሊፈጥርብን ይገባ ነበር! ነገር ግን በሥጋዊ ዐይናችን ስለምንመለከት እዉነተኛዉ ዐይነ ኅሊናችን ስላልተከፈተልንና በምድራዊ ነገር ብቻ ስለደነዘዝን ታላቁ ማንነታችንና ክብራችንን አላስተዋልንም፤ አቃለነዋል፤ አጥላልተነዋል፤ ክደነዋል::

ወደ ጥያቄያችሁ ስመለስ እግዚአብሔር « በዚህ ቀን እንዲህ ይሆናልና ተዘጋጁ፣ ዓለም በዚህ ቀን ታልፋለችና ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ » በማለት ለፍጥረቱ ዓመቱን፣ ወሩን፣ ቀኑን ገልጾ አይናገርም:: ምክንያቱም ሰዎች በነጻ ኅሊናቸዉ በነጻነት ተመላልሰዉ ሁሉ ጊዜ ለእግዚአብሔር የሚመች ሕይወት ይዘዉ እንዲገኙና ሁል ጊዜ በንስሐ እየጸዱ በንጽህናና በቅድስና ሕይወት እንዲኖሩ ነዉ ፈቃዱ እንጂ « ይህን ጊዜ ስላለህ እስከዚያ ጊዜ እንደፈለከዉ ሁን፤ ቀኑ ሲደርስ ግን እኔን በመፍራትና ለኔ በመገዛት ኑር::» ብሎ ፍጥረቱን አያዝም:: ለዚህም ነዉ በሥጋ የምንሞትባት ቀን ሳናዉቅ ሞታችንን ተሸክመን የምንዞረዉ:: ስለዚህ እኛ ሁል ጊዜ እግዚአብሔርን በእዉነትና በመንፈስ እያመለክነዉ በንስሐ በሥጋ ደሙ ተወስነን ነዉ መኖር ያለብን እንጂ «በዚህ ዓመት፣ በዚህ ወር፣ በዚህ ቀን» እንዲህ ይሆናል ብለን በአጉል ተስፋ ዉስጥ መመላለስና መጨነቅ የለብንም:: «ዓለም በዚህ ቀን ታልፋለች::» የሚሉ ሰዎች በራሳቸዉ የፈጠሩት ወይንም ሸዋጁ መንፈስ በኅሊናቸዉ እንዲፈነጭባቸዉ ስላደረጉ እየተጫወተባቸዉ መሆኑን ነዉ የሚያሳየዉ::

እግዚአብሔር ስለ ዓለም እልፈት የተናገረዉ ከእንግዲህ በኃላ ሶስት ዋንኛ ትንቢቶች ናቸዉ የሚቀሩት::

፩. የዓለም ሕዝብ በዐመጻዉና በክህደቱ እንዲሁም በርኩሰቱ ተግባርና ንግግር እግዚአብሔርን እጅግ ስላስቆጣ ከቅርብ አመታት ወዲህ እንደምታዩትና እንደምተሰሙት የተለያዩ የእግዚአብሔር ቁጣ መገለጫ የሆኑት እግዚአብሔር የለሹ ትዉልድ «የተፈጥሮ አደጋ» የሚላቸዉ የተላያዩ መቅሰፍቶችና ቅጣቶች በዚህ ትዉልድ ላይ ይመጣል:: በተለያየ መንገድ እያንዳንዱ አገር(መንግስት) ፣ ቡድን ፣ ድርጅት፣ ግለሰብ የዘራዉን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፍሬዉን መራራ ቢሆንም ያጭዳል ጽዋዉንም ይጠጣል::

፪. የዲያብሎስ እንደራሴ ሆነዉ የእርሱን ፈቃድ የሚያስፈጽሙትና የሚፈጽሙት « የዐመጻ ልጆች» የተባሉት ሁሉ ከዚህች ምድር ከተጠረጉና ምድሪቱም ከሕዝብ ደም መጣጮችና ጨቋኞች እንዲሁም ከበደለኞች፣ ከግፈኞች፣ ከዐመጻኞች ከጸዳች በኋላ ኢትዮጵያም ሆነች ሌላዉ የዓለም አገራት ሁሉ በእግዚአብሔርና በእመቤታችን ድንግል ማርያም ዘንድ ሞገስን ያገኙ ለተመረጡና ለተቀቡ ለሁለት ኢትዮጵያዉያን ሥጋዊዉም መንፈሳዊዉም ወንበር ተላልፎ ይሰጣል:: እነሱም በሥጋዉም በመንፈሳዊዉም ሕይወት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ እየፈጸሙ እያስፈጸሙ በዓለም ዘንድ በረሀብ፣ በልመና፣ በድርቅ፣ በጦርነት ፣ በስደት፣ በችግር፣ የምትታወቀዉን እናት አገራቸዉን ኢትዮጵያን በእዉነትና በመንፈስ ብቻ በማገልገል በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግስት ስርዐት እንዲዘረጋ አድረገዉ ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያዉያን ብቻ አይደለም የዓለም የሥጋዊዉም የመንፈሳዊዉም መሪና አገልጋይ ሆና በእግዚአብሔር እንደራሴ መንግስትነቷ ህልዉናዋ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ይቆያል:: እግዚአብሔር እሰከመጨረሻዉ ድረስ ከእርሷ ጋር ነዉና ማንም ምንም ሊያደርጋት ስለማይችል ስንዱ እመቤት ሆና እስከመጨረሻዉ(ዓለም ፍጻሜ) ድረስ በእግዚአብሔር መንግስትነቷ ትኖራለች::

፫. በዚህች ምድር ዉስጥ ያሉት ከቁጥር በላይ የሆኑት ርኩሳን መናፍስተ(ሰይጣናት) ቁጥር በዚህች ምድር ዉስጥ፣ በገነት ዉስጥ፣ በማረፊያ ቦታ ዉስጥ፣ በሲዖልና በሰማያት ዉስጥ ከሚኖሩት ሰዎች(ነፍሳት) ጠቅላላ ድምር ቁጥር ጋር ሲቀራረብ በቅርቡ የሚከሰተዉንና የሚታየዉን የእግዚአብሔርን ማጥሪያና ማበጠሪያ ኃይሉን የሚዘነጋና የሚክድ እንዲሁም ከማጥሪያዉና ከማበጠሪያዉ ወቅት በኋላ የሚፈጠረዉን መልካም ዘመን የኢትዮጵያ ትንሳኤ የሚታይበትን ዘመን የሚዘነጋ ትዉልድ በዓለም ( በዚህች ምድር) ዉስጥ ይወለዳሉ::

በዚያን ዘመን ዋናዉ የዐመጻ ልጅ የተባለዉ ሐሳዊ መሲህ (ሐሳዊ ክርስቶስ) (ሐሳዊ አምላክ) በዓለም ዉስጥ ይወለዳል:: በዚያን ጊዜ ትዕቢት፣ ክፋት፣ ዐመጻ የተባሉት የፈርዖን፣ የይሁዳ፣ የአርዮስ ወንድምና እህቶች ዋና ተከታዮቹና ስራ አስፈጻሚዎቹ እንዲሁም

አጫፋሪዎቹ ይሆናሉ፡፡ በዚያን ጊዜም ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት አሁን ካለዉና ከሚታየዉ በባሰ መልኩ ይነግሣል፡፡ ዋናዉ የዐመጻ ልጅ( ሐሳዊ መሲህ) ከኀሊና በላይ በሆነዉ ተአምራቱና ኃይሉ እንዲሁም ቅጣቱ ምክንያት አእምሮ ህጻናትና አእምሮ ቀላሎች ተከታዮቹ ይሆናሉ፡፡ አእምሮ አዋቂዎችም የተባሉት ምርጥ ነፍሳት ለጥቅማቸዉ፣ ለክብራቸዉ፣ ለስልጣናቸዉ፣ ለዝናቸዉ፣ ለብልጽግናቸዉ ሲሉ በጽናት ስለ እዉነት ከመቆምና ከመመስከር ይልቅ ልክ እንደአሁን ዘመን ያሉ ሰዎች፤ ለእግዚአብሔር እዉነት ይቆማሉ ብለን ስንገምት ከዲያብሎስ እንደራሴዎች ጋር ሽር ጉድ ሲሉ የፖለቲካ አስፈጻሚ ሲሆኑ እንደምንመለከተዉ በባሰ ሁኔታ የዲያብሎስ (በሥጋ የሚገለጸዉ የዋናዉ የዐመጻ ልጅ) ስራ ፈጻሚና አስፈጻሚ በመሆን ተሰናክለዉ ይቀበሉትል፡፡ አእምሮ ጽንአን የሚባለት የበቁ ነፍሳት ግን በተለያየ ድንቃድቅ ተአምራቱና በቁጣዉ ቢፈተኑም እስከመጨረሻዉ ድረስ የእግዚአብሔር አገልጋይና አማኝ ሆነዉ በመጽናት ይቃወሙታል እንጂ አይቀበሉትም፡፡ ለሶስት አመት ተኩል ዋናዉ የዐመጻ ልጅና የአጫፋሪዎቹ እንዲሁም የተባባሪዎቹ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ጽዋ ሲሞላና በምድር ዉስጥ ያሉት የሰይጣናት ቁጥርና በምደር ዉስጥና ከምድር ዉጭ ባሉት ቦታዎች ያሉት የሰዉ ዘሮች ነፍሳት ቁጥር እኩል በሚሆንበት ዘመን የዐመጻ ልጆች ባለጊዜነት ይሻራል፡፡

በዚያን ዘመን የዐመጻ ልጆች በምድር ላይ ለወራቶች ያህል በተለያየ መቅሰፍት ይሰቃያሉ፤ በመጨረሻም በመቅሰፍት ሞት ወደ ማረፊያ ቦታ ይጠራሉ፡፡ በእግዚአብሔር የታመኑት እዉነተኛ አገልጋዮችና አማኞች ደግሞ በምህረት ሞት ወደ ማረፊያ ቦታ ይጠራሉ፡፡ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስም ከእልፍ አእላፋት ቅዱሳን መላእክትና ከበቁ ነፍሳት ጋር፤ ከሰማያት በታችና ከዓለምና ከሲዖል በላይ ወደ ሆነችዉ እንዲሁም በመጨረሻ ዘመን ከምትዘጋጀዉ ከገሃነመ እሳት ጎን በምትሆነዉ ማረፊያ ቦታ ላይ የመጨረሻ ፍርድ ለመስጠት ይገኛል፡፡ በዚህች ምድረ ዉስጥ ያሉት ሰይጣናት(ርኩሳን መናፍስት) ከመሪያቸዉ ዲያብሎስ ጋር ወደ ማረፊያ ቦታ መተዉ በቀጥታ ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ይጣላሉ፡፡ በዚህች ትልቋ ዓለም ዉስጥ ከምደር(ከትንሿ ዓለም) ጉን በስተቀኝ በምትገኘዉ ገነት ዉስጥ ያሉት ነፍሳት ወደ ማረፊያ ቦታ ተጠርተዉ በቀጥታ ወደ ሰማያት ዉስጥ ይገባሉ፡፡ ከትልቋ ዓለም ጉን በስተግራ በምትገኘዉ ሲዖል ዉስጥ የሚገኙት ነፍሳት ወደ ማረፊያ ቦታ ተጠርተዉ በቀጥታ ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ይጣላሉ፡፡ በማረፊያ ቦታ የተገኙት ነፍሳት እንደ ነፍስ ብቃታቸዉ ለሰማያዉ መንግስት የሚያበቃ ሕይወት የያዙት ተፈርዶላቸዉ ወደ

ሰማያት ሲገቡ፤ ለሰማያዊ መንግስት የሚያበቃ ሕይወት ያልያዙት ደግሞ እንደ ዐመጻ ደረጃቸዉ ፍዳቸዉን ለመቀበል ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ይጣላሉ፡፡ በዚህ መልክ ለእያንዳንዱ ሕያዋን ፍጥረት እንድ ስራዉና እምነቱ ተፈርዶለትና ተፈርዶበት፤ ትልቋ ዓለም፣ ሲያል፣ ማረፊያ ቦታ ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋሉ፡፡ በቦታዉ አማናዊ ሕዋ ይተካል፡፡ ሰማያትና ገሃነመ እሳት ቦታ ብቻ በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ይቀራሉ፡፡

በሰማያት ዉስጥ የሚገቡት ሰዎች(ነፍሳት) እንደ ጽድቅና ቅድስና ብቃታቸዉ ክብርንና ጸጋን አግኝተዉ እስከ ሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ ከቅዱሳን መላእክት ጋር እግዚአብሔርን እያመለኩ በፍጹም ቅድስናና ደስታ ሕይወት ብቻ ይኖራሉ፡፡ ቅዱሳን መላእክት ሁሉም ቅዱስ ቢባሉም ስልጣናቸዉና ክብራቸዉ እንደ እምነት ጽናታቸዉና ብቃታቸዉ ይለያያል፡፡ ይኸዉም ዲያብሎስ ጥንት በሰማያት ዉስጥ « እኔ ነኝ አምላካችሁ እኔን አምልኩ፡፡» በማለት ዐመጻና ክህደት ሲፈጽም እንደመቃወማቸዉና እንደአለመቀበላቸዉ እምነትና ጽናት ነጥብ ተሰቷቸዉ ነዉ በሰማያት ዉስጥ የተለያየ ስልጣንና ክብር ያገኙት፡፡ ለምሳሌ ቅዱስ ሚካኤል በዲያብሎስ ላይ ባሳየዉ የተቃዉሞና ለአምላኩ በታመነዉ እምነትና ጽናት የቅዱሳን መላእክት ሁሉ አለቃ እንዲሆን ተሹሟል፡፡ በዚህም በስልጣንና በክብር ከሁሉም መላእክት ይበልጣል፡፡ በመቀጠል ደግሞ ቅዱስ ገብርኤል ባሳየዉ የተቃዉሞና ለአምላኩ በታመነዉ እምነትና ጽናት የቅዱሳን መላእክት ሁሉ ሁለተኛ አለቃ ሁኖ ተሹሟል፡፡ ሌሎቹም እልፍ አእላፋት ወትእልፊት መላእክት እንድ እምነታቸዉና እንዳሳዩት ጽናት ደረጃ ነዉ በሰማያት ዉስጥ ስልጣንና ክብር አግኝተዉ የኖሩትና የሚኖሩት፡፡

በዚሁ መልክ ነዉ ሰዎች በምድራዊ ዘመናቸዉ በሚያሳዩት የእምነትና የምግባር ብቃት በሰማያት ዉስጥ ስልጣንና ክብር የሚያገኙት፡፡ 90 ነጥብ ያገኘዉ ጻድቅ ሆነ 80 ነጥብ ያገኘ ዉ ቅዱስ ነፍሳት ተብለዉ በሰማያት ዉስጥ ቢገቡም የሚያገኙት ክብር እንደ ነጥባቸዉ ይለያያል፡፡ በሰማያት ዉስጥ የሚኖሩት ቅዱሳን መላእክት ሆኑ ቅዱሳን ሰዎች(ነፍሳት) የሚገለጹት በረቂቅ አካል (በምሳሌያዊ ባሕርይ) ሲሆን፤ ከቅዱሳን መላእክት ሆነ ከቅዱሳን ነፍሳት በእምነቷና በሕይወቷ እጅግ በቅታ የተገኘችዉ የእግዚአብሔር እናት ለመሆን የበቃችሁ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ግን በሰማያት ዉስጥ አሁንም የተገለጸችበት ወደፊትም የምትገለጽበት አካል እንደ ልጇ መድኃኔለም በብርሃናዊ ባሕርይ ነዉ እንጂ እንደ መላእክትና ነፍሳት በምሳሌያዊ ባሕርይ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ከፈጣሪ ከልጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ በታች ከፍጡራን በላይ ሆና ትከብራለች፤ ትመሰገናለች፡፡

እስከ ሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ በሰማያት ዉስጥ ቅዱሳን መላእክትና ቅዱሳን ነፍሳት አምላካቸዉን በእዉነትና በመንፈስ እያመለኩ በቅድስናና በደስታ ሕይወት ከኖሩ በኋላ ጸጋቸዉ እጅግ ይበዛል:: በዚህም ምክንያት ሁሉም ቅዱሳን መናፍስትና ቅዱሳን ነፍሳት የመጨረሻዉን ቅድስና ብቃት ላይ ስለሚደርሱ ብርሀናዊ ባሕርይ እንዲለብሱ ተደረጎ ተገልጸዉበት የነበረዉ ፍጥረት የሆነዉ ረቂቅ አካል ምሳሌያዊ ባሕርይ ከመኖር ወደ ወደ አለመኖር ያልፋል:: የመጀመሪያዉ ምሳሌያዊ ባሕርይ ቦታ የሆነዉ ሰማያት በአማናዊ ሕዋ ይተካል:: ምሳሌያዊ ባሕርይ የሆነዉ የመጀመሪያዊ ፍጥረት ቦታ ሰማያት ዉስጡ ያለዉ ፍጥረት ሙሉ በሙሉ ከመኖር ወደ አለማኖር ያልፋል:: ከዚያም እግዚአብሔር ጥንት እንደነበረዉ አኗኗር እንደ አማናዊ ባሕርይዉ መጀመሪያና መጨረሻ በሌለዉ አማናዊ ሕዋ ዉስጥ ሕያዉ ሆኖ ይኖራል:: ቀድሞ ያልነበሩት ከሕያዉነት ዘመን በኋላ ካለመኖር ወደ መኖር የመጡት ቅዱሳን መናፍስትና ቅዱሳን ነፍሳት እንደ አማናዊ ባሕርያቸዉ በብርሃናዊ ባሕርይ ተገልጸዉ ለሕያዉነት ዘመን ከፈጣሪያቸዉ ከእግዚአብሔር ጋር ሕያዉ ሆነዉ ይኖራሉ:: እንደ አምላካቸዉና እንደ እዉነተኛ አባታቸዉ የማይኖሩበት ጊዜ አይኖርም::

ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ በእኛ በሰዎች ኅሊና ቁጥር ለሕያዉነት ዘመን ቢባል የሚቀል ሲሆን፤ ምክንያቱም ከዛሬ እስከ እግዚአብሐር መጀመሪያ ከሌለዉ ጥንት (ያልኖረበት ጊዜ የሌለ) ጊዜ ድረስ ያለዉን ዘመን በእኛ አእምሮ ወይንም በፍጡር አእምሮ ደረጃ ልናሰለዉ ሆነ ልንገምተዉ እንደማንችል ሁሉ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ ያለዉን ዘመን ማለት የዘመኑን መጠን በፍጡር አእምሮ እንዲሁ ልናሰላዉና ልንገምተዉ አንችልም:: ይኸዉም በሂሳብ ስሌት ሲታይ ከኔጌቲቭ ኢንፊኒቲ(-∞) እስከ አሁን ያለዉ ዘመን ኢንፊኒቲ(∞) ስለሆነ ከፍርድ ቀን እስከ ሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን ድረስ የተባለዉም ለእኛ ኅሊና መጨረሻ የሌለዉ ኦንፊኒቲ(∞) ነዉ:: በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ዘመኑ ይታወቃል:: በምሳሌ ብቻ ብንገልጽ ኳትሪሊዮንን ቁጥር ኳትሪሊዮን ጊዜ እየተደጋገመ ቢባዘ ወይንም

$(10000000000000000000000000000000000)^{100000000000000000000000000000000000000000000000000}$

ከሚሰጠን ቁጥረ እጅግ እጅግ ለሚበልጥ ዘመን ማለት ነዉ:: ይህ በእኛ ኅሊና ለሕያዉነት ዘመን ብለን ብንናገረዉ የሚቀል ነዉ::

በዚህ ዘመን ማለትም ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ ቅዱሳን መናፍስትና ቅዱሳን ነፍሳት እንደአማናዊ ባሕርይ( እንደ ነፍሳቸዉ ባሕርይ) ብቻ በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ መኖር ሲጀምሩ፤ በገሃነመ እሳት ዉስጥ በተገለጹበት ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) እንደ ኃጢአታቸዉ ደረጃ እየተቀጡና እየተሰቃዩ የሚኖሩት ርኩሳን መናፍስትና ርኩሳን ነፍሳት

ለሕያዉነት ዘመን ፍዳቸዉን ከተቀበሉ በኋላ የእግዚአብሔር ቸርነት ይበዛል፡፡ በዚህም ምክንያት ልክ ነፍሳችን ሕያዉ ብትሆንም በምናቀላፋበት ወቅት አንዳች እንደማታስተዉልና እንደማታዉቅ ሁሉ እነዚህ ዐመጸኛና ከሃዲ የሆኑት ርኩሳን መናፍስትና ርኩሳን ነፍሳት ምንም እንዳያዉቁና እንዳያስተዉሉ ተደረጎ ህልዉናቸዉን ያጣሉ፡፡ ምሳሌያዊ ባሕርይ የሆነችሁ አምስተኛዉ ቦታ ገሃነመ እሳት ዉስጡ ካሉት ምሳሌያዊ ባሕርይ ፍጥረቶች ጋር ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፋል፡፡ በአማናዊ ሕዋ ይተካል፡፡ በመጨረሻም መጀመሪያና መጨረሻ የሌለዉ አማናዊ ሕዋና ርኩሳን መናፍስትና ርኩሳት ነፍሳት ህልዉናቸዉን አተዉ የሚኖሩበት ነጥብ ቦታ ብቻ ይቀራል፡፡ እግዚአብሔርና ቅዱሳን መናፍስትና ቅዱሳን ነፍሳት ብቻ ሕያዉ ሆነዉ በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ይኖራሉ፡፡

ልክ ምሳሌያዊ ፍጥረት ወይንም በዚህ በሥጋዊ አይናችን የምናያቸዉ ፍጥረቶች በዓለም ፍጻሜ ጊዜ ከመኖር ወደ አለመኖር አልፈዉ ምሳሌያዊ ባሕርይ ብቻ በሰማያትና በገሃነመ እሳት ዉስጥ እንደሚቀር ሁሉ ከሕያዉነት ዘመን አንድ ቀን በኋላ ፍጥረት የሚባል ወይንም ምሳሌያዊ ባሕርይ ከመኖር ወደ አለመኖር አልፎ የቅዱሳን መላእክትና ቅዱሳን(ጻድቃን) ሰዎች ነፍስ እንደ አማናዊ ባሕርያዋ የመጨረሻዉን ቅድስናና ደስታ አግኝታ በብርሃናዊ ባሕርይ ብቻ ተገለጻ ከእዉነተኛ አባቷ እግዚአብሔር ጋር በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ሕያዉ ሆና ስትኖር፤ ሰይጣናትና የተኮነኑ ሰዎች የተገለጹበት ምሳሌያዊ ባሕርይ ከመኖር ወደ አለመኖር ያልፍና ምንም እንዳያዉቁና እንዳያስተዉሉ ተደርጎ የራሳቸዉን ህልዉና እንዲያጡ ከተደረገ በኋላ በብርሃናዊ ባሕርይ ተሸፍነዉ በነጥብ ቦታ በአማናዊ ሕዋ ዉስጥ ለሕያዉነት ዘመን በበድን ሕይወት ይኖራሉ፡፡ ይኸዉም በእናቱ ማኅፀን ዉስጥ ያለ ህጻን እንደማንኛዉም ሰዉ ሕያዉ ፍጥረት ቢሆንም አንዳች የሚያዉቀዉና የሚያስተዉለዉ ነገር እንደሌለና አንዳች እንደማይሰማዉ ሁሉ እነዚህ ዐመጸኛ ነፍሳትም ለሕያዉነት ዘመን ፍዳቸዉን ከጨረሱ በኋላ በዚህ መልክ በነጥብ ቦታ በዚህ መልኩ ይኖራሉ፡፡

እንግዲያ የእኛ የሰዉ ዘሮች ተስፋ እጅግ እጅግ የላቀ በአንደበት የማይገለጽ መሆኑ በዚህ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን ይህን ታላቅ ተስፋችንን ትተን የከፋዉንና የከረፋዉን፣ የሸተተዉንና የጠነባዉን ዓለም ሙጭጭ አድርገን ይዘን በከፋ፣ በከረፋ፣ በሸተተ፣ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት፣ ባጠቃላይ በኃጢአት ሕይወት እንመላለሳለን፡፡ ሌት ተቀን የምንወጣዉ የምንወርደዉ ለዚህ ቅርፊት ሥጋችን ለአፈር አስረክበን ለምንሄደዉ መሆኑን ሳስብ ነፍሴ እጅጉን ታዝናለች፤ ታነባለች፡፡ እናንተ እግዚአብሔር መርጧችኋልና ያልጠየቃችሁትን ምስጢር ሁሉ ነዉ እግዚአብሔር ያሳወቃችሁ፡፡ ምክንያቱም እኔም እንደእናንተ ፍጡር የሆንኩ ሥጋ ለባሽ ነኝና ይህን ምስጢር ቀድሞ አለዉቀዉም ነበር፡፡ አሁን ነዉ እንደእናንተ የተነገረኝና የተገለጸልኝ፡፡ ከእንግዲህ ነፍሳችሁን ወደ ኋላ የሚያስቀርና የሚያዳክም ኃይል

የሚኖር አይመስለኝም:: ለመፈታተን የሚመጣዉ የዲያብሎስን ኃይል በተማራችሁት መሰረት ድል እንደምታደርጉ ጥርጥር የለኝም::

ታዲያ ከላይ በተገለጸላችሁ መሰረት ስለ ዓለም ፍጻሜ ምልክቱ ነዉ የተነገራችሁ እንጂ «በዚህ ዓመተ ምህረት፣ በዚህ ወራት፣ በዚህ ቀን» ተብሎ አንድም ቦታ አልተገለጸም:: ስለዚህ እናንት ዓለም በዚህ ቀን ታልፋለች ብላችሁ አንዳች መጨነቅ ሆነ ማሰብ የለባችሁም:: የእያንዳንዳችን የዓለም እልፈት ቀን እለተ ሞታችን ስለሆነ፤ ይኸዉም ዳግም የንስሐ እድል ስለማናገኝና እለተ ሞታችንን ስለማናዉቅ ሁል ጊዜ ዝግጅዎች ሆነን መገኘት ይኖርብናል:: ሌላዉ በኅሊናችሁ « ይህች ደሀ ኋላ ቀር የተባለች አገር አሁን ደግሞ በጎጥና በቋንቋ ተከፋፍላ፣ ዘፈኑና ዳንኪራዉ፣ ክፋትና ተንኮሉ፣ ዐመጻዉና ክህደቱ፣ ርኩሰቱ የነገሠባት አገር ኢትዮጵያ እንዴት ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱ፣ ቤተምልክናዉ በአንድ መንፈስ ቅዱስ ተዋህዶ በእግዚአብሔር መንግስትነት ትገለጻለች? ስንት ኃያላን የተባሉ አገራት እያሉ የዓለም መሪ ትሆናለች?» የሚል ጥያቄ በኅሊናሁ እንደሚፈጠር እገምታለሁ:: ማወቅና ማስተዋል ያለባችሁ ከእግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈጸምበት ስርዐት ቀርቶ የዲያብሎስ ስርዐት የዲያብሎስ ፈቃድ የሚፈጸምበት ስርዐት ለዘመናት በዓለም ላይ ተዘርግቶ ሰዎች ሲኖሩበት፣ ሲመላለሱበት፣ ሰምተናል፤ አሁንም በእኛ ዘመን እያየን ነዉ:: ታዲያ ሊሆን የማይቻለዉ ሲሆን እየሰማንና እያየን ሊሆን የሚችለዉ ከእግዚአብሔር የሆነዉ መልካሙማ እንዴት እጅግ አብልጦ ሊሆን አይችልም?! እጅግ ይሆናል::

የቅርብ ታሪኮችን ብንመለከት  ከሰዉ መፈጠር ጀምሮ እግዚአብሔር በኪዳነ ልቦና፣ በኪዳነ ኦሪት፣ በኪዳነ ወንጌል የሚመለክባት አገር፤ «ሀገረ እግዚአብሔር የተባለች ቅድስት ኢትዮጵያ ዉስጥ  በአስራ ሰባቱ አመት በደርግ(በኢሠፓ) ዘመን በሶሻሊስት ስርዐት « እግዚአብሔር የለም መመሪያችን የማርክስ የኤንግልስ የሌኒን ፍልስፍና ነዉ::» በማለት ትዉልዱ በክህደት፣ በዐመጻ፣ በርኩሰት ሕይወት እንዲመላለስ አልተደረገም ወይ? አሁን ደግሞ ለሃያ አመት በወያኔ(ኢህአዴግ) ዘመን በአብዮታዊ ዲሞክራሲ እግዚአብሔር የለሽ የሶሻሊስት ልጅ በሆነዉ ስርዐት ዉስጥ አንድ የነበረዉ ሕዝብ በቋንቋ፣ በጎሳ፣ ተከፋፍሎ፤ በጥላቻ፣ በቂም በቀል፣ በጥል፣ በመለያየት፣ በመከፋፈል ሕይወት ዉስጥ ሲኖርና በግልጽ የዐመጻዉ፣ የክህደቱና የርኩሰት ተግባር ሲፈጸም አላየንም ወይ? እነዚህ እንክርዳድ ተግባራት ሊከሰቱ የማይችሉ ቢሆንም በኃጢአታችን ምክንያት በእኛ ትዉልድ ሊከሰትና ተግባርዊ ሊሆን ችሏል:: ታዲያ ንስሐ ብንገባና እጃችንን ለእግዚአብሔር ሰተን «አንተ ንገሥብን፤ አንተ አስተዳዳሪያችንና መጋቤያችን ሁን» ብንለዉ፤ እንዴት በረከት፣ ፍቅር፣ ሰላም፣ ደስታ፣ ጤና፣

ብልጽግና የሞላበትን ስርዐት መስርቶልን፤ ድህነትን፣ ችግርን፣ ስቃይን ፣ ስደትን ፣ ጥልን ፣ ጥላቻን፣ ጦርነትን፣ ግድያን፣ በደልን፣ መከፋፈልን፣ መለያየትን፣ ክፋትን፣ ተንኮልን፣ ዐመጻን፣ ክህደትን ፣ ዉርደትንና ጉስቁልናን ከኛ አርቆልን ሰማየዊ ስርዐት እንዴት አይዘረጋልን?! በመቶ እጥፍ ይዘረጋልናል::

ከላይ የተገለጹት የዐመጻና የክህደት ስርዐቶች በኛ ትዉልድ ላይ እንደተከሰቱ ሁሉ እግዚአብሔር፤ ስለ እናቱ ድንግል ማርያምና ስለቅዱሳኑ እንዲሁም በዚህች ምድር ዉስጥ በሥጋ እያሉ እርሱን በመፍራት ስለሚመላለሱ በእዉነትና በመንፈስ አምልኮ ስለሚፈጽሙት ምርጦቹ ሲል እግዚአብሔር በኛዉ ትዉልድ ሰማያዊ ስርዐቱን መስርቶልን ስማችን በዓለም ይታደሳል:: ከራሳችን አልፈን ለዓለም ሕዝብ እንተርፋለን:: ያቺን ቀን በትዕግስትና በተስፋ ልንጠባበቅ ይገባል እንጂ በምንም መልኩ ስለዐመጻና ስለክህደተ ተግባራቸዉ ከሚጠረጉ የዐመጻ ልጆች ጋር አንድነትና ህብረት መፍጠር የለብንም:: የእነሱ ተባባሪና ጉዳይ አስፈጻሚም መሆን የለብንም:: እዚህ ላይ የማሳስባችሁ አሁን በዓለም ላይ እየተከሰተ ስላለዉ ችግር ለወደፊቱም በከፋ መልኩ በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም የሚከሰተዉን፣ እንዲሁም ከመጨረሻዉ የእግዚአብሔር ቁጣ በኋላ በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም ላይ ስለሚዘረጋዉ ሰማያዊ ስርዐት፣ ባጠቃላይ የዐመጻ ልጆች እንዴት ከምድር እንደሚጠረጉና የኢትዮጵያ ትንሳኤ እንዴት እንደሚመጣ በዝርዝር ከ፲፱፻፺፰እስከ፳፻፩ (ከ1998 እስከ 2001) ዓ.ም ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ የተላለፈዉን የሶስት ጊዜ መልእክት በአንድ ላይ ተጠርዞ «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል ርእስ የተላለፈዉን የእግዚአብሔርን መልእክት አንብቡ::

በቅርቡ በዓለም ላይ ሆነ በኢትዮጵያ ዉስጥ ከሃዲያንና የዐመጽ ሰዎች ለጥቂት ወቅት ባለ ጊዜ መሆናቸዉና የእግዚአብሔር ቁጣ ሆነዉ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ በዐመጻቸዉ የተቀመጡትን ከወንበራቸዉ ለመቁረጥና ዋጋ ለመክፈል መመጣታቸዉ አይቀርም:: ይህም የዐመጻ ልጆች በእግዚአብሔርና በእዉነተኛ አገልጋዮቹ እንዲሁም አማኞቹ ላይ የፈጸሙት በደልና ግፍ፣ ክህደትና ዐመጻ በዚህ ምድር ዉስጥ ጭምር ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍል እንዲያዉቁና ተራና አቅመ ቢስ መሆናቸዉን ለማሳወቅ ነዉ እንጂ የሚጸና አይደለም:: እነሱም የዐመጻና የግፍ ጽዋቸዉ ሲሞላ እግዚአብሔር ስለተመረጡት አገልጋዮቹና ሕዝቦቹ ሲል በመለኮታዊ ቁጣዉ እንዳልነበሩ ያደረጋቸዋል:: ስለዚህ ማንም ሰዉ የእግዚአብሔር ቁጣ ሆነዉ ከሚመጡት ከተከታዮቹ የዐመጻ ልጆች ጋር ህብረትና አንድነት እንዳይፈጥር ከአደራ ጭምር አሳስባችኋለሁ:: በምድርም በሰማያም ዋጋ ለማግኘት የሚፈልግ ሰዉ ሁል ጊዜ አንድነቱና ህብረቱ ከእዉነት ጋር ብቻ ማድረግ ነዉ የሚጠበቅበት::

እናቶቼ፣ እህቶቼና ልጆቼ አንዳንዶቻችሁን ስመለከት ገጻችሁ የኀዘንና የዚህች ዓለም ከንቱነት የተረዳችሁና «ለምን ይህችን ዓለም ንቀን በምነና በብቸኝነት ሕይወት አንኖርም?» ብላችሁ ለኅሊናችሁ እንደጠየቃችሁ እገምታለሁ:: እዚህ ላይ ግብታዊ የሆነዉን የሥጋና የደም ስሜታችሁንና ሸዋጁን (አታላዩን) የዲያብሎስን መንፈስ መረዳትና ማወቅ ይኖርባችኋል:: ለዚህ ትምህርት እንዲሆናችሁ የአንድ ወንድም ሕይወት ታሪክ ልንገራችሁ:: ይህ ወንድም በከፍተኛ ትምህርት ተቋም እየተማር እያለ በመሃል ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ያደላና የቅዱስ ጳዉሎስን መልእክት ሲያነብ በብቸኝነት ሕይወት መኖር የበለጠ ለእግዚአብሔር አገልግሎት እንደሚጠቅም ስለተረዳ ወዲያዉ ማንንም ሳያማክር ከሚወዳት ከምትወደዉ ለጋብቻ ከተሳሰባት ሴት ጓደኛዉ ጋር « እኔ አሁን ቆርቤያለሁ፤ በትዳርም የመኖር ፍላጎት ስለሌለኝ ከዛሬ ጀምሮ እግዚአብሔር ከሚፈራና ከሚቆርብ ወንድም ጋር አንቺም ቆራቢ ሆነሽ ጋደኝነትና ጋብቻ መመስረት ትችያለሽ» በማለት ተለያት:: በዚያ ብቻ አላበቃም ሊመረቅ አንድ አመት ሲቀረዉ የዚህችን ዓለም ከንቱነት ሲረዳና የራሱንም ከንቱነት ሲያስተዉል ገና በሃያ አንድ አመቱ ለመመነን ወሰነና አሁንም ማንንም ሳያማክር ትምህርቱን አቋራጦ የምነናዉን ሕይወት አስቀድሞ ለመለማመድ ወደ አንድ ወደሚያዉቀዉ ገዳም ጉዞ አደረገ:: ታዲያ ያሰበዉ ሳይሳካለት « በጀት ስለሌልን አሁን አንቀበልህም::» ስላሉት ወደ ቤተሰቡ ተመልሶ የእግዚአብሔርን ጥሪና ፈቃድ ለሁለት ዓመት ጠበቀ:: ነገር ግን አንዳች ምላሽ ሳይመጣለት በመቅረቱ ከሁለት ዓመት በኋላ ወደ አቋረጠዉ ትምህርት ተመለሰና ተመረቀ:: ወደ ስራ ዓለም ተሰማራ:: ከዚያም ትዳር ያዘ:: የልጆች አባት ሆነ:: በዚህች ዓለም በቅዱስ ቁርባን ተወስኖ ከባለቤቱና ከልጆቹ ጋር በፍቅር፣ በሰላም፣ በበረከት ይኖራል::

ታዲያ ከዚህ ወንድም ብዙ ትምህርት ልንወስድ እንችላለን:: ይኸዉም ገና በሃያ አንድ ዓመቱ ለምናኔ ሕይወት ሲወስን ንስሐ አባቱንና መምህራንን ሳያማክር በሥጋና ደም ስሜቱ ተገፋፍቶ ነዉ የወሰነዉ እንጂ የእግዚአብሔር ጥሪ ደርሶት አይደለም:: የሸዋጁን (የአታላዩን) የዲያብሎስ መንፈስ ተግባሩን በግልጽ አላወቀም:: ይኸዉም ይህ ሸዋጅ መንፈስ ኅሊናችን(ነፍሳችን) ጋር ተጠግቶ ልክ ነፍሳችን ጸጋዉን ካገኘች የእግዚአብሔርን ድምጽ መስማት እንደምትችል ሁሉ፤ ሰይጣናትም መንፈስ ናቸዉና ነፍሳችንን በቀጥታ አጠገቧ ሆነዉ ይናገሯታል:: በዚህ ምክንያት ይህ ወንድም የሰይጣንንም፣ የእግዚአብሔርንም፣ የራሱንም አሳብ ለይቶ አላወቀምና በኅሊናዉ ያ ክፉ ጠላት ያሰሰበዉ የምናኔ ሕይወት የእግዚአብሔር መስሎት ነዉ ትምህርቱን አቋራጦ ለምነና የወጣዉና አልሳካ ሲለዉ ደግሞ ወደ ልቡ ተመልሶ የእግዚአብሔርን ቀጥተኛ ጥሪ ለሁለት ዓመት ለመጠበቅ የተገደደዉና ምንም ምላሽ ሲያጣ ወደ ትምህርት ገበታዉ የተመለሰዉ::

ይህ ወንድም በየዋህነትና በቅንነት የቅዱስ ጳዉሎስን መልእክት በማንበብ ለአምላኩ በመቅናት « በብቸኝነት ሕይወት በመኖር ሙሉ ሕይወቴን ለእግዚአብሔር አገልግሎት እሰጣለሁ» በማለቱ እርሱ ባሰበዉ መልክ ባይሆንም እግዚአብሔር የልቡን ዉሳኔ ተመልክቶ በሥጋዊ ሕይወቱ አንዳች ነገር ሳያጎልበት በመንፈሳዊ ሕይወቱም ያላሰበዉን ምስጢርና ሕይወት ሰቶታል። የሚገርማችሁ ለመመነን ዉሳኔ ላይ የደረሰዉ ከዓለም የኃጢአትና ርኩሰት ሕይወት ራሱን ለይቶ ገና አንድ ዓመት እንኳ የማይሞላ መንፈሳዊ ሕይወት ሳያሳልፍ ነዉ። ስለዚህ እናንተም በቅንነትና በየዋህነት የምታደርጉት ነገር የሚጎዳችሁ ባይሆንም በራሳችሁ ፈቃድ ፈተና በራሳችሁ ላይ እንዳታመጡ፣ የሰይጣንን ጭከናና ተንኮል ተግባር ልታዉቁ ይገባል። እርሱ የ7503 ዓመት ልምድ ያለዉ የእያንዳንዳችንን የእምነት ብቃት የሚከታተልና በጉድለታችንና በድክመታችን ገብቶ ለመጣልና ለማጎሳቆል ሌት ተቀን የሚተጋ የዘመናት ጠላታችን ነዉ። ስለዚህ በቀላሉ መነቀል እንዳትችሉ ስር እየሰደዳችሁ እንደተሰጣችሁ ጸጋ መጠን በመንፈሳዊ ሕይወታችሁ ልታድጉ ይገባል እንጂ በአንድ ጊዜ የብቃት ደረጃ ላይ እንደርሳለን ብላችሁ ከአቅማችሁና ከጸጋችሁ በላይ ለመመላለስ ከተነሳችሁ ያላሰባችሁትና ያልጠበቃችሁት ፈተና ሊመጣባችሁ ይችላል። በዚያም ልትወድቁና ልትሰናከሉ ትችላላችሁ።

ለእግዚአብሔር ራስን ጃንደረባ አድርጎ መኖር የሚቻለዉ ለተፈቀደላቸዉና ለተመረጡ እንጂ ለሁሉ አይደለም። ለአዳም ዘር ሁሉ የተፈቀደዉ በአዳምና ሔዋን አንድ ለአንድ የጋብቻ ስርዐት ጸንቶ እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት ሕይወት በቅንነት፣ በእዉነተኛነት ፣ በመልካም ተግባር መመላለስ ነዉ። ለዚህም ነዉ በአሁን ዘመን አንዳንድ አገልጋዮችና ምእመናን ካለጥሪና ካለ እግዚአብሔር ፈቃድ በሥጋና ደም ስሜታቸዉ ተመርተዉ ቆብ ይደፉና ብዙ ሳይቆዩ ቆባቸዉን የሚጥሉትና እየተደበቁ ዝሙትን በመፈጸም ምእመኑን የሚያሳዝኑትና የሚያሰናክሉት። እንዲሁም አንዳንዶቹ «አገልጋይ» የተባሉ፤ «ዓለምን ንቀናል ሙሉ ሕይወታችንን ለእግዚአብሔር አገልግሎት እናዉላለን» ብለዉ ቃል ከገቡና ቆብ ከደፉና አስኬማ ካደረጉ በኋላ ዓለም እንደገና ትናፍቃቸዉና በዓለም ካሉት ሰዎች ብሰዉ ለስልጣን፣ ለገንዘብ፣ ለክብር፣ ለዝና የሞት ሽረት ትግል ሲያደርጉ፤ በእግዚአብሔር ቃል ሲነግዱ፣ ሲሸቅጡ፣ ሀብትና ንብረት ለማከማቸት ሲሯሯጡ፣ ሲጣሉ፣ ሲወነጃጀሉ፣ እንመለከታለን፤ እንሰማለን።

እግዚአብሔር በግድ ቆብ ድፉ፤ አስኬማ አድርጉ አላለም። ራሳቸዉ ፈቅደዉና መርጠዉ ነበር ሙሉ ሕይወታቸዉን ለእግዚአብሔር አገልግሎት ለማዋልና ቅዱስ ጳዉሎስን ለመምሰል ቆብ የደፉትና ቃል ኪዳን የገቡት። ነገር ግን ቅዱስ ጳዉሎስን መምሰል አይደለም

በዓለም ዉስጥ ትዳር መስርተዉ ልጆች ወልደዉ ሀብትና ንብረት አፍርተዉ ከሚኖሩት ሰዎች እኩል እንኳ እግዚአብሔርን ማስደሰትና ለሃይማኖታቸዉ፣ ለአገራቸዉ፣ ለወገናቸዉ መቆርቆር አልቻሉም:: አንዳንድ ምእመናን ከቅንና እዉነተኛ ሕይወት እንዲሁም ከመልካም ተግባር አልፈዉ በዓለም ዉስጥ እየተመሳለሱ የብህትዉና ኑሮ የሚኖሩ አሉ:: እንዲሁም በብቸኛነት ኑሮ ቆብ ሳይደፉ መንፈሳዊ ሰዉ ሳይመስሉ ራሳቸዉን ሰዉረዉ የቅዱሳንን ስራ የሚሰሩ እግዚአብሔር የሚያዉቃቸዉ ሰዎች አሉ:: ስለዚህ በሥጋና ደም ስሜት ተገፋፍተን በግብታዊነት እንዲሁም በአታላዩ መንፈስ ተታለን እግዚአብሔር ከፈቀደልን ከአዳምና ሔዋን የጋብቻ ሕይወት መለየት የለብንም:: «የእግዚአብሔር ጥሪ ነዉ» ብለን ብናስብ እንኳ በዓለም ዉስጥ እየተመላለስን ለአምስትና ለአስር አመት ራሳችንን ልንፈትን ይገባል፤ እንዲሁም እግዚአብሔርንም ጥሪያችንን በጸሎት በግልጽ እንዲያጸናልን መጠየቅ ይገባል እንጂ ቆብ ደፍተን አስኬማ አድርገን የዐመጻ ተግባር የምንፈጽም ከሆነ ከማንም በላይ እጅግ የባሰዉን የፍዳ ፍርድ እንደምንቀበል በሚገባ ልናዉቅና ልናስተዉል ይገባል::

በመሆኑም እናንተን የምመክረዉ እንደማንኛዉ የአዳም ዘር ሕይወታችሁን በንስሐ እየመረመራችሁ በሥጋና ደሙ ተወስናችሁ ኑሩ:: ትዳር ያልመሰረታችሁ ደግሞ አምላካችሁን እዉነተኛ የትዳር አጋር እንዲሰጣችሁ በጸሎት በመጠየቅ እስከዚያዉ ድረስ ግን ራሳችሁን በመግዛት በሥጋና ደሙ ተወስናችሁ መኖር ይጠበቅባችኋል:: እዚህ ላይ አንዳንድ አገልጋዮችና ምእመናን ወደ ሥጋና ደሙ እንዳትቀርቡ ሊያስፈራሯችሁ ይችሉ ይሆናል:: እነሱ ስለ ነፍስ መዳን ደንታ የሌላቸዉ፤ በዘልማድ የሚመላለሱ፤ አገልግሎታቸዉንም እንደ ገቢ ማስገኛ ስራ መስክ ቆጥረዉ ለመተዳደሪያነት ብቻ የሚጠቀሙ፤ በተለያዩ ተቋማት ቢማሩ ዲፕሎማዉንና ድግሪዉን በመያዝ ሥጋዊ ኑሮዋቸዉን ለማደላደል እንጂ ነፍሳትን በወንጌል ለመመገብና ለማሳረፍ እንዲሁም ምእመናን በእዉነተኛ እረኝነት ለመጠበቅ አይደለም:: እንደነዚህ አይነቶቹ ናቸዉ ጥቅም እስካገኙበት ድረስ ሃይማኖታቸዉን ለመቀየርና በቤተክርስቲያናቸዉ ላይ ደባ ከመፈጸም የማይመለሱት::

አንዳንድ አገልጋዮች ደግሞ እነሱ እርስ በእርስ እየተጣሉ፣ እየተወነጃጀሉ፣ አሁን ልነግራችሁ የማልፈልገዉን ድርጊት እየፈጸሙ ወደ ቤተ መቅደስ እየገቡ ይቀድሳሉ፤ ይቆርባሉ፤ ያቆርባሉ:: ምእመኑን ግን ወደ ቅዱስ ቁርባን እንዳይቀርብ «ወደ ገሃነመ እሳት፣ ወደ ሲዖል ትገባላችሁ::» እያሉ ያስፈራሩታል:: ይህ የሚያሳየዉ ለሰዎች ነፍስ የሚራራ፣ የሚያዝን እዉነተኛ እረኛ መጥፋቱን ነዉ:: የራሳቸዉን ሕይወት በደንብ ቢገመግሙ ኖሮ ምእመኑ ከእነሱ ይልቅ ንጹህ መሆኑን ይረዱ፤ ያስተዉሉ ነበር:: ምክንያቱም ምእመኑ እንኳን በድፍረት ወደ ቅዱስ ቁርባን ሊቀርብ ቀርቶ «ከቆረብኩ በኋላ በተግባር፣ በንግግር፣ በአሳብ

ብበድልስ? እግዚአብሔርን ባሳዝንስ?» በማለት እንኳን በግልጽ ዝሙት እየፈጸሙ ወደ ቁርባን መቅረብ አይደለም፤ «በንግግርንና በአሳብ ኃጢአት ብንፈጽምስ» በማለት አምላካቸዉን የሚያከብሩና የሚፈሩ ናቸዉ:: ታዲያ ይህን ምእመን ወደ ቁርባን እንዳይቀርብ ልናስፈራራዉ ይገባል ወይ?! እኛን ደፋሮቹንና አንገተ ደንዳናዎቹን የታገሰ፣ በቸርነቱ ለእዉነተኛ ንስሐ እድሜ የሰጠ አፍቃሪና ርኅሩኅ አምላክ ለየዋህ ምእመናቹ የቸርነቱን ስራ አይሰራምን?!

እዉነተኛ አገልጋዮች ግን ምእመኑን በሚገባ አስተምረዉ ለንስሐ፣ ለቅዱስ ቁርባን ያበቁታል:: ለነፍሳቸዉ መዳን ይተጋሉ፣ ይጸልያሉ፣ የደከሙትን ያበረታሉ፣ የዛሉትን ያጠነክራሉ፣ በኃጢአት የወደቁትን ያነሳሉ፣ ያዘኑትን ያጽናናሉ፣ በኑሮዋቸዉና በሕይወታቸዉ ለምእመኑ አርአያ ሆነዉ ይገኛሉ:: እንዲሁም ነፍሳችሁን ያሳርፋሉ፣ የከበደዉን ሸክም ያቀሉላችኋል እንጂ ነፍሳችሁን አያስጨንቁም፤ የከበደ ሸክምም አያሸክሟችሁም:: የእርሱ የእግዚአብሔር ሸክም ቀላል የሆነ ቀንበሩም የለዘበ የማያደማችሁ፣ የማይጎዳችሁ፣ የማያጎሳቁላችሁ፣ በእዉነትና በመንፈስ እንድትመላለሱ ስር ሰዳችሁ ቀስ በቀስ እንድታድጉና እንደትጠነክሩ የሚያደርግ እንዲሁም ለታላቅ ክብርና መንግስት የሚያበቃችሁ ነዉ::

በመንፈሳዊ ሕይወት በምትመላለሱበት ወቅት ሆነ በማንኛዉም ጊዜ «እኔ ቅዱስና ንጹህ ነኝ::» ብሎ ቅዱስ ቁርባን የሚቀበል ካለ እርሱ ሐሰተኛና ዋና ኃጢአተኛ አስመሳይ ሰዉ መሆኑን ልታዉቁ ይገባል:: እንኳን በዓለም የሚወጣ የሚወርደዉ፣ በተለያየ ፈተና የሚፈተነዉ ደካማዉ ሰዉ ቀርቶ፤ ነፍሳቸዉን ብቃት ደረጃ ያደረሱ ጻድቃን እንኳ « እኛ ዋና ኃጢአተኞችና በደለኞች ነንና እግዚአብሔር ሆይ ይቅር በለን፣ በቸርነትህና በምህረትህ ለቅዱስ ቁርባን አብቃን እንጂ እንደ ኃጢአታችን አትመልከተን » በማለት እየጸለዩ፤ በትህትና ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉ ነዉ ወደ መለኮት ወደ ተዋሃደዉ ሥጋና ደም የሚቀርቡት እንጂ ራሳቸዉን አያመጻድቁም፤ አያስታብዩም:: ስለዚህ እናንተም ሆናችሁ እኛ ሁልጊዜ ተራ ወራዳ ኃጢአተኛ መሆናችንን እያመን ስለ ተግባራችንና ንግግራችን ኃጢአት ብቻ አይደለም ስለ አሳባችን ኃጢአት ጭምር በኅሊናችን ልንጸጸትና እግዚአብሔርንም ይቅርታ ልንጠይቅ ይገባል:: ከዚያም ከንስሐ አባታችን ጋር በመመካከር ወደ ቅዱስ ቁርባን መቅረብ አለብን:: ያን ጊዜ ነዉ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ፣ የምናስታዉሰዉ ሆነ የረሳነዉ ኃጢአት ሁሉ ከእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ የሚደመሰስልንና በፍርድ ቀን የማያስጠይቀን የሚሆነዉ እንጂ ከሥጋና ደሙ ዉጭ ኃጢአትን የሚደመስስ ሌላ መሳሪያ የለም::

የጾሙ፣ የጸሎቱ፣ የስግደቱ፣ የምጽዋት ዉጤት ሁሉ ለሥጋና ደሙ እንድንበቃና በሥጋና ደሙ ጸንተን እንድንኖር ለማስቻል ነዉ። ትልቁ ለሰዉ ልጆች የተሰጠዉ ስጦታ ንስሐና ሥጋና ደሙ ነዉ። እነዚህ ባይሰጡ ኖሮ ማንም ለእግዚአብሔር መንግስት አይበቃም ነበር። ታዲያ አንዳንድ ለነፍሳት መዳን ደንታ የሌላቸዉ ሆዳቸዉ አምላካቸዉ የሆነ በዘልማድ ብቻ የሚመላለሱ « ይህን አምጡ፣ ይህን አድርጉ፣ እንዲህ ሁኑ፣ ይህን ተጠቀሙ ኃጢአታችሁ ይደመሰሳል፤ በአቋራጭ መንገድ ወደ መንግስተ ሰማያት ትገባላችሁ።» በማለት የሚሸነግሏችሁንና ከሥጋና ደሙ የሚለያችሁን፣ የሚያርቋችሁን አስመሳይ አገልጋዮችን አትስሙ። እነሱ ስለነፍሳችሁ አንዳች የማያስቡ፣ የማይጨነቁ፣ ለሆዳቸዉና ለጥቅማቸዉ ያደሩ ናቸዉ።በእግዚአብሔር ስም የሚነግዱ የባሰም ፍርድ የሚጠብቃቸዉ ናቸዉ።

ሌላዉ እንድታዉቁት የምፈልገዉ የራሳችሁን ማንነትንና ሰይጣናትን ጭምር ነዉ።እናንተ በሥላሴ አርአያና ምሳሌ የተፈጠራችሁ ሕያዋን ፍጥረቶች የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ። እግዚአብሔርን እንድትመስሉ ያደረጋችሁ በሥጋዊ ዐይናችን የምናየዉ ፍጡሩና ደካማዉ፣ ጎስቋላዉ ሥጋችሁ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ባሕርይ የተላበሰችዉ ነፍሳችሁ ናት። የምትገኘዉም ከግንባራችሁ ፊት ለፊት በአንጎላችሁ ዉስጥ ነዉ። አእምሮ፣ ኅሊና እያልን በተለምዶ የምንጠራት እርሷ ናት። ከእርሷ በሚወጠዉ ኃይል ይህን ሥጋችን ተዋህዳ ስለምትገኝ በሥጋችን ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ሁሉ ይሰማታል። የምታወራዉ፣ የምትሰራዉ፣ የምትንቀሳቀሰዉ እርሷ ናት እንጂ ይህ ሥጋ ከእርሷ ሕይወት ባያገኝ ኖሮ በድን ነዉ የሚሆነዉ። የህጻናት፣ የወጣቶች፣ የጎልማሳ፣ የአዛዉንት ነፍስ አንድ አይነት ነዉ። ይህም ማለት ነፍስ እንደ ሥጋ አታድግም፣ አትወፍርም፣ አትከሳም፣ አታረጅም፣ አትሞትም። ቢበዛ በሥጋ ድካም ምክንያት በተጽህኖ ዉስጥ ትወድቃለች እንጂ። እግዚአብሔር በፈቀደላት መጠን ታስተዉላለች፣ ታዉቃለች እንጂ ሰዉ በራሱ ተጠቦ የተለየ ምስጢር ሆነ እዉቀት ሊያመጣ አይችልም። እግዚአብሔር ሲፈቅድ ብቻ ነዉ ምስጢራትም፣ ጥበብም፣ እዉቀትም የሚገለጸዉ። ሰዉ ግን በተሰጠዉ እዉቀት፣ ጥበብ፣ ምስጢራት በነጻ ኅሊናዉ በመልካም ነገር መጠቀምን ትቶ ለጥፋትና ለክህደት እንዲሁም ለርኩሰት ቢያዉለዉ የሚጠየቅበት በዐመጻ የተሰማራዉ ሰዉ ነዉ እንጂ የሰዉ ልጆች እንዲጠቀሙበት እግዚአብሔር የገለጸለት ሰዉ አይደለም። የተገለጸለት ሰዉ ለመጥፎ ነገር ካዋለዉ ደግሞ ከማንም በላይ የሚጠየቅበትና ፍዳዉን የሚቀበል ይሆናል።

አንዳንዴ ይህ ሥጋዊ ዐይናችን የሚመለከት ቢመስልም አንጎል ዉስጥ ያለችዉ ነፍስ ካልተመለከተች ሥጋዊዉ አይን አያስተዉልም፤ አይረዳም፤ አያይም። በሥጋዊ ዐይናቸዉ

እዉርነት ምክንያት ምሳሌያዊ የሆኑ ፍጥረቶችን የማይመለከቱት ዐይነ ስዉራን ነፍሳቸዉ ግን ትመለከታለች፡፡ በተገለጸችበት ሥጋ ስለተገደበች ነዉ እንጂ እንኳን ምድራዊዉን ቀርቶ ከተፈቀደላት ሰማያዊዉን ምስጢርንና ረቂቃኖቹን ሰይጣናትን ጭምር ልትመለከት ትችላለች፡፡ እግዚአብሔር ምክንያት ስላለዉ ነዉ እነዚህ ሰዎች ነፍሳቸዉ በሥጋዊዉ ዐይናቸዉ አማካይነት እንዳትመለከት ያደረገዉ እንጂ ነፍሳቸዉ ሁል ጊዜ የምትመለከት ናት፡፡ ነፍስ የማታረጅ በመሆኑ ሰዉ ምን ያህል እድሜዉ ቢገፋ እንኳ ምላሱ አይደክምም፡፡ ምክንያቱም ተናጋሪዋ የማታረጀዉና የማትደክመዉ ነፍስ ናት እንጂ ምላስ ወይንም አፍ አይደለም፡፡ ምላስንም አፍንም የምታንቀሳቅስ እርሷ በአንጎል ዉስጥ በአካል ደረጃ የተቀመጠችሁ ሕያዊት ነፍስ ናት፡፡

አንዳንዱ በህጻንነት እድሜ ያለ ሰዉ በእድሜዉ እንደጎለመሰ ሰዉ ነገሮችን የሚያዉቀዉና የሚያስተዉለዉ አእምሮዉ ቶሎ እንዲከፈትለት በመደረጉ ነዉ እንጂ ልዩ ፍጡር ሆኖ አይደለም፡፡ ለዚህም ነዉ በአንዳንድ ገድላትና ተአምራት ላይ እግዚአብሔር ለተለየ ዓላማዉ ከማህጸን ጀምሮ የመረጣቸዉ ጻድቃን በተወለዱ በሰስተኛዉ ቀን ለአምላካቸዉ ምስጋና በማቅረብ ልዩ ምልክት የሚታይባቸዉ፡፡ እንኳን የተወለደ ህጻን አይደለም በማህጸን ዉስጥ ያለ ሰዉ የሕያዊት ነፍስ ባለቤት ነዉና በማህጸን ዉስጥ ሆኖ የተለያየ ተአምራትና ምልክትን ሊያደርግ ይችላል፡፡ እንኳን እነዚህ ቀላል ነገሮች አይደለም ከኅሊናችን በላይ የሆነ ተአምራትን እግዚአብሔር በተመረጡት ላይ አድሮ ሊሰራ ይችላል፡፡ ዋናዉ ተአምርም ሆነ ምልክት እንዲሁም ፈዉስ የሚያደርገዉ ፍጹም እግዚአብሔር መሆኑን አዉቀን ልናመልከዉና ልናገነዉ እንዲሁም ልናመሰግነዉ የሚጋበዉ እርሱ ባለቤቱን እግዚአብሔርን እንጂ ፍጡሩን ሰዉ መሆን እንደሌለበት ልናዉቅ ይገባል፡፡

ምንም እንኳን የእግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳንና ጻድቃንን መለያቸዉ የቅድስናና የጽድቅ ስራቸዉ እንዳይታወቅ እግዚአብሔር ብቻ ከፍ ከፍ እንዲል ቢሆንም እግዚአብሔር ግን እኛ የአዳም ዘሮች የበረከታቸዉና የጸጋቸዉ ተካፋይ እንድንሆን ለእኛዉ ጥቅም ሲል ነፍስ ከሥጋቸዉ ከተለየችና እስከመጨረሻዉ ጥሪ ድረስ የሚጠበቅባትን ኃላፊነት ተወታ ወደ እርሱ እቅፍ ስትሄድ በተለየ ሁኔታ መታሰቢያ ተደርጎላቸዉ እንዲዘከሩና እንዲከበሩ ፈቃዱ ነዉ፡፡ እግዚአብሔር ከፈለገ ሰዎች ሥጋዊዉን ሞት ሳይሞቱ ነፍሳትን ሊወስድ ይችላል፡፡ ከፈለገ ደግሞ ለብዙ መቶ አመታት አንዳች ሳይሆኑ በምድር እንዲመላለሱ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ከፈለገም በህጻንነት እድሜ ሊጠራ ይችላል፡፡ ከፈለገም በሰማዕትነት ሊጠራ ይችላል፡፡ ስለዚህ ከእኛ የሚጠበቀዉ እንደ ፈቃዱ መመላለስ ብቻ ነዉ፤ ሌላዉ ግን የእግዚአብሔር ድርሻ ነዉ፡፡

ሰይጣናት ደግሞ በረቂቅ አካል(በምሳሌያዉ ባሕርይ) ተገልጸዉ ነዉ በዚህች ምድር እየተቀጡ ያሉት። እግዚአብሔር በግልጽ ሳይገለጽላቸዉና ሳይታያቸዉ በፊት በነጻ ኀሊናቸዉ ተመርተዉ ዐመጻና ክህደት ስለፈጸሙ ፍርዱ ቀሎላቸዉ በጎሰቆለ ባሕርይ ብቻ ማለትም ሰላምና እርካታ የሌላቸዉ ቅብዝብዝ፤ እረፍት የሌላቸዉ፤ በስጋትንና በጭንቀተ ዉስጥ የሚመላለሱ ሆነዉ ነዉ በዚህች ምድር ዉስጥ የሚኖሩት። እኛ የአዳምና ሔዋን ዘሮች ግን እግዚአብሔር በግልጽ ለአዳምና ሔዋን በብርሃናዊ ባሕርይዉ ተገልጾላቸዉ « ይህን ፍሬ እንዳትበሉ፤ ከበላችሁት ግን የሞት ሞትን ትሞታላችሁ።» ብሎ አዧቸዉ የዲያብሎን ፈተና ማለፍ ተስኗቸዉ በድፍረት «አትብሉ» የተባሉትን ከምሳሌያዉ ባሕርይ በገነት የተፈጠረችዉን ፍሬ በመብላታቸዉ ምክንያት ዐመጻንና ክህደትን ፈጽመዉ ከገነት ወደዚህች ምድር ስለተባረሩ ይህች ምድር ቀድሞ ድቅድቅ ጨለማ የሞላባት የሰይጣናት መቀጫ ነበረችና ለተከታዮቹ ዐማጽያን ነፍሳት መቀጫ ትሆን ዘንድ አሁን በዐይናችን የምናያቸዉም የማናያቸዉም የተለያየ ፍጥረታት በዚህች ምድር ተፈጥረዉ፤ በገነት ተገልጸዉበት የነበረ ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ወደ አለመኖር አልፎ፤ ስለመብል ነዉና ነፍሳቸዉ ያመጸችበት በመብል እንድትቀጣ ታስቦ ይህን ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰጎለ ባሕርይ የተላበሰዉን ሥጋ በዚህች ምድር ከዐመጻ በኋላ ከተፈጠረዉ መሬት ተበጅቶ እንድትዋሀደዉ ተደርጎ፤ ይኸዉ እኛ ዘሮቻቸዉ ጭመር እየተቀጣን እንገኛለን።

የዲያብሎስን የሽንገላና የማስመሰል ስብከት ሰምተን ነዉና ከገነት የወጣነዉ ይኸዉ በዓለም ዉስጥ የዲያብሎስ ፈቃድ ገኖና ተቀባይነትን አግኝቶ ሌት ተቀን በዐመጻ ሕይወት ዉስጥ እንመላለሳለን። ከሰይጣናት የተሻለ እድል ያገኘነዉ ደግሞ እኛ ነን። ይኸዉም በንስሐ ወደ ቀድሞ ቦታችን ገነትና ወደተፈጠርንበት ዓላማ ወደ መንግስተ ሰማያት የመግባት እድል በማግኘታችን ነዉ። ይኽም የሆነበት ዋንኛዉ ምክንያት አዳምና ሔዋን እዉነተኛ ንስሐ ስለገቡ እንዲሁም እኛ ዘሮቻቸዉ ባለወቅነዉና ባልፈጸምነዉ ዐመጻ ምክንያት ፍርዱ በእኛ ላይም ስለጸና ነዉ። ይህ ደግሞ ለኛ እጅግ ትልቅ እድል ነዉ። ስለዚህ ከእግዚአብሔር በጥምቀት ዳግም ተወልደን በሥጋና ደሙ ታትመን ወደገነትና መንግስት ሰማያት የመግባት እድል አለን። ወደ ገነት ስንመለስም ቀድሞ አዳምና ሔዋን ሲፈጠሩ የተገለጹበትን ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ለብሰን የምንኖር ሲሆን ከፍርድ ቀን በኋላ ደግሞ እንደቅዱሳን መላእክት የበለጠዉን ረቂቅ አካል(ምሳሌያዊ ባሕርይ) ለብሰን ነዉ ወደ ሰማያት ዉስጥ የምንገባዉ።

በዚህች ምድር ዉስጥ የሰይጣናት ዋና ስራቸዉ ሌት ተቀን እኛን የአዳም ዘሮችን መፈታተንና ኃጢአት በማሰራት ለገሃነመ እሳት መዳረግ ነዉ። ምክንያቱም የእነሱን ቃል

ሰምተን በዐመጻ ስለወደቅናና በእነሱ ምትክ የተፈጠርን ስለሆነ ኃይለኛ ቅናት ስላደረባቸዉ በምቀኝነት ሕይወት ስለሚመላለሱ ነዉ። የእነሱ እርካታ የኛ የአዳም ዘሮች ዉድቀትና ጉስቁልና ማየት ነዉ። ስለዚህ ሁሉ ጊዜ የነሱን ክፋትና ተንኮል አዉቀን በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት፣ በመልካም ተግባር መመላለስ፤ አምላክንም በስራችን፣ በንግግራችን፣ በአሳባችን ጭመር ልንፈራና ባጠቃላይ ፍጹም እግዚአብሔር በሚደሰትበት ሕይወት ብቻ መመላለስ ነዉ የሚጠበቅብን። በዚህ ሥጋዊ ዐይናችን አናያቸዉም እንጂ እልፍ አእላፋት ነዉ ቁጥራቸዉ። በዚህች ምድር የሌሉበት ቦታ የለም። የሚመቻቸዉ ሰዉ ካገኙ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩት በአንድ ሰዉ ላይ ሊያድሩና ሊያሰቃዩት እንዲሁም ከሰዉነት ማዕረግ ሊያሶጡት ይችላሉ። የዚህን ያህል ነዉ ጭከናቸዉ። እንዲሁም ጻድቁን ሆነ ኃጢአተኛዉን ከመፈታተን ወደ ኋላ የማይሉ ባገኙት አጋጣሚ ኃጢአት ለማስፈጸምና ከአምላካችን ጋር ለማጣለት ለዐይን ቅጽበት ያህል እንኳ ከሰዉ ዘሮች ኅሊናና አካል የማይለዩ ናቸዉ። <u>ስለዚህ በዋናነት ከኃጢአት መጠበቅ ያለብን ከሓሳባችን ነዉ።</u> ምክንያቱም ሰይጣናት እያሰብን ያለዉን ሁሉ ስለሚያዉቁና ስለሚሰሙ፤ የክፋት ሆነ የርኩሰት አሳብ ቢመጣብን እንኳ ወዲያዉ ልንቃወመዉና መንገዱን ልንዘጋባቸዉ ይገባል። ያለበለዚያ ያንን የክፋትና የርኩሰት አሳብ በኅሊናችን በመደጋገም ሹክ እያሉን ለኃጢአት ስራ ሊያሰልፉንና ወደ ተግበር እንድንለዉጠዉ ሊፈታተኑን ይችላሉ። እነሱ በእርግጠኝነት የማያዉቁት እያሰብን ካለነዉ ዉጭ የወደፊቱን አሳብ፣ ተግባር፣ ንግግር ጭምር ነዉ። ነገር ግን እንደ ማንኛዉም ሰዉ አቋማችንን በመመልከት ስለ ወደፊቱ በራሳቸዉ ግምት እየሰጡ በምን መንገድ እንደሚያሰናክሉንና በፈተና እንደሚጥሉን ይራቀቁብናል። እኛም ታዲያ ንጹህ ኅሊና በመያዝ እነሱን የምናሳፍርበትና ድል የምናደርግበትን ከዚያም አልፎ ሌተ ተቀን የምንቀጣበትንና የምናቃጥልበትን የተለያዩ መሳሪያዎችን ጸሎት፣ ጾም፣ ስግደት፣ ምጽዋዕት መያዝ ይኖርብናል።

ረቂቃን ስለሆኑ ወደማንኛዉም ሰዉ ኅሊናና አካል ይገባሉ፤ ይወጣሉ። ይህ ሥጋችን ለእነሱ ሰፋፊ ወንፊት ነዉ። በዚህች ምድር ዉስጥ ሊገድባቸዉ የሚችል ምሳሌያዊ ፍጥረት ሆነ ምስሌያዊ ባሕርይ የለም። እንኳን የእኛ አካል ቀርቶ መስታወት ለእነሱ በጣም ሰፋፊ ወንፊት ያህል ነዉ የሚታየዉ። በዉሎዋችንና በአዳራችን ከኛ እንደማይለዩን ለማወቅ ከፈለጋችሁ ወደ ኅሊናችንና አካላችን እኛን ለፈታተንና ለማዳከም የሚገቡት ረቂቃን ርኩሳን መናፍስት በአፋችን በኩል በማስፋሸክና በማዛጋት ይወጣሉ። በአፍንጫችን በኩል ደግሞ በማስነጠስ ይወጣሉ። በጉሮሯችንና በአፋችን በኩል በማሳል ይወጣሉ። በቆዳችን በኩል በማሳከክ ይወጣሉ። በመገጣጠሚያችን በኩል በማንጠራራት ይወጣሉ። በፊንጢጣችን በኩል በማስፈሳት ይወጣሉ። ከእግዚአብሔር ጸጋ የተለዩ ጎስቋሎች ስለሆኑ እኛ በምንጸየፈዉ እነሱ

ደግሞ ዙፋን መቀመጫቸዉ በሆነዉ ዐይነምድርና ሽንት እንዲሁም ንፍጥና አክታ ላይ አድረዉ አብረዉ ይወጣሉ:: በእግዚአብሔር መንፈስ ምንም ምልክት ሳያሳዩ ከኅሊናችን ሆነ ከአካላችን ተቃጥለዉ ብን ብለዉ ይወጣሉ:: ይህም የሚያሳየዉ ከእግዚአብሔር ጸጋ መለየት ለእንደዚህ ለተጎሳቆለና ለተዋረደ ሕይወት እንደሚዳርግ ነዉ::

እዚህ ላይ የምነግራችሁ ሰይጣናት ወደ ኅሊናችን ሆነ አካላችን ቢገቡም፣ ቢወጡም ነፍሳችንን ሆነ ሥጋችንን በራሳቸዉ ስልጣን አንዳች ጉዳት ሆነ ጥቃት ሊፈጽሙ አይችሉም:: ሊጎዱ ሆነ ሊያጠቁ የሚችሉት ለእነሱ በኃጢአት ባሪያ የሆነዉን ሰዉ ነዉ:: ፈቃዳቸዉን የምንፈጽም ከሆነ በነፍሳችን ሆነ በሥጋችን ላይ ሊሰለጥኑ ይችላሉ:: ከዚያ ዉጭ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚመላለሱትን ሰዎች አንዳች የመጉዳትና የማጥቃት ስልጣን የላቸዉም:: ይልቁኑ ለመፈታተን ወደ ኅሊናችንና አካላችን ሲገቡ እየተቃጠሉ፣ እየተሰቃዩ ፣ እየነደዱ ይወጣሉ፤ ይኖራሉ:: ለመጉዳት እንኳ ቢያስቡ የእግዚአብሔር መልአክ ካሉበት ከሰማያት ከኅሊናችን ርቀት በላይ የሆነዉን ርዝማኔ ከዐይን ቅጽበት ባነስ ጊዜ ዉስጥ አቋርጠዉ በመምጣት ርምጃ ይወስዱባቸዋል፤ አይቀጡ አቀጣት ይቀጧቸዋል:: ስለዚህ ሰይጣናት «እንዲህ ያደርጉናል » ብለን አንዳች ልንሰጋና ልንፈራ አይገባም::

አቅማቸዉንና በቅዱሳን መላእክት እንደምንጠበቅ ስለሚያዉቁና እኛን በቀጥታ ሊጎዱን ስለማይችሉ፤ ሊያጠቁንና ሊጎዱን የሚችሉት ለዚያዉም ዋጋ እንድናገኝበት እግዚአብሔር ከፈቀደ ብቻ በሰዎች ኅሊና ላይ በማደር የክፋትና ጥላቻ ስሜት በኅሊናቸዉ በመፍጠር በመገፋፋትና በመፈታተን ለጥቃት በማነሳሳት ነዉ:: ይህም የሚሆነዉ ምንም እንኳን የሰዎች ነፍስ ነጻ ፈቃድ ያላት ቢሆንም ኃይሏ ግን የተገደበ ነዉ:: ለክፋት ሆነ ለጥፋት ከመሰማራቷ በፊት ከዐይን ቅጽበት ባነሰ ጊዜ ዉስጥ እግዚአብሔር ካለበት ቦታ እርምጃ ሊወስድባት ወይን በቅዱሳን መላእክት ርምጃ ሊያስወስድባት ይችላል:: በመሆኑም ሰዎች የእግዚአብሔርን ምርጦችን ካልተፈቀደላቸዉ በስተቀር እንኳን መግደልና ጉዳት ማድረስ ቀርቶ አንዲቱን ጸጉር እንኳ የመንቀል ኃይልና ስልጣን የላቸዉም::

ነብያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን የተለያዩ መከራና ስቃይ የደረሰባቸዉ እግዚአብሔር ለታላቁ ሰማያዊ ክብርና ሽልማት ሊበቃቸዉና ትዉልዱም ስለ እዉነት ራሱን በመካድ እስከመጨረሻዉ እቅታ ድረስ እንዲጸና ትምህርት እንዲወስድበት ነዉ እንጂ እነዚያን ዐመጸኛችንና ግፈኞችን በዐይን ቅጽበት ጊዜ ዉስጥ እንዳልነበሩ ሊያደርጋቸዉ ይችል ነበር:: እንኳን ፍጡሮቹ ሰዎች አይደለም እርሱ ፈጣሪ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዉ ሆኖ በዚህች ምድር በተመላለሰበት ዘመን ከኅሊናችን በላይ የተለያየ መከራና ስቃይ ደርሶበታል:: ስለዚህ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ የተለያየ መከራና ስቃይ ቢመጣብን እስከመጨረሻዉ ድረስ

ከእዉነት ጋር መቆም ነዉ ያለብን እንጂ ቅርፊት ሥጋ ለባሾችን ፈርተን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ፈጻሚና ተባባሪ መሆን የለብንም። ግፈኞችና ዐመጸኞች ሰዎች የግፍና የዐመጻ ጽዋቸዉ ሲሞላ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ በዚህች ምድርም ፍዳቸዉን ተቀብለዉ ነዉ ወደ ይግባኝና ንስሐ እድል ወደሌለበት የመቀጫ ቦታ የሚሄዱት። እኛ ግን መቼም ይሁን መች በምድራዊ ሕይወት ዘመናችን ሁሉ ስለ ሰዎች ስንል እግዚአብሔር የማይፈቅደዉንና የማይወደዉን ስራ መስራት የለብንም። እንዲሁም ሰዉን በመፍራት የእግዚአብሔርን ሕግና ትዕዛዝ መጣስ እግዚአብሔርንም መካድ የለብንም።

በመንፈሳዊ ሕይወት ጉዟችሁ የምታቀርቡት ጸሎት፣ ጾም፣ ስግደት፣ እንዲሁም ምጽዋት በግብታዊነትና በስሜት መሆን እንደሌለበት ላሳስባችሁ እወዳለሁ። ምክንያቱም ሰይጣናት ቅናተኞች ስለሆኑ ከአቅማችሁ በላይ እንድትፈጽሙ በማድረግ ለተለያየ ፈተናና ለወረተኛነት ሕይወት ሊዳርጓችሁ ይችላሉ። ስለዚህ ጸሎታችሁን ከአቡነ ዘበሰማያትና በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል ትጀምሩና የዘወትር ጸሎት በማስከተል ወደ የየእለቱን ዉዳሴ ማርያምና ይዌድስዋ መልአክትን መጸለይ፤ እየጠነከራችሁና ጸጋዉ እየበዛላችሁ ሲሄድ ደግሞ አንቀጸ ብርሃንን ፣ መዝገበ ጸሎት ላይ ያለዉን ወዳሴ አምላክ የየእለቱን፣ እንዲሁም መልክአ ኤዶም፣ ከእለት እለት ስትጠነክሩ ደግሞ ወርሃዊ መታሰቢያ የሚደረግላቸዉ ከሥላሴ ፣ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ፣ እንዲሁም ከእመቤታችን ድንግል ማርያም በመነሳት የቅዱሳንና የጻድቃንን መልክአ መልክ በመታሰቢያቸዉ ቀን ፣ ሲሆንላችሁ ደግሞ ዲያብሎስ የሚዳመጥበትን የእመቤታችን ዉዳሴ የያዘዉ መጽሐፈ አርጋኖን፣ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ እኔ ያልጠቀስኳቸዉ የጸሎትና የምስጋና መጽሐፍቶችን ልትጸልዩ ትችላላችሁ። እነዚህ ጸሎቶች ላይ ለመድረስ ዓመታትና አስራ ዓመታት ሊፈጅባችሁ ይችላል። ነገር ግን እንደ ተሰጣችሁ ጸጋ መትጋት ይገባችኋል። ቢያንስ ቢያንስ ግን ለሰይጣናት ኃይል ማዳከሚያ ዋና መሳሪያ የሆነዉን የእመቤታችንን ወዳሴ ማርያም የየእለቱን ማድረስ ይጠበቅባችኋል። እዚህ ላይ የማስታዉሳችሁ ትዉልዱ እስከ አሁን ድረስ ችላ ያለዉን የኢትዮጵያዉያን የቅዱሱ ኪዳን ጸሎት የሆነዉን የኢትዮጵያዉያን ቃል ኪዳን ጸሎት ልክ እንደ ጸሎተ ሃይማኖት ከጸሎታችሁ መጨረሻ ላይ ሁል ጊዜ ልትጸልዩት ይገባል።

አምላካችን ሰዉ ሆኖ በምድር በተገለጸበት ዘመን በመዋዕለ ሥጋዌዉ ያስተማረን ጸሎትና በእርሱ መንፈስ በተመሩት ቅዱሳን ያዘጋጁልን ሁል ጊዜ የሚጸለየዉ ጸሎት በግእዝ ቋንቋችን «አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምጻእ መንግሥትከ። ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም። ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመ

ንሕነኒ ንኀድግ ለዘአበሰ ለነ። ኢትአብአነ እግዚኦ ዉስተ መንሱት። አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኲሉ እኩይ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሓት ለዓለም ዓለም።

በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዝእትየ ማርያም ሰላም ለኪ። ድንግል በኅሊናኪ ወድንግል በሥጋኪ። እመ እግዚአብሔር ጸባዖት ሰላም ለኪ። ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ። ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስለኪ። ሰአሊ ወጸልዩ ኀበ ፍቁር ወልድኪ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመ ይስረይ ለነ ኀጣዉኢነ።»

በኢትዮጵያዉኛ(አማርኛ) ቋንቋችን ሲተረጎም ደግሞ «አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደሆነች እንዲሁም በምድር ትሁን። የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ በደላችንንም ይቅር በለን እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንል። ወደ ፈተናም አታግባን ከክፉ አድነን እንጂ መንግሥት ያንተናትና ኃይል ምስጋናም ለዘላለሙ አሜን።

እመቤቴ ማርያም ሆይ በመልአኩ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለሁ። በአሳብሽ ድንግል ነሽ በሥጋሽም ድንግል ነሽ። የአቸናፊዉ የእግዚአብሔር እናት ሆይ ላንች ሰላምታ ይገባል። ከሴቶች ሁሉ ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽና የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነዉ። ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ እግዚአብሔር ካንቺ ጋር ነዉና ከተወደደዉ ልጅሽ ከጌታችን ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይቅርታንና ምህረትን ለምኝልን ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን ዘንድ ለዘላለሙ አሜን። የሚል ነዉ።

### የሃይማኖት ጸሎት፤

እኛ ኢትዮጵያውያን ኹሉን በያዘ÷ ሰማይንና ምድርን÷ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚኤብሔር አብ እናምናለን።

ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋር በነበረ÷ አንድ የአብ ልጅ÷ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፡ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ÷የተወለደ እንጂ ያልተፈጠረ÷ በመለኮቱ፡ ከአብ ጋራ የሚተካከል÷ኹሉ በእርሱ የኾነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሰማይ ካለው÷ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ ምንም ምን የኾነ የለም። ስለእኛ ስለሰዎች፡ እኛን ለማዳን፡ ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ ሥጋ÷ ከነፍሷ ነፍስ ነሥቶ፡ ፍጹም ሰውን ኾነ። በጴንጤናዊው

ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ መከራን ተቀበለ:: ተሰቀለ:: ሞተ:: ተቀበረ:: በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ:: በክብር በምስጋና ወደሰማይ ዐረገ:: በአባቱም ቀኝ፡ በዙፋኑ ተቀመጠ:: ዳግመኛም፡ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ፡ በምስጋና ይመለሳል:: ለመንግስቱም ፍጻሜ የለውም::

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን:: እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጥ፥ ከአብ የሠረፀና በነቢያት አድሮ የተናገረው፥ በሐዋርያት ላይ የወረደውና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ዓለሙን በጸጋው የሞላው፡ ቅድሱ የእውነት መንፈስ ነው:: ለእርሱም፡ ከአብና ከወልድ ጋራ፡ በአንድነት እንሰግድለታለን፤ እናመሰግነዋለንም::

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በአበው ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሐዋርያት ጉባኤ በፈጸማት፥ የእርሱ ሥጋና ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚቀርብባትና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎች በሚሰጡባት፡ በአንዲት ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እናምናለን::

ኃጢአት በሚሠረይባት በአንዲት ጥምቀት እናምናለን::

በሙታን ትንሣኤ፥ በሚመጣውም ሕይወት እናምናለን::

ለዘለዓለሙ አሜን::

## የኢትዮጵያውያን የቃል ኪዳን ጸሎት ደግሞ፤

እኛ ኢትዮጵያውያን፡ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች፡ የሰጣቸውን ቃል ኪዳናት፡ ጠብቆ በኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን እናምናለን::

አምላካችን፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ በመጀመሪያዉ የአበው ዘመን፡ በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፡ በኪዳነ ልቦና መሥርተው፤ ከዚያም በኖኀ ቀስተ ደመና፥ በመልከ ጼዴቅ ቁርባንና በአብርሃም ግርዛት፡ ገንብቶ አሳደገው፤ በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡ በሙሴ፡ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ፡ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የማክዳንና የእሥራኤላዊውን ንጉሥ፡ የሰለሞንን የዘር ሐረጎች በማዋሃድ፡ በኪዳነ ኦሪት አከናወነው፤ በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡ ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው ልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አጽንቶና ዘለዓማዊውን ዘውድ አቀዳጅቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው::ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ ቤተ ሕዝቧን ፣ ቤተ ክህነቷንና ቤተ ምልክናዋን፡ አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግስት እንደኾነች እናምናለን::

እርሱ፡ "ክርስቶስ" ተብሎ፡ እኛን "ክርስቲያን" ያሰኘን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ በቀደመው ዘመን፡ ምሳሌው ኾኖ በተገለጠው፡ በመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊነትና ሹመት፡ ከሴም፥ ከካምና ከያፌት ዘሮች ተወልዶ፡ የዘለዓለም ካህናችንና ንጉሣችን እንደኾነ እናምናለን::

እርሷ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ እኛን "ኢትዮጵያውያን" ያሰኘችን፡ ድንግል ማርያም፡ አምላክን በመውለዷ፡ አማናዊቷ የሕያዋን እናትና ዘለዓለማዊቷ ተቦተ ጽዮን ÷ የሰማይና የምድር ንግሥትም እንደኾነች እናምናለን፡፡

አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የኾነው፡ የቀስተ ደመና ምልክት፡ በኖኅ አማካኝነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው፡ የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን እንደኾነ እናምናለን፡፡

የቅዱስ ኪዳን ፍጻሜ ለኾነው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው፡ "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚለው፡ መለኮታዊ ቃልና ለድንግል ማርያም የተነገረው፡ "ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" የሚለው ትንቢታዊ ቃል፡ ከአምላካችን ያገኘነው፡ የዘለዓለም ማኅተማችን እንደኾነ እናምናለን፡፡

በቅዱስ ኪዳን ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር በመንፈስ፡ የመወለደን ክብር ስላገኘን፡ በዚህ በልጅነታችን፡ የእግዚአብሔር መንግስት ወራሾችና አገልጋዮች እንደኾንን እናምናለን፡፡ ይህን ልጅነታችንን አጽንተን ለመጠበቅ የመንግስቱ ወራሽነታችንን ለማረጋገጥና ንጹሕ አገልግሎታችንን ለመቀጠል፡ ኃጢአታችንን ዘወትር፡ በንስሐ እያጠራንና የክርስቶስን ሥጋና ደም እየተቀበልን መኖር እንዳለብን እናምናለን፡፡

የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በይፋ የሚገለጠውና ተለይቶ የሚታወቀው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ፍቅር ኾነን በምንፈጽመው፡ የኢትዮጵያዊነት ምግባራችን እንደኾነ እናምናለን፡፡

የቅዱስ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ በየልቦናችን ጽፎ ያስተማረን÷ ጠብቀነው እንድንኖር ያደረገም፡ እንደ ቃል ኪዳኑ፡ እግዚአብሔር እንደኾነ እናምናለን፡፡

ለዘለዓለሙ፤ አሜን፡፡

ሌላዉ አደራ የምላችሁ ጸሎታችሁ ትጠርም፣ ትርዘምም የምትጸልዩትን በማስተዋል እየተረዳችሁ ልተጸልዩ ይገባል እንጂ በዘልማድ የምታነበንቡ ከሆነ ላትጠቀሙበት ትችላላችሁ፡፡

ጸሎታችንን ወደ ፈጣሪ ስናቀርብ ሰይጣንን በምጣድ ላይ ጥደነዉ ከስር እሳት እያነደድንበትና እያቃጠልነዉ መሆኑን ልናስተዉል ይገባል፡፡ በተመስጦ ስንጸልይ ሰይጣን መሃል ለመሃል በተፋፋመ እሳት ዉስጥ እየነደደ መሆኑን ልናዉቅ ይገባል፡፡ አሳባችንን የሚሰርቅብን ከሆነ ግን ከቃጠሎዉ ለመዳን ሲል ዳር ዳሩን ብቻ እሳቱን እንደምንቆሰቁስበትና ፍሙ ሳይሆን ዳር ዳር ላይ የተቆሰቆሰዉ እሳት ብቻ መጠነኛ መለብለብ የሚደርስበት መሆኑን ልንረዳ ይገባል፡፡ ስለዚህ ጸሎታችንን በተመስጦ፣ ጾማችንን በትጋት፣ ስግደታንን በጽናት፣ በምናቀርብበት ጊዜ ሰይጣናት እጅግ ስለሚቃጠሉ ከእኛ ይርቃሉ፤ ኃይላቸዉ ስለሚዳከም

የእግዚአብሔር ጸጋ ይበዛልናል፤ ነፍሳችን በሥጋችን ላይ የበላይነትን ትጎናጸፋለች፤ በዚህም ምክንያት ራሳችንን እንገዛለን፤ ስሜታችንንም እንቆጣጠራለን፡፡ ዋናዉ መንፈሳዊነት መገለጫ የሆነዉ ራስን መግዛት ነዉና፤ ይህ ደግሞ የሚሆነዉ ነፍሳችን በሥጋችን ላይ የበላይነትን ስትጎናጸፍ ነዉ፡፡

ጾሙም ዋንኛ የሰይጣናት ድል መንሻና ራስን መግዣ መሳሪያ መሆኑን ተረድታችሁ ለዚህ ሥጋችሁ ሳትሳሱ ልትጾሙ ይገባል፡፡ ሥጋችሁ ሁል ጊዜ ያማረዉን የፈለገዉን መብላትና መጠጣት ነዉ የሚፈልገዉ፡፡ ነፍሳችሁ ደግሞ ሥጋችሁ እንደፈለገዉ ከሆነ ልትቆጣጠረዉና ልትመራዉ አቅምና ኃይል ያንሳታል፡፡ ስለዚህ ጾም ዋና የነፍሳችሁ መሳሪያ መሆኑን ልታዉቁ ይገባል፡፡ ጾሙንም ስትጀምሩ በመጀመሪ ከጥሉላት ምግብ ከሥጋዉ፣ ከቅቤዉ ፣ ከእንቁላሉ፣ ከወተቱ ..ወዘተ ከመሳሰሉት ተከልከሉ፡፡ ከዚያም ለተወሰነ ሰዐታት ካለመብልና ካለመጠጥ መቆየትን ልመዱ፡፡ ያኔ የጾሙ ጥቅም ስለሚገባችሁ ማንም ሳያዛችሁ በራሳችሁ ጊዜ የጾሙን ሰዐት ከእለት እለት እየጨመራችሁ ትሄዳላችሁ፡፡ « ጥቅሙን ስትረዱ ለምን ቀኑን ሙሉ አንጾምም?» ትላላችሁ እንጂ ሥጋችን ተጎዳ ደከመ ብላችሁ አትመረሩም፡፡ ጾሙንም ቢሆን ግብታዊ አይሁን፤ ሲያስፈልጋችሁ በጠዋት፣ ሲያስፈልጋችሁ ስድስት ሰዐት፣ ሲያስፈልገችሁ እስከ ምሽት አታድርጉ፡፡ ቀስ በቀስ የሚጨምር እንጂ አንዴ ወደ ላይ አንዴ ወደታች የሚዋዥቅ አጿጿም አትጹሙ፡፡

«ከሚገባዉ በላይ ጹሙ ከሚገባዉ በታች ጹሙ» የሚል አሳብ ቢመጣባችሁ፤ ያንን መንፈስ ተጠራጠሩት፡፡ ምክንያቱም ከልክ በላይ አጹሞ ለበሽታ ሊዳርጋችሁ ይችላል፡፡ ወይንም ከልክ ያነሰ አጹሞ ዋጋችሁን ሊያሳንስባችሁ ይችላል፡፡ ብዙ የጸለየና የጾሞ የበለጠ ጸጋ እንደሚያገኝ የታወቀ ነዉ፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ሲያሳስባችሁ ነዉ የትሩፋት ስራ መስራት ያለባችሁ እንጂ በሥጋና ደም ስሜታችሁ ከሆነ የግብታዊነት ስራ ይሆንና «ለምን አደረኩ» ብላችሁ ልትጸጸቱበትና ዋጋ ልታጡበት ትችላላችሁ፡፡ አንዳንዶች የበለጠ ጸጋ ለማግኘ ት ቤተክርስቲያኒቱ ካወጀችዉ ሰባቱ አጿማት በተጨማሪ በፈቃዳቸዉ የጽጌን ጾም የሚጾሙ አሉ፡፡ አንዳንዶች ደግሞ ከዓመት እስከ ዓመት የሚጾሙ አሉ፡፡ እንዲሁም ከለሰለሰ መብል ራሳቸዉን ለይተዉ በጥራጥሬ ብቻ የሚኖሩም ጻድቃን አሉ፡፡ የተለየ ጸጋ ታድሏቸዉ ካለመብል ለብዙ ጊዜ የሚቆዩ ጻድቃን አሉ፡፡ ታዲያ ይህ ሁሉ እግዚአብሔር ለፈቀደላቸዉ ነዉ እንጂ ለሁላችንም አይሆንልንም፡፡ ካለመብልና መጠጥ መኖር የሚችል ሰዉ የመመረጥን እድል ያገኘ ነዉ፡፡ እናንተ ግን በዓለም ዉስጥ ያላችሁ ናችሁና በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ስርዐት መሰረት ለመመላለስ ራሳችሁን አለማምዱ፤ በእምነቷና በስርዐቷ ኑሩ፡፡

ስግደቱንም ቢሆን በዘወትር ጸሎት ዉስጥ «እሰግድ ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ሶስት ጊዜ በል፤ እሰግድ ለእግዝትነ ማርያም፣ እሰግድ ለመስቀለ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ» የሚል አለና እንዲሁም በተለያዩ ጸሎት መጽሐፍት ላይ ስለስግደት ስታነቡ በመስገድ በዚያ ራሳችሁን አለማምዱ:: ከዚያ በኋላ ደግሞ እንደተሰጣችሁ ጸጋና አቅም ለአምላካችሁ መስገድ ትችላላችሁ:: ባጠቃላይ ስለ ጸሎቱ ሆነ ጾሙ እንዲሁም ስግደቱ ያነሳሁባችሁ በግብታዊነት ስሜት እንዳትመላለሱና ወረተኛ ሕይወት እንዳትይዙ፣ ራሳችሁን በመግዛት እንደተሰጣችሁ ጸጋ ብቻ እንድትኖሩ፣ ያልተሰጣችሁን ጸጋ በራሳችሁ ኃይልና ብልጠት ለማግኘት ከሄዳችሁ ፈተና ሊያይልባችሁና ልትሰናከሉ እንደምትችሉ እንድታዉቁ ለማሳሰብ ፈልጌ ነዉ እንጂ ለወደፊት በየሰንበት ትምህርት ቤቱና በአጫጭር ስለጠናዎች እንዲሁም ስብከቶችና ትምህርቶች፣ ከመጽሐፍት፣ እንዲሁም ከመምህራንና ሊቃዉንት ስለ እምነትና ስርዐት በሚገባ እንደምትማሩ አምናለሁ::

በዚሁ አጋጣሚ ልነግራችሁ የምፈልገዉ በአንዳንድ የጸሎት ሆነ የምስጋና እንዲሁም የእዉቀት መጽሐፍቶች ዉስጥ በመጀመሪያዉ ወይንም በመጨረሻዉ ወይንም በመሀልም ሊሆን ይችላል አንዳንድ ሰዎች በክፋት ሳይሆን በየዋህነት ከንቱ ሥጋዊ ጥበብ በመጠበብ በስንዴ ዉስጥ እንክርዳድ ዘርተዉ ብታገኙ በቅንነት አይታችሁ በስንዴዉ ብቻ ተጠቀሙ:: ከዚያ ዉጭ ደግሞ አንዳንድ የአገር ዉስጥና የዉጭ አገር ሰዎች ሆን ብለዉ በስንዴ ዉስጥ ቤተክርስቲያኗንና ብቸኛይቱን የሕይወት መንገድ ተዋህዶ ሃይማኖትን ለማስነቀፍና ለማስተቸት የዘሩት እንክርዳድ አለና እግዚአብሔር እዉነተኛ እንደራሴዎቹን በእዉነተኛ ወንበር ላይ ሲያስቀምጥ ያኔ በግልጽ እንክርዳዱ ይለያል:: እስከዛዉ ድረስ ግን የራሳችሁን አካሄድ ሳትሄዱ የሚቀርብላችሁን ሁሉ በእዉነትና በመንፈስ እየመረመራችሁ ስንዴዉን ብቻ በልባችሁ እያኖሯችሁ እንክርዳዱን እንደእንክርዳድነቱ አይታችሁ ከልባችሁ አለማኖር:: ከዚያ ዉጭ በራሳችሁ ሥጋና ደም ስሜት « ይህ ስንዴ ነዉ፤ ይህ እንክርዳድ ነዉ::» የምትሉ ከሆነ ከዚህ ቀደም ብዙዎች ተሰናክለዉ በትዕቢትና በዐመጻ ልብ ከሕይወት መንገድ ወተዋል፤ ከእግዚአብሔር ጸጋ ተለይተዋል፤ ሰይጣናት በጎሊቻቸዉ እንዲፈነጩባቸዉ ፈቅደዉላቸዉ የሕይወት መንገድን እስከማጥላላትና መካድ እንዲሁም ቅዱሳንና ጻድቃንን እስከመናቅና እስከመሳደብ ደርሰዋል::

ባጠቃላይ እኔም ከሳብኩት በላይ እናንተም ከፈለጋችሁት በላይ እግዚአበሔር እንዳስተማረንና እንደተናገረን አምናለሁ:: ለወደፊት ከጥምቀት በኋላ የሚሰጣችሁን የክርስትና ስማችሁን እንድትልኩልኝ በማሳሰብ ምላሼን በዚህ ላይ እደመድማለሁ:: አቡነ ዘበሰማያት እንበል::» በማለት ንግግራቸዉን የቋጩ ሲሆን፤ እግዚአብሔር የመረጣቸዉ ከአገሪቱ የተለያየ

ቦታዎችና ከዉጭም አገራት የመጡት የእስልምና እምነት ተከታዮች የነበሩት ሴቶች በተሰጣቸዉ ምላሽ ተደስተዉ እንዳንዶቹ « እግዚአብሔር ይስጥልን፤ ቸሩመድኃኔዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ይስጥልን፤ እመ ብርሃን ወላዲተ አምላክ ድንግል ማርያም ትስጥልን» ሲሉ አንዳንዶቹ ደግሞ« አመሰግናሉ፣ ታንኪዩ፣ አላህ ይስጥልኝ:» በማለት የመረቁና ያመሰገኑ ሲሆን፤

እኛ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት አገልጋይ የሆኑት አባት « አንዴ ይቅርታ፤ ከመበተናችሁ በፊት አንዲት ማሳሰቢያ አለችኝ:: ይኸዉም በዘልማድ እኛ አገልጋዮች ሆን ምዕመናን እግዚአብሔር ስሙ እንዳይጠራና እንዳይመሰገን አድርገናል:: ሁሉን የሚያደርግ እግዚአብሔር ነዉ:: አሁንም ምላሽ የሰጣችሁ እርሱ ነዉ እንጂ እኔ አይደለሁም:: እኔ መተላላፊያ መሳሪያ ነኝ እንጂ በእኔ አንደበት የተናገራችሁ እርሱ ርኅሩኅና አፍቃሪ አምላካችሁ ነዉ:: ስለዚህ ዛሬም ሆነ ለወደፊት ለሚደረግላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን ነዉ ማመስገን ያለባችሁ እንጂ ደካማ ፍጡሩን እኔን ሆነ መሰሎቼን አይደለም:: ይህን ልናገራችሁ የቻልኩት አንዳንዶቻችሁ የምጠቀምበትን ምርቃት ያበረከታችሁልኝ ሲሆን የተወሰናችሁት ደግሞ ከእግዚአብሔር ዋጋ የሚያሳጣኝን ንግግር ነዉ የተናገራችሁት:: ይኸዉም «አመሰግናለሁ፣ ታንኪዉ» ስትሉ ለኔ አንዳች የሚጠቅመኝ ሳይሆን የእግዚአብሔርን ምስጋና በመቀበሌ የምጎዳበት ነዉ:: ስለዚህ ለኔ የሚጠቅመኝ «እግዚአብሔር ጤናዉንና ጽናቱን ይስጥህ፤ ለሰማያዊ መንግስትና ክብር ያብቃህ፤ ማስተዉሉና ጥበቡን ይስጥህ፤ የቅዱሳን በረከታቸዉንና ጸጋቸዉን በመቶ እጥፍ ያድልህ:: እመ አምላክ ፍቅሯን ጣዕሟን ታሳድርብህ፤ አንተንም ቤተሰብህንም ትጠብቅልህ» ብትሉኝ ነዉ:: «አላህ» ይስጥልኛ ያላችሁት ደግሞ አላህ ማን እንደሆነ በደንብ የተረዳችሁ ይመስለኛልና ለወደፊት የእዉነተኛ አምላካችሁን ስም እንደምትጠሩ ተስፋ አደርጋለሁ::

እንግዲህ እናቶቼ፣ እህቶቼ፣ ልጆቼ፤ እግዚአብሔር ያናገረኝን ተናግሬያለሁ፤ እናንተም እንዳስተዋላችሁ አምናለሁ:: እንባዬን በግድ እየተቆጣተርኩት ነዉ እንጂ እያነባዉ ተናግሬያችሁ ቢሆን ደስ ባለኝ፤ ነገር ግን ሌላ ስሜት ዉስጥ ትገባላችሁ በማለት ነዉ የግዴን የከለከልኩት:: ለኔ ባነባዉ የዉስጤ ኀዘን ይቀልልኛል:: ስታዩኝም የተመቸኝ የደላኝ ይመስላችኋል:: ኅሊናዩ ስለ እዉነት ለዓመታት ቆስሏል፤ ደምቷል፤ አንዳንዴም የማየዉንና የምሰማዉን መቋቋም እያቃተኝ ምንም ማድረግ ባለመቻሌ «በዚህ ምድር መወለድ አልነበረብኝም» እያልኩ አማርራለሁ:: ለሰዉ «ኀዘንተኛና መከረኛ ሰዉ ነኝ» ብል ማንም አያምነኝም:: በዚህች ምድር እኔ አጎደልኩበት እንጂ እግዚአብሔር አንዳች ነገር አላጎደለብኝም:: በዓለም አንዳች የምመኘዉ የግል ብልጽግና፣ ስልጣን፣ ክብር የለም:: ምድራዊ

ቆይታዬንም የምፈልገዉ ያን ምስኪን አባትና አምላክ ራቁቱን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ፍቅሩን ለአዳም ዘር የገለጸዉን በአራቱም ማዕዘን እንዲመለክ ፣ እንዲመሰገን ፣ እንዲገን ለማድረግ፤ እንዲሁም ከሰዉ ዘሮች ድኅነት ጋር በምንም መልኩ ልተለይ የማትችለዉን የእርሱ የእግዚአብሔር እናት ለመሆን የበቃችዉን የመዳኛ ምክንያታችን የሆነችዉና አሁንም በሰማያት ከብራና ገና መኖር ስትችል የኛ የአደራ ልጆቿ ጥፋትና ወድቀት አላስችል እያላት የእግዚአብሔርን ቁጣ በማብረድና ምሕረትን በመጠየቅ ለዘመናት በኀዘን ላይ ያለችዉን እመ አምላክ ድንግል ማርያም የሰማይና የምድር ንግሥትን እንደ ልጇና አምላኳ በአራቱም ማዕዘን እንድትመሰገንና እንድትገን ለማድረግ ነዉ፡፡ እንዲሁም በኃላፊነት ተንከባክቤ የማሳድጋቸዉ ችግኞች ስለተሰጡኝ እነሱን ለመልካም ፍሬ ለማብቃት ነዉ የዚህች ምድራዊ ዘመኔን የምፈልገዉ እንጂ በዚህች በከፋችና በከረፋች ዓለም ዉስጥ አንዲት ቀንን መቆየት አልፈልግም፡፡

ከዚህ ዓለም በሥጋ ሞት ተለይተን ወደተዘጋጀልን ቦታ ስንሄድ እንደ ምኞታችንና ፍላጎታችን የሚሆንልን ነገር የለምና ለወደፊት እንዳይቆጨን በዚህች ምድር እያለን ለወገኖቻችን ለአዳም ዘር ለነፍሳቸዉም ለሥጋቸዉም የሚጠቅም ነገር ሰርተን መሄድ ይኖርብናል እንጂ፤ ነፍሳችን ከሥጋዋ ከተለየች በኋላ ዳግም የመወለድና በዚህች ምድር የመመላለስ እድል ስለሌላት ስለወገኖቻችን ከማሰብና ምህረት ከመጠየቅ ዉጭ እኛ ወደ ምድር ተመልሰን « ንስሐ ግቡ፤ ከአምላካችሁ ታረቁ፤ የእግዚአብሔር እዉነት ይህ ነዉ፤ የባሰ ስቃይና መከራ ቦታ ስላለ ከኃጢአት ተከልከሉ፤ የሚጠብቃችሁ መልካም ስፍራ ተዘጋጅቶላችኋልና በተቀደሰ ሕይወት ተመላለሱ.. ወዘተ» ብለን የማስተማርና ስለ እዉነት የመመስከር እድል አናገኝም፡፡ አሁን በሕይወተ ሥጋ እያለን ነዉ የፈለግነዉን ማድረግና ስለ እዉነት መመስከር የምንችለዉ፡፡

ብቻ እናንተ « አንተ እዉነተኛ ፈጣሪ አምላክ! እኛ በራሳችን እዉቀት አንገድብህም፤ እዉነትን ብቻ እንድታሳዉቀን ነዉ የምንፈልገዉና በሕይወት መንገድ ዉስጥ ለመመላለስ የወሰነዉ፡፡ ስለዚህ እንደ እዉነተኛ ፈጣሪነትህና አባትነትህ እዉነታዉን ገልጸህልንና ማስተዋሉን ሰተኽን እንደ ቃልህ ሆነን እንድንኖር አድርገን፡፡ የእኛ ጸሎትና ምኞት አንተን በእዉነትና በመንፈስ አምልከን ፣ በእዉነት ኖረን በመንግስትህ ሕያዉ ሆነን ከአንተ ከእዉነተኛዉ አባታችን ጋር መኖር ነዉ ፍላጎታችን» በማለት አጥብቃችሁ ለምኑት፡፡ እርሱ ከእኛ በላይ ለእኛ ያስባልና በቅንነት፣ በየዋህት፣ በእዉነት ፣ በመልካም ሕይወት ከተመላለስን እርሱ እዉነተኛ አምላካችንንና አባታችንን በሚገባን መልኩ በዚህ ምድር ዉስጥም እያለን እናዉቀዋለን፤ እናስተዉለዋለን፡፡ እኛ ሙሉ ፈቃደኞች ከሆንና እንደ ፈቃዱ ከተመላለስን

ከእርሱ ጋርም ቃል በቃል መነጋገር እንድንችል ፈቃዱ ነዉ፡፡ ግንኙነታችንም እንደ ጌታና ባሪያ ሳይሆን የሚፈልገዉ እንደ አባትና ልጅ ግንኙነት እንዲኖረን ነዉ የሚፈልገዉ፡፡» በማለት ለሴቶቹ ማሳሰቢያ ሰተዉ አሰናብተዋቸዋል፡፡

እኔ የጨለማዉ ገዥ በሴቶቹም አሳብና አቋም እንዲሁም በእኛ አባት ትምህርትና ምክር እጅግ ስለተበሳጨዉና ስለተናደድኩ በሴቶቹ ባሎቻቸዉና ቤተሰባቸዉ ላይ ክፉ ምክር መክሬ እንዲሁም በኢትዮጵያ ዉስጥ ባሉት የተለያዩ ሃይማኖቶች መሪዎችና በአንዳንድ አስመሳይ አገልጋይና አስመሳይ ምእመን ላይ አድሬ፣ እንዲሁም በመንግስት ካድሬዎችና ባለስልጣናት ላይ ነግሼ እኛን አባት ያላደረጉትንና ያልፈጸሙትን ወንጀል ከላይ የተጠቀሱት ሰዎችና አካላት በጣምራ አንድነት ፈጥረዉ በተቀነባባረ መረጃ እኛ አባት « ሚስቶቻችንን አባልገዋል፣ አስክደዋል፣ ሃይማኖተ በሃይማኖት ላይ አነሳስተዋል፣ የሃይማኖት አባቶችን ሰድበዋል፣ መንግስትን ተቃዉመዋል፣ ሕገ መንግስቱን ጥሰዉ ሽብርና ሁከት ፈጥረዋል.. ወዘተ» በማለት ባጠቃላይ ሲታይ እንኳን ለአንድ ምስኪን አባት አይደለም ለአንድ አገር መንግስት የማይሰጠዉን የዉንጀላ ክስ አስመስርቼ የሞት ፍርድ ያስፈረድኩባቸዉ ቢሆንም፤ ለምልካሙ ዘመን ለኢትዮጵያ ትንሳኤ ታጭተዋል መሰለኝ ዋናዉ ባለቤቱ እግዚአብሔር እንዲሞቱ አልፈቀደምና ይኸዉ እስከ አሁን ድረስ ፍርዱ ተፈጻሚነት ሳይገኝ በእንጥልጥል ላይ ይገኛል፡፡ እኔ ግን እስከ አሁን ድረስ የመለሱት መልስና ትምህርት እያብገነገነኝ እገኛ ለሁ፤ የሞታቸዉንም ቀን በናፍቆት እየተጠባበኩ እገኛለሁ፡፡» **ይላል ሐሰተኛዉና የሐሰት አባት የሆነዉ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከጭፍሮቹ ሰይጣናት ጋር በመሆን፡፡**

## ምእራፍ ሁለት

« በዓለም ዉስጥ የተለያዩ አገራት መሪዎች በአገራቸዉ ዉስጥ ያሉትን የተለያዩ ሃይማኖቶች እምነትና እንዲሁም ባህላዊ አምልኮ የሚፈጽሙትን ጭምር የሚወክሉ ከእያንዳንዱ ሶስት ሶስት ሰዉ አዘጋጅተዉ ልዩ ስሙ ጻድቃኔ ወደ ተባለ ቦታ የላኩና ከ195 አገራት በላይ እያንዳንዱን የሚያምኑበትን እምነት የሚወክሉ ሰዎች ለሰባት ቀን ሱባኤ እንዲገቡ አድርገዋል። ዋናዉ ዓላማቸዉም የዓለም መንግስታት በመደበኛዉ ስብሰባቸዉ « እግዚአብሔር አለ ከተባለ ሊኖር የሚችለዉ አንድ እግዚአብሔርና አንድ ሃይማኖት መሆን ሲገባዉ በዓለም ዉስጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠር አምላክና ሃይማኖቶች ስለተፈጠሩ ሕዝቡም በዚህ ግራ ስለተጋባ እዉነተኛዉ አምላክና እምነት እንዲለይ የኦርቶዶክሱም፣ የተዋህዶዉም፣ የካቶሊኩም፣ የፕሮቴስታንቱም ባጠቃላይ በክርስትና ስም የሚጠራዉ ሁሉ እንዲሁም የይሁዲዉም፣ የእስላሙም፣ የቡዲሂዝሙም፣ የሂንዱዝሙም፣ የተለያዩ የባህላዊዉም፣ የጨሌዉም፣ የጣዖታቱም፣ ባጠቃለይ ከእምነት ጋር የተያያዘዉ ሁሉ ሶስት ሶስት ሰዉ ወክለዉ በጋራ ሱባኤ በመግባት እዉነተኛዉን አምላክና እዉነተኛዉ እምነት እንዲገለጽላቸዉ እንዲጠይቁ፤ ያለበለዚያ ደግሞ «እኛ ለጥቅማችን፣ ለስልጣናችን፣ ለክብራችን፣ ለዝናችን ስንል ነዉ አምላክ እያልን ሕዝቡን የምናደናግረዉና የምናስፈራራዉ እንጂ አምላክ ፈጣሪ የሚባል ነገር የለም።» ብለዉ በግልጽ ለዓለም ሕዝብ እንዲያሳዉቁ» ተብሎ በመወሰኑ ምክንያት ነዉ ከሁሉም እምነት የተወጣጣ ቡድን ወደ ስፍራዉ የተላከዉ።

የሁሉም አገራትና እምነት ተወካዮች ምንም እንኳን አብዛኛዉ ተወካይ የላመዉንና የሚጥመዉን ምግብ የለመደ ቢሆንም በሱባኤዉ ቦታ የሚፈቀደዉ ቆሎና በሶ ብቻ ስለነበረ ካለፍላጎታቸዉና ምርጫቸዉ በፈቃዳቸዉ ነዉና የመጡት እየተሰቀቁና እያጉረመረሙም ቢሆን ለሰባት ቀን በሱባኤ ሊቆዩ ችለዋል። በመጨረሻም በተባበሩት መንግስታት ስብሰባ ማእከል ተገኝተዉ የተገለጸላቸዉን በዝርዝር አቅርበዋል።

በመጀመሪያ እንዲያቀርቡ እድል የተሰጣቸዉ ከሰሜንና ከደቡብ አሜሪካ አገራት ተወክለዉ የሄዱት ሲሆን፤ እነሱም በጋራ በመሆን « በእዉነቱ ነፍሳችን የምትፈልገዉን መብልና መጠጥ ማግኘት አለመቻሏ ለጊዜዉ ቅር ብንሰኝም በመጨረሻ ግን የተሰበረ ልቦናና ከልብ የማናመልከዉ እዉነተኛ አምላካችን በደላችንና ኃጢአታችንን ሳይመለከት፤ « ልጆቼ በዚህች በተቀደሰች አገርና ቦታ ላይ ተገኝታችሁ እኔን አምላካችሁንና እዉነተኛ አባታችሁን ደጅ ልትጠኑና እዉነተኛዉ ሃይማኖት እንዲገለጽላችሁ በጋራ በመገኘታችሁ ይህን ፍላጎታችሁንና ድካማችሁን ተመልክቼ ነዉ እዉነተኛዉን ሃይማኖት ልገልጽላችሁ ፈቃዴ ሆኖ ወደ እናንተ በተለየ ሁኔታ የመጣሁት። እኔ በነጻነት የምገዛ አምላክ ነኝና እዉነቱን

እነግራችኋለሁ እንጂ በዚያ እምነት ዉስጥ እንድትኖሩ አላስገድዳችሁም:: ነገር ግን እዉነቱን እየነገርኳችሁ ባትኖሩበትና እዉነትን ብትክዱ ከማንም በላይ የባሰ ፍርድ እንደሚጠብቃችሁ ልታዉቁ ይገባል:: ምክንያቱም ይህን እድል ብዙዎች አላገኙም:: እናንተ ግን ሳይገባችሁ እኔን ፈጣሪያችሁን በግልጽ አዉቃችኋል:: ቃሌንም ሰምታችኋል::

በዓለም ዉስጥ የተለያዩ አይነት እምነት መኖሩን ባዉቅም ያ እምነታቸዉ እንደሚያዛቸዉ የሚኖሩ ግን እጅግ ጥቂቶች ብቻ ናቸዉ:: ሁሉም ማለት ይቻላል ለይስሙላ ነዉ ሃይማኖት አለኝ እምነት አለኝ የሚለዉ እንጂ የያዘዉን እምነት እንኳ በአግባቡ አያዉቅም፤ የሚባለዉንም አይፈጽምም:: በዘልማድ ነዉ ትዉልዱ የሚመላለሰዉ:: በተለይ በክርስትና ስም የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ እምነት ድርጅቶች ዉስጥ ያሉ የሃይማኖት አባቶችና አማኞች ከሁሉ በላይ የባሰዉ ፍርድ ነዉ የሚጠብቃቸዉ:: ምክንያቱም በመስቀል ላያ የተከፈለላቸዉን ዋጋ እያወቁ ከንቱ በማድረጋቸዉና በስሙ በመነገዳቸዉ ጭምር ነዉ:: እንደ ቃሉና ትዕዛዙ አይኖሩም:: ይልቁኑ በቃሉ ያስመስሉበታል፤ ይነግዱበታል፤ ያዘፍኑበታል ያስጨፍሩበታል፤ ብቻ የማያደረጉበት ነገር የለም:: በመሆኑም ከሌሎች እምነት ተከታዮች ይልቅ ብዙ ፍሬ ሲጠበቅባቸዉ እንኳን መልካም ፍሬ ሊያፈሩ ቀርቶ ሌላዉን ላለማሰናከል እንኳ ጥናቃቄ አያደርጉም:: የሚያምነዉንም የማያምነዉንም ነዉ የሚያሰናክሉት:: ለዚህም ነዉ የባሰ ፍርድ ይጠብቃቸዋል ያልኩት::

ሌሎቹ በእስልምና፣ በቡዲሂዝም፣ ሂንዱዚም፣.. ወዘተ እምነት የሚመላለሱት ከወላጆቻቸዉ በወረሱት እምነት ሲሆን፤ ብዙዎቹ እምነቱ የሚያዛቸዉን ይፈጽማሉ:: ምንም እንኳን ለሰማያዊዉ ሕያዉ ሕይወት የሚያበቃ እምነት ባይኖራቸዉም፣ ከእዉነተኛዉ ፍረድ ባያመልጡም፤ ምክንያቱም በአራቱም ማዕዘን ስሜ ሲጠራ ይሰማሉና « በመስቀል ላይ ምን ዋጋ ተከፈለ?» ብለዉ መጠየቅ ሲገባቸዉ ለመጠየቅ ሆነ ለመስማት ፈቃደኛ ባለመሆናቸዉ ነዉ:: ነገር ግን አምነዉ ከሚያምጹት አስመሳይ አገልጋዮችና አማኞች ይልቅ ፍርዱ ይቀልላቸዋል:: ሌሎቹ በጨሌዉ ፣ በጣኦትና ባዕድ አምልኮ የሚመላለሱ፣ በየወንዛወንዙና ተራራ እንዲሁም ምናምንቴ ቦታ ላይ አምልኮትና ርኩሰትን የሚፈጽሙ፤ በግልጽ ዲያብሎስን እያመለኩ ስለሆነ እኔንም እጅግ ስላስቆጡኝ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ የሚጠብቃቸዉ ፍርድ ይጠብቃቸዋል::

ባጠቃላይ ከኔ ከእዉነተኛዉ አምላክ አምልኮትና ትዕዛዝ ስርዐት ዉጭ የሚመላለሱ ሰዎች እንደ ምድራዊ የኃጢአት ተግባራቸዉ ደረጃ ፍርድ ይጠብቃቸዋል:: እጅግ የከፋ ዐመጻና ክህደት እንዲሁም ርኩሰት የፈጸሙና የሚፈጽሙ ሰዎች እጅግ ሊቋቋሙት

የማይችሉት ቅጣት ነዉ የሚጠብቃቸዉ:: አነስተኛ ኃጢአት የፈጸሙ ደግሙ እንደደረጃዉ አነስተኛ ሊቋቋሙት የሚችሉት ቅጣት ነዉ የሚጠብቃቸዉ:: ለእያንዳንዱ እንደ ስራዉና እምነቱ ነዉ የሚፈረድለትና የሚፈረድበት እንጂ በስም ክርስቲያን በመሆን ብቻ የሚድንና ከቅጣት የሚያመልጥ የለም:: በኔ ዘንድ አንዳች አድሎ የለም:: ፍትሐዊ ፍርድ ነዉ የምሰጠዉ:: እዉነትን እያወቀ በእዉነት የማይኖር ከሁሉ የባሰ ቅጣት ነዉ የሚጠብቀዉ:: የሰዉ ዘሮች ሆኑ ሰይጣናት የሚቀጡበት ቦታ አንድ ገሃነመ እሳት፣ እሳቱ የማይጠፋ ትሉ የማያንቀላፋበት ቦታ አንድ ቢሆንም፤ የሚሰማቸዉ የቅጣቱ ስሜት ግን እንደ ዐመጻቸዉ ደረጃ ይለያያል::

እናንተ ሕይወትንና ድኅነትን ፈልጋችሁ፣ እዉነትንም ለዓለም ሕዝብ ልታስተዋዉቁ እምነታችሁን ወክላችሁ ነዉ የመጣችሁት:: በአገሮቻችሁ የሚፈጸመዉ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር እጅግ በመክፋቱ ንስሐ ካልገባችሁና እጃችሁን ለእኔ ለአምላካችሁ ካልሰጣችሁ እንደ ኖኅ ዘመን ያላሰባችሁት ጥፋት ይመጣባችኋል:: እናንተ ራሳችሁ «እምነት አለን፤ አገልጋይ ነን፤» ትላላችሁ እንጂ አንዳች መልካም ምግባር የላችሁም:: በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት ፣ በዘፈን ፣ በዳንኪራ፣ በጥንቆላ፣ በመተት፣ በአስማት፣ በስካር፣ በጥላቻ፣ በቂም በቀል፣ በግድያ፣ በስርቆት፣ በዘረኝነት፣ በጎጠኝነት፣ በዝሙት፣ በመዳራት፣ በሴሰኝነት ፣ በግብረ ሰዶም፣ በጣዖትና በባዕድ አምልኮ፣ ብቻ ምኑ ተዘርዝሮ ያልቃል ለነፍሳችሁ ቀርቶ ለሥጋችሁ አንዳች በማይጠቅም በሚያጎሳቁላችሁና በሚጎዳችሁ ሕይወት ዉስጥ ትመላለሳላችሁ:: ምርጫችሁን በዉል ያልተረዳችሁ የሚያመዛዝናና የሚያገናዝብ ኅሊና(ሕያዉ ነፍስ) እያላችሁ የምትሰሩትን የማታዉቁ፣ በደመ ነፍስ የምትመላለሱ፣ የምትወጡ፣ የምትወርዱ ናችሁ:: ደግሞ በዚህ ሕይወት ዉስጥ እየተመላለሳችሁ «የሃይማኖት አባት ነን:: የእግዚአብሔር እንደራሴ ነን:: የሕዝቡ እረኛ ጠባቂ ነን» ትላላችሁ:: እግዚአብሔር መምሰልን የተላበሰች ኅሊናችሁን (ነፍሳችሁን) ማፈሪያና ያበደ አእምሮ እንዳደረጋችኋት ልትረዱ ይገባችኋል::

በብሉይ ዘመንና በሐዲስ ዘመን የተፈጸመዉን ድርጊት ሆነ ትምህርት በሚገባ አንብባችሁ ተረዱ:: ለእናንተ የአዳም ዘር ምን ያልተደረገላችሁ ነገር አለ!? ምን ያልተከፈለላችሁ ዋጋ አለ!? እንደዉ ሌላዉን ባታስተዉሉ እንኳ ማደሪያ ቦታ ጠፍቶ በከብቶች በረት ዉስጥ የተወለደዉን፣ ከዚያም እንደ አቅመ ቢስ ሄሮድስን ሸሽቶ ከእናቱ ከድንግል ማርያምና ከአሳዳጊዉ ዮሴፍ ጋር በረሀ ለበረሀ የተንከራተተዉን፣ እንደ ሰዉ ጥቂት በጥቂቱ ያደገዉንና የሰዎችን አኗኗር የኖረዉን፣ በተወለደዉ ሥጋ ሰላሳ አመት ሲሞላዉ የእዉነትን

ቃል ለዓለም የገለጸዉንና ያስተማረዉን፣ የተለያዩ በሽተኞችን የፈወሰዉና ያጽናናዉን፣ የለያዩ ተአምራትን ያደረገዉን፣ በመጨረሻም እዉነትን በመናገሩና በማስተማሩ ክፉ ቅናት ያደረባቸዉ «የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነን፤ ሕጉና ትዕዛዙን እንጠብቃለን፤ እናስጠብቃለን፡፡» የሚሉ አስመሳይ አገልጋዮች የነበሩ የአይሁድ ካህናት፣ ጸሐፍት፣ ፈሪሳዉያን በሐሰት ወንጅለዉት የተገረፈዉን፣ የተሰደበዉን፣ የተተፋበትን ፣ የተደበደበዉን፣ የተሰቃየዉን፣ የተዘበተበትን ፣ ራቁቱን ያደረጉትን ፣ በመጨረሻም በመስቀል ላይ የሰቀሉትን ፣ ባለቀ ሰዐት ላይ እንኳ በመስቀል ላይ ሆኖ «ተጠማሁ እባካችሁ የምጠጣዉን ዉሃ ስጡኝ?» ሲል እንኳ፤ ስንት የሚጣፍጠዉን መብልና መጠጥ የሰጠ፤ ተጨክኖበት መራራ ሐሞት የቀረበለትን ፣ ባጠቃላይ የተለያዩ ጸዋትዎ መከራ የተቀበለዉን ኢየሱስ ክርስቶስን ታዉቁታላችሁ ወይ? ማንነቱንስ አስተዉላችኋል ወይ? እስቲ ምን ያላደረገላችሁ ነገር አለ? ምን ያልሆነላችሁ አለ? ምን ያህል ፍቅሩን እንደገለጸላችሁ አስተዉላችኋልን? ምን ያህል እንደለመናችሁና እንደተለማመጣችሁ ተረድታችኋልን? ምን ያህል እንዳከበራችሁና እንደሳሳላችሁ ተገንዝባችኋልን? ብቻ እንደ እናንተ እንባ ቢኖረኝ <u>አሁንም ባነባዉላችሁ</u> በወደድኩ!

ያ ይህን ሁሉ ያደረገላችሁ፤ ሕይወት የሚሆናችሁን ሥጋዉን ቆርሶ ደሙስ አፍሶ ራሱን በመስቀል ላይ ሰዉቶ «ሥጋዬን ብሉ፤ ደሜንም ጠጡ፤ የዘላለም ሕይወትን ታገኛ ላችሁ፤ በሰማያዊ መንግስትም ዉስጥ ሕያዉ ሆናችዉ ትኖራላችሁ፡፡» ያለዉ እኔ አምላካችሁ ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔር ነኝ፡፡ **<u>እኔ ይህን ያህል እያፈቀርኳችሁና እየፈለኳችሁ እኔን የሚያፈቅረኝና የሚፈልገኝ ሰዉ አጣሁ፡፡</u>** ዝም ብዬ እንዳልምራችሁ ባሕርዬ ይገድበኛል፤ ይልቁኑ ፍርዴ እጅግ ጥብቅና ፍትሐዊ ነዉ፡፡ ዝም ብም ብዬ እንዳልፈርድባችሁ ባሕርዬ ይገድበኛል፤ ይልቁኑ ርኅራኄና ፍቅሬ እጅግ ያይላል፡፡ **<u>እኔም እንደ ሌሎቹ ሕያዋን ፍጥረቶቼ ቅዱሳንና ጻድቃን በእናንተ ኀዘተኛ ነኝ፡፡</u>** ከፍርድ ቀን በኋላ ግን ማንም ሰዉ ሆነ ሰይጣናት በእዉነተኞች፣ በቅኖችና በየዋሃን ላይ አንዳች ጥቃት ሆነ ጉዳት አያደርሱም፡፡ የሚያስቆጣኝንም ተግባር አይፈጽሙም፡፡ እንደ ዐመጻቸዉ ደረጃ ነጻነታቸዉ ተገድቦ በአንድ ቦታ ፍዳቸዉን ይቀበላሉ፡፡ እናንተ ግን ካዳችሁኝ፣ አስካዳችሁኝ፣ ሰደባችሁኝ፣ አሰደባችሁኝ፣ አዋረዳችሁኝ፡፡ ይኸዉም ስትፈልጉ « ሐሳች ነዉ፡፡» ስትፈልጉ «ተራ ሰዉ ነዉ፡፡» ስትፈልጉ « ነብይ ነዉ፡፡» ስትፈልጉ «አማላጅ ነዉ፡፡» ስትፈልጉ « ፍጡር ነዉ፡፡» ስትፈልጉ « አንድ ኢየሱስ ነዉ፤ አብ መንፈስ ቅዱስ የሚባሉ የሉም፡፡» .. ወዘተ እያላችሁ በሞትና በክህደት ሕይወት ትመላለሳላችሁ፡፡ ታዲያ ታላቅ ዋጋ የከፈልኩላችሁ አምላክ ስለ ዐመጻና ክህደት ሕይወታችሁ ከገሃነመ እሳት በላይ መቅጫ ቦታ አዘጋጅቼ ብቀጣችሁ አያንሳችሁምን!

ከእኔ ይልቅ፤ሌት ተቀን የሚፈታተናችሁንና የሚያስቃያችሁን፣ የሚቀጠቅጣችሁንና የሚያጎሳቁላችሁን ዲያብሎስንና ጭፍሮቹን ሰይጣናትን መምረጣችሁና ፈቃዳቸዉን ለመፈጸምና ለማስፈጸም መትጋታችሁ ስለ ምን ይሆን!? ይህ ምድራዊ ሕይወታችሁ ሕይወት ሆነና ነዉ ሌት ተቀን በዐመጻና በርኩሰት ሕይወት የምትመላለሱት? እኔን በሚያስቆጣ ተግባርና ዲያብሎስን በሚያስደስት ሕይወት የምትኖሩት? ይህ ሕይወት ሆነና ነዉ እርስ በእርስ የምትጣሉትና በስግብግብነት ሕይወት የምትመላለሱት? በስስት ሕይወት የምትኖሩት? ይህ ምድራዊ ሕይወታችሁ ሕይወት ሆነና ነዉ በቀለም፣ በዘር፣ በነገድ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት ተለያይታችሁና ተባድናችሁ በዲያብሎስ ስርዐት በመመራት በጦርነት ፣ በግድያ፣ በግፍ፣ በጭቆና፣ በአድሎና በበደል ሕይወት የምትኖሩት?

ማስተዋሉን አጣችሁ እንጂ በዚህች ምድር አጭር ዘመን ቆይታችሁ እንኳን በከፋና በከረፋ ሕይወት ዉስጥ ልትመላለሱ ቀርቶ አንዲት ቀን እንኳ ሊዋልባትና ሊታደርባት የማትመረጥ መኖሪያ ናት:: ነገር ግን ይህች ምድር ቀድሞ የእናንተ ያልሆነች የሰይጣናት መቀጫ ቦታ ብቻ የነበረች በአዳምና በሔዋን ዐመጻ ምክንያት ከገነት ሲባረሩ ለእነሱ መኖሪያና መቀጫ በሚሆን መልኩ ተዘጋጅታ የገቡባት፤ እናንተም በመጀመሪያ ወላጆቻችሁ ዐመጻ ምክንያት እየተቀጣችሁበትና እየጠራችሁበት ያለች ቦታ ናት እንጂ የእናንተ እዉነተኛዉ መኖሪያ ቦታችሁ ገነትና ሰማያት ናቸዉ:: እናንተ ግን በአጭር ዘመን ቆይታችሁ እኔን በመፍራትና በማምለክ ተመላልሳችሁ ወደ እዉነተኛ መኖሪያ ቦታችሁ ከመግባት ይልቅ ከቀድሞ ወላጆቻችሁ ብሳችሁ የበለጠ ዐመጻንና ክህደትን በመፈጸም ራሳችሁን ለበለጠዉ መቀጫ ቦታ ሲያልና ገሃነመ እሳት ትዳርጋላችሁ:: በዚያ ዳግም የንስሐ እድል የሌላችሁ መሆኑን አሁንም ደግሜ አሳዉቃችኋለሁ:: የእናንተ የንስሐ እድል በዚህች እጅግ እጅግ ለአጭር ዘመን በነጻነት በምትንቀሳቀሱባት ምድር ዉስጥ ብቻ ነዉ:: እኔ በፍጥረቴ አንዳች አድሎ አላደርግም:: ሰይጣናትም በዐመጻቸውና በክህደታቸዉ ምክንያት ነጻነታቸዉን ገድቤ በገሃነመ እሳት የምቀጣቸዉ ከሆነ እናንተ የአዳም ዘሮች የንስሐ እድል ተሰቷችሁና ታላቅ ዋጋ ተከፍሎላችሁ በዐመጻና በክህደት ሕይወታችሁ ከጸናችሁ እንዴት አብልጬ አልቀጣችሁ!? እጅግ እቀጣችኋለሁ::

እንግዲህ ይህን ሁሉ የተናገርኳችሁ እዉነትን ፈልጋችሁ በመምጣታችሁና ራስችሁን ዝቅ አድርጋችሁ በደጄ በመዉደቃችሁ ነዉ እንጂ በየቦታዉ አገልጋዮቼና ምስክሮቼ ስለ እዉነት ሊያስተምሯችሁና ሊነግሯችሁ ይችሉ ነበር:: ታዲያ እዉነተኛዉን ሃይማኖት የሚወክሉት እነዚህ የኢትዮጵያ ቀጥተኛዉ ተዋህዶ ሃይማኖት «ወኪል ነን» ብለዉ ከእናንተ ጋር እዚህ ሱባኤ ቦታ የመጡት ሰዎች እንዳይመስሏችሁ:: እነሱን በደንብ አዉቃቸዋለሁ፤

እንደእናንተ በስሜ የሚነግዱ፣ ትዕዛዙንና ሕጉን ይናገራሉ እንጂ እንደ ቃሉ የማይኖሩ፣ እዉቀታቸዉን የሚያመልኩና የሚያስመልኩ፣ በኔ ቦታ ላይ ሆነዉ መመስገንና መከበርን የሚፈልጉ፣ አንዴ በቤተክርስቲያን አንዴ በዐመጻዉና በርኩሰቱ ቦታ እየተገኙ ቡራኬ የሚሰጡ፣ ለሃይማኖቷ ሆነ ለስርዐቷ ደንታ የሌላቸዉ፣ ሌት ተቀን ለጥቅማቸዉ ብቻ የሚሯሯጡ፣ ጥቅምና ክብር ካገኙ የዐመጻና የክህደት ተግበር ከመፈጸምና ከማስፈጸም ወደ ኋላ የማይሉ፤ ባጠቃላይ በእዉነተኛዋና በብቸኛዋ የሕይወት መንገድ በቀጥተኛዋ(ኦርቶዶክስ) ተዋህዶ ሃይማኖት ዉስጥና በብቸኛይቱና እዉነተኛይቱ ቤተክስቲያን ዉስጥ ሆነዉ እንደ ቃሌ የማይኖሩ አስመሳይ አገልጋዮች ናቸዉ። ወደዚህ ስፍራ ተመርጠዉ የተላኩት የተለየ ምድራዊ ጥቅም የሚገኝበት ስለመሰላቸዉና «የሃይማኖቱ ተጠሪና መሪ ነኝ፤ የክርስቶስ እንደራሴ ነኝ።» ብለዉ በዐመጻ በወንበር ላይ የተቀመጡት ዕጨጌ ወዳጅና በዘመድ አዝማድ፣ በጎጥ፣ በጥቅማ ጥቅም የተገናኙ ስለሆነ ነዉ እንጂ በቅድስና ሕይወታቸዉ ተመርጠዉ የተላኩ አይደሉም።

እነዚህ ተወካዮች የሚያገኑትና ከፍ ከፍ የሚያደርጉት እንዲሁም የሚያስመልኩትን ለማወቅ ከፈለጋችሁ ከዚህ ሱባኤ እንደወጣችሁ በቤተ ክህነቱ አዳራሽ ዉስጥ በአራቱም አቅጣጫ ግድግዳ ላይ በሳንቲ ሜትር ርቀት ለቁጥር በሚታክት ብዛት የተለጠፈዉን የአንድ ሰዉ ስዕል መመልከት ትችላላችሁ። እኔ ፈጣሪ እግዚአብሔር ሆንኩ እናቴ ድንግል ማርያም እንዲሁም ቅዱሳኖቼ እንኳ አንድ ሺህኛዉ ያህል እንኳ አልገነንም፤ ከፍ ከፍ አላልንም። ከስዕሉ ጋር መጠኑ አነስ ቢልም የገነነዉን የዲያብሎስ አርማ የሆነዉን ኮኮብ በየቦታዉ ተንጠልጥሎ ማየት ትችላላችሁ። በተጨማሪም ቦሌ መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን መግቢያ በር ጋር የቆመዉን በሕይወተ ሥጋ እያለ « እኔ ቅዱስ ነኝ» በማለት በአጫፋሪዎቹ አማካይነት ያስቆመዉን ሐዉልት መመልከት ትችላላችሁ። የዲያብሎስ ስርዐት የዘረጉት የተለያዩ የአገራት መሪዎች እንኳ ራሳቸውን በዚህ መልክ አላገነኑን፤ አላስመለኩም። እነዚህ ተወካዮች ሌላዉ የሚታወቁበት ልዩ ተግባር ደግሞ «የሃይማኖት መሪ ነኝ» ብለዉ ከተቀመጡት ዘንድ ሞገስንና ሽልማትን፣ ስልጣንን ለማግኘት ሲሉ እዉነተኛ አገልጋዮችን የሚያሳድዱ፣ የሚወነጅሉ፣ የሚያንከራትቱ፣ የሚያሳስሩ፣ የሚያስደበድቡ፣ የሚያስገድሉ፣ ባጠቃላይ ለበላይ አለቆቻቸዉ ታማኝ ሆነዉ ኀሊቸዉን በመሸጥ የሚመላለሱ በመሆናቸዉ ነዉ እንጂ ስንት ጻድቃንና እዉነተኛ አገልጋዮች እያሉ እነዚህ እለት እለት በዐመጻቸዉ የሚያስቆጡኝ አስመሳይ አገልጋዮች ወደዚህ የተቀደሰ ስፍራ ባልተላኩ ነበር።

እዚህም እንደ ዓለም ስራቸዉ እናንተንም፣ እኔንም አታለዉ ተመሳስለዉና የተለየ የከበሬታ ወንበር አግኝተዉ  ለመመለስ እንደእናንተ ደጅ ጠኝ መስለዉ ተገኝተዋል፡፡ ይህን ሕይወት ከረሱት ብዙ ዓመታት አስቆጥረዋል፡፡ እሁን ግን ግድ ስለሆነባቸዉ ነዉ እንደ እናንተ በመብሉ እየተንገሸገሹ «መች ቶሎ ባለቀልን?» እያሉ ከሱባኤ የሚወጡበትን ቀን የሚጠብቁት፡፡ ከትቢያ አንስቻቸዉና  የቆሎ ተማሪነት ጊዜያቸዉን ዘንግተዉ አሁን ላሉበት ደረጃ ሲደርሱ ያ በረከትና ጸጋ ያገኙበት የነበረዉን ሕይወት ከናካቴዉ ረስተዉና አሁን ያሉትን  ተማሪዎችና መምህራንን ማስታወስና አስፈላጊዉን ሊፈጽሙላቸዉ ሲገባ፤ እነሱ ግን እንኳን ይህንን ሊያደርጉ ቀርቶ አሁን ያሉበትን ወንበር በማምለክ በኔ ቦታ ተቀምጠዉ መመስገንና መመለክን ይፈልጋሉ፡፡ እናንተ ግን መጀመሪያ ላይ ብታጉረመርሙም አሁን ግን ደስ ብሏችሁ «ለካስ በሱባኤ እንደዚህ የተሰበረ ሕይወት ይገኝበታል» በማለት ለወደፊትም ሱባኤ እንደምትገቡ ለራሳችሁ ቃል የገባችሁት፡፡

ከእንግዲህ እናንተ መመልከት ያለባችሁ እነዚህን አስመሳይ አገልጋዮችን ከነፈሰዉ ጋራ የሚነፍሱትን፣ እንደ ቦይ ዉሃ ወደ ወሰዷቸዉ የሚሄዱትን ፣ ለሆዳቸዉ ብቻ ያደሩትን ሳይሆን፤ ጊዜያቸዉን ሰዉተዉ «ደከመኝ፣ ሰለቸኝ፣» ሳይሉ፤ «ተራብን ፣ ተጠማን ፣ ተቸገርን» ሳይሉ፤ በእዉነተኛ አምልኮ ሆነዉ ስለ እዉነት እየመሰከሩ፣ ምዕመኑን ከዘልማድ ሕይወት የሚያላቅቁትንና ለንስሐ ለሥጋ ወደሙ የሚያበቁትን፤ ለመልካም ተግባር የሚያሰልፉትን፤ እንዲሁም ዘመናቸዉን ሁሉ ከሰዉ እንዳች ሳይጠብቁ «ከእግዚአብሔር ነዉ ዋጋ የምናገኘዉ፡፡» በማለት መምህራንንና ሊቃዉንትን የሚያፈሩ በየቦታዉ የተረሱና አስተዋሽ ያጡ እዉነተኛ አገልጋዮቼን ሊቃዉንትንና የብሉያቱና የሐዲሳቱን እንዲሁም የዜማዉ፣ የዝማሜዉ፣ የአቋቋም፣ የቅኔ፣ የቅዳሴ..ወዘተ መምህራንን፤ ካህናትን ፣ መነኮሳትን፣ ሰባኪያንን ፣ዲያቆናትን፣ እንዲሁም ዘመናቸዉን ሁሉ በየገዳሙና በየዋሻዉ ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉ በመኖር ለአገራቸዉና ለዓለም ሕዝብ ሌት ተቀን የሚጸልዩትንና የሚያነቡትን መናንያንና ባሕታዉያንን ነዉ፡፡

በአስመሳይ አገልጋዮች ሳትሰናከሉ እዉነተኛ አገልጋዮቼ በሚያዟችሁ መሰረት በኢትዮጵያ በቀጥተኛዋ ተዋህዶ ሃይማኖት ስር ሆናችሁ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በመጠመቅ፣ ሕይወት በሚሆናችሁ በሥጋዬና በደሜ ታተሙ፡፡ በምድራዊ ሕይወት ዘመናችሁም በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት፣ በመልካም ተግባር በመመላሰስ ሰማያዊ መንግስታችሁን በመናፈቅ ኑሩ፡፡ ያኔ በምድርም በረከትን ታገኛላችሁ፤ በሕይወታችሁም

በፍቅር፣ በሰላም፣ በእርካታ፣ በጤና መኖር ትችላላችሁ፡፡» በማለት ነዉ ያላሰብነዉና ያልጠበቅነዉ ምላሽ የተሰጠን በማለት አቅርበዋል፡፡

የሌሎቹም ክፍለ አህጉር ተወካዮች ተጠይቀዉ «አሁን ከተነገረዉ ጋር አንድ አይነት ምላሽ ነዉ የተሰጠን፡፡» ብለዉ ሁሉም በአንድ ድምጽ መልሰዋል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጰያ ቀጥተኛ ተዋህዶ ሃይማኖት ተወካዮች « እኛ በእዉነቱ ሁል ጊዜ ከአምላካችን መልስ የምናገኝና የምንገናኝ ስለሆነ በዚህ ሱባኤ ላይ አንዳች የተባልነዉ ነገር የለም፡፡ የሌሎቹ አገራትና የተለያየ እምነት ተወካዮች «በሱባኤዉ እንዲህ ተባለ፡፡» ብለዉ በአንድ ድምጽ የተናገሩት ተመካክረዉ ነዉ እንጂ ለእኛ ለሃይማኖቱ ባለቤቶች ያልተገለጸዉ ለእነሱ እንዴት ይገለጽላቸዋል?» በማለት ንስሐ ከመግባት ይልቅ ስለክብራቸዉና ለጥቅማቸዉ በመቆም ዓለም እዉነታዉን እንዲያዉቅ እግዚአብሔር የተናገረዉን የእዉነት ቃል እንደ ቀደሙት ጸሐፍት ፈሪሳዉያንና አይሁድ ካህናት አጣጣሉት፡፡

በመጨረሻም የተባበሩት መንግስታት የሶስቱን የኢትዮጵያን የተዋህዶ ሃይማኖት ተወካዮችን አስተያየት ሰምተዉ ድምጽም በድምጽ የመሻር ስልጣናቸዉ ተጠቅመዉ ከ195 አገራት ባላይ የተቀበሉትን እዉነተኛ የሕይወት መንገድ የሆነችዉን የኢትዮጵያ ተዋህዶን ሃይማኖት በራሳቸዉ በኢትዮጵያዉያን የተዋህዶ ሃይማኖት ተወካዮች ተቃዉሞ ስለገጠመዉ፤ « እናንተ ተወካዮች በብልጠት ተመካክራችሁ የሌለዉን እግዚአብሔር አለ በማለት ልታታልሉን ብትሞክሩም ይኸዉ አብረዋችሁ የነበሩት እናንተ «ትክክለኛ ሃይማኖት ነዉ፡፡» ያላችሁትን የሚወክሉ «ዉሸት ነዉ አልተገለጸላቸዉም» በማለት ስላረጋገጡልን፤ ዓለም እግዚአብሔር እንደሌለ እንዲያዉቅና ተፈጥሮ በለገሰችዉ ዘመን ሁሉ በዘፈንና በዳንኪራ ራሱን እያስደሰተ ይኑር፡፡ «ሲያል፣ ገሃነመ እሳተ፣ ገነት፣ መንግስተ ሰማያት» የሚባለዉ ሁሉ ዉሸት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡» በማለት መግለጫ በመሰጠቱ በድንጋጤ ዉስጥ የነበርኩት እኔ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ያላሰብኩት ዉሳኔ በመሰጠቱ እኔና ሠራዊቶቼ ሰይጣናት ደስታችንን ለአንድ ወር ያህል በመዝፈንና በመጨፈር ልናሳልፍ ችለናል፡፡» **ይላል የጨለማዉ ጌታ ሰዎችን ስለ ክብራቸዉና ጥቅማቸዉ የሞት መንገድን የሚያስመርጥ ሐሰተኛዉና አታላዩ መንፈስ ዲያብሎስ፡፡**

# ምእራፍ ሦስት

« አንዳንድ ምእምናን ተሰብስበዉ ቅሬታቸዉን ለማቅረብ ወደ ሃይማኖት አባቶች በመቅረብ «የተከበሩ የኔታ! እኛ ብዙዉን ጊዜ ስንማርና ስንሰበክ ጻድቃን ናችሁ፤ እዚህ በመምጣታችሁ ድናችኋል፤ አንዳንዶቹ ደግሞ እዚህ መታችሁ በማጨብጨባችሁና እልል በማለታችሁ መንግስተ ሰማያትን ትወርሳላችሁ፤ አሜን ካላችሁም ገነት ትገባላችሁ፤ የተመሰገናችሁ ቅዱሳ ናችሁ።» እያሉ ደስ የሚል ስብከትና እኛም በቀጥታ መንግስተ ሰማያት ዉስጥ ያለን እስኪመስለን ድረስ ነዉ የምንሰማቸዉ የነበረዉ። ባለፈዉ ሳምንት ግን አንድ የማናዉቃቸዉ አባት ሰባኪ ይሁኑ ተሳዳቢ አናዉቅም « እናንተ ምዕመናን ሆናችሁ አገልጋዮች እግዚአብሔር እንደ ሰዉ አይታለልም። እንኳን የምትሰሩትንና የምትናገሩትን ቀርቶ ጠማማና ርኩሰት የሞላዉ አሳባችሁን በሰማያዊ መዝገቡ ላይ የሚመዘግበዉና ንስሐ ላልገባችሁበትና ላልተጸጸታችሁበት ኃጢአት ሁሉ እንደምትጠየቁ ልታዉቁ ይገባል። ስለዚህ እናንተ ያማረ ለብሳችሁ ብትታዩም እርሱ ባለቤቱ ደግሞ ዉጫችሁን ሳይሆን ዉስጣችሁን ነዉ የሚመለከተዉ። በመሆኑም ከማስመሰል ሕይወት ተለይታችሁ እዉነተኛ ንስሐ ግቡ፤ ኃጢአታችሁን እየተናዘዛችሁና እየተጸጸታችሁበት የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ተቀበሉ። ከዚያ ዉጭ በብልጣብልጥነትና በአቋራጭ መንገድ የእግዚአብሔርን መንግስት እንወርሳለን ብላችሁ አታስቡ። የምትማሩትን ሆነ የምትሰሙትን ቃል በሕይወታችሁ ለዉጣችሁ እንደ ቃሉ ሆኖ በመገኘት በመልካም ምግባርና ሕይወት ተመላለሱ። ያኔ በረከተ ሥጋና በረከተ ነፍስ ታገኛላችሁ። ጸጋዉ ይበዛላችኋል። በመጨረሻም ለሰማያዊ መንግስት ትበቃላችሁ። ከዚያ ዉጭ በዘልማድና ጊዜ ለማሳለፍ ወደ ቤተክርስቲያን ስለተመላለሳችሁ ብቻ ለመንግስተ ሰማያት የምትበቁ እንዳይመስላችሁ።

ወደ እግዚአብሔር ቤት እንደምትመጡ አዉቃችሁ እለት እለት ፊታችሁን እንደምትታጠቡ ሁሉ ለፈጸማችሁት የተግባር ሆነ የንግግር ኃጢአት ንስሐ ሁል ጊዜ ልትገቡና ስለ ክፋትና ርኩሰት አሳባችሁ በኀሊናችሁ ልትጸጸቱ ይገባችኋል። ያለፈዉ የማስመሰል የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ የዘፈን ፣ የዳንኪራ፣ የዝሙት፣ የመዳራት፣ የሴሰኝነት ፣ የጥል፣ የጥላቻ፣ የቂም በቀል፣ የግድያ፣ የስርቆት፣ የባዕድና የጣዖት አምልኮ፣ የክፋት፣ የተንኮል፣ የምቀኝነት ..ወዘተ ዘመን ይበቃችኋል። እስከ አሁን እግዚአብሔር የንስሐ እድሜ ሰቷችሁ ለዚህ ዘመን በቅታችኋል።» በማለት ባዶነት እንዲሰማንና ኃጢአተኞች እንደሆን አደርገዉ በመቁጠር «ንስሐ ግቡ» አሉን። ከሁሉ የሚገርመዉ ደግሞ እስከዛሬ ማንም ያልተናገረንን «አትዝፈኑ፤ ዳኒኪርተኛ አትሁኑ» አሉን። እኛን ከሚናገሩ ለምን ቀን ከሌሊት በቴሌቭዥና በሬዲዮን የሚያቀርቡትን አይናገሩም? ክልክል ቢሆን ኖሮ በተለያዩ

ሚዲያ አይተላለፍም ነበር:: ደግሞ የባህላችን መገለጫ የምንዝናናበትና የምንጨፍርበት ነዉ:: ሌላዉ ደግሞ የተለያዩ ባህላዊ አምልኮ  እኛም ሆነ ቤተሰቦቻችን ወቅት እየጠበቁ ያከብራሉ፤ አስፈላጊዉንም ግብር ያቀርባሉ:: ይህም አንዱ የማንነታችንና የባህላችን መገለጫ ነዉ:: እኛ ብዙዉን ጊዜ በቤተክርስቲያን በዐላት ላይ ተገኝተን ታቦት እናከብራለን፤ እንዳንዴ እንቅልፍ ካላሸነፈን እሁድ እሁድ ቤተክርስቲያን መተን እንሳለማለን:: ታዲያ ምን ጎደለ ብለዉ ነዉ እንዲህ ባዶነት እንዲሰማን አድርገዉ የሚያስተምሩንና የዘልማድ ሰዎች አድርገዉ የሚቆጥሩን?

እንዲህ የሚናገሩን ከሆነ ደግሞ እንደልባችን የምንሆንበትን የጴንጤዎችን እምነት እንከተላለን:: እነሱ ሁል ጊዜ «ጌታን ከተቀበላችሁ ትድናላችሁ፤ ስለምግባር አታስቡ፤ «ዋናዉ የሱስ ጌታ ነዉ::» ብላችሁ ከመሰከራችሁ መንግስተ ሰማያት ሰተት ብላችሁ ትገባላችሁ::» እያሉ ያባብሉናል:: እኛ ደግሞ «ከቤተሰባችን የወረስነዉ እምነት ስላለ ወደ እናንተ አንመጣም::» እያልን እስከአሁን ድረስ ሃይማኖታችንን አለወጥንም:: አሁን የምታከብዱብን ከሆነ እኛ እንደልባችን የምንሆንበትን፣ መጾም የሌለበትን፣ በፈለጉት ጊዜ በፈለጉት የአለባበስ ስታይል ከፈለጉ በተወጣጠረ ሱሬ፣ ከፈለጉ ደረትና ጡት በተገላለጠ አለባበስ፣ ከፈለጉ በአጭር ቀሚስ፣ ከፈለጉ በታይት፣ ከፈለጉ በቁምጣ  ወደ አዳራሽ እየሄዱ የሚዝናኑበትን፣ እንዲሁም በዘመናዊ መሳሪያ የሚዘፈንበትንና የሚጨፈርበትን መዝሙር እናዳምጣለን፤ ጭፈራዉንም እንመለከታላን፤ እኛም ሲያስፈልገን እንደ ብሔር ብሔረሳችን እንጨፍርበታለን፤ በመሬት ላይ እየተንከባሉና እየተንፈራገጡ የሚያሳዩትን ትዕይን በመመልከት በመንፈስ እንሞላለን:: » በማለት ቅሬታቸዉንና አቋማቸዉን አቅርበዋል::

ቅሬታቸዉን የሰሙት አንድ የቤተክርስቲያኑ አገልጋይ « ምን ጉድ መጣ? ምን ተብለዉ ተሰብከዉ ይሆን እንዲህ በቁጣ የመጡት?» በማለት አሳብ ዉስጥ አስገብታችሁኝ ነበር:: አሁን ንግግራችሁን ስሰማ ተረጋጋዉ:: መቼስ እኛ ሰዎች ስንባል የሚያመሰግነንን፣ የሚክበንን፣ የሚሸነግለንን ሰዉ ነዉ የምንወደዉና ንግግሩን ለማዳመጥ የምንፈልገዉ እንጂ ካለማስመሰልና ካለይሉኝት የሚናገረንንና የሚያስተምረንን አንወደዉም:: ብናስተዉል ግን እዉነቱን የሚነግረንን እንዲሁም ስለ ኃጢአታችን የሚገስጸንን ነበር መስማትና ማዳመጥ የነበረብን:: ምክንያቱም እርሱ ነዉና እዉነተኛ የነፍስ እረኛ:: እኛ ያስተማሯችሁ አባት ገና በትምህርት ያልጠነከራችሁ መሆናችሁን ስለተረዱ ነዉ እንጂ ብትጠነክሩ ኖሮ ጥልቅ ትምህርት ያስተምሯችሁ ነበር:: የበለጠ ይገስጿችሁ ነበር:: እናንተ እንዳላችሁኛ ከሆነ የለዘበ ቀለል ያለ ትምህርት ነዉ ያስተማሯችሁ እንጂ እናንተን አንዳች የሚያስቆጣና የሚያሳዝን ነገር አልተናገሯችሁም:: ከኔ ጀምሮ ሁላችንም ኃጢአተኞች መሆናችንን ሁል ጊዜ ልናምን

ይገባል እንጂ ራሳችንን አንዳንድ እምነት ድርጅቶች እንሚሉት « ጻድቅ ነን» እያሉ ራሳቸዉን እንደሚያመጻድቁት ሰዎች አስተሳሰብ ካለን ዋና ኃጢአተኞች መሆናችንን ልናዉቅ ይገባል:: እንኳን በባዶ ሕይወት ዉስጥ ሆነን ቀርቶ በቅድስናና በጽድቅ ሕይወት ዉስጥ ብንሆን እንኳን ራሳችንን ተራ ወራዳ ኃጢአተኞች ሰዉ አድርገን ነዉ ወደ አምላካችን መቅረብ ያለብን እንጂ ነገ የምንሆነዉን ስለማናዉቅ በጽድቅ ስራችን ልንመጻደቅ አይገባም:: ብዙዎች ራሳቸዉን በማመጻደቃቸዉና በማስታበያቸዉ ምክንያት ነዉ አይወድቁ አወዳደቅ የወደቁትና የተዋረዱት::

አንዳንድ አባቶችና ወንድሞች የሚያመሰግኗችሁ «ጻድቃን ናችሁ፤ እዚህ በመምጣታችሁ መንግስተ ሰማይት ትገባላችሁ፤ ቅዱሳን ናችሁ.. ወዘተ» እያሉ ደስ ደስ የሚል ትምህርት የሚሰጧችሁና እናንተም ደስ ብሏችሁ ንስሐ ከመግባት ይልቅ በኃጢአታችሁ እንድትጸኑ እያደረጉ መሆኑን ስላላስተዋሉና እናንተም ስለምታበሏቸዉ፣ ስለምታጠጧቸዉ፣ አባት አባት፣ መምህር መምህር፣ ቅዱስ ቅዱስ፣ ብጹዕ ብጹዕ .. ወዘተ» ስለምትሏቸዉ፤ በይሉኝታ ተጠፍረዉና ክብራቸዉንና ጥቅማቸዉን በማስቀደማቸዉ ምክንያት ነዉ::

እኝህ አባት ግን ዋሻ ዉስጥ የነበሩ የዚህን ዓለም ስልጣን፣ ክብር፣ ብልጽግና፣ ዝና የናቁ፤ ዘመናቸዉን ሁሉ በዋሻ ዉስጥ ያሳለፉ፤ ለአገራቸዉና ለሕዝቧ ሌት ተቀን የሚጸልዩና የሚያነቡ፤ አምላካቸዉንና እናቱን ድንግል ማርያምን « ይህች ቅድስት አገር ካልተማረችና እዉነት ካልነገሠባት በቀር በጫማ አልረግጣትም» በማለት እንደምታያቸዉ በባዶ እግራቸዉ የሚንቀሳቀሱ፤ እንዲሁም ለአስራዎቹ አመታት በጸጉራቸዉ ሆነ በጺማቸዉ ላይ ምላጭ ሆነ መቀስ ሳያሰርፉ በመቆየታቸዉ የተጎነጎነ ጸጉራቸዉና ጺማቸዉ እብድ ያስመሰላቸዉ፤ አንዳንድ ያልገባቸዉ ሰዎች ራሳቸዉን ለንስሐና ለተቀደሰ ሕይወት ማብቃት ሲገባቸዉ «በባዶ እግር በመሄድ አይጸደቅም:: እንደ እብድ መንጨባረር ከእግዚአብሔር አይደለም» እያሉ የማይመለከታቸዉን ቢዘባርቁም፤ እርሳቸዉ ግን ለዚህ ለተጎሳቆለ ገጽታ የተዳረጉበትን ምክንያትና ዓላማቸዉን ያዉቃሉና የሚተቿቸዉን በዝምታ በማለፍ እስከአሁን ድረስ በዚህ አቋማቸዉ ጸንተዉ ያሉ፤ ከባዕታቸዉም « ምህረት እስካልተደረገ ድረስ አልወጣም» በማለት ብዙ ዘመናትን ያሳለፉ ሲሆን፤ አሁን እዚህ ሊመጡ የቻሉትም እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም « ልጆቼ ምእመናን እረኛ እንደሌላቸዉ በጎች ተቅበዝብዘዉብኛልና ሰብስብልኝ፤ በእዉነት የሚያስተምር፣ በሕይወቱ አርአያ የሚሆን፣ በነገረ መስቀሉ ፍቅር የሚቃጠል፣ ስለ እዉነት ራሱን ክዶ የሚመሰክር፣ ካለማስመሰልና ካለሽንገላ የሚያስተምር አገልጋይ እዉነተኛ

እረኛ አጥቻለዉና ሂድና ሕዝቡን አስተምር፤ ወንጌልን ስበክ፤ ለንስሐ ለቅዱስ ቁርባን አብቃ። አንዳንድ «ሰባኪ ነን» እያሉ ምዕመኑን የሚያደናግሩ እንደ መናፍቃኑ የመዝናኛ ጉባኤ እያዘጋጁለት ወደ ልቡ እንዳይመለስና ወደ ንስሐ እንዳይቀርብ አድርገዉታል። ስብከታቸዉም እንደ መናፍቃን የሆነ፤ መዝሙራቸዉም ዘፈን ዘፍን ያለ፤ ምስጋናቸዉም ጭፈራ የመሰለ፤ ባታላዩ መንፈስ የሚመሩ፤ «ሰባኪ ነን» የሚሉትም በትዕቢትና ዐመጻ ሕይወት የሚመላለሱ ተኩላዎች ስለሆኑ ምእመኑ በእነዚህ ተኩላዎች ከመበላታቸዉ በፊት እዉነተኛ የቤተክርስቲያኗን አስተምሮ የጠበቀ ትምህርት ስጥ።

በእረኝነት በወንበር ላይ የተቀመጡት ሲሆን ሲሆን ራሳቸዉ እየተንቀሳቀሱ ምእመኑን ሊያስተምሩትና ለንስሐ ሊያበቁት ሲገባ፤ ያም ካልሆነላቸዉ የቤተክርስቲያኒቱን እምነትና ስርዐት፣ አስተምሮና ትዉፊት መጠበቅ ሲገባ፤ ለጥፋት ሰዎች ከለላና ጠበቃ ሆነዉ የዐመጻና የክህደት ተግባር የሚያሰሩ ስለሆነ፤ አንተ በአራቱም ማዕዘን እየተንቀሳቀስክ ከፈቀዱልህ በየአብያተክርስቲያኑ በዉስጥ፣ ከከለከሉህ ደግሞ እንደ ተገፊ በዉጭ ሆነህ አስተምር፤ ስበክ። እኔ አብሬህ ነኝ አትፍራ። እነሱ ልጄን ራቁቱን በመስቀል ላይ ሰቅለዉ እያላገጡበትና በቁስሉ ላይ እንጨት እየከተቱበት ነዉ። መስቀሉንም የያዙት ሊነግዱበታ፣ ለያስመስሉበት፣ ሊከበሩበት እንጂ መከራን ሊቀበሉበትና ስለ እዉነት ሊመሰክሩበት አይደለም። ቀኑ ሲደርስ ዋጋ ስለሚከፍሉበት አንተ ግን ምእመኑን በሚገባ አስተምር፤ ስለ እዉነት መስክር።» በማለት ስለታዘዙ ነዉ ወደ ዓለም አልወጣም ብለዉ ተደፍተዉ ከሚኖሩበት ዋሻቸዉ መተዉ ለማስተማር የተገደዱት።

እናንተ አሁን «ተሰደብን» የምትሉት እንኳን መሰደብ ቀርቶ ግሳጼ አልደረሰባችሁም። ቃሉን አስተዉላችሁ ቢሆን ኖሮ በቅዱሳት መጽሐፍት ዉስጥ እንደተጻፈልን ጌታችን መድኃኒታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመዋዕለ ሥጋዌዉ ወንድሙን «ደንቆሮ» ብሎ የሚሰድብ «ገሃነመ እሳት ይገባዋል» ብሎ አስተምሮናል። በሌላ በኩል ደግሞ ጆሮዋቸዉ እየሰማ ቃሉን በተግባር የማይፈጽሙትን ዐይናቸዉ እያየ ምንም እንዳላየ ኅሊናቸዉን የሚያደነድኑትን የወቅቱ የሃይማኖት መሪዎችንና «የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን» የሚሉትን አስመሳይ አገልጋዮችን « እናንተ ደንቆሮዎችና እዉራን» በማለት ገስጿቸዋል። እንዲሁም «በዉጭ አምረዉ የምትታዩ በዉስጥ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን የምትመስሉ።» በማለት ገስጻቸዋል። እንዲሁም የአዳም ዘሮች ፍጥረቶቹና ልጆቹ መሆናቸዉን ቢያዉቅም፤ የዲያብሎስን ስራ በመስራታቸዉና በዐመጻቸዉና በክፋታቸዉ ፍጹም ሰይጣናትን በመምሰላቸዉ «የዲያብሎስ ልጆች» በማለት ገስጿቸዋል። ታላቅነቱ የተመሰከረለት የሐዋሪያት አለቃ ቅዱስ ጴጥሮስ ሳይቀር የሥጋና ደም ስሜቱ

አሸንፎት ለግል ጥቅሙና ለክብሩ ቅድሚያ በመስጠት ስለ እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግስት ራሱን መካድ ተስኖት፤ ጌታችን ለሰዉ ዘሮች ሁሉ ሊፈጽም ያሰበዉን መስዋዕትነት ለማከላከልና ወደ ኋላ ለመጎተት ሲያስብና ሲናገር «አንተ ሰይጣን» ተብሎ ተገስጿል።

ስለዚህ በዚህ መልኩና ከዚህም በላይ ብትገሰጹ እንኳ ስድብ ሳይሆን ማንነታችሁን አዉቃችሁ ባዶነት ተስምቷችሁ በንስሐ ወደ አምላካችሁ እንድትቀርቡና ተወዳጆቹ ልጆች እንድትሆኑለት፤ እንዲሁም ራሳችሁን እንዳታመጻድቁና እንዳታስታብዩ፣ ስለ እዉነትም ራሳችሁን እንድትክዱ ቆራጦች ለማድረግ ስለሚፈልጉ ነዉ እንጂ እናንተን ለማዋረድ ወይንም ክብራችሁን ለመንካት ፈልገዉ አይደለም። ሌላዉ ማወቅ ያለባችሁ፤ አካለ ስንኩልን ማለትም ዐይነስዉር፣ ደንቆሮ፣ ሽባ፣ ባጠቃላይ በተለያየ ምክንያት አካሉ የጎደለበትንና በበሽታ የተጎዳን ሰዉ በጉድለቱ ብትሰድቡትና ብታሾፉበት የሰደባችሁትና ያሾፋችሁበት በእርሱ ሳይሆን በፈጠረዉ አምላክ ላይ በመሆኑ ምድራዊ ፍርድ ብቻ አይደለም ሰማያዊዉ ፍርድ የሆነዉ ገሃነመ እሳት እንደሚፈረድብን በማስተዋል ልታዉቁ ይገባል። እንኳን በአፈጣጠሩ ምክንያት መስደብ ቀርቶ፤ አንድ የአዳም ዘርና የእግዚአብሔር ፍጥረትን ልጅ የሆነዉን ሰዉ ምንም እንኳ እንደማንኛዉ ሰዉ ሙሉ አካለ ቢኖረዉና ድሀና ችግረኛ ቢሆን ስለ ድህነቱና ችግርተኛ ነቱ ብትሰድቡትና ብታዋርዱት የሚያስጠይቃችሁ መሆኑን ልታዉቁ ይገባል።

ሌላዉ ደግሞ በኔና በመሰሎቼ አገልጋዮች እንዳትሰናከሉ። እኛ እርስ በእርስ በመጣላታችን፤ በዘር፣ በጎጥ፣ በቋንቋ ተቧድነን ሁለተኛዋ ባቢሎን በመሆናችን አትገረሙ። ለስልጣን፣ ለጥቅም፣ ለዝና፣ ለሽልማት ስንሯሯጥ፤ እርስ በእርስ ስንጠላለፍ፤ ጉድጓድ ስንማማስ፤ ወጥመድ ስናጠምድ ብትመለከቱ እንዳትሰናከሉ። ሐሰትን ስንናገር፣ ኀሊናችንን ስንሸጥ፣ በምናስተምረዉ ቃል ሆነን መገኘት ሲሳነን ፣ ስለ እዉነት ራሳችንን ክደን መመስከር ሲያቅተን እያያችሁ አትታዘቡን።

እናንተ፤ የተለያየዉን ፈተና ተቋቁመዉ ሌት ተቀን በቅንነትና በእዉነት እንዲሁም በመልካም ሕይወት በገጠርም፣ በከተማም፣ እናት ቤተክርስቲያንንና እናት አገራቸዉን የሚያገለግሉትን አገልጋዮችን ተመልከቱ። ይህ እኛ የምንጣላበትንንና የምንወነጃጀልበትን ስልጣንና ክብር፣ ጥቅምንና ድሎትን ንቀዉ በየዋሻዉና በየገዳማቱ ወድቀዉ ሌት ተቀን ለአገራቸዉና ለዓለም ሕዝብ የሚጸልዩትንና የሚያነቡትን ተመልከቱ። እንዲሁም ከእኛ በላይ እዉቀት ይዘዉ ማንም ሳያስታዉሳቸዉና ቦታ ሳይሰጣቸዉ «የአባቶቻችን ትምህርት እንዳይፋለስ።» በማለት አቋቋሙን፣ ሰዐታቱን፣ ድጓዉን፣ ቅዳሴዉን ፣ ኪዳኑን፣ ብሉያቱንና ሐዲሳቱን፣ የተለያዩ እዉቀቶችንና ድርሳናትን ለቀጣይ ትዉልድ እንዲተላለፍ ድርሻችንን

እንወጣ።» በማለት በየቦታዉ የአብነት ተማሪዎችን የሚያስተምሩትን ሊቃዉንትንና መምህራንን ተመልከቱ።

እኔም ሆንኩ አንዳንድ አባቶቼና ወንድሞቼ በላያችን ላይ ከላይ ሰላይ ስለተመደበብንና የማስተማሩንም እድል ስላልተሰጠን ለጎሊናችን በማህሌቱ ፣ በሰዐታቱ፣ በኪዳኑ፣ በቅዳሴዉ እናገለግላለን እንጂ እናንተን የማስተማሩን እድል ቢሰጠን እንደኝህ አባት ባይሆንም እንደአቅማችን ካለማስመሰልና ካለሽንገላ እንደምናስተምራችሁ አምናለሁ። ነገር ግን ቦታ ስላልተሰጠን ቢያንስ ቢያንስ ቤተክርስቲያን እንዳትዘጋ በተማርነዉ አምላካችንን እናመሰግናለን ፣ የአብነቱን ትምህርት የሚማሩ ልጆች ካገኘን ደግሞ ለቀጣይ ትዉልድ አገልጋይ እንዳይጠፋ በምንችለዉ መንገድ እናስተምራለን በማለት ነዉ እንጂ የዘልማድ ሕይወትና አገልግሎት በመስጠታችን ደስተኞች አይደለንም። አሁን ያለዉ ትዉልድ የአብነቱን ትምህርት ብዙም የሚፈልገዉ አይመስልም፤ ምክንያቱም መንፈሳዊዉን ትምህርትና አገልግሎት እንደ ዓለማዊ የስራ መስክ ቆጥሮት ለገቢ ማስገኛ ስለሚያዉለዉ ለአጭር ወራት ተምሮ በየአደባባዩ መታየትንና ራሳን መካብ ነዉ የሚፈልገዉ። ለዚህም ነዉ ቃሉን እንደ ሽቀጥ የሚነግዱበትና በሕይወት ሳይኖሩ «መምህር፣ መምህር።» ብቻ በመባል የሚመላለሱት፤ መልካም ስነምግባር የሌላቸዉ፤ ምዕመኑን የሚያሰናክሉና የሚያስመርሩ አስመሳይ አገልጋዮች የተፈጠሩት።

አሁን አሁንማ አንድፊቱኑ «በዋሻና በገዳም ተሰዉረን በኖርን ይሻላል» እስከማለት ደርሰናል። እና ምእመናን፤ አሁን ለነፍሳችሁ የሚያስብ፣ የሚያዝን፣ የሚራራ እዉነተኛ እረኛ እንዳገኛችሁ ተረድታችሁ በእኝህ አባት ልትጠቀሙ ይገባል እንጂ «ለምን ጻድቃን ፣ ቅዱሳን አይሉንም።» በማለት ያሰማችሁት ቅሬታ አግባብ አለመሆኑን እነግራችኋለሁ። ስለዚህ በላያችን ላይ የተመደቡት ሰላዮች ወደ ላይ ሪፖሪት አድርገዉ እስከሚያስባርሯቸዉ፣ እንደአስፈላጊነቱም እስከሚያሳስሯቸዉና እሰከሚያስደበድቧቸዉ ድረስ ተጠቀሙባቸዉ። በዚህች ሳምንት ስብከታቸዉ እንኳ ብዙ ምእመናን ወደ ንስሐ ቀርበዋል፤ «ሥጋዉና ደሙን እንዴት አድረገን ነዉ የምንቀበለዉ?» በማለት ሲጠይቁ ተደምጠዋል፤ ከወላጆቻቸዉ የወረሱትን ጨሌ አምጥተዉ አቃጥለዋል፤ ከባዕድ አምልኮ እንደሚለዩ ቃል ገብተዋል። እናንተም በእዉነት በእግዚአብሔር መንግስት ሕያዉ ሆናችዉ መኖር ከፈለጋችሁ እንደዚህ አይነት አባቶችና ወንድሞች ናቸዉ የሚጠቅሟችሁ። ሌሎቻችን በእግዚአብሔር ፣ በእመቤታችን ድንግል ማርያም፣ በቅዱሳን መላእክትና በቅዱሳን ሰዎች ስም የምንነግድ የጻድቃንን ፈለግ የማንከተል፤ እንደ ቃሉ ሆነን የማንገኝ አስመሳዮች ነን።» በማለት ምላሽ የሰጧቸዉ ሲሆን፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ በመልሳቸዉ ስለተበሳጨዉ ከዛች እለት ጀምሮ እስከ

አሁን ድረስ ለመበቀል  በእሳቸዉ ላይ ጭምር ነገር እያሴርኩባቸዉ እገኛለሁ፡፡» **ይላል የእዉነት ተቃዋሚ ዲያብሎስ ከግብረአበሮቹ ጋር በመሆን፡፡**

# ምእራፍ አራት

« አንዳንድ ለኢየሱስ የቀኑ የመሰላቸዉ «አገልጋዮችና አማኞች ነን» የሚሉ፤ « እግዚአብሔር ሆይ! እኛ የዳነዉ በላከዉ ልጅህ አማካይነት ነዉ:: ሉሙም ኢየሱስ ነዉ:: ታዲያ ስለምን አንተንና ተላላኪህን ኢየሱስን ብቻ አናምንም? አናመከልክም? አናመሰግንም? ስለምን የኢየሱስ እናት የማርያም ስም አብሮ ይነሳል? ስለምን አብራ ትከብራለች? ስለምን «ገብርኤል፣ ሚካኤል» እየተባለ ስማቸዉ ከአንተ ጋር ይነሳል? ስለምን «ጊዮርጊስ፣ ተክለሃይማኖት፣ አርሴማ» እየተባለ ስማቸዉ አንተ በምትጠራበት ቦታ ላይ ይጠራል? እነሱም ፍጡሮች እኛም ፍጡር ነንና ስለምን ከእኛ በላይ እናከብራቸዋለን? በተለየ ሁኔታስ ስማቸዉን እናስባለን? እኛ ለአንተና ለአማላጃችን ኢየሱስ ቀንተናልና «የሱስ» እያልን የልጅህን ስም ስንጠራና ስናገን ብዙ «አማኞች ነን» የሚሉ በጨለማ ሕይወት ያሉ ሰዎች ይቃወሙናል:: ከተለያዩ አማልእክቶቻችሁ ተለዩ ስንላቸዉ ደግሞ «መናፍቅ እያሉ» ስማችንን ያጠፋሉ:: ስለዚህ እኛ ለየሱስ ስም ቀንተናልና እነዚህ ጣዖት የሚያመልኩ የኦርቶዶክስን አማኞች ከምድሪቱ አጥፋ፤ ወደ እኛ በረት ሰብስባቸዉ» በማለት ጸሎትና እንባ ጭምር ሲያቀርቡ፡

እግዚአብሔር የአንዳንድ አላዋቂዎችና እዉነተኛዉ የድንግል ማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ያገኙ መስሏቸዉ ወደዚህ ድርጅት ዉስጥ ባለማወቅ የገቡትን የየዋህን ልቦናቸዉን ተመልክቶ «እናንተ ለመሆኑ እግዚአብሔርና ኢየሱስ ልዩነት አላቸዉ ወይ? ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አንሶ የተላለኪነትና የማማለድ ተግባር ይፈጽማል ወይ? እናንተ «የሱስ(ኢየሱስ)» የምትሉትና ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ አይነት ናቸዉ ወይ? ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አንሶ ከእርሱ በላይ ላለዉ የሚያማልድና የእርሱ ተላላኪ ከሆነ ከቀደሙት ነብያት የተለያየ መከራ ከተቀበሉት፣ ደማቸዉ ካፈሰሱት፣ በተለያየ መንገድ ከአስመሳይ አገልጋዮችና ከማያምኑ ሰዎች ከተሰቃዩት ፍጡራን ሰዎች በምን ትለዩታላችሁ? ምክንያቱም አማለጅ ሆነ ተላላኪ የሚሆነዉ ያዉ ፍጡር ስለሆነ፤ ከእግዚአብሔር እኩል ተደርጎ ሊቆጠር ቀርቶ ሊተካካል የማይችል በመሆኑ የተለየ አምልኮ ሊፈጸምለት አይገባምና:: ለመሆኑ እናንተ ስሟን የምታቃልሉትና እለት እለት የምታዋርዷት፣ የምትሰድቧት ድንግል ማርያም የማን እናት ናት? የአማላጁ የሱስ ወይስ የተማለጁ ኢየሱስ? ወይስ የፍጡር ተግባር የሚሰራዉ አማለጁ ኢየሱስ ወይስ የሁሉ ፈጣሪ የሆነዉ የተማላጁ እግዚአብሔር?

የምትጠሏቸዉና የምታጥላሏቸዉ ቅዱሳን መላእክት ሆኑ ቅዱሳን ጻድቃን ሰዎች የሚኖሩት በኔ መንግስት ዉስጥ ስለሆነ እንዴት ከምትጠሉትና ከምታጥላሉት ጋር አብራችሁ መኖር ትችላላችሁ? ወይስ እናንተ ከዚህ ሥጋችሁ ተለይታችሁ ስትመጡ ስለምትጠሏቸዉና

ስለምትንቋቸዉ እነሱን አዉጥቼ እናንተን የማስገባ ይመስላችኋልን? እናንተስ እነሱ ባሉበት አንገባም ልትሉ ይሆን? ህብረታችሁና አንድነታችሁ ከእነርሱ ጋር ካልሆነ ከማን ጋር ልታደርጉ ነዉ? ወይስ የእነሱ ተቃራኒ ከሆኑት ሰይጣናት ጋር ለማድረግ ፈልጋችሁ ይሆን? በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት፣ በመልካም ተግባር ሆነዉ ራሳቸዉን ክደዉ ስለ እዉነት በመመስከራቸዉ ምክንያት ከፍ ከፍ ስላደረኳቸዉ እንደ ሰይጣናት በቅናት ተቃጥላችሁ ይሆን? ወይስ እኔ በባለሟሎቼ ከፍ ከፍ በማለታቸዉ እንደእናንተ የምቀና መስሏችሁ ይሆን? እነሱ ከፍ ከፍ ማለትንና መግነንን የሚፈልጉ መስሏችሁ ይሆን? እኔ ስለፈቀድኩና በተለየ ሁኔታ መታሰቢያ ተደርጎላቸዉ እንዲከበሩ ስለፈለኩ ነዉ እንጂ እነሱ አንዳች መመስገንን ሆነ መግነንን እንደማይፈልጉ አታዉቁምን? እናንተም እኮ የእነሱን ፈለግ ተከትላች በቅድስናና በብቃት ሕይወት ብትኖሩና እስከ መጨረሻዉ ታምናችሁ ወደ እኔ ብትመጡ እናንተ ባትፈልጉት እንኳ እኔ ስለቅድስናና ጽድቅ ስራችሁ በእዉነተኛ አገልጋዮቼና አማኞቼ ዘንድ እንድትታሰቡ አስደርግ ነበር፡፡

ነገር ግን እናንተ ጎሊናችሁ እዉነትን ስለማይፈልግና ለዲያብሎስ አሳልፋችሁ ስለሰጣችሁት ይኸዉ እንደ ካስ ይጫወትባችኋል፡፡ እኔን ከእግዚአብሔርነቴ አሳንሳችሁኝ በእኔ በሁሉ ፈጣሪ አምላክ ሌላ እግዚአብሔር ሾማችሁብኝ እለት እለት ትሰድቡኛላችሁ፤ ታዋርዱኛላችሁ፡፡ ለመሆኑ ስለ አብ ሆነ ስለመንፈስ ቅዱስ ማነዉ የነገራችሁ? እኔ አይደለሁምን? «እኔና አብ አንድ ነን፡፡» ያለዉ ማነዉ? «እኔን ያየ አብን አየ» ብሎ የተናገረ ማነዉ? «እኔ ስለእናንተ አብን የምለምን አይምሰላችሁ፤ በስሜ ለምኑ ሁሉን እኔ አደርገዋለዉ» ያለዉ ማነዉ? እኔ አይደለሁምን? እናንተ ግን ልታለያዩንና ልታበላልጡን ትፈልጋላችሁ!

አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የምናባል በስም፣ በአካል፣ በግብር ሶስት የሆን፤ በመፍጠር፣ በህልዉና፣ በስልጣን፣ በክብር፣ በአገዛዝ፣ በመለኮት፣ ባጠቃላይ በባሕርይ አንድ የሆን የማንበላለጥና የማንተናነስ ነን፡፡ ለዐይን ቅጽበት እንኳ መቀዳደም በኛ ዘንድ የለም፡፡ «የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ!» በሚል አርስት በመጀመሪያ መልእክቴ በክፍል ሁለት ዉስጥ የተገሰጻችሁበትን አላነበባችሁምን? ይኸዉም፡

«እናንተ ኢየሱስ ክርስቶስን በነብይነት፣ በአማላጅነትና በፍጡር ደረጃ የምትቀበሉ፤ በውኑ የእግዚአብሔር ቃልን ማስተዋል በእናንተ ዘንድ አለን? አንዳች የለም፡፡ ቢኖርማ እርሱ ከእግዚአብሔር የሆነ፤ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ያነሰ እውነተኛ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ሰው ሆነ ሌላ ፍጡር፤ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተካክል ማን ደፋር ነው? «እኔና እግዚአብሄር አንድ ነን» የሚል ማን ደፋር ነው? «እኔ አልፋና ዖሜጋ መጀመሪያውና መጨረሻው ፊተኛውና ኋለኛው ነኝ» የሚል የትኛው የእግዚአብሄር መልእክተኛ ነው? «እኔን አያችሁ ማለት እግዚአብሔርን አያችሁ ማለት ነው» ብሎ የሚያስተምር የትኛው

የእግዚአብሄር መልእክተኛ ነው? የእግዚአብሔርን ስም ሳይጠራ በራሱ ስልጣን ሊያድን፣ ሊፈውስ፣ ይቅር ሊል የሚችለው፤ በአጠቃላይ የእግዚአብሔር መልእክተኛ የሆነ ፍጡር ማነዉ ደፋር ነዉ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተካክለው!?

ታላቁ የእምነት አባታችሁ አብርሃም እንኳን፤ የእግዚአብሔርን ክብርና የራሱን ማንነት ተረድቶና አስተዉሎ «እኔ አፈርና አመድ ነኝ» ያለው፤ ታላቁ ንጉሥ እንደ ልቤ የተባለው ዳዊት«እኔ ትል የሞተ ውሻ ነኝ » ያለው፤ ታላቁ ሐዋርያ ጳውሎስ «እኔ ጭንጋፍ ጥራጊ ነኝ» ያለው፤ ታድያ በእምነታቸው ታላቅ የተባሉ እግዚአብሔር ቅድስና ማእረግ የሰጣቸው አባቶች፤ ምንም እንኳን አካሄዳቸው ከእግዚአብሔር ጋር ቢሆንም የአምላካቸውን ቅድስናና ክብር የራሳቸውን ደካማነትና ማንነት በሚገባ ስለተረዱና መሪያቸው መንፈስ ቅዱስ ሰለሆነ፤ የበዛላቸውን ጸጋ ቦታ ሳይሰጡት፤ ራሳቸውን በእግዚአብሔር ፊት አዋርደዋል፤ ዝቅ ዝቅ አድርገዋል ፡፡

ታላቁ ነብይ ሙሴ ፤ ምንም እንኳን አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ያደረገ እግዚአብሔርም ከፍ ከፍ ያደረገው ቅዱስ አገልጋይ ብዙ ተኣምራትን በእግዚአብሔር ስም ያደረገ ቢሆንም፤ በመጨረሻ ሰዓት በእስራኤል ልጆች መካከል በምድረ በዳ የእግዚአብሔርን ስም ሳይጠራ በራሱ ስልጣን ውሃ አውጥቶ በመስጠቱ ተገስጿል፤ ተስፋ የተሰጣቸውን የከነዓንን ምድር በርቀት ተመለከታት እንጂ አልገባባትም፡፡ እግዚአብሄር በአምልኮቱ ቀነኢ ነውና ፍጡር ሆነ የእርሱ መልእክተኛ እንኳን ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያስተካክለውን ቀርቶ በሚገባ የማያከብረውን ይገስጻል፤ ይቀጣል፤ ያዋርዳል፡፡

እንግዲህ እናንተ ማስተዋል ያጣችሁ የአዳምና የሔዋን ዘሮች፤ እኔ አምላካዊ ባህርዬን ዝቅ አድርጌ ሰው ሆኜ በዚህች ምድር ላይ በምመላለስበትና በማስተምርበት ወቀት በዘመኑ ለነበሩ የተናገርኩትን ሕያው ቃል የኔን መከራ በማሰብ በሐዘን የኖረው እጅግ የምወደው ደቀመዝሙሬ ዮሐንስ በወንጌሉ ላይ እንደጻፈላችሁ « እኔ ና አብ አንድ ነን፣ እኔን ያየ አብን አየ፣ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በኔ አለ፣ ማንኛውም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ፣ እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ሕያዋን ትሆናላችሁ፣ ትዕዛዜን በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ፣ ራሴን እገልጽለታለሁ፤ ስለ እናንተ አብን እንደለምን የምላችሁ አይደለሁም፡፡» እያለ ያስተማረውና የተናገረው ማነው? እኔ አይደለሁምን፡፡ ታድያ ፍጡር፣ ነብይ ፣ የእግዚአብሔር መልእክተኛ አማላጅ ሆኖ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚያደርግ አለን! ? ከላይ የተነገሩትን አባባሎች ደፍሮ የሚናገር የእግዚአብሔር መልእክተኛ አለን ? እግዚአብሔር በባሕርይው ለአምላክነቱ ቀናኢ የሆነ እንጂ፤ የሚደፋፈረውን ፍጡር ሆነ ነብይ ወይም አማላጅ ዝም የሚል ይመስላችኋልን !? እኔ ግን በባሕርይ፣ በህልውና፣ በአገዛዝ፣ በስልጣን፣ በመፍጠር፣ ከአብ ጋር ፍጹም አንድ የሆንኩ ፤የማንበላለጥ፣ የማንቀዳደም፣ የነበርን፣ ያለን ፣ ሕያው ሆነን የምንኖር ስለሆነ፤ አምላካችሁና ፈጣሪያችሁ በመሆኔ፤ ከላይ ያሉትን ትምህርቶች ሰጥቻለሁ፡፡ እናንተ ግን ማስተዋል የጎደላችሁ ስለሆነ፤ የምትሰናከሉበትን ቃላት እየመረጣችሁ በሞትና በክህደት ሕይወት ትመላለሳላችሁ፡፡

ይህው ምርጡ ደቀመዝሙር ዮሐንስ በራእይ መፅሐፉ የጻፈላችሁን አስተውሉ «ያለውና የነበረው የሚመጣው ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ» ይላል ፡፡ እንዲህም አለ «አትፍራ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፤ ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፤ የሞትና የሲዖል መክፈቻ አለኝ ፡፡» እንዲህ ብሎ ጻፍ «ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል» ታድያ ማነው ፍጡር፣ ነብይ ፣ አማላጅ ሆኖ ራሱን «ፊተኛውና መጨረሻው፣ አልፋና ዖሜጋ፣ የነበረው ሕያውም የሆነው» እያለ የእግዚአብሔርን ስምና ክብር የሚይዝ አለ ወይ? እንዲህ ሲል እግዚአብሔር ዝም ይለዋል ወይ? ከእግዚአብሔር እንደሆነ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል ወይ? እኔ ግን እግዚአብሄር ስለሆንኩ ከላይ የተባሉትን ተናገርኩ፡፡ እናንተ ግን በቅን ሐሳብና በመልካም ሕይወት ሆናችሁ እውነትን ስላልፈለጋችሁ፤ እግዚአብሔር መሆኔን አላስተዋላችሁም፡፡ ከዚያም አልፋችሁ ክዳችሁኝ ታስክዱኛላችሁ፤ ሰድባችሁ ታሰድቡኛላችሁ፤ ተጠራጥራችሁኝ እንዲጠራጠሩኝ ታደርጋላችሁ፤ ታድያ እንዴት እጅግ የባሰ ፍርድ አትቀበሉም!? በደንብ ትቀበላላችሁ ፡፡

እናንት በቅዱሳን መጽሐፍ ላይ የተጻፈዉን የማታስተዉሉ ክፉ ትንቢት ፈጻሚዎች ብትሆኑም የዋሀን እንዳይሰናከሉ፤ እኔም እንደፍጡር ምዕራፍና ቁጥር እየተቀስኩ ላስረዳችሁ፤ «ሰዎች ሁሉ አብን እንዲያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ ፍርድ ሁሉ ለወልድ ሰጠሁ እንጂ አብ በአንድ ሰው ስንኳ አይፈርድም፡፡» ዮሐ. ፭፥፳፪-፳፫(5፥22-23)፣ ማነው ፍጡር ሆነ፤ የእግዚአብሔር መልእክተኛ አማላጅ እንደ እግዚአብሔር አክብሩኝ የሚል? «አብን ያየ ማንም የለም ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር እርሱ አብን አይቷል፡፡ እውነት እላችኋለሁ በኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፡፡» ዮሐ.፮፥፵፮-፵፯(6፥46-47)፡፡ማነው ፍጡር ሆኖ እግዚአብሔርን እንደ እግዚአብሔርነቱ በአማናዊ ባሕርይው ያየው?

«እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም» ዮሐ. ፰፥፲፪(8፥12)፣ የትኛው ፍጡር ወይንም የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው እንደዚህ በድፍረት ሊናገር የሚችለው ?

«መልካም እረኛ እኔ ነኝ፣ አብ እንደሚያውቀኝ እኔም አብን እንደማውቀው የራሴን በጎች አውቃለሁ የራሴም በጎች ያውቁኛል ነፍሴም ስለበጎች አኖራለሁ፡፡ ከዚህ በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ እነርሱንም ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምጼንም ይሰማሉ **አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ**፡፡» ዮሐ. ፲፥፲፬-፲፮(10፥14-16)፣ ማነው ፍጡር ሆኖ ወይንም ከእግዚአብሔር ያነሰ ሆኖ እግዚአብሔርን እንደ አምላካዊ ባሕርይው አውቀዋለሁ ብሎ በእርግጠኝነት ስለሚሆነው ነገር መናገር የሚችል? እኔ ግን እግዚአብሔር ነኝና በእርግጠኝነት ተናገርኩ፡፡ እንግዲህ በጎቼ የሆናችሁ ወደ እውነተኛዉ ቤቴ ትመጣላችሁ፤ በአንድ እረኛም ትጠበቃላችሁ፡፡

«እኔና አብ አንድ ነን፡፡» ዮሐ.፲፥፴(10፥30)፣ የትኛውም ፍጡር ወይንም የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነዉ እኔና እግዚአብሔር አንድ ነን የሚል፡፡ ፍጡር ሆኖ ከእግዚአብሔር የሆነ ይህን የድፍረት ቃል ቢናገር የደቂቃ እድሜ እግዚአብሔር የሚሰጠዉ ይመስላችኋልን!?

አይሰጠዉም፤ያዋርደዋል፤ ያጠፋዋል እንጂ። እኔ ግን ከኔ በላይ ማንም ስለሌለ ፈጣሪ እግዚአብሔር ስለሆንኩ በድፍረት ይህን አልኩ።

«እኔ የአባቴን ስራ ባላደርግ አትመኑኝ ባደርገው ግን፣ እኔን ስንኳ ባታምኑ አብ በኔ እንደሆነ እኔም በአብ እንደሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ።» ዮሐ. ፲፥፴፯-፴፰(10፥37-38)፣ ራሱ እግዚአብሔር ካልሆነ በስተቀር ማነው እንዲህ ደፍሮ ሊናገር የሚችለው ?

«ኢየሱስም - እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። እኔንስ ብታውቁ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር። ከአሁን ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል አለ ።

ፊልጶስ - ጌታ ሆይ አብን አሳየና ይበቃናል አለው። ኢየሱስም አለው - አንተ ፊልጶስ፣ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል እንዴትስ አንተ - አብን አሳየኝ ትላለህ? እኔ በአብ እንዳለው አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁ ቃል ከራሴ አልተናገርሁ፤ ነገር ግን በኔ የሚኖረው አብ እርሱ ስራውን ይሰራል። እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ባይሆንስ ስለራሱ ሰለ ስራው እመኑኝ ።

እውነት እውነት እላችኋለሁ በኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ስራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፣ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና አብም ስለወልድ እንዲከብር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ። ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ።» ዮሐ.፲፬፥፮-፲፬)14፡6-14፣ እናንተ ማስተዋል የጎደላችሁ፤«ኢየሱስ ነብይ ነዉ፣ አማላጅ ነዉ፣ ፍጡር ነዉ» እያላችሁ የምትሰድቡኝ፤ ከእግዚአብሔርነቴ ያሳነሳችሁኝ፤ ነገረ መስቀሌን ከንቱ ያደረጋችሁ፤ ማነው ፍጡር ከእግዚአብሔር ያነሰ ሆኖ ይህን ቃል ሊናገር የሚችል? እኔ ራሴ እግዚአብሔር ሰለሆንኩ በድፍረት የተናገርኩት፤ ከኔ በላይ አለቃ የኔ ፈጣሪ የለምና፤ እኔው ነኝ የነበረው፣ ያለው፣ ሕያው ሆኖ የሚኖረው አምላክ ።

«ይህን በምሳሌ ነግሬአችኋለሁ፤ ነገር ግን ስለ አብ ለእናንተ በግልጥ የምናገርበት እንጂ ከዛ ወዲያ በምሳሌ የማልናገርበት ሰዓት ይመጣል ። በዚያም ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ እኔም ስለእናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም፤ እናንተ ስለወደዳችሁኝ ከእግዚአብሔር ዘንድ እኔ እንደ ወጣሁ ስላመናችሁ አብ እርሱ ራሱ ይወዳችኋልና ። ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ደግሞ ዓለምን እተወዋለሁ ወደ አብም እሄዳለሁ ።» ዮሐ. ፲፮፥፳፭-፳፰(16:25-28)፣ ያለው እኔ አይደለሁምን? ታድያ እናንተ እኔ ሁሉን አድራጊ ሆኜ ሳለ ከእግዚአብሔርነቴ አሳንሳችሁኝ አማላጅ ነው እያላችሁ የምትሰድቡኝ፤ የምታስክዱኝ፤ በውኑ እናንተ ክርስቲያን የሚለውን ስም ስለያዛችሁ ከኔ የሆናችሁ ይመስላችኋልን? እናንተ የዲያብሎስ ናችሁ። እርሱ እኔን ለማስካድና ለማስቆጣት በፈጠረላችሁ «ኢየሱስ፣ ክርስቲያን» የሚል ስያሜ እንድትጠቀሙ እያደረገ ከሕይወት መንገድ ወደ ሞት፣ ከእምነት ወደ ክህደት የወሰዳችሁ ናችሁ ።

«ያለውና የነበረው የሚመጣው ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክ አልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል።» ዮሐ.ራዕይ ፩፥፰(1:8)፣ «ባየሁት ጊዜ እንደሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ ስር በታች ወደቅሁ ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህ አለኝ - አትፍራ፣ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፣ሞቼም ነበርሁ እነሆም ፣ ከዘለዓለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፣ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ። እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ።» ዮሐ.ራዕይ፩፥፲፯-፲፱(1:17-19) ብዬ እጅግ ለምወደው ደቀ መዝሙሬ ዮሐንስ የተናገርኩት እኔ አይደለሁምን? እኔ አልፋና ዖሜጋ መጀመሪያና መጨረሻ ፈጣሪ እግዚአብሔር ባልሆን ኖሮ፤ እንዲህ ብዬ እናገራለሁኝ? ሰው ባልሆን ኖሮ ሞቼም ነበርሁ ብዬ ይህንን ቋንቋ እጠቀም ነበርን? ለእናንተ ስል ነው ባሕርዬን ብቻ ዝቅ አድርጌ ካለሁበት ቦታ ሁሉ ሳልጎል፤ አምላክነቴ ሳይለወጥ፤ ክብሬ ሳይቀነስ ሰው የሆንኩት ።

«በሰምሬኔስም ወደለው ቤተ ክርስትያን መላእክ እንዲህ ብለህ ጻፍ - ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል» ዮሐ.ራዕይ ፪፥፰(2:8) ብሎ የተናገረው እኔው እግዚአብሔር አይደለሁምን? እኔ ሞቼ ነበር ብዬ ስናገር ያላፈርኩ፤ እናንተ ግን እግዚአብሔር ሰው ሆነ፣ መከራ ተቀበለ፣ ተሰደበ፣ ተገረፈ፣ በመስቀል ላይ ተሰቀለ፣ ሞተ፣ ተቀበረ፣ በሶስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ ፣ ከዚያም ወደ ቀደመው ክብሩ ተመለሰ፣ ዐረገ ለማለት ይከብዳችኋል፤ ታፍሩበታላችሁ። ተጠራጥራችሁ ታጠራጥራላችሁ። እናንተ በውኑ ከእኔ ትበልጣላችሁን? የማንስ መልእክተኞች ናችሁ? የሚያጠራጥራችሁ የዲያብሎስ ናችሁ።

« በትያጥሮንም ወዳለው ወደ ቤተክርስትያን መላአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ - እንደ እሳት ነበልባል የሆኑ ዓይኖች ያሉት በእቶንም የነጠረ የጋለ ናስ የሚመስሉ እግሮች ያሉት የእግዚአብሔር ልጅ እንዲህ ይላል» ዮሐ.ራእይ፪፥፲፰(2:18) ብሎ የተናገርው እኔ የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ የተባልኩት አምላካችሁ ፈጣሪያችሁ ጌታችሁ ኢየሱስ ክርስቶስ አማኑኤል መድኃኔዓለም አይደለሁምን? ስለምን በእግዚአብሔርነቴ ትጠራጠራላችሁ ? ስለ አብ ሆነ ስለ መንፈሰ ቅዱስ ማወቅ የምትችሉት በመጀመሪያ እኔን እንደ እግዚአብሔርነቴ ስታውቁኝና ስታምኑብኝ ብቻ ነው! ያኔ እኔ ወልድ ቃል የተባልኩትን ፣ አብን ፣ መንፈስ ቅዱስን በሚገባ ታውቃላችሁ፤ መጀመሪያ እኔን ሳታውቁ አብንም፣ መንፈስ ቅዱስንም በአጠቃላይ እውነት የተባላችሁን በምንም ዓይነት ልታውቁ አትችሉም። እኔ ብቻ ነኝ የእውነት ምስጢር የምገልጽ፤ በዚህች ምድር ሁኑ በሌላ ዓለም ሁኑ ቤትም ስፍራ ሁኑ ሁሉን የምቆጣጠር፤ የማውቅ የሁሉ ፈጣሪና አስገኚ እኔ ብቻ ነኝ። ከኔ በላይ እኔን የሚያዝ እኔን የፈጠረ ማንም የለም። የነበረ ያለሁ ሕያው ሆኜ የምኖር አልፋና ዖሜጋ እኔ ብቻ ነኝ።

ከዚህ በተጨማሪ ምንም ዓይነት ጥርጣሬ እንዳይገባችሁና እንዳትሰናከሉ ይኸው እጅግ ለምወደው ደቀመዝሙር ለዮሐንስ የገለጽኩለትን ምስጢር በወንጌሉ መጀመሪያ ላያ «በመጀመሪያ ቃል ነበር፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፣ ቃልም እግዚአብሔር ነበር። ይህ በመጀመሪያዉ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር። ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ስንካ ያለ እርሱ አልሆነም ። በእርሱ ሕይወት ነበረች፣ ሕይወትም የሰው ብርሃን ነበረች።»

ዮሐ.፩፥፩-፭) 1:1-5 ና «ቃል ስጋ ሆነ ጸጋንና እዉነትንም ተሞልቶ በእኛ አደረ፣ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለሁ ክብር የሆነዉን ክብሩን አየን።» ዮሐ.፩፥፲፬-፲፭(1:14-15) ብሎ የጻፈላቸሁ፤ ከኔ ሌላ ፈጣሪ እንደሌለ፣ መጀመሪያውም መጨረሻውም የሁሉ አስገኝ እንደሆንኩ እንድታዉቁና እነደ እግዚአብሔርነቴ እንድታመልኩኝ ነበር። ይሁንና ውስጣችሁ አመጻና ትዕቢት፣ ክፋትና ተንኮል ስለሞላባችሁ ወደ እውነት ማወቅ ልትመጡ አልቻላችሁም።

እናንተ በእውነተኛ እምነት ውስጥ ሆናችሁ ነገር ግን ተጠራጣሪዎች የሆናችሁ፤ በጎቼ እንዲጠራጠሩ በማድረግ በሁለት ልብ ያላችሁ፤ እኔ ስናገር ያላፈርኩትን «ሞቼም ነበርሁ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ» እንዳላልኩ «ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል» እንዳላልኩ፤ እናንተ ምንድናችሁና ነው? የኔን መከራ መቀበል፣ መሰቀል፣ መሞትና መነሳት ለመመስከር መድፈር ያቃታችሁ? እንኳን እኔ፤ እናንተም እኮ አትሞቱም፤ ነገር ግን ቋንቋችሁ ስለሆነ ነፍስ ከሥጋ ስትለይ «ሞተ» ስለምትሉ፤ ይህንኑ ቋንቋችሁን ተጠቅሜ« ሞቼም ነበርሁ ሞቶ የነበረው» እያልኩ ስናገር እንደ እናተ ፍጡር ወይስ ከእግዚአብሔር ያነስኩ መልእክተኛ ተላላኪ አድርጋችሁ ቆጠራችሁኝን? ወይስ ለኔ ቀንታችሁ እንዴት እግዚአብሔር ተሰቀለ፣ ሞተ እንላለን እያላችሁ ጥብቅና ቆማችሁልኝ ነውን? አስመሳይ ሸንጋዮች፤ በእምነታችሁ ባዶ የሆናችሁ፤ ፍሬ የማታፈሩ የወንጌል እንቅፋቶች ናችሁ። እናንተም ወደ መንግስቴ አትገቡም ሌላውም እውነትን አውቆ ሰማያዊ መንግስቴን ወርሶ ከኔ ጋር እንዳይኖር ማሰናከያ ሆናችሁ። የባሰ ፍርድ ይጠብቃችኋል።» ብዬ ነዉ እናንተንና መሰሎቻችሁን የገሰጽኩት።

እንግዲህ ያ የምታመልኩትና የምታስመልኩት የዲያብሎሱ የሰ-ስ ከሞት የሚያድናችሁና ወደ መንግስተ ሰማያት የሚያስገባችሁ ከሆነ እለት እለት ልታመልኩትና ልታስመልኩት ትችላላችሁ። እኔ ግን አልፋና ዖሜጋ መጀመሪያዉና መጨረሻዉ የሁሉ ፈጣሪ ካለእኔ ፈቃድ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊደረግ የማይችል፤ ሁሉ በኔ ለኔ የሆነ ለእያንዳንዱ እንደስራዉና እምነቱ የምፈርድለትና የምፈርድበት እግዚአብሔር የሆንኩ፤ እኔን ማንም ሊያዘኝ ሆነ ሊያስገድደኝ የማይችል፤ እናንተን የሰዉ ዘሮችን ለማዳን የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ገደማ ከመዳኛችሁ ምክንያት ከአደራ እናታችሁ ድንግል ማርያም ከአካሏ አካልን ከባሕርይዋ ባሕርይ ነስቼ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በመሆን በተዋህዶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ ሆኜ የተገለጽኩትና የተለያየ መከራ ተቀብዬ በመስቀል ላይ የተሰቀልኩት የባሕርይ አምላክ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ነኝ።

ስለዚህ ሕይወትን ከፈለጋችሁ ከዚህ ከሞተና ከክህደት እምነታችሁ ተለይታችሁ እግዚአብሔር በአንድነትና በሦሥትነት የሚመለክበት፤ የመዳኛችሁ ምክንያትና መጽናኛችሁ እናቴ ድንግል ማርያም የምትፈቀርበትና በተለየ ሁኔታ የምትከበርበት፤ ቅዱሳንና ጻድቃን

በሚታሰቡበት፤ ብቸኛዋ የሕይወት መንገድን የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖትን ተከተሉ:: እንድ እምነቷና ስርዐቷ ብቻ ተመላለሱ:: «አይ እኛ የሱስን(ኢየሱስ) ነዉ የምንከተለዉ» ብለችሁ በዐመጻችሁ ከጸናችሁ ደግሞ በኔ ዘንድ አንዳች አድሎ ፍርድ የለምና በስሜ ነዉና የነገዳችሁት ሕዝቡንም ያሰናከላችሁት ከማንም በላይ የባሰዉን ፍርድ እንደምትቀበሉ አሳዉቃችኋለሁ::

እናንተ ኢትዮጵያዉን በዚህ የፕሮቴስታንት ወይንም የዐመጻ እምነት ዉስጥ የገባችሁ፤ ሌላዉ ዓለም «ከወላጆቹ በወረሰዉና ሌላ አማራጭ በማጣት በዚህ እምነት ዉስጥ ገባ» ይባላል፤ የእናንተ ከእዉነተኛ የሕይወት መንገድ ዉስጥ ወታችሁ በዚህ የክህደትና የዐመጻ እምነት ዉስጥ መግባታችሁ ምን ይባላል! የእናት አገራችሁ ፍቅር ሳይኖራችሁና ታማኝ ሳትሆኑ እንዴት ያላያችሁት አገር የሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም ፍቅር ሊኖራችሁ ይችላል? እንዴትስ ልትታመኑላት ትችላላችሁ? እንግዲህ ማስተዋሉ ካላችሁ እዉነትን ለመቀበል ፈቃደኛ ከሆናችሁ ኢትዮጵያና ተዋህዶ ሃይማኖት የአንድ ሳንቲም ገጽታ ናቸዉ:: በአገራችሁ ላይ ክህደትና ዐመጻ ፈጸማችሁ ማለት በተዘዋዋሪ በሃይማኖታችሁና በእምነታችሁ ላይ ክህደትና ዐመጻ መፈጸማችሁን ልትረዱ ይገባችኋል:: እንግዲህ እዉነትን የመቀበልና ያለመቀበል ምርጫዉ የእናንተ ነዉ:: የዐመጻዉ እምነት ይሻለናል ካላችሁ ምርጫችሁ ነዉ:: ነገር ግን በዚህች ምድር ዉስጥም ከቅርፊት ሥጋችሁም ተለያታችሁ ስትመጡም ነጻነታችሁ ተገድቦ በአንድ ቦታ ዋጋ ትከፍሉበታላችሁ:: ምርጫችሁ እዉነት ከሆነ እዉነት የምትላችሁን ፈጽሙ::» በማለት የመለሰላቸዉ ሲሆን፤

እኔ የጨለማዉ ገዥ ግን «በአቋማችሁ ጽኑ፤ አሁን የተናገራችሁ የኔ ተቃራኒ መንፈስ ነዉና አትቀበሉት፤ አትስሙት::የኔን መንግስት አወርሳችኋለሁ:: በመንግስቴም «ድንግል ማርያም፣ ቅዱሳን መላእክት፣ ነብያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን፣እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ» የሚባሉ ስለሌሉ ካለምንም ሃፍረትና መሳቀቅ ትኖራላችሁ:: ቢበዛ እኔ ላይ የሚፈረደዉ ፍርድ ነዉ የሚገጥማችሁ::» በማለት አጽናኝቻቸዋለሁ::» **ይላል አታላዩና በዐመጻና በክህደት ሕይወት የሚያጸናዉ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ሰይጣናት ጭምር::**

# ምእራፍ አምስት

« አንዳንድ የኦርቶዶክ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮች የሆኑ ሴቶች ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በመሰባሰብ የደረሰባዉን ግፍና በደል እንዲሁም ርኩሰት ተግባር ለማሳወቅና መፍትሔ እንዲፈለግላቸዉ ለማሳሰብ አንድ ሌት ተቀን ስለ አዳም ዘርና ስለ አገራቸዉ ኢትዮጵያ የሚያነቡ አገልግሎታቸዉንም በእዉነትና በመንፈስ ለሚያከናዉኑ አባት አቀረቡ:: ይኸዉም « የተከበሩ የእግዚአብሔር አገልጋይ፤ መቼስ እንደዚህ በዝተን ሲያዩን ታቦት ለማንገስ የመጣን ሊመስሎት ይችላል:: ነገር ግን እኛ ከመላዉ ኢትዮጵያ ካሉ ከገጠርና ከከተማ አብያተክርስቲያናት ተወጣተን ምሬታችንን ወደ እርሶ ልናሰማና እርሶም ወደ ፈጣሪ አቤት እንዲሉልን ነዉ የመጣነዉ:: እኛ ለዘመናት የቤተክርስቲያናችንንና የሃይማኖታችንን ገበና አናወጣም ብለን ለራሳችን ምስጢር አድርገን ያለፉት አልፈዉ የቀረነዉ ነን በልባችን አምቀነዉ ስንብከነከንበት የነበረዉን በደልና ግፍ ለእርሶ ለማቅረብ እርሶም ለፈጣሪና ለሚመለከተዉ አካል ያሳዉቁልናል በሚል ተስፋ የመጣነዉ::

የተፈጸመብን ግፍና በደል አይነቱ ብዙ ሲሆን ጥቂቶቹን ለመግለጽ ያህል እኛ ምእመናን «የቤተክትስቲያን አገልጋይ ነዉ፣ ጳጳስ፣ መነኩሴ፣ ቄስ፣ መምህር፣ መርጌታ፣ ዲያቆን፣ ሰባኪ፣ ዘማሪ ነዉ::» ሲባል ከእግዚአብሔር ጋር የተለየ ግንኙነት አላቸዉ በሚል እምነት ትልቅ ቦታ የምንሰጥና በየዋህነት በግልጽ እንቀርባቸዋለን:: ታዲያ አንዳንዶቹ በጥሩ አንደበት የእግዚአብሔርን ቃል እየጠቀሱልን ከተግባባን በኋላ በጎሊናችን እንኳ የማናስበዉን የዝሙት ጥያቄ ያቀርቡልናል:: አንዳንዶቻችን ለጋብቻ እንበቃለን በሚል እምነት አብረን ዝሙትን እንፈጽማለን:: አንዳንዶቻችን በሥጋ ፍላጎታችን ተሸንፈን በዝሙት እንወድቃለን:: አንዳንዶቻችን ሳንፈልግ በግድ እንደፈራለን:: ታዲያ በዚህ ሂደት ዉስጥ አንዳንዶቹ «ኮንደም ስለምንጠቀም አታረግዙም ስለኮንደም አጠቃቀም እናስተምራችኋለን» እያሉ በማደፋፈር ነዉ ዝሙትን የሚፈጽሙት:: አንዳንዶቹ በንስሐ አባትነት ስም ቀርበዉ ነዉ ዝሙት የሚፈጽሙት:: አንዳንዶቹ ደግሞ በተለይ ቆብ የደፉት ሽጉጥ በማሳየት አስፈራርተዉ ነዉ ዝሙትን የሚፈጽሙት:: አንዳንዶቹ ወንጌልን እንሰብካለን በማለት ነዉ ዝሙት የሚፈጽሙት:: አንዳንዶቹ ደግሞ «ቅብአ ቅዱስ ልቀባሽ በማለት እራቁታችንን እንድንሆን አድርገዉ በማፍዘዝ ነዉ ዝሙት የሚፈጽሙት:: ታዲያ የዝሙቱ ሳያንስ አንዳንዶቹ ይገሉናል:: አንዳንዶቹ የተረገዘዉን ጽንስ በግድ እንድናስወርደዉ ያስገድዱናል:: አንዳንዶቹ ደግሞ «ልጁ የኛ አይደለም» በማለት ይክዱናል:: አንዳንዶች ደግሞ እንደ እቁባት አድርገዉ ሕይወታችንን ይጫወቱበታል:: አንዳንዶቹ ደግሞ በቂ ተቆራጭ ለዲቃላዎቻቸዉ አይደርጉም:: አንዳንዶቹ ሀብት ንበረታችንን ዘርፈዉ ይሄዳሉ:: አንዳንዶቹ እኛንም ቤተሰቦቻችንን በመተት ተብትበዉ ችግርና ስቃይ እንዲደርስብን አድርገዉ ይጠፋሉ:: የተወሰነዉን ደግሞ ቆብ

አስደፍተዉ ለቆብ ደፌዎች ስዉራን ሚስቶች ያደርጉናል፤ ብቻ ምኑ ተነግሮ ያልቃል ለዘመናት ታምቆ የነበረዉን ነዉ ለመተንፈስ የተገደድነዉ:: ሌላዉ ቢቀር ዲቃላ ልጆቻቸዉን እንኳ አምነዉ ለመርዳትና ለማሳደግ እንዲሁም ለማስተማር ፈቃደኞች አይደሉም:: አሁን ደፍረን ለመግለጽ የቻልነዉም በሚዲያ «አንድ መነኩሴ ከመንፈሳዊ ኮሌጅ የተመረቀ ቆቡን ጥሎ በተክሊል ሚስት አገባ::» ተብሎ ሲነገር ሰምተን፤«ይህማ ቆቡን ደፍቶ መልከስከስን ያልፈለገ እኛ ላይ ከተፈጸመዉ በደልና ግፍ አንጻር ሲታይ የቅድስና ተግባር ነዉ የፈጸመዉ » ብለን ነዉ ወደዚህ ደፍረን ለመናገር የመጣነዉ:: » በማለት ጉዳያቸዉን ሲገልጹ፤

እኛም አባት በሰሙት ሁሉ እያነቡ ነበርና ስሜታቸዉን መቆጣጠር ተስኗቸዉ « አይ አንተ ፈጣሪ፣  አይ አንቺ አዛኝቷ ምኑን ታሰሚኝ! ያለሁበት ወሰን የሌለዉ ኀዘን አንሶ ነዉ ይህ ኀሊናን የሚያደማና የሚያቆስል ልቋቋመዉ የማልችለዉን መርዶ የምታሰሚኝ? ይህን የዘመናት ችግር አንቺዉ መፍቴ መስጠት ተስኖሽ ነዉ ወደ እኔ የምትልኪያቸዉ? ምንስ አቅምና ብቃት ኖሮኝ ነዉ ለእንደዚህ አይነቱ መፍትሔ መስጠት የምችለዉ?  ከአንዳንድ ሰዎች በወሬ ደረጃ ብቻ « ዲያቆን እገሌ እንዲህ አደረገ፣ ሰባኪ እገሌ እንዲህ አደረገ፣ ዘማሪ እገሌ አደረገ፣ ቄስ እገሌ እንዲህ አደረገ፣ ጳጳስ እገሌ እንዲህ አደረገ፤.. ወዘተ» ሲባል መፈጠሬን እረግም ነበር:: አሁን ግን ይኸዉ በደሉና ግፉ የተፈጸመባችሁ፣ ለዝሙት ሕይወት የተዳረጋችሁ፣ ዲቃላ የታቀፋችሁ ካለምንም እፍረትና ይሉኝታ በቆራጥነት ለምስክርነት መጣችሁ::

አሁን በኔ በኩል የምላችሁ ነገር የለም:: ብቻ አይዟችሁ ስሜታችሁ አይጎዳ:: እናንተም በተዝዋዋሪ የኃጢአት ተባባሪ ሆናችኋል:: ይኸዉም «እንቢ ኃጢአት አልፈጽምም» በማለት ልታሳፍሯቸዉና በሌሎች እህቶቻችሁ ላይ ተመሳሰይ ተግባር እንዳይፈጸም ቢሰሟችሁም ባይሰሟችሁም ለሚመለከተዉ አካል ልታጋልጧቸዉና ክህነታቸዉን ልታሽሩ ሲገባ ዝም በማለታችሁ ነዉ ይኸው ለዘመናት ችግሩ እየባሰ፣  እየከፋና እየከረፋ የመጣዉ:: አሁን ግን የሆነዉ ሆኗል ስላለፈዉ እናንተም ንስሐ ግቡ እነሱም ለንስሐ እንዲበቁ ጸሎታችንና ምኞታችን ነዉ:: ስለወደፊቱ ግን የርኩሰቱ ጽዋ ሞልቶ እየፈሰሰ ነዉና አስመሳይ አገልጋዮችና አሰናካዮች ዋጋ እንደሚከፍሉበት ልታዉቁ ይገባችኋል:: እም አምላክም ድንግል ማርያም ከልጇ ከወዳጇ ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ መፍትሔ እንድታመጣ እኔም ሆንኩ ወንድሞቼ እናንተም በጋራ ልንጸልይና ልናለቅስ እንዲሁም ምህላ ልናደርግ ይገባል:: በአንዳች ነገር ተስፋ እንዳትቆርጡ፤ በቅርቡ እግዚአብሔር ሁሉን እንደሚያስተካክልና ለነፍሳችሁ የሚቆረቆርና የሚያዝን እረኛ እንደሚሰጣችሁ እተማመናለሁ::» በማለት ቢያጽናኗቸዉም፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ በአቋማቸዉና በምክራቸዉ ስላልተደሰትኩ አንዳንድ የድርጊቱ

*ፈጻሚዎችን አነሳስቼ ዋናዉ የሃይማኖት አባት የወዳጆቻቸዉንና የተላላኪዎቻቸዉን ወሬ ሁሉ ስለሚቀበሉ በሐሰት በመወንጀል ካሉበት አጥቢያ አስነስቼ ወደ ዋሻ እንዲሰደዱ አድርጌያለሁ፡፡*

*አንዳንድ ደረታቸዉንና ጡታቸዉን፣ ታፋና ዳሌያቸዉን፣ እምብርትና ቂጣቸዉን ገላልጠዉ በየመንገዱና በየጥጋጥጉ የሚሄዱና የሚቆሙ እንዲሁም በተወጣጠረ ሱሬ አካላቸዉንና ቅርጻቸዉን እያሳዩ የሚሄዱ ሴቶች፤ የሃይማኖት አባቶችንና ሰባክያንን « እንዴት ይህ ገላችን ፈራሽ በስባሽ የሚሸት ነዉ እያላችሁ ታስተምራላችሁ? እኛ ሕገ መንግስታችን ባጎናጸፈን ዴሞክራሲ መብታችን እንኳን የተወሰነ ገላችን የሆነዉን ደረትና ጡት ታፋና ዳሌያችን ብቻ አይደለም መላ አካላችንን ገላልጠን ብንሄድ ምን ገዷችሁ ነዉ የከበረዉንና ገናናዉን የራሳችሁን ገላ ጨምራችሁ ከንቱ መሆኑን የምትናገሩትና የምታስተምሩት?» በማለት ቅሬታቸዉን አቅርበዋል፡፡*

*ቅሬታ የቀረበባቸዉ አባቶችና ሰባኪያንም « እህቶቻችን! እንዳላችሁት ይህ ሰዉነታችሁ የከበረ ነዉ፡፡ ነገር ግን ለኃጢአት ተግባር የምናዉለዉና የምናስመልከዉ፣ ለዝሙት ማነሳሻ የምንጠቀምበት ከሆነ ደግሞ ጥቅም እንደሌለዉ ጣዖት እንዳደረግነዉ ልታስተዉሉ ይገባል፡፡ እንዲሁም ሰዎችን ስላሰናከልንበት የባሰ ፍርድ የምንቀበልበትና የምንጠየቅበት መሆኑን ልትረዱ ይገባችኋል፡፡ ጽድቅ ሰርተንበት ለመንግስተ ሰማያት የምንበቃዉ በዚሁ በተገለጽንበት በከበረዉ ሰዉነታችን አማካይነት ሲሆን ኃጢአትም ፈጽመንበት ለሲዖልና ለገሃነመ እሳት የምንዳረገዉ በዚሁ ክብሩን ባዋረድንበትና ባቃለልንበት እንዲሁም ባራከስነዉና ባልከሰከስነዉ በተገለጽንበት ሥጋችን አማካይነት ነዉ፡፡*

*«እኛ ሟች፣ ፈራሽ፣ በስባሽ አይደለንም» ላላችሁት ደግሞ፤ የምትመኩበትና የምትመጻደቁበት ሕገ መንግስታችሁ እንዳትሞቱ፣ እንዳትፈርሱ፣ እንዳትበሰብሱ የማድረግ ብቃት ካለዉ በዴሞክራሲ መብታችሁ አለመሞትና አለመበስበስ ትችላላችሁ፡፡ እኛ ግን በሰማያዊ ሕገመንግስታችን መሰረት ሕያዋን የሆናችዉ የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጆች መሆናችሁን እንዲሁም የማትሞት፣ የማትፈርስ፣ ከመኖር ወደ አለመኖር የማታልፍ ሕያዉ ነፍስ እንዳላችሁና እንደ ስራችሁና እምነታችሁ እንደሚፈረድላችሁና እንደሚፈረድባችሁ ሁሌም እንመሰክራለን እንጂ፤ ይህ ገላ እንዲመለክና የተለየ ተደርጎ እንዲቆጠር ለማድርግ የተለየ ስም የማንሰጠዉና ይልቁና ነፍሳችን ተገልጻበት ያለ እየተቀጣንበትና እየጠራንበት መሆኑንና ቅርፊት ስለሆነ ለተፈጠረበት አፈር አስረክበን የምንሄድና የኛ እዉነተኛ ገንዘብ ሕያዉ ነፍሳችን ብቻ መሆኗን እናስተምራለን፤ እንመሰክራለን» በማለት ምላሽ በመስጠታቸዉ እኔ የጨለማዉ ገዥ እንዲመለክ ያደረኩትና ለተለያየ ዓላማ የምጠቀምበት ገላ እንዲህ ከንቱ መሆኑ በመነገሩ እጅግ የተበሳጨዉ መሆኔን በዚሁ እገልጻለሁ፡፡*

የተወሰኑ ዘማሪያንና ሰባኪዎች እንዲሁም መጽሐፍ ጸሐፊዎች በአንድላይ በመሰባሰብ ቅሬታቸዉንና ጥያቄያቸዉን ወደ መንበረ ፓትሪያሪክ አቀረቡ:: ይኸዉም « እኛ ዘማሪያን፣ ሰባኪያን ፣ እንዲሁም የተለያዩ መጽሐፍትን የምንጽፍ አገልጋዮች፤ ከሌሎች ተለይተን በየቤተክርስቲያኑ መድረክና በተለያዩ ጉባኤ ላይ ያወጣነዉ ካሴትና ሲድ እንዲሁም መጽሐፍት ለምእመኑ አለመተዋወቁና ተሸጦ የገቢ ምንጫችን እንዲሆን ባለመደረጉ ቅሬታ ግብቶናል:: ለሌሎቹ በየአዉደ ምህረቱና በተለያዩ ጉባኤ እንደሚደረገዉ የማስተዋወቂያ ሽያጭ እኛም የቤተክርስቲያን ልጆች ነንና ለኛም እንዲደረግልን ?» በማለት ቅሬታቸዉንና ጥያቄያቸዉን አቅርበዋል::

የመንበረ ፓትሪያሪኩም ተወካይ: « አካሄዱን ስላላወቃችሁት ነዉ እንጂ የእናንተም ስራ ለምእመኑ ተዋዉቆላችሁ እንኳን ለኑሮዋችሁ ድጎማ አይደለም ለመኪናና ለፎቅ መስሪያ ይተርፋችሁ ነበር:: ዝም ብላችሁ በእግራችሁ ከመሄድ አንዳንዴ በእጅም መሄድን ብታዉቁ የተሻለ መሆኑን እመክራችኋለሁ:: እኔጋ ለመቅረብ በሄዳችሁበት አካሄድ በየአብያተክርስቲያኑ ብትደግሙትና ለኛ አካሄድ የሚመችና ከቡድናችን ጋር የሚጣጣም መዝሙር፣ ስብከት፣ መጽሐፍ ካዘጋጃችሁ ተወካዮቻችን በየቦታዉ ስላሉ እነሱ በደንብ ያስተዋዉቁላችኋል፤ ያሻሽጡላችኋል:: ነገር ግን መዝሙራችሁና ስብከታችሁ የወግ አጥባቂነት ይዘት ካለዉና መጽሐፋችሁም የተለያዩ ሃይማኖቶችን የሚተችና የሚቃወም ከሆነ ባጠቃላይ ለአንድ ሃይማኖት ብቻ ጥብቅና የሚቆም ከሆነ ምእመኑ ስለማይቀበሏችሁ ወኪሎችችን ፈቃደኛ ሆነዉ አያስተዋዉቁላችሁም:: ስለዚህ መዝሙሩም እንደ ምእመኑ ፍላጎት ወደ ዘፈን ወሰድ የሚያደርገዉና ሞቅ ሞቅ የሚያደርግ፤ ስብከቱም እንደ መናፍቃኑ ባይሆንም እዛም የሚሰበከዉ አንድ ወንጌልና አንድ ኢየሱስ ስለሆነ ስለ ኢየሱስ የሚሰብክ መሆን አለበት:: ስለዚህ መስተካከል ያለበት አቋም ካለ አስተካክሉ፤ አቋማችሁ እንደ እኛ አቋም ከሆነ ደግሞ የላካችሁን አካል በመንገር ወኪሎቻችንን መገናኘት ትችላላችሁ::» በማለት መልሰዉላቸዋል::

በወቅቱ አጠገባቸዉ የነበሩ ወደ ፓትርያሪኩ ለመግባት ወረፋ ይዘዉ የነበሩ አንድ አባት፤ ጥያቄና መልሳቸዉን ይሰሙ ነበርና ስሜታቸዉን መቆጣጠር ተስኗቸዉ « እናንተ ቅሬታ አቅራቢዎች ሆናችሁ መላሹ የፓትርያሪኩ ተወካይ፤ የእግዚአብሔር ቤት ምእመናን የነፍስ ግብይት የሚያደርጉበት ነዉ እንጂ መሸጫና መሸቀጫ ቦታ አይደለም:: ወይስ አሁንም ጌታችን በጅራፍ እያገረፈን እንዲያወጣን ተፈልጎ ነዉ? ወይስ የራስን የተሰወረ የክህደትና የመናፍቅነት ትምህርት በመዝሙር፣ በስብከት፣ በመጽሐፍ ሽፋን ለማስፋፋት ተፈልጎ ነዉ? በእናንተም ጥያቄ በእሳቸዉም መልስ እጅጉን አዝኛለሁ:: እኔም ጉዳዬን ለማስፈጸም በቀጠሮ እንድመላለስ የሚደረገዉ ለካስ በእጅ መሄድ ተስኖኝ ነዉ:: ነገሩ አሁን ነዉ የገባኝ:: የዚህን

ያህል የከፋና የባሰበት ደረጃ ላይ የደረሰ አልመሰለኝም ነበር:: ለካስ ብልሽቱ የጀመረዉ ከአናት ነዉ:: እኔም ጉዳዬ ይፈጸምልኛል ብዬ ሁለተኛ እዚህ ድርሽ አልልም::ወደመጣሁበት እመለሳለሁ:: ስራችሁንም ለምእመናን እገልጻለሁ::

እናንተ «ዘማሪያን ፣ ሰባኪያን ፣ መጽሐፍት ጸሐፊዎች ነን» የምትሉ፤ ለመሆኑ ዝማሬዉ፣ ስብከቱ፣ መጽሐፉ በእዉነተኛ አገልጋዮች ተመርምሮ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት እምነትና ስርዐት የጠበቀ መሆኑ ተረጋግጦላችኋልን? ከሆነ ደግሞ ዓላማዉ ምእመናን ለማስተማርና ለማነጽ፣ ለማጽናናት ነዉ ወይ? ወይስ እንደ ንግድ ለገቢ ምንጭነት ነዉ ያዘጋጃችሁት? ለንግድና ለትርፍ ከሆነ ያዘጋጃችሁት ከእግዚአብሔር አንዳች ዋጋ እንደማታገኙበት እገልጽላችኋለሁ:: እንዲሁም ነገዴዎች ስላሉ እነሱ እንዲሸጡላችሁ ማድረግ ትችላላችሁ:: ምክንያቱም ለአገልግሎት ሳይሆን ለጥቅም ነዉና ያወጣችሁት፤ ዋጋችሁን በምድር ትቀበላላችሁ፤ በነፍሳችሁ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል መነገጃና ለግል ኑሮ ብቻ ማበልጸጊያ ስላደረጋችሁ ዋጋ ትከፍሉበታላችሁ:: ለምእመናን አስባችሁ ለአገልግሎት ከሆነ ደግሞ አሁን ምንም ባታገኙበት እንኳ አንድ ቀን ምእመኑ ሆነ ቤተክርስቲያን ድካማችሁን አስበዉ ይከፍሏችኋል:: ያም ባይደረግላችሁ እንኳ እግዚአብሔር ታላቅ ዋጋ ይከፍላችኋል::

ስለዚህ ተስፋ ማድረግ ያለባችሁ ሰማያዊዉን የበለጠዉን እንጂ ከምድር አንዳች አትጠብቁ:: ዞሮ ዞሮ ጊዜያችሁን፣ እዉቀታችሁን፣ ስጦታችሁን፣ ገንዘባችሁን ተጠቅማችሁ ለምእመናንና ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ከተሰለፋችሁ ዋጋ ከፍላችሁበታልን በምድርም በሰማይም ከእግዚአብሔር በተለያየ መልኩ ዋጋ እንደምትቀበሉበት ልትጠራጠሩ አይገባም:: እንኳን ለምእመናንና ለቤተክርስቲያን አስባችሁ፣ ወርዳችሁ፣ ወታችሁ፣ አገልግላችሁ ቀርቶ፤ እግዚአብሔርን በእዉነትና በመንፈስ ብቻ ካመለካችሁት ሰማያዊ ዋጋ በምድርም በሰማይም ታገኛላችሁ:: የአሁን አካሄዳችሁ ግን አግባብ ስላልሆነ ከእንደዚህ አይነት አካሄድ ተለዩ:: ሌሎችን አትምሰሉ:: እግዚአብሔር አንድ ቀን ቤቱን በጅራፍ ብቻ አይደለም በቁጣዉ ጭምር ማጽዳቱ አይቀርምና ሁሉን እስከሚያስተካክል ድረስ በእምነታችሁና በስርዐታችሁ ጸንታችሁ በእዉነትንና በመንፈስ እያመለካችሁ ተገኙ::» በማለት በመናገራቸዉ፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ ቂም ይገባቸዉ ከበላይ ደብዳቤ በማጻፍ ካሉበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን አስተዳዳሪነት እንዲሻሩ አድርጌ ከአገልግሎታቸዉ እስከአሁን ተፈናቅለዉ ይገኛሉ:: ወደ አንዱ ገዳምና ዋሻ እንዳይሄዱ ደግሞ የቤተሰብ ኃላፊ ስለሆኑ እስከአሁን ድረስ በቤታቸዉ ሱባኤ ይዘዉ ይገኛሉ::» **ይላል የመልካም ነገርና የእዉነት ተቃራኒዉ ዲያብሎስ ከሠራዊቶቹ ሰይጣናት ጋር በመሆን::**

# ምእራፍ ስድስት

« አንዳንድ « የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታዮች ነን» የሚሉ ዘማሪያንና ሰባኪያን ወደ መንበረ ፓትርያርክ ጥያቄያቸዉን ለማቅረብ ወደ ግቢዉ ሲገቡ የመንበረ ፓትርያርክ ተወካይ ታላቅ አቀባባል አደረጉላቸዉ። እነዚህ «አጉራ ዘለል ሰባኪና ዘማሪ እንዲሁም ሕገ ወጥ ሰባኪያንና ዘማሪያን » የሚባሉት ለተወካዩ፤ «የተከበሩ አባታችን እርሶን አገኘን ማለት ቅዱስ አባታችን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳዎሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ዘአክሱም ወእጬጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት የዓለም አብያተክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንትን አገኘን ማለት ነዉ። ታዲያ ይህን ሁሉ የረዘመ ስም የጠራነዉ እንደ ቀድሞዉ ጓድ መሪ በመፍራት ሳይሆን ታላቅነታቸዉንና የቅድስና ብቃታቸዉን ስለሚያሳይ እንዲሁም እንደዚህ ሲጠሩ ደስ ስለሚላቸዉ እኛ ልጆቻቸዉ ደግሞ እንኳን ይችን ቀላል ነገር በየንግግራችን እንደ አቡነዘበሰማያት መደጋገም ቀርቶ አይሮፕላን ለማሸለም የተዘጋጀን የቁርጥ ቀን ልጆቻቸዉ ነን። ይህን ደግሞ ከእኛ ባላይ እርሶ ያዉቁታል።

የመጣንበት ዋና ዓላማ በአሁን ሰዐት የትዉልዱን ዘፈን መዉደድና ዳንኪራን ማፍቀር እንዲሁም ፕሮቴስታንቲዝም ስብከት መፈለግ ተመልክተን ምእመኑን እያዝናናነዉ ወደ ዘፈንና ዳንኪራ የተጠጋ መዝሙርና ምስጋና እንዲሁም ስብከቶቹ ልክ እንደ ወንድሞቻችን ፕሮቴስታንት አገልጋይና ፓስተሮች የሱስን ብንሰብክ ምናለበት? አንዳንድ ወግ አጥባቂዎችና ካህን ወንጉሥ መሆን የሚፈልጉ « ዝማሬዉም ሆነ ስብከቱ ያሬዳዊ ዜማንና የቤተክርስቲያኒቱን አስተምትሮና ትዉፊት በጠበቀ መልኩ መሆን አለበት» እያሉ በየቤተክርስቲያኑና በየስነጽሑፉ እያስቸገሩን ስለሆነ በቅዱስ አባታችን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳዎሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ዘአክሱም ወእጬጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት የዓለም አብያተክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንትን በበላይ በሚመራዉ ቅዱስ ሲኖዶስ ላይ «ዓለምን በዘመናዊ መዝሙር ለማዳረስና ወንጌልን በየሱስ ስም በአራቱም ማዕዘን ለመስበኩ የተነሱ የዘመኑ ሳራ የወለደቻቸዉ ምርጥ ልጆች ስላሉና እንዲሁም የጨለማዉ ገዥ በበላይ የሚመራቸዉ በሥጋዊ ወንበር ላይ የተቀመጡ መሪዎችና ባለስልጣኖች የመሰረቱትን የጨለማ ስርዐት አክብረዉ የሚንቀሳቀሱና የሚቀበሉ እንዲሁም ከእግዚአብሔር ተቀብተዉ የነገሡ መሆናቸዉን የሚያምኑና በእነሱ በበላይ የሚመራዉን የዘረኝነትና ጎጠኝነት፣ ዘፋኝነትና ዳንኪርተኛነት ፣ ክፋትና ተናኮል፣ ጥላቻና ቂም በቀል፣ ጭከናና አድሎ፣ ዝሙትና

አመንዝረኛነት ፣ ግድያና ስርቆት፣ ክህደትና መናፍቅነትን፣.. ወዘተ ሁሉን የሚደግፉና አንዳች ተቃዉሞ የሌላቸዉ ናቸዉ።

በሌላ በኩል ደግሞ ለቅዱስ አባታቸዉ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳዉሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት የዓለም አብያተክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንትን ያላቸዉ አክብሮትና ማግነን በሐዉልት ስራና በባለ ሶስት ሚሊዮን ብር መኪና ሽልማት ሳይገደቡ ለአይሮፕላን ሽልማት እየተዘጋጁ ያሉና የቅዱስ ፓትሪያሪኩ ቅድስና ከቅዱሳን መላእክት ባልተናነሳ ደረጃ ስለሆነ በሕይወተ ሥጋ እያሉም ታቦት ቢቀረጽላቸዉ ከማንም በላይ ድጋፋቸዉን የሚገልጹ ናቸዉ» በማለት የኛ አገልጋዮችንንና ዘማሪያን ጥያቄ እንዲቀርብልንና እነዚያ ወግ አጥባቂዎችንና ከስልጣን ጥማታቸዉ የተነሳ ካህን ወንጉሥ ለመሆን የሚሯሯጡትን መለዮዋቸዉን አስቀምጠዉ መስቀልና ወንጌል የያዙት ላይ የማያዳግም እርምጃ እንዲወሰድልን ለኛም ልዩ ፈቃድ ተሰቶን በየአብያተ ክርስቲያኑ እንድንሰብክና እንድንዘምር ልዩ መመሪያ ለቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪዎች እንዲሰጥልን ነዉ እዚህ ቅዱሳን ብጹዐን የሞሉቡት ቅዱስ ቦታ የመጣነዉ» በማለት ጥያቄያቸዉን ለተወካዩ ያቀረቡ ሲሆን፤

ተወካዩም « ይህ ቅሬታና ጥያቄያችሁ ቀደም ሲል እነ ወ/ሮ እገሌና እን አባ እገሌ ለቅዱስ አባታችን አቅርበዉ አፋጣኝ እርምጃ የተወሰደና እየተወሰደ ያለ በመላዉ ሀገረ ስብከትም «ተሐድሶ በሚል በማንም ሰባኪ ሆነ ዘማሪ ላይ ተቃዉሞ ሆነ እገዳ እንዳይቀርብ መመሪያ መተላለፉን እናንተም የምታዉቁት ነዉ። ተግባራዊነቱ ላይ ግን እስከ አሁን በደንብ ስላልተፈጸመ በቀጣይ በቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ላይ እርምጃ እንደሚወሰድና እንደ አስፈላጊነቱ ታላቅነቱን ከመሰከራችሁለትና በደጀን ከቆማችሁለት መንግስታችሁና መንግስታችን ዘንድ ድጋፍ በመጠየቅ አስፈላጊዉን ሁሉ የሚፈጸምላችሁ መሆኑን እንገልጽላችኋለን። እኛምጋ አንዳንድ ወግ አጥባቂና የአንዳንድ ማኅበራት ደጋፊ የሆኑ የሲኖዶስ አባላት ስላሉ እንደምንፈልገዉ ወሳኔያችን ተግባራዊ ማድረግ ባንችልም ለወደፊት ግን በተለያየ መልኩ እያዳከምንና እርምጃ እያስወሰድንባቸዉ ሲኖዶሱን ሙሉ በሙሉ የምናዝበት ጊዜ ሩቅ አይመስለኝም:: « እኛ የምንመራበት መንፈስና ተቃዋሚዎቻችን የሚመሩበት መንፍስ አንድ አይነት አይደለምና ምንም አንድነትና ህብረት የለንም እስከመጨረሻዉ ድረስ እንፋለማቸዋለን» በማለት የተናገራችሁት ንግግራችሁም፤ ምን ያህል ቆራጥ ጀግና መሆናችሁን የሚያሳይና የሚመራችሁ መንፈስ እነ ፈረኦንን ካደነደነዉ እጅግ የላቀ መሆኑን ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ:: አሁንም በአቋማችሁ ጽኑ፤ በእብሪትና በትዕቢት ንግግራችሁም ድል እንደምታደርጉ እተማመንባችኋለሁ::

እስከዛዉ ግን ዝማሬያችሁንና ስብከታችሁን በተጠናከረና በተደራጀ መልኩ ቀጥሉበት እንጂ አንዳች ተስፋ ቆርጣችሁ ወደ ኋላ እንዳትሉ:: ታዲያ አደራ የምላችሁ ምእመኑ ዓላማችሁን አዉቆ እንዳይተፋችሁ እኔጋ ዝም ብላችሁ «የሱስ የሱስ» እንደምትሉ በአገልጋሎታችሁም እንዲህ እንዳትሉ:: ይህ ወደ መጨረሻ ግብ ላይ ሲደረስ በግልጽ የምንለዉ ይሆናል:: አሁን ግን « በስብከታችሁ ሆነ በመዝሙራችሁ አልፎ አልፎ እመቤታችን፣ ቤተክርስቲያናችን፣ ሃይማኖታችን፣ አንዳንዴ ደግሞ የፈለጋችሁትን የቅዱሳን ስም ጣል አድርጉ:: ምንቸገራችሁ « ለምን የማርያንና የቅዱሰን ስም ትጠራላችሁ?» እያለ የሚጠይቃችሁ ግለሰብ ሆነ አካል ካለ « ለብልሃት ነዉ፤ ምእመኑን ለመሳብና ቀስ እያልና ወደ እናንተ የሱስ ለማምጣት ነዉ» በሏቸዉ:: እንዲሁም «ከዚህ በፊት ተቻኩለዉ በግልጽ የሱስን ስለመሰከሩና በአሮጊቷ ሳራ ላይና በእንቁላሉ ቅርፊት ላይ ተቃዉሞ በማሰማታቸዉ ከቤተክርስቲያን የተባረሩትንና የተወገዙትን ወንድሞቻችሁን አስቡ» በሏቸዉ:: ከዚህ በተጨማሪም «ተቃዋሚዎቻችን የረቀቁ ስለሆነ እኛም ልንራቀቅባቸዉ ስለሚገባ በአንዳች ነገር አታስቸኩሉን ቀስ ብለን ወደ ጋራ አገልግሎት መተን ዓለምን በወንጌል እናዳርሳለን የሱስንም እናነግሣለን::» በሏቸዉ::

ሌላዉ የምመክራችሁ በአዲሱ ጣቢያ በኢቢኤስ በታኦሎጎስ ቻናል ላይ በምታስተላልፉት ታላቅና ድንቅ አገልግሎት ላይ ብልጥ ሁኑ:: ለምትናገሩት ንግግር ጥንቃቄ አድርጉ:: እየተቀዳ ለመረጃነት ስለሚቀርብ እኛም ጥያቄና ፈተና እንዳይበዛብን በማንኛዉም ቀረጻ ሊካሄድ በሚችልበት ቦታ ላይ በግልጽ ተቃዉሞና ስድብን ነገር አትናገሩ:: ከፈለጋችሁ ደግሞ እንደ አባ ሰላማ ብሎግ ማንነታችሁን ሰዉራችሁና በምእመናንና በአገልጋዮች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸዉንና እንዲሁም በተለያየ መንገድ የሚታሙትንም አባቶች በመጨመር በተለያየ አቅጣጫ ድጋፍ ለማግኘት በሕይወት ከሌሉትም ካሉትም ስዕላቸዉን እያሳያችሁ «እኛ የአባቶቻችንን የአትናቴዎስ፣ ቄርሎስ፣ ዮሐንስ አፈወርቅ፣ አባ ሰላማን ሃይማኖት ነዉ የምንመሰክረዉ:: የኦርቶዶክስ ሃይማኖት የድኅነት ሃይማኖት እንደሆነ እናምናለን:: ከጊዜ በኋላ ነዉ በሃይማኖት ዉስጥ አንዳንድ የማያስፈልጉ ነገሮች የተጨመሩት» በማለት እንደ ሉተር «የማንቀበላቸዉ ነገሮች አሉ አንድ፣ ሁለት» እያላችሁ ለሲኖዶስ በማቅረብ አቋማችሁን በደንብ አሳዉቁ:: እንዲሁም መስደብና ስም ማጥፋት የምትፈልጉትን በግልጽ በድረ ገጽ ላይ ማጥፋት ትችላላችሁ:: ማንም አዉቆ ሊጠይቃችሁ አይችልም:: ዋናዉ ማንነታችሁን መሰወር ይጠበቅባችኋል::

እንዲሁም «እኛ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ትክክል እንደሆነ ስላመን ነዉ እስከ አሁን ሌላ ሃይማኖት ያልመሰረትነዉ እንጂ ፕሮቴስታንቱ እጃችንን ስመዉ ነዉ የሚቀበሉን» በማለት ራሳችሁን ካብ ካብ አድርጉ:: እናንተ ግን አንዳንዴ የሚገፋፉችሁ መንፈስ አይታወቅም «

ተሐድሶ ማለት እኔ ነኝ» በማለት ትፎክራላችሁ:: ሲያሰኛችሁ ደግሞ «ማህበረ ሰይጣን» እያላችሁ ትሳደባለችሁ:: አንዳንዳዴ ልክ ዛሩ እንደተነሳበት ሰዉ ትራገማለችሁ:: ትንሽ ነዉ ሽማግሌ ነዉ ሳትሉ «የእንጨት ሽበቶች» እያላችሁ ልቅ ስድብ ትሳደባላችሁ:: ይህ ታዲያ ሽዋጁ መንፈስ እንዴት አድርጎ እየተጫወተባችሁና እያላገጠባችሁ መሆኑን ስለሚገልጽ አንደበታችሁ በቅመም የተቀመመ መሆን አለበት:: ቅዱስ አባታንን አትመለከቱም! እሳቸዉ በንግግራቸዉ ፈሊጠኛ ናቸዉ፤ ተጠንቅቀዉ ነዉ የሚናገሩት:: ራሳቸዉን አጋፍጠዉ አይሰጡም:: የሚበቀሉት ሆነ የሚያደርጉት ከጀርባ ነዉ:: ስለዚህ የመሪያችሁን ፈለገ ከተከተላችሁ ዉጤታማ ትሆናላችሁ:: ዝም ብላችሁ ግትሮች ከሆናችሁ ከመሰረታችሁ ልትነቀሉ ትችላላችሁና አንደበታችሁን እንደ አንዳንድ ጓደኞቻችሁ ብዙ ምእመን በተገኘ ብትና ዋና አባቶች ባሉበት ፍጹም ኦርቶዶክሳዊ ስብከት ብቻ መስበክ አለባችሁ:: በራሳችሁ መድረክና ጉባኤ ደግሞ መደበላለቅ ትችላላችሁ::

መቼስ ለጥያቄ የመጣ ሰዉ ራሱ ሲጠየቅ ደስ እንደማይለዉ ቢታወቅም አንዲት ቀለል ያለች ጥያቄ ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ:: ይኸዉም በፕሮግራማችሁ፣ በስብከታችሁ ርእስ፣ በመዝሙራችሁ ግጥም፣ እንዲሁም በመጽሐፍቶቻችሁ ዉስጥ ልክ እንደ ፕሮቴስታንቱ ለየት ያሉ ያልተለመዱ ቃላትን የምትጠቀሙት ስለምን ይሆን? ምናልባት አዲሱ ትዉልድ አዲስ ነገር ይፈልጋልና ታኦሎጎስ፣ ማራናታ እያልን ብናቀርብለት ለዉጭ (ለባዕዳን) ልዩ ፍቅርና እንደ አምላክ ስለሚቆጥራቸዉ፤ ከዉጭ የመጣ ቋንቋ መስሎት ጆሮዉን ይሰጠናል በሚል አስተሳሰብ ይሆን? ወይስ ፕሮቴስታንቱ ለልዩ ፕሮግራማቸዉ የሚጠቀሙብትን ያልተለመዱ ቃላቶች ስንጠቀም በእነሱ ዘንድ ሞገስን እናገኛለን ብላችሁ ይሆን? ወይስ ትዉልዱ የራሱ ማንነትና መገለጫ የሆነዉን «አኮቴት፣ ስምዐ ጽድቅ፣ ልሳነ ተዋህዶ.. ወዘተ» የሚለዉ ቋንቋ ስለሰለቸዉ እንደ ወረተኛነቱ ዘመናዊ ስያሜ እናዘጋጅለት በማለት አስባችሁላቸዉ ይሆን?

ትዉልዱ እንደ እናንተ አርቆ አሳቢና አስተዋይ ቢሆን ኖሮ እስከ አሁን ድረስ ዓለም በፕሮቴስታንቱ አይነት ስብከት፣ መዝሙርና ምስጋና መሰለ በዘፈንና በዳንኪራ ትጥለቀለቅ ነበር:: በወንጌልም ጌታ የሱስን (የሱስን) ለዓለም ታዳርሱ ነበር:: ምን ያደርጋል ታዲያ! ይህ ወግ አጥባቂ ትዉልድ ነፍሱ በወንጌል የምትጠገንበትን ስብከት እየፈለገና ወደ ሰማየ ሰማያት የሚነጥቀዉንና ኅሊናዉ የሚመሰጥበትን ያሬዳዊ ዜማ፣ አቋቋሙን፣ ዝማሜዉን፣ ድጓዉን፣ ሰዐታቱን፣ ኪዳኑን፣ ቅዳሴዉን ፣ ቅኔዉን፣ ሽብሸባዉን ..ወዘተ እየመረጠ በራሱ ጊዜ ከሚዝናናበትና ከሚደሰትበት ዓለም እየለየ ይገኛል:: እናንተ ግን በቆራጥነት በልዩ ስብከታችሁ፣ መዝሙራችሁና መርሐ ግብራችሁ ዘመናዊዉን ወንጌልና መዝሙር ለዓለም ለማዳረስ ቆርጣችሁ መነሳታችሁ በዚህ አጋጣሚ ያለኝን አድናቆት ልገልጽላችሁ እወዳለሁ::

ከዚህ በፊት የአፍ ወለምታ እያስቸገራችሁና ማንነታችሁ ከልባችሁ ሞልቶ እየፈሰሰ ተቸግራችሁ « ኢየሱስን እግዚአብሔር አትበሉ። ድንግል ማርያምን ወላዲተ እግዚአብሔር አትበሉ።» እያላችሁ በግልጽ የመሰከራችሁት ታላቅ ምስክርነት ምን ያህል ዉዝግብና ተቃዉሞ እንዳመጣባችሁ ከኛ በላይ እናንተ ታዉቃላችሁ። ስለዚህ «እንደ እባብ ልባም፤ እንደ ርግብ የዋህ ሁኑ» ተብሏልና፤ ስሞችን ሆነ አስተምሮዎችን ቀስ በቀስ በሰዉ ኅሊና ማለማመድና ራሱ ምእመኑ እናንተ ምንም ሳትሉት በሂደት ራሱን ወደ እናንተና ወደኛ ፍላጎት ልትለዉጡት ትችላላችሁ። ሌላዉ ድግሞ ፖለቲካዊ ብልጠት ይኑራችሁ። መንግስታችን ኢህአዴግ ከልብ የሚቀናቀኑትን የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዴት አድርጎ በነፍስ በሥጋቸዉ እንደሚጫወትባቸዉ ያስተዋላችሁ ይመስለኛል። ከመሀከላቸዉ አንድ ኅሊናዉን የሚሸጥ ወይንም የሚገለባበጥ ሰዉ ካገኘ በዛ ሰዉ ተጠቅሞ ብትንትናቸዉን ያወጣል። የራሱ ተለጣፊና ጠበቃ ያደርጋቸዋል።

ምንም እንኳን እናንተ እንደ መንግስት ኃይል ባይኖራችሁም ለስልጣናቸዉና ለወንበራቸዉ ሌት ተቀን የማይተኙ ስለሆነና ከወንበራቸዉ ከተቆረጡ መኖር የማይችሉ ስለሚመስላቸዉ በስስ ብልታቸዉ በመግባት፤« እነዚህ ማኅበራት ሌት ተቀን ወንበራችሁን ለመገልበጥ ነዉ የሚሯሯጡት እንጂ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት አይደለም። ስለዚህ ብትንትናቸዉን ማዉጣት አለባችሁ» በማለት የሐሰት ፕሮፖጋንዳ መንዛት አለባችሁ። ያኔ እናንተ በቤተ ክርስቲያኒቱ እንደልባችሁ መፈንጨት ትችላላችሁ። ይህ ካልሆነላችሁ ደግሞ ከእናንተ መካከል ብዙ የማይታወቅ ሰዉ እነዚህ በሚያስቸግራችሁና ስማችሁን በሚያጠፉት «ማህበረ ሰይጣናት» በምንላቸዉ መካከል በማስገባት ቀስ ብሎ አንጃ እንዲፈጥር አድራጋችሁ ከቤተክህነትና ከመንግስት ጋር የሚጋጩበትን መንገዶች በመፍጠር ከመንግስት ጋር በመቀናጀት ልናጠፋቸዉ እንችላለን። እንዲሁም እስከዛዉ ድረስ ልክ ከዚህ በፊት የእነሱ ማኅተም በማስመሰል አንድ ጽሑፍ እንዳወጣችሁና እንደበተናችሁ ያ ዉጤት ባያመጣም፤ አይነቱን ለዉጣችሁ አንዳንድ የቤተክርስቲያኒቱ እዉነተኛ አገልጋዮችና በዓለም ታዋቂ የሆኑ ሰዎችን እንደወነጀሉና ዘመቻ እንዳደረጉ በማስመሰል በጽሑፍ ሆነ በወሬ እንዲሁም በአባ ሰላማ ድረ ገጽ አሰራጩ። በተቻላችሁ መንገድ ሁሉ ምእመናንና እዉነተኛ አገልጋዮች እንዲጠሏቸዉ ካለደረጋችሁ በስተቀር በአራቱም ማዕዘን በምእመኑና በእዉነተኛ አገልጋዮች ዘንድ ስር የሰደዱ ስለሆነ ለመንቀል ሆነ ለማጥፋት እንኳን እኛ የቤተክህነት ሰዎች አይደለም መንግስት ራሱ እንደሚቸገር በደንብ ይታወቃል።

ሌላዉ ደግሞ ፕሮቴስታንት ወንድሞቻንና አገልጋዮች የቀድሞ አካሄዳቸዉን ማሻሻያ በማድረግ ይኸዉም ቀደም ሲል ለኛ ኅሊና እንኳ ሳይቀር በሚከብድ መልኩ ማርያምንና ቅዱሳንን ሲያጥላሉ፣ ሲሰድቡ፣ ሲያዋርዱ ነበር። አሁን ግን ብልጥ ሆነዉ እናንተ ትሁኑ ማን

እንዳስተማራቸዉ አላዉቅም « እኛ ማርምን እናከብራለን ነገር ግን አታማልድም፤ የሱስ አምላክ ነዉ  ግን የእኛ አማላጅ ነዉ» እያሉ የቀድሞ የስድብ አካሄዳቸዉን በማሻሻል ምእመኑን ለመሳብ ጥረት እያደረጉ ስለሆነ እናንተ ደግሞ ከእነሱ በረቀቀ መንገድ  ከመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ ነገሮች እየጠቃቀሳችሁ  የተነሳችሁለትን ዓለማ ማሳካት አለባችሁ፡፡

በዚሁ አጋጣሚ የማሳስባችሁ ባለፈዉ ፳፻ወ፪(2002) ዓ.ም በታህሳስ ወር በሚሊኒየም አዳራሽ ያቀረባችሁት የስብከት ፕሮግራም ብትደግሙና ለእናንተም መደጎሚያ ለማኅበራችሁም ማጠናከሪያና አባላት ማፍሪያ ይሆናችኋል፡፡ ከዚያም አልፎ ለቅዱስ አባታችን ከመቶ ሺህ ብር በላይ ወጭ አድርጋችሁ የመመረቂያዉን መድረክ እንዳደመቃችሁት ሁሉ አሁንም ደስ ብሏቸዉ ሽልማትና እዉቅና እንዲሰጧችሁ በየአብያተ ክርስቲያኑ ከአምስት መቶ አመት በላይ ሊቆይ የሚችለዉን ሐዉልት ብታሰሩላቸዉና በፀሐይና በብርድ መፈራረቅ ምክንያት ያዘኑበትን በየአብያተክርስቲያኑ የተሰቀሉ ስዕሎቻቸዉን እድሳት ብታስደርጉና ሌሎች አዳዲስ ፖስተሮችን(ቢል ቦርድ) በመላዉ ቤተክርስቲያን እንዲሰቀል ብታደርጉ የተሻለ መሆኑን አባታዊ ምክሬን እመክራችኋለሁ፡፡ ታዲያ እንደ ዶጆችሽ አይዘጉ ማኅበራት ሞኝ አለመሆናችሁን በማስመስከራችሁ አድናቆቴን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡ ምክንያቱም እነሱ የተገኘዉን ገቢና እርዳታ ለተጎዱ አብያተክርስቲያናት ላይ ሲያዉሉና የተለያዩ መንፈሳዊ ተግባራት ሲያሰሩበት፤ እናንተ ግን የተገኘችሁን ገቢና እርዳታ ለኪሳችሁ መሙያና ለተለያየ ጉባኤያችሁ ማስፋፊያ እንዲሁም በዓለም ዘንድ ታዋቂነት ያተረፈላችሁና ከቅዱስ አባታችን ሞገስ አግኝታችሁ ለሽልማት እንድትበቁ ያስቻላችሁን የሐዉልቱን ምርቃት ለማድመቅና ለማግነን ለወንጌል አገልግሎት ብላችሁ ከሰበሰባችሁት ብር ከመቶ ሺህ ብር በላይ ወጭ አድርጋችሁ የመመረቂያዉን መድረክ ማድመቃችሁ ነዉ፡፡

አሁን ለጥያቄዎቻችሁ የመጨረሻ እልባት እስከምታገኙ ድረስ በተረጋጋ ሁኔታ አገልግሎታችሁን ቀጥሉ፤ እኛ ከጎናችሁ ነን፡፡ አይዟችሁ በርቱ፡፡ ታዲያ ያች ቃል የገባችሁልኝንና የጀመራችኋትን ነገር ከፍጻሜ አድርሷት፡፡» በማለት መክረዋቸዉና አጽናንተዋቸዉ ተመልሰዋል፡፡ እኔም የጨለማዉ ገዥ በጎሊቸዉ «አይዟችሁ ከጎናችሁ አለሁኝ፡፡ ለመሳደብ ሆነ ለመራገም አንዳች ፍራት አይደርባችሁ፡፡ አንዳችም መጸጸት ሆነ ንስሐ የሚባል ነገር በጎሊናችሁ እንዳይመጣ፤ በአቋማችሁ ጽኑ፡፡ እናንተ ለኔ ዉዶቼ ናችሁ፤ እኔም ለእናንተ» በማለት አበረታትቻቸዋለሁ፡፡ ሞራል ሰጥቻቸዋለሁ፡፡» **ይላል በእዉነተኛዉ በእግዚአብሔር ቤት አንደበቱን አንደበታቸዉ አድርጎ የሚያናግርና ኅሊናዉን ኅሊናቸዉ አድርጎ የሚያሳስብ የእዉነተኛዉ አምላክ የእግዚአብሔር የኢየሱስ ክርስቶስ ተቃዋሚና «የሱስ» በመባል የሚታወቀዉ ሸዋጁ መንፈስ የሆነዉ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ ሰይጣናት ጭምር፡፡**

# ምእራፍ ሰባት

« አንዳንድ የሥላሴ ፣ የመድኃኔዓለም፣ የድንግል ማርያም፣ የቅዱሳን መላእክት ፣ የጻድቃን ሰዎች ስዕል አክብሮት ያላቸዉ አገልጋዮችና ምእመናን በጋራ በመሆን ለመንበረ ፓትርያርክ ተወካይ ጥያቄና ቅሬታ አቀረቡ:: ይኸዉም «በየአብያተክርስቲያኑና በጸሎት ቦታ በአክብሮት ተቀምጠዉ የረቀቁትንና የራቁትን ለኅሊናችን አቅርበን ከፈጣሪና ከቅዱሳን ጋር የምንገናኝበትን ስዕል በየመንገዱ ተነጥፎና ተረግጠዉ ለንግድ አገልግሎት ሲዉሉ፣ በካሴትና በሲድ እንዲሁም በአንዳንድ ገቢ ማስገኛና ማስተዋወቂያ ፖስተሮች ላይ ተለጥፈዉ ለትርፍ ማግኛ ሲዉሉ፣ አንዳንዶች በየመንገዱ ስዕል አንጥፈዉ መስቀል ይዘዉ መለመኛ ሲያደርጉ፣ አንዳንዶች ደግሞ መልካም ያደረጉ እየመሰላቸዉ የቁልፍ ማንጠልጠያ ሲያደርጉ፣ ባጠቃላይ ከቁም ነገር ሳይቆጠሩ በየቦታዉ እየተጣሉና እየተቀዳደዱ እንዲሁም እየተረገጡ ለማይገባ አገልግሎት እያዋሉ ማየት ኅሊናችን ስለከበደዉና ቅዱሳኑም እየተቃለሉ፣ ለመሸቀጫ አገልግሎት ብቻ እየዋሉ መሆኑን ስለተረዳንና ኅሊናችን ስላዘነ ስርዐት የሚያሲዝ አካል ካለ ስርዐት እንዲያሲዝልንና ለማስመሰል ሳይሆን ተግባራዊ ሊሆን የሚችል መመሪያና ሕግ እንዲዘጋጅልን፣ እኛም በአግባቡ እንደንገለገልበት እንዲደረግ ለማሳሰብ ነዉ የመጣነዉ» በማለት ለተወካዩ የተሰማቸዉን ቅሬታና ጥያቄያቸዉን አቅርበዋል::

የመንበረ ፓትርያርክ ተወካዩም «ለቅዱሳት ስዕል ያላችሁ አክብሮት መልካም ቢሆንም ከቅዱሳን እኩል የተቆጠሩትና ቅድስና ማዕረግ የተሰጣቸዉ ቅዱስ አባታችን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳዉሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት የዓለም አብያተክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዚዳንት ስዕላቸዉ በየመሰብሰቢያ አዳራሽ፣ በየቢሮዉ፣ በየአብያተ ክርስቲያኑ፣ በየግድግዳዉና በሩ ሲለጠፍ በአግባቡ በክብር የማትጠብቁትና አንዳንዶቻችሁ ደግሞ ለመቅደድ የምትደፋፈሩ፤ በየአብያተ ክርስቲያኑ በፖስተር መልክ በትልቁ የተሰቀለዉ ስዕላቸዉ ፀሐይ፣ ዝናብ፣ ሙቀትና ቅዝቃዜ ሲፈራረቅበት ያልከበዳችሁና ያልተሰማችሁ፤ ወደ ቤተ መቅደስ ገብቶ እንለማመንበት አለማለታችሁ፤ እንደማካካሻ ቆጥራችሁ ደግሞ ከአምስት መቶ ዓመት በላይ የሚቆይ ሐዉልት በየአብያተ ክርስቲያኑ እናቆምላቸዋለን አለማለታችሁ፤ ባጠቃላይ የቅዱስ አባታችን ማለትም ቅዱስ እግዚአብሔርን ሳይሆን በቅድስናቸዉ ከእግዚአብሔር ጋር በመቀራረባቸዉ ምክንያት «ቅዱስ አባታችን» የሚል ማዕረግ በቅዱስ ሲኖዶስ የተሰጣቸዉን ማለቴ ነዉ፤ ለስዕላቸዉ የተለየ መንከባከብና ጥበቃ ሳታደርጉና ክብር ሳትሰጡ ለማታያቸዉና ለማታዉቋቸዉ ቅዱሳት ስዕል የዚህን ያህል

መቆርቆራችሁና መጨነቃችሁ ከልብ መሆኑ ያጠራጥራል፡፡ ስለዚህ በመጀመሪያ ለቅዱስ አባታችን ስዕል የሚሰጠዉን ክብርና ጥበቃ ስትሰጡ በቀጣይ ለእግዚአብሔር ሆነ ለቅዱሳን ስዕል አቀራረብና አጠቃቀም የተለየ መመሪያ ልናወጣ እንችላለን፡፡» በማለት እኔን የጨለማ ገዥ ደስ በሚያሰኝ መልኩ ምላሽ ሰተዉልኝ አፍረዉ ሊመለሱ ችለዋል፡፡

አንዳንድ የቆሎ ተማሪዎችና ለማኞች ለሚመለከተዉ አካል ቅሬታቸዉን አቀረቡ፡፡ ይኸዉም « ምርኩዝ የምትሆነንና ብንራብና ብንጠማ የምንመገብባትና የምንተጣባት፣ ብናዝን የምንጽናናባት፣ ብንወድቅ የምንነሳባት፣ ብንገዳገድ የምንጠነክርባት፣ ብንደክም የምንበረታባትን ድንግል ማርያም «በእንተ ስማ ለማርያም» እያልን ሕዝቡ ራርቶ እንዳያበላንና እንዳይራራልን ስሟ እንዳይጠራ ብቻ አይደለም እየተሰደበች፣ እየተቃለለች፣ እየተጥላላች ስለሆነ አንደበታቸዉን የዲያብሎስ አንደበት ያደረጉ ሰዎች ስርዐት እንዲይዙልን እንጠይቃለን፡፡» በማለት ለሚመለከተዉ የመንግስት ተወካይ አቅርበዋል፡፡

የመንግስት ተወካዩም « እናንተ ባልጠፋ ስም ማርያም ማርያም እያላችሁ መጥራታችሁ የሚያስገርም ነዉ፡፡ ስንት የባለ ሀብት ስም እያለ፣ የሥጋዉ መሪ የፀሐዩ ንጉሣችን ስም እያለ፣ የመንፈሳዊ መሪ የቅዱስ አባታችን ስም እያለ፣ ስንት ተዋቂና ዝነኛ ሰዎች በዓለም ላይ እያሉ የእርሷን ስም ሆነ « ቅዱሳን፣ ጻድቃን ፣ እግዚአብሔር» እያላችሁ መጥራቱ ጥቅሙ አልታየኝም፡፡ ይልቁኑ ተፈጥሮ ባደለቻችሁ የተለያዩ ትዕይንት ዉስጥ በመሳተፍ እርዳታ ብትጠይቁ፣ ከጎበዛችሁ ደግሞ እንደ መንግስታችን ግብረ ሰዶም ፈጻሚዎችን ሳትቃወሙ የኤድስና የአባላዘር በዐል እያላችሁ ገንዘብ መለመን ትችላላችሁ» በማለት እኔን የጨለማዉ ገዥ ደስ የሚያሰኝ መልስ ሰተዉልኛል፡፡

አንዳንድ ምስጋናና ዉዳሴ የሚፈልጉ በስራቸዉ የሚመጻደቁ ሰዎች በእግዚአብሔር ባሕርይ ላይ ተቃዉሞ አሰሙ፡፡ ይኸዉም « አንተ እግዚአብሔር! እኛ ስንት ስራ ስንሰራ፣ ስንወጣ፣ ስንወርዱ አንድ ቀን እንኳ አላመሰገንከንም፡፡ ታላቅ ስራ ሰርታችኋል አላልከንም፡፡ እኛስ ይሁን፣ ምክንያቱም አንዳንዴ እናስመስላለን፡፡ ነገር ግን እነዚያ ሰዎች በእዉነትና በመንፈስ እያመለኩህ ሌት ተቀን በአገልግሎት እየተጉ፣ ስለባለሟልነታቸዉ ትመሰክርላቸዋለህ፣ ከፍ ከፍ አደርጋችኋለሁ ትላለህ እንጂ አታደንቃቸዉም፣ ታላቅ ናቸዉ አትላቸዉም፣ አታመሰግናቸዉም፡፡ ይልቁኑ « ገና ብዙ አልሰራንም፣ የሰራነዉም መስራት የሚገባንን ነዉ፡፡» በሉ እያልክ ትናገራቸዋለህ፡፡ ታዲያ ማነዉ ባንተ ዘንድ ሊመሰገን ሆነ ቅዱስ፣ ጻድቅ ሊባል የሚችለዉ?» በማለት አምላካቸዉን ጠይቀዋል፡፡

እግዚአብሔርም የዋህነታቸዉንና አለማስተዋላቸዉን ተመልክቶቸ « እንኳን እናንተ ቀርቶ እናንተ የምታመሰግኗቸዉና የምትመሰክሩላቸዉ ሰዎች ነገ ምን እንደሚሰሩ ታዉቃላችሁን? መጨረሻቸዉ ምን እንደሚሆን አዉቃችሁ ነዉ እንዲህ የምታገኟቸዉና ከፍ ከፍ የምታደርጓቸዉ? ስንቶች «ታላቅ፣ ብፁዕ፣ ቅዱስ፣ ክቡር» ተብለዉ የማይገባ ስራ ሲሰሩ አልተመለከታችሁምን? አልሰማችሁምን? አላነበባችሁምን? ስንቶቹ አንቱ የተባሉ ሰዎች በማይገባ ሕይወት ሲልከሰከሱ አላያችሁምን? ስንቶች እዉነተኛ መስለዉ ቀርበዋችሁ ዋና ሐሰተኛ ሆነዉ አላገኛቸዋቸዉምን? ስንቶች «የእግዚአብሔር አገልጋዮችና መልእክተኞች ናቸዉ::» ብላችሁ ተማምናችሁባቸዉ በመጨረሻ የዐመፃና የክህደት አገልጋይና የዲያብሎስ መልእክተኞች ሆነዉ አልተገኙምን? እኔም ለዚህ ነዉ ማንም ይሁን ማን የፈለገዉ ቅድስናና ብቃት ደረጃ ላይ ይድረስ እስከ መጨረሻ ድረስ ታምኖ ነፍሱ ከሥጋዉ ተለይታ እስከምትመጣ ድረስ የቅድስና ሆነ የጽድቅ ማዕረግ የማልሰጠዉና የማላመሰግነዉ::

በእዉነተኛ ባሕርያችሁና ገንዘባችሁ በረቂቅ ነፍሳችሁ ወደ እኔ እስከምትመጡ ድረስ ማንኛችሁንም አላምናችሁም:: ስቶቹን ከትቢያ አንስቻቸዉ ከፍ ከፍ ካደረኳቸዉና ለታላቅ ወንበር ካበቃዋቸዉ በኋላ እጅግ ያስቀጡኝና ያሳዘኑኝ ብዙ ሰዎች አሉ:: ነገር ግን ነፍስ ከሥጋቸዉ ከተለየች በኋላ ስለዐመፃቸዉ በመቶ እጥፍ ዋጋ እንዲከፍሉበት አድርጌያለሁ:: አሁንም በስሜ በሚነግዱበትና በኔ ቦታ ላይ ሆነዉ ራሳቸዉን የሚያስመልኩትንና የሚያመልኩትን በመቶ እጥፍ ዋጋ እንዲከፍሉበት አደርጋለሁ::» በማለት ምላሽ እንዳገኙ፤ ወደ ልባቸዉ ተለመልሰዉ « ወይ አለማስተዋል! በእኛ ዘመን እንኳ ስንት ጉድ አይተናል:: የእግዚአብሔርንና የቅዱሳንን ስም ይዘዉ ተግባራቸዉ፣ ንግግራቸዉ፣ አሳባቸዉ የዲያብሎስ የሆነ፤ የእግዚአብሔርን ስም እየጠሩና እያስመሰሉ ስንቱን ምእመን ከበረት አስወጥተዋል፤ እንደ እግዚአብሔር መልአክ ተመልክተናቸዉ በኋላ በማይገባ ሕይወት ሲልከሰከሱ ስንቱን ተመልክተናል!» በማለት ለጎሊናቸዉ ተናግረዉ እስከ እለተ ሞታቸዉ ድረስ አንዳች ምስጋናን ሆነ ሽልማት ሳይፈልጉ በንጽህናና በቅድስና ሕይወት ለመኖር የወሰኑ ሲሆን፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ ግን በአቋማቸዉ አልተደሰትኩም:: ምክንያቱን ስንቱን በከንቱ ዉዳሴ ጥያለሁና፤ እንዲሁም ስንቱን ራሱን እንደተለየ አድርጎ እንዲቆጥር አድርጌ በዐመፃና በክህደት እንዲሁም በርኩሰትና በትዕቢት ሕይወት አሰልፌዋለሁና ነዉ::

እናንተ «የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን፤ መንፈሳዊ ነን ::» እያላችሁ የነቢያት የሐዋርያት የሰማዕታት የጻድቃን ተጋድሎ ብቻ በአንደበታችሁ ሌት ተቀን የምታወሩ፤ የእነሱን ታጋድሎ ግን አንደ አስረኛዉን እንኳ ለመፈጸም ፈቃደኞች ያልሆናችሁ፤ በስማቸዉ የምትነግዱ፤ የእናንተ ሆድ ከሞላ ከተከበራችሁ « ቅዱስ ቅዱስ፣ ብጹዕ ብጹዕ፣ መምህር

መምህር፣ ሊቅ ሊቅ፣ አባት አባት፤» ከተባላችሁ፣ ከተመቻቸላችሁ፣ ምእመኑ እዉነትን አወቀ አላወቀ ደንታ የሌላችሁ፤ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ተጠበቀ አልተጠበቀ ግድ የማያላችሁ፤ ወንጌል ተሰበከ አልተሰበከ አንዳች ስሜት የማይሰጣችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕግና ሥርዐት ተጠበቀ አልተጠበቀ ከግል ጥቅማችሁ አንጻር ብቻ የምትመለከቱ፤ ሕግና ሥርዐት በመጣስ ጥቅም የሚገኝበት ከሆነ ዋና ተባባሪና አስፈጻሚ የምትሆኑ፤ በእግዚአብሔር ቃል የምትነግዱ፤ ስለ እዉነት ራሳችሁን ክዳችሁ መመስከር አይደለም የኔ የጨለማዉ ገዥ እንደራሴዎቼና ባለማሎቼ አንዳች ሳያዟችሁና ሳያስገድዷችሁ በጸበል ላይ እንደሚለፈልፍ «እኛ የዲያብሎስ እንደራሴዎችና ባለሟሎች ጉዳይ አስፈጻሚ ነን። የሕይወት መንገድ የሆነችዉን ተዋህዶ ሃይማኖት ለማጥፋትና ክህደትና መናፍቅነት ለማስፋፋት የሚተጋ መንግስት(ድርጅት) አባላትና የዐመጻ፣ የክህደት፣ እንዲሁም የርኩሰት ተግባራቸዉን የምናስፈጽም ካድሬዎች ነን። ቀሪዎቻችንም የዚሁ የዐመጻ ድርጅት(ቡድን) ደጋፊ ነን።» የምትሉ፤ እኔ «ጎሊናችሁን ሽጡልኝ፤ የኔን ስራ እንደጥሩ አድርጋችሁ መስክሩልኝ» ሳልላችሁ፤ እናንተ ግን ከኔ ከጨለማዉ ገዥ ሽልማት የምታገኙ ይመስል አንዳችሁ አዳችሁን ለመቅደም በቴሌቭዥን፣ በሬድዮ፣ በመጽሔት፣ በጋዜጣ፣ በኢንተርኔት፣ ባጠቃላይ መገናኛ ብዙኃን በወርቃማ ቃላትና አባባል ታጅባችሁ ምስክርነትን ትሰጡልኛላችሁ።

እኔ የጨለማዉ ገዥ ለዘመናት ያየሁትና የማዉቀዉ እናንተ « ነቢያት፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን ፣ ቅዱሳን» የምትሏቸዉ በዚህች ምድር ቆይታቸዉ ምንም ሳይባሉ ጎሊናቸዉን መሸጥ አይደለም፤ በተቃራኒዉ ስለ ጎሊናቸዉ ራሳቸዉን በመካድ ስለ እዉነት በመመስከራቸዉና በእዉነት በመኖራቸዉ ምክንያት የተለያየ ፈተናና መከራ ደርሶባቸዉ ወደ አምላካቸዉ እቅፍ ሲሄዱ ነዉ እንጂ « ቅዱስ፣ ብጹዕ፣ መልአክ፣ ሊቅ፣ ጻድቅ» ተብለዉ በምድራዊ ሕይወት ዘመናቸዉ ሲጠሩ አልሰማሁም፤ አላየሁም።» **ይላል ከተራዉ እስከ ታላቅ እስከተባሉት ሰዎች ድረስ ለመገንደስና ለማዋረድ፣ እንዲሁም ኃጢአት ለማስፈጸም፣ ከፈጣሪ ለማጣላት ወደ ኋላ የማይለዉ ጨካኙ የጨለማዉ ጌታና ገዥ ዲያብሎስ ከሰይጣናት ጋር በመሆን።**

# ክፍል ሦስት

## ምእራፍ አንድ

« በኢትዮጵያ ከሰማኒያ  በላይ ቋንቋ የሚናገሩ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተወካይ፣ የተለያዩ ሃይማኖት አባቶች፣ የተለያዩ አገራት ተወካዮች፣ የአዲስቷ የፌደራላዊ ዴሞክራሲ ሪፐብሊክ ኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትርና ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ እንዲሁም ካድሬዎቻቸዉ፣ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ፕሬዘዳንቶችና ከፍተኛ አመራሮቻቸዉ፤ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች አባላትና ደጋፊዎች፣ የአገር ሽማግሌዎች ፣ የኀሳ መሪዎች፣ እንዲሁም ከተባበሩት መንግሰታት የየአገሩ መሪዎች ተወካይ፣ ከአፍሪካ ህብረትና ከአዉሮፓ ህብረት በታዛቢነት በተገኙበት፣ ባጠቃላይ የተለያዩ አካላትን የሚወክሉ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ከአገር ዉስጥም ከዉጭ አገርም ታላቅ የዉይይት መድረክ ተፈጥሮላቸዉ ታሪካዊ ስብሰባ በኢትዮጵያ ምድር በተመረጠዉና በተለየዉ ቦታ ላይ ተደርጓል።

በመጀመሪያ ንግግር እንዲያደርጉ እድል የተሰጣቸዉ ከሰማኒያ በላይ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሆኑት የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦ ተወካዮች ሲሆኑ እነሱም፤ « የተከበሩ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትርና ከፍተኛ ባለስልጣኖች፣ እንዲሁም ከአገር ዉስጥና ከዉጭ የተጋበዛችሁ እንግዶች በሙሉ፤ እኛ አሁን የምናቀርበዉ ጥያቄና አስተየያት ባስተማራችሁንና በሰበካችሁን ትምህርት ተነስተን ነዉ። ይኸዉም «እናንተ የእግዚአብሔር ፍጥረቶች አይደላችሁም ። የገዥ መደቦች ለመጨቆን እንዲያመቻቸዉና እናንተን አስፈራርተዉ እንድትገዙላቸዉ ለማድረግ «እግዚአብሔር ምንትስዬ» እያሉ ተፈጥሮ የለገሰቻችሁን በአግባቡ እንዳትጠቀሙ ለማድረግ ነዉ እንጂ «ዘሮቻችሁ እንስሳ መሰል ጦጣዎች የሆኑ፤ እናንተም በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ (በኢቮልሽን) አማካይነት አሁን ላላችሁበት ሰብእና የበቃችሁ ናችሁ። «የአዳም ዘሮች ናችሁ፣ አንድ ወገን አንድ ቤተሰብ ናችሁ፤..ወዘተ» የሚባለዉ ተረት ተረት ነዉ» እያላችሁ ነዉ። በዚሁ ትምህርታችሁ መሰረት ይኸዉ ተፈጥሮ ባደለችንና የመጨረሻዉ ሰብእና ብቃት ደረጃ መድረሳችን በሚያሳየዉ የአፍ መፍቻ ቋንቋችን እንድንናገርና ሁላችንንም በአንድነት ሊያዋህደንና ሊያግባባን የነበረዉን የነፍጠኞችንና

የትምክህተኞችን ቋንቋ የሆነዉን አማርኛ ቋንቋ ከመነጋገሪያነት፣ ከመማሪያነት፣ ከመስሪያነት፣ ባጠቃላይ ከጫንቃችን ላይ አሽቀንጥራችሁ ስለጣላችሁልን በመጀመሪያ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስም እናመሰግናችኋለን::

ነገር ግን በስራ ቦታ፣ በትምህርት ቤት፣ በተለያዩ የእምነት ተቋማት፣ በገበያዉ፣ በእድሩ ሳይቀር በአኗኗራችን ተቸግረናል:: ይኸዉም የአንዱ ብሔር ቋንቋ በአንድ በኩል፣ የአንዱ ብሔር ቋንቋ በሌላ በኩል፣ ባጠቃላይ በአራቱም አቅጣጫዉ ተከፋፍሎ ልንደማመጥና ልንሰማማ፣ ልንግባባ አልቻልንም:: ለሁላችንም አስተርጓሚ እያስፈለገን ነዉ:: ስለዚህ ሁላችንም ልንደማመጥበትና ልንግባበት የምንችልበትን ቋንቋ ከብሔር ብሔረሰቡ እንደ ሕዝቡ ብዛት ተዋጽኦ እየተወጣጣ ቃላት ተፈጥሮልን በአንድነት የምንናገረዉ፣ የምንማርበት፣ የምንሰራበት፣ ባጠቃላይ በአራቱም ማዕዘን ልንግባባበትና ልንነጋገርበት፣ ልንማርበትና ልንሰራበት የምንችለዉን ቋንቋ በአምስቱ አመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዘመን እንድታዘጋጁልን እንጠይቃለን::

« የአፍ መፍቻ ቋንቋችሁ የማንነታችሁና የታላቅነታችሁ መለያ ነዉ ::» በማለት ነጋ ጠባ የምትነግሩን እኛ ፈልገነዉ ወይንም ተመኝተነዉ አይደለም ያገኘነዉ:: ከተወለድንበት ቤተሰብ ወረስነዉ እንጂ፤ አሁን ከተወለድንበት ቤተሰብ ዉጭ ተወልደን ቢሆን ኖሮ የዚያን ቤተሰብ ቋንቋ ነበር የምንይዘዉ:: ስለዚህ ሰዎች እንዲግባቡበት እንጂ የተለየ የታላቅነት ወይንም የብቃት ደረጃ መለያ ሆኖ እንዳልተሰጠን በመሃይም እዉቀታችን ቢሆንም ኅሊናችን ይመሰክርብናል:: የአገራችንና ብሔራዊ ቋንቋችንን እንድንጠላዉና እንዳንግባባበት፣ እንዳንማርበት፣ እንዳንሰራበት መደረጉ ግራ ገብቶናል:: እኛ በዉጭ አገር ተወልደን ቢሆን ኖሮ የዉጭዎቹን ቋንቋ ነበር የምንናገረዉ እንጂ አሁን እየተናገርን ያለዉን ቋንቋ አንናገርም ነበር:: ሌላዉ ቀርቶ ተማርን ተመራመርን እያላችሁ ሌላዉ አገር የራሱ ባልሆነ ቋንቋ በእንግሊዘኛዉ፣ በአረብኛዉ፣ በፈረንሳይኛዉ... ወዘተ ተዋህዶበት ሲገኝ፤ እኛ በራሳችን በኢትዮጵያዉያን ኢትዮጵያዉኛ ቋንቋ (አማርኛ) እንዳንግባባበትና እንዳንዋሀድበት የተደረገበት ምክንያት ለኛ ለኢትዮጵያዉያን ግልጽ አይደለም::

የእግዚአብሔር ቁጣ ሆናችሁ እንደ ባቢሎን ሰዎች እንድንከፋፈልና እንዳንደማመጥ እንዳደረጋችሁ ሁሉ፤ አሁን ደግሞ የእግዚአብሔር በረከት ሆናችሁ ከሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች የተወጣጣ ቃላት መስርታችሁ በአንድነት የምንነጋገርበት፣ የምንግባባበት፣ የምንማርበት፣ የምንሰራበት፣ ባጠቃላይ የምንዋሀድበት የጋራ ቋንቋ ትፈጥሩልን ዘንድ በማክበር እንጠይቃችኋለን::

ሌላዉ የተቸገርነዉ «እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ቋንቋዉን በማሳደግ ለአሁኑ ክልላዊ መንግስትነት ለወደፊቱ ደግሞ ለነጻ መንግስታትነት ማብቃት አለበት» ብትሉንም:: አንዳንድ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታችን ተወላጆች ጋብቻቸዉን የአፍ መፈቻ ቋንቋቸዉን እንደ ዋና መስፈርት ሳይመለከቱ የሌሎችን ብሔር ብሔረሰቦች አፍ መፍቻ ቋንቋ የሚናገሩትን እያገቡ የአፍ መፍቻ ቋንቋችንና ታላቅነታችንን የሚያስመሰክረዉን የማያዉቁና የማይናገሩ ልጆች እንዲወለዱ አድርገዋል:: ይህም በአፍ መፍቻ ቋንቋችን ላይ አደጋ የፈጠረና በሂደትም ብሔር ብሔረሰቦች ሊዋሀዱና ወደ አንድ መግባቢያ ቋንቋ ሊመጡ ስለሚችል፤ ይህም ታላቁ መንግስታችን ኢህአዴግና አጋር ድርጅቶች ህልዉናቸዉ የተመሰረተዉ በቋንቋ ክፍፍል ላይ ስለሆነ፤ የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር በተለመደዉ በአንድ ቀን ማርቀቅና ማጸደቅ ብቃቶት ተጠቅመዉ ጥያቄያችንን ለተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ «ማንም ብሔር ብሔረሰብ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ከማይመሳሰለዉ ብሔር ብሔረሰብ ጋር እንዳይጋባ::» ብለዉ አዋጅ እንዲያጸድቁልን በዚሁ አጋጣሚ እንጠይቃለን » በማለት አስተያየትና ጥያቄ አቅርበዋል::

ለጥያቄያቸዉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሲመልሱ « ይህች ቀን ለኔ ልዩ ቀን ናት:: ምክንያቱም ምኞቴና እቅዴ ሰምሮ ከሰማኒያ በላይ የብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋ መስማት በመቻሌና ሁላችሁም በአንድ ቋንቋ መግባባትና መናገር አቁማችሁና ተስኗችሁ በአፍ መፍቻ ቋንቋችሁ በአስተርጓሚ እኛ ዘንድ መቅረብ በመቻላችሁ ነዉ:: የቀኒቷን ታላቅነት ከሚያሳዩት ዋንኛ ክስተት አንዱ ደግሞ ይህ ነዉ:: ነገር ግን ያልገባችሁ አንድ ነገር አለ:: እኛ ሁላችሁም የምትግባቡበትና አንድ የምትሆኑበትን፤ በጋብቻ፣ በስራ፣ በትምህርት የምትዋሀዱበትን ቋንቋ ጠፍቶን አይደለም:: በመሆኑም ከየብሔር ብሔረሰቡ ቋንቋ እንደ ብሔረሰቡ ተዋጽኦ ቃላት ተፈጥሮ በአንድነት የምትነጋገሩበትን ቋንቋ መፍጠሩ አስፈላጊነቱ አልታየንም::

እኛ የታገልነዉ እኮ በጫንቃችሁ ላይ ለዘመናት የተጫነባችሁን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ያልሆነዉን ቋንቋ ልናስወግድላችሁና ለወደፊት እያንዳንዳችሁ ነጻ መንግስታትን ስትመሰርቱ የትምህርትና የስራ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን፤ የመነጋገሪያና የመግባቢያ፣ እንዲሁም የአፍ መፍቻ ቋንቋችሁ የወደፊት ነጻ መንግስታችሁንና አገራችሁን የምትመሩበት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ፕሬዘዳንት፣ ሚኒስትር፣ ባለስልጣን፣ ኃላፊ.. ወዘተ የምትሆኑበት ነዉ:: ስለዚህ ያቺን ዘመን በናፍቆትና በጉጉት ልትጠብቋት ይገባል እንጂ አሁን መግባባት አለመቻላችሁን፣ መደማመጥ አለመቻላችሁን፣ መከፋፈላችሁን፣ መቀራረብና መዋሀድ አለመቻላችሁን እንደትልቅ ጸጋና መንገድ ጠራጊነት ቁጠሩት::

ያለፈዉ ቀንበር የተጫነባችሁን የነፍጠኞችን ስርዐት ናፋቂና ተስፈኞች አትሁኑ:: ሌላዉ በመጨረሻ ያቀረባችሁት አስተሳሰብና ጥያቄ ምስጋናና ሙገሳ የሚቸረዉ ነዉ:: እስከዛሬ ድረስ ይህን ለልማትና ለእድገት የሚጠቅመዉን ማሰብ አለመቻሌና በአዋጅ አለማጸደቄ ራሴን እንደበደለኛ ቆጥሬዋለሁና በመስከረም በሚከፈተዉ በተከበረዉ ምክር ቤት ላይ አቅርቤ ካወያየዉ በኋላ አጸድቅላችኋለሁ:: እስከዛዉ ድረስ ግን በምታደርጉት ስብሰባ ላይ ለብሔር ብሔረሰቡ ግንዛቤ አስጨብጡ:: ይህን አሳብ ያመጣዉ ምሁር በዚሁ አጋጣሚ አድናቆቴን እየገለጽኩለት በብሔር ብሔረሰቦች ቀን ብሔራዊ ሽልማት እንደሚሸለም አዉቆ በብሔር ብሔረሰቦች አለባበስና ባህላዊ እምነት እንዲሁም ዘፈንና ጭፈራ እንዲገኝ በዚሁ ለማሳሰብ እወዳለሁ::

ሌላዉ እንድታዉቁት የምፈልገዉ እኔ ራሴ የሁላችሁንም ቋንቋ ብችል እንኳ መልሱን በአፍ መፍቻ ቋንቋችሁ  ብሰጥ ደስ አይለኝም:: ምክንያቱም በእናንተ ላይ ጫና የፈጠርኩ ስለሚመስለኝ ነዉ:: አማርኛንም የምናገረዉ ለጊዜዉ ከከፍተኛ ባለስልጣናትና ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ጋር ስለምንግባባበት ነዉ እንጂ ለወደፊት ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ራሳቸዉን ችለዉ ነጻ መንግስትነትን ሲመሰረቱ በአስተርጓሚ እንነጋገራለን:: ያኔ በብሔር በብሔር ፣ በጎጥ በጎጥ ተለያይቶ ማዉራት፣ መጫወት፣ መነጋገር፣ መወያየት የማያዳግም መፍትሔ ስለሚያገኝ በአንዳች ነገር አሳብ አይግባችሁ:: ከዚህ በተጨማሪ የክልላቱ

መንግስታት አስተያየታቸዉን ይሰጧችኋል::» በማለት ለቀጣይ ተናጋሪ ድምጽ ማጉዉያዉን ሰተዋል::

ቀጣይ ተናጋሪዉ የነበሩት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተወካይ ሲሆኑ እሳቸዉም « እናንተ ለዘመናት በገዥ መደቦች ጭቆናና ባርነት ዉስጥ የነበራችሁ፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋችሁ እንዳትማሩ፣ እንዳትሰሩ፣ እንዳትናገሩ የተደረጋችሁ ብሔር ብሔረሰቦች፤ እድሜ ለኢህአዴግ መንግስት ይኸዉ ሁላችሁም በአስተርጓሚ በአፍ መፍቻ ቋንቋችሁ ጥያቄዎቻችሁንና አስተያየታችሁን አቅርባችኋል:: ለዚህም የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር በዚህ አጋጣሚ እንኳን ደስ ያሎት እላለሁ:: ለወደፊቱ ደግሞ ሰማኒያ ብሔር ብሔረሰቦች ራሰቸዉን ችለዉ በነጻ መንግስትነት የራሳቸዉን ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ሚኒስትሮችና ባለስልጣናትን ሹመዉ ባስተርጓሚ እንዲገናኙ ተፈጥሮ ረጅም እድሜ እንድትሰጦት እመኛለሁ::

እኛ በክልላዊ መንግስታችን በራሳችን አፍ መፍቻ ቋንቋ መናገር፣ መማር፣ መስራት እንድንችል ሙሉ ዴሞክራሳዊ መብት ስለተጎናጸፍን ጎንበስ በማለት ምስጋናችንን እናቀርባለን:: በዚሁ አጋጣሚ ከብሔራዊ ክልላዊ መንግስታችን ወተዉ የሌሎች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ዉስጥ ድንበር ዘለዉ ቋንቋችንን በማስፋፋት ኢትዮጵያዉያን በጋብቻ፣ በጉርብትና፣ በስራ፣ በትምህርት እንዲዋሀዱ ያደረጉ የቀድሞ ገዥ መደቦች ነፍጠኞች የሰሩት ኢሰባዊና ግፍ ተግባር እያወገዝን፤ አሁን ግን በታላቁ መንግስታችን የበቃ አመራር አማርኛን ቋንቋ ከትምህርት፣ ከስራ ቋንቋነት እንዲወገድ ማድረጋችሁና በጋብቻ የተዋሀደዉንና የተዋለደዉን ሕዝብ ወደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ክልል እንዲገባ፣ እንዲፈናቀል፣ እንዲፋታ፣ እንዲለያይ በማድረጋችሁ በድጋሜ አድናቆቴን ለመግለጽ እወዳለሁ:: ለወደፊትም ቋንቋዉ በሰማኒያዉ ብሔር ብሔረስብ መንግስታት ዉስጥ ማንኛዉ አገልግሎት እንዳይሰጥበት ለማድረግ የሚጠበቅብንን ሁሉ ከመንግስታችን ጎን በመሰለፍ አስፈላጊዉን ሁሉ የምንፈጽምና ከዚህ በፊት የበደለዉን ያህል በቀል እርምጃ እንዲወሰድበት እናደርጋለን::

አንዳንድ ትምክህተኞች « ኢትዮጵያዉያን አይደላችሁምን? እስቲ ጎላ ጎላ ያሉትን የተጎናጸፋችሁትን ነጻነትና መብት እንዲሁም ዴሞክራሲ ግለጹልን?» በማለት ይጠይቁናል:: እኛም እድሜ ለልማታዊ መንግስታችን በየዓመቱ ሽልማት ይሰጠናል:: በፊት «እኛ አማራ

ነን» እንዳንል ተጽህኖ ይደረግብን ነበር:: አሁን ግን በአማራነታችን ኮርተን ይኸዉም በግልጽ «አማራ ነን::» እያልን እንናገራለን፤ እንመሰክራለን:: ለወደፊቱም ሕገ መንግስታችን በአንቀጽ 39 መሰረት የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከመገንጠል ድረስ ስለሆነ ለዘመናት ከተጨቆንበት ኢትዮጵያዊ ስያሜ ራሳችንን በመለየት ነጻ መንግስታችንን በመመስረት ታላቋን አማሪያን በመፍጠር አማራዊ ዜግነታችንን እናረጋግጣለን:: ለዚህ ዕድል ላበቃን ኢህአዴግ መንግስትና ለተሰፋችን ብአዴን ዘወትር ብናመሰግናቸዉ ያንሳቸዋል እንጂ አይበዛባቸዉም::

አንድ ትንሽ ቅሬታችንን በዚሁ አጋጣሚ እንገልጻለን:: ይኸዉም ብሔር ብሔረሰቡ በራሱ አፍ መፍቻ ቋንቋ እየተናገረ ምስጢሩን ሲጠብቅ፤ ብሔራዊ ቋንቋ ነዉ ተብሎ አማርኛ ብዙ ሰዉ ስለሚናገረዉ ምስጢራችን እየተሰማ ስለተቸገርን ለወደፊቱ በክልላዊ መንግስታችን ስር ብቻ እንዲነገር ቢደረግና ሌላ ብሔራዊ ቋንቋ ተፈጥሮ በአስተርጓሚ ብንግባባ የተሸለ መሆኑን በዚሁ አሳባችንን እናቀርባለን::» በማለት አስተያየታቸዉንና ቅሬታቸዉን በማቅረብ ለቀጣይ ተናጋሪ ድምጽ ማጉያዉን  አስተላልፈዋል::

በመቀጠልም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተወካይ « የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር ለዚህች እለት በመድረሶ እንኳን ደስ ያሎት እያልን፤ ነፍጠኞች ሳንፈልግ እንድናዉቀዉና እንድንነጋገርበት ባደረጉት ቋንቋ በአማርኛ በመናገራችን በመጀመሪያ ይቅርታ ይደረግልን እያልን በአፍ መፍቻ ቋንቋችን «ተናገሩ» የሚሉን ከሆነ በእሱ ማቅረብ ይቻላል» በማለት ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩም « ለወደፊት የራሳችሁን  ነጻ መንግስታችሁን ስትመሰርቱና አስተርጓሚ እስከምንመድብ ድረስ፤ እኔም ሳልፈልግ ነፍጠኞች እንዳዉቀዉና እንድናገርበት ስለተደረገ ሁለታችንም የተገፋንና በደል የተፈጸመብን ስለሆነ ለጊዜዉ በአማርኛ ቋንቋ ተናገር::» በማለት ስለመለሱላቸዉ፤ ተወካዩ ንግግራቸዉን በመቀጠል «እኛ ብሔር ብሔረሰቦች ለዘመናት የገዥ መደቦች በቋንቋችን እንዳንነጋገርበት፣ እንዳንማርበት፣ እንዳንሰራበት፣ ተጨቁነን፤ ባህላችንና ሃይማኖታችንን እንዳናሳድግ ተጽህኖ ተደርጎብን ነበር:: አሁን ግን እድሜ  ለፀሐዩ ንጉሣችን ሙሉ ነጻነታንንና መብታችንን ተጎናጽፈናል::

ይኸዉም በቋንቋችን እንድንነጋገርበትና ከሌሎች ልቀን የተገኘንበት መሆኑ እንዲታወቅ ተደርጓል። በዚህ ብቻ ሳያበቃ እንድንማርበትና የስራ ቋንቋችን እንዲሆን ተደርጓ። እንዲሁም ነፍጠኞች የጫኑብንን  የአማርኛ ፊደል የሆነዉን ሀ ሁ አስወግደን በላቲን ፊደላችን እንድንጽፍ ተደረጓል። የመንግስታችን ኢህአዴግና የተስፋችን ኦህዴድ ዓላማ ያልገባቸዉ ሰዎች «ሀ ሁ ፊደል የነፍጠኞች ሳይሆን የኢትዮጵያዉያን ነዉ። ሀ ሁ ፊደል የግእዝ ቋንቋ ፊደል ነዉ እንጂ  የአማርኛም የትግርኛም አይደለም። ሁለቱም ቋንቋዎች ከግእዝ ቋንቋ በኋላ በቅርብ ዘመናት የተፈጠሩ ናቸዉ እንጂ የጥንቱ የኢትዮጵያዉያን ብሔራዊ ቋንቋ የነበረዉ ግእዝ ነዉ። አማርኛም ቋንቋ የተፈጠረዉ ከተለያዩ ቋንቋዎች በመሆኑ የአንድ ጎሳ ቋንቋ ሳይሆን የሁሉም የኢትዮጵያዉያን የጋራ ቋንቋቸዉ ነዉ።» በማለት አስተሳሰባችንን ለመለወጥ ይጥራሉ።

እኛ ግን ለመንግስታችንና ለድርጅታችን ታማኝ በመሆን የማንነታችን መገለጫ የሆነዉን ላቲን ፊደላችንን ለቀጣይ ትዉልድ እንደምናስተላልፍ በዚሁ ቃል እንገባለን። በኛ በኩል ያለን አንዲት ቀለል ያለች ቅሬታ ሲሆን፤ ይኸዉም ቀደም ሲል የብሔር ብሔረሰብ መብታችን ተከብሮ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታችንን በመመስረት ወደ ዙፋን ላይ ስንወጣ እንደ ዘር ሀረጋችን አገራት አዉሮፓና አሜሪካ የዘመን አቆጣጠራችንን እየተጠቀምን እያለ ሳንፈልግ በአበሾች አቆጣጠር እንድንጠቀም በመደረጉ ነዉ። ነገር ግን «ነጻ መንግስታችሁን ስትመሰርቱ ያኔ ትጠቀሙበታላችሁ።» ብለዉ ቃል ስለገቡልን የተጽናናን መሆናችንንም እናሳዉቃለን። እዚህ ላይ እኛን ኦሮሞዎችን የማይወክሉ ጠባቦች « ብሔራዊ ክልላት መንግስታት የራሳቸዉን ነጻ መንግስት እስኪያቋቁሙ ድረስ የፌደራል መንግስቱ በብዙኃኑ ብሔረሰብ እንጂ በአናሳ ብሔረሰብ መመራት የለበትም» እያሉ የሚናገሩ የኤርትራ ቅጥረኛና አሸባሪዎች መኖራቸዉን በዚሁ ላነሳ እፈልጋለሁ። ለዚህ አስተሳሰባቸዉም ጠቅላይ ሚኒስትራችን አፍ የሚያዘጋ ምላሽ እንደሚሰጧቸዉ እገምታለሁ።

ከሁሉ በላይ ደግሞ የተጫነብንን የገዥ መደቦች ሃይማኖትና አምልኮ እንድናስወግድና በራሳችን ሃይማኖትና ባህል እምነት እንድንመላለስ ተደርጓል። ለዚሁም ማስረጃ ይሆን ዘንድ በየወንዛወንዙ ከምንፈጽመዉ አምልኮ በተጨማሪ በአገርና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቀዉን

በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች ከአገር ዉስጥና ከዉጭ መተዉ የሚያከብሩትንና የሚያመልኩትን የወንዙን አምላክ በቢሾፍቱ እዉቅና ተሰቶን እንድናከብርና አምልኮታችንን በተለያየ ምልኩ እንድንፈጽም ተደርጋል፡፡ ዱሮ እንኳን እንዲህ በግልጽ እንድናመልክ አይደለም «ጨሌ ባዕድ አምልኮ ነዉ፡፡ በየወንዛወንዙና በየተራራዉ የሚፈጸመዉ አምልኮ የአህዛብ አምልኮ ነዉ፡፡» በማለት ባህላችንንና እምነታችንን ያጥላሉብን ነበር፡፡አሁን ግን ፈረንጅ ሳይቀር ከአራቱም ማዕዘን መቶ የኦሮሞን አምላክ ያመልካሉ፡፡ ዶሮ የሚቃወሙትና የሚያጥላሉት የነበሩት የኦርቶዶክስ ሃይማኖት መሪዎች ዘመናዊዉን ቀሲስ ወክለዉ በመላክ በበዐላችን ላይ ተገኝተዉ ቡራኬ እየሰጡን አምላካችንን እንድናመልክና የተለያዩ አምልኮታችንን እንድፈጽም ያበረታቱናል፡፡ እግረመንገዳቸዉንም በሕገ መንግስቱ የሚከለከሉትን ወንጀሎች እንዳንፈጽም ይመክሩናል፡፡» በማለት ከተናገሩ በኋላ ለቀጣዩ ተናጋሪ ቦታዉን ለቀዋል፡፡

ቀጣይ ተናጋሪ የነበሩት የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተወካይ ሲሆኑ እሳቸዉም « የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር! ወድ ታጋዮቻችን መስዋዕትነትን ከፍለዉ ደማቸዉን አፍሰዉ በገዥ መደቦች በጭቆና ዉስጥ የነበሩት ወገኖቻችን ኤርትራዉያን ነጻነታቸዉን ተጎናጽፈዉ ነጻ መንግስታቸዉን መስርተዉ በዐይኖት እንዳዩ ሁሉ አሁንም ከሰማኒያ መንግስት በላይ እጬዎች ማየቶት የእድለኞች እድለኛ ያሰኞታልና እንኳን ደስ ያሎት፡፡ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ነጻ መንግስታቸዉን መስርተዉ እኛም በአንድነት እየተጋበዝን በራሳቸዉ አፍ መፍቻ ቋንቋ ሲናገሩ፣ ሲማሩ፣ ሲዳኙ፣ ሲሰሩ፣ ባጠቃላይ እቅዶትና ምኞቶት ተሳክቶሎት ይህች የገዥ መደቦች የሌሎችን እምነትና ባህል ጨፍልቀዉ የራሳቸዉ ሃይማኖትና ባህል አስፋፍተዉ የብሔር ብሔረሰቦች መጨቆኛ አገር የነበረችዉ «ኢትዮጵያ» የምትባል አገር ጠፍታ ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦች ነጻ መንግስት መስርተዉ ሲኖሩ ለማየት ያብቃዎት፡፡ ያብቃን፡፡

እናንተ ብሔር ብሔረሰቦች ደግሞ ከኅሊናችሁ ሊጠፉ የማይገባዉን የነፍጠኞች ግፍንና ጭካኔን ላስታዉሳችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ይኸዉም እነዚያ የገዥ መደቦች የሴቶቻችሁን ጡት እየቆረጡ፤ የወንዶቹንም ብልት እየሰለቡ ለዘመናት ሲያሳቃያችሁና ሲጨቁኗችሁ ነበር፡፡

ከሃይማኖታችሁ፣ ከባህላችሁ፣ እንዲሁም ከቋንቋችሁ ዉጭ ስማችሁን እንኳ ሳይቀር እየለወጡ ዮሐንስ፣ ኃይለማርያም፣ ወልደገብርኤል፣ ጳዉሎስ፣ ጴጥሮስ፣ ኢያሱ ..ወዘተ እያሉ ማንነታችሁን በመለወጥ በደል አድርሰዉባችኋል::

አሁን ግን እድሜ ለመንግስታችን የብሔር ብሔረሰብ ማንነታችሁን የሚገልጽ ስያሜ ለልጆቻችሁ በማዉጣት እናንተም በፍርድ ቤት ስማችሁን በማስለወጥ ላይ ትገኛላችሁ:: በሃያ ዓመት ዉስጥ ለእኩልነታችሁ፣ ለብልጽግናችሁ፣ ለማንነታችሁ ማረጋገጫ፣ ለዴሞክራሲ መብታችሁና ለነጻነታችሁ መረጋገጥ የልጆቻችሁ ስም ብቻ በቂ ምስክር ሊሆን ይችላል:: በኛ ክልላዊ መንግስታችን ወደጥንት ማንነታችን ለመመለስና ስም አወጣጣችንን ለማስተካከል የገዥ መደቦች የጫኑብን የሃይማኖት ተጽህኖ ከእናንተ ዘመናትን ያስቆጠረ በመሆኑ ሙሉ በሙሉ የትምክህተኞችና የነፍጠኞች መሸሸጊያ የሆነችዉን ቤተክርስቲያንን ስንቆጣጠር ያኔ የፈለግነዉን መስራትና መለወጥ እንችላለን:: ምንም እንኳን እላይ ያሉትን እንደፈለግነዉ ማሽከርከር ብንችልም፤ ሕዝቡ ገና ንቃተ ኅሊናዉ ስላልዳበረና «ሃይማኖትና እግዚአብሔር» የሚባለዉን ገዥ መደቦች ለመጨቆኛ የፈጠሩት መሆኑን ስላላወቀ፣ እንደ ፍላጎታችንና እቅዳችን በፍጥነት ልናከናዉንና ያሰብነዉ በቀላሉ መፈጸም አልቻልንም::

እኛ ጥቅም እስካገኘንበት ድረስ ማንኛዉም ሃይማኖት በአገሪቱ እንዲንሰራፋ እንፈልጋለን:: የዉጪ ፖሊሲያችን ማንኛዉንም ዓላማ የያዘ ሰዉ ብር ይዞ ይምጣ እንጂ ካለምንም ገደብ የፈለገዉን እንዲያከናዉን ሙሉ ነጻነትና ዴሞክራሲ የሚያጎናጽፍ ነዉ:: ያኔ ሕዝቡ በተለያየ ተጽህኖ ዉስጥ ስለሚወድቅ አሁን ያለዉን የግትርነት አቋሙን አስተካክሎ እኛ በምንፈልገዉ ርዕዮተዓለም እንደሚመላለስ ተስፋ እናደርጋለን:: ለዚህም ማሳያ በብሔራዊ ክልላዊ መንግስታችን ዋና ከተማ በመቀሌ የብሔር ብሔረሰቦች ቀን ሲከበር አብዛኛዉ ሕዝብ የብሔር ብሔረሰቡን የዳንኪራና የዘፈን ትዕይንት ሰማያዊ ትዕንት አድሮጎ ነዉ የቆጠረዉና የተያዩ የብሔር ብሔረሰቦች ሰንደቅ ዓለማን ሰማያዊ ሰንደቅ ዓለማ አድርጎ በመመልከት በታላቅ ሐሴትና ፈንጠዚያ ነዉ በዐሉን ያደመቀዉና ያገነነዉ:: በዚህም ምክንያት ጌታችን መሪያችን ገዥያችን የተለያዩ ምሶቹ የሆኑት ዘፈንና ዳንኪራ ስለቀረበለትና ዓርማዉን ኮኮብ

ስላገነንለት እንዲሁም ሕዝቡን ከጎናችን አሰልፈን ታላቅ ተግባራችንን ስለፈጸምንና ስላስፈጸምን ታላቅ ዋጋ እንደምናገኝ እናምናለን።

ታዲያ አንዳንድ የኛን ታላቅ ተግባር የማይደግፉና «የጽዮን ልጆች ነን» የሚሉ ትምክህተኞች፣ የገዥ መደቦች ርዝራዦችና የነፍጠኛ ስርዐት ናፋቅዎች፤« ስንትና ስንት ቅዱሳን ጻድቃን ከወጡበት ስፍራ፣ ታቦተ ጽዮን በቅርብ ርቀት ሆና እየታዘበችና ስለ ዐመጻ፣ ስለክህደት፣ ስለአምልኮ ምንዝርና ተግባራችሁና ንግግራችሁ ላይ ከምትመሰክርበት ቦታ፤ በቅዱስ ኪዳኑ ላይ ዐይን ያወጣ ዐመጻ እየፈጸማችሁና እያስፈጸማችሁ፣ በኢትዮጵያዊነትና በሰንደቅ ዓላማ ላይ ዐይን ያወጣ ክህደት እየፈጸማችሁና እያስፈጸማችሁ ሕዝቡ ተስፋዉን ምድራዊ አድርጎ እንዲኖርና እንዲመላለስ አድርጋችኋል። እንዲሁም ሕዝቡን በተለያየ ጥቅማ ጥቅምና ስልጣን ዐይኑን አሳዉራችሁት ለጥፋትና ለዉድቀት እየዳረጋችሁት ነዉ። ቀድሞ ለሃይማኖቱ ይቆረቆር እንዲሁም ለእግዚአብሔር ሕግና ስርዐት ዘብ ይቆም የነበረዉን የቅዱስ ኪዳን ሕዝብ ሳይቀር አሳምጻችሁታል፤ ርኩሰትን አስፈጽማችሁታል።

ስለዚህ እዉነተኛ ንስሐ ካልገባችሁ እናንተም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከወንበራችሁ ትቆረጣላችሁ፤ እናንተና መሰሎቻችሁ ዐመጻና ክህደት ከፈጸማችሁባትና ካስፈጸማችሁባት፣ ርኩስት ካነገሣችሁባት፣ እንዲሁም ብቸኛይቱን የሕይወት መንገድ ተዋህዶ ሃይማኖትን ለማጥፋት ቆርጣችሁ ከተነሳችሁበት ከቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ በእግዚአብሔር ቁጣ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ትጠረጋላችሁ።» በማለት የሚናገሩ ዐመጸኛና ሁከት ፈጣሪዎች ቢኖሩም፤ እኛ ግን የአገሪቷ ዋና ምሰሶ የሆነዉን የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል ድረስ የያዘዉን አንዳች እንከን የሌለዉን ሕገ መንግስታችንን ይዘን፣ የብሔር ብሔረሰቦችን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ አድርገን፣ ብቸኛዉን የሕይወት እምነታችንን አብዮታዊ ዴሞክራሲን ይዘን፣ የጨለማዉን ገዥ ጌታችንን አምነን ማንም ሊነካንና ሊነቀንቀን አይችልም። ይልቁኑ ስንት ምሁራን ከጎናችን ተሰልፈዉና ታላቅ ተግባራችንን እያደነቁና ምስክርነትን እየሰጡ፤ አብዮታዊ ዲሞክራሲ ስርዐታችንን አንቀበልም የሚሉትን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንደመስሳቸዋለን።

የገዥ መደቦች የሃይማኖት፣ የቋንቋ፣ የባህል ነጻነትን ገድበዉ በራሳቸዉ ሃይማኖትና ባህል እንዲሁም ቋንቋ ስር እንድንኖር በመደረጉ በስቃይና በመከራ ሕይወት ለዘመናት ኖረናል። አሁን ግን እድሜ ለመንግስታችንና ለተስፋችን ሕወሐት(ወያኔ) የሃይማኖትና የባህል ነጻነት ተሰቶን የፈለግነዉን ሃይማኖት እንድንከተልና ባህላችንንና ቋንቋችንን ልናሳድግ ችለናል።

በዚህ አጋጣሚ አንድ ቅሬታችንን መግለጽ እንወዳለን። ይኸዉም ከክልላችን ወተዉ በራሳቸዉ አፍ መፍቻ ቋንቋ መነጋገር፣ መምራት፣ ማስተዳደር ሲገባቸዉ እኛ እንዳንነጋገርበት፣ እንዳንማርበት፣ እንዳንሰራበት በተደረገዉ አማርኛ ቋንቋ በመጠቀም እየተነጋገሩበት፣ እየተማሩበት፣ እየሰሩበት ስለሆነ፤ ይህም በአፍ መፍቻ ቋንቋችን ላይ ተጽህኖ እያመጣብን ስለሆነ ቋንቋዉን ቢችሉ እንኳ በአስተርጓሚ ቢናገሩና ቢሰሩ ይሻላል እንጂ ለብሔር ብሔረሰቦች አርአያ መሆን ሲገባ እኛዉ ራሳችን  ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋዉን እንዲጠቀሙ እያደረግን ለወደፊት ነጻ መንግስታቸዉ ዉስጥ ቋንቋዉ የመናገር እድል እንዲኖረዉ እያደረግን ስለሆነ ጥንቃቄ ሊደረግበት እንዲሚገባ በዚሁ አሳስባለሁ። ሌላዉ ደግሞ አንዳንዶች «ነጻ መንግስትነታችን እንደ ኤርትራ ቶሎ መታወጅ ይኖርበታል» እያሉ ያቻኩሉናል። እዚህ ላይ ኤርትራ ቶሎ መገንጠሏና ከመንግስታችን ጋር ቅራኔ በመፍጠሯ ተጎዳች እንጂ አልተጠቀመችም። ስለዚህ ቀስ ብሎ መገንጠል ጥቅም አለዉ እንጂ  ጉዳት እንደሌለዉ በዚህ አጋጣሚ እንድታዉቁት እፈልጋለሁ። » በማለት አስተያየታቸዉን ሰተዋል።

በማስከተልም የሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተወካይ « ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር በቅድሚያ እንኳን ደስ ያሎት እያልን፤ አንድ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነዉ የወገኖቻችን ሱማሊያ ሕዝብ በጎሳ እርስ በእርሱ ተከፋፍሎ ሲገዳደል፣ አንድ መንግሰት መመስረት ተስኗቸዉ ለአስራ ዎቹ  ዓመታት መንግስት አልባ ሆነዉ መኖራቸዉን አስተዉለዉ፣ በአርቆ አሳቢነቶ እርሶም በአንድ ቋንቋ ሊግባባና ሊዋሀድ የነበረዉን የኢትዮጵያን ሕዝብ፤ በአንድ ቋንቋ ከተግባባ የሱማሊያ አገር እጣ ፈንታ ይደረስባቸዋል በሚል ስጋት በብሔር ብሔረሰብ ቋንቋ ልዩነት የክልል መንግስታትን ፈጥረዉ ሕዝቡ እንዲከፋፈልና እንዲለያይ እንዲሁም እንዳይዋሃድና አንድነት እንዳይፈጥር በማድረጎት ምን ያህል አስተዋይ ሰዉ መሆኖትን

የሚገልጽ ስለሆነ በዚሁ አጋጣሚ ለእርሶ ያለንን አድናቆት ለመግለጽ እፈልጋለሁ:: ለወደፊት ደግሞ በፍጥነት ሰማኒያዉም ብሔር ብሔረሰቦች ነጻ መንግስታቸዉን መስርተዉ የራሳቸዉ ጠቅላይ ሚኒስትርና ሚኒስትሮች እንዲሁም ባለስልጣናት ኖሯቸዉ ማየትን እመኛለሁ::

እዚህ ላይ ቅሬታ ሳይሆን የጠቅላይ ሚኒስትራችንን ርኅራኄ ለመናገር እፈልጋለሁ:: ይኸዉም ራሳቸዉ «የምንመድብላችሁን ገንዘብ በደንብ ተጠቀሙበት::» እያሉ እኛም እድሜ ለፀሐዩ ንጉሣችን እያልን ያልደከምንበትንና ያለፋንበትን ገንዘብ ቁጭ ብለን እንድንበላ፣ እንድንቅምበት አድርገዉ አንዳንዴ ሲበሳጩ እንደሚናገሩት የትግል አጋሮቻቸዉን እንኳ ሳይቀረ «የበከተ አስተሳሰብ፤ የበከቱ » እያሉ ስለሚሳደቡ እኛንም አንዳንዴ ሲመጣባቸዉ «የተቀደደ በርሜል» እያሉ የብር አባካይነታችንን ቢናገሩንም፤ ተመልሰዉ « በፓለቲካዉ ታማኝ ሁኑ፣ ኅሊናችሁን ለእኛ አመቻችታችሁ «በሉ፤ አድርጉ::» የምንላችሁን ፈጽሙ እንጂ አንዳች ስጋት አይግባችሁ:: እኛም እንደእናንተ በግልጽ ባይሆንም በብልጠት የምናደርገዉ ነገር ነዉ::» እያሉ ስለሚያጽናኑን በዚሁ ደግነታቸዉን ለመግለጽና እስከመጨረሻ ድረስ ታማኝ መሆናችንን እንዲያዉቁልን እንፈልጋለን::» በማለት አስተያየታቸዉን ሰተዋል::

በማስከተልም የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተወካይ «ለዚህች ቀን ያደረሰን አብዮታዊ ዴሞክራሲ መንግስታችን ምስጋና ይድረሰዉ እያልኩ ያለኝን አስተያየት አቀርባለሁ:: እኛ ለዘመናት በጭቆናና በግፍ ሕይወት ስንማቅቅ ኖረን አሁን የራሳችን መንግስት መመስረት እንድንችልና በከተማ እንዳንኖር ተከልክለን የነበረዉ የገዥ መደቦች ዉሳኔ ተሽሮ በሚያማምሩ ከተማ ዉስጥ እንድንኖር በመደረጉ ለጠቅላይ ሚኒስትራችንና ለመንግስታችን ታላቅ ምስጋና እናቀርባለን:: በዚሁ አጋጣሚም አጎራባች መንግስታት የሆነዉ የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በተለየ ሁኔታ ከጎናችን በመሰለፉና ለወደፊቱ ነጻ መንግስትነት ምስረታ ለማብቃት ከፍተኛ ጥረት በማድረጉ ምስጋናችንን በተለየ ሁኔታ እናቀርብለታለን » በማለት ተናግረዋል::

በማስከትል የሐረሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተወካይ « የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር እንኳን ደስ ያሎት እያልን በክልላችን መንግስት አቋቁመን በቋንቋችን እንድንነጋገር እድሉን ስለተሰጠን እናመሰግኖታለን:: በክልላዊ መንግስታችን ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች በጋር

ስለሚኖሩ እንዳንዶቹ ደግሞ ከብዙ ብሔር ብሔረሰቦች የተዋሃዱ ስለሆነ ለወደፊቱ ነጻ መንግስት ለመመስረት ልንቸገር እንደምንችል ያለንን ስጋታችንን በዚሁ አጋጣሚ እንገልጻለን:: ይኸዉም የነጻ መንግስታችን ቋንቋ መሆን ያለበት የራሳችን አፍ መፍቻ ቋንቋ መሆን እንዳለበት ብናምንም በዙሪያችንና በከተማችን የኦሮምኛና የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ስለሚበዙ ከወዲሁ ጥምር ቋንቋ እንዲዘጋጅልን ወይንም የመነጋገሪያ፣ የመማሪያና የስራ ቋንቋን የአፍ መፍቻ ቋንቋችን እንዲሆን ከወዲሁ ማረጋገጫ እንዲሰጠን እንጠይቃለን?» በማለት አስተያየታቸዉንና ጥያቄዎቻቸዉን አቅርበዋል::

በማስከተልም የጋንቤላ ብሔራዊ ክልል መንግስትና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት « ያለን አስተያየት ተመሳሳይ ስለሆነ በአንድ ተወካያችን ነዉ የምናቀርበዉ::» በማለት በተወካያቸዉ በኩል « እንኳን ደስ ያሎት ጠቅላይ ሚኒስትራችን:: ብሔራዊ ክልሎቻችን የተለያዩ ብሔር ብሔረሰብ ተዋህደዉበትና በአንድላይ ተጨፍልቀን የምንተዳደር ስለሆነ፤ እንደሌሎቹ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የየራሳችን ክልላዊ መንግስት እንዲፈጠርልንንና ቋንቋችንን የመነጋገሪያ፣ የመማሪያ፣ እንዲሁም የስራ ቋንቋ እንዲሆንል እንጠይቃለን?» በማለት አስተያየታቸዉንና ጥያቄዎቻቸዉን አቅርበዋል::

በማስከተልም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ተወካይ « የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር! እኛ እንኳን ደስ ያሎት ለማለት ይከብደናል:: ምክንያቱም «ለእኩልነት፣ ለነጻነት፣ ለዴሞክራሲ የቆምን ነን» እያላችሁ፤ ይኸዉ ዱሮ በአንድነት ተጨፍልቀን እንድንኖር የተደረገብን ግፍና በደል በእናንተ ዘመን እንደገና መደገሙና ከአምሳ በላይ ብሔር ብሔረሰቦችን በአንድላይ ጨፍልቃችሁ በነፍጠኞች ቋንቋ እንድንነጋገር፣ እንድንግባባ፣ እንድንማርበት፣ እንድንሰራበት በመደረጉ ነዉ:: ከኛ መሀል እንኳ አንዳንድ ብሔሮችን እየመረጣችሁ በራሳቸዉ በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲናገሩ፣ እንዲማሩበት፣ እንዲሰሩበት ታደርጋላችሁ፤ ብዙዎቻችንን ግን በመጨፍለቅ ታስተዳድሩናላችሁ::

«ኢትዮጵያዉያን ናችሁ፤ በአንድ ላይ ኑሩ::» የሚሉን ከሆነና «ኢትዮጵያ» የምትባል አገር መኖሯን ከልቦት ካመኑና «ኢትዮጵያዉያን» የሚባሉ ዜጎች መኖራቸዉን ካስተዋሉ፤

ይህን የተንኮልና የመሰሪነት እንዲሁም የበቀለኝነት አገዛዞትን ይተዉና በዘር፣ በጎጥ፣ በቋንቋ ሳንከፋፈልና ሳንጠላላ እንዲሁም ሳንለያይ እንደ ኢትዮጵያዊነታችንና እንደ አዳም ዘርነታችን በፍቅር፣ በሰላም፣ በአንድነት እንድንኖር አድርጉ እንጂ በአንዱ ጎሳ ላይ አንዱን ጎሰ፤ በአንዱ ብሔር ላይ አንዱን ብሔር እያነሳሳችሁ በቋንቋ ሽፋን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ልክ እንደ ኤርትራ ለመገንጠልና ኢትዮጵያዊነት ዜግነትን ለማስካድ የምታደርጉትን የወደፊት ምኞታችሁንና እቅዳችሁን ለማሰካትና የትግራይ አገርና ትግራዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ የኦሮሚያን አገርና ኦሮሚያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ የአማሪያን አገርና አማራዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ሱማሊያን2 አገርንና ሱማሌያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ አፋሪያን አገርንና አፋራዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ሐረሪያን አገርና ሐረሪያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ጋምቤሊያን አገርና ጋምቤሊያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ቤንሻንጉሊያን አገርና ቤንሻንጉሊያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ሲዳሚያን አገርና ሲዳማዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ሃዲዩያን አገርና ሃዲያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፤ ወላይቲያን አገርና ወላይታዉያን ዜጎችን ለመፍጠር.. ወዘተ ዜጎችን ፈጥረዉ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ለማጥፋት መነሳሳቶትን ያቁሙ:: በአሁን ሰዐት የክፋትና የተንኮል ተግባራችሁን ሕዝቡ በደንብ አዉቋል:: ዝም ያላችሁም በጦራችሁና በደጎንነታችሁ ኃይል ተመክታችሁ ስላስፈራራችሁት ነዉ እንጂ ከተፋችሁ ብዙ ዓመታትን አስቆጥሯል:: በፊትም ተንኮላችሁ ስላልገባዉ ነዉ እርሱ በእርሱ የተጣላዉና የተገዳደለዉ፣ የተከፋፈለዉ::

ከጎኖትም የተሰለፉት እንሆዱ አምላካቸዉና የስልጣን ጥመኞች ለጥቅም፣ ለክብር፣ ለዝና ሲሉ ኅሊናቸዉን የሚሸጡት ናቸዉ:: «በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳንባ ነዉ የሚተነፍሱ::» የሚባሉት ናቸዉ አብሮዎት ከልብ የሚያገለግሎት እንጂ ሕዝቡ ማንነታችሁን ስላወቀ ሁሉን ነገር ትቶ ለአምላኩ እጁን ከሰጠ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል:: አብሮት ያሉት የሚያጫፍሮትም ጊዜ እስከሚካዳዎት ነዉ እንጂ ወደ ልባቸዉ ሲመለሱና የማን እንደራሴ መሆኖትን ሲያስተዉሉ አንቅረዉ ነዉ የሚተፎት:: ስለዚህ እርሶም ቢሆን ወደልቦት ተመልሰዉ እጆትን ለፈጣሪ ቢሰጡና ወንበሩንም በእግዚአብሔር ለተመረጡትና ለተቀቡት

ለእዉነተኛ እንደራሴዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ቢለቁ ያተርፋሉ እንጂ አይጎዱም:: እንቢ ብለዉ እንደፈርኦን ኀሊናዎን ካደነደኑ ደግሞ ደንዳናዎች የገጠማቸንዉን ጽዋ እንደሚጎነጩ አንዳች አይጠራጠሩ::

ከዛሬ ቀን ጀምሮ ስለኢትዮጵያና ስለ ኢትዮጵያዊነት ለማዉራት ብቃቱና ሞራሉ ስለሌሎት ከእርሶና ከቢጤዎቾ ጋር ምንም አንድነትና ህብረት ፈጥረን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር አንሰራም፤ ተባባሪም አንሆንም:: እናንተ የዘረኝነትና የጎጠኝነት ፓሊሲ አራማጆች፤ በብሔር ብሔረሰቦች ስም የምትነግዱ፤ ኀሊናችሁን የምትገለባብጡና የምትሸጡ አስመሳይ አገልጋዮች፤ የዲያብሎስ ስርዐት ፈጻሚና አስፈጻሚ ሆናችሁ ሕዝቡን መከራዉንና ፍዳዉን የምታሳዩ፤ እርስ በእርስ እያጣላችሁና እየከፋፈላችሁ የራሳችሁን መሰሪ ተግባር የምትፈጽሙ፤ ስለ ክፋትና ጭከና ተግባራችሁ ዋጋ እንደምትከፍሉበት ልታዉቁ ይገባል::

ኀሊናችሁ በክህደት ፍልስፍና የተሞላ፤ የማርክስ፣ የኤንግልስ፣ የሌኒን፣ የቻርልስ ዳርዊን የመሳሰሉት የክህደት እምነቶችን አምጥታችሁ « ዘሮቻችሁ  አዳምና  ሔዋን ሳይሆኑ ጦጣ መሰል እንስሳዎች ናቸዉ:: በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ(በኢቮልሽን) አማካይነት ነዉ ሰዉ የሆናችሁት:: አምላክ የሚባል ያመጡት እናንተን ለመጨቆኛ መሳሪያ እንዲሆናቸዉ የገዥ መደቦች ናቸዉ::» በማለት የምትናገሩና የምታስተምሩ አንዳች ሀፍረት የማይታይባችሁ ከሃዲዎች ናችሁ:: እዉነተኛ ማንነታችንን ያስካዳችሁና አሁን ደግሞ በቋንቋ ለያይታችሁን እርስ በእርስ በጥላቻና በቂም በቀል እንድንመላለስ ያደረጋችሁ ዐመጸኞች ናችሁ:: አሁን ግን ልታፍሩ ይገባችኋል::

እኛ የአንዱ እግዚአብሔር ፍጥረቶችና ልጆቹ የሆን ዘሮቻችንም ጦጣዎች መሰል እንስሳት ሳይሆኑ የከበሩ ሕያዋን ፍጥረቶች አዳምና ሔዋን ናቸዉ:: ነገዳችንም የኖኅ ልጆች የሆኑት የካም፣ የሴም፣ የያፌት ዉህድ ዘር የሆነዉ ኢትዮጵያዊ ነን:: ብሔራችንም ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነዉ:: እናንተ ግን እዉነተኛ ማንነታቸንን እያጠፋችሁ «የማንነታችሁ መለያ የሆነዉ ቋንቋችሁ ነዉ» በማለት የራሳችሁን መሰሪ ፍላጎት ማሚያ አደረጋችሁን:: ዓለም ወደ አንድ መንደርነት እየተለወጠችና አገራት እየተዋሀዱ ባለበት ዘመን እናንተ ትንሿን

አገር በጎጥ ከፋፍላችሁ፣ ምንም እንደማናዉቅ ሰዎች አድርጋችሁ በመቁጠር « ይህ የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነዉ። ያ ደግሞ የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ነዉ። ብሔር ብሔረሰቦች ዙፋን ላይ ስላስቀመጥናችሁ ለስልጣናችሁና ለክብራችሁ ዙፋኑን ላለመልቀቅ እስከ መጨረሻዉ ድረስ የሞት ሽረት ማድረግ አለባችሁ።» በማለት እንኳን የተማረ ፊደል የቆጠረ አይደለም ሀ ሁ ን እንኳ የማያዉቅ መሃይም ይህን አስተሳሰብ ፈጥሮ ኢትዮጵያዉያንን አያጃጅልም ነበር። እናንተ ግን ተማርን የምትሉ ይህን ለመፍጠርና ወደ ተግባር ለመለወጥ ኅሊናችሁ ፈቃደኛ ሆነ። ወደተግባርም ለወጠዉ። ይህም አስገራሚ ፍጡሮች መሆናችሁን ነዉ የሚያሳየዉ።» በማለት በምሬት እየተናገሩ እያለ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ትዕግስታቸዉ አልቆ ወዲያዉ ወደ ልዩ እስርቤት ተይዘዉ እንዲሄዱ ትዕዛዝ ለሚመለከተዉ አካል በመስጠታቸዉ፤ ተወካይ ተናጋሪዉ ለሰዉ ርኅራኄ በሌላቸዉ ልዩ ኃይሎች እየተዳፋና እየተቀጠቀጡ ተወሰዱ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩም ከተቀመጡበት በቁጣና በንዴት ተነስተዉ «የብሔር ብሔረሰቦች ተወካዮችና የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ተወካዮች እንዲሁም ተጋባዥ እንግዶች፤ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ተወካይ በስተቀር ሁላችሁም አርቆ አሳቢና አስተዋይ መሆናችሁን ንግግራችሁ ይገልጻል። ለዚህም በታላቁ መሪያችንና ገዥያችን ስም አመሰግናችኋለሁ። እስከዛሬ ድረስ ጨርቁን ሰንደቅ ዓላማና አዲሲቷን ኢትዮጵያ በትዕግስት የጠበኩት በቅድሚያ መስተካከል ያለባቸዉ ነገሮች እንዲስተካከሉ በማሰብ ስለነበረ አሁን በምንፈልገዉ የኢኮኖሚ፣ ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊ ደረጃ ስለደረስን ከሚከጥለዉ ዓመት ጀምሮ እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ነጻ መንግስትን መስርቶ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን የሚለዉን ስም ከምድረ ገጽ ማጥፋት ይችላል።

እኔ ተልእኮዬንና ሩጫዬን ጨርሻለሁ። እናንተ አጉል ተስፈኞች «የኢትዮጵያ ትንሳኤ ይመጣል።» በማለት የምትጠባበቁ ከዛሬ ጀምሮ ተስፋችሁን ሙሉ በሙሉ ልትቆርጡ ይገባል። ከፈለጋችሁ ወደ አዉሮፓ፣ አሜሪካ፣ ኤሽያና አረብ አገራት መሰደድ ትችላላችሁ። ከሚቀጥለዉ ዓመት ጀምሮ «ኢትዮጵያ » የሚባል ስም በብሔር ብሔረሰቦች አገራት አይጠራም» በማለት ንግግራቸዉን የቋጩ ሲሆን፤ እኔ የጨለማዉ ገዥና የእሳቸዉ ደጋፊዎች

በንግግራቸዉና በዉሳኔያቸዉ ደስታችንንና ጭፈራችንን በብሔር ብሔረሰቦች ዘፈንና ዳንኪራ ሳናጣጥም እንዲሁም አንዳንዶች የስብሰባዉ ተሳታፊዎች በጠቅላይ ሚኒስትሩ ንግግር ከመደሰታቸዉ የተነሳ ራሳቸዉን እስከሚስቱ ሲዘሉና ሲፈነድቁ እንዳለ፤

ወዲያዉ ከወዴት እንደመጡ የማይታወቁ አንዳንዶቹ ባዶ እግራቸዉን ካለ ጫማ፣ አንዳንዶቹ ራቁታቸዉን ሰንሰለት ታጥቀዉ፣ አንዳንዶቹ ጸጉራቸዉና ጺማቸዉ አድጎ እብድና ሽፍታ መስለዉ፣ አንዳንዶች ከእድሜዉ ብዛት ቆብ ይሁን ባርኔጣ ወይንም ሰሌን ምን እንደሆነ ተለያቶ የማይታወቀዉን በአናታቸዉ ላይ ደፍተዉ፣ አንዳንዶቹ ሆድ ያላቸዉ እንኳ የማይመስል ከአንጀታቸዉ ጋር የተጣበቀ፣ አንዳንዶቹ ጉንጭ የሚባል ያላቸዉ እንኳ የማይመስል ጉንጭና ጉንጫቸዉ የተጣበቀ፣ አንዳንዶቹ ከመጎሳቆላቸዉ የተነሳ ሰዉ የማይመስሉ ቡቱቶ ለብሰዉ፣ አንዳንዶቹ ነጭ የአገር ባህል ለብሰዉ፣ ባጠቃላይ ያልተጠበቁ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ የቀይ ዳማ መልክ የተላበሱ ሰዎች ወደ ስብሰባዉ መድረክ መጡ።

በጠቅላይ ሚኒስትሩና በባለስልጣናቱ ፊት በመቆም « እናንተ አባቶች እናቶች ወንድሞችና እህቶች ሁላችሁም እንዳላችሁት በእናንተ አገላለጽ ባይሆንም ዛሬ የተለየች ቀን የእግዚአብሔር እዉነት ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝቦች የሚገለጽበት ነዉ። ለዚህች ቀን ያበቃንን ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን። አሁን ከፊታችሁ የምታዩን ሰዎች እናንተ እንድንሆን እንደምትፈልጉትና እንደምትመኙት ትግራዉያን ፣ ኦሮሚያዉያን ፣አማራዉያን ፣ ሱማሊያዉያን ፣ አፋሪያዉያን ፣ ሐረሪያዉያን ፣ ጋምቤላዉያን ፣ ቤንሻንጉልያዉያን ፣ ደቡባዉያን ፣ ሰሜንያዉያን ፣ ምዕራባዉያን ፣ ምስራቃዉያን ፣ ኤርትራዉያን ሳንሆን፤ የእግዚአብሔር ምስጢር አገሩ የሆነችዉ የኢትዮጵያ ዜጎች የሆን ኢትዮጵያዉያን ብቻ ነን። የማንንም ጎሳ በሉ ብሔር ብሔረሰብ እንዲሁም ቋንቋና ዘር አንወክልም። እኛ የአንዱ ፈጣሪ እግዚአብሔር ሕያዋን ፍጥረቶቹና ልጆቹ የሆን ፣ የዘር ግንዳችንም አዳምና ሔዋን ብቻ የሆኑ፣ የኖኅ ልጆች የሆኑት የካም የሴም የያፌት ነገዶች ዉህድ የሆነዉ ዘር ኢትዮጵያዉያን ነን።

እናንተ ግን አስተሳሰባችሁ፣ ንግግራችሁ፣ ተግባራችሁ እጅግ ይገርማል:: ራሳችሁን ከሰዉነት ባሕርይ እንደለያችሁ ይሰማናል:: በእርግጥ በተለይ እናንተ «ተማርን፣ ተመራመርን፣ አዋቂዎች፣ ምሁሮች ነን» የምትሉ፤ የዘር ሐረጋችሁ አዳምና ሔዋን ሰዎች መሆናቸዉን ክዳችሁ «ከእንስሳ መሰል ከጦጣ በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ(በኢቮልሽን) አማካይነት ነዉ አሁን ላለንበት ሰዉነት ደረጃ የደረስነዉ:: እኛ እንስሳት ነን::» በማለት በራሳችሁ ላይ ማንነታችሁን እየመሰከራችሁና እያሳወቃችሁ ቢሆንም፤ እኛ የሚያሳዝኑን ከህጻንነታቸዉ ጀምሮ እግዚአብሔርን በመፍራትና በማምለክ የሚያድጉት ሕዝቦች ገና ትምህርታቸዉን ሲጀምሩ በክህደት ፍልስፍና መመረዛቸዉና በዘረኝነትና በጎጠኝነት ሕይወት እንዲመላለሱ አድርጋችሁ አስተሳሰባቸዉ አሁን እንደምናየዉና እንደምንሰማዉ ሆኖ እንዲገኝ ማድረጋችሁ ነዉ::

ማን? ምን? ኬት? መሆናችሁን ዘንግታችሁ በዚህ የከፋና የከረፋ አስተሳሰብ ዉስጥ ሆናችሁ፤ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወታችሁና አቋማችሁ መጽናታችሁ ምን ያህል ደንዳና ልቦና እንደያዛችሁ የሚገልጽ ነዉ:: ማንነታችሁንና አቅማችሁን አስተዉላችሁ ቢሆን ኖሮ ከኛ በበለጠ ሁኔታ በከተማ፣ በገጠር፣ በዋሻና በጫካ ዉስጥ ሆናችሁ ራሳችሁን ዝቅ በማድረግ ወደ አምላካችሁ ተደፍታችሁ ለአገራችሁና ለሕዝቡ ትጸልዩና ታነቡ ነበር:: አገሪቷም ከዐመጻ፣ ከክህደትና ከርኩሰት ሕይወት የምትጸዳበትን ጊዜ ትናፍቁ ነበር::

ነገር ግን እናንተ የኀሊናችሁ መሪ ያደረጋችሁት የክፋት፣ የተንኮል፣ የምቀኝነት ፣ የጥላቻና የበቀል እንዲሁም የዐመጻና የክህደት መንፈስ አባት የሆነዉን ዲያብሎስን ስለሆነ፤ እንዴት ወደ ልባችሁ ትመለሱ!? እንዴት ቀና ታስቡ? እዉነትን ትናገሩ? መልካም ትሰሩ? ስለ እዉነት ትመስክሩ? የአገርና የወገን ፍቅር ይኑራችሁ? እንዴት እግዚአብሔር መፍራት ይደርባችሁ? ተስፋችሁን ሰማያዊ አድርጋችሁ በሰላም፣ በፍቅር፣ በእርካታ፣ በአንድነት፣ በበረከት፣ በመተሳሰብ፣ በመረዳዳት፣ በመተዛዘን ትኖሩ? እንዴት ያደፈና የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርያችሁን አስተዉላችሁ በእግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁ ትኖሩ? እንዴት ጎስቋላ ኑሮዋችሁንና ሕይወታችሁን ተገንዝባችሁ፤ የሕዝብ አገልጋይ ባሪያ መሆናችሁን

ተረድታችሁ፤ ለሕዝቡ የሚጠቅመዉን፣ የሚበጀዉን፣ የማይጉላላበትን ፣ የማይማረርበትን፣ የማይሰቃይበትን ፣ የማይቸገርበትን፣ የማያዝንበትን፣ አድሎና በደል የማይፈጸምበትን፣ ግፍና ጭቆና የማይደረግበትን፣ ለእስርና ለስደት የማይዳረግበትን፣ ደኅንነቱ የሚጠበቅበትን፣ አንድነቱና ህብረቱ የሚጠናከርበትን ስርዐት ትዘረጉ? እንዴት ትዉልዱ አምላኩን አዉቆ በእዉነትና በመንፈስ አምልኮቱን በመፈጸም በምድራዊ ሕይወቱም ዘመን ተባርኮ ለሰማያዊ ሕያዉ ሕይወት እንዲዘጋጅ ታደርጉ? እንዴት ስለ እዉነት ራሳችሁን ክዳችሁ በእዉነት ትኖራላችሁ? ስለ እዉነትም ትመሰክራላችሁ?

አዎ! እናንተ ከተመቻቸላችሁና ከደላችሁ ምኞታችሁ ከሰመረ፤ ሕዝቡ ተመቸዉ አልተመቸዉ ስሜት አይሰጣችሁም፤ ተራበ አልተራበ፣ ተቸገረ አልተቸገረ፣ አዘነ አላዘነ ደንታ የላችሁም። ሕዝቡ እርስ በእርስ ተከፋፈለ አልተከፋፈለ፣ ተጣላ አልተጣላ፣ ተገዳደለ አልተገዳደለ፣ አገሪቷ ተበታተነች አልተበታተነች፣ ጠፋች አልጠፋች አንዳች የማይቆረቁራችሁ፤ ይልቁኑ ከጀርባቸዉ ሆናችሁ የምታቀጣጥሉ፣ የምትደግፉ፣ የምታበረታቱ፤ ዐመጻን ፣ ክህደትን ፣ ርኩሰትን ያነገሣችሁ ናችሁ። የዲያብሎስ ፈቃድ ፈጻሚና አስፈጻሚ በመሆን ክፋትን ፣ ተንኮልን፣ ጥላቻንና በቀልን፣ ምንዝርናን፣ ባዕድአምልኮትን፣ ዘፋኝነትንና ዳንኪርተኛነትን ፣ ባጠቃላይ እግዚአብሔር የሚጠላዉንና የጨለማዉ ገዥ ደስ የሚሰኝበትን ሕይወትና ተግባር የምታስፋፉ የዲያብሎስ አገልጋዮችና ባለሚሎች ናችሁ።

እናንተ « ሕዝቡን ከፋፍለናል፤ ለአንድ ዓላማ እንዳይቆሙ አድርገናል፤ ጥላችንና በቀልን ዘርተናል፤ ኢትዮጵያዊነትንና የአንዲት ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ቀንሰናል፤ አጥፍተናል፤ ኅጣዊ አስተሳሰብን አንግሠናል፤ አንዱን በአንዱ ላይ አነሳስተናል፤ ካድሬዎቻችንን አብዝተናል፤ ትዉልዱ ኅሊናዉን እንዲሸጥና እንደ ቦይ ዉኃ እንዲነዳ አድርገናል፤ ማንነቱንም አስጠፍተናል፤ ሕዝቡ እርስ በእርስ እንዳይተማመን ደኅንነቶቻችንና ካድሬዎቻችንን በየቦታዉ ሰግስገናል፤ ጦራችንንም አጠናክረናል፤ ልዩ ኃይል አቋቁመናል። በመሆኑም ማንም ከወንበራችን አያወርደንም፤ ስልጣናችንን ለትዉልድ እናስተላልፋለን፤ የፈለግነዉን እንደፈለግን እናደርጋለን» በማለት ታብያችኋል።

ነገር ግን የየዋሁና የቅኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ አምላክ ስለ ሕዝቦቹ ሲል የዘራችሁትን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ የዘረኝነት ፣ የጎጠኝነት ፍሪያችሁን በቅርቡ እንደሚያሳጭዳችሁና መራራዉን ፍሬያችሁን ከዐመጸ ተባባሪዎቻችሁ ጋር እንደምትጠጡ ልታዉቁ ይገባል:: የስልጣንና የባለጊዜነታችሁ ጊዜ በአራት ነጥብ ተደምድሞባችኋል:: ስንት «ኃያላን» የተባሉ «ማንም አይነካቸዉም፣ አይነቀንቃቸዉም» የተባሉ ሰዎችና መንግሥታት እንዳልነበሩ ሲሆኑና መታሰቢያቸዉ ከምድረ ገጽ ሲጠፋ አልተመለከታችሁምን? ከተለያዩ ታሪኮችና ዜና መዋዕሎች አላነበባችሁምን? በዘመናችሁ አልተፈጸመምን? እናንተ በእዉነት ማስተዋል የጎደላችሁ ናችሁ::

ቢያንስ በጦሩና በስለላዉ ተቋም ተመክቶ የነበረዉ የደረግ(ኢሠፓ) አወዳደቅ አስተዉላችሁ ቢሆን ኖሮ ወደ ወንበር እንደመጣችሁ ሕዝቡን በቅንነትና በእዉነት ለማገልገል ታጥቀችሁ ትነሱ ነበር እንጂ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ታጥቃችሁ አትነሱም ነበር:: እንዲሁም በራሳችሁ ትግልና ታላቅነት ደርግን ያስወገዳችሁ አድርጋችሁ ባለመቁጠር ራሳችሁን ዝቅ አድርገችሁ አምላካችሁን ታከብሩና ታገኑ ነበር እንጂ በጦራችሁ፣ በስለላ መዋቅራችሁ፣ በስልጣናችሁ፣ በኃይላችሁ ተመክታችሁና ታብያችሁ በሕዝብ ጫንቃ ላይ አትረማመዱም፣ በደልና ግፍ አትፈጽሙም ነበር:: ሕዝቡንም ለዐመጻ፣ ለክህደትና ለርኩሰት ሕይወት አታነሳሱም ነበር::

ከእንግዲህ ግን የዐመጻ፣ የክህደቱ፣ የርኩሰቱ ዘመናችሁ የማብቃቱን መርዶ ለእናንተ ልናረዳ ለሕዝቡ ደግሞ ልናበስር ነዉ ከያለንበት ከአምላካችን ታዘን የመጣነዉ:: በዚሁ አጋጣሚ ለሕዝቡ፣ ከእንግዲህ እግዚአብሔር በአራቱም ማዕዘን ከፍ ከፍ የሚልበትና የሚነግሥበት ዘመን መድረሱንና ፈቃዱ በአራቱም ማዕዘን የሚፈጸምበት ወቅት የደረሰ መሆኑን ለማሳወቅ እንፈልጋለን::

እናንተ «ስልጣናችንን ለትዉልድ እናስተላልፋለን፤ መታሰቢያችንን ለዘለዓለም እናጸናለን::» በማለት ሌት ተቀን በክፋት፣ በተንኮል፣ በዐመጻ፣ በክህደት የምትመላለሱ ሰዎች፤ እንኳን ለትዉልዳችሁ ስልጣናችሁን ልታስተላልፉ ቀርቶ በእናንተዉ ዘመን ተዋርዳችሁ ከወንበረችሁ ትቀረጣላችሁ:: መታሰቢያችሁም ለዘለዓለም ከምድር ይደመሰሳል::

እኛ እስከዛሬ ለአገራቱና ለዓለም ሕዝብ ጭምር ስንጸልይ ስናነባ ነበር፡፡ እግዚአብሔርም ልመናችንንና እንባችንን ተመልክቶ ስለተመረጡ ቅዱሳኖቹና ከሁሉ በላይ ስለ እመ አምላክ ድንግል ማርያም ሲል በንስሐ አልመለስ ብለዉ ኅሊናቸዉን ያደነደኑትን ዐመጸኞችንና ከሃድያንን ፣ ግፈኞችን ከምድሪቱ ሊያጸዳ በመወሰኑና እዉነተኛ ቀኖች የዋህን አገልጋዮችን ወደ ወንበር ሊያመጣ የመጨረሻዉን ዉሳኔ ስለወሰነ ምስጋናችንን በዚሁ እያቀረብን የኢትዮጵያን ትንሳኤ በመጠባበቅ ላይ ነን፡፡ እንግዲህ የተማመናችሁበት የጨለማዉ ገዥ «ጌታችን ገዥያችን መሪያችን» የምትሉት ዲያብሎስ ከጠረጋዉ እንደሚያድናችሁ በቅርቡ የምናየዉ ሲሆን፤ እኛ ግን እንደ ወገንነታችን የምንመክራችሁና የምንለምናችሁ በንስሐ እጃችሁን ለእግዚአብሔር እንድትሰጡና ከመጠረጋችሁ በፊት ወንበሩንም እግዚአብሔርና እመቤታችን ለመረጧቸዉና ለቀቧቸዉ ትለቁ ዘንድ ነዉ » በማለት ንግግራቸዉን አቅርበዋል፡፡

ሕዝቡም በንግግራቸዉ አዝኖና ተክሶ ስለነበረ ወዲያዉ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ባለስልጣኖቻቸዉ እንዲሁም የክልል መንግስታት ተወካዮች በአንድ ላይ በመሆን « እናንተ ብሔር ብሔረሰቦች! እኛ ስንት መስዋዕትነት ከፍለን ለዚህ ራሳችሁን በራሳችሁ የምታስተዳድሩበትን ስርዐት ዘርግተንላችሁ ለወደፊትም በሕገ መንግስታችን አንቀጽ 39 መሰረት እንድትገነጠሉ አመቻችተንላችሁ እያለ እንዴት ልባችሁ ወደነዚህ ወፈፌና እብዶች ንግግር ያዘነብላል? የጤነኛ ንግግር አድረጋችሁ ከቆጠራችሁ እኛ ሳናዉቅ እስከአሁን ድረስ «እብዶችን ነበር ለካስ እናስተዳድርና እንመራ የነበረዉ» ለማለት እንገደዳለን፡፡ እነዚህ የምትመለከቷቸዉና የሰማችዋቸዉ ሰዎች በየዋሻዉ፣ በየጫካዉ፣ በየገዳማቱ፣ በየገጠሩና በየከተማዉ ሲንከራተቱ የተለከፉ ልክፍተኞች ናቸዉ እንጂ ጤነኛ ሰዎች አይደሉም፡፡ እኛ አሁን ዐይናችሁ እያየ በሕጋችን መሰረት በአሸባሪነትና ሁከት ፈጣሪነት የእድሜ ልክ እስራትና የሞት ፍርድ ልናስፈርድባቸዉ እንችላለን ፡፡ እናንተ ግን የራሳችሁን ነጻ መንግስት እስከምትመሰርቱ ድረስ የብሔር ብሔረሰብ መብታችሁን በመጠበቅና በማስጠበቅ እነዚህ ቋንቋችሁን፣ ባህላችሁን፣ እምነታችሁን ለማጥፋት በመጡት ሰዎች ላይ ለፍርድ ቤቱ ምስክርነት በመስጠጥ በአጭር ጊዜ ዉስጥ አስፈላጊዉ እርምጃ እንዲወሰድ ሰላማዊ ሰልፍ

ልትወጡና እርምጃ ልታስወስዱባቸዉ ይገባል እንጂ አንዳች ጆሮዋችሁን መስጠት የለባችሁም» በማለት እንድተናገሩ፤

ከተሰብሳቢዎቹ የክብር እንግዶች ከነበሩት አንዳንድ ጥምጣም የጠመጠሙና አናታቸዉ ላይ ቆብ መሰል የደፉ የምክር ቤት አባላትና የተለያዩ ሃይማኖት ተወካዮች በጋር በመነሳት « የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትርና ከፍተኛ ባለስልጣኖች፣ እንዲሁም የብሔር ብሔረሰቦች ተወካዮች፤ በመጀመሪያ ለዚህች ቀን ያደረሱንን ዉድ የቁርጥ ቀን ልጆች ሰማዕታት ታጋዮቻችንን ለአንድ ደቂቃ እናስባቸዉ፡» በማለት መግቢያ ንግግር ካደረጉ በኋላ፤ እነዚህ በእግዚአብሔር ስም የሚያጭበረብሩ፣ የራሳቸዉን የግል ፍላጎት በእግዚአብሔር ስም ሽፋን ለማራመድ የሚፈልጉ መሆናቸዉን ተረድተናል። በእርግጥ ቀደም ሲል እናንተ ጥሩ ብላችኋል። ወፌፌ፣ እብድ፣ ቀባጣሪ፣ ጸረ ልማት የሆኑ፤ የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነትንና ነጻነትን የማያከብሩ፤ በሃይማኖት ሽፋን ሁከትና ሽብር ፈጣሪ፣ ጸረ ሰላምና ጸረ አንድነት ኃይሎች መሆናቸዉን እኛም እንመሰክራለን።

ሁላችንም እዚህ የተገኘነዉ የራሳችን ሃይማኖት፣ እምነት፣ ባህል ያለን መሆኑ ይታወቃል። ፈጣሪም የእያንዳንዳችን አምልኮን ይቀበላል። እንደ ምርጫችን በመቅደስም፣ በመስጂድም፣ በአዳራሽም፣ በወንዛወንዙም፣ በየጓዳዉ ዉስጥም፣ ባጠቃላይ በምናምንበት እምነት ዉስጥ ሆነን የምናቀርበዉን ጸሎት እንደሚቀበለን እናምናለን። ይህንንም ነጻነት ደግሞ የኢህአዴግ መንግስታችን በተለየ ሁኔታ ሰቶናል። ይኸዉም በሕገ መንግስታችን ዉስጥ ማንም ሰዉ የፈለገዉን በፈለገዉ መልክ የማምለክና የማመን ነጻነት ተሰቶታል። ስለዚህ እንኳን «አምላክ አለ» ብለን አይደለም «እንጨቱ አምላክ ነዉ» ብለን የማመን ሙሉ ነጻነትና ዴሞክራሲ መብት ተሰቶናል፤ ተጎናጽፈናል። ብሔር ብሔረሰቦችም ቋንቋቸዉን የሚወክለዉን አምላክ የማመንና የማምለክ ሙሉ ነጻነትን ተጎናጽፈዋል። ታዲያ ይህ ታላቅ መንግስት የአማልክቶቻችንን ማለት የኦርቶዶክስ አምላክ ፣ የእስልምና አምላክ ፣ የካቶሊክ አምላክ ፣ የፕሮቴስታን አምላክ ፣ የይሁዲዉ አምላክ ፣ የቡድሃ አምላክ ፣ የሂንዱ አምላክ ፣ የብሔር ብሔረሰቡ አምላኮች፣ ባጠቃላይ የተለያዩ አምላኮቻችንን በነጻነት እንድናመልክ በመደረጉ

የአምላኮቻችን እዉነተኛ እንደራሴ እነደሆኑና የእነሱን ፈቃድ እየፈጸሙ ያሉ ምርጥ ባለሟሎች እንደሆኑ  እናምናለን።

የአምላኮቻችን ምርጥ ባለሟሎች መሆናቸዉን ከሚያረጋግጡል አንደኛዉና ዋንኛዉ ማስረጃ በምርጫ 2002 ሁሉም ብሔር ብሔረሰቦችና እንዲሁም የሁሉም ሃይማኖቶች ተከታዮች ኢህአዴግንና አጋር ድርጅቶቹን ሙሉ በሙሉ በመምረጡ ነዉ። ታዲያ ይህን የአምላኮቻችንን ምርጫ የሚቃወም ከዲያብሎስ ነዉ እንጂ እንዴት ከአምላኮቻችን ይሆናል? ስለዚህ እናንተ የተከበራችሁና የተመረጣችሁ የብሔር ብሔረሰቦች እንደራሴዎችና ባለስልጣናት በነዚህ ለፍላፊና ወፈፌ ሰዎች ንግግር አንዳች ቅር አይበላችሁ። እናንተም ብሔር ብሔረሰቦች ጎሊናችሁ አንዳች እንዳይከፋፈል፤ መንግስታችን መንግስታችሁ ይሁን። እኛም እንደ ሃይማኖት አባትነታችን የአምላኮቻችን ተወካዮች ነንና በአምላኮቻችን ስም እነዚህ እብዶችን ከአሁን ጀምሮ አዉግዘናቸዋል። በመንግስት በኩል የሚወሰድባቸዉ ማንኛዉንም እርምጃ ከአሁን ጀምሮ የምንደግፍ መሆኑን በዚሁ እናሳዉቃለን» በማለት ሕዝቡን አረጋግተዋል።

እነዚያ «ወፈፌ፣ እብድ» የተባሉት ሰዎችም፤  እናንተ «የአገሪቱ መሪዎች ነን፤ ባለስልጣናት ነን፤  የክልል መንግስታት ተወካዮች ነን፤ የምክር ቤት አባላት ነን፤ የተለያዩ ሃይማኖቶች ተወካዮች ነን፤ » በማለት የተናገራችሁትንና የመሰከራችሁትን ንግግርና ምስክርነት በሚገባ ሰምተናል። በተለይ «የሃይማኖት ተወካዮች ነን» ብላችሁ ለራሳችሁ የተለያዩ አምላኮች ፈጥራችሁ አንዱን ፈጣሪና አምላክ በነገድ፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በአምልኮ መከፋፈላችሁ የማን ተወካዮች መሆናችሁን በራሳችሁ ላይ መስክራችኋል። እኛ «የእምነት ወይንም የሃይማኖት ተወካዮች ነን» ስላላችሁ የዲያብሎስ ወኪሎች ናችሁ አንልም። ነገር ግን እንደሃይማኖታችሁ የማትኖሩ አስመሳይ አገልጋዮች መሆናችሁን እንመሰክራለን።

በእርግጥ በፊታችሁ ስንታይ ለዐይናችሁ አንሞላም፤ ጎስቋሎች ነን። « እብድ፣ ወፈፌ፣ ለፍላፊ ናቸዉ» ስላላችሁም ቅር አይለንም። ለዘመናት ስንባል በደንብ ተለማድነዋል። ልዩ መለያ መታወቂያችንም ሆኗል። በፊታችሁ የተናቅን ቢሆንም እግዚአብሔር ሳይገባን ሞገስን ሰቶን ነዉ በፊታችሁ የቀረብነዉ እንጂ እኛ ሁል ጊዜ «ኃጢአታችን እንደ ሰማይ ከዋክብትና

እንደ ምድር አሸዋ የበዛ ነዉና ይቅር በለን» እያል ነዉ አምላካችንን የምንጠይቀዉ እንጂ አንድም ቀን «ቅዱስ፣ ንጹህ፣ ብጹዕ ነን» ብለን አናዉቅም።

እዚህ ስብሰባ ቦታ ላይ የተገኘነዉም «የእናንተ ምስክርነት ለኢትዮጵያም ሆነ ለዓለም ለመነሳታቸዉም፣ ለዉድቀታቸዉም ምክንያት ስለሚሆን፤ የሚቀበሏችሁ ከሆነ በንስሐ እዉነትን ይቀበሉ፤ እንቢ ብለዉ ራሳቸውን ካደነደኑና ከታበዩ ደግሞ በዓለም ላይ የሚመጣዉ ቁጣ እነሱንም እንደሚጠርጋቸዉ ንገሯቸዉ።» ስለተባል ነዉ የመጣነዉ እንጂ አንዳች የስልጣን፣ የጥቅም፣ የክብር ፍላጎት ኖሮን አይደለም። ስለ እዉነት ከመመስከርና ስለ እዉነት ከመቆም ዉጭ አንዳች ለጊዜያዉ ስልጣንና ጥቅም ብለን ኅሊናችንን የማንሸጥ መሆኑን ልታዉቁ ይገባል። ሁሉንም ንቀነዉ ነዉ አሁን ለምታዩት በእናንተ ዘንድ የተጎሳቆለ ሕይወት የሚመስለዉን የሕይወት መስመር መርጠን እየተጓዝን ያለነዉ። አንደኛዉ አባት በነጭ ባህላዊ ልብስ የተገለጹትም ልብሱ በባለቤቶቹ ኢትዮጵያዉያን ዘንድ የተናቀና ተራ ተደርጎ ስለተቆጠረና የማንነታችን አንዱ መገለጫ ስለሆነ ነዉ።

ሌላዉ ማወቅ ያለባችሁ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ እንኳን «አሸባሪ፣ ሁከት ፈጣሪ» ተብለን መታሰርና መገደል አይደለም እዚህ አሁኑኑ ብትገሉን ሰማያዊ አክሊል የምናገኝበት፤ ከዚህ ከጉስቁልና ኑሮና ሕይወት እንዲሁም ካደፈና ከጎሰቆለ ባሕርይ የምንገላገልበት፤ እንደ ቅዱሳን መላእክት አኗኗር የምንኖርበትን ሕያዉ ሕይወት የምናገኝበት ነዉ እንጂ አንዳች መልካም ነገር በዚህች ቆስቋላ ዓለም ዉስጥ የሚቀርብንና የምንጓጓለት አንዳች ነገር የለም። እኛን ለመጉዳት ቢፈቀድላችሁ እንኳ ልትጎዱን የምትችሉት ይህን በሥጋዊ ዐይናችሁ የምታዩትን የተገለጽንበትን ቅርፊት ሥጋን ለአፈርና ለምስጥ አስረክበነዉ የምንሄደዉን ነዉ እንጂ እዉነተኛ ገንዘባችን የሆነችዉን ነፍሳችንን ግን እንኳን መግደል ቀርቶ መጉዳት አትችሉም።

እዚህ ላይ ልትረዱት የሚገባችሁ እግዚአብሔር ሳይፈቅድላችሁ እንኳን በሥጋችን ላይ ጉዳት ማምጣት ቀርቶ አንዲቱን ጸጉራችንን እንኳ ምንም የማድረግ ስልጣን በራሳችሁ የሌላችሁ ተራና አቅመቢስ ልምሾ መሆናችሁን ልታዉቁ ይገባል። እግዚአብሔር ከፈለገ በዐይን ቅጽበት ጊዜ ዉስጥ ሊያተናችሁና ሊያበናችሁ የሚችል፤ ቢይዛችሁ የምትጨፈለቁ፣

ቢለቃችሁ ደግሞ ብትንትናችሁ የሚወጣ፣ የፈለገዉን ሊያደርገባችሁ የሚችል፤ አንዳች የሚሳነዉ ነገር እንደሌለ ልትረዱ ይገባል፡፡

ነገር ግን እርሱ እንደ ፍጡሮቹ እንደኛ ሰዎች አይቸኩልም፡፡ ለሁሉ የሚሰራበት ወቅትና ጊዜ ስላለዉ ነዉ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ስራችሁን እየተመለከተና ንግግራችሁን እያዳመጠ ለዓመታት ዝም ያላችሁ፡፡ አሁን ግን የዐመጻና የግፍ ጽዋችሁ ሞልቶ እየፈሰሰ ይገኛል፡፡ በዚህም ምክንያት አሁን ንስሐ ገብታችሁ ለአምለካችሁ እጅ ካልሰጣችሁ በስተቀር የዘራችሁትን የዐመጻና የክህደት ጽዋችሁን መራራ ቢሆንም ከነተባባሪዎቻችሁ ጠጥታችሁ ማለፋችሁ አይቀርም፡፡ የሚያሳዝነዉ ደግሞ ነፍስ ከሥጋችሁ ከተለየች በኋላ ዳግሞ የንስሐ እድል የላትም፡፡ እኛም «እባካችሁ እጃችሁን ለአምላክ ስጡ?» የማለት እድል አናገኝም፡፡ ነጻነታችሁ በአንድ ቦታ ተወስኖ እንደ ዐመጻ ደረጃችሁ ፍዳችሁን ትቀበላላችሁ፡፡ ለዚህም ነዉ ያ እድል እንዳያጋጥማችሁ ንስሐ ግቡ! እጃችሁን ስጡ እያልን ለዓመታት የምንከራተተዉ፡፡ ምክንያቱም የአዳም ዘር ወገኖቻችን ናችሁና፡፡

ምናልባት በነፍሶቻችሁ የሚጫወቱትና በአምላክ ስም የሚነግዱት አስመሳይ አገልጋዮች « ይህ የሚሆነዉ በዓለም ፍጻሜ በእለተ ምጽአት ነዉ» በማለት ኅሊናችሁን ሊያደነድኑ ይችሉ ይሆናል፡፡ ነገር ግን እንድታዉቁ የምንፈልገዉ እኛ እንደ ፍጡርነታችን ቀኒቷን በእርግጠኝነት ባናዉቃትም እግዚአብሔር በነገረን መሰረት አሁን በቅርቡ በእናንተና በኛ ትዉልድ ዘመን የተናገርናችሁ ሁሉ ይፈጸማል፡፡ የኢትዮጵያም ትንሳኤ ለዓለም ይገለጻል፡፡ የእናንተ ዐመጻኞች መታሰቢያ ደግሞ ለዘለዓለም ይጠፋል፡፡ እግዚአብሔር ሊያደርገዉ የፈለገዉን በፈለገዉ ጊዜ ያከናዉናል፡፡ የዓመት፣ የወራት ዝግጅት አያስፈልገዉም፡፡ ዛሬ ከወንበሩ ሊቆርጣችሁ ከፈለገ ዛሬዉኑኑ ባለሰባችሁትና ባልጠበቃችሁት መንገድ ከወንበራችሁ ሊቆርጣችሁ እንደሚችል ልታዉቁ ይባችኋል፡፡» በማለት አንዳች ተስፋመቁረጥና ፍርሐት ሳይታይባቸዉ እስከ ሰማዕትነት ድረስ ዝግጁ መሆናቸዉን አሳዉቀዋቸዋል፡፡

እኔም የጨለማዉ ገዥ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወሰድ ለእንደራሴዩ መሪ በኅሊናዉ እንዳሳሰብኩት፤ ወዲያዉ ያልተጠበቁ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ሻርፕ ያደረጉና ሙሉ በሙሉ ልብስ አድርገዉት የለበሱ እንዲሁም በትረ መስቀላቸዉ ላይ የሚያዉለበልቡ፤

አንዳንዶቹ ደግሞ የአንበሳ ምልክት በመሀሉ ላይ ያለዉን ሰንደቅ ዓላማ በመያዝ ቀደም ካላቱ « እብዶች» ከተባሉት ሰዎች ጋር ተቀላቀሉ::

ወዲያዉ ዐይናቸዉ ደም የለበሰዉ የብአዴን ከፍተኛ አመራሮች በጋራ በመጮኽ « ይኸዉ ቀደም ሲል እንደተናገርነዉ የነፍጠኞችን ስርዐት ለመመለስ የመጡ ትምክህተኞችና አሸባሪዎች መሆናቸዉ በዚህ ይታወቃል:: የያዙት ሆነ የለበሱት ሰንደቅ ዓላማ የአዲሲቷን ኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ የማይወክል፣ ኮኮብ የሌለበት፣ ጥንትዊቷን ኢትዮጵያ የሚገልጽ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የኛ ኅሊና የሚመራበት መንፈስ የሚወደዉና የሚቀበለዉን ኮኮብ ዓርማችንን አስወግደዉ የኛ ኅሊና  መንፈስ የማይቀበለዉና የሚጠላዉን የአንበሳ ዓርማ ያለበትን ሰንደቅ ዓለማ ነዉ ያደረጉት::

ስለዚህ እነዚህ አዲሲቷን ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦችን አገር ስለማይወክሉና ጥንታዊዋን ኢትዮጵያ ናፋቂዎች ስለሆኑ ከፈለጉ የጥንቶቹ ሰዎች መተዉ ይስሟቸዉ እንጂ እኛ ቦታ ሰተናቸዉ ልናዳምጣቸዉ አይገባም:: አሁን «ብሔራችሁ ምንድነዉ? እኛ ብሔራችን አማራ ነዉ» ብለን ብንጠይቃቸዉ፤ «ኢትዮጵያዊ ነን» የሚሉ ትምክተኞች የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነትና ነጻነትን የማይፈልጉ የቀድሞ ስርዐት ርዝራዦች ናቸዉ:: በመሆኑም ቀጥተኛ እርምጃ ቢወሰድባቸዉ እያልን እንጠይቃለን» በማለት ንዴታቸዉንና ቁጣቸዉን ገልጸዋል::

አዲስ የመጡትም መልእክተኞችም « በእርግጥ እናንተ እንደምትፈልጉት የማንንም ጎጥ ሆነ ቋንቋ ወክለን አይደለም በፊታችሁ የቆምነዉ:: በኢትዮጵያዊነታችንም አናፍርም እስከ መጨረሻዉ እቅታ ድረስ እንመሰክራለን:: እንኳን እናንተ የስም ኢትዮጵያዉያን ፣ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የተሰለፋችሁ የዐመጻ ልጆች አይደለም፣ «በእግዚአብሔር አምናለዉ የሚልና የኖኅ ልጆች የካም፣ የሴም፣ የያፌት ዘሮች ነን፤» የሚሉትን የዓለም ሕዝብ ሁሉ የምንወክል ኢትዮጵያዉያን መሆናችንን ልታዉቁ ይገባል::

እናንተ አሁን በእብሪትና በድንፋታ የተናጋራችሁ ሰዎች! ለስልጣን፣ ለጥቅም፣ ለሆዳችሁ ስትሉ ኅሊናችሁን የሸጣችሁ፤ ከኢትዮጵያዊነታችሁ ይልቅ የዘረኝነትና የጎጠኝነት ሕይወት የነገሠባችሁ፤ እንኳን «የዓለም ሕዝብ የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጆቹ ናቸዉ፣

የአዳም ዘር ወንድምና እህቶቻችን ናቸዉ» ብላችሁ ልታስቡ ቀርቶ፤ «ኢትዮጵያዉያን ሁሉ ወንድምና እህቶቻችን ናቸዉ» ብላችሁ የማታምኑ፤ አስተሳሰባችሁ ምድራዊ፤ ሆዳችሁና ክብራችሁ አምላካችሁ የሆነ ነዉ::

እኛ ደግሞ ለሆዳችን ያደርን ሳይሆን ተስፋችንን ሰማያዊ አድርገን ስለ እዉነት ብቻ ልንመሰክርና ልናገለግል የመጣን የእግዚአብሔር ባሪያዎች ነን እንጂ በጨለማ ሕይወት በጥላቻ፣ በበቀል በተመረዘ ኅሊና የምንመላለስና እዉነተኛ ማንነታችንን የምንክድ አይደለም:: እናንተ እንኳን « አማራ ነን» ማለት ቀርቶ «አማራዉያን ነን:: ትግራዉያን ነን:: ኦሮሚያዉያን ነን:: ኤርትራዉያን ነን::.. ወዘተ» በማለት ማንነታችሁን ልትክዱ ትችላላችሁ:: ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሕዝብ እስከ አሁን ድረስ እርስ በእርስ እያጣላችሁና እያገዳደላችሁ እንዲሁም እየከፋፈላችሁ ብዙ ደም እንዲፈስ፣ በደልና ግፍ እንዲፈጸም ስላደረጋችሁ፤ እዉነተኛ ንስሐ ገብታችሁ ለአምላካችሁ እጃችሁን ካልሰጣችሁ በስተቀር ከመሰሎቻችሁ ጋር ዋጋ ሳትከፍሉበት እንደማታልፉ ልታዉቁ ይገባችኋል::

ሌላዉ ደግሞ ስለ ሰንደቅ ዓላማ የመናገሩ ሞራሉና ብቃቱ የሌላችሁ፤ የዲያብሎን ዓርማ ያገነናችሁ፤ እናንተና መሰሎቻችሁ ታላቅ ክህደትን የፈጽማችሁ፤ ሕዝቡንም በማስፈጸም ላይ ያላችሁ መሆኑን ልታዉቁ ይገባል:: ይህን ሰንደቅ ዓላማ የተረከብነዉ ከፍጡር ሰዉ ሳይሆን እርሱ እግዚአብሔር ለሰዉ ልጆች በኖኅ አማካይነት የሰጠዉ ከቅዱሱ ኪዳን አንዱ ነዉ:: ማንም ሊያጠፋዉ የማይችል ሰማይና ምድር የሚመሰክሩት ነዉ:: አንበሳዉ ዓርማም ቢሆን ግለሰቦች ለራሳቸዉ አድርገዉ በተሳሳተ መንገድ ቢጠቀሙበትም እዉነቱ ግን አሸናፊዉ አንበሳ «ሞአ አንበሳ » የተባለዉ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጫ መለኮታዊ ዓርማ የምንጠበቅበት ነዉ እንጂ እንደ እናንተ ለዲያቢሎስ ተገዥነታችሁን በግልጽ ለዓለም እንዳስመሰከተራችሁት የዲያብሎ ዓርማ የሆነዉ ኮከብ አይደለም:: ይህን ክህደት እናንተ ብቻ ሳትሆኑ የፈጸማችሁት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የሚነግዱት የቤተ ክህነት ሰዎች ጭምር ናቸዉ:: ለዚህም እዉነተኛ ንስሐ ካልገቡና እጃቸዉን ለእግዚአብሔር ካልሰጡ ታላቅ ዋጋ በቅርቡ እንደሚከፍሉበት በዚሁ እንናገራለን::

ሌላዉ እንድታዉቁት የምንፈልገዉ ቤተ ሕዝቡን፣ ከቤተ ክህነቱና ከቤተ ምልክናዉ ለያይታችሁ ለዲያብሎስና ለእግዚአብሔር እንዲገዛ የዘረጋችሁት የዲያቢሎስ ስርዐት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እግዚአብሐር በቁጣዉ እንደሚደመስሰዉና፤ ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱና ቤተመንግስቱ በአንድ ላይ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራበት ሰማያዊ ስርዐት በቅርቡ እንደሚዘረጋ ልንገልጽላችሁ እንወዳለን:: ምናልባት ኃይላችሁንና ጦራችሁን አስባችሁ «ይህማ በምንም ሁኔታ ሊሆን አይችልም » ትሉ ይሆናል:: ምክንያቱም ከጸጋ እግዚአብሔር የራቃችሁ፤ በኅሊናችሁ የዲያብሎስ መንፈስ የነገሠባችሁ ስለሆነ በዚህች በጠባቧ አእምሮዋችሁ በማስላት ከንቱ የሆነ ንግግር አድርጋቹት እንደምታስቡ እንገምታለን::

ኢትዮጵያ እንኳን ዜጎቿን «ኢትዮጵያዉያን ነን» የሚሉትን ቀርቶ የዓለምን ሕዝብ ትመራለች ብንላችሁ «ኡኡ» ልትሉ ስለምትችሉ የንስሐ እድሜ ካገኛችሁ ተፈጽም እንደምታዩ እንነግራችኋለን:: በዐመጻችሁ ጸንታችሁ ከተጠረጋችሁ ደግሞ ቅኖችና የዋህን ትዉልዶች እንደሚያዩት በእግዚአብሔር ስም እናረጋግጥላችኋለን:: እንደእናንት የእግዚአብሔርን ኃይል የምንጠራጠር አይምሰላችሁ:: እግዚአብሔር፤ ንጉሡ ሰናክሬም የተመካባቸዉንና የተማመነባቸዉን 185000 (አንድመቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ» ሠራዊት በዐይን ቅጽበት ዉስጥ እንዳልነበሩ አድርጎ እንዳረገፋቸዉ ከመጽሐፍ ቅዱስ አላነበባችሁምን? ሲወራስ አላዳመጣችሁምን?

እግዚአብሔር አሁን በኛ ዘመን ኃጢአት እጅግ በነገሠበት ወቅት ደግሞ 185000 አይደለም 1850000000 (አንድ ቢሊዮን ስምንት መቶ ሃምሳ ሚሊዮን ) ሠራዊት በዐይን ቅጽበት ዉስጥ ማርገፍ የሚያቅተዉ ይመስላችኋልን? እናንተ ሆናችሁ በዓለም ዉስጥ ያለዉ ትዉልድ ማንም ይሁን ማን በዐመጻዉ ከጸናና እጁን ለእግዚአብሔር አልሰጥ ካለ በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ዐመጸኛ ትዉልድ ረግፎ እንደ ኖኅና ቤተሰቡ ቅንነት፣ የዋህነት፣ እዉነተኛነት የተላበሱትን ሰዎች ብቻ የማያስቀር ይመስላችኋልን?

ስለዚህ «ሠራዊቱ፣ ደኅንነቱ፣ ጠባቂዬ፣ ዘሬ፣ ጎጤ ኃያላን መንግስታት፣ የአዉሮፓ ህብረት፣ የአፍሪካ ህብረት .. ወዘተ» የሚባሉት እንኳን እናንተን ራሳቸዉንም ማዳን እንደማይችሉ በዚሁ ልንነገልጽላችሁ እንወዳለን:: ከእግዚአብሔር ቁጣ ሊድኑ የሚችሉት

በእዉነተኛ ንስሐ ለእግዚአብሔር እጃቸዉን ሲሰጡና በኢትዮጵያ በቅርቡ እግዚአብሔር ለሚዘረጋዉ መንግስቱ ለሥጋዊዉም ለመንፈሳዊዉም ስርዐት ተገዥ ሲሆኑ ብቻ ነዉ:: በተቀረ ግን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ጽዋቸዉን እያንዳንዱ መንግስት፣ ቡድን ፣ ድርጅት፣ ግለሰብ እየጠጣ ነጻነቱ ተገድቦ ወደሚኖርበትና እንደ ዐመጻዉ ደረጃ ፍዳዉን ወደሚቀበልበት ቦታ መሄድ ነዉ የሚቀረዉ:: ይህን ሁሉ የተናገርነዉ መቼስ እጃችሁን ለእግዚአብሔር ትሰጣላችሁ ብለን በማሰብ ሳይሆን የእናንተ ልበደንዳናነት ቢታወቅም ባለማወቅ በቅንነትና በየዋህነት አብሯዋችሁ የተሰለፉ ሰዎች ካሉ ከዛሬ ጀምሮ ከእናንተ ጋር አንድነትና ህብረት መፍጠራቸዉን አቁመዉ ከእዉነትና ከአምላካቸዉ ጋር ብቻ አንድነትና ህብረት እንዲፈጥሩ፣ እንዲሁም በእዉነተኛ ንስሐ እንዲመለሱ ለማሳሰብ ነዉ::

በመጨረሻ ለሁላችሁም የምንለዉ አለ:: ይኸዉም የኛም ፈጣሪና አምላክ የእናንተም ፈጣሪና አምላክ  አንድ ብቻ ነዉ እንጂ የተለያዩ አምላኮች የሉም:: እኛ ሰዎች ነን ለሥጋዊ ጥቅምና ክብር  አንዱን አምላክ ከፋፍለን ለግላችን መጠቀሚያ ያዋልነዉ:: « እግዚአብሔር የለም» በሚል ስርዐት የተጠመቃችሁ ብዙ ብትሆኑም፤ አብዛኛዉን ሕዝብ ወክለዉ የተገኙት ግን የሃይማኖቶች ተወካዮች እንዲሁም የባህል፣ የባእድና ጣዖት አምልኮ ተከታዮች ናቸዉ:: ስለዚህ እስከአሁን ድረስ ለሥጋዊ ጥቅምና ክብር ብለን ኅሊናችንን የሸጥንበትና ያስመሰልንበት ዘመን ያበቃ ስለሆነ በግልጽ እግዚአብሔርን የምንል እግዚአብሔርን መርጠን በእግዚአብሔር ስርዐት እንመላለስ፤ ዲያብሎስን የምንል ደግሞ በግልጽ ዲያብሎስን መርጠን በእርሱ ስርዐት ከሰይጣናት ጋር እንኑር እንጂ በተለያዩ ወርቃማ ቃላት ተሸፋፍነን «እዉነቱን ሐሰት፣ ሐሰቱን እዉነት፣ ብርሃኑን ጨለማ፣ ጨለማዉን ብርሃን፤» እያልን ያስመሰልበትና ያታለልንበት  የዐመጻ፣ ክህደትና የርኩሰት ዘመን ይብቃ::

አሁን « እምነት አለን፤ ሃይማኖት አለን ፤ እንዲሁም የኛ እምነትና ሃይማኖት አምላክ ነዉ እዉነተኛ አምላክ» የምትሉ ሁሉ፤ የነብዩ ኤልያስ አምላክ፣ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ፤ አሁንም እርሱ ነዉና እዉነተኛዉ አምላክ እያንዳንዳችን ለእርሱ የሚሆን ጸሎትና የምስጋና መስዋዕት እናቅርብ:: ለእዉነተኛዉ እምነት(ሃይማኖት) ምልክትና ተአምራትን እንዲሰጠን እንጠይቀዉ፤ በአስመሳዮች ላይም ቁጣዉን እንዲያሳይ፤ ከዚያም

ሁሉም ምልክት ወደታየበት እዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ እንዲመለስና አምላኩን በእዉነትና በመንፈስ እንዲያመልክ ፈቃዱንም እንዲፈጽም እንስማማ፡፡ ይኸም ራሳችሁን ከጥፋትና ከዉድቀት ትታደጉ በማሰብ ነዉ እንጂ እግዚአብሔር በእዉነትና በመንፈስ ብቻ መመለክን የሚፈቅድ እንጂ ሰዎች በተአምራትና በምልክት እንዲያምኑት የማይፈልግ ነዉ፡፡» በማለት ንግግራቸዉን አቆሙ፡፡

በዚህን ጊዜ መልስ ሊሰጣቸዉ የደፈረ አንድም ሰዉ አልተገኘም ነበር፡፡ ነገር ግን አንድ አስኬማ ያደረጉ ከተቀመጡበት በመነሳት «የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትርና ባለስልጣናት እንደማዕረጋችሁ፣ ከአገር ዉስጥም ከዉጭም አገር ተወክላችሁ በእንግድነት የተጋበዛችሁ፤ እንዲሁም ቅዱስ አባታችን፣ ብፁዐን ጳጳሰት፣ ካህናትና ሊቃዉንት፤ የተለያዩ ሃይማኖትና እምነት ተወካዮች፤ ባጠቃላይ የተለያዩ ህብረተሰብን ወክላችሁ ከአገር ዉስጥም ከዉጭዉ ዓለምም የተገኛችሁ ትዉልደ ኢትዮጵያ የሆናችሁ ያልሆናችሁ በሙሉ! እግዚአብሔር የንስሐ እድሜ ሰቶን ለዚህች ቀን ስላደረሰን በቅድሚ አመሰግነዋለሁ፡፡

አሁን በፊታችሁ የቆምኩት እንዳለፉት ጊዜ ልሸነግላችሁና ኅሊናዬን ለመሸጥ ሳይሆን እስከዛሬ ድረስ ለምድራዊ ስልጣን፣ ክብር፣ ጥቅም፣ ምቾትና ድሎት ኑሮ ከነፈሰዉ ጋር በመንፈሴ፤ እንደ ቦይ ዉኃ ወደ ወሰዱኝ በመሄዴ፣ ባጠቃላይ ስለ እዉነት ቆሜ ራሴን በመካድ ስለ እዉነት መመስከርና በእዉነት ማገልገል ተስኖኝ ለዓመታት ኅሊናዬን በመሸጥ ስለተመላለስኩ በዚህ ባሰናከልኩት ሕዝብ ፊት አምላኬን ይቅርታ እንዲያደርግልኝ ለመጠየቅ ነዉ፡፡

እንዲሁም አንዲት የሕይወት መንገድ የሆነችዉ «አንድ ሃይማኖት፣ አንድ ጥምቀት፣ አንድ ጌታ » ተብሎ በሐዋርያዉ ቅዱስ ጳዉሎስ የተመሰከረላት ቀጥተኛ(ኦርቶዶክስ) ተዋህዶ ሃይማኖት ብቻ መሆኗን ብናዉቅም፤ «ተመሳስለህና ኅሊናህን ሸጠህ ኑር፡፡» በሚለዉ ግልጽ ባልሆነዉ የሃይማኖትና የአገራት መሪዎች መመሪያ መሰረት እኔም ሆንኩ ሌሎች ወንድሞቼና አባቶቼ አገልጋዮች ስለ እዉነት መመስከርና በእዉነት መኖር ተስኖን የመሪዎቻችን ጭራ ሆነን ፈቃዳቸዉን ስንፈጽምና ስናስፈጽም ኖረናል፡፡ በተለያየ ነገሮችና ጥቅማጥቅሞች ተደልለን ዓለምን ወደን፤ ያ ከዉሻ ጋር እየተናጠቅን የኖርንበትን የቆሎ ተማሪነት

ሕይወታችንን፣ በየአብነት ትምህርት ቤቱና በየገዳማቱ ለመንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት የተጋንበትን ፣ ራሳችንን ዝቅ አድርገን የተመላለስንበትን ፣ እዉነተኛዉን ሕይወት ዘንግተን፣ ሳይገባን ከዚያ ሕይወት አንስቶን አሁን ላለንበት የክብር ሹመትና አገልግሎት አብቅቶን  እያለ እኛ ግን ይህን ያደረገልንን አምላክ ዘንግተን በአታላዩ በዲያብሎስ መንፈስ በሚመሩት ፖለቲከኞች ተጽህኖ ስር በመዉደቃችን ይኸዉ እግዚአብሔርን በእዉነት ከማገልገል ይልቅ በመንፈሳዊነት ሽፋን የእነሱን ፈቃድና የራሳችንን የሥጋ ፈቃድ ስንፈጽምና ስናስፈጽም እንገኛ ለን፡፡

ስለ እዉነት ቆመን ቢሆን ኖሮ ከራሳችን ምእመን አልፈን በተለያዩ የክህደትና የመናፍቅነት እምነት ዉስጥ የሚመላለሱትና በተለያዩ ባዕድና ጣዖት አምልኮ የሚኖሩትን በኢትዮጵያና በዓለም ዉስጥ የሚገኙ የአዳም ዘር ወገኖቻችንን ለእዉነተኛ ጥምቀትና መለኮት ለተዋሀደዉ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም እናበቃቸዉ ነበር፡፡ እኛ ግን እኳን በተለያየ እምነት ዉስጥ ያሉትም ወገኖቻችንን አይደለም በአርባና በሰማኒያ ቀን ከእግዚአብሔር በመንፈስ የተወለዱትን ወገኖቻችንን እንኳ በሚገባ ልናስተምርና ልንጠብቅ አልቻልንም፡፡

ይልቁኑ እዉነተኛ አገልጋዮችን እንወነጅላለን፣ እናሳድዳለን፣ እናሳስራለን፣ እናስገድላለን ፣ እናሰድባለን፣ እናስደበድባለን፡፡ በዘር፣ በጎጥ፣ በዘመድ አዝማድ ተተብትበንና ተቧድነን እርስ በእርስ እንጣላለን፤ እንጠላለፋለን፤ ጉድጓድ እንማማሳለን፣ ወጥመድ እንጠማመዳለን፡፡ ምእመኑም በእኛ ሕይወትና ምግባር አልባ ትምህርት ተሰናክሎ ወደ ዓለም ሕይወትና አንዳንዶች ደግሞ ወደ ክህደትና ምንፍቅና እምነት ገብተዋል፡፡ ለነዚህ ሁሉ ነፍሳት የመጀመሪያ ተጠያቂዎች እኛ ሳይገባን በወንበር ላይ የተቀመጥን የሃይማኖት መሪዎችና መስቀሉን የያዝን ካህናት ነን፡፡

በእዉነትና በመንፈስ ብናመልክና አገልግሎታችንን ብንፈጽም ኖሮ እንኳን ለኢትዮጵያዉያን  አይደለም ለመላዉ ዓለም እንተርፍ ነበር፡፡ ይሁንና «ተመሳስሎ ኑሮ» በሚለዉ መርህ በኦርቶዶክስ፣ በእስልምና፣ በፕሮቴስታንት፣ በካቶሊክ፣ በባህላዊ እምነት፣ በባዕድና ጣዖት አምልኮ ያሉት ሁሉ፤    « ፀሐዩ ንጉሣችሁ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪ

ባጎናጸፋችሁ ዴሞክራሲ መብትና ነጻነት አምላኮቻችሁን የማምለክ እድል ስለገጠማችሁ እድለኞች ናችሁ:: መሪዎቻችንም ለአገሪቱ ታላቅ ስራ እየሰሩ ስለሆነ እስከመጨረሻዉ ድረስ ከጎናቸዉ ተሰልፈን የተግባራቸዉ ፈጻሚና አስፈጻሚ እንሆናለን» እያልን በየቦታዉ፣ በየስብሰባዉ፣ በቴሌቭዥን፣ በሬዲዮን ምስክርነትን የምንሰጥ፤ «የተለያዩ አምላኮች ትክክል ናቸዉ ለእግዚአብሔር መንግስት ያበቃሉ::» በሚል አስተሳሰብ እየተሸነጋገልንና እያስመሰልን እስከ አሁን ድረስ ቆይተናል::

እግዚአብሔር ግን በተለያየ ሁኔታ ስራዉን የሚያከናዉንበት ጊዜ መድረሱ ስለተሰማኝና ወደ እዉነተኛዉ ልቤ ስለተመለስኩ ከእንግዲህ ማንኛዉም እርምጃ ቢወሰድብኝም ኅሊናዬ ነጻ አድርጌ አምለኬንና እስከአሁን ድረስ ያሰናከልኩትን ምእመን በግልጽ ይቅርታ እጠይቃለሁ:: ከእንግዲህም እግዚአብሔር እዉነተኛ እረኞችን ለአገሪቱና ለሕዝቡ ይሰጥ ዘንድ ነዉ ጸሎቴና ምኞቴ:: አሁን የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ ምልክቱ ባይገለጽ እንኳ ከዛሬ ጀምሮ አስኬማዬን አስቀምጬ በቆቤ ብቻ ወደ አንዱ ገዳም ወይንም ዋሻ እገባለሁ እንጂ ከዐመጻ፣ ከክህደትና ከርኩሰት ስራ አስፈጻሚዎች ጋር አንድነትና ህብረት አልፈጽምም:: እግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ አሁን እርምጃ ቢወሰድብኝ እንኳ አምላኬን ስላለፈዉ በደሌና ማስመሰል ሕይወቴ «ይቅር በለኝ፤ በቸርነትህ መልከ ጼዴቅ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ሙሴ ፣ ነብያት ፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን ባረፉበት ገነት መንግስት ሰማያት አሳርፈኝ::» ብዬ ነፍሴን አስረክቤያለሁ::» በማለት ለመሰል አገልጋዮቻቸዉ ጥሪ ለማቅረብ ምልክት ሲያሳዩ፤

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የጦር ሠራዊት፣ የፌደራል ፖሊስ፣ የደኅንነት ኃይል፣ ልዩ የጥበቃ ኮማንዶዎች፣ ባጠቃላይ ጦር መሳሪያ የታጠቁ ወታደሮችና ፖሊሶች በተጠንቀቅ እንዲቆሙ ወዲያዉ መመሪያ የሰጡ ሲሆን፤ በዐይን ቅጽበት ዉስጥ የእግዚአብሔር መላእክት፤ በጦር ኃይላቸዉ፣ በስልጣናቸዉ፣ በጉልበታቸዉ፣ በሀብታቸዉ ተመክተዉ የእግዚአብሔር መልእክተኞች ላይ ጥቃት ሊፈጽሙ የተነሱትን ሁሉ ከነመሳሪያዎቻቸዉ እንዳልነበሩ አድርገዉ ሊያጠፋቸዉና ሊደመስሷቸዉ ሲመጡ፤ የእግዚአብሔር መልእክተኞች

ወዲያ የእግዚአብሔር ቁጣ ከመሪዎች ሆነ ከባለስልጣኖች እንዲሁም ከተሰበሰቡት ሰዎች እንዲርቅ በመለመናቸዉ፣ በነብዩ በዮናስ ዘመን በነነዌ ሰዎች ላይ እንደታየዉ ምልክት የመጣዉ የእሳት ነበልባል በዐመጸኛ ሰዉ አናት ላይ ወርዶ ከመሃል አናታቸዉ ያለችዉን ጸጉር በልታ ተመለሰች::

በወቅቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ የታየ ምልክት ስላልነበረ አናታቸዉ ጸጉራቸዉ የተበላች ባለስልጣናትና አስመሳይ አገልጋዮች፤ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ የተለየ ምልክት ባለመታየቱ «ይህ የእነዚህ አስማተኞች ተግባር ነዉ እንጂ የእግዚአብሔር ምልክት አይደለም:: የጠቅላይ ሚኒስትራችን ጌታ ታላቅና ዋና ስለሆነ የታየዉን ምልክት አናምንም፤ አንቀበልም » በማለት ልክ ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለበት ወቅት ፀሐይ ስትጨልም፣ አለታት ሲሠነጣጠቁ፣ እንዲሁም በሦስተኛዉ ቀን ከሙታን በኃይሉ ሲነሳ  ወደ ልባቸዉ እንዳልተመለሱና ከቁም ነገር እንዳደልቆጠሩት ይልቁኑ የተደረገዉን ምልክት ሁሉ «ሐሰት ነዉ» ለማስባል የፈጠራ ወሬዎችን እንዳዘጋጁት  ጸሐፍት፣  ፈሪሳዉያን ፣ አይሁድ ካህናትና አለቆች፣ እንዲሁም ሥጋዉያን መሪዎችና ባለስልጣናት፤ የአሁኖቹም እጃቸዉን ለእግዚአብሔርና ለእንደራሴዎቹ ከመስጠት ይልቅ እንደ ቀደሙት መሰሎቻቸዉ ኅሊናቸዉን አደንድነዉ በዐመጻና በክህደታቸዉ ጸኑ::

በዚያዉ ወቅት አንድ አዛዉንት በኀዘንና በርኅራኄ ገጽ ባዶ እግራቸዉን ሆነዉ በአረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ላይ የአንበሳ ምልክትና አንድ ሴት እጇን ዘርግታ የሚታይ ሰንደቅ ዓላማ ለብሰዉ በድንገት በመድረኩ ላይ መጡ:: እሳቸዉም « ከአስር ዓመት በፊት የእግዚአብሔርን መልእክት በተለያየ መልኩ ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝብ አቅርቤያለሁ:: መልእክቱንና ማሳሰቢያዉን የሰማ፣ ሰምቶም የተቀበለና የፈጸመ ይገኝ እንደሆነ የሚያዉቀዉ እግዚአብሔር ብቻ ነዉ:: እኔ በዚህ ነገር ልመሰክር አልችልም:: ደግሞም በዚች በእግዚአብሔር የእዉነት ተልዕኮ ከእኔ ጋር በዓላማ የተባበረና በተግባር የተሰለፈ ይኖር እንደሆነ፣ ከኖረም እስከመጨረሻ የሚጸናዉ ማን እንደሆነ እስካሁን ከእግዚአብሔር በቀር ሌላ የሚያዉቅ የለም::

ባሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዉያንን በሚመለከት እጅግ ብዙ የሆኑ ባዕዳን የሆኑ አስተሳሰቦች፣ አስተያየቶችና ትችቶች በቃልና በጽሑፍ በግልና በጉባዔ በመጽሔት ሆነ በድምጽ ማሠራጫ በየቦታዉና በየመድረኩ ሲገለጡ፣ ሲቀርቡና ሲሠነዘሩ ይሰማል፤ ይታያልም። የኢትዮጵያ መሠረቷ፣ ግድግዳዋና ጣራዋ፣ ጉልላቷም ስለሆነዉ ስለ ቅዱስ ኪዳኗና በእርሱ ስለተገኘዉ የኢትዮጵያዊነት ግን የሚናገርና የሚጽፍ ቀርቶ የሚያስብ እንኳ ያለ አይመስልም። ይህም የራስ የሆነዉን ከመናቅና ከማቃለል የተነሳ መሆኑ ለኢትዮጵያዊዉ ይታወቀዋል።

ነገሩ እንግዳ አይደለም። የዛሬ ሁለት ሺህ ዓመት ግድም በዘመኑ ለነበሩት ሰዎች «የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለችና ... መንገዱን አዘጋጁ፤ ጥርጊያዉንም አቅኑ!» ደግሞ «እናንተ የእፉኝትና የእባብ ልጆች! ከሚመጣዉ ቁጣ፣ ጥፋትና መቅሰፍት እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ? እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ መልካም ፍሬ አደርጉ!... መልካም ፍሬ የማያፈራዉን ሁሉ ሊቆረጥ መጥረቢያዉ በዛፎች ላይ ተሠንዝሯልና... ንስሐ ግቡ!» እያለ የእግዚአብሔርን ቃል የሰበከ ያዋጅ ነጋሪ ነበር።

ነገር ግን ይህን ሰባኪ የሚሰማዉ ማንም እንደማይኖር አስቀድሞ በመንፈስ የተገለጠለት ነብይ፣ ያዋጅ ነጋሪዉን ቃል ፡«በምድረ በዳ የሚጮህ ሰዉ ድምጽ» በሚል ቅጽል አብራርቶት ነበር።

ዛሬም ሰሚ ቢኖርም ባይኖርም የእግዚአብሔር መንግስት ለሆነችዉ ኢትዮጵያ የቃል ኪዳን አገልግሎቴን የማበረክተዉ እኔ ትሑት ኢትዮጵያዊ እግዚአብሔር እስከፈቀደዉ ድረስ ተልዕኮዬን ከመቀጠል ወደ ኋላ አልልም። ለዚህም ይህ የቃል ኪዳን ምስክርነት የዛሬዉ ማረጋገጫ ይሆናል።

ኢትዮጵያዊዉ ባሁኑ ትዉልድ ሁኔታ እንዳይገረምና ተስፋ እንዳይቆርጥ እንዲህ የሚለዉ የእግዚአብሔር ቃል እዉነቱን እየገለጠ በበለጠ ያጽናናዋል። «እናንተ ግብዞች ኢሳይያስ ስለናንተ «ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነዉ፤ የሰዉም ሥርዐት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል።» ብሎ በእዉነት ትንቢት

ተናገረ።» ሲል መሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ ስለነበረዉ ትዉልድ የጠቀሰዉ የነቢዩ ቃል ነዉ።

ደግሞም፡«ከሃዲና ዓመጸኛ፣ አመንዝራ የሆነ ትዉልድ ምልክትን ይሻል፤ ከነቢዩ ከዮናስ ምልክት በቀር ሌላ ምልክት አይሰጠዉም፤... የነነዌ ሰዎች በፍርድ ቀን ተነስተዉ ከዚህ ትዉልድ ጋር ይፋረዳሉ፤ ያሳፍሩታልም፤ በዮናስ ስብከት ንስሐ ገብተዋልና፤ እነሆ ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ። ንግስት አዜብ በፍርድ ቀን ተነስታ ከዚህ ትዉልድ ጋር ትፋረዳለች፤ ታሳፍረዋለችም፤ የሰሎሞንን ጥበብ ትሰማ ዘንድ ከምድር ዳርቻ መጥታለችና፤ እነሆ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ።» ብሎ ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለራሱና በዘመኑ ስለነበረዉ ትዉልድ የተናገራቸዉ ቃላት ለዚህ ትዉልድ ብርቱ ማስጠንቀቂያዎች ናቸዉ።

ከላይ የተገለጸዉና ከዚህ ቀደም በቃልም በጽሑፍም ደጋግሜ ያሳሰብሁትን እንደገና እያስታወስኩ አሁንም በዚህ የቃል ኪዳን ምስክርነቱ መዝጊያ ላይ ለሚመለከታቸዉ ሁሉ ምክሬን አበረክታለሁ፤ የማስጠንቀቂያ ቃሌንም እሰጣለሁ።

**ለእዉነተኞቹ ኢትዮጵያዉያን!**

በመጀመሪያ በዚህ መልእክት ዉስጥ የተመለከተዉን የቅዱሱን ኪዳን ሃይማኖትና ምግባር ጠብቃችሁ የምትገኙ ኢትዮጵያዉያን ካላችሁ በዚህ አቋማችሁ በያላችሁበት ጸንታችሁ ቁሙ! ይህ ዛሬ በእናንተ ላይ የመጣዉ መከራ ከባድ በመሆኑ እግዚአብሔር መላእክትን ሊፈትን ተሠዉሯቸዉ ሣለ የነበረዉን ሁኔታ ይመስላል።

ይህን ዓይነቱ መከራ ለእነርሱና ለእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ወዳጆች፣ ይልቁንም ለራሱ ለባለቤቱ ለኢየሱስ ክርስቶስ እንኳ አልቀረም። ለእኛም ትምህርትና መቀጣጫ ይሆነን ዘንድ ከጥንት ሲያያዝ የመጣዉ ዜና ታሪካችን ይህንን ሁሉ ያስታዉሰናል።

ከቀደሙት የተላለፈልን የመላእክቱ የፈተና ታሪክ እንደሚያስረዳዉ ሳጥናኤል በሚል ስም የመላዉ ነገደ መላእክት የበላይ አለቃ የነበረዉና ከዉድቀቱ በኋላ ዲያብሎስ የተባለዉ መልአክ ራሱ ተሳስቶ መልአክትንም ሊያስታቸዉ «የፈጠርኳችሁ እኔ ነኝ» አላቸዉ።

ይህን የሐሰት ነገሩን ካልተቀበሉት መካከል አንዱ ሊቀ መልአክ ቅዱስ ገብርኤል፡ «አምላካችን እስኪገለጥ በያለንበት እንርጋ!» የሚል ያዋጅ ቃል አሰማ።

ያዋጁን ቃል የተቀበሉት፣ በፈጣሪያቸዉ ፊት የበለጠ ሞገስን አግኝተዉ በዘላለማዊዉ የእግዚአብሔር ጸጋ የከበሩ ቅዱሳን ሲሆኑ፣ ያዋጁን ቃል ተቃዉመዉ ሳጥናኤልን የተከተሉት ግን ከፈጣሪያቸዉ ፊት ተወግደዉ በዘላለም ፍዳ የሚሠቃዩ ርኩሳን ሆኑ::

ስለዚህ እናንተም የእግዚአብሔር የሆናችሁ የኢትዮጵያ መንግሥት ለጊዜዉ ዛሬ በመንፈስ ነገ ደግሞ በገሃድ በምትገለጽበት ጊዜ የዓመፀኞቹና የከሃዲያን ክፉ ዕድል ሳይሆን የደጋጎቹና የታማኞቹ መላእክት መልካም ዕድል ደርሷችሁ ደስ ይላችሁ ዘንድ በቃል ኪዳናችሁ ጸንታችሁና የሚገባችሁን እየፈጸማችሁ አምላካችሁ የሚያደርገዉን ተአምርና ኃይል በትእግሥት ጠብቁ::

ቀጥሎ በዉጭ አካላችሁ ብቻ ሳይሆን በዉስጥ ሰዉነታችሁ «ኢትዮጵያዊ ነኝ» የሚል እንደ ዉኃ የጠራና እንድ እሳት የሚያቃጥል ስሜት ያላችሁ ኢትዮጵያዉያን የምትገኙ ከሆነ ያ «ኢትዮጵያዊነታችሁ ሰዉ ሠራሽ ወይንም ጊዜ ያመጣዉ «ኢትዮጵያዊነት» ሳይሆን ከእግዚአብሔር በቃል ኪዳን የተገኘዉ «የእዉነተኛዉ ኢትዮጵያዊነት» ምልክት ነዉና ደስ ይበላችሁ!

ለእናንተ ይህን እላለሁ - ቃል ኪዳኑን ባፈረሱት ላይ እንዲሁም ባገር ዉስጥና በዉጭ ባሉ ግብረአበሮቻቸዉ ላይ ከዚህ የባሰዉ የሚያስጨንቀዉ የቅጣት ቀን ሳይመጣ እግዚአብሔር ከዚያ ቀን እንዲሰዉራችሁ፣ ይህንንም የፈተናዉን ዘመን አሳልፎ ምሕረቱና ሰላሙ በዓለሙ ሁሉ ሳይቀር የሚሰፍኑባት መንግሥቱ ከምትገለጥበት ጊዜ እንዲያደርሳችሁ ራሳችሁን በቶሎ በንስሐ አጽድታችሁና አስተካክላችሁ በእዉነተኛዉ ኢትዮጵያዊነት ታደሱ:: «ቅዱስ ሥጋዉን በልታችሁ፣ ክቡር ደሙንም ጠጥታችሁ» ለንጉሣችሁ ለኢየሱስ ክርስቶስና ለንግሥት እናቱ ክብር መገለጥ የተዘጋጃችሁ ሁኑ::

የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዉያን ጉዳይ የሚወሰነዉ ችግራቸዉም መፍትሔ የሚያገኘዉ በሰዉኛ ሳይሆን በእግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ ከእርሱ ጋር ባለችሁ ቃል ኪዳን ከመጽናት በስተቀር በሌላዉ አትድከሙ:: ከቃል ኪዳን አምላካችሁ ሊለያችሁ የተነሣዉን ተቃዋሚ ኃይል መስማትና መከተል ትታችሁ የዘላለማዊ መሪያችሁ የኢየሱስ ክርስቶስና የእናቱ አገራችሁ የድንግል ማርያም ቃል የሆነዉን የቅዱስን ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁን ብቻ በሃይማኖት

ጠብቁ፤ መጠበቃችሁንም በይፋ አስታዉቁ:: በይፋ የምታሳዉቁትም « ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» በሚለዉ የነብዩን ቃልና የኢየሱስ ክርስቶስ ዓርማ የሆነዉ «ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ» የሚለዉ ምልክት በሠፈረበት «ያረንጓዴ ቢጫና ቀይ »ሰንደቅ ዓላችሁ ዙሪያ ስትሰባሰቡ ነዉ::

በዚህ ጊዜ እዉነቱን በየሕሊናችሁ ታገኙታላችሁ:: ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት እንዳላችሁ ይሰማችኋል፤ በእርሱ እዉነት ደስ ይላችኋል፤ እርስ በእርሳችሁ ፍቅር ከሰዉም ጋር ሰላም ይሆንላችኋል፤ በሁሉ ዘንድ ስምምነት ታገኛላችሁ:: የምትታወቁት በዚህ ኢትዮጵያዊነታችሁ ስለሆነ፣ ባገራችሁና በዓለም ላይ የናቋችሁና ያጠቋችሁ የጠሏችሁና ያዋረዷችሁ የሕዝብ ወገኖች ሁሉ ተጸጽተዉ ይቀበሏችኋል፤ ያከብሯችኋል፤ ይወድዷችኋል፤ይፈሯችኋል:: ከእግዚአብሔርም የጠበቃችሁትም ሁሉ ይሆናል::

በመጨረሻም ከቤተክነቱና ከቤተ ምልክናዉ፣ ከቤተ ሕዝቡም ወገን በዚህ ትዉልድ ክህደትና ዓመፅ ዉስጥ ተካፋዮች ለሆናችሁት ሁሉ: ይህን እላለሁ:- ዛሬ በኢትዮጵያዉያን ላይ እየወረደ ያለዉ መከራ የመጣበት ምክንያት ምን እንደሆነ በየጊዘዉ ገልጫለሁ:: ይኸዉም በእግዚአብሔርና በኢትዮጵያ መካከል ጸንቶ በኖረዉ ከዚህ በላይ በተመለከተዉ በቅዱስ ኪዳን ላይ ይህ ትዉልድ ቀደም ብሎ የልብ ክህደቱን ከፈጸመ በኋላ በኃይል ዓመፅ በመነሣቱ መሆኑን የሚያስረዳ ነዉ::

ይኸዉ የትዉልዱ ሁኔታና አድራጎት በእግዚአብሔር ፊት ጽዋዉ የሞላ ታላቅ ኃጢአት ሆኖ ስለተገኘ ላገራችን መርገም ሆነ፤መርገሙም በግልጽ የሚታየዉን ቅጣት መቅሰፍት አመጣ:: እግዚአብሔር ግን ለመከራዉና ለፈተናዉ ብቻ አጋልጦ አልተወንም፤ ፈጽመን ከመጥፋት አድኖን ለንስሐ የሚያስፈልገዉን ጊዜ በቸርነቱ እያራዘመልን እንሆ ለሰላሳ ሰባት ዓመታት አቆይቶናል:: ለሰላሳ ስምንተኛዉ ግን ዋስትና የለንም::

ስለዚህ እየቀጠለ በሄደዉ የመከራ ዘመን ዉስጥ ከስሕተታችሁ በንስሐ ያልተመለሳችሁ ሁሉ: በዚህ ምክንያት በመጣዉ ኃጢአትና መርገም ተይዛችሁ እንዳትቀሩ የባሰዉ ጥፋት ከመድረሱ በፊት ንስሐ ገብታችሁ ሥጋዉና ደሙን በመቀበል ሳትዘገዩ ከፈጣሪያችሁ ጋር

ታረቁ:: ራሳችሁን በቅዱስ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችሁ አስተካክላችሁ በተቀደሰዉ ሰንደቅ ዓላማችሁ ዙሪያ ተሰባሰቡ::

ይህን ካላደረጋችሁ ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የከበራችሁበትን ኢትዮጵያዊነታችሁን ተገፍፋችሁ፣ ልትይዙት የተመኛችሁትንም ሳታገኙ: ሁሉንም አጥታችሁ በሥጋችሁም በነፍሳችሁም ፈጽማችሁ እንደምትጠፉ እወቁ::

እንዲሁም እናንተ የዓለም መንግስታትና ድርጅቶች! ኢትዮጵያን በሚመለከት: ለዓለም ሕዝቦችና ለኃያላኑ መንግስታት፣ ለዓለም ዓቀፍ ድርጅቶችም ስለተሰጠዉ ማስጠንቀቂያና ስለደረሰባቸዉ ጉዳት የቅርቡን ታሪክ እዚህ ላይ መጥቀስ አግባብ ይሆናል::

በአደባባይና በአዋጅ፣ በጽሑፍና በማንተም፣ ለኢትዮጵያ የገቡትን ቃል ኪዳን እርስ በርሳቸዉ በመመሳጠር ክድዉና ሽረዉ የቅዱስ ኪዳን ታማኝ የሆነዉን ኢትዮጵያዊዉን ዘር በመደምሰስና የቀረ ሕዝቧን በመለያየት ይህችን የእግዚአብሔር አገር ለማጥፋትና መንግስቷን ለማፈራረስ ሴራ አድርገዉ ተነሥተዉ የነበሩትን ኢጣልያንን እንግሊዝንና ፈረንሳይን እንዲሁም የዓለም መንግስታት ማኅበር ይባል የነበረዉን ተባባሪያቸዉን ድርጅትና አባል አገሮቹን እዉነተኛዉ ዳኛ እግዚአብሔር በ፪ኛዉ የዓለም ጦርነት የብረት በትር እንዴት አድርጎ እንደቀጣ አይዘነጋም::

ዛሬም ይህንኑ የክፋት ዓለማቸዉን በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዉያን ላይ ለመፈጸም በተንኮል ተነሣስተዉ በነበሩት ሶቬዬት ኅብረት ይባል በነበረዉ ከሃዲ መንግስት ዩጎዝላቪያንና ሱማልያን በመሳሰሉት ተባባሪዎቹ አገሮች እንዲሁም በመካከለኛዉ ምስራቅ በሚገኙ አንዳንድ የኢትዮጵያ ተጻራሪ መንግስታት ላይ እየደረሰ ያለዉ ቅጣት እነሆ ዓለም በሙሉ ይመለከተዋል::

**ኢትዮጵያ: የእግዚአብሔር መንግስት በመሆኗ** ከሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት በፊት በነበረዉ ዓለም ላይ እንደደረሰዉና በዚያን ጊዜ እንደሆነዉ ሁሉ ዛሬም ለኢትዮጵያዊዉ ብቻ ሳይሆን ለያንዳንዱ ባዕድ ግለሰብ፣ ለያንዳንዱ የሃይማኖት ተቋም፣ ለያንዳንዱ ሕዝብና መንግስት፣ ለኃያላኑም ሆነ ለንዑሳኑ፣ እንዲሁም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለተባለዉና

ለመሳሰሉት ዓለም አቀፍ ጭምር፡ **የእርሷ የኢትዮጵያ ጉዳይ ለታላቅ ፈተና የቀረበ የእግዚአብሔር የዳኝነቱ ሚዛን ነዉ፡፡**

የዚህ ፈተና ዉጤትና የዳኝነቱ ፍጻሜ ግን በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ላይ ለተፈጸመዉ የቃል ኪዳን መፍረስ የቅጣት ኩነኔ አድርጎ እንዳመጣዉ እንደ ሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት የፍርድ ወሳኔ እንዳይሆን ለሁሉም ማን በነገራቸዉ? እኔንማ እንዴት ይሰሙኛል?

የዚህ ዓለም ሰዎች የፍርድ ቃል ደርሶ እስኪፈጸምባቸዉ ድረስ ስለ እግዚአብሔር መንግስት የሚነገረዉ ቃል ተናጋሪዉን ጭምር የሚቃወሙና የሚጠሉ፣ የሚንቁና የሚያቃልሉ መሆናቸዉን ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ ለነበረዉ ትዉልድ የጠቀሰዉ እንዲህ የሚለዉ የነቢዩ ቃል የሚገኝበት የሐዋርያዉ መልእክት ያስረዳል፡-

« እነሆ የተመረጠንና የከበረን የማዕዘን ራስ ድንጋይ በጽዮን አኖራለሁ፤ በእርሱ የሚያምን አያፍርም» ብሎ ተጽፏልና፡፡ እንግዲህ ክብሩ ለእናንተ ልምታምኑ ነዉ፤ ለማያምኑ ግን «ግንበኞች ንቀዉ የጣሉት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ የዕንቅፋትም ድንጋይ፣ የማሰናከያም ዓለት ሆነ»፡፡ የማያምኑ ስለሆነ በቃሉ ይሰናከሉበታልና፤ ለዚህ ደግሞ የተመደቡ ናቸዉ፡፡»

ይህ ቃል ዛሬ በባዕዳኑም በኢትዮጵያዉያኑም ዘንድ ሲፈጸም ይታያል፡፡ ይልቁኑም ባሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ያለዉ «በእግዚአብሔር አምናለሁ» የሚለዉ ሳይቀር በአብዛኛዉ ሰዉ ወይም ሕዝብ ወይም መንግስት የዛሬዉ ኢትዮጵያዊዉ ትዉልድ ጭምር አምልኮቱ፣ ታዛዥነቱና ትዉክልቱ ወደ እግዚአብሔር መሆኑ ቀርቶ ወደ ምድራዊዉ ገንዘብና ሀብት፣ ወደ ሥጋዊዉ እዉቀትና ጥበብ፣ ወደ ዓለማዊዉ ኃይልና ሥልጣን ብቻ መሆኑን ማየት እጅግ ያሳዝናል፡፡

በዚህ አንጻር በእዉቀታቸዉ፣ በገንዘባቸዉና በኃይላቸዉ ተመክተዉ እግዚአብሔርንና የእርሱ የሆነዉን ሁሉ የሚንቁትንና የሚያቃልሉትን የዚህን ዓለም ሰዎች ሊያሳፍር በእነርሱ ዘንድ አላዋቂዎች፣ ደካሞችና ድሆች ተብለዉ የተናቁትንና የተጠሉትን ኢትዮጵያዉያንንና በሩቅ ባዕዳንን እያስነሳ በእርሱ መሣሪያነት እግዚአብሔር የሚሰራዉን ድንቅ ሥራ መመልከት ደግሞ ያጽናናል፡፡

ሌላዉ የሚያስገርመዉ ሁኔታ፡-

ባንድ በኩል በኢትዮጵያ ምክንያት ያ ታላቅ መለኮታዊ ፍርድ ያስከተለዉ ፪ኛዉ የዓለም ጦርነት በመላዉ የሰዉ ዘር ላይ ያደረሰዉን እልቂት በዓይናቸዉ ያዩት በዚያ ዘመን የነበሩት የዛሬዎቹ የኢትዮጵያ አዛዉንትና ታሪኳን የሚያዉቀዉ ወጣት ትዉልድ አቋም ሲሆን፤

በሌላዉ በኩል ደግሞ እነዚያ ከመለኮታዊዉ ዳኝነት የተነሣ የቅጣቱ በትር በብርቱ የገረፋቸዉ ሕዝቦችና የእነርሱ የዓለም መንግስታት ድርጅት አድራጎት ነዉ፡፡

እነዚህ ሁለቱም ወገኖች ዛሬ በኢትዮጵያና በመላዉ ዓለም እየተካሄደ ያለዉን አምላካዊ ፍትሕ እየተመለከቱ አሁንም እንደቀድሞዉ ቃል ኪዳናቸዉን በማፍረስ በዚያዉ ተመሳሳይ ድርጊት ተሰማርተዉ ኢትዮጵያን ለማጥፋትና የእግዚአብሔር የሆነዉን መንግስታዊ አቋሟን ለማፈራረስ፣ ልጆቿንም ለመደምሰስ በኅብረት ሙከራ ሲያደርጉ እነሆ ይታያል፡፡

ኢትዮጵያዊዉ ግን በቃል ኪዳኑ በመተማመን እጆቹን ወደ እግዚአብሔር ብቻ ዘርግቶ በሚያቀርበዉ አቤቱታ ለሁሉም ለያንዳንዱም የማይቀረዉን፣ ለዚህ ሥራቸዉ ምላሽ የሚሆነዉን መለኮታዊ ፍርድ በትእግስት ይጠባበቃል፡፡

ከእግዚአብሔር ዳኝነት ማምለጥ የሚችል ማንም የለምና፤ ከዋይታዉ ለመዳን ይህን የተንኮል ዓላማ የተከተሉት ሁሉ ባገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ያሉ ግለሰቦች ጭምር ከክፋት መንገዳቸዉ በንስሐ ይመለሱ ዘንድ እማጸናለሁ፤» እንዳሉ የተቆጣጠሩት እንባቸዉ ርግፍ ርግፍ ሲል ወደ መጡበት አቅጣጫ ወደ ሕዝቡ ተመለሱ፡፡

ወዲያዉ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ባለስልጣኖች እንዲሁም ካድሬዎች ሁሉም « ምንድነዉ የዛሬዉ ቀን! የአንብሳዉ ዓርማ ሲገርመን፣ ደግሞ ሰምተነዉና አይተናዉ የማናዉቀዉን «ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር» ብለዉ እንደ አንበሳዉ ዘዉድ የደፋች ሴት እጆቿን ዘርግታ ያሳዩን እንዴ! ስለ ታላቁ ዓርማችን ከኮብ አንድ ሰዉ እንኳ አይመሰክርልንምን? የብሔር ብሔረሰቦች አገር ስለ ሆናችዉ ስለ አዲሲቷ ኢትዮጵያ አንድም ሰዉ ታላቅ ምስክርነትን አይሰጥም እንዴ? ታላቁን አንቀጽ የብሔር ብሔረሰቦች መብትንና

ነጻነት እስከ መገንጠል ድረስ የሚለዉን የያዘ የዓለም አገራት እንኳ ይህን አይነት አንቀጽ የሌላቸዉ ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ ምሰሶ ስለሆነዉ ሕገ መንግስታችን የሚያዳንቅና የሚያገን ሰዉ ይጥፋ? ከሌላዉ ዓለም ሕዝብ በተለየ ሁኔታ የፖለቲካችን ማጠንጠኛ ለሆነዉ የግብር አባታችን ያዘጋጀልንን «ብሔር ብሔረሰቦች» የሚለዉን ሲያሜዉን እንደ አቡነ ሰበሰማያት የሚደጋግምልን ሰዉ ይጥፋ? ደግሞ ከአገራቸዉ አልፈዉ ስለ ዓለም እንዲህ መናገራቸዉ ምን ይባላል? አንድ ሰዉ እንኳ «የዚህ ብሔር ነጻ አዉጭ ነኝ፤ የዚህ ጎሳ ተወካይ ነኝ» ብሎ የሚቀርብ ሰዉ ይጥፋ? እረ ዘንድሮ ስንቱን ጉድ አሳየን፤ ምን አይነት ንክ ጭንቅላት ቢኖራቸዉ ነዉ ከጎሳቸዉና ከብሔራቸዉ ዉጭ የሚያስቡትና እንዲሁም ከአገራቸዉ አልፈዉ ለዓለም ሕዝብ የሚቀረቀሩት? ወይስ ስለ ብሔር ብሔረሰቦች አገር ስለ አዲሲቷ ኢትዮጵያ የማያዉቁ ከማርስ ወይንም ከጨረቃ የመጡ የጥንቷ ኢትዮጵያዉያን ይሆኑ እንዴ?» እያሉ እየሳቁና እያፌዙ እንዲሁም አንዳንዶቹ እርስ በእርስ እየተወያዩ ሳለ፡-

አንድ ጎልማሳ ጃኬትና ሱሬ ያደረጉ ከመሃል በድንገት በቁጣና በብሩህ ተስፋ ገጽ ወደ መድረኩ ሲመጡ አይተዉ « አሁን እንኳ ለእኛ የሚቆምና የሚመሰክር ዘመናዊ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብ የሚወክል በድንገት ወደ መድረኩ መቶ ይናገርልን እንጂ! » እያሉ የጎልማሳዉን ንግግር በጉጉት እጠበቁ ሳለ፡

ጉልማሳዉ ሰዉ «ዓለም እነ ጳዉሎስን እብዶች ብላለች፤ዓለም በልዑል ስም የመጡትን እነማንን ተቀበለች? ተሳለቀች፣ ገደለች፣ አሳደደች እንጂ ዓለም ለእግዚአብሔር ባለአእምሮ የሆነን ሰዉ ለእናንተ እብድ ነዉ ትላላች:: ስለዚህ የእግዚአብሔር መልእክተኞችን ሰምታ አታዉቅም:: በመሆኑም ብትሰሙ ስሙ ባትሰሙም አትስሙ ነጻ ኅሊናና ፈቃድ አላችሁ:: እናንተ እንደምትሉት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ቃል «የእብዶች ቃል ነዉ» ሰምታችሁ ሳቁ፣ ተሳለቁበት፣ ይምሽ፣ ይንጋ፣ አይምሰላችሁ በሳቅና በፌዝ የፈጃችሁት ጊዜ በሺህ እጥፍ ዋጋ ትከፍሉበታላችሁ::

እኛ እናንተ የምታላግጡባትና ልታጠፏት የተሰለፋችሁት የጥንቲቷ ኢትዮጵያ ዜጎቿና ልጆቿ ነን:: በሌላ ዓለማት ዉስጥ ያልነበርን ለአስራዎቹ ዓመታት በኢትዮጵያ ሆነ በዓለም የሚከናወኑትን ድርጊትና ንግግሮች አብረናችሁ ሆነን የምንመለከትና የምንከታተል ነን::

ስራችሁንና ንግግራችሁን ለአስራዎቹ ዓመታት የተመለከትንና ያዳመጥን ሲሆን በእግዚአብሔር እዉነታ ላይ ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት በመፈጸማችሁና በማስፈጸማችሁ ኅሊናችን የደማና የቆሰለ፤ እግዚአብሔር ስራዉን የሚሰራበትን ጊዜ በትእግስት እየተጠባበቅን ያለን ሰዎች ነን ::

የሰዉ ዘር ስሙ የሥላሴ ባሪያ፣ የድንግል ማርያም ያደራ ልጅ፣ የከበሩ መላእክት ወደጅ፣ እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ ባዘዘኝና በተናገረኝ መሰረት የመጀመሪያዉን የእግዚአብሔር መልእክት ኅዳር፯፥፲፱፻፺፰ (7/1998) ዓ.ም፣ ሁለተኛዉን መልእክት ግንቦት፳፯፥፳፻ (ግንቦት27/2000) ዓ.ም፣ ሶስተኛዉን መልእክት መጋቢት፲፱፥፳፻፩ (መጋቢት 19/ 2001) ዓ.ም ለአገራት መሪዎች ፣ ለተባበሩት መንግስታት፣ ለተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ፣ ለተለያ ግለሰቦች፣ ባጠቃላይ ለአዳም ዘር እንዲተላለፍ መልእክቱን የላኩ ቢሆንም እስከአሁን ድረስ ከአገሬ ኢትዮጵያ መንግስት ጀምሮ አንድም መንግስት መልእክቱን ለሕዝቡ አላስተላለፈም:: ለዚህም ኃላፊነቱን እንደሚወስዱ ጭምር አስጠንቅቄ ነበር:: ነገር ግን እነሱም በንስሐ እጃቸዉን ለእግዚአብሔር መስጠትና ሕዝቡም በንስሐ እጁን ለአምላክ እንዲሰጥ ማድረግ ሲጠበቅባቸዉ ተቃራኒ ተግባርና የእብሪትና የትዕቢት ንግግር ይናገራሉ፤ መልእክቱንም ከቁም ነገር አልቆጠሩም:: ይህም የሚያሳየው ምን ያህል ልበ ደንዳኖች መሆናችሁንና እግዚአብሔርንም ምን ያህል እንደናቃችሁ ነዉ የሚያሳየዉ::

እኔ ጸሎቴና ምኞቴ « እናንተ የእግዚአብሔርን መልእክት አንፈልገዉም፣ አንቀበለዉም::» ብትሉ እንኳ ሕዝቡ መልእክቱን ሰምቶ ራሳኑ ከጥፋትና ዉድቀት እንዲያድን ነበረ:: መልእክቱ በሰዎች እንዳይዳረስ ደግሞ «ማንም ሰዉ መልእክቱን እያባዛ እንዳያስተላልፍ ለተላላኪዎቻችሁ ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጣችሁ:: የደረሳቸዉም ሰዎች ቢሆን ኅሊናቸዉ በቴሌቭዥኑ፣ በሬዲዮኑ፣ በመጽሔቱ፣ በጋዜጣዉ፣ በመጽሐፍ፣ በኢንተርኔት .. ወዘተ በመሳሰሉት በሚታዩት፣ በሚደመጡት፣ በሚነበቡት ስለደነዘዘ ለእግዚአብሔር መልእክት አንዳች ቦታ አልሰጠም::

«የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን፡፡» የሚሉት ሳይቀር አጣጥለዉታል፤ ንቀዉታል፡፡ ለሁሉም እያንዳንዱ ዋጋ መክፈሉ አይቀርም፡፡ አሁን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በመልእክቱ እንደተገለጸዉ በዓለም ላይ ያልታሰቡና ያልተጠበቁ ክስተቶች ሲከሰቱ እያየ አሁን ትዉልዱ ደንገጥ ማለት ጀምሯል፡፡ ይህ ገና ምልክት ነዉ እጅግ የከፋዉና የማይገመተዉ ክስተት በቅርቡ በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም ላይ ይመጣል፡፡ እያንዳንዱ መንግስት፣ ቡድን ፣ ድርጅት፣ ግለሰብ የዘራዉን የዐመጻና የክህደት እንዲሁም የርኩሰት ፍሬዉን ያጭዳል፤ መራራ ጽዋዉንም ይጠጣል፡፡

አሁንም መንግስታት ባትሰሙኝም ሕዝቡ ግን እንዲሰማኝ እፈልጋለሁ፡፡ ይኸዉም «ኢትዮጵያ የዓለም ብርሃን» በሚል የተላለፈዉ የሶስት ጊዜ ጥራዝ መልእክትን አንብባችሁ፣ መጭዉን ጊዜ አዉቃችሁ፣ ራሳችሁን ለእዉነተኛ ንስሐ አብቅታችሁ እንድትገኙ፡፡ እናንተ የየአገራት መሪዎችና ተወካዮች፣ ባለስልጣናት፣ የተለያዩ ተቋማትን ወክላችሁ እዚህ የተገኛ ችሁ፣ ባጠቃላይ በተለያየ ወንበርና ኃላፊነት ላይ ያላችሁ፤ አሁንም እግዚአብሔር የመጨረሻ እድል ሰቷችኋል ፡፡ ስለሆነም ሳትወዱ በግድ ከወንበራችሁና ከኃላፊነታችሁ ተቀርጣችሁ ከመዋረዳችሁ በፊት ወንበሩን ለድንግል ማርያም ባለሟሎችና ምርጥ የአደራ ልጆች፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለሚፈጽሙና ለሚያስፈጽሙ ልቀቁ፡፡

እናንተም የተለያዩ አገራት(መንግሰታት) መሪዎች ከሕዝቦቻችሁ ጭምር እጃችሁን ለሠራዊት ጌታ፣ አገልጋዮቹን በተመረጠችዉና ሞገስ ባገኘችዉ አገር በኢትዮጵያ በዙፋን ላይ ለሚያነግሠዉ ስጡ፡፡ ያኔ በረከተ ሥጋንና ድኅነተ ነፍስን ታገኛለችሁ፡፡ ሃይማኖታችሁም የኢትዮጵያ ተዋህዶ ኦርቶዶክስ ብቻ አድርጉ፡፡ «አይ! እኛ የዲያብሎስ ስርዐትን ፣ ራሳችንን ያነገሥንበትንና ከፍ ከፍ ያደረግንበትን ይሻለናል» የምትሉ ከሆነ ምራጫዉ የራሳችሁ ነዉ፡፡ ነገር ግን የሚመጣባችሁን የእግዚአብሔር ቁጣ በጸጋ መቀበልና ዳግም የንስሐ እድል ወደማታገኙበትና ነጻነታችሁ ተገድቦ እንደ ዐመጻችሁ ደረጃ ፍዳችሁን ወደምትቀበሉበት ሲዖል እንደምትሄዱ ልታዉቁ ይገባል፡፡ ሕዝቡን ባለማሰወቃችሁ ምክንያት እንደምትጠየቁበትና የባሰዉ የእግዚአብሔር ቁጣ እንደሚመጣባችሁ ላሳዉቃችሁ እወዳለሁ፡፡ ለብዙ ዓመታት

ጥፋት እንዳይመጣ የራሴን ጥረት ባደርግም የሚቀበለኝ በማጣቴ በእንባ ጭምር ነዉ የአሁኑን መልእክቴን ያደረስኳችሁ፡፡» በማለት ወደ ወጡበት ቦታ ተለመለሱ፡፡

አንዳንድ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት አባቶች « ቴዎድሮስ የሚባል ንጉሥ ይነግሣል፤ ኢትዮጵያም ሆነች ዓለም በአንድ ንጉሥና በአንድ የሃይማኖት አባት ትመራለች እየተባለ ለዘመናት ሲነገር የነበረዉ ጊዜ ደረሰ እንዴ?» በማለት ሲያሾኮሹ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰምተዉ፡

« እናንተ በዛሬዉ እለት በዚህ ቦታ የተገኛችሁ ከአገር ዉስጥም ከዉጭም የመጣችሁ ተጋባዥ እንግዶችና የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ከሚቀጥለዉ ዓመት ጀምሮ ነጻ መንግስታችሁን ታዉጃላችሁ ብዬ የተናገርኩት ያላሰብኩትን መዘዝ ስላመጣብኝ፤ በመስከረም ወር በሚከፈተዉ የተከበረዉ ምክር ቤት ላይ አሁን የተባሉትንና ሌሎች ጉዳዮችን በመወያየት አስፈላጊዉን እርምጃና ዉሳኔ የምናደርግ መሆኑን አሳዉቃለሁ፡፡

አሁን ሁላችሁም በተረጋጋ ሁኔታ ወደመጣችሁበት እንድተመለሱና ሕዝቡን እንድታረጋጉ በጥብቅ አሳስባለሁ፡፡ እስከዚያዉ ድረስ ደግሞ እድሜ ማራዘሚያ ኪኒን የሆነዉን ልዩ ቋንቋዬን « ብሔረ ብሔረሰብነታችን ለብዙኃነታችን፣ ለአንድነታችን፣ ለህዳሴያችን» የሚለዉን እንደ አቡነ ዘበሰማያት በተለያዩ መድረኮች በማነብነብ ያንቺን የምናጠፋበትን ወይን የምንጠፋበትን ጊዜ መጠበቅ ይኖርብናል» በማለት ተናግረዋል፡፡ እኔ የጨለማዉ ገዥ ግን እነዚያ «የእግዚአብሔር መልእክተኞች ነን» ባሉት ላይ በሕዝብ ፊት ቀጥተኛ እርምጃ ይወሰድባቸዋል እያልኩ በጉጉት ስጠባበቅ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያላሳሰብኩትና ያላዘዝኩትን ንግግር በማደረጉ እስከአሁን ድረስ ብስጭቱ ባይለቀኝም እድሜ ከተሰጣቸዉ በመስከረም ወር ላይ ግን የብቀላ እርምጃ እንዲወሰድ ከማሳሰብ እንደማልቦዝን እገልጽላችኋለሁ፡፡» **ይላል የጨለማዉ ገዥ መንግስታትን የሚያደነድንና የሚያሳምጽ ዲያብሎስ ከጭፍሮቹ ሰይጣናት ጭምር፡፡**

# ምእራፍ ሁለት

« የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥታት ሰንደቅ ዓላማ ፍቅር ያቃጠላቸዉ የብሔር ብሔረሰቦች ተወካዮች ለአገሪቱ መሪና ለከፍተኛ ባለስልጣናት ቅሬታቸዉን አሰሙ:: ይኸዉም« እኛ የብሔር ብሔረሰቦች ወያኔ(ኢህአዴግ) አባታችንና መንግሥታችን ስንት መስዋዕትነት ከፍሎ ነጻነታችንን አጎናጽፎን ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብታችንን ጠብቆ፤ የተዋደቀለትንና የተጋደለለትን ሰንደቅ ዓላማችንን የተለየ የክብር ቦታ አለመሰጠቱ ቅር አሰኝቶናል:: ምክንያቱም ለወደፊቱ ራሳችንን ችለን ነጻ መንግስታት እንደምንሆን እየታወቀ በታላላቅ ሆቴሎችና መሰብሰቢያ ቦታዎች ላይ ከሌሎች አገራት መንግስታት እኩል ከፍ ብሎ አለመዉለብለቡና ለወደፊት ከነአካቴዉ ከሚቀረዉና ከሚሻረዉ የፌደራሉ መንግስት ሰንደቅ ዓላማ እኩል እንኳ አለመቆጠሩ አሳዝኖናል:: በተለይ የጨለማዉ ገዥ ዓርማ ኮኮብ የተደረበት የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት፣ የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰንደቅ ዓላማዎች እንደ ሌሎቹ ክልላዊ መንግስታት እኩል መቆጠራቸዉና ከፌደራሉ መንግስት እኩል መዉለብለብ አለመቻላቸዉ ዋናዉን የኮከቡ ባለቤት እንደመናቅ ሊታይ ስለሚችል ቢታሰብበት » በማለት ቅሬታቸዉንና አስተያየታቸዉን አቅርበዋል::

የአገሪቱ መሪም፤ ጨለማዉን ነጭ፣ ነጩን ጨለማ ለማለት ወደ ኋላ የማይመለሰዉን ታማኙን አገልጋያቸዉንና አፈቀላጤያቸዉን ምላሽ እንዲሰጡ የጋበዙ ሲሆኑ፤ ተጋባዡም «እናንተ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ተወካዮች፤ ለወደፊቱ ነጻ መንግስታችሁ ከአሁኑ በመቆርቆር ለክልላዊ መንግስታችሁ ሰንደቅ ዓላማ ያላችሁ የነደደ ፍቅር እጅጉን አኩርቶናል:: እንኳን በፌደራሉ መንግስት ቀርቶ በተባበሩት መንግስታት መሰብሰቢያ አዳራሽ «ለወደፊቱ ነጻ የሚሆኑ የመንግስታቱንም ቁጥር ከፍ የሚያደርጉ የክልላት መንግስታት ሰንደቅ ዓላማ» ተብሎ ከፍ ብሎ ቢዉለበለብ ደስታዉን አንችለዉም::

በፌደራሉ ብሔራዊ መንግስት ግን ይኸዉ «የብሔር ብሔረሰቦች ሰንደቅ ዓላማ ቀን» ተብሎ በያመቱ እየተከበረና የክልላት መንግስታት ሰንደቅ ዓላማ ከፌደራሉ መንግስት ሰንደቅ

ዓላማ እኩል ሲዉለበለብ እየታየ ስለሆነ በዚህ አንዳች ቅሬታ የሚገባችሁ አይመስለኝም፡፡ የፌደራሉ መንግስት ሰንደቅ ዓላማ የነፍጠኞችና የትምክህተኞች ስላልሆነ ዋናዉ የጨለማዉ ገዥ አርማ ኮኮብ ስለተደረገበት ከክልላት ሰንደቅ ዓላማ ጋር አብሮ በመዉለብለቡ እንዲሁ ቅር እንማደትሰኙበት እናምናለን፡፡ ለወደፊት ነጻ መንግስታችሁን ስትመሰርቱ ከናካቴዉ ስለምታስወግዱት የምትጠሉትም ከሆነ ለትንሽ ጊዜ መታገስ ይጠበቅባችኋል፡፡

ለሌሎች የክልላት መንግስታት የግብር አባታችን አርማ የሆነዉ ኮኮብ ሰንደቅ ዓላማ ላይ እንዲታይ ያላደረግነዉ አድሎ ለመፍጠር ሳይሆን ዋናዉ መሪያችን «ሌሎቹም ሰንደቅ ዓላማዎች በኔ በጨለማዉ ገዥ መሪነት የተዘጋጁ ስለሆነ ማዕረጋቸዉ እንደ ኮኮቡ ስለሚቆጠር ልዩነት የለዉም» ስላለን ነዉ፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ጠቅላይ ሚኒስትራችንን ሆነ ሌሎቻችሁ ባለስልጣናትን «አንደበትህ አንደበታችን ነዉ፡፡» ብላችሁ ሙሉ ዉክልና ስለሰጣችሁኝና የኢህአዴግ መንግስትን አቋም እንድገልጽ ስላደረጋችሁ በጨለማዉ ገዥ ስም አመሰግናችኋለሁ፡፡ አደራ የምለዉ የጦር አዛዥነትን ዉክልና እንዳትሰጡኝ ነዉ፡፡ ምክንያቱም ኅሊናዬ በቀልና ጥላቻ የሞላዉ ስለሆነ ለማንም ምህረት የማላደረግና ሳላዉቅ በደጋፊዎቻችን ላይ ጭምር እርምጃ ልወስድ እችላለዉ የሚል ስጋት ስላለኝ ነዉ፡፡ » እንዳሉ  ሳቅና ሞቅ ያለ ጭብጨባ ቀርቦላቸዋል፡፡

በዚያ አጋጣሚ አንድ ከፍተኛ ባለስልጣናት ተነስተዉ «የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር! አንዳንዶቻችን ባለስልጣናት ቀድሞ ስማችን ያልሆነዉን ስም ይዘን ብሔር ብሔረሰቦችን ስናስተዳድር በተለያየ መልኩ ያሙናልና ለምክንያቱ ማብራሪያና ምላሽ ቢሰጡልን?» በማለት የጠየቁ ሲሆን፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩም «ይህን በመሪያችን መንፈስ መሪነት የወጣላችሁን ስም ማግኘታችሁ የእድለኞች እድለኞች ያሰኛችኋል እንጂ አንዳች ሊያሳማችሁ አይገባም፡፡ ምክንያቱም የራሱን ስም በተለይ ከክርስትና ጋር የተያያዘ ስም ያለዉ የጨለማዉ ገዥ መንፈስ ስለማይወደዉና ስለሚጸየፈዉ በአዲስ በጨለማዉ መሪያችን መንፈስ የመወለድ እድል ስለሚያጋጥማችሁ ነዉ፡፡ ይህን እድል ያጋጠማቸዉ ደግሞ በእርሱ ዘንድ ሞገስን ያገኙ እጅግ ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸዉ፡፡ ለወደፊት የጨለማዉን መሪችሁን መንፈስ ፍላጎት

ተረድታችሁ እርሱ የማይፈልገዉን ስም ለልጆቻችሁ እንዳታወጡ በዚሁ አሳስባችኋለሁ» በማለት ያለዉን እዉነታ ለሁሉም አሳዉቀዋል::

በማስከተል ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዐይናቸዉ የጠቀሷቸዉ አንድ ካድሬ እጃቸዉን አዉጥተዉ «የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትርና ከፍተኛ ባለስልጣናት፤ የኢህአዴግ መንግስታችን አሳቦችን በግልጽ ማቅረብና መወያየት እንድንችል ዴሞክራሲ መብታችንን ያጎናጸፈን ሲሆን፤ ምንም እንኳን ጥያቄዉ በቀጥታ የኔ ባይሆንም አንዳንድ ብሔር ብሔረሰቦች በቋንቋ አጠቃቀም ላይ ቅሬታ አሰምተዋል:: ይኸዉም «በሕግ መንግስታችን ማንኛዉም ብሔር ብሔረሰብ በራሱ ቋንቋ መናገር፣ መወያየት፣ መስራት፣ መማር ይችላል» ይላል:: ነገር ግን ለብቻችን ሆነን በብሔራችን ፣ በጎጣችን፣ በቋንቋችን ተቧድነን ስንነጋገርና ስንወያይ አንዳንድ ባለስልጣናትና ካድሬዎች «ጠባቦችና ጎጠኞች» ይሉናል:: እኛ ጠባቦችና ጎጠኞች የሆነዉ መንግስታችን ኢህአዴግ ሺህ ዓመት ይንገሥና ወያኔ (ኢህአዴግ) አገሪቱን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ ማስተዳደር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ነዉ:: እንዲሁም በተለያየ መገናኛ ብዙኃንና በስብሰባ ላይ የምንማረዉና የምንሰበከዉ በዚሁ በጎጠኝነት ሕይወት እንድንመላለስ ነዉ:: ታዲያ አሁን ምን መጣና ነዉ በአፍ መፍቻ ቋንቋችን ተቧድነንና ገንጠል ብለን በማዉራታችንና በመሰባሰባችን ምክንያት ይህ ስም በተለጣፊነት የሚሰጠን? ወይስ ከብሔር ብሔረሰቦች ጋር እንድንዋድ የተሻሻለ ሕግ ወቷል ወይ?» በማለት ጥያቄ አቅርበዋል::

በወቅቱ መልስ የሚሰጥ ጠፍቶ ለአስር ደቂቃ ያህል ዝምታ ነግሦ የነበረ ቢሆንም፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ « እኔም ዝም ያልኩት ድፍረታችሁን ልገመግም ነዉ:: ሁላችሁም የኔን ልዩ ትዕዛዝ በመጠበቃችሁ ምን ያህል ታማኝ አገልጋዮቼ መሆናችሁን ያረጋገጥኩበትና ስለ አቋማችሁም ያለኝን አድናቆት በዚሁ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ:: ጠያቂዉ ጋድ ያቀረበዉ ቅሬታ በተለያየ ጊዜ እኔም የሰማሁት ሲሆን፤ እኛ የተዋጋነዉና የተጋደልነዉ እንዲሁም ብዙ ሰማዕታት ደማቸዉን ያፈሰሱት የብሔር ብሔረሰቦች መብት ለማስከበር፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸዉ እንዲናገሩ፣ እንዲማሩ፣ እንዲሰሩ ለማስቻልነዉ:: የህልዉናችን መሰረት ይኸዉ በቋንቋ የተከፋፈለ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ስለሆነ በቋንቋ በኩል አንዳች መደራደር የለም::

አንዳንድ ባለስልጣናትና ካድሬዎች «ጠባቦችና ጎጠኞች » የሚሉት እናንተን ሳይሆን አንዳንድ ብሔር ብሔረሰቦች እንደ ፈጣን ሎተሪ ሲፋቁ ማንነታቸዉን እየለወጡና ተቃዋሚ እየሆኑ ገበናችንን እያወጡ ስለተቸገርን ነዉ እንጂ በጎጥና በቋንቋ ተቧድናችሁና ተከፋፍላችሁ ብትኖሩ ለኛ ህልዉና የበለጠ ዋስትና የምናገኝበት ስለሆነ የምናበረታታዉና አስፈላጊዉን ድጋፍ የምናደርግለት መሆኑን በዚሁ አሳዉቃለሁ::

እዚህ ላይ ታዲያ «ጠባቦችና ጎጠኞች» እንዳትባሉ ቢያንስ አንድ የኛ ታማኝ ካድሬ በመሃላችሁ አድርጋችሁ ልታወሩ፣ ልትወያዩ ፣ ልትመካከሩ ይገባል እንጂ «ምስጢራችንና ወሬያችን አይሰማም» ብላችሁ መንግስት ልትገለብጡና ሊታሴሩ እንዲሁም ዐመጻ፣ ሁከት፣ ሽብር ልትፈጥሩ ስለምትችሉ የኛ ታማኝ በሌለበት ሁኔታ በብሔራችሁ ተቧድናችሁ መነጋገር ሆነ መሰባሰብ በግልጽ ባይሆንም በዉስጥ ለዉስጥ መመሪያ ክልክል ነዉ:: ነገር ግን በአብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚመሩ የትኛዉንም ካድሬዎቻችንን በንግግራችሁ፣ በዉይይታችሁ፣ በስብሰባችሁ በማስገባት በፈለጋችሁት አፍ መፍቻ ቋንቋችሁ መናገር ትችላላችሁ:: ከዚያ ዉጭ ደግሞ ማንም ሰዉ በሚሰማዉ በአማርኛ ቋንቋ መወያየትና መሰብሰብ ትችላላችሁ:: ከዚህ ዉጭ ግን የጠባብነትና የጎጠኝነት ስያሜ ብቻ አይደለም «ተገንጣይ፣ ወንበዴ፣ አሸባሪ» የሚል ስያሜ በመስጠት ከእስራት እስከ ግድያ እርምጃ የምንወስድ መሆኑን እያንዳንዱ ሰዉ ሊያዉቅ ይገባል:: » በማለት የድርጅታቸዉን ጽኑ አቋም ለካድሬዋቻችዉና ለብሔር ብሔረሰቦች አሳዉቀዋል:: እኔም የጨለማዉ ገዥ በንግግራቸዉ ስለተደሰትኩ ከአስር ደቂቃ በላይ በጭብጨባና በፉጨት ድጋፍ እንዲገለጽላቸዉ አስደርጌያለሁ:: » **ይላል የጨለማ ስራ የግብር አባት የሆነዉ ዲያብሎስ::**

## ምእራፍ ሦስት

« የተለያዩ ሃይማኖት፣ የተለያዩ ባህላዊ እምነት፣ የተለያዩ ባዕድ አምልኮ፣ እንዲሁም በግልጽ ሰይጣናትን የሚያመልኩ ተወካዮች የአገሪቱን መንግስት ለማሳማን በቤተመንግስት በመገኘት ንግግር አቅርበዋል። በመጀመሪያ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት መሪ የተወከሉት ቀሲስ(ቄስ) ሲሆኑ፤ እሳቸዉም « በመጀመሪያ ለዚህች የተቀደሰች ቀን ያደረሰን የተመሰገነ ይሁን። ቅዱስ አባታችን በዚህ ታላቅ ክብረ በዐል ላይ መገኘት ያልቻሉት ትንሽ የጤና መታወክ ስላጋጠማቸዉ ነዉ። ስለሆነም የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር በስልክ እንደተነገሮት « መምጣት ባለመቻሌ ይቅርታ፤ ነገር ግን አንደበቱ አንደበቴ የሆነዉን ታላቁን አገልጋዬን ነዉ የላኩላችሁ ከእኔ የሆነዉን ሁሉ ይነግራችኋል» ብለዉ ስለሆነ እኔ ልመጣ የቻልኩት በዚያዉ መሰረት እንደምታዳምጡኝ አምናለሁ።

የተከበሩ የአዲሲቷ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሳዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር! ከፍተኛ ባለስልጣናት፣ እንዲሁም የኢህአዴግ አባላት እንደማዕረጋችሁ፣ ተጋባዥ እንግዶች በሙሉ፤ እኔ እዚህ የተለየ ቦታ ከተመረጡ ሰዎች ዘንድ ቀርቤ ንግግር እንዳቀርብ እድሉ ስለተሰጠኝ የእናንተ የምርጦቹ አምላክን አመሰግነዋለሁ። መንግስታችን ባጎናጸፈን ዴሞክራሲ መብትና ነጻነት እንዲሁም እድገትና የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት፣ የሃይማኖት እኩልነትና ልዑላዊነት፣ እዉነተኛ ፍትሕ ያጎናጸፈን በመሆኑ እንደ ዉዳሴ ከንቱ ካልተቆጠረብኝ «መንግስታችን የመላእክት ስብስቦች የሞሉበት ነዉ» ብል ማጋነን አይሆንብኝም።

ይህን ካልኩ ዘንድ ለየት ያሉ ነጻነትንና እኩልነትን ከሚገልጹ ታላላቅ ተግባሮች አንዳንዶቹን ለመግለጽ እፈልጋለሁ። መንግስታችን ለሃይማኖታችን ሙሉ ነጻነትን ሰቶ የተለያዩ አምልኮቶችን በጋራ እንድናከብር በማድረጉ ነዉ። ለምሳሌ ቀድሞ ነፍጠኞችና የገዥ መደቦች አምልኮታችንን በነጻነት እንዳይፈጸም አምላኮቻችንንም እንዳናከብር እንዳልተደረገ ሁሉ፤ በሃያ አመቱ የሰላም፣ የዴሞክራሲ፣ የነጻነት ፣ የእኩልነት ዘመን ዉስጥ ለበዐላችንና ለአምላካችን ትልቅ እዉቅና ተሰቶ በየወንዛወንዙ አምልኮታችንን እንድንፈጽምና እኛም የሃይማኖት አባቶች መስቀላችንን ይዘን በተለይ በዋናዉ የቢሾፍቱ አምላክ በሚከበረዉና አምልኮት በሚፈጸምበት ቦታ ላይ በእሬቻ በዐል ላይ ቡራኬና ትምህርት እንድንሰጥ እድሉን ስላገኘን ነዉ።

እኛም የመንግስታችን ስራ አስፈጻሚና ፈጻሚ መሆናችንን በግልጽ መመስከራችን ይታወቃል። ይኸዉም « በቤተ ክርስቲያን ሆነ በዚህ በተቀደሰ በዐል ላይ መታችሁ አምልኮ

መፈጸም ክልክልነት የለዉም፤ ክልክልነት ያለዉ በሕገመንግስቱ የተገለጹትን ወንጀሎች መፈጸም ብቻ ነዉ እንጂ አምልኮታችሁን በተለያየ ምልኩ ብትገልጹ ችግር የለዉም። « ታቦትና ጣዖት አንድነት የላቸዉም፤ ባዕድ አምልኮና የክርስትና እምነት አንድነትና ህብረት የላቸዉም፤ ዲያብሎሳዊና እግዚአብሔራዊ መንፈስና ስርዐት አንድነትና ህብረት የላቸዉም፤ .. ወዘተ» የሚለዉ አባባል በዴሞክራሲያዊ መንግስታችን ስለቀረና ሁሉም እኩልና አንድ እንደሆኑ ስለተረጋገጠ በዚሁ እድለኞች ናችሁ እኛም ነን። ስለዚህ በብሔር ብሔረሰቦች አምልኮ ሆነ ሌሎች ባህሎች በአንድ ላይ በህብረት አምልኮትን ልንፈጽም ይገባል።

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እንደምርጫችንና ፍላጎታችን የሃይማኖት መሪዎቻንን ሐዉልት እንድናቆምና ስዕላቸዉንም በመለጠፍና በማቆም እንድንለማመንባቸዉና እንድናገናቸዉ ሙሉ ነጻነት ስለተሰጠን ታላቁ መንግስታችንን እናደንቃለን። ከዚህ በተጨማሪ በየብሔር ብሔረሰባችን ተከፋፍለንና ተቧድነን በዘር፣ በጎጥ፣ በቋንቋ ተለያይተን በዘመድ አዝማድ ተተብትበን ሃይማኖታችንንና ቤተክርስቲያናችንን በነጻነት እንድናገለግል እንዲሁም አንዳንዶቻችንም ለደኅንነታችን መሳሪያ እንድንታጠቅ ስለተፈቀደልን ባለእድለኛነታችንን ያሳያል። በሽልማት አንጻርም ምእመኑ ለልዩ ሽልማት እንዲያዋጣ እየተደረገ ልዩ መኪና እንዲገዛ እየተደረገ ዓለምን ለናቁ ለእግዚአብሔር ራሳቸዉን ጃንደረባ ላደረጉ ቅዱሳንና ብጹዐን አባቶች እንዲሸለሙና የሀብት፣ የንብረት፣ የህንጻ፣ የንግድ ተቋማት ባለቤት እንዲሆኑ ስለተደረገና እንዲሁም እኛም በነጻነት ከፈለግን በተሐድሶ፣ ከፈለግን በጸጋና ቅባት፣ ከፈለግን በምንፍቅናና በክህደት ብንመላለስ፤ ቅዱስ አባታችን ከመንግስታችን ሙሉ ስልጣን በተሰጣቸዉ ድምጽን በድምጽ መሻር መብታቸዉ ተጠቅመዉ ነጻነትን አጎናጽፈዉናል። ጠበቃም ይሆኑናል። ሲፈልጉም ይሾሙናል። ባጠቃላይ ለዚህ ሙሉ ነጻነትን ላጎናጸፈን ለመንግስታችን የምስጋናም ምስጋና ሊገባዉ ይገባል።» ሲሉ በአዳራሹ የተሰባሰቡት እድምተኞች ከአስር ደቂቃ በላይ በጭብጨባና በእልልታ አዳራሹን አናግተዉት ነበር።

በመሀል መድረኩን የሚመሩት አስተናጋጅ «ሰዐት ስለሌለን አንዴ ጸጥ በሉ» በማለት ካሳሰቡ በኋላ ለቀጣይ የእስልምና ሃይማኖት መሪ ተወካይ ሰተዋል። ተወካዩም « እኛ ሙስሊሞች ለዘመናት ተጨቁነን የኖርን፤ በአገራችን እንደ ሁለተኛ ዜጋ የምንታይ፤ እኛ ባለንበት የነፍጠኞች ገዥ መደቦች ቤተክርስቲያን አቋቁመዉ ሲያስቸግሩን ነበር። እድሜ ለኢህአዴግ መንግስታችን ይኸዉ ሃይማኖታችንን በነጻነትና በእኩልነት እንድናከብር፣ በአካባቢያችን ቀድሞ ተሰርተዉ የነበሩትን አብያተክርስቲያናትን እንድናፈርስና በአካባቢያችን ያሉትን ክርስቲያኖችን እንድናሳድድ፣እንድንበቀል፣ ተጽህኖ እንድናደርስ፣ ባለስልጣናትና

ካድሬዎቻችሁ ጥሩ አድርገዉ ስለሰበኩን፤ ይኸዉም በቴሌቭዥን፣ በሬዲዮኑ፣ በጽሑፍ፣ በስብሰባ፣ በመንደርና በሰፈር ዉስጥ «ነፍጠኞች ወይንም አማሮች ወይንም ክርስቲያኖች የሆኑት የገዥ መደቦች ሃይማኖታችሁን፣ ባህላችሁን፣ ቋንቋችሁን ያጠፉባችሁና ወንዶቻችሁን በመስለብ፣ ሴቶቻችሁን ጡታቸዉን በመቁረጥ ግፍና በደል የፈጸሙባችሁና የገደሏችሁ መሆኑን እንድታቁ። አሁንም ይህን ስርዐት ለመመለስ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ስላሉ ዝም እንደትሉ።» በማለት ኅሊናችንን ስለመረዙትና ለበቀል ስላነሳሱት የፈለጋችሁትን ፍሬ በማፍራት ወደ ተግባር ለዉጠን በማሳየት ምን ያህል ከጎናችሁ እንደቆምን አስመስክረናል። ለወዲፊቱም በበለጠ ሁኔታ በቀድሞ ስርዐት ዉስጥ የተመላለሱትን እንደምኞታችሁና ፍላጎታችሁ ብዙ እናሳያችኋለን።

መንግስታችንም ይህንኑ ታማኝነታችን አይቶ ትልቅ ዉለታ የዋለልንን በዚሁ ለመግለጽ እንወዳለን። ይኸዉም የቀድሞ ነገሥታት ክርስቲያኖች ብቻ ተደርጎ ይቆጠር የነበረዉን ማስተካከያ እንዲደረግበት አድርጎና እዉነቱን አዉጥቶ የመጀመሪያ እስልምና እምነት የተቀበለዉንና ብሔራዊ ሃይማኖት ያደረገዉን ንጉሥ አልነጃሺን እዉቅና ሰቶልን ከተለያዩ ከአረብና ከአፍሪካ አገራት የእምነቱ ተከታዮች መተዉ በተቀደሰዉ በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዉስጥ አምልኮታቸዉን እንዲፈጽሙ በማድረጉ ነዉ። ሌላዉ ቀደም ያሉት አባት እንደገለጹት የተለያየ አምልኮታችንን በጋራ እንድንፈጽም በመደረጉና ለአምላኮቻችንም እዉቅና በመሰጠቱ በድጋሜ ለታላቁ መንግስታችን ምስጋና እናቀርባለን።» በማለት እንድተናገሩ የተለመደዉ ጭብጨባ ሲቀርብ፤ ተናጋሪዉ ሰዐት ያለቀ መስሏቸዉ «ለወደፊት ደግሞ ብዙ የምንመሰክረዉ አለ» በማለት ንግግራቸዉን አቋመዋል።

በማስከተል ደግሞ የካቶሊክ ሃይማኖት ተወካይ « ይህች እለት እኛም የተመረጠችና የተቀደሰች ናት እንላለን። ታላቁ መንግስታችን ባጎናጸፈን ዴሞክራሲና ነጻነት መብትና እኩልነት ይኸዉ የኦርቶዶክስ ምእመናን « ይህ የኛ ቤተክርሲያን አይደለም ወይ? ዜማዉስ የኛ አይደለም? ስርዐቱን የኛ አይደለም? አገልጋዮቹስ የኛ አይደሉ ወይ?» ብለዉ እስከሚቸገሩ ድረስ ቤተክርስቲያናችንንና አምልኮታችንን በማመሳሰል ብዙ ነፍሳትን በቀላሉ መማረክ ችለናል። ምእመኑንም ከኋላ ቀር አለባበስ ለይተነዉ በዘመናዊ ደስ ባለዉ አለባበስ እንዲመላለስና የጾምና የጸሎት ሸክም አቅለንለት እንደ ሥጋዊ ፍላጎቱና ምርጫዉ አምልኮቱን እንዲፈጽም አድርገናል። መንግስትም የኦርቶዶክስ አማኞችን በቀላሉ ወደ በረታችን ዉስጥ ለማስገባት እንድንችል መንገዱን በደንብ ስላመቻቸልን ዛሬም ዘወትርም እናመሰግነዋለን።» በማለት ንግግራቸዉን እንዳቀረቡ፤ የተለመደዉ ጭብጨባ ስለቀጠለ ለቀጣይ ተናጋሪዎች

ማህፀናቸዉ ከአምስት መቶ አመት በፊት ለፈለፈለቻቸዉ ለልጆቻቸዉ ለፕሮቴስታን ክፍልፋይ ድርጅቶች ተወካይ ሰተዋል።

ተወካዩም « እኛ የመንግስታችንን ታላቅነት ለመናገር አንደበት ያጥረናል። ብቻ ዝም ብለን «እጹብ፣ እጹብ፣ እጹብ» ብንል የሚቀል ይመስለኛል። ለኛ ያወጣልንን ፀሐይ ለሌላ አልወጣም ብንል ማጋነን አይሆንብንም። ዱሮ በቁጥር ይታወቁ የነበሩት የእምነት ድርጅቶቻችን አሁን እንደ አሜሪካ አገር ለቁጥር የሚታክቱ ድርጅቶች ተፈጥረዋል። ዱሮ ለመግባት እንቸገርባቸዉ የነበሩ ክልሎችና ብሔር ብሔረሰቦች ክፍት ሆነዉልን እንዲሁም ዋና መሪዎች ሆነዉልን በአራቱም ማእዘን በተለያዩ ስያሜዎች ገብተን የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትን እያዳከምንና ምእመኑንም ከእናታችን ከካቶሊክ በላይ ወደ እኛ እያፈለስን እንገኛ ለን። ምክያቱም እንኳን ምእመኑ አይደለም አገልጋዮቹ ሳይቀር በጾምና በጸሎት ስለተመረሩ፣ እንቅልፋቸዉን አተዉ በማገልገላቸዉ ነፍሳቸዉ እረፍት በማጣቷ እረፍት ስለምትፈልግ፣ ጥሩ መዝናኛ የሚፈልጉ ምእመናን ደግሞ በፈለጋቸዉ አለባበስ ከፈለጉ ደረትና ጡታቸዉን ገላልጠዉ፣ ከፈለጉ በተወጣጠረ ሱሬ መላ አካላቸዉን እያሳዩ፣ በመዝሙር የሚዘፍኑበትንና የሚጨፍሩበትን አዳራሽ ስለተዘጋጀላቸዉ፤ እንዲሁም እኛ ጋር መተዉ የሱስን ከተቀበሉ ምግባር ኖራቸዉ አልኖራቸዉ ስለ መጽደቃቸዉ ዋስትና ስለምንሰጣቸዉ፣ ባጠቃላይ ጠባቡን መንገድ አስወግደንና ንደን ሳይጨናነቁና ሳይጋፉ በሰፊዉ መንገድ ወደ መንግስተ ሰማያት እንዲገቡ ስለምናደርግ ምርጫቸዉን እኛን ንጹሀንንና ቅዱሳንን ስለሚያደርጉ ነዉ። እንዲሁም በቀንና በሌሊት መንፈሳችንን ስለምንልክላቸዉ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ሙሉ በሙሉ ወደ እኛ ይገባሉ ብለን እንገምታለን። ለዚህ ነጻነትና እኩልነት ብቃት ላበቃን መንግስታችን አሌ ሉዣ እንላለን።» በማለት ሲናገሩ የተለመደዉ ጭብጨባ ቀርቶ ሁሉም ሳያስቡት የተናጋሪዉ መንፈስ አሸንፏቸዉ «የሱስ ጌታ ነዉ አሜን ሀለ ሉዣ፤ የሱስ ጌታ ነዉ አሜን ሀለ ሉዣ፤ የሱስ ጌታ ነዉ አሜን ሀለ ሉዣ፤ ኦ የሱስ፣ ኦ የሱስ፣ ኦ የሱስ» እያሉ ለብዙ ደቂቃዎች እንደለፈለፉ የተወሰኑት መሬት ላይ ተንፈራግጠዉ «መንፈስ ተሞላን» በማለት ምስክርነትን ሰተዋል።

በማስከተል የባህላዊ እምነት ተከታዮች ተወካይ፤ «መንግስታችን የአማልክቶቻችን ጸጋና በረከት ይድረሰዉ» በማለት ከመረቁ በኋላ «እኛ ለዘመናት አምልኮታችንን በስዉር በሽራኩቻዉ ተደብቀን ተሸማቀን ነበር ስንፈጽም የነበረዉ። እድሜ ለዴሞክራሳዊ መንግስታችን ይኸዉ በየአደባባዩና በየወንዛወንዙ በግልጽ እዉቅና ተሰቶን አምልኮታችንን እንፈጽማለን። «ባዕድ አምልኮ» እየተባልን ከሌሎች ሃይማኖቶችና አምላኮች ዝቅ ይሉ የነበረዉ አማልእክቶቻችን ይኸዉ አሁን በአገር አቀፍ ደረጃ እየተከበሩና እየተመሰገኑ ናቸዉ።

ይኸም ባለ ጊዜ የመሆን እድል እንዳጋጠመንና የኛ መንፈስ የበላይነትን የተጎናጸፈ መሆኑን ያሳያል። ሕዝቡም ከፈለገ በቤቱ በጨሌዉ ፣ በቦረንትቻዉ፣ በአርሲዋ እመቤት፣ በወሎ መጀን ፣ በታዬ ከራማ፣ በጠንቋዩ ፣ በአስማተኛዉ፣ በመተተኛዉ መንፈስ እየተለማመነ አምልኮቱን በነጻነትና እኩልነት በመፈጸም ላይ በመሆኑ ትልቋን ፀሐይ ለኛ በተለየ ሁኔታ እንዳወጣችሁልን ነዉ የምናምነዉ። ለዚህም እንደ አማልክቶቻችን እግራችሁ ስር ወድቀን ብናመሰግናችሁ ደስ ይለናል» በማለት በጠቅላይ ሚኒስትሩና በባለስልጣኖቹ እግር ስር ወደቁ።

ወዲያ በቅናት የተቃጠለዉ የቀጥተኛዉ አዉሬ መንፈስ ተወካይ « እናንተ ያለቦታዉ የወደቃችሁ ተነሱ» በማለት የባህላዊ እምነት ተወካዮችን እንዲነሱ ካዘዘ በኋላ « በመጀመሪያ የጨለማዉ ገዥ ጌታችንን ዲያብሎስን እንድናመሰግን ሁላችሁም ተነሱ» በማለት ሲናገር ተሰብሳቢዎቹ የዲያብሎስ ስም በመጠራቱ ተደናግጠዉ ባሉበት ፈዘዙ። ወዲያዉ ተወካዩ « በእርግጥ እስከአሁን ድረስ በሥጋ የተገለጡ ወኪሎቻችንን ሲሆኑ ያዳመጣችሁት፤ ሁሉም የእኛን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ምስክርነትን ስለሰጡና ለመንግስታችንም ታላቅ ምስጋናንና አድናቆትን ስላቀረባችሁ በዚሁ አጋጣሚ በጨለማዉ ስማችን እናመሰግናችኋለን።

ለወደፊት ደግሞ «ኀሊናችንን አንሸጥም፣ ከነፈነሰዉ ጋር አንነፍስም፤» በማለት የኛ ተቀዋሚ በሆነዉ መንፈስ የሚመሩና «የምናመልከዉ አምላክ አንድ አምላክ ነዉ። እርሱም አልፋና ያሜጋ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለዉ የፍጥረታት ጌታና ፈጣሪ የሆነ ሁሉ በእርሱ ለእርሱ የተፈጠረ በአንድነትና በሶስትነት የሚመለክ አንድነቱንና ሶስትነቱንም የገለጸዉ ከሶስቱ አካላት አንዱ አካል እግዚአብሔር ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ በመሆን በተዋህዶ ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ በሆነዉ በመስቀል ላይ በተሰቀለዉ አምላክ በጌቶች ጌታ በነገሥታን ንጉሥ በሆነዉ በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነዉ።» በማለት የኛን የተለያዩ አማልክቶችን የሚቃወሙና የሱስን የማይቀበሉትን ምእመናንና አገልጋዮችን በግድም ይሁን በዉድ እንደ አሁኑ አይነት የምስክርነት አደባባይ አዘጋጅታችሁ አሁን የተሰጠዉን ምስክርነት እነሱም እንዲሰጡ አድርጉ። ይህ ካልሆነ ግን በአጭር ጊዜ ዉስጥ በሥጋዊዉም ሆነ በመንፈሳዊዉም ወንበር ላይ የተቀመጣችሁ ስልጣናችሁ እንደሚሻርና ለሌላ ለተሻለ ብቃት ላላቸዉ ምርጥ ባለሚሎቼ ወንበሩን አሳልፌ እንደምሰጥ በታላቁ የግበር አባታችሁ ዲያብሎስ ስም እምላለሁ» ብዬ እኔ የጨለማዉ ገዥ ተሰወርኩ።

በመቀጠል የአገሪቱ መሪ « በእርግጥ ይህች ቀን የተመረጠች ብዙ ድንቃድንቅ ያልተጠበቁ ንግግሮችና ተአምራቶች የታዩበት ነዉ። ትንሽ የሚከብደዉ በመጨረሻ የታዘዝነዉን ተግባራዊ ማድረግ ላይ ቢሆንም በአምስቱ ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን

የሽግግር ዓመት ዉስጥ ጉን ለጎን ተግባራዊ ለማድረግ እንድንችል እዚህ የተገኛችሁ ባለስልጣናትና የኢህአዴግ አባላት እንዲሁም አጋር ድርጅቶች፤የተለያዩ የሃይማኖትና እምነት ተወካዮች በጋራ መሰለፍ ይጠበቅባችኋል:: ምክንያቱም ለህልዉናችን የመሪያችንን ፈቃድ ግድ መፈጸም አለብን:: ያለበለዚያ ከወንበራችን እንቆረጣለን:: እንደመሰሳለን:: መታሰቢያችንም ለዘለዓለም ይጠፋል:: በመሆኑም እንደ በፊቱ ንግግሬ «መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ» የምል አይደለም:: ተግባራዊ ለማድረግ የሞት ሽረት ልናደርግ እንደሚገባ ከልመና ጋር ነዉ የምማጸናችሁ::» በማለት የተለያዩ ሃይማኖቶች፣ የተለያዩ ባህላዊ እምነት ተከታዮች ተወካይ ዉይይቱ በምርቃት እንዲዘጋ በማድረግ በቤት ስራ ተለያይተዋል:: እኔም የጨለማዉ ገዥ ትዕዛዜ ተግባራዊ እንደሚሆንና እንደማይሆን መጨረሻቸዉን እየተጠባበኩ ነዉ::» **ይላል የጨለማዉ ገዥ አታላዩ በሰዉ ጎሊና በመንገሥ የዐመጻና የክህደት ስራ የሚያሰራዉ ሸዋጁ መንፈስ ዲያብሎስ ከጭፍሮቹ ጋር በመሆን::**

## ምእራፍ አራት

« አንዳንድ ሌት ተቀን በመንፈሳዊ አገልግሎትና አምልኮ የሚመላለሱ አገልጋዮችና ምእመናን እኔን የጨለማዉ ገዥ በሚያስቆጣ ተግባርና ንግግር ዉስጥ በመግባት ጥያቄያቸዉን ለተለያዩ አካላት አቀረቡ። ይኸዉም «እኛ አገልጋዮችና ምእመናን በሕገ መንግስቱ ጣልቃ እንዳትገቡ ብላችሁ በተደጋጋሚ ማስጠንቀቂያ መስጠታችሁና እናንተም በመንፈሳዊ አገልግሎትና አምልኮ ዉስጥ ጣልቃ እንደማትገቡ ገልጻችሁ ነበር። ምንም እንኳን በሕገ መንግስቱ የሰፈረዉ ለደንቡና ለማስመሰል እንጂ ተግባራዊ እንደማይሆን ብናዉቅም አሁን የሕግ ጥሰቱ ከልክ በማለፉና ሊሆን የማይችለዉ ሲሆንና ሲደረግ በማየታችን ነዉ የፈቀደዉ ይምጣ ብለን ወደ እናንተ ቅሬታችንን ለማሰማት የመጣነዉ።

በዝርዝር ለማቅረብ እናንተ በግልጽና በተዘዋዋሪ መንገድ በሥጋዊ ወንበር ላይ የተቀመጣችሁት የሥጋ ፈቃዳችሁን ለመፈጸምና ለማስፈጸም፤ ዝሙት፣ ጣዖትና ባዕድ አምልኮ፣ ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት፣ ዘረኝነት ፣ ጎጠኝነት ፣ ዘፈን ፣ ዳንኪራ ለማስፋፋት፤ የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከመገንጠል ድረስ ለማስጠበቅ፤ ስግብግብነትን፣ ራስ ወዳድነትን ፣ አድሎን ፣ በደልን ፣ ጥላቻን፣ በቀልን፣ ጭከናን፣ ግፍን፣ የመሳሰሉትን በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ የዲያብሎስ ፍሬዎችን ለማፍራትና ተግባራዊነቱንም ለማፋጠን ሙሉ ዴሞክራሲ ለመስጠት መሆኑ እየታወቀ፤ እኛን የተወሰን አገልጋዮችንንና ምእመናንን የሚወክሉ ተጠሪዎቻችንንና አለቆቻችንን በራሳቸዉ አንደበት « አብዛኛዎቻችን ከላይ የተገለጹትን ተግባራት ለማስፈጸም የተሰለፍንና ቀሪዎቻችንም ደግሞ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፈጻሚዎችንንና አስፈጻሚዎችን የምንደግፍ ነን።» በማለት መግለጫ እንዲሰጡ ማስደረጋችሁና ያለዉ እዉነታ ደግሞ ተቃራኒ መሆኑንን እያወቃችሁ ማስተባበያ መስጠት አለመቻላችሁ ቅር አስኝቶን ነዉ ወደ እናንተ ሥጋዊና መንፈሳዊ መሪዎች የመጣነዉ።» በማለት ቅሬታቸዉን አሰምተዋል።

በመጀመሪያ ምላሽ የሰጡት በሥጋዊ ወንበር ላይ ያሉት መሪዎችና ባለስልጣናት ሲሆኑ፤ ይኸዉም « በእርግጥ ሕገ መንግስታችን የሕዝቦችን ነጻነት ያወጀ፤ የብሔር

ብሔረሰቦችን መብት የሚያስከብር፤ ቋንቋቸዉን፣ ባህላቸዉን፣ አምልኮታቸዉን በፈለጉት መልኩ እንዲፈጽሙ፤ ከፈለጉም ከፌደራል መንግስቱ ራሳቸውን በመገንጠል ነጻ መንግስትን መመስረት እንደሚችሉና ከፈለጉም በነጻ መንግስታቸዉ ዉስጥ ብሔራዊ ሃይማኖት ሊመሰርቱ እንደሚችሉ፤ የራሳቸው ሉዐላዊነት መንግስት መገለጫ የሆነዉ ሰንደቅ ዓላማቸዉን በክልላዊ መንግስታቸዉ ከፍ አድርገዉ እንዲያዉለበልቡ፣ ባጠቃላይ የብሔር ብሔረሰቦች ለዘመናት በጭቆና የነበሩበትን ስርዐት አስወግደን ስር ነቀል ለዉጥና ነጻነት ያጎናጸፍናቸዉ መሆኑ ይታወቃል።

እዚህ ላይ  በደንብ መታወቅ ያለበት ሕገ መንግስቱ ሙሉ ነጻነትን ይሰጣል እንጂ በግድ ዘሙቱ፣ አመንዝሩ ፣ ጣዖትና ባዕድ አምልኮ ፈጽሙ፣ ዝፈኑ፣ ጨፍሩ፣ ዘረኛ ጎጠኛ ሁኑ፣ ዐመጻና ክህደት ፈጽሙ፣ .. ወዘተ የማይልና እንደ ታላቁ መሪያችን የጨለማዉ ገዥ ማንንም አስገድደን አናስፈጽምም። አንዳንዴ የበቀልና የግፍ እርምጃ የምንወስደዉም ያጎናጸፍናቸዉን ዴሞክራሲ መብት «አንጠቀምም፤ ኀሊናችንን አንሸጥም፤ ለኀሊናችን ነዉ የምናድረዉ፤ ..ወዘተ» በማለታቸዉ ነዉ እንጂ እንደኛና መሰሎቻችን በየጊዜዉ አቋማቸዉን ቢገለባብጡና «አድርጉ » የተባለዉን ቢያደርጉ፤ «አታድርጉ» የተባለዉን ባያደርጉ ማንንም ቢሆን አናስርም፤ አንገልም፤ አናሳድድም፤ አንወነጅልም፤ ሀብትና ንብረቱን አናዘርፍም፤ አንወስድም ።

ታዲያ አሁንም እናንተን እንወክላለን ያሉ አለቆቻችሁ ነጻ ዴሞክራሲ መብታቸዉን ተጠቅመዉ ነዉ እንጂ፤ ማንም «በሉ» ብሎ ሳያስገድዳቸዉ ኀሊናቸዉን የማገለባበጥና የመሸጥ መብታቸዉንና ነጻነታቸዉን ተጠቅመዉ ነዉ «እኛ አብዛኛዎቻችን የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊ ነን» ያሉት እንጂ፤ እኛ አስገድደን ወይንም አዘናቸዉ አይደለም። ለዚህም ከፈለጋችሁ የእናንተ አምላክ ወይንም የኛ አምላክ የጨለማዉ ገዥ ሊመሰክር ይችላል። ስለዚህ በዴሞክራሲ መብታቸዉንና ነጻነታቸዉን ተጠቅመዉ የፈጸሙትን የምትተቹና የምትቃወሙ ከሆነ ይልቁኑ እናንተ ናችሁ ሕገ መንግስቱን የጣሳችሁት እንጂ እኛ አይደለንም።

እንደ እዉነቱ ከሆነ ደግሞ እኛ በጥርጣሬና በዐይነ ቁራኛ  የምናያችሁ ስለነበረ፤ ይህን መግለጫችሁን ስንሰማ በመጀመሪያ ደረጃ የገመገምነዉ የኛን የጨለማዉ ጌታንና የእናንተንም ጌታ የሚያገለግሉ ዉዶቻችንን ሲሆን፤ እነሱ ግን «ወደ ምትፈልጉት አቅጣጫ ለመምራትና ለእናንተም ጌታ አገልጋይ እንዲሆኑ የተደረገ ታላቅ መስዋዕትነት ስለሆነ ልንሸለምና ልንመሰገን ሲገባ መገምገማችን ተገቢ አይደለም፡፡» በማለት ቅሬታ ያቀረቡብን ቢሆንም፤ «እኛ የገመገምናችሁ በአንደበታችሁ ብቻ በመናገር በተግባር ባለመፈጸሙና የሽወዳና የሽንገላ ንግግር ስለመሰለን ነዉ እንጂ እኛም ያልጠበቅነዉ ሲሳይ ነዉ» ብለን አጽናንተናቸዋል፡፡

እንዲሁም « ምንም እንኳ ለጊዜዉ ከእኛ ጋር ህብረትና አንድነቱ የጠበቀ መሆኑን በመገለጹ ያስደሰተን ቢሆንም፤ በአብዮታዊ ዴሞክራሲና በአምስቱ ዓመት  እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዉስጥ የበለጠ ተሳታፊ ሆነዉ እንዲያገለግሉና ብሔር ብሔረሰቦችን እንዲያነቁ አንድታደርጉ፤ አንዳንድ ጥሩ ጅማሮች በማሳየታችሁ ተደስተናል፡፡ ይኸዉም «ብሔር ብሔረሰቦች በራሳቸዉ አፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ባህል፣ አምልኮና ፊደል ሊማሩ፣ ሊገለገሉ ይገባል» ብላችሁ ይህን የነፍጠኞችንና የትምክህተኞችን ፊደል የሆነዉን የአማርኛ ፊደል አስወግዳችሁ በላቲን ፊደል መጻሕፍትንና ጽሑፎችን አዘጋጅታችሁ የላቲኑን ፊደል በደንብ ለሚያነበዉ በገጠር ላለዉ ገበሬና አርብቶ አደር ማቅረባችሁና የአማርኛ ፊደል ለማንበብ ለሚቸግረዉ ለተማረ ክፍል ማቅረባችሁ አርቆ አሳቢነታችሁንና አስተዋይ መሆናችሁን ያስመሰክራል፡፡

ከተወሰነ ዓመት ወዲህ ተመሳስለህ ኑር ፖሊሲን ተግባራዊ ማድረግ የጀመራችሁና የብሔር ብሔረሰቦች መብትን ነጻነት እስከ መገንጠል ድረስ ያለዉን ሕገ መንግስታችንን በደንብ መጠበቅና ማስጠበቅ ስለጀመራችሁ ያ የማይጠቅማችሁን ግትርነትና ቆራጥነት ከራሳችሁ ማስወገዳችሁ ጥሩ ጅማሮ መሆኑን  እንገልጽላችኋለን፡፡ በቀጣይ ደግሞ በየብሔራዊ ክልላቱ መንግስታት በሰማኒያዉም ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋና በላቲንና በአረብኛ ፊደላቸዉ ድጓዉን፣ አቋቋሙን፣ ሰዐታቱን፣ ቅዳሴዉን  ኪዳኑን፣ ቅኔዉን፣ እንደምታቀርቡና እንደምታጽፉ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ እንዲሁም የብሔር ብሔረሰቡን ባህልና አምልኮ በጠበቀ

መልኩ በየወንዛወንዙ፣ በየጥንቆላዉ፣ በየዛፉ ቦታ ጉን ለጉን ማስፈጸም ይጠበቅባችኋል፡፡ በኛና በጨለማዉ ገዥ ዘንድ የተሸራረፈ ዴሞክራሲና ነጻነት ዋጋ የለዉም፡፡

በዚሁ አጋጣሚ « እኛ ለእዉነተኛዉ መንግስታችንና ለፀሐዩ ንጉሣችን ማንኛዉንም መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጆዎች ነን፡፡ ለህዳሴዉ ግድብ በመስሪያ ቤት ያዋጣነዉ ገንዘብ ስለማይበቃ በተጨማሪ በማኅበራችን ስም የአንደ ወር ደሞዛችንን ከአራት መቶ ሺህ ብር በላይና እንዲሁም ከአገልግሎታችን የተትረፈረፈዉን ገንዘብ ከሁለት መቶ ሺህ ብር በላይ ቦንድ እንገዛበታለን፡፡» በማለት በቴሌቭዥን፣ በሬድዮን ፣ በሕትመት ዉጤቶች ላይ በግልጽ ስላስነገራችሁ አድናቆታችንን እንገልጽላችኋለን፡፡ ለወደፊትም ለወንበራችን አደገኛ የሚሆኑ አካላት ቢነሱ ማንኛዉንም መሳሪያ በመጠቀም ደጀን እንደምትሆኑን እንተማመንባችኋለን፡፡» በማለት ለሁለት ጌታዎች ለሚያገለገሉ ዉዶቻችን ከመናገር ዉጭ አሁን ላቀረባችሁት ቅሬታ ግን ማንንም አስገድደን ሆነ መሳሪያ ደግነንበት መግለጫ አላሰጠንም፡፡» በማለት ምላሽ ሰተዋል፡፡

በመቀጠል በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡት መሪዎችና ኃላፊዎች « ልጆቻችን! ነገሮች ሳይገባችሁና ሳትረዱ የህጻንነት ስሜታችሁን በነዚህ በታላላቅ መሪዎችና ባለስልጣናት ፊት እንዲሁም በእኛ አባቶቻችሁ ፊት ማቅረባችሁ አሳዛኝ ቢሆንም እዉነቱን በሥጋዊ ወንበር ላይ ያሉት አባቶቻችን፣ እናቶቻችን፣ ወንድሞቻችን፣ እህቶቻችን ስለመለሱላችሁ እኛ ብዙም የምንላችሁ ነገር የለም፡፡

ይሁንና ለአስራ ዘጠኝ ዓመት ያህል እነሱንም እኛንም እንዴት አደርጋችሁ ስታስቸግሩን እንደነበረ ዓለም ያዉቀዋል፡፡ ዋናዉ ግን በድርጊታችሁ ተጸጽታችሁ ትክክለኛ መሪያችንንና ድርጅታችንን በአባልነት ሆነ በደጋፊነት ከጎኑ በመሰለፋችሁ እንዲሁም የድርጅቱን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ቆርጣችሁ በመነሳት ሳትፈሩና ሳታፍሩ በሚዲያ መግለጫ መስጠታችሁ ያለፈዉን ኃጢአታችሁን የሚያስደመስስላችሁና እኛም ቅሬታችንን የምናነሳ መሆኑን እናሳዉቃችኋለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በዚሁ አቋማችሁ ከጸናችሁ መንግስታችን ሆነ እኛ ዋና የሃይማኖት መሪዎች የያዝንባችሁን የዓመታት ቂምና በቀል ሁሉ እርግፍ አድረገን የምንተዉ መሆኑነ በዚሁ አጋጣሚ በግልጽ እንነግራችኋለን፡፡

እናንተ ቅሬታ ለማሰማት የመጣችሁ ዞሮ ዞሮ ከማኅበራችሁ አቋም ስለማትወጡ እንደእነሱ አድርገን የነገርናችሁ ለዚህ ነዉ፡፡ « እኛ በእነሱ አቋም አንመራም፤ አንሄድም » ብትሉ ደግሞ የሚደርስባችሁን ሕገ መንግስቱ በደንብ ስላስቀመጠዉ ወይን በክህደት ያለበለዚያ በሁከት መፍጠርና በሽብርተኛነት ተወንጅላችሁ ወደሚመለከተዉ ቦታ እንደምትገቡ ልታዉቁ ይገባችኋል፡፡ ስለዚህ እናንተም ወደ ልባችሁ ተመልሳችሁ «ተመሳስሎ ኑሮ» የሚለዉን መርህ መምረጥ ይገባችኋል እንጂ ምን ብትብገነገኑ፣ ብትቆጡ፣ ብትንጫጩ፣ ብትናደዱ «ተልባ ቢንጫጫ በአንድ ሙቀጫ » የሚባለዉን ንግግር ሳታዉቁት አይቀርምና አንዳች የምታመጡት ነገር የለም፡፡ ይኸንንም በያዝነዉ መስቀል እናረጋግጥላችኋለን፡፡» በማለት ምንም የማያወላዳ ምላሽ ሰተዋቸዋል፡፡

ቅሬታ አቅራቢዎቹም «እንግዲህ ተመሳስሎ ኑሮ ትርጉሙ ስላልገባን መዝገበ ቃላት ላይ እንመለከታለን፡፡» በማለት ተስፋ አስቆራጭ መልስ ሰምተዉ የተመለሱ ሲሆን፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ በምላሹ ስለተደሰትኩና ቅሬታ አቅራቢዎቹም ከመጀመሪያዉ ቅሬታ ዉጭ ብዙ እላፊ ንግግር ስላላደረጉ ቀጣይ እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ አላሳሰብኩም፡፡» **ይላል፤ ከትልቅ እስከ ትንሽ ከተመረጡ እስከ ዐመጸኞች ድረስ ያሉትን የሚፈታተንና የሚገነድሰዉ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ፡፡**

# ምእራፍ አምስት

« ለፓለቲካ መጠቀሚያ በስማቸዉ የሚነገድባቸዉ አንዳንድ ቆራጥ ሴቶች ቅሬታቸዉን ለሴቶች ጉዳይ ጽ/ቤት አቅርበዋል። ይኸዉም «እኛ ሴቶች ስንፈጠር እንደማንኛዉም ወንድ ሕያዊት ልባዊት ነባቢት ነፍስ እንዲኖረን ተደርጎ በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠርን፤ አንዳች ከወንዶች ጋር የመበላለጥ ሆነ የመተናነስ ተፈጥሮ የሌለን ነን። እናንተ ግን ለፓለቲካችሁ ይመቻችሁ ዘንድ በመደብ እየከፋፈላችሁን በወንድሞቻችን፣ በባለቤቶቻችን፣ በአባቶቻችን ላይ ጥላቻ የምታሳድሩብን ለምንድነዉ? ለመሆኑ በተፈጥሮ «ሴቶች ከወንዶች ያነሱ ናቸዉ።» የሚል ግለሰብ ሆነ አካል አለ ወይ? እናንተ ግን የማን መልእክተኞች እንደሆናችሁ ባናዉቅም እኛን ከወንዶች እያሳነሳችሁን « ከወንዶች እኩል እናደርጋችኋለን» ትላላችሁ።

ወይስ እንደ የግብር አባታችሁና መምህራችሁ ጾታችንን ወደ ወንድነት ለመለወጥ ነዉ ፍላጎታችሁ? ወይስ በተፈጥሮ ያልተፈቀደልንን እኛ ማስረገዝ ወንዶች ደግሞ ማርገዝ እንዲችሉ ለማድረግ ነዉ በስማችን የምትነግዱት? ወይስ «ቀድሳችሁ እንድታቆርቡና ጳጳስ እንድትሆኑ እናደርጋችኋለን» ልትሉን ይሆን? ወይስ «በሃይማኖት አባቶች ተጽህኖ ተደርጎባችኋልና ሃይማኖት የሚባል ነገር አያስፈልጋችሁም» ልትሉን ፈልጋችሁ ይሆን? ወይስ «እኩልነትን ያረጋገጠላችሁ እናንተ እንደምትሉት እግዚአብሔር ሳይሆን መንግስት ነዉና ኀሊናችሁን ለመሸጥ እንደ ቦይ ዉኃ ለመወሰድ ተዘጋጁ» ልትሉን ይሆን? ወይስ «ሌሎች ፓርቲዎች የሴቶችን እኩልነት አያምኑምና ነጻ ያወጣችሁን ኢህአዴግን ድርጅት ምረጡ» ለማለት ፈልጋችሁ ይሆን? ወይስ የመደብ ልዩነት በመፍጠር የስልጣን ጥማታችሁን ለመወጣትና የተለየ ጥቅም ለማግኘት ይሆን? ወይስ «ከዚህ በፊት በነጻነት ሲጃራ በየቦታዉ ሲያጨሱ የነበሩት ወንዶች ብቻ ነበሩ አሁን ግን ዴሞክራሲ መብታችሁን ተጠቅማችሁ በማንኛዉም ቦታ ማቡነን ትችላላችሁ» ለማለት ፈልጋችሁ ይሆን?

የእናንተ አካሄድ አሳፋሪ ቢሆንም እኛ የአዳምና ሔዋን ዘሮች የአንዱ እግዚአብሔር ፍጥረቶችና ልጆቹ ነን። ወንድና ሴት የሚል ልዩነት ያለዉ በተገለጽንበት ሥጋችን እንጂ

በነፍሳችን አንዳች የጾታ ልዩነት የሌለን ሕያዋን ፍጥረት ነን። የእግዚአብሔር ልጆች ያስባለችን የነፍሳችን ባሕርይ ነዉ እንጂ ይህ የጾታ ልዩነት የፈጠረብን ሟች፣ ፈራሽ፣ በስባሽ ሥጋችን አይደለም። በዚህች ምድር ቆይታችን ዉስጥ ወንድ የራሱ ድርሻ ብቻ የሆነ ስራ አለዉ። ሴትም የራሷ ብቻ የሆነ የስራ ድርሻ አላት። ከዚያ ዉጭ ግን በመማር፣ በማስተማር፣ በማሰብ፣ በመናገር፣ በመስራት፣ በማሰራት፣ በኃላፊነት፣ በአስተዳዳሪነት ፣ በመሪነት ፣ ከወንዱ እኩል የሆን ነን።

አንዳች በሴትነት ጾታችን «ለዚህ ኃላፊነትና ስራ ብቁ ልትሆኑ አትችሉም» ያማንባል፤ ተስፋችንም ሰማያዊ የሆነ የቅዱሳን መላእክት አኗኗር የምንናፍቅና የምንጠባበቅ ነን እንጂ እናንተ ኅሊናችንን መርዛችሁና አጥባችሁ እንደምታስቡት አይደለንም። እናንተ ግን ለፓለቲካችሁና ለስልጣናችሁ፣ ለጥቅማችሁ ስትሉ «ለፍልፉ» የምትባሉትን የምትለፈልፉ፤ «ቀባጥሩ» የምትባሉትን የምትቀባጥሩ፤ ለኅሊናችሁ ያልቆማችሁ፣ ተስፋችሁን ምድራዊ አድርጋችሁ የምትመላለሱ፣ ይህን ቅርፊት ሥጋችሁን የምታመልኩና የምታስመልኩ ናችሁ።» በማለት አሳባቸዉንና አቋማቸዉን አቅርበዋል።

የሴቶች ጉዳይ ኃላፊዎችም «እኛ የምንሰማዉ በሕገ መንግስታችን እኩልነታችንን ያረጋገጠልን መንግስታችንን ነዉ እንጂ እናንተ ጤንነታችሁ በሚያጠራጥር መልክ የምታናገሩትን አይደለም። ምናባዊ አስተሳሰባችሁ በእኛ በአብዮታዊ ዴሞክራሲ በምናምን ሴቶች ዘንድ ተቀባይነትና ቦታ የለዉም። ንግግራችሁ ሁሉ እኩልነታችሁን ያረጋገጠላችሁንና ያጎናጸፋችሁን ዴሞክራት መንግስታችንን ለመቃወም ፣ ለማጣጣል፣ እንዲሁም ለማንቋሸሽ አስባችሁ መሆኑንና የአንዳንድ የፓለቲካ ድርጅቶች ቅጥረኞች መሆናችሁን ይገልጻል። እኛ ግን ከአህዛብ መንግስታችን ጎን በመሰለፍ የሴቶች እኩልነትን እስከመጨረሻዉ እናረጋግጣለን።» በማለት ምላሽ የሰጡ ስለሆነ እኔም የጨለማዉ ገዥ በምላሻቸዉ ስለተደሰትኩ ለበለጠ ለታላቅ ሹመት አብቅቻቸዋለሁ።

በማግስቱ ደግሞ አንዳንድ በዝሙት የሚተዳደሩ ሴተኛ አዳሪዎች በሴቶች ጉዳይ ዘርፈ የሴተኛ አዳሪዎች ችግር አስወጋጅ ዳያሬክተር ለሆኑት ጉዳያቸዉን አቅርበዋል። ይኸዉም «እናንተ ለሴቶች ነዉ የቆምነዉ፤ ለእኩልነታችሁና ለዴሞክራሲ መብታችሁ እንታገላለን»

ትላላችሁ:: ነገር ግን አንድ ቀን የኛ ሕይወት አሳስቧችሁ አያዉቅም:: እናንተ ለፖለቲካችሁ ብቻ ሌት ተቀን የምትሯሯጡ ናችሁ እንጂ «እነዚህ እህቶቻችን በምድራዊ ኑሮዋቸዉም በሚያጎሳቁልና በሚያዋርድ ሕይወት ዉስጥ ይኖራሉ:: በእግዚአብሔር ዘንድም የኃጢአት ተግባር እየፈጸሙ ነዉ :: ስለዚህ ከዚህ ሕይወት ልናላቅቃቸዉና ራሳቸዉን የሚረዱበትን ስራ ልንፈጥርላቸዉ ይገባል::» ብላችሁ አንድ ቀን እንኳ ለሥጋችን ሆነ ለነፍሳችን አስባችሁልን አታዉቁም::

ይልቁኑ እግዚአብሔርን በሚያስቆጣ ተግባር የተሰለፈዉና ለኛም ሕይወት አንዳች ስሜት የሌለዉ መንግስታችሁ በዝሙት ሕይወታችን እንድንገፋበት የሚያበረታታ ማስታወቂያዎችን በቴሌቭዥንና በሬዲዮን እንዲሁም በሕትመት ዉጤቶች ላይ እያወጣ ሲያስፈልገዉ « ሕይወት የሆነዉን ኮንደም ተጠቀሙ ኤድስ የሚባል ነገር አይደርስባችሁም» ይላል:: ሲያስፈልገዉ ደግሞ «የደስታና የእርካታ ምንጭ የሆነዉን ሰንሴሽን ተጠቀሙ::» እያለ በብሔር ብሔረሰቦች ዘፈንና ዳንኪራ እያጀበ ትዉልዱን ለዝሙት እያነሳሳና እያገፋፋ እንዲሁም እያደፋፈረ ነዉ:: ምንም የማያዉቁት ሴቶችና ወንዶች ቢያንስ የእግዚአብሔር ቁጣ የሆነዉን ኤድስ በሽታ እንኳ እንዳይፈሩ « ኮንደም ኤድስን የመከላከል ብቃት አለዉና ዝሙትን አትፍሩ፤ ድፈሩ::» እያለ ሌት ተቀን የሚለፍፍ ነዉ::

የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ ደግም የሃይማኖት አባቶችና የእምነት ተቋማት ይህ በግልጽ የዲያብሎስ ስራ የሆነዉን የርኩሰት ማስታወቂያ ሊያስቆሙና ሊያወግዙ ሲገባ፤ የርኩሰት ስራ አስፈጻሚ ከሆነዉ መንግስት ጋር እጅና ጓንት በመሆን በዐመጻዉ ስራ ተሰልፈዋል:: እርዳታንና ገንዘብን ለማግኘት ሲሉ በአጭሩ «አታመንዝር፤ አትዘሙት» በሚለዉ የእግዚአብሔር ሕግ መፍትሔ ሊያገኝ የሚችለዉን ችግርና በሽተኞቹንም « ንስሐ ግቡ፤ ቅዱስ ቁርባንን ተቀበሉ፤ ጠበሉንና እምነቱን ተጠቀሙ፤ ራሳችሁን ጠብቁ፤» በማለት መምከርና ማጽናናት ሲገባቸዉ፤ እንዲሁም ሕዝቡንም «በኤድስ የተያዘዉን ሆነ በሌላ በሽታ የተያዘዉን ሰዉ አድሎና መገለል አታድርጉ፤ ወገኖቻችሁ ናቸዉና እርዷቸዉ፤ ተንከባከቧቸዉ፤ አፍቅሯቸዉ::» በማለት ሊያስተምሩ ሲገባ፤ በጨለማዉ ገዥ በሚመራዉ

ሥርዓት ዉስጥ በመመላለስ  አብረዉ ከመንግስት ጋር በመሰለፍ እንድ ትልቅ ስራ «ኤድስን እንከላከል፣ የአባላዘር በሽታ እንከላከል» እያሉ ወሬ በማራገብ በእግዚአብሔር ቁጣ ላይ ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ የሚያደርጉና  በተዝዋዋሪ ዝሙት የሚስፋፋበትን መንገድ የሚደግፉና የሚያበረታቱ እንዲሁም ግብረ ሰዶምነትን ጭምር በይሉኝታና በጥቅም ኀሊናቸዉን አሳዉረዉ ማዉገዝ ያልቻሉ ለስልጣናቸዉና ለሥጋዊ ክብራቸዉ የቆሙ ናቸዉ።

እኛ ግን ከምድሩም ሳይደላን ከሰማዩም ሳንሆን ለሥጋችንና ለነፍሳችን የሚያስብልን ግለሰብና አካል አተን በአየር ላይ ተንሳፈን የቀረን ምስኪኖች ነን። እናንተ በእዉነት ለሴቶች የምታስቡ ቢሆን ኖሮ የፖለቲካ ወሬያችሁን ትታችሁ ከዚህ ሰቆቃ ሕይወት የምንገላገልበትን ኑሮ ታመቻቹልን ነበር። መንግስታችሁ ደግሞ «የዴሞክራሲ መብታችሁን ስላጎናጸፍናችሁ ማንኛዉንም መብታችሁን በመጠቀም ማመንዘርና መዘሞት ቀርቶ በግልጽ የሥራ መተዳደሪያና የገቢ ማግኛ ልታደርጉት ትችላላችሁ።» ብሎ የሕግ ሽፋን ስለሰጠን ሳንፈራና ሳንሸማቀቅ በግልጽ እንደ ስራ መስክ ቆጥረነዉ ገላችንን እንሸጣለን። በሕግ እንኳ ብንገደብ ሌሎች አማራጭ ስራዎችን እንፈልግና ሕይወታችንን እንለዉጥ ነበር። እናንተም ሆናችሁ መንግስታችሁ ሌት ተቀን የምትሯሯጡት የሰዎችን ኀሊና አደንዝዛችሁ የራሳችሁን መሰሪ ዓለማ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ነዉ እንጂ የሰዉ ሕይወት አንዳች የሚያሳስባችሁ አይደለም። ከዚያም አልፎ አንዳንዶች ባለስልጣናትና ካድሬዎች ዉሏቸዉንና አዳራቸዉን ከኛጋ እያደረጉ ዝሙት ስራችንን ያበረታታሉ፤ ይደግፋሉ።» በማለት በምሬት ብሶታቸዉን አቅርበዋል።

ዲያሬክተሯም ሐፍረትና ኀዘን ተሰምቷቸዉ ወደ ልባቸዉ በመመለስ «ለካስ መንግስታችን ሕዝቡን ብቻ ሳይሆን እኛን ካድሬዎቹን ጭምር አደንዝዞናል። ከዚህ በኋላ እነዚህን እህቶቻችንን ከዚህ ጎስቋላና መከራ ሕይወት ልናወጣቸዉና የስሜት ጉዳታቸዉንም ልንክሳቸዉ ይገባል። በየቦታዉ የወደቁ ወገኖቻችን የሆኑትን አባቶቻችንን እናቶቻችንን ወንድምና እህቶቻችንን ልናስባቸዉ ይገባል እንጂ ነጋ ጠባ የፖለቲካ ስራ መስራት የለብንም።» በማለት ለኀሊናቸዉ በመናገር፤« እህቶቼ ንግግራችሁ ዐይኔን ከፍቶልኛል ለወደፊት ምን ማድረግ እንዳለብኝ አስተምራችሁኛል። እስከአሁን ድረስ ሴቶች እያልን በስማችሁ በመነገዳችን ይቅርታ አድርጉልኝ። ከዚህ ሕይወት የምትለዩበትን መንገድ

እናመቻቻለን፡፡» በማለት የሚያጽናና መልስ የሰጡ ሲሆን፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ ለጎሊናቸዉ የነገሩትንም እዛዉ ጎሊናቸዉ ጋር ሆኜ በደንብ አዳምጫለሁና ከዚያ በተጨማሪ መልካም ምላሽ በመስጠታቸዉና ለእንደራሴዎቼ ዘብ ሆነዉ የሚያሳፍርና የሚያዋርድ መልስ ባለመስጠታቸዉ ተናድጄ ስለነበር በታማኝ ካድሬዎቼ አማካይነት ከበላይ ላሉት ባለስልጣናት ሪፓርት አስደርጌ ከወንበራቸዉ እንዲሻሩና ታማኝ ዉዶቼ እንዲመደቡ አስደርጌያለሁ፡፡

አንዳንድ አገርና ወገን ወዳድ እንዲሁም የዓለም ምሁራን አንድ ላይ ሆነዉ ለሚመለከተዉ የተባበሩት መንግስታት ተወካይ ቅሬታቸዉን አቀረቡ፡፡ ይኸዉም «የእኛ ፍላጎትና ምኞት ቴክኖሎጂዉ፣ እዉቀቱ፣ ጥበቡ፣ ፍልስፍናዉ ሁሉ የአዳምና የሔዋን ዘሮችን የሚጠቅም፤ ከጉስቁልና ኑሮና ሕይወት የሚለይ፤ ረሀብ፣ ችግር፣ ስቃይ፣ ህመም፣ ድንቁርና፣ እርዛት ባጠቃላይ ሰዎች ሁሉ እደሰዉነታቸዉ ብቻ ተከብረዉ፣ ተፈቅረዉ፣ በልተዉ፣ ጠጥተዉ፣ ተምረዉ፣ መጠለያና መጠጊያ አግኝተዉ፣ እንዲኖሩ ነዉ እንጂ ለብዙ ሰዎች ለችግር ማቃለያና ለመርጃ የሚጠቅመዉ በቢሊዮንና በትሪሊዮን የሚቆጠር ብር ፈሰስ እየተደረገ ለተለያዩ ጦር መሳሪያና ለሕዋ ምርምር መደረጉ አግባብነት የሌለዉና ለእነዚህ የሚወጣዉ ገንዘብ ለልማት ስራ ቢዉል ኖሮ በምድራችን ረሀብ፣ ችግር፣ ሰቆቃ የሚባለዉ ቀርቶ ስማቸዉ እንኳ አይታወቅም ነበር፡፡

የየአገራቱ መሪዎች ሆኑ ባለስልጣናት ለክብራቸዉ፣ ለጥቅማቸዉ፣ ለዝናቸዉ ፣ ለታላቅነታቸዉ፣ ለስልጣናቸዉ የቆሙ አምባገነን ናቸዉ፡፡ የወገናቸዉ የአዳም ዘር ሰቆቃና ችግር አንዳች አይሰማቸዉም፡፡ እነሱ ከገነኑ፣ ከተመሰገኑ፣ ከበሉ፣ ከጠጡ፣ ከተዝናኑ፣ ከጨፈሩ፣ ከዘፈኑ፣ ከተመለኩ፣ ሁሉ በእነሱ ቁጥጥር ዉስጥ ከሆነላቸዉ ለሌላዉ ወገናቸዉ አንዳች ስሜት የሌላቸዉ ናቸዉ፡፡

ከዚያም አልፈዉ በእብሪትና በትዕቢት «ከእኛ በላይ ማንም የለም፣ ቀና ብትሉ ጣርና ጣሪያ ነዉ» እያሉ የሚደነፉ፤ ሕዝብን የሚያስጨንቁና ግፍ የሚፈጽሙ ናቸዉ፡፡ የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ ደግሞ ወደ ተግባር የማይለዉጡትን ለመሸንገያና ጎሊናን ለማሽጫ ለመጠቀም « እኛ ለሰላም፣ ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲ፣ ለእኩልነት፣ ለነጻነት፣ ለብልጽግና የቆምን ነን» ይላሉ፤ ተግባራቸዉ ግን ጦረኝነትና ግፈኝነት፣ አድሎና በደል ነዉ፡፡

ስለዚህ አላስፈላጊ ለሆነዉ የተለያዩ ጦር መሳሪያና ለተለያዩ ፕላኔቶች ግኝት የሚወጣዉ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ለሕዝብ አገልግሎት ለትምህርት፣ ለጤና ፣ ለመኖሪያ ቤት፣ ለመስኖ፣ ለትራንስፖርት፣ ለመብራት፣ ለስልክ.. ወዘተ ለመሳሰሉት አገልግሎት ላይ እንዲዉል እንጠይቃለን::» በማለት አስተያየታቸዉንና ጥያቄያቸዉን አቅርበዋል::

ኢትዮጵያዊዉ ምሁር ተጨማሪ አስተያየት አለኝ ብለዉ፤« እኛ የሰዉ ዘሮች የፈጠረን አምላክ ረስተን እኛ ሳናስተዉለዉ ለጨለማዉ ገዥ ለዲያብሎስ ባሪያዎች ሆነን ሌት ተቀን ፈቃዱ በሚፈጸምበት የጨለማ ስርዐት ዉስጥ በመመላለሳችን ነዉ መንግስታት ሆኑ ባለስልጣናት እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበትን መልካም ተግባር መፈጸምና ማስፈጸም ተስኗቸዉ ሕዝቡን ለጦርነት የሚያነሳሱትና ሀብትና ንብረት በጥቂት ሰዎች ቁጥጥር ዉስጥ እንዲሆን አድርገዉ በረሀብና በችግር እየቀጡት ያለዉ::

ታዲያ የሕዝብ እንባ አንድ ቀን እንደ ጎርፍ ሆና እንዳይጠራርጋቸዉ እሰጋለሁ:: እንደኔ አስተያየት ለሁሉም መፍትሔ የሚሆነዉ በዲያብሎስ መንፈስ የሚመራ መንግስታት ሆኑ ባለስልጣናት በምንም መልኩ ኅሊናቸዉን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ሊያደርጉትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሊፈጽሙና ሊያስፈጽሙ ስለማይችሉ ይህ አሁን በዓለም ላይ የሚታየዉ የዲያብሎስ ስርዐት ሊወገድና በምድራዊ ሕይታችንም የምንጠቀምበት ለሰማያዊ ሕይወታችንም በእግዚአብሔር መንግስት ሕያዉ ሆነን የምንኖርበት ሰማያዊ ስርዐት ልንዘረጋና ከላይ የተገለጹትና መልካም ተግባራትን ልንፈጽም ይገባል:: ነገር ግን አሁንም «በዲያብሎስ ስርዐት እንመራ» ከተባለ ይህ ቅርፊት ሥጋዉን የሚያመልክና የሚያስመልክ እንዲሁም ተስፋዉን ምድራዊ ያደረገ ትዉልድ ከላይ የተገለጹትን መልካም ተግባሮች ለመተግበር እንደሚቸገር ለመግለጽ እወዳለሁ» በማለት አስተያየታቸዉንና ስጋታቸዉን ገልጸዋል::

የመንግስታቱም ተወካይ « በእርግጥ አስተሳሰባችሁና አስተያየታችሁ ጥሩ ቢሆንም ለዚህ ምላሽ መስጠት የሚችሉት አምስቱ ኃያላን አገራት የተባሉት አሜሪካ እንግሊዝ ፈረንሳይ ሩሲያና ቻይና ናቸዉ:: ዓለምን እንደፈለጉ እያሽከረከሩት ያሉት እነሱ ስለሆኑ አሁን ባለሁ ሁኔታ የሚሰማችሁና የሚቀበላችሁ ግለሰብ ሆነ አካል ያለ አይመስለኝም:: ምናልባት

ለወደፊት የአዳም ዘር ሁሉ (የዓለም ሕዝብ ሁሉ) ወገኔ አባቴ እናቴ ወንድሜ እህቴ ልጆቼ ናቸዉ የሚል ትዉልድ የሚፈጠርበት አገር ካለ ያኔ አሳባችሁና ጥያቄያችሁ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችላል እንጂ አሁን ይህን አሳብ ብታቀርቡ የእብድ አስተሳሰብ አድርገዉ ነዉ የሚቆጥሩት፡፡» በማለት ስለመለሱላቸዉ ጥያቄያቸዉ ዋጋ ቢስ ሆኖ ቀርቷል፡፡ እኔም የጨለማዉ ገዥ «ማን ጀግና ደፋር ነዉ ይህን መልካም ተግባር ሊፈጽምና ሰማያዊ ስርዐት ሊዘረጋ የሚችል!» በማለት ታብያለሁ፡፡» **ይላል የትዕቢት አባት ዲያብሎስ፡፡**

## ምእራፍ ስድስት

« በአገር ዉስጥ ያሉና ከአገር ዉጭ ያሉ አንዳንድ የተቃዋሚ ድርጅት ተወካዮች የአዲሲቷን ኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አነጋገሩ። ይኸዉም «የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር! ሕገ መንግስቱ የመደራጀት፣ አሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የመናገር፣ የመጽሐፍ፣ የመሰብሰን .. ወዘተ በሰጠን መብትና ነጻነት ተጠቅመን ለአገራችን ይጠቅማሉ ብለን የምናስባቸዉን ፖሊሲዎችና አስተሳሰቦች ስናራምድ በእርሶ በኩል የተለያየ ስያሜ ይሰጠናል። አንዳንዴም እኛን ለማጥፋትና ለመደምሰስ ይነሳሳሉ፤ በእብሪትና በትዕቢት ይደነፋሉ። ስለዚህ ምን አይነት ተቃዋሚ ድርጅቶች እንድንሆን ነዉ የሚፈልጉት?» በማለት ጥያቄ አቅርበዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩም ሲመልሱ «በመጀመሪያ የመንግስቴን ታላቅነት አምናችሁ የኔንም ዋና አዛዥነት ተቀብላችሁ አቋማችሁ ምን መሆን እንዳለበት እንድትመከሩ በመምጣታችሁ የአርቆ አስተዋይነታችሁንና ተመሳስሎ መኖር ፓሊሲ ለማራመድ ዝግጁ መሆናችሁን የሚያመላክት ታላቅ የእድገት መገለጫ ነዉ።

የኛ ተቃዋሚ ለመሆንና ከኛ ጋር አብሮ መጓዝ ከፈለጋችሁ በመጀመሪያ ደረጃ የዘወትር ጸሎታችሁ ማድረግ ያለባችሁ መመሪያችንን የብሔር ብሔረሰቦች የሚለዉን ልዩ የመጠመቂያ ስም ልትጠመቁና በንግግራችሁ ዉስጥ መጀመሪያ ላይ ሆነ መሀል እንዲሁም መጨረሻ ላይ እንደ አቡነ ዘበሰማያት መደጋገም ይጠበቅባችኋል። ከዚያ በማስከተል መንፈሳችሁ መንፈሳችን ስለሚሆን የተለያየ አቋም ልትይዙ አትችሉም። በማስከተል ደግሞ በወረቀቶች ላይ ያሉ ሁሉ «ተግባራዊ ይሁኑ » ብላችሁ አትከራከሩ።

እኛ በትግል እያለን «ለፍትህ፣ ለእኩልነት፣ ለነጻነት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለሰላም፣ ለእድገት፣ ለብልጽግና .. ወዘተ» እያልን ነበር ስንለፍፍ የነበረዉና ወደ ወንበር የመጣነዉ። «ከበሮ በሰዉ እጅ ያምር ሲይዙት ያደናግር» እንደሚባል ሁሉ፤ ያን የተነሳንበትን ዓላማ እርግፍ አድርገን «ከራስ በላይ ነፋስ» የሚላዉ የጨለማዉ ገዥ መሪያችን መመሪያ ተከትለን ለሰዎች ጎሊና የሚስማማዉንና ተቀባይነት ያለዉን በወረቀት ላይ ለማስመሰል ነዉ ያስቀመጥነዉ እንጂ ተግባራዊነቱ ላይ የምንመራበት መንፈስ ስለማይፈቅድልን ይኸዉ ከአገር

ክህደት ጀምሮ ኢሰብአዊ ተግባርና የከፋና የከረፋ አሳብ ፈጥረን ንጹህ ኅሊና ላለዉ ሰዉ የሚዘገንን ተግባር ፈጽመናል፡፡ ነገር ግን የሚመራን መንፈስ ስለሚደሰትበትና ፈቃዱ ስለሆነ እስከ አሁን ድረስ በአቋማችን ጸንተናል፡፡ ስለዚህ እናንተም ለአፋችሁ ዴሞክራሲ፣ ነጻነት ፣ ፍትህ፣ እኩልነት.. ወዘተ እያላችሁ ሃያ አራት ሰዐት ብትለፈልፉ ችግር የለዉም፡፡ የሽዋጁ መንፈስ መገለጫዉ ይኸዉ ነዉና፡፡

ሌላዉ ተቃዉሚችሁን ከልማታዊ መንግስታችሁ ጉን በመሰለፍ በምክር ቤት አባልነታችሁ በምታገኙት ክፍያና ጥቅማ ጥቅም ኑሮዋችሁን በመደጎምና የተለየ የከበሬታ ወንበር በመያዝ ሰላማዊ ተቃዉሞ ማድረግ ነዉ፡፡ ይህም «ተቃዋሚ» የሚለዉን ስያሜ በመያዝ ነገር ግን የይስሙላ ክርክር በመፍጠር በመጨረሻ ግን በኛ ዉሳኔ በመሸነፍና ወደ እኛ ትክክለኛ አስተሳሰብ መምጣታችሁን ለሕዝብ መግለጽና ዉስጥ ለዉስጥ የኛ ደጋፊ መሆን ይጠበቅባችኋል፡፡

በመጨረሻ ላሳሰባችሁ የምፈልገዉ እንደ አንዳንዶች ተቃዋሚ ዐይን ያወጣ ድጋፍና ለኛ ከኛ በላይ ጥብቅና መቆም በኛ ዘንድ ሞገስ ብታገኙበትም በሕዝቡ ዘንድ ስለሚያስገምተችሁና ስለሚያሳማችሁ አቋማችሁ ቢበዛ እንደአጋር ድርጅት ቢያንስ ደግሞ እንደ ተለጣፊ ድርጅቶች መሆን አለበት» በማለት መክረዋቸዋል፡፡ እኔም የጨለማዉ ገዥ በምክራቸዉ ስለተስማማሁ ተጨማሪ ማሳሰቢያ አልሰጠዋቸዉም፡፡ ተቀዋሚዎቹንም በኔ የጨለማዉ መንፈስ የሚመሩና የበለጠዉን ፈቃዴን የሚፈጽሙ  ከሆነ ወንበሩን አሳልፌ የማልሰጣቸዉ አንዳች ምክንያት የሌለ መሆኑን በኅሊናቸዉ አሳስቤያቸዋለሁ፡፡ አሳቤንና የእንደራሴዬን ምክር የመቀበል ያለመቀበል ምርጫዉ የእነሱ ስለሆነ ዴሞክራሲ መብታቸዉን እንዲጠቀሙ ሙሉ ነጻነት ሰጥቻቸዋለሁ፡፡ እስከ አሁን ድረስ በኔ ዘንድ ሞገስ ስላላገኙ ወደ ወንበር አላመጠዋቸዉም፡፡

አንዳንድ ኢትዮጵያዊነታቸዉን የካዱ ከተገንጣይ ቡድን ጋር አብረዉ የነበሩ ሰዎች ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪ ያላቸዉን አድናቆታቸዉንና ሙገሳቸዉን ገለጹ፡፡ ይኸዉም « እኛ በኢትዮጵያዊነታችን ላይ ክህደት የፈጸምን ቢቻለን ኖሮ ከመንግስቻችን ጉን በመሰለፍ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ልናጠፋ የነበርነዉን፤ እርሶ ታላቅ የእግዚአብሔር ሰዉ ስለሆኑ በወንጌል የተጻፈዉን «ጠላታችሁን ዉደዱ» የሚለዉን ቃል ተከትለዉና አክብረዉ ከካድሬዎቹ

ዉጭ ላሉት ለሌሎች ኢትዮጵያዉያን ዜጎች ያልተሰጠዉን የሁለተኛ ድግሪ የመማር እድል ስለሰጡንና እንዲሁም «በኢትዮጵያዊነታችሁ ካለማናችሁ፣ በክህደታችሁ ከጸናችሁ፣ አዲሲቷን ኢትዮጵያን በዘረኝነትና በጎጠኝነት ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሳችን ተባባሪ ከሆናችሁ፣ ከነፍጠኞቹና ከትምክተኞቹ መንጋጋ አዉጥተንላችሁ ነጻነቷን የተጎናጸፈችዉን እናት አገራችሁን ኤርትራን ነጻነቷን እስከ መጨረሻዉ ድረስ ከጠበቃችሁ፣ ሁሉም ኢትዮጵያዉያን ያላገኙትን የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመማር እድል እንሰጣችኋለን፤ በኢትዮጵያዊነታችሁ ክህደት በምታሳዩት ብቃት ደግሞ እስከ ፒችዲ ድረስ እናስተምራችኋለን።» በማለት ቃል ስለገቡልን ነዉ።

የአዲሲቷ ኢትዮጵያ መሪ ለዚህ አድናቆትና ሙገሳ ምላሽ ሲሰጡ « ዉድ የቁርጥ ቀን ልጆች! በጫካ እያለን ወንድምና እህቶቻችን ኤርትራዉያንንና ትግራዉያንን ለማስገንጠል ታላቅ መስዋዕትነት በመክፈላችሁና ኤርትራን ነጻ በማዉጣታችሁ እንዲሁም አዲሲቷ ኢትዮጵያ በብሔር ብሔረሰቦች በቋንቋ ተከፋፍላ የተለያዩ የክልላት መንግስታት ተመስርተዉ ለወደፊት ደግሞ ራሳቸዉን ሲችሉ እንደ እናት አገራችሁ ኤርትራ ለመገነጣጠል ያኮበከቡ የወደፊቱ ነጻ አገራት የአሁኖቹ እጩ አገራትን ለማየት ስላስቻላችሁን በቅድሚያ ታላቅ ምስጋናችንንና አድናቆታችንን እናቀርባለን። ታዲያ አንድ ያልገለጻችሁትን የታላቅነታችን መለያ የሆነዉን ታላቅ ተግባር አለ። ይኸዉም በአገር ዉስጥ ስንቶቹን በአገር ክህደት፣ በአሸባሪነት እየወነጀልን እንደምናስርና ፍዳቸዉን በማሳየት እንደምናሳድድ ስላልገለጻችሁ ነዉ። ከእነዚህ ሁሉ አስበልጠን ነዉ ለእናንተ ኢትዮጵያዊነተችሁን በግልጽ ለካዳችሁት ይህን የመሰለ እንክብካቤ በማድረጋችን «ቅዱስና ጻድቅ» የሚለዉን ስያሜ ልታበረክቱልኝ ይገባ ነበር።

ሌላዉ የታላቅነታችን መለያ እኛ እንኳን እናንተን ለኤርትራ መገንጠልና ነጻነት ለጥንቷ ኢትዮጵያ መከፋፈልና ወደ ጥፋት ማምራት ታላቅ ዉለታ ያደረጋችሁትን ዉዶቻችንን ቀርቶ በዉጭ ኢትዮጵያዊነታቸዉን ክደዉ ዜግነታቸዉን የለወጡትን አይደለም ለኢትዮጵያ መጥፋት የሚተጉ ክህደትንና መናፍቅነትን የሚያስፋፉ ሰዎች ብራቸዉን ይዘዉ ይምጡልን እንጂ ከኢትዮጵያዉያን በላይ እንክብካቤ አድርገንላቸዉ የፈለጉትን

እንፈጽምላቸዋለን:: በተቃራኒዉ ደግሞ ኢትዮጵያዉያን ዜጎችን እያጎሳቆልን ፍዳቸዉን እናሳያቸዋለን:: በዚህ መልኩ ነዉ የዘመናት በቀለኝነታችንን እየፈጸምን ያለነዉ::

ስለዚህ እናንተም የኛ አጋር ሆናችሁ ዓላማችንን ካሳካችሁ ከማንኛዉም «ኢትዮጵያዊ ነኝ::» ብሎ ከሚናገር ሰዉ በላይ እንክብካቤ የምናደርግላችሁና በእነሱ ላይ እንደምናሰለጥናችሁ ቃል እንገባላችኋለን:: ዋናዉ በኢትዮጵያና በኢትዮጵያዊነታችሁ ላይ በፈጸማችሁት የክህደትና የዐመጻ አቋም መጽናት ነዉ የሚጠበቅባችሁ::

እኛ ዘንድ «አንድነትና ዉህደት» የሚባል ነገር የለም:: እንኳን ከሌሎች ጋር አንድነትና ዉህደት መፍጠር ቀርቶ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ዜጎች ሁሉ የኢትዮጵያዊነት ብሔራቸዉን አስክደን «እኔ ብሔሬ ኢትዮጵያዊ ሳይሆን እኔ ትግሬ ነኝ:: እኔ አማራ ነኝ:: እኔ ኦሮሞ ነኝ:: እኔ አፋር ነኝ:: እኔ ሱማሌ ነኝ:: እኔ ሐረሪ ነኝ::... ወዘተ» በማለት በሰማኒያ ብሔር ብሔረሰቦች ስለከፋፈልን የኢትዮጵያዊነት ስሜት በዉስጣችሁ ካለ ከወዲሁ እርማችሁን እንድታወጡ በዚሁ አጋጣሚ እናሳስባችኋለን::» በማለት ምክርና ማስጠንቀቂ ጭምር ሰተዋቸዋል:: እኔም የጨለማዉ ገዥ በምክሩ ሆነ በማስጠንቀቂያዉ የተደሰትኩ በመሆኑ ትክክለኛ እንደራሴ ማዘጋጀቴን ለራሴዉ ማረጋገጫ ሰጥቻለሁ::

አንዳንድ ከእናት አገራቸዉ ከኢትዮጵያ መገንጠል ላይ በምርጫ ያልተሰለፉና በወቅቱ ልጆች የነበሩ በአንድላይ በመሰባሰብ «እኛ «ኤርትራዉያን» የምንባልና «ኢትዮጵያዉያን» የሚባሉ ዜጎች በስብሰባ ላይ ሆነ በተለያዩ ቦታዎች ሲታዩ መለያ የላቸዉም:: መልካቸዉ ሆነ ጠባያቸዉ ተመሳሳይ የሆነ አንድ አይነት ናቸዉ:: ይህም ልዩነት የፈጠሩት የተወሰኑ ግለሰቦችና ቡድኖች መሆኑን ይገልጣል:: ትንቢተ ኤርምያስ ም.፲፫፥፳፫(13:23) **«በዉኑ ኢትዮጵያዊ መልኩን፣ ወይስ ነብር ዥንጉርጉርነቱን ሊለዉጥ ይችላልን?»** ብሎ ለተናገረዉና ለጠየቀዉ፤ «እኛ ኤርትራዉያን ነን እንጂ ኢትዮጵያዉን አይደለንም» ያልን ሰዎች፤ መልሳችን «አዎን» መሆኑ ምን ያህል ከእግዚብሔር ፈቃድ ዉጭ መሆናችንን ያሳያል:: ይኸዉም ለእግዚብሔር ጥያቄ « አዎን ነብር ዥንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያም መልኩን ሊለዉጥ

ይችላላ።» በማለት የማይሆን ጠማማ መልስ እንደሰጠነዉ ይታመናል።» በማለት ከተወያዩ በኋላ፤

«ስለዚህ ለምን ኢትዮጵያዊ ዜግነታችን ለወጥን? ማን ለወጠዉ?» በማለት ጥያቄያቸዉን ከኢትዮጵያ በመገንጠላቸዉ ለሚቆረቆሩ ለሃይማኖት አባቶች ያቀረቡ ሲሆን፤ የተሰጣቸዉም መልስ «ልጆቻችን! በእርግጥ ኢትዮጵያዊ መልካችሁ ባይለወጥም፤ ታላላቆቻችሁና ወላጆቻችሁ እኛም ጭምር ክህደትን ፈጽመናል። ሌላዉ ቢቀር የቃል ኪዳን አገር መሆኗን ከብዙ ሺህ ዓመት በፊት ነብየ እግዚአብሔር ዳዊት «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች» የተባለዉን የዘነጋንና በሁለት ከሃዲና ዐመጸና ቡድኖች «ሻዕብያና ወያኔ » በሚባሉት ተጽህኖና የክህደት ተግባር ነዉ ለማንፈልገዉ ሕይወት የተዳረግነዉ።

እነሱ ተስፋቸዉ ምድራዊ ስለሆነና በስልጣን ጥማት የተቃጠሉ፤ ጥላቻ፣ ቂምና በቀል ያረገዙ በመሆናቸዉ ፍጹም የዲያብሎስ እንደራሴ ሆነዉ ፈቃዱን ሲያስፈጽሙለት፤ እኛ ግን እነሱን ተከትለን ምርጫችንን ዲያብሎስ ማድረጋችንንና እግዚአብሔርን መካዳችን፣ በስሙ መነገዳችን ነዉ የሚያሳዝነዉና የሚያስገርመዉ። ለዚህ ለአገርና ሃይማኖት ክህደታችን ሁላችንም ዋጋ እየከፈልንበት ነዉ። ለወደፊትም የባሰዉን ዋጋ እንደምንከፍል ልናስተዉል ይገባል። ከአስር ዓመት በፊት እናንተ ወጣቶች እያላችሁ እነዚህ ሁለት ወንበዴዎች ለስልጣናቸዉ የበላይነትና ጥቅም ሲሉ ሕዝቡ እንዲነጣጠልና እንዲገነጣጠል ያደረጉት አንሶ እርስ በእርስ አገዳደሉት፤ ደሙ በከንቱ እንዲፈስ አስደረጉ፤ እነሱ ግን በተደላደለ ወንበር ላይ ቂብ ብለዉ ዙፋናቸዉን በሕዝብ ደም ላይ ዘርግተዉ በተንደላቀቀ ሕይወት ይወጣሉ፤ ይገባሉ። አሁንም ሲፈልጉ ጦርነት ከማወጅና ሕዝቡን ወደ እሳት ከመማገድ የማይመለሱ ጨካኝ አረመኔ ለሕዝቡ አንዳች ርኅራኄ የሌላቸዉ የዲያብሎስ ምርጦችና ባለሟሎች ናቸዉ።

አሁን እናንተ እንሰደድ ብላችሁ ወደ እናት አገራችሁ ኢትዮጵያ ብተሰደዱ የወያኔ(የኢህአዴግ) መንግስት አይቀበላችሁም። ምክንያቱም «እኛ ኢትዮጵያዉያን ነን» ስለምትሉ፤ እንደ አገር ክህደት ቆጥሮ ወይን ራሱ ይወነጅላችኋል ወይንም ለአባቱ ሻዕብያ አሳልፎ ይሰጣችኋል። ባጠቃላይ «በኢትዮጵያ ዉስጥ ገብተዉ አንድነት ያመጣሉ፤ ለክልላዊ መንግስታቱ ህልዉና አደጋ ይሆናሉ፤ ኢትዮጵያዊነት ብሔር ይቀሰቅሳሉ፤» በሚል ስጋት

አይቀበላችሁም:: ነገር ግን « እኛ ኤርትራዉያን ነን:: ኢትዮጵያዉያን አይደለንም:: የሻዕብያን ስርዐት ብቻ ተቃዉመን ነዉ የመጣነዉ፤» የምትሉ ከሆነ ለእናንተ አስቦ ሳይሆን ለፖለቲካ መጠቀሚያ ሊቀበላችሁና ለራሱ ለጥፋት ዓላማ ሊያሰልፋችሁ ይችላል::

የእኛ ምክር ግን ሁለተኛ ክህደት ከመፈጸም እዚሁ ኤርትራ ዉስጥ ሆናችሁ በልቦናችሁ ኢትዮጵያዊነታችሁን አምናችሁ ስላለፈዉ ክህደታችሁ ንስሐ ገብታችሁ ፈጣሪያችሁን በእዉነትና በመንፈስ እያመለካችሁ የኢትዮጵያን ትንሳኤ ብትጠባበቁ የተሻለ መሆኑን እንመክራችኋለን:: እኛ ቀደም ሲል የሻዕብያ መንግስት ኅሊናችንን የመረዘዉ «የገዥ መደቦች በደል ፈጸሙብን ፤ አድሎ አደረጉብን ፤» በማለት ሲሆን ወደ ልባችን ስንመለስ ግን አድሎና በደል የተፈጸመበት ሁሉም ዜጋ በአራቱም ማዕዘን ያለዉ ኢትዮጵያዊ ላይ ጭምር ሲሆን ፤ በሕዝብ ስም የሚነግዱት ደግሞ እንደ አሁን ዘመን ባለጊዜ እንደሆኑት የተወሰኑ ግለሰቦችና ቡድኖች ናቸዉ እንጂ ብሔሮች ወይንም ጎሳዎች አለመሆኑን በሚገባ ተረድተናል:: ታዲያ ያኔም ቢሆን ወደ ክህደቱ ከመግባት እንደ ሃይማኖት አባትነታችን ማንንም ሳንወግን «እግዚአብሔር ሆይ! ከግፈኞች፣ ከጨካኞች፣ አድሎና በደል ከሚፈጽሙ ሰዎች ገላግለን፤ ያንተን ሰማያዊ መንግስት አቋቁምልን፤ ያንተን ፈቃድ ብቻ የሚፈጽሙና የሚያስፈጽሙ እንደራሴዎችህን በሥጋዊዉና በመንፈሳዊዉ ወንበር ላይ አስቀምጥልን::» በማለት መለመንና መጸለይ ሲገባን እንደ ሥጋዉያኑ ሃይማኖት የሆነዉ ኢትዮጵያዊነትን ክደናል፤ የዐመጻ ተባባሪና አስፈጻሚ ሆነናል::

አሁን ግን እኛ የተወሰን አባቶችና እናቶች እንዲሁም ወንድሞችና እህቶች ስለ ክህደትና ዐመጻ ተግባራችን ንስሐ ገብተን ከእናት አገራችን ከኢትዮጵያ ከድንግል ማርያም ጋር ለመዋሀድና ከሃይማኖታችን ተዋህዶ ጋር አንድነት ለመፍጠር እግዚአብሔርን በጸሎት እየጠየቅንና ምህላ እያደረግን እንገኛለን:: እናንተም በሁሉም ቦታ ጸሎታችሁንና ምህላችሁን አጠናቅሩ:: በኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ትንሳኤን የሚጠባበቁ ወገኖቻችን በጸሎትና በምህላ ላይ እንዳሉ እናዉቃለን:: ሁለቱም ቡድኖች ሻዕብያና ወያኔ በቅርቡ የዘሩትን የዐመጻና የክህደት ፍሬያቸዉን እንደሚያጭዱና የኢትዮጵያ ትንሳኤ እንደሚመጣ በእዉነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ተነግሮናል::

*መሪዎች ሆኑ ሕዝቡ ካለፉት ታሪክ ትምህርት መዉሰድ ሲገባቸዉና ከእዉነት ጋር መሰለፍ ሲጠበቅባቸዉ « እኛ ምርጫችን የዲያብሎስ እንደራሴዎችን ነዉ፡፡ የምንፈጽመዉም የእነሱን ፈቃድ ነዉ» በማለታቸዉ፤ እንደምርጫቸዉ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰቱ ጽዋ ሲሞላ የእግዚአብሔርን ቁጣን መቀበላቸዉ ስለማይቀር እየንዳንዱ ሰዉ ንስሐ ገብቶ እጅኑ ለአምላኩ ቢሰጥ የሚያዋጣዉ መሆኑን በዚሁ ምክራችንን እንገልጻለን፡፡» በማለት አሰናብተዋቸዋል፡፡ እኔ የጨለማዉ ገዥ በምክራቸዉና በአቋማቸዉ ተቆጥቼ በደኅንነቶቼ አማካይነት ለበላይ ባለስልጣናት ሪፖርት አስደርጌ ይኸዉ እስከ አሁን ድረስ በእስር ይገኛሉ፡፡»*
**ይላል የክፋት፣ የዘረኝነት ፣ የጎጠኝነት አባት የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከሠራዊቶቹ ጋር በመሆን፡፡**

# ምእራፍ ሰባት

« *አንዳንድ ምሁራን «የእድገት መለኪያዉ መስፈርት ትክክለኛ የአገርና የሕዝብ እድገትና ብልጽግና አይገልጽም » በማለት ለአገሪቱ ለምጣኔ ሀብት ባለሙያተኞች አስተያየታቸዉን አቅርበዋል፡፡ ይኸዉም «በተለይ እጅግ አብዛኛዉ ኢትዮጵያዉያን በችግር ዉስጥ እያሉና በጣት የሚቆጠሩ ሰዎች ብቻ በብልጽግናዉ ዓለም እየተንዙ እያለ «አገሪቷ ከ10*% *በላይ እድገት አሳይታለች፡፡ በጥቂት ዓመታት ዉስጥ እንደቻይናና ህንድ ትሆናለች» እያሉ ሕዝቡን ማደንዘዛቸዉና ከግምት ዉስጥ የሚያስገባቸዉን ወሬ ነጋ ጠባ ማዉራቱ አግባብነት የለዉም፡፡ እንዲሁም «በአገሪቱ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ተሰርተዋል፤ የተለያዩ መንገዶች፣ የተለያዩ ተቋማት፣ የተለያዩ የልማት አዉታሮች.. ወዘተ ተሰርግተዋል፡፡ ጂዲፒ ከፍ ብላል» እየተባለ ሕዝቡ ግን በችግር፣ በጉስቁልና፣ በልመና፣ በረሀብ፣ በእርዳታ፣ እየተማረረና እያዘነ የሚኖር ከሆነ፤ በጥቂቶች ሰዎች መበልጸግና መግነን እንዲሁም በህንጻ መሰራትና በተቋማት መብዛት እንዴት በለጸግን፣ ኢኮኖሚያችን አደገ ለማለት እንደፍራለን?» በማለት አስተያየታቸዉንና ጥያቄያቸዉን አቅርበዋል፡፡*

*የሚመለከታቸዉም አካል፤ «በእዉነቱ ለአገሪቱ እድገት ተቆርቁራችሁ አስተያየት መስጠታችሁ አግባብ ቢሆንም የእኛ ስሌት በዓለም አቀፍ ስሌት መሰረት ስለሆነ፤ የዓለም አቀፉ ስሌት መድኸየትን እንደ እድገት የሚቆጥር ቢሆን እንኳ፤ እኛም በዚያዉ መሰረት ነዉ የምናሰላዉ እንጂ እንደ ማንነታችን ወይንም ስሙን እንኳ ብዙ ጊዜ እንዲጠራ ባይፈለግም ሰላይ ስለሌለብኝ ለጊዜዉ ብጠራዉ ችግር የለዉምና ይኸዉም እንደ ኢትዮጵያዊነታችን አይደለም የምናሰላዉ፡፡ ብዙዎቻችን በካፒታሊስት መንፈስ የተጠመቅንና ከኢትዮጵያዊነታችን ይልቅ ለጌቶቻችን «ብሔር ብሔረሰቦች» እያልን ኅሊናችንን መሸጣችንን ብናስመሰክር ነዉ ሞገስና ስልጣን የምናገኘዉ፡፡ ለዚህም ነዉ እየተሰቀኩ «እንደ ኢትዮጵያዊነታችን» ያልኩት ፡፡*

*ከእናንተ ቀደም ብለዉ የተወሰኑ «አገር ወዳድ ነን» ብለዉ ወደ እኛ በመምጣት የሚያስገርምና የሚያስቅ የብልጽግናና እድገት ትንታኔ አቅርበዉልን ነበረ፡፡ ይኸዉም « እኛ ኢትዮጵያዉያን ድሆችና ጎስቋሎች አይደለንም፡፡ ከማንም የዓለም ሕዝብ በላይ ሀብታሞች ነን፡፡ እናንተ ተስፋችሁ ምድራዊ ስለሆነና ለልመናና ለእርዳታ እንዲያመቻችሁ ልመና ሐፍረት ያልሆነባችሁ ከየመንግስታቱ «እኛ ለማኞች ድሆች ነን» እያላችሁ የተለያዩ አገራት መንግስታትን ደጅ የምትጠኑ አሰዳቢዎች ናችሁ፡፡ ሕዝቡን ራስ ወዳድና ስግብግብ አደረጋችሁት እንጂ እዉነተኛ ለአገሩና ለሕዝቡ የሚቆረቆር መንግስት ቢኖር ለፖለቲካዉ ዓለማ ሲል በህዳሴ ግድብ ስም በተለያየ መንገድ ከሕዝቡ ገንዘብ እንዳሰባሰበ ሁሉ በፈቃደኝነት*

ላይ የተመሰረተ «ወገን ለወገኑ ይድረስለት» በማለት ሕዝቡ እርስ በእርስ እንዲተሳሰብ፣ እንዲተዛዘን፣ እንዲረዳዳ፣ እንዲፋቀር፣ አንድ እንዲሆን አድርጎ ቢሆን ኖሮ አንድ ለማኝ ለማየት ብርቅ ይሆንብን ነበር፡፡

ነገር ግን መንግስታችሁ ነጋ ጠባ «ለብሔር ብሔረሰብ፣ ለሰንሴሽን ኮንደም፣ለዘፈንና ለዳንኪራ.. ወዘተ» ቅስቀሳ የሚያደርግና በእግዚአብሔር እዉነታ ላይ የሚያሳምጽ፤ ሕዝብ በሕዝብ ላይ እንዲጨካከን ያደረገ ጨካኝ ነዉ፡፡ «ኢኮኖሚ አደገ» ሊባል የሚችለዉ ደግሞ ሁሉ በልቶ ሲኖርና ራሱን ችሎ መኖር ሲችል ብቻ ነዉ እንጂ ሕንጻና የተለያዩ ተቋማት በመሰራታቸዉ «አደግን፣ተመነደግን ፣ ኢኮኖሚዉ ከፍ አለ» ልንል አንችልም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ በመንፈስ ደሀ የሆነ መንግስትና ሕዝብ ነዉ ደሀና ጎስቋላ እንጂ እግዚአብሔርን የሚያመልክ ፣ ራሱ ፈቅዶ እየጾመ የሚራብ፣ የጾመዉን ደግሞ የሚበሉትና የሚቀምሱት ለሌላቸዉ ወገኖቹ የሚሰጥ ሰዉና ሕዝብ አይደለም፡፡ ይልቁኑ ይህ አይነቱ ሕዝብ እዉነተኛ ባለጸጋና ባለሀብት ነዉ፡፡

ምን ዋጋ አለዉ የብዙ ሀብትና ንብረት ባለቤት ሆኖ ባዶነት በተሞላ ሕይወት መኖር!? ምን ዋጋ አለዉ ምድራዊ ሕይወትን ብቻ ተስፋ ያደረገ ኑሮ መኖር? ስንቱ ነዉ በስግብግብነትና በራስ ወዳድነት የሰበሰበዉን ሀብትና ንብረት ሳይበላና ሳይጠቀምበት ለማንም አስረክቦና በትኖ በሥጋ ሞት ወደ ሁለተኛ ዓለም የተጓዘዉ? ስንት ችግረኛንና ድሀን ረግጦና ዞር ብሎ ሳያይ በስግብግብነት ለራሱ ብቻ ያከማቸዉን ሀብትና ንብረት እንኳን ራሱ ሊጠቀምበት ቀርቶና «ለትዉልዴ አስተላልፋለዉ» ብሎ የተጨነቀበትና የተጠበበት ከንቱ መኖ ሆና የሚቀርበት አጋጣሚ የለምን? ስለወደፊቱ ማን እንደሚጠቀምበትና እንደሚበላዉ በእርግጠኝነት መናጋር ይቻላልን? አይቻልም፡፡ ታዲያ እያንዳንዱ ባለሀብት ምናለ ምስኪን ወገኑን ቢያስብ? ወገኑን ቢያስብ ኖሮ እዉነተኛ እርካታንና በረከትን ያገኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ባለሺህዉ ባለመቶ ሺህ፣ ባለመቶ ሺህዉ ሚሊየነር፣ ባለ ሚሊየነሩ ቢሊየነር ለመሆን ነዉ ሌት ተቀን የሚሯሯጠዉ እንጂ በየቦታዉ የወደቀዉን የአዳም ዘር ወገኑን ዞር ብሎ የሚያይ ባለሀብት ስለሌላ ይኸዉም እንደምናየዉ በተቅበዘበዘና እርካታ በሌለዉ ሕይወት ሲባዝኑ ነዉ የሚታየዉ፡፡

ምስኪኑ ወገን ደግሞ የሚመለከተዉ በሥጋዊ ዐይን የሚታየዉን ኮልኮሌ ነገሮችን ስለሆነ፤ እርሱም በምኞች ይቃጠላል እንጂ ባለዉ ተመስገን እያለ ረክቶ መኖርን አይመርጥም፡፡ እንዲህ ስንል ደግሞ ሰዉ ኑሮዉን ለማሸነፍ አይዉጣ፣ አይዉረድ፣ አይንቀሳቀስ ለማለት ሳይሆን አቅም ያለዉ ሰዉ የተቸገረዉ ወገኑን «ቤተሰቤ ፣ ዘመዴ፣

ዘሬ፣ ጎጤ» ብሎ ልዩነት ሳይፈጥር እንዲረዳ፣ እንዲያግዝ ለማሳሰብ ነዉ እንጂ በዚህች ስደት አገራችን ምድር ዉስጥ ወተን፣ ወርደን እንድንሰራና እንድንኖር ነዉ የታዘዝነዉ:: በሃይማኖታችንም ቢሆን ስንፍና የተከለከለና እያንዳንዱ ሰዉ ሰርቶ እንዲበላ ነዉ የታዘዘዉ:: ስለዚህ ሁላችንም በትጋትና በንቃት መስራት እንደሚጠበቅብን ይታወቃል::» በማለት ነበር ብሶታቸዉንና ፍልስፍናቸዉን ያቀረቡት::

በወቅቱም የጠቅላይ ሚኒስትሩ ተወካይ የሰጧቸዉ ምላሽ « እናንተ ናቸዉ አገራችንን ደሀ ያደረጋችሁት:: የገዥ መደቦች ናቸዉ ብሔር ብሔረሰቦችን ለመጨቆንና ለማድኸየት «እግዚአብሔር ፣ መንግስተ ሰማያት፣ ገነት፣ ሲያል፣ ገሃነመ እሳት .. ወዘተ» እያሉ አገራችን እንደ አሜሪካና ቻይና እንዳትሆን «በእለተ ሰንበት እሁድ ሙሉ ጊዜያችሁን በመንፈሳዊ አምልኮና ተግባር ላይ ብቻ አዉሉ፤ ዐበይት በዐላት በሆኑት ዘመን መለወጫ፣ በመስቀል፣ በልደት፣ በጥምቀት፣ በስቅለት፣ በትንሳኤ..ወዘተ የሥጋ ስራ አትስሩ፤ መንፈሳዊ ተግባር በመፈጸም ነፍሳችሁን አሳርፉ» በማለት ሕዝቡ ከዓመት እስከ ዓመት ሃያ አራት ሰዐት ለሥጋዊ ኑሮዉ እንዳይሯሯጥ ያደረጋችሁት:: እንዲሁም ተስፋችን የሆነችዉን ምድር ሕንጻ በሕንጻ እንዳትደምቅና በዉስጧም በዘፈንና በዳንኪራ እንዳንዝናና ነፍሳችንን እየጨቆናችሁ ያላችሁት እናንተና መሰሎቻችሁ ናችሁ:: ይብላኝ ለእናንተ እንጂ እናንተ ለነፍስ ሕንጻ ስታስቡ እኛ ደግሞ ለሥጋ ሕንጻ የሚመች የብልጽግና የብሔር ብሔረሰቦች ጎዳናን የጀመርን ስለሆነ ወደ ኋላ እንመለስም:: ይልቁኑ መጥገብ አይደለም ገና በደንብ ያልቀመሳችሁትን ሕግ መንግስታችንን ብታታጣጥሙት ኖሮ ርሀባችሁንና ችግራችሁን ማስወገድ ትችሉ ነበር» በማላት ምላሽ የሰጧቸዉ ሲሆን፤

ሰዎቹ ግን የተወካዩ ንግግር አሳዝኗቸዉና አስቆጥቷቸዉ ነበርና ወዲያዉ «እናንተ ሐፍረተ ቢሶች ናችሁ:: ብላችሁ ብላችሁ አሜሪካን፣ አዉሮፓን፣ ኤሽያን፣ ከቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ጋር ታነጻጽራላችሁን!? የመጨረሻ ጎስቋላና ድሀ አገራትን ከቅድስት ኢትዮጵያ ጋር ለማነጻጸር ኅሊናችሁ እንዴት ደፈረ? ወይስ በማያየዉ ዐይናችሁና ማስተዋል በጎደለዉ አእምሮዋችሁ ተመልክታችሁ ይሆን? ወይስ እንደ ቁስ አካላዉያን ይህ ቅርፊት ዐይናችሁ የሚያየዉ ሰዎች ጎስቋላ ኑሮና ሕይወታቸዉ እንዲቀልላቸዉ የሚያደርገዉን የተለያዩ ሕንጻዎች፣ ለትራንስፖርት አገልግሎት የሚዉሉ የተለያየ መንቀሳቀሳዎችን፣ የተለያዩ የልማት አዉታሮችን ብቻ ነዉ? ወይስ ዐይናችሁና ኅሊናችሁ ዋናዉንና እዉነተኛዉን ሕንጻ ነፍሳችሁን ማየት አልተቻለዉ ይሆን?

እነዚህ በሥጋዊ ዐይናችን የምናያቸዉ ለሥጋችን የሚጠቀሙና ጉስቁልና ሕይወታችንን የሚያቃልሉ ሁሉ ምሳሌያዊ ፍጥረት የሆኑ ኮልኮሌዎች ናቸዉ እንጂ ለእዉነተኛ ገንዘባችን ለሕያዉ ነፍሳችን ድኅንነትና ብልጽግና የሚሰጡ አይደለም። በዚህም ምክንያት እናንተ እንደ ታላቅ አገር በቆጠራችዋቸዉ አገራት በየእለቱና በየጊዜዉ በሚሊዮኖችና በቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ነፍሳት( ሰዎች) እዉነተኛ ድኅነትና ብልጽግና አተዉ እየተጎሳቆሉና እየሞቱ ይገኛ ሉ። እኛ ኢትዮጵያዉያን ግን ምንም እንኳ በአንዳንድ ተጽህናና በራሳችን ስንፍና ምክንያት በሥጋዊ ብልጽግናችን እነሱ ላይ ባንደርስም በነፍሳቸን ግን እጅግ የበለጸግንና ያልተጎሳቆልን ነን። የሥጋዊ ብልጽግናዉንም ራሳችንን ከስንፍና፣ ከክፋት፣ ከተንኮል፣ ከምቀኝነት ፣ ከትዕቢት፣ ከዐመጻ፣ ከክህደት፣ ከርኩሰት፣ ከራስ ወዳድነት፣ ከስግብግብነት፣ ከጥላቻ፣ ከመከፋፈል፣ ከመለያየት፣ ከዘረኝነት ፣ ከጎጠኝነት ..ወዘተ ከመሳሰሉት ካጸዳንና በቅን አሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ ሕይወት ከተመላለስን በአጭር ጊዜ ዉስጥ እነሱ ከደረሱበት በላይ ልንደርስ እንችላለን።

እነሱ ግን በዐመጻና በክህደት፣ እንዲሁም በርኩሰተ ሕይወት ዉስጥ ሆነዉ ስለሆነ ለዚህ የደረሱት፤ ብልጽግናቸዉና ስልጣኔያቸዉ አንዳች ዋስትና የለዉም፤ በጥቂት ቀናት ዉስጥ በእግዚአብሔር ቁጣ ( በተለያዩ መቅሰፍቶች) እንዳልነበረ ሊሆን የሚችል ነዉ። ምክንያቱም እጅግ በጣት የሚቆጠሩ ሰዎችን አበለጸጉ እንጂ ለሕዝቡ አንዳች ነገር አላመጡለትም። ለዚህም ነዉ ሕዝባቸዉ በአሜሪካ ሆነ በአዉሮፓ እንዲሁም በኤሽያና በመካከለኛዉ ምስራቅ አገራት እየተቃወማቸዉና ብሶቱን በአዳባባይ እያሰማ ያለዉ። ለመንግስታቱም በግልጽ « እናንተ የምትወክሉት አንድ ፐርሰንት የማይሞሉትን ግለሰቦች ነዉ እንጂ እኛን ዘጠና ዘጠኝ ፐርሰንት የምንሆነዉን አትወክሉምና ከወንበራችሁ ወርዳችሁ እኛ ን ብዙዎቻችንን ሊወክሉ የሚችሉ በወንበሩ ተቀምጠዉ ያገልግሉን» በማለት ድምጻቸዉን እያሰሙ ያሉት።

ደግሞ በዚህ ምድር ዉስጥ የፈለግነዉ ነገር ሁሉ ተሟልቶልን ነፍሳችን ግን ከእግዚአብሔር መንገድ ከወጣችና ሕያዉ ሆና ለምትኖርበት ለእግዚአብሔር መንግስት መብቃት ካልቻለች ምን የተለየ ጥቅም እንሰጣታለን? ሥጋዊዉ ፍላጎቷ ብቻ ቢሟላላት ምን ትርጉም አለዉ? ከምድራዊ ሕይወት ዘመን በኋላ ለሕያዉነት ዘመን ከምንኖረዉ ሕይወት አንጻር የዚህች ምድር ኑሮ የዐይን ቅጽበት እድሜ እንኳ አይሞላም። ታዲያ በዚህች ምድር ዉስጥ የዓለም ሀብትና ንብረት የኛ ቢሆን እንኳ ነፍሳችን ሕያዉ ሆና ለእግዚአብሔር መንግስት መታጨት ካልቻለችና ለሕያዉነት ዘመን በሲዖልና በገሃመ እሳት ዉስጥ እንደ ዐመጻ ደረጃ ፍዳዋን የምትቀበል ከሆነ የዚህ ምድር ቆይታዋ ምን ይጠቅማታል? የድሎቱና

የመንደላቀቁ ሕይወት ለነፍሷ ምን ያደርግላታል? ይልቁና ሰላም፣ እርካታ፣ ፍቅር፣ ደስታ ከማታገኝበት የድሎቱና የመንደላቀቂያዉ ሕይወት ቀርቶባት አምላኳን አምናና እንደ እርሱ ፈቃድ ተመላልሳ በምድራዊ ዘመኗም በእዉነተኛዉ ብልጽግና በበረከት፣ በሰላም፣ በፍቅር፣ በደስታ ሕይወት መመላለስና ከሥጋ ሞት በኋላ ደግሞ በቅዱን መላእክት አኗኗር በፍጹም ቅድስናና ደስታ ሕይወት ሕያዉ ሆኗ በመንግስተ ሰማያት መኖር አይሻላትምን?

እዉነታዉ ይህ ስለሆነ ነዉ እነዚህ በሥጋዊ ዐይናችን ስንመለከት የበለጸጉ የሚመስሉት አገራት በሙሉ ድሆችና ጎስቋሎች ናቸዉ ያልናችሁ:: እኛ ኢትዮጵያዉያን ግን አምላካችንን በእዉነትና በመንፈስ እያመለክነዉ በተለያየ ስጦታዉ እየተጠቀምን ለሕያዉነት ሕይወት የሚሆነን ቅዱስ ቁርባን ስንቃችንን ይዘን በበረከት፣ በጸጋ፣ በርካታ፣ በኅሊና ሰላም፣ በፍቅር፣ በደስታ እየኖርን ያለነዉና ከዚህች ጎስቋላ ዓለም የምንገላገልበትንና ወደ አምላካችን እቅፍ የምንሄድበትን ቀን እያናፈቅን በታላቅ ተስፋ የምንኖረዉ::

በእርግጥ እናንተ «ተማርን ተመራመርን ዶክተር ፣ ፕሮፌሰር ነን፤» ብላችሁ ኅሊናችሁን የምትሸጡ እዉነቱን ኅሊናችሁ እየመሰከረባችሁ ለጊዜያዊ ስልጣን፣ ክብር፣ ጥቅም፣ ድሎት፣ ምቾት ስትሉ ኅሊናችሁን በማደንደን ጨለማዉን ብርሃን ፣ ብርሃኑን ጨለማ፣ ዐመጻዉንና ክህደቱን እንደ ታላቅ ስራ፣ ታላቁን ስራ እንደ ዉርደትና ክህደት አድርጋችሁ የምታቀርቡ እነ ሆዱ አምላኩ ናችሁ:: ነዉሩንና ዉርደቱ እንደ ክብርና ታላቅ የምትቆጥሩ፣ በሕዝብ ስምና በኢትዮጵያ ስም የምትነግዱ የዐመጸኛዉና የከሃዲዉ መንግስት ካድሬ የሆናችሁ  ባዶ ቀፎ ሰዎች ናችሁ:: እምነታችሁ የቻርልስ ዳርዊን እምነት የሆነዉ « እኛ የእግዚአብሔር ፍጥረቶችና ልጆች አይደለንም:: ዘሮቻችንም አዳምና ሔዋን አይደሉም:: ከጦጣ መሰል እንስሳ በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ(በኢቮልሽን) አማካይነት የኒያንደርታንና የክሮማግነን ሰዉነት ደረጃ አልፈን  አሁን ላለንበት ሰዉነት ማዕረግ የበቃነዉ» ብላችሁ የምታምኑ::  በራሳችሁ ላይ ማፈሪና ያበደ አእምሮ መያዛችሁን የምትመሰክሩ ናችሁ:: እኛን የሚሳዝነን ግን የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ሕዝቦች በእናንተ ዐመጸኞችና ከሃዲዎች መመራቷና የእናንተ ርኩሰት ተግባር በተቀሰደሰችሁ አገር ነግሦ ማየታችን ነዉ:: ሕዝቡንም በጨለማዉ ስብከታችሁ በቴሌቭዥኑ፣ በሬዲዮኑ፣ በሕትመት ዉጤቶች፣ በስብሰባዉ አደንዝዛችሁት ለዲያብሎስ እየገበራችሁት መሆኑን  በመመልከታችን ነዉ::

እንግዲህ ወደ ልባችሁ ለመመለስ ፈቃደኞች ከሆናችሁ ዛሬ ነገ ሳትሉ እዉነተኛ ንስሐ በመግባት ራሳችሁን ከጥፋትና ከዉድቀት አድኑ:: እንዲሁም ይህን የተሳሳተ አስተሳሰብና አመለካከት አርማችሁ እንደ እዉነተኛ ማንነታችሁ እንደ ኢትዮጵያዊነታችሁ ልታስቡ፣

ልትናገሩ፣ ልትሰሩ ይገባል እንጂ በአህዛብ ስርዐት እየተመላለሳችሁ ራሳችሁን ድህና ለማኝ ማድረግ የለባችሁም፡፡ እዉነተኛ ደሀ በመንፈስ ደሀ የሆነ ብቻ ነዉ፡፡ የኅሊና ሰላምና እርካታ የሌለዉ ተስፋ ቢስና በተቅበዘበዘ ሕይወት የሚኖር እርሱ ነዉ የመጨረሻ የዓለም ደሀና ጎስቋላ እንጂ፤ የኅሊናዉ ሰላም የተጠበቀ የኅሊና ርካታ ያለዉ ሰዉ እርሱ እዉነተኛና በደስታ ሕይወትና ኑሮ የሚኖር ነዉ፡፡ በዓለም ሆነ በአገራችን ኢትዮጵያ ብዙዎቹ አምላካቸዉ ሆዳቸዉ ክብራቸዉ ነዉራቸዉ ስለሆነ በዐመጻና በክህደት ሕይወት ዉስጥ ሆነዉ ወደ ሞትና መቀመቅ ዉስጥ እየሄዱ ስለሆነ ልታድኗቸዉና ወደ ሕይወት መንገድ ልታመጧቸዉ ይገባል፡፡ እንዲሁም እዉነተኛ ብልጽግናና እድገት ምን እንደሆነ በቅዱስ ኪዳን ሕዝብነታችሁ ልትመሰክሩና ልታስረዷቸዉ ይገባል እንጂ እናንተ በአህዛብ አስተሳሰብ ልትመሩ አይገባል፡፡ እዉነተኛዉ ብልጽግናና ደስታ እንዲሁም ሰላም ለማግኘት ከተፈለገ እግዚአብሔር እንደ እዉነተኛ ፈጣሪነቱና አባትነቱ ተከብሮና ተፈቅሮ ሊመለክ ይገባል፡፡» በማለት ተሰምቶም፣ ታይቶም የማይታወቅ ፍልስፍናና ምክር የሰጡ ቢሆንም፤ እኛ ግን ከእብድ ንግግር ባልተለየ መልኩ ነበር የሰማናቸዉ፡፡

የእናንተ አቀራረብ ግን እንደ እኛዉ ተስፋችሁን ምድራዊ አድርጋችሁ ስለሆነ ለሥጋ የሚመች ማንኛዉንም አስተያየት ለመቀበል ዝግጁዎች ብንሆንም ከፖለቲካችን በተለይ ከብሔር ብሔረሰብ ክፍፍላችን የሚቃረን ወይንም የማይጣጣም አሳብ ከሌላችሁና እንኳን ለአገር የሚበጀዉን አሳብ ቀርቶ «ዝርያችሁ ጦጣዎች ናቸዉ፡፡ ሁሉም ነገር የተፈጠረዉ ከቁስ አካል ስለሆነ እግዚአብሔር ሆነ ሰይጣን የሚባል ነገር የለም፡፡ «መንግስተ ሰማያት፣ ሲዖል፣ ገሃነመ እሳት» የሚባል ነገር የለም ተረት ተረት ነዉ» እያላችሁ ምሁራዊ ትምህርትና ትንታኔ ስትሰጡን በደንብ ተቀብለናችኋል፡፡ በዚህም መሰረት የመጀመሪያዉ የማርክዚስትና ሌኒዚስት ፍልስፍናችሁን አሻሽላችሁ ከሶሻሊዝም ስርዐት ወደ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ስታሸጋግሩንም በደስታ ነዉ የተቀበልናችሁ፡፡» በማለት አሰተያየትና መላሽ ስለሰጡ እኔ የጨለማዉ ገዥ በመጨረሻ ንግግራቸዉ ስለተደሰትኩ ቀደም ሲል ስለ ኢትዮጵያ ቀባጥረዉ በነበረዉ ንግግራቸዉ ላስመታቸዉ አስቤ የነበረዉን ክፉ አሳብ ለጊዜዉ አንስቼላቸዋለሁ፡፡ » **ይላል የጨለማዉ ገዥ ትዉልዱን በሥጋዊ ዐይን በሚታየዉ ያደነዘዘዉና በብልጭልጭ ዓለም ኅሊናዉን ያሳመጸዉ ዲያብሎስ፡፡**

## ምእራፍ ስምንት

« በኑሮ ዉድነት የተማረሩና ለመኖር የተቸገሩ እጅግ ብዙ ኢትዮጵያዉያን ቅሬታቸዉን ለአገሪቱ መሪና ለከፍተኛ ባለስልጣናት እንዱሁም ለዉጭ መንግስታት አቀረቡ። ይኸዉም «እኛ ኢትዮጵያዉያን በችግርና በችጋር እንድንኖር የተፈረደብን አስኪመስል ድረስ በየወራቱና በየቀናቱ መሰረታዊ የፍጆታ እቃዎች ላይ ዋጋቸዉ እየጨመረ መሄዱና ለተወሰነ ቀን የዋጋ ተመን ቢወጣም ወዲያዉ ተሽሮ፤ በቀል በሚመስል መልኩ ዋጋቸዉ በእጥፍ እጥፍ ጨምሮብናል። ለድሀ የሚያስብ አካል ካለ አፋጣኝ ምላሽ ይሰጠን ዘንድ በአክብሮት እንጠይቃለን።» በማለት በኀዘንና በለቅሶ ብሶታቸዉን አቅርበዋል።

ለጥያቄያቸዉ የአገሪቱ መሪና ከፍተኛ ባለስልጣናት ምላሻቸዉን በሚከተለዉ መልክ ሰተዋል፡ «እኛ ጥቂቶች አገሪቱንና ሕዝቡን እንደፈለግነዉ ማሽከርከር እንደምንችለዉ ሁሉ በንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ጥቂቶች ነጋዴዎች እንዲሁ ንግዱን እንደፈለጉት ማሽከርከር ችለዋል። እኛ ኃይላችን ከእነሱ በላይ የሆነ መስሎን የዋጋ ቁጥጥር ለማድረግ ሙከራ ያደረግን ሲሆን፤ ያልጠበቅነዉ መልስ ምት ስለተሰጠንና ጠንከር ያለ ስለሆነብን ለስልጣናችንና ለህልዉናችን አደጋ ስለሆነ ወዲያዉ ነዉ እጅ የሰጠነዉና አቅማችን ወደሚችለዉ ሕዝብ ዞር ያልነዉ። ምክንያቱም እናንተ አቅማችሁንና ልባችሁን ስለምናዉቅ ምረጡን ስንላችሁ ግልብጥ ብላችሁ የምትመርጡን፤ ለድጋፍ ዉጡ ስንላችሁ ግልብጥ ብላችሁ ስለምትወጡልን፣ እንዲሁም ተቃወሙልን ስንላችሁ ግልብጥ ብላችሁ ስለምትቃወሙልን እንደልባችን ስለሆነችሁልን በስልጣናችንና በህልዉናችን ላይ አደጋ የማታመጡ ምስኪኖች በመሆናችሁ ከጥቂት ኃያላን ነገዴዎች ጋር ከመጣላትና ያላሰብነዉ ጣጣ ከማምጣት ሸክም የምታቃልሉልን ሰፊዉ ሕዝብ የዋጋ ንረቱን ቢሸከም ያዋጣናል በሚል እምነት ነዉ። በመሆኑም እስከአሁን ለምስጋናዉ የዘገየን ቢሆንም በዚሁ አጋጣሚ ስለመልካም አሸካከማችሁ ምስጋናችንን እናቀርባለን። ለወደፊት ደግሞ የአሸላለም ሁኔታዉን በመቀየር ይኸዉም ባለጸጎችን በየክልሉ ስንሸልምና ስናገን እንደነበረ ሁሉ ለወደፊት ደግሞ የዋጋ ንረቱን በብዛት በመሸከም የሚታወቀዉን ሰፊዉ ሕዝብን እንሸልማለን። ስለዚህ የሚሻላችሁ ያንቺን ሽልማት ለማግኘት የሚመጣባችሁን ሸክም ሁሉ ታግሳችሁ መሸከም ነዉ። እዚህ ላይ በምስጢር ያዙት እንጂ አንዳንዶቹን ነጋዴዎች በተለያየ መልኩ የምንበቀላቸዉ መሆኑን በዚሁ አጋጠሚ እናሳዉቃችኋለን።» በማለት መልስ ሰተዋቸዋል።

በሌላ ጊዜ ደግሞ ነጋዴዎች ባሉበት በማወያየት ነጋዴዎች አሳብ እንዲሰጡበት ተደርጋል። ይኸዉም « እኛ ነጋዴዎች ምን እናድርግ? በዚህ በተጨካከነ ሕይወት እንድንኖር ያደረገን ብልጡና መሰሪዉ መንግስት ነዉ። እነሱ ያላቸዉ ሀብትና ንብረት በቂ ሆኖ ሳለ

«አልጠገብንም» በማለት የአገሪቱን ሀብትና ንብረት ሲበዘብዙና ሲቀራመቱ እንዲሁም ለግል መጠቀሚያቸዉ ሲያደርጉ፤ የሕዝቡ በድህነት አረንቋ ዉስጥ መሆንና መቸገር አንዳች ስሜት ያማይሰጣቸዉ ጨካኝ በመሆናቸዉ፤ እኛም የእነሱን ፈለግ ተከትለን ነዉ ራሳችንን ብቻ የምናበለጽግበትና ለልጅ ልጆቻችን ብቻ የሚተርፍ እንዲሁም ከሁሉ በላይ ለመሆን ካለን የስግብግብነትና የራስ ወዳድነት ጠባይ የተነሳ ነዉ በአጭር ዓመታት ዉስጥ ከሁሉ በላይ የሆነ ሀብትና ንብረት ለማከማቸትና ምኞታችንን ለማሳካት ስንል ትርፋችንን እጥፍ በእጥፍ የምንጨምረዉ እንጂ እኛ የምንበላዉ፣ የምንጠጣዉ፣ ለልጅ ልጆቻችን የሚተርፍ አተን አይደለም።» በማለት ተናግረዋል።

የዉጭ መንግስታት ተወካይ የሕዝቡንም የነጋዴዉንም አስተያት ካዳመጡ በኋላ «ይህ ዴሞክራሳዊ ጥያቄያችሁ ተገቢ ቢሆንም፤ ይህ ችግር የመጣባችሁ ከልማታዊ መንግስታችሁ ጉን በጋራ ተሰልፋችሁ መስራት ካለመቻላችሁና ነጻ የኢኮኖሚ ግብይት ምን ማለት እንደሆነ ትርጉሙ በደንብ ስላልገባችሁ ነዉ። ይኸዉም ነጻ ግብይት ማለት አቅምና ኃይል ያለዉ ግለሰብ ሆነ ነጋዴ ከፈለገ የዓለምን ሀብት ጠቅልሎ በመያዝ ዓለምን ሆነ የዓለምን ሕዝብ እንደፈለገዉ ማሽከርከር ይችላል። የግለሰቦች መድህየትና መቸገር ብዙም ቦታ አይሰጠዉም። የሚችል ይኖራል፤ የማይችል አይኖርም። ይልቁኑ የዓለም አቀፍ ችግር የሆነዉን የአየር ንብረት ችግርና ኤድስና አባላዘር በሽታ ትኩረት ብትሰጡትና፣ እንዲሁም ወንዶች ከወንዶች እንዲጋቡ ሙሉ ሰብአዊ መብታቸዉ እንዲረጋገጥ ቢደረግ ችግራችሁ ሊቃለልና እርዳታም በደንብ ልታገኙ ትችላለችሁ። ስለዚህ የማይገባ ችግር በማቅረብ የመንግስታችሁን ወርቃማ ጊዜ አታባክኑ። እናንተ ነጋዴዎች ደግሞ ለዚህ ብልጽግና ያበቃችሁን ወዳደጉት አገራት ደረጃ ለማድረስ ደፋ ቀና የሚለዉን መንግስታችሁን ማማት አልነበረባችሁም። እናንተም እንደነሱ ብልጥ ሆናችሁ በሀብት ላይ ሀብት፣ በህንጻ ላይ ህንጻ፣ በንብረት ላይ ንብረት መጨመሪ እንጂ ስለ ድሆችና ስለችግረኞች እኛ ስላለን ብዙም ሊያስጨንቃችሁና ሊያሳስባችሁ አይገባም።» በማለት አስተያየታቸዉን ሰተዋል።

ሕዝቡም « እሺ ወደማን ነዉ አቤት የሚባለዉ!? የመጣነዉ በዉኑ እነዚህ የእኛ ወንድምና እህት ወደሆኑት የአዳም ዘሮች ነዉ? ወይስ በሥጋ የተገለጹ የጨለማዉ ገዥ አገልጋዮች ናቸዉ እንደዚህ የሚያስቡትና የሚላግጡብን? እዉነተኛ ፈራጅ እግዚአብሔር የለም ብለዉ አስበዉ ይሆን?» በማለት በኀዘንና በምሬት ወደቤታቸዉ ተመልሰዋል።

በማግስቱ ደግሞ ንዴቱ አልበርድ ያላቸዉ ሰዎች ተመልሰዉ ጥያቄቸዉንና ብሶታቸዉን ለማቅረብ ወደሚመለከተዉ አካል ቢሄዱም « ባለጉዳይ የሚስተናገደዉ በሳምንት አንድ ቀን ስለሆነ ማክሰኞ ኑ» ተብለዉ ተመለሱ። ማክሰኞን ጠብቀዉ ሲሄዱ

«የሚያነጋግሯችሁ ስብሰባ ስለገቡ ሳምንት ኑ» ተባሉ:: ሳምንት ጠብቀዉ ሲሄዱ «ለስልጠና ስለሄዱ ከወር በኋላ ኑ» ተባሉ:: ወር ጠብቀዉ ሲሄዱ «ኀዘን ስላጋጠማቸዉ ዛሬ አይገቡም» ተባሉ:: እኔም የጨለማዉ ገዥ በሕዝቡ መጉላላትና በመሪዎቻቸዉ መጨከን እንዲሁም ለዓለም ሕዝብ እንቆማለን የሚሉት የተባበሩት መንግስታት ተስፋ አስቆራጭ መልስ ተደስቼ እስከአሁን ሕዝቡ በችግርና በረሀብ አለጋ እያስገረፍኩት እገኛለሁ::

ስለ አገራቸዉ የግንባታ ጥራት ያሳሰባቸዉ አንዳንድ ሥራ ተቋራጮች፣ የኮንስትራክሽን ቁጥጥር አማካሪ ድርጅቶች፣ የኪነ ህንጻ ባለሙያተኞች፣ መሀንዲሶች፣ የተለያዩ ባለሙያተኞች፣ ለተለያዩ ግንባታ የሚዉሉ የተለያየ ግብአት (የተፈጥሮና የምርት ዉጤት) አቅራቢዎች፤ በአንድ ላይ በመሰባሰብ፤ « በአገራችን ቀደም ሲሉ የተገነቡ የህንጻ፣ የመንገድ፣ የፋብሪካ ፣ የተለያዩ መሰረተ ልማቶች ጥራታቸዉን የጠበቁ እስከ አሁን ድረስ የጎላ ጉዳትና መበላሸት የማይታይባቸዉ ሲሆን ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ያሉ የተለያዩ ግንባታዎች ሁለትና ሶስት አመት እንኳ አገልግሎት ሳይሰጡ የተለያየ ብልሽት የሚያጋጥማቸዉና አገልግሎት ለመስጠት አስቸጋሪ የሚሆኑ ሁሉ አሉ:: የሚገርመዉና የሚያሳዝነዉ በኢትዮጵያዉያን ባለሙያተኞች እየተሰሩና ቁጥጥር እየተደረገባቸዉ ነዉ ይህ ሁሉ ጉድለትና ብልሽት የሚያጋጥማቸዉ:: እኛ ኢትዮጵያዉያን ለራሳችን ንብረት ትኩረትና ጥንቃቄ ካላደረግን ማን ሊያደርግልን ይችላል?» በማለት እርስ በእርስ የተወያዩ ሲሆን፤ ሁሉም ተሰብሳቢዎች በተነሳዉ አሳብ ተመሳሳይ አቋም ያላቸዉ መሆኑን በመግለጽ «ችግሩ ምንድ ነዉ?» በማለት ለዉይይት አቅርበዉታል::

ከተሰብሳቢዎቹ መካከል የግንባታ ግብዐቶችን የሚያቀርቡና የሚያመርቱ አካላት፤ « እንግዲህ ሁላችንም የአገረና የወገን ፍቅር አስገድዶን ነዉ በራሳችን ፈቃድ የተሰባሰብነዉ:: ስለዚህ ስለማንም ሳይሆን ለኅሊናችንና ስለ አገራችን ስንል ያለዉን ችግር በግልጽ ልንወያይና የራሳችን ችግር ካለም በግልጽ ማስቀመጥ ይኖርብናል:: ለምሳሌ በኛ በኩል በአጭር ጊዜ ዉስጥ ከኛ በላይ እንደሆኑት ሀብታሞች ለመሆንና ለመክበር ስለምንፈልግ ጥራት የጎደለዉና ደረጃዉን ያልጠበቀ ግብአት እናመርታለን፤ እናቀርባለን:: በዚህም ምክንያት ወደ ግንባታ ሲለወጡ በሂደት በግንባታዉ ላይ የጥራት መጓደልና መበላሸት ይታያል» በማለት አስተያየት ሰተዋል::

በማስከተል ከስራ ተቋራጮች፤« በእርግጥ በግልጽ እንነጋገር ተብሏልና እኛም ስራ ተቋራጮች በአጭር ጊዜ ዉስጥ ለመክበርና ለመበልጸግ ካለን ፍላጎትና ከኛ በላይ የሆኑት ባለጸጋዎች ላይ ለመድረስ ከዚያም ለመብለጥ ካለን ምኞት የተነሳ ከፍ ያለ ትርፍ ማግኘ

ታችንን እንጂ ግንባታዉ በጥራት ደረጃዉን በጠበቀ መልኩ እንደራሳችን ህንጻ በመመልከት አይደለም የምንሰራዉ:: የዱሮዎቹ ተቋራጮች ሆኑ ባለሙያተኞች ከገንዘብ ፍቅር ይልቅ ለስማቸዉ ቅድሚያ ስለሚሰጡ ከራሳቸዉ ጥቅም ይልቅ የአገራቸዉንና የሕዝባቸዉን ጥቅም ነዉ የሚያስቀድሙት የነበረዉ:: ለዚያም ይመስለናል በድሮ ስራዎች ላይ ብዙ ብልሽትና ጉድለት የማይታየዉ::

አሁን ያለነዉ ነጋዴዎች እንደአጠቃላይ ሲታይ ራስ ወዳዶች፣ ስግብግቦች ስለሆን በሀብት ላይ ሀብት፣ በሕንጻ ላይ ሕንጻ፣ በንብረት ላይ ንብረት እንዲኖረን ነዉ የምንፈልገዉ እንጂ አገራዊና ሕዝባዊ አስተሳሰብ የለንም ማለት ይቻላል:: ስለዚህ ይህ አስተሳሰባችን በመጀመሪያ ደረጃ ሊታደስ ይገባል:: ያኔ ለአገርና ለወገን ማሰብ እንጀምራለን:: መስገብገብና ራስ ወዳድነት አይደለም ከገንዘባችን በተጨማሪ ለአገራችንና ለሕዝባችን እንደ ቀደሙት አባትና እናቶቻችን ደማችንን ጭምር መስዋዕት ከማድረግ አንመለስም:: አሁን ባለን አስተሳሰብ ግን የዓለም ሕዝብ ሀብቱና ንብረቱ የእኛ ብቻ ቢሆንና እኛን ሌት ተቀን ደጅ ቢጠናን ምርጫችን ነዉ» በማለት አስተያየታቸዉን ሰተዋል::

አርክቴክቶች፣ መሐንዲሶችና የተለያዩ ባለሙያተኞች፤« ጥንት ኢትዮጵያዉን በራሳቸዉ ልጆች ለዓለም የሚያስደንቅ የጥበብ ስራና ግንባታ አሳይተዋል:: ከተወሰኑ ዓመታት በፊት ደግሞ እነዚያ ጥበበኛ ኢትዮጵያዉያን ጠፍተዉ ኢትዮጵያዉያን ባልሆኑ ባለሙያተኛ ነበር የዲዛይኑና የቁጥጥሩ ስራ ይከናወን የነበረዉ:: አሁን ደግሞ ብዙ ባለሙያተኞችን አገሪቷ አፍርታ ሳለ ከዱሮ በበለጠ የተሻለና ጥራቱን የጠበቀ ህንጻ፣ መንገድ የመሳሰሉት ሊኖረን ሲገባ ከዱሮ ያነሰና የሚያስተችን ሆኗል:: ይህም የሙያ ስነምግባር ጠብቀን ስለማንሰራና ከሥራ ተቋራጩ ጋር ተሻርከን እኛም ገቢያችንን ከፍ ለማድረግና በኋላም ሥራ ተቋራጭና አማካሪ ለመሆን ነዉ የምንሰራዉ እንጂ ለስራዉ ጥራት ትኩረት ስለማንሰጥና በአቋራጭ ለመክበር ስለምንፈልግ ግንባታዉን በጥራት መቆጣጠር አልቻልንም» በማለት አስታየታቸዉን ሰተዋል::

በመቀጠል የኮንስትራክሽን ግንባታና ቁጥጥር አማካሪ ድርጅቶችም፤ « በሥራ ተቋራጭ ሆነ በዕቃ አቅራቢዎችና አምራቾች ዘንድ ችግር ቢኖር እንኳ በኛ በኩል በአግባቡ በመቆጣጠር የግንባታ ጥራቱንና ደረጃዉን ጠብቆ እንዲሰራ ማድረግ ሲጠበቅብን በአግባቡ የስራ ድርሻችንን ስላልተወጣን እኛም ለስራዉ ጥራት መጓደልና መበላሸት አስተዋጽኦ አድርገናል:: ይህም የሆነበት ዋንኛ ምክንያት እያንዳንዳችን ባለሙያተኞች ከጥናት፣ ከዲዛይን ፣ ከግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ጀምሮ ስራችንን እንደ ትርፍ ስራ (ሁለተኛ ስራ) አድርገን እየተመለከትን ስለምንሰራና በጋራ ተቀናጅተን ጥራቱንና ደረጃዉን በጠበቀ መልኩ እንዲሰራ ለአንድ ዓላማ

መቆም ስላልቻልን ነዉ። ይባስ ብሎ በሙያችን እየተከፋፈልንና እየተቧደን እርስ በእርስ የምንተቻች፤ የምንጠላለፍ፤ አገራዊና ሕዝባዊ አስተሳሰብ የሌለን ፤ የራሳችንን ሙያ ብቻ ከፍ እያደረግን የሌላዉን የምናጥላላና የምናኳስስ፤ የአንድ አካል የተለያዩ ብልቶች መሆናችንን የዘነጋን ፤ ጆሮ በዐይን ላይ፣ እጅ በእግር ላይ ጥሩ አመለካከት የሌለዉ፤ የአንዱ ዉድቀትና መበላሸት ለሌላዉም እንደሚተርፍ ያላስተዋልን ነን ። ባጠቃላይ ለአንድ ዓላማ መቆም ያልቻልን ፤ ለጥራት ስራ አንዳች የማንቆረቆር፤ ደሞዛችንን በየወሩ ከመዉስድ ዉጭ አንዳች አገራዊና ወገናዊ ፍቅር ተሰምቶን ለግንባታ ጥራትና እድገት ስሜት አልባ በመሆናችን ምክንያት ነዉ ጥራቱ ሆነ ደረጃዉን ያልጠበቀ ስራ ሊሰራ ያቻለዉ» በማለት አስተያየታቸዉን ሰተዋል።

በመጨረሻም ሁሉም የራሳቸዉ ጉድለት አምነዉ በቀጣይ ለአንድ ዓላማ በተቀናጀ መልኩ ጥራት ላለዉ ግንባታ በመሰለፍ የበደሉትና አገርና ሕዝብ ለመካስ ቆርጠዉ የተነሱ መሆናቸዉን በመግለጽ ለሚመለከተዉ አካል አቋማቸዉን ለማሳወቅ እየተዘጋጁ ሳላ፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ የመልካም ነገር ተቃራኒ ነኝና አንድ ልብ እንዳይሆኑ በዘር፣ በጎጥ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት ከፋፍዬ፤ ዉይይቱንም በካድሬዎቼ አማካይነት ከፖለቲካ ጋር እንዲያያዝ አድርጌ መልካም አሳባቸዉንና እቅዳቸዉን አኮላሽቻለሁ።

አንዳንድ የጤና ባለሙያተኞች በአገር ዉስጥ ስለሚሰጠዉ የጤና አሰጣጥ ድክመትና ስነምግባራዊ ባልሆነ መንገድ የሚሰሩ ስራዎችን በተመለከተ ዉይይትና አቋም መዉሰዳቸዉ ታዉቃል። ይኸዉም በዉይይታቸዉ« እኛ ሀኪሞች፣ ጤና መኮንኖች፣ ነርሶች፣ ጤና ረዳቶች፣ የላብራቶሪ ቴክኒሺያኖች፣ እንዲሁም ተዛማችነት ባለዉ ስራ በጋራ የምንሰራ ሰራተኞች ሕዝቡን ቃል በገባነዉ መሰረት በትህትናና በቅንነት ማገልገል ሲገባን በአገባቡ ማስተናገድና አገልግሎት መስጠት አልቻልንም። ምክንያቱም እኛ አገልጋይ መሆናችንን በመዘንጋት ገና በሽተኛዉ ሲመጣ የምናመናጭቅና ሌላ ያላሰበዉን በሽታ የምንጨምርበት ሆነን ተገኝተናል። ከዚህ በተጨማሪ ቀልጠፍ ያለ አገልግሎት መስጠትና ጥንቃቄ የሞላበት ህክምና መስጠት ሲገባን የምናጉላላና ጥንቃቄ የጎደለዉ የቸልተኛነት ስራ በመስራታችን አንዳንዶቹ ለሞትና ለከፋ ጉዳት ዳርገናቸዋል። ስለዚህ በተለያየ መልክ ሕዝቡ ስለተማረረብን በመልካም ስነምግባር እንደ ወላጆቻችንና ቤተሰቦቻችን በመመልከት ልናስተናግዳቸዉና ልናገለግላቻዉ ይገባል።» በማለት በጋራ ተወያይተዋል።

በማስከተል በግል ህክምና የሚሰሩት ደግሞ « እኛ በግል ህክምና የምንሰራ ባለሙያተኞች ከፍ ያለ ገቢ ለማስገኘትና በአጭር ጊዜ ዉስጥ ለመክበር እንዲሁም በአጭር

ጊዜ ዉስጥ የራሳችን የንግድ ሆስፒታል ለመክፈት ስንል ስነምግባር በጎደለዉ መልኩ ምርመራ ሊደረግበት የማይገባዉን የተለያየ ምርመራ ዉጤት እንዲቀርብ በማዘዝ የማያስፈልግ ወጭ በሕዝቡ ላይ ጭነናል:: ሙያችንን ልክ እንደ ንግድ ስራ በመመልከት በአንዴ የምነበለጽግበትን መንገድ ነዉ የምንፈልገዉ እንጂ ወገናችንንና ቤተሰባችንን የምናክም መሆኑን ዘንግተነዋል:: በመሆኑም ከእንግዲህ ታካሚዎችን እንደ አባቶቻችን እናቶቻችን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በመቁጠር በቅንነትና በእዉነት ለማገልገል ቃል እንገባለን» በማለት በመንግስትና በግል የህክምና ተቋም የሚሰሩ የተለያዩ የጤና ባለሙያተኞች ስምምነት ያደረጉ ቢሆንም፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ የቅንና የእዉነት ተግባር ተቃዋሚ ነኝና የአፍ ዉይይት ብቻ እንዲሆን አድርጌ እስከአሁን ድረስ ተግባራዊ እንዳይሆንና ህመምተኛዉም እንዲማረር አድርጌያለሁ::

በሌላ ጊዜ ደግሞ በየትምህርት ተቋሙ ያሉ መምህራን በትምህርት አሰጣጥና በተማሪዎች ጉዳይ በጋራ ተሰብስበዉ ዉይይት ያደረጉ ሲሆን፤ በዉይይታቸዉም « እኛ መምህራን ከማንኛዉም ሙያ በላይ ትዉልዱን በእዉነተኛ አስተሳሰብና ሕይወት ልንቀርጸዉ የሚገባና አገራዊና ዓለማቀፋዊ አስተሳሰብ እንዲኖረዉ እንዲሁም እግዚአብሔር መፍራት ባለበት ሕይወት እንዲመላለስ ማድረግ ሲገባን የመንግስትን ፖሊሲና ፖለቲካ ተግባር ለማስፈጸም ስንል ኅሊናችን ሳይፈቅድ በዉስጣችን በተሰገሰጉ ካድሬዎች አማካይነት በተቃራኒዉ ተግባር ተሰልፈናል:: ይኸዉም ገና ከህጻንነት እድሜ ጀምሮ ትዉልዱ በዘረኝነትና በጎጠኝነት አስተሳሰብ እንዲያድግ አለቆቻችን ባመጡልን በዓለም ላይ ተሰምቶም ታይቶም የማይታወቀዉን «ብሔር ብሔረሰቦች» የሚለዉን ኅሊና ማሽጫ ቋንቋና የአባልነት ማጥመቂያ መንፈስ ኅሊናቸዉ ዉስጥ እየዘራን በዘፈንና በዳንኪራ እያሳበድን ይኸዉ በአገሩ ላይ፣ በሰንደቅ ዓላማ ላይ፣ በአምላኩ ላይ ዐመጻና ክህደት የሚፈጥር ርኩሰትን የሚያነግሥ ትዉልድ አፍርተናል::

አሳዛኙና አስገራሚዉ ደግሞ ተማርን ተመራመርን የተባልን ሰዎች ነን፤ ከታች ከመዋዕለ ህጻናት ጀምር እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ያለን መምህራን የመንግስት እንደራሴ ሆነን የመሪያችንን አንደበት አንደበት፣ መንፈሱን መንፈስ አድርገን ለዐመጻ፣ ለክህደት፣ ለርኩሰት እንዲመች አድርገን ትዉልዱን እየቀረጽን ያለነዉ:: ወላጆቻችን አንዳች ሳይማሩ እናት አገራቸዉን ኢትዮጵያን፣ የተቀደሰዉን ሰንደቅ ዓላማቸዉን፣ ፈጣሪቸዉን አላስካዱም፣ አላጥላሉም፣ ዐመጻም አላስፈጸሙም:: እኛ ግን የዐመጻኛዉና የከሃዲዉ መንግስት አገልጋይ ሆነን በየትምህርት ተቋሙ ትዉልዱን ከእዉነት አርቀነዋል:: የፈጠረዉን አምላክ አስክደነዉ «የዘር ሐረጎችህ አዳምና ሔዋን አይደሉም:: ፈጣሪህም አንዱ እግዚአብሔር

አይደለም። ከጦጣ መሰል እንስሳ በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ (በኢቮልሽን) አማካይነት ነዉ አሁን ላለህበት ደረጃ የበቃኸዉ፤ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣችህ ተፈጥሮ ነች፤ እንደፈለክ በዚህ ምድር ላይ ተመላለስ እንጂ «መንግስተ ሰማያት፣ ገነት፣ ሲዖል፣ ገሃነመ እሳት» የሚባሉት የገዥ መደቦች ለመጨቆኛ ያመጡት ነዉ» በማለት ከሰዉነት ባሕርይ አስወጥተነዋል። በዚህም ምክንያት ክብሩ ታላቅ የነበረዉ የመምህርነት ሙያችን ሞገሱ ተገፎ እኛም በተማሪዎቻችን እየተናቅን እንገኛለን።

ስለዚህ ከእንግዲህ መንግስት ከፈለገ ለእሱ ጨለማ አገዛዝ የሚመች ትዉልድ ካገኘ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቷቸዉ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ትምህርት ያስተምራቸዉ እንጂ የቅዱስ ኪዳኗን ኢትዮጵያ ሕዝቦችን ከእንግዲህ አናሳምጽም፤ እግዚአብሔር መፍራት ያለበትን ትምህርት እንዲሁም በሥጋቸዉም በነፍሳቸዉም የሚጠቀሙበትን እዉቀትና ጥበብ ብቻ ነዉ የምናስተምረዉ እንጂ ዳግም የካድሬነት ተግባር አንፈጽም» በማለት በአንድ አቋም የተስማሙ ቢሆንም፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ ስለ ድፍረት ዉይይታቸዉና እንደራሴዎቼ የሆኑትን መሪዎች ፣ ባለሟሌ የሆኑትን ባለስልጣናት፣ እንዲሁም ዉዶቼ የሆኑትን ካድሬዎች ስላጣጣሉብኝና ስለናቁብኝ እንዲሁም የጨለማዉ ተግባሬን አናስፈጽምም በማለታቸዉ ዋንኛ አስተባባሪዎችን ለአለቆቻቸዉ በዉዶቼ አሳሳቢነት ወደ እስርና ስደት ዳርጌያቸዋለሁ።» **ይላል ዓለምን እንፈለገዉ እያሽረከረ ያለዉ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ።**

## ምእራፍ ዘጠኝ

« ስለ እዉነት እንኳን እኔን ዲያብሎስን ቀርቶ እዉነተኛ አምላካችሁን የማትሰሙና የማትፈሩ ደንዳኖችና ቆራጥ ጀግኖች በመሆናችሁ የ 7503 ዘመን የጥናቴን ግኝት በምስጢር ለእናንተ ለምርጦቼ መሪዎችና ለባለሚሎቼ ባለስልጣናት እንዲሁም ለዉዶቼ ካድሬዎች ብቻ አቀርባለሁ:: አደራ የምላችሁ ይህን ምስጢሬን ብዙ የደከምኩበት ስለሆነ ከቢጤዎቻችሁ በስተቀር በኔ ላይ አድማና ዐመጻ ለፈጸሙብኝና ለሚፈጽሙብኝ በአገር ዉስጥ ሆነ በዉጭ አገር ላሉ ጠላቶቼ እንዳትገልጹ:: እናንተ ብቻ በጸጋዬ ተጠቀሙ::

1. ለረጅም ዘመን ባጠናሁት ጥናቴ እያንዳንዱ መንግስት፣ ቡድን ፣ ግለሰብ የዘራዉን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ የክፋት፣ የተንኮል ፍሬዉን አጭዶና መራራ ቢሆንም ጭለት አድርጎ በመጠጣት ያልፋል እንጂ፤ ማንም ይሁን ማን ከተፈቀደለትና ከተቆረጠበት ቀን አንድ ቀን እንኳ በራሱ ስልጣንና ኃይል የስልጣን እድሜዉን አያስረዝምም::

ታዲያ እንዲህ ስላችሁ «በተፈቀደልን እድሜ ቀና እናስብ፣ መልካም እንስራ፣ እዉነተኞች እንሁን፣ እግዚአብሔርንም በእዉነትና በመንፈስ አምልከን ራሳችንን ለሰማያዊ መንግሰት እናብቃ፣ ስላለፈዉ ዐመጻችንና ክህደታችን ንስሐ እንግባ» እንድትሉ አይደለም:: ይልቁኑ እንደታለቁ ፈርኦን « እግዚአብሔርንም አናዉቅም ፤ ለሕዝቡም አንራራም፤ በዐመጻና በክህደት ሕይወታችን እንጸናለን፤ አንድነታችንና ህብረታችን ከጨለማ ገዥ ከዲያብሎስ ከግብር አባታችን ጋር ነዉ::» እንድትሉና እስከመጨረሻዉ እቅታ ድረስ ታማኝነታችሁን እንድትገልጹልኝ ነዉ::

2. እግዚአብሔር የፈለገዉን ለማድረግ እንደሰዉ ወይንም እንደ እኔና እንደ እናንተ የዓመታት፣ የወራቶች፣ የቀናት ዝግጅት እንደማያስፈልገዉና የፈለገዉን በፈለገዉ መንገድና ቀን ማድረግ እንደሚችልና ካለ እርሱ ፈቃድ በባለሚሎቹ ላይ ማንም ይሁን ማን አንዳች የማድረግ ስልጣን እንደሌለዉ ነዉ:: እንኳን ግዙፉ ነገር ቀርቶ እናንተ በሳይንሱ «አተም» የምትሉት ረቂቅ ነገር በእርሱ እይታና ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆነ ከእርሱ ፈቃድ ዉጭ አንዳች ሊሆን ሆነ ሊደረግ አይችልም::

ታዲያ እንዲህ ስላችሁ ተስፋ ቆርጣችሁ እጃችሁን ለእግዚአብሔር እነድትሰጡና ከእዉነት ጋር አንድነትና ህብረት እንድትፈጠሩ ሳይሆን ይልቁኑ በበደል ላይ በደል፣ በዐመጻ ላይ ዐመጻ፣ በርኩሰት ላይ ርኩሰት በእጥፍ በእጥፍ እንድትጨምሩና ማንም የማያገኘዉን የሚጣፍጠዉን የግፋችሁንና የጭከናችሁን ጽዋ እንድትጠጡ ነዉ::

3. እስካዉን ድረስ የራሱን አገርና ሃይማኖት ለማጥፋትና ሕዝቡንም ለዐመጻ፣ ለክህደት፣ ለርኩሰት፣ ለጥላቻ፣ ለበቀል፣ለዘረኝነት ፣ ለጎጠኝነት ፣ ያሰለፈ እንደልቤ የሆነ በዓለም ላይ እንደ ወያኔ ወይንም ኢህአዴግ መንግስት አላጋጠመኝም:: በዚሁ አጋጣም ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ በተለይ ለመሪዎቹ ታላቅ ምስጋናዬንና እስከአሁን ድረስ ላደረጋችሁልኝ እንደልብ መታዘዘ አድናቆቴን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ::

4. ለታላላቅ ባለሟሎቼ እንኳ የዓመታት አይደለም የአንዲት ቀን ዋስትና መስጠት አለመቻሌንና አቅመቢስነቴን ተረድቻለሁ:: ታዲያ እንዲህ ስላችሁ ኃይል የለኝም፤ የፈለኩትን ለፈለኩት መስጠጥ አልችልም፤ ከጥፋትና ከዉድቀት መታደግ አይቻለኝም ለማለት ፈልጌ ሳይሆን፤ መቼስ ስለ እዉነት መሸነፍን ሆነ እዉነትን መቀበል ዉርደት መሆኑን ከኔ በላይ እናንተ ሳታዉቁ አይቀርም ብዬ እገምታለዉና፤ አቅማችሁን እንኳ ብታስተዉሉ በአንደበታችሁ ኃያል መሆናችሁን መግለጽና ማንኛዉንም ሰዉ በተለያየ መንገድ ማስፈራራት፣ ማስጨነቅ አለባችሁ እንጂ «በእግዚአብሔር ጭብጥ ዉስጥ ነኝ፣ አጥብቆ ቢይዘኝ የምጨፈለቅ፣ ጨክኖ ቢለቀኝ ብትንትኔ የሚወጣ ነዉ፤ እንኳን በራሴ ስልጣን ልሰራና ልናገር ቀርቶ ማሰብ የማልችል ደካማ ነኝ» ብላችሁ ራሳችሁን ዝቅ አድራገችሁ ዉርደት በሆነዉ በትህትና ሕይወት እንዳትኖሩ ለማሳሰብ ነዉ::

5. እናንተ የዓለም ሕዝቦች  በተለይ ኢትዮጵያዉያን «የቅዱሱ ኪዳን ሕዝቦች» የምትባሉ ለወደፊቱ «አንድ በእግዚአብሔር የተቀባ እዉነተኛ ኢትዮጵያዊ ንጉሥ «ቴዎድሮስ» የሚባል ይነግሣል፤ በዚያን ዘመን እዉነተኛ ሰላም፣ ፍቅር፣ ፍትህ፣ እኩልነት፣ ነጻነት፣ ብልጽግና፣ አንድነት ይሆናል:: ምድሪቱም ከሕዝብ ደም መጣጮችና ተባዮች ትጸዳለች፤ ሀገረ እግዚአብሔር የተባለች ኢትዮጵያ የድንግል ማርያም አስራት አገርን ሊያጠፏት የተነሱና የሚነሱ መንግስታት፣ ቡድኖች፣  ድርጅቶች፣ ግለሰቦች በእግዚአብሔር ቁጣ ይጠፋሉ፤

አገሪቱና ቀሪዉ ዓለም አገራት በእግዚአብሔር በተመረጡና በተቀቡ በአንድ ንጉሠ ነገሥትና በአንድ እጨጌ ይመራሉ፤ ከምድረ ገጽ እንድትጠፋ የተፈለገችዉ ታላቋ ኢትዮጵያ በእዉነተኛ ልጆቿ በዓለም ትገናለች፤ ማንም ምንም ሊያደርጋት አይችልምና ስንዱ እመቤት ሆና ከፍ ከፍ ትላለች:: ቤተሕዝቡ፣ ቤተክህነቱና ቤተምልክናዉ በአንድ ላይ ሆነዉ በመንፈስ ቅዱስ ይመራሉ፤ ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግስት ትሆናለች::» የሚባል ንግርት አለና ይህ የሚጣፍጠዉ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት፣ የክፋት፣ የተንኮል ተግባራችሁ ሳይቆምና ሳያልቅ ቶሎ ቶሎ እንድትበሉትና እንድትጠጡት አሳስባችኋለሁ::

መቼም ይህን ንግርት ከተረት ተረት ዉጭ አድርጋችሁ የማታዩ በእዉቀታችሁና በኃይላችሁ የታበያችሁ መሆኑን ስለማዉቅ ነዉ በጥናቴ ላይ ያስፈረኩት እንጂ ለ7503 ዘመን የተቆጣጠርኩትን መንግስቴን ለማንም አሳልፌ እንደማልሰጥና ዲያብሎሳዊ ስርዐቴ የሆነዉን ሕዝቡ ሲፈልግ እኔን እንዲያገለግልና እንዲያመልክ ሲፈልግ የራሱን አምላክ እንዲያመልክ ሙሉ ዴሞክራሲ መብቱን ያጎናጸፍኩትን ታማኝ ጌታዉን ክዶ መቼም ለእግዚአብሔርና ለእንደራሴዎቹ ይታዘዛል የሚል አንዳች እምነት የለኝም::

እነሱን የሚቀበል ከሆነ ደግሞ ጣዖታትንና ባዕድ አምልኮ እንዳይፈጽም አግደዋለዉ፤ በዝሙትና በአመዝራነት ሕይወት እንዳይኖር ተጽህኖ አደርስበታለዉ፤ ዘፈኑንና ዳንኪራዉን በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን እንዲያቀርብ እድል አልሰጠዉም፤ ጥላቻና ቂም በቀል እንዳይፈጽም ኃይልን አሳጠዋለሁ፤ በተንኮል፣ በክፋት፣ በግፍ፣ በአድሎ ፣በስረቀት፣ በዉንብድና፣ በጭቆና፣ በበደል ሕይወት ዉስት እንዳይኖር መንገዶቹን ሁሉ እዘጋበታለሁ፤ እንዳያዉቀዉና እንዳያስተዉለዉ አድርጌ ያደነዘዝኩትን ኅሊናዉን ከፍቼለት ይህን ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎስቆለ ባሕርይዉንና ጎስቋላ ኑሮዉንና ሕይወቱን እንዲያስተዉ አድርጌ ምድራዊ ሕይወቱን እንዲንቅና በዐይኑ ያላየዉን ሌላ ዓለም እንዲመኝ አደርገዋለሁ:: ባጠቃላይ እንደፈለገዉ የሚፈጽመዉን የኃጢአት ተግባርና ንግግር እገድብበታለሁ:: ይህንንም በታላቁ ስሜ ዲያብሎስ በመማል አረጋግጣለሁ::

በተላይ እናንተ እንደልቤ የሆናችሁ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክና የብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግስታት መሪዎችና ባለስልጣናት፤ ከሁሉ በላይ

የኔ ስጦታ የሚቀርባችሁ እናንተ ስለሆናችሁ፤ ኃይላችሁን የተለያዩትን ስሜን፣ አርማችሁን ደግሞ ኮከቤን አድርጋችሁ እስከመጨረሻ እቅታችሁ ድረስ እንድትፋለሙና በጽናት እንድትቆሙ እያልኩ፤ ለወደፊትም ታላቁን የጨላማ መንግስቴን የምትወርሱና ሺህሞታችሁንም በዚያ የማጸናላችሁ መሆኑን በዚሁ ቃል እገባላችኋለሁ፡፡ እናንተም ምስጋናዬን እግሬ ስር ተንበርክካችሁና ተረግጣችሁ እንደምትቀበሉ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

6. በኢትዮጵያ ዉስጥ ሆነ በሌላዉ ዓለም ለሰማያዊ የእግዚአብሔር መንግስትና ለምድራዊ የእግዚአብሔር መንግስት የምታበቃ ብቸኛ እምነት የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት እንደሆነች በመረዳቴ በተለያየ ጊዜና መንገድ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ አሁንም በተጠናከረ መንገድ እያደረኩ ነዉ፡፡ እንደምሳሌ የሩቁን ዘመን ልተዉና የአሁኑ ትዉልድ በዐይኑ ያየዉን በጆሮ የሰማዉን ላቅርብ፤ ያለፈዉ የደርግ ወይንም የኢሠፓ መንግስት መሪ ከግብረ አበሮቹ ጋር ሆኖ እግዚአብሔር የለሽ የክህደት ስርዐት ቢዘረጋም በብቃትና በትጋት ኃላፊነታቸዉን ባለመወጣታቸዉ ምክንያት ይህችን እምነት ማጥፋት ሳልችል ቀርቻለሁ፡፡

ነገር ግን ለአሁኑ መንግስቴ ለወያኔ ወይንም ለኢህአዴግ ለዐመጻ፣ ለክህደት፣ ለርኩሰት ተግባር ጥሩ መንገድ ጠራጊ ሆነዉ ስላለፉ በዚህ አጋጣሚ ምስጋናዬን ልቸራቸዉ እፈልጋለሁ፡፡ ለዚህም ነዉ የአሁኑ መሪ ከግብረአበሮቹ ጋር በስልጣን ወንበር ላይ ሲቀመጥ በቀላሉ ኅሊናዉን የሚሸጥ ትዉልድ ማፍራት የቻለዉና የዘረኝነት ፣ የኅጠኝነት ፣ የክፋት፣ የጥላቻ፣ የበቀል፣ የግድያ፣ የራስ ወዳድነት፣ የስግብግብነት፣ የመጨካከን፣ የስርቆት፣ የማጭበርበር፣ የዘፋኝነት ፣ የዳንኪርተኛነት፣ የዝሙት፣ የአመንዝራነት፣ የባዕድና የጣዖት አምልኮ፣ የዐመጻ፣ የትዕቢት ... ወዘተ ባጠቃላይ ለኔ የሚመች ስርዐትና ሕይወት መፍጠር የቻለዉ፡፡

ታድያ እናንተ «ወያኔ ወይንም ኢህአዴግ» በመባል የምትታወቁ እስከ አሁን ድረስ ራሳችሁን፣ አባሎቻችሁን፣ ደጋፊዎቻችሁን ነዉ የምትወክሉት እንጂ ወገናችሁን፣ ነገዳችሁን ፣ ቋንቋዋችሁን የማትወክሉ ስለሆነ ከእንግዲህ በኋላ ሁሉንም ወገን፣ ነገድ፣ ቋንቋ ባንድላይ

አሰልፋችሁልኝ በዓላማዬ ዙሪያ እንድታሰባስቡና የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባራችሁ ላይ ሙሉ ተሳታፊና ተባባሪ እንድታደርጉ አስጠነቅቃችኋለሁ:: አንዳንድ መልካም ጅማሮች ቢታዩም ይኸዉም በህዳሴዉ ግድብ ሽፋን ከህጻን እስከ አዋቂዉ፣ ካልተማረዉ እስከ ምሁሩ፣ ከደሀዉ እስከ ሀብታም ቱጃር ድረስ በዓላማችሁ ዙሪያ ማድረጋችሁና ሁሉም ኅሊናዉን በብልጠት እንዲሸጥ በማስደረጋችሁና ከዚያም አልፎ ቁልፍ የሃይማኖት አባቶችን ከጎናችሁ አስልፋችሁ «ከፀሐዩ ንጉሣችን ጉን ያልተሰለፈና ኅሊናዉን እንደ ቦይ ዉኃ ያላገለባበጠና ወደ ተፈለገዉ አቅጣጫ የማይመራ ኢትዮጵያዊ በራሱ ጊዜ ኢትዮጵያዊነቱን ሰርዟል» በማለት መግለጫ እንዲሰጡ አስደርጋችኋል::

እናንተ መሪዎችና ባለስልጣናት! ነፍሳችሁ ይማራል ወይ? ምን አስችሏችሁ ነዉ ትንሽ በተሸጠዉ ኅሊና ሳትጫወቱበት ወዲያ የህዳሴዉ አሰባሳቢ ዋና ጸሐፊዉ የአገርና የወገን ፍቅር ያላቸዉ በኢትዮጵያዊነትና በሰንደቅ ዓለማ ፍቅር በነደዱት በአፈቀላጤያችሁ አማካይነት « እኛ ዋና ዓለማችን ለህዳሴዉ ግድብ ገንዘብ ማሰባሰቡ ሳይሆን ሁላችሁም ከዓለማችን ጉን (ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ከማጥፋት፤ ዘረኝነትና ጎጠኝነት ከማስፋፋት፤ ዘፈንና ዳንኪራን ከማንገሥ፤ ክፋት፣ ተንኮል፣ ጥላቻ፣ ቂም በቀል፣ ዝሙት፣ አመንዝራነት ፣ ባዕድና ጣዖት አምልኮ፣ ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት.. ወዘተ የመሳሰሉትን በትዉልዱ ኅሊና መዝራት ላይ በመሰለፋችሁና ሆ ብላችሁ የኛ ደጋፊና ጠበቃ መሆናችሁን ነዉ:: በዚህም ምክንያት በደሞዝ መልክ በካድሬዎቻችን ተጽህኖ የአንድ ወር ደሞዛችሁን እንድትለግሱ ያስደረግነዉን ማሻሻያ አድርገን ወደ ቦንድ ለዉጠንላችኋል:: ዋናዉ ጥሩንባ ንፉ ስንላችሁ መንፋት፤ ለድጋፍ ዉጡ ስንላችሁ መዉጣት፤ ለተቃዉሞ ዉጡ ስንላችሁ መዉጣት፤ አዉግዙ ስንላችሁ ማዉገዝ፤ ባጠቃላይ እንደልባችን እንድትሆኑልን ነዉ ፍላጎታችን» በማለት የወራት እድሜ እንኳ ሳይቆጠር መግለጫ እንዲሰጥ ማስደረጋችሁ?

እዚህ ላይ ሕዝቡን በአንድነት የምታሰልፉልኝ እንደ 97ቱ ምርጫ እንዳሳፈሯችሁና ገበናችሁን ለዓለም እንዳጋለጡት ከልብ የማይመስል የድጋፍ ሰልፍና እንዲሁም የ2002ቱ አይነት ተስፋ በመቆረጥ ከልብ በማይመስል ድጋፍ ሳይሆን፤ እንዲሁም ለሰባት አመት ያህል «እከክልኝ፣ ልከክልህ፣ በሞቴ! ይህን የኢትዮጵያ ሕዝብ ፍዳዉንና መከረዉን አሳይተን

እንበቀለዋለን፣ ሀብት ንብረቱንም በደንብ እንቀራመተዋለን፤ ብላልኝ፣ ጠጣልኝ፡፡» በማለት ከአንገት በላይ ፍቅር እንደመሰረታችሁትና በኋላ ደግሞ «አይንህን ለአፈር» እንደተባባላችሁት የሻዕቢያ ቡድንና የእናንተ ቡድን  ወዳጅነት አይነት ሳይሆን፤ ልባዊ ታማኝነትና ሎሌነት በተሞላ አንድነት መሆን አለበት፡፡

በዚሁ አጋጣሚ ሕዝቡን መጨፍጨፋችሁንና ለእስር፣ ለስደት፣ ለችግር መዳረጋችሁ፤ እንዲሁም አገርን ያህል ስትገነጥሉና ስታስገነጥሉ አንዳች ያልመሰላችሁና ያልተሰማችሁ፣ የተለየ ዉጤት ላላመጣችሁበት፣ ትዕቢታችሁንንና እብሪታችሁን እንዲሁም ጨካኝነታችሁን ያስመሰከራችሁበት፤  ልታጠፉት የነበረዉን ትዉልድ ለጦርነት አሰልፋችሁ አሟሟቱ እንኳ እንዳያምር አድርጋችሁ በምድረበዳ ሬሳዉ እንዲወድቅ ያደረጋችሁትን ዉለታ የዘነጋዉባችሁ አይምሰላችሁ፡፡ ይልቁኑ ይህ ታላቅ ተጋድሏችሁ ሙሉ በሙሉ እንዲታሰብ ከፈለጋችሁ ከላይ በዝርዝር ያስጠነቀቅዋችሁን በአፋጣኝ ተግባራዊ አድርጉ፡፡ ያለበለዚያ እኔ የጨለማዉ ገዥ በምድርም በሰማይም መታሰቢያ እንዳይኖራችሁ አድርጌ እንድትደመሰሱና ሙሉ በሙሉ ትዕዛዜን ተግባራዊ ለሚያደርግ አዲስ መንግስት ወንበራችሁን አሳልፌ የምሰጥ መሆኔን እንድታዉቁ  እፈልጋለሁ፡፡

7. የቅርብ ጥናቴ የሚገልጸዉ፤ ባለሚሎቼ  ባለስልጣናትና ዉዶቼ ካድሬዎች «ጎሊናዬን በቀላሉ አልሸጥም» ብሎ የሚያስቸግረዉን ትዉልድ፤ በቀላሉ የዓላማቸዉ ተባባሪና ደጋፊ እንዲሆንና የዐመጻና የክህደቱ ፈጻሚና አስፈጻሚ በመሆን አብረዉ ተሰላፊ ለማድረግ የተጠበቡት መጠበብ በሚፈለገዉ መጠን ባይሳካላቸዉም በተወሰነ ደረጃ  የተሳካላቸዉ ስለሆነ በዚሁ አጋጣሚ እንኳን ደስ ያላችሁ ለማለት እፈልጋለሁ፡፡

መቼስ እናንተ የጥናቴ አካል ስለሆናችሁ ጉዳዩን በደንብ ብታዉቁትም የዋሁ ኢትዮጵያዊ አያዉቀዉምና ለሱ ትንሽ ማብራሪ ብሰጠዉ ለወደፊት ማንነታችሁን አዉቆ የበለጠ ደጋፊያችሁና ተባባሪያችሁ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ፡፡ እናንተ አገራችሁንና ሃይማኖታችሁን የምትወዱ የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር በልቦናችዉ የተተከለ  ለኔ አስቸጋሪ የሆናችሁ እዉነተኛ ኢትዮጵያዉያን! « ስንት ችግርና ሰቆቃ እያለብን፣ የምንበላዉና የምንጠጣዉን አተን፣ በየመንገዱና በየጥጋጥጉ ወድቀን ፣በየቤቱ ተዘግቶብን፤ ስንት ቅድሚያ

ሊሰጠዉ የሚገባ ተግባር እያለ በወርቃማ ቃለት ተሸፍኖ፣ ያልሆኑትን የአገርና የወገን ተቆርቋሪና አሳቢ መስሎ እንዴት ይህ ይመከራል? ለራሳቸዉ መሰሪ ዓላማ ያሰልፉናል፤» ብላችሁ ቅሬታ እንደማይሰማችሁ ስለምተማመን፤ ምስጢር በማዉጣቴ ደግሞ እንደራሴዎቼና ባለሚሎቼም ቅር እንደማይላቸዉ አዉቃለሁ፡፡

ምክንያቱም ጌታቸዉ እኔ አታላዩ(ሸዋጁ) መንፈስ ነኝና፡፡ ታዲያ ዋና አገልጋዮቼና ባለሚሎቼ በተለያየ መንገድ ድጋፍ ለማግኘትና ሕዝቡን ከጎናቸዉ ለማሰለፍ የተጠቀሙበት «የህዳሴ ግድብ» በሚል ሽፋን ሕዝቡን በዙሪያቸዉ ማሰባሰብ ነበር፡፡ መቼስ እናንተ ሚሊየነርና ቢሊየነር ያስደረጓችሁ በዚህ ቅር እንደማትሰኙ ተስፋ እንደርጋለሁ፡፡ ምክንያቱም በተዝዋዋሪ በመቶ እጥፍ እንደሚሰጧችሁ እገምታለሁና፡፡

ዋናዉ ግባቸዉና ግቤ በወርሀዊዉ ገቢ መኖር አቅቶት በመንገዳገድ ላይ ያለዉን ደሞዝተኛ በካድሬዎቻቸዉ ቀስቃሽነትና ተጽህኖ የአንድ ወሩ ደሞዝ ላይ አስፈርዶ ማስመረርና አነስተኛ ገቢ ያለቸዉንም አስጨንቆ መቀበል ነዉ፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ ምንም የሌለዉን ደሀና በየመንገዱና በየጥጋጥጉ የወደቁትን፣ ቤት ዉስጥ ተመልካች አተዉ የተዘጋባቸዉ ላይ « እኛ በሚሊዮኖች አይደለም በሰማኒያ ቢሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ ማሰባሰብ የምንችል ጀግኖችና ትጉሆች ነን፡፡ እናንተ ግን እንኳን ለሌላ ነገር ቀርቶ በሕይወት ለመቆየት እንኳ ለራሳችሁ መስብሰብ ያልቻላችሁ ድሆች ናችሁ» ብለን በድሆች ላይ ማላገጥ ነዉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከኛ ተባባሪ አስተባባሪ ያልሆነዉን ደግሞ በየመስሪያቤቱ፣ በገጠርም፣ በከተማም፣ በሃይማኖት ተቋማትና በየትምህርት ቤቱ ሳይቀር «ጸረ ልማት፣ ጸረ መንግስት፣ ሽብርተኛ» በማለት ተለጣፊ ስም መስጠትና እንደሁኔታዉ መበቀል ነዉ ዋና ዓላማችን የነበረዉ፡፡ «አንተ የረቂቁ መንፈስ ምስክርነት አይበቃምና ከሥጋ ለባሽ እስቲ ማስረጃ አቅርብ» እንደምትሉ እገምታለሁና ሥጋ ለባሹ የእንደራሴዬ አፈ ቀላጤ የአሰባሳቢዉ ምክርቤት ጸሐፊ ንግግር እንድታስተዉሉትና የማን ስራ አስፈጻሚና ፈጻሚ መሆኑን እንድታዉቁ እንሚከተለዉ ንግግሩን አቀርባለሁ፡፡ « እኛ የገንዘቡ ጉዳይ ሳይሆን ዋናዉ ቁም ነገር ሕዝቡ ሁሉ ከኛ ጎን በጋራ መሰለፉና አንድነት መፍጠሩ ነዉ፡፡ ይህም በየመስሪያ ቤቱ ጭምር

ስለተረጋገጠልን፤ በስጦታ የተሰጠን የአንድ ወር ደሞዝ ወደ ቦንድ እንዲለወጥ አድርገናልና እንግዲህ ሳትሰቀቁ በየዓመቱ የአንድ ወር ደሞዛችሁን በኛ ዘንድ አስቀምጡ:: እኛ እስካለን ድረስ ነዉና የቦንድ ዋስትናችሁ፤ በዉስጥም በዉጭም የኛን ደኅንነት ለመጠበቅና ለማስጠበቅ ታጥቃችሁ መነሳትና መንግስታችሁን ኢህአዴግን በመደገፍ በቆራጥነት እንድትሰለፉ ነዉ ጥሪያችን» ያሉት በቂ ማስረጃ እንደሚሆን አምናለሁ::

ሌላዉ የቅርቡ ጥናት የሚያሳየዉ ባሪዬ መንግስቴ «ጨርቅ ነዉ» እያለ የናቀዉንና ያስናቀዉን ሰንደቅ ዓላማ ለማክበርና ለማስከበር ቆርጦ መነሳቱ ነዉ:: መቼስ እናንተ ትምክህተኞች ለክልላዊ መንግስታቶቼ ያቀዳጀዋቸዉን ነጻነትና ነጻ መንግስትነታቸዉን የሚያዉጁበትን ሰንደቅ ዓላማዬን ብታጣጥሉና የአሸናፊዎች አሸናፊ የሆነዉን ኮኮብ ዓርማዬን ከፍ አናደርገዉም ብትሉም፤ እድሜ ለዉድ አገልጋዮቼ በመላዉ ፌደራልዊና ክልላዊ መንግስታቶቼ ዘንድ ከፍ ብሎ እንዲዉለበለብ አዋጅ ወቶልኛል:: እናንተ « የዲያብሎስ እንደራሴ የሆነዉ መንግስት ያመጣዉን የዲያብሎስ ዓርማ ኮኮብና የጎጥ ሰንደቅ ዓላማ የሆነዉን አናዉለበልብም፤ አባቶቻችን ያስረከቡንን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማችን ብቻ ነዉ የምናዉለበልበዉ» የምትሉትን ደግሞ፤ ብልሁና አስተዋዩ እንደራሴዬና እንደቦይ ዉኃ ወደ ወሰዷቸዉ የሚነዱት ባለሟሎቼ እንደወንጀለኛ የምትቀጠሩበትን አዋጅ ስላወጡ «ወዮላችሁ!» ከማለት ዉጭ ሌላ ምንም አልላችሁም::

8. ሌላዉ ጥናቴ ተማርን እያሉ ራሳቸዉን የተለየ ቦታ ላይ ያስቀመጡ ሰዎች ምንም ከማያዉቁት «አልተማሩም» ከሚባሉት ሰዎች ጋር ቅራኔ መግባታቸዉን ነዉ:: ይኸዉም አልተማሩም ተብለዉ የተፈረጁት ሰዎች «አሁን ክልል ተብሎ በቋንቋ የተከፋፈለዉ ቦታ ከዛሬ መቶ፣ ሁለት መቶ፣ ሶስት መቶ፣ አራት መቶ፣ አምስት መቶ፣ ስድስት መቶ.. ወዘተ ዓመት አሁን ሰዉ በሚኖርበት ቦታ ላይ አሁን ያሉት ሰዎች ቀርቶ ዘር ማንዘሮቻቸዉ ያልኖሩበት፤ በደንና በአራዊት የተሞላ፤ ሕዝቡ እየበዛ ሲሄድ ምድሪቱ የኢትዮጵያዉያን ናትና በምድራቸዉ እበዙ፣ እየሰፉ በመሄዳቸዉ አሁን ያላችሁበት ቦታ ላይ መኖራችሁ እየታወቀ «ይህ ያንተ ክልል አይደለም፣ ይህ ያንተ ክልል ነዉ፤ ..ወዘተ» በመባባል እርስ በእርስ በጥላቻና በግድያ

በመከፋፈል እንዲኖሩ ያደረጋችሁት እናንተ «ፊደል ቆጥረናል፣ ተምረናል፣ አዋቂዎች ነንና እናዉቅላችኋለን፤ »የምትሉን ናችሁ::

እስከዛሬ ድረስ እኛም ባለማወቅ የእናንተ ዐመጻና ግፍ ተግባር ላይ ተሳታፊና ተባባሪ ሆነን ቆይተናል:: አሁን ወደ ልባችን ስንመለስ ግን የስልጣን እድሜያችሁን ለማስረዘምና የራሳችሁን መሰሪ ተግባር ለመፈጸም መሆኑን በደንብ ተረድተናል:: ስለዚህ የኢትዮጵያዉያን ያልሆነ ክልል ካላ ከፈለጋችሁ እዚያ ሄዳችሁ ኢትዮጵያዉያን ያልሆኑትን አስተዳድሩ:: እኛ ግን እግዚአብሔር በሰጠን ምድር ላይ እንኳን ኢትዮጵያዊዉን ቀርቶ ኢትዮጵያዊ ያልሆነዉ ባዕድ በሚገባ እናኖራለን፤ የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ እናደርገዋለን:: ሁሉም የአንዱ እግዚአብሔር ፍጥረትና ልጆች እንዲሁም የአዳም ዘሮች ናቸዉ:: በእግዚአብሔር ፊት እንደልጅነታቸዉ ከኖሩ «ልጆቼ» የሚባሉ በእኩልነት የሚታዩ፤ ከካዱት ደግሞ እንደ ሰይጣናት ተቆጥረዉ «ዐመጸኞች» የሚባሉ፤ ሁሉም እኩሉ የሆኑና በእኩልነት የሚታዩ ናቸዉ:: » በማለት ምሬት በተሞላበት ንግግርና ግሳጼ ጭምር በማቅረባቸዉ ነዉ::

የተማሩት ግን ይህ አባባላቸዉ ያስቆጣቸዉና ይልቁንም « በመጀመሪያ ደረጀ «ይህ እግዚአብሔር ሰጠን» የምትሉት ምድር በራሳችሁ የፈጠራችሁት ሐሳባዊ እምነት ሲሆን:: ይህች መሬት ከብዙ ቢሊዮን አመታት በፊት በአጋጣሚ የተፈጠረችና እናንተም በቀስ በቀስ ለዉጥና እድገት(በኢቮሊሽን) አማካይነት ከጦጣ መሰል እንስሳነት የተለወጣችሁ፤ የጥንት አባቶቻችሁ አዳምና ሔዋን የምትሏቸዉ ሳይሆኑ ከሚሊዮን አመታት በፊት ኒያንደርታንና ግሮማግነን የተባሉ ከአሁኖቹ ጉሬላና ዝንጀሮ እንዲሁም ጦጣ ጋር ተቀራራቢ የሆኑ ሲሆን፤ ከዚያም ለምን ያህል ዘመን እንደኖሩ መረጃ ማቅረብ ባይቻልም እንደሰዉ የጥንታዊ ጋርዮሽ ስርዐት ለዘመናት ከኖሩ በኋላ በባሪያ አሳዳሪና በፊዉዳል ስርዐት አልፋችሁ አሁን ለትልቁ ማዕረግ ለአብዮታዊ ዴሞክራሲና ለካፒታሊስት ስርዐት በቅታችኋል:: ለዚህም ፈጣሪ የምትሉትን ሳይሆን ተፈጥሮንና መንግስታችን ኢህአዴግን ልታመሰግኑ ይገባል::

የቋንቋ መለያየት በተመለከተ እናንተ እንደምትሉት የሰዎች የክፋት፣ የዐመጻ፣ የክህደትና የርኩሰት ተግባር ሲያይል እግዚአብሔር እንዳይግባቡና አንድ እንይሆኑ አድርጎ በመቅጣቱ «የኃጢአት ዋጋ ነዉ» ያላችሁት ሳይሆን፤ ተፈጥሮ አንዳንዴ ራሱ በራሱ

ለመደሰትና ለማስደሰት ሰዎች በቋንቋ እንዲለያዩ ስለተደረገ ነዉ:: በኛ በቁሳዉያን ዘንድ «ጽድቅ፣ ኩኔነ ፣ ምንትስዬ» የሚባል ነገር የለም እንጂ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በባህል፣ በአኗኗር ደሀ ሀብታም፣ መሃይም አዋቂ፣ ተቃዋሚ ፓርቲ መንግታዊ ፓርቲ፣ ጥቁር ነጭ ፣ ሴት ወንድ፣ ታላቅ ብሔር ታናሽ ብሔር ፣ ታላቅ ጎሳ ታናሽ ጎሳ፣ ታላቅ አጥነት ታናሽ አጥንት.. ወዘተ በሚል መለያየቱ የጽድቅ ዋጋ ነዉ:: ተለያይተዉና ተከፋፍለዉ፣ በመጋጨትና በመጣላት እንዲሁም በመቀዋወም መኖራቸዉ ልዩ ዉበትና የተፈጥሮ ሕግ ነዉ::

በዚህ ሕግ «አልኖርም፣ አልመራም» የሚል ካለ ደግሞ ተፈጥሮን የሚቃረን ስለሆነ በምድር ላይ እንዲኖር ሆነ እንዲሰራ፣ እንዲመላለስ ስለማይፈቀድለት ዘመኑን በእስር ወይንም በመሞት፣ ወይንም በመራብና በመጠማት፣ ወይንም በችግርና በስደት ባጠቃላይ በስቃይ እንዲኖር ይፈረድበታል:: ስለዚህ « እኛ የአዳም ዘር ነን፣ የኖህ ልጆች ነን፣ የወንድማማቾቹ የካም የሴም የያፌት ነገድ ነን፣ እንዲሁም የሶስቱ ነገድ ዉህድ የሆነዉ ኢትዮጵያዊ ነን፣ ከሁሉ በላይ የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጆች ነን::» ብትሉ በአገርና በመንግስት ላይ ክህደት እንደፈጸማችሁ ተቆጥሮ እናንተ «የዲያብሎስ ሕገ መንግስት » በምትሉት በታላቁ ሕገ መንግስታችን የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከ መንገንጠልና ማስገንጠል ድረስ አዋጅን በያዘዉ መሰረት አስፈላጊ እርምጃ እንወስድባችኋለን» በማለት ማስፈራሪያ በተሞላ ንግግር ምላሽ ሰተዋል::

«አላዋቂ» የተባሉትም « አይ አንተ ፈጣሪ ምኖቹን ነዉ ያዘዝክብን፤ አንደበታቸዉ የሰላ፤ በኃይላቸዉና በጦራቸዉ የሚመኩ፤ አንተን የካዱና የናቁ እብሪተኞች፤ ብለዉ ብለዉ የጦጣ ዘር ናችሁ ይበሉን! » በማለት አንብተዉና እንባቸዉን ወደ ሰማይ ሲረጩ፤ በፌደራልና ፈጥኖ ደራሽ እንዲሁም በልዩ ኮማንዶ የታጀቡት እንደራሴዎቹና ባለሟሎቹ እዚያ በመሳሪያቸዉ አርከፍክፈዉ ከምድሬ ያሰናብቱልኛ ብዬ ስጠብቅ፤ የተወሰኑትን በሞት ፍርድና በእድሜ ልክ እስራት፣ የተወሰኑትን በአምሳ አመት፣ ያልተናገሩትን ነገር ግን አብረዉ የታዩትን በአስር አመት፣ በሽብርተኛነትና ሕገ መንግስቱን በመጣስ በሚለዉ አንቀጽ

በሹመኞቻቸዉና በቅጥረኞቻቸዉ በሐሰት ተወንጅለዉ ስላስፈረዱባቸዉና በመልስ ንግግራቸዉ ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በተወሰነ ደረጃ በአገልጋዮቼ ደስ ያለኝ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ልገልጽላቸዉ እወዳለሁ::

ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ ልደሰት እችል የነበረዉ፤ ራሳቸዉን ከዘረኝነትና ከጎጠኝነት ለይለተዉ በኢትዮጵያነታቸዉ ብቻ የሚያምኑ ሰዎች፤ ዲያብሎሳዊ ስርዐቴን አደጋ ላይ የሚጥሉ ናቸዉና እንኳን ደፍረዉ የተናገሩትን ቀርቶ ያሰቡትን ሁሉ ወዲያዉ ከዚህች ምድር ያጠፉልኛል ብዬ ተስፋ አድርጌ ነበርና:: በኋላ ግን ቁጣዬ ሲበርድ « አሃ! ለካስ ሥጋ ለባሽ መሆናቸዉን ዘንግቻለሁ» በማለት በእርምጃቸዉ ደስታዬን ሙሉ ለማድረግ ጥሬያለሁ:: ይኸዉም አሳቤ አሳባቸዉ ቢሆንም ከታላላቅ መንግስታቴ የሚያገኙት እርዳታ እንዳይቀርባቸዉ በሕግ ሽፋን እርምጃ መዉሰድ እንዳለባቸዉና አካሄዳቸዉ ፈሊጥ የተሞላበት መሆኑን ስላስተዋልኩ ነዉ::

9. በኢትዮጵያ የፖለቲካ ዘርፍ ሙሉ ተወካይ የሆነዉ ኢህአዴግ መንግስቴ ከእዉነተኛ መረጃ መራቁ በጥናቴ ተረጋግጧል:: ይኸዉም ከስድስት ሚሊዮን በላይ አባላት እንዳሉት ቢገልጽም፤ በዚህም ቢፈነድቅም፤ አጫፋሪዎቹም ቢያሽረግዱም፤ እዉነታዉን በደንብ ስለማዉቅ እኔ አልተቀበልኳቸዉም:: ምክንያቱም እንኳን ስድስትና ሰባት ሚሊዮን አባላት ቀርቶ በመቶ ሺህ እንኳ የሚቆጠሩ የኔን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም በቆራጥነት የቆሙ የሉሙ:: እጅግ ብዙዎቹ ለሆዳቸዉ፣ ለስልጣን፣ ለጥቅም ፣ለክብር ሲሉ ኅሊናቸዉን የሸጡ ናቸዉ እንጂ ቀን ዞር ስትል ወዲያዉ ግልብጥ የሚሉ ለኔ እንደልቤ ያልሆኑ ናቸዉ:: ለዚህም ነዉ ወደ ዋና መሪነትና አመራርነት እንዲሁም ስራ አስፈጻሚነት የማላመጣቸዉ:: ነገር ግን ኅሊናቸዉን በመሸጥ የዐመጻና የክህደት ስራ አስፈጻሚ በመሆናቸዉ እንደ ብቃታቸዉ ደረጃ በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን ፣ በክልል፣ በፌደሬሽንና በተወካዮች ምክርቤት፣ እንዲሁም በተለያዩ መስሪያ ቤቶች በወንበር ላይ እንዲምነሸነሹ እፈቅድላቸዋለሁ:: ማንኛዉንም ድርጊት ለመፈጸም ሙሉ በሙሉ ቆራጦች ከሆኑ ደግሞ ከፍ ወዳለዉ የስልጣን ወንበር አመጣቸዋለሁ::

መቼስ በኔ ዘንድ ኀዘኔታ ባይኖርም ዋናዉ የአገሪቱ መሪና ባለስልጣኖቹ በኔ በሸዋጁ ዲያብሎስ መንፈስ እንደሚመሩ ያላስተዋሉ፤ እንደነሱ ሥጋዊ መንግስት ለመመስረት ሌት ተቀን የሚጥሩ ሰዎችና እንዳንዶች ደግሞ የኢትዮጵያዊነት ስሜትና የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር አስገድዷቸዉ የሕዝቡ መበደል አንገብግቧቸዉ « ሕገ መንግስቱ የመናገር፣ የመጻፈ ነጻነት ሰቶናል » በማለት በቃልም፣ በጽሑፍም የመንግስቴን ገበና ሲገልጡ፤ ቂመኛዉ መንግስቴ ካለምንም ማስጠንቀቂያ በድብደባ፣ በእስር፣ በግድያ፣ ሀብትና ንብረት በመዉረስ፣ በማሳደድ፣ ፍዳቸዉን ሲያሳያቸዉና ሲያሰቃያቸዉ በማየቴና « ምነዉ እንደአንዳንዶቹ «ተቃዋሚ» ተብለዉ ለመንግስቴ ጥብቅና እንደሚቆሙትና ለመገለባበጥ እንደማይቸገሩት ሰዎች ቢሆኑ ፍርዱ ይቀልላቸዉ ነበር» በማለት ነዉ የማዝንላቸዉ::

እንግዲህ እናንተ ተቃዋሚዎች ሥጋዊ መንግስት ለማቋቋም ቆርጣችሁ በመነሳታችሁ በኔ ዘንድ ተቀባይነት ያለዉ ሲሆን፤ ወደ ወንበር ለመምጣት የመጀመሪያዉ መስፈርት ሙሉ በሙሉ የኔን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ዝግጁ መሆን ይጠበቅባችኋል:: በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ይህንኑ የዘረኝነትና የጎጠኝነት ስርዐት ተጠብቆ በብሔር ብሔረስቦች ክልላዊ መንግስታቴ ስር ሆኖ ለመተዳደር ፈቃደኝነታችሁን በግልጽ ልታሳዉቁኝ ይገባል:: በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ የምትሰሩት የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባር ከኢህአዴግ መንግስቴ ቢያንስ በሃምሳ ፐርሰንት መብለጥ ይጠበቅባችኋል:: ከዚህ ዉጭ ግን ከራሳችሁ ምኞትና ሐሳብ ጋር የተደበላለቀ ስልትና እቅድ ካላችሁ በኔ ዘንድ ሞገስ ለማግኘት እንደምትቸገሩ እየገለጽኩ፤ አማራጭ ሳጣ ግን ለወደፊት ዉሳኔዬን ላሻሽል እንደምችል ከወዲሁ አሳዉቃችኋለሁ::

በኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግስት ለመዘርጋት በተስፋ ያላችሁ ግን ለእናንተ ምንም አይነት አስተያየት የለኝም:: ምክንያቱም ምንም አይነት በአንድነት ሆነ በህብረት ለመስራት የሚያስችል ስልት ሆነ እቅድ ያልነደፋችሁ፣ ተስፋችሁ ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊ አድርጋችሁ የምትኖሩ፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ብቻ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የተዘጋጃችሁ፣ አንዲት ክፍት ቦታ እንኳ ለኔ ያልተዋችሁ ጨካኞች በመሆናችሁ ነዉ:: እኔም በሥጋዊ

መንግስቴ አንዲት ክፍት ቦታ ለእናንተ የማልሰጥ መሆኔን በተለመደዉ ባዶ ቀፎ በሆነዉና በእብሪት ንግግሬ በዚሁ አጋጣሚ እገልጽላችኋለሁ።

10. ሌላዉ ጥናቴ ምስጥ እንደበላዉ ግንድ ሊገነደስ አንድ ጎሙስ የቀረዉ ኢህአዴግ መንግስቴ፤ የክፋት፣ የተንኮል፣ የበቀል፣ የጥላቻ፣ የዘረኝነት፣ የጎጠኝነት ተግባር የበለጠ አጠናክሮ የስልጣን እድሜዉን ማስረዘም ሲገባዉ፤ «የህዳሴ ግድብ፣ የአምስት አመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን፣ የሰንደቅ ዓላማ ቀን» እያለ፤ የብሔር ብሔረሰቦችን መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል የሚለዉን ችላ ማለቱ ዉድቀቱን ማፋጠኑን ጠቋሚ ምልክት ሆኖ አግኝቸዋለሁ።

በዚሁ ለዘብተኛነት ተግባር ከቀጠለ ግን ገበናቸዉን ከመግለጽ ወደ ኋላ የማልል እንደሆንኩ ሊያዉቁ ይገባል። ይኸዉም በዋናዉ ድርጅቴ «ወያኔ ወይንም ሕወሐት» በመባል በሚታወቀዉ ዉስጥ የተሰባሰቡት ወርቃማ ባለሟሎቼ ከማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በላይ ለኢትዮጵያዊነት፣ ለእዉነተኛዉ ሰንደቅ ዓላማ፣ ለተዋህዶ ሃይማኖት፣ ለኢትዮጵያ ፊደልና ለብሔራዊ ቋንቋቸዉ ጥብቅና ሊቆሙና እስከ ሰማዕትነት ድረስ መስዋዕት ሊከፍሉ ሲገባቸዉ «የእሳት ልጅ አመድ» እንደሚባለዉ በተቃራኒ ጎራ ተሰልፈዉና በአራቱም ማዕዘን ያሉትን ኢትዮጵያዉያንን አስተባብረዉ ከላይ የተገለጹትን ለማጥፋት መሰለፋቸዉ ነዉ። ይህ ለማስደንገጫ ነዉ እንጂ እጅግ ብዙ የሆነዉን ሌሎቹን ገበናችዉን አሁን መግለጽ አልፈልግም። በአቋማችሁ ከጸናችሁና የመጨረሻ ግቤን ኢትዮጵያዊነትንና ተዋህዶ ሃይማኖትን ማጥፋት ካልቻላችሁ ግን ሙሉ ገበናችሁን ለዓለም ገልጬ እንደልቤ ለሚሆኑ ቡድኖች ወንበራችሁን አሳልፌ እሰጣለሁ።

11. ሌላዉ ጥናቴ የሚያሳየዉ እንደራሴዎቼና ምርጥ ባለሟሎቼ ምንም እንኳን በሃያ አመቱ እቅዳቸዉ መሰረት ሃምሳ በመቶዉን ብቻ ቢያከናዉኑም ቀሪ ያልተከናወኑትን ቢያንስ በአንድ ዓመት ዉስጥ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ያደርጉታል በሚል ተስፋ ያከናወኑትን ታላላቅ የተፈጸሙና በመፈጸም ላይ ያሉትን ተግባራት እገልጽላችኋለሁ።

ሀ.ትልቁ መመሪያቸዉ የነበረዉ የቋንቋ ክፍፍልና በጎጥ ማደራጀት በተወሰነ ደረጃ ተሳክቶላቸዉ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና በሁለተኛ ደረጃ ትምህር ቤት የሚማሩ

ተማሪዎች ሳይቀር በኢትዮጵያዊኛ ቋንቋቸዉ አማርኛ መናገር አይደለም ራሳቸዉን ማስተዋወቅ የማይችሉ ትዉልዶችን መፍጠር ችለዋል፡፡ ለዚህም እድል የበቁት ተማሪዎች ጠቅላይ ሚንስትሩንና ፕሬዘዳንቱን እንዲሁም ከላይ እስከታች ያለሁትን ባለስልጣናትንና ኃላፊዎችን « ብሔራዊ ቋንቋችን የሆነዉን አማርኛን እንዳንማርበት፣ እንዳንነጋገርበት፣ የስራ ቋንቋ እንዳናደርገዉ፣ ከዚያም በላቀ ሁኔታ ራሳችንን እንዳንገልጽበትና በንግግራችን ዉስጥ እንኳ ባዕድ ቋንቋ የሆነዉን እንግሊዘኛዉን ቃላት ስንቀይጥ ምንም የማይመስለን አማርኛን ስንቀይጥ እንድንሸማቀቅና ትችት እንዲቀርብብን በማድረጋችሁ አድናቆታችንን እንገልጻለን፡፡

አሁን ደግሞ የምንፈልገዉ እናንተና ልጆቻቸሁ እኛን ከምትመሩበት መመሪያ በተለየ ሁኔታ ዉስጥ ስላላችሁ ይኸዉም የአፍ መፍቻ ቋንቋችሁን እርግፍ አድርጋችሁ በመተዉ፣ አገሪቱን እንድንጠላ ባደረጋችሁት ቋንቋ እየመራችሁንና ስብሰባዎችን ሆነ ሌሎች ስራዎችን በዚህ «የበከተ ቋንቋ» ባላችሁት እየተነጋገራችሁበትና ለመሪነት፣ ለኃላፊነት በቅታችሁበት እኛን ዱዳ ማድረጋችሁ አግባብነት ስለሌላዉ፤ ኢትዮጵያዊ ያልሆነዉን ቋንቋ እንግሊዘኛን የአገሪቱ ቋንቋ እንድታደርጉልን፡፡ እናንተም ተጠሪነታችሁን ለእንግሊዝ መንግስት እንድታደርጉ፡፡ እንዲሁም የስራም፣ የመማሪያም፣ የመነጋገሪ ቋንቋዉ በመላዉ አገሪቱ እንግሊዘኛ ይሁን» በማለት አሳብና ጥያቄ አቅርበዋል፡፡

መሪዎቹና ባለስልጣኖቹ ለዚህ ሲመልሱ « በመጀመሪያ ደረጃ ቅሬታችሁን በአስተርጓሚና አንዳንዶቻችሁ ደግሞ ብሔራዊ ቋንቋችሁን መናገር ተስኗችሁ በእንግሊዘኛ ቋንቋ በማቅረባችሁ ያለንን አድናቆታችንን እንገልጽላችኋለን፡፡ እኛ በቀድሞዎቹ መሪዎችና በወላጆቻችን ተጽህኖ ምክንያት ነዉ ይህን የነፍጠኞችና የትምክህተኞች ቋንቋ አማርኛን አቀላጥፈን የተናገርነዉ፡፡ ልጆቻችንም ቢሆን የኛን የወላጆቻቸዉ ስዉር ተግባር ስለገባቸዉና ብልጦች፣ አስተዋዮች ስለሆኑ እንዲሁም አገራዊና አለማቀፋዊ ራእይ ስላላቸዉ ነዉ ቋንቋዉን በጥላቻ ሳይመለከቱ የተማሩበትና የሚናገሩበት፡፡

እንግሊዘኛን ቋንቋ በተመለከተ «ምሁራንና አዋቂዎች» ስለሚያስብለንና እናንተ ላይ ለመንገሥና እንደፈለግነዉ ለመሸከርከር ያስቻለንና ታላላቅ ዶግማና ቀኖናችን የሆነዉን የማርክዚስት ሌኒዚስት እንዲሁም ሌሎች ፍልስፍናዎችን የተማርንበትና ያወቅንበት

ባለዉለተኛ ቋንቋችን ነዉ፡፡ የሁላችሁም ፍላጎት ከሆነ ይህን ባለዉለተኛ ቋንቋችን የመማሪያ፣ የመነጋገሪያና የስራ ቋንቋ በሂደት ልናደርገዉ እንቻላለን፡፡

ተጠሪነታችሁም ለእንግሊዝ መንግስት አድርጉ ላላችሁት ግን እኛ የወደፊት እቅዳችን እናንተም በጎጣችሁ ቋንቋ እንድትገደቡና ብሔራዊ ቋንቋችሁን እንዳትግባቡበት፣ እንዳትማሩበት፣ እንዳትሰሩበት ያደረግነዉ ኢትዮጵያዊ ስሜትና ፍቅር እንዳይኖራችሁ አንድነት እንዳትፈጥሩ አንዳትዋሀዱበት በማድረግ በሕገ መንግስታችን አንቀጽ 39 መሰረት የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከመገንጠል በሚለዉ ወርቃማ ሕጋችን «ትግሪያ» የምትባል አገር ለማቋቋምና ትግራዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፡፡ «ኦሮሚያ» የምትባል አገር ለማቋቋምና ኦሮሚያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፡፡ «አማሪያ» የምትባል አገር ለማቋቋምና አማሪያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፡፡ «ሱማሊያ» አገር ለማቋቋምና ሱማሊያዉያን ዜጎችን ለመፍጠር፡፡ «አፋሪያ» አገር ለማቋቋምና አፋሪያዉያን ዜጎችን ለምፍጠር፡፡ «ሐረሪያ» አገር ለማቋቋምና ሐረሪያዉያን ዜጎች ለመፍጠር፡፡ «ጋምቤሊያ» አገር ለማቋቋምና ጋምቤሊያዉያን ዜጎች ... ወዘተ ለመፍጠር ነዉ፡፡

ባጠቃላይ በብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋ መሰረት ማዕከል ያደረገ የተለያዩ መንግስታትን አቋቁመን «ኢትዮጵያ» የምትባል አገር ስለማትኖር ራሳችሁን በራሳችሁ ስለምታስተዳድሩ የራሳችሁ መንግስት ስለሚኖራችሁ የእንግሊዝ መንግስት በበላይ ሆኖ ማዘዙን አስፈላጊነቱ አልታየንም፡፡ «አዋቂ ምሁር» ለመባል የማትፈልጉ ከሆነ ደግሞ እንግሊዘኛ ቋንቋ ትታችሁ ለወደፊት ሙሉ በሙሉ ነጻነቱን እንዲጎናጸፍ በሚደረገዉ ሉዐላዊ መንግስታችሁ የማንነታሁ መገለጫና ታላቅነታችሁን በሚያሳየዉ የአፍ መፍቻ ቋንቋችሁን የመነጋገሪያ፣ የመማሪያ፣ የስራ ቋንቋ ማድረግ ትችላላችሁ፡፡

ያኔ አማርኛን አወቃችሁ አላወቃችሁ ችግር የለም፡፡ እንኳን ባለስልጣን መሆን ቀርቶ ጠቅላይ ሚንስትር፣ ፕሬዚዳንት መሆን ትችላላችሁ ፡፡ ያንቺን የነጻነት ዘመናችሁን በናፍቆትና ዝም በማለት መጠበቅ ነዉ ያለባችሁ እንጂ እኛን በሚያሳጣን ተግባርና ንግግር ዉስጥ አትግቡ፡፡ ለወደፊት የብሔር ብሔረሰቦች መብታችሁን እስከመገንጠል ድረስ እናስከብራለን

ለዚሁ ማረጋገጫ ይኸዉም በሃይማኖት አባቶች ፊት ቃል እንገባለን::» በማለት ምላሽ ሰተዋል::

የሃይማኖት አባቶችም አስተያየት የሰጡ ሲሆን፤ በመጀመሪያ እድሉ የተሰጣቸዉ ፓትርያርኩ ነበሩና የሚከተለዉን ታሪካዊ አስተያየት ሰተዋል፡ « ልጆቼ! እነዚህ መሪዎችና ባለስልጣኖች ለዚህ ወንበር ለመብቃት ታላቅ መስዋዕትነት ከፍለዉ ነዉ:: ስንቶቹ ሰማዕታት ኤርትራን ለመገንጠልና ለማስገንጠል በየዱሩና በየጫካዉ ወድቀዋል፤ ስንቱ ሰማዕት አረመኔዉን የደርግ መንግስት ለመጣል ተሰዉተዋል:: እነዚህ የምታያቸዉ መሪዎችና ባለስልጣናት በኔና በወንድሞቼ ጸሎት ነዉ የተረፉት:: ታድያ የተጋደሉለትን ዴሞክራሲ፣ እኩልነት፣ ነጻነት ፣ ፍትህ፣ የብሔር ብሔረሰቦች ነጻነትና መብት እስከመገንጠል ድረስ አሳዉጀዉላችሁ ከዚህ በላይ ምን እንዲመጣላችሁ ነዉ የምትፈልጉት? ስለ ቋንቋስ የዚህን ያህል ምን አስጨነቃችሁ፤ የሚቀርባችሁ ነገር ቢኖር የአገር መሪና ባለስልጣን እንዲሁም የሃይማኖት መሪ ሊቀጳጳስ መሆን እንጂ፤ ሰርታችሁ ከመኖር ምን የሚያግዳችሁ ነገር አለ? ለወደፊት እኛ ባንደርስበትም በነጻ መንግስታችሁ ደግሞ የአገር መሪ ሆነ ባልስልጣን መሆን ትችላላችሁ:: እነዚህ አባቶቼን ፣ እናቶቼን ፣ ወንድምና እህቶቼን መሪዎችና ባለስልጣናትን የሚያስቆጣና ያልተገባ ነገር አትጠይቁ:: በዚህ ምድር ባይመቻችሁ እንኳ በሰማይ እንዲደላችሁ ስለምናደርግ ብዙ አታስቡ፤ የሚሏችሁን ሁሉ አድርጉ::» በማለት አስተያየታቸዉን አቅርበዋል::

በመቀጠልም የሙስሊሙ ህብረተሰብ የሃይማኖት አባት የሆኑት፡ « ፓትርያርኩ ያሉትን እኔም በሙሉ የምደግፈዉና የማምንበት መሆኑን እየገለጽኩ፤ ከዚህ የምጨምረዉ የትህምክተኞችንና የጠባቦችን አስተሳሰብ ማራመድ አግባብ አለመሆኑና ከልማታዊ መንግስታችን ጋር ተሰልፈን ለአምስቱ ዓመት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ሙሉ ኃይላችንን ማዋል ይጠበቅብናል::» በማለት አስተያየት ሰተዋል::

በመቀጠልም የካቶሊኪና የልጆቻቸዉ ፕሮቴስታንት ተከታይ የሆኑት ተወካይ ሊቀ ጳጳስ «መንግስታችን የእምነት ነጻነትን ያጎናጸፈንና ራሳችንን በራሳችን እንድናስተዳድር ያደረገ ስለሆነ ዘወትር ለመንግስታችን ከመጸለይ ወደ ኋላ የማንል መሆናችንን እየገለጽን፤ ከዚሁ

መንግስታችን ጋር ከዚህ በፊት እንደገለጹት አባቶች እጅና ጓንት ሆነን ለመስራት ቃል እንደምንገባ በዚሁ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን ::» በማለት አስተያየታቸዉን ገልጸዋል::

በመጨረሻም የባህላዊ እምነት ተከታዮች ተወካይ « እኛ ዛሬ ቦታ ተሰቶን ከነዚህ አባቶች እኩል እንድንታይና የፈለግነዉን አምልኮ በነጻነት እንድንፈጽ ያደረገዉ ኢህአዴግ መንግስትና አጋር ድርጅቶች ጭምር በመሆኑ በተለያዩ አማልክቶቻችን ስም ምስጋናችንን እናቀርብላቸዋለን:: እኛ ዱሮ ተጨቁነን ጠንቋዮች፣ አስማተኞች፣ መተተኞች፣ ሟርተኞች፣ ጨሌ አምላኪዎች፤ የቦረንትቻ፣ የዉቃቢ፣ ባለዛር፣ የአዳል ሞቴ .. ወዘተ አምላኪዎች፤ የወንዝ፣ የዛፍ፣ የተራራ አምላኪዎች እየተባል ስንቋሸሽና ስንሰደብ ነበር:: አምልኮታችንን ተደብቀንና ተሸማቀን ለማቅረብ ተገደን የነበረ ሲሆን እድሜ ለፀሐዩ መሪያችን ይኸዉ በነጻነት በየአደባባዩና በየወንዛወንዙ በከበረ መልኩ አምልኮታችንን ለመፈጸም ችለናል::

ታዲያ ይህን ነጻነትና ዴሞክራሲ ያጎናጸፈንን አብዮታዊ ዴሞክራሲ ስርዐት ለመቀልበስና የትምክህተኞችንና የነፍጠኞችን ስርዐት ለመዘርጋት ነዉ ወይ እንደዚህ ድፍረት በተሞላ ንግግር ጌቶቻችንን የምትናገሩት? እኛ ለወደፊት ስንት መታሰቢያ ልናቆምላቸዉና እንደ አማልክት ቆጥረን ለዘላለሙ ልንዘክራቸዉ ያሰብናቸዉን መሪዎችንና ባለስልጣናትን ፊት በድፍረት መቆማችሁ እንኳ እንደ ኃጢአት ስለምንቆጥር በእግራቸዉ ስር ወድቃችሁ ይቅርታ ጠይቁ::» በማለት አስተያየት ሰተዋል::

በአስተያየታቸዉ የተደሰቱት በአዳራሽ ዉስጥና በሬድዮ፣ በቴሌቭዥን ይከታተሉ የነበሩት ካድሬዎችና የኢህአዴግ አባለትና ደጋፊዎች፣ ከተቀመጡበት በመነሳት ለሰላሳ ደቂቃ በላይ ሲጨፍሩ፣ ሲዘፍኑ፣ ሲሽልሉ፣ ሲሳሳሙ፣ ሲያጨበጭቡ፣ ሲጨባበጡ፣ ሲስቁ ሲፈነድቁ ተሰተዉሏል::

**12.** ሌላዉ ጥናቱ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት በአብዛኛዉ ከታላላቅ አድባራት እስከ ገጠር አብያተ ክርስቲያናት ድረስ በኃላፊነትና በቁልፍ ቦታዎች ላይ የሚሾሙት ከሃይማኖቷ መሪ ከቅድስነታቸዉ የተነሳ ከእግዚአብሔር እኩል «ቅዱስ አባታችን» ተብለዉ ከሚጠሩትና ከቢጤዎቻቸዉ ተከታይ ሃይማኖት መሪዎች ጋር በተለያየ ጥቅማጥቅም የተገናኙና ከምእመናን የሚገኘዉን ገንዘብ፣ ሀብትና ንብረት ላይ በተለያየ መንገድ

እንደሚፈነጩበትና እንደሚቀራመቱት ከዉስጥ አዋቂ መረጃ የቀረበ ሲሆን፤ እኔም የጨለማዉ ገዥ አንዳች ተጨማሪ መረጃ ሳይስፈልገኝ ማን ከማን ጋር፣ በምን መልኩ ጭምር እንደሚቀራመቱትን በምእመኑ ላይ እንደሚያላግጡ እንዲሁም እዉነተኛ የሆኑትን ለአምላካቸዉ የታመኑን እግዚአብሔር መፍራት ያለባቸዉን አገልጋዮችን እንዴት አድርገዉ ፍዳቸዉን እንደሚያሳዩ ገና ከአሳብ ደረጃ የማዉቀዉ ስለሆነ ያልተሟላ ብዙ የጎደለዉ መረጃ እንደቀረበ እየገለጽኩ፤ ነገር ግን የምርጦቼ ገበና በመጋለጡ ቅር የተሰኘዉ መሆኔን በዚሁ አጋጣሚ ለማሳወቅና ሌሎች ታላላቅ ምስጢራቸዉንና የርኩሰት ገበናቸዉን እንዳይወጣ መገዶቹን ሁሉ እንደምዘጋላቸሁ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

13. ምእመናን በሚሰጠዉ መንፈሳዊ አገልግሎትና በሚያዩት ስነ ምግባር ችግር መመረራቸዉን በጋራ በመሰባሰብ ለሚመለከተዉ ቅሬታቸዉንና ጥያቄያቸዉን አቀረቡ፡፡ ይኸዉም « እኛ መንፈሳዊ ሕይወታችን እንዲጎለብት እግዚአብሔርን ደስ አሰኝተን ገነት መንግስተ ሰማያትን ለመዉረስ በቅን ሐሳብ፣ በመልካም ተግባር፣ በእዉነተኛ አምልኮ ለመመላለስ ደፋ ቀና ስንል በተለያዩ መንፈሳዊ መድረኮችና በቤተክርስቲያን፣ በቤተክህነት የሚታየዉ ድርጊትና ትዕይንት እጅጉን አሳዝኖናል፡፡ በተለይ ስለ እግዚአብሔር መንግስት ራሳቸዉን ጃንደረባ ያደጉ ቆብ የደፉ አገልጋዮች ለስልጣን፣ ለጥቅም፣ ለግል ብልጽግና፣ ለገንዘብ፣ ለሽልማት፣ ለክብር፣ በየጎራዉ ተቧድነዉ እርስ በእርስ ሲጣሉና ሲጠላለፉ፤ ያልሆነዉን ሆነ የሆነዉን አልሆነም እያሉ በሐሰት ሲወነጃጀሉና ሲካሰሱ በማየታችንና በመስማታችን የስምንተኛዉ ሺህ መጨረሻዉ እንደደረስ አስተዉለናል፡፡ በዘመናችን «ሞቻለሁ፣ ከዓለም ሕይወት ተለይቻለሁ፣ ሙሉ ሕይወቴን ለእግዚአብሔር ሰጥቻለሁ» ያለ ሰዉ ነፍስ ዘርቶ ለምድራዊ ኑሮዉ የሞት ሽረት ጦርነት ሲያደርግ በማየታችን እጅጉን ገርሞናል፤ አሳዝኖናል፡፡

የሚያሳዝነዉ ግን በየገዳማቱ፣ በየዋሻዉ፣ በየሸርኩቻዉ ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉ፤ ሥጋቸዉን እየቀጡ፣ ነፍሳቸዉን እያበለጸጉ፣ ለአገራቸዉና ለዓለም ሕዝብ ሌት ተቀን እየጸለዩ ፣ ሆዳቸዉ ከአንጀታቸዉ የተጣበቀ፣ የእንቅልፍ ሰዐታቸዉን ገድበዉ በጸሎት በምስጋና በሚያሳልፉ፣ የጣመዉን የላመዉን ንቀዉ በጉሮሯቸዉ የሚተናነቃቸዉን ምግብ በመረጡ፣ ባጠቃላይ በሥጋቸዉ ሰዉ ቢሆኑም በሕይወታቸዉ ሰማያዊ መላእክት በሚመስሉ መነኮሳትና

ባህታዉያን ቆብና ሕይወት መነገዱ ነዉ:: አሁን አሁንማ ቆብ የሚደፋዉ ስልጣን ለማግኘት፣ ለገቢ ምንጭ፣ ኃላፊና አስተዳዳሪ ለመሆን ስለሆነ ብዙዎች፤ እኛ ምእመናን ለመፈጸም የሚከብደንን ዝሙት ተደብቀዉና በግልጥ ሲፈጽሙ፣ አንዳንዶች ደግሞ ቆባቸዉን ወርዉረዉ ዓለማዊ ሕይወታቸዉን ሲቀጥሉ በማየታችን «ማን አስገድዷቸዉ ነዉ ቀድሞዉኑ ቆብ ያደረጉት?» እያልን ስለድርጊታቸዉ ነፍሳችን እጅግ አዝናለች::

ደግሞ በየመድረኩ «የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጠብቁ፣ አትስረቁ፣ አትዘሙቱ፣ አታመንዝሩ .. ወዘተ» እያሉ እነሱ ያልጠበቁትን ትዕዛዝ እዉነተኛ አገልጋይ ለመምሰል ያስተምራሉ:: እኛ ግን አምላካችን «የሚሏችሁን አድርጉ፣ ነገር ግን እነሱን አትምሰሉ የማያደርጉትን ያዛሉና» ብሎ ስላስተማረን፤ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ለእነሱ ብለን ሳይሆን ለኀሊናችንና ለአምላካችን ስንል እንጠብቃለን:: አንዳንዱ ኀዘናችን ሲብስ « ፓትሪያሪክ፣ ጳጳስ፣ መነኩሴ ፣ ቄስ፣ ዲያቆን ፣ ሰባኪ፣ ዘማሪ መሆን ለምን ያስፈልጋል!» እያልን እናማርራለን:: በአንድ በኩል ደግሞ እግዚአብሔርን በመፍራት በሚመላለሱ እዉነተኛ አገልጋዮች ጳጳሳት፣ መነኮሳት፣ ቀሳዉስት፣ ዲያቆናት፣ ሰባኪያን ፣ ዘማሪያን በሆኑት እግዚአብሔር በሚጠቀምባቸዉ እንጽናናለን::

አሁን አሁንማ የሃይማኖት መሪዎች ሳይቀር በሕይወተ ሥጋ እያሉ እንደ አህዛብ ነገሥታት ሐዉልታቸዉን፣ ስዕላቸዉን በየአብያተክርስቲያኑ እያስቆሙ ራሳቸዉን ከፍ ከፍ ያደርጋሉ፤ ያስመልካሉ:: እንደ ቅዱሳን ስዕል ከቅዱሳን በላይ ተሰቅሎ ምእመናኑ እንዲለማመኑበት ሲደረግ «ምነዉ ፈጣሪ ይህን ሳታሳየኝ በጠራኸኝ» እንላለን:: በየስብሰባዉ፣ በየመድረኩ፣ በየጽሑፉ ድርጊቱ አግባብ እንዳልሆነና የቤተክርስቲያን ትዉፊት አለመሆኑን ቢገለጽም ስለ እዉነት ራሱን የሚክድና በእዉነት የሚመሰክር ለአምላኩ ታማኝ ቆራጥ የሆነ አገልጋይና ምእመን ጠፍቶ በእዉነተኛዉ ቦታ ርኩሰቱ ቆሞ በማየታችን፤ በሌላዉም በራሳችን ላይም አዝነናል::

በመንፈሳዊዉም ሆነ በሥጋዊዉም ወንበር ላይ አምባገነን መሪዎች በአገራችን ሲታዩ በማየታችን በኃጢአታችንና ምርጫችንን ባለማወቃችን ምክንያት እየተቀጣን መሆኑን ተገንዝበናል:: የእግዚአብሔር ቃል ግን ስለ እዉነት ራሱን ክዶ በእዉነት የማይኖርና ስለ እዉነት የማይመሰክር እንኳን «አገልጋይ የእግዚአብሔር እንደራሴ» ሊባል ቀርቶ ደቀመዝሙርነት እንኳ አይገባዉም:: አንድፊቱኑ እንደ ዓለማዉያን አገልግሎቱን ለገቢ ማስገኛ ና ኑሮ መደጎሚያ፣ መበልጸጊያ ቢያደርጉት ፍርዱ ይቀልላቸዉ ነበር:: እነሱ ግን መንፈሳዊ

ሽፋን ሰተዉ ታላቅ ዋጋ የተከፈለበትን ቅዱስ ሥጋዉ የተቆረሰበትን ክቡር ደሙ የፈሰሰበትን መስቀልን ያህል ይዘዉ ስለ ዓለማዊ ነገር ሲመሰክሩ፣ ከእዉነት ጋር የሚቃረነዉን የመንግስትን ስራ ሲያስፈጽሙ ይታያል፡፡ በዚህ ምክንያት ራሳቸዉ ተሰናክለዉ ሌሎችንም በማሰናከል ላይ በመሆናቸዉ ከገሃነመ እሳት ቦታ የከፋ ሌላ ቦታ እንዲዘጋጅ አምላካቸዉን እየተፈታተኑት መሆኑን ይሰማናል፡፡

ከሁሉ የሚያሳዝነዉና የሚገርመዉ ደግሞ የራሳቸዉ በደልና ዐመጻ አንሷቸዉ እዉነተኛ አገልጋዮችን በሐሰት እየወነጀሉ ማሳሰራቸዉ፣ ማሳደዳቸዉ፣ ማስገደላቸዉ፣ ማሰደባቸዉ፣ ማስደብደባቸዉ ነዉ፡፡ የሃይማኖቱ መሪማ « ልጅ ካለ ማንም ምንም ሊያደርገኝ አይችልም» እያሉ ሲፎክሩ ይደመጣሉ፡፡ እኛ ግን የሥጋ ትምክህት ከንቱ መሆኑና ዐመጸኞችና ከሃዲዎች እንኳን ሌላዉን ሊታደጉ ቀርቶ ራሳቸዉን ሊያድኑ እንደማይችሉና መታሰቢያቸዉም ከምድረ ገጽ እንደሚጠፋ፤ በተቃራኒዉ ደግሞ በእግዚአብሔር የሚታመኑና የሚመኩ ሰዎች ሰማይ እንደ መጅ መሬት እንደ ወፍጮ ቢጣበቁ እንኳ አንዳች እንደማይሆኑ ነዉ፡፡ ባጠቃላይ አሁን ወደ እርሶ የመጣነዉ ለዉጥ እናገኛለን ብለን ሳይሆን የተሰማንን ቅሬታ ለማቅረብና ተስፋ የምናደርገዉ እግዚአብሔርን ብቻ መሆኑን በመግለጽ ምእመኑ በምህላ ጸሎቱን፣ እንባዉን ለማቅረብ በየአብያተክርስቲያኑ ሲሰባሰብ እንዳይከለከሉ ለማሰሰብ ነዉ እዚህ ተሰባስበን የመጣነዉ » በማለት ለሚመለከተዉ አካል ተወካይ ቅሬታቸዉን ያቀረቡ ሲሆን፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ ግን አካሄዳቸዉ ስላላማረኝ በሃይማኖቱ መሪ አማካይነት በማንኛ ዉ ቤተክርስቲያን ምህላ እንዳይደረግ አሳዝዣለዉ፡፡

14. አንዳንድ ማኅበራትና ምእመናን የቤተክርስቲያን ነገር አሳስቧቸዉ « በአሁን ሰዐት ፈተና ዉስጥ ነዉ ያለነዉ፡፡ መናፍቃንና ከሃድያን ከዉጭ በተለያየ መልክ የሚፈታተኑንና የሚያጠቁን አንሶ፤ በቤታችን ዉስጥ ተመሳስለዉ በየአብያተክርስቲያኑ ዉስጥ ተሰግስገዉ የቤተክርስቲያናችንን እምነት፣ ስርዐት፣ አሰተምሮ፣ ትዉፊት በመለወጥ ላይ ናቸዉ፡፡ ሲያስፈልጋቸዉ ፈጹም እግዚአብሔር የሆነዉን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን «እግዚአብሔር አትበሉ» ድንግል ማርያምንም «ወላዲተ እግዚአብሔር አትበሉ» እንደፕሮቴስታንቱ «የሱስ ዉይንም ኢየሱስ» በሉ፡፡ «እግዚአብሔር የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ስም ብቻ ነዉ፡፡» በማለት የንስጥሮስን ትምህርት ያስፋፋሉ፡፡ ሲፈልጉ አምላካችን መድኃኒታችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚለዉ ስም ብዙ የማንቀርቀሪያ ማንጠልጠያ ስለበዛበት «አንድ የሱስ (ኢየሱስ)» በሉ ይላሉ፡፡ እመቤታችን እመ አምላክ ቅድስት ድንግል ማርያም ማለታችሁን ተዉና «ማርያም» በሉ፡፡ መዝሙርም በተመለከተ «ሕዝቡን መሳብ የሚችለዉን ዘፈን ዘፈን ቢልም ዘምሩ፣ ያሬዳዊ ዜማ ነዉ አይደለም እያላችሁ አትቸገሩ ዋናዉ ሕዝቡን መሰብሰብ

ነዉ:: ሌላዉ ወግ መጠረቅ ነዉ እንጂ ወንጌል አገልግሎት አይደለም:: በጸሎቱ ሆነ በቅዳሴዉ በምስጋናዉ ለማርያም የሚቀርበዉ ምስጋና በዝቷልና ይቀነስ:: ጾሙም ቢሆን የሰዉ ስርዐት ነዉ እንደፈለጋችሁ ብትሆኑ ችግር የለዉም፤ ኢየሱስ በቅዱሳን ስም ተሸፍኗል ወንጌል አይሰበክም...ወዘተ» እያሉ የእናት ቤተክርስቲያን አስተምሮ፣ እምነት፣ ስርዐት ወደ ፕሮቴስታንትነት በመለወጥ ላይ በመሆናቸዉ አስፈላጊዉ እርምጃና ማስተካከያ እንዲወሰድ:: እነዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለመነገድ የሚፈልጉ ናቸዉ እንጂ ቤተክርስቲያናችን ከመሰረቷ እስከ ጉልላቷ ድረስ ክርስቶስን የምትሰብክ ፣ ሌት ተቀን ስሙን የምትጠራና የምታመሰግን ናት::

በእነዚህ የመናፍቃን ቅጥረኞች ልትጠቃና ልትታደስ አይገባም:: እኛ በሕይወታችን መታደስና በንስሐ መታጠብ ወደ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መቅረብ ይጠበቅብናል እንጂ እንደ መናፍቃኑ ቤተክርስቲያናችንን የዳንኪራና የዘፈን አዳራሽ ለማድረግ መነሳሳት የለብንም:: ስለዚህ እናንተ የሃይማኖት አባቶች ለቤተክርስቲያናችን በቆራጥነት መቆም አለባችሁ::» በማለት ቅሬታቸዉንና አስተያየታቸዉን ቢሰጡም የተወሰኑት አባቶች በኀዘን ያዳመጧቸዉ ሲሆን፤ በሃይማኖቱ መሪ የተወከሉት ግን « እናንተ ቤተክርስቲያናችን ቤተክርስቲያናችን ትላላችሁ ነገር ግን ቤተክርስቲያናችን  የኛም እናንተ የምትቃወሟቸዉም አገልጋዮች ጭምር ናት ለአንዱ እናት ለአንዱ የእንጀራ እናት አይደለችም:: ስለዚህ የመናፍቃን ቅጥረኞችና ተሐድሶዎ ናቸዉ ማለት አትችሉም::» በማለት አፋቸዉን አዘግተዉልኝ ስለመለሷቸዉ፤ እኔ በመልሳቸዉ በመደሰቴ ቀጣይ እርምጃ አላስወሰድኩም::

15. አንዳንድ ኢትዮጵያዉያን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ኮከብ አርማ ካልተደረገ  በወንጀል እንደሚያስቀጣ በአዋጅ በመደንገጉ ስጋት አድሮባቸዉ « በአንገታችን ላይ ያለዉ ማህተብ (ክር) አረንጓዴ ቢጫ ቀይ የሆነ አባታችን ኖኅ ከእግዚአብሔር የተቀበለዉን ቃል ኪዳን የሚያመላክትና ከሰባቱ ኪዳናት አንዱ ስለሆነ ኮከቡን እንዴት አድርገን ማስቀመጥ ስለተቸገርንና በሰማይ ቀስተ ደመና ላይ ያ ኮከብ ተስሎ ማየት ስላልቻልን አንድ መፍትሔ ቢሰጠን?» በማለት ከሌሎች ጥያቄዎች ጋር  ለተወካዮች ምክር ቤት አቅርበዋል::

የምክር ቤቱ ኃላፊም « ጉዳያችሁን ለተከበረዉ የተወካዮች ምክር ቤት አቅርበን መፍትሔ እናሰጣችኋለን:: ነገር ግን የተወካዮች ምክር ቤት አባላት ሆኑ ባለስልጣናቱ እንዲሁም ካድሬዎች መሪያቸዉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ መንፈስ ስለሆነ፤ ብዙ ከመድከማችሁ በፊት አፋጣኝ ምላሽ ለማግኘት በቀጥታ ጠቅላይ ሚኒስትሩን ብትጠይቁ የተሸለ መሆኑን

እገልጽላችኋለሁ:: በጣም ከቸኮላችሁ ደግሞ እኔም የምመራዉ በሷቸዉ መንፈስ ስለሆነ መልሳቸዉን እንደሚከተለዉ አቀርብላችኋለሁ::

ኮኮብ አርማቸዉ ከትግል ዘመን ጀምሮ ከግብር አባታቸዉ የተቀበሉት የሚመሩበት መንፈስ ኃይል ስለሆነ በዚህ ለዉጥና ማሻሻያ የሚያደርጉ አይመስለኝም:: ቢበዛ «ለምን የግብፅን ቀይ ነጭ ጥቁር ሰንደቅ ዓላማ ወይንም የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰንደቅ ዓላማ አትጠቀሙም ነዉ የሚሏችሁ:: በጣም አስተያየት ካደረጉላችሁ ደግሞ ኮኮብ ዓርማዉን በልባችሁ ሰሌዳ ላይ ከሳላችሁና መስቀሉን ከልባችሁ ካወጣችሁ በፈለጋችሁት ክር ማኅተም አድርጋችሁ መጠቀም ትችላላችሁ:: ዋናዉ አረንጋዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ከልባችሁ መመንገሉን ነዉ የሚፈልጉት::

ሌሎቹን ጥያቄዎች ባታነሱ ጥሩ ነበር:: ምክንያቱም ቀደም ሲል እንደነገርኳችሁ የተወካዮች ምክር ቤት አቋምና ዉሳኔ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አቋምና ዉሳኔ ነዉ:: የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ እንደማለት ነዉ:: ሲፈልጉ ባለስልጣኖቻቸዉንና ካድሬዎቻቸዉን « በማያስፎግር መልኩ ብትሰርቁ፣ ብትበለጽጉ ራሱ የስራ ጥበብ ነዉና ችግር የለዉም» ይላሉ:: ሲፈልጉ ከሳቸዉ አስተሳሰብና አመለካከት ዉጭ የሆነዉን አባላቸዉን በአንድ ምሽት አርቅቀዉና በአንድ ቀን አጽድቀዉ ሕጋዊ ሽፋን ሰተዉ በፀረ ሙስና ብቀላን ያካሄዳሉ:: ሲፈልጉ «አሰራረቅህ ዐይን ያወጣነዉ ብልጠት የለበትም ነገር ግን ታማኜ ስለሆንክ ሌላ ስልጣን እሰጥሃለዉ» ብለዉ ከፕሬዘዳንትነት ወደ አፈ ጉባኤነት ይለዉጡሃል:: ሲፈልጉ «ታማኝነትህ አጠራጣሪ ነዉ፤ ለጥቂት ጊዜ ከስልጣንህ ትገለላለህ፤ ታማኝነትህ ከተረጋገጠ ደግሞ የበለጠ ስልጣን ይሰጥሃል::» በማለት ከፕሬዘዳንትነት ወደ ከንቲባነት ይለዉጠሃል:: ሲፈልጉ «ታማኝ ከሆንክ ማሃይምም ብትሆን ትሾማለህ» ይሉሃል:: ሲፍልጉ« በብሔር ብሔረሰብ ተዋጽኦ ነዉ የምንሾመዉ» ይላሉ:: ሲፈልጉ «የቁርጥ ቀን ልጆችን በእሳት የተፈኑትን ወርቆችን ነዉ የምንሾመዉ ይላሉ::» ሲፈልጉ «እዉቀትና ብቃት ያላቸዉን ነዉ የምንሾመዉ» ይላሉ:: ባጠቃላይ ተለዋዋጭና ተገለባባጭ አቋም ስለሚያሳዩ አፋችሁን ከማበላሸትና ራሳችሁን ለበቀል ከመዳረግ ሌሎቹን ጥያቄ ባታቀርቡ የተሻለ መሆኑን እመክራችኋለሁ::

ትንሽ ሰዉ ይታዘበኛል የማይሉ ጎሊናቸዉን ያደነደኑ መሆኑን እናንተ ከኛ በላይ ታዉቃላችሁ:: ባለፈዉ ዓመት ሀብት ማስመዝገብ ብለዉ ሕዝቡን መሸንገላቸዉንና ማስመሰላቸዉን እንኳን እናንተ እኛም ታዝበናቸዋል:: እኛ ታላላቅ ባለስልጣናት የተባልነዉ ሰዎች የሰራነዉን ስራ በደንብ እያወቅን እንደ ንጹህ ሰዉ በቴሌቭዥን ቀርበን ፈርመናል:: እንኳን የኛ ገበና ቀርቶ የእሳቸዉና የቤተሰባቸዉ ገበና ዓለም ያዉቀዋል:: ብቻ እሳቸዉም ሆኑ

እኛ ኅሊናችንን እየሸጥንና እያገለባበጥን ባለጊዜነታችንን ተጠቅመን ይህን ሕዝብ እንደፈለግነዉ እናደርጋለን:: በስሙ እንነግድበታለን::

አሁን ያቀረባችሁት ከመጀመሪያዉ ጥያቄያችሁ ጋር የተያያዘዉ « በልብሳችን ላይ የሚታየዉ ኮኮብ የሌለበት ሰንደቅ ዓላማ ምን እናድርግበት?» ላላችሁት፤ ሊመልሱላችሁ የሚችሉት « እንደ ሰንደቅ ዓለማዉ ኮኮቡን መሃሉ ላይ ለጥፉብትነዉ» የሚሏችሁ:: ለዚህም በ፳፻፬ (2004) ዓ.ም. የብሔር ብሔረሰቦች ሰንደቅ ዓላማ ቀን ሲከበር በየልብሱ ላይ ኮኮብ አርማዉን በደንብ የተመለከታችሁት ይመስለኛል::

ሌላዉ «በሰንደቅ ዓላማችን ላይ መለኮታዊ ዓርማችን የዲያብሎስን ኃይል ድል የምናደርግበትን ሞአ አንበሳ ያለበት ሰንደቅ ዓላማ ወደ ኮኮቡ በምን መልኩ እንለዉጠዉ?» ላላችሁት መንፈሳችን የማይፈልገዉን በኛ ዘንድ ባትጠሩ መልካም ነዉ:: መሪያችንንም ባትሰድቡብን ፍላጎታችን ነዉ:: «ሞአ አንበሳ» ላላችሁት ዓርማ እኛ ባለስልጣኖች ሆን ካድሬዎች የማንፈልገዉ፤ ከሰንደቅ ዓላማዉ እንዳስወገድነዉ ከሌሎች ቦታና ስያሜዎች ቀስ በቀስ ለማጥፋት ነዉ በአምስቱ አመት እድገትና ትራንስፎርሜሽን ዉስጥ የያዝነዉ:: ለዚህ ማስረጃ ይሆናችሁ ሰንድ አንበሳ ባስ እያላችሁ ትጠሩት የነበረዉን የኛ መንፈስ የሚፈልገዉና የተለያየ ግብር የምናቀርብለት የኮኮቡ ባለቤት የግብር አባታችን የሚስማማዉን ስያሜ ቢሾፍቱ ባስ በማለት እየለወጥን ነዉ:: ስለዚህ ይህ «ሞአ አንበሳ»( አሸናፊ አንበሳ) የምትሉት ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረዉ ስያሜ ከኛ የአሸናፊዎች አሸናፊ ስለማይበልጥ በሰንደቅ ዓላማዉ ላይ ሆነ በየመስሪቤት መገልገያ ወረቀቶች ላይ የመሪያችን መንፈስ ያዘጋጀልንን ኮኮብ ከፍ ከፍ እናደርገዋለን፤ እናስመልከዋለን፤ እኛም «ኃይላችን ድል ማደረጊያችን ነዉ» ብለን እንመካበታለን:: ዞሮ ዞሮ ጥያቄዎቻችሁ ሁሉ እኔንም ስላላስደሰተኝ ከዚህ በኋላ ላነጋግራችሁ ሆነ ልመለከታችሁ ፈቃደኛ አይደለሁም::» በማለት በቁጣ አይን እያያቸዉ ጠያቂዎቹን አሰናብተዋል:: እኔም በመጨረሻዉ ምላሽ ስለረካዉ ቀደም ሲል ዉዱ እንደራሴዬ መሪያቸዉን ስላሙ የተናደድኩባቸዉን ይቅር ብያቸዋለሁ::

16. ብዙዎች አባቶችና እናቶች « ለዚህ ጸያፍ ስድብ ሕግ ይዉጣልን:: አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ከፍ አድረጎ ያዉለበለበና የዲያብሎስን ዓርማ ኮኮብ አላዉለበልም የሚል ግለሰብ እንደ ወንጀለኛ እንዲቀጣ በተከበረዉ የተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀ፤ ለምን «እናትህ እናትሽ እንዲህ ትሁን፤ አባትህ አባትሽ እንዲህ ይሁን» እየተባለ በየቦታዉ የወለዱ እናትና አባት ሲሰደቡ፣ ሲዋረዱ ለምን ጥብቅ ሕግ አይወጣም? እናንተ ወላጅ የሌላችሁ ሰዎች ናችሁን?» በማለት ቅሬታቸዉንና ጥያቄያቸዉን ለፍርድ ቤት አቅርበዋል::

የፍርድ ቤቱ ኃላፊም፤ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደተላኩና እንዳልተላኩ ካረጋገጡ በኋላ « እኛ እንኳን ይህን ተራ ነገር ቀርቶ ከባድ ጉዳይ እንኳ ከአገሪቱ መሪ ወይንም ከተወካዮቻቸዉ መመሪያ ካልተሰጠን በቀር በወንጀል መጠየቅ ሆነ መክሰስ አንችልም። ከእነሱ ከተነገረን ግን የሞት ፍርድ ፍረዱ ብንባል እንኳ ከመፍረድ ወደ ኋላ አንልም።» በማለት ሲመልሱ፤ ከቅሬታ አቅራቢዎች ከሥጋዊዉም ከመንፈሳዊዉም እዉቀት ያላቸዉ አንድኛዉ አባት ተነስተዉ «እግዚአብሔር እናንተን ለፈራጅነት በዚህ ወንበር ያስቀመጣችሁ እንደሱ ሆናችሁ እንድትፈርዱ ነበር። ነገር ግን ለኅሊናችሁ ታማኝ ሆናችሁ ስለ እዉነት መፍረድና መቆም ሲገባችሁ በጥቅማ ጥቅምና በበላይ ባለስልጣኖች ልዩ ትዕዛዝ ያልበደለዉና ያላጠፋዉን እንደበደለኛና እንዳጥፊ ትፈርዱበታለችሁ። በደለኛዉንና አጥፊዉን ነጻ ታወጣላችሁ። ደሀ ተበደለ ፍርድ ተጓደለ የሚል አካል በመጥፋቱ እርስ በእርስ ከበላይ ኃላፊዎቻችሁና ጌቶቻችሁ ጋር ተባድናችሁ ሕዝቡን ታስጨንቃላችሁ፤ ትበድላላችሁ።

እናንተ ብቻ ሳትሆኑ አቃቤ ሕግና ጠበቃ የተባሉትም ስለ እዉነት በጋራ ተሰልፈዉ ወንጀለኛዉ በወንጀሉ እንዲጠየቅና አግባብ ያለዉ ቅጣት እንዲያገኝና ንጹህ ደግሞ በንጽህናዉ ነጻ እንዲወጣ ማድረግ ሲገባቸዉ፤ ስርዐቱ የዲያብሎስ ነዉና በሁለቱም ወገን የሐሰት ማስረጃ በማሰባሰብና በማቀናበር ተቃራኒ ተግባር ይፈጽማሉ። መረጃ ማቅረብ ያልቻለና አሳቡን በደንብ መግለጽ የማይችል ተበዳይ እንደተበደለ እየታወቀ አይፈረድለትም። በተቃራኒ ደግሞ በዳይ በደሉ እየታወቀ በጉቦና በዘመድ አዝማድ በደሉ እንዲዳፈንና ለሌላ በደል እንዲዘጋጅ ይደረጋል። በእግዚአብሔር ስርዐት ብትመሩ ኖሮ ዳኛዉም ጠበቃዉም አቃቤ ሕጉም ስለ እዉነት ብቻ በመቆም የእግዚአብሔርን ፍርድ ትፈርዱ ታስፈርዱ ነበር። ነገር ግን ብዙዎቻችሁ ለእንጀራችሁ ብቻ ያደረችሁ ስለሆነ ገቢ ማግኘታችሁን እንጂ ስለ እዉነት አትቆሙም፤ አትፋረዱም። እናንተ እዉነተኛ ፍርድ መፍረድ አልቻላችሁምና ለእዉነተኛ ፈረጅ ዳኛ ሁሉን በእኩልነትና ካለ አድሎ ለሚዳኘዉ አምላክ አቤት እንላለን።

ማስተዋሉ ቢኖራችሁ ቃሉ የሚለዉ እንኳን ይህን ጸያፍ ስድብ የሚሳደብ ቀርቶ ማንኛ ዉንም ሰዉ በድህነቱ፣ ባለመማሩ፣ «ደሃ ቡቱታም ማሃይም ደንቆሮ» ብሎ የሚሳደብ የሸንጎ ፍርድ እንደሚገባዉና ዐይነ ስዉሩ አያይም ብሎ የሚያላግጥበትና ደንቆሮዉም አይሰማም ብሎ የሚሳደበዉን ባጠቃላይ በአካለ ስንኩልነቱ ምክንያት የሚሳደበዉን ተሳዳቢን ደግሞ ምድራዊ ፍርድ ብቻ ሳይሆን ሰማያዊ ፍርድ ገሃነመ እሳት እንደሚጠብቀዉ ነዉ ቃሉ የሚያስተምረዉ። ምክንያቱም ያላገጠዉና የተሳደበዉ እነዚያ የማያዩትንና የማይሰሙትን ወይንም ጉዳት የደረሰባቸዉን ሳይሆን የእነሱን ፈጣሪ አምላክ ነዉና። ታዲያ የወለደች እናት በማህፀን ዉስጥ እያለ የተለያዩ ስቃይ ስሜቶችን ተቋቁማና ታግሳ፣ አምጣ ወልዳ፣ ተንከባክባ

አሳድጋ፣ በጸያፍ ስድብ ስትሰደብ እንዴት የበለጠዉ ምድራዊ ሆነ ሰማያዊ ፍርድ አይገባም! እናንተ ግን እንኳን ስለስድብ ስለ ርኩሰት ተግባር ደንታ የላችሁም:: ዐመጻና ክህደት፣ ርኩሰት ለሚፈጽሙትና ለሚያስፈጽሙት የዲያብሎስ እንደራሴዎችና ባለሟሎች ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ታጥቃችሁ የተነሳችሁ ስለሆነ ከእንግዲህ ኀዘናችንና ብሶታችንን ለአንድዬ እንሰጣለን እንጂ ለመጉላላትና «ምነዉ ጉዳዬን በፍርድ ቤት ባላቀረብኩ» ብለን ለማማረር ወደ እናንተ አንደርስም፤ አንመጣም» በማለት ከዚህ በፊት ብዙ መጉሏሏት ደርሶባቸዉ ነበርና እንባቸዉን ወደ ሰማይ እየረጩ ከሕዝቡ ተለይተዉ ሄዱ:: እኔ የጨለማዉ ገዥ ግን በመጉላላታቸዉና በፈራጆቹም ዉሳኔ ደስተኛ ነበርኩ::

ሌሎቹ በዉስጣቸዉ ብዙ ብሶት ነበረባቸዉና « እኛ በየቀበሌዉ፣ በየክፍለ ከተማዉ፣ በየማኅበራት ማደራጃዉ፣ በየመስሪያ ቤቱ ስንሄድ በግርግዳ ላይ እንደ አስርቱ ትዕዛዛት «ግልጽነት፣ ታማኝነት፣ ቅንነት፣ሀቀኝነት፣ ሕዝብን ማገልገል፣ አድላዊነትን አለመፈጸም፣ ተጠያቂነት፣ ምስጢር መጠበቅ፣ አመራር ሰጪነት፣ ሕግ መጠበቅ.. ወዘተ» የሚሉ ወርቃማ ቃላቶችና መመሪያዎች ቢለጠፉም በተግባር የሚፈጸመዉ ተቃራኒዉ ነዉ:: ሕዝቡ ሁል ጊዜ ሲጉላላ፣ ሲማረር፣ ሲያነባ፣ ሲጮኽ፣ መከራና ፍዳዉን ሲበላ፣ አድሎና በደል ሲፈጸምበት ነዉ የሚታየዉ:: ታዲያ እነዚህ ሕዝቡን የሚያስመርሩና በባለ ጉዳዮች መጉላላት ደስ የሚሰኙ - የሰይጣናት የግብር ወንድምና እህቶች ለተወሰኑ ሰዎች በዘመድ አዝማድና በገንዘብ እንዲሁም በበላይ ትዕዛም መመሪያ ጭምር እየጣሱ ጉዳያቸዉን የሚፈጽሙ የሚያስፈጽሙ ናቸዉ:: ለሌሎች ግን መመሪያ እንኳ እየፈቀደ የሆነ ያልሆነ ምክንያት እየፈጠሩ ጉዳያቸዉ እንዳይፈጸም እንቅፋት የሆኑ ናቸዉ:: ታዲያ ሕዝቡን በማጉላላታቸዉና አድሎና በደል በመፈጸማቸዉ የአባልነት መታወቂያ አላቸዉና ማንንም ሰዉ ሆነ አለቃቸዉን እንኳ አይፈሩም:: አቤት ለማለት ወደ ዋናዉ ኃላፊዎች ስንሄድ ደግሞ «እነሱን ማግኘት ማለት እግዚአብሔርን ማግኘት ነዉና አትልፉ ዉሳኔያቸዉ ዉሳኔያችን ነዉ» በማለት በአንድ በተንኮል፣ በክፋት፣ በበደልና በዐመጻ መንፈስ እንደሚመሩ ስለሚነግሩን ተስፋ በመቁረጠ መፈጠራችንን እስከምናማርር እንደርሳለን:: ደግሞ ለሕዝብ የሚቀረቀርና የሚያስብ መንግስት ያለ ይመስል በየግድግዳዉ « ከልማታዊ መንግስታችን ጎን ተሰልፈን የማንፈታዉ ችግርና ድህነት፣ የማኅበራት ጥያቄ ..ወዘተ የለም» በማለት ተለጥፏል:: እረ ተዉ እናንተ ሆዱ አምላኩ የሆናችሁ ሰዎች!

እኛ በመሃይም እዉቀታችን እንኳ ነገሮችን በሚገባ እናመዛዝናለን፤ እናገናዝባለን፤ ለሕዝብ የሚበጀዉን እናዉቃለን:: እናንተ ግን በትዕቢት ለመደንፋትና ለማንጓጠጥ፣ ለመሳደብ

ወደ ኋላ የማይሉትን አንዳች እግዚአብሔር መፍራት የሌለባቸዉን ሌባ፣ ቀማኛ፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ወንበዴ የሆኑትን በእኛ ላይ ትሾማላችሁ:: እናንተ በበላይ እየመራችዋቸዉ መከራችንንና ሐሳራችንን ታሳዩናላችሁ:: እንደ እዉነቱ ከሆነ እናንተ የምትጠየቁት በአስሩ ትዕዛዛትና በስድስቱ ቃላተ ወንጌል ብቻ ሳይሆን በየግድግዳዉ ላይ በጻፋችሁትና በተግባር ባልፈጸማችሁት ጭምር ነዉ:: ለእናንተ ፍርዱ ይብስባችኋል::» በማለት ተመርረዉ ሲናገሩ ሕዝቡ ሁሉ የተመረረ ነበርና እንባዉን እያነባ ለምህላና ለጸሎት ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲያመሩ አንድ ጠና ያሉ እናት « ምነዉ ሥጋዊዉ ሆነ መንፈሳዊዉ የስራ ቦታዎች አገልግሎታቸዉ ማጉላላት እንደሌለበት የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ጽ/ቤት ቢሆን እኛም ተማረን ወደ ፈጣሪ አቤት ለማለት አንመጣም ምስጋናን ብቻ ነበር የምናቀርበዉ» በማለት አብረዉ ተጉዘዋል:: እኔ የጨለማዉ ገዥ ግን ሕዝቡ በመጉላላቱ፣ አድሎና በደል ስለተፈጸመበት እነዚያ «የሕዝብ አገልጋይ ነን» ብለዉ በስሙ በሚነግዱበት ሰዎች ተደስቻለሁ:: ለወደፊቱም በበለጠ ሕዝቡን እንዲያሰቃዩና እንዲያጉላሉ መክሬያቸዋለሁ::

17. ባጠቃለይ የ7503 ዘመን ጥናቴ የሚያሳየዉ እያንዳንዱ ቡድን ሆነ ግለሰብ ለሚሰራዉና ለሚናገረዉ ዋጋ የሚከፍለዉና የሚቀበለዉ ከምድራዊ ዘመኑ በኋላ ባለዉ ዘመን ብቻ ሳይሆን፤ በዚህች ምድር ዉስጥ ለሚሰራዉና ለሚናገረዉ መጥፎ ተግባርና ንግግር፣ ክፋትና ተንኮል፣ ጭከናና ርኩሰት ተግባር፣ ትዕቢትና ዐመጻ ጭምር በምድራዊ ሕይወት ዘመኑም ዋጋ ይከፍልበታል:: በተቃራኒዉ ደግሞ ለሚሰራዉ መልካም ተግባርና ንግግር ደግሞ በምድርም በሰማይም ዋጋ ይቀበልበታል::

ታዲያ እንዲህ ስል መልካም ስራ ስሩ፣ ጥሩ ተናገሩ ለማለት ፈልጌ ሳይሆን፤ በዚህ ምድር መጥፎ ተግባራችሁንና ንግግራችሁን በዚህ ምድር ዋጋ ብትከፍሉበት እንኳ ከሥጋ ሞት በኋላ ባለዉ ሕይወታችሁም ከኔ ከጨለማዉ ገዥ ዋጋ ትቀበሉበታላችሁ፤ በዚያም የኔን ዋጋ በክብር ታገኛለችሁ:: በተቃራኒዉ ደግሞ በዚህች ምድር መልካም ብትሰሩና ብትናገሩ፤ በምድርም መልካም ብታገኙና ዋጋ ብትቀበሉም እንኳ በኔ መንግስት ግን አንዳች ድርሻ የሌላችሁና ዋጋችሁን የማልሰጥ መሆኔን በዚሁ አጋጣሚ ለማሳወቅ ፈልጌ ነዉ::

በመጨረሻ መቼም ከኔ መልካም ምክር እንደማትጠብቁ ባዉቅም እኔም «በዚህች ምድር አንድ ቀን ለመቆየት በራሳችሁ ዋስትና የሌላችሁ፣ ከዐይን ቅጽበት በኋላ ስለሚሆነዉ በእርግጠኝነት የማታዉቁ፣ ተስፋችሁም እኔን የጨለማዉን ገዥና ምድርን አድርጋችሁ

የምትኖሩ፣ «ማፈሪያና ያበደ አእምሮ የያዛችሁ» ተብሎ ግሳጼ የደረሰባችሁ፤ እኔና እናንተ ያለን ልዩነት እኔ በረቂቅ አካል ተገልጬ በእግዚአብሔር ላይ በማመጼ እናንተ ደግሞ በግዙፉ አካል በሥጋ ተገልጻችሁ በዐመጻ ሕይወት ብቻ አይለም፤ እኔ እንኳ የእግዚአብሔርን ህልዉና ያልካድኩ እናንተ ግን በክህደትና በርኩሰት ሕይወትና ዉስጥ የምትመላለሱ፤ በፍርድ ቀን ከኔ የባሰ ፍርድ የሚጠብቃችሁ፤ ነገረ መስቀሉን ከንቱ ያደረጋችሁ፤ የወራዶች ወራዶች፣ የዐመጸኞች ዋና ዐመጸኞች ናችሁ፡፡» ብዬ አንዳንድ የኔን አገዛዝ አልቀበልም ያሉ ሰዎች እንድመሰክር የሚፈልጉትን አልናገርም፡፡ነገር ግን እናንተ ተስፋችሁ ምድርንና እኔ አድርጋችሁ የምትመላለሱ መንግስታቶቼና አገልጋዮቼ፤ የኔ አቅም እናንተ በወንበር ላይ እስካላችሁ ድረስ ለክፋት፣ ለተንኮል፣ ለጥላቻ፣ ለበቀል፣ ለዐመጻ፣ ለክህደት፣ ለርኩሰት፣ ለጭከና፣ ለግፍ፣ ለአድሎ፣ ለበደል፣ ባጠቃላይ ለኃጢአት ተግባርና ንግግር ማነሳሳትና ለዐይን ቅጽበት እንኳ ከኅሊናችሁ(ከነፍሳችሁ) ባለመለየት እንደ እምነትና አስተሳሰባችሁ ብቃት የሚመቻችሁና የምትሰናከሉበትን አሳብ ነፍሳችሁ ብቻ በምትሰማዉ ቋንቋ ሹክ ማለት ነዉ እንጂ የወንበር እድሜ ለማስረዘም አልችልም፡፡ ነገር ግን ለማሳጠር የምችል መሆኔንና ታላቅነቴን ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡ ይኸዉም የዐመጻና የግፍ ጽዋችሁ ቶሎ እንዲሞላ፣ የግፍና የጭከና ተግባር እንድታከናዉኑ በማሳሰብ እንደ ልቤ በሆነዉ ኅሊናችሁ ላይ በመንገሥ ነዉ፡፡» **ይላል የሕዝብ መጉላላት የሚያስደስተዉ የክፋትና የዐመጻ ምንጭ ጨካኙ ዲያብሎስ ከሠራዊቶቹ ሰይጣናት ጋር በመሆን፡፡**

# ክፍል አራት

## ምእራፍ አንድ

« እኔ ዲያብሎስ ከእልፍ አእላፋት ሰራዊቴ ሰይጣናት ጋር በእሳት ሰንሰለት ተጠፍሬያለሁና ሳልቀባጠርና ሳልዋሽ ተግባሬንና ንግግሬን ለኢትዮጵያዉያንና ለዓለም ሕዝቦች በድጋሜ አስተላልፋለሁ:: በዚኛዉ ክፍል ቀደም ሲል ሽፈንፈን እያደረኩ የተናገርኩትን በደንብ ገለጥለጥ እንዳደርግ ስለተገደድኩ ነዉና ሁሉን ገለጥለጥ አድርጌ ያቀረብኩት፤ ስለዚህ ምርጦቼ መሪዎች፣ ባለሟሎቼ ባለስልጣናት፣ ወዶቼ ካድሬዎቼና ደጋፊዎቼ፣ እንዲሁም ስዉራን ምርጦቼ ሰዎች ቅር እንዳትሰኙብኝ ከወዲሁ አሳስባችኋለሁ::

እናንተ የአዳም ዘር፤ ከሁሉ ከሁሉ ነፍሴን የሚያረኳት ሰዎች የትኞቹ መሰሏችሁ! ልክ በክፍል ጉብዝናቸዉ ከአንደኛ ወደ ሶስተኛ ከዚያም ወደ አምስተኛ እንደሚሸጋገሩ ጎበዝ ተማሪዎች ሁሉ ኃጢአታቸዉን አክፍተዉ የንስሐ እድሜ እንኳ እንዳያገኙ በኃጢአት ላይ ኃጢአት፣ በግፍ ላይ ግፍ፣ በዐመጻ ላይ ዐመጻ፣ በክህደት ላይ ክህደት፣ በርኩሰት ላይ ርኩሰት ወዲያዉ ወዲያዉ ፈጽመዉ በአጭር እድሜያቸዉ የሚቀጩ ሰዎች ናቸዉ:: ምንም እንኳን ናፍቆቴን ሳልወጣ ቶሎ ተለይተዉኝ ቢሄዱም በገሃነመ እሳት ዉስጥ እንገናኛለን በሚል ተስፋ እጽናናለሁኝ::

እናንተ የአሁኖቹ ባለሟሎቼ መሪዎችና ባለስልጣናት፤ «ባለ ጊዜ ነን» ብላችሁ ስታስሩ፣ ስታሰቃዩ ፣ ስታጉላሉ፣ ስታሳድዱ፣ ስትገሉ አንዳች ኀዘኔታና ርኅራኄ የሌላችሁ፤ «ነግ በእኔ ይደርሳል» ብላችሁ አንዳች ስጋት የማይገባችሁ የእኔ ምርጦችና ጀግኖች፤ የእናንተ ዐመጻ ፣ ክህደትና ርኩሰት ጽዋ ሞልቶና ፈሶ ከባለ ጊዜነታችሁ ብትሻሩ ምን ይዉጣችኋል? የት ትገባላችሁ? ምን ይደረስባችኋል? ምን ታገኛላችሁ? መልሱ ቀላል ነዉ:: ወይ እኔ፣ ወይን ጉድጓድ ይዉጣችኋል:: ወደ ሲዖል ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ትገባላችሁ:: እንደ ግፋችሁና ጭከናችሁ ደረጃ ዋጋ ትቀበላላችሁ::

እናንተ የአዳም ዘሮች፤ የኔን የጨለማዉ ገዥ ክፋትና ጭከና አስተዉላችሁ ቢሆን ኖሮ በአንድ ቀን ከኔ ጋር ያላችሁን አንድነትና ሕብረት ታቋርጡ ነበር:: ነገር ግን የልባችሁን

ደንዳናነት ስለማዉቅና ጽናትና ቆራጥነት የሌላችሁ መሆኑን ስለተረዳዉ ከዚህ በፊትም ማንነቴን ገልጬላችኋለሁ አሁንም ወደፊትም እገልጽላችኋለሁ፡፡ እኔ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከነጭፍሮቼ ሰይጣናት የምንገባዉና የምንወጣዉ ወደ እናንተ ኅሊናና አካል ብቻ ሳይሆን ወደ ሕይወት ወዳላቸዉ እንስሳት፣ አዕዋፋት፣ አራዊት ጭምርና የስልጣኔዬን ዙፋን በእነሱ ፋንድያ፣ እበት፣ ኩስ፣ አር ላይ ጭመር ዘርግቼ የምቀመጥና የምኖር መሆኔን እንድታዉቁ እፈልጋለሁ፡፡ እንኳን እነሱን አዝርዕቱን፣ እፀዋቱን፣ ቅጠሉን፣ ባጎሳቁል፤ ባበላሽ፤ ባረግፍ ምርጫዬ ነዉ፡፡፡ ምክንያቱም ሁሉም ፍጥረቶች ለእናንተ አዳም ዘሮች የተፈጠሩ ናቸዉ እንጂ ለኔ ስላልሆኑ ቅናትና ምቀኝነት አለብኝ፡፡

አዳምና ሔዋን የተባሉት ነፍሳት በጎረቤት አገር በስተቀኝ በኩል በገነት ወስጥ በምሳሌያዊ ባሕርይ (በረቂቅ አካል) ተገልጸዉ በሚኖሩበት ወቅተ በዚህች በቀድሞ ድቅድቅ ጨለማ ብቻ በተሞላባት ምድር ዉስጥ እንኳን እንስሳት፣ አዕዋፋት፣ እፀዋት አይደለም ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት .. ወዘተ በዐይን የሚታዩትም የማይታዩትም ፍጥረቶች አልነበሩሙ፡፡ እኛ ሰይጣናትና ድቅድቅ ጨለማ ብቻ ነበር የነበረዉ፡፡

ታዲያ እኔ ምቀኛዉና ክፉዉ፣ ጀግናዉ የጨለማ ገዥ በኛ ምትክ ሌላ ሕያዉ ፍጥረት መፈጠሩ ገብቶኝ ቅናት ስላደረበኝ ወደ ገነት የመግባት ፈቃድ አግኝቼ በመጀመሪያ በእንደኔዉ ምሳሌያዊ ባሕርይ (ረቂቅ አካል) የተገለጹ ሁለት ነፍሳት መኖራቸዉን ካረጋገጥኩ በኋላ እናንተ አሁን በምድራዊ ስሟ ሔዋን የምትሏት አንደኛዋን ነፍስ ጠጋ ብዬ የማታለያና የሽንገላ ሰላምታ ሰጥቻት የገነት አኗኗራቸዉን ጠየኳት፡፡ እሷም ርኅሩኅ ደግ የዋህ ነበረችና እንደ ወዳጅ ባልንጀራዋ ተመልክታኝ አንድ ምስጢር ሳትደብቀኝ አምላካቸዉ የተናገራቸዉን ሁሉ ዘክዝካ ነገረችኝ፡፡ እኔም አላማዬ የኔን ዕጣ ፈንታ እንዲደርስባቸዉ ለማድረግና ለኔም አስታያየት እንዲደረግልኝ ለመጠየቅ ስለሆነ የተንኮልና የክፋት ምክሬን « እናንተ አትብሉ የተባለችሁትን ፍሬ ብትበሉ እንደ አምላካችሁ ትሆናላችሁ እንጂ አንዳች የምትሆኑት ነገር የለም፡፡ እግዚአብሔርም ይህችን ምስጢራዊ ፍሬዉን ብትበሉ እንደሱ እንደምትሆኑ ስለሚያዉቅ ነዉ በትዕዛዝ መልክ የተናገራችሁ፡፡ እኔ ግን በግልጽ ሁሉን ስለነገርሽኝ ቅንነትሽን አይቼ ነዉ እኔም የማዉቀዉን ምስጢር ሳልደብቅ የነገርኩሽ፡፡» በማለት ልቧን

አንጠልጥዬ ሹልክ ብዬ እንደገባዉ ሹልክ ብዬ ወደ ጨለማዉ ግዛቴ ወደዚህች ምድር ተመለስኩ፡፡

ለካስ ያቀረብኩላቸዉን ፈተና በጥሩ ዉጤት አልፈዉ ኖሯልና ወዲያዉ ይህች ጨለማ ምድር የተለያዩ ፍጥረቶች ይፈጠሩባት ጀመረ፡፡ እኔም «ምን ሊደረግልኝ?» ይሆን እያልኩ ሳስብ፤ በዐይን የሚታዩትም የማይታዩትም ፍጥረቶች ተፈጥረዉ ካለቁ በኋላ በእለተ አርብ በወንድና በሴት ጾታ ሁለት ሰዎች ተፈጥረዉ ተመለከትኩ፡፡ የባሰ ቅናት አደረብኝ፡፡ በኋላ ሳጣራ ለካስ እነዚያ በረቂቅ አካል (በምሳሌያዊ ባሕርይ) ተገልጸዉ በገነት በቅዱሳን መላእክት አኗኗር ይኖሩ የነበሩት ሁለት ነፍሳት «አትብሉ» የተባሉትን ፍሬ በምኞት ተሸንፈዉ በልተዉት ኖሯልና፤ ያ የተገለጹበት አካላቸዉ ተወግዶ ይህን አሁን እናንተ የተገለጻችሁበት ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርይ የተላበሰዉን ግዙፉን ሥጋ ለብሰዉ ነዉ በዚህች ምድር ጻጋቸዉ ተገፎ፤ ከክብር አንሰዉ እንደኛ በረቂቅ ዓለም ሳይሆን በግዙፍ ዓለም እንዲቀጡ እግዚአብሔር ፈርዶባቸዉ ወደ እኛ ግዛት ዉስጥ ያስገባቸዉ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በከፋ መልኩ እኛ በረቂቅ አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) በመናፍስትነት በዚህች ምድር ዉስጥ እየተቀጣን እንገኛለን፡፡ እናንተ ደግሞ በመጀመሪያ ወላጆቻችሁ አዳምና ሔዋን ዐመጻ ምክንያት በግዙፍ አካል (ምሳሌያዊ ፍጥረት) በሆነዉ በሥጋ በሰዉነት ተገልጻችሁ በግዙፉ ምድር እየተቀጣችሁ ትገኛላችሁ፡፡

በሁለቱም ነፍሳት ዉድቀትና ቅጣት ደስ ያለኝ ቢሆንም ለኔ ግን አንዳች አስታያየት ስላልተደረገልኝ ይልቁንም ስለክፋቴና ተንኮል ምክሬ የበለጠዉን ዋጋ እየከፈልኩ በመሆኑ ቅሬታ የገባኝ ቢሆንም፤ እነሱ የኔ ባሪያ በመሆናቸዉ ግን አርክቶኛል፡፡ ነገር ግን ከእለት ወደ እለት ያደርጉት የነበረዉ ኀዘንና ለቅሶ እኔ የምቀጣበትና የምናደድበት፣ የምበሳጭበት ስለነበረ «ምንዉ እዚያዉ ገነት ኖረዉ ቢሆን ይሻለኝ ነበር» ለማለት ተገድጄ ነበር፡፡ ምክንያቱም ንስሐ ሲገቡ፣ ሲጸጸቱ እቃጠል ነበርና ነዉ፡፡ ይባስ ብሎ ደግሞ ያ ከገነት አዉጥቶ ወደዚህች ምድር አስገብቶ የቀጣቸዉ አምላክ ንስሐቸዉንና መጸጸታቸዉን ተመልክቶ ዳግም ወደ ገነት እንደሚመልሳቸዉ እንዲሁም ለተፈጠሩበት ዓላማ እኔ ከተባረርኩበት መንግስተ ሰማያት ዉስጥ እንደሚያስገባቸዉ ጭምር ተሰፋ ሲሰጣቸዉና ቃል ሲገባላቸዉ የምሆነዉንና

የማደርገዉን ነበር ያሳጣኝ:: እነሱን በገነት ገብቼ በመፈታተኔ ዋጋ ከፈልኩበት፤ እርር ድብን አልኩኝ:: እስከ አሁን ድረስ በብስጭትና በንዴት ዉስጥ ነዉ ያለሁት::

በዚህም ምክንያት ለአንድ የአዳም ዘር ሳላዝንና ሳልራራ ከህጻን እስከ አዋቂ ድረስ እፈታተናለሁ፣ አዳክማለሁ፣ አጎሳቁላለሁ፣ መከራና ችግር አመጣለሁ፣ የሕይወትን መንገድ እንዳያዉቁና እንዳያስተዉሉ፣ እንዲሁም እንዳይኖሩበት የሞት ሽረት ትግሌን አካሄዳለሁ:: አሁን አሁን ግን ተስፋዬ እየመነመነ፣ አቅሜ እየተዳከመ፣ ምስጢሬ እየተጋለጠ፣ ገበናዬ እየታወቀ፣ እዉነት ለዓለም እየተገለጸ ስለሚገኝ መጨረሻዬ የደረሰብኝ እየመሰለኝ በዋይታና በሮሮ ሕይወት ዉስጥ  እገኛለሁ::  ስለዚህ ወዳጆቼ ለኔም እዘኑልኝ፤ ራሩልኝ:: እናንተ በየጊዜዉ እንደምትራቀቁ  እኔም የጨለማዉ ገዥ ፈተናዬንና ጥቃቴን ማራቀቅ እንዳለብኝ ስላመንኩ ነዉ እንዲህ እያልኩ ልባችሁን እያራራሁ ልጫወትባችሁ ያቀድኩት::

እናንተ የአዳም ዘሮች አንድ ትዝብቴን ልግለጽላችሁ:: ይኸዉም ስንቶቹን እንደራሴዎቼን መሪዎቻችሁንና ባለሟሎቼን ባለስልጣናትን፣ እንዲሁም ዉዶቼን ካድሬዎችን ከላይ ከመሪዎች እስከ ታች ቀበሌ ድረስ ያሉትን አገልጋዮቼን ቃለ መጠይቅ ስታደርጉ እኔ የግብር አባታቸዉንና ጌታቸዉን አንዲት ቀን ለመጠየቅ ፈቃደኛ ባለመሆናችሁ ነዉ:: እናንተ ባትጠይቁኝም ከጭፍሮቼ ሰይጣናት አንዱ አንድ ቀን የጠየቀኝን ልንገራችሁ፡

« ጌታዬና አምላኬ ዲያብሎስ በዘመንህ ሁሉ እስቲ እጅግ የተደሰትክበትና ያዘንክበትን ገጠመኝህን ንገረን?» በማለት ለጠየቀኝ የሰጠሁት መልስ፤ -እስከአሁን ድረስ ልዩ ደስታ የሰጠኝ በብሉይ ዘመን የተለያዩ ኃጢአት ተግባር ዉስጥ ተሰማርተዉ እግዚአብሔርን እጅግ ያስቆጡት ሰዎች፤ አምነዉና ተጸጽተዉ እንዲድኑበት  ኖኅ መርከብ ቢሰራላቸዉም እንኳ ሊገቡ ቀርቶ  ሲያላግጡበትና ሲያሾፉበት ቆይተዉ ኖኅ ከነቤተሰቡ እና ለቀጣይ ሕይወቱ አስፈላጊ የሆኑትን ፍጥረታት ከሰዉ ተሸለዉ «እሺ እኛ ታዛዥ ነን፣ ግቡ የምትለን ቦታ ዉስጥ እንገባለን» ብለዉ ከገቡ በኋላ ኃይለኛ ዝናብ በተከታታይ ዘንቦ እነዚያ እብሪተኛ፣ ጥጋበኛ፣ አላጋጭና አሿፊ ሰዎች ዐይናቸዉ ቁልጭ ቁልጭ እያለች ከምድረ ገጽ በመቅሰፍት ሲወገዱና በንፍር ወኃ ሲቀቀሉ ያየሁ እለት ነዉ:: ምክንያቱን እነሱ በዐመጻቸዉና በግፋቸዉ ምክንያት ከምድር  ባይወገዱ ኖሮ እስከ አሁን ድረስ የሰዉ ዘሮች ቁጥር ከኛ ከሰይጣናት

ቁጥር እኩል ይሆንና ይህች ዓለም ወደ አለመኖር አልፋ  የኛም ነጻነት ተገድቦ በአንድ ቦታ በገሃነመ እሳት ዉስጥ ከቢጤዎቻችን ሰዎች ጋር እንቀጣ ነበርና ነዉ::

አሁንም እንደዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ የሚያላግጡና ዐመጻን፣ ክህደትን፣ ርኩሰትን የሚፈጽሙ ሰዎች ከምድሬ ቢጸዱልኝ ደስተኛ ነኝ:: ምክንያቱም የዚህ ምድር ዘመናችን ቆይታ ይረዝምልናልና ነዉ:: ቀደም ብዬ እንደገለጽኩላችሁ የዓለም እልፈት የሚሆነዉ የእኛ ሰይጣናት ቁጥርና የሰዉ ልጆች በምድር፣ በገነት፣ በሲዖል፣ በማረፊያ ቦታና በሰማያት ዉስጥ ያሉት ነፍሳት ቁጥር ተደምሮ እኩል በሚሆንበት ዘመን ስለሆነ፤ አሁን የዓለም ሕዝብ ከምድር በእግዚአብሔር ቁጣና በመቅሰፍት ተጠረጉልን ማለት፣ ለኛ ምድራዊ እድሜያችን ተራዘመልን ማለት ነዉ:: ሌላዉ ምክንያት ደግሞ አሁን በዓለም ላይ የሚታየዉ የርኩሰት፣ የግፍ፣ የጭከና ተግባር ቀድሞ በብሉይ ዘመን እንኳ ያላየሁት፤ እንኳን በፈጣሪ ዘንድ በኔ በጨለማዉ ገዥ እንኳ የሚዘገንን ድርጊትና ትዕይንት ስለሆነ፤ የኔም ዐይን ይህን ከማየት ታርፍ ዘንድና ይህ የለመድኩትን ኃጢአት ቀርቶ ለወደፊት ለየት ያለና ረቀቅ ያለ የኃጢአት ተግባርና ትዕይንት ተስፋ በማድረግ  የአሁን  ትዉልዶች ይደመሰሱ ዘንድ የኔም ፈቃድ ነዉ::

እዚህ ላይ « ጌታቻን አምላካችን ዲያብሎስ» የሚሉኝ ጭፍሮቼ ሰይጣናት ብቻ ሳይሆኑ እናንተ የአዳም ዘሮች በባዕድ፣ በጣዖት፣ በባህላዊ አምልኮ የምትመላለሱና በተዘዋዋሪ ደግሞ በክህደት፣ በመናፍቅነት፣ በዐመጻ እምነት ዉስጥ የምትመላለሱት ጭምር መሆኑን ብገልጽላችሁ እንደ ጎርፍ  እዉነተኛዉ አምላክ ወደ ሚመለክበት ወደ ብቸኛይቱ የሕይወት መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት ትጎርፋላችሁና በግልጽ አልነግራችሁም::

እንዲሁም እንደራሴዎቼ መንግስታትና ባለስልጣናት፤ ዐመጻን፣ ክህደትን፣ መናፍቅነትን የሚያስፋፉልኝ ስለሆነ ቅር እንዳይላቸዉ ገበናቸዉን አልገልጽም:: ዞሮ ዞሮ ሳልፈልግ የእዉነተኛዉን አምላክ ስም ለኔ ለጨለማዉ ገዥ ሰታችሁኝ ስላመለካችሁኝ እናንተዉ ናችሁ የምትጠየቁት እንጂ እኔ ማንንም ሰዉ « የዚህ አምላክ ነኝ፤ ፈጣሪ ነኝ፤ ..ወዘተ» እያልኩ አምልኩኝ አላልኩኝም:: እናንተ ናችሁ ሲያስፈልጋችሁ በጨሌዉ ፣ ሲያስፈልጋችሁ በጣዖቱ፣ ሲያስፈልጋችሁ በየወንዛወንዙ፣ ሲያስፈልጋሁችሁ በየተራራዉና

ሽሎቆዉ፣ ሲያስፈልጋቸሁ በየጠንቋዩና ዛሩ፣ ሲያስፈልጋችሁ በየመመተተኛዉና አስመተኛዉ ቤት፣ ሲያስፈልጋችሁ በየአዳራሹና በተከለለ ስፍራ የተለያየ ስም ሰታችሁኝ « ጌታቻንና አምላካችን» እያላችሁ የምታመልኩኝ፣ የምትገብሩልኝ፣ የምታመሰግኑኝ።

እኔ ግን ጥንትም፣ አሁንም፣ ወደፊትም፣ እዉነተኛ አምላካችሁ ጌታችሁ ፈጣሪያችሁ በመስቀል ላይ ዋጋ የከፈለላችሁ አማላጅ ያልሆነ፤ ነብይ ያልሆነ፤ ፍጡር ያልሆነ፤ መጀመሪያዉና መጨረሻዉ፤ ያልኖረበት ጊዜ የሌለ የማይኖርበትም ጊዜ የማይኖር፤ የአዳምና ሔዋን ፣ የሄኖክና የኖኅ፣ የመልከ ጼዴቅና የአብርሃም፣ የዮቶርና የሙሴ ፣ የዳዊትና የማክዳ፣ የነብያትና የሐዋርያት፣ የሰማዕታትና የጻድቃን ፣ ባጠቃላይ የሰዉ ዘሮች አባትና አምላክ የሆነዉ «ቃል» «ወልድ» በመባል የሚታወቀዉ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ከእርሱ ጋር በመለኮት አንድ የሚሆኑ የማያንሱት የማይበልጡት ለዐይን ቅጽበት እንኳ የማይቀዳደሙ «አብ» «መንፈስ ቅዱስ » በመባል የሚታወቁ እርሱ ራሱ የገለጻቸዉ አካላት እንዳሉ እመሰክራለሁ።

ምክንያቱም እንደእናንተ ኅሊናዬን አደንድኜ በገሃነመ እሳት ዉስጥ የባሰ ቅጣት እንዲጠብቀኝ አልፈልግም። የቀድሞ ዐመጼና ክህደቴ ይበቃኛል። ለዚያም አሁንም ዋጋ እየከፈልኩበት ስለሆነ እናንተንም በመፈታተኔ ዋጋ ስለምከፍል በእነዚህ የሚደርስብኝ ቅጣት ለእኔ በቂዬ ነዉ። እናንተ ደግሞ ነጻ ኅሊና አላችሁና የፈለጋችሁትም መምረጥ ትቻላላችሁ። ታዲያ እንዲህ ስል «አታምልኩኝ፤ አታመስግኑኝ፤ አትገብሩልኝ» ለማለት ፈልጌ እንዳልሆነ የሚገባችሁ ይመስለኛል። እናንተ በማታዩት በእሳት ሰንሰለት ታስሬ እየተቃጠልኩ ስለሆነ የምለፈልፈዉ እንደ እዉነት አድርጋችሁ እንደማትወስዱት ተስፋ አደርጋለሁ። ምክንያቱም እኔ የጨለማዉ ገዥ ካለእናንተ እንዴት ይሆንልኛል!

አሳዛኝ ገጠመኜ ደግሞ ብዙ ሲሆኑ አንዱን እንደ ምሳሌ ብገልጽ፣ በኢትዮጵያም ሆነ በዓለም አገራት ለጊዜያዊ ስልጣን፣ ጥቅም፣ ክብር፣ ዝና ሲሉ ኅሊናቸዉን ለእንራሴዎቼ መንግስታት ሲሸጡ፣ ሲገለባብጡ፣ «ጨለማዉን ብርሃን፤ ብርሃኑን ጨለማ፤ እዉነቱን ሐሰት፤ ሐሰቱን እዉነት» ሲሉ ቆይተዉ የተመኙትን ስልጣንና ክብር፣ ጥቅም ሳያጣጥሙ

ለእስር፣ ለስደት፣ ለግድያ፣ ለመከራና ለችግር የተጋለጡትን፤ የሚጋለጡትን አእምሮ ቀላሎች የሆኑ አገልጋዮቼን ስመለከት ነዉ::

ታዲያ እናንተ የተገፋችሁ ዉድ አገልጋዮቼ! ከዚህች ምድር የተመኛችሁትንና ኅሊናችሁን የሸጣችሁበትን ነገር ባታገኙም በወደፊቱ በጋራ መንግስታችን በገሃነመ እሳት ፍላጎታችሁን የማሟላ መሆኑን በዚሁ አጋጠሚ አሳዉቃችኋለሁ:: አሁን በሕይወት ያላችሁም በዚህ ተስፋ እንድትጽናኑ እመክራችኋለሁ:: ስለዚህ ስላፈዉ በደልና ግፍ ተግባራችሁ ንስሐ እንዳትገቡ:: ይልቁና ሌላ የምትበቀሉበት አጋጣሚ ካገኛችሁ እንደበፊቱ ለአዲሱ ባለወንበር ኅሊናችሁን ሽጣችሁ ኃይለኛ በቀላችሁን እንድትፈጽሙ በታላቁ በጨለማዉ ስሜ እመክራችኋለሁ::

ሌላዉ ለአዳም ዘር ለመናገር የምፈልገዉ እኔ የጨለማዉ ገዥ ስለ መንግስተ ሰማያት፣ ስለ ሲዖል፣ ስለ ገሃነመ እሳት ምስክርነትን ስሰጥ ከእኔ ስለሆነ አንዳች እንደማትጠራጠሩና ተግባራዊ እንደምታደርጉ አዉቃለሁ:: ነገር ግን ከእግዚአብሔር ምስክርነት ሲመጣ ግን ለምን ጆሯችሁ አይከፈትም? ኅሊናችሁ አይረዳም? አያስተዉልም? እግዚአብሔር « የኢትዮጵያና የዓለም የመጨረሻ ፍርድ አፈጻጸም ዉሳኔ!» በሚል አርእስት ባስተላለፈዉ መልእክቱ ላይ ግልጽ ባለ መልኩ መጀመሪያና መጨረሻ በሌለዉ አማናዊ ሕዋ ዉስጥ ያሉትን የተለያዩ ቦታዎች እንደሰማያት፣ ዓለም፣ ምድር፣ ገነት፣ ሲዖል፣ ማረፊያ ቦታ፣ ገሃነመ እሳት ቦታዎችን ቢገልጽላችሁም ለመቀበልና ለማመን ፈቃደኛ አይደላችሁም:: ይህም የኅሊናችሁ ድንዳኔ ከኔ የላቀ በመሆኑ በዚሁ አጋጣሚ አድናቆቴን እገልጽላችኋለሁ:: በተለይ እናንተ በእምነት ሽፋን ተደራጅታችሁ «ገሃነመ እሳት፣ ሲዖል የሚባል ቦታ የለም» የምትሉና «ይህች ምድር ገነት ናት» የምትሉ ሰባኬ ዲያብሎስ እናንተን ደግሞ ማድነቅ ብቻ አይደለም በጨለማዉ ስሜ እመርቃችኋለሁ::

ይኸዉም እኔ የጨለማዉ ገዥ ያልካድኩትን አምላክና ገሃነመ እሳት ከኔ ብሳችሁ «እግዚአብሔር የለም» በማለታችሁና «የሲዖልና ገሃነመ እሳት ፍርድ የለም» በማለት የአዳም ዘርን ለክህደት፣ ለዐመጻ፣ ለርኩሰት ሕይወት በማደፋፈራችሁ ነዉ:: ለእናንተ አንድ ቅኔ ብቀኝላችሁ ደስ ይለኛል::

ኦ ሰባኪ ዘመደ ርኩስ እጉየ

ፍዳ  እሳት እንተ ትወርስ ልብየ

ታዲያ ቅኔ ተቀኝቶልናል ብላችሁ እንዳትፈነድቁ:: በእግዚአብሔር ዘንድ በፍርዱ አድሎ ያለ አይምሰላችሁ:: እኔም ዲያብሎስ ሆንኩ መሰሎቼ ሰይጣናት በአንዲት ጥፋታችንና በዐመጻችን ምክንያት ነዉ ጉስቁልና ሕይወት ከሌለባት ፍጹም በሆነ በቅድስናና በደስታ ከሚኖርባት ከሰማያት ዉስጥ ተወግደን ጉስቁልና ሕይወት የሞላባት፣ ቅድስናና ደስታ የማይገኝባት እዚህች ምድር ዉስጥ ተጥለን ሌት ተቀን በስቃይ፣ በጭንቀት፣ በመከራ ሕይወት ፍዳችንን የምናየዉ::

እንዲሁም አዳምና ሔዋን በአንድ ጊዜ ስህተታቸዉና ዐመጻቸዉ ምክንያት ነዉ መራብ፣ መጠማት፣ መድከም፣ ማንቀላፋት፣ መዳህ፣ ማልቀስ፣ መዉጣት፣ መዉረድ፣ መጨነቅ፣ መስጋት፣ መጣላት፣ መገዳደል፣መሰራረቅ፣ አድሎ፣ በደል፣ በቀል፣ መለያየት፣ መከፋፈል፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ቅናት፣ ምቀኝነት ፣ ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት፣ ማዘን፣ መተከዝ፣ ባዶነት፣ መቅበዝበዝ፣ ሰላምና እርካታ ማጣት፣ መድማት፣ መቁሰል፣ መታመም፣ መሰቃየት፣ መሞት፣ ያደፉና የጎደፉ ባሕርያት የሆኑት ዐይነ ምድር፣ ሽንት፣ ላበት፣ አክታ፣ ንፍጥ..ወዘተ የመሳሰሉት ከማይታይባት፤ ሌት ተቀን በሰይጣናት ከማትፈተኑበት፤  ባጠቃላይ ያደፈ፣ የጎደፈ፣ የጎሰቆለ ባሕርይ ከማታዩበት፤ ጉስቁልና ኑሮና ሕይወት ከማይከሰትበት፤ በሙቀት ከማትቃጠሉበት፣ በብርድ ከማትኮራመቱበት፣ ዝናብና ቅዝቃዜ ከማይፈራረቁበት፣ ከፀሐይ ከዝናብ ለመከላከል መጠለያ ከማያስፈልጋችሁ፣ ችግርና መከራ  ከሌለባት ገነት ተባረዉ ወደ እዚህች ምድር የገቡትና እናንተም በእነሱ ምክንያት ሌት ተቀን እየተቀጣችሁ ፍዳችሁን የምታዩት::

እናንተ ይህ እየኖራችሁበት ያለዉን ሕይወት «ሕይወት ነዉ» ብላችሁ እርስ በእርስ እየተጣላችሁ፣ እየተከፋፈላችሁ፣ እየተለያያችሁ፣ በጥላቻ በበቀል ሕይወት ትኖራላችሁ:: በተለይ ለሐዲስ ዘመን ሰዎች ፍርዱ እጅግ ይብስባችኋል:: ምክንያቱም ታላቅ ዋጋ በመስቀል ላይ ተከፍሎላችሁ ከንቱ በማድረጋችሁ፣ እንዲሁም ምን ማድረግ እንዳለባችሁና ምን ማድረግ እንደሌለባችሁ እግዚአብሔር በሥጋ ማርያም ተገልጾ በግልጽ አስተምሯችኋልና ነዉ:: ስለ

እዉነትና ስለ እግዚአብሔር መንግስት የተለያየ ፈተናና መከራ ቢመጣባችሁ፤ ተሰዶ፣ ተዋርዶ፣ ተሰድቦ፣ ተገርፎ፣ ተተፍቶበት፣ ተገርፎ፣ ተሰቃይቶ፣ ተንገላቶ፣ በመጨረሻም በመስቀል ላይ ተሰቅሎ በትዕግስትና በጽናት እንዲሁም በአኮቴት እንድትቀበሉ ሁሉ ተደርጎበት ሁሉን ሆኖ አሳይቷችኋልና ነዉ።

እናንተ ግን ተስፋችሁን ሰማያዊ አድርጋችሁ አንድነታችሁንና ህብረታችሁን ከአምላካችሁ ጋር በመፍጠር ከዚህ እየተቀጣችሁበት ካለዉ ሕይወት ቶሎ ተገላግሎ ወደ እዉነተኛዉ መኖሪያ ገነትና መንግስተ ሰማያት ለመግባት መናፈቅ ሲገባችሁ እኔን የጨለማዉ ገዥን «በግድ ንገሥብን፣ ቀጥቅጠን፣ መከራና ስቃይ አምጣብን» እያላችሁ፤ ከኔ አልላቀቅ ብላችኋል። እኔ እንኳ እግዚአብሔር መሆኑን ያልካድኩትን ዋጋ የከፈለላችሁንና መንግስቱን ሊያወርሳችሁ ፈቃደኛ የሆነዉን አምላካችሁን ክዳችሁ እለት እለተ «አማለጅ ነዉ፤ ፍጡር ነዉ፤ ነብይ ነዉ፤ ተራ ሰዉ ነዉ፤ ሐሰተኛ ነዉ» እያላችሁ፤ በክህደት፣ በዐመጻ፣ በርኩሰት፣ ባጠቃላይ በኃጢአት ሕይወት ትመላለሳላችሁ። ታዲያ አንዳች ዋጋ ያልተከፈለልን ሰይጣናት ገሃነመ እሳት ፍርድ የሚጠብቀን ከሆነ እናንተማ እለት እለት አምላካችሁን በተግባር፣ በንግግር፣ በአሳብ፣ ባጠቃላይ በኃጢአት ሕይወት የምታስቆጡትማ እንዴት ከገሃነመ እሳት በላይ ፍርድ አይጠብቃችሁ!? እጅግ ይጠብቃችኋል። እንደ እኔ ቢሆን ገሃነመ እሳት እጥፍ ይገባችኋል።

ነገር ግን የመቀጫዉ ቦታ አንድ ቦታ ገሃነመ እሳት ቢሆንም የሚሰማን የስቃይ፣ ጭንቀት፣ ጉስቁልና፣ መከራ ግን እንደኃጢአታችን ደረጃና ንጽጽር ስለሚለያይ ፍርዱ ለኛ ለሰይጣናት ይቀልልናል። እጅግ ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት የፈጸመች ነፍስ እጅግ ልትቋመዉ የማትችለዉ ስቃይ ነዉ የሚጠብቃት። እጅግ ያነስ ኃጢአት የፈጸመች ነፍስ ደግሞ ከእግዚአብሔር ፍርድ ባታመልጥም የስቃዩ ስሜት የማይጎዳትና የምትቋቋመዉ፣ እንዲሁም በገሃነመ እሳት ዉስጥ ከመኖር ዉጭ አንዳች የስቃይና የመከራ ስሜት የማይሰማት ይሆናል። እንግዲህ እናንተ የአዳም ዘር በምሳሌ ካልተብራራላችሁ አይገባችሁምና በምሳሌ ላስረዳችሁ፡

አንድ በቀዝቃዛ አየር ጸባይ አካባቢ ተወልዶ ያደገ ሰዉ ወደ ሞቃት በረሀ አካባቢ ቢሄድ እዛ ከሚኖር ሰዉ ጋር እንዲኖር ቢገደድ ሁለቱም ሥጋ ለባሽ ሰዎች ቢሆኑም ከደጋ የመጣዉ

ሰዉ ከለመደዉ አየር ጸባይ ዉጭ ስለሆነ የሙቀቱን ግለት  መቋቋም እንደማይችልና ስቃዩ እንደሚበረታበት ሁሉ፤ በተቃራኒዉ ደግሞ በበርሀ የሚኖረዉ ሰዉ ስለለመደዉ ሙቀቱን እንደሚቋቋምና የስቃይ ስሜት እንደማይሰማዉ፤  እኛ ሰይጣናት ሆን እናንተ በኃጢአት ሕይወት በመመላለስ ዐመጻና ክህደት፣ ርኩሰት የምትፈጽሙ የአዳም ዘሮች፤ ሁላችንም ነፍሳችን በረቂቅ አካል (በምሳሌያዊ ባሕርይ) ተገልጻ፣ በምሳሌያዊዉ ባሕርይ ቦታ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ከምሳሌያዊ ባሕርይ ከሚፈጠሩት መቅጫ ከሚሆኑት ከማይጠፋዉ እሳትና ከማይሞተዉ ትል ጋር አብረን ብንኖርም የሚሰማን የስቃይና የጭንቀት መጠን እንደ ዐመጻችን ደረጃ ይለያያል፡፡

በዐመጻዉ ከመቶ 99  ነጥብ ያገኝ ሰዉ ከ90 ነጥብ ካገኘዉ ሰዉ ይልቅ ስቃዩ ይበረታበታል፤ እንዲሁም 50 ነጥብ ያገኘዉ 20 ነጥብ ካገኘዉ ሰዉ ይልቅ ስቃዩና ጭንቀቱ ይበራታበታል፤10 ነጥብ ያገኘዉ 1 ነጥብ ካገኘዉ ሰዉ ስቃዩና ጭንቀቱ ይበረታበታል፡፡ ባጠቃላይ እናንተም የህጻንነት እድሜያችሁን ጨርሳችሁ ነገሮችን ማወቅና ማመዛዘን ከጀመራችሁበት ጊዜ አንስቶ የሰራችሁት ኃጢአት፣ ንስሐ ያልገባችሁበትና ያልተጸጸታችሁበት ሁሉ የረሳችሁትም ሆነ ያልረሳችሁት በተግባርም፣ በንግግርም፣ በአሳብም ጭምር የፈጸማችሁት ተሰልቶ ነጥብ እንደሚሰጠዉና በዚያም መሰረት እንደምትቀጡ ባልነግራችሁ ደስ ባለኝ፡፡ ነገር ግን በእሳት ሰንሰለት ታስሬ እየተቃጠልኩ ስለሆነ ለመናገር ተገድጃለሁ፡፡ እንዲሁም በእዉነተኛ ንስሐ እዉነተኛዉን  ምሳሌ ያልሆነዉን መለኮት የተዋሀደዉን የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙ የተቀበላችሁ ሰዎች የምታስታዉሱትንም የማታስታዉሱትንም ኃጢአት ቅዱስ ቁርባን በተቀበላችሁ ጊዜ ከሰማያዊ ከእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ እንደሚደመሰስላችሁ ባልነግራችሁ ፈቃዴ ቢሆንም ያዉ ተገድጄ ነግሬያችኋለሁ፡፡

ታዲያ ለመምከር አልተከለከልኩምና የምመክራችሁ ነገር ቢኖር ቅጣቱን ፈርታችሁ ከኃጢአት ተግባር እንዳትከለከሉ፡፡ ንስሐ ገብታችሁ መለኮት የተዋሀደዉን እዉነተኛ የክርስቶስን ሥጋና ደም እንዳትቀበሉ፡፡ እናንተ «የክርስቶስን ሥጋና ደም ምሳሌ ነዉ እንጂ

መለኮት የተዋሀደዉ አይደለም» እያላችሁ እንደመብልና መጠጥ የምትወስዱ ሰዎች፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ ዋስትና ስለምሰጣችሁ በዚያዉ በክህደታችሁ ቀጥሉ:: እናንተ መለኮት የተዋሀደዉን ቅዱስ ቁርባን በኃጢአት ሕይወት እየተመላለሳችሁ፣ መንፈሳዊዉን አገልግሎት እንደ ስራ መስክ ቆጥራችሁ በድፍረት የምትቀበሉና የምታቀብሉ «አገልጋዮች ነን» የምትሉ ደፋሮችና ለእኔ ጀግና የሆናችሁ ሰዎች ደግሞ እዛ በአካለ ነፍስ ስንገናኝ የኒሻን ሽልማት የምሰጣችሁ መሆኑን አስቀድሜ አሳዉቃችኋለሁ::

የኔ ፍላጎትና ምርጫ እናንተ በጊንጥ እኔ ደግሞ በአለንጋ እንድንገረፍ ነዉ:: ምክንያቱም ነፍሳችሁን በፈቃዳችሁ አሳልፋችሁ ሰታችሁኛልና ነዉ:: እንኳን እናንተን ነፍሳችሁን ፈቃደኛ ሆናችሁ የሰጣችሁኝን ቀርቶ ፈቃደኛ ያልሆኑትን አንዳንድ ጊዜ በግላጭ ሳገኛቸዉ ካለፍላጎታቸዉ በህልማቸዉ ነፍሳቸዉን የማልከሰክስና የማስጨንቅ አረመኔ ጨካኝ ነኝ:: መቼስ በግላጭ ስላችሁ ሳይገባችሁ እንደማይቀር እገምታለዉ:: ምክንያቱም ባታምኑም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚመላለሱ፣ የሚወጡ፣ የሚገቡ ሰዎች የቅርብ ጠባቂ መልአክ አላቸዉና እንኳን እናንተ ግዙፎቹ ሰዎች ቀርቶ እኔ ረቂቁ ካልተፈቀደልኝ በስተቀር አንዲቱን ጸጉራቸዉን እንኳ መንካት አልችልም:: በራሴ ስልጣን ቢኖረኝ ኖሮ «ኃጢአትን አንፈጽምም» እያላችሁ የምታስቸግሩኝን ሰዎች እንቅ እያደረኩ እገላችሁ አስጨንቃችሁ ነበር:: ነገር ግን ስልጣኔ ሆነ ኃይል ተገድቧል::

እኔ የገረመኝና ሁሌ የሚያብገነግነኝ  እናንተ ጨካኞችና ዐመጸኛ ለሆናችሁ ለአዳም ዘሮች እግዚአብሔር ሰዉ ሆኖ ተገልጾ ማስተማሩ፣ መፈወሱ፣ ተአምራት ማድረጉ ሳያንሰዉ በእናንተ የተለያየ መከራ መቀበሉ፣ መዋረዱ፣ መሰደቡ ነዉ:: ክብርና ድኅነትን እንደማትፈልጉ እያወቀ ደግሞ « ይህን እዉነተኛ መብል ሥጋዬን ብሉ፤ እዉነተኛ መጠጥ ደሜን ጠጡ» ማለቱ ነዉ:: እንዲሁም እናንተን እንደ ሰዉ ቆጥሮ ስለ እናንተ ማልቀሱ ነዉ:: ከሁሉ ከሁሉ ደግሞ ይህን ሁሉ አድርጎላችሁ ከስድስት ቢሊዮን ሕዝብ በላይ እለት እለት በተግባር፣ በንግግር፣ በአሳብ በሚፈጸሙ ኃጢአቶች እያስቆጣችሁት በትእግስት ዝም ማለቱ ደንቆኛል::

እኛ የእናንተን እድል ብናገኝ ኖሮ ሌት ተቀን እግዚአብሔር በሚደሰትበት ተግባርና ንግግር ብቻ አይደለም በቅንና በንጹህ አሳብ ብቻ ነበር የምንመላለሰዉ። በኃጢአት ሕይወት ከምንመላለስና ኅሊናችንን ሸጠን ከዐመጻ ሰዎች ጋር ከምንሰለፍ በሕይወታችን ዘመን ሁሉ በኀዘን፣ በለቅሶ፣ በስቃይ፣ በችግር መኖርን ነበር የምንመርጠዉ። እንኳን አንዳች ጥቅም በማናገኝበት በጥላቻ፣ በጥል፣ በግድያ፣ በስርቆት፣ በክፋት፣ በተንኮል፣ በቅናት፣ በምቀኝነት ፣ በትዕቢት፣ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት፣ በዘረኝነት ፣ በጎጠኝነት ፣ በጣዖትና ባዕድ አምልኮ፣ በዘፋኝነት፣ በዳንኪራ፣ በመተት፣ በጥንቆላ፣ በሟርት፣ በአስማት፣ በስካር፣ በዝሙት፣ በአመንዝራነት፣ ብቻ ምኑ ተዘርዝሮ ያልቃል ባጠቃላይ ለነፍሳችሁም ለሥጋችሁም በማይጠቅም ሕይወት መመላለስ አይደለም ያለመብላትና ያለመጠጣት ጸጋዉ ቢሰጠን ዘመናችንን ሁሉ ካለመብልና መጠጥ እንኖር ነበር።

ምን ያደርጋል ታዲያ! እኛ እንደ እናንተ መሆን አይቻለንም። ምክንያቱም ሁላችንም ሰይጣናት ከኔ ከአለቃቸዉ ዲያብሎስ ጭምር በነጻ ኅሊናችን ካለምንም ተጽህኖና ፈተና በእግዚአብሔር ላይ ስላመጽን የእናንተን እድል አላገኘንም። እናንተ ግን አዳምና ሔዋን «አትብሉ» የተባሉትን በልተዉ፣ ትዕዛዝ አፍርሰዉ በዐመጻቸዉ ከገነት የተባረሩት፣ ምንም እንኳን በነጻ ኅሊናቸዉ ተመርተዉ የኔን ፈተና አለመቀበልና በእግዚአብሔር ትዕዛዝ መጽናት ቢችሉም ነጻ ፈቃዳቸዉን ተጠቅመዉ እኔን የጨለማዉ ገዥን አምነዉ በኔ ፈተና በመዉደቃቸዉና እናንተም ባላወቃችሁትና ባልፈጸማችሁት ዐመጻ በዚህ ምድር እንድትገለጹ በመደረጉ ምክንያት የምትድኑበትን እድል ተሰጣችሁ። በምድራዊ ዐመጻችሁም እጅግ ታገሳችሁ።

እናንተ ግን በተሰጣችሁ እድል አለመጠቀም ብቻ አይደለም ከአዳምና ሔዋን በላይ በዐመጻና በክህደት ሕይወት መመላለስን መረጣችሁ። ለዚህም እኔ ምስክር ነኝ። ይኸዉም ሌት ተቀን እዛዉ አእምሯችሁ(ኅሊናችሁ) ወይንም ግንባራችሁ ፊት ለፊት አንጎላችሁ ዉስጥ ያለችሁ ነፍሳችሁ ጋር መጥቼ «ይህን አድርጉ፣ እንዲህ ሁኑ፣ በራሴ ፈጥሬ እንዲህ ተደርጎባችኋልና እንዲህ አድርጉ.. ወዘተ» ስላችሁ፤ በቀጥታ የኃጢአትን ተግባር ስትፈጽሙ እለት እለት እመለከታችኋለዉና ነዉ። እናንተ ግን ለዐመጻ ተግባራችሁ ራሳችሁን

እያሳመናችሁ በኃጢአታችሁ ትጸናላችሁ። በዚህ ፈተና እንዳትወድቁ አስቦላችሁ ነበር አምላካችሁ በመዋዕለ ሥጋዌዉ በአሳባችሁ ጭምር ኃጢአት እንዳታስቡ ያስተማራችሁና ያስጠነቀቃችሁ። እናንተ ግን ነጻ ፈቃዳችሁን ተጠቅማችሁ ከቀላል ኃጢአት ጀምሮ እጅግ እስከሚዘገንን ኃጢአት ድረስ አሳባችሁን ወደ ተግባርና ንግግር በመለወጥ ትፈጽማላችሁ።

በዚህም ምክንያት እኔ የማሳስባችሁንና እናንተም የምታስቡትን የኃጢአት አሳብ ወደ ተግባር ስለምትለዉጡ በዚህች ምድር አምላካችሁ ብቻ ሳይሆን እኔም ፍዳችሁን አሳያችኋለሁ። በዚህ ቅጣቴ አምላካችሁ ዉለታዬን አስቦ የገሃነመ እሳት ፍርዱን ባይሽረዉም እንደሚያቀልልኝ ተስፋ አደርጋለሁ። እናንተ ግን በምድሩም ሳይደላችሁ ለሰማያዊ መንግስትም ሳትበቁ ከሁለት ያጣችሁ መሆኑን ሳዉቅ ነፍሴ ሐሴት ታደርጋለች። አሁንም በጭከና በግፍ፣ በርኩሰት፣ ባጠቃላይ በኃጢአት ሕይወታችሁ ጸንታችሁ ኑሩ። ለእኔም ሁል ጊዜ እንደልቤ ሆናችሁልኝ ተመላለሱ፤ የማሳስባችሁን ሁሉ ወደ ተግባር እየለወጣችሁ አስደስቱኝ እንጂ በመጽሐፈ ምሳሌ ም.፮፥ቁ.፲፮-፲፱(6:16-19) «እግዚአብሔር የሚጠላቸዉ ስድስት ነገሮች ናቸዉ። ሰባተኛዉን ነፍሴ አጥብቃ ትጸየፈዋለች፤

1.ትዕቢተኛ አይን 2. ሐሰተኛ ምለስ 3. ንጹህን ደም የምታፈስ እጅ

4. ክፉ አሳብ የሚያበቅል ልብ 5.ወደ ክፉ የምትሮጥ እግር

6. በሐሰት የሚናገር ሐሰተኛ ምስክር 7.በወንድማማች መካካል ጠብን የሚዘራ።» ተብሎ የተገለጸዉ እናንተን የማይመለከት መሆኑን አዉቃችሁ፤ በተለይ ደግሞ እግዚአብሔር አጥብቆ የሚጸየፈዉን ሰዉን ከሰዉ የምታጣሉ ምርጥ ሰዎች፤ ቅኖችና እዉነተኞች፣ እግዚአብሔር መፍራት ያለባችሁ መሆናችሁን እኔ በደንብ ስለማዉቅ በፍርድ ቀን እመሰክርባችኋለሁ።

እስቲ እናንተ የአዳም ዘር አንዲት ቀላል ጥያቄ ልጠይቃችሁ። ስንት አምላክ አለ? እንኳን እናንተ ስንት ዋጋ የተከፈለላችሁ የሰዉ ዘሮች ቀርቶ እኔ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ እንኳ አንድ መሆኑን አዉቃለሁ። እመሰክራለሁ። ታዲያ የትኛዉ አምላክ ይሆን እዉነተኛ

አምላክ? የኦርቶዶክስ ተዋህዶ? የፕሮቴስታንት? የካቶሊክ? የእስልምና? የቡድሃ? የሂንዱ? የኢሬቻዉ? የተለያዩ ባዕድና ጣኦት? መቸስ አንድ አምላክ ከሆነ የሁሉ ሊሆን አይችልም።

እናንተ ኢትዮጵያዉያን! አምላካችሁ፤ ዘመናዊ እንዴራሴዎቼ መሪዎቻችሁና ባለስልጣናት እንዳዘጋጁላችሁ « የትግሬ፣ የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የአፋር፣ የሱማሌ ፣ የሐረሪ፣ የጋምቤላ፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች» አምላክ ይሆን? ወይስ «አምላክ የሚባል የለም፤ ብዙ አማልክቶች ናቸዉ ያሉት።» ብላችሁ ነዉ የምታምኑትና የምታሳምኑት? ወይስ እዉነተኛ አምላክ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ አምላክ ነዉ ብላችሁ ነዉ የምታምኑት?

እኔ የጨለማዉ ገዥ በእሳት ሰንሰለት ባልታሰርና ባልገደድ ኖሮ እዉነተኛዉ አምላክ የሚገኘዉ በረከተ *ሥጋና* ድኅነተ ነፍስ በምታገኙት <u>በኦርቶዶክስ ተዋህደ ሃይማኖት</u> (**እግዚአብሔር በአንድነትና በሶስትነት ከሚመለክበት፣ በስም «አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ» የሚባል በመለኮት ወይንም በባሕርይ አንድ የሆነ፤ የሁሉ ፈጣሪና አስገኝ የሆነ፤ በተለየ አካሉ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከ*ሥጋዋ ሥጋ* ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ከሁለት ባሕርይ አንድ ባሕርይ ከሁለት አካል አንድ አካል በመሆን ፍጹም አምላክ ፍጹም ሰዉ የሆነ፤ እግዚአብሔር ወልድ በመዋዕለ *ሥጋዌዉ* ባስተማረዉ መሰረት የአዳምና ሔዋን ዘሮች በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም (በ*ሥ*ላሴ ስም) ተጠምቀዉ ከእግዚአብሔር በመንፈስ ዳግመኛ ካልተወለዱ በስተቀር ወደ እግዚአብሔርን መንግስት እንደማይገቡ፤ እንዲሁም የእርሱን መለኮት የተዋህደዉን ቅዱስ *ሥጋና* ክቡር ደም ያልበላ፣ ያልጠጣ በእግዚአብሔር መንግስት ሕያዉ ሆኖ መኖር እንደማይችል፣ የሰዉ ዘሮች በረከተ *ሥጋና* ድኅነተ ነፍስ አግኝተዉ ለእግዚአብሔር መንግስት ሊታጩ የሚችለዉ እምነትን ከምግባር ጋር አዋህደዉ ሲገኙ ብቻ መሆኑን የምትገልጥ፤ በአምልኮት ዉስጥ ከኢየሱስ ክርስቶስ የድኅነት ተግባር ጋር ፈጽሞ ልትለይ የማትችለዉ የሰዉ ዘሮች መዳኛ ምክንያት የሆነችዉ ድንግል ማርያም ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች በሆነ መልኩ የምትፈቀርበትና የምትከበርበት፤ እንዲሁም የእግዚአብሔር ባለሟሎችና ወዳጆች የሆኑት ቅዱሳን መላእክት፣ ነብያት ፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታትን ፣**

ጻድቃን በተለየ ሁኔታ ከሚከበሩበት) እምነት ዉጭ ባሉ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት «እምነት» ነዉ ብዬ አስተምርና እመሰክር ነበር።

አንድ ታላቅ እዉቀቴን ብገልጽላችሁ፡ ነፍሳችሁ (ኅሊናችሁ) እዛዉ አጠገቧ ሆኜ የምናገራትን የክፋትና የተንኮል ንግግር ሰምታ ወደ ተግባር ለመለወጥና ለመፈጸም የሰላ ጆሮ እንዳላት ሁሉ እግዚአብሔር የሚነግራትን ለሕይወቷ የሚጠቅማትን ለመስማትና ወደ ተግባር ለመለወጥ ፈቃደኛ አለመሆኗን ማወቄ ነዉ። ይህም የሆነዉ ልክ ለሥጋዊ ጥናቷ የተለያዩ መቀመሪያ ፎርሙላ እንደምትጠቀም ሁሉ ለነፍሷም ድምጽ በራሷ ፎርሙላ በማዘጋጀት «የምትሰማዉ ድምጽ= ቅርብ ድምጽ+ ርቀት = ዉጤት » ብላ የእኔን የጨለማዉን ድምጽ በቅርብ ርቀጥ በሚሊሜትር የአምላኳን ድምጽ ለዐይን ቅጽበት እንኳ እንደማይለያት አላወቀችም መሰለኝ ከኅሊናዋ በላይ አድጋ ስለቆጠረች በብርሃን ዓመት ርቀት አስልታዉ የትየለሌ (ኢንፊኒት) ርቀት ስለመጣባት «አልቦ(ዜሮ) ዉጤት» ብላ ልትሰማዉ አልፈቀደችምና በዚህም ምክንያት ለኔ እንደልቤ ልትሆን ችላለች።

አደራ የምላችሁ ቀላችሁ እንዳትገኙ ለኃጢአታችሁ ምክንያት «ሰይጣን ነዉ እንዲህ ያስደረገኝ» ብላችሁ እንዳትናገሩ። ምክንያቱም እኔ ማንንም አስገድጄ ኃጢአት አላሰራም። ቢበዛ በኅሊናዉ ሹክ ብዬ አሳስበችኋለሁ እንጂ፤ ለዚህም እናንተ ባትቀበሉም የኔም የእናንተም ፈጣሪ ያዉቃል። አስገድጄ ኃጢአት ባሰራችሁ ኖሮ ፈጣሪያችሁም ስለ ኃጢአታችሁ አይጠይቃችሁም ነበር፤ አይፈርድባችሁም ነበር። ነገር ግን ነፍሳችሁ በእግዚአብሔር አርአያና ምሳሌ የተፈጠረች ሕያዉ ፍጥረት ስለሆነችና የማመዛዘንና የማገናዘብ እዉቀት ስላላት እንዲሁም አምላኳን የመምሰል ብቃት ያላት ስለሆነ ነዉ ስለ ጥፋቷ እጅግ የጠበቀ ፍርድ የሚፈርድባት።» ይላል የክህደት፣ የዐመጻ፣ የርኩሰት፣ ባጠቃላይ የኃጢአት ሥራ አስፈጻሚዎች ዋና ጠቅላይ አዛዥ የክፋት፣ የጭከናና የግፍ ንጉሥ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ።

## ምእራፍ ሁለት

« እናንተ «ራስን መግዛት» የሚለዉን በተግባር መፈጸም ቀርቶ ትርጉሙን በዉል ማወቃችሁ የሚያጠራጥር ባለቆቦች ሰዎች፤ በየገዳማቱና በየዋሻዉ በአምላካቸዉ ፊት ራሳቸዉን ዝቅ አድርገዉ ሌት ተቀን በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በእንባ፣ በምስጋና የሚተጉ፤ በሕይወታቸዉ ሰማያዉያን መላእክትን የሚመስሉ፤ ለወጎኖቻቸዉና ለእናት ለአገራቸዉ እንዲሁም ለዓለም ሕዝብ የሚጸልዩና የሚያነቡ ጻድቃንን ለማስጠላትና ለማሰደብ በተቃራኒ አቋም ተሰልፋችሁ ቆቡን ስልጣን ለማግኛና ለመበልጸጊያ፣ እንዲሁም በየከተማዉ ለመከበሪያ የምትጠቀሙበት ሰዎች፤ ታላቅ ዋጋ የተከፈለበትን መስቀሉንም በኪሳችሁ ይዛችሁ በማቃለል በየጉዳንጉዱና በየምናምንቴዉ ቦታ በዝሙት የምትልከሰከሱ፤ ሲያሰኛችሁ ደግሞ ቆቡን አሽቀንጥራችሁ በመጣል ወደ ዓለም ሕይወታችሁ የምትመለሱ ምርጦቼ ሰዎች፡

እናንተን በጨለማዉ ስሜ ማመስገን ብቻ አይደለም አድናቆቴንም ጭምር ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡ «ሁለመናችንን ለእግዚአብሔር ሰተናል ፤ሌት ተቀን ለማገልገል ያመቸን ዘንድ ራሳችንን ጃንደረባ አደርገናል» በማለት ቃል ኪዳን የገባችሁለትን አምላክ ለማስቆጣት ለምድራዊ ጥቅም፣ ድሎት፣ ዉዳሴ ፣ ሽልማት፣ ሹመት ለማግኘት ከሌሎች ለዚህ ብቃት ለመድረስ መስቀልንና ወንጌልን ያህል ይዘዉ ከሚፋለሙት መሰሎቻችሁ በልጦና ልቆ ለመገኘት ስትሉ ከመግደል፣ ከማስገደል፣ በሐሰት ከመወንጀል፣ ከማሳሰር፣ ከማሳደድ፣ ከማስደብደብና ከማሰደብ፣ ከመስረቅ ከማሰረቅ፣ ወደ ኋላ የማትሉ የጀግኖች ጀግኖች በመሆናችሁ የሚሰማኝ አካል ካለ የተለየ የኒሻን ሽልማት የሚገባችሁ መሆኑን እኔ የጨለማዉ ገዥ እመሰክርላችኋለሁ፡፡

ታዲያ ቆብ ሳይደፉ፣ መስቀል ሳይዙ፣ ሌት ተቀን አምላካቸዉን በእዉነትና በመንፈስ የሚያገለግሉትን አገልጋዮችንና ምእመናን እንዳትመለከቱ፡፡ እነሱ የምድራዊ ምስጢር ያልገባቸዉ፤ ራሳቸዉን በመግዛት ከዝሙት፣ ከግድያ፣ ከስርቆት፣ ከክፋት፣ ከተንኮል፣ ከምቀኝነት፣ ከትዕቢት፣ ከክህደት፣ ከባዕድና ጣዖት አምልኮ፣ ከዘፋኝነት ፣ ከዳንኪራተኛነት፣ ከዘረኝነት፣ ከጎጠኝነት፣ ከስካር፣ ብቻ ምኑ ተነግሮ ያልቃል ለሰዉ ልጆች ልዩ የደስታ

ምንጮች ከሁኑት ከዐመጻና ከርኩሰተ ተግባር ራሳቸዉን ያገለሉና ኋለቀር በሆነዉ አስተሳሰብ በትዕግስት፣ በትህትና፣ በፍቅር፣ በደስታ፣ በሰላም፣ በቅንነት፣ በእዉነት ፣ በየዋህነት፣ በልባምነት፣ በማስተዋል የሚመላለሱ፤ ተስፋቸዉ የማይታየዉንና የማይጨበጠዉን ሰማይ ያደረጉ፤ በምድራዊ ዘመናቸዉም ካለ ሀብትና ካለ ንብረት ረክተዉ ደስተኛ ሆነዉ የሚኖሩ፤ በበረከትና በጸጋ የተሞሉ፤ የኅሊና ሰላም ያላቸዉ፤ በአንዳች ነገር የማይጨነቁ ያልታደሉ አሳዛኝ ፍጥረቶች ናቸዉ::

እንዲሁም ቆቡን ደፍተዉ፣ መስቀሉን ይዘዉ በእዉነት እየኖሩ፣ ስለ እዉነት ራሳቸዉን ክደዉ የሚመሰክሩ ፣ ከኃጢአት ሕይወት ርቀዉና በምግባራቸዉ ለሁሉ አርአያ ሆነዉ ክህነታቸዉን በሚያስከብሩ፤ ባጠቃላይ እንደ ክህነት ስልጣናቸዉ በተግባራቸዉ፣ በንግግራቸዉ፣ በአሳባቸዉ እግዚአብሔርን በመፍራት በመመላለስ ምእመናንን በሚገባ የሚያገለግሉ ጳጳሳትን ፣ ሊቃዉንትን ፣ መምህራንን፣ ካህናትን ፣ መነኮሳትን ፣ ዲያቆናትን ፣ሰባኪያንን ፣ ዘማሪያንን አትመልከቱ::

እነሱ ሞኝነት ስላጠቃቸዉ፣ መንደላቀቁንና የድሎት ሕይወትን የማግኘት እድል ስላልሰጠዋቸዉ ቂም ይዘዉብኝ ነዉ ከእናንተ ተቃራኒ ሕይወት ዉስጥ የሚመላለሱት:: እነሱ፣ ሰዎች በዚህች ምድር ዉስጥ ተዝናንተዉ፣ ዘፍነዉ፣ ጨፍረዉ፣ ዘሙተዉ፣ ደስ ብሏቸዉ እንዳይኖሩ ለማስፈራራት «ሲኦል፣ ገሃነም እሳት» የሚባል ዓለም ፈጥረዉ የሚያወሩትና «ገነት፣ መንግስት ሰማያት» እያሉ የሌሉትን ዓለማት ፈጥረዉ ወርቃማ ጊዜያቸዉን በከንቱ የሚያጠፉ ናቸዉ::

እነዚህ እንደ ልቤ አልሆን ያሉኝ ያመጹብኝ ሰዎች፤ የምርጦቼን አገልጋዮች ክህነታቸዉን ያህል አቃለዉና እንደ ሥጋ ፈቃዳቸዉ የሚመላለሱትንና በሥጋና ደም ስሜት የሚያገለግሉትን ቆብ ደፊዎችንና «ካህን ነን» በሚል ስያሜ መስቀል የያዙትን ፣ እንዲሁም « መምህር፣ ሰባኪ፣ ዘማሪ ፣ ዲያቆን ፣ ባሕታዊ» በሚል ስያሜ የራሳቸዉን ዓላማ ለማሳካትና ኑሮዋቸዉን ለመደጎም የሚሯሯጡትን፤ የሚኖሩትን አኗኗራቸዉን የማየቱ እድል ቢሰጣቸዉ ኖሮ የኔን የጨለማዉን ገዥ ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም ይተጉ ነበር

እንጂ « አምላካችንን፤ ኀሊናችንን፤» በማለት ከእዉነት ጋር ሙጭጭ ብለዉ አያስቸግሩኝም ነበር::

እናንተ ግን እነሱን ተዋቸዉ፤ በፍርድ ቀን ማን እንደሚያቀርባቸዉና ወዳጅ እንደሚያደርጋቸዉ እንተያያለን፤ ብዙ እድል ሰጥቻቸዉ ነበር በእድላቸዉ ሊጠቀሙ አልቻሉም:: እናንተ ግን እስከመጨረሻዉ በተግባራችሁና በአቋማችሁ ጽኑ፤ በርቱ፤ የመጨረሻዉ መንግስቴ ወራሽ አደርጋችኋለሁ:: ታዲያ እናንተን ብቻ አይደለም ሌሎች መስቀሉን ያሚያቃልሉልኝና መጫወቻና ማላገጫ ያደረጉልኝን ባለሚሎቼ በየደረታቸዉ አንጠልጥለዉ በዘፈናቸዉና በዳንኪራቸዉ የሚያዘልሉልኝ፤ እንዲሁም ደረታቸዉንና ጡታቸዉን ገላልጠዉ ለፀሐይና ለአላፊ አግዳሚዉ የሚያስመቱና ለዝሙት የሚያነሳሱ፣ ቅርፊት ሥጋቸዉን የሚያስመልኩ « መስቀሉን በደረታችንና በጡታችን ላይ ያደረግነዉ ታላቅ ዋጋ የተከፈለበት መሆኑን አምነን ሳይሆን ለጌጥነት ብቻ ነዉ » በማለት የሚያቃልሉልኝ ባለሚሎች ብዙ ስላሉኝ በአንድ ላይ በመጨረሻ ዋጋ እከፍላችኋለሁ:: እንደ ትጋታችሁና ድፍረታችሁ እንዲሁም እንደ ቆራጥነታችሁ ደረጃ የጨለማዉን አክሊሌን አድላችኋለሁ::

እናንተ ሌት ተቀን የኔን የጨለማዉን ገዥ ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የምትተጉ የአዳም ዘሮች ሁሉ፤ ኃያልነቴን በደንብ እንደምታዉቁና እንደምትመሰክሩልኝ አንዳች ጥርጥር የለኝም:: እንዲሁም የእናንተ ኃይልም አንዳች ለመስራት ሆነ ለመከላከል የማይችል ልምሾ የሆነ ሰዉን እንደምትመስሉ በራሳችሁ ላይ እንደምትመሰክሩ እገምታለሁ:: ምክንያቱም ሌት ተቀን ስቀጠቅጣችሁ፣ ሳሰቃያችሁ፣ ባዶነት እንዲሰማችሁ ሳደርግ፣ የኅሊና ሰላማችሁን ነስቼ ሳቅበዘብዛችሁ፣ ሳበሳጫችሁ፣ ሳስንራችሁ፣ ሳስጮሃችሁ፣ አንዳች የመከላከል ሆነ የማጥቃት ሙከራ አለማድረጋችሁና ከኃጢአት ተግባራችሁ ለመለየት አለመወሰናችሁ ነዉ::

ስለዚህ ዛሬም ወደፊትም አቅመቢስነታችሁን ተረድታችሁ በኔ ፊት ራሳችሁን ዝቅ አድርጋችሁና አዋርዳችሁ የተለያዩ ምሶቼን ማቅረብ ይጠበቅባችኋል እንጂ፤ እኔን ሌት ተቀን እንደሚያቃጥሉኝ፣ እንደሚያበሳጩኝ፣ እንደሚያናድዱኝ፣ እንደሚያሰቃዩኝ፣ እንደሚያስለፈልፉኝ፣ እንደሚያስሩኝ ጠላቶቼ፤ እግዚአብሔርን በማክበርና ለሕጉና ለትዕዛዙ

በመገዛት፤ በጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በምስጋና እንደሚተጉ ሰዎች ከሆናችሁ እንደምበቀላችሁና ክርስት መንግስቴ እንደምለያችሁ በተለመደዉ በባዶ ቀፎ አንደበቴ በጨለማዉ ስሜ በመማል አረጋግጥላችኋለሁ።

እናንተ «እዉነተኛ አገልግሎትና ምስክርነት ነዉ የምንሰጠዉ፤» በማለት ራሳችሁን የምታመጻድቁና በእዉነት ላይ የሥጋ ፈቃዳችሁን የምታደባልቁ ከእግዚአብሔርም ከኔ ከጨለማዉ ገዥም የምታጣቅሱ ሰዎች፤ አቋማችሁን በአጭር ጊዜ ዉስጥ አስተካክላችሁ ይህን የተደበላለቀ ሕይወት አቁማችሁ፣ እነዚያን በአገልግሎታቸዉና በምስክርነታቸዉ ላይ እንክርዳድ የማይቀይጡትን ፤ ከኔ ከጨለማዉ ገዥ የማያጣቅሱትን ፤ የሥጋ ፈቃዳቸዉን የማይጨምሩትን አገልጋዮችን በሰላ ብእራችሁና ንግግራችሁ ተቿቸዉ፤ አዋርዷቸዉ፤ አጣጥሉልኝ፤ ጽሑፋቸዉ ሆነ ትምህርታቸዉ ተረት ተረት ነዉ አስብሉልኝ።

ለዚህም ዉለታችሁ ለማንኛዉ የአዳም ዘር ክፍት የሆነዉ መንግስቴን በመጨረሻዉ ፍርድ ቀን ክፍት አድርጌ እጠብቃችኋለሁ። ከዚህ በተጨማሪ ስለ እንክርዳድ ተግባራቸዉና ሕይወታቸዉ የተተቹባችሁ ወዳጆቻችሁንና ዉለታ የዋሉላችሁን በሥጋ ይኑሩም አይኑሩም ጠበቃ ሆናችሁላቸዉ «ጻድቃን ናቸዉ፤ ቅዱሳን ናቸዉ፤ ታቦት ሊቀረጽላቸዉ ይገባል።» በማለት ለወደፊት በሐዉልት ማቆም ብቻ አይደለም «ታቦት ይቀረጽልኛል» ብለዉ ተስፋ የሚያደርጉትን ቅዱስ አባታችሁን ይዛችሁ « እነዚህ የሞቱት ሆኑ በሕይወት ያሉት ወዳጆቻችን ዉጭያቸዉ እንደእርሶ ያማሩ፣ ንግግራቸዉ እንደ እርሶ በቅመም የተቀመመ፣ ፈሊጥ የሞላበት ስለሆነ፤ ምንም እንኳን ዉስጣቸዉ የተለሰነ መቃብር በዉስጡ እንደያዘዉ ቢመስልም፤ ነግ በኔ ነዉና የቅድስና ማዕረግ ተሰቷቸዉ መታሰብያ ሊደረግላቸዉ ይገባል» በማለት ልታሳምኑ ይጠበቅባችኋል። ያኔ እናንተም የቅድስና ማዕረግ የምትደርሱበትን የጨለማዉ ጸጋዬን እሰጣችኋለሁ። የአምላካችሁን ስራና ጸጋ ለማቃለል ወደ ኋላ እንደማትሉ ሁሉ የኔን ጸጋ «እናቃልላለን፤ እንንቃለን» ብትሉ ከሁለት ያጣችሁ እንደምትሆኑ በግልጽ አስጠነቅቃችኋለሁ።

እናንተ ከመንፈሳዊ እዉቀት ጋር ጎን ለጎን የኔን የጨለማ ገዥ ትምህርት የምትማሩና የምታስተምሩ አገልጋዮቻችንና በጠቢቡ ሰሎሞን ስም የምትነግዱ « ኑ በሰሎሞን ጥበብ

መስተፋቅር እንዳርግላችሁ፣ ይህን ክፉሉን ለዚህ በሽታ ፈዉስ እናደርግላችኋለን፣ የተለያየ ተአምራትን እናሳያለን መጫኛ እናቆማለን፣ ከጠበሉ ይልቅ ጽፈት የሚችል ሰዉ አገናኛ ችኋለሁ .. ወዘተ» የምትሉና ነፍሳትን ለኔ ለጨለማዉ ገዥ አሳልፋችሁ የምትሰጡ፤ « አብርቃኤል ስርቃኤል ቢስሚላሂ ሽርላኤል እንደ ዉሻ በቁልቁለት በቤት በማጀት አስፈሳ» የሚለዉን በመድገም፤ «ሚስቶቻችሁ ከሌላ ወንድ ጋር እንዳይገናኙ ማስፈራሪያ እንደግምላችኋለን፤ ሀብት ንብረት እንድታገኙ ገንዘብ እንዲበዛላችሁ እናደርጋለን፤ የተጣላችሁትንና የምትመቀኙትን ሰዉ በተለያየ መተት ጉዳት እንዳርስላችኋለን .. ወዘተ» በማለት የጨለማ ስራዬን የምታስፋፉልኝ መተተኞች፣ አስማተኞች፣ ጠንቋዮች፣ መጽሐፍ ገላጮች፣ ለእናንተ የበለጠዉን የጨለማ ጸጋዬን ላድላችሁ የተዘጋጀሁ ነኝና ድርጊታችሁን በደንብ አጠናክሩ ::በአዳም ዘር ላይ የክፋትና የጭከና ተግባራችሁን በደንብ ፈጽሙ:: ታዲያ ሕዝቡና ምእመኑ በእግዚአብሔር ስጦታ በሆኑት በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በእምነት፣ በጸበል፣ በሥጋና ደሙ ፈዉስ ሆነ ጸጋ እንዳያገኙ «እኛ ነን እንጂ የምናድን ሌላዉ የሰይጣናትን ኃይል ማሸነፍ አይችልም::» በማለት የእግዚአብሔር ጸጋን አቃሉ፤ አጣጥሉ::

ሌላዉ ደግሞ አንዳንድ በሥላሴ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በድንግል ማርያም፣ በቅዱሳን መላእክትና በቅዱሳን ጻድቃን ሰዎች ስም፤ በተዋህዶ ሃይማኖትና በቅድስት ቤተክርስቲያን ስም፤ ካለምንም ክፍያና ማታለያ በጸሎቱና በጸበሉ ፈዉስ የሚያርጉ፤ የተመተተዉን የሚፈቱ፤ ገበናዬን የሚያጋልጡ፤ የተንኮል ተግባሬን የሚያጋልጡ፤ ባሮቼን ሰይጣናትን እያስለፈለፉ የሚያቃጥሉ፤ የእናንተንም የኔንም ምስጢራችንንና ገበናችንን የሚያስወጡ፤ ያስቸገሩኝ ሰዎች አሉና የእናንተም ገበና እየተጋለጠባችሁ፤ የከሃዲያንና የመናፍቃን ባዶነት ሕይወት ዓለም እንዲያዉቀዉ እየተደረገ ስለሆነ፤ የተለያየ ስያሜ በማሰጠት ይኸዉም «በአስማት ነዉ የሚሰሩት፤ በእፅ ነዉ የሚያስለፈልፉት፤ ሐሰተኛ በዲያብሎስ መንፈስ ነዉ የሚመሩት.. ወዘተ» እያስባላችሁ፤ እንዲሁም አንዳንድ በሥጋና ደም ስሜታቸዉ የሚመላለሱ፣ ከእነሱ አስተሳሰብና አመለካከት ዉጭ ያለዉን የማይቀበሉ፣ ነጥብ በማትሞላዉ እዉቀታቸዉ የሚመጻደቁ፣ የእግዚአብሔርን ጸጋ በራሳቸዉ እዉቀት እየገደቡ፣ ልክ ክርስቶስ በምድር በተመላለሰበት ዘመን የሰንበት ጌታና የሙሴ አምላክ አጠገባቸዉ እያለ ቃላት እየሰነጠቁኑና አቃቂር እያወጡ እንዲሁም «ለምን የሰይጣናትና የአገልጋዮቹ አስማተኞችና መተተኞች ገበና ይጋለጣል? የመናፍቃንና የከሃዲያን ባዶ ሕይወት ለምን ዓለም እንዲያዉቀዉ ይደረጋል? ለምን በሽተኞች ከታሰሩበት ይፈታሉ? ለምን ፈዉስን ያገኛሉ? የሙሴ ሕግ አልተጠበቀም፣ ሰንበት ተሽሯል፣ ይህን ሁሉ የሚደረገዉ በአጋንንት አለቃ

አጋንንትን እያዘዘ ነዉ እንጂ ከእግዚአብሔር አይደለም.. ወዘተ» በማለት ጥብቅና እንደቆሙልኝ ጸሐፍት ፈሪሳዉያንና አይሁድ ካህናት፤ አሁንም ከእግዚአብሔር እዉነት ጋር የሚጣሉና የሚላተሙ አንዳንድ አገልጋዮችና ምእመናን ጠበቃዎች ስላሉኝ እነሱንም እንደ መሳሪያ ተጠቅማችሁ ስማቸዉን ማስጠፋትና ከምእመኑ መለየት ይጠበቅባችኋል:: እንዲሁም ወደ እናንተ እንዲመጡና ካልፈለጉ ደግሞ ወደ ተለያዩ የእምነት ድርጅቶቼ እንዲመጡ በማስደረግ በአገልጋዮቼ ፓስተሮች አማካይነት ለጊዜዉ እየወጣን አንዳችን አንዳችንን እያዘዝን እንጫወትባቸዋለን:: ዋናዉ የዚያች ጠላታችን «ቅድስት ድንግል ማርያም» የሚሏት አገልጋዮችንንና ባለሚሎችን ስማቸዉን በማስጠፋትና አገልግሎታቸዉ ላይ እንቅፋት በመፍጠር ከቤተክርስቲያን ቅጽር አስወጡልኝ:: በሌላ ቦታም አንዳች አገልግሎት እንዳይሰጡ አስደርጉልኝ::

እናንተ «ከእኛ በላይ ቅድስና ያለዉ የለም፤ ስራችን ሁሉ የጽድቅ ስራ ብቻ ነዉ፤ በቅተናል፤ ነቅተናል፤ » የምተሉና ራሳችሁን አመጻድቃችሁ ለሰማየ ሰማያት ያጯችሁ፤ የስም ቅዱሳንና ጻድቃን ሰዎች፤ መቸስ የቅድስናና የጽድቅ ስራችሁን ባዉቅም አንዲት ቀላል ተግባር መፈጸም ባለመቻላችሁ እንኳን ፈጣሪያችሁ እኔ የጨለማዉ ገዥ ታዝቤያችኋለሁ:: ይኸዉም በየመንገዱ የወደቁ እንጨትና ድንጋዮች ዋጋ ኖሮዋቸዉ ሲሳካ በግልጽ ሳይሳካ በስርቆት ሁሉም ሲያስጠጋቸዉ፤ ትልቁ የአዳም ዘር ወገናችሁ በየመንገዱ ወድቆ ዋጋ እንደሌለዉ፤ ከእንጨትና ከድንጋይ አሳንሳችሁት፣ ተመልካችና ሰብሳቢ እንዲሁም የሚያስጠጋዉ ሰዉ ሲያጣ ራሳችሁን ማመጻደቃችሁ ከንቱ መሆኑን ይመሰክርባችኋል:: እኔ ግን የሰዎች መጎሳቆልና መቸገር ስለሚያስደስተኝ እንኳን በመንገድና በየጥጋጥጉ የወደቁትን አይደለም ከተቻላችሁ በቤት ዉስጥ ያሉትን ሁሉ አፈናቅላችሁ ብታስወጡልኝና ለችግርና ለመከራ ሕይወት ብትዳርጉልኝ በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችሁ ነበር:: » **ይላላ እዉነቱንና ሐሰቱን እያደበላለቀ የሚያሳምጸዉና ለሞት ሞት የሚዳርገዉ ክፋትና ተንኮል እንዲሁም ጭከና የተሞላዉ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከሠራዊቶቹ ጋር በመሆን::**

# ምእራፍ ሦስት

« እናንተ « የአዳም ዘር ነን፤ ሰዎች ሁሉ ወገኖቻችን፣ ወንድምና እህቶቻችን ናቸዉ፤» በማለት ለዘረኝነትና ለጎጠኝነት ስብከቴ እንቅፋት የሆናችሁና ብቃቴን ባሳየሁት ስም አወጣጤ ይኸዉም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተገለጻዉን ወገን፣ ነገድ፣ ቋንቋ፣ ዘር፣ በቅርብ ደግሞ ህብረተስብ፣ ማህበረስብ፣ ሕዝብ፣ ዜጋ እየተባለ ሲጠራ የነበረዉን በመደምሰስና በመሰረዝ፤ ዓለም እስካሁን ያልፈጠረዉን ልዩ ስያሜ የፈጠርኩትን ወርቃማ ቃሌ የሆነዉን «ብሔር ብሔረሰቦች» የሚለዉን የምታጥላሉና የምታናንቁ ሁሉ፤ ለስልጣን ሆነ ለኃላፊነት ለመታጨት እንዲሁም ለእንደራሴዎቼ ታማኝነታችሁን ለመግለጽ ይህንኑ ቋንቋዬን በየመድረኩና በየቦታዉ እንደ አቡነ ዘበሰማያት ካልደጋገማችሁ አንዳች ሞገስ እንደማታገኙና እንኳን ለኃላፊነት ቀርቶ መብታችሁን በአግባቡ እንዳትጠቀሙበት የማደርግና እንደአቋማችሁ ሁኔታም በከፋ ሁኔታ እንደምበቀላችሁ በተለመደዉ በጉራና በባዶነት በተሞላዉ አንደበቴ አስጠነቅቃችኋለሁ።

በተለያየ ጊዜ የወሰድኩትን እርምጃ ሳታስተዉሉት አይቀርም፤ በእድሜ ልክ እስራት ካልሆነ ደግሞ በሞት ነዉ የማሰናብታችሁ። እኔ ዘንድ አንዳች ርኅራኄ የለም። ለኔ ለጨለማዉ ገዥ የጥምቀት ዉሀ የሆነዉን ለመንፈሴ ማጥመቂያ የሚጠቅመኝንና ሁል ጊዜ ብተደጋግሙልኝ የማይሰለቸኝ «ብሔር ብሔረሰቦች» የሚለዉ ልዩ ቋንቋዬ ስለሆነ፤ ከኔ ፍጹም ባለሟልነትን ለማግኘት ይህንኑ ቃሌን በቴሌቭዥንም ሆነ በሬድዮን፣ በስነጽሑፍም ሆነ በስብሰባ መደጋገም ይጠበቅባችኋል። «ሕሊናዬን አልሸጥም፤ እንደቦይ ዉኃ አልነዳም፤» የምትሉ ከሆነ የተለመደዉ ችግርና ችጋር ልክ ያስገባችኋል።

እናንተ የአዳም ዘሮች፤ «እግዚአብሔርን እናመልካለን፤ የእሱ ተገዢ ነን» ትላላችሁ። ነገር ግን ቀን ከሌሊት የኔን ፈቃድ ስትፈጽሙና ስታስፈጽሙ ነዉ የምመለከተዉ። ሙሉ በሙሉ የኔ ተገዢ መሆናችሁን ለማረጋገጥ ሌላ ብዙ ማረጋገጫ ሳያስፈልገኝ በቴሌቭዥን፣ በሬድዮን፣ በጋዜጣ፣ በመጽሔት፣ በመጽሐፍት፣ በፊልም፣ በኢንተርኔት፣ በመሳሰሉት የምታቀርቡትና የምታስተላልፉት ትዕይንትና ወሬ መልእክት ብቻ በቂ ማስረጃዬ ነዉ። ለነገሩ

ለእንደራሴዎቼ ትዕዛዝ የምሰጥ ዋና አዛዥ እኔ ስለሆንኩ፤ እናንተ መልካም ነገር እናስተላልፍበት ብትሉም አትችሉም:: የምትጠየቁበት ግን ማመዛዘንና ማገናዘብ የሚችል ኅሊና እያላችሁ የኔ የጨለማዉ ገዥ እንደራሴዎቼን ለመሪነት ሆነ ለአስተዳዳሪነት መምረጣችሁ ነዉ:: ለነገሩ «እምቢ አንመርጥም» ብትሉስ ምን ታመጣላችሁ? ባስታጠኳቸዉ መሳሪያ ልክ ያስገቧችኋል:: «እግዚአብሔር ይሁናችሁ» እንዳልል ያዘንኩላችሁ ስለሚመስልና እንደራሴዎቼ ቅር ስለሚላቸዉ «እኔዉ ልሁናችሁ» ብዬ አጽናናችኋለሁ:: ብቻ እድሜ ለእንደራሴዎቼ ወርቃማ ቃላት እየተጠቀሙልኝ ትዉልዱን ደኅና አድርገዉ አንደዘዉልኛል፤ አሳምጸዉልኛል:: ለዚህም መልካም የግፍ፤ የጭቆና፤ የበደል፤ የአድሎ፤ የክህደት፤ የዐመጻ፤ የርኩሰት ዘመን እመኝላቸዋለሁ::

ለእንደራሴዎቼ አንድ እዉነት ሳልነግራቸዉ ብቀር ለወደፊት ይጸጽተኛልና - እናንተ እንደራሴዎቼ! እስከዛሬ ድረስ በታማኝነት ስላገለገላችሁኝ በታላቁ ስሜ ሉሲፈር ወይንም የጨለማዉ ባለስልጣን ወይንም ዓለም በሚያዉቀኝ ዲያቢሎስ ስሜ በቅድሚያ አመሰግናችኋለሁ:: በመቀጠል ደግሞ የስልጣን እድሜያችሁን በብልጣብልጥነትና በሥጋዊ ጥበብ የምታስረዝሙ መስሏችሁ ሌት ተቀን መትጋታችሁ የሚደነቅ ቢሆንም ከተቆረጠላችሁ ቀን አንዲት ቀን ማስረዘም የማትችሉ መሆኑን ሳዉቅ ስለ አቅመቢስነቴ እጅግ ባዝንም ባለተረኛ ስለሚተካ በዚያ እጽናናለሁ:: እናንተ ለሃያ ዓመታት እኔን የጨለማዉ ገዥን በቅንነትና በታማኝነት፣ ትጋት በተሞላ አገልገሎታችሁ አስደስታችሁኝ የአንድ ቀን ዋስትና መስጠት አለመቻሌና እግዚአብሔር የፈለገዉን በፈለገዉ ጊዜ ማከናወን መቻሉና እርሱ ሳይፈቅድ ደግሞ ምርጥ ባለሟሎቼ ላይ አንዳች ሊደረግባቸዉ አለመቻሉ እጅጉን ያስቆጨኛል፤ ያንገበግበኛል::

እንደኔ ቢሆን ምንም እንኳን የአንደኝነት ማእረግ ባልሰጣችሁም ከኢራቁና ከሊቢያዉ መሪ ልዩ ባለሟሎቼ ከነበሩት በማስከተል እናንተ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የክልሎች መሪዎች ከዋናዉ ከርዕሰ ክልላት መሪያችሁ ጭምር የስልጣን እድሜ ማራዘሚያ ዋስትና እሰጣችሁ ነበር:: ምን ያደርጋል ታዲያ! እንኳን ለእናንተ ዋስትና ልሰጥ ቀርቶ ለራሴ አንዳች ዋስትና

የሌለኝ ተራ ደካማ ፍጡር በመሆኑ ኀዘኔ እጅግ የከፋ ነዉ:: ስምህ ያጽናናህ እንድትሉኝ እፈልጋለሁ:: እናንተንም ርኩስ የሆነዉ ስሜ ያጽናናችሁ::

ታዲያ ይህን አባባሌን እንዳታጣጥሉት:: እግዚአብሔር እንኳን እናንተን ቀርቶ ማንም አይነካቸዉም አይነቀንቃቸዉም የተባሉትን ነገሥታት፣ ፕሬዘዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ባለስልጣናት፣ ባጠቃላይ ኃያላን የተበሉትን እንኳ እንዳልነበሩ አድርጓቸዉ መታሰቢያቸዉን ሳይቀር ከምድር ደምስሷል:: እናንተ ዋና ዐመጻኞችንና ከሃዲዎችን እንዴት አብልጦ አይደመስሳችሁ! እጅግ ይደመስሳችኋል::

ታዲያ እንዲህ ስላችሁ ስለዐመጻና ክህደት ተግባረችሁ እንድትጸጸቱ፣ ንስሐ እንድትገቡ ልመክራችሁ ፈልጌ አለመሆኑን በክፋትና በተንኮል፣ በበቀለኝነት የተሞላዉ ልቦናችሁ እንደሚነግራችሁ ምንም አልጠራጠርም:: ስለዚህ የዘራችሁትን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ፍሬያችሁን ማጨዳችሁ ስለማይቀር፤ ልክ እንደ አጥፍቶ ጠፊዎቼ የመጨረሻዉን ኒሻን ተሸላሚ እንድትሆኑ፤ እናንተም መጥፋታችሁ ስለማይቀር ኢትዮጵያ የተባለች አገርና ሕዝቧን እንድታጠፉልኝ የመጨረሻ ታላቁን ምክሬን እለግሳችኋለሁ::

ጊዜ ያለ መስሏችሁ «ቀስ በቀስ ጎሊናን እያደነዘዝንና እየመረዝን በወርቃማ ቃላቶች እየታጀብን በሕገ መንግስትህ ተመርተን የብሔር ብሔረሰቦች መብት እስከመገንጠል በሚለዉ አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ መሰረት ተግባራዊ እናደርጋለን፤ እጅግ ጠግበን እስከምናስታዉክ ድረስ ትንሽ ታገሰን » እንዳትሉኝ በጥብቅ አሳስባችኋለሁ:: እኔ ተረብሻለዉ፤ ኃይለኛ ጭንቀት ላይ ነኝ ያለሁት:: በአራቱም ማእዘን ያሉ የዓለም መንግስታት፣ የተለያዩ ቡድኖችና ግለሰቦች የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ጽዋቸዉን እየተጎነጩ በማለፍና ፍዳቸዉን በመቀበል ላይ ናቸዉ:: በተለይ አንተ አእምሮህ አንዳንዴ ከኔ ላቅ እያለ የምታስቀናኝ ጠቅላይ ሚኒስትር ላንተ ምክር ባያስፈልግም የልቤን ታዉቃለህና የምታደርገዉን በፍጥነት አድርግ::

ስለ እንደራሴዎቼ ተግባርና ማንነት ኃያላኑን መንግስታቴን ትቼ፤ ሌት ተቀን ለኔ ታማኝነታቸዉን በማረጋገጥ የኃያልነት ማዕረግ እንድሰጣቸዉ በልዩ አምልኮ ደጅ ስለሚጠኑኝ የዚህችዉ የአዲሲቷ የኢትዮጵያ እንደራሴዎቼን ምሳሌ በማቅረብ ታላቅነቴን ለማሳወቅ እፈልጋለሁ:: እነዚህ የቀድሞ የጫካና የዋሻ ምልምሎቼ ለማርክሲስት ሌኒኒስት ፍልስፍናና

የሶሻሊስት ስርዐቱን በሚገባ ካስጠናዋቸዉና ዉሳጣቸዉ ያለዉን የክህደት፣ የዐመጻ፣ የርኩሰት፣ የጥላቻና የበቀል ስሜታቸዉን በደንብ ካጠናከርኩ በኋላ፤ የመጀመሪያ የእጩ መኮንንነት ማዕረግ በመስጠት እንደመመሪያ በያዝኩት «በፊት ለፊት ወርቃማ ቃላቶችንና አባባሎችን ማስቀደም» በሚለዉ መርህ እነዚሁ እጩ መኮንኖቼ የዐመጻዉና የክህደቱ ጽዋ የሞላባቸዉ የቀድሞዉ መኮንኖቼ ከወንበራቸዉ ሲሰናበቱ አዲሶቹ እጮዎቼ በወርቃማ አባባሎቼ በሆኑት ነጻነት ፣ ፍትህ፣ እኩልነት፣ በኔዉ ስያሜ ዴሞክራሲ ታጅበዉ በግንቦት ፲፱፻፹፫(1983) ዓ.ም.ወደ ተከበረዉ ወንበሬ መጡ::

በበላይ መሪያቸዉ እኔ አታላዩ(ሸዋጁ) መንፈስ ነበርኩና የዉስጣቸዉን ጥላቻና በቀል በደንብ አዉቅ ነበርና ይህች እንድትጠፋ እፈልግ የነበረችዉን «ሀገረ እግዚአብሔር» የምትባለዉን ኢትዮጵያን፤ «ብሔር ብሔረሰቦች» በሚለዉ ተወዳዳሪና ተቀራራቢ በሌለዉ ወርቃማ ቃሌ በመጠቀም አገራዊና የሰንደቅ ዓላማ ፍቅር እንዲቀንስ በማድረግ የተለያዩ መንግስታት እንዲመሰረቱ አስደረኩ:: እዚህ ላይ አስደረኩ ስል አስገድጄ ሳይሆን ያቀረብኩላቸዉን አሳብ ቀደም ሲል በጫካዉ ዉይይታችን ተግባራዊ ለማድረግ በደስታ የተቀበሉት ስለነበረ፤ በወንበር ሲቀመጡ ወዲያዉ ተግባራዊ ለማድረግ አልተቸገሩም::

እዚህ ላይ የመንግስታቱን ስያሜ በተመለከተ «በሂደት ሳናስፎግር እንዳንተ እቅድ መሰረት ስያሜዎቹን መሉ በመሉ ተግባራዊ እንዳርጋለን፤ ለጊዜዉ ኢትዮጵያ የሚለዉን ስያሜ ሊቀናቀንና ሊተካ የሚችለዉን «ኦሮሚያ» በማለት እንሰይማለን ፤ ሌሎቹንም በሂደት ትግሪያ፣ አማሪያ፣ ሱማሊያ፣ አፋሪያ፣ ሐረሪያ፣ ጋምቤሊያ፣ ቤንሻንጉሊያ፣ ሃዲይያ፣ ወላይትዪያ፣ ጉራጊያ፣ ስልጢይያ፣ ሲዳማዩያ.. ወዘተ በማለት እናስተካክላለን፤ ለጊዜዉ ግን በምትፈልገዉ በብሔር ብሔረሰቦች ስም የተለያዩ መንግስታትን እናቋቁማለን፤ ለዚህም እኛ የጫካ ታማኝ እጭዎችህ በርኩስ ስምህ እንምልልሃለን::» በማለት ምህላ ስለፈጸሙልኝ መንግስታቸዉን ሙሉ እዉቅና ሰጥቻለሁ::

እንደእቅዴና ምኞቴ ኢትዮጵያ የሚለዉ ስያሜና የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ቶሎ ባይጠፉም፤ በልዩ የጥላቻና የበቀል ስብከቴ አገልግሎት ላይ በተሰማሩት እጩዎቼና

ካድሬዎቻቸዉ አማካይነት ልቤን ሙሉ በሙሉ ባያረካም የተወሰኑ አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዉልኛል፤ ክርስቲያኖችም ተጨፍጭፏዋል፤ የቀሩትም ከትዉልድ ቄያቸዉ ተፈናቅለዋል፤ መከራና ችግር ደርሶባቸዋል፤ ሌሎቹም ተሳቀዉ በጭንቀትና በስጋት እንዲኖሩ ተደርገዋል:: ለወደፊት ደግሞ እንደራሴዎቼ ከዚህ በላይ ፍሬ ያፈሩልኛል ብዬ ተስፋ በማድረግ ይኸዉ ለሃያ አመት የማማከር አግልግሎት በመስጠት ላይ እገኛለሁ::

በዚሁ አጋጣሚ በጥላቻና በበቀል ቅስቀሳ ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጋችሁ የምትፈልጉትን የስልጣን እርከንና ብልጽግና ሳይሳካላችሁ ቀርቶ የተወሰናችሁ ታስራችሁ ሌሎቻችሁ ልታጠፏት ከነበረችሁ ቅድስት ምድራችሁ ኢትዮጵያ ተሰዳችሁ በጨለማዉ ግዛቴ በስደት ዓለም ያላችሁና በአገር ዉስጥ ምኞታችሁ ተፈጽሞላችሁ በድሆች አናት ላይ ያላችሁ ዉድ ባለሟሎቼ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ:: እስከ ሕይወታችሁ ፍጻሜ ድረስ ለኔ ያላችሁን ታማኝነት እንድትገልጹልኝ እያሳሰብኳችሁ፤ በዋናዉ እንደራሴና በአጫፋሪዎቹ ቅሬታ ያላችሁ ግን በአጭር ጊዜ ዉስጥ ቅሬታችሁን ለኔና ለቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ማቅረብ የምትችሉ መሆኑን እግልጻለሁ:: በቅሬታችሁ ግምገማ ዉጤት እንደራሴዎቼ የእናንተን ያህል ዓላማዬን ለማሳካት ሳይጥሩ ቀርተዉ ከሆነ በአንድ ዓመት ዉስጥ ወደ ወንበሬ አመጣችኋለሁ:: አይዟችሁ እኔ እስካለዉ ድረስ የክህደት፣ የዐመጻ፣ የርኩሰት፣ የግፍ፣ የበቀልና የጥላቻ ዉለታችሁን አልረሳም:: ለዚህም በታላቁ ስሜ ዲያብሎስ እምልላችኋለሁ::

እናንተ ኢትዮጵያዉያን! ዉድ እንደራሴዎቼ ያመጡትን የዘረኝነትና የጎጠኝነት ስርዐት «አሜን» ብላችሁ በመቀበላችሁና የአዳም ዘር መሆናችሁን፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ የካም፣ የሴም፣ የያፌት ነገድ ዉህድ የሆነዉ የቅዱሱ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ሕዝብ መሆናችሁን፣ አባታችሁ አንዱ እግዚአብሔር መሆኑን ክዳችሁ ይህች ምድር መኖሪያችሁ ሳትሆን በአዳምና ሔዋን ዐመጻ ምክንያት በሥጋ ተገልጻችሁ እየተቀጣችሁ፣ እየጠራችሁ መሆኑን በመዘንጋትና ሰማያዊ ተስፋችሁን በማጨለም እዉነተኛ ገንዘባችሁ የሆነች ነፍሳችሁን በዐመጻ ተግባር ላይ በማሰለፋችሁ፣ እንዲሁም በእንደራሴዎቼ አማካይነት ተግባራዊ ያደረኩትን የብሔር ብሔረሰቦች የጎጠኝነት ክፍልፋይ አገዛዜን መቀበል ብቻ አይደለም «እኔ የዚህ ቋንቋ ተናጋሪ ነኝና ይህ ክልሌ ነዉ፤ ያንተ ክልል አይደለም፤» በማለት የከፋ የከረፋዉን ስብከቴን ተግባራዊ

በማድረጋችሁና ባጠቃላይ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተባባሪ ለመሆን ሙሉ ፈቃደኞች በመሆናችሁ ከፍ ያለዉን ምስጋናዬን አቀርባለሁ:: መቼም እንደምታጨበጭቡልኝና እንደራሴዎቼና አጫፋሪዎቻቸዉ ደግሞ የብሔር ብሔረሰብ ዘፈንና ጭፈራ እንደምታቀርቡልኝ ሙሉ በሙል እተማመናለሁ::

በተለይ «የሃይማኖት አባት ነን፣ ባለመስቀል ነን» ብላችሁ በዚሁ በከፋና በከረፋዉ ስርዐቴ ተሳታፊና አስፈጻሚ የሆናችሁ የተለየ ምስጋና ሊቸራችሁ ይገባል:: ምክንያቱም ሌላዉን እንኳ እንደ ኳስ ብጠልዘዉ፣ ባንከባለዉ፣ ብወረዉረዉ፣ ብረግጠዉ፣ ባጠቃላይ እንደልቤ ባደርገዉ ብዙም አይደንቀኝም:: ምክንያቱም ሆዱ አምላኩ የሆነዉን በሆዱ እገባበታለሁ፤ ስልጣኑን፣ ክብሩን የሚያመልከዉን በስልጣንና በክብሩ እገባበታለሁ፤ ገላዉን የሚያመልከዉን ገላዉን አስመልክለታለሁ፤ ምስጋናን የሚፈልግ ከንቱ ዉዳሴ አስቀርብለታለሁ፤ ብልጽግናን የሚፈልገዉን በገንዘብ እጥለዋለዉና ነዉ:: እናንተ ግን በአፋችሁ ሁል ጊዜ « እነዚህን ናቁ፣ ተስፋችሁን ገነት መንግስተ ሰማያት አድርጉ ስለምትሉና እናንተ በተግባር የምትፈጽሙ እየመሰለኝ በቁጥጥሬ ስር ማዋል ያዳግተኛል እያልኩ እጨነቅ ነበርና ነዉ:: አንዳንዶቻችሁማ ከሥጋዉያኑ ብሳችሁ ሳገኛችሁ፤ - እነዚህ ለካስ የሥጋዉ መንገድ ጠፍቶባቸዉ ነዉ ለዘመናት በስቃይ ሕይወት ዉስጥ ሲዳክሩ የነበሩት እላለሁ::

አንዳንዶቻችሁ ግን እኔን በማስቀናት ላይ በመሆናችሁ እርማት ማድረግ ይጠበቅባችኋል:: ይኸዉም እናንተ በቁማችሁ ሐዉልት እያስቆማችሁ መከበርና መግነን ፣ መመለክ ከፈለጋችሁ እኔ በጣዖታት ላይ አድሬ የምመለከዉን ማን ያስታዉሰኛል በሚል ስጋት ሲሆን፤ በየቤተክርስቲያኑ ተሰቅሎ ምእመናን ስለሚለማመኑበት ሥዕል (ባነር) ግን እግዚአብሔርና ቅዱሳን አስተያየታቸዉን ቢሰጡ የተሻለ ነዉ እያልኩ አንድ ምስክርነት ለመስጠጥ ግን እፈልጋለሁ:: ይህም እኔ የማዉቀዉ ስዕላት ሰዎች በምድራዊ ቆይታቸዉ የቅድስናና የጽድቅ ስራ ሰርተዉ ወደ አምላካቸዉ እቅፍ ሲሄዱና ቅድስናቸዉ በእግዚአብሔር ሲረጋገጥ ነበር ለጻድቃኑ ሥዕላቸዉ ተዘጋጅቶ በአብያተ ክርስቲያን ዉስጥ ይሰቀል የነበረዉ::

ይሁንና ጽድቁና ቅድስናዉ ያልተረጋገጠለት ሰዉ በሕይወት እያለ «ቅዱስ፣ ብጹዕ ነኝ» ስለሚል፤ እንኳን ስዕል ቀርቶ ታቦት ቢቀረጽላቸዉ እግዚአብሔር ስለሚቆጣና እዉነተኛ ቅዱሳኑም ስለሚያዝኑ እኔ ደስ ይለኛል፡፡ ሌላዉ ደግሞ አድሏዊ አሰራራችሁን ትታችሁ በአዲስ አበባ የተጀመረዉ የጣዖት ማቆምና ስዕላትን መስቀል በየክልላቶቼ መንግስታት ዉስጥ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ጭምር እንድታቆሙ አሳስባለሁ፡፡ እናንተ በሐዉልት ማቆምና ስዕላትን በመስቀል ዋና አስተባባሪዎችና ጣዖት አስመራቂዎቼ፤ «አይሮፕላን ይገዛል» የምትሉትን የማስመሰል አሳባችሁን ትታችሁ ለኔ በሚጠቅመዉ በቀድሞ ተግባራችሁ እንድትቀጥሉ እናንተንም በጥብቅ አሳስባለሁ፡፡ እምቢ ካላችሁ ደግሞ ከመሪያችሁ ጋር ያስተሳሰራችሁትን ህትብት እቆርጥባችኋለሁ፡፡

ዱሮ ዱሮ እነዚህ በሥጋዊ ሆነ በመንፈሳዊ ወንበር ላይ የተቀመጡት እንደራሴዎቼና ባለሟሎቼ አንዳንዴ በንግግራቸዉ የሚያሰሙት ወርቃማ ንግግሮች ተግባራዊ ያደርጉት ይሆን እያልኩ እሰጋ ነበር፡፡ አሁን ግን ብዙ ጊዜ ንግግራቸዉና ተግባራቸዉ አለመገናኘቱንና ዉጫቸዉና ዉስጣቸዉ አንድ አለመሆኑን ስረዳ፤ ሺህ ወርቃማ ንግግሮች እንኳን ኢትዮጵያዉያን ቀርቶ ዓለም የሚቀበለዉን ወሬ ቢያወሩ ከቁም ነገር የማልቆጥረዉና አንዳችም ስጋት የማይታይብኝ ሆኗል፡፡ ምክንያቱም ሙሉ በሙሉ ተገዢዎቼ ሆነዋልና ይልቁኑ ተደማጭነትና ተቀባይነት እንዲኖራቸዉ ከልባቸዉ ያልሆነዉን መልካም ንግግሮችን አሳስባቸዋለሁ፡፡ ወደ ተግባር ሲመጣ ደግሞ ተቃራኒዉን አስፈጽማቸዋለሁ፡፡ እነሱን ብቻ ሳይሆን በእነሱ መንፈስ የሚመሩትን እስከ ገጠር ቀበሌ ገበሬ ማኅበርና ቤተ ክርስቲያን ድረስ ተግባራዊ አስደርጋለሁ፡፡ «አሻፈረኝ ኅሊናዬን አልሸጥም» የሚለዉን ከስራ በማፈናቀልና ወደ ማይፈልገዉ ቦታ በማዛዛር እበቀላለሁ፤ ሲብስ ደግሞ በእስራትና በግድያ እርምጃ ለማስወሰድ ማንኛዉንም ጥረት አደርጋለሁ፡፡

እንዲገባችሁና በፍርሐት እንድትዋጡ በምሳሌ ጭምር ላስረዳችሁ እችላለሁ፡፡ እንደራሴዎቼ ሆኑ ባለሟሎቼ ኅሊናቸዉን ለመገለባበጠ የማይቸገሩ በመሆናቸዉ አስቀድሜ ምስጋና አቀርብላቸዋለሁ፡፡ ምሳሌ አንድ: የሥጋዊዉ መሪ ስለ ኢትዮጵያዊነት ሆነ ስለ ሰንደቅ ዓላማ ደንታ የሌለዉ ይልቁንም ኢትዮጵያዊነትና ሰንደቅ ዓላማን ለማጥፋት ቀን ከሌሊት

የሚተጋ ዉስጡ ጥላቻና በቀል የሞላበት መሆኑን እሱም እኔም በደንብ እናዉቃለን፡፡ ከእርሱም በላይ እኔ አዉቃለሁ፤ ይኸዉም አንዳንድ ንግግሮቹንና ተግባሮቹን እርሱ ስለሚዘነጋ እኔ ደግሞ አንዱንም ስለማልረሳ ነዉ፡፡ ገና ከወጣትነቱ ጀምሮ አሳቦቹ ሁሉ ለኔ የሚመቹ በማርክስና በሌኒን ፍልስፍና የተሞሉ «እግዚአብሔር የለም» በሚል፤ በከሃዲዎች ርዕዮተ ዓለም የሚመራ ስለነበረ፤ከሁሉ ይልቅ እንደልቤ መሆን በመቻሉ ለባለወንበርነት አጨሁት፡፡

ከዚያም ያ ያፈጀዉን ተሐድሶ ያልተደረገበት የሶሻሊስት ስርዐትና መሪዎቹ ከወንበራቸዉ ሲገነደሱ እሱን በወንበር ላይ ቀብቼ አስቀመጥኩ፡፡ ታዲያ አንዳንዴ በአስተሳሰቡ ከኔ ላቅ ይላልና ህዝቡ በሶሻሊስት ስርዐት መንገሽገሹን ተረድቶ ኀሊናዉን ወዲያዊ ገልበጥ አድርጎ ያላሰብኩትን የካፒታሊስት ስርዐት ዘረጋልኝ፡፡ ታድያ ጭንቅላቱ እንዳልኳችሁ ከሁሉ የመጠቀ ነዉና የትግል ጓዶቹ ቅር እንዳይላቸዉ ያቀበልኩትን ልዩ ቃሌን «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» ስያሜ በማዉጣት ዓርማቸዉና መመሪያቸዉ እንዲሆን አስደረኩ፡፡ በዚህም ብልጠቱ በሂደት የሚቀናቀኑትን ሁሉ ደምስሶ እንዲገንና አምባ ገነን እንዲሆን ሙሉ ስልጣንን አጎናጸፍኩት፡፡

ታዲያ ከመጀመሪያዉ ኢትዮጵያን ለማጥፋትና የሰንደቅ ዓላማን ፍቅር ለመቀነስ ታጥቆ የተነሳ ታጋዬ ነበርና፤ ኢትዮጵያን በተለያየ መንግስታት ከፋፈለልኝ፤ ሰሜን ክፍል የነበረችዉንም «ኤርትራዊያን ናቸዉ እንጂ ኢትዮጵያዉያን አይደሉም» ብሎ አዋጅ አስነገረልኝ፡፡ ሰንደቅ ዓላማዉንም ከፋፍሎ «የትግሬ ሰንደቅአላማ፣ የኦሮሞ ሰንደቅአላማ፣ የአማራ ሰንደቅአላማ፣ የሱማሌ ሰንደቅአላማ፣ የአፋር ሰንደቅአላማ፣ የሐሪር ሰንደቅአላማ፣ የጋንቤላ ሰንደቅአላማ፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ሰንደቅአላማ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሰንደቅ አላማ» በማለት ሁሉም የጎጡን ሰንደቅዓላማ ከፍ ከፍ እንዲያደረግና « አይ ይህን ሸወዳ አንቀበልም፤ የኢትዮጵያን ሰንደቅዓላማ ነዉ ከፍ የምናደርገዉ» ብለዉ ያስቸገሩትን ደግሞ ወርቃማ ዓርማዬን ኮኮብ በመሃሉ ጉብ አደረገዉና አንጆቴ እስከሚርስ ድረስ በመላዉ ኢትዮጵያ ከፍ ከፍ እንዲል አስደረገ፡፡

በእሱ መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እቅዱንና ንግግሩን ተግባራዊ አደረጉ፡፡ እንኳን ኮኮብ ዓርማዬን ቀርቶ ስዉሩ ምስጢራዊ ቁጥሬን «666 ይደረግበት» ቢባል፤ ይህ ኀሊናዉን የሸጠ

ትዉልድ በፈንጠዝያ ነዉ የሚቀበለዉ:: ለዚህም ምስክር እንዲሆን ሕገ መንግስቱ በሚጸድቅበት ወቅት «የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከ መገንጠል ድርስ ነዉ» ተብሎ በእንደራሴዎቼ ሲበሰር በአዳራሽ ዉስጥ የተዘለለዉ ዝላይና ጭፈራ፣ እልልታና ሆሆታ መጥቀስ ይቻላል:: ይህ ደግሞ የሚያሳየዉ ትዉልዱ ለኔ ጨለማ ፈቃድ ምን ያህል ታማኝና ዝግጁ መሆኑን በሚገባ ያስረዳል:: ለኔ ኮከቡ በቂዬ ስለሆነ ከፈለጉ «የቅድስና መገለጫ ነዉ» ይበሉት፤ ሲፈልጉ «የብሔር ብሔረሰቦች መገላጫ ነዉ» ይበሉት፤ ዞሮ ዞሮ መመለኬንና ከፍ ከፍ ማለቴን ነዉ የምፈልገዉ::

ስለሰንደቅ ዓላማ አንዳች ፍቅር የሌለዉና ገና በትግል ዉስጥ እያሉ ኮኮብ ዓርማዬን ዓርማቸዉ አድርገዉ ሲታገሉ የነበረ፤ እዉነተኛዉን ሰንድቅዓላማ «ጨርቅነዉ» ብሎ እንዳላጥላላ፤ አሁን ደግሞ ኅሊናዉን እንደ አክሮባት ገለባብጦ የኢትዮጵያ ወዳጅ ለመምሰልና የሰንደቅዓላማ ፍቅረ እንዳለዉ ለማስመሰል «የሰንደቅ ዓላማ ቀን» ብሎ ያስከብራል:: በምስጢር ስለምንተዋወቅ «ልዩ እንደራሴ እደግ ተመንደግ» ብዬ እመርቀዋለሁ:: ምክንያቱም ዋና ዓላማዬ እዉነተኛዉን ስንደቅ ዓላማና እዉነተኛዉን የመለኮት ዓርማ ከአገሪቱ ማስወገድና ክህደት ማስፈጸም ነዉና ፍላጎቴ:: ይኸዉ ተሳክቶልኝ ከምድሪቱ በአዋጅ ማስወገድና እዉነተኛዉን ሰንደቅ ዓለማ የሚያዉለበልብም በወንጀል እንዲቀጣ ብቻ አይደለም ዓርማዬ ከፍ ብሎ ከክልሎቼ ሰንደቅዓላማ ጋር ቀን ተይዞለት እንዲዉለበለብ ተደርጎልኛል::

ለዚህ አስተዋጽኦ ላደረጋችሁ የተወካዮች ምክርቤት አባላት፣ የፌደሬሽን ምክርቤት አባላት፣ የክልል መንግስታት ምክርቤት አባላት፣ ከታች እስከላይ ያላችሁ ከድሬዎቼና ደጋፊዎቼ፤ ከእግሬ ስር በመርገጥ በከበረዉ ዲያብሎስ ስሜ አመሰግናችኋለሁ:: ለወደፊትም ቆራጡ መሪ «ኮኮብ ብቻ አይበቃም የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነትና ነጻነት የሚገልጽ ምስጢራዊ ቁጥር አለ ይደረግበት» ቢላችሁ፤ መቼም ከሱ በላይ ኅሊናችሁን ማገለባበጥ የምትችሉ ብልሆች መሆናችሁን ስለማዉቅ እናንተን መምከር ሆነ ማሰልጠን አያስፈልገኝምና እንደሚላችሁ ሁኑለት::

ምክንያቱም በኢኮኖሚዉ በኩል «ወገኔ፣ ፈቃዴን የሚፈጽሙ» በማለት ስለሆነ ብልጽግናን የሚያድለዉ፤ በተቃራኒዉ ደግሞ በአስተሳሰብ ከእሱ የተለዩትን የሚመሩትን

ድርጅት ለማጥፋት ወደ ኋላ የማይልና ከባሰም ለማሳሰር፣ ለማሳደድ፣ ለማስገደል አንዳች ርኅራኄ የሌለዉ መሆኑን እናንተም ሳታዉቁ ትቀራላችሁ ብዬ አልገምትም::

እስቲ የትኛዉ ባለሃብት ነዉ ወቶ፣ ወርዶ፣ ላቡን አፍሶ፣ በድካሙ የበለጸገ? ሚሊየነርና ቢሊየነር የሆነ? እንዳትዋሹ በደንብ እንተዋወቃለን:: ይኸዉም በአቋራጭ መንገድ፣ በስርቆት፣ በብልጣብልጥነት፣ በክህደት፣ በዘመድ አዝማድ፣ በጎጥ በመቧደን መሆኑን እንዳልደብቅላችሁ ዓለም ያዉቀዋል:: በንጹህ ስራ ቢሆን፤ ይህ መንግስቴ ካለዉ የጭከናና የአድሎ ፖሊሲ፤ እንኳን ሚሊየነርና ቢሊየነር ልትሆኑ ቀርቶ አንዲት ያማረ መኖሪያ ቤትና መንቀሳቀሻ መኪና አይኖራችሁም ነበር:: ታዲያ እናንተ ባለስልጣናትና ባለሃብቶች፤ ለእንደራሴ መንግስቴ ታማኝ ብትሆኑና ኅሊናችሁን በመሸጥ « አድርጉ፣ በሉ» የሚላችሁን ብታደርጉ፣ ብትሉ ከኔ ልዩ ሽልማት የሚሰጣችሁ አይመስላችሁ:: እኔ ካለምንም ጥቅም እንደቦይ ዉኃ የሚነዳልኝን ነዉ ሞገስና ክብር የምሆነዉ እንጂ፤ ከጥቅሙ ጋር የሚገለባበጥ ሌላ የተሻለ ጥቅም የሚያገኝበት አጋጣሚ ካገኘ ወዲያዉ ሊክደኝ እንደሚችል እገምታለሁና አላምነዉም:: ዞሮ ዞሮ ከትቢያ አንስቶ ለዚህ ያበቃችሁን መንግስቴንና እኔን ከእግሬ ስር በመዉደቅ ልታመሰግኑንና ልትሰግዱልን ይገባችኋል::

እንቢ ካላችሁ ደግሞ ለእናንተ እንዲመች አድርጌ ያስቀረጽኩትን ፓሊሲ ይኸዉም በሀብት ላይ ሀብት፤ በቦታ ላይ ቦታ፤ በስልጣን ላይ ስልጣን፤ በኃላፊነት ላይ ኃላፊነት እንዲጨመርላችሁና ምስኪኑ ወገናችሁ ለመኖር እስኪያቅተዉ ድረስ እንዲንገዳገድ፣ እናንተም በአናቱ ላይ እንድትረማመዱ ያስደረኩትን፤ ደሀዉ እንዲያዝንና እንዲንከራተት፣ በየጥጋጥጉ እንዲወድቅ፣ ባለ ደሞዝተኛም የቤትና የቦታ ባለቤት እንዳይሆን፣ ቦታዎችሁ ሁሉ በሊዝ አቅም ላለዉና ለባለጊዜ እንዲቸበቸብ ያደረኩትን ለዉጥና ማሻሻያ አድርጌ:-

«ሁለት ልብስ ያሉት አንዱን ለሌለዉ» እንደተባለዉ፤ ይህን ጥቅስ በመጥቀሴ ቅር እንዳትሰኙ፤ ካለቦታዉ መጠቃቀስ የለመድኩት ከእንደራሴዎቼ መሪዎቻችሁና ከካድሬዎቻቸዉ ስለሆን በዚሁ አጋጣሚ ስለእግዚአብሔር ቃል መጠቃቀሴ ይቅርታ እያልኩ፤ እኔ ግን የራሴን «ሁለት ቤት ያለዉ አንዱን ለሌለዉ ያድል፤ እኔ ብቻ ልበልጽግ የሚለዉ ከህብረተሰቡ ጋር አብሮ ይበልጽግ፤ በአቋርጭና በዘመድ አዝማድ በጎጥ ተቧድኖ የሕዝብን

ሀብት መመዝበር ይቁም፤ ማጭበርበርና መስረቅ ይቁም፤ ባጠቃላይ በኢትዮጵያዉያን ስም በልመና ሆነ በብድር መልክ መቶ የተወሰነ ግለሰቦችና ቡድኖች በበለጸጉበት ሀብት ንብረት ሕዝቡን ይካሱ፤ አገራቸዉንና ሕዝባቸዉን በታማኝነት ያገልግሉ፤ ከሕዝብ በተለያየ መንገድ የሚሰበሰበዉ ገንዘብ ለትክክለኛ ዓላማ ይዋል ..ወዘተ» የሚለዉን ፓሊስ ተግባራዊ እንዲሆን ከማድረግ ወደ ኃላ እንደማልመለስ አዉቃችሁ፤ እስከመጨረሻዉ ድረስ ታማኙ እንድትሆኑና የሕዝቡን ሀብትና ንብረት ብቻችሁን ተቀራምታችሁ፣ ጠግባችሁ እስከምትፈነዱ ድረስ ሕዝቡን እንድታጎሳቁሉና እንድታደኸዩ ምክሬን እለግሳችኋለሁ፡፡ ከፊለኩ በደርግ ጊዜ ያስወሰድኩትን እርምጃ በእናንተ ላይም የማሶሰድ ስልጣንና ብቃት እንዳለኝም ልታዉቁ ይገባችኋል፡፡

እናንተ ባለሀብቶች እጅጉን ታዝቤያችኋለሁ፡፡ ይኸዉም እለት እለት ሀብት ላይ ሀብት ብጨመርላችሁም እርካታ የሌላችሁ፣ የተቅበዘበዛችሁ፣ «ተመስግን» ማለትን የማታዉቁ በመሆናችሁ ነዉ፡፡ እስቲ ምስኪን ወገኖቻችሁን ተመልከቱ፤ አገኙ አጡ ፈጣሪያቸዉን ያመሰግናሉ፤ ባላቸዉ ረክተዉ፣ ተደስተዉ ይኖራሉ፡፡ እናንተ ግን ስንትና ስንት ሀብት ንብረት እያለችሁ እንኳ ሰላምና ደስታ ሊኖራችሁ ቀርቶ ራሳችሁን ታጠፋላችሁ፤ ታማርራላች፤ ሁልጊዜ ችግርና ሮሮ ብቻ ታወራላችሁ ፡፡ እናንተ በምድር ያልደላችሁ እንዴት በወደፊት መንግስቴ ይደላችኋል!?

እንግዲህ ምስኪኖቹ አምላካቸዉን እንደሚያመሰግኑ እናንተም እኔን ሌት ተቀን ካላመሰገናችሁኝ፤ ከበፊቱ በእጥፍ ሰላማችሁን፣ እርካታችሁን፣ ደስታችሁን የምወስድና ለተቅበዘበዝና ተስፋቢስ ለሆነ ሕይወት እንምዳርጋችሁ፤ እንዲሁም ለተለያየ ሱስ ተገዢ እንድትሆኑ አድርጌ እንደ ኳስ የማንጠባትባችሁ መሆኔን እንድታዉቁ ፡፡ እኔጋ ቀልድ እንደሌለ በደንብ የምታዉቁ ይመስለኛል፡፡ እንኳን እናንተን ለራሳችሁ የምትኖሩትን ቀርቶ የምርጥ ምርጥ ባለሚሎቼ ጠንቋዮች፣ መተተኞች፣ አስማተኞች፣ ሚርተኞች የመሳሰሉትን ሳይቀር ሰላምና እርካታ ነስቼ የማሳብድና ፍዳ የማሳይ ጨካኝ አረመኔ ነኝ፡፡

እናንተ የአዳም ዘሮች፤ የተቆጣጠርኳችሁ በልዩ ቋንቋዬ ዘፈንና ዳንኪራ ብቻ ሳይሆን እንዲሁ በፍላጎታችሁ እጃችሁን በምትሰጡበት በተለያየ ሱስ ጭምር ነዉ፡፡ ይኸዉም እዛዉ

ነፍሳቸዉ(ሕሊናቸዉ) አጠገብ ጉብ ብዬ ነፍሳቸሁን ስፈታተንና ሳስጨንቃችሁ ያስለመዳችሁኝን የተለያዩ ምሶቼን ስለምታቀርቡልኝ ነዉ፡፡ እኔም ለጊዜዉ ተንፈስ እንድትሉ ራቅ እልላቸኋለሁ፡፡ ወዲያዉ ደግሞ ተመልሼ በነፍሳቸሁ ላይ እነግሥና እንደፈለኩ አሽከረክራችኋለሁ፡፡

ታዲያ እንዲህ ስል ያ ጥሩ መዐዛ ያላዉን ምሴን ሲጃራ አታቡኑልኝ ማለቴ አይደለም፤ ያን ኅሊናችሁን የሚያመረቅነዉን ጫት አትቃሙልኝ ማለቴ አይደለም፤ ያ ኅሊናችሁን የሚያሳብደዉን አደንዛዥ ዕፅ አትዉሰዱ ማለቴ አይደለም፤ ያ ራሳችሁን እንዳትገዙ አድርጎ ኃጢአትን እንድትደፋፈሩ የሚያደርጋችሁን አስካሪ መጠጥ ጠጥታችሁ አትስከሩ ማለቴ አይደለም፤ ያ ከራሳችሁ ጀምሮ እስከ እንስሳ የምታፈሱልኝ ደም አስቀሩ ማለቴ አይደለም፤ ያ በአመድና በርኩሰት ላይ የምትንደባለሉልኝን ትርኢት አቁሙ ማለቴ አይደለም፤ ያ በየዓመቱ ይምታቀርቡልኝ አቴቴና የመሳሰሉትን ባዕድና ጣዖት አምልኮ እንድታቆሙ ማለቴ አይደለም፤ በየምናምንቴዉ ቦታ የምታጫጭሱልኝን እንድታቆሙ ማለቴ አያደለም፤ ያ የሰዶም ሰዎች የቅድስና ተግባራቸዉን ለማሰብ የምትፈጽሙትን ግብረሰዶም እንድታቆሙ ማለቴ አይደለም፤ ባጠቃላይ ምሴን በደንብ እንድታቀርቡና ሙሉ በሙሉ የደስታዬና የርካታዬ ተካፋይ እንድትሆኑና መጨነቃችሁና ሰላም፣ እርካታ ማጣታችሁ አሳስቦኝ መሆኑን እንድታዉቁልኝ እፈልጋለሁ፡፡

እናንተ የዴሞክራሲ አባቶች፣ እናቶች፣ ወንድሞች፣ እህቶች በቅድሚያ የሕዝቡን ነጻነትና መብት በማስከበራችሁና በማክበራችሁ በታላቁ ስሜ ዲያብሎስ አመሰግናችኋለሁ፡፡ የቀድሞ ነፍጠኞችና ትምክህተኞች ያጠፉብኝን የአምልኮት ስርዐቴን እንዲመለስ በማድረጋችሁና ሕዝቡም በነጻነት፤ እየተሽማቀቀ በየስርቻዉ የሚያቀርብልኝ የነበረዉን የአቴቴ በዐሌን እንዲሁም በየወንዛወንዙ የሚፈጸምልኝ እንደ ቦረንትቻ፣ አዳል ሞቴ፣ እሬቻ የመሳሰሉ የከበሩ በዐሌን፣ እንዲሁም ጥበብ የሆነዉ ዛሩና ማጓራቱን እዉቅና እንዲሰጠዉ በማስደረጋችሁ ነዉ፡፡

ታዳይ እናንተን ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የሃይማኖት አባቶችንንና ሰባኪዎችን ጭምር ላመሰግንና ሙገሳዬንም ላቀርብላቸዉ እወዳለሁ፡፡ ይኸዉም የእንደራሴዎቼ ተባባሪና አስፈጻሚ

በመሆናቸዉና ታማኝነታቸዉንም « እግዚአብሔር ረቂቅ ነዉና ከፈለጋችሁ ቤተ ክርስቲያንና መስኪድ ሄዳችሁ ማምለክ ትችላላችሁ፤ ካልፈለጋችሁ በየወንዛወንዙና በጨሌዉ አማካይነት አምልኮታችሁን ልትፈጽሙ ትችላላችሁ፤ ከፈለጋችሁ «የእናቴ ዉቃቢ፣የአባቴ ከራማ፣ የአርሲዋ እመቤት፣ የወሎ መጀን.. ወዘተ» ስያሜ በመስጠት ብታመልኩ ችግር የለዉም:: ዋናዉ ከወንጀል መከልከልና «በመስቀል ላይ የሁሉ ፈጣሪ አምላክ አልተሰቀለም:: በእርሱ አትመኑ:: እዉነተኛዉ ፈጣሪ አምላክ ይህን ልዩ ሐይቅና ወንዝ የፈጠረዉና ሳሩን የሚያለመልመዉ ነዉ:: እግዚአብሔር በምንም መልኩ ሰዉ ሆኖ ሊገለጥ አይችልም.. ወዘተ» በማለት ምስክርነትን ስጡ እንጂ፤ በብሔር ብሔረሰብ መብታችሁና ነጻነታችሁ እንዲሁም በራሳችሁ ባመናችሁበትና በባህላችሁ እንኳን «ፈጣሪ አለ» ብላችሁ አይደለም፤ «ሰይጣን ራሱ አምላክ ነዉ» ብትሉ ስህተት የለዉም» በማለታችሁ ነዉ::

በተለይ ደግሞ መስቀል ይዛችሁ የሃይማኖት ስርዐቴ በሚገባ ካለመሸማቀቅና ካለ ይሉኝታ እንዲከበር ቡራኬ የምትሰጡና ምእመኑ በግልጽ ዐመጻና ክህደት እንዲሁም የአምልኮ ምንዝርና እንዲፈጽም የምታደርጉ የሃይማኖት አመንዛሪና ሴሰኞች፤ ለጌቶቻችሁ ለእንደራሴዎቼና ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታቴ መሪዎችና ባለስልጣኖች ታማኝነታችሁንና አጋርነታችሁን መግለጻችሁና አንድነት ፈጥራችሁ በመሰላፋችሁ ላቅ ያለዉ ሙገሳዬ ይድረሳችሁ እላለሁ::

የታዘብኳችሁና አነስ ያለ ሙገሳዬን የማቀርብላችሁ ደግሞ፤ስንቱን የዐመጻ ስራዬና መድረኬ ላይ ቡራኬ እየሰጡኝ በእሬቻ በዐሌ ላይ ተወካዮትን ለዚያዉም የሊቀ ጵጵስና ማዕረግ የሌለዉን ካህን ልከዉ ቡራኬ ያሰጡት «የሃይማኖት መሪ የክርስቶስ እንደራሴ» በመባል የሚታወቁትንና መሰሎቾትን ጭምር ነዉ:: ለወደፊቱ እርሶና መሰሎቾት መተዉ ቡራኬ ይሰጣሉ በሚል እምነትና ለዚህ ስህተቶትም ይቅርታ ይጠይቃሉ በሚል ተስፋ ስለተባባሪነቶ ብቻ በድጋሜ አነስተኛ ሙገሳዬን አቀርባለሁ:: ምክንያቱም እግዚአብሔርን እንደማትፈሩና እንደማታፍሩ ስለማዉቅ እዉነተኛ አማኞችን አፍራችሁ እንደሆነ በመገመት ነዉ::

ሌላዉ የታዘብኳችሁ የከበረዉ በዐሌን ለማክበር የተገኛችሁ ምእመናኖቼ ዋናዉን ኮኮብ ዓርማዬን ዘንግታችሁ በደረጃ ዝቅ ባለዉ የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቴ ሰንደቅዓላማ ብቻ መታጀባችሁ ነዉ:: ያ የምንጠላዉ የነፍጠኞችና ትምክተኞች አረንጋዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ እድሜ ለእንደረሴዎቼና ለመሪዎቻችሁ ማንነቱን እኮ አበላሽተነዋል:: ይኸዉም ያማረ ነጭ ጋቢ ወይንም ነጠላ መሃሉ ላይ ዐይነምድር ወይንም ፋንድያ ወይም ኩስ ብታገኙበት እንደምትጸየፉትና እንደማትለብሱት ሁላ የኮኮቡን አርማዬን በማድረግ እንዲሁ አበላሽቼላችኋለዉና ለወደፊቱ ኮኮብ ዓርማዬን ከፍ ከፍ ለማድረግ አትሰቀቁ::

ስለሰንደቅ ዓላማ ካነሳዉ አይቀር በዚህ አጋጣሚ የተለየ ምስጋናና ዉዳሴ ለማቅረብ የምፈልገዉ አካላትን ለመጥቀስ እፈልጋለሁ::

ሀ.የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት፤ የሃይማኖት መሪዎች እንደ ክብር ማዕረጋችሁ

ለ.የዚሁ ሃይማኖት ተከታይ ምእመናን

ሐ.ኢትዮጵያንና ሰንደቅዓላማዋን እንወዳለን የምትሉ ሁሉ፤

ምክንያቱም ያ እጠላዉና እጸየፈዉ የነበረዉን መለኮታዊ ዓርማችሁ የአዳኛችሁና የአምላካችሁ የኢየሱስ ክርስቶስ መገለጫ የሆነዉን «ሞአ አንበሳ» (አሸናፊ አንበሳ) ከሰንደቅ ዓላማችሁ ላይ ድራሹን በማጥፋታችሁና ርኩስ የጨለማዉ ዓርማዬን ኮኮቡን መርጣችሁ «አንተ ትበልጥብናለህና አንተ የአሸናፊዎች አሸናፊ ነህ ንገሥብን» በማለታችሁ ነዉ::

እናንተ ቀድሞ በብሉይ ዘመን የእርግማን ምልክትና መቅጫ መሳሪያ የነበረዉን መስቀልን በሐዲስ ዘመን ለድኅነት የምትተቀሙ ሰዎችና በብሉይ ዘመን ለአማኞች ልዩ ዓርማ የነበረዉንና አሁን በሐዲስ ዘመን ደግሞ ለኔ ለጨለማዉ ገዥ ልክ እንደ መለኮታዊዉ ዓርማ የኢየሱስ ክርስቶስ ስያሜ የሆነዉን «ሞአ አንበሳ) ዓርማ እኔም ዲያብሎሳዊ ዓርማ በማድረግ በዓለምና በኢትዮጵያ ጭምር ያገነንኩትና ለኔ አገልጋይ መሆናቸዉን በዓርማዬ ማረጋገጫ የምሰጠዉን ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆናችሁ ሰዎች፤ በዓርማዬ ኮኮብ ላይ ክህደት እንደፈጸማችሁ በመቁጠር እርምጃ የማሶስድባችሁ መሆኑን በተለመደዉ በልምሾ አቅሜና በባዶ አንደበቴ በጥብቅ አሳዉቃችኋለሁ::

እዚህ ላይ ከምርጥ እንደራሴዎቼ መሪዎችና ከባለሟሎች ባለስልጣናት፣ እንዲሁም ከዉዶቼ ካድሬዎች በላይ በተለየ ሁኔታ የማደንቃቸዉና በጨለማዉ ስሜ የማመሰግናችሁ

ሰዎች አሉ:: እነዚህም መለኮታዊዉን ዓርማ አንበሳ አስወግደዉ የኔን የዲያብሎስን ዓርማ የሆነዉን ኮኮብ በሰንደቅ ዓላማ ላይ ከፍ ከፍ ብሎ እንዲወለበለብና በየመድረኩ «ኮኮብ የሌለበት ሰንደቅ ዓላማ የኛን ቤተክርስቲያን ስለማይወክል ኮኮብ የሌለበትን ሰንደቅ ዓላማ አታምጡ፤ አትያዙ» በማለት የሚሰብኩት «የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት መሪ ነን፤ አገልጋይ ነን፤» የሚሉትን ከሥጋዉያን መሪዎች ቀጥሎ « እንደ ልቤ» ለመባል የበቁትን ነዉ:: ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ «ሞአ አንበሳ ዘምነገደ ይሁዳ» ተብሎ የተነገረዉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን በደንብ እያወቁ፣ ራሳቸዉን ለኔ ለጨለማዉ ገዥ ሲሉ ክደዉ፣ ታላቅ መስዋዕትነት በመክፈል መለኮታዊዉን ዓርማ ክደዉ ዲያብሎሳዊዉን ዓርማ የሆነዉን ኮኮብ ከጌቶቻቸዉ ሥጋዉያን ጋር የሚያገኑትንና ከፍ ከፍ በማድረግ ምእመኑ ከእግዚአብሔር በኖኅ አማካይነት ያገኘዉን ቃል ኪዳን ዘላለማዊ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ክህደት እንዲፈጽሙ ስላስደረጉ ነዉ:: ታዲያ ለነዚህ «አገልጋዮች ነን» ለሚሉት ምስጋና ብቻ አይደለም ለአስር ደቂቃ የሚቆይ ጭብጨባ ይገባቸዋል::

እናንተ « ከክርስቶስ መንፈስ ተቃራኒ በሆነ መንፈስ የሚከናወን አምልኮ ዉስጥ አትሳተፉ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነዉ፤ ከዚህ አምልኮ የወጣ የክህደትና የዐመጻ፣ እንዲሁም ባዕድና ጣዖት አምልኮ ነዉ» በማለት፤ የአማኞቼን ነጻነትና መብት የማታከብሩ ኢ-ዴሞክራት የሆናችሁ ሁሉ፤ በራሴ ርኩስ ስምና በእንደራሴዎቼ ስም እምላለዉ፤ ዴሞክራሲ መብቴን ተጠቅሜ የእናንተን እምነትና ሃይማኖት ከምድረገጽ ከማጥፋት ወደ ኋላ የማልመለስና እናንተንም ከመንግስቴ ከገሃነመ እሳት የምለያችሁ መሆኔን በጥብቅ አሳዉቃችኋለሁ::

በተለይ በተለይ እናንተ የተከደነዉን እየገለጻችሁ፣ የተሰወረዉን እያሳወቃችሁ ለዓለም ሕዝብ ገበናዬን እገለጻችሁና ባዶዬን ልታስቀሩኝ ሌት ተቀን የምትተጉ፤ አንዴ «ቅዱሱ ኪዳኗ ኢትዮጵያና የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ» እያላችሁ፤ የሕዝቡን ምርጫ የማታከብሩ፤ ሕዝቡ በግልጽ እያመለከኝና «አንተ ከሁሉ ትበልጥብናለህና በሁለመናችን ላይ ንገሥ፣ ፈቃድህን እንፈጽማለን፣ እናስፈጽማለን፣ ለመሪነት የምትቀባልንን ሁሉ በደስታና በፈንጠዚያ እንቀበላለን፣ የፈለግነዉን የዐመጻና የርኩሰት ተግባር በነጻነት እንድንፈጽም ሙሉ ያልተሸራረፈ ዴሞክራሲ አንተ እዉነተኛ አምላካችን ስለምትሰጠን ካንተ ዉጭ ማንንም አንቀበልም» እያሉኝ፤ እናንተ ለምድነዉ ከምርጫቸዉና ከፍላጎታቸዉ ዉጭ ባለ ሕይወት

እንዲመላለሱ የምታስተምሩትና መልእክት የምታስተላልፉት? ብትጠነቀቁ ይሻላችኋል:: እኔ እንኳን ለእናንተ ቀርቶ ለማንም የማልመለስ መሆኔን እንደምታዉቋቸዉ አምባገነኖች በባዶ ሕይወት እንደሚደነፉት የአንደበት እብሪተኛ ነኝ::

እንደራሴ መንግስቴ ወያኔ(ሕወሐት) ወይንም ኢህአዴግ፤ መቸስ ልዩ ስማችሁን ለዓለም ባስተዋዉቅ ደስ ነዉ የሚላችሁ እንጂ ከንቱ ዉዳሴ ይሆንብናል እንደማትሉ ትህትናችሁን ስለማዉቅ በግልጽ ምስጋናዬን ባቀርብ የተሸለ ነዉ በሚል ድንቅ ምስክርነታችሁንና አገልግሎታችሁን ለዓለም አሳዉቃለሁ:: ይኸዉም በስብሰባና በሚዲያ «ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የነፍጠኞችና የትምክህተኞች ምሽግ ናት፤ ቋንቋችሁንና ባህላችሁን ያጠፉት እነዚህ ነፍጠኞችና ትምክተኞች ናቸዉ::» በማለት ምስክርነትን ስለሰጣችሁና ምኑንም የማያዉቁትንና እንደ ቦይ ዉሃ ወደ ወሰዷቸዉ የሚሄዱትን ሰዎችና ዉስጣቸዉ በቀልና ክፋት ጥላቻ የሞላባቸዉ ሰዎች በጋራ ኅሊናቸዉ በእናንተ ስብከት እንዲመረዝ አድራጋችሁ አብያተ ክርስቲያናትን እንዲያቃጥሉ፤ ክርስቲያኖችንንም እንዲጨፈጭፉ፤ «ከክልሌ ዉጡ» እንዲሉ አስደርጋችሁ ክርስቲያኖች ላይ ችግርና መከራ እንዲደርስባቸዉ በማስደረጋችሁ ነዉ:: ይህ ታላቅ ድርጊታችሁ ለዘላለም ታስቦ እንዲኖር በተለያዩ ቦታዎች በሐዉልትና በፖስተር ላይ ማንነታችሁም ከፍ ከፍ እንደማስደርጋችሁ በዚሁ አጋጣሚ በጨለማዉ ስሜ ቃል እገባላችኋለሁ::» **ይላል ሰዎችን ለበቀል፣ ለጥላቻ፣ ለክፋት የሚያነሳሳዉ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከጭፍሮቹ ሰይጣናት ጋር በመሆን::**

## ምእራፍ አራት

« እናንተ የአዳም ዘር ከእግዚአብሔር ጸጋ ለመለየት ሌት ተቀን የምትተጉ ሰዎች፤ ልክ እንደኔ የጨለማዉ ገዥ ዉሎዋችሁንና ዙፋናችሁን በተዝዋዋሪ በሚሸተዉ፣ በሚጠነባዉ፣ በሚገማዉ በዐይነ ምድሩ፣ በሽንቱ ፣ በቆሻሻ ላይ ለማድረግ እየታገላችሁ መሆኑን ልታዉቁ ይገባል:: በዚህም ምክንያት ምርጫቹ ከተቀደሰ ስፍራ ይልቅ የርኩሰት ቦታ ነዉ:: ለመሪነት ሆነ ለአገልጋይነት የምትመርጡት የሚያጎሳቁላችሁን፣ የሚቀጠቅጧችሁን፣ የሚያስጨንቃችሁን፣ ፍዳና መከራ የሚያሳያችሁን፣ ተቧድኖ ራሱን ብቻ የሚያበለጽገዉን፣ እናንተን ግን በድህነት፣ በረሀብ፣ በችግር የሚቀጣችሁን ሰዉ ነዉ::

ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑት ደግሞ ኢትዮጵያዉያን ናቸዉ:: ይኸዉም በምርጫ 2002 በአራቱም ማዕዘን ያላችሁ የኔን የጨለማዉ ገዥ እንደራሴ መሪና ባለሟሎቼን ባለስልጣናትን እንዲሁም ዉዶቼን ካድሬዎቼን ከመቶ ከ ዘጠና ዘጠኝ እጅ በላይ በሆነ ብዛት መርጣችኋል:: ይህም የሚያሳየዉ ምርጫችሁ እኔን የጨለማዉ ገዥን መሆኑንና « እኛ የምንፈልገዉ መሪ ሆነ ባለስልጣን እንዲሁም ኃላፊ ዉስጡ ተንኮል፣ ክፋት፣ ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት፣ ጥላቻ፣ በቀል የሞላዉ፤ ኅሊናዉ በዘረኝነትና በጎጠኝነት የተበከለና የተመረዘ ጨካኝ፤ አስመሳይና ሸንጋይ፤ ኅሊናዉን የሚገለባብጥ ሰዉን ነዉ» በማለት ስለመረጣችሁ ምርጫዬ ምርጫችሁ በመሆኑ በዚሁ አጋጣሚ በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችኋለሁ::

ታዲያ በራሳችሁ ምርጫ « እንዲህ ሆን ፣ እንዲህ ተቸገርን፣ ፍዳችንንና መከራችንን አየን፣ ተሰቃየን.. ወዘተ» በማለት አምላካችሁን እንዳታማርሩ:: ምክንያቱም በነጻ ኅሊናችሁ ተመርታችሁ ነዉና የመረጣችሁት ምርጫችሁን ያከብራል:: ነገር ግን የምርጫችሁን ፍሬ ነዉ የሚሰጣችሁ እንጂ የእርሱን ፍሬ አይሰጣችሁም::

በተቃራኒዉ ደግሞ « እግዚአብሔር ሆይ! ምርጫችን አንተን ነዉ፤ አንተ ንገሥብን ፤ አንተ አስተዳድረን::» ካላችሁ ደግሞ እንደምርጫችሁ የራሱን መንግስት አቋቁሞላችሁ ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተ ክህነቱ፣ ቤተ መንግስቱን በአንድላይ በመንፈስ ቅዱስ እንዲመራ አድርጎ ምድራዊ በረከትን፣ ፍቅርን፣ ሰላምን፣ እርካታን የምታገኙ፤ ከሥጋችሁ ስትለዩ ደግሞ

ለሕያዉነት ዘመን በሰማያዊ መንግስቱ በቅዱሳን መላእክት አኗኗር እንድትኖሩ ያደርጋችኋል:: ይሁንና እናንተም እንደ እኔ ጨለማዉ ገዥና እንደ ጭፍሮቹ ሰይጣናት ክብር የማይወድላችሁ ስለሆነ ምርጫችሁ ከእግዚአብሔር ጸጋ መለየትንና መራቅን ፣ በጉስቁልና ሕይወት መመላለስን፣ በመከራና በፍዳ ኑሮ መኖርን ስለሆነ ይኸዉ ፍዳችሁንና መከራችሁን ትቀበላላችሁ:: በዚህ ሳያበቃ ነፍሳችሁ ደግሞ ዳግም የንስሐ እድል በማታገኙበት በሲዖል ነጻነቷን ተገድቦ ትኖራለች:: በመጨረሻም በፍርድ ቀን «ምርጫህ ምራጫችን ነዉ::» ካላችሁኝ ከግብር አባታችሁና ጌታችሁ ጋር በገሃነመ እሳት ዉስጥ ተከባብረን እንኖራለን::

እናንተ የአዳም ዘሮች፤ በእንደራሴዎቼና በባለስልጣኖቼ፣ እንዲሁም በካድሬዎቼ ስብከት ተታላችሁና ኅሊናችሁ ተበክሎ የአህዛብያዉያን አምልኮ የሆነዉ ባህላዊ ( ባዕድ) አምልኮና ጣዖት አምልኮ « እምናታችን ነዉ» ብላችሁ በዐመጻና በክህደት እንዲሁም በአምልኮ ምንዝርና ሕይወት ተመላልሳችሁ የእግዚአብሔርን መንግስት መዉረስ ቀርቶ፤ በሰማያዊ አባታችሁና አምላካችሁ ክርስቶስ ስም ክርስቲያን የሚለዉን ስያሜ ይዘዉ የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ የፕሮቴስታን «እምነት» ተከታዮችን እንኳ በተለያየ ምልኩ መጫወቻ አድርጌያቸዉ ከእግዚአብሔር መንግስት ለይቻቸዋለሁ::

ይኸዉም በአታላዩ(በሸዋጁ) ርኩስ መንፈሴ መሪነት ባዘጋጀዉላቸዉ የእምነት መመሪያ (ዶክትሪን) ነዉ የሁሉ ፈጣሪ እግዚአብሔር የሆነዉን ኢየሱስ ክርስቶስን « አማላጅ ነዉ:: ፍጠር ነዉ :: ነብይ ነዉ:: ተራ ሰዉ ነዉ :: አብና መንፈስ ቅዱስ የሚባሉ የሉም አንድ ኢየሱስ ብቻ ነዉ::» እያስባልኩ ወደ ክህደትና ሞት መንገድ የመራዋቸዉ:: እኔን የሚገርመኝ እስከ ዛሬ ድረስ ለዉድቀትና ለጥፋት የተጠበብኩባቸዉን አለማወቃቸዉ ብቻ ሳይሆን በከፋፍለህ አዳክም መመሪያዬ መሰረት አንድ እንዳይሆኑ «አንዱ አማላጅ፣ አንዱ ፍጡር፣ አንዱ ኢየሱስ ብቻ» በሚል «የእምነት» ድርጅት እንዲያቋቁሙ በማድረግ ከአስራ ሺህ ድርጅቶች በላይ አቋቁሜ በእምነት አንድ አለመሆናቸዉን እያወቁ «ልሳን » የሚባለዉን ዘመናዊ የዛርና የሚርት ትዕይንት «መንፈስ ወረደልን» በሚል ስሜት እንዲመለከቱ አድርጌ በሁሉም ድርጅቶቼ እንዲከሰት እያደረኩ፤ አንድ ሰዉ እንኳ «ተቃራኒ እምነት እያለን እንዴት

ተመሳሳይ ልሳን ምልክት በሁላችን ላይ ይታያል? የሆነ የተታለልነዉና የሳትነዉ እዉነት አለ» ብሎ የሚጠይቅና እዉነትን የሚፈልግ የለም፡፡

ሁሉም ለቅርፊት ሥጋዉ በሚመች ሕይወትና ስርዐት መመላለስ ስለሆነ ምርጫዉ፤ በአንደበቱ « እግዚአብሔር ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ወንጌል» እያለ በሞት መንገድ ዉስጥ እንዲመላለሱ በማድረጌ አንደኛዉን የሚሊኒየም ግቤን አሳክቻለሁ፡፡ ታዲያ ብዙ ተከታይ እንዲያገኙ እኔን «ዲያብሎስ» እያሉ እንዲያጥላሉኝና እንዲረግሙኝ ሙሉ ነጻነትንና ፈቃድ ሰጥቻቸዋለሁ፡፡ ልክ እንደዘመኑ አንዳንድ «ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ነን» በማለት የመንግስት መሳሪያ የሆኑና ተቃዋሚ ላማስመሰልና ደጋፊ ለማግኘት ሲሉ አንዳንዴ መንግስትን ሲቃወሙና ሲኮንኑ መንግስት የራሱ ተለጣፊ መሆናቸዉን ስለሚያዉቅ አንዳች እንደማይላቸዉና ቂም ይዞባቸዉ እንደማይበቀላቸዉ ሁሉ፤ እኔም የጨላማዉ ገዥ እነዚህ በእግዚአብሔር ሆነ በኢየሱስ ስም የሚነገዱ አገልጋዮቼ በኔ ቁጥጥር ዉስጥ ስለሆኑ ቢሰድቡኝ ሆነ ቢረግሙኝ አንዳች የማይሰማኝ ሲሆን፤ ዋናዉ ፍላጎቴ በእዉነተኛዉ አምልኮና እምነት ዉስጥ ያሉ ምእመናን « እግዚአብሔር የሚሰበክበትና ዲያብሎስ የሚረገምበት አዳራሽ ነዉ» በማለት ወደ እኔ ጨለማዉ ገዥ የእምነት ድርጅቴ ዉስጥ እንዲመጡ ነዉ፡፡

ኀሊናቸዉን በራሳቸዉ ጊዜ አደነደኑት እንጂ መሪያቸዉ መንፈስ ቅዱስ ቢሆን ኖር እንኳን አስራ ሺህ ቤት ድርጅት ሊቋቋም ቀርቶ ሁለት የተለያዩ ተቋም አይሆኑም ነበር፡፡ ነገር ግን ምርጫቸዉን እኔን ስላደረጉና ሁሉም ድርጅቶች በበላይ የምመራቸዉና የማሳስባቸዉ እኔ ስለሆንኩ እያንዳንዱን የድርጅቴን አባል እንደ ኳስ ልጫወትበትና ከእዉነት ላርቀዉ ችያለሁ፡፡

የሚያሳዝነዉና የሚገረመዉ ደግሞ ከእዉነተኛነት፣ ከቅንነት ፣ ከየዋህነት፣ ከልባምነት ሕይወት መራቃቸዉና፤ በደመ ነፍስ በመመላለስ በክህደት፣ በዐመጻ መኖራቸዉ ሳያንሳቸዉ፤ እኔ እንኳ የማልዳፈረዉን በትዕቢትና እብሪት በሞላዉ ንግግር ቅዱሳን መላእክትን፣ ነብያትን፣ ሐዋርያትን፣ ሰማዕታትን፣ ጻድቃንን፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ የአደራ እናታቸዉን ለሰዉ ዘሮች ደኅንነት ሁል ጊዜ ኀዘንተኛ መሆንን የመረጠችሁንና ለሰዉ ዘር በሙሉ ጥብቅና የምትቆመዉን ድንግል ማርያምን ያዋርዳሉ፤ ያቃልላሉ፤ ይሰድባሉ፡፡ በዚህ ብቻ ሳያቆሙ እለት እለት እዉነተኛዉን አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን «አማላጅ ነዉ ፤ ፍጡር ነዉ » እያሉ

ይሰድባሉ፤ ያዋርዳሉ:: ታዲያ ይህን ድርጊታችሁን ማቅረቤ ማንነታችሁን ለመግለጽና ወደ እዉነተኛ የሕይወት መንገድ ዉስጥ በንስሐ እንድትመለሱ ፈልጌ ሳይሆን ከእኔ በላይ የሆነዉን ድፍረታሁንና ጀግንነታችሁን ለማድነቅ ፈለጌ መሆኑን እናንተም የምትረዱት ይመስለኛል::

እናንተ ኢትዮጵያዉያንና የዓለም ሕዝቦች፤ እንደራሴዎቼ መሪዎቻችሁ፣ ባለሟሎቼ ባለስልጣናት፣ ዉዶቼ ካድሬዎች፣ እንዲሁም ጠንቋዮች፣ አስማተኞች፣ መተተኞች፣ ባለዛሮች.. ወዘተ ያመጡላችሁን የባህልና የክህደት፣ የርኩሰት አምልኮና ስርዐት ርግፍ አድራጋችሁ በመተዉ፤ በእዉነተኛ ንስሐ የቀደሙ ወላጆቻችሁ ያመጡላችሁን በብሉይ ዘመን በእዉነትና በመንፈስ የሚከናወነዉን ኪዳነ ልቦና፣ በኋላም በሙሴ አማካይነት የመጣዉን ኪዳነ ኦሪት፣ በመጨረሻም የካም፣ የሴም፣ የያፌት ነገድ ዉህድ ዘር ከሆነችዉ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰዉ የሆነዉ አምላክ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ በመሰረተዉ ኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ተመርታችሁ፤ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም በመጠመቅ ከእግዚአብሔር እዉነተኛ ልጅነትን ብታገኙ፣ ሕያዉ ሆናችሁ በመንግስተ ሰማያት እንድትኖሩ የሚያስደርገዉንና ኃጢአታችሁን ከእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ የሚደመስስላችሁን ቅዱስ ሥጋዉንና ክቡር ደሙን ብትቀበሉ፤ በእዉነተኛነት፣ በቅንነት፣ በየዋህነት፣ በልባምነት ሕይወት ብትመላለሱ፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ደስ የማይለኝ ስለሆነ ከኔ ጋር ያላችሁን ወዳጅነት ሆነ አንድነት ወዲያዉ እንድታቋርጡ የማደርግ መሆኑን በጥብቅ አሳዉቃችኋለሁ:: ስለዚህ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወታችሁ እስከመጨረሻ እንድትጸኑ አሳስባችኋለሁ::

ሌላዉ አደራ የምለዉ ሰባቱ ቅዱስ ኪዳናት የተባሉትን መመሪያችሁ አድርጋችሁ ብትኖሩ፤ በምድራዊ ሕይወት ዘመናችሁ በረከት፣ ሰላም፣ ፍቅር፣ እርካታ፣ አንድነት፣ ቅድስና በተሞላዉ ኑሮና ሕይወት እንድትመላለሱና ከሥጋ ሞት በኋላ ደግሞ በእግዚአብሔር መንግስት ሕያዉ ሆናችሁ በቅዱሳን መላእክት ሕይወት አይነት አኗኗር በቅድስናና በደስታ ሕይወት ብቻ እንድትኖሩ ስለሚያደርግ፤ ይህ ድርጊታችሁ ደግሞ በኔ ላይ ክህደትና ዐመጻ እንደፈጸማችሁ ስለሚያስቆጥር የክህደትና የሽብርተኛነት አዋጅ አስወጥቼ ከምድረ ገጽ

ለማጥፋት ሆነ ለማጥቃት እንዳልችል ልምሾ ብታደርጉኝም፤ እንዲሁም ሌት ተቀን እረፍት ነስታችሁኝ በመከራ፣ በስቃይ፣ በምሬት ሕይወት ዉስጥ እንድኖር ብታስገድዱኝም፤ እናንተን እስከ መጨረሻዉ እቅታ ድረስ ልበቀላችሁ ወደ ኃላ የማልል መሆኔን  በተለመደዉ ጉራ፣ እብሪትና በዶነት በተሞላዉ አንደበቴ አስጠነቅቃችኋለሁ::

መቼስ እኔ የማዝንለት ግለሰብ ሆነ ቡድን፣ መንግስት፣  የእምነት ተቋም የሌለ ቢሆንም፤ «ግድ እዘንላቸዉ» ብባል የሚያሳዝኑኝ ሙስሊም ወገኖቻችሁ ናቸዉ:: ዉዱ ባለዉለታዬ የሆነዉ፤ ፍጹም እግዚአብሔር የሆነዉን አምላክ በድፍረት «ኢየሱስ (ኢሳ) እንደ እኔ ነብይ ነዉ እንጂ አምላክ አይደለም::» በማለት ትዉልዱ በክህደት እምነት እንዲመላለሱ በማድረጉ ምክንያትና በእምነቱ ዉስጥም « ሰዉ ሰዉን ገሎ፣ ግፍና ጭከናን ፈጽሞ ገነት ይገባል» የሚል  አሰተምርሮ ስላለዉ በአራቱም ማዕዘን ፈቃዴን ለማስፈጽም እጅግ ስላመቻቸልኝ በዚሁ አጋጣሚ በጨለማዉ ስሜ ባለበት ቦታ አመሰግነዋለሁ::

ታዲያ አሳዛኞቹ ደግሞ በእምነቱ ዉስጥ ባለዉ አንዳንድ እዉነት ማስመሰያ አስተምሮ አምላካቸዉን በመፍራት በጾሙ፣ በጸሎቱ፣ በስግደቱ፣ በምጽዋዕቱ.. ወዘተ የሚመላለሱ፤ ከአህዛብ የራቁትነት አለባበስ  ራሳቸዉን ለይተዉ እግዚአብሔር መፍራት ያለበት የጨዋ አለባበስ የሚለብሱ፤ ከዳንኪራዉ፣ ከዘፈኑ ራሳቸዉን የለዩ፤ ከሱስና ከስካር የራቁ፤ የአሜሪካንና የአዉሮፓን የአህዛብ ባህል የማይከተሉ፤ ሌሎች ወገኖቻቸዉን የሚወዱና የሚያከብሩ፤ ባጠቃላይ እኔ የጨለማዉ ገዥ ደስ በማይለኝ ሕይወት የሚኖሩት በእምነቱ ዉስጥ የሚመላለሱት ሰዎች ናቸዉ::

ዞሮ ዞሮ የሕይወት መንገድን ስለሳቱልኝ ፍርዱ ቢቀልልላቸዉም እንደ እግዚአብሔር ቃል « በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ (በሥላሴ) ስም  ተጠምቆ ከእግዚአብሔር ልጅነትን ያላገኘና መለኮት የተዋሀደዉን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ያልተቀበለ የእግዚአብሔር መንግስት አይወርሱም::» በሚለዉ የፍርድ ቃል እጽናናለሁ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር ወልድ በሥጋ ማርያም ተገልጾ የተናገረዉ ስለሆነና « ቃሌ ከሚያልፍ ሰማይና ምድር ቢያልፍ ይቀላል» በማለት ቃሉ ምን ያህል ጥብቅ መሆኑን ለአዳም ዘር ስለገለጸ ለኔም ሆነ ለእናንተ አንዳች

አድሎ እንደማያደርግ የታወቀ ነዉና። ስለዚህ ከተፈረደባችሁ አይቀር እኔ ደስ በምሰኝበት የኃጢአት ተግባርና ሕይወት ብትመላለሱ የተሻለ መሆኑን እመክራችኋለሁ።

በዚሁ አጋጣሚ አንድ ሥጋቴን እገልጽላችኋለሁ፤ ይኸዉም የቅዱሱ ኪዳን ሕዝብ ለማጥፋትና ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለመደምሰስ የተሰለፋችሁ የጥፋት ሰዎችና የዐመጻ ልጆች የሆናችሁ ዉዶቼ፤ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ጽዋችሁ ሲሞላ የመጨረሻ ዕጣ ፈንታችሁ የሚሆነዉ በዚህች ምድርም መዋረድ፣ መከራና ስቃይን መቀበል፣ በመጨረሻም መጠረግና በቀጥታ ካለምንም ጥያቄ ወደ ጨለማዉ ቦታ ሲኦል መግባት መሆኑን አዉቃችሁ እጃችሁን ለእግዚአብሔር ትሰጣላችሁ የሚል ነዉ።

ታዲያ አንዳንዶች የኔን አሰራር ያልተረዱ ባለሚሎቼና ዉዶቼ ያልገለጽኩላቸዉን ምስጢር አሁን ብገልጽላቸዉ ምን እንደሚሉ ባላዉቅም፤ የጥፋት ሰዎችና የዐመጻ ልጆች ለኔ ዉዶቼ የሆናችሁ ግን ትምህርት እንዲወስዱ ቀኝ ገዢዎች ከእናት አገራቸዉ ለይተዉ «ሱማሊያ» የሚል ስያሜ አዘጋጅተዉ የዐመጻና የክህደት ተግባር ሲያስፈጽሟቸዉ የደረሰባቸዉንና እየደረሰ ያለባቸዉን ችግርና መከራ ዓለም ስለሚያዉቀዉ ብዙ አልናገርም። በተዝዋዋሪ ኢትዮጵያን ለማጥፋት የተሰለፉት የኢራቁና የሊብያዉ መሪ ምን አይነት እድል እንደገጠማቸዉ ዓለም ስለሚያዉቅ ስለዚህም አልናገርም።

ስለ ሁለተኛዉ ዓለም ጦርነትም ማስታወስ አልፈልግም። እኔ የምናገረዉ በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ የተቀደሰችዉን አገር ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለማጥፋት የተሰለፉ መንግስታት፣ ቡድኖች(ድርጅቶች)፣ ግለሰቦች ካለፉት መማር አልቻሉምና በእግዚአብሔር ቁጣ እንዳልነበሩ ቢሆኑና ቢጠረጉ እኔ አንዳች እንደማልጠየቅ እየገለጽኩ፤ በመጨረሻ ግን «እናንተ ዉዶቼንና ባለሚሎቼ እናንተን የማጣ ከሆነ አዘንተኛ እንደምሆን አዉቃችሁ አሁን ባለቀለት ሰዓት ቢሆንም «ምናለ ብታጽናኑኝና ብታስደስቱኝ? » በማለት የመሰናበቻ ጥያቄ አቀርብላችኋለሁ።

ምክንያቱም ለወደፊት ፈቃዴን የሚፈጽም የሚያስፈጽም እንደራሴና ባለሚል አጣለሁ የሚል ስጋት ስላለብኝ ነዉ። መቸስ ተማሪ አጥንቶ አጥንቶ ጥሩ ዉጤት እንደሚጠብቅ ሁሉ

እኔም በኃጢአት አሰልጥኜ አሰልጥኜ ጥሩ ዉጤት እንደምጠብቅ እንኳን እናንተ ምርጦቼ የጥፋትና የዐመጻ ልጆች ቀርቶ ጠላቶቼ የሆኑት «የእግዚአብሔር ባለሟልና ልጆች» የሚባሉት ከአምላካቸዉ ጋር አንድነትና ህብረት ፈጥረዉ ከኔ ፈቃድ የወጡና ያፈነገጡት ሰዎች ጭምር ያዉቃሉ፡፡» **ይላል የኢትዮጵያንና የኢትዮጵያዉያንን መጥፋት የሚፈልገዉ የጨለማዉ ገዥዉ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ፡፡**

## ምእራፍ አምስት

« እናንተ የዓለም ሕዝቦች! መቼስ የእርሷን መራብ፣ መቸገር፣ መለመን ፣ ድርቅ፣ አደጋ፣ በሽታ፣ ስደት፣ ጦርነት ባጠቃላይ ጉስቁልና መስማትና ማሰማት እንጂ እንቁነቷን መስማት ሆነ ማሰማት ባትፈልጉም ሳልወድ በግድ በእሳት ሰንሰለት ታስሬ ነዉና የምለፈልፈዉ ስለ ቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ እዉነቱን እገልጽላችኋለሁ::

እናንተ ያልጠበቃችሁትን ሰባቱን ቅዱስ ኪዳናት የሆኑትን በኪዳነ ልቦና የተመሰረተዉ የአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፣ ከዚያም በኖኅ ቀስተደመና፣ በመልከ ጼዴቅ ቁርባንና በአብራሃም ግርዘት ተገንብቶ ያደገዉን፣ በመካከለኛም የሕግ ዘመን በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት የማክዳንና የእሥራኤላዊዉን ንጉሥ የሰሎሞንን ዘር ሐረጎች በማዋሐድ በኪዳነ ኦሪት የተከናወነዉን፣ በመጨረሻም የሕይወት ዘመን ከዚህ ምሉእ ትዉልድ ከተገኘችዉ ከድንግል ማርያም በተወለደዉ ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አጽንቶና ዘላለማዊ ዘዉድ አቀዳጅቶ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ የፈጸመዉን ኪዳናት በታማኝ ዜጎቿ ተጠብቆ ያለ ነዉ::

ቀደም ሲል ከላይ ለተገለጹት ጎስቋላ ኑሮና ሕይወት የዳረጓት ዐመጸኛና ከሃዲ የሆኑት የኔ የጨለማዉ ገዥ እንደራሴዎችና ባለሟሎች፣ እንዲሁም ዉዶቼ ናቸዉ:: ይኸዉም ሕዝቡን በጦር አፈ ሙዝ አስገድደዉትና አስጨንቀዉት ቅዱሱን ኪዳን እንዳይጠብቀ አድርገዉ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት እንዲመላለስ ስላደረጉት ነዉ:: ነገር ግን የቃል ኪዳን አገር ናትና ቅዱስ ኪዳኑን በጠበቁ ዜጎች አማካይነት ለእናንተ በእግዚአብሔር እንደራሴ መንግስትነቷ መሪያችሁና እዉነተኛ አገልጋያችሁ ትሆናለች:: ዉድቀቷንና ጥፋቷን የሚመኙትን ሁሉ የምታሳፍር ታላቅ ገናና አገር ትሆናለች:: እናንተ ግን ልዩ የኳስ መጫወቻ ሜዳ ሆናችሁ ስላገኘዋችሁ እንደፈለኩ እጫወትባችኋለሁ፤ ለጥፋትና ለዉድቀት እዳርጋችኋለሁ::

በኢትዮጵያ ምድር እንዴት ቁም ስቃዬን እንደማይ አይታችሁና አዉቃችሁ ቢሆን ኖር ከኔ የባርነት አገዛዝ ተላቃችሁ እጃችሁን ለአምላካችሁ በመስጠት በቅዱስ ኪዳኗ

የእግዚአብሔር መንግስት በሆነችዉና በምትሆነዉ በኢትዮጵያ ትመሩ ነበር፡፡ አሁን አሁንማ በአራቱም ማዕዘን መከራዉና ስቃዩ አንገሽግሾናልና « ምናል እነዚህ ኢትዮጵያዉያን የኔ የተለያዩ የፕሮቴስታንት እምነት ድርጅቶች መሪ የሆነዉን የጨለማዉን ጌታ የሱስን በየቦታዉ ቢያገኑልኝ፣ ቢያመልኩልኝ፣ ቢያመሰግኑልኝ » እያልኩ ቀን ከሌሊት በምርጥ አገልጋዮቼ አማካይነት ስተጋ፤ እነሱ በታቃራኒዉ በከተማም፣ በገጠርም፣ በመንደር፣ በሰፈርና በበረሀዉ ሳይቀራቸዉ ሥላሴ፣ አማኑኤል፣ መድኃኔ ዓለም፣ ኢየሱስ፣ ባለወልድ፣ ማርያም፣ ልደታ፣ ባዕታ፣ ቁስቋም፣ ኪዳነምህረት፣ ሚካኤል፣ ገብርኤል፣ ዑራኤል፣ ራጉኤል፣ ሳቁኤል፣ ፋኑኤል፣ አርሴማ፣ ክርስቶስ ሰምራ፣ ጊዮርጊስ፣ መርቆርዮስ፣ ተክለሃይማኖት፣ ገብረመንፈስ፣ ጴጥሮስ፣ ጳዉሎስ፣ ማቲዎስ፣ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ፣ ስጢፋኖስ፣ አብርሃ ወአጽብሃ፣ ሰላማ፣ አረጋዊ፣ ገሪማ፣ ላሊበላ፣ ይምርሀነ ክርስቶስ፣ ኢየሱስ ሞዐ፣ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ፣ ዜና ማርቆስ፣ ሀብተማርያም፣ ቂርቆስ፣ ኤልያስ፣ ኪሮስ፣ ያሬድ..ወዘተ ምኑ ተነግሮ ያልቃል፡፡» የሚል ስያሜ እየሰጡ አብያተ ክርስቲያናትን እያነጹ ከወር እስከ ወር እግዚአብሔርን፣ ድንግል ማርያምን፣ ነብያትን ፣ ሐዋርያትን ፣ ሰማዕታትን ፣ ጻድቃንን እያሰቡ ፍዳዬን ያሳዩኛል፡፡

ዱሮ በገዳሙ፣ በዋሻዉ ዉስጥ ራሳቸዉን በአምላካቸሁ ፊት ዝቅ አድርገዉ በሚኖሩት ጻድቃን ፍዳዬን እመለከት የነበረዉ አሁን ግን የእነሱ አልበቃ ብሎ በከተማም፣ በገጠርም፣ ባጠቃላይ በአራቱም ማዕዘን በጸሎት፣ በጾም፣ በስግደት፣ በትምህርት፣ በስብከት፣ በጠበል፣ በእምነት፣ በቅዳሴዉ ፣ በማህሌቱ ፣ በሰዐታቱ፣ በቅኔዉ፣ በኪዳኑ፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ በቅዱስ ሥጋዉና በክቡር ደሙ..ወዘተ ስፍር ቁጥር በሌላዉ መሳሪያ መከራዬን እያየሁ እገኛለሁ፡፡ እኔ የጨለማዉ ገዥያችሁ ምን እንደማደርግ ግራ ገብቶኛል፡፡

አሁን ግን የሱስ የሚለዉ ስያሜዬ በክርስትና ሽፋን ስም የተላበስኩት አላዋጣኝ ስላለ ሌላኛዉን የክህደት ስሜን ተላብሼ የተለያዩ ስልቶችን ተጠቅሜ በጨለማዉ ተግባሬ ድራሻቸዉን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ቆረጬ መነሳቴን በዚሁ አጋጣሚ በተለመደዉ በእብሪትና በባዶ ቀፎ አንደበቴ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ፡፡ ከዚያ በፊት ግን ፈቃደኛ ከሆናችሁ ወደ እኔ

ህብረትና አንድነት እንድትመጡና የኔን ፈቃድ ለመፈጸምና ለመስፈጸም የጨለማዉን ጸጋዬን እንድትቀበሉ በተለመደዉ ልምሾ በሆነዉ ኃይሌ የመጨረሻ እድል እሰጣችኋለሁ::

ይኸዉም በኔ በጨለማዉ ጌታ በየሱስ የምታምኑና የድርጅቶቼ አባል ከሆናችሁ እነሱ በመዝሙር ሽፋን የእግዚአብሔርን ቃል ጥሩ መጫወቻ በማድረግ እንደሚዘፍኑበትና እንደሚጨፍሩበት፣ እንዲሁም እንደሚያጓሩበት፣ እንደሚፈራገጡበት፣ ባጠቃላይ እንደሚዝናኑበት ሁሉ እናንተም ኅሊናችሁ አንዳች ሳይከብደዉና ሳያስፈራዉ እንድትዝናኑበት ብቻ አይደለም ከፈለጋችሁም ጫት መቃሚ እንድታደርጉበት ሙሉ ነጻነትን እሰጣችኋለሁ::

ለዚህም ምስክር እንዲሆንላችሁ ከእናንተ መካከል አንዳንዶቹ ለኔ ለጨለማዉ ገዥ እንደልቤ ስለሆኑልኝ የኔን የሱስን ለመስበክና ለማግነን ፈቃደኛ ስለሆኑልኝ ዝማሬዉንና ግጥሙን ማሻሻያ አድርጌላቸዉ እንደታማኝ አገልጋዮቼ በመዝሙር ሽፋን እንዲዘፍኑና ግጥሙንም በኔ ሸዋጁ መንፈስ እያረምኩላቸዉ ልዩ ድንቅ የሆነ ተሰምቶ የማይታወቁ እነዚያ የምጠላቸዉ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት አገልጋዮች እስከሚሰቀቁና እስከሚዘገንናቸዉ፣ እንዲሁም እስከሚያዝኑና እስከሚያነቡ ድረስ ኅሊናቸዉን ሰረስሮ የሚገባና የሚያናድድ፣ የሚያስቆጣ እኔን የጨለማዉን ገዥ ደግሞ ነፍሴን የሚያረካ መዝሙር መሰል ዘፈን ፣ ምስጋና መሰል ጭፈራ፣ ስብከት መሰል ክህደት እንዲያቀርቡ ሙሉ እድል እንዳገኙት ሁለተኛ ደረጃ ምርጥ አገልጋዮቼ አይነት እድል ይሰጣችኋለሁ::

ሁለተኛ ደረጃ ምርጥ አገልጋዮቼ የሆኑት «አታስቸኩለን፣ ቀስ በቀስ እኛም ሙሉ በሙሉ እጃችንን እንሰጣለን፣ ሌሎቹንም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታዮችንና አገልጋዮችን እናመጣለን፤ ብቻ አንዳንዴ በስብከታችንና አገልግሎታችን እመቤታችን፣ ቅዱሳን፣ ቤተክርስቲያናችን፣ ሃይማኖታችን፣ አምላካችን » እያልን በስብከታችን ሆነ በዝማሬያችን ላይ ስናስገባ ቅር አትሰኝብን፤ ከምእመኑ ልብ የድንግል ማርያምን፣ የቅዱሳንን ፣ የጻድቃንን፣ እንዲሁም የእዉነተኛዉ አምላክ የድንግል ማርያም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር ከልቦናቸዉ መንግለን ለማዉጣትና የአንተን የጨለማዉ ገዥ የሱስን ፍቅር ለማስገባት በእነዚህ ቃላቶች መታጀብ አለብንና በምንጠራቸዉ ጊዜ አንዳች ቅር እንዳትሰኝብን፤ ይልቁኑ እንደ መጠበብ ቁጠርል::» በማለት በረቀቀ መንገድና ጥበብ መንጋዉን ለኔ አገልግሎት

ለማሰለፍ ቃል ቢገቡልኝም፤ እኔ የጨለማዉ ገዥ አንዳንዴ ትዕግሰት አጣና በስብከቱም «ኢየሱስን እግዚአብሔር አትበሉ፤ድንግል ማርያምንም ወላዲተ እግዚአብሔር አትበሉ» እያስባልኩ፤ እንዲሁም «ስለመዝሙሩ አትጨነቁ፣ ያሬዳዊ ሆነ አልሆ ዋናዉ ሕዝቡን ማስደሰቱና ወደ እኛ ማምጣቱ ነዉ የሚፈለገዉ» እንዲሉ እያደረኩ፤ ያሰብኩት እቅዴ ሳይሳካ በምእመኑና በእዉነተኛ አገልጋዮች ዘንድ ፈተና እንዲደርስባቸዉና ገበናቸዉ እንዲጋለጥ ሳላስበዉ በማስደረጌ እጅግ ይቆጨኛል።

ነገር ግን እንድሜ እንደልቤ ለሆኑት የሃይማኖት መሪና አጃቢዮቻቸዉ፣ እንዲሁም አጫፋሪዎቻቸዉ፤ እስከአሁን ድረስ አንዳች እርምጃ እንዳይወሰድባቸዉ ወጥሬ ይዤላቸዋለሁ። በተቃዋሚዎቻቸዉ ላይም በአንድም ይሁን በተለያየ መንገድ ፈተና እያመጣዉባቸዉ እገኛለሁ። በዚሁ አጋጣሚ ምርጥ አገልጋዮቼን የሚንከባከብልኝን የሃይማኖት መሪ ሆነ አገልጋይ ከአምስት መቶ አመት በላይ በመታሰቢያነት የሚቆይ ሐዉልት በየአብያተ ክርስቲያኑ በሕይወተ ሥጋ እያለ አስቆምለታለሁ። ስዕሉንም በየአብያተክርስቲያኑ እንደቅዱሳን ስዕል ከፍ ከፍ እንዲል አስቆምለታለሁ። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ደግሞ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ብር አስወጥቼ መኪናና አይሮፕላን አስሸልመዋለሁ። ዋናዉ ለኔ የጨለማ አሰራር ድጋፍና እርዳታ መስጠጥ፣ እንዲሁም በአንድነትና በህብረት ከሥጋዊ ሆነ ከመንፈሳዊ አገልጋዮቼ ጋር መሰለፍ ብቻ ነዉ የሚጠበቅባችሁ።

እስከመጨረሻ ድረስ ታማኝነቱን ለገለጸልኝ ምርጥ አገልጋይ ደግሞ በምድር ብቻ አይደለም «ቅዱስ» የማስብለዉ በወደፊቱ መንግስቴ ጭምር «ቅዱስ፣ ሰማዕት፣ ጀግና» አስብለዋለሁ። ታዲያ አንዳንድ አቅሜ እስከምን ያህል ድረስ እንደሆነ የማያዉቁ አገልጋዮችና ምእመናን የሚሉትን አትስሙ። ይኸዉም « የነ ማርክስ፣ ኤንግለስ፣ ሌሊን ሐዉልት እንኳ አይወድቁ አወዳደቅ ወድቋል፤ ተከስክሳል፤ መታሰቢያቸዉም ከምድር ተደምስሷል፤ ተዋርደዋል» የሚሉትን አንዳች አትስሙ።

እነሱ ይህ እድል የገጠማቸዉ የቀድሞዎቹ ሥጋዉያን እንደራሴዎቼና ባለሟሎቼ፣ እንዲሁም ዉዶቼ እንደአሁኖቹ ሥጋዉያን እንደራሴዎቼና ባለሟሎቼ እንዲሁም ዉዶቼ ብልጥ ስላልሆኑና በእብሪትና በጀብደኝነት በግልጽ «እግዚአብሔር የለም፤ ተፈጥሮን በአጭር

ጊዜ እንቆጣጠራለን፤ ከፍጡሩ ፈጣሪያችን መሪያችን ጋድ ጋር ወደፊት» እያሉ በሚሄዱ፣ ኅሊናቸዉን በፍጥነት በማይገለባብጡ ግትሮችና ጨካኞች ስለተደገፉና ስለተያዙ ነዉ እንጂ፤ እንደአሁኖቹ እንደራሴዎቼ ብልጥ፣ የሰላ አንደበት፣ ወዲያዉ ወዲያዉ የሚገለባበጥ ኅሊና፣ ተንኮልና በቀል የሞላዉ ልቦና ባላቸዉ ሰዎች ተደግፈዉና ተይዘዉ ቢሆን ኖሮ፤ በፊሊጥ የክህደቱን ሆነ የመናፍቃኑ «እምነት» እንዲሁም የባዕድና የርኩሰቱ አምልኮ በደንብ እንዲስፋፋልኝ ስለሚያደርጉልኝ ዋስትና እሰጣቸዉ ነበር፡፡ ይሁንና የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ተግባራቸዉ ብዙ ስላላረካኝ ከእነሱ በእጥፍ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት የሚያስደስቱኝን አገልጋዮቼን ከጫካና ከበረሀ ወደ ወንበር ላመጣቸዉ ችያለሁ፡፡

እናንተ የአዳምና ሔዋን ዘሮች፤ በዚህ ቅርፊት በሆነዉ *ሥጋችሁ* ቆዳና መልክ ፣ ቋንቋ፣ ባህል፣ እምነት ልዩነት ፈጥራችሁ እርስ በእርስ ስትጣሉ፣ ስትከፋፈሉ፣ ስትናናቁ፣ በጥላቻ ስትተያዩ ፣ በቂም በቀል ለመገዳደል ስትፈላለጉ፣ ስትጨካከኑ፤ እንዴት መሰላችሁ እኔን የጨለማዉን ገዥ የምታስደስቱኝ! የዚህን *ሥጋችሁን* ምድራዊ ክብሩን አስተዉላችሁና የነፍሳችሁን ማንነት አዉቃችሁ ቢሆን ኖሮ ራሳችሁን በራሳችሁ እጅግ ትታዘቡና የአዳም ዘር ሁሉ ወንድምና እህታችሁ መሆናቸዉን አስተዉላችሁ በዚህች በኮንትራት አገራችሁና ዘመናችሁ ተፋቅራችሁ፣ ተሳስባችሁ፣ ተረዳድታችሁ፣ ተቻችላችሁ፣ በአንድነት፣ በእዉነት ፣ በሰላም፣ በፍቅር፣ በእርካታ ትኖሩ ነበር፡፡

ተስፋችሁንም ሰማያዊ አድርጋችሁ በቅን አሳብ፣ በእዉነተኛ ሕይወት፣ በመልካም ተግባር ትመላለሱ ነበር፡፡ አንድነታችሁንና ህብረታችሁን ከአምላካችሁ ጋር በመፍጠር ከዚህች ምድር የምትገላገሉበትን ቀን በናፍቆት ትጠባበቁ ነበር፡፡ ነገር ግን እድሜ ለእንደራሴ መንግስታትና ባለስልጣናት እንዲሁም ካድሬዎቼ በቀለም፣ በነገድ፣ በዘር፣ በቋንቋ በሃይማኖት እንድትለያዩ፤ እንድትከፋፈሉ፤ እርስ በእርስ እንድትባሉ፤ እንድትገዳደሉ፤ እንድትጣሉ፤ በጥላቻ እንድትተያዩ አድርገዉልኝ ለጨለማዉ መንግስቴ ይገብሯችኋል፡፡ እኔም የጨለማዉ ገዥ ለዉለታቸዉ በስልጣን ላይ ስልጣን፣ በገንዘብ ላይ ገንዘብ፣ በሹመት ላይ ሹመት እየጨመርኩላቸዉ ለመጨረሻዉ የጨለማ ግዛቴ ለታላቅ ኃላፊነት አጫቸጨዋለሁ፡፡ እሳቱን

መንግስቴን ሌሎችን የሚያቃጥለዉን እናሱን ግን እንደ ወርቅ የሚያጠራዉን እንዳች ጉዳት የማያመጣባቸዉን አወርሳቸዋለሁ::

አሁን አሁን ደግሞ ሥጋዊዉን መድረክ ሙሉ በሙሉ ስለተቆጣጠርኩ ወደ መንፈሳዊ መድረክ ሙሉ ኃይሌን አሰማርቼ ጉደኛ ትዕይንት እያሰራዉ እገኛለሁ:: ዋና ዓላማዬ ተዋህዶ ሃይማኖትን ለማጥፋት ነዉ:: በዚህ ምክንያት የተለየ ቡድን አቋቁሜ በየአብያተክርስቲያኑ አገልግሎት ዉስጥ ሰግስጌ ክፍፍሉን በሃይማኖት አባቶች ዘንድ ጭምር በሰፊዉ እያስፋፋዉ እገኛለሁ:: እነዚህ ምርጥ ባለሟሎቼ ብልጥ ናቸዉና በዋና ጉባኤና የሃይማኖት አባቶች ባሉበት « እመቤታችን ፣ ቅዱሳን» እያሉ የሚጠሩ በራሳቸዉ ልዩ ጉባኤ ደግሞ እንኳን ድንግል ማርያምንና ቅዱሳንን በክብር ሊጠሩ ቀርቶ እዉነተኛዉን አምላክ እግዚአብሔርን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ፕሮቴስታንቱ አማላጁ የሱስ በተዝዋዋሪ ወደ እኔ ጨለማዉ ጌታ የሰሱ ለመለወጥና የሱሴ የሱሴ ከማለት የማይመለሱ፤ ድንግል ማርያምንም ስንት የክብር ስሟን አስወግደዉ ማርያም እያሉ የሚጠሩ፤ ቅዱሳንንም እንደ ቆሎ ጓደኛቸዉ ገብርኤል፣ ጳዉሎስ፣ ጊዮርጊስ እያሉ ከመጥራት የማይመለሱ ቆራጥና ደፋሮች ናቸዉ:: አንዳንዴም ሞቅ ሲላቸዉ ኢየሱስን «እግዚአብሔር አትበሉ» ቅድስት ድንግል ማርያምንም «ወላዲተ እግዚአብሔር አትበሉ» ከማለት ወደ ኋላ የማይመለሱ የጀግኖች ጀግኖች ናቸዉ:: ይህን የዋህ ምእመንን እያታለሉትና እየሸወዱት ወደፈለጉት አቅጣጫ ለመዉሰድ የሞት ሽረት እያደረጉልኝ ይገኛሉ:: ለዚህ ታላቅ ተጋድሏቸዉ በጨለማዉ ስሜ በዚህ አጋጣሚ አመሰግናቸዋለሁ::

ትዉልዱም ቀን ከሌሊት ኅሊናዉ በዘፈንና በዳንኪራ ስለደነዘዘ በዚሁ መልኩ ለኅሊናዉ ምቹ የሆነዉን የዘፈንና የዳንኪራ «መዝሙር»፣ የክህደትና የጥርጥር «ስብከት» እንዲያወጡ እያደረኩ እንደ ፕሮቴስታንት ድርጅቴ አባላቶቼ እነሱ « ዘማሪያን» የሚሏቸዉ ምርጥ ዘፋኞቼና «ሰባኪያን ወንድሞቼ» የሚሏቸዉን ምርጥ ምስክሮቼን ተከትለዉ የእግዚአብሔርን ቃል መጫወቻና መነገጃ አድርገዉልኛል:: ታዲያ አንዳንድ ምእመናንና አገልጋይ ይህን ዘፈን ዘፈን የሚለዉን መዝሙርና በድንፋታና በእብሪት የተሞላዉ ስብከታቸዉን እንደኔ ሲደሰቱበትና ሲዝናኑበት እጅጉን እረካለሁ:: እኔ የምጠላዉ መዝሙርና ስብከት የሰዎች ነፍስ ወደ ሰማየ

ሰማያት የምትመጥቅበትና ራሷን ለንስሐ የምታዘጋጅበትን ነዉ:: እድሜ ለምርጥ አገልጋዮቼና ባላሚሎቼ ይኸዉ በእግዚአብሔር ቃል እያስጨፈሩልኝ፣ እያዝናኑልኝ ነዉ:: ከዚህ በተጨማሪ ለጫት መቃሚያም እያዋሉልኝ ነዉ::

የኔን ታላቅነት የሚያስመሰክር ያላሰብኩት ሲሳይ በ፳፻ወ፫(2003) ዓ.ም ገጥሞኛል:: ይኸዉም ለአሰራ ዘጠኝ አመት በቀላሉ ጎሊናቸዉን አልሸጥም እያሉ ሲያስቸግሩኝ የነበሩ የኔን ምርጥ አገልጋዮችና ባለሚሎችን ገበናቸዉን እያጋለጡ ሲያሳቸግሩኝ የነበረ፤ ቤተክርስቲያናቸዉን ለብዙ ዓመታት በትጋትና በመንፈሳዊ ቅናት ሲያገለግሉ የነበሩ ባለቀለት ሰዐት፤ ዘረኝነትና ጎጠኝነት እያስፋፋ፤ ክህደትን፣ ዐመጻን፣ ርኩሰትን እየፈጸመና እያስፈጸመ ያለ መንግስቴን፣ እንደ ሌሎቹ መንግስታቴ ዘፈኑንና ዳንኪራዊን ያነገሠልኝን ዉዴ የሆነዉ ኢህአዴግ ድርጅቴ፤ የእነሱም ማኅበራት አብዛኛዉ አባልት ከላይ የተገለጹትን ፈጻሚና አስፈጻሚ የሆኑና እንዲሁም ቀሪዎቹ ደግሞ ደጋፊና ድርጊቱን ባያስፈጽሙም በመፈጸሙ ድጋፍ የሚያደርጉ መሆናቸዉን ለዓለም ያስተዋወቁበት በመሆኑ ነዉ::

መቼስ እዉነታቸዉን ከሆነ አብዛኛዉ አባላት የኢህአዴግ አባልና ደጋፊ ከሆኑ ለስራ አስፈጻሚነት ሆነ ለአመራርነት ሊመርጧቸዉ የሚችሉት የኢህአዴግን አባላትና የኢህዴግ ደጋፊ የሆኑ ሰዎችን መሆኑን ምንም ጥርጥር የለዉም:: ምክንያቱም አባልና ደጋፊ ሆኖ የሚቃወምን ወይንም ገለልተኛን የሚመርጥ በዓለም ላይ እስከ አሁን ባለኝ 7503 ዓመት ጥናቴ ዉስጥ አልተመለከትኩም:: ቢበዛ በጥናቴ የታየዉ ሰዎች ራሳቸዉን ለማዳን፤ ከመጥፋትና ከመጠረግ ራሳቸዉን እንኳ የማያድኑትን ደካማና ዐመጻኛ፣ የክህደትና የርኩሰት ጽዋቸዉ የሞላባቸዉን ሰዎች « እኛን ያድኑናል፤ ከለላ፣ አምባ፣ መጠጊያ ይሆኑናል:: » ብለዉ ያልሆኑትን «ነን» ሲሉ ብቻ ነዉ::

ታዲያ በዚህ ክፍተት ገብቼ የአስራ ዘጠኙን ዓመት ብስጭቴን ለመበቀልና እንዳልነበሩ ለማድረግ ብነሳም፤ ያቺ የዘመናት ደመኛዬና ጠላቴ ሁልጊዜ አባላቱ ስሟን የሚጠሩ፣ የሚዘክሩ፣ የሚያመሰግኑ፣ «ድንግል ማርያም» የምታባለዉ ከዉድቀትና ከጥፋት

ታደገቻቸዉ። ያ የሚመኩበት አምላክኢትዮጵያን ትተዉ ምስጥ በልቶት ሊገነደስ የደረሰን ዛፍ መጠጊያና መከለያ የሚደርጉ ከሆነም ምሳር እንደሚበዛባቸዉ ማስጠንቀቂያ ደረሳቸዉ።

እኔ ግን የቤተክርስቲያኒቱንና የኢትዮጵያን ተዋህዶ ሃይማኖት እምነቷን፣ ስርዐቷን፣ ዜማዋን፣ ቋንቋዋን፣ ባህሏን፣ ትዉፊቷን ባጠቃላይ የቀደሙት አባቶቻቸዉና እናቶቻቸዉ ያወረሷቸዉም ከእግዚአብሔር የሆነዉን እምነትና ቅርስ ለቀጣይ ትዉልድ ለማስተላለፍ ሌት ተቀን የሚተጉ መሆናቸዉን ስለማዉቅ መቼም ቢሆን እነሱንና መሰሎቻቸዉን ለማጥፋ ወደ ኋላ የማልል መሆኑን በተለመደዉ በጉራና በእብሪት በባዶ ሕይወት በተሞላዉ አንደበቴ ዓለም በዚሁ አጋጣሚ እንዲያዉቅልኝ እፈልጋለሁ።

ሌላዉ የረሳሁት ደግሞ እናንተ የሃይማኖት መሪዎችና «የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን» የምትሉ፤ እንደራሴዎቼን የአገራት መሪዎችን፣ ምርጥ ባለሟሎቼን ባለስልጣናትን፣ እንዲሁም ዉዶቼ ካድሬዎችን ተከትላችሁ በቴሌቭዥኑ፣ በሬድዮኑ፣ በተለያዩ የሕትመት ዉጤቶችና በድረ ገጾች ..ወዘተ የሚተዋወቁትን ለዝሙት የሚያነሳሱና ለኃጢአት ተግባር የሚያሰለፉ ማስታወቂያዎችን ይኸዉም « ሕይወት የሆነዉን ኮንደም ተጠቀሙ፤ የደስታና የእርካታ ምንጭ የሆነዉን ሰንሴሽን ኮንደም ተጠቀሙ፤ ታላቅ ርካታ የምታገኙበትን ኮንደም ወይንም ሰንሴሽን በቀላል ዋጋ እየተጠቀማችሁ ተደሰቱ ..ወዘተ» እያሉ ፈቃዴን የሚፈጽሙትን ሥጋዉያንን ተከትላችሁና የእነሱ ተባባሪ ሆናችሁ በእግዚአብሔር ቁጣ ላይ መገዳደራችሁን በዚሁ አጋጣሚ እመሰክርባችኋለሁ። በእርግጥ እናንተ ሆናችሁ እነሱ ለእግዚአብሔር ትዕዛዝ ደንታ የሌላችሁ መሆኑን ባዉቅም፤ ገንዘቡን፣ ጥቅማጥቅሙን ለማግኘት እንደምትተጉ የእግዚአብሔርን ሕግ ለማስጠበቅ አለመትጋታችሁና ተቃራኒዉን ተግባሪ ከሚያስፈጽሙ እንደራሴዎቼ ጋር እጅን ጓንት ሆናችሁ በጋራ መሰለፋችሁ ምን ያህል ኀሊናችሁን ያደነደናችሁ ቆራጥና ጀግና መሆናችሁን በዚሁ ታላቅነታችሁን እመሰክርባችኋለሁ።

ታዲያ አንዳንድ ያልገባቸዉ ሰዎች « እነዚህ የሃይማኖት መሪና አገልጋይ ነን» የሚሉ ሰዎች፤ ከቻሉ ይህን ማስታወቂያ ማዉገዝና ማስቆም ሲገባቸዉ ካልሆነላቸዉ ደግሞ

«ከዐመጻና ርኩሰትን ከሚያስፈጽሙ የዐመጻ ልጆች ጋር አንድነትና ህብረት የለንም፤ በእግዚአብሔር ሕግና ስርዐት ላይ አናምጽም» በማለት ከእዉነት ጋር መሰለፍ ሲገባቸዉና «ኤድስ ሆነ የአባላዘር በሽታ የመጣዉ በኃጢአታችን ምክንያት ነዉ፤ ካልደረሱበት አይደርስም፤ ስለዚህ ከዝሙትና ከአመንዝራነት ሕይወት እንዲሁም ከግብረ ሰዶም ተለዩ፣ በበሽታዉም የተያዛችሁ ንስሐ ገብታችሁ ቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙን ተቀበሉ፤ እምነቱን፣ ጠበሉን ተጠቀሙ፤ ሌሎቻችሁም ደግሞ በኤድስ ሆነ በማንኛዉም አይነት በሽታ የተያዘን ሰዉ አታግሉ፣ አድሎና መገለል አትፈጽሙ፣ እርዱ፣ ተንከባከቡ፣ አግዙ፣ ሁሉንም አፍቅሩ::» በማለት በግልጽ ማስተማርና በሽተኞችንም ማጽናናትና በሕክምና ሆነ በተለያየ መንገድ መርዳት ሲገባ እንደ ዓለማዉያኑና ሌት ተቀን ስለገንዘብ የሚያስቡ እርዳታን ለማግኘትና በአቋራጭ መንገድ ገንዘቡን ለመበልጸጊያ እንደሚጠቀሙ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ትዕዛዝ መጠበቅ ደንታ ሳይኖራቸዉ እንደ ሥጋዉያኑ አካሄድ ነዉ የሚሄዱት» እያሉ የሚተቿችሁን አንዳች አትስሙ::

እነሱ ተስፋቸዉ ሰማያዊ፣ አገልግሎታቸዉም እዉነተኛ መንፈሳዊ ስለሆነና የኔን የጌታችሁን አካሄድ ስላላወቁ ለእናንተም ለኔም የሚያስቸግሩ የእግዚአብሔር እዉነተኛ አገልጋዮች ስለሆኑ ነዉ:: እናንተ ግን በመንፈሳዊ ሽፋን የሥጋ ፈቃዳችሁን የምትፈጽሙ፣ ምድራዊ ክብርን፣ ጥቅምን፣ ስልጣንን፣ ዝናን፣ ድሎትንና ምቾትን የምትፈልጉ መሆኑን በደንብ አስረዷቸዉ:: የኔን ወዳጅነት ከፈለጉ የእናንተን ፈለግ ተከትለዉ በኔ አታላዩ(ሸዋጁ) መንፈስ ተመርተዉ ፈቃዴን ይፈጽሙ፤ ያስፈጽሙ:: ያኔ ከኔ ዘንድ እንደእናንተ ሞገስ አግኝተዉ ለታላቅ አገልግሎት አሰልፋቸዋለሁ::» **ይላል ትዉልዱን በቀለም፣ በነገድ፣ በዘር፣ በጎጥ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት ከፋፍሎ እያጣላዉና እያባላዉ እንዲሁም በጊዜያዊ ጥቅምና ድሎት ዐይነ ኅሊናዉን በማሰወር ለዐመጻና ለርኩሰት ሕይወት የዳረገዉ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከሡራዊቱ ሰይጣናት ጋር በመሆን::**

# ምእራፍ ስድስት

« እናንተ ኢትዮጵያዉያን መሪዎች፣ ባለስልጣናት፣ እንዲሁም የተለያዩ የሃይማኖት መሪዎች፤ ወደ ትዝብቴ ከመግባቴ በፊት በመጀመሪያ እንኳን ለታላቁ በዐሌና በዐላችሁ ለአስራ ስድስተኛዉ ዓለም አቀፍ የኤች አይቪ ኤድስና አባላዘር በሽታ አደረሳችሁ አደረሰን እያልኩ ወደ ትዝብቴ እገባለሁ፡፡ ይኸዉም እንደራሴዎቼ ሥጋዉያን መሪዎቻችሁና ባለሟሎቼ ባለስልጣናት ፲፱፹፫(1983)ዓ.ም ወደ ወንበር ሳመጣቸዉ በዓለም ዘንድ ሞገስ ካገኙባቸዉ አገራት አንዷ የሆነችዉ የአሜሪካ የታላቋ ባቢሎን መሪ የነበሩት ለዚሁ ታላቅ ክብረ በዐሌ «ሀገረ እግዚአብሔር» ወደተባለች ወደተቀደሰችዉ አገር ኢትዮጵያ ሲመጡ ከሰማይ መልአክ እንደመጣ ቆጥራችሁ ዳግም ሞገስን ለማግኘት እንደ ህጻን ልጅ ከኋላ ኋላ ድክ ድክ እያላችሁ ስትሯሯጡ በመመልከቴ ነዉ፡፡

ይህ ደግሞ የሆነበት ዋንኛ ምክንያት ከጸጋ እግዚአብሔር መራቃችሁና ነዉራችሁን ክብራችሁ በማድረጋችሁ ምክንያት ከእግዚአብሔር የምታገኙት ግርማና ሞገስ ከእናንተ ተወስዶ ማፌሪያ እንድትሆኑ ለሌላ በመሰጠቱ ነዉ፡፡ እስቲ አንዲት ጥያቄ ልጠይቃችሁ! የኤድስ ሆነ የአባላዘር በሽታ ምንጩ ማነዉ? እኔ የጨለማዉ ገዥ ከሠራዊቶቼ ከሰይጣናት ጭመር አይደለንምን? ታዲያ እኛን በስብሰባ፣ በዐል በማክበር፣ በእርዳታ፣ በልመና ልታጠፉን ትችላላችሁን? «አዎን፡፡» ከማለት ወደ ኋላ የማትመለሱ ደፋሮች መሆናችሁን ባዉቅም የኮምደሙንና የሴንሴሽኑን ማስታወቂያ በደንብ ለትዉልዱ እያስተዋወቃችሁልኝ ዝሙትንና አመንዝራነትን እንዲሁም ግበረ ሰዶምን አሳፋፉልኝ፡፡ ያኔ ከምድረ ገጽ እንጠፋላችኋለን ወይንም እናጠፋችኋለን፡፡

በለመዳችሁት የማስመሰልና ሸንገላ አደበታችሁ ለእኔ ጥብቅና ቆማችሁ «እኛ ኤድስን ሆነ አባላዘር በሽታ በሥጋዊ መጠብብና እንዲሁም መከላከያ ኮንደም በመጠቀም ከምድራችን እንዲቀንስና እንዲጠፋ እናደርጋለን » ብላችሁ እንደምትከራከሩልኝ እተማመንባችኋለሁ፡፡ ምክንያቱም በዚህ መልኩ ጥብቅና ካልቆማችሁልኝ ገንዘብና እርዳታ ለማግኘት እንደምትቸገሩ አዉቃለሁና፡፡ እንዲሁም የሰዎች ሰብአዊ መብታቸዉና እኩልነታቸዉ እንዲጠበቅላቸዉ ግበረ

ሰዶምን ካልደገፋችሁና ካልተቀበላችሁ ሞገስና እርዳታ ከምታገኙባቸዉ አገራትና ድርጅቶች፣ እንዲሁም ግለሰቦች ያ ሌት ተቀን የምታስቡለትንና ዐይነ ኅሊናችሁን ያሳወረዉን ገንዘብ አታገኙምና:: ስለዚህ በተቀደሰችሁ አገር ሳይቀር ታላቁን በዐሌን ለማክበር እድል በማግኘታችሁ ስትፈነድቁና ስትደሰቱ በማየቴ ይህ ሁሉ ትዝብት ላይ ጥሏችኋል::

ታዲያ አንዳንድ የኔን ምስጢር ያልተረዱ ሰዎች የሚሉትን እንዳትሰሙ:: ይኸዉም «እነዚህ ኢትዮጵያዉያን ጸጋቸዉ ባይገፈፍና ከእግዚአብሔር ዘንድ ግርማና ሞገስ ቢኖራቸዉ ኖሮ እንደ ሰማይ መላእክት ሊታዩ የሚገባቸዉ እነሱ ነበሩ:: እንዲሁም የተለያዩ አገራትና የዓለም ሕዝብ ሁሉ እዉነተኛዉን አምላክ አዉቀዉ በበሽታ፣ በድህነት፣ በችግር፣ በልመና፣ በድርቅ፣ በጦርነት ፣ በረሀብ የምትታወቀዉን አገር ክብሯ ተመልሶላት «አምላከ ኢትዮጵያ» ተብሎ ፈጠሪ እግዚአብሔር በእዉነትና በመንፈስ በአራቱም ማእዘን ይመለክ ነበር::

የሚደረገዉ በዐል ሆነ ስብሰባ «የእግዚአብሔር ሕግ ይከበር፤ የሰዉ ሰር ከአመንዝራነትና ከዝሙት እንዲሁም የእሳት ዲን የሚያስመጣዉን ግብረ ሰዶም በአራቱም ማዕዘን በዓለም ላይ ይቁም» በማለት ትምህርት የሚሰጥበትና የርኩሰቱም ተግባር የሚወገዝበት ጉባኤ ይሆን ነበር እንጂ የእግዚአብሔር ቁጣ የሆነዉን ኤድስ ሆነ አባላዘር በሽታን - በሥጋዊ መጠበብ ሆነ በኮንደም እንከላከል ተብሎ ለስንት ችግር የሚሆነዉ ገንዘብ በከንቱ አይባክንም ነበር:: እንዲሁም በተቀደሰዉ ስፍራ ርኩሰቱ ይንገሥ አይባልም ነበር:: አሁን የሚታየዉና የሚደመጠዉ ሁሉ « እግዚአብሔር ሆይ ጥገባችንና እብሪታችንን እንዲሁም ዐመጻችንና ክህደታችን፣ ርኩሰታችን ሰማየ ሰማያት እንዴት እስከ አሁን ድረስ አልደረሰም? ስልምን በመአትህ አታጠፋንም?» እያልን ፈጣሪን እንዲያጠፋን እያስገደድነዉ መሆኑን ኢትዮጵያዉያን ሆኑ ዓለም ሊያዉቅ ይገባዋል» በማለት የሚናገሩትን አትስሙ:: እነሱ የዚህችን ዓለም ጣፋጭነት ያልተረዱ በዝሙት፣ በግብረ ሰዶም የሚገኘዉን ደስታና ሕይወት ያላወቁ መአትን ብቻ በማዉራት ዘመናቸዉን ከሰላም፣ ከእዉነተኛ እርካታ፣ ከጤና የራቁ ናቸዉ:: አምላካቸዉንም የመአት አምላክ አድርገዉ የሚቆጥሩ ናቸዉ:: እናንተ ግን

አምላካችሁ የምህረት አምላክ ስለሆነ እንኳን ይህን ቀላል ተግባር ቀርቶ በግልጽ ዝሙቱን ሆነ ሌላዉን ብትፈጽሙ ከመንግስቱ አይለያችሁም፤ የገሃነመ እሳት ፍርድም አያመጣባችሁም።

ታዲያ አንዳንዶች የንስሐ ምስጢር ያልገባቸዉ ሰዎች የሚሉትን አትስሙ። ይኸዉም «የንስሐ እድል የሚያገኙትና ወደ ልባቸዉ ተመልሰዉ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነትና ህብረት ሊፈጥሩ የሚችሉ ሰዎች ባለማወቅና በሥጋ ድካም በኃጢአት የወደቁ ሰዎች ናቸዉ እንጂ ኅሊናቸዉ እያወቀና እየተቃወማቸዉ በድንዳኔ ኃጢአት የሚፈጽሙ ሰዎች የንስሐ እድል አያገኙም። ነፍሳቸዉም ወደ ልቧ ተመልሳ ከአምላኳ የመታረቅና አንድነት የመፍጠር እድል አታገኝም። ምክንያቱም የድፍረት ድፍረት ኃጢአት ስለሚፈጽሙና የመንፈስ ቅዱስን ስራ በድፍረት ስለሚቃወሙ ነዉ። በዚህም ምክንያት ከማንም በላይ የባሰዉ ፍርድ እንደ ፈርኦን፣ ይሁዳ፣ አርዮስና መሰሎቻቸዉ እንደሚጠብቃቸዉ ማወቅ አለባቸዉ» በማለት የሚናገሩትን ነዉ። ምክንያቱም እናንተ በተለያየ አቋራጭ መንገድ ወደ እግዚአብሔር መንግስት የምትገቡበትን በር ስላዘጋጀችሁና መንገዱንም አስፍታችሁ እንደልባችሁ የምትወጡበት የምትገቡበት ስላደረጋችሁ አንዳች ስጋት አይግባችሁ ።

በዚህ አጋጣሚ በግልጽ ኃጢአትን ለምትፈጽሙ አንድ መልእክት አለኝ፤ ይኸዉም እናንተ እዉነተኛ ርካታ፣ ጤና ፣ ሰላም፣ ደስታ፣ ቅድስና ያላችሁ ስለሆነ ከቻላችሁ አንድ ለአንድ ተወሰኑ ብዬ ባልመክርም በሕይወት ትረስ ኮንደምና የደስታ ምንጭ በሆነዉ በቀላል ዋጋ በምታገኙት ሰንሴሽን ተጠቅማችሁ ዝሙትን ፈጽሙ፣ ተዝናኑ፣ ዝፈኑ፣ ጨፍሩ። ምክንያቱም የእናንተ ህልዉና የሚያበቃዉ በዚህች ምድር ስለሆነ አንዳች የሲዖል ሆነ የገሃነመ እሳት ነገር አያሳስባችሁ። እነዚያ ሞኞች ያላዩትን ገነትና መንግስተ ሰማያትን ተስፋ የሚያደርጉትን አትከተሉ ፤አትስሙ።

እናንተ ኢትዮጵያዉያን የዉጭዉን (የባዕዳንን) ወይንም የኢትዮጵያዉያን ያልሆነዉን ሕይወትና ባህል እንደ ታላቅ መሆን ቆጥራችሁ ይህን ቅርፊት ሥጋችሁን ለማስመለክ ሌት ተቀን መትጋታችሁ እኔን የጨለማዉን ገዥ ቢያስደስትም፤ እግዚአብሔርንና ቅዱሳንን ማሳዘኑን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። ይኸዉም ጡታችሁንና ደረታችሁን፣ እምብርታችሁን፣ ቂጣችሁን፣ ዳሌና ታፋችሁን ገላልጦ በሚያሳይ አለባበሳችሁና በተወጣጠረ ሱሬና ልብስ ይህን

ዘለዓለማዊ ሐዉልት ሆኖ የሚቆየዉን የማይፈርስ አካላችሁን ለዝሙት ማነሳሻ በመጠቀማችሁና መንገደኛዉን ሁሉ በኀሊናዉ ስላስረከሳችሁልኝ ነዉ። « ወደ ሴት አይቶ ለዝሙት የተመኘ ሁሉ እንዳመነዘረ ይቆጠራል።» የተባለዉን ቃል ተፈጻሚ እንዳስደረጋችሁ ሁሉ « ማሰናከያ ለሚያመጣ ሁሉ ወዮለት!» የተባለዉ ደግሞ በእናንተ ተፈጻሚ ስለሚሆን በመሃል በሁለታችሁም ዉድቀት ተጠቃሚዉ እኔዉ የጨለማዉ ገዥ በመሆኔ የእድለኞች እድለኛ መሆኔን በዚሁ አጋጣሚ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ። በራቁትነት ማሳበደ የቀረችን ይህች «የእግዚአብሔር አገር » የተባለች ኢትዮጵያ ነበረች፤ እድሜ ለእንደራሴዎቼ መሪዎችና ለዴሞክራሲ ፍልስፍናዬ ይኸዉ በስልጣኔና በባህል ሽፋን ርኩሰትን አንግሼባታለሁ። ከዚህ በኋላ ጥፋታችሁንን እንጂ « ይህን ሳለደርግ ቀረሁ» ብዬ አንዳች የምቆጭበት ነገር እንደሌለም እኔ የጨለማዉ ገዥ ላሳዉቃችሁ እወዳለሁ።

የደረቱን፣ የጡቱን፣ የታፋና የዳሌ፣ ባጠቃላይ የከበረዉን ገላ ወደ ተራነት ለዉጣችሁ በየአደባባዩና በየመንገዱ ገላልጣችሁ ለአላፊ አግዳሚዉ ስታሳዩ ትዝ ያለኝ ከዛሬ ሶስት ሺህ ዓመት በፊት እስራኤላዉያን ከግብጽ ባርነት ነጻ ወተዉ ወደ ከንዓን ሲጓዙ በሞአብ ንጉሥ ትዕዛዝ የሞአብ ሴቶች የእስራኤልን ወንዶች ለመማረክና በዝሙት ለመጣል በኋላም እግዚአብሔር እንዲያጠፋቸዉና እንዲቀስፋቸዉ ለማድረግ ለበልዐም የመከርኩትንና ያሳሰብኩትን ክፉ አሳብ ተግባራዊ ያስደረገልኝን ነዉ። የአሁኖቹ ግን አዛዥ ንጉሥ ሳይኖርባቸዉ፣ ሳይገደዱ፣ ሳይመከሩ፣ በነጻ ኅሊናቸዉና ፈቃዳቸዉ ተመርተዉ በአካል፣ በቴሌቭዥን፣ በፊልም፣ በማስታወቂያ .. ወዘተ በመሳሰሉት የከበረዉን ገላ አራክሰዉና ገላልጠዉ በማሳየት ትዉልዱ በፍትወት እንዲቃጠል፤ በተግባር፣ በንግግር፣ በአሳብ እንዲረክስ በማድረጋቸዉ በዚሁ አጋጣሚ የጥንቶቹንም የበለጠ ደግሞ ካለምንም ተጽህኖ በራሳችሁ ነጻ ፈቃድ ፈቃዴን እየፈጸማችሁልኝ ያላችሁትን የአሁኖቹ ዘመናይ ሰዎችን በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችኋለሁ።

እናንተ ኢትዮጵያዉያን ሆናችሁ ሌሎች የዓለም ሕዝቦች፤ ዘፈኑንና ዳንኪራዉን እንደምትመለከቱት ባለመድረኮቹ ጥቂቶቹ ናቸዉ። አጫፋሪዎቹና የድርጊቱ ተቀባዮች የአዳም ዘሮች ናቸዉ። ዘፋኞቹንና ዳንኪርተኞቹን ሙሉ በሙሉ ኅሊናቸዉን ስለምቆጣጠር እነሱ

«ጥበብ፣ አርት ነዉ» ብለዉ ራሳቸዉንም «አርቲስትና ጥበበኛ ነን» በማለት ስለሰየሙ፤ ትዕይንቱን ሲያቀርቡ ነፍሳቸዉ በዚያች ወቅት እያበደችና ሌሎችንም እሳበደች መሆኑን አያስተዉሉም፡፡ ዱሮ በየጠንቋዩ፣ በየዛሩ፣ በየሚርቱ ቤት የሚቀርብልኝ ምሴን አሁን ደግሞ በዘመናዊ መልክ ሲቀርብልኝ ለጊዜዉ በጎሊናቸዉ የምፈታተነዉንና የማስጨንቀዉን ፈተናዬን ገታ አደርግና ተያያዥ የሆኑትን የርኩሰት አሳቦች በወንዱም በሴቱም አመጣለሁ፡፡ ይኸዉም ስኳሩን፣ ዝሙቱን፣ ሴሰኝነቱም.. ወዘተ በማሳሰብ ወደ ሞትና ጉስቁልና ሕይወት እመራቸዋለሁ፡፡ በመጨረሻም ሰላማቸዉን፣ እርካታቸዉን ነስቼ ለማይገባ ባሕርይና ጠባይ በመዳረግ ሙሉ በሙሉ ኅሊናቸዉን በመቆጣጠር እንደ ሱሰኞች ባሮቼ አደርጋቸዋለሁ፡፡

አንዳንዶች ግን ወደ ልባቸዉ ተመልሰዉ ከዚህ ተግባር ራሳቸዉን ከለዩ በኋላ የቀድሞ የእብደት ተግባራቸዉን ሲያስተዉሉ ለወገኖቻቸዉ ያዝናሉ፡፡ እነሱ የተከፈተላቸዉ ዐይን ለወገኖቻቸዉም እንዲከፈትላቸዉ ይጸልያሉ፤ ይለምናሉ፡፡ ምክንያቱም አምላካቸዉን ራቁቱን ሰቅለዉ ራሳቸዉን በማታለልና በማጃጃል « ዘፈኑና ዳንኪራዉ የደስታ ምንጭ ነዉ» በማለት ተታለዉ ነፍሳቸዉን እያሳበዱ በዐመጻ ሕይወት መመላለሳቸዉን በማስተዋለቸዉ ነዉ፡፡ እኔ የጨለማዉ ገዥ ግን ምሴ ስለሆነ ከፈለጋችሁ «ባህል ነዉ» በሉ፤ ከፈለጋችሁ «የብሔር ብሔረሰቦች መገለጫ ነዉ» በሉት፤ ከፈለጋችሁ «ጥበብ ነዉ» በሉ፤ ምሴን እንዳታቋርጡ፡፡ ነፍሳችሁንም ከማሳበድ ወደ ኋላ እንዳትለዩ፡፡

ሌላዉ ደግሞ ዱሮ ጥንት በአህዛብ ነገሥታትና ባለስልጣናት አማካይነት ሰዎችን ከአራዊት ጋር እያታገልኩና እያጋጠምኩ እዝናና ነበር፡፡ አሁን ደግሞ በዘመናዊ መልክ ሰዉን ከሰዉ፣ ቡድንን ከቡድ እያጋጠምኩ ኳስ እያስረገጥኩ ትዉልዱ ስለ እዉነትና ስለ ነገረ መስቀሉ እንዳይሰማና እንዳያስተዉል እንዲሁም ለነፍሱና ለሥጋዉ አንዳች ጥቅም በማያገኝበት ሕይወት ዉስጥ እንዲመላለስ በማድረግ አእምሮዉን ተቆጣጥሬ አድንዝዣዋለሁ፡፡ ትዉልዱ ነጋ ጠባ « እገሌ አሸነፈ፤ እገሌ ይህን ያህል ጎል አገባ፤ እገሌ ድንቅ ተጨዋች ነዉ፤ እገሌ በዚህን ያህል ብር ተሸጠ፤ እገሌ ከእገሌ ጋር ተጣላ ..ወዘተ» እያለ ቅርፊት ሥጋ ለባሽን እያገነነና እያመለከ ስለ ሕያዊት ነፍሱ አንዳች እንዳያስብ አድርጌ ከሕይወት መንገድ አስርቄዋለሁ፡፡ ታዲያ በራሱ ነጻ ፍቃድ የመረጠዉና የሚፈጽመዉ እያንዳንዱ ግለሰብና ቡድን

ስለሆነ እኔ የጨለማዉ ገዥ በዚህ የምጠየቅበት አንዳች ነገር የሌለ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ አሳዉቃችኋለሁ፡፡

እናንተ ኢትዮጵያዉያን ዶሮ ከሃያ አመት በፊት «ወንበዴ እያላችሁ የምትሰድቧቸዉና አገር ገንጣዮ አስገንጣይ» እያላችሁ ካለስማቸዉ ስም የሰጣችኋቸዉ ምርጥ እንደራሴዎቼና ባለሟሎቼ ወያኔዎች(ኢህአዴግ)፤ በዚህ አጋጣሚ በዚህ ስም ልጠራቸዉ የቻልኩት እነሱም የሚመኩበት፣ የሚመጻደቁበት፣ የሚታበዩበት፣ የሚወዱት ስም ስለሆነ ነዉ እንጂ እኔ የጨለማዉ ገዥ ልክ እንደ ኢህአዴግ ልዩ ስም ልሰጣቸዉ ነበር ፍላጎቴና ምኞቴ የነበረዉ፡፡

ነገር ግን የባለማሎቼን ምርጫ አከብራለሁ፤ ያወጣሁትን ዴሞክራሲ መብት እጠብቃለሁ፡፡ ታዲያ አሁን ላሉበት ስልጣንና ክብር ያበቃዋቸዉ ከጫካ ጀምሮ ታማኝነታቸዉን ስላረጋገጡልኝና የተነሱበት ዓላማ በሚገባ ስላሳኩልኝ ነዉ፡፡ ይኸዉም ገና ከመሰረቱ እግዚአብሔር የለሽ ስርዐት ሶሻሊዝምን በማርክዚስት ሌኒዝስት ፍልስፍና ለመመራትና ዓላማቸዉንም ለመፈጸምና ለማስፈጸም ልክ ክርስቲያኖች ኃይል እንዲሆናቸዉ አርማቸዉን መስቀል እንደሚያደርጉ ሁሉ እነሱም እኔ የጨለማዉ ገዥ ኃይል እንድሆናቸዉ ዓርማዬን ኮኮብ በማንሳት ስለተዋጉልኝ በአግባቡ ዓርማዬን ያላስከበረዉን ደርግ(ኢሠፓ) ድል አድርገዉ ወደ ወንበር ሊመጡ ችለዋል፡፡

በኋላም ዉለታዬን ሳይዘነጉ ኃይል የሆናቸዉን ዓርማዬን ከድርጅታቸዉ ዓርማ በተጨማሪ ለወደፊት ነጻ መንግስታቸዉ ለአሁኑ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታቸዉ ለትግራይ (ለትግሬ ) መንግስታቸዉ ሰንደቅ ዓላማ አዉለዉታል፡፡ በማስከተል ለወደፊቱ ነጻ መንግስት ለአሁኑ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታቸዉ ለአማሪያ (ለአማራ) መንግስታቸዉ ሰንደቅ ዓላማ አዉለዉታል፡፡ በመቀጠልም ለወደፊቱ ነጻ መንግስት ለአሁኑ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታቸዉ ለአፋሪያ (ለአፋር) መንግስታቸዉ ሰንደቅ ዓላማ አዉለዉታል፡፡ በማያያዝም ለወደፊቱ ነጻ መንግስት ለአሁኑ ለብሔራዊ ክልላዊ መንግስታቸዉ ለጋንቤሊያ (ለጋንቤላ) መንግስታቸዉ ሰንደቅ ዓላማ አዉለዉታል፡፡

በመጨረሻም በሕገ በአዋጅ አጽድቀዉ በኢትዮጵያ ምድርና በአራቱም ማዕዘንና በመላዉ ዓለም ከፍ ብሎ እንዲዉለበለብ አድርገዉልኛል፡፡ ይህ ብቻ አይለም እዉነተኛዉን

የኢትዮጵያ ሰንድቅ ዓላማ የሆነዉ ኢትዮጵያዉያን በአባታቸዉ ኖኅ አማካይነት ከእግዚአብሔር የተቀበሉትና ዘላለማዊ ሰንደቅ ዓላማ ቃልኪዳን የሆነዉን አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሰንደቅ ዓላማ  ኮኮብ አርማዬ የሌለበትን ከፍ ብሎ አይደለም ዝቅ ተደርጎ እንኳ የሚያዉለበልብ ከተገኘ በወንጀል እንዲቀጣ ማድረጋቸዉ ለኔ ለጨለማዉ ገዥ ምን ያህል ታማኝነታቸዉን እንዳረጋገጡልኝ ነዉ የሚያሳየዉ::

በዚሁ አጋጣሚ አድናቆቴን ልገልጽላቸዉ የምፈልገዉ የእነዚህን ምርጥ ባለሟሎቼን አሳብ ተቀብለዉ ተግባራዊ ያደረጉትና ያጸደቁ ዉድ ባለሟሎቼን የተወካይ ምክር ቤት አባላትንና በአገርና በዉጭ አገር ያሉ ይህንን ተግባራዊ ለማድረግ የተጉ ዉዶቼን ጭምር ነዉ::

ከሁሉ በላይ ሙገሳዬን የምገልጽላቸዉ ደግሞ ያለፈዉ ባለሟሌ መንግስት ያስወገደልኝን የምጸየፈዉና የምጠላዉ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረዉን «ሞኣ አንበሳ» በሚል ሲያሜ የሚታወቀዉን መለኮታዊ ዓርማ ለማስወገድ ወደ ኋላ ያላሉት የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት መሪዎችና አገልጋዮችን ነዉ:: ምክንያቱም አሁን ደግሞ ባስወገዱት መለኮታዊ ዓርማ ምትክ « ወያኔ(ኢህአዴግ) ያመጣልን ዲያብሎሳዊ ዓርማ ኮኮብ የአሸናፊዎ አሸናፊ ስለሆነ እሱን ነዉ ክፍ አድርገን የምናዉለበልበዉ» በማለት በየአብያተክርስቲያኑ እንዲዉለበለብ ስላደረጉልኝ ነዉ:: ለቅዱስ ኪዳን ፍጻሜ ለሆነዉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ የተነገረዉ «ሞአ አንበሳ ዘምነገደ ይሁዳ» የሚለዉ መለኮታዊዉ ዓርማ የምቃጠልበትና የምዋረድበት ስለሆነ እንኳን ከፍ ብሎ እንዲዉለበለብ አይደለም በወረቀት ላይ እንኳ እንዲታይ አልፈልግም:: ታዲያ ዋናዉ ባለቤቶቹ ሲያቃልሉልኝና ሲያስወግዱልኝ እንዴት ምስጋናና አድናቆት አልቸራቸዉ!

እዚህ  ላይ ኮኮብ አርማዬን «የአሸናፊዎች አሸናፊ» ያሉት እነሱ ናቸዉ እንጂ፤ ስለ ክህደታቸዉ የእግዚአብሔር ቁጣ ቢመጣባቸዉ አንዳች ለመታደግ ዋስትና የምሰጣቸዉ አይደለም:: እንኳን እነሱን  አይደለም ሙሉ በሙሉ ኮኮብ ዓርማዬን የኃይል ምንጫቸዉ አድርገዉ የተቀበሉት እንደራሴዎቼንና ባላሟሎቼን እንዲሁም ዉዶቼን መታደግ የማልችል መሆኑን ብገልጽላችሁ ቅር እንደማትሰኙ በጨለማዉ ስሜ አምናለሁ:: እንኳን እናንተን የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ስራ አስፈጻሚዎቼን ቀርቶ ራሴን እንኳ መከላከል የማልችል

ተራ ፍጡር መሆኔን በየጠበል ቦታና በየአብያተክርስቲያኑ ስለፈልፍ ሳትታዘቡኝ እንዳልቀረ እገምታለሁ።

በዚሁ አጋጣሚ በቤተክርስቲያን አባቶች የታዘብኩት ነገር ለመግለጽ እፈልጋለሁ። ይኸዉም እነዚያ በሕይወተ ሥጋ እያሉ ያስቸገሩን አንሶ አሁንም በአጸደ ነፈስ ሆነዉ የሚረብሹኝና የሚያስጨንቁኝን የምጠላቸዉንና በተለያዩ እምነት ድርጅቴ አማካይነት የማጥላላት፣ የማስናቅ፣ እንዲሁም የማሰደብ ዘመቻ የማደርግባቸዉ ነብያት ፣ ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን ፣ እንዲሁም ሰማያዉያን መላእክት፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ የዘመናት ደመኞዬ ጠላቶቼ ድንግል ማርያምና ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚታሰቡበት የተለያዩ ቅዱሳን መካናት በዓመታዊ ሆነ በወርሃዊ በዐል ላይ ያ ሁሉ ምእመን ከአራቱም ማዕዘን ተመዉ ሲመጡ ዐይኔ ሲመለከት እጅጉን እናደዳለሁ፤ እበሳጫለሁ። ምክንያቱም ይህ ሁሉ ሕዝብ ወደ ልቡ ቢመለስና ንስሐ ቢገባ ምን ያህል ነፍሴ እንደምታዝንና እንደምትበግን እኔ የጨለማዉ ገዥ ነኝ በደንብ የማዉቀዉ። ነገር ግን ለነፍሳቸዉ የሚያዝንና የሚቆረቆር አገልጋይ አለመኖሩንና እንዲሁ በዘልማድ ሲመላለሱ ስመለከት እጽናናለሁ።

ይሁንና ትልቅ ስጋት አለብኝ። ይኸዉም አንድ ቀን የምእመኑን የዋህነትንና ትጋት እግዚአብሔር ተመልክቶ ለነፍሳቸዉ የሚያዝኑና የሚተጉ እረኞች አስነስቶ ምእመኑ ከዘልማድ ሕይወት ተለይተዉ ንስሐ እንዲገቡ ቅዱስ ቁርባን እንዲቀበሉ መታሰቢያ የሚደረግለትን ቅዱስ ወይንም ቅድስት ተጋድሎ ሕይወት በሚገባ አዉቀዉ የእነሱን ፈለግ እንዲከተሉ፤ አምልኳቸዉንም በእዉነትና በመንፈስ እንዲያደርጉ፤ «ዋጋ እናገኝበታለን» ብለዉ የሚመጡ በረከትን ፣ ረድኤትን ፣ ጸጋን እንደሚያገኙበት፤ በተቃራኒዉ ደግሞ ለመዝናናትና ጊዜ ለመሳለፍ የሚመጡ ደግሞ አንዳች ሰማያዊ ዋጋ እንደማያገኙበት ካለማስመሰልና ካለሸንገላ የሚያስተምር መምህርና አገልጋይ ካገኙ ሁሉም ንስሐ ሲገቡና ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙን ሊቀበሉ ይችላሉ በማለት ነዉ።

ዞሮ ዞሮ እስከአሁን ድረስ በትዝብቴ አብዛኛዎቹ የሃይማኖት አባቶች «ቅዱስ፣ ብጹዕ፣ መልአክ፣ ሊቅ፣ መምህር » ከተባሉ ቅድሚያ የሚሰጡት ለክብራቸዉ፣ ለጥቅማቸዉ፣

ለምቾታቸዉ፣ ለድሎታቸዉ፣ ለመመስገን፣ ለመግነን፣ ለመሸለም እንጂ፤ ምእመኑ እምነቱን አወቀ አላወቀ፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ጠበቀ አልጠበቀ፣ የእግዚአብሔርን ሕግና ስርዐተ አከበራ አላከበረ፣ ንስሐ ገባ አልገባ፣ ቅዱስ ቁርባንን ተቀበለ አልተቀበለ፣ መልካም ምግባር ያዘ አልያዘ፣ ለሰማያዊ መንግስት የሚያበቃ ትምህርት ተሰጠዉ አልተሰጠዉ፣ ወንጌል ተሰበከለት አልተሰበከለት፣ ባጠቃላይ ምእመናን ከኃጢአት ተግባር ራሳቸዉን ለይተዉ እግዚአብሔር ደስ በሚሰኝበት ሕይወት ተመላለሱ አልተመላለሱ አንዳች ስሜት የማይሰጣቸዉ ስለሆነ፤ ዋናዉ ሆዳቸዉ ከሞላ፣ ጥቅማቸዉ ከተጠበቀ ለእኔ አንዳች ስጋት የለብኝም:: እንዲሁም የኔ እንደራሴዎቼ ሥጋዉያን መሪዎችና ባለሟሎች ባለስልጣናት፣ እንዲሁም ዉዶቼ ካድሬዎች «አድርጉ» የሚሏቸዉን ማንኛዉንም ነገር ከማድረግ ወደ ኋላ የማይሉ ቆራጦችና ጀግኖች ስለሆነ በአሁን ሰአት ብዙም የሚያሳስበኝ ነገር የለም::

ዱሮ ዱሮ ምሴ የሆነዉ ዛሩ፣ ማርቱ፣ ማጓራቱ በስዉር በየጉዳንጉዱ፣ በየምናምንቴዉ ቦታ ላይ ተሰዉረዉ፣ ተሸማቀዉ፣ ተሰቀዉ ሲያቀርቡ ነበር:: አሁን ግን በአራቱም ማዕዘን በዓለም ዉስጥ ምሴ እዉቅና ተሰቶት በየመድረኩ፣ በየቴሌቭዥኑ፣ በየሬድዮኑ ስለሚቀርብልኝ እንደኔ የጨለማዉ ገዥ እድለኛ ፍጡር የሌለ እስከሚመስለኝ ድረስ አንዳንድ ቀን ስፈነድቅ እዉላለሁ፤ አድራለሁ:: እኔ የማላዉቃቸዉ የተለያዩ ዘፈኖች፣ ዳንኪራዎች በየጊዜዉ ሲፈለሰፉ ትዉልድ ለኔ ምስ ምን ያህል እዉቀት እንዳለዉና መፈራገጡ፣ መንቀጥቀጡ፣ መወራጨቱ፣ መንዘፍዘፉ፣ መንበርከኩ፣ መገለባበጡ፣ መራቆቱ፣ መዳራቱ፣ መተሻሸቱ፣ መሳሳሙ፣ እንጣጥ እንጣጥ ማለቱ፣ የተለያዩ የሰዉነት አካላትን በተለየ ሁኔታ እያሳዩ ለዝሙት ማነሳሳቱ፣ ብቻ ምኑ ተነግሮ ያልቃል የተለያየ ትዕይንት መታየቱ እጅግ ስላስደሰተኝ፤ ይህ ስርዐቴ በሲዖልና በገሃነመ እሳት ቢቀጥል የተሻለ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ለእንደራሴዎቼ መሪዎች፣ ለባለሟሎቼ ባለስልጣናት፣ ለዉዶቼ ካድሬዎች አሳብ አቀርባለሁኝ::

ታዲያ በዚህ የዐመጻ ሕይወት እያላችሁ በሥጋ ሞት ብትጠሩ ሳለማልቀስና ሳለመኮነን በኔ በኩል ዋስትና የማልገባላችሁ መሆኑን አስቀድሜ ባልገልጽላችሁ መልካምመሆኑን ባዉቅም እንደ በፊቱ ተገድጄ ነዉ የገለጽኩት:: ታዲያ ከመምከር አልተከለከልኩምና እነዚያ አምላካቸዉ በመስቀል ላይ ራቁቱን ተሰቅሎ እየታያቸዉ ቀንና ሌሊት በያሬዳዊ ዜማ

አምላካቸዉንና እናቱን ድንግል ማርያምን የሚያመሰግኑትን ኢትዮጵያዉያንን አትመልከቱ፡፡ እነሱ በዚህ ሕይወት የሚመላለሱት የምድራዊ ሕይወት ምስጢር ስላልገባቸዉና «ገነት፣ መንግስተሰማያት አሉ፤ በዚያም በመላእክት ሥርዓት እግዚአብሔርን ለሕያዉነት ዘመን እያመሰገን በቅድስናና በደስታ ሕይወት እንኖራለን፡፡» በማለት በአጉል ተስፋ ሕይወት ስለሚኖሩ ነዉ፡፡ እነሱን በምንም መልኩ አትምሰሉ፡፡

ይህ መስራት እየተቻለዉና ከራሱም አልፎ ሌላዉን መርዳት የሚችለዉ የአዳም ዘር በልመና ራስን መረዳትና ማበልጽግ እንደጥበብና ብልጠት ቆጥሮት «ለማኝ» የሚለዉ ስያሜ ሳያሰቅቀዉና ሳያሳፍረዉ በየመንገዱ የሚለምነዉ ትዉልድ፤ ስራ ሳይንቁ ከጫማ ጠራጊነት ተነስተዉ አንድ ራሳቸዉን አይደለም ለሺህዎች የተረፉ ባለሀብቶች መኖራቸዉን ቢያዉቅና ቢያስተዉል ጊዜዉን በከንቱ ማሳለፉ «እንዴት አይቆጨዉ?» ብዬ ለራሴ ስጠይቅ «ለካስ እኔዉ የጨለማዉ ገዥ ይሆን እንዴ አፍዝ አደንግዝ አድርጌበት ለማኝ አድርጌ ያስቀረዉት» ብዬ ራሴን በራሴ እጠራጠራለሁ፡፡ ይህ የኔ የሆነዉ የከፋዉና የከረፋዉ ስርዐት ሳይለወጥ ትዉልዱ ለስራ ይነሳሳል ብዬ አልገምትም፡፡ ብቻ ትልቁ እንደኔዉ ሕያዉ ፍጥረት የሆነዉ ሰዉ አጭሩን ኮንትራት ዘመኑን በትጋትና በስራ ማሳለፍ ተስኖት ራሱን ለረሀብና ለልመና ሲዳርግ እንዲሁም በተለያየ ሱስ ደንዝዞ ስመለከት « ትዉልዱ እኔ የጨለማዉ ገዥ ስንፍናን እንዳርቅለት እየጠበቀ ነዉ እንዴ በዚህ ሕይወት የሚመላለሰዉ?» በማለት ለራሴ ጥያቄ አቀርባለሁ፡፡ » **ይላል ማንንም ለመፈታተንና ለመጣል ወደ ኋላ የማይለዉ ጨካኙ ርኩሰትን የሚያነግሠዉ የስንፍና አባት የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ፡፡**

## ምእራፍ ሰባት

« እናንተ የመንግስት ፍርድ ተቋማት፤ ምስጋና በጨለማዉ ስሜ ልቸራችሁ እፈልጋለሁ። ይኸዉም ለፍትሕና ለዴሞክራሲ፣ ለእኩልነትና ለነጻነት ለቆመዉ መንግስቴ አጋር ሆናችሁ እዉነተኛዉንና ኀሊዩን አልሸጥም የሚለዉን፣ ስለእዉነት የሚመሰክረዉን ሰዉ የመወንጀያ መረጃ አቀነባብራችሁ ካለጥፋቱና ወንጀሉ በተቀነባበረ ሴራ ለእስርና ለሞት ፍርድ ስላበቃችሁ፣ እንዲሁም ግፈኛዉን፣ ሌባ ቀማኛዉን፣ ወንበዴዉን፣ ወንጀለኛዉን ጥሩ በተቀነባበረ መረጃ ነጻ አዉጥታችሁ በመፍረዳችሁ ምክንያት ነዉ።

ከዚህ በተጨማሪ ተበድለዉ «ደሀ ተበደለ፣ ፍርድ ተጓደለ» የሚል መንግስት አለና «ፍርድ እናገኛለን» ብለዉ ፍርድ ቤት የሚቀርቡ ተበዳዮችን፣ ለኀሊናቸዉ ሳይሆን ለገንዘብና ለጥቅማቸዉ በቆሙ ዳኞች፣ ጠበቆች፣ አቃብያን በሐሰት መረጃና ተበዳይም የሚፈለገዉን ሊያቀርብ እንዳይችል ተደርጎ፣ ይልቁኑም «ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ባላመጣሁ» ብሎ እስኪመረር ድረስ «ይፈረድልኛል» ብሎ እዉነተኛ ፍርድ የሚጠባበቀዉን ሰዉ ፍዳዉን ስለምታሳዩልኝ ነዉ። በዚህም ምክንያት እለት እለት በሀብት የምትበለጽጉበትን መንገድ አመቻችላችኋለሁ። ዋናዉ እናንተ መቆም ያለባችሁ ለኀሊናችሁ ሳይሆን ለጨለማዉ ስርዐቴና ገንዘብ ለምታገኙበት ጉዳይ ብቻ መሆን አለበት።

ታዲያ እዚህ ላይ የገረመኝና እጅግ ያስደነቀኝ ይህ አይነቱ የፍርድ አሳራርና አወሳሰን የሚፈጸመዉ ምንም ባልተማሩ ወገኖች ሳይሆን «ተማርን፣ ከደሀዉ ቤተሰብ ነዉ የወጣነዉ» በሚሉ ግለሰቦች መፈጸሙ ነዉ። የጥንት ዳኛች ሆኑ ጠበቃዎች ካለምንም ሰርተፍኬት፣ ዲፕሎማ፣ ድግሪ ሳይዙ እዉነተኛዉን ፍርድ እግዚአብሔር እንዲፈርድ ኀሊናቸዉን አሳልፈዉ ስለሚሰጡ በዳኞች ላይ አድሮ እግዚአብሔር ነበር የሚፈርደዉ እንጂ ስለ ደሞዝና ስለጥቅም ሲሉ የበደለዉን ነጻ ፣ የተበደለዉን እንዳልተበደለ አድርገዉ አይፈርዱም ነበር። ያንን ዘመን ያሳለፈልኝ ይመስገን እንዳልል በተዝዋዋሪ እግዚአብሔርን ማመስገን ይሆንብኛልና እኔዉ ራሴን በራሴ አመሰግናለሁ። እንዲሁም ይህን የከፋና የከረፋ ስርዐት ያመጣችሁልኝን ሁሉ በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችኋለሁ።

የፍርድ ቤትን ጉዳይን ከሌሎቹ መስሪያ ቤቶች በተለየ ሁኔታ አንስቼ ምስጋናዬን የቸርኳችሁ፣ ሌሎቹ መስሪያ ቤቶች ሳያስደስቱኝ ቀርቶ ሳይሆን ጠበቃ፣ አቃቤሕግ፣ ዳኛ ለእዉነት ብቻ ቆመዉ በበደለኛዉ ላይ ማስፈረድ፤ ለተበዳዩ ደግሞ እንዲፈረድለት ካላደረጉ፣ በፍርዱ አድሎ የሌለዉ፤ በዘመድ አዝማድ፣ በትዉዉቅ፣ በገንዘብ፣ በጥቅም የማይፈርደዉ እዉነተኛ ፈረጃ ዳኛ እግዚአብሔር፤ ስለተገፉ፣ ስለተበደሉ፣ ስላዘኑ፣ ስለተከዙ፣ ስለተመረሩ ሰዎች ሲል በስርዐቱ ላይ የማያዳግም ፍርዱን አምጥቶ የንግሥናዬ ዘመን እንዳያጥር ካለኝ ስጋት አንጻር ብቻ መሆኑን ላሳዉቃችሁ እወዳለሁ፡፡

እናንተ በየመስሪያ ቤቱ ሕዝቡን የምታጉላሉና ፍዳዉን የምታሳዩልኝ ወኪል አገልጋዮቼ «ለምን የተለየ ምስጋና አልተቸረንም?» ብላችሁ አንዳች ቅሬታ እንዳይገባችሁ፡፡ ስርዐቴ እስካለ ድረስ እናንተም ትኖራላችሁና አንዳች የተለየ ምስጋና ከኔ እንዳትጠብቁ፡፡ ምክንያቱም በኋላ ተገልብጣችሁ ሕዝቡን በቅንነትና በእዉነት ብታገለግሉ ምን ዋስትና አለኝ? በቅንነትና በእዉነት ላለማገልገል ዋስትና የሚሰጠኝ ግለሰብ ካለ የተለየ ምስጋና በጨለማዉ ስሜ ላቀርብለት እችላለዉ፡፡ ዋናዉ ደግም እምነታችሁ ስለሆነ በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት፣ በጭከና፣ በጠማማነት፣ ባጠቃላይ ቅንነትና እዉነተኛነት በሌለዉ አገልግሎት ዉስጥ የምትመላለሱ ሰራተኞች ሁሉ በጨለማዉ ስሜ እንደተመሰገናችሁ ልታዉቁ ይገባል፡፡

ታዲያ ፍርድ ቤትን ካነሳዉ አይቀር ዉዶቼ ካድሬዎች የተሰገሰጉበትን ክፍለከተማ የመሳሰሉ መስሪያ ቤቶቼን ሳለመሰግናቸዉ ባልፍ ኅሊናዬ ስለሚወቅሰኝ በእናንተ የተመሰገንኩ ልሁን እላለሁ፡፡ ምክንያቱም ሳይማር ያስተማራችሁን ሕዝብ ብቻ አይደለም የተማረዉንም ጭምር በካድሬነት መታወቂያችሁ ተመክታችሁ ፍዳቸዉን በማሳየት ስለምታጉላሉትና በአግባቡ እንኳ ጉዳያቸዉን ሰምታችሁ ለማስተናገድ ፈቃደኛ አለመሆናችሁ ብቻ አይደለም ከፍ ዝቅ እያደረጋችሁ የምታዋርዱና የምትሳደቡ በመሆነችሁ ጭመር ነዉ፡፡ እንዲሁም ራሳችሁን አድራጊ፣ ፈላጭ፣ ቆራጭ አድርጋችሁ በመቁጠር ለፈለጋችሁት የፈለጋችሁትን ስታደርጉ፤ ላልፈለጋችሁት ደግሞ አንድ አመት አይደለም ከአስር አመት በላይ እንዲመላለስ፣ እንዲጉላላ የምታደርጉ ጨካኞች ስለሆናችሁ በዚህም ልትመሰገኑ ይገባችኋል፡፡

እነዚህ አገልጋዮቼ እንኳን ተራዉን ሕዝብ አይደለም በሕዝብ ስም የሚነግዱትን ለአፋቸዉ ይምስል «መልካም አስተዳደር » እያሉ የሚያለግጡትንና ሕዝቡን የሚሸነግሉትን እንደራሴዎቼ መሪዎችና ባለሚሎች ባለስልጣናት መልካቸዉን ለዉጠዉ ለመስተናገድ ቢመጡ ያዉ ሕዝቡ ላይ የሚደረሰዉ መጉላላትና እንግለት በእነሱ ላይም ከማድረስ ወደ ኋላ የማይሉ፤ ከእነሱ በተቀበሉት የዐመጻ አገልጋይነት ምስክር ወረቀት በመመካት ታላቅነታቸዉንና ጀግንነታቸዉን ስለሚያሰዩ፣ በዚህ አቋማቸዉ ከጸኑ ደግሞ ለወደፊቱ የመሪነቱንና የባለስልጣንነቱን ወንበር እንደሚረከቡ ተስፋ አድርጋለሁ::

ግምት ዉስጥ የጣላቸዉን ሳልጠቁም ብገልጥ «አድሎ ተደረገብን» የሚሉ ወገኖቻችሁ አገልጋዮቼ አሉና፤ የተለየ ተግባራችሁን ለዓለም ማሳወቅ እፈልጋለሁ:: ይኸዉም በዘመድ አዝማድ፣ በበላይ ባለስልጣናት፣ እንዲሁም በገንዘብ ኃይል የሚቀርቧችሁን ሁሉ እንኳን መመሪያዉ ፈቅዶላቸዉ አይደለም ሳይፈቅድላቸዉም የሚመቻቸዉን መመሪያ ራሳችሁ በመፍጠር ጉዳያቸዉን ሳይመላለሱና ሳይጉላሉ ትፈጽሙላችዋላችሁ::

በተቃራኒዉ ደግሞ ለምስኪኖች እንኳን ጉዳያቸዉን መፈጸም አይደለም በትህትና እንኳ ለማነጋገር ፈቃደኞች አይደላችሁም:: ሊፈጸምላቸዉ የሚችለዉን ጉዳይ እንከንና ጉድለት እየፈለጋችሁ በራሳችሁ (መስሪያ ቤቱ) በፈጠረዉ ስህተትና ጉድለተ ባለጉዳዩን ለዓመታት እንዲቀጣ፣ እንዲጉላላ ታደርጋላችሁ:: የሚገርመዉና ትዝብት ላይ የጣላችሁ ደግሞ በግርግዳ ላይ « ሕዝብን በቅንነትና በግልጸኝነት ለማገልገል ካለአድሎና ካለ ሙስና ለማገልገል በቁርጠኝነት ተነስተነናል» ብላችሁ ትለጥፋላችሁ:: በእርግጥ ይህን በቃላት ማታለልና በተግባር ተቃራኒዉን መፈጸም ከኔ ከግብር አባታችሁ ከጨለማዉ ገኸ የተማራችሁት ቢሆንም፤ እኔ ግን ለሁሉም ሰዉ ጥሩ ተግባር እንዲፈጸም አልፈልግም:: እናንተ ግን ሰዉን እየመረጣችሁ ለፈለጋችሁት ብቻ መልካም መልካም መስተንግዶ ታደርጋላችሁ::

እዚህ ላይ ለማስጠንቀቅ የምፈልገዉ በቅንነትና በእዉነተኛነት ሕዝብን ለማገልገል የተሰለፋችሁ የኔ የጨለማዉን መንፈስ አሰራር የምትቃወሙ ሰራተኞች፣ በአጠቃላይ ስርዐቱን በበላይ ሆኜ የምመራዉ እኔ ስለሆንኩ አገልጋዮቼንም አታልዩ(ሸዉጂ) ፈቃዴን

የማስፈጽም ስለሆነ፤ ከስራ የመባረር ሆነ በሌላ የመጠቃት እድል እንዳያጋጥማችሁ በኔዉ መንፈስ ብትመሩ የሚሻላችሁ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ እንግራችኋለሁ፡፡

እናንተ ምርጦቼ ሕዝብን የምታጉላሉልኝ ግን ከፍ ከፍ አደርጋችኋለሁ፡፡ ታዲያ አንዳንድ ሰዎች የሚሉትን አትስሙ፡፡ ይኸዉም «እነዚህ ደሞዝ የሚከፈላቸዉ የሚያጉላሉን ሰዎች ገንዘቡ መቼስ ከሰማይ እንደማይዘንብ ይታወቃል፤ ከኛዉ በተለያየ መልኩ ከሚሰበሰበዉ ነዉ የሚከፈላቸዉ፤ እንኳን ለእነሱ አይደለም አገሪቷን ለሚመሩና ለባለስልጣኖቹ ሳይቀር የሚከፈለዉ ከኛዉ ከተሰበሰበዉ ገንዘብ ነዉ፡፡ ታዲያ እኛ ሕዝቦች እንደዚህ ለሚያጉላሉንና ለሚያሰቃዩን ሰራተኞች «አንከፍልም» ብንል፤ ደጅ መጥናትና መጉላላት ምን እንደሆነ ያዉቁ ነበር፡፡ አሁን ግን የሚያገኙት ገንዘብ ስላሰከራቸዉ የሰዉ ድካምንና እንግልትን ሊያዉቁ አይደለም ሊሰሙ ፈቃደኞ አይደሉም» በማለት የሚናገሩትን አንዳች እንዳትሰሙ፡፡ ይልቁኑ «ቀድሞ በአለንጋ ነበር የምናሰቃያችሁ አሁን ደግሞ በጉጠት ነዉ ፍዳችሁን የምናሳያችሁ » በማለት ዲያብሎሳዊ ስርዐቴን ለማስጠበቅ እስከ ደም መስዋዕትነት እንድትከፍሉ አሳስባችኋለሁ፡፡ ለዓለማዬ ማሳካትም ቴሌቭዥኑን፣ ሬድዮኑን፣ የተለያዩ ሕትመቶችን፣ ስብሰባዎችን፣ እድሮችንና ሰንበቴዎችን ሳይቀር በመጠቀም ትዉልዱን በወሬ፣ በማስመስልና በሽንገላ ቃላት ልታደነዝዙት ይገባል፡፡

ምክንያቱም የማመዘዘንና የመገምገም ጊዜ ካገኙ ምርጡ እንደራሴዬ የሆነዉ መሪያችሁን « ታላቁ፣ አንገት ያለዉ፣ አስተዋዩ መንግሥታችን» እያላችሁ የምታገኑትን የመንፈስ አባታችሁን ሊቃወሙና ሊተቹ ይችላሉ፡፡ ለዚሁ ማስረጃ እንዲሆናችሁ ሳይቸግራችሁ የምርጫ ነጻነት ሰታችሁ በዘጠና ሰባት ዓመት ምህረት ያ ሁሉ መሪያችሁን ለመደገፍ የወጣዉ ሕዝብ ግልብጥ ብሎ ተቃዋሚዎቻችሁን የመረጠዉና እናንተንም ከነመሪያችሁ ስጋትና ጭንቀት ዉስጥ የጣላችሁ መሰሪ የሆነዉን ተግባራችሁን ሕዝቡ እንዲያዉቅ ስለተደረገ ነዉ፡፡

ይሁንና እግዚአብሔር ሕዝቡ ሰዉን ተስፋ እንያደርግና በእሱ ብቻ እንዲተማመኑ እንዲሁም እሱን ብቻ ተሰፋ እንዲያደረጉ ለማስተማርና ተስፋ የተደረገባቸዉ ሰዎች በህብረት የተነሱት ያዉ የሥጋና ደም ስሜታቸዉን ለመፈጸም እንጂ የእግዚአብሔር ፈቃድ

ለመፈጸምና ለማስፈጸም ባለመሆኑ ያ ሁሉ ስጋታችሁና ጭንቀታችሁ ተወግዶላችሁ ካለምን ተቀናቃኝ ይኸዉ በወንበሮቻችሁ ላይ ቂብ ብላችሁ ተቀምጣችኋል፡፡

መንግስታችሁም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጥሩ ትምህርት በመዉሰዱ እነዚያ ያስጨነቁትንና ለዓለም ገበናዉን ያጋለጡበትን በእስር፣ በማሳደድ፣ በማስደብደብ፣ በማስገደል፣ አካለ ስንኩል በማድረግ፣ ሀብትን ንብረታቸዉን በመቀማት፣ ጎሊናን በማሸጥ .. ወዘተ ፍዳቸዉን አሳይቶልኛል፡፡ እኔም ይህን ቆራጥነቱንና ጀግንነቱን እንዲሁም ጭካኔዉንና በቀለኝነቱን ስላወኩ ነዉ ለመሪነት ያጨዉትና ለወንበር ያበቃሁት፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ ላልነግራችሁ ብፈልግም እንደበፊቱ በአሳት ሰንሰለት ተጠፍሬያለዉና የዐመጻ ጽዋችሁ ከሞላ ግን እኔም ልታደጋችሁ እንደማልችል፤ እናንተም ራሳችሁን ማዳንና ከወንበራችሁ ላለመቆረጥ እንደማትችሉ ሳዉቅ ሆዴን ባር ባር ይለዋል፡፡ ምክንያቱም ምስኪኑ ወገናችሁ ሲራብ፣ ሲቸገር፣ ሲጠማ፣ ሲታረዝ፣ በየመንገዱ እንደ ቆሻሻ ሲጣል፣ መከራና ስቃይ ሲደርስበት፣ ባጠቃላይ ሲጎሳቆልና ሲማረር፣ ሲያነባ ዝም ብላችኋልና፤ እንዲሁም የራሳችሁን በቢራ በመራጨት፣ በዘፈኑና በዳንኪራዉ በመመላለስ፣ « ማን ይነካኛል » ብሎ በመታበይ ሕይወት ዉስጥ እየተመላለሳችሁ በመሆኑና ተንኮላችሁና ጭከናችሁ ከኔ ከጨለማዉ ገዥ በላይ ሆኖ ስለተገኘ፤ ከእናንተ በላይ ተንኮለኛና ጨካኝ እንደሚታዘዝባችሁ እገምታለሁ፡፡ ዞሮ ዞሮ በሥጋ ብትለዩኝ እንኳ የኔን የጨለማ መንግስት በነፍሳችሁ እንደማታጡና በዚያም አሁን ያለዉ ሹመታችሁ እንደሚጠብቃችሁ አሳዉቃችኋለሁ፡፡ በዚህም እንድትጽናኑና እስከመጨረሻዉ ድረስ እንድትታመኑልኝ እመክራችኋለሁ፡፡» **ይላል በተለያየ ስልት የአዳምን ዘር እያሰቃየ ያለዉ አላጋጩ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከነሠራዊቱ፡፡**

## ምእራፍ ስምንት

« እናንተ የዓለም ጠበብት፣ ምሁራንና ሳይንቲስቶች! ለእናንተም ያለኝን ሙገሳ መግለጽ እፈልጋለሁ:: ምክንያቱም እግዚአብሔር፤ የአዳም ዘር ከጉስቁልና ሕይወቱ እንዲላቀቅ በገለጸላችሁ እዉቀትና ጥበብ የተለያዩ ጠቃሚ መሳሪያዎችን መፈልሰፍ ሲገባችሁ፣ እናንተ ግን ሕዝብ ከሕዝብ የሚጫረስበትንና የሚጎዳዳበትን የተለያዩ የጦር መሳሪያዎችን በመፍጠራችሁ ነዉ:: እንዲሁም እንደ ባቢሎን ሰዎች ታብያችሁ ወደ አልተገባችሁ ቦታ በመሄድ ለስንትና ስንት ድሆች የሚሆነዉን ገንዘብ ለዐመጻ ስራችሁ በማፍሰሳችሁና መንኮራኩር ፈጥራችሁ በተለያዩ ፕላኔቶች ላይ ለመኖር በማቀዳችሁ እንዲሁም እብሪተኛና ጥጋበኛ መሆናሁችሁን በግልጽ በማስመስከራችሁ ነዉ::

የጦር መሳሪያዎቻችሁ ጥሩ ዉጤት ቢያመጡልኝም፤ እስከ አሁን ድረስ ሙሉ በሙሉ የአዳም ዘርን ስላላጠፉልኝ ቅር ብሰኝም ለወደፊት ያጠፉልኛል ብዬ ተስፋ እያደረኩ ስለሆነ በዚያ እጽናናለሁ:: በመንኮራኩር ስራችሁና ጉዞዋችሁ እኔም የጨለማዉ ገዥ ተባባሪና ተጓዥ ብሆንም እስከአሁን ድረስ የረባ ዉጤት ያላመጣችሁ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ እመሰክርባችኋለሁ::

እዚህ ላይ ግን አንድ ስጋቴን እገልጽላችኋለሁ:: ይኸዉም የእናንተ እዉቀትና ጥበብ በኢትዮጵያዉያን ሰዎች ለወደፊት ከንቱ እንዳይሆንና ለሰዉ ዘሮች የሚጠቅም መሳሪያ ብቻ በመስራት ሊያሳፍሯችሁ እንደሚችሉ እገምታለሁ::

ምክንያቱም የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት ሊቃዉንትና መምህራን እንደእናንተ በተፈጠረ ነገር ላይ ተነስተዉ የሚያስፋፉ፣ የሚራቀቁ ሳይሆን በቅጽበት ጊዜ ዉስጥ ወዲያዉ የሚፈጥሩ ነገር ግን እስካሁን ድረስ ይህን ብቃታቸዉን እያሳዩ ያሉት በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ብቻ ቢሆንም፤ ለወደፊት እነዚህ የቅዱስ ኪዳኗ ኢትዮጵያ ዜጎች በሥጋዊ አግልግሎት ላይ የተለየ ስጦታቸዉን እንዲያዉሉ ከተፈቀደላቸዉ አሁን እናንተ ከምትፈጥሩትና ከምትፈላስፉት እዉቀትና ጥበብ በመቶ እጥፍ ሊፈጥሩና ሊያሳዉቁ ይችላሉ:: ያ እዉቀትና ጥበብ የሰዉ ዘሮችን ከቁስቁልናና ከችግር ኑሮ የሚያላቅቅ፣ እግዚአብሔር መፍራት ያለበት

ስልጣኔ ነዉ የሚሆነዉ እንጂ እንደእናንተ የክህደትና የዐመጻ፣ እንዲሁም የመታበይ አይሆንም።

አሁን ያለዉን መንፈሳዊ እዉቀትና ጥበብ እንዲሁም ፍልስፍና ብነግራችሁ እንኳን እናንተ እጅግ እጅግ አብዛኛዉ ኢትዮጵያዊ አያዉቀዉም፤ አያስተዉለዉም። ምክንያቱም ስሙን ብቻ ቅኔ ሲባል ይሰማል እንጂ «ዉስጡ ምን ይዟል? በምን መልኩ ነዉ የሚቀርበዉ?» ለሚለዉ አንዳች እዉቀቱና ማስተዋሉ የላቸዉም።

እኔ የሚገርመኝ ቅኔዎቹ ራሳቸዉ አይነታቸዉ መብዛቱ ይኸዉም ግእዝ ጉባኤ ቃና፣ እዝል ጉባኤ ቃና፣ ዘአምላኪየ፣ ሚበዝኁ፣ ሥላሴ ፣ መወድስ፣ እጣነ ሞገር፣ ዋዜማ.. የመሳሰሉት ናቸዉ። በነዚህ ቅኔዎች እያንዳንዳቸዉ የራሳቸዉ ሕግ ያላቸዉ ሲሆን፤ ቅኔ በሚቀኝበት ጊዜ ዝም ብሎ ቤት መምታት ብቻ ሳይሆን በመጀመሪያ ከወቅቱ ጋር የሚሄድ ታሪክ መነሻ ተደርጎ በሰምና በወርቅ የሚቀርብ ነዉ። እንዲሁም እያንዳንዱ ስንኝ የመጀመሪያዉ መደብ ከነተቀባዩና ቤተ መምቻዉ መደብ እስከ ተቀባዩ በአራቱ ንባባት በተነሽ ፣ በተጣይ፣ በሰያፍ፣ በወዳቂ ሲነገሩ የራሳቸዉ የፊደል መጠን ለመደቡም ለተቀባዩም ያላቸዉ ነዉ። ለሁሉም የተለያየ ሲሆን የዜማ ልኩን ለመጠበቅ እያንዳንዱ በሚፈቀድለት ሕግ መሰረት ነዉ የሚያቀርበዉ እንጂ ቤት ሰለመታና ሰምና ወርቅ ስለያዘብ ብቻ ቅኔ አያስብለዉም።

ታዲያ እንዚህ ሊቃዉንትና መምህራን ይህ ብዙ ነገሮች የሚጠበቅበትን ቅኔ የሚያቀርቡት እንደእናንተ ወረቀት ይዘዉ፣ መጽሐፍ አገላብጠዉ፣ ተዘጋጅተዉ ሳይሆን፤ አቅርቡ በተባሉበት ወቅት ነዉ ወዲያዉ ከኅሊናቸዉ በማፍለቅ የሚያቀርቡት። ታዲያ ይህ አእምሮ እናንተ የተማራችሁትን ዘመናዊ ትምህርት የመማር እድል ቢያጋጥመዉ እናንተ ከምትራቀቁበት በላይ በመቶ እጥፍ እንደሚራቀቁበት ስለገመትኩ ነዉ ስጋት የገባኝና እንዳትበለጡ እነሱ «ገነት፣ መንግስተ ሰማያት» እያሉ ለመንፈሳዊ ሕይወት እንደሚተጉ ሁሉ እናንተ ደግሞ በሰራችሁት መሳሪያ ተጨራርሳችሁ በተመኛችሁትና ባቀዳችሁት በአንደኛዉ ፕላኔት ላይ ብትኖሩ የገነትና የመንግስተ ሰማያት ያህል እንደሚቆጠርላችሁ በዚሁ አስታዉሳችኋለሁ።

እናንተ ኢትዮጵያዉያን ምርጥ እንደራሴዎቼ መሪዎቿ ፣ ባለሟሎቼ ባለስልጣናት፣ እንዲሁም ወዶቼ ካድሬዎች፤ አሁን አሁን ግራ የገባኝ ነገር እንዳለ ልገልጽላችሁ እወዳለሁ:: ይኸዉም ሲመቻችላችሁና ሲደላደልላችሁ ወደ ወንበር ያመጣኋችሁን ዓላማን እየዘነጋችሁና ያላዘዝኳችሁን እየደባለቃችሁ ትገኛላችሁ:: እኔ የጨለማዉ ገዥ ለዚህ ወንበር ያበቃዋችሁ ኢትዮጵያዉያንን በሰማኒያ ብሔር ብሔረሰብ ስም ከፋፍላችሁ፣ የቋንቋ ልዩነት ፈጥራችሁ፣ በጎጥ አቧድናችሁ በአጭር ጊዜ ዉስጥ ልክ እንደ ቀድሞ ጌቶቻችሁ ኤርትራዉያን ፣ ብሔር ብሔረሰቦች ኢትዮጵያዊነታቸዉን ክደዉ የራሳቸዉን ነጻ መንግስት በማቋቋም የምጠላት ደመኛ ጠላቴን ኢትዮጵያን እንድታጠፉልኝ ነበር::

እኔ ሳደራጃችሁ በጎጣችሁና በቋንቋ ልዩነት ነበር:: ይኸዉም የትግሬ ነጻ አዉጪ፣ የትግሬ ልማት ማህበር፣ የኦሮሞ ነጻ አዉጪ ፣የኦሮሞ ልማት ማህበት፣ የአማራ ነጻ አዉጪ፣ የአማራ ልማት ማህበር .. ወዘተ በሚል ስም እንድትደራጁና ዘረኝነትንና ጎጠኝነቱን በማጠናከር መከፋፈልና መለያየት ብቻ አይደለም ባዘጋጀዉላችሁ ሕገመንግስት መሰረት አንቀጽ 39 መሰረት «የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከመገንጠል ድረስ» የሚለዉን በመጠቀም እንድትገነጣጠሉ ነበር::

ይሁንና እናንተ ግን «ገና ጠግበን አላስታወክንም፤» በሚል ስሜትና «የተገነጠለችዉም ኤርትራ አለበጃትምና መጨረሻዋን እንመልከት» በሚል አስተሳሰብ ይመስላል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሁሉም ጉሳዎች እንዳይዋሀዱ «የአማራ ጥቃቅንና አነስተኛ ማኅበር፣ የኦሮሞ አነስተኛና ጥቃቅን ማህበር፣ የትግሬ አነስተኛና ጥቃቅን ማኅበር» እያላችሁ በሰማኒያዉም ብሔር ብሔረሰቦች መከፋፈል ሲገባችሁ፤ በደፈናዉ «አነስተኛና ጥቃቅን ማኅበር» ብቻ በማለት ያደራጃችሁት አደረጃጀት ደስ ያላሰኘን መሆኑን እገልጽላችኋለሁ::

ምክንያቱም የብሔር ብሔረሰቦች በቋንቋቸዉ የመደራጀትን መብት ስለነካችሁና የተለያዩ ጎሳዎች በአንድ ላይ ተዋህደዉ እንዲሰሩ በመፍቀዳችሁ ነዉ:: ያ ከሆነ ደግሞ በጎጣችሁና በቋንቋችሁ ለፖለቲካዉ የበላይነት የተደራጃችሁት አደረጃጀት አደጋ ላይ ስለሚወድቅባችሁ ለእናንተ በማሰብ ነዉ:: ፖለቲካችሁ በብሔር ብሔረሰብ ዙሪያ ካላጠነጠነ ጥሩ ዉጤት እንዳማያመጣ ከኔ በላይ እናንተ እንደምታዉቁ እገምታለሁ:: እስቲ ስታስቡት

ጎጡን ነጻ ለማዉጣት የሚያስብ ዘረኛና ጎጠኛ፤ «ኢትዮጵያዉያን ሁሉ ወገኖቼ ናቸዉ» ብሎ በእኩልነት ለማገልገል ይነሳል?! ስለዚህ ኅሊናችሁ ለተዘጋጀበት መገንጠል ዓላማ መፋጠን አለባችሁ።

እዚህ ላይ ታዲያ «ትዉልዱ በጎጥና በቋንቋ ክፍፍል ሊደራጅልን ስላልቻለ ነዉ ካለ ቋንቋ ልዩነት ማደራጀት የጀመርነዉ።» ብላችሁ ልታታልሉኝ ብትሞክሩ ደግሞ የትዉልዱን ኅሊና አቋም አዉቀዋለሁ። ይኸዉም እንኳን ለእለት እንጀራቸዉ የሚተጉትን፣ ለሆዳቸዉ ሲሉ ኅሊናቸዉን ለመሸጥ ወደ ኋላ የማይሉትን ምስኪኖች ቀርቶ «ባለሀብትና ምሁር፣ ዶክተር ፣ ፕሮፌሰር.. ወዘተ» የተባሉትን ሳይቀር በጎጥ ድርጅታችሁ አባልና የዐመጻ ስራችሁ ተባባሪ ማድረግ የቻላችሁ ትጉሃን ሰራተኞቼ መሆናችሁን እናንተም እኔም የጨለማዉ ገዥ በደንብ እናዉቃለን፤ እንተዋወቃለን።

የአሁን ትዉልድ እንኳን «ጥቅም ታገኝበታለህ፤ ትበለጽግበታለህ፤» ተብሎ በጎጥ ማደራጀት ቀርቶ « ዝርያህ ጦጣዎች ናቸዉ፤ በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ (በኢቮልሽን) አማካይነት ነዉ ሰዉ የሆንከዉ፣ በመጨረሻም ከሰዉ ደረጃ ልቀህ በመገኘትህ «ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ አማራ፣ አፋር፣ ሱማሌ ፣ ሐረሪ፣ ጋምቤላ ቤንሻንጉል፣ ሲዳማ፣ ስልጤ፣ ጉራጌ፣ ሃድያ፣ ከፊቾ ባስኬቶ ፣ ኒዌር፣ ወላይታ፣ አገዉ .. ወዘተ » የመባል የብሔር ብሔረሰቦች ቅድስና ማዕረግ ደርሰሃል ቢባል፤ «አልቀበለዉም፤ እኔ የእግዚአብሔር ፍጥረትና ልጅ፣ የአዳምና የሔዋን ዘር፣ የኖኅ ልጆች የሆኑት የካም፣ የሴም፣ የያፌት ነገድ ዉህድ የሆነዉ ኢትዮጵያዊ የቅዱስ ኪዳኑ ሕዝብ ነኝ» ለማለት የማይደፍር፤ በዘረኝነትና በጎጠኝነት ፓለቲካ ስብከታችሁ የተመረዘና የተበከለ ነዉ። ትልቁ ግላዊ ሥጋዊ ጥቅሙን፣ ክብሩንና ስልጣኑን፣ ዝናዉን ከጠበቃችሁልት ኅሊናዉን የሚሸጥ፣ እንደቦይ ዉኃ ወደ ወሰዳችሁት የሚነዳ ስለሆነ አንዳች የሚያስቸግራችሁ አይመስለኝም።

የሚያስቸግረችሁን ደግሞ «ጸረ ሰላም፣ ጸረ ልማት፣ አሸባሪ ፣ ሁከት ፈጣሪ፣ የብሔር ብሔር መብት የማያከብር፣ ትምክህተኛ፣ ነፍጠኛ ..» ወዘተ እያላችሁ ፍዳዉንና መከራዉን ስለምታሳዩት ብዙም አያስቸግራችሁም። ስለዚህ መጀመሪያ ለተነሳችሁበት ዓላማ ጸንታችሁ

ቁሙ እንጂ አንዱ አገራዊ ራእይ፣ አንዱ ጎጣዊ ራእይ አትያዙ:: ከሁለቱ ያጣችሁ እንዳትሆኑ:: የሚያዋጣችሁንና በኔ ዘንድ ሞገስ እንድታገኙ ያደረጋችሁን የዘረኝነትና የጎጠኝነት አስተሳሰባችሁን አጠናክሩ እንጂ ለራሳችሁ መሰሪ ዓላማ ለመጠቀም «አንዱ የህዳሴ ግድብ፣ አንዱ የሰንደቅ ዓላማ ቀን ፣ አንዱ የአምስት ዓመቱ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ፣ አንዱ የብሔር ብሔረሰቦች መብትና ነጻነት እስከመገንጠል ድረስ፣ አንዱ በብሔራችሁ ተደራጁ ..» ወዘተ እያላችሁ የምታደባልቁትን ተግባርና ንግግር እንድታስተካክሉ በጥብቅ አስጠነቅቃችኋለሁ::

ስለዚህ በአፋጣኝ ኢትዮጵያ የሚለዉን መጠሪያ እያዳከማችሁ የተለያዩ ክልል መንግስታት እንዳቋቋማችሁ ሁሉ የተለያዩ ንግድ ድርጅቶቻችሁንም የትግራይ (የትግሬ) ባንክ ፣ የአማራ ባንክ፣ የኦሮሚያ(የኦሮሞ) ባንክ፣..ወዘተ እያላችሁ በሰማኒያ ብሔር ብሔረሰቦች መሰየም ይጠበቅባችኋል እንጂ፤ ጥቅም እናገኝበታለን የሚትሉትን አገራዊ ሽፋን እንዲይዝ፣ ስልጣናችንን ያጠናክርልናል የምትሉትን ጎጣዊና ቋንቋዊ ስያሜ መስጠታችሁ በኔ በጨለማዉ ገዥ ግምት ዉስጥ ጥሏችኋል:: ስለዚህ የሀገሪቱን ሀብት ሙሉ በሙሉ በፓለቲካና በጎጣዊ ድርጅታችሁ አድርጋችሁ ሕዝቡን በሆዱ ብትደልሉት እነደሚያዋጣችሁ ሳልመክራችሁ ባልፍ ለወደፊት ይቆጨኛልና በድርጅት አባሎቻችሁ፣ በፖለቲካ ድርጅቶቻችሁ እያሰባሰባችሁ፣ ድሀዉን እያጎሳቆላችሁና እያፈናቀላችሁ፣ በእዉነታ ላይ የዐመጻና የክህደት ተግባራችሁን የበለጠ ብታጠናክሩ እንደሚያዋጣችሁ በጨለማዉ ስሜ እመክራችኋለሁ::

እኔ የሊቃዉንት ሊቅ፣ የምሁራን ምሁር፣ የሳይንቲስቶች ሳይንቲስት፣ የአርቲስቶች አርቲስት የሆንኩትን የጨለማዉ ገዥ ቃለመጠይቅ የሚያደርግልኝ ሰብአዊ ፍጡር ባላገኝም የምጠላቸዉን ነገር በዝርዝር አቀርብላችኋለሁ:

የምጠላዉ የሚዋደዱ፣ የሚፋቀሩ፣ የሚተሳሰቡ፣ የሚረዳዱ ባልና ሚስትን ነዉ:: ለዚህም ነዉ በትዳር ዉስጥ በተለያየ መልኩ እየገባዉ ሰላማቸዉን የምነሳዉና እንዲጣሉ ብቻ አይደለም እንዲፋቱ፣ እንዲለያዩ ፣ እንዲገዳደሉ፤ የሆነዉን ያልሆነዉን ፈጥሬ በጎሊናቸዉ ሹክ የምለዉ:: እንዲሁም አገሩንና ወገኑን የሚወድና ለአገሩን ለወገኑ ለአዳም ዘር ራሱን አሳልፎ የሚሰጥ ሰዉን፤ እግዚአብሔርን በተግባሩ፣ በንግግሩ፣ በአሳቡ ጭምር የሚፈራ

እዉነተኛ ሰዉን፤ ለሃይማኖቱ ቀናዒ የሆነና አምላኩን በእዉነትና በመንፈስ የሚያገለግልና የሚያመልክ ሰዉን ነዉ።

እንዲሁም በሕይወቱ ቅንና እዉነተኛ የሆነ፣ መልካም ምግባር ያለዉ፤ ለሰዎች ርኅራኄና ቸርነት የሚያደርግ አዛኝ፤ ጥላቻዉንና ቂሙን ትቶ ከልቡ ይቅር የሚልና ይቅርታ የሚጠይቅ የዋሃና ትሁት ሰዉን ነዉ። ባጠቃላይ እግዚአብሔር ደስ የሚሰኝበት ሕይወትና ኑሮ የሚኖሩ ሰዎችን አልወድም፤ እጅግ እጸየፋቸዋለሁ። ከዚህ ሕይወትና ኑሮ ተለይተዉ በኃሰቀለና በመጥፎ ሕይወትና ኑሮ እንዲመላለሱ ሌት ተቀን እፈታተናቸዋለሁ።

በተቃራኒዉ የምወዳቸዉ ሰዎች ደግሞ ሰዉን ከሰዉ የሆነዉን ያልሆነዉን እየፈጠሩ የሚያጣሉ፣ የሚያገዳድሉ፣ የሚያፋቱ፤ ዉስጣቸዉ ክፋት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ ጥላቻ የሞላባቸዉ፤ ሁል ጊዜ ጎሊናቸዉን ለክፋት የሚያዘጋጁ፤ እንዲሁም ጎሊናቸዉን በማገለባበጥና በመሸጥ ለዐመጻ፣ ለክህደት፣ ለርኩሰት ተግባር የተሰለፉትን ሰዎችን ነዉ። ባጠቃለያ ለኔ የጨለማዉ ገዥ እንደልቤ የሚሆኑልኝን ሰዎችን ነዉ።

ብዙዎቻችሁ የፖለቲካ ጠበብትና ሊቀምሁር መሆኔን አልተረዳችሁልኝም። እናንተ የምታዉቋቸዉ ፖለቲከኞች ሁሉ የኔ ምልምሎችና እጩዎች እንዲሁም ስልጡኖች በመሆናቸዉ ቢያንስ ቢያንስ ጥበበኛ መሆኔን ባትቀበሉም እዉቀቴ የመጠቀና የረቀቀ መሆኑን ሳትገነዘቡልኝ የሚቀር አይመስለኝም። ለዚሁ «እስቲ ማስረጃ አቅርብ?» የሚል ሰዉ አላዋቂ ካለ ቀዳሚዉንና ግልጹን ማስረጃ አቀርብለታለሁ።

ይኸዉም የአንዱ አምላክ የእግዚአብሔር ፍጥረቶችና ልጆች መሆናችሁ እናንተ ባታምኑም እኔ እመሰክርባችኋለሁ። ለክህደትና ለዐመጻ እንዲሁም ለርኩሰት ተግባራችሁ ሽፋን ለመስጠት የአምላካችሁን ህልዉናና የአዳም ዘር መሆናችሁን ክዳችሁ፣ ሃይማኖትንና መንግስትን በማለያየት ለይስሙላ ሕዝቡ ሲፈልግ ለሃይማኖት አምላኩ እንዲገዛ፣ በተቃራኒዉ ደግሞ በዋናነት ትዉልዱ በሚታየዉና በሚጨበጠዉ ነገር ስለሚያምን ለኔ ለጨለማዉ ገዥ በመንግስት ስም እንዲገዛና ፈቃዴን እንዲፈጽምና እንዲያስፈጽም በማስደረጌ ነዉ። ወርቃማ ቃለቴ የሆነዉን « አገር የጋራ፣ ሃይማኖት የግል» እያስባልኩና በሕገ መንግስቴ በማሳወጅ ትዉልዱ ወደ እዉነተኛዉ የሕይወት መንገድ እንዳይመጣና በሙሉ ሕይወቱ ለአምላኩ

እንዳይገዛ፣ ፖለቲከኛ እንደራሴዎቼን በመጠቀም የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይኸዉ ለዘመናት ተጫዉቼበታለሁ::

ከዓለም አገራት ሁሉ እጅግ ያስደሰቱኝ ኢትዮጵያዉያን ፖለቲከኞች ናቸዉ:: ይኸዉም « እኛ በአንዱ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ አንመራም፤ እግዚአብሔር በእኛ ላይ እንዲነግሥ አንፈልግም፤ ቤተሕዝብ፣ ቤተ ክህነት፣ ቤተምልክና የሚባል አናዉቅም፤ አንፈልግም፤ ራሳችንን በራሳችን መምራትና ማስተዳደር የምንችል አዋቂ ምሁሮች ነን፤ ተስፋችን ምድራዊ ስለሆነ ስንፈልግ እንደፈለግነዉ እናመነዝራለን ፣ ከፈለግን እንዘፍናለን ፣ ዳኪርተኛነታችንንም ለዓለም እናስተዋዉቃለን፤ ዴሞክራሲ መብታችንን ተጠቅመን በባዕድና በጣዖት አምልኮ እንመላለሳለን፤ ስንፈልግ በዛሩ አምላክ ፣ ስንፈልግ በዛፉ አምላክ ፣ ስንፈልግ በወንዙ አምላክ ፣ ስንፈልግ በጨሌዉ አምላክ ፣ ስንፈልግ በጠንቋዩ አምላክ ፣ በመሳሰሉት አማልእክት በማመንና በማምለክ የአምልኮ ምንዝርና እንፈጽማለን:: ይህንንም ነጻነትን የሚሰጠንን መሪ ነዉ የምንፈልገዉና የምናነግሠዉ» በማለት ኢትዮጵያ እስከአሁን ድረስ ተጠብቃበት ባለዉ በቅዱስ ኪዳኑ ላይ ዐመጻና ክህደት በመፈጸማቸሁና በኔ የጨለማዉ ገዥ እንደራሴዎቼና አገልጋዮቼ ለመመራት ፈቃደኛ ሆናችሁ ስላነገሣችሁኝ፣ ስላገነናችሁኝ፣ ፈቃዴን ለመፈጸም ሌት ተቀን ስለምትተጉልኝ፣ ባጠቃላይ በአንድም ይሁን በተለያየ መልኩ ስለምታመልኩኝ ነዉ::

እናንተ የአዳም ዘሮች፤ አንዳንድ ከኔ ከጨለማዉ ገዥ ያፈነገጡ ሰዎች የሚሉትን አትስሙ:: ይኸዉም « እናንተ የአዳም ዘሮች ራሳችሁን እንደተለየ ነገር በመቁጠር ከፍ ከፍ ታደርጋላችሁ፣ ታገናላችሁ፣ አምላካችሁን ክዳችሁ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት ትመላለሳላችሁ፤ እዉነታዉ ግን ተራ፣ ደካማ፣ ጎስቋላ መሆናችሁን የሚያሳዩ ማንነታችሁን በግልጽ የሚያሳዉቁ ጉስቁልና ሕይወታችሁንና ኑሮዋችሁን የሚገልጹት የሚከተሉት ናቸዉ:

አዳምና ሔዋን ከገነት በዐመጻቸዉ ተባራዉ ወደዚህች ምድር ባይገቡ ኖሮ ብርሃንና ጨለማ አይፈራረቅባችሁም ነበር:: ሁል ጊዜ ሙቀት፣ ቃጠሎ የሌለዉ የማይቋረጥ ብርሃናዊ ባሕርይ ብቻ ነበር የሚበራላችሁ:: ሙቀትና ቅዝቃዜ አያገኛችሁም ነበር:: ዝናብ፣ ፀሐይ ለመከላከል መጠለያ አይስፈልጋችሁም ነበር:: ምግባችሁ፣ መጠጣችሁ ምስጋና ስለነበረ

ለሆዳችሁ ስትሉ አትወጡም፣ አትወርዱም ነበረ፡፡የምትበሉትና የምትጠጡት እንደዚህ ምድራዊ ምሳሌያዊ ፍጥረት (በሥጋዊ ዐይን የሚታይና በሥጋዊ እጅ የሚዳሰስ ያልሆነ) መብልና መጠጥ ስላልነበረ ከምትገለጹበት ረቂቅ አካል (ነፍሳችሁ ከምትገለጽበት ምሳሌያዊ ባሕርይ) ጋር ስለሚዋሀድ ወደ ዐይነምድር፣ ሽንት፣ ላበት የሚለወጥ ነገር አልነበረም፡፡

ሁላችሁም በአዳምና በሔዋን ምሳሌያዊ ባሕርይ ግንኙነት አማካይነት በእግዚአብሔር እቅድ መሰረት ተራ በተራ ካለመኖር ወደ መኖር ትመጡ (ትወለዱ) ስለነበረ ማርገዝ፣ ማማጥ፣ መዳህ፣ ማልቀስ፣ ማደግ፣ መወፈር፣ መክሳት፣ ማርጀት፣ መታመም፣ መሞት የሚባል ነገር አይኖርባችሁም ነበረ፡፡ «ይህ አባቴ ነዉ፣ ይህች እናቴ ናት፣ ይህ ወንድሜ ነዉ፣ ይህች እህቴ ናት፣ ይህ አጎቴ ነዉ፣ ይህች አክስቴ ናት፣ ይህ ዘመዴ ነዉ፣ ይህ ባዳ ነዉ .. ወዘተ» በማለት ስለማትለያዩ ሁሉም የአዳምና ሔዋን ልጆች ቤተሰብ ሆነዉ ቁጥራቸዉ ወደ ምድር ከተጣሉት ሰይጣናት ጋር እኩል እስከሚሆን ድረስ በገነት ቆይተዉ ከዚያም ወደ ሰማያት ዉስጥ በመግባት በመላእክት ስርዐት ነበር የሚኖሩት፡፡

ሁሉም በመልክ፣ በቁመት፣ በዉፍረት ስለማይለያዩ በአንድ አይነት ሕይወት ነበር የሚመላለሱት፡፡ ሀብታም፣ ደሀ፣ ታላቅ፣ ታናሽ የዚህ ዘር፣ የዚያ ዘር፣ የዚህ ቋንቋ፣ የዚያ ቋንቋ የሚባል ልዩነት ስለማይኖር ሁሉም በአንድ የእግዚአብሔር ልጅነታቸዉና አዳምና ሔዋን ዘርነታቸዉ በአንድ ቋንቋ ተፋቅረዉ በአንድነት በአንድላይ ይኖሩ ነበር፡፡

ያደፉና የጎደፉ እንዲሁም የጎሰቆሉ ባሕርይ ስለማይከሰቱባችሁ ማዘን፣ መተከዝ፣ ሰላም ማጣት፣ መቅበዝበዝ፣ መጨነቅ፣ መድከም፣ ማንቀላፋት፣ እርካታ ማጣት አይከሰትባችሁም ነበር፡፡ ለመኖር መብልና መጠጥ፣ አየር መፈለግ አይጠበቅባችሁም ነበር፡፡ ጥገኛ የምትሆኑባቸዉ ፍጥረቶች አንዳች አያስፈልጓችሁም ነበር፡፡ መድማት፣ መቁሰል አይታይባችሁም ነበር፡፡ ይህን ለመቀጣትና ለመጥራት የለበሳችሁትና የተገለጻችሁበት ሥጋ ያልነበረና ይልቁኑ ቀድሞ በገነት በምሳሌያዊ ባሕርይ (በረቂቅ አካል ብቻ) ስለተገለጻችሁ በምድር ዉስጥ በዐይን የሚታዩትም የማይታዩትም ምሳሌያዊ ፍጥረቶች በገነት ዉስጥ አልነበሩም፡፡

ሰይጣናት ለመፈታተን ወደ ኅሊናችሁና አካላችሁ የመግባት እድል ስለማያጋጥማቸዉ ማፋሸክ(ማዛጋት)፣ ማስነጠስ፤ መንጠራራት፤ ማግሳት፤ መሳል፤ ማከክ፤ መፍሳት፣ ንፍጥና አክታ አይታይባችሁም ነበር። ባጠቃላይ ያደፉና የጎሰቆሉ ባሕርያት አይከሰቱባችሁም ነበር። በዚህች ምድር የሚታየዉ መከራና ችግር፣ ስቃይና እንግልት አይደርስባችሁም ነበር።» በማለት ተራና የመከራ ኑሮ እንደምትኖሩ የሚነግሯችሁን ሰዎች ጆሮዋችሁን ሰታችሁ አትስሙ።

እነሱ ተሰፋቸዉ ሰማያዊ፣ ሕያዉ ሆነዉ በእግዚአብሔር መንግስት ለመኖር የሚፈልጉና ያደፈና የጎሰቆለ ባሕርይ የሌለበትን የገነት ኑሮን የሚናፍቁ ተስፈኞች ናቸዉ። እናንተ ደግሞ ተስፋችሁ ምድራዊ በሚታይና በሚጨበት የምታምኑ፤ አምላካችሁ እናንተዉ ቢበዛ እኔ የጨለማዉ ገዥ፤ ይህን ያደፈና የጎደፈ ሕይወትን የምትመርጡና የምትሟሟቁለት፤ የምትጣሉበት፤ የምትገዳደሉበት፤ የምትርመጠመጡበት፤ የምትለያዩበት፤ የምትከፋፈሉበት፤ ባጠቃላይ በከፋና በከረፋ ሕይወት የምትመላለሱበት ነዉ።

ስለዚህ እናንተ ጥሩ ምርጫ በማደረጋችሁ ተመጻድቃችሁና ራሳችሁንም እንደ ታላቅ ሰዉ አስታብያችሁ በድንፋታና በእብሪት «እኛ ከተፈጥሮ የተገኘን፤ ዘሮቻችንም ጦጣ መሰል እንስሳት ናቸዉ እንጂ አዳምና ሔዋን የሚባለዉ ተረት ተረት ነዉ» ብላችሁ በማሳፈር ልትመልሱላቸዉ ይገባል። በእርግጠኝነት የምነግራችሁ የእናንተ ተስፋ ታላቅ መሆኑን ነዉ። ይኸዉም በመጀመሪያ በድቅድቅ ጨለማ ዉስጥ የምትዘናኑ በኋላም በእሳትና በትሎች መሃል የምትጨፍሩ የኔ እድል የሚገጥማችሁ እድለኞች መሆናችሁን ነዉ። » **ይላል አንዳች ለአዳም ዘር ርኅራኄ የሌለዉ ጨካኙ ዲያብሎስ።**

## ምእራፍ ዘጠኝ

« ዉድ ኢትዮጵያዉያ፣ እናንተ የኖኅ ቀስተ ደመና የሆነዉን የቃል ኪዳን ሰንደቅ ዓላማ ከፍ ከፍ አድርጋችሁ ለማዉለብለብና ለመስቀል ታፍሩና ትጠሉ የነበረ አሁን ደግሞ ዓርማዬ የሆነዉም ኮኮብ ከፍ አድርጋችሁ ስላዉለበለባችሁልኝ ስለ መልካም አቀባበላቸዉ በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችኋለሁ፡፡ ታዲያ እስከመጨረሻዉ ዓርማዬ ዓርማችሁ እንዲሆን አሳስባችኋለሁ፡፡

ታዲያ አንዳንድ የኮኮብ ዓርማዬ ተቃዋሚዎችና መለኮታዊዉን ዓርማ ከፍ ከፍ ለማድረግ የሚፈልጉ ሰዎች « የኖኅ ቀስተ ደመና አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ዘለዓለማዊ ሰንደቅ ዓላማችን ከእግዚአብሔር የተቀበልነዉ ቃል ኪዳን የሆነ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በኢትዮጵያዉያን ተጠብቀዉ ከቆዩት ሰባቱ ቅዱስ ኪዳናት አንዱ የሆነ ነዉ፡፡ የአንድነትና የሦስትነት መገለጫ የሆነ፤ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክነት ! የነፍስ የሥጋና የመንፈስ አንድ ሰዉነት ! የኢትዮጵያዉያን አንድ የዉሕደት ዘር ሴማዊነት ካማዊነትና ያፌታዊነት ! የኢትዮጵያዉያን መለኮታዊ መንግስት ሕዝባዊነት ክህነታዊነት መለካዊነት የሚያስረዱ ናቸዉ፡፡ አንበሳዉ ደግሞ «ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ » ተብሎ በእግዚአብሔር ቃል የተነገረለትን፡ ዘለዓለማዊዉን ካህንና የጽዮንን ንጉሥ፥ የብሔረ ኢትዮጵያና የፍጥረተ ዓለሙም ንጉሠ ነገሥት ለሆነዉን ኢየሱስ ክርስቶስን ብቻ የተሰየመ ነዉ፡፡» በማለት ከኔ እንደራሴነትና ባለሚልነት እንዲሁም ዉድነትና አገልጋይነት ሊለያችሁ፣ የጨለማዉ ጸጋዬን ሊያሳጧችሁ ቀን ከሌሊት የሚተጉትን እንዳትሰሙ፤ እንዳትቀበሉ፡፡

እኔ ከኮከቡ በተጨማሪ ጨረቃዉን ለማስደረግ እንደምተጋ እነሱ ደግሞ ከመለኮታዊ ዓርማቸዉ በተጨማሪ ያች የምጠላት የዘመናት ደመኛዬን ጠላት ድንግል ማርያምን በመካከል ላይ ለማድረግና «ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር እንደዘረጋች የሚያሳይ ስለሆነ ይህችዉ እመቤት የአምላክ እናት፥ የጽዮንና የብሔረ ኢትዮጵያና የፍጥረተ ዓለሙም ንግሥት የሆነችዉ ድንግል ማርያም መሆኗን ያመለክታል፡፡» በማለት የሚያስተምሩትንና የሚናገሩትን አንዳች እንዳትቀበሉ፤ እንዳትሰሙ፡፡

ከተቀበላችሁ ግን የኔና የእናንተ ግንኙነት የመጨረሻ እንደሚሆን አስቀድሜ እገልጽላችኋለሁ፡፡ ስለዚህ እስከመጨረሻዉ የኔ ባለሟልና ባሪያ እንድትሆኑ እኔ የምላችሁን ተግባራዊ እንድታደርጉ በታላቁ የጨለማዉ ገዥ ስሜ አዛችኋለሁ፡፡ ይልቁኑ ለዋናዉ ድርጅቴ ሕወሐት(ወያኔ)ና ትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስቴ፣ ለሁለተኛዉ ልዩ ድርጅቴ ብአዴንና ለአማራብሔራዊ ክልላዊ መንግስቴ፣ ለሶስተኛዉ ልዩ ድርጅቴ ኦህዴድ፣ ለአጋር ድርጅቶቼና ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስቴ፣ ለጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስቴ፣ እንዲሁም ለተለያዩ ተለጣፊ ድርጅቶቼ የኮከቡን ዓርማዬን ለድርጅታችሁና ለክልላዊ መንግስታቶቼ ለሰንደቅ ዓላማ እንደተጠቀማችሁና አረንጓዴ ቢጫ ቀይ መደቡን እንዳጠፋችሁ ሁሉ፤ የፌደራል መንግስቴን አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ መደቡን ጭምር ብታስወግዱልኝ ምርጫዬ መሆኑን አሳዉቃችኋለሁ፡፡ እናንተም ምርጫዬን ምርጫችሁ እንደምታደርጉ እተማመንባችኋለሁ፡፡

እናንተ ኢትዮጵያዉያን « ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ» (ከይሁዳ ነገድ አሸናፊዉ አንበሳ) የሚለዉ የቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜ ለሆነዉ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረዉንና መለኮታዊ ዓርማ የሆነዉን ከማንኛዉ ቦታና ሕትመት ያስወገዳችሁና የኔን ጨለማዊ ዓርማ ኮከብ በየቦታዉና ሕትመቱ ላይ ከፍ ከፍ ያደረጋችሁልኝ፤ ሳይገባኝ ለኔ «የአሸናፊዎች አሸናፊ » ስልጣንና ማዕረግ የሰጣችሁኝ ሁሉ፤ ለመልካም ተግባራችሁና ተገዥነታችሁ በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችኋለሁ፡፡

ሌሎች አገሮች ኮከቡን ዓርማዬን ቢያገኑልኝም የእናንተን ያህል አድናቆትና ሙገሳ አልቸራቸዉም፡፡ ምክንያቱም እነሱ በኔዉ ቁጥጥር ዉስጥ የነበሩ፤ የመለኮታዊዉ ዓርማ ማንነት ምንነት ያላወቁና ያላስተዋሉ ናቸዉ፡፡ እናንተ ግን መለኮታዊዉ ዓርማ ለዘመናት በነጻነት ጠብቋችሁ በዓለም ዘንድ ሞገስን ሰቷችሁ አሽቀንጥራችሁ በመጣላችሁና ኮከቡን ዓርማዬን ዓርማችሁ አድርጋችሁ በመቀበላችሁና ራሳችሁን ከስደት፣ ከዉርደት፣ ከረሀብ፣ ከጦርነት፣ ከልመና፣ ከጥል፣ ከችግር፣ ከድርቅ፣ ከበሽታ መጠበቅ ስለቻላችሁና በዓለም ዘንድ በብልጽግናችሁና በእድገታችሁ ገናቸሁ ለዓለም ዉርደት ሳይሆን ሞገስና ክብር ሆናችሁ በማየቴ ነዉ፡፡ እንዲሁም በመላዉ ዓለም እንደ መልአክ ተቆጥራችሁ ስትፈቀሩና ለጋብቻ

ሰዎች ሁሉ ሲሻሙባችሁ በማየቴ ምን ያህል ይህ ኮኮብ ዓርማዬ ግርማ ሞገስ እንደሆናችሁ ስመለከት «አይ ከክብር ይልቅ ነዉርን መምረጥ ለዚህ ላልተጎሳቆለና ላልተዋረደ ሕይወት ይዳርጋል ለካስ!» ብዬ ራሴን በራሴ እገመግምና በዚህ በተመረጠዉና በተወደደዉ በዓለም ዘንድ ሞገስ ባገኛችሁት ሰብእናችሁ ቀንቼ የበለጠዉን ዉድቀትና ጥፋት ላመጣባችሁ እተጋለሁ።

ክቡራን ታላላቅ የየአገራቱ መንግስታት መሪዎች፣ ፕሬዘዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ነገሥታት፣ ከፍተኛ ባለስልጣኖች፣ እንዲሁም አናሳ የክልል ፕሬዘዳንቶችና ነገሥታቶች፤ መቸስ የጨለማዉ ገዥ ተግባርና ንግግር የሆነዉ የኔ መልእክት ሲደርሳችሁ የኀዘን ስሜት እንደማይሰማችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። ምክንያቱም የኔ ተስፋ መቁረጥና ባለጊዜነት ሊሻር መድረሱና ለዓለም የዘረጋሁት የጨለማዉ ስርዐቴ ሊደመሰስ አንድ ኀሙስ የቀረዉ መሆኑን እናንተም ሳትገምቱ እንዳልቀረ እገምታለሁ።

ታዲያ እስከመጨረሻዉ ሰዐት ደማችሁን ሳይቀር እንደምትገብሩልኝ ብተማመንም፤ አሁን አሁን ግን በዋናነት እንድታጽናኑኝ « አይዞህ የግብር አባታችን ዲያብሎስ! የአንተን ፈቃድ ለመፈጸምና ለማስፈጸም የተጋን ስለሆነ አንዳች ተስፋ መቁረጥ እንዳይሰማህ» እንድትሉኝ እፈልጋለሁ።

ለነገሩ እኔስ ኃይሌ ልምሾ ቢደረግ እንኳ በረቂቅ አካሌ ተገልጬ በዚህች ምድር ከመኖርና ከመመላለስ አልከለከልም። እናንተ ግን በግዙፉ አካል በሥጋ ስለተገለጻችሁ የዐመጻ፣ የክህደት፣ የርኩሰት ጽዋችሁ ሞልቶ ሲፈስ እንደኔ የጨለማዉ ገዥ ረቂቅ አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) ለብሳችሁ በሁለተኛዋ የጨለማ ቦታ ነጻነታችሁ ተገድቦ አንዳች በነጻ ኅሊናችሁ ተመርታችሁ ዐመጻ በማትፈጽሙበት ቦታ በሲኦል ስለምትኖሩ «ማን ያጽናናቸዋል?» እያልኩ አስብላችኋለሁ፤ እጨነቅላችኋለሁ። «እናትና ልጅ ይሁኗችሁ» ብል ደግሞ የፌዝ ስለሚመስልብኝ ዝም ማለትን መርጫለሁ።

ይኸዉም በእናትና በልጇ ላይ በማመጽ ተወዳዳሪ ያልተገኘላችሁ ዐመጸኛና ከሃዲ፣ የርኩሰት ስራ ዋና ፈጻሚና አስፈጻሚ ስለሆናችሁ፤ ከኔ ከታላቁ መጠጊያችሁና ወዳጃችሁ ለይተዉ አይወስዷችሁም በሚል ስጋት ነዉ። ምንም እንኳን በሥጋ የምትለዩኝ ጊዜ የተቃረበ

በመሆኑ እጅግ ባዝንም በነፍሳችሁ ለወደፊቱ በጋራ መኖሪያችንና  ስለ ዐመጻ ሕይወታችን ዋጋ በምንከፍልበት በታላቁ ቦታ መገናኘታችን አይቀርምና እስከዚያዉ ድረስ ባስተማርኳችሁ ተግባርና ንግግር ጸንታችሁ ተገኙ፡፡

እናንተ የአዲሲቷ ኢትዮጵያና የክልላት መንግስታት እንደራሴዎቼ መሪዎች፣ ባለሚሎቼ ባለስልጣኖች እንዲሁም  ዉዶቼ ካድሬዎች፤ በአንዳንድ እርምጃዎቻችሁ ብደሰትም አድሎ በማድረጋችሁ እኔ የጨለማዉ ገዥ ቅር ተሰኝቼባችኋለሁ፡፡ ይኸዉም ነፍጠኞችና ትምክህተኞች ያመጡትን ደመኛዬ ጠላቴን «ኢየሱስ ክርስቶስ፣ መድኃኔ ዓለም፣ ክርስቶስ» በመባል የሚታወቀዉን የክርስቲያኖችን አምላክ ለማሰብ፤ ያደገበትን፣ የተወለደበትን፣ ያስተማረበትን፣ የተለያዩ ተአምራትንና ፈዉስ ያደረገበትን ቦታ ስም ለማሰብ «ናዝሬት፣ ደብረዘይት » ብለዉ የሰየሙትን ስም ብቻ ከአገሪቱ ደምስሳችሁ ያቺ የምጠላት የዘመናት ጠላቴ «ድንግል ማርያም፣ ወላዲተ አምላክ» በመባል የምትታወቀዉ የክርስቲያኖች መመኪያና አማላጅ የሆነችዉ የምትታሰብበትን ቦታ «ሀገረማርያም፣ መርጦለማርያም» እንዲሁም ቅዱሳን የሚታሰቡበትን «ደብረማርቆስ» የሚባሉትን ስም ከአገሪቱ ባለመደምሰሳችሁ ነዉ፡፡

እንዲሁም ለጥንቲቱ ኢትዮጵያ  ታሪክ የሰሩትን እነ  ገላዉዴዎስን፣  ኃይለማርያም፣ መኮንን ፣.. የመሳሰሉት በትምህርት ቤት፣ በሆስፒታል፣ በአዳራሽ የተሰየመላቸዉን መታሰቢያ ብቻ ለይታችሁ፤ ሌሎች ስንት ያበሳጩኝን ትታችሁ እንዲሁም የኔ ፈቃድ አልፈጽምም ብለዉ ያለፉትን ለአገራቸዉ ደማቸዉን ያፈሰሱላትን ጭምር ሙሉ በሙሉ ባለመደምሰሳችሁ ነዉ፡፡ ነገር ግን ለወደፊት ሙሉ በሙሉ ትደመስሳላችሁ በሚል ግምት በማስጠንቀቂያ ብቻ አልፌያችኋለሁ፡፡

እዚህ ላይ ሌላዉ የማሳስባችሁ ልዩ የአምልኮት ስፍራዬን ለማስታወስ በየባሱ ላይ «አንበሳ ባስ» የሚለዉን ስያሜ አስወግዳችሁ «ቢሾፍቱ ባስ» በማለት በመተካታችሁ ሙገሳዬን እየገለጽኩ፤ ለወደፊቱ ደግሞ አንበሳ የሚል ዓርማና ስያሜ ያላቸዉን ሁሉ ከአገሪቱ

ደምስሳችሁ የተለያዩ ባዕድና ጣዖት አምልኮ የሚመለክባቸዉን ልዩ ስያሜዎችን በመስጠት አገልግሎታችሁን ምሉእ እንደምታደርጉ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

እዚህ ላይ ታዲያ «ለምን የተዉነዉን ነፍጠኛ፣ ትምክህተኛ የሚለዉን ስም ታነሳብናለህ?» ብላችሁኝ እንደማትጠይቁኝ እገምታለሁ፡፡ ምክንያቱም ለዚህ ስልጣን እድሜ ያበቃችሁ ይህ ስም ኃይላችሁ ሆኖ ልክ እንደ ብሔር ብሔረሰቦች ቋንቋዬ፤ ልዩነት ለመፍጠርና እርስ በእርስ ደም ለማፋሰስ፣ ለማጣላት፣ ለመከፋፈል፣ ለማገዳደል የረዳችሁ ታላቅ ባለዉለተኛ ስያሜ መሆኑን ከኔ በላይ እናንተ እንደምታዉቁ እገምታለሁ፡፡ ስለዚህ እናንተን የሚያዋጣችሁ ነጋ ጠባ በየቴሌቭዥኑ፣ በየሬዲዮኑ፣ በየሕትመት ዉጤቶች «ብሔር ብሔረሰቦች፣ ነፍጠኞች፣ ትምክህተኞች» እያላችሁ ጥላቻ መፍጠርና መከፋፈል እንጂ « የሰንደቅ ዓላማ ቀን፣ የህዳሴ ግድብ፣ የአምስት አመቱ እድገትና ትራንስፎርሜሽን.. ወዘተ» የሚሉት ለኔ የጨለማዉ ገዥ የማይመቹኝና ሕዝቡ ወደ አንድነት የሚያሰባስብ የዘረኝነትና የጎጠኝነትን መሪያችሁን መንፈስ የሚፈታተን ስለሆነ በቀደመዉ የጨለማ መንፈሴ ብቻ መመራት እንዳለባችሁ አሳስባችኋለሁ፡፡ እንዲሁም «አንድነት፣ አገር፣ ምንትስዬ» የምትሉትን የማስመሰል አባባላችሁን ብታቆሙ ለረጅም እድሜያችሁ የሚሻላችሁ እንደሆነ በጨለማዉ ስሜ እመክራችኋለሁ» **ይላል እዉነትን ሙሉ በሙሉ ከኢትዮጵያ ምድር ለማጥፋት ታጥቆ የተነሳዉ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከግብር አበሮቹ ጋር በመሆን፡፡**

## ምእራፍ አስር

« እናንተ «ጸሎተኛ ነን፤» እያላችሁ በዘልማድ ብቻ የምታነበንቡ ከመልካም ምግበር የተለያችሁ፤ እንዲሁም «ቆራቢ ነን፤» እያላችሁ በክፋት፣ በተንኮል፣ በምቀኝነት ፣ በትዕቢት፣ በርኩሰት፣ በጥላቻ፣ በቂም በቀል፣ በዘረኝነት ፣ በጎጠኝነት ፣ በዘፋኝነት ፣ በዳንኪርተኛነት ፣ በአምልኮ ምንዝርና፣ በስካር ..ወዘተ በመሳሰሉት ሕይወት የምትኖሩ ሰዎች፤ መቼስ በዚህ ሕይወታችሁ መንግስት ሰማያትን የምትወርሱ ከሆነ እኔም የጨለማዉ ገዥ ከመንግስተ ሰማያት በላይ የሆነ ቦታ እንደሚዘጋጅልኝ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ምክንያቱም በዚህች ምድር ላይ እንዲህ የምታስመስል ዐመጸኛ ነፍስ ከሥጋዋ ስትለይ የምትገለጽበትን ረቂቅ አካል (ምሳሌያዊ ባሕርይ) ብቻ ትለብሳለች እንጂ በዚህ ምድር ላይ ያላት ባሕርይና ሕይወት አብሯት ስለሚሆን፤ ከኔ ዐመጻ በላይ ዐመጸኛ ሆና፣ ይኸዉም በመስቀል ላይ የተከፈለላትን ታላቅ ዋጋ ከንቱ አድርጋ፣ ይልቁንም በማስመሰል ሕይወት እያላገጠችና እየተሳለቀች ገነት፣ መንግስተ ሰማያት የምትገባ ከሆነ፤ እግዚአብሔር በባሕርይዉ አድሎ ስለማያደርግና ፍትሐዊ ፍርድ ስለሚሰጥ፤ እኔንና ሠራዊቶቼን ሰይጣናትን ያላስመሰልነዉና ያላላገጥነዉን እንዲሁም አንዳች ዋጋ ያልተከፈለልንን ዐመጸኞችን ወደ መንግስቱ ቅድሚያ ሰቶን ሰተት አድርጎ እንደሚያስገባኝ እናምናለን፡፡ ታዲያ በእናንተ ሕይወት በደንብ እንድንጽናና ኃጢአታችሁን በላቀ መልኩ አጠናክራችሁ ቀጥሉበት እያልን በጨለማዉ ስማችን እንመክራችኋለን፡፡

እናንተ «በምድር ዉስጥ በተዘረጋዉ የጨለማዉ መንግስትና ስርዐት የዲያብሎስ ነዉና አንመራበትም፤ እኛ የምንመራዉና የምንመላለሰዉ በእግዚአብሔር መንግስት ቤተ ሕዝቡ፣ ቤተ ክህነቱ፣ ቤተ ምልክናዉ በአንድላይ በመንፈስ ቅዱስ ብቻ በሚመራበት ስርዐት ነዉ» የምትሉና በኔ በጨለማዉ ገዥ በዲያብሎ ላይ ዐመጻ በመፈጸም «ያንተን ፈቃድ አንፈጽምም፤ አናስፈጽምም» በማለት «ላንተ አንገዛም፤ አንታዘዝም፤ ከሃዲ፣ ዐመጸኛ፣ ርኩስ ነህ፤» እያላችሁ የምታወግዙኝና እግዚአብሔር በሰጣችሁ መሳሪያ ሌት ተቀን የምታቃጥሉኝ፣ የምታስሩኝ፣ የምታበሳጩኝ፣ የምታናድዱኝ፣ ባጠቃላይ ፍዳዬን የምታሳዩኝ ሰዎች ሁሉ፤

እኔን የማትከተሉና ፈቃዴን የማትፈጽሙ ከሆነ እንደበገናችሁ፣ እንዳዘናችሁ ምድሬን ለቃችሁ ወደ ምትሄዱበት ትሄዳላችሁ እንጂ ለምርጥ ባለሚሎቼ የማድለዉን ስልጣንና ብልጽግና በተለመደዉ በባዶ ቀፎ በሆነዉ አንደበቴ አልሰጣችሁም ። በኔ ዘንድ ርኅራኄ፣ ይሉኝታ የሚባል ነገር የለም። ከአዳም ዘር የባስኩ ጨካኝ ነኝ። ስለዚህ የመጨረሻ አንድ እድል እሰጣችኋለሁ። ምድራዊ የጨለመዉ መንግስቴን ስርዐት አክብራችሁ የምትኖሩ ከሆነ በምድሬ መኖር ትችላላችሁ። «የእግዚአብሔርን መንግስት እንመሰርታለን፣ የእሱን ፈቃድ ብቻ እየፈጸምን ሕዝቡንም እናስፈጽማለን።» የምትሉ ከሆነ ከዚህች ምድሬ ለቃችሁ ወደምትሄዱበት እንድትሄዱ በጥብቅ እነግራችኋለሁ። የጨለማዉ ገዥ እናንተ ከምትመሩበት መንፈስ አንድነትና ህብረት ስለሌለዉ በህብረትና በአንድነት የምድሪቱን መንግስቴን ለማገልገል እንደማይቻል ከኔ ከጨለማዉ ገዥ በላይ እናንተ የምታዉቁ ይመስለኛልና በኔ ዘንድ አንዳች ድርሻ የሌላችሁ መሆኑን በተለመደዉ ተራና ባዶ በሆነዉ ፉከራዬ እንድታዉቁ ለመግለጽ እወዳለሁ።

እናንተ «ለመንፈሳዊ አገልግሎት የተሰለፍን ነን» ብላችሁ፤ የኔን የጨለማዉ ገዥ ዉዶቼን (ካድሬዎችን) እናንተም እየመለመላችሁ አባልና ደጋፊ በማድረግ የምታሳምጹብኝ ሰዎች ወዮላችሁ! ከመቼ ወዲያ ነዉ የዲያብሎስ ፈቃድ ፈጻሚና አስፈጻሚ የእግዚአብሔር ፈቃድ ፈጻሚና አስፈጻሚ ሲሆን የታየዉ? ከመቼ ወዲያ ነዉ በዲያብሎስ መንፈስ የሚመራ ሰዉ በእግዚአብሔር መንፈስ ሊመራና ከእግዚአብሔር ብቻ የሆነዉን ለመፈጸም የሚችለዉ? ወይስ እንደ ይሁዳ ሕይወት ሁለቱንም እያጣቀሱ መጨረሻቸዉ እንዳያምር ተፈልጎ ይሆን? ወይስ እናንተም እንደ ምርጦቼ ሥጋዉያን መሪዎች በካድሬ ብዛት የምታምኑና ብዙ አባላት ስላላችሁ ብዙ ፍሬ የምታፈሩ መስሏችሁ ይሆን? ወይስ እንደ እንደራሴዎቼ ዓለማዉያኑ በጦር ኃይላቸዉ ብዛት እንደሚያምኑ እናንተም በሥጋዉያኑ መሪዎች ለመመካትና አምባ መጠጊያ ለማድረግ አቅዳችሁ ይሆን? ወይስ እንደ ዓለማዉያኑ ከንቱ ሥጋዊ መጠበብን አድርጋችሁ እግዚአብሔርን ደስ የምታሰኙት መስሏችሁ ይሆን?

እንግዲህ የኔ የጨለማዉ መንፈስና የእግዚአብሔር መንፈስ ምንም አንድነት የሌለንና ህብረትም ልንፈጥር የማንችል መሆኑን ልታዉቁ ይገባል። ስለዚህ ከሁለታችን አንዳችንን

መምረጥ ይኖርባችኋል፡፡ ወይ እኔን የጨለማዉ ገዥንና እንደራሴዎቼን መንግስታት፣ ከነባለስልጣኖቻቸዉና፣ እንዲሁም አባሎቻቸዉን (ካድሬዎችን) ወይንም በእዉነትና በመንፈስ ብቻ እግዚአብሔርን የሚያምኑና የሚያመልኩ እንዲሁም የሚያገለግሉትን፡፡ እንኳን በእግዚአብሔር ዘንድ ከሁለት እያጣቀሱ መኖር አይደለም በኔ ዘንድ ከሁለት የሚያጣቅሱትን አልፈልጋቸዉም፡፡ እኔ የምፈልገዉ በአንድ ልብ ሆነዉ የሚተጉልኝን ነዉ እንጂ የነፍሳቸዉ ነገር እያሳሰባቸዉ ግማሽ ልባቸዉን ብቻ የሚሰጡኝን አልፈልጋቸዉም፡፡ በአንድ አቋም ካልጸኑ በወላዋይነታቸዉ እንድ ይሁዳ አስከፊዉን እርምጃ እንደምወስድባቸዉ አዉቀዉ ከወዲሁ ከእናንተ አባልነትና ደጋፊነት ወተዉ ሙሉ ሕይወታቸዉን ለኔ ለጨለማዉ ገዥ ማዋል ይጠበቅባቸዋል፡፡

እግዚአብሔር ከፈለገ በአንድ ሰዉ የአእላፍና የአእላፋት (የሚሊዮንና የቢሊዮዎን) ሰዎችን ስራ ሊያሰራ እንደሚችል አዉቃችሁና አስተዉላችሁ ቢሁን ኖሮ የኔን የጨለማዉ ገዥ አባላትን አባል አታደርጉብኝም ነበር፡፡ ክርስትና በአስራ ሁለት ሐዋርያት ለዓለም እንደተዳረሰ እንዲሁም እስራኤላዉያን በአንድ ሙሴ ከግብጽ ባርነት ነጻ ወተዉ ወደከነዓን ምድር እንዲገቡ እንደተደረገ የተማረና ልብ ያለ ሰዉ «በአባላት ብዛት ፍሬ እናፈራለን፤ የእግዚአብሔርን እዉነት ለዓለም እናዳርሳለን» ብሎ የኔን ፈቃድ ፈጻሚና አስፈጻሚዎችን አባልና ደጋፊ በማድረግ ከንቱ የሆነ ሥጋዊ መጠበብን አያደርግም ነበር፡፡ ይሁንና «ፊደል ቆጠርን፤ ተማርን፤ ተመራመርን» በሚል አስተሳሰብ እንደ ሥጋዊያኑ በብልጣብልጥነት ከሁለት እያጣቀሱ መኖር ከሁለቱ አንዱንም ማጣት እንደሚያስከትል አዉቋችሁ እኔን ወይንም «እናመልከዋለን » የምትሉትን አምላክ በግልጽ ለይታችሁ መምረጥ አለባችሁ፡፡ ያለበለዚያ በኔም ሆነ በአምላካችሁ እንደምትተፉ ልታዉቁ ይገባችኋል፡፡

እናንተ ኢትዮጵያዉያንና የዓለም ሕዝቦች! እግዚአብሔር በተለያየ ዘመናትና ዓመታት መልእክቱን በተለያዩ አገልጋዮቹ ቢያስተላልፍም «አንቀበልም፣ አንፈጽምም፣ እጃችንም ለእግዚአብሔር አንሰጥም» በማለት የታበያችሁና ያመጻችሁ በመሆኑ፤ ክብር ስላልወደደላችሁ በቁጣዉ እናንተ ሳታስተዉሉትና ሳትጠብቁት በተለያየ መንገድ ከምድር

መጠረጋችሁና መጽዳታችሁ ስለማይቀር፤ ነጻነታችሁ ተገድቦ ወደ ሲዖል እንደምትጋዙ ቢታወቅም፤ የመጨረሻዉ የጨለማ ምክሬ ግን ተጠርጋችሁ እስከምትሄዱ ድረስ በዐመጻ፣ በክህደት፣ በርኩሰት፣ ባጠቃላይ በኃጢአት ተግባራችሁና ንግግራችሁ እንዲሁም አሳባችሁ ጽኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እጅ በመስጠት ንስሐ እንዳትገቡ።

እንዲሁም በተመረጠችዉና በተቀደሰችዉ አገር ኢትዮጵያ ለሚመሰረተዉ የእግዚአብሔር መንግስት ሆነ ለቅዱስ ኪዳኗ ሃይማኖት ለተዋህዶ እጃችሁን እንዳትሰጡ። ምክንያቱም ሰላም፣ፍቅር፣ እረፍት፣ በረከት፣ እርካታ የምታገኙት፤ እግዚአብሔር ለሚመሰርተዉ መንግስት እጃችሁን ከሰጣችሁና በኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖት አማካይነት ከእግዚአብሔር ልጅነትን ካገኛችሁ ብቻ ነዉና። እናንተ ግን ምርጫችሁ ጦርነት፣ ግድያ፣ ስርቆት፣ ክፋት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ ዘረኝነት፣ ጎጠኝነት፣ ትዕቢት፣ ዐመጻ፣ ክህደት፣ ርኩሰት፣ ግፍ፣ ጭከና፣ በደል፣ አድሎ.. ምኑ ተነግሮ ያዉቃል የኔን የጨለማዉ ገዥ ፈቃድ ስለሆነ ነዉ።

እናንተ የቀደሙት የጸሐፍት፣ ፈሪሳዉያንና የአይሁድ ካህናት ሕይወት የያዛችሁና በእግዚአብሔር ስም የምትነግዱና የምታስመስሉ «አገልጋዮችና ምእመን ነን » የምትሉ፤ ዋናዉን የኃጢአት ስራ ከቁም ነገር ሳትቆጥሩ ወጋችሁንና ልማዳችሁን እንደ ሕግ የምትቆጥሩና ምእመኑ በእዉነትና በመንፈስ አምላኩን እንዳያመልክ እንቅፋትና ማሰናከያ የሆናችሁ ሰዎች፤ የራሳችሁን የኃጢአት ስራ ያማትመለከቱና የሌላዉን እንደ ኃጢአት እንኳ የማይቆጠረዉን የምታራግቡና የምታብጠለጥሉ፣ ባጠቃላይ በዘልማድ ሕይወት የምታገለግሉና የምትመላለሱ እንዲሁም ለኔ ለጨለማዉ ገዥ እንደ ልቤ የሆናችሁ ወዳጆቼና አገልጋዮቼ፤ በያዛችሁት አቋምና ሕይወት እንድትቀጥሉበት እመክራችኋለሁ።

መቼስ ለድርጊታችሁ ሆነ ለንግግራችሁ ምክንያትና መረጃ ማዘጋጀትና መፍጠር የማይሳናችሁ፣ ብቃታችሁ ከኔ አንዳንዴ የሚልቅ ነዉና ለእያንዳንዱ የማስመሰልና የባዶነት እንዲሁም የግብዝነት ተግባራችሁና ንግግራችሁ ተቀባይነት እንዲኖረዉ ከቅዱሳትና ከአዋልድ

መጽሐፍት እየጠቃቀሳችሁ ማሳመን አለባችሁ እንጂ ትዉልዱ ከእናንተ የነቃና የመጠቀ ስለሆነ እንደ ቀድሞ በቁጣና በማስፈራራት ብትናገሩት አይሰማችሁም፤ አያምናችሁም፡፡

ስለዚህ ለምሳሌ « ክርስቶስ ኦሪትና ነብያትን ለመሻር አልመጣሁም፣ ልፈጽም ነዉ እንጂ» ብሏልና፤ ሙሴ ያወጣዉን የተለያዩ ፍርዶችና ስርዐት ተግባራዊ አድርጉ፤ ለምሳሌ የገደለ ይገደል፤ የሰረቀ እጁ ይቆረጥ፤ አይን ያወጣ አይኑ ይዉጣ፤ ያመነዘረች ወይን ያመነዘረ ተወግራ ወይንም ተወግሮ ትገደል ወይንም ይገደል፤ በሰንበት የዘረጋዉን እግር ያጠፈ፣ የተፈወሰበትን አልጋ ተሸክሞ የሄደ፣ በሽተኛን ይዞ የተንቀሳቀሰ፣  ምግቡን አብስሎ የበላ፣ መጠጡን አሙቆ የጠጣ ወዮለት ይኮነናል፤ ወር አበባ የታያት ሴት ርኩስ ናት ፤ የወለደች ሴት ርኩስ ናት፤ ወደ መቃበር የሄዱ ሰዎች ርኩሶች ናቸዉ፤ ሚስቱ ወይንም ባሏ የደበረችዉ ወይንም የደበራት፣ የሰለቸችዉ ወይንም የሰለቻት የፍቺ ወረቀት እተሰጣጡ ይፋቱ፤ እንደገና ደግሞ የፈለጉትን ያግቡ፤ ለዚህች አጭር ዘመናቸዉ ምን አጨናነቃቸዉ፤ ባልታጠበ እጅ የሚበላ ሰዉ ርኩስ ነዉ ኃጢአትን ፈጽሟል፤ ለታይታ ብቻ በየመንገዱና በየቦታዉ የማይጸልይና በእዉነትና በመንፈስ ብቻ የሚጸልይ ሰዉ ጸሎቱ በፈጣሪ አይሰማም፤ የብሉይ ዘመን ሕግና ስርዐት ይጠበቅ፤ የእንሳሱት መስዋዕት ይፈጸም.. ወዘተ በማለት፤ ባጠቃላይ በሙሴ ዘመን እንደነበሩት ሰዎች ሕይወት የአሁኑ የሐዲስ ዘመን ሰዎችም በዚያ ሕይወት ይመላለሱ፡፡» በማለት የጨለማዉን የብሉይ ዘመን ሕይወት ተግባራዊ አድርጉ፤ አስደርጉ፡፡ ይህን በማድረጋችሁና በማስደረጋችሁ እንደ ጸሐፍት፣ ፈሪሳዉያን ፣ አይሁድ ካህናትና አለቆች የተለየ የከበሬታ ወንበር ታገኛለችሁ፡፡ ትመሰገናላችሁ፡፡ ትከብራላችሁ፡፡ ትገናላችሁ፡፡

ታዲያ አንዳንድ ያልገባቸዉ ሰዎች «በሐዲስ ዘመን ሁሉ በእዉነትና በመንፈስ ነዉ የሚፈጸመዉ፤ የብሉይ ዘመን የአምልኮት ስርዐትና የፍርድ አፈጻጸም የወጣዉ በወቅቱ ካለዉ ትዉልድ አስተሳሰብና ንቃተ ኅሊና እንዲሁም ደንዳናነትና ዐመፃ በመነሳት ነዉ፡፡  እያንዳንዱ የብሉይ ዘመን ሥርዓትና ፍርድ ከዘመኑ አንጻር ምክንያት የነበረዉና በዘመኑ ለነበሩ ሰዎች የሚገባ ነዉ፡፡ ሰዎች በራሳቸዉ ሥጋና ደም ስሜት የፈጠሩት ወግና ልማድ ግን እንደ እምነትና አምልኮ ስርዐት የሚታ አይደለም፡፡

በሐዲስ ዘመን ራሱ ባለቤቱ እግዚአብሔር በሥጋ ተገልጾ አስርቱን ትዕዛዛትን በማጽናት ሌሎች ስርዐቶችና ፍርዶችን በከፊልና ሙሉ በሙሉ ያሻሻለዉና የለወጠዉ እንዲሁም ሰዎች ስለ ወጋቸዉና ልማዳቸዉ የእግዚአብሔርን ሕግና ስርዐት እያሻሩ ስለነበረ ገስጿቸዋል እንጂ ወግና ልማዳቸዉ እንደ ሕግና ስርዐት እንዲታይ አላደረገም፡፡ ስለሆነ በክርስቲያናዊ ስርዐትና ልማድ ሕይወት ነዉ የምንመላለሰዉ እንጂ በጨለማዉ ሕይወትና ልማድ አንመላለስም፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ የባርነት ቀንበራችንን ሰብሮልናል፡፡ ሸክማችንን አቃሎልናል፡፡ ለሕያዉት ሕይወት የሚሆነን መብልና መጠጥ ራሱ ተሰዎቶልን ቅዱስ ሥጋዉንና ክቡር ደሙን ሰቶናል፡፡ እለት እለት ሕይወታችንን በንስሐ እየመረመርን እንበለዋለን፤ እንጠጣዋለን፤ አንድነታችንን ከእርሱ ጋር እንፈጥራለን ፡፡

በተለያየ መንገድ ተተብትበን የነበረዉን እስራት ፈቶልናልና በግብዝነትና በባዶ ቀፎ ሕይወት አንመላለስም፡፡ እግዚአብሔር ሰንበትን እንድናርፍ ያዘዘዉ የተለየ ጥቅም ሊያገኝበት ፈልጎ ሳይሆን እኛ የአዳም ዘሮች ነፍሳችን እረፍት እንድታገኝበትና ለሰማያዊ ሕይወት የሚረዳትን ሰማያዊ መብልና መጠጥ እንድትበላበት፣ እንድትጠጣበት ፈልጎ ለእኛዉ ፍጥረቶቹና ልጆቹ አዝኖልን ነዉ፡፡ ጋብቻንም በተመለከተ አንድ ወንድ ለአንድ ሴት ብቻ ያጸናልንና ማንም ይሁን ማን በክሳት፣ በህመም፣ በችግር፣ በጉስቁልና፣ ባጠቃላይ በምድር ላይ በተለያየ ምክንያት ሊከሰት በሚችል ክስተት ምክንያት ማንም ሰዉ ሚስቱን ሆነ ባሉን መፍታት እንደማይችልና ካደረገ ደግሞ በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ዐመጻ እንደ ፈጸመ እንደሚቆጠርበት በግልጽ አስተምሮናል፡፡ ባጠቃላይ እስከ እለተ ሞታችን ድረስ እግዚአብሔርን በስራችን፣ በንግግራችን፣ በአሳባችን ጭምር እርሱን በመፍራትና እሱ ደስ በሚሰኝበት ሕይወት ብቻ እንመላለሳለን፤ እንኖራለን.. ወዘተ » በማለት የሚናገሩትንና የሚያስተምሩትን አንዳች እንዳትሰሙ፡፡

እነሱ ነፍሳቸዉ በሚመቻት ስርዐትና ሕይወት ለመመላለስ የሚፈልጉ ናቸዉ እንጂ ለሥጋቸዉ አንዳች አያስቡለትም፡፡ መመስገንና መግነን እንዲሁም መመለክን የማይፈልጉ፤ እግዚአብሔርንና ምእመኑን በቅንነትና በእዉነት ለማገልገል የሚፈልጉ፤ ተስፋቸዉን ሰማያዊ

አድርገዉ የሚኖሩ፣ ስለ እዉነት ራሳቸዉን ክደዉ የሚመሰክሩና በእዉነት የሚኖሩ ስለሆነ፤ ለእናንተ ሕይወትና አገልግሎት ስለማይመቹ ከእነሱ ጋር አንዳች ህብረትና አንድነት እንዳትፈጥሩ በጨለማዉ ስሜ አደራ እላችኋለሁ፡፡

እነዲሁም አንዳንድ አገልጋዮችና ምእመናን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ሆዳቸዉ አምላካቸዉ የሆነና ከንቱ ሥጋዊ መጠበብ አድርገዉ በተለያዩ አዋልድ መጽሐፍትና የእዉቀት መጽሐፍት ወስጥ የሥጋና ደም አሳባቸዉና ፍላጎታቸዉን በማስገባት ምእመኑ ለእግዚአብሔር ትዕዛዝና ሕግ ቦታ እንዳይሰጥ፣ መለኮት ከተዋሀደዉ ከቅዱስ ሥጋዉና ክቡር ደሙ እንዲርቅ፣ በእዉነተና በመንፈስ እንዳያመልክ፣ መልካም ምግባር ሳይኖረዉና ስለ ኃጢአቱ እዉነተኛ ንስሐ ሳይገባ በዘልማድና በማስመሰል ሕይወት እንዲመላለስ የሚያስተምሩትን ትምህርት ተቀበሉ፡፡

እንደ ሥጋ ፈቃዳችሁ ብትመላለሱም፣ ራሳችሁን ለንስሐ ባታበቁም፣ ወደ ሥጋዉና ደሙ ባትቀርቡም ወደ እግዚአብሔር መንግስት የምትገቡበት የተለያዩ ሰፋፊ መንገዶች አሉና ነፍሳችሁን አንዳች አታስጨንቁ፡፡ «እንኮነናለን» ብላችሁ አንዳች ስጋት አይግባችሁ፡፡ እንኳን እናንተ ልትኮነኑ ቀርተ በሲኦል ያሉትን ነፍሳት ከፈለጋችሁ ዘመዶቻችሁን፣ ከፈለጋችሁ ጓደኞቻችሁን፣ ከፈለጋችሁ የማታዉቁትን ሰዉ ጭመር እዚሁ ምድር ላይ እያላችሁ ወደ ገነት ሰተት ብለዉ እንዲገቡ ማድረግ ትችላላችሁ፡፡ ስለዚህ በምድራዊ ሕይወታችሁ ዘመን ዘና ብላችሁ፣ ስትፈልጉ ትዕዛዙን መጠበቅ፣ ስትፈልጉ ትዕዛዝን በመሻር፣ የሥጋ ፍላጎታችሁንና ስሜታችሁን በማርካት ልትኖሩ ትችላላችሁ፡፡ ለዚህም እኔ የጨለማዉ ገዥ ሙሉ ዋስትና እሰጣችኋለሁ፡፡

ታዲያ አንዳንድ የኔን የጨለማዉ ገዥ ድንቅ ስራ ያልገባቸዉ ሰዎች «ማንም ይሁን ማን ከሥላሴ በጥምቀት ልጅነትን ካላገኘ፣ ሕይወት የሚሆነዉን መለኮት የተዋሀደዉን ቅዱስ ሥጋና ክብር ደሙን ካልበላና ካልጠጣ፣ በምድራዊ ዘመኑም መልካም ስራ ካልሰራ፣ እንዲሁም በኃጢአት ሲወድቅ እዉነተኛ ንስሐ ካልገባና ኃጢአቱ ከሰማያዊ መዝገብ ላይ እንዲደመሰስለት ቅዱሰ ቁርባን ካልተቀበለ በስተቀር በዘልማድና በማስመሰል እንዲሁም በዐመፃና በክህደት፣ በርኩሰት ሕይወት እያለ  የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርስም»

በማለት የሚያስተምሩትን ሰዎች አንዳች እንዳትሰሙ:: እነሱ ከምትደሰቱበትና ከምትዝናኑበት የኃጢአት ሕይወት ሙሉ በሙሉ ሊለያችሁና ከኔ አራርቀዉና አጣልተዉ ለእግዚአብሔር ብቻ እንድትገዙ ለማድረግ ቆርጠዉ የተነሱ የኔ የጨለማዉ ገዥ ተቃዋሚና ጠላቶች ናቸዉ::

እኔ አዝኜላችሁ በዚህ ምድር እንደፈለጋችሁት ሆናችሁ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለማስገባት ከፍተኛ ትግል እያደረኩ፤ እነሱ ግን ከኔ ተቃራኒ በመቆም ሥጋችሁን ሊጎዱና ነፍሳችሁን ብቻ ሊጠቅሙ ይሯሯጣሉ:: ስለዚህ እንናተ መምረጥ ያለባችሁ ኃጢአት እየፈጸማችሁ እንዲሁም በዐመፃና በክህደት ሕይወት እየተመላለሳችሁ በቀላሉ ጻድቃን የገቡበት ገነትና መንግስተ ሰማያት ዉስጥ ለመግባት የሚያስችላችሁን መንገድ እንጂ ሥጋችሁ የሚጎዳበትና ነፍሳችሁ ብቻዋን የምትጠቀምበትን መንገድ በምንም መልኩ እንዳትመርጡ በጨለማዉ ስሜ እመክርችኋለሁ::

እናንተ ቆብ በመድፋታችሁ ብቻ እግዚአብሔርና ምእመኑ በእዉነት የሚገለገሉበትን ወንበር ተቆጣጥራችሁ «እዉነተኛና ብቸኛ የሕይወት መንገድ» ተብላ የተመሰከረላትን የኢትዮጵያ ተዋህዶ ሃይማኖትን ለዘመናት ሳትበረዝና ሳትደለዝ ተጠብቃ ለአሁን ትዉልድ እንድትደርስ ያደረጉትን መምህራንና ሊቃዉንትን አግልላችሁና አርቃችሁ፣ ስልጣኑን በመቆጣጥር የሥጋ ፈቃዳችሁን የምትፈጽሙና የምታስፈጽሙ፤ ምእመኑንም ለተኩላና ለወንበዴ አሳልፋችሁ የሰጣችሁ፤ « እዉነተኛ እረኞች እኛ ብቻ ነን» በማለት ምእመኑን ለዐመፃና ለክህደት ሕይወት የዳረጋችሁ፤ ለሥጋዊ ጥቅም፣ ለክብር፣ ለዝናና ለግላችሁ ሥጋዊ ብልጽግና ታላቅ ተጋድሎ የምታደርጉ፤ በተለያየ የቅድስናና የመልአክ ስም የምትጠሩ ልዩ አገልጋዮቼ! ለእናንተ ልዩ እድናቆቴንና ሙገሳዬን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ::

ምክንያቱም ለቤተክርስቲያኒቱ ታላቅ ዉለታ የዋሉ፤ እናንተንም አስተምረዉ ለዚህ ያበቋችሁ፤ በየቦታዉ ወድቀዉና ተጥለዉ፣ ተረስተዉ ማየት እኔን የጨለማዉ ገዥ እጅግ ያስደስተኛልና ነዉ:: እነሱ ናቸዉ እጅግ አምርሬ የምጠላትን «ኢትዮጵያ» የምትባል አገርና «ተዋህዶ» የምትባል ሃይማኖት እንደሌላዉ ዓለም ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሬያቸዉ እንዳልፈነጭባቸዉና ሃይማኖቷም ተጠብቃ እንድትቆይ ያደረጉት:: የዘመናት ደመኛ ጠላቶቼን

ስላራቃችሁልኝና አስተዋሽ አተዉ የዘረጉት ጉባኤ እንዲዘጋ አስተዋጽኦ በማድረጋችሁ እዴት ምስጋናና አድናቆት አይገባችሁም! እጅግ ይገባችኋል።

አሁን ደግሞ አደራ የምላችሁ እንደጀመራችሁት የከተማዉ ኑሮ ደስ የሚልና የሚጣፍጥ ስለሆነ ዓለምን ንቀዉ ለአገራቸዉና ለዓለም ሕዝብ እየጸለዩና እያነቡ ያስቸገሩኝን መነኮሳት በየገዳማቱና በየዋሻዉ ስላሉ፣ በዋና ዋና ከተማ ባሉት በተመረጡና ጥሩ ገቢ ባላቸዉ አድባራት ላይ «ገዳም» የሚል ስያሜ እየሰጣችሁ ለአስተዳዳሪነትና ለአገልጋይነት እያበቃችኋቸዉ፤ ካህናቱን፣ መምህራኑን፣ ሊቃዉንቱን፤ «እናንተ በዚህ በከተማ ዉስጥ ባለ ገዳም መቀደስ ሆነ ማገልገል አይገባችሁምና «ነፍሳችንን» የምትሉ ከሆነ ከፈለጋችሁ ልጆቻችሁን ይዛችሁ፣ ካልፈለጋችሁ ደግሞ ብቻችሁን ሆናችሁ ሰዉ ወደ ማይገኝበት ገዳምና ዋሻ ሄዳችሁ ማገልገል ትችላላችሁ፤» በማለት ምእመናን ካሉበት ከተማ ሆነ ገጠር ብታርቁ ለወደፊት አገሪቷን ሙሉ በሙሉ ልትቆጣጠሩና በስልጣናችሁም ማንም ተቀናቃኝ እንዳይገባባችሁ ልታደርጉ የሚያስችላችሁ መሆኑን በጨለማዉ ስሜ እመክራችኋለሁ።

ሌላዉ ደግሞ እናንተ «የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን፤ የምእመናን እረኛ ነን» የምትሉ፤ እኔ ለዘመናት የማዉቃቸዉ እዉነተኛ እረኞች « እስከዚህ ሰዐት ድረስ እንራባለን፣ እንጠማለን፣ እንራቆታለን፣ እንጎሰማለን፣ እንከራተታለን፣ በገዛ እጃችን እየሠራን፣ እንደክማለን፣ ሲሰድቡን እንመርቃለን፤ ሲያሳድዱን እንታገሳለን፤ ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን፤ እስከ አሁን የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጉድፍ ሆነናል» እያሉ ነበር መንፈሳዊ አገልግሎትን የሚፈጽሙት።

እናንተ ግን ያማራችሁን እየበላችሁ፣ እየጠጣችሁ፣ ባማረ ቤት እየኖራችሁ፣ የፈለጋችሁትን ትራንስፖርት እየተጠቀማችሁ፣ እንደ አምላክ እየተከበራችሁና እየተፈራችሁ፣ ሁሉ በእንክብካቤ እየተሟላላችሁ፤ ምን ቀረብን፣ ምን ጎደለብን ብላችሁ ነዉ ምእመኑን ለኔ ለጨለማዉ ገዥ አሳልፋችሁ የምትሰጡኝ? ምን ቀረብን፣ ምን እናገኛለን ብላችሁ ነዉ ከሥጋዉያን መሪዎችና ባለስልጣናት ብሳችሁ ለምድራዊ ስልጣን፣ ክብር፣ ጥቅም፣ ለግል ብልጽግና፣ ዝና፣ እርስ በእርስ የምትጣሉትና የምትወነጃጀሉት? የምትከፋፈሉት?

በምግባራችሁና በንግግራችሁ ምእመኑን የምታሰናክሉት? እግዚአብሔርንም እጅግ የምታስቆጡት?

ሌላ ምን ይጨመርልን ብላችሁ ነዉ በዘመድ አዝማድ በጎጥ ተቧድናችሁ የእግዚአብሔር በጎችን ምእመናን ለኔ ለጨካኙ ለዲያብሎስ እያጣደፋችሁ የምታቀርቡልኝ? እረ ምን እንሁን ብላችሁ ነዉ መስቀልን ያህል ይዛችሁና የእግዚአብሔር ቃል የሰፈረበትን መጽሐፍ ቅዱስ መመሪያ አድርጋችሁ የመስቀል ተቃራኒ ተግባር ለመፈጸም ሌት ተቀን የምትተጉ?

እንግዲህ በ7503 ዓመት ጥናቴና ልምዴ መሰረት እንኳን ሰማያዊዉን ትዕዛዝና ሕግ የጣሰ አይደለም፤ ምድራዊዉን ሕግ እንኳ በይሉኝታና እንዲሁም ለጥቅም ሲል የሚጥስ ሰዉ ዋጋ ይከፍልበታል፡፡ በመሆኑም እናንተ « የእግዚአብሔር አገልጋይ ነን» የምትሉ ሆነ፤ «በእግዚአብሔር እናምናለን» የምትሉ እንደ ዐመጻና ክህደት፣ እንዲሁም ርኩሰት ሥራ አስፈጻሚነታችሁና ተባባሪነታችሁ በምድርም በሥጋ እያላችሁ፣ ነፍስችሁም ከሥጋ ከተለየች በኋላ ነጻነቷ ተግድቦ በረቂቅ አካል(ምስሌያዊ ባሕርይ) ተገልጻ ዋጋ ትከፍሉበታላችሁ፡፡

ታዲያ ይህን ማለቴ ዋጋ የምትቀበሉበትን እንጂ ዋጋ የምትከፍሉበትን ተግባር እንዳትፈጽሙ ለማሳሰብ ፈልጌ ሳይሆን «ከእኛ በላይ ለአሳር የምትሉ፣ በእዉቀታችሁና በስልጣናችሁ የምትመኩ፣ ራሳችሁንንም ንጹህና ቅዱስ አድርጋችሁ የምትቆጥሩ፣ ከእናንተ በላይ እኔ የጨለማዉ ገዥ ማንነታችሁን ስለማዉቅ በተቀደሰዉና በተመረጠዉ ስም መነገዱ አያዋጣችሁምና የሚያዋጣችሁ በእግዚአብሔር ስም ከመነገድ ይልቅ እንደ ሥጋዉያን መሪዎቼና ስራ አስፈጻሜዎች በግልጽ «እግዚአብሔር የለም» በሚለዉ የጨለማዉ ስርዐቴ ስር እንድተመላለሱና ክህደታችሁን በግልጽ ለዓለም በማሳወቅ ፍርዳችሁን ብታቀሉ የተሻለ እንደሆነ ለመምከር በማሰብ ነዉ» **ይላል ለማንም የማይተኛዉ፣ ከቅድስና እስከ ተራ ማእረግ ያለን ሰዉ የሚፈታተነዉና ከተቻለዉም በኃጢአት ተግባርና ሕይወት የሚያልከሰክሰዉ የጨለማዉ ገዥ ዲያብሎስ ከጨካኞቹ ጭፍሮቹ ሰይጣናት ጋር በመሆን፡፡**

# ምእራፍ አስራ አንድ

« እናንተ «ቅዱሳን ሰማዕታት» ተብለዉ የሚጠሩትን ሰዎቸ (ነፍሳት) ለመጠጥና ለመራገጫ ስያሜ በመስጠት «ጊዮርጊስ ቢራ፣ ጊዮርጊስ ቡድን» እያላችሁ ስሙን መጠጫና መጫወቻ በማድረግ ላይ ያላችሁ ደፋሮችና ታታሪዎች ሰዎች፤ ይህን ተግባራችሁን አጠናክራችሁ በመቀጠል ወደ ሌሎች «ቅዱሳን ፣ ጻድቃን» በሚል ስያሜ የሚታወቁትን እንዲሁ ለተለያዩ መጠጥና የቡድን ስያሜዎች እንድታደርጉ እያሳሰብኳችሁ ችላ ያላችሁትን የኔን ስም ትኩረት ሰታችሁት ከፈለጋችሁ ሰይጣኒዝም፣ ከፈለጋችሁ የፈለጋችሁትን ስያሜ እንደ ፕሮቴስታንት ክፍልፋይ ድርጅቶቼና ቡድኖቼ ስያሜ በመስጠት እንድታስቡኝና ፈቃዴን እንድትፈጽሙልኝ በጨለማዉ ስሜ አሳስባችኋለሁ::

ታዲያ እናንተ የኳስ ቡድኖች፤ አንዳንድ ያልገባቸዉ ሰዎች « የስፖርቱ ጨዋታ ልክ እንደ ዘፈኑ የዓለም ቋንቋ ሆኖ ትዉልዱን ለሥጋዉ ሆነ ለነፍሱ አንዳች ጥቅም በማያገኝበት ጊዜዉን ያስባክናል፣ ኅሊናዉንም ያስደነዝዛል፣ ከዚያም አልፎ ለስንት ሥጋዊ ሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ሊዉል የሚችለዉን ገንዘብና ንብረት ፈሰስ ይደረግበታል፣ ያሸነፈዉ ሲፈነጥዝ የተሸነፈዉ ደግሞ ያዝናል፣ እርስ በእርስ እንዲጣሉ ያስደርጋል፣ የባሰበት ደግሞ እንዲታመምና ራሱን እንዲያጠፋ ያስደርጋል፣ ጥንት አህዛብ እግዚአብሔርን አያመልኩምና ተስፋቸዉ ምድራዊ ስለሆነ ለጊዜ ማባከኛና ማጥፊያ እንዲሁም ለመዝናኛ የሚጠቀሙበት ትዕይንት የነበረ ሲሆን፤ የአሁኑ ልዩነቱ እንደ ድሮ ሰዉና አዉሬን ጭምር እያተገሉ መዝናናቱ መቅረቱ ነዉ እንጂ አጠቃላይ ሕይወቱና ስርዐቱ «ሞተን፣ በስብሰን እንቀራለን፤ ባለችን አጭር ዘመን እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንዝፈን፣ እንደለቅ፣ እንዝናና» እንደሚሉት በዘመናዊ መልክ የቀረበ የአህዛብና እግዚአብሔር የለሽ ሰዎች ልማድና የሰይጣን ማደንዘዣ ትዕይንት ነዉ::» በማለት ከዚህ ታላቅ ተግባራችሁና ግለሰቦችን በማግነንና በማድነቅ መለስተኛ አምልኮ እንዳታቀርቡላቸዉ ከእነሱ ሊለያችሁ ከሚፈልጉ ሰዎች ተለዩ:: ንግግራቸዉን አትስሙ::

እነሱ በዚያ ትዕይንት ዉስጥ ኅሊናችሁ ሲባዝን የኔን የጨለማዉ ገዥ መንፈስ ፈተና እንደማታስተዉሉ፣ ከተለያዩ አሳቦች እንደምትለዩ ስላልገባቸዉና ሁሌ ለቅን አሳብ፣ ለመልካም ተግባር ብቻ እንድትነሳሱና በእረፍታችሁ ጊዜም ነፍሳችሁ ወደ ሰማይ ሰማያት እንድትመሰጥ፣ ባላያችሁት ሰማያዊ ሕይወት በተስፋ እንድትሞላ ስለሚፈልጉና ከምድራዊ አስተሳሰብ እንድትለዩ ለማድረግ ነዉ ከዚህ ጊዜ ማባከኛና ማቃጠያ ትዕይንት ሊለያችሁ የሚፈልጉት::

እናንተ ግን «ጊዜያችንን በምን እናሳልፍ? ምን እናዉራለን? እነዚያ ጎበዝ ተጫዋቾችን ማን ያደንቃቸዋል? ታሪካቸዉንና ተጋድሏቸዉን ማን ይናገርላቸዋል? የገቢ ምንጫችን ስለሆነ እንዴት ከዚህ ታላቅ ተግባር እንለያለን? የጥንት አህዛብ ነገሥታትና ባለስልጣኖች ለራሳቸዉ ብቻ የሚጠቀሙበትና የሚዝናኑበትን አሁን ለሕዝቡ ጭምር እንዲተርፍ አደረግን፣ ተጫዋቾቹም በዘመናዊ መልክ እየተሸጡ ባሪያ እንዲሆኑና ገቢ እንዲያገኙ አደረግን እንጂ ምን ጉዳት አደረስን? ተመልካቹም ሌት ተቀን የሚያስበዉ፣ የሚያመሰግነዉ፣ የሚያገነዉ፣ የሚያደንቀዉ ዘመናዊ ጣዖት አዘጋጀንለት እንጂ ምን የከፋ በደል ፈጸምን ? » በማለት አፋቸዉን አዘጉ::

እኔም ከጎናችሁ ቆሜ ጥብቅና እቆምላችኋለሁ:: እናንተ ከበላችሁ፣ ከጠጣችሁ፣ ከተዝናናችሁ፣ ከጨፈራችሁ፣ ከዘፈናችሁ፣ ከሰከራችሁ፣ እንደፈለጋችሁ ከሆናችሁ፤ ሌላዉ ቢራብ፣ ቢጠማ፣ ቢታረዝ፣ ቢያዝን፣ መከራና ችግር ቢደርስበት ምን ቸገራችሁ! «ከራስ በላይ ንፋስ» የሚለዉን መርህ ተከትላችሁ ተስፋችሁን በምታዩትና በምትዳስሱት ላይ አድርጋችሁ በዚህች ምድር እንደፈለጋችሁ በአህዛብ አኗኗር መኖር እንጂ፤ አንዳንዶች ያልገባቸዉና በማይታይና በማይዳሰስ ነገር ተስፋ የሚያደርጉ ሐሳባዉያን « ይህች ምድር የእኛ ግዛት አይደለችም፣ በሥጋ ተገልጾን ጠርተንና ነጥረን ወደ እዉነተኛ ግዛታችን ገነትና መንግስተ ሰማያት መሸጋገሪያ ድልድይ ናት::» በማለት ታላቅ ግዛቴን የሚያናንቁትንና የሚያጥላሉትን አንዳች አትስሟቸዉ:: እነሱን አትምሰሉ፤ አንድነትና ህብረት አይኑራችሁ:: እነሱ ሁሌ ማሰብና ማመስገን የሚፈልጉት ያ በመስቀል ላይ የተሰቀለዉ አምላካቸዉን ነዉ:: እኔ

የጨለማዉ ገዥ ደግሞ ያኔ ራቁቱን ሲሰቀል ደስ እንዳለኝ አሁን ደግሞ የምደሰተዉ ትዉልዱ አንዳች ነገረ መስቀሉን ባለማስታወሱና ባለማሰተዋሉ ነዉ።

እናንተ ጋብቻችሁን በአህዛብ ስርዐት የምትፈጽሙ ፈጣሪያችሁ በማይከብርበትና በማይባርክበት መልኩ በዳንኪራዉና በዘፈኑ፣ በስካሩ የምታስተናግዱ፤ እኔን የጨለማዉ ገዥ ደግሞ በታላቅ አጠራር ጠርታችሁኝ የአህዛብን ( እግዚአብሔርን የማያመልኩ ሰዎችን) ስርዐት እንድባርክላችሁ፣ እንድመራላችሁ በማድረጋችሁ በመጀመሪያ በጨለማዉ ስሜ አመሰግናችኋለሁ።

ለወደፊትም ልጆቻችሁንና ዘመዶቻችሁን ስትድሩ ከቻላችሁ የኔ ልዩ ቦታ አስመጥታችሁ የጨለማዉ ጸጋዬን እንዳድላቸዉ ብታደርጉ። ካልተቻላችሁ ደግሞ በተለመደዉ የአህዛብ ስርዐት አከናዉኑ እንጂ ያ እሳት የሆነዉን ቅዱስ ቁርባን ብትቀበሉ እግዚአብሔር እንዲባርካችሁና በመካከላችሁ ከእናቱ ድንግል ማርያም፣ ከቅዱሳን መላእክት፣ ከነብያት፣ ከሐዋርያት፣ ከሰማዕታት፣ ከጻድቃን ጋር እንዲገኝ በመዝሙር እንዲፈጸም ብታደርጉ ከኔ ይልቅ ተጎጂዎች ራሳችሁ መሆኑን እንድታዉቁ።

ምክንያቱም አህዛብ ተስፋቸዉ ምድራዊ ስለሆነ « ከሞትን በኋላ ሕይወት የለምና በዚህች አጭር ዘመናችን እንብላ፣ እንጠጣ፣ እንዝፈን ፣ እንጨፍር፣ እንደለቅ።» በማለት ስለሚዝናኑ፤ እናንተ ግን በመንፈሳዊ መልኩ እንዲፈጸም ካደረጋችሁ የእነሱ እድል አያጋጥማችሁምና ነዉ። እንዲሁም የጎሊና እርካታና ሰላም ብቻ አግኝታችሁ ትደሰታላችሁ እንጂ ቀድሞ በየጥንቆላዉ፣ በየጣዖት ማምለኪያዉ፣ በየባዕድ አምልኮ ቦታ፣ በየምናምንቴ ቦታ ይቀርብ የነበረዉ ዛሩ፣ ሚርቱ፣ ማጓራቱ፣ መንዘፍዘፉ፣ መዘረሩ፣ መወራጨቱ፣ ጎንበስ ቀና ማለቱ፣ መሽከርከሩ፣ እንጣጥ እንጣት ማለቱ፣ ብቻ አይነቱ ብዙ የሆነዉ ትዕይን አሁን ደግሞ በዘመናዊ መልክ «ጥበብ» ተብሎ በተለያዩ መሳሪያ ታጅቦና የሰዉ ጎሊና እንዲቀበለዉ ተደርጎ የመጣዉ ዘፈንና ዳንኪራ የማየትና እናንተም በዛ ትዕይንት ዉስጥ የመሳተፍ እድል አያጋጥማችሁም።

በዚሁ አጋጣሚ እናንተ ክብራችሁን ከቁም ነገር ሳትቆጥሩ ድንግልናችሁን በየቦታዉ ጥላችሁ ታላቅ ተጋድሎ እንደፈጸመ ሰዉ፤ ራሳቸዉን በመግዛት ድንግልናቸዉን

እስከመጨረሻ ሰዐት ጠብቀዉ ለዚያ ጽናታቸዉ የሚደረግላቸዉን ሽልማት የሆነዉን አክሊል (ተክሊል) በአቋራጭ መንገድ ካለእፍረት በማድረጋችሁ እጅጉን አደንቃችኋለሁ:: ቅዱስ ቁርባኑንም ስትቀበሉ እንደ ተክሊሉ ለታይታ አድርጉት እንጂ « ሕይወት እናገኝበታለን፣ ኃጢአታችን ይደመሰስበታል፣ ለሰማያዊ ክብር እንበቃበታለን::» በሚል እምነት እንዳይሆን የጨለማዉን ታላቅ ምክሬን እመክራችኋለሁ::

እናንተ በዚህች ምድር ቆይታችሁ ዉስጥ ራሳችሁን ማወቅ ከጀመራችሁበት ጊዜ ጀምሮ « የሰራናቸዉ፣ የተናገርናቸዉ፣ የተሳደብናቸዉ፣ ያሰብናቸዉ የኃጢአት ተግባር፣ ንግግር፣ ስድብ፣ አሳብ እኛ ከረሳናቸዉ እግዚአብሔርም አያስታዉሳቸዉም::» ብላችሁ የምታምኑና ነፍሳችሁ ከሥጋ ከተለየች በኋላ « ምንም የምታዉቀዉ፣ የምትረዳዉ፣ የምታስተዉለዉና የምትጠየቅበት አንዳች ነገር የለም» የምትሉ ሊቀ ምሁራን፤ ስለመጠቀና ስለተራቀቀ እዉቀታችሁ ያለኝን አድናቆት አስቀድሞ እገልጽላችኋለሁ::

ታዲያ አንዳንድ እዉቀት የሌላቸዉ ሰዎች «ነፍስ ካወቅን ጊዜ ጀምሮ የሰራነዉ፣ የተናገርነዉ፣ ያሰብነዉ ጭምር በእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ የሚሰፍሩ፣ የሚታወቁ፣ የማይረሱ፤ ከሥጋ ሞት በኋላ የተረሳዉም፣ ያልተረሳዉም የኃጢአት ተግባር፣ ንግግር፣ ስድብ፣ አሳብ ጭምር ነፍሳችን በምትገለጽበት ረቂቅ አካል( ምሳሌያዊ ባሕርይ) ሆና እስከፍርድ ቀን ድረስ በሲዖል ዉስጥ እያስታወሰችዉ ትጨነቃለች:: ትሰቃያለች:: «ምን አይነት ይሆን የመጨረሻ ፍርድ የሚጠብቀኝ?» እያለች ታስባለች፣ ታወጣለች፣ ታወርዳለች:: በዚህም ምክንያት ካለ እረፍት ትጨነቃላች:: እንደ ምድራዊ ዘመኗ እንኳ በማንቀላፋት አታርፍም::

በተቃራኒዉ ደግሞ ስለ ኃጢአታቸዉ እዉነተኛ ንስሐ የገቡና ስለ ኃጢአታቸዉ የተጸጸቱ ሰዎች መለኮት የተዋሀደዉን የክርስቶስን ሥጋና ደም ሲቀበሉ በተግባርም፣ በንግግርም፣ በአሳብም የፈጸሙት ኃጢአት ሁሉ ከእግዚአብሔር ባሕርይ መዝገብ ላይ ሙሉ በሙሉ ይደመሰሳል:: በምድር ያልረሱትም ኃጢአት ሆነ የረሱት ኃጢአት ልክ ህጻን ልጅ በልጅነቱ የሰራዉን ድረጊት፣ ንግግር፣ ያሰበዉን አሳብ እንደማያስታዉስ ሁሉ ነፍሳቸዉ ከሥጋቸዉ ስትለይ አንዳች አያስታዉሱትም:: ያለፉበት የመከራና የፈታና ሕይወት

አይታወሳቸዉም:: ነገር ግን መከራና ስቃይ ከነበረበት ዓለም መምጣታቸዉን ልብ ይላሉ:: በንስሐ መታደሳቸዉን ያስተዉላሉ:: ኑሮዋቸዉም ቀደም ካሉ ጻድቃን ጋር በንጹህ ኅሊና በመሆን ይቀላቀላሉ:: አምላካቸዉንም በእዉነትና በመንፈስ ብቻ ያመልካሉ:: በመጨረሻዉ ፍርድ ቀንም በማረፊያ ቦታ የሚካሄደዉን የመጨረሻ ፍርድ እንደ ቅዱሳን መላእክት ተመልክተዉ በቀጥታ ወደ መንግስተ ሰማያት ይገባሉ:: በሰማያዉያን መላእክት አኗኗር በረቂቅ አካላቸዉ ሕያዉ ሆነዉ ይኖራሉ:: እንኳን የምድሩን የስቃይ ኑሮ ቀርቶ የገነቱን አኗኗር ረስተዉ በአዲስ ልዩ ብቃት በተሞላዉ ሕይወት በቅድስናና በደስታ ሕይወት ብቻ ይኖራሉ::

በዚህ ምድር ዉስጥ እምነትና ምግባራቸዉ ያልታየና ያልጠሩና ያልነጠሩ የህጻናት ነፍስ እንዲሁም በነጻ ኅሊናቸዉ ብቻ ተመርተዉ በቅን ሐሳብ በመልካም ተግባር ሕይወታቸዉን ያሳለፉ ነገር ግን በእዉነተኛዉ አምልኮ ዉስጥ ያልተመላለሱ ወይንም ከሰብአዊነት አንጻር ብቻ በቅን አሳብና በመልካም ሕይወት የተመለለሱ ሰዎች፤ ነፍስ ከሥጋቸዉ ስትለይ በቀጥታ ከዓለም ዉጭ ከሲያል አጠገብ ወዳለችሁ ወደ ማረፊያ ቦታ ነዉ የሚገቡት:: በዚያ በሚኖራቸዉ ዉስጣዊ የእምነት ብቃት ደረጃ በፍርድ ቀን ተፈርዶላቸዉ ወደ መንግስተሰማያት የመግባት እድል አላቸዉ:: በነጻ ኅሊናቸዉ ተመርተዉ የሚፈለገዉ የእምነት ብቃት ደረጃ ላይ ያልደረሱ ነፍሳት ደግሞ በሲያል ካሉት ጋር ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ይጣላሉ፤ በዚያም እንደ ዐመጻና ክህደት ደረጃቸዉ ይቀጣሉ::

በመጨረሻዉ የዓለም ፍጻሜ ዘመን የሚኖሩት ጻድቃን ሰዎች ደግሞ በምህረት ሞት በቀጥታ ወደ ማረፊያ ቦታ ይጠራሉ:: ኃጢአተኞችና ዐመጸኛ፣ ከሃዲዎች ሰዎች በመቅሰፍት ሞት ወደ ማረፊያ ቦታ ይመጣሉ:: ጻድቃን በገነት ከነበሩት ጋር በአንድላይ ወደ መንግስተ ሰማያት ሲገቡ፤ ኀጥአን ደግሞ ለዘመናት በምድር ዉስጥ በዐመጻና በክህደት ሕይወት ከኖሩት ሰይጣናትና ከአለቃቸዉ ዲያብሎስ ጋር ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ ይጣላሉ::

በዚያም ያለዉ ቅጣታቸዉ በምድር ቆይታቸዉ እንደፈጸሙት የኃጢአት ደረጃ ቅጣታቸዉ የሚለያይ ሲሆን፤ እጅግ የከፋ ኃጢአት የፈጸሙ እጅግ ሊቋቋሙት የማይችሉት ስቃይ ይጠብቃቸዋል:: አነስ ያለ ኃጢአት የፈጸሙ በዚያዉ ልክ ቅጣቱ ይቀልልላቸዋል:: ልክ

ሰዎች በተመሳሳይ ሥጋ አካል የተገለጹ ቢሆንም ደገኛዉ ሰዉ ወደ በረሀ እንዲኖር ቢደረግ በረሀ ከሚኖረዉ ሰዉ ይልቅ የሙቀቱና የቃጠሎዉ ስቃይ እንደሚበረታበትና መቋቋም እንደሚያቅተዉ ሁሉ፤ ለሁሉም ዐመጸኞች የመቀጫዉ ቦታ ገሃነመ እሳት ቢሆንም ሰይጣናት ሆኑ ሰዎች የሚቀጡበት ደረጃ እንደ ምድራዊ ዐመጻና ክህደት ሕይወታቸዉ ይለያያል። እንኳን በገሃነመ እሳት አይደለም በመንግስተ ሰማያት የሚገቡት የጻደቁ ነፍሳት በተመሳሳይ ረቂቅ አካል ቢገለጹም የሚያገኙት ደስታና እርካታ እንዲሁም ክብር እንደምድራዊ የቅድስና ብቃታቸዉ ይለያያል። ከፍጡራን በላይ ከፈጣሪ በታች ለመሆን የበቃችሁ እመ አምላክ ድንግል ማርያም ከቅዱሳን መላእክት ሆነ ከጻደቁ ሰዎች(ነፍሳት) በተለየ መልኩ በምሳሌያዊ ባሕርይ (በረቂቅ አካል) ሳይሆን የምትገለጸዉ እንደ ልጇና አምላኳ በብርሃናዊ ባሕርይ ነዉ ተገልጻ በንግሥትነት ከአማነዊዉ ንጉሥ ነገሥት ከጌታችን ከአምላካችን ከእግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በሰማያት ዉስጥ የምትኖረዉ።

እዚህ ምድር ጸጋዉ የተሰጠዉ ሰዉ ልክ የሩቆቹን ከዋክብት በሥጋዊ ዐይን እዚህ ሆና ማየት እንደሚቻል ሁሉ ነፍሳችንም እዚሁ ሆና ከምድር ጉን ያለችዉን ገነት፣ ከዓለም ዉጭ ያሉትን ሲያልና ማረፊያ ቦታ፣ እንዲሁም እልፍ አእላፋት ወትእልፊት የሆኑት ቅዱሳን መላእክት የሚኖሩበትን ሰማያትን መመልከት ይችላሉ። ከተፈቀደላቸዉ ደግሞ በዚያ የሚከናወነዉን ስርዐትና ሕይወት መመልከት ይችላሉ።

በፍርድ ቀን በምድር ዉስጥ ያሉ በእምነታቸዉና በምግባራቸዉ የጸኑት ሰዎች በአሁን ሰዐት ማንም ሰዉ በሥጋዊ ዐይኑ ፀሐይን መመልከት እንደማይችል በዚያን ዘመን ግን እርሱ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማያት ዉስጥ ከእልፍ አእላፋት ቅዱሳን መላእክት ጋር ሆኖ ሲመጣ፤ ከዓለም ዉጭ ከሲያል ከፍ ብላ ከሰማያት ዝቅ ብላ ያለችዉን ማረፊያ ቦታ ከዚህ ዓለም ጋር በምትነካካበት አቅጣጭ በግልጽ እንደ ፀሐይ እየታያቻቸዉ በምህረት ሞት በቀጥታ ነፍሳቸዉ በረቂቅ አካል (በምሳሌያዊ ባሕርይ) ተገልጻ ወደዛ ቦታ ይነጠቃሉ።

በተቃራኒዉ ደግሞ ዐመጸኛ ሰዎች ሆኑ ርኩሳን መናፍስት (ሰይጣናት) በመቅሰፍት ቅጣት ከዚህ ምድር ተለይተዉ ከማረፊያ ቦታ ዝቅ ተደርጎ ከሲዖል አጠገብ የሚዘጋጀዉ እሳቱ የማይጠፋበትን ትሉ የማያንቀላፋበትን ገሃነመ እሳትን እየተመለከቱ ነዉ ወደ ማረፊያ ቦታ ተጠርተዉ በቀጥታ የመጨረሻዉን ፍርድ ተቀብለዉ ወደ ገሃነመ እሳት ዉስጥ የሚጣሉት» በማለት ተረተ ተረት የሚናገሩትን ሰዎች አንዳች እንዳትሰሙ።

ይልቁኑ « እኛ እግዚአብሔርንም አናዉቅም፤ የሰይጣንንም ህልዉና አናምንም። ተፈጥሮ ናት ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣችንና ያስገኘችን። ሞተን፣ በስብሰን ፣ የምንቀር ነን። ዝርያዎቻችንም ጦጣዎች ናቸዉ። በቀስ በቀስ እድገትና ለዉጥ (በኢቮልሽን) አማካይነት ነዉ ተለዉጠንና የክሮማግነንና የኒያንደርታን ሰዉነት እድገት ደረጃ አልፈን አሁን ላለንበት ስብእና የበቃነዉ» በማለት አሳፍሯቸዉ። የኔን የጨለማዉ ገዥ ህልዉና ካዳችሁ ብዬ አንዳች ቂም አልይዝባችሁም። በቁስአካላዊ አስተሳሰባችሁ እስከመጨረሻዉ ጽኑ ።

እነዚህ ሐሳብያዉያን « ከቁስ አካል በፊት መንፈስ አለ። ሁሉ የተፈጠረዉ በመንፈስ ኃይል ነዉ። ሁሉ በእርሱ ቁጥጥር ዉስጥ ነዉ።» በማለት አዋቂነታችሁንና ምሁርነታችሁን ዝቅ ሊያደርጉ ነዉና ትግላቸዉ እናንተ በቅሬተ አጽም ጥናታችሁ በሚሊዮንና በቢሊዮን የሚቆጠር እድሜ እየሰጣችሁ ትዉልዱን በእግዚአብሔር ላይ ያለዉን እምነት እንዲጠራጠርና እንዲክድ እንድታደርጉ የጨለማዉ ምክሬን እለግሳችኋለሁ። በዚህ ዉለታችሁም እናንተ ባታምኑኝም ቸርነትን አድጌ እኔ የምወርሰዉን መንግስት አወርሳችኋለሁ።» **ይላል የጨለማዉ ገዥ ትዉልዱን በተለያየ የክህደት ትምህርትና ትዕይንት አደንዝዞ ወደ ሞትና መቀመቅ በመዉስድ ላይ ያለዉ ዲያብሎስ ከሠራዊቱ ሰይጣናት ጋር በመሆን።**